# ማክሲም ጎርኪይ

# እናት

ልብ ወለድ

«ራዱጋ» አሳታሚ ድርጅት ።
ሞስኮ ።

ተርጓሚው ፤
ግዕዛን የማነ ።

М. Горький
МАТЬ
*на амхарском языке*

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

© «ራዱጋ» አሳታሚ ድርጅት እ.ኤ.አ. 1986

© የፕሮግሬስ የመጻሕፍት ማዘጋጃና ማሳተሚያ ቤት
የአማርኛ ትርጉም እ. ኤ. አ. 1981 ዓ. ም.

በሶቪየት ኅብረት ታተመ ።

Г $\frac{4702010200-414}{031(01)-86}$ без объявления

ISBN 5-05-001622-3

## መቅድም ።

በአንድ ሀገር ቋንቋ የሥነ-ጽሁፍ ታሪክ ውስጥ እጅግ ዓይነተኛ የሆኑ ፣ እንደውም አዲስ የሥነ-ጽሁፍ ምዕራፍ የሚከፍቱ መጻሕፍት አሉ ። ምንም እንኳን ሩስያዊው ስመ-ጥር ደራሲ ማክሲም ጎርኪይ «እናት» በሚል ርእስ የጻፈው መጽሐፍ የሶቭየት ሥልጣን ከመመሥረቱ አሥር ዓመታት አስቀድሞ የተጻፈ ቢሆንም ፤ ለሩስያውያን አዲስ የሥነ-ጽሁፍ ምዕራፍን የከፈተ ነው ። ይህንን መጽሐፉን ለእኛ ለሶቭየት ሥነ-ጽሁፍ እንደመጀመርያ የመሠረት ድንጋይ አድርገን እንቆጥረዋለን ።

«እናት» የተሰኘው የጎርኪይ መጽሐፍ ሩስያ ውስጥ በመጀመርያ የታተመው በ 1907 ዓ. ም.* ነበር ። ጎርኪይ ይኸንን መጽሐፉን ሲጽፍ ታሪካዊ ተልእኮውን በሚገባ የተገነዘበ ፤ አዕምሮውም ተደላድሎ የበሰለ ደራሲ ነበር ። በዚያን ጊዜ ዕድሜው አርባ ዓመት ይጠጋው ነበር ። ጎርኪይ ለአሥራ አምስት ዓመታት እርሱነቱን ለሥነ-ጽሁፍ እና ለሕዝባዊ ተግባራት ሰጥቶ ነበር ። ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ ዓለም-አቀፍ ታዋቂነት ያስገኙለትን ልብ-ወለድ ታሪኮች (novels) ፣ አጫጭር ልብ-ወለድ ታሪኮች (stories) እና የቲያትሮች ድርሰቶች (plays) ጽፎ ነበር ። በፖለቲካዊ ተግባሮቹ እና

---

* በዚህ መጽሐፍ ላይ ዓመተ ምህረቶች የሚቀርቡት እንደአውሮጳውያን የዘመን አቆጣጠር ነው ። (ተርጓሚው ።)

ከቦልሸቪክ ፓርቲ ጋርም በነበሩት ግንኙነቶቹ ምክን
ያት በዛሩ (ንጉሣዊው) መንግሥት ተግዞ ነበር ። ከአንድ
ጊዜ በላይም ታሥሮ ነበር ። ይኸ ሁኔታ ግን ፤ ተግባሮ
ቹን ከመፈጸም ሊያግደው አልቻለም ። በ 1905 ዓ. ም.
የሩስያ ሬቮሉሺን ጊዜ ፤ ማለትም «እናት» በሩስያ ውስ
ጥ ታትሞ ከመውጣቱ ሁለት ዓመታት በፊት ፤ ለከእ
ንግዲህ ወዲሁ ታላቅ ወዳጁ ከሆነው ከቭላዲሚር
ሌኒን ጋር ለመጀመርያ ጊዜ ተዋወቀ ።

በ 1890 ዓ. ም. አካባቢ በሩስያ ውስጥ ከቦታ-ቦታ
በመመላለስ ያደረገው ጉዞ ፤ ማኅበራዊ ጉዳዮችን በሚመ
ለከት ረገድ የነበረው አትኩሮት እና ሬቮሉሺናዊ
ግንዛቤው ፤ በዚያን ጊዜ ከነበሩት ተመሳሳዮቹ መካከል
ጥቂቶቹ ብቻ ተሳክቶላቸው የነበረው ሩስያን የመመል
ከት እና የመረዳት ችሎታ እንዲኖረው ሊያደርገው
በቃ ። የትውልድ ሀገሩ እጅግ ሰፊ በመሆኗ ፤ በሐገሩ
ውበት እና ምድሯም ባቀፈቻቸው ልዩ-ልዩ ትዕይንቶ
ች ልቡ በአንክሮ የተነካ ሲሆን ፤ ከዚሁ ጋር በአንድ
ነትም ፤ በሐገሩ ሕዝቦች ላይ ይታይ በነበረው ድንቁ
ርና ፥ ድህነት እና ሥቃይ መንፈሱ በማዘን ተረብሾ
ነበር ።

መላው የጎርኪይ የድርሰት ሥራዎቹ ማኅበራዊ
ጉዳዮችን በአትኩሮት መገንዘቡን የሚያሳዩ ናቸው ።
ይሁን እንጂ ይህ ለሩስያ ሥነ-ጽሁፍ አንድ ብቸኛ
የሆነ ጉዳይ አይደለም ። ለሩስያ ሬቮሉሺን የመጀመር
ያዎቹ ትውልዶች ናቸው በማለት ጎርኪይ ቀጽሎአ
ቸው በነበሩት በታኅሣሣውያን (ዴካብሪስት) ግጥሞች
መካከልም ታይቶ የነበረ ጉዳይ ነው ። የዘውድ አገዛ
ዝን እና ገባርነትን በመቃወም በዲሴምበር 14 ቀን
1825 ዓ. ም. በተካሄደው እንቅስቃሴ ተሳትፈው የነበሩ
ት ባለቅኔዎች ከልባቸው ሪፑብሊክን ደጋፊዎች
የነበሩ ሲሆኑ ሕዝቦችን ለማገልገል እና የሕዝቦች



የወደፊት ኑሮም የተቃና እንዲሆን በድርሰቶቻቸው
አማካይነት ይታገሉ ነበር ። የሩስያ ታላላቅ ደራስያን
እና ባለቅኔዎች እነ ፑሽኪን ፤ ሌርሞንቶቭ ፤ ሄርዘን ፤
እና ስለእነርሱም አንድ ልብ-ወለድ መጽሐፍ ሊጽፍ
አስቦ የነበረው ፤ «ጦርነት እና ሰላም» የተሰኘው መጽ
ሐፉም ሬቮሉሺናዊ መልዕክት እንዲኖረው ያደረገው
ሌቭ ቶልስቶይ እንኳን ሳይቀር በታኅሣሣውያን ተመ
ስጦ ነበር ።

ከጎርኪይ ጋር በአስተሳሰብ የተመሳሳይነት ቅርበት
የነበራቸው «ራዝኖቺንጽዕ»* በሚል ቅጽል ይታወቁ የ
ነበሩት ሬቮሉሺናውያን በአሥራ ዘጠኝኛው ክፍለ-ዘ
መን አጋማሽ ላይ ይገኙ ነበር ። እነርሱም ፤ ስመ-ጥር
በሆኑት ደራስያን በእነ ኔክራሶቭ እና ሳልቲኮቭ-ሼ
ድሪን ይደገፉ የነበሩት እነ ቸርኒሼቭስኪይ እና ዶብ
ሮሉቦቭ ነበሩ ። የዚህ ሥነ-ጽሁፍ ትውልዶች ሰፋ ያ
ለ ማኅበራዊ አመለካከት የነበራቸው ሲሆኑ ፤ አመለካ
ከታቸውን ለመግለጽም ብርታት ነበራቸው ።

በ 19 ኛው ክፍለ-ዘመን አጋማሽ ላይ ይቀርቡ የነ
በሩት የሩስያ ልብ-ወለድ መጽሐፎች ለሩስያ ሥነ-ጽ

---

* ራዝኖቺንጽዕ (የተለያየ ማዕርግ እና መጠርያ
ያላቸው ሰዎች) ሩስያ ውስጥ በ 18 ኛው ክፍለ ዘመን
ማክተምያ እና በ 19 ኛው ክፍለ-ዘመን መባቻ ላይ
አንድ ራሱን የቻለ መደብ የማይወክሉ የኅብረተሰ
ቦች ክፋዮች የሆኑትን የካህናት ወገኖች ፤ የነጋዴ ወገ
ኖች ፤ የዝቅተኛ ቡርዧ ወገኖች ፤ የዝቅተኛ ሹማምንት
ወገኖች ያጠቃለለ መጠርያ ነው ። እነዚህ የኅብረተሰብ
ክፋዮች አብዛኛዎቹ በአዕምሮ ሥራ ተሠማርተው የ
ነበሩ ሲሆኑ ፤ የቡርዧ ዴሞክራሲያዊ እና የሬቮሉሺና
ዊ ዴሞክራሲ አይዲዮሎጂ አንቀሳቃሾችም ነበሩ ።
(ተርጓሚው)

ሁፍ ዝናን አስገኝተዋል ። ልብ-ወለድ መጽሐፎቹ የተ
ለያዩ እንደመሆናቸው ሁሉ ፤ ሁሉም መጽሐፎች ፤ መው
ጫ-መንገዱ ከጠፋበት የሩስያ ማኅበራዊ ኑሮ እንደም
ን ሊወጣ እንደሚቻል መንገድ-መንገዱን በመሻት
ያመለክቱ ነበር ። ይኸን የመሰለው ድርጊት ፤ በ 19 ኛው
ክፍለ-ዘመን ላይ የሶስዮ-ሳይኮሎጂ (ማኅበራዊ እና
ሥነ-ልቡናዊ) ልብ-ወለድ መጻሕፍትን በመጻፍ እጅግ
ስሙ-ጥር የሆኑትን እንደ ሌቭ ቶልስቶይ እና እንደ
ፌኦዶር ዶስቶየቭስኪይ የመሳሰሉትን ደራስያን ይመለ
ከታል (ከዚህም በስተቀር እነ ፑሽኪን ፤ ጎጎል ፤ ሌርሞ
ንቶቭ ፤ ቱርጌኔቭ እና ጎንቻሮቭ የተሰኙትን ቀደም ባ
ለው ጊዜ የነበሩትንም ደራስያን ይመለከታል) ።

ማክሲም ጎርኪይ ክላሲካል ለሆነው ለሩስያ የሥ
ነ-ጽሁፍ ማኅበራዊ ወግ ከፍተኛ ዋጋ ይሰጥ ነበር ።
እንደውም ፤ ሥነ-ጽሁፍን በሚመለከት ረገድ አንጋፋ
ወንድሞቹ የሆኑት ፤ በተለይም ቶልስቶይ እና ቼኾቭ
ውለታ የጣሉበት መሆናቸውን በይፋ ይገልጥ ነበር ።
ከእነርሱ የቀሰመው የሥነ-ጽሁፍን ጥበብ ብቻ አል
ነበረም ። ሩስያን እና ሩስያውያንን እንዲያውቅ ፤ የሩስ
ያውያንን መንፈሳዊ (spiritual) አኗኗር እና ሥነ-ል
ቡናዊ ምኞት ለመገንዘብ እንዲችል አብቅተውታል ።

እነሆ ስለዚህም ፤ ማክሲም ጎርኪይ የሩስያ ክላሲ
ካል ሥነ-ጽሁፍ ስሙ-ጥር ወጎችን ተከትሎ በማዳበር
የቀጠለ መሆኑን እንመለከታለን ። ይሁን እንጂ ፤ ከዚ
ሁ ጋር በአንድነትም አዳዲስ የድርሰት አደራረስ
ዘዴዎችን ፈጣሪ ፤ የሶቭየት ሥነ-ጽሁፍን መሥራች ነ
በር ። ጎርኪይ የክላሲካል እና የሶቭየት ሥነ-ጽሁፎችን
የሚያገናኝ «ህያው ድልድይ» ነው በማለት ከሶቭየት
ታላላቅ ደራሲዎች መካከል አንዱ የሆነው አሌክሴ
ይ ቶልስቶይ ተናግሮአል ። በአሁኑ ጊዜ ፤ ፑሽኪን የመ
ጀመርያው ሁኖ የሚገኝበትን የሩስያ ክላሲካል ደራ



ስያን የያዙትን ቦታ ለጎርኪይም ያለአንዳች ማመን
ታት ሰጥተነዋል ። ቀደም ባለ ጊዜው ባበረከታቸው
ድርሰቶቹ ውስጥ ፤ ከፑሽኪን እስከ ቼኾቭ ድረስ ይገ
ኙ የነበሩት ታላላቅ ደራሲዎቻችን ባሕርይ የሆነውን
ከመላው ብሔሮች እና ከመላው የሰው ልጆች ጋር
የወንድማማችነት መንፈስ የመመሥረት ስሜትን ይ
ሻ የነበረ 'መሆኑን በህሊናችን እንገነዘባለን ። የእኛን
የሩስያን ኅብረተሰብ ከሚመለከቱት ጉዳዮች ጎን-ለጎን
የመላው የሰው ልጆችን ጉዳዮች ፤ እንደዚሁም የግለሰ
ቦችን መብቶች እና ግዴታዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮ
ችን አንስቶአል ። የሩስያ ሥነ-ጽሁፍ በውስጡ ይዞት
ይገኝ የነበረው ይህ ባሕርይ ፤ በተለይም በቶልስቶይ
እና በዶስቶየቭስኪይ የቀረቡት ድርሰቶች በውስጣቸ
ው በያዙዋቸው እነዚህን መሳይ መልዕክቶች በዓለ
ም ላይ አድናቆትን እና ተቀባይነትን እንዲያገኙ አ
ድርገዋቸው ነበር ። ምንም እንኳን የቶልስቶይን እና
የዶስቶየቭስኪይን አመለካከቶች ጎርኪይ ያሄስ ቢሆን
ም ፤ የሰዎች ማኅበራዊ አኗኗር እንደምን በመሰለ
ሁኔታ እንደገና መደራጀት እንደነበረበት እነርሱ ያቀ
ርቡት የነበረውን አስተሳሰባቸውንም በመሠረቱ ይቃ
ወመው የነበረ ቢሆንም ፤ ምንም ጊዜ ቢሆን ፤ በተሟሟ
ቀ ክርክር ላይ በሚገኝበት ጊዜ እንኳን እነርሱን
ሲጠቅሳቸው ፤ የሰውን ልቡና ጠልቀው በመግባት እ
ና የታሪክ አጋጣሚዎችንም በሚገባ በመገንዘብ ረገ
ድ አንዳችም የሚስተካከላቸው የለም በማለት ይገል
ጻቸው ነበር ።

ጎርኪይ የሩስያ ሥነ-ጽሁፍን ግሩም ወግ ይከተል
የነበረ እና የአዳዲስ ነገሮችም ፈጣሪ ነው ስንል ፤ የሩ
ስያ ሥነ-ጽሁፍ በዕድገቱ የደረሰበትን አዲስ ምዕራፍ
ሊያስገኝ የቻለ እርሱ ብቻ ነበር ማለታችን አይደለም ።
ሂደቱ ቀስ-በቀስ ይከናወን የነበረ እና ውስብስብም

የሆነ ነበር ። ይኸንን በዓይነቱ ፍጹም አዲስ የሆነ
መጽሐፍ ጎርኪይ ሊጽፍ በነበረበት ዋዜማ ላይ (እ
ዚህ ላይ የምናወሳው ስለዚህ ስለሚያነብቡት መጽሐ
ፍ ነው ።) ደራስያን አዲስ ዓይነት የአጻጻፍ ገለጻ ዘዴ
ን ይሹ ነበር ። በ 1880 ዓ. ም. መጀመሪያ ላይ ፤ ለሩስያ
ሥነ-ጽሁፍ አድናቆትን ያስገኘ ፤ ታላላቅ ከሆኑት የሶ
ሻል እና የሳይኮሎጂ-ነክ ልብ-ወለድ መጻሕፍት መካከ
ል የመጨረሻ ማብቂያ የሆነው መጽሐፍ በዶስቶየ
ቭስኪይ ተጽፎ ነበር ። ዶስቶየቭስኪይ አረፈ ። ቱርጌኔ
ቭ ፤ የመጨረሻ ድርሰቱን ከጻፈ ስድስት ዓመታት በ
ኋላ አረፈ ። ቶልስቶይ ፤ «አና ካሬኒና» በሚል ርእስ የ
ጻፈውን ልብ-ወለድ መጽሐፉን በ 1877 ዓ. ም. ላይ የ
ጨረሰ ሲሆን ፤ «ትንሳኤ» በሚል ርእስ የጻፈውን መጽ
ሀፉን ግን እስከ 19 ኛው ክፍለ-ዘመን የመጨረሻው
ዓመት ድረስ ፤ ማለትም እስከ ሃያ ዓመት ድረስ ጽፎ
አልጨረሰም ነበር ። የቲያትር እና የአጫጭር ልብ-ወ
ለድ ታሪኮች ደራሲ የሆነው አንቶን ቼኾቭ ፤ ምንም
እንኳን ልብ-ወለድ ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ያስብ
የነበረ ቢሆንም ፤ አንዳችም ልብ-ወለድ ድርሰት አልጻ
ፈም ነበር ። ለመጻፍ ለሚፈልገው ልብ-ወለድ ድርሰት
በመጽሐፉ ውስጥ የሚያቀርበው ተስማሚ የሚሆን
የባሕርያት መሪ-ባሕርይ (hero) ልክ እርሱ በሚፈልገ
ው ዓይነት ለማግኘት (ለመፍጠር) ያልቻለ ሁኖ ስለአ
ገኘው ፤ ልብ-ወለድ መጽሐፍ ለመጻፍ ያልቻለ መሆኑ
ን ገልጾአል ። በእነዚያው ዓመታት ውስጥ ቶልስቶይ
«ትንሳኤ» በሚል ርእስ ያቀርበው ለነበረ መጽሐፉ
ቅር-አሰኚ የሆነውን ዲሚትሪ ኔኽሉዶቭ የተሰኘውን
መሪ-ባሕርይ ለመጽሐፉ የፈጠረ ሲሆን ፤ ይኸንን የፈ
ጠረውን ባሕርይ በመጽሐፉ ውስጥ ዋናው ተዋናይ
እያደረገ ያራምደው ጀመር ። በዚህ የቶልስቶይ የመጨ
ረሻው ልብ-ወለድ መጽሐፉ በሆነው እና እንደዚሁ



ም ለ 19 ኛው ክፍለ-ዘመንም የሩስያ የመጨረሻው ልብ-
ወለድ መጽሐፍ በሆነው በዚህ መጽሐፉ ውስጥ ሬ
ቮሉሺናዊ የሃሳብ መልዕክት ይገኝበታል ። ምንም እ
ንኳን ቶልስቶይ እስከሕይወቱ መጨረሻ ድረስ በሬቮ
ሉሺናዊ አሠራር ተግባሮች ኅብረተሰብን ማስተካከል
ን የሚቃወም ቢሆንም ፤ ብልህ በሆነ አዕምሮው ፤
ሬቮሉሺናዊ እንቅስቃሴዎች እንዲኖሩ የሚያደርጉ ኃይ
ላት ምን እንደሆኑ በጥልቀት በመመራመር ሊገነዘባ
ቸው ችሎአል ። ከዚህ በበለጠም የዚህ ሬቮሉሺናዊ
እንቅስቃሴ ዓይነተኛ አባላት የሆኑትን ፤ ስሜታቸውን
በቅን መንፈስ በመረዳት ያንጸባርቃቸው ነበር ።

በ «እናት» አማካይነት ጎርኪይ የተለመደውን የሩስ
ያ የልብ-ወለድ መጽሐፍ የአቀራረብ ዘር በአዲስ መ
ሬት ላይ ዘራ ። የሩስያ ሥነ-ጽሁፍ ሕይወት ሊታደስ
የሚችለው ይኸንን በመሰለ ሁኔታ ብቻ ነበር ። ይህ
መጽሐፍ የወዝ-አደሩን መደብ በሚመለከት ረገድ የተ
ጻፈ የመጀመርያው የሩስያ ልብ-ወለድ መጽሐፍ ነው ።
መጽሐፉም የወዝ-አደሩ መደብ የሰው ልጅ በታሪኩ
ያከማቻቸውን መላውን ቆሳቁሳዊ እና መንፈሳዊ
ሀብቶች እንደነበሩ በመጠበቅ ሕዝቦችን ነፃ ለማ
ውጣት የሚችል ኃይል አድርጎት ቀርበዋል ። ማክሲ
ም ጎርኪይ በሩስያ ሥነ-ጽሁፍ ውስጥ አዲስ ባሕር
ይን (ጀግናን) አስተዋወቀ ። አዲስ የሆነ ኪነታዊ ዘዴን
ሳይቀበሉ ፤ በመጽሐፍ ውስጥ የሚፈጠሩ የታሪክ ገባ
ርያንን (ገባርያነ-ታሪክ) በአዲስ ዘዴ የሚቀርቡበት መን
ገድ ሳይፈጠር ፤ አዳዲስ የአደራረስ ዘዴዎች ሳይፈጠሩ ፤
ይኸንን ተግባር ማከናወን የማይቻል መሆኑ ግልጽ
ነው ።

ጎርኪይ «እናት» ን ከመጻፉ ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ
በሥነ-ጽሁፍ ዓለም የወዝ-አደሩ መደብ ተወካዮች ይ
ቀርቡ ነበር ። ይኸም ሁኔታ ይታይ የነበረው በሩስያ

ሥነ-ጽሁፍ ውስጥ ብቻ አልነበረም ። ለማስረጃም ያህ
ል ፣ ሁለት የእንግሊዝ ደራሲዎችን ለመጥቀስ ብቻ ፣
ቻርልስ ዲከንስ እና ጆርጅ ኢሊዮት ከጎርኪይ ቀደ
ም ብለው ስለወዝ-አደሩ መደብ ጽፈው ነበር ። የሌሎ
ች የአውሮጳ ሀገሮች ደራሲዎችም እንደዚሁ በተመሳሳ
ይ ሁኔታ ስለወዝ-አደሩ መደብ ጽፈዋል ። ጎርኪይ
ግን በደራሲነት ተግባሩ ወስዶት የነበረው እርምጃ
ሠርቶ-አደሩን ሰው ፍትሕ-አልባ የሆነ ሥርዓት ባለበ
ት ሁኔታ የሚበደል አድርጎ በማቅረብ ብቻ ሳይሆን ፣
ታሪክን ሠሪ እንደሆነ አድርጎ ፣ በጊዜው የሚታየውን
ማኅበራዊ ፍትሕ-አልባነት በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚታ
ገል ሰው አድርጎ በማቅረብ ጭምር ይጽፍ የነበረ
ደራሲ ነው ። ይኸንን በሚመለከት ሁኔታ ለዓለም ሥ
ነ-ጽሁፍ አርዐያ የተወ ሲሆን ፣ በእርግጥም አዳዲስ የ
ድርሰት ባሕርያትን የፈጠረ ነው ሊባል ይቻላል ።

ጎርኪይ ያከናወነው የሥነ-ጽሁፍ ተግባር በዕርግጥ
ም አስደናቂ ነው ። እንዲህ አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ
የተዋጣላቸው ደራሲዎች የመሆን ሁኔታ የሚያጋጥማ
ቸው ደራስያን ጥቂቶች ናቸው ። በ 20 ኛው ክፍለ-ዘመን
መጀመርያ ላይ ፣ ማለትም በሥነ-ጽሁፍ መድረክ ብቅ
ማለት ከጀመረ ከአሥር ዓመታት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ፣
የጎርኪይ ስም በመላው ዓለም ታውቆ-ተደንቆ ነበር ።
ይበልጥ የሚያስገርመው ደግሞ ፣ ይኸ ሊሆን የቻለ
ው እንደ ቶልስቶይ እና ቼኾቭን የመሳሰሉ ታላላቅ
ደራስያን በዚያን ወቅት ይገኙ በነበረበት ጊዜ መሆ
ኑ ነው ። አዲሱ ክፍለ-ዘመን ጎርኪይ ላይ ያተኩር
ጀመር ። እንደ ሄንሪ ኢብሰን ፣ በርናርድ ሾው ፣ አናቶል
ፍራንስ የመሳሰሉ ዝነኛ ደራስያን ምናልባትም አነስ
ባለ ሁኔታ የተደነቁ ሳይሆን አይቀርም ። ጎርኪይ ራ
ሱም ቢሆን የበቀለው «ከዝቅተኛው አዘቅት» ፣ ከኅብረተ
ሰብ መረማመጃ ሥር ሲሆን ፣ በኅፃንነቱ ፣ በለጋነቱ እና



በጎልማሳነቱ ጊዜ ደርሶበት ለነበረው ሥቃይ ፣ ዕድል-ፈ
ንታው ደርሶለት የካሰው እና ያቻቻለለት ይመስላ
ል ። አዲሱ ክፍለ ዘመን ተተብትቦ ይገኝበት የነበረው
ን የህልውና እንቆቅልሽ የሚፈታው እርሱ ይመስል ፣
ከአዲሱ ክፍለ ዘመን ምርጥ ሰዎች መካከል አንዱ
እነሆ እርሱ ነበር ።

ይሁን እንጂ ፣ ምንም እንኳን ተሸጋጋሪ (አላፊ) ቢሆ
ኑም አስደናቂ የሥነ-ጽሁፍ ታሪክ ፣ የስኬት ምልክት
የሚታይባቸው እጅግ ብዙ የድርሰት ማስረጃዎችን
ያበረክትልናል (ለሰባ ዓመቶች ያህል ሥራዎቹ አላፊ-ጠ
ፊ ሳይሆኑ መቆየታቸው ተጨባጭ ማስረጃዎች በመ
ሆናቸው ።) የጎርኪይ ሥራዎች ተዋጥተውለት የነበሩት
ከላይ በተጠቀሰው መንገድ አልነበረም ። የዚህም ምክ
ንያቱ ፣ ጎርኪይ የአዲሱን ፣ የሃያኛውን ክፍለ-ዘመን ዋና
መፍቻ-ቁልፍ የሆነውን የወዝ-አደሩን መደብ በመጨ
በጡ እና ለድርሰቶቹም ሁሉ ዋና መፍቻ-ቁልፍ አድ
ርጎ በመጠቀሙ ነው ። በ 20 ኛው ክፍለ-ዘመን ላይ
ሠርቶ-አደር ሰው ጉዳዮችን በቁጥጥሩ ሥር የሚያውል ፣
ሁኔታዎችን ለርሱ በሚያስፈልጉት አቅጣጫዎች የሚ
መራ ዋና ባሕርይ ሁኖ በታሪክ መድረክ ብቅ አለ ።
ማክሲም ጎርኪይ የጻፈው እና አርጋጅ-አውራጅ የሆ
ነው ለዚህ ሠርቶ-አደር ሰው ታሪክ ነው ። ይህንን
ተግባሩንም እጅግ በተሟላ እና ፍጹም ኪነታዊ
በሆነ ሁኔታ «እናት» በተሰኘው መጽሐፉ ላይ
አቅርቦ እንዳሳየው ያህል በሌሎቹ ድርሰቶቹ ላይ
አላቀረበም ።

እርግጥ ነው ፣ ይህ ተግባሩ በአንድ ጊዜ በአዕም
ሮው ውስጥ ሠርጾ የተገኘ ውጤት አይደለም ። በመጽ
ሐፉ ላይ የወዝ-አደሩን መደብ ምንነት ያሳየው
ቀስ-በቀስ ደረጃ-በደረጃ በመዝለቅ ነው ። ቀደም ሲል
«ከኅብረተሰብ ዝቃጭ አተላዎች» ላይ አጥልሎ በጻፉ

ቸው የአጫጭር ታሪክ ጽሁፎቹ ላይ በስተኋላ ጊዜ
ያቀረባቸውን የመጻሕፍቶቹን ባሕርያት ፍንጭ እንመ
ለከታለን ። በ 1890 ዓ. ም. ማብቂያ ላይ እና በ 20 ኛው
ክፍለ-ዘመን መጀመርያ ላይ ከፈጠራቸው መሪ-ባሕር
ያት እና ዋና-ዋና ንድፈ-ሃሣቦቹ ጋር በሚገባ ተቀራ
ኝቶ እናገኝዋለን ። ይኸውም ፤ የሶሻሊስት ዝንባሌ ስላ
ላቸው ሠርቶ-አደሮች «ሦስቶቹ» በሚል ርእስ በጻፈው
አጭር ልብ-ወለድ ድርሰቱ ፤ እንደዚሁም «አልባሌዎች»
እና «ጠላቶች» በሚል ርእስ ባቀረባቸው የቴያትር ድር
ሰቱ ላይም ይህንኑ አሳይቶአል ።

የ 1905 ዓ. ም. የሩስያ ሬቮሉሺን ጎርኪይን በደራሲ
ነቱ አዲስ እርምጃ እንዲራመድ ለማድረግ ያበቃው
አዲስ የዕድገት ምዕራፉ ነበር ። በዚህ ሬቮሉሺን ላይ
በበላይነት ቁሞ የነበረው የወዝ-አደሩ መደብ ነበር ።
ሬቮሉሺኑ ድል ሁኖ ነበር ፤ ይሁን እንጂ ፤ ወዝ-አደሮች
በተሸናፊነት ከመሰቃየት ይልቅ ድልን ለመቀዳጀት
የሚችሉ መሆናቸውን ሬቮሉሺኑ መረጃ-ማረጋገጫ ሁኖ
ላቸውም ነበር ።

ጎርኪይ ካቀረባቸው ሥራዎቹ ሁሉ እጅግ ስሙ-ጥር
የሆነውን እና በአጠቃላይም ከዓለም ሥነ-ጽሁፍ
ድርሰቶች መካከል ስሙ-ጥር የሆነውን ድርሰቱን
ያቀረበው በዚህ ሬቮሉሺን ዋዜማ ላይ ፤ በ 1903
ዓ. ም. ነበር ።

ይህ የጎርኪይ ልብ-ወለድ መጽሐፍ ተመሥርቶ
የተጻፈው በዕውነተኛ ድርጊቶች ላይ ነው ። በመጽሐ
ፉ ውስጥ ፤ በ 1902 ዓ. ም. ሶርሞቮ ላይ የተካሄደው «የወ
ዝ-አደሮች ቀን» (May Day) ሰልፍ ፤ የሶርሞቮ ፓርቲ ድር
ጅት ተግባሮች ፤ ሰላማዊ ሰልፉ ከተበተነ በኋላ የፓር
ቲው አባሎች ለፍርድ መቅረብ ይገኝበታል ። ጎርኪይ
ራሱ እንደዚህ በማለት አዘክሮአል ፡ — «ስለ ሠርቶ-አ
ደሮች አንድ ልብ-ወለድ መጽሐፍ ለመጻፍ ያሰብ



ኩት ሶርሞቮ ውስጥ ከተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ በኋ
ላ ኒዥኒ-ኖቭጎሮድ በተሰኘች ከተማ ውስጥ ነው ።
መጽሐፉን ለመጻፍ የሚያስፈልጉኝን ማቴርያሎች ወዲ
ያውኑ በመሰብሰብ እና በመመዝገብም ማከማቸት
ጀመርኩኝ ።» በሌላ አባባል ለማቅረብም ፤ የጎርኪይ ል
ብ-ወለድ መጽሐፍ አንድ ታሪካዊ የሆነ ዶኩሜንት
እንደማለት ነው ። ይሁን እንጂ ፤ ድርጊቶቹ ኪነታዊ በ
ሆነ ሁኔታ ከሀሳቡ አውጠንጥኖ እና አምጦ በፈጠ
ራቸው ሃሣቦች እንደገና ተቀናብረው የቀረቡ ናቸው ።
የድርሰቱ ባሕርያት ፒዮትር ዛሎሞቭ እና እናቱ ፈጥ
ሮ ያቀረባቸው የፈጠራ አቀራረቡ ናቸው ። ፈጣሪው
እንደሚመቸው አድርጎ ያቀረባቸው የፈጠራ ተዋንያ
ን ባሕርያቶቹ ናቸው ። በዚህም ሁኔታ ፤ «እናት» የተሰኘ
ው መጽሐፉ በ 1905 ዓ. ም. ሬቮሉሺን ዋዜማ ላይ የሩ
ስያ የሠራተኛ መደብ ያካሄዳቸውን የረዥም ትግሎ
ች ጠቅላላ መልክ ሰፋ ባለ እና አጠቃላይ በሆነ
ሁኔታ የቀረበ የኪነት ውጤት ሁኖ እናገኘዋለን ።

የጎርኪይ ሠርቶ-አደር ሰው ፤ በራሱ ሀገር ውስጥ
ለሚገኘው ለራሱ የሠራተኛ መደብ ብቻ የሚያስብ
ሳይሆን ፤ ለመላው ዓለም በጎነት የሚያስብ ሠርቶ-አደ
ር ሰው ነው ። የጎርኪይ ሠርቶ-አደር ሰው ፤ ሙሉ በ
ሆነ የቃሉ ትርጉም ተመራማሪ ምሁር ማለት ነው ።
ይህም ብቻ አይደለም ። የሚያስተውል እና የሚፈላሰ
ፍ የድርጊት ሰውም ጭምር ነው ። ድርጊቶችንም ብ
ቻውን አያከናውንም ። ድርጊቶችን የሚያከናውነው የሰ
ፊው ሕዝብ ተወካይ በመሆን ነው ። ድርጊቶቹን የሚ
ያከናውነው እጅግ ክቡር እና ሰብአዊ በሆኑ አስተሳ
ሰቦች ላይ በመመርኮዝ ነው ። ይህ «እናት» የተሰኘው
ልብ-ወለድ መጽሐፍ ፤ ለሩስያ የወደፊቱ የተሻሻለ ኑሮ ፤
የወዝ-አደሩን መደብ የትግሉ መሪ አድርጎ ያቀርባል ።
ከፍተኛ የሆነ አመለካከት ያለው መሆኑን በማረጋ

ገጥ ላይ ስለሚገኘው ስለ ወዝ-አደሩ መደብ የተጻፈ ልብ-ወለድ መጽሐፍ ነው ። የወዝ-አደሩ መደብ አባሎች እርባና ያላቸው መሆናቸውን እና የፖለቲካ እና የርዕዮተ-ዓለም ብስለታቸውም ገና ጮርቃ መሆኑን እንዲገነዘቡ ለማድረግ የሚያበቃቸው ፤ ለወዝ-አደሩ መደብ አባሎች የተጻፈ መጽሐፍ ነው ። መጽሐፉ በተጻፈበት ጊዜ ለሩስያ የወዝ-አደር መደብ እና ለመላው የሩስያ ሕዝብ አስፈላጊ መጽሐፍ ነበር ። «እናት» በሚል ርእስ ስለቀረበው ስለዚህ መጽሐፍ ሌኒን በ 1907 ዓ. ም. የሚከተለውን አስተያየት ሰጥቶበት ነበር ፡ — «እጅግ ጠቀሜታ ያለው መጽሐፍ ነው ። ሬቮሉሺናዊውን እንቅስቃሴ ለምን እንደተቀላቀሉት ሳይገነዘቡ እንደዚሁ የተቀላቀሉት ብዙ ሠርቶ-አደሮች ‘እናት’ ን ካነበቡ በኋላ ፤ ሬቮሉሺኑን ለምን እንደተቀላቀሉ ይገነዘባሉ ።»

የኪነት ሥራ የተሳካ ኅብር (harmony) ሊኖረው የሚችለው ባሕርያቱ ኅብር ስለአላቸው ሳይሆን ፤ ወይንም ድርጊቱ ኅብር ያለው በመሆኑ ሳይሆን ፤ የደራሲው ሥነ-ልቡናዊ አቋም ኅብር ያለው ሁኖ ሲገኝ ነው በማለት ቶልስቶይ አንድ ጊዜ የኪነትን ጉዳይ አስመልክቶ ተናግሮ ነበር ። የጎርኪይ ሥነ-ልቡናዊ አቋም «እናት» በተሰኘው መጽሐፉ ላይ ዋናይቱ ተዋናይት ባሕርይ ሁና በምትገኘው ኒሎቭና በተሰኘችው አማካይነት ይገለጻል ። «እናት» የተሰኘውን የመጽሐፉን መጠርያ የያዘች ፤ ይህች አንዲት ተራ ሠርቶ-አደሪት ሴት ነች ። ኒሎቭና ፤ በመጽሐፉ መጀመርያ ላይ ፤ በፋብሪካዎች ውስጥ ከአቅማቸው በላይ ከሚሠሩት እና እቤት ውስጥም ሰካራም በሆኑ ፀበኛ ባሎቻቸውም ከሚረገጡ-ከሚደበደቡ ብዙ መቶ የወዝ-አደሩ መደብ አባላት ከሆኑት እናቶች በመጽሐፉ መጀመርያ ላይ በምንም መንገድ የተለየች አይደለችም ። ይሁን እንጂ ፤



ልጅዋ ፓቬል የሠራተኞች መኖርያ በሆነው አካባቢ የነበረውን የኑሮ ሁኔታ እርግፍ አድርጎ በመተው ሬቮሉሺናዊ ሲሆን ፤ ኒሎቭናም የእርሱን አቋም በመከተል ከእርሱ ጋር ጎን-ለጎን መራመድ ትጀምራለች ። ኒሎቭና በመጽሐፉ ላይ የምታሳየው ግሥጋሴ ፤ ሬቮሉሺኑን የተቀላቀሉ መላው ሠርቶ-አደሮች ከሚያደርጉት ግሥጋሴ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ነው ። አንባቢ የኒሎቭናን ዓለም በዐይኖቿ አማካይነት የሚቃኝ ሲሆን ፤ ድርጊቶችንም እርሷ በምታቀርባቸው መመዘኛዎቿ አማካይነት በመመልከት በአንክሮ ያደንቃቸዋል ። ኒሎቭናን የልጅዋ የፓቬል ጓዶችም እናት ብለው ይጠሯት ነበር ። እነዚህ ሬቮሉሺናዊዎች ዕውነተኛ ወንድማማችነታቸውን የተገነዘቡት በእርሷ በኩል ፤ ለእናት ባላቸው አቋም በኩል ነበር ። በእርሷ አማካይነት ስለ መላው ሰዎች ወንድማማችነት ግንዛቤ ሊኖራቸው በቃ ። የፓቬል የቅርብ ጓደኛ የሆነው አንድሬይ ናኾድካ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚከተለውን ይናገራል ፡ — «ሁላችንም የአንዲት እናት ልጆች ነን ። ሁላችንም በመላው ዓለም የሚገኙ ሠርቶ-አደሮች ወንድማማችነት የማይናወጽ የጋለ የስሜት ማዕበል ውስጥ ተውጠን እንገኛለን ።» ገበሬው ሪቢንም ቢሆን ይኸንን ይገነዘባል ፡ — «ሰዎች አንድነታቸውን እንዲገነዘቡት ማድረግ ታላቅ ቁም ነገር ነው ። ብዙ ሚሊዮን ሰዎች አንተ የምታደርገውን ለማድረግ የሚሹ መሆናቸውን ስታውቅ ደግሞ ሁኔታው ልብህን ያገራዋል ።»

ኪነት ሰዎችን አንድ የማድረጊያ ዘዴ መሆኑን ስንገነዘብ ፤ በአጠቃላይ የጎርኪይን ሥራ ፤ በተለይም «እናት» በሚል ርእስ ያቀረበውን ልብ-ወለድ መጽሐፍ ከማድነቅ አንቆጠብም ። ቀደም ሲል እንደተናገርነው

ሁሉ ፤ «እናት» ስለወዝ-አደሩ መደብ ፤ በሰዎች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች ስለማሻሻል ጉዳይ የተጻፈ መጽሐፍ ነው ። ይህም ማለት ፤ መጽሐፉ የቀረበው ለወዝ-አደሩ መደብ ብቻ ሳይሆን ፤ በመላው ዓለም ለሚገኙ ሕዝቦችም ጭምር ነው ።

ፕሮፌሰር ቦሪስ ቡርሶቭ ።

# ክፍል አንድ

# 1

ከሠርቶ-አደሮች የመኖሪያ ሠፈር ከፍ ብሎ የሚገ
ኘው የፋብሪካ ጡሩምባ ፤ በጥቀርሻ እና በዘይት የተበ
ከለውን ቆሻሻ አየር ሰንጥቆ ው! ው! ው! በማለት በየ
ቀኑ ያጓራል ። የጡሩምባውን ጥሪ በማክበርም ፤ እንቅ
ልፋቸውን ገና ጠግበው ያልጨረሱ እና ፊታቸውንም
ያጨፋገጉ ሰዎች ግራጫማ ከሆኑት ትንንሽ ጎጆዎ
ቻቸው ውስጥ በመውጣት ልክ እንደደነገጠ በረሮ
ከው-ከው እያሉ በፍጥነት እርምጃ መንገዳቸውን ይዘ
ው ይጓዛሉ ። ብርዳማ በሆነው የማለዳ ጭለማ የእግ
ረኛ መንገዳቸውን ይዘው እና በቆሸሸ ዘይት የተበከ
ሉት ብዙ መብራቶች ብዥ-ብዥ በሚል ብርሃናቸው
መንገዱን እያበሩላቸው ቀዝቃዛ አቀባበል ወደሚያደ
ርግላቸው ወደ ፋብሪካው ትልቅ የድንጋይ ግንብ ቤ
ት ያመራሉ ። ጭቃው ከእግራቸው ሥር ጮቅ-ጮቅ
ይላል ። ገና ከእንቅልፉ የነቃ ሰው የሚያሰማውን ጎር
ናና ድምፅ በማሰማት አየሩን በባለጌ ፀያፍ ስድቦች
እንዲወረር ያደርጉታል ። ከዚሁ ጋር በአንድነትም ሌሎ
ች ድምፆች በማጀብ ይቀበሏቸዋል ፡ — እነዚህም ፤ የ
ፋብሪካው ከባድ የጩኸት ድምፅ እና ትሽ-ትሽ!
ትሽ-ትሽ! የሚል ድምፅ የሚያሰማው ተን ነው ። የቀ
ፈፋቸው እና የተኮሳተሩ የሚመስሉት ፤ ረዣዥም የሆ
ኑት እና የጠቆሩት የፋብሪካው ጪስ-ማውጫዎች ከሠ
ርቶ-አደሮቹ መኖርያ ሠፈር ከፍ ብለው እንደ ሞላ
ላ ግንዲላ ተጀንነው ተገትረዋል ።

ምሽት ላይ ፀሀይቱ ዘቅዘቅ በማለት በየቤቶቹ

መስኮቶች ቢጫማ የብርሃን ጨረሮቿን ስታንፀባርቅ ፤
ፋብሪካው ሠራተኞቹን ከድንጋያማ ሆድ-ዕቃው ውስ
ጥ እንደብረት ዝቃጭ በመዘርገፍ ተፍቷቸው እንደ
ገና የእግር መንገዱን ይያያዙታል ። — መልካቸው ጥ
ላሸት ተለቅልቆ ጠቁሮ ፤ የተራበው ጥርሳቸው ግጥጥ
ብሎ እና ከአካላቸው የሚወጣው ሙጫማ የሞተር
ዘይት ሽታም አየሩን አውዶት ወደየጎጆዎቻቸው የሚ
ያመራውን የእግር መንገድ ይያያዙታል ። እስከሚቀጥ
ለው ቀን ድረስ ሥራው ስላበቃ እና በየጎጆአቸው
ውስጥም እራት እና ዕረፍት የሚጠብቃቸው በመሆኑ
ምክንያት ፊታቸው ፈካ ማለት ብቻ ሳይሆን ደስተ
ኛም ይሆናል ።

የፋብሪካው ማሺኖች የሠርቶ-አደሮቹን ጉልበት
የሚበቃቸውን ያህል እንደሎሚ ከመጠጡ በኋላ አ
ሁን የዕለቱ የሥራ ጊዜ አክትሞአል ። አንዳችም ቀሪ
ምልክት ሳይተው ዕለቱ ሕይወትን ትቶ ነጉዶአል ።
ሕዝበ-አዳምም ወደ መቃብሩ ጉድጓድ የሚያመራ
ውን ጎዳና አንድ ዕርምጃ በተጨማሪ ተራምዶአል ።
አሁን ግን የሚሻው አረፍ ብሎ እ-ፎ-ይ! ማለትን እ
ና በትምባሆ ጭስ የታፈነ የመሸታ ቤት ሁካታን
ሲሆን ፤ ይኸውም ያረካዋል ።

እሁድ-እሁድ እና በበዓላት ቀናት ሰዎቹ እስከቀ
ኑ አራት ሰዓት ድረስ ይተኛሉ ። ከዚያም በኋላ ጨ
ዋዎች ናቸው የሚባሉ ባለትዳር ባሎችና ሚስቶች
ሁሉ ለሃይማኖት ግድ የለሾች የሆኑ ወጣቶችን በ
መዝለፍ የክት ልብሶቻቸውን እየለበሱ ወደ ቤተክር
ስቲያን ሊያስቀድሱ ይሄዳሉ ። ከቅዳሴ በኋላም ወደ
ቤታቸው በመመለስ ፒሮጊ* ከተመገቡ በኋላ እንደ
ገና እስከምሽት ተመልሰው ይተኛሉ ።

---

* ፒሮጊ — አምባሻ ፤ ቂጣ ማለት ነው ። (ተርጓሚው ።)



ለብዙ ዓመታት በሥራ ከመናወዝ የተነሳ ድካማ
ቸው ተከማችቶ አንጀታቸውን ምግብ እንዳይሻ ያደረ
ገው በመሆኑ ምክንያት ፤ ምግብ እንዲያባላቸው በማለት
ቆሽት የሚቀቅለውን ቮድካ በብዛት ይጠጣሉ ።

ምሽት ሲሆን በጎዳናዎች ላይ ይንሸራሸራሉ ። ምድ
ሩ ደረቅ በሆነበት ጊዜ እንኳን ባለላስቲክ ቡት መ
ጫሚያ ያለው ሁሉ ይኸንኑ መጫሚያውን ይጫማል ።
የምሽቱ የአየር-ንብረት ጃንጥላ የማያስፈልገው
ቢሆንም እንኳን ፤ ጃንጥላ ያለው ሁሉ ጃንጥላውን
ይይዛል ።

እርስ-በእርስ የሚተዋወቁት እንደተገናኙ ስለፋብሪ
ካው ፤ ስለማሺኖቹ ይነጋገራሉ ። በፋብሪካዎች ውስጥ
አለቃዎቻቸው የሆኑትን ካቦዎችም ይዘልፉአቸዋል ።
ከሥራቸው ጋር ግንኙነት ስለሌላቸው ስለአንዳችም
ነገሮች አያስቡም ፤ አያወሩምም ። አሰልቺ በሆኑት ቀናቶ
ቻቸው ውስጥ አልፎ-አልፎ የተድበሰበሱ የሃሣብ ነ
ጸብራቆች ከአዕምሮአቸው ብልጭ-ድርግም ይላሉ ። ወ
ንዶቹ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ከሚስቶቻቸው ጋር
የሚነዛነዙ ሲሆኑ ፤ ብዙውን ጊዜም ሚስቶቻቸውን
ይደበድቡዋቸዋል ። ወጣቶቹ ፤ አኮርዲዮን ወደሚጫወቱበ
ት ፤ የብልግና ዘፈኖችን ወደሚዘፍኑበት ፤ ዳንስ ወደሚ
ደንሱበት አስጸያፊ የሆኑ የብልግና ንግግሮች ወደሚ
ለዋወጡበት እና በሥካር ጥንብዝብዝ ወደሚሉበት
ወደየጓደኞቻቸው ቤቶች ወይንም ወደየመሸታ ቤቶች
ይሄዳሉ ። አድካሚ በሆነ ሥራ ውልቅልቃቸው የወጣ
በመሆኑ ምክንያት መጠጡ ቶሎ ብሎ ራሳቸው
ላይ ይወጣል ፤ ከደረታቸው ውስጥ-ለውስጥ ደግሞ
ምንነቱን ሊረዱት ያልቻሉት ነገር ልውጣ-ልውጣ
እያለ ይተናነቃቸዋል ። ስለዚህም ፤ ይኸንን ከመሰለው
ደስ-የማይል ስሜት ትንሽ ፋታ ለማግኘት በመሻት
እዚህ ግባ በማይሉት በረባ-ባልረባው ነገር ሁሉ ፀብ

በማንሳት እና እንደ ዱር-አራዊት አስፈሪ በሆነ ሁ
ኔታ በመጣላት ግብ-ግብ ይገጥማሉ ። የዚህም ውጤቱ
ደም መፋሰስን የሚያስከትል ድብድብ ነው ። ድብድ
ቡ አንዳንድ ጊዜ በከባድ የአካል ጉድለት የሚያበ
ቃ ሲሆን ፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የሞት አደጋን እስከ
ትሎ ያበቃል ።

በመካከላቸው የሚታየው የእርስ-በእርስ ሰብአዊ
ግንኙነታቸው የተመሠረተው በክፉ-አሳቢነት መንፈ
ስ ሁሉም ራሱን አድፍጦ በመጠባበቅ ላይ ነው ።
ይኸንን መሳዩ ስሜታቸውም በሥራ ብዛት ተበልቶ-
ተበልቶ እንዳለቀው አካላቸው ረዥም ዕድሜ የቆየ
በመሆኑ ፤ ከቶ ምንም ፈዋሽ መድሀኒት ሊገኝለት አይች
ልም ። ሰዎቹ የተወለዱት ከየአባቶቻቸው ከወረሱአቸ
ው ከእነዚህ የልብ ልክፍቶች ጋር በመሆኑ ይኸንን
ዓላማ-ቢስ የሆነ የጭካኔ ተግባራቸውን ይኸው ልክፍ
ታቸው እንዲገፉበት እየገፋፋቸው እስከዕለተ-ሞታቸው
ድረስ እንደጥላቸው አብሮአቸው እያንዣበበ ሲከተላቸ
ው ይኖራል ።

እሁድ-እሁድ ወጣቶቹ ወደቤት የሚገቡት ከመሸ
በኋላ ዘግይተው ነው ። ልብሶቻቸውም ተቀዳድደው ፤ በ
ቆሻሻ እና በጭቃ ተለውሰው ፤ ዓይኖቻቸው ደም አግ
ተው ጠቁረው እና አፍንጫዎቻቸውም ደም-በደም
ተለውሰው ነው ። አንዳንድ ጊዜ ጓደኞቻቸውን ደህና
አድርገው በቡጢ ስላደባዩዋቸው ፤ እንዲህ ነኝ እኔ!
በሚል ጉራ ተጀንነው ወደቤት ይገባሉ ። ሌላ ጊዜ
ደግሞ በኩርፊያ ለንቦጫቸውን ጥለው ፤ ተበሳጭተው
ወይንም በደረሰባቸው ውርደት የእልህ ሲቃ ይዞአቸ
ው ወደቤታቸው ይመለሳሉ ። የሰከሩ እና የሚያሳዝኑ ፤
ገደ-ቢሶች እና አሳፋሪዎች ናቸው ። አልፎ-አልፎ ከወ
ላጆች መካከል እናትየዋ ወይንም አባትየው ልጆቻ
ቸውን ጥንብዝ ብለው ሰክረው አጥር-ለአጥር ሲላተሙ ፤



ወይንም መሸታ ቤቱ ወለል ላይ ተዘርረው ያገኙአ
ቸዋል ። ከፍ-ዝቅ አድርገው በመስደብ በቮድካ የተነ
ከረ አካላቸውን በቡጢ እየደበደቡ እቤት ከወሰዱቸ
ው በኋላ ፤ እንደገና የማለዳው ጡሩምባ ጨለማውን
ሰንጥቆ ከማጓራቱ በፊት ትንሽ እንቅልፍ እንዲያገኙ
በማባበል እንዲተኙ ያደርጓቸዋል ።

ወላጆች ልጆቻቸውን የስድብ ናዳ ያወርዱባቸዋል ።
ያለርኅራኄም ይደበድቧቸዋል ። ይሁን እንጂ ፤ የወጣቶቹ
እርስ-በእርስ መደባደብ እና ፡ መስከር እንደ አንድ እ
ንደተለመደ የዘወትር ጉዳይ ተወስዶአል ። አባቶቻቸው
ም እንደነርሱ ወጣት በነበሩበት ጊዜ ተደባዳቢዎች
ነበሩ ። ጠጪዎችም ነበሩ ። በአባቶቻቸው እና በእናቶ
ቻቸው ይደበደቡ ነበር ። ህይወት ምንግዜም ይህንን
መሳይ ነበረች ። ይኸን መሳይዋ ሕይወት ፤ ከዓመት-ዓመ
ት በዝግታ እና ውሀ-ልኩን ሳይለቅ እንደሚጓዝ የደ
ፈረሰ ምንጭ ትፈስስ ነበር ። ማናቸውም ነገር ቢሆን
ጥልቀት ባላቸው ወጎች እና ልማዶች አስተሳሰብ ተተ
ብትቦ የተሳሰረ ከመሆኑም በስተቀር ፤ በየአንዳንዱ ቀ
ን ተመሳሳይ የሆነ ድርጊት በመደጋገም ይፈጸማል ።

አንዳንድ ጊዜ በፋብሪካው የሠፈራ መንደር አዳ
ዲስ ሰዎች ለመኖር ይመጣሉ ። አዲስ-መጤ በመሆና
ቸው ብቻ ፤ ለመጀመርያ ጊዜ በዚያ ያለውን ነዋሪ
ይማርካሉ ። ከዚያም በኋላ ቀደም ሲል ይሠሩባቸው
ስለነበሩት ቦታዎች በማውራት ስለእነርሱ አንድ የይ
ስሙላ ዝንባሌ በሌሎቹ ላይ ያድራል ። ወዲያውኑ
ግን ለእነርሱ ያለው ወረት አልቆ ነዋሪዎቹ ስለሚለ
ምዱቸው ከምንም አይቆጥሩዋቸውም ። አዲስ-መጤዎቹ
ከተናገሩት ለመረዳት እንደሚቻለው ፤ በየትም ቦታ ቢ
ሆን የሠርቶ-አደሮች ኑሮ ተመሳሳይ መሆኑ ግልጽ
ነው ። ይኸ ደግሞ እርግጥ ከሆነ ፤ ታዲያ ምን አዲስ
ነገር አለና ነው መወያየት የሚቻለው?

ነገር ግን ፤ ከአዲስ-መጤዎቹ መካከል አንዳንዶቹ
በዚህ የመኖርያ ሠፈር ተሰምቶ የማይታወቅ ወሬ
ያወራሉ ። ስለሚያወሩት ወሬ ፤ ልክ ነው-አይደለም በማ
ለት የሚከራከር የለም ። ሁሉም ፤ አሄ ፤ ይኸ እንኳን
እንዴት ሊሆን ይችላል ፤ በሚል የተጠራጣሪነት ስሜ
ት ዝም ብለው ወሬውን ያደምጣሉ ። አዲስ-መጤዎቹ
ባወሩት ወሬ አንዳንዶቹ ተበሳጭተው ፤ ሌሎቹ ደግሞ
ያልታወቀ ሥጋት ለራሳቸው በመፍጠር ነቅተው ይጠ
ባበቃሉ ። ሌሎቹ ደግሞ ቦግ-ድርግም በሚል ተስፋ
በመረበሻቸው ምክንያት ኑሮን የበለጠ ውስብስብ እ
ንዲሆን ያደረጉባቸውን እነዚህን የወሬ ማስጠንቀቂ
ያዎች ከአዕምሮአቸው ለማስወገድ የወሬው ሁኔታ ከባ
ድ ጠጪዎች እንዲሆኑ አድርጎአቸዋል ።

የሠፈሩ ነዋሪዎች በአንድ አዲስ-መጤ ላይ ከዚ
ህ ቀደም አይተውት-ለምደውት የማያውቁት ነገር ቢ
ያዩበት ይኸንን ሰው ረዘም ላለ ጊዜያት ሳይዘነጉት
ያስታውሱታል ። እነርሱን ስለማይመስል ስለማንኛውም
ሰው ምንነትም ይሠጋሉ ። ምንም እንኳን አስቸጋሪ
ቢሆንም ፤ ገና ያልተቀሰቀሰውን ቀፋፊ አኗኗራቸውን
ምስቅልቅሉን ስለሚያወጣባቸው የሚፈሩት ይመስላሉ
ዓይነቶች ናቸው ። በማንኛውም ጊዜ መጠኑ እኩል
በሆነ ሁኔታ የኑሮ ጭንቅን ተሸክመው መቆየት የለ
መዱ በመሆናቸው እና ከዚሁ ሁኔታ የሚላቀቁበት
ተስፋ የሌላቸውም በመሆኑ ማናቸውም ለውጥ ሥቃ
ያቸውን የባሰ ያንርባቸው መስሎአቸው በእርግጥ ያ
ምናሉ ።

አዳዲስ ሃሣቦችን የሚያቀርብ ማንንም ሰው ሠር
ቶ-አደር ሕዝቦች በዝምታ ከእነርሱ ያርቁታል ። ስለ
ዚህም ፤ አዲስ መጤዎቹ ብዙውን ጊዜ ከዚህ ቦታ
ለቀው ይሄዳሉ ። አልፎ-አልፎ በዚህ ቦታ የሚኖሩ
ባይታጡም እንኳን አኗኗራቸውን ልክ እንደሌሎቹ



አመሳስለው ይኖራሉ ። ወይንም ደግሞ ከሌሎቹ ለብቻ
ቆፈንግጠው በገለልተኛነት ይኖራሉ ...

አንድ ሰው ይህንን የመሰለ ኑሮ ለሃምሳ ዓመታ
ት ያህል ከኖረ በኋላ ይሞታል ።

2

መላ ሰውነቱን ፀጉር የወረረው ፤ አመለካከቱ ጭ
ፍግግ ያለ በመሆኑ የቀፈፈው ፤ በተጠራጣሪነት የሚመ
ለከቱ ትናንሽ ዐይኖች ያሉት እና የቅንድቦቹን
ሽፋሽፍቶችም በአጓጉል አመለካከት ከፍ-ዝቅ የሚያ
ደርጋቸው ሚኻኢል ቭላሶቭ የተሰኘው ሜካኒክ ይኸ
ንን የመሰለ አኗኗር ይኖራል ። ፋብሪካው ውስጥ ከ
ሚሠሩት ሁሉ በችሎታው እጅግ የተደነቀ ሜካኒክ
ሲሆን ፤ በሚኖርበት አካባቢም እጅግ ጠንካራ የሆነ
ጉልበታማ ሰው እርሱ ነው ። ከበላይ አለቆቹ ጋር
ግን የማይስማማ በመሆኑ ምክንያት የደሞዝ ዐበሉ
ዝቅተኛ ነው ። በማንኛው የበዓል ቀን ከአንዱ ካገኘ
ው ሰው ጋር በመጣላት ያንን የተጣላውን ሰው አ
ፈር-መሬት አስግጦ ስለሚለቀው ሰው ሁሉ የጠላው
እና የፈራው ነው ። እርሱንም በተራቸው ለመደብደብ
ብዙዎች ሞክረዋል ። ነገር ግን የሚሞክርላቸው አይ
ደለም ። እርሱን ለመደብደብ የሚቃጣ ማናቸውንም
ሰው ባየ ቁጥር ፤ ቭላሶቭ አጠገቡ ያገኘውን ድንጋይ ፤
ወይንም ፍልጥ እንጨት ፤ ወይንም የብረት ቆመጥ
አፈፍ አድርጎ በመጨበጥ እና እግሮቹንም አንፈራጦ
ጦ በመከፈት ሊመታው የቃጣውን ሰው ቆሞ ይጠ
ብቀዋል ። በፀጉር የተወረሩት እጆቹ እና ፊቱ ፤ ከዐይኖ
ቹ አንስቶ እስከ አንገቱ ድረስ ተንዠርግጎ የወረደ
ው ጥቁር ጢሙ ማንንም የሚያስበረግግ ነው ። ሰዎ

ች ግን በተለይ የሚፈሩት ዐይኖቹን ነው ፡ — ዐይኖ ቹ ትናንሾች ናቸው ። ነገር ግን በጥልቀት አተኩረው የሚመለከቱ ስለሆኑ ፤ በሌላው ሰው አዕምሮ ውስጥ ጠልቀው የሚገቡ ይመስላሉ ። እነዚሁኑ ዐይኖቹን የተ መለከተ ማንም ሰው ቢሆን ፤ በሃሣቡ የሚያሰላስለው ፤ አንዳችም ፍርሀት የሌለበት እና ይቅርታ-ቢስ ከሆነ አጥቂ አውሬ ፊት የቆመ መስሎት ነው ።

«እናንት የውሾች ልጆች! ድራሻችሁ ይጥፋና ፤ አት ጠፉም ከዚህ!» በማለት በጢም ከተከበቡት ከናፍሮ ቹ ውስጥ በልዘው ቢጫ የሆኑ ፍልጥ-ፍልጥ የሚያ ካክሉ ጥርሶቹን ግጥጥ በማድረግ ጎርናና በሆነ ድም ፅ ይናገራል ። ከዚያም አጠገቡ የነበሩት ሰዎች ተነስ ተው በመሄድ ላይ ሳሉ የፈሪ ስድባቸውን ፈራ-ተባ እያሉ ይጣጥላሉ ።

«የውሾች ልጆች!» ይላቸዋል ፤ ዐይኖቹን ከጉድጓዶ ቹ እንደወስፌ አሹሎ በማውጣት እና በንቀት አመ ለካከትም በመመልከት እየተከተላቸው ። ከዚያም እነ ርሱን እየተከተለ እና ጭንቅላቱን ከፍ በማድረግም እንደሚከተለው ጮሆ ይናገራል ፡ —

«ታዲያስ ፤ ማነው መሞት የሚፈልግ?»

ማንም የሚፈልግ የለም ።

ቭላሶቭ ብዙ አይናገርም ። «የውሻ ልጅ» የሚለው ስድቡ ግን ተወዳጅ የሆነ አባባሉ ነው ። ፖሊሶችን ፤ ባለሥልጣኖችን ፤ የፋብሪካውን አለቆች ለመስደብ የ ሚጠቀምበት ቃል ይኸው ነው ። ሁልጊዜም ሚስቱን ይጠራት የነበረው ፡ — አንች ውሻ በማለት ነበር ።

«አንቺ ውሻ ፤ አታዩም እንዴ እዚህ ፤ ሱሪዬ እኮ ተቀድዷል!»

ልጁን ፓቬልን የአሥራ-አራት ዓመት ልጅ ሁኖ ሳለ ፤ የጭንቅላቱን ፀጉር ጨምድዶ በመያዝ አባቱ ወደላይ ሊያንጠለጥለው ፈለገ ። ፓቬል አንድ ት



ልቅ መዶሻ አፈፍ በማድረግ አነሳና በአጭሩ እንደ ሚከተለው ተናገረ ፡ —

«እንዳትነካኝ!»

«ምን አልክ?» አለ አባትየው ፤ ደመና ከሰማይ ሁኖ አንድን ትልቅ ነጭ ዛፍ ወደታች እያንዣበበ እንደ ሚንጎባለል ሁሉ ፤ ረዥሙን እና ሸንቃጣውን ልጁን ወደታች እየተመለከተ ።

«የሚበቃኝን ያህል ከዚህ በፊት ተደብድቤአለሁ ። ከእንግዲህስ ወዲህ አልደበደብም» አለ ፓቬል ። እናም መዶሻውን ከወዲያ-ወዲህ ያወዛውዝ ጀመር ።

አባትየው ልጁን ገልመጥ ብሎ እያየ በፀጉር የተወረሩ እጆቹን ወደጀርባው በማድረግ ፡ —

«እሺ ይሁን ...» አለ ፈገግ እንደማለት ብሎ ። ከዚ ያም በረዥሙ ተነፈሰ እና የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«ቆይ ግዴለም አንተ ፤ ውሻ ...»

ከዚያም ጥቂት ቆየት ብሎ ወደ ሚስቱ ዞር አለና የሚከተለውን ተናገራት ፡ —

«ከእንግዲህ ወዲህ ለቤት ወጪ አንዳችም ገንዘብ እንዳትጠይቂኝ ። ከአሁን በኋላ የሚቀልብሽ ፓቬል ነው ።»

«አንተ ደግሞ የምትቀበለውን ደሞዝ በሙሉ ልት ጠጣበት ነዋ?» በማለት ሚስቱ ስትፈራ-ስትቸር በቀስ ታ መለሰችለት ።

«ይኼ አንቺን የሚያገባሽ ጉዳይ አይደለም ፤ አንች ውሻ! ከፈለገኝ በላይሽ ላይ ውሽማ መወሸምም እች ላለሁኝ!» አላት ።

ውሽማ አልወሸመም ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከሞተ እስከ ሁለት ዓመት ጊዜ ድረስ ግን ልጁ ን የት ደረሰ ብሎ እንኳን ዞር ብሎም ያላየው ከመሆኑም በስተቀር ፤ ፈጽሞ አላነጋገረውምም ነበር ።

እንደርሱው ትልቅ እና ፀጉራም የሆነ ውሻ አለ

ው ። ሁልጊዜ ጧት በማለዳ እስከፋብሪካው ድረስ ተከትሎት የሚሄድ ሲሆን ፤ በምሽት ላይ ደግሞ ከፋብሪካው ደጅአፍ ላይ ቁሞ ይጠብቀዋል ። ቭላሶቭ የበዓላት ቀኖችን የሚያሳልፈው ከአንዱ መሸታ ቤት ወደ ሌላ መሸታ ቤት በመዞር ነው ። ከመሸታ ቤት መሸታ-ቤት በሚዞርበት ጊዜ አንዳችም ነገር አይናገርም ። በመንገድ ሲጓዝም አንዳች እቃ እንደጠፋው ሰው የአላፊ-አግዳሚዎቹን ሰዎች መልክ ከፍ-ዝቅ አድርጎ ይቃኛል ። ውሻውም ፀጉራማ ጭራውን እየቆላ ቀኑን ሙሉ ጌታውን በመከተል ከጌታው ሥር እንዘጭ-እንዘጭ ሲል ይውላል ። ቭላሶቭ ሰክሮ ወደ ቤቱ በመመለስ ለእራት ወደ ገበታ ሲቀርብ ውሻውንም ራሱ በሚመገብበት ሳሕን ያበላዋል ። አንድም ጊዜ ቢሆን ውሻውን ሰድቦትም ሆነ ወይንም መትቶት አያውቅም ። ይሁን እንጂ ደግሞ ፤ አንድም ጊዜ ቢሆን የጨዋታ ንግግር አሰምቶትም ሆነ አሻሽቶት አያውቅም ። ከእራት በኋላ ሚስቱ የማዕዱን ሳሕኖች ከማንሳት ዘግየት ካለች ፤ ሳሕኖቹን መሬት ላይ ይወረውራቸዋል ። ከዚያም ከፊት-ለፊቱ አንድ ጠርሙስ ቮድካ ያስቀምጥና ጀርባውን ለግድግዳው ሰጥቶ ዐይኖቹን በመጨፈን እና አፉን በሰፊው ከፍቶ በማዛጋት በተሳሰረ አፉ ዘፈን ለመዝፈን ያላዝናል ። ሪዙ ላይ የተንጠባጠቡትን የዳቦ ፍርፋሪዎች ለማራገፍ ሪዙን ሲነካካ አስጠሊታ የሆነ የዘፈን ዜማው ይበልጡኑ ይተሳሰርበታል ። የሚዘፍናቸው የዘፈን ግጥሞች ግልጽ ያልሆኑ እና በስካር በመንተባተቡ ምክንያትም የተሳሰሩ በመሆናቸው ዜማዎች ልክ በክረምት የሚያላዝኑ ተኩላዎችን ድምፅ ይመስላሉ ። ቮድካው እስካለቀ ድረስ ይዘፍናል ። ከዚያም ማልዶ የፋብሪካው ጡሩምባ እስኪነፋ አግዳሚው ወንበር ላይ ይንጋለላል ፤



ወይንም ጠረጴዛው ላይ ጭንቅላቱን ደፍቶ ያንቀላፋል ። ውሻውም አጠገቡ ይተኛል ።

የሞተው ፤ የደም ጋኑ በመፈንዳቱ ነበር ። ፊቱ ጥላት መስሎ ፤ ዐይኖቹ ተከድነው ጥርሶቹን እያፋጨ ለአምስት ቀናት ከአልጋው ሳይወርድ ቆየ ። አልፎ-አልፎ ሚስቱን እንዲህ በማለት ይጠይቃት ነበር ፡—

«ስናምፋር ስጪኝ ... መርዢኝ ...»

ዶክተሩ ሙቅ ውሃ በገላው እንዲይዝ አዝዞ ነበር ። ይሁን እንጂ ሚኻኢል ኦፔራስዮን መደረግ ስለአለበት አሁኑኑ ሆስፒታል መሄድ አለበት ብሎም አዝዞ ነበር ።

«ገደል ግባ! አንተ የውሻ ልጅ ፤ ያላንተ እጋዥነት እሞታለሁኝ!» በማለት ቭላሶቭ ለዶክተሩ መለሰለት ።

ዶክተሩ ከሄደ በኋላ ፤ ሚስቱ እያለቀሰች ኦፔራስዮን እንዲሆን ብትጠይቀው የእጅ ጣቶቹን አጣፍሮ ወደርሷ በማመልከት በስድብ መልክ እያወዛወዘ የሚከተለውን መለሰላት ፡—

«ወዮልሽ! ከበሽታዬ ብድን ፡— ሥቃይሽ እጥፍ-ድርብ ይሆናል!»

ጡሩምባው ሠራተኞችን ለሥራ በሚጠራበት ማለዳ ጧት ላይ ሞተ ። አፉ ተከፍቶ እና በግንባሩ ላይ አግድም ያገደሙት ሽብሽብ መሥመሮችም ደስተኛ ባለመሆን መልክ በመኰማተር ተሸብሽበው ፤ ቭላሶቭ ሬሳ-ሳጥኑ ውስጥ ተጋድሞአል ። ሚስቱ ፤ ልጁ ፤ ውሻው ፤ ዴሶቭሺኮቭ (አንድ በሌብነት የታወቀ እና ሠካራም የሆነ ከፋብሪካ የተባረረ ሽማግሌ ሰው) እና የመንደሩ ጥቂት ለማኞችም ጭምር በቀብሩ ሥርአት ላይ ተገኙለት ። ሚስቱ አንዳችም የልቅሶ ድምፅ ሳታሰማ ጥቂት እምባ አፈሰሰችለት ። ልጁ ፓቬል ግን ፤ ለቅሶም አላለቀሰም ፤ እንባም አላነባም ። እነዚህ ጥቂት ሰዎች ያጀቡት አስከሬን ሲያልፍ የተመለከቱት የመንደ

ሩ ነዋሪዎች እያማተቡ ከመካከላቸው ገሚሶቹ የሚከተለውን እርስ በርሳቸው ስለሟቹ ተነጋገሩ ፡ —

«ክፉ ሰው ነበር ። እሰይ! ኧረ እንኳን የሞተ ...»

ገሚሶቹ ደግሞ ፡ —

«ውሻ ነበር ፤ እንደ ውሻ ሞተ!» እያሉ ተነጋገሩ ።

አስከሬኑ ከተቀበረ በኋላ ፤ በቀብሩ ላይ የተገኙት ሰዎች ተመለሱ ። የሟቹ ውሻ ግን ትኩሱ መቃብር ላይ ቁጭ ብሎ መቃብሩን በፀጥታ ሁኖ በማሽተት ያነፈንፍ ነበር ። ከጥቂት ቀናት በኋላም የሟቹን ውሻ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው ገደለው ...

## 3

አንድ እሁድ ቀን ፤ አባቱ ከሞተ ሁለት ሳምንት በኋላ ፤ ልጅየው ፓቬል ቭላሶቭ ጥንብዝ ብሎ ሰክሮ ወደቤቱ መጣ ። ወደቤትም እየተንገዳገደ በመግባት እና ማዕድ ከሚቀርብበት ዋና ቦታ በመቀመጥ ልክ አባቱ ያደርግ እንደነበረው ሁሉ ፤ ጠረጴዛውን በጡጫ በመደብደብ ፡ —

«እራት!» እያለ ጮኸ ።

እናቱም መጥታ ከልጇዋ አጠገብ በመቀመጥ እጆቿን እላዩ ላይ ፤ ጭንቅላቱን ደረቷ ላይ ጋለል አድርጋ ያዘችው ።

«እማማ! ድረሺልኝ! ...» በማለት እጆቿን መነጨቃት ።

«የማትረባ ልጅ» በማለት እናቱም ለልጇዋ ባላት የመውደድ ስሜት እየተመለከተችው እጆቿን ሰበሰበች ።

«እስኪ ትምባሆ ልጠጣ! ስጪኝ የአባባን የትምባሆ መጠጫ ፒፓ!» በማለት ፓቬል በሠከረ አንደበቱ እየተንተባተበ ተናገረ ።



ከተወለደ ጀምሮ ለመጀመርያ ጊዜ መስከሩ ነው ። ቮድካው አካሉን አዝሎታል ። ይሁን እንጂ ፤ ህሊናውን አልሳተም ። እና በአዕምሮው ውስጥም የሚከተለው ጥያቄ ይመላለስ ጀመር ፡ —

«ሰክሬአለሁኝ እንዴ? ሰክሬአለሁኝ እንዴ?»

በእናቱ ርኅራኄ እና ለርሱም በማዘን ባሳየችው አመለካከቷ ተሸበረ ። ለቅሶ-ለቅሶ ከጀለው ። ይሁን እንጂ ከስካሩ የበለጠ የሰከረ በመምሰል እንባውን ለመግታት ራሱን በራሱ ታገለ ።

እናቱም የተመሳቀለ ፀጉሩን እያሻሸች በቀስታ አነጋገር ፡ —

«እንዲህ ያለ ነገር ማድረግ አያስፈልግህም ነበር» አለችው ።

ማጥወልወል ጀመረው ። ክፉኛ ካስታወከው በኋላ እናቱ አልጋው ላይ አስተኛችው እና የገረጣ ግንባሩ ላይ በቀዝቃዛ ውሀ የተነከረ ጨርቅ አስቀመጠችለት ። አሁን ትንሽ ስካሩ በረድ ያለለት መሆኑ የተሰማው ቢሆንም ፤ ራሱን ያዞረዋል ። የዐይኖቹ ቆቦች ከብደውት መክፈት አቅቶታል ። አፉ ውስጥ የቀረውን መራራ ጣዕም እያጣጣመ እና በዐይኖቹ ሽፋሽፍቶች መካከልም በጭላንጭል የእናቱን ሰፋ ያለ ፊት ባሻገር እያስተዋለ እንዲህ በማለት ያስብ ጀመር ፡ —

«እኔ ገና አሁንም ልጅ ነኝ መሰለኝ ። ሌሎቹ ይጠጣሉ ። ግን ምንም አይሆኑም ። እኔን ግን አጥወለወለኝ ...»

ቤቱ ውስጥ ራቅ ካለው ቦታ ፤ የእናቱ ለስላሳ ድምፅ እንደዚህ ሲል ተሰማው ፡ —

«ጠጪ መሆን ከጀመርክ ታዲያ እንዴት አድርገህ ነው እኔን የምትደግፈኝ?»

ዐይኖቹን ቀስ ብሎ ዘጋና ፡ —

«ሁሉም ይጠጣል» በማለት መለሰላት ።

እናቱም ቁና-ቁና ተነፈሰች ። ዕውነቱን ነው ። ሰዎ
ቹ ያችኑ ቅንጣት የምታህል ደስታቸውን አንጠፍ
ጥፈው የሚጨርሱበት ቦታ የመሸታ ቤት ብቻ እንደ
ነበር እርሷም ታውቃለች ። ያም ሁኖ ግን ፤ የሚከተለ
ውን ተናገረች ፡ —

«አንተ ግን መጠጣት የለብህም! አባትህ ለሁለታች
ሁም ከሚበቃ በላይ ጠጥቶአል ። ልጁ ፤ አባትህ የሚበ
ቃኝን ያህል አሠቃየኝ ... ደግሞ አንተም እኔ እናት
ህ እንድሰቃይብህ ነውን? ኧረ እንዴት?»

አሳዛኝ እና ለስላሳ የሆኑትን እነዚህን ከአንደበቷ
የሚወጡትን ቃላቶቿን በሚያዳምጥበት ጊዜ ፤ አባቱ
በሕይወት በነበረበት ጊዜ ፍጹም የማትናገር በመ
ሆኗ ፤ አባቱም ከአሁን-አሁን ይደበድባት እየመሰላት
በጣም ትፈራ የነበረች በመሆኗ የእናቱን በቤት ውስ
ጥ ሕልው ሁና መኖሯ እንኳን የማይታወሰው የነበረ
መሆኑን አሰላሰለ ። እርሱም ራሱ ቢሆን ፤ ከአባቱ ጋር
እንዳይገናኝ እቤት መዋልን በተቻለው ያስወግድ የነ
በረ በመሆኑ ፤ ከእናቱ ተነጥሎ አደገ ። አሁን ፤ ቀስ በቀ
ስ ስካሩ ሲበርድለት አተኩሮ እናቱን ይመለከት ጀ
መር ።

ቁመተ-ረዥም እና ከወደ ትከሻዋ ትንሽ ጎበጥ
ያለች ነች ። ከአንድ ነገር ጋር ትጋጭ መስሏት እንደ
ምትፈራ ሁሉ ፤ በከባድ ሥራ እና በባሏ ድብደባ የጎ
በረው እና የተሰባበረው የሠራ አካላቷ ቀጥ ማለቱ
ቀርቶ የጎድን የአግድሞሽ ዘመም ብሎአል ። ሰፋ
ያለ ክብ ፊቷ ሽፍሽፋቶች አበጅቶ ተጨማድዶአል ።
ዐይኖቿም የፍርሃት እና የሥጋት መልክ ያረበበባቸ
ው ሲሆኑ ፤ ሁኔታቸውም በሠፈሩ ውስጥ እንደሚኖሩት
እንደ አብዛኛዎቹ ሴቶች ዐይኖች ሁኔታዎች ነው ። በቀ
ኝ ቅንድቧ በኩል ከፍ ብሎ አንድ ጎርጎድ ያለ ቁ
ስል ጠባሳ ትቶላት አልፎአል ። ይኸ ጠባሳዋም ቅንድ



ቧን ወደላይ ትንሽ ከፍ እንዲል የሳበው በመሆኑ ፤
ከግራ ጆሮዋ ይልቅ የቀኝ ጆሮዋ ከፍ ብሎ የተሰቀለ
እንዲመስል አድርጎታል ። ይኸም ሁኔታ ፤ ሁልጊዜ በመ
ሥጋት ምክንያት በተጠንቀቅ ሁኖ የሚጠባበቅ ሰው
መልክ ያላት እንድትመስል አድርጎአታል ። ጥቅጥቅ ያ
ሉት ወፋፍራምና ጥቁር ፀጉሮቿ አልፎ-አልፎ በሽበ
ት ተወርረዋል ። ሁለንተናዋ ለስላሳ ፤ አዘንተኛ እና ት
ሁት ነው ...

ከዐይኖቿ የእንባ ዘለላዎች ኩልል እያሉ በጉንጮ
ቿ ላይ ፈሰሱ ።

«አታልቅሺ! ዝም በይ ። እምጠጣው ስጪኝ» በማለት
ልጅዋ ጠየቃት ።

«ውሀ በበረዶ አመጣልሀለሁኝ» አለችው ።

ይሁን እንጂ ውሀውን እስክታመጣ እርሱ ዱሮ
ተኝቶአል ። የውሀው ጭልፋ በእጅዋ ላይ እየተንቀጠ
ቀጠ እና በረዶውም እየሟሟ ለጥቂት ደቂቃ ቆማ
ተመለከተችው ። ከዚያም ጭልፋውን ጠረጴዛ ላይ
አስቀመጠችና እቤቷ ግድግዳ ላይ ከተሰቀሉት ከቅዱ
ሳን ስዕሎች ፊት በተመስጦ እና በፀጥታ ተንበረከ
ከች ። ውጪ ካለው መንገድ አኳያ የሠከሩ ሰዎች
ድምፅ በመስኮቱ በኩል ሲያስተጋባ ይሰማል ። ወራቱ
በልግ በመሆኑ ፤ ሰማይ-መሬቱ ላይ የተጋገረውን
ድቅድቅ ጭለማ የአኮርዲዮን የሙዚቃ ድምፅ ሰንጥ
ቆት ያልፋል ። አንዱ በመጮህ ይዘፍናል ። ሌላው
ደግሞ አስነዋሪ የሆኑ ፀያፍ ስድቦችን ያዥጎደጉዳል ።
የፈሩ እና የደከሙ ሴቶች ሲጮኹ ድምፃቸው ይሰ
ማል ።

በእነ ቭላሶቭ ትንሽ ቤት የሚታየው የለኗኗር
ሁኔታ ከቀድሞው ይበልጥ የተረጋጋ እና
ጸጥታ የሰፈነበተ ነው ። ከሌሎቹ በአካባቢው ከሚ
ገኙት ቤቶች ውስጥ ከሚታየው የአኗኗር ሁኔታም

የተለየ ነው ። የእነርሱ መኖርያ ቤት ይገኝ የነበረው
ረግረጋማ ወደሆነው ቦታ በሚያመራው መንገድ በኩ
ል አድርጎ ሲሆን ፣ ምንም እንኳን ይኸ ቤታቸው የ
ተሠራው ጉብታማ ቦታ ላይ ባይሆንም ኮራ ብሎ
ደረቱን ከነፋ ቦታ ላይ ከሚገኘው ከሰፈሩ በስተመ
ጨረሻ አኳያ በስተራስጌ በኩል ነው ። ከቤቱ ስፋት
ሩቡን ያህል የማዕድ ቤቱ የያዘው ሲሆን ፣ እናቲቱ
የምትተኛበት ክፍልም በስተጥግ በኩል በትንሽ ክ
ፍል ተከፍሎአል ። የተቀረው የቤቱ ሁለት-ሦስተኛ
ደግሞ ሁለት መስኮቶች ያሉት እና ባለ አራት ማ
ዕዘን ሁኖ የተሠራ ነው ። አንደኛው ጥግ ላይ የፓቬ
ል አልጋ ተዘርግቶበታል ፣ ሌላው ጥግ ደግሞ ጠረጴ
ዛ እና ሁለት አግዳሚ ወንበሮች ተዘርግተውበታል ።
የተቀሩት የቤት ዕቃዎች ፡— ጥቂት ወንበሮች ፣ ትንሽ
መስተዋት እላዩ ላይ ያለበት የልብስ ኮሞዲኖ (ቁም
ሳጥን) ፣ ልብስ ያለበት ሰንዱክ ፣ ግርግዳ ላይ የግርግዳ
ሰዓት እና በቤቱ በስተጥግ በኩል ደግሞ ሁለት የ
ሚፀለይባቸው ቅዱሳን ስዕሎች ግርግዳው ላይ ተሰ
ቅለው የሚገኙት የቤት ዕቃዎች ናቸው ። የቤታቸው
ዕቃ ይኸው ነው ።

ፓቬል ፣ አንድ ወጣት ያደርገው ዘንድ የሚገባውን
ሁሉ ያደርጋል ፡— አኮርዲዮን ፣ ከደረቱ ላይ በአሚዶ
የሚደርቅ ሸሚዝ ፣ ብሩኅ ቀለም ያለው ከራቫት ፣ የላስቲ
ክ ቡት ጫማ እና ከዘራ ገዝቶ ነበር ። በዚህም ምክ
ንያት በእርሱ ዕድሜ የሚገኙትን ወጣቶች ይመስላል ።
የምሽት የግብዣ ቦታዎች የሚሄድ ከመሆኑም በስተቀር
ተወዳጅ የሆኑትን ካድሪል እና ፖልካ የተሰኙትን
የዳንስ ውዝዋዜዎች በሚገባ አጥንቶአል ። እሁድ-እሁ
ድ እቤቱ የሚገባው ሰክሮ ነው ። ቮድካ ሲጠጣ ግን
ሁል ጊዜም ያጥወለውለዋል ። ሰኞ-ሰኞ ጧት ከእንቅ
ልፉ ይነሳ የነበረው እራስ ምታት ይዞት እና ልቡን



ም ቃር-አቅሮት ሲሆን ፊቱም ጥውልግ በማለት ደ
ብቶት ነው ።

እናቱ አንድ ጊዜ የሚከተለውን ጠየቀችው ፡—

«እህ ፣ ታዲያስ ፣ የትላንትናው ምሽት ጥሩ ነበርን?»

እርሱም ጨፍግጎት እና ቀፎት እንደሚከተለው
መለሰላት ፡—

«ኧረ ተይኝ ፣ እንደው ባታነሺብኝ ይሻላል! መጠጡ
ን ትቼ አሣ ባሠግር ይሻለኛል ። ወይንም ጠመንጃ
ገዝቼ አደን ባድን ይሻለኛል ።»

አንዳችም ቀን ከሥራ ቦታው ሳይተጓጎል ፣ ወይን
ም ዘግይቶ በመሄድ የገንዘብ ቅጣት ሳይቀጣ ሥ
ራውን በትጉህነት ይሠራል ። በጠባዩ ዝምተኛ ሲሆን ፣
ሰማያዊ ቀለም ያላቸው ዐይኖቹ ደግሞ እንደ እናቱ
ዐይኖች ትላልቅ ናቸው ። አመለካከታቸውም የተጠራጣ
ሪነት አመለካከት አላቸው ። አደን የሚያድንበት ጠመ
ንጃ አልገዛም ። አሣ ለማስገርም አይሄድም ። ይሁን
እንጂ ፣ ሌሎቹ የሚዘልቁትን የአኗኗር ጎዳና እርሱ
የተወ እና ያፈነገጠ መሆኑ ግልጽ ሁኖ ይታይ ጀ
መር ። ወደ ምሽት የግብዣ ቦታዎች የሚሄደው አል
ፎ-አልፎ ሲሆን ፣ እሁድ-እሁድ ወደቤት ይመለስ የነበ
ረውም ምንግዜም ሳይሰክር ሆነ ። የልጅዋ ፊት እየመነ
መነ የሚሄድ ፣ ዐይኖቹ ይበልጥ የአስተዋይነትን አመለ
ካከት እየተመለከቱ እና ሁለቱ ከናፍሮቹም ግጥም
ብለው አንድ ቀጭን መስመር ይመስል የመጋጠም
ሁኔታ ማሳየት የጀመሩ መሆናቸውን አትኩረው አስተ
ዋይ የሆኑት የእናቱ ዐይኖች ሁኔታውን ተገነዘቡ ። አንዳ
ች ነገር አበሳጭቶት ፣ ወይንም ደግሞ በሽታ አካሉን
እየመጠመጠው በመሄድ ላይ ይመስላል ። ቀደም ባ
ለው ጊዜ ፣ ጓደኞቹ እርሱን ለማየት ብዙውን ጊዜ
እቤት ይመጡ ነበር ። አሁን ግን ፓቬል ብዙውን
ጊዜ እቤት የማይገኝ ሁኖ ስላገኙት አዘውትረው መ

ምጣታቸውን ተው ። ልጅዋ ፤ ፋብሪካውቹ ውስጥ እንደ ሚሠሩት እንደሌሎቹ ወጣቶች ባለመሆኑ እናቱ ተደ ስታለች ። ይሁን እንጂ ፤ የተለመደውን ድፍርስ የአኗኗ ር ሁኔታ ገሸሽ አድርጎ ለመተው ከባድ ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑን በመመልከቷ ደግሞ ምክ ንያቱን ያልተገነዘበችው ባዶ ፍርሀት በልቧ ውስጥ አደረባት ።

አንዳንድ ጊዜ በሚከተለው ሁኔታ ትጠይቀዋለች ፡ —

«ፓቬል ፤ አሁን እርግጥ ጤና ነህ?»

እርሱም እንደሚከተለው ይመልስላታል ፡ —

«ፍጹም ጤና ነኝ!»

እርሷም በረዥሙ ከተነፈሰች በኋላ ፡ —

«በጣም ከስተሃል!» ትለዋለች ።

መጻሕፍቶችን ማምጣት ጀመረ ። ያመጣቸውን መጻ ሕፍትም ሳይታይበት ለማንበብ ይጥራል ። ካነበባቸ ውም በኋላ ይደብቃቸዋል ። አንዳንድ ጊዜም ከመጻሕ ፍቱ ላይ ምንባብ በወረቀት ይገለብጥና ወረቀቱን ይደብቃል ።

እናት እና ልጅ የሚተያዩት በጣም አልፎ-አልፎ ሆነ ። ጨርሶ አይነጋገሩም ሊባል እስከሚቻልበት ደ ረጃ ድረስ ዝም ይባባሉ ጀመር ። ጧት ሻዩን በፀጥ ታ ጠጥቶ በቀጥታ ወደሥራ ቦታ ከሄደ በኋላ ቀትር ላይ ለምሳው ይመጣል ። ማዕድ ላይ ብቻ የሚወያዩ ሲሆን ፤ ማዕድ ከተነሳ በኋላ ወጥቶ ሂዶ እስከምሽት ይቆያል ። ማታ ተመልሶ ሲመጣም ከተጣጠበ በኋላ እራቱን ይበላ እና የመጻሕፍት ንባቡን ይቀጥላል ። እሁድ-እሁድ ማለዳ ተነስቶ ከቤት ይወጣል ። ወደ ቤት ተመልሶ የሚገባው አምሽቶ ነው ። ወደ ከተማ መውጣቱን እና አንዳንድ ጊዜም ቲአትር ቤት የሚገባ መሆኑን እናቱ ታውቅ የነበረች ብትሆንም ፤ ከከተማ እርሱን ለማየት የሚመጣ



ግን አንዳችም ሰው አልነበረም ። ከጊዜ-ጊዜ ከመናገ ር የመቆጠብ ሁኔታው ከፍ-ከፍ እያለ ሄደ ። እርሷ ልትረዳቸው የማትችላቸውን ቃላቶች በንግግሩ ውስጥ ጣልቃ እያገባ ታገኘው ጀመር ። ቀደም ሲል ይጠቀም ባቸው የነበሩትን ተርታ የሆኑ የሃሣብ አገላለጾቹንም ከጊዜ-ጊዜ እርግፍ አድርጎ የተወ ሁኖ ተሰማት ። አዳዲስ የሆኑት የጠባዮቹ ሁኔታዎች ለእርሷ ጉልህ ሁነው ይታዩዋት ጀመሩ ፡ — በእዩኝ-እዩኝ ባይነት የመሽቀርቀር አለባበሱን ትቶ ፤ ለሰውነቱ እና ለልብሱ ጽዳት ቅድሚያ ይሰጥ ጀመር ። አካሄዱ ቄንጥ የማያ ወጣለት ነፃ የሆነ የግዴለሽ አካሄድ ሆነ ። በጠባዩም ያልተኮፈሰ እና ያልተገበዘ ሆነ ። የእነዚህ ሁኔታዎች ምክንያቶች ምን እንደሆኑ እናቲቱን ያሳስባት ጀመር ። ለእርሷ የሚያሳየው ሁኔታም ጨርሶ አዲስ ዓይነት ሁኔታ ሆነ ፡ — አንዳንድ ጊዜ የቤታቸውን ወለል ያ ጥባል ። ሁልጊዜ እሁድ-እሁድ አልጋውን የሚያዘጋጅ እርሱ ሲሆን ፤ በማናቸውም ሁኔታ እናቱን ለማገዝ ይሞ ክራል ።

አንድ ቀን ስዕል አመጣና ግድግዳው ላይ ሰቀለ ው ። በስዕሉ ላይ ተስሎ የነበረው ሦስት ሰዎች በተ መስጠ እየተነጋገሩ በጎዳና ላይ ሲጓዙ የሚያሳይ ስዕ ል ነበር ።

የስዕሉንም ምንነት ፓቬል እናቱን ሲያስረዳት ፡ —

«ከመቃብር ያረገው ክርስቶስ ወደ ኤማሁስ ሲሄድ ነው» አላት ።

ስዕሉ ለእናቱ በጣም አስደሰታት ። ነገር ግን የሚከ ተለው ሃሣብ በአዕምሮዋ ውስጥ መመላለስ ጀመረ ፡ —

«ክርስቶስን እንደዚህ በከፍተኛ ሁኔታ የሚያፈቅር ከሆነ ፤ ለምን ቤተ ክርስቲያን አይሄድም?»

የፓቬል ወዳጅ የሆነው አናጢ በሠራው የሚያም ር የመጻሕፍት መደርደርያ ላይ ያሉት መጻሕፍት ብ

ዛታቸው ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ሄደ ። የቤታቸውም ክፍል ደስ የሚያሰኝ ይዞታ ኖረው ።

ብዙውን ጊዜ እናቱን የሚጠራት «እርስዎ» በሚል የአክብሮት አጠራር እና «እማማ»በማለት ሲሆን ፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ይበልጥ በማቆላመጥ «እናትዬ» እያለ ይጠራታል ፡ —

«እናትዬ ስለእኔ እንዳታስቢ ። ዛሬ ወደቤት የምመለሰው ትንሽ አምሽቼ ነው» አላት ።

ይኽ አባባሉ ደስ አሰኛት ። አንድ ጠንከር ያለ እና ቁም ነገራም የሆነ ጉዳይ እንዳለ ከአነጋገሩ ተገንዝባለች ።

ይሁን እንጂ ፤ ሥጋቷ ከጊዜ-ጊዜ እየጨመረ ሄደ ። የመሥጋቷ ምክንያቶች ይበልጥ ተጨባጭ ሁነው አይደለም ፤ ያም ሁኖ ግን ከዚህ ቀደም ተደርጎ ባልታየ አዳዲስ ሁኔታው ምክንያት ልቧ አልረጋ ይላት ጀመር ። አንዳንድ ጊዜ በልጅዋ ትከሻ እና ከዚያም የሚከተለውን ዓይነት ሃሣብ በአዕምሮዋ ውስጥ ታመላልሳለች ፡ —

«ለምንድነው ጠባዩ እንደሌሎቹ ሰዎች ያይደለው? ጠባዩ እንደመነኩሴ ነው ። ይኽንን ዓይነት ጠባይ ደግሞ በእርሱ እድሜ ባሉ ሰዎች የሚታይ አይደለም ።»

እንደገና ሌላ ሃሣብ በአዕምሮዋ ውስጥ ይጉላላል ፡ —

«ምንአልባትም አንዲት የሚወዳት የልጃገረድ ጓደኛ አግኝቶ ይሆናል ።»

የልጃገረድ ጓደኛ ለመያዝ ደግሞ ገንዘብ ያስፈልጋል ። ከደሞዙ ጥቂት ብቻ ለኪሱ አስቀርቶ ቀሪውን በሙሉ የሚሰጠው ለእናቱ ነው ።

እና ይህን በመሰለ ሁኔታ ሳምንታት እና ወራት ለሁለት ዓመት እየተፈራረቁ አለፉ ። እንዲህ ደብዛው ባልታወቀ አስተሳሰብ ፤ እንዲህ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ በሚሄድ የእናት ጭንቀት ፤ እንዲህ ከዚህ ቀደም ባልተለመደ እንግዳ በሆነ እና በፀጥታ በተመላ ኑሮ ሁለት ዓመት አለፈ ።



4

አንድ ምሽት ከእራት በኋላ ፓቬል የመስኮቱን መጋረጃ ዘጋና ፋኖሱን ከሚቀመጥበት ወንበር በላይ ከፍ አድርጎ ግድግዳ ላይ በምስማር በመስቀል ከወደ ጥግ በኩል ቁጭ ብሎ ማንበብ ጀመረ ። እናቱ ከማዕድ የተነሱትን ሳሕኖች ማዕድ ቤት ወስዳ ካጣጠበች በኋላ ድምጿን ሳታሰማ ቀስ ብላ ወደ እርሱ ተጠጋች ። ፓቬልም ከተቀመጠበት ቦታ ሁኖ ራሱን ቀና አደረገና በማተኮር ሁኔታ ይመለከታት ጀመር ።

«አይ ፤ ምንም አይደል ፓሻ* ፤ እንደው እንዲሁ ነው የመጣሁት» በማለት ወዲያው በፍጥነት ለአመለካከቱ መልስ ከሰጠችው በኋላ በመሸበር መንፈስ የዐይኖቿን ሽፋሎች ክፍት-ዝግት እያደረገች ወደ ማዕድ ቤቷ ተመልሳ ሄደች ። ይሁን እንጂ ፤ እዚያም ሄዳ አልቆየችም ። ለጥቂት ጊዜ ከሃሣቧ ጋር ተሟገተችና ሳህን ያጠበችባቸውን እጆቿን ተጣጥባ እንደገና ወደርሱ ዘንድ መጣች ።

«ይህ የምታነበው ነገር ምንድነው እያልኩኝ ለመጠየቅ ሁልግዜም ልቤ ይፈልጋል ። ለመሆኑ እንደዚህ የምታነበው ምንድነው?» በማለት ቀስ ብላ ጠየቀችው ።

---

* ፓሻ — ፓቬል የሚለውን ስም ማቆላመጫ ነው ። እናት ልጅዋን በማቆላመጥ እከልዬ እንደምትለው ያለ ። (ተርጓሚው ።)

ፓቬል የሚያነበውን መጽሐፍ አጠፈው ።

«ነይ ቁጭ በይ ፤ እናት...» አላት ።

እናቱም የጉዳዩን ምንነት ለማወቅ በጉጉት በመጠባበቅ ሁኔታ ከወገቧ ቀና ብላ ተቀመጠች ።

ፓቬልም ቀስ ባለ አነጋገሩ ኮስተር ብሎ እና የእርሷንም ፊት ሳይመለከት እንደሚከተለው ተናገረ ፡ —

«የማነብበው የተከለከሉ መጻሕፍቶችን ነው ። እነዚህ እኔ የማነብባቸው መጽሐፍቶች የእኛን የሠርቶ-አደሮችን ሁኔታዎች ዕውነቱን አፍርጠው የሚናገሩ በመሆናቸው እንዳናነብባቸው ተከልክለዋል ። እነዚህ መጻሕፍቶች የሚታተሙት ማንም ሳያውቅ በምሥጢር ነው ። መጻሕፍቶቹን ይዤ ብገኝ እሥር-ቤት ይከትቱኛል ። ዕውነትን ለማወቅ ስለምሻ እሥር-ቤት ይከትቱኛል ማለት ነው ። ገባሽ?» አላት ።

እናት ድንገት ትንፋሿን መተንፈስ ተሳናት ። ዐይኖቿን ገለጥ አድርጋም ልጅዋን ትመለከተው ጀመር ። ሌላ ሰው እንጂ ውነትስ እርሱ ልጅዋ ነው ብላ ማመንም ተሳናት ። ሲናገር ድምፁ ከቀድሞው የተለየ ነበር ። ጥልቀት ነበረው ። ወዝ ነበረው ። አጣጣል ነበረው ። ሳይበዛ አነስ ብሎ እላይኛው ከንፈሩ ላይ የተደመደመ ሪዙን በእጣቶቹ ከወዲያ-ወዲህ እያሻሸ ከተቀመጠበት ጥግ ያለውን ቦታ በመገረም አመለካከት ያማትር ነበር ። እናት የልጅዋ ጉዳይ አሳሰባት ። አዘነችበት ።

እንዲህ በማለትም ጠየቀችው ፡ —

«ፓሻ ፤ ምነው ልጄ ፤ ለምንድነው ይኼንን ማድረግህ?»

ፓቬልም ራሱን ቀና አደረገና ተመለከታት ። ከዚያም ፡ —



«ዕውነትን ለማወቅ ስለምሻ ነው» በማለት በረጋ መንፈስ እና በዝግታ መለሰላት ።

ድምፁ ለስለስ ያለ ቢሆንም ጠንካራ አወራረድ ነበረው ። ዐይኖቹም ከጉድጓዶቻቸው ወጥተው በአትኩሮት ፊት ለፊት ይመለከቱ ነበር ። አንድ ምሥጢራዊ እና አሥጊ ከሆነ ጉዳይ ጋር ለምንጊዜውም የተቆራኘ መሆኑን ተገነዘበች ። ወደድኩም-ጠላሁ የሚያጋጥመኝ ነገር ሁሉ መድረሱ የማይቀር ነበር በሚል ዕምነት ነገሮችን ሳታሰላስል እንዳመጣጣቸው የምትቀበል በመሆኗ ምክንያት ፤ በከፍተኛ ሀዘን እና ጭንቀት ልቧ ተሰበረ ። የምትናገረው መላ-ቅጡ ጠፋት ። እንደው ዝም ብላ እንባዋን ማንባት ቀጠለች ።

«አታልቅሺ» በማለት በቀስታ እና በርኅራኄ የማባበል አነጋገር ፓቬል ተናገራት ። ለእርሷም ይኼ አባባሉ እንግዲህ ደህና ሰንብቺ ያላት መስሎ ተሰማት ።

«እናቴ ፤ የምንኖረው ኑሮ ምን ዓይነት እንደሆነ እስቲ ዝግ ብለሽ አስተውይው! ይኸውና ዕድሜሽ አርባ ዓመት ነው ። ለመሆኑ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ያሳለፍሺው ኑሮ ፤ ኑሮ ነው ይባላልን? አባቴ ይደበድብሽ ነበር ። አባቴ በሕይወት በነበረበት ጊዜ ለምን ይደበድብሽ እንደነበር አሁን ልገነዘበው በቅቻለሁኝ ። በኑሮው ላይ ደርሶበት የነበረውን ምሬቱን ፤ ቁጭቱን እና ብስጭቱን ሁሉ ይወጣ የነበረው በአንቺ ላይ ነበር ። ኑሮው ከባድ ስለነበረ ጭንቱ ፤ ሸክሙ ይሰማው ነበር ። ኑሮውን እንዲህ እንዲከብድ ያደረገው ምን እንደሆነ ግን ለመገንዘብ አልቻለም ነበር ። እዚህ አሁን አለንበት ሠፈራችን ሠላሳ ዓመት ሙሉ በባርነት አገለገለ ። ሥራ መሥራት የጀመረው ፋብሪካው ገና ያኔ ሁለት የመሥሪያ ክፍሎች ብቻ በነበሩት ጊዜ ነበር ። አሁን ግን ፋብሪካው ሰባት ክፍሎች አሉት!»

ሥጋት ቢያድርባትም እንኳን ንግግሩን በጥሞና አዳመጠችው ። የልጅዋ ዐይኖች ደስ በሚያሰኝ ብሩኅ አመለካከት ኅላ-ኅላ ብለው ከጉድጓዳቸው ወጥተው ነበር ። ደረቱን ጠረጴዛው ላይ አስደግፎ እና በእንባ የታጠበውን ፊቷን ቀረብ ብሎ የዕውነትን ምንነት በሚመለከት ረገድ እስካሁን የተገነዘበውን በዚህ የመጀመርያ ንግግሩ አሰማት ። ባልተቆጠበ የወጣት ጉልበቱ ፤ የማወቅ ጽኑ ፍላጎት ያደረበት ተማሪ ስለቀሰመው ዕውቀት ኮርቶ እና በቀሰመው ዕውቀትም አምኖበት ለርሱ ግልጽ ሁነው የታዩትን ጉዳዮች በንግግሩ አማካይነት እንደሚያሰማ ሁሉ ፤ ፓቬልም የመጀመርያ ንግግሩን ለእናቱ ያሰማት በዚህ ሁኔታ ነው ። እርሱነቱን ከመፈተን ይልቅ እናቱን በማረጋጋት ለማሳመን ሲል ንግግሩን ያቀረበው አጠር አድርጎ ነው ። ቃላት አጥረውት ከንግግሩ ጋብ ባለ ጊዜም ፤ ከፊት-ለፊቱ በሀዘን ተኮማትሮ የተደቀነው የእናቱ ፊት ፤ በሃዘን እና በአድናቆት የሚመለከቱት ፤ ሊፈስሱ በተዘጋጁ ድቅን እንባዎች የታጀቡት የእናቱ ዓይኖች አተኩረው ይመለከቱታል ። ለእናቱ አዝኖአል ። እንደገና ያሰማው ንግግር ስለእርሷ እና ስለኑሮዋ ነው ።

«በሕይወትሽ ተደስተሽ ታውቂያለሽ? እስከአሁን በኖርሽው ዘመንሽ ትዝ የሚልሽ እና ቀደም ሲል ያሳለፍሽው ጥሩ ጊዜ የት አለና ነው?»በማለት ጠየቃት ።

እርሷም ፤ በሀዘን የተሠበረ ልቧን ያቀፈላት የሚመስል እና ደስታም ሀዘንም የተቀላቀለው እንግዳ ስሜት ተሰምቷት እያዳመጠችው ባዘንተኛ መንፈስ ፤ ዕውነትክን ነው በሚል ሁኔታ ራሷን ነቀነቀች ። ስለርሷ ኑሮ ይኸንን በመሰለ ሁኔታ ካሁን ቀደም የተናገረ አንድም አልነበረም ። እነዚህ የልጅዋ ቃላቶችም ለረዥም ጊዜያት ተረስተው የቆዩ ስሜቶቿን ቀሰቀሱ



ባት ። ሊሞት የተቃረበውን እና ኑሮ ጣዕም-የለሽ መሆኑን ፣ የሚያስታውሷትን እነዚያን የወጣትነት ጊዜ ስሜቶቿን እና ፍላጎቶቿን እንደገና ከልጅዋ አንደበት የተሰሙት ቃላቶች ቀሰቀሱባት ። በወጣትነቷ ጊዜ ለልጃገረድ ጓደኞቿ ስለ ኑሮ አኗኗር ታወራላቸው ነበር ። ስለማንኛውም ሁኔታ በሰፊው ታወራ ነበር ። ቢሆንም ሁሉም ጓደኞቿ እና እርሷም ጭምር ኑሮአቸውን እንዲህ ከባድ እንዲሆን ያደረገውን ምክንያት ለማወቅ ሳይሹ ፤ ከባድ በመሆኑ ብቻ ይበሳጩ ነበር ። አሁን ልጅዋ አጠገቧ ተቀምጦ የሚገኝ ሲሆን ዐይኖቹ ፤ ፊቱ እና አንደበቱ ያቀረቡት ገለጻዎች ፤ የእናቱን የኑሮ ሁኔታ ደህና አድርጎ የተገነዘበው ይኼ ልጅዋ ፤ ይኼ ስለአለባት ሥቃይ የሚያዋያት እና ያዘነላት ልጅዋ ልቧን በኩራት ስሜት እጅጉን ነካው ።

ለእናቶች አይታዘንላቸውም ።

ይኸንን ታውቃለች ። ስለሴቶች ኑሮ ልጅዋ የተናገረው መራር እና የተለመደ የሆነውን የአኗኗር ዕውነት ሲሆን ፤ ከአሁን ቀደም ሰምታው የማታውቀው የማባበል እና የማጽናናት ድርብ ስሜቶች ልቧን ነኩት ።

«ምን ለማድረግ ነው የምትሻው?» በማለት ንግግሩን አቋርጣ ጠየቀችው ።

«መጀመርያ እኔ እማራለሁ ። በኋላ ደግሞ ሌሎችን አስተምራለሁ ። እኛ ወዝ-አደሮች መማር ያስፈልገናል ። ኑሮአችንን እንዲህ ከባድ እንዲሆን ያደረገው ምን እንደሆነ ውስጠ-ምሥጢሩን ፈልገን ማግኘት እና መገንዘብ አለብን» በማለት መለሰ ።

ሁልጊዜም ጠንቃቃ እና ኮስታራ የሆኑት ሰማያዊ ዐይኖቹ አሁን ለስላሳ እና ሩኅሩኅ በሆነ አመለካከት ተመልተው በማየቷ እጅጉን ደስ አላት ። በተሸበሸቡት ጉንጮቿ ላይ አሁንም እን

ባዎቿ ኩልል እያሉ የሚፈስሱ ቢሆኑም ፤ ከናፍሮቿ በፈገግታ ተሞልተዋል ። የኑሮን መራራነት ደህና አድርጎ የቀመሰው ልጅዋ በአንድ በኩል የኩራት ስሜት ሲያሳድርባት ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ገና ወጣት ሁኖ ሳለ አነጋገሩ ግን እንደማናቸውም እንደሌሎቹ ሰዎች ባለመሆኑ ፤ እንደዚሁም ሌሎቹ ሰዎች እና እር ሷም ጭምር ችለው የተቀበሉትን የኑሮ ሁኔታ እር ሱ ለመቃወም በመነሳሳቱ ስሜቷ በመነካት ከሁለት ተከፈለባት ። እንደሚከተለው ልትናገረውም ቃጣት ፡ — «ታዲያ ብቻህን ምን ማድረግ እችላለሁ ብለህ ነው ፤ ልጄ ሆይ?»

ይሁን እንጂ ፤ እንዲህ በድንገት ብልህ ሁኖ ያገኘ ችው እና ምንነቱንም ልትረዳው ላልቻለችው ለዚህ ለልጅዋ ያላት አድናቆት ይቀነስባት መስሏት ስለሠጋ ች ያሰበችውን መጠየቁን ተወችው ።

ፓቬል የእናቱ ከናፍሮች በፈገግታ ተመልተው ፤ ፊቷ በአድናቆት ተውጠ ፤ ዐይኖቿ በፍቅር ዐይን ሲያ ዩት ተመለከተ ። የቆመለትን ዕውነት ልትገነዘብለት እንድትችል ለማድረግ የበቃ ሁኖ ገመተ ። ከአንደበቱ የሚወጡት ቃላት ተደማጭ መሆናቸው በራሱ ተማማ ኝ እንዲሆን በማድረግ የወጣትነት ኩራት አሳደሩበት ። አንዴ እየሳቀ ፤ አንዴም እየተኮሳተረ በስሜት ተውጦ ይናገር የነበረ ሲሆን ፤ አንዳንዴም ከአንደበቱ የሚወጡ ትና የጥላቻ ስሜቱን የሚገልጽባቸው ቃላቶች ስልታ ቸውን እየሳቱ የእንቅጥቃጤ ሁኔታ ያሳዩ ነበር ። እናት ፤ ራሷን በመነቅነቅ የሚከተለውን መለሰችለት ፡—

«ወይ ጉድ ፤ ገዳዩ እንዲህ ነው እንዴ ፤ ፓሻ?»

እርሱም ሲመልስላት ፡ —

«አዎን እንዲህ ነው!» ያላት ከመሆኑም በስተቀር ፤ በጎ ተግባር ለመፈጸም ጥረት ያደርጉ የነበሩ ሰዎች ፤ በሰፊ ሕዝቦች መካከል የዕውነትን ዘር የሚዘሩ ሰዎ ች ፤ ሕይወትን እና ኑሮን ተቀናቃኝ በሆኑ ጠላቶች እንደ አውሬ እየታደኑ ወደእሥር ቤት የሚወረወሩ እና በባርነትም ወደ ግዞት ቦታ የሚጋዙት ብዙ ብ ዙ ሰዎች መሆናቸውን ነገራት ።

«እነዚህን የመሳሰሉ ታጋዮችን አይቻለሁኝ! የዓለምን ምሬት የሚያጣፍጡ ጨው ናቸው!» በማለት በጋለ ስሜት ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ።

እነዚህን የመሳሰሉት ሰዎች ሁኔታቸው በሃሣቧ መጥቶ አስፈራራት ። አሁንም ሁኔታቸውን «ወይ ጉድ ፤ ለካ እንዲህ ያሉ ሰዎች ናቸው?» በማለት ልጅዋን ለመጠየቅ ፈለገች ። ይሁን እንጂ አላደረገችውም ። ልክ ነው ብላ ባለመወሰን እና በተጠራጣሪነት ስሜት እ የተነፈሰች ማንነታቸውን ልትገነዘባቸው ስለማትችለው ፤ ይሁን እንጂ እንዲህ አደገኛ የሆኑ ነገሮችን እን ዲናገር እና እንዲያስብ ልጅዋን ያስተማሩ እነርሱ መሆናቸውን ስላወቀቻቸው ስለእነዚህ ሰዎች ምንነት ሲያወራላት በዝምታ ታዳምጠው ጀመር ። በመጨረሻም የሚከተለውን ተናገረችው ፡ —

«ሊነጋ ምንም አልቀረውም ። ወደአልጋህ ሂድና ትንሽም ቢሆን ተኛ ።»

«እሺ እተኛለሁ» በማለት መለሰ ። ከዚያም ፤ ወደር ሷ ራሱን ደፋ አድርጎ ፡ — «የነገርኩሽን ተረድተሽ ዋልን?» አላት ።

«አዎን!» አለችው በረዥሙ ተነፈሰችና ። እንደገና እንባዎቿ ይፈስሱ ጀመር ። ድንገትም ተንሰቅስቃ አለ ቀሰች ። ከዚያም ፡ — «መጥፊያህ ነው ፤ ልጄ!» በማለት ተናገረች ።

ከተቀመጠበት ብድግ አለና በክፍሉ ውስጥ ተንጎ ራደደ ። እንደሚከተለውም መለሰላት ፡ —

«ይኸው እንግዲህ ምን እንደማደርግ እና የት እንደምሄድ ታውቂያለሽ ። ሁሉንም ነገር ነግሬሻለሁኝ ።

እናት ፤ እኔን የምትወጂኝ ከሆነ ፤ ይህን አርግ ፤ ይህን አታርግ እያልሽ እንዳታስቸግሪኝ እለምንሻለሁኝ!»
እርሷም ለቅሶዋን በመቀጠል ፡—
«ምነው የኔ ልጅ ፤ የኔ ሸጋ ። ምንአልባት ... ምንአልባትም እኮ ይኸንን ሁሉ ነገር ባትነግረኝ ኖሮ ይሻለኝ ነበር!» አለችው ።
እጅዋን በእጆቹ ጨብጦ ያሻሽ ጀመር ።
«እናት» የሚለውን ቃል በተናገረበት ጊዜ ባሳየው ሞቃት ስሜት እና ካሁን ቀደም አድርጎት በማያውቀው እጅዋን በማባበስ የማሻሸት ሁኔታ እጅጉን አድርጎ ልቧ ተነካ ።
«ይህን አርግ ይህን አታርግ በማለት አላስቸግርህም!» አለችው በእንባ ሲቃ በተመላ ንግግር ። «ብቻ ተጠንቀቅ ። ልብ አድርግ ብያለሁኝ ተጠንቀቅ!» አለችው ።
ከምን መጠንቀቅ እንዳለበት የማታውቅ በመሆኗ በሀዘን ሁኔታ ዐይን-ዐይኖቹን እየተመለከተችው ዳግመኛም የሚከተለውን ተናገረች ፡—
«ከሳትህ ከጊዜ-ጊዜ እየጨመረ ይሄዳል ...»
ጠንካራ እና ረዥም አካሉን አጥብቃ አቀፈችውና በእናትነት የርኅራኄ ፍቅር እየተመለከተችው እንደገና የሚከተለውን ወዲያውኑ በቀስታ ተናገረችው ፡—
«ላንተ ትክክል መስሎ እንደታየህ ኑር ። እኔ በዚህ በኩል ምንም አላስቸግርህም ። አንድ ነገር ብቻ እጠይቅሀለሁኝ ፡— ከምትገናኛቸው እና ከምታወራቸው ሰዎች ተጠንቀቅ ። ሰዎች ክፉ ስለሆኑ መፍራት አለብህ ። እርስ-በእርሳቸው ይጠላላሉ ። እርስ-በእርሳቸው የሚመቀኙ እና የሚቀናኑ ከመሆናቸውም በስተቀር ፤ ለመጎዳዳትም ይሻሉ ። አንድ ጊዜ እጣትህን በነርሱ ላይ አመልክተህ ከወቀስካቸው ይጠሉሃል! ያጠፉሃልም!» አለችው ።
እነዚህ በጭንቀት የተመሉ ቃላቶች ከአንደበቷ እየወጡ ሲነገሩ ልጅዋ ከክፍሉ በራፍ መዳረሻ ላይ ሁኖ ያዳምጣል ። ንግግሯን እንደጨረሰችም ፈገግ በማለት የሚከተለውን ተናገረ ፡—
«ልክ ነሽ ። ሰዎች መጥፎዎች ናቸው ። ይሁን እንጂ ፤ በዓለም ላይ ዕውነት መኖሯን ስገነዘብ ፤ የሰዎች መጥፎነትም ከዚሁ ጋር በአንድነት ተሻሽሎ ታየኝ ።»
ከዚያም እንደገና ፈገግ አለና ንግግሩን እንዲህ በማለት ቀጠለ ፡—
«እንዴት እንደዚህ ሊሆን እንደቻለ ግን አላውቅም ። ገና ሕፃን ልጅ በነበርኩበት ጊዜ ሁሉንም ሰው እፈራ ነበር ። ከዚያም በዕድሜ ከፍ ካልኩኝ በኋላ ሁሉንም ሰው እጠላ ጀመር ። አንዳንዶቹን መጥላት የጀመርኩት የአውሬነት ባሕርይ ስለነበራቸው ሲሆን ፤ ሌሎቹን ደግሞ ለምን እጠላቸው እንደነበረ አላውቅም ። አሁን ግን ሁሉም ነገር ተለውጦ ይታየኛል ። ምናልባትም በዚህ ምክንያት ይሆናል ለሰዎች የማዝነው ። ሆነም-አልሆነም ፤ ሰዎች የአውሬነት ባሕርይ ያላቸው ስለሆኑ ፤ ወቀሳው ሁልግዜም በእነርሱ ላይ መዥጎድጎድ እንደሌለበት በተገነዘብኩኝ ጊዜ ግን ልቤ ይራራላቸው ጀመረ ...» በገዛ ራሱ ውስጥ አንዳች ድምፅን የሚያዳምጥ ይመስል መናገሩን አቋረጠ ። ከዚያም ረጋ ብሎ እና በሃሣብ ባሕር ጠልቆ የሚከተለውን ተናገረ ፡—
«ይኸውልሽ ፤ የዕውነት እስትንፋስ ይህ ነው!» አላት ።
«እግዚአ መሀረነ ክርስቶስ! ልጄ ፤ አስጊ በሆነ ሁኔታ ተቀያይረሃል!» አለችው ።
ልጅዋ እንቅልፍ ይዞት በተኛ ጊዜ ፤ እናቱ ከአልጋዋ ላይ ቀስ ብላ ተነሳችና ወደርሱ ድምፅ ሳታሰማ ሄደች ። ቀይማ የሆነው ፤ ግትር እና ቁጡ ፊቱ በነጭ የትራሱ ልብስ ላይ ተጋድሞ በጀርባው ተኝቷል ። አንዳችም ድምፅ ባለማሰማት ከንፈሮቿ ብቻ እየተነቃ

ነቁ እና በጉንጮቿ መሃከል እንባዎቿ እንደምንጭ ውሀ ሳያቋርጡ እየፈሰሱ የማታ ልብሷን ለብሳ እና ባዶ እግሯን ሁና አልጋው አጠገብ ቆማ እናት ልጅዋን ትመለከት ጀመር ።

## 5

ምንም እንኳን ግንኙነታቸው የቀረበ ቢሆንም አሁንም እንደቀድሞው ፀጥታ የሰፈነበትን እና የመራራቅ ሁኔታ የሚታይበትን ኑሮ ይኖራሉ ።

በሳምንቱ አጋማሽ ላይ በዋለ በአንድ የበዓል ቀን ፓቬል ከቤት ሊወጣ ሲል ፊቱን ወደ እናቱ ዘንድ መለስ አደረገና የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«ቅዳሜ እኔን ለመጎብኘት ከከተማ ሰዎች ይመጣሉ ።»

«ከየት? ከከተማ?» በማለት እናት ከጠየቀች በኋላ ወዲያውኑ እንደማጉረምረም አለች ።

«ምነው ፤ ምን አለበት እናትዬ?» ብሎ ቅር በተሰኘ መንፈስ ፓቬል ጠየቃት ።

ባሸረጠችው የምግብ መሥሪያ ሽርጥ ፊቷን ጠራረገችና በረዥሙ በመተንፈስ ፡ —

«አይ ፤ ምንም አይደል ። እንደው ነው» አለችው ።

«ፈራሽ እንዴ?» አላት ።

«አዎን!» ብላ ዕውነቱን ነገረችው ።

ወደ እርሷ ጎንበስ ብሎ እና ልክ እንደአባቱ ቆጣ ብሎ የሚከተለውን ነገራት ፡ —

«የእኛ የሁላችንም መጥፊያችን ይሄ ፍርሃት ነው ። የእኛ የበላይ አለቆች የሆኑትም በዚህ በፈሪነታችን በመጠቀም ይበልጥ ያስፈራሩናል» አላት ።

እናቱም ደስታ በተለየው ሁኔታ የሚከተለውን ተናገረች ፡ —



«ኡኮ አትበሳጭ ። ልጄ ፤ ለምን አልፈራም? መላ ሕይወቴን ስፈራ ነው የኖርኩት ። ነፍሴ ያደገችው ከፍርሀት ጋር ነው!» አለችው ።

ፓቬልም በቀስታ ድምፅ አለሳልሶ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«ይቅርታ አድርጊልኝ ። ምንም ማድረግ አልችልም ። እንግዶቹ ይመጣሉ!» አላት ።

ከዚያም ወጣና ሄደ ።

ለሦስት ቀናት ስትፈራ እና ስትርበተበት ቆየች ። ነግቶ ስትነሳ እነዚያ አይታቸው የማታውቃቸው እና አስፈሪ መስለው የሚታዩዋት ሰዎች እቤቷ የሚመጡ መሆኑ ትዝ ይላታል ። በአሁኑ ጊዜ ልጅዋ የሚከተለውን የሕይወት ጎዳና ያመለከቱት እነርሱ ናቸው ...

ቅዳሜ ማታ ፓቬል ከፋብሪካ ሥራ በኋላ ተመልሶ ወደቤቱ መጣ ። ተጣጥቦ ልብሱን ለወጠና እንደገና ተመልሶ ሊወጣ ሲል እናቱን ቀና ብሎ ሳይመለከት የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«እኔን የሚፈልጉ ሰዎች ቢመጡ ቶሎ ተመልሶ ይመጣል በይልኝ ። እና ደግሞ ፤ እባክሽን ይኸንን መፍራትሺንም ተወት አድርጊው...» አላት ።

ድክምክም ባለ መንፈስ አግዳሚው ወንበር ላይ ኩርምትምት ብላ ሰውነቷ ሁለት ላይ እጥፍ ብሎ ተቀመጠች ። ፓቬልም ኮስተር ባለ አመለካከት ተመለከታትና የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«ምናልባት አንቺ ... ዛሬ ወደ አንዱ ቦታ ወጣ ማለት ትፈልጊ ይሆን እንዴ?» የሚል ሃሣብ አቀረበላት ።

አነጋገሩ ቅር አሰኛት ። የሚከተለውንም መለሰችለት ፡ —

«አልፈልግም ። ለምን እሄዳለሁ?»

የኖቬምበር ወር ማብቂያ ነው ። ረፋዱ ላይ በቀዘቀዘው መሬት ደረቅ በረዶ ደህና አድርጎ የወረደበት ሲሆን ፤ ፓቬል ከውጪ ሲራመድ ከመጫሚያው በታች የሚረግጠው በረዶ ሲጥ-ሲጥ ሲል ይሰማታል ። ቤቱ ውስጥ ሁኖ በመስኮቱ መስተዋት ውጪው ሲታይ ድቅድቅ ጭለማ ተጋግሮበታል ። በሁለት እጆቿ አግዳሚ ወንበሩን ጨብጣ እና ኩርምት ብላ በር-በሩን በመመልከት ተቀምጣለች ...

እንግዳ የሆነ አለባበስ የለበሱ የሚመስሏት እነዚያ መጥፎ ሰዎች ከውጪው ጭለማ ውስጥ ወደቤት በመምጣት ላይ ያሉ መስሎ ታያት ። አሁን ሰው ከበስተውጪ በኩል መጥቶ በእጁ በሩን ሲነካካው ተሰማት ።

ሌላው ከውጭ ሲያፏጭ ሰማች ። ይኸ የፉጨት ድምፅ በጭለማው እና በፀጥታው ውስጥ በቀጭኑ ተሽሎክልኮ በመምጣት የሚሰማ ሲሆን ፤ የዜማው ወዘናም አንድ ሰው የሚፈልግ ሌላ ያዘነ ሰው የሚዘፍነውን ዓይነት ጥሩ ጣዕም የነበረው ሲሆን ድምፁም ቀስ-ቀስ እያለ በቅርበት ይሰማ ጀመር ። ድንገትም ፉጨቱ ከግርግዳ ላይ ተለጥፎ የቆየ ድምፅ ይመስል በመስኮቱ በኩል በጉልህ ተሰማ ።

ደጃፉ ላይ በረዶ ከመጫምያ ሲራገፍ ይሰማል ። እናትም ዐይኖቿን በመክፈት እና የግንባሯን ቆዳ ወደላይ ሰብስባ በማሸብሸብ በድንጋጤ ተነሳች ።

በሩ ተከፈተ ። መጀመርያ ትልቅ ፀጉራማ ቆብ ያደረገ አንገት ከውጭ ወደውስጥ ሾከክ ብሎ ብቅ አለ ። ከዚያም አንድ ቁመተ ረዥም አካል አጭር ከሆነው ከበሩ ደፍ ሥር ጎንበስ ብሎ በመምጣት በሩን ገብቶ እንደጨረሰ ቀጥ ብሎ ቆመ ። ድምፅ



አሰምቶ ከተነፈሰ በኋላ ቀኝ እጁን ለመጨበጥ ዘርግቶ ፡ —

«ጤና ይስጥልኝ ፤ እንደምን አመሹ!» አለ ።

እናትም መልስ ሳትመልስለት ጨበጠችውና እጅ ነሳች ።

«ፓቬል እቤት የለም እንዴ?» አለ ።

ከዚያም እንግዳው ሰው ቀስ ብሎ ፀጉራማ ካፖርቱን አወለቀ ። አንደኛውን እግሩን ከፍ አድርጎ ቡት መጫሚያው ላይ የነበረውን በረዶ በቆቡ አራግፎ ካበቃ በኋላ ፤ ሌላኛው እግሩንም ከፍ አድርጎ በረዶውን አራገፈ ። ከዚያም ቆቡን ወደጥግ መሬት ላይ ጣል አደረገና ቤቱን መሀል ለመሀል እያቋረጠ ጎርደድ-ጎርደድ አለ ። ቢቀመጥበት ይችለው አይችለው እንደሆነም የአንዱን ወንበር ጥንካሬ በእጁ ሞከር አድርጎ ቁጭ በማለት አፉን በእጁ ሸፍኖ አዛጋ ። ጥሩ ሞላላ ጭንቅላት ያለው ሲሆን ፤ ፀጉሩም በሚገባ ተበጥሮአል ። ጉንጮቹን ልቅም አድርጎ ተላጭቶአል ። ከላይኛው ከንፈሩ ላይ የሚገኘው ሪዙ ጎንና ጎኑን በዛ ያለ ፀጉር አሉት ። ትልልቅ በሆኑ እና ጎላ-ጎላ በማለት ከጉድጓዳቸው ወጣ ወጣ ባሉ ግራጫ ዐይኖቹ የቤቱን ግራና ቀኝ ደህና አድርጎ ቃኘ ።

አንደኛውን እግሩን ሌላኛው እግሩ ላይ ደርቦ እና ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ከፊት ወደኋላ መለስ-ቀና እያለ የሚከተለውን ጥያቄ ለፓቬል እናት አቀረበ ፡ —

«ይህ ጎጆ የእናንተ ነው ወይንስ ተከራይታችሁት ነው?»

ከፊት ለፊቱ ተቀምጣ የነበረችይቱ እናትም የሚከተለውን መለሰችለት ፡ —

«ተከራይተነው ነው ።»

«ይኸን ያህልም ጥሩ ቤት አይደለም!» በማለት እስተያየቱን አቀረበ ።

«ፓሻ አሁን ይመጣል ። ይጠብቁት!» አለችው ።

«አዎን እርሱኑ እየጠበቅሁኝ ነው!» በማለት ግዙፍ አካል ያለው ይህ እንግዳ ሰው መለሰ ።

የረጋ እና ለስላሳ ድምፅ ያለው በመሆኑ እንደዚሁም መልኩ እንደማንኛውም ተራ መልክ በመሆኑ ተጽናናች ። አመለካከቱ ግልጽ እና የወዳጅነት መንፈስ ያልተለየው ነው ። ግልጽ ከሆኑት ዐይኖቹ ውስጥም ደስ የሚያሰኙ ነጸብራቆች እስክስታ ይወርዱ ይመስላሉ ። መላ ቁመናው ደስ ያሰኛል ። የአካሉ ቅርጽ በማዕዘን የተስተካከለ ፤ እግሮቹም ረዣዥም ዠርጋዶች ነበሩ ። ሰማያዊ ሸሚዝና እስከ መጫምያው ድረስ ተንዠርግጎ የወረደ ጥቁር ቦላሌ ሱሪ ታጥቆአል ። ማን እንደሆነ ፤ ከየት እንደመጣና ካሁን ቀደምም የእርሷን ልጅ አይቶት ያውቅ እንደሆነ ልትጠይቀው ከጀለች ። ድንገት ከወንበሩ ላይ ወደፊት ወዘወዝ እንደ ማለት አለና ንግግር ለመጀመር እርሱ ቀዳሚ ሁኖ ተገኘ ። የሚከተለውንም ጥያቄ አቀረበላት ፡ —

«እምዬ ፤ ለመሆኑ እንዲህ ራስዎን የፈነከተው ማነው?»

ጥያቄውን ሲያቀርብ ዝግ ባለ ድምፅ ነው ፤ ዐይኖቹም ይስቁ ነበሩ ። ይሁን እንጂ እርሷ ግን ይኸን ጥያቄ በማቅረቡ ቅሬታ ተሰማት ።

ለስለስ ባለ ትህትና እና ዝግ ባለ ሁኔታ በመናገርም የሚከተለውን መልሳ ጠየቀችው ፡ —

«የኔ ወጣት ፤ ይኸንን ለመጠየቅ ለመሆኑ እርስዎን ምን ያገባዎታል እባክዎ?» አለች ።

መላ ሰውነቱን ወደ እርሷ አስጠግቶ ከአንገቱ ጎንበስ በማለት

«ምነው ፤ አይቆጡ እንጂ ፤ እኔ የጠየቅሁዎት የእኔ የጡት እናትም ልክ እንደርስዎው ተመሳሳይ ዓይነት ጠባሳ ያለባት ስለሆነ ነው ። አብራው የምትኖረው ሰው በድብደባ ያበረከተላት ምልክት ነው ። መጫሚያ ሰፊ ነው ። የእግር ቅርጽ በሚያወጣበት እንጨት ፈነከታት ። እርሷ ልብስ አጣቢ እርሱ ጫማ ሰፊ ናቸው ። እኔን የጡት ልጅዋ ካደረገችኝ በኋላ ፤ የሀዘኗ መጽናኛ ቢሆን ብላ መረጠችው ። ሰካራም ነው ። አቤት ፤ እንዲህ እንዳይመስልዎ ፤ እንዴት መሰለዎ ይደበድባት የነበረው! እኔ ከፍርሃቴ የተነሳ ሲደበድባት ዐይኖቼ ተጉረጥርጠው ከጉድጓዳቸው ይወጡ ነበር!»

የፓቬል እናት በእንግዳው ሰው ግልጽነት ተረጋጋች ። በማይገባ ሁኔታ ቀደም ሲል መልስ ስለሰጠችውም ፓቬል ሲመጣ ይቆጣ ይሆናል ብላ ማሰብ ጀመረች ።

ከዚያም የጥፋተኛ አሳሳቅ እየሳቀች ፡ —

«ቅድም እኮ አልተቆጣሁኝም ነበር ። ድንገት ሳላስበው እርስዎ ጥያቄ ስለጠየቁኝ ነው ። ነፍሱን ይማረውና ፤ እኔንም እንዲህ ያደረገኝ የኔው ሰውዬ ነበር ። ለመሆኑ እርስዎ ታታር * ነዎትን?» አለችው ።

እንግዳው ሰው እግሩን ጎነጥ አደረገ ፤ ከዚያም ጆሮዎቹ እስኪነቃነቁ ድረስ ብዙ ፈገግ አለ ። ከዚያም ከልቡ በሆነ የቀልድ አነጋገር ፡ —

«እስከአሁን አይደለሁም» በማለት መለሰ ።

ይህ እንግዳ ሰው ባቀረበው የቀልድ መልስ ሳቅ ብላ የሚከተለውን እንደገና ተናገረች ፡ —

«አነጋገርዎ ግን የሩስያዊ አነጋገር አይመስልም» አለች ።

እንግዳው ሰውም ጭንቅላቱን በፈገግታ እያነቃነቀ ፡ —

---

* ታታር ፡ — በሩሲያ ውስጥ የሚገኙ ሩስያዊ ያይደሉ የቱርክ ቋንቋ ቤተሰብ ተናጋሪ ከሆኑት መካከል የአንዱ ብሔር ስም ነው ። (ተርጓሚው ።)

«ከሩስያዊ የተሻለ ነው ። እኔ ከካኔቭ የመጣሁኝ ኾኾል* ነኝ» በማለት መለሰ ።

«እዚህ ከመጡ ብዙ ጊዜ ሆነዎትን?» አለችው ።

እንግዳው ሰውም ሪዙን እያሻሸ የሚከተለውን መለሰ ፡—

«ከተማው ውስጥ አንድ ዓመት ያህል ኖሬአለሁኝ ። ወደዚህ ወደፋብሪካው ከመጣሁኝ ግን አንድ ወር ያህል ቢሆነኝ ነው ። እዚህ ልጅዎን ፓቬልን እና ሌሎችም እርሱን የመሳሰሉ አንዳንድ ጥሩ ሰዎች አሉ ። ስለዚህም ፤ እንደሚመስለኝ የምኖረው እዚህ ሳይሆን አይቀርም ።»

በጣም ደስ አሰኛት ። ስለልጅዋ የሙገሳ ጥሩ ቃላት ከአንደበቱ በመውጣቱም ልትክሰው ፈለገች ። እንደዚህ በማለትም ጠየቀችው ፡—

«ሻይ ላምጣልዎትን?» አለችው ።

እርሱም ትከሻውን በመወዝወዝ ፡—

«እኔን ብቻዬን ሊጋብዙኝ! ሌሎቹ እስኪመጡ ድረስ ይቆዩ ። ሁሉም ሲመጡ ሁላችንንም ይጋብዙናል...» አላት ።

ይኸ «ሌሎቹ እስኪመጡ» የተሰኘ አነጋገሩ ፍርሃቷን አስታወሳት ።

«ምነው ሌሎቹን የሚመጡትንም እንደዚህ እንግዳ ሰው ቀና ሰዎች ባደረገልኝ!» በማለት ታስብ ጀመር ።

አሁንም እንደገና ከበሩ መግቢያ ላይ የፓቬል እናት ድምፅ ሰማች ። በሩም በችኮላ ተከፈተ ።

---

* ኾኾል ፡— ሩስያውያን ፤ ኡክራይናውያንን በቅጽል ስም ሲጠሯቸው ኾኾል ይሏቸዋል ። ትርጓሜውም ራሱን ተላጭቶ ጋሜ የቀረው ማለት ነው ። (ተርጓሚው ።)



እንደገና እናት ከተቀመጠችበት ተነሳች ። መቸስ እንዴ ፣ ይግረምሽ ብሏት የለ ፤ አሁን ደግሞ የመጣችው አንዲት ወጣት ልጃገረድ ነች ። እርሷም ወደ ማዕድ ቤቱ አልፋ ገባች ። ልጃገረዲቱ ቁመተ-አጭር ፤ መልከ-ተራ ስትሆን ረዥም ፀጉሯን በልሙጡ ወደኋላ አስተኝታዋለች ። በቀስታ አነጋገር እንዲህ በማለት ልጃገረዲቱ ጠየቀች ፡—

«ዘገየሁ እንዴ?»

ኾኾል ከበስተበራፉ በኩል እየተመለከተ ፡—

«የለም አልዘገየሽም ። በእግርሽ ነው እንዴ የመጣሽው?» አላት ።

«ታዲያስ በእግሬ ነው እንጂ ። እርስዎ የፓቬል ሚኻይሎቪች እናት ነዎትን? ጤና ይስጥልኝ እንደምን አመሹ ፤ ናታሻ እባላለሁኝ» በማለት ልጃገረዲቱ ከፓቬል እናት ጋር ተዋወቀች ።

«በአባትዎ ስምስ ማን ይባላሉ?» በማለት እናት ጠየቀች ።

«ቫሲሌቭና እባላለሁኝ ። እርስዎስ?» በማለት ልጃገረዲቱ መልሳ ጠየቀች ።

«ፔላጌያ ኒሎቭና እባላለሁኝ» በማለት እናት መለሰች ።

«ይኸው እንግዲህ ተዋወቅን ...» አለች ልጃገረዲቱ ።

«አዎን» አለች እናትም ፤ በትንሹ እየተነፈሰች እና ልጃገረዲቱንም በፈገግታ እየተመለከተቻት ።

ልጃገረዲቱ ካፖርቷን ስታወልቅ ኾኾል ለመቀበል እያገዛት የሚከተለውን ጠየቃት ፡—

«ይበርዳልን?»

«አዎ ፤ ሜዳው ላይ በጣም ይበርዳል ። ነፋሱ ኃይለኛ ነው ...» አለች ።

ድምጿ ጉልህ እና ግልጽ ነው ። አፏ ጠባብ ሁኖ ከናፍሮቿ ዳጎስ ያሉ ናቸው ። እንደው በጠቅላላ

ው ድቡልቡል ያለች ለጋ ፍሬ ማለት ነች ። ካፖርቷን ካወለቀች በኋላ ሮዝማ የሆኑ ጉንጮቿን በብርድ በቀዘቀዙት እጣቶቿ እያሻሸች እና ወለሉንም በኮፍ መጫምያዋ ቋ-ቋ እያደረገች በመርገጥ ወደክፍሉ ገባች ።

«እንዴት ያለቡት ጫማ ትሄዳለች!» የሚል ሃሣብ በእናት አዕምሮ ተመላለሰ ።

«ኡ-ት-ት-ት-ት! ቅዝቃዜው በረዶ አድርጎኛል!» አለች ልጃገረዲቱ ።

«ቆይ ፤ አሁኑኑ ሳሞቫሩን* እጥደዋለሁኝ» በማለት እናት በፍጥነት ተቻኩላ ወደማዕድ ማዘጋጃ ክፍል እየሄደች ፡ — «አሁን ነው የሚደርስ» አለች ።

ይህችን ልጃገረድ ረዘም ካለ ጊዜ ጀምሮ የምታውቃት ያህል ሁኖ ተሰማት ። በእናትነት የርኅራኄ ፍቅርም ወደደቻት ። እሌላኛው ክፍል የሚወራውን ወሬ እናት ከማዕዱ ማዘጋጃ ክፍል ሁና በማዳመጥ ከናፍሮቿ በፈገግታ ተመሉ ።

«ናሆድካ ፤ ምነው እንዲህ ፍዝዝ አልክ?» በማለት ልጃገረዲቱ ጠየቀችው ።

«አይ ፤ ኧረ እንደው ነው» በማለት ኾኾል በዝግታ ድምፅ መለሰ ።

«እኚህ የሚች ሚስት ዐይናቸው የደስ-ደስ አለው ። ምንአልባት የእናቴ ዐይኖችም የእሳቸውን ዐይኖች ይመስሉ ይሆናል ብዬ ነበር በመተከዝ የማስበው ። ስለእናቴ ብዙ አስባለሁኝ ። በሕይወት አለች የሚል ስሜት ይሰማኛል» አለ ።

«ሞተዋል ብለህ ነበርኮ» አለችው ።

«የሞተችው የጡት እናቴ ነች ። አሁን የምናገረው ስለወላጅ እናቴ ነው ። ምናልባት ኪየቭ ከተማ ውስጥ

---

* ሳሞቫር ፡ — ማለት የሻይ ማፍያ ነው ።



በሚገኙት መንገዶች ትለምን ይሆናል ። ቮድካም ትጠጣ ይሆናል ። በሰከረች ቁጥርም ፖሊሶች እያዳፉ በጥፊ ይመቷት ይሆናል ...»

«ውይ ምስኪን ልጅ!» በማለት አሰበች እና እናት ማዕድ ክፍል ሁና በረዥሙ ተነፈሰች ።

ናታሻ አንድ እናት ልትሰማው ያልቻለችውን ነገር በፍጥነት ፤ በለስላሳነት እና በስሜት ተናገረች ። አሁንም እንደገና የኾኾል ድምፅ በጉልህ ተሰማ ።

«አይ ፤ ጓዲት ፤ አንቺ ገና ትንሽ ኅፃን ነሽ ። ገና በልቶሽም አልጠገብሽም ። መውለድ ከባድ ነገር ነው ። ሰውን በጎ ምግባር ያለው አድርጎ ማሳደግ ደግሞ እጅግ አስቸጋሪ የሆነ ጉዳይ ነው ...»

«አይ አንተ!» ካለች በኋላ ኾኾልን በማጽናናት ለመናገር እናት ማዕድ ክፍል ሁና ትጠባበቅ ነበር ። ይሁን እንጂ ድንገት የውጪው በር ቀስ ብሎ ተከፈተና የሌባው ሽማግሌ የዳኒሎ ልጅ ኒኮላይ ቬሶቭሺኮቭ የተሰኘው ሰው ወደቤት ገባ ። ኒኮላይ ከሰው የማይስማማ ለመሆኑ ድፍን የመንደሩ ሰው የሚያውቀው ነው ። ሰውን ሲቀርብ በእኩራፊነት በመሆኑ ምክንያት የሠፈሩ ሰው ብዙም አያቀርበውም ። እናት በመደነቅ መልክ የሚከተለውን ጠየቀችው ፡ —

«ምነው ፤ ምን ነበር ፤ ኒኮላይ?» አለችው ።

ፊንጣጣ የጠቀጠቀው ሰፊ ፊቱን በመዳፉ እየጠራረገና እንደምን አመሹ ሳይልም ፡ —

«ፓቬል የለም እንዴ?» በማለት ቀስ ብሎ ጠየቀ ።

«የለም» አለችው ።

ወደውስጥ ቃኘት-ቃኘት አደረገና ገባ ። ከዚያም ፡ —

«ጓዶች ፤ እንደምን አመሻችሁ!» አለ ።

«እሱም ደሞ?» በማለት እና ባለማመን እናት ወይጉድ እያለች ከራሷ ጋር ስትወያይ ፤ ናታሻ ደስ ብሏ

ትና እንኳን ደህና መጣህ በሚል መንፈስ ስትጨብጠ
ው ተመለከተች ።

ከዚያም ገና ሎጋ የሆኑ ሁለት ትንንሽ ወጣቶች
መጡ ። ከሁለቱ መካከል አንደኛውን እናት የምታው
ቀው ሲሆን ፤ እርሱም የፋብሪካ ሠራተኛ ሲዞቭ የተሰ
ኘው ሽማግሌ ዘመድ የሆነው ፌዶር ሲሆን ፊተ-ኮስ
ታራ በረድፍ-በረድፉ ጥቅልል-ጥቅልል እያለ የሚቀመ
ጥ የራስ ፀጉር ያለው እና ግንባረ-ሰፊ የሆነ ነበር ።
ሌላኛው ደግሞ ዐይን-አፋር ሲሆን ፤ ፀጉሩንም ወደፊ
ት በልሙጡ አስተኝቶታል ። ከዚህ ቀደም አይታ አታ
ውቀውም ። ቢሆንም ደግሞ አስፈሪ የሆነም አልነበ
ረም ። በመጨረሻም ከሁለት ከምታውቃቸው የፋብሪካ
ሠራተኞች ጋር ሁኖ ፓቬል መጣ ። ከዚያም እናቱን
በማቆላመጥ እንደሚከተለው ተናገረ ፦

«ሳሞቫር ጥደሻላ? ጎሽ እናመሰግናለን!»

«ወጥቼ ቮድካ ብጤ ልግዛላችሁ?» አለች እናት ፤
አንድ ልትገልጸው ላልቻለችው ጉዳይ ምሥጋናዋን
እንዴት እንደምታቀርብ ግራ ባጋባት መንፈስ ።

«የለም ፤ የለም ፤ ቮድካ አንጠጣም!» በማለት በፍቅር
ፈገግታ መለሰላት ።

በርሷ ለመሳቅ ብሎ ልጅዋ የነርሱን ስብሰባ
አደገኛነት አጋንኖ ያወራላት መስሎ ድንገት ታሰባት ።

«እነዚህ መሆናቸው ነው እንዴ ፤ ሕገ-ወጦቹ ሰዎ
ች?» በማለት ቀስ ብላ ጠየቀችው ።

«እኚሁልሽ እነዚህ ናቸው!» በማለት ፓቬል ወደ
ሌላኛው ክፍል አመራ ።

«እሱን ተወው» በማለት በፍቅር አነጋገር እየተከ
ተለችው በመግባት በርኅራኄ አስተሳሰብ በመንፈሷ
«አሁንም ገና ልጅ እኮ ነው!» ብላ አሰበች ።



# 6

ሳሞቫሩ እንደፈላ እናት ወደ ቤቱ ክፍል ወሰደ
ችው ። እንግዶቹ ጠረጴዛውን ከበው ተቀምጠዋል ። ናታ
ሻም ፋኖሱ ከተሰቀለበት ግድግዳ ሥር ከበስተጥግ
በኩል መጽሐፍ በእጅዋ ይዛ ተቀምጣለች ።

«ሰዎች በምን ምክንያት እንደዚህ ዓይነት መጥፎ
አኗኗር እንደሚኖሩ ለመረዳት ...» ብላ ናታሻ ገና
ንግግሯን ሳትጨርስ ፦

«እና ደግሞ ሰዎች ራሳቸውም ለምን እንዲህ
መጥፎዎች እንደሆኑ ለመረዳት ...» በማለት ኾኾል
በንግግሯ ላይ ጣልቃ ገባ ።

«ማኅበራዊ የሆነውን የአመጣጣቸውን መሠረት
መመራመር አለብን» አለች ።

«ተመራመሩ ፤ የኔ ውዶች ፤ ደህና አርጋችሁ ተመራመ
ሩ!» አለች እናት ሻይ እየቀዳች ።

በክፍሉ ውስጥ ያሉት ሁሉ መናገራቸውን አቆሙ ።

«እንዴ ፤ ምነው እናት?» በማለት ፓቬል ኮስተር
ብሎ ተናገረ ።

«ምነው?» አለች ። ቀና ብላ ብትመለከት ሁሉም
እርሷን እርሷን ይመለከታሉ ። እርሷም በማፈር መል
ክ የሚከተለውን በማጉረምረም ተናገረች ፦ «እረ
እንደው ነው ። ከራሴው ጋር እያወራሁ ነበር ። መመራ
መር ከፈለጉ ለምን አይመራመሩም? በማለት ባሳቤ
ሳስብ ነው ድንገት የተናገርኩት!» አለች ።

ናታሻ ሳቀች ። ፓቬልም ፈገግ አለ ። ኾኾልም ፦

«እምዬ ፤ ላቀረቡልኝ ሻይ አመሰግናለሁኝ» አለ ።

«መቼ ጠጡትና ፤ ጠጥተውት ነው እንጂ ማመሥ
ገን!» አለች ። ከዚያም ወደልጅዋ ተመለከተችና ፦ «አ
ስቸገርኩኝ መሰለኝ?» በማለት ጠየቀች ።

ናታሻም የሚከተለውን መለሰች ፡ —
«ኧረ ባክዎ እንዲህ አይበሉ ። ምን ማለትዎ ነው ፤
እርስዎ አስተናጋጅ ሁነው እንግዶችን ያስቸግራሉ
ማለት ነው እንዴ?»
ከዚያም እንደ ጎፃን ልጅ አጠያየቅም የሚከተለ
ውን ጥያቄ ናታሻ ለእናት አቀረበች ፡ —
«የኔ እምወድዎ! ሻይ ቶሎ ይስጡኝ! ብርዱ መላ
ሰውነቴ ውስጥ ገብቶ ያንቀጠቅጠኛል ። አካላቴ እንደ
በረዶ ቀዝቅዟል!» አለች ።
«አሁን ነው የማመጣው ፤ አሁኑኑ!» በማለት እናት
በፍጥነት መለሰች ።
ናታሻ ሻይዋን ከጠጣች በኋላ ጎላ አድርጋ በረኸ
ሙ በመተንፈስ በስተደረቷ በኩል ዘንፈል ብሎ ወ
ርዶ የነበረውን ፀጉሯን ወደጀርባዋ መለስ አደረገች
ውና በቢጫ ገበታ ተለብጦ ስዕሎች ያሉበትን መ
ጽሐፍ ማንበብ ጀመረች ። እናት ሻይ በምትቀዳበት
ጊዜ አንዳችም ድምፅ ሳታሰማ ረጋ ብሎ የሚወር
ደውን የናታሻን ንባብ ታዳምጣለች ። የናታሻ ወዝ
ያልተለየው ድምጿ ሻዩ ከሳሞቫሩ ውስጥ ሲቀዳ በረ
ቂቁ ከሚሰጠው የሙዚቃ ድምፅ ጋር ቅኝቱን አስማ
ምቶ ይንቆረቆራል ። አስደሳች የሆነው ይህ የንባብ
መጋረጃ የተገለጠውም ፤ ከረኸም ዘመናት በፊት በዋ
ሻዎች ውስጥ ይኖሩ ስለነበሩና አውሬዎችንም በድን
ጋይ በመደብደብ ያድኑ ስለነበሩ ጥንታውያን ሰዎች
ሁኔታ ነበር ። የእነዚህን ጥንታውያን ሰዎች ታሪክ
ሲሰሙት ተረት ይመስላል ። እናቲቱም መላልሳ ልጅዋ
ን በመመልከት እነዚህን የመሳሰሉት ታሪኮች እንዳ
ይሰሙ ሕገ-ወጥ በመሆን የሚከለከሉበት ምክንያት
ለምንድነው? ብላ ለመጠየቅ ፈልጋ ነበር ። ይሁን እን
ጂ ፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ታሪኩን በማዳመጥ መከታተል
ስለሰለቻት ልጅዋም ሆነ ሌሎቹ ሳያስተውሏት በክፍ



ሉ ውስጥ ያሉትን እንግዶች ሁኔታ ዝግ ብላ ማስተ
ዋል ጀመረች ።
ፓቬል ከናታሻ ቀጥሎ ተቀምጦአል ። በክፍሉ
ውስጥ ከነበሩት ሁሉ መልከ-መልካሙ እርሱ ነው ።
ናታሻ መጽሐፏን በማንበብ ከአንገቷ ደፋ ስትል
የራሷ ፀጉር ከራሷ ጎን እና ጎን ቅንጦቿ ላይ ዘፍ
ብሎ ስለሚወርድ ከራሷ ቀና እያለች ወደ ጀርባዋ
ትመልሰዋለች ። ራሷን ነቅነቅ እያደረገችና ድምጿን
ም ዝቅ በማድረግ አዳማጮቿን በፍቅር ዓይን እየተ
መለከተች የራሷን አስተያየት በማከል ትጨምራለች ።
ኾኾል ከጠረጴዛው አንድ ጥግ በኩል ሰፌ ደረቱን
በመዘረር ተቀምጦ ዐይኖቹ በአፍንጫው አኳያ ወደ
ታች ቁልቁል እያማተሩ በማድረግ የገዛ ሪዙን
የግራና ቀኝ ጫፎች እያሻሸ ለመመልከት ይጥራል ።
ቬሶቭሺኮቭ ጉልበቶቹን በመዳፎቹ እያሻሸ እና ፈንጣ
ጣ የጠቀጠቀው ሽፋል-የለሽ ፊቱን ወዲያ-ወዲህ ሳያ
ነቃንቅ ይሁነኝ ብለው እንደተከሉት ምሶሶ እዚያው
አለበት ቦታ በመርጋት ቀጥ ብሎ ተቀምጦአል ። ጥል
ቅ በሆኑት ዐይኖቹ ወደ ሳሞቫሩ አማትሮ ይመለከ
ታል ። ወዲያ-ወዲሁን ሳይቃኝ እና በሳሞቫሩ የብርሃን
ነጸብራቅም ዐይኖቹ ቦግ-ድርግም ሳይሉ ቁልጭ ብለው
ይመለከታሉ ። አኳኋኑ ትንፋሽ የሚተነፍስም ሰው አይ
መስልም ። ትንሹ ፌዎዶር መጽሐፉ በሚነበብበት ጊዜ
ያንኑ የተነበበውን መልሶ ድምፅ ሳያሰማ የሚያነበን
ብ ይመስል በተነበበ ቁጥር ከናፍሮቹን ያነቃንቃል ።
ሌላኛው ጓደኛው ደግሞ ከወገቡ በላይ ያለ አካሉን
ጎንበስ በማድረግ ክርኖቹን ጉልበቶቹ ላይ ፤ ጉንጮቹን
ም በመዳፎቹ አስደግፎ በማስተዋል ፈገግታ ፈገግ
እያለ ተቀምጦአል ። ከፓቬል ጋር የመጣው ከርደድ
ያለ ቀይ ፀጉር ያለው ሲሆን አንድ ለመናገር
የሚፈልገው ነገር ያለ ይመስል ይቁነጠነጣል ። ሌላኛ

ው ነጭ ፀጉር ያለው እና ፀጉሩንም በአጭሩ የተቀመቀመው እጁን አዘውትሮ ራሱ ላይ በማሳረፍ ፀጉሩን የሚያሻሽ ሲሆን ፤ መሬት መሬቱን ስለሚመለከት እናት ፊቱን አታይም ። ክፍሉ በሚያስደንቅ አኳኋን የደስ-ደስ ያለው ሁኖአል ። ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የታጀበ ሲሆን ፤ ናታሻ መጽሐፉን በምታነብበት ጊዜም ወጣት ሁና ሳለ ጫጫታ የተመላበት የግብዣ ፓርቲ እንደምን የመሰለ እንደነበር ፤ ትንፋሻቸው ሁል ጊዜም ቮድካ-ቮድካ ይል ከነበሩት ልጆች አንደሰት ይሰሙ ስለነበሩት አጸያፊ የሆኑ ንግግሮች እና የባለጌ ቀልዶች ሁኔታ አስታወሰች ። ሁኔታዎቹን በማስታወስና ራሷን በራሷም ስላለፈው ጊዜ በመውቀስ ልቧ ታውኮ ድው-ድው አለ ።

ባሏ እንዴት እንዳጫት አስታወሰች ። ከነዚያ ካሳለፈቻቸው የግብዣ ፓርቲዎች መካከል በአንዱ ላይ ጨለም ካለው መተላለፊያ ውስጥ አፈፍ አድርጎ ይዞአት ነበር ። ከግድግዳ ጋር ያጣበቃት ። ከዚያም በተበሳጨ ድምፅ የሚከተለውን የጠየቃት ፡ —

«ታገቢኛለሽ?»

ከግድግዳው ጋር መላ ሰውነቷን አጣብቆ ስለያዛት አሟት የነበረ ከመሆኑም በስተቀር በድርጊቱ ተቀይማም ነበር ። እርሱ ግን በሚያሳምም ሁኔታ ጡቶቿን እያሻሸ ትኩስ እና ርጥበት ያለው ትንፋሹን ፊቷ ላይ ይተነፍግባት ነበር ። አጣብቆ ከያዛት ቦታ በመገፍተር ተመንጭቃ ለመላቀቅ ሞከረች ።

እርሱም በቁጣ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«የትነው የምትሄጅው? ስሚ እንጂ! መልሱን አትነግሪኝም እንዴ?» አለ ።

በማፈሯ እና እንዲህ በመደፈሯ ትንፋሽ አጥሯት መልስ ለመመለስ አልቻለችም ነበር ።



ከዚያም አንዱ በሩን ከፈት ሲያደርግ ቀስ ብሎ ለቀቃት ።

«እሁድ አማጭ እልካለሁኝ...» አለ ።

ብሎም አልቀረ ፤ ላከ ።

እናት ዐይኖቿን ዘግታ በረዥሙ ተነፈሰች ...

«እኔ ለማወቅ የምሻው ሰዎች ወደፊት እንዴት መኖር እንዳለባቸው ነው እንጂ ፤ ያለፈውን ጊዜያቸውን እንዴት እንደኖሩት አይደለም!» በማለት በመቃወም ዓይነት ድምፅ ቬሶቭሺኮቭ ተናገረ ።

«ልክ ነው!» አለ ቀይ ፀጉር ያለውም ብድግ እያለ በመናገር ።

«እኔ በፍጹም አልስማማም!» በማለት ፌዎዶር ጮኸ ።

በሚከራከሩበት ጊዜ ቃላቶች ከአንደበታቸው ዱብ-ዱብ እያሉ እንደ ነበልባል ይንበለበሉ ነበር ። እናት በምን ጉዳይ ላይ እንደሚከራከሩ አልገባትም ። የሁሉም መልክ በስሜት ተውጦ የነበረ ሲሆን ፤ በግልፍተኛነት የቁጣ መልክ ያሳየ ወይንም ብዙ ጊዜ እርሷ እንደምትሰማው ያለ የብልግና አነጋገር ያሰማ ሰው ግን ከመካከላቸው አንድም አልነበረም ።

«ልጃገረዲቱ ፊት ስለሆኑ የብልግናውን ቃል እርስ-በርሳቸው ለመለዋወጥ አፍረው ይሆናል!» በማለት እናት ገመተች ።

እነዚህን ወጣቶች ገና ሕፃናት እንደሆኑ ዓይነት አድርጋ ሁሉንም በአትኩሮት ስትመለከት በናታሻ ፊት ላይ ያረበበው ኮስታራ ገጽታ እጅጉን አስደሰታት ።

«አንድ ጊዜ ፤ ጓዶች!» በማለት ናታሻ ድንገት ተናገረች ። ከዚያም ሁሉም ንግግራቸውን አቆሙና እርሷን ይመለከቱ ጀመር ።

«ሁሉንም ነገር ማወቅ አለብን በማለት ከእኛ መሃል የተናገራችሁት ጓዶች ልክ ናችሁ ። በዳፍንት

ጭለማ ትግሉን የሚያካሂዱት እኛን ለማየት እንዲችሉ የምርምርን ብሩኅ ፋና በእኛ ውስጥ ማብራት አለብን ። ለማንኛውም ነገር ቢሆን ዕውነተኛ እና ትክክለኛ የሆነ መልስ መስጠት አለብን ። ማናቸውንም ዕውነት እና ማናቸውንም ሀሠት አንጥሮ ማወቅ ያስፈልጋል ...»

ናታሻ ቃላቶቿን ስትጥል ፤ ኾኾልም ከምትሠነዝራቸው ቃላቶች ጋር አስተካክሎ ጭንቅላቱን ይወዘውዛል ። ቬሶቭሺኮቭ እና ባለቀይ ፀጉሩ ፤ እንደዚሁም ከፓቬል ጋር አብሮ የመጣው የፋብሪካ ሠራተኛ በአንድ በኩል ተሰባሰቡ ። ለምን እንደሆነ ባታውቀውም ለእናት እነዚህ ሰዎች ደስ አላሰኟትም ።

ናታሻ ንግግሯን ስትጨርስ ፤ ፓቬል ከመቀመጫው ተነስቶ ቆመ ። ከዚያም በአንድ ወገን የተከማቹትን ሦስቱን በመመልከት የሚከተለውን በዝግታ ጠየቀ ፡ —

«ለመሆኑ ከርሳችንን መሙላት ብቻ ነው እንዴ የምንሻው? አይደለም! ከጀርባችን ላይ የታዘሉትን እና በዐይኖቻችን እንዳናይ አድርገው የሸፈኑንን ሁሉ ፤ ማናቸውንም ነገር የምናይ መሆናችንን ማሳየት አለብን ። እኛ እንከፎች አይደለንም ። ከርሳችንን ከመሙላት በስተቀር ሌላ አንዳችም ነገር የማንሻ አውሬዎችም አይደለንም ። ሰብአውያን ፍጡሮች ሊኖሩ የሚገባቸውን ዓይነት አኗኗር መኖር እንሻለን ። በባርነት ቀንበር ጠምደው ቢይዙንም ፤ በተመራማሪነት እኛም ከእነርሱ እኩል ልንሆን እንደምንችል ፤ እንደውም ከእነርሱም ልንበልጥ እንደምንችል ለጠላቶቻችን በተጨባጭ ማረጋገጥ አለብን!...»

የልጅዋን ንግግር በምታዳምጥበት ጊዜ እናት ልቧ ተነካ ። ኤዲያ ፤ አሳምሮ መናገርንስ ልጄ ይወቅበት! በማለት አሰበች ።

«ከርሳቸው እንደነጋሪት እስኪቆዘር የሚበሉ አያ



ሌ ሲሆኑ ፤ ዕውነተኞች ግን ጥቂት ናቸው! በዚህ ረግረጋማ በሆነው የአውሬነት አኗኗር ላይ ለወደፊቱ የሰው ልጆች የወንድማማችነት መንግሥት መሸጋገሪያ የሚሆነውን ድልድይ መመሥረት አለብን ። ጓዶች ፤ ከፊት-ለፊታችን ተደቅኖ የሚጠብቀን ተግባር ይህ ነው!» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

«የመታገያችን ጊዜ አሁን ከሆነ ፤ እጆቻችንን አጣጥፈን የምንቀመጥበት ምክንያት ምንድነው?» በማለት ቬሶቭሺኮቭ በተቃውሞ መልክ በማጉረምረም ተናገረ ።

ስብሰባቸው ያበቃው ዕኩለ-ሌሊት አልፎ ውድቅቱ ላይ ነበር ። መጀመርያ ቀድመው ከቤት የሄዱት ቬሶቭሺኮቭ እና ባለቀዩ ፀጉር ሲሆኑ ፤ ይኸ ሁኔታም እናትን አላስደሰታትም ነበር ።

«ምነው ተቻኮሉ!» በማለት እና ከሙሉ ልብ ባልሆነ ሰላምታ አሰጣጥ እናት ተሰናበተቻቸው ።

«ናሆድካ ፤ ትሸኘኝ የለም እንዴ?» በማለት ናታሻ ኾኾልን ጠየቀችው ። ኾኾልም ፡ —

«እንዴታ ፤ እሸኝሻለሁኝ» በማለት መለሰ ።

ናታሻ ካፖርቷን ማዕድ ቤት ሁና ስትለብስ ፤ እናት የሚከተለውን ተናገረች ፡ —

«የእግር ሹራቦችዎ ለእንደዚህ ዓይነቱ ክረምት አይሆኑም ። ስሶች ናቸው ። ሱፍ እግር ሹራቦች ልሥራልዎትን?» አለቻት ።

«አመሰግናለሁኝ ፤ ፔላጌያ ኒሎቭና! ሱፍ እግር ሹራቦች የሰው እግር ይቧጥጣሉ!» በማለት ናታሻ ፈገግ ብላ መለሰች ።

«እኔ የምሠራልዎት የማይቧጥጥ ዓይነት ነው» በማለት እናት ተናገረች ።

ናታሻ የዐይኖቿን ሽፋሽፍቶች የመጨፈን ያህል አቀራረባ በማጋጠም እናትን ተኩራ ትመለከታት ጀመር ። ይኸ አመለካከቷም እናትን ግራ አጋባት ።

«ቂላ-ቂል በመሆኔ ይቅርታ ያድርጉልኝ ። እኔ የጠየቅሁዎት ከልቤ ነው!» በማለት እናት በቀስታ ተናገረች ።

«እርስዎ በጣም ተወዳጅ ነዎት!» በማለት ናታሻም እናትን በእጆቿ አጥብቃ በመጨበጥ ቀስ ብላ ተናገረች ።

«እምዬ ፤ ደህና ይደሩ!» በማለት ኾኾል ናታሻን ለመድረስ በሩን ሲወጣ እናትን ዐይን-ዐይኗን እየተመለከተ ተናገረ ።

እናት ልጅዋን ተመለከተች ። ፈገግ ብሎ በራፉ ላይ ቆሞ ነበር ።

«ምን ያስቅሃል?» በማለት ግራ ገብቷት እናት ልጅዋን ጠየቀችው ።

«ምንም የሚያስቀኝ አዲስ ነገር የለም ። እንደው ደስ ስላለኝ ነው!» በማለት መለሰ ።

«እርግጥ ነው ፤ እኔ አሮጊትም ሞኝም ነኝ ። ነገር ግን ደግሞ ፤ ክፉና በጎውን እለያለሁኝ» አለች ትንሽ የተከፋች በመምሰል ።

«ጎሽ ፤ ይኼ ጥሩ ነው! አሁን ጊዜው ብዙ መሽቷልና ብትተኚ ጥሩ ነው!» አላት ።

«አሁን እተኛለሁ!» አለች ።

በጣም ተደስታና ጠረጴዛውን ጉድ-ጉድ በማለት እየዞረች ሻይ ቀርቦባቸው የነበሩትን ዕቃዎች ማነሳሳት ጀመረች ። ደስታዋ ከልኩ አልፎ የነበረ ከመሆኑ የተነሳ ላቧ ይንቆረቆር ነበር ። ሁሉም ነገር ደስ የሚያሰኝ ስለነበረ እና በሰላም ስላበቃም ተደስታ ነበር ።

«ፓቨሉሻ ፤ እንዲህ ያለ ነገር ለማድረግ ማሰብህ ጥሩ ነው ። ኾኾል በጣም ጥሩ ሰው ነው ። ልጃገረዲቷም ጭምር — ኡ-ይ ፤ እንዴት ያለች ብልህ ልጅ ነች እባክህ! ለመሆኑ ምንድነች?» በማለት እናት ጠየቀች ።



«አስተማሪ ነች!» በማለት ክፍሉ ውስጥ እየተንጎራደደ በቀስታ መለሰላት ።

«በጣም ድሀ መሆን አለባት ። ልብሷ ሁሉ ለክረምት የሚሆን ልብስ አይደለም ። በዚህ አለባበሷ ጉንፋን ወዲያው ነው የሚይዛት ። ለመሆኑ ቤተሰቦቿ የት ናቸው?» አለችው ።

«ሞስኮ ናቸው» በማለት ፓቬል መለሰላት ። ከዚያም ኮስተር ብሎና በቀስታ አነጋገርም የሚከተለውን ነገራት ፡—

«ይኸውልሽ እንግዲህ ፡ አባቷ ሃብታም ነው ። ብረታ ብረቶች ይነግዳል ። የሚያከራያቸው አያሌ ቤቶችም አሉት ። አሁን የምትጓዘውን የህይወቷን አቅጣጫ ለኑሮዋ መመርያ አድርጋ በመምረጧ አባትየው ከዳት ። አስተዳደጓ በሞቀ በደመቀ ፤ ሲሳዩ በተትረፈረፈ ቤት ውስጥ ነበር ። ሁሉም በእጅዋ ሁሉም በደጅዋ ተርፎ ይገኝ ነበር ። አሁን ግን ይኸው እንዲህ ብቻዋን በጭለማ ሰባት ቬርስታ* ርቀት በእግሯ ትጓዛለች...»

ይኸንን በመስማቷ እናቱ በድንጋጤ ተዋጠች ። ዐይኖቿን በልጥጣ በመክፈት የግንባሯን ቆዳ ሸብሸባና ልጅዋንም ዐይን ዐይኑን እየተመለከተችው ከቆመችበት መሀል ቦታ ላይ ተገትራ ቀረች ። ከዚያም ዝግ ባለ አነጋገር የሚከተለውን ጠየቀችው ፡—

«አሁን ወደከተማ ነው የሄደችው?»

«አዎን» አላት ።

«ውይ! ውይ! አትፈራም እንዴ?»

«አንቺ ራስሽም አይተሻት የለም እንዴ? አትፈራም» አላት ፓቬል እየሳቀ ።

«ግን ለምን ሄደች? እዚሁ ቀርታ ከኔ ጋር ታድር ነበርኮ?» በማለት እናት ተናገረች ።

---

* ቬርስታ ፡ — የርቀት መለኪያ ነው ። 1 ቬርስታ ከ 1 ኪሎ ሜትር ትንሽ በለጥ ይላል ። (ተርጓሚው)

«ይኽ ሊሆን አይችልም ነበር ። ጧት ሰዎች ሊያዩዋት ይችላሉ ። ይኽ እንዲሆን ደግሞ አንፈልግም» አላት ።

እናት በሃሣብ ተውጣ ውጪ ውጪውን በመስኮት በኩል ታስተውል ጀመር ። ከዚያም ፡ —

«ፓቬል ፣ አደጋው የቱ ላይ እንደሆነና ፣ ክልክልነቱስ የቱ እንደሆነ እኔ ሊገባኝ አይችልም ። የምትፈጽሙት ስሕተተኛ ተግባር የለም ። ለመሆኑ ስሕተት ትፈጽማላችሁ እንዴ?» በማለት ጠየቀችው ።

የሚያሳስባት ጉዳይ ይኽ ነበር ። ስለዚህም ትክክለኛውን ማረጋገጫ ልጅዋ እንዲነግራት ፈለገች ። እርሱም በተረጋጋ መንፈስ እና ዐይን-ዐይኖቿንም እየተመለከተ የሚከተለውን መለሰላት ፡ —

«የለም ፣ ስህተት አንፈጽምም ። ያም ሁኖ ግን ፣ አንዱን ቀን ሁላችንም እሥር ቤት እንገባለን ። ይኽንን ማወቅ አለብሽ ...» አላት ።

እጆቿ ተንቀጠቀጡ ። ዝግ ባለ አነጋገርም የሚከተለውን ጠየቀችው ፡ —

«ምናልባትም ደግሞ — የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ታክሎበት እሥር-ቤት ከመግባት ትድኑ ይሆናል?» አለችው ።

«የለም ። እኔ በውሸት አንቺን ልሸነግልሽ አልሻም ። እሥር-ቤት ከመግባት አናመልጥም!» አላት ።

ፈገግ አለ ።

«ሂጂና ተኚ ። ደክሞሻል ። ደህና እደሪ!» አላት ።

ብቻዋን ሁና ሳለ ፣ ወደመስኮቱ አጠገብ ሂዳ ውጪ-ውጪውን ትመለከት ጀመር ። ውጪው ብርዳማና ጭጋጋማ ነው ። ዘመም ብለው ከቆሙት ትንንሽ ጎጆዎች ላይ የተከመሩትን በረዶዎች ነፋሱ ከግድግዳ-ግድግዳ እያጋጨና መሬት ሲደርሱም የፉጨት ድምፅ



እያሰማ እንደገና እየጠራረገ በመውሰድ በመንገዱ አኳያ ያንከወክዋቸዋል ።

«ፈጣሪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ይቅር በለን!» በማለት ቀስ ብላ ተናገረች ።

ልቧ በሀዘን ተሰበረ ። ቢራ-ቢሮ በምሽት ሰተት ብላ ወደቤት ድንገት እንደምትገባ ሁሉ ፣ ልጅዋ ፓቬል በተረጋጋ ሙሉ ልብ ወደፊት ይጠብቀናል ብሎ የነገራት የመከራ ጊዜም ድንገት ሰተት ብሎ ከሠራ አከላቷ በመግባት አሸበራት ። ከፊት-ለፊቷ በረዶ የተጋገረበት ጉብታ ያለ መስሎ ታያት ። አንድ ነጭ አውሎ ነፋስ በጉብታው በኩል እየነፈሰ በረዶውን በመበታተን ወደላይ በቀጭኑ አሞልሙሎ ሲያወጣው የታያት መሰላት ። ከጉብታማው ቦታ መሀከሉ ላይ ጥቁር ልብስ የለበሰች አንዲት ትንሽ ልጃገረድን ነፋሱ ከወዲያ-ወዲህ ያንገላታታል ። ነፋሱ ጥቅልል ብሎ እግሯ ሥር እየነፈሰ ከገባ በኋላ የለበሰችውን ቀሚስ በመገላለብ በቅዝቃዜው ተናዳፊ የሆነውን በረዶ ፊቷ ላይ ያርከፈክፈው ጀመር ። የልጅ እግሯ በበረዶው ክምር ውስጥ ጥልቅ-ጥልቅ እያለ መራመድ ስለተሳናት የምትጓዘው በችግር ነው ። ቀዝቃዛ እና አሥፈሪ ውድቅት ነበር ። በዚህ አበላሽና አጥፊ በሆነው የበልግ ነፋስ ውስጥ አንድ ብቻዋን ሁናና አዘንብላ እንደቆመች አክርማ ፤ ከሰውነቷ ጎበጥ ብላ ዊን-ዊን በማለት ትራመድ ነበር ። በስተቀኟ በኩል ከረግረጋማው ቦታ አንስቶ ተንጣልሏል ። ክረምት በመሆኑ ምክንያት ቅጠሎቻቸው ከላያቸው ላይ የረገፉባቸው ቤርዮዝካ የተሰኙትን ዛፎች ፣ እና አሲና የተሰኙትን ዛፎች ደግሞ ነፋሱ በላያቸው ሽው እያለባቸው ያፏጫሉ ። ከሩቅ ባሻገር የከተማው ብርሃን ብዥ-ብዥ ሲል ይታያል ።

«ቸሩ መድሃኔ ዓለም ፣ ምህረትህን አውርድልን!»

በማለት በፍርሃት እየተንቀጠቀጠች እናት ቀስ ብላ ተናገረች ።

7

ቀኖቹ ሳምንታትን እየወለዱ ፣ ሳምንታትም ወራትን እየወለዱ ልክ አንገት ላይ እንደሚታሠሩ የጌጥ ዶቃዎች አንዱ ቀን በሌላው ቀን ላይ እየተደራረበ ይገሠግሥ ጀመር ። ሁልጊዜ ቅዳሜ-ቅዳሜ የፓቬል ጓደኞች እርሱ ቤት ይሰበሰቡ የነበረ ሲሆን ፣ እየአንዳንዱ ስብሰባም ፤ አንድ በሩቅ ከታቀደ ዓላማ ላይ ለመድረስ ከፍተኛ ርዝማኔ ባለው የመወጣጫ ደረጃ በኩል ሰዎች ዝግ ብለው ደረጃውን አንድ-በአንድ እያሉ እንደሚወጣጡት ዓይነት ነበር ።

ቀድሞ ይሰበሰቡ በነበሩት ሰዎች ላይ ሌሎች አዳዲስ ሰዎችም ታከሉባቸው ። ቭላሶቭ ቤት ውስጥ የምትገኘው ትንሽ ክፍል ጢቅ ብላ በሰዎች ትመላ ጀመር ። ናታሻ ሁል ጊዜም ስትመጣ ደክሟትና በርዷት ሲሆን ፣ ሁልጊዜም ደግሞ ደስተኛ ሁና ትታይ ነበር ። የፓቬል እናት ለናታሻ የእግር ሹራቦች ሠርታላት ፤ እርሷው ራሷ እግሯ ውስጥ አጠለቀችላት ። ናታሻ ሳቀች ። ይሁን እንጂ ድንገት በዝምታ ተውጣ ታስብ ጀመር ።

ከዚያም ዝግ ባለ የቀስታ አነጋገር የሚከተለውን ተናገረች ፡ —

«አንድ ጊዜ ልክ እንደርስዎ ደግ የነበረች አሳዳጊ ሞግዚት ነበረችኝ! ይገርማልኮ ፣ ፔላጌያ ኒሎቭና ፣ አዩ ፣ የሠርቶ-አደሮች አኗኗር ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ከፍተኛ ችግር የተመላበት አኗኗር ነው ። ያም ሆኖ ግን ከነዚያ ከሌሎቹ ሰዎች ይበልጥ ደጎች ናቸው» በማለት «እነዚያ ሰዎች» ያለቻቸውን ለማሳየት በሩቅ-በሩቅ አመለከተች ።



«ይኼውልዎት እንግዲህ ፣ ከወላጆችዎ ተነጥለው እንዲህ ብቻዎን ነው ያሉት ማለት ነው...» ካለች በኋላ እናት ንግግሯን መጨረስ አቅቷት ነበር ፤ ይሁን እንጂ የናታሻን ፊት በምትመለከትበት ጊዜ አንድ ምክንያቱ ላልገባት ነገር ምሥጋና ለናታሻ ለማቅረብ ከጀላት ። ወለሉ ላይ ከናታሻ ፊት ለፊት ቁጭ አለች ። ናታሻም ፈገግ በማለት ከአንገቷ ጎንበስ ብላለች ።

«ሀ! ከወላጆችሽ ተነጥለሽ አሉኝ!» በማለት ናታሻ የእናትን አነጋገር ደግማ አነሳች ። ከዚያም ፡ — «ይኼ ንን ከምንም አልቆጥረውም ። አባቴ ክፉ ሰው ነው ። ወንድሜም እንደርሱ ክፉ ነው ። ጠጪም ጭምር ነው ። ታላቅ እህቴ በኑሮዋ ደስተኛ አይደለችም ። ከእርሷ በዕድሜ ብዙ ዓመት የሚበልጣትን ነው ያገባችው ። ባሏ ሀብታም ቢሆንም በጣም ቆንቋና ስስታም ነው ። እናቴ ግን ፣ በጣም ታሳዝነኛለች ። ልክ እንደርስዎ ቅን ሴት ነች ። እንደጥንቸል ትንሽ ነች ። ልክ እንደጥንቸል ፈጣን ስትሆን ፣ ያየችውን ሁሉ ትፈራለች ። እንዲህ እንዳይመስልዎት ፣ አንዳንድ ጊዜ እርሷን ለማየት እንዴት መሰለዎት የምጓጓው!» አለች ።

«አይ የኔ ምስኪን!» አለች እናት ራሷን በሀዘን ስሜት በማወዛወዝ ።

ናታሻም ወዲያው ፈጥና ራሷን ቀና አደረገች ። አንዳች ነገርን ወዲድ ከዚህ ብላ እንደምትገፋ ዓይነት እጅዋን አንቀሳቀሰችና የሚከተለውን ተናገረች ፡ —

«አይደለም ፣ አይደለም ። አንዳንዴ በጣም እደሰታለሁኝ — እጅግ በጣም እደሰታለሁኝ!» አለች ።

ፊቷ ፍም መሰለ ፣ ሰማያዊ ዐይኖቿም ቦግ-ቦግ አሉ ። እጆቿን በእናት ትከሻዎች ላይ አሳርፋ የሚከተለውን በዝግታ እና ስሜት በሚቀሰቅስ አባባል ተናገረች ፡ —

«እንደምን ያለ ታላቅ ተግባር በማከናወን ላይ

መሆናችንን የሚያውቁ ቢሆኑ ኖሮ ፣ የተገነዘቡ ቢሆኑ ኖሮ ይኽንን ባላሉም ነበር!» አለች ።

ቅናት ነው ሊባል ምንም ያልቀረው ዓይነት ስሜት በፔላጌያ ቭላሶቫ ልብ ውስጥ አደረ ። ከወለሉ ላይ እየተነሳችም በትካዜ ስሜት የሚከተለውን ተናገረች ።

«እኔማ ለማወቁም ለመገንዘቡም አሮጊት ነኝ ። ወዲህም ደግሞ ያልተማርኩ መሀይሚት ...» አለች ።

አሁን ረዘም ላለ ጊዜ እና በሞቀ ክርክር ብዙውን ንግግር የሚያሰማው ፓቬል ነው ። ከጊዜ ጊዜም እየከሳ በመሄድ ላይ ነው ። ናታሻን ሲመለከትና ከርሷ ጋርም ሲነጋገር አተኩረው በኮስታራነት ተመልካች የሆኑት ዐይኖቹ ረገብ ይላሉ ፣ ድምፁም ይበልጥ ዝቅ ይላል ፣ ጠባዩም የረጋ ይሆናል ።

«አይ ፣ ፈጣሪዬ በዚሁ እንዲቀጥል አድርግልኝ!» ብላ እናት በልቧ አሰበች ። ፈገግም አለች ።

በስብሰባቸው ላይ የሚያደርጉት ክርክር እጅግ የተሟሟቀ እና ጨኸቱም የበረታ በሆነ ቁጥር ፣ ኾኾል ከተቀመጠበት ብድግ በማለት እንደደወል ምላስ ከወዲያ-ወዲህ በመወዛወዝ ግልጽ እና በጎ የሆኑ ጥቂት ቃላቶችን ጣል ያደርጋል ። ይኸ ንግግሩም በክፍሉ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም በመረጋጋት ቀዝቀዝ እንዲሉ እና በጥሞና እንዲያተኩሩ ያደርጋቸዋል ። ቅፍፍ ያለው የሚመስለው ቬሶቭሺኮቭ ሁልጊዜም ሌሎችን አንድ ነገር እንዲያደርጉ ይጠይቃል ። ክርክሮቹን ሁሉ የጀመሩት እርሱ እና ሳሞይሎቭ የተሰኘው ባለቀዩ ፀጉር ናቸው ። ራሰ ሞላላ የሆነውና በአሻቦ ጨው የታጠበ የሚመስለው ኢቫን ቡኪንም የነርሱን ሃሣብ ደጋፊ ነው ። ለስላሳ እና ንጹህ የሆነው ያኮቭ ሶሞቭ የተናገረው ትንሽ ሲሆን ፣ ንግግሩ ግን ኮስተር ባለ ድምፅና በቁም-ነገር የተመላ ነው ። እርሱ



እና ግንባረ-ረኸሩ ፌዎዶር ማዚን ሁልጊዜም ፓቬልን እና ኾኾልን ይደግፋሉ ።

አንዳንድ ጊዜ በናታሻ ምትክ ኒኮላይ ኢቫኖቪች የተሰኘው ፣ የዐይን መነጽር የሚያደርግና አነስ ያለ ነጭ ጺም ያጤመው ሰው ለስብሰባው ይመጣል ። የትውልድ ቦታው ራቅ ካለ ጠቅላይ ግዛት ሲሆን ፣ ባነጋገር ሥልታቸው ደግሞ የሚናገሯቸውን ቃላቶች «ኦ» በሚል ፊደል በመደምደማቸው የታወቁ ሕዝቦች ከሚኖሩበት ጠቅላይ ግዛት ነው ። እንደው በጠቅላላ «የዳር አገር ሰው» ነበር ። የሚያቀርባቸው ንግግሮች ሁሉ የተመሠረቱት ሰዎች የዕለት-በዕለት ኑሮዋቸውን ለመኖር በሚያስፈልጓቸው ተራ በሆኑ ነገሮች ላይ ነበር — ስለቤተሰብ አኗኗር ሁኔታ ፣ ስለሕፃናት ፣ ስለንግድ ፣ ስለፖሊሶች ፣ ስለ ዳቦ እና ሥጋ ዋጋ እነዚህን በመሳሰሉ ነገሮች ላይ ነበር ። ይኸንን ገለጻ በማድረጉም ፣ ትክክለኛ ያልሆነውን ፣ ጅላ-ጅል እና አስቂኝ የሆነውን ሁሉ ፣ ነገር ግን ደግሞ ሰፊውን ሕዝብ ጎጂ የሆነውን ሁሉ ይናገር ነበር ። ሰው ሁሉ ደምበኛ እና ሀቀኛ የሆነ አኗኗር ከሚኖርበት ሩቅ ከሆነ ቦታ የመጣ ሰው መሆን አለበት በማለት እናት ገምታለች ። እዚህ አሁን የሚገኝበት አካባቢ ያለው አኗኗር ሁሌ ግራ ያጋባው ከመሆኑም በስተቀር ሊለምደው የማይችለው እና ከቶውንም የማይቀበለው ዓይነት አኗኗር ሁኖበታል ። የአኗኗሩን ዓይነት ጠልቶታል ። ይኸ ጥላቻውም የረጋ እና አንድ የፀና መንፈስን ያሳደረበት ሲሆን ይኸውም ሁኔታዎችን ለርሱ በሚስማማ ዓይነት ለመለወጥ የመሻቱ መንፈስ ነው ። ፊቱ ቢጫማ ነው ። ከዐይኖቹ በላይም ቀጫጭን መሥመሮች ተጋድመውበታል ። ድምፁ ለስላሳ ሲሆን እጆቹ ደግሞ ሁልጊዜም ሞቃት ናቸው ። ፔላጌያ ቭላሶቫን ሲጨብጣት ሁልጊዜም እጇዋን ሙሉ-በሙሉ ግጥም አድርጎ በመጨበጥ

ሲሆን ፣ ይኸንን ከመሰለ የእጅ ለእጅ መጨባበጥ በኋላም እናት ልቧ ረግቶ ትዝናናለች ።

በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ ሌሎችም ሰዎች ከከተማ ይመጣሉ ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል አዘውትራ ትመጣ የነበረችውም አንዲት ረዥም እና ሸንቃጣ የሆነች ፍም የመሰለ መልክ ጎላ-ጎላ ያሉ ዐይኖች ያሏት ልጃገረድ ነበረች ። ስሟም ሳሻ ይባላል ። አረማመዷ እና እንቅስቃሴዋ ልክ እንደወንድ ነው ። ስትናገር በመኮሳተር መልክ ሁለቱንም ቅንድቦቿን ወደላይ በልጠጥ አድርጋ ትሸበሸባቸዋለች ። እንደስንደዶ ቀጥ ብሎ በርዝመት የወረደው የቀዳዶች አፍንጫዋ ጠባብ ቀዳዶች በምትነጋገርበት ጊዜ ይርገበገባሉ ።

«እኛ ሶሻሊስቶች ነን» በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ ጉልህ እና ግልጽ በሆነ ንግግር ያስታወቀችው እርሷ ነበረች ።

እናት ይኸንን አባባል ስትሰማ በዝምታ እና በመደነቅ ስሜት ልጃገረዲቱን ተመለከተቻች ። ከዚህ ቀደም ዛርን* የገደሉ ሶሻሊስቶች መሆናቸውን እናት በወጣትነቷ ሰምታለች ። ዛሩ ፣ ገባሮችን ከመሬት መኳንንት የበላይ ገዢነት አላቅቆ ነፃ ስላወጣቸው ፣ ይኸንን ቁጭታቸውን በዛሩ ላይ እስካልተበቀሉ ድረስ ፀጉራቸውን ላይቆርጡ እርስ-በእርሳቸው ተማምለው ነበር የሚባል ወሬ በዚያን ጊዜ ተወርቶ ነበር ። ሶሻሊስቶች የተባሉትም በዚህ ምክንያት ነበር ። አሁን ደግሞ ልጅዋና ጓደኞቹ ራሳቸውን ሶሻሊስት ብለው ለምን እንደሚጠሩ እናት ግራ ገብቷታል ።

ሰዎቹ በሙሉ ከሄዱ በኋላ ፓቬልን እንደሚከተለው ጠየቀችው ፡ —

---

* ዛር ፡ — የሩሲያ ንጉሠ ነገሥታት መጠርያ ነው ። (ተርጓሚው)



«ፓሻ ፤ አንተ ሶሻሊስት ነህ እንዴ?»

እንደወትሮው ፊት-ለፊቷ ቀጥ ብሎ እና ጠንከር ብሎ በመቆም ፡ —

«አዎን ፣ ነኝ ። ምነው?» አላት ።

እናቱም በረዥሙ ተነፈሰችና ዐይኖቿን ከርሱ ላይ መለስ አድርጋ የሚከተለውን ጠየቀችው ፡ —

«ፓቬል ፣ ዕውነትክን ነው እንዴ? ሶሻሊስቶች እኮ ዛሩን የሚቃወሙ ናቸው ። እንደውም ከዚህ ቀደም አንድ ዛር ገድለዋል» አለችው ።

ፓቬልም አገጩን በእጁ እያሻሸ የነበሩበትን ክፍል በመንጎራደድ እና አጠር ያለ ሳቅ እየሳቀ የሚከተለውን መለሰላት ፡ —

«እኛ እንደዚህ ያሉ ነገሮችን ማድረግ አንሻም!» አላት ።

ከዚያም መራራ በሆነ እና ረጋ ባለ ድምፅ ረዘም ላለ ጊዜ አወራላት ። እርሷም ፊት-ፊቱን እየተመለከተች በሃሳቧ የሚከተለውን አሰበች ፡ —

«እንዲህ ያለ አንዳችም ስህተት አይፈጽምም ። ኧረ አያደርገውም!» በማለት አሰበች ።

ከዚያ በኋላ ይኸ አስፈሪ የሆነ «ሶሻሊስት» የተሰኘ ቃል በቤታቸው እስኪሰለች ድረስ በተደጋጋሚ ይሰማ የነበረ ሲሆን ፣ እንደሌሎቹ እንግዳ እንደነበሩት ቃላት ስለለመደችው በቃሉ አጠራር አትደነግጥበትም ። ይሁን እንጂ ሳሻን አልወደደቻትም ። እርሷ ስትኖርም መንፈሷ ከመረበሹም በስተቀር ቅር ይላታልም ።

ባለመደሰት መንፈስ ከንፈሮቿን ግጥም ካደረገች በኋላ ስለ ሳሻ ያላትን አስተያየት አንድ ቀን ለኾኾል ነገረችው ፡ —

«ሳሸንካ* በሃሳበ ጽኑነት ግትር ነች! ሁሉንም ታዝ

---

* ሳሸንካ ፡ — ሳሻ የሚለው መጠርያ ተቆላምጦ ሲጠራ ነው ። (ተርጓሚው)

ዛለች ። ይኸን አድርጉ! ያን አታድርጉ! ትላለች» አለችው ።

ኾኾል ልቡ ተነክቶ በመንከትከት ሳቀ ። ከዚያ ም ፡ —

«እምዬ ፣ እርስዎ እንደው የዝምብ ጠንጋራም ቢሆ ን ለይተው ያውቃሉ ማለት ነው! አይደለም እንዴ ፣ ፓቬል?» በማለት ፓቬልን ከጠየቀ በኋላ ፣ ዐይኖቹን ብልጭ-ድርግም በማድረግም ቀጠል አድርጎ «ይኸ የ እርስዎ ክቡርነት ነው!» በማለት እናትን ተናገረ ።

ፓቬልም ድርቅ ባለ አነጋገር ፡ —

«ጥሩ ልጅ ነች» አለ ።

ኾኾልም የፓቬልን አባባል እንደገና በማረጋገጥ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«እርግጥ ነው ጥሩ ልጅ ነች ። ነገር ግን አንድ ነገር እርሷ አትገነዘብም ። ይኸውም እርሷ አንድን ነገር ማድረግ 'አለብኝ' ባይነች ። እኛ ደግሞ ያንኑ ነገ ር መደረግ 'ይቻላል' ፣ ልናደርገውም 'እንችላለን' ነው የምንለው!» በማለት መለሰ ።

ከዚያም እናት በማወቅ ልትደርስበት በማትችለው ሁኔታ ስለአንድ ጉዳይ መከራከር ጀመሩ ።

ሳሻ በፓቬል ላይ ይበልጥ ግትርና ጠንካራ እንደ ሆነች እናት ተገንዝባለች ። እንደውም አንዳንድ ጊዜ በቁጣ ትጮህበታለች ። በዚህን ጊዜም ፓቬል ምንም አይልም ። በናታሻ ላይ እንደሚያደርገው ሁሉ ለስለስ ባለ አመለካከት እየተመለከታት ብቻ ይስቃል ። እናት ደግሞ ይኸን የልጃገረዲቱን ሁኔታ አልወደደችም ።

አንዳንድ ጊዜ እክፍሉ ውስጥ የተሰበሰቡት በሙ ሉ ፣ ድንገት በደስታ ማዕበል ተውጠው ሲታዩ እናት ሁኔታውን እያየች ትደነቃለች ። ብዙውን ጊዜ ይኸንን ዓይነቱ ሁኔታ የሚደርሰው የውጭ ሀገር ወዝ-አደሮ ችን እንቅስቃሴ ስለሚመለከቱ ጉዳዮች ጋዜጣዎችን ማታ-ማታ በሚያነቡበት ጊዜ ነው ። ከዚያም ዐይኖቻ



ቸው በደስታ ፈክቶ ግልፅ እና ጉልህ የሆነ ሳቃቸው ን በመሳቅ እርስ-በርሳቸው በፍቅር ስሜት ትከሻ ለትከሻ እየተጓሸሙ ልክ እንደሕፃን ልጅ አኳኋን በደስታ ፍንድቅድቅ ይላሉ ።

ደስታውን እንደመጠጥ ጠጥቶት የሠከረ ያሕል ከመካከላቸው አንዱ ፡ —

«እንዲህ ነው ፣ የጀርመን ጓዶች!» በማለት ይጮሃል ።

«የኢጣልያን ወዝ-አደሮች ለዘለዓለም ይኑሩ!» በማ ለት ደግሞ በሌላ ቀን ይጮሃሉ ።

እንደዚህ የመሳሰሉ የደስታ መግለጫ መልካም ምኞቶቻቸውን ከእነርሱ ብዙ ርቀው ለሚገኙት እና ማንነታቸውንም ለማያውቋቸው ቋንቋቸውንም ለማይገ ባቸው ወዝ-አደሮች ደስታ በተመላበት ጩኸት ሲያ ስተላልፉ እነዚህ የማያውቋቸው የሌላ ሀገር ወዝ-አ ደሮች የሰሙዋቸው እና ደስታቸውንም የተካፈሉዋ ቸው ያህል እየገመቱ ነበር ።

ኾኾል ዐይኖቹ በደስታ ፍልቅልቅ ብለው የሚከተ ለውን ተናገረ ፡ —

«ለእነርሱ ደብዳቤ መጻፍ ጥሩ ሃሣብ አይደለምን? ሩሲያ ውስጥም እንደእነርሱው በተመሳሳይ ሥራ ላይ የተሠማሩ ወዝ-አደር ጓዶች መኖራቸውን እና ተመሳ ሳይ የሆነ ዕምነትንም የሚያሠራጩ መሆናቸውን ፣ ተመሳሳይ ለሆነ ዓላማ የሚኖሩ እና ተመሳሳይ የሆ ነ ድልን ለመቀዳጀት የሚሹ ጓዶች መኖራቸውን እንዲያውቁት ማድረግ ጥሩ ሃሣብ አይደለምን?» አለ ።

ለፈረንሳይ ፣ ለእንግሊዝ ፣ ለስዊድን ወዝ-አደሮችም እንደ ጓደኞቻቸው ፣ የቅርብ እና የልብ ወዳጅ እንደ ሆኑ ዓይነት ፣ ደስታቸውን እና ሀዘናቸውን አብረው እንደሚካፈሉ አድርገው ተመሳሳይ በሆነ የደስታ መ ንፈስ ተውጠው ይናገራሉ ።

በዚች ጠባብ በሆነች ትንሽ ክፍል ውስጥ ከመላ

ው ዓለም ወዝ-አደሮች ጋር በወንድማማችነት የመተሳሰብ ስሜት ተፈጥሮባት ነበር ። ይህ ስሜት እናትነ ጨምሮ ሁሉንም የነካ ስሜት ሲሆን ፣ ምንም እንኳን እናት የዚህን ስሜት ምንነት አውጠንጥና መገንዘብ ባትችልም ኃያልነቱን ተረድታው ነበር — ማለትም ይህ ስሜት እጅግ ወጣት የሆነ ፣ ደስታው እንደመጠጥ የሚያሰክር እና የወደፊቱን ብሩኅ ተስፋም የተጎናጸፈ ኃያል ስሜት ነው ።

አንድ ጊዜ ኾኾልን እንደሚከተለው ተናገረችው ፦ —

«ኧረ እንዴት የተባረካችሁ ናችሁ! አይሁዶች ፣ አርመኖች ፣ አስትርያኖች ፣ ሕዝቦች ሁሉ ጓዶቻችሁ ናቸው ። ለሁሉም ታዝናላችሁም ትደሰታላችሁም!» አለችው ።

ኾኾልም እንደሚከተለው መለሰላት ፦ —

«የኔ እምዬ! እንዴታ ለሁሉም እንጂ ፣ ለሁሉም! እኛ ከጎሣ ጎሣ እና ከዘር ዘር አንለይም ። እኛ የምንለየው ጓዶችን እና ጠላቶችን ብቻ ነው ። በዓለም የሚገኙ ወዝ-አደሮች ሁሉ ጓዶቻችን ናቸው ። የዓለም ሃብታሞች ፣ የዓለም መንግሥታት ሁሉ ጠላቶቻችን ናቸው ። በዚች ዓለም ላይ ዐይናችንን ገለጥ አድርገን እኛ ወዝ-አደሮች ምን ያህል ብዙ እንደሆንን ስንመለከት ፣ ምን ያህል ጠንካሮች እንደሆንንም ስንገነዘብ ለደስታችን ማብቂያ የለውም ። ልባችንም በታላቅ የበዓል ስሜት ይረካል! አዩ እምዬ ፣ የፈረንሳዩም ሆነ የጀርመኑ ወዝ-አደር ሁኔታዎችን የሚመለከታቸው ልክ እኛ እንደምናደርገው ባለ ሁኔታ ነው ። የጣሊያኑም ቢሆን ፣ ሁሉም ቢሆኑ ። ሁላችንም የአንዲት እናት ልጆች ነን ። ሁላችንም በመላው ዓለም የሚገኙ የሠርቶ-አደሮች ወንድማማችነት የማይናወጹ የጋለ የስሜት ማዕበል ውስጥ ተውጠን እንገኛለን ። ይህ ስሜት ልባችንን በደስታ ያሞቀዋል ። ፍትሕ በሰፈነበት



ሁኔታ በሰማዩ ላይ ብርሃኗን እንደምትፈነጥቅ ፀሐይ ማለት ነው ። ያ ሰማይ ደግሞ የወዝ-አደሩ ልብ ነው ። ማንም ሆነ ማን ፣ የፈለገውን ዓይነት መጠርያ ስም ቢኖረው ፣ ትላንትናም ሆነ ዛሬ ፣ ለወደፊቱም ቢሆን እስከዘለዓለመ-ዓለም ድረስ ሶሻሊስት የሆነ ሁሉ የመንፈስ ወንድማችን ነው!» በማለት ተናገረ ።

ይህ የልጅ ስሜት የሚመስል ፣ ነገር ግን እጅግ ጠንካራ የሆነ ስሜት ፣ ልዩ ልዩ በሆኑ መንገዶች ወደማይበገር ኃያልነት በመዳበር ከጊዜ ወደጊዜ በመደጋገም በሁኔታዎቻቸው ላይ ይከሠት ነበር ። እናትም ይኸንን ስትመለከት ፣ ዕውነትም በዓለም ላይ ልክ በዐይኖቿ እንደምታየው እንደ ፀሐይ ታላቅ እና በጎ የሆነ ነገር የተፈጠረ መሆኑ እንዲሁ በስሜት ታወቃት ።

ብዙውን ጊዜ ያዜማሉ ። ማንም የሚያውቃቸውን የዘፈን ዜማዎች ጉልህ እና አስደሳች በሆነ ድምፅ ያዜማሉ ። አንዳንድ ጊዜ ግን ቁም ነገር ያለው መልዕክት የያዙ አዳዲስ መዝሙሮችን ደስ በሚያሰኝ እና ከዚህ ቀደም ባልተሰማ የዜማ ምት ያሰማሉ ። እነዚህን የመሳሰሉትን መዝሙሮች የሚያዜሙት ልክ በዝግታ እንደሚዜም የቤተ-ክርስቲያን ዜማ ዓይነት ቀስ ባለ የለሆሳስ ድምፅ ነው ። የአዚያሚዎቹ ፊቶች በስሜት ፍም የሚመስሉ ሲሆኑ ከአንደበታቸው የሚወረወሩት ቃላትም አዚያሚዎቹ በመንፈሳቸው ታላቅ ኃይል ያበጁ መሆናቸውን ያመለክታሉ ።

እናት እነዚህን ከመሳሰሉት መዝሙሮች መካከል በአንዱ መዝሙር በተለይ ተመስጣለች ። ይህ መዝሙር በተጠራጣሪነት እና ሙሉ-በሙሉ እርግጠኛ ባለመሆን መንፈስ መውጫ መግቢያው ከማይታወቅ ቦታ የምትገኝ የተጎሳቀለች ነፍስ የምታሰማውን ዓይነት ድምፅ የሚያሰማ ዜማ አልነበረም ። ወይንም ደግ

ም በእጦት የተጎሳቆሉ፣ በፍርሃት አዘቅት የተዋጡ፣ ማንነታቸው እና ሰብአዊ ክብራቸው የተረገጠባቸው ሰዎች የሚያቀርቡትን እሮሮ የሚያንጸባርቅ አልነበረም። የጭፍን የዳሰሳ አየርን ለመጨበጥ በሃዘንና በትካዜ ሁኖ እህህ በሚል እንጉርጉሮ አንድ ኃይል እንደሚያሰማው ዜማ ዓይነትም አልነበረም። አንዱን ከሌላው ሳይለይ በበጎውም በክፉውም ጉዳይ ላይ ተወርውሮ ጉብ ሊልበት የሚሻ የአጓጉል ደፋርነት ምልክትም አልነበረም። በቂም በቀል መንፈስ ተነሳስቶ ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ የነበረውን ለማፈራረስ እንጂ መልሶ ለመገንባት የማይቻለው መሆኑን የሚያሳይ ስሜት በመዝሙሩ ውስጥ አይገኝበትም። በዚህ መዝሙር ውስጥ የቀድሞው የባርነት ዓለም መንፈስ፡ አይገኝበትም።

መዝሙሩ በውስጡ የያዛቸውን ኃይለ-ቃላት እና ኮስታራ ጣዕመ-ዜማ እናት ያልወደደችው ቢሆንም ቃላቱን እና ጣዕመ-ዜማውን ሸፍኖ ሰውን በሃሣብ ማዕበል የሚያጥለቀልቅ አንድ ስሜትን ቀስቃሽ የሆነ አንዳች ኃይል በውስጡ ይዞ ነበር። ይኸንን አንዳች ኃይል በክፍሉ ውስጥ በነበሩት ወጣቶች ዐይኖች እና ፊቶቻቸው ላይ ተመልክታለች። ይህ አንዳች ኃይል በእነርሱ ውስጥ ሰርጾ የሚገኝ መሆኑን ከመገንዘቧም በስተቀር፣ ከቃላቶቹ እና ከጣዕመ-ዜማው ባሻገር ከሚገኘው ከዚህ መዝሙር አንዳች ኃይል ሥር ራሷን በማዋል ከማንኛውም መዝሙር ይልቅ ይኸንን መዝሙር በታላቅ ጥሞና እና በከፍተኛ የስሜት መቀስቀስ እናት ታዳምጠዋለች።

ይህንን መዝሙር የሚዘምሩት ዝግ ባለ ድምፅ ቢሆንም፣ የመዝሙሩ ጣዕመ-ቃና ጎልቶ የሚሰማ ነው። የመዝሙሩን ዘማሪዎችም እንደ ጸደይ አየር በአንድነት አዋህዶ የድምጻቸውን ላህይ ያስማማዋል።



«ይህንን መዝሙር አደባባይ ወጥተን ማዜም አለብን!» በማለት መዝሙሩ በተዘመረ ቁጥር ቬሶቭሺኮቭ ፊቱን አኮሳትሮ ይናገራል።

አባቱ አሁንም እንደገና በሌብነት ተይዞ እሥር ቤት በገባ ጊዜ ልጁ ቬሶቭሺኮቭ የሚከተለውን ለጓደኞቹ ነገራቸው፡—

«ከእንግዲህ እኔ ቤት መሰብሰብ እንችላለን...»

ብዙውን ጊዜ ከሥራ በኋላ ምሽቱ ላይ ከፓቬል ጓደኞች መካከል አንደኛቸው እቤት በመምጣት ለመታጠብ እንኳን ጊዜ አጥተውና ተቻኩለው መጻሕፍትን የሚያነብቡ ከመሆናቸውም በስተቀር የሚያነብቡትንም ምንባብ በጽሁፍ ያሠፍራሉ። ራታቸውን ሲበሉና ሻይም ሲጠጡ መጻሕፍቶችን በእጆቻቸው ይዘው ሲሆን፣ ስለሚወያዩት ጉዳይ ምንነት ለመረዳትም ከጊዜ ጊዜ ለእናት እየከበደባት ይሄድ ጀመር።

«እያተምን የምናወጣው የራሳችን ጋዜጣ ያስፈልገናል!» በማለት ፓቬል አዘውትሮ ይናገራል።

ህይወታቸው ፋታ በማጣት የተጣደፈ እና የተጋጋለ በመሆን ከመገስገሱም በስተቀር፣ ንቦች ከአንድ አበባ ወደሌላ አበባ በመዘዋወር ማር እንደሚቀስሙ ሁሉ፣ እነርሱም ከአንዱ መጽሐፍ ወደሌላው፣ ከዚያም ወደሌላው-ወደሌላው እያሉ ዕውቀትን ይቀስማሉ።

«ስለእኛ እያወሩ ናቸው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይይዙናል!» በማለት ቬሶቭሺኮቭ አንድ ቀን ተናገረ።

«አሣ የተፈጠረው ወጥመዱ ከሆነው መረብ ውስጥ ገብቶ ሊያዝ ነው!» በማለት ኾኾል መለሰ።

እናት ኾኾልን ከጊዜ ጊዜ ይበልጥ ትወደው ጀመር። ኾኾል «እምዬ» ብሎ በሚጠራት ጊዜ የኅፃን ለስላሳ እጆች ጉንጯን የሚዳብሷት ያህል ይሰማታል። ፓቬል እሁድ እሁድ ሌላ ሥራ ላይ ከሆነ፣ ኾኾል ለእናት እንጨት ይፈልጥላታል። አንድ ቀን

6 596

ኾኾል በትክሻው የጣውላ እንጨት ተሸክሞ መጣ ። ከዚያም በመጥረቢያ በሚገባ አስተካክለውና በረንዳው ላይ የነበሩትን የበሰበሱ መረማመጃ የእንጨት ደረጃዎች ነቃቅሎ ይህንን ያመጣውን ጣውላ በምትኩ ሠራው ። ሌላ ጊዜ ደግሞ አዘንብሎ ሊወድቅ ምንም ያልቀረውን አጥራቸውን አቅንቶ በደንብ አቆመው ። እነዚህን የመሳሰሉ ሥራዎችን በሚሠራበት ጊዜ ደስ የሚያሰኝና ሀዘን የተቀላቀለው የዜማ እንጉርጉሮ በፉጨት ያሰማል ።

«ኾኾልን ከእኛ ጋር አዳብለን ለምን አናኖረውም? እርስ-በርሳችሁ ከቤት-ቤት በመፈላለግ ከምትሯሯጡ ለሁለታችሁም ይበጃችኋል» በማለት እናት አንድ ቀን ልጅዋን ጠየቀችው ።

«ለምን በችግር ላይ ችግር እንዲደራረብብሽ ትፈልጊያለሽ?» በማለት ፓቬል ትክሻውን ነቅነቅ አድርጎ መለሰላት ።

«የማትረባ ። ከዚህ ቀደም የኖርኩት ኑሮ በሙሉ ፋይዳ-ቢስ የሆነ ኑሮ ነበር ። እርሱን ለመሰለ ጥሩ ሰው ብቸገር ምናለበት?» በማለት መለሰችለት ።

«እሺ ፥ እንዳልሽ ይሁን ። በበኩሌ ከእኛ ጋር ቢኖር እጅግ ደስ ይለኛል!» አለ ።

ኾኾልም ከእነርሱ ጋር ተዳብሎ መኖር ጀመረ ።

8

ከሠፈሩ ዳርቻ ላይ የሚገኘው ይኸ ትንሽ ቤት የሰዎችን ዐይን መሳብ ጀመረ ። አያሌ ሰዎች በአጥሩ በኩል ስግግ እያሉ በጉጉት ለመመልከት ማሾለቅ ጀመሩ ። ወሬው ከወዲያ ወዲህ ይነፍስ ጀመር ። ፈንጠር-ፈንጠር እያሉ ከበስተዳርቻው በኩል በመቆም



ከቶውንም ምን የተደበቀ ምሥጢር እንደሚካሄድ አድፍጦ ለማየት ይሞክራሉ ። በምሽት ደግሞ ሰዎቹ ወደቤቱ ሾከክ ብለው በመጠጋት በመስኮት ጭላንጭል ውስጡን ለማየት ያሾልቃሉ ። ከመካከላቸው አንዱ አንድ ቀን የመስኮቱን መስተዋት አንኳኩቶ ነበር ። ይሁን እንጂ ሁሉም በፍርሃት በረሩ ።

የወይን-ጠጅ ቀለም ያለው ወፍራም ሰደርያ ሁል ጊዜ የሚለብሰው እና ሰለክላካ በሆነ ደም-መሳይ አንገቱ ላይም ጥቁር የሀር መንዲል የሚያሥረው የደስ-ደስ ያለው ቤጉንጾቭ የተሰኘ ሽማግሌ የመሸታ-ቤት ባለቤት ፔላጌያን መንገድ ስትሄድ ድንገት አግኝቶ አቆማት ። ሰልከክ ብሎ በወረደው አፍንጫው ላይ ፍሬሙ ከኤሊ አጥንት የተሠራ የዐይን መነጽር ጉብ ብሎበቿል ። በዚህ ምክንያትም «ባለአጥንቱ ዐይን» እያለ ሰው ሁሉ በቅጽል ስም ይጠራዋል ።

ሽማግሌው እናትን መንገድ ላይ አግኝቶ እንዳቆማት ፋታ ሳይኖረው እና ከእርሷም አንዳችም ምላሽ ሳይጠብቅ የሚከተሉትን ቃላቶች በአንድ ትንፋሽ እያከታተለ ይደረድርላት ጀመር ፡ —

«ጤና ይስጥልኝ ፥ ፔላጌያ ኒሎቭና ፥ እጅጉን እንደምነዎት ፤ ደህናም አይደሉን? ልጅዎስ እንደምንድነው ፤ ደህናም አይደለምን? አሁንም ልጅዎ ሚስት ለማግባትገና አላሰበም እንዴ? እንደሚመስለኝ እርሱ በአሁኑ ጊዜ ለጋብቻ የደረሰ ያሸተ ፍሬ ነው ። ልጆች ቶሎ ከተዳሩ ለወላጅም ይቀላል ። እንጉዳይን ከኾምጣጤ ጋር አዋህደው ሲያቀርቡት ልክ ሁኖ ጣዕሙ ተጣጥሞ እንደሚስማማ ሁሉ ፥ ሰውም ጎጆ ወጥቶ ቤተሰብ ሲመሠርት ሥጋው እና ነፍሱ በመጣጣም ይስማሙለታል ። እኔ እርስዎን ብሆን እድረው ነበር ። ይሄ አሁን የምንኖርበት ዘመን ፥ አንድ ሰው ጊዜውን እንዴት እንደሚያሳልፍ በዐይነ-ቁራኛ ሊቆጣጠሩት የሚ

ገባ ዘመን ነው ። በዚህ በጊዜያችን ሰዎች እንዳሻቸው መኖር ጀምረዋል ። በዛሬው ጊዜ ሰዎች የሚያስቡት እና የሚፈጽሙት ነገር ሁሉ መላ-ቅጡ የጠፋ ነው ። ሰዉ እንደሆን ወደ ቤተእግዚአብሔር መሄዱን ትቶታል ። ሰዎች ከሚሰበሰቡባቸው ቦታዎች ራስን በማግለል እና በየስርቻው ሥር በመሸጎጥ እየተንሾኳሾከ ሁሉም ምሥጢሩን ይመሳጠራል ። እኔ እኮ ግራ ግብት የሚለኝ ፥ ይሄ ሁሉ ምሥጢር መመሣጠር ከቶ ለምኑ ነው? እያልኩኝ ነው ። ሰው ከሰዉስ ለምን ይገለላል ። ከቶ ሰዉ ከሰዎች ፊት በይፋ መናገርን የሚፈራው ምኑን ነው? አሁን ለምሳሌ ከመሸታ-ቤት ሁኖ በግልጽ ማውራት ምን ነውር አለበት? ወይ ምሥጢር! የምሥጢር ቦታው ቤተእግዚአብሔር ብቻ ነው ። በየሥርቻው የተወሳ ምሥጢር አዕምሮ በስሕተት የሚፈጽመው ምሥጢር ነው ። ፔላጌያ ኒሎቭና ፥ በሉ ጤና ይስጥልኝ ፥ በደህና ይዋሉ!» አላት ።

ሽማግሌው ቤጉንጾቭ ንግግሩን ካሰማት በኋላ ባርኔጣውን ከራሱ ላይ አንስቶ እናትን እጅ ነስቷትና ሃሣብ ላይም ጥሏት መንገዱን ሄደ ።

ሌላ ጊዜ ደግሞ የቭላሶቭ ቤተሰቦች ጎረቤት የሆነች ፥ ባሏ ቀጥቃጭ የነበረ የሙት ሚስት ፥ ከፋብሪካው በራፍ ላይ ምግቦችን በመሸጥ ኑሮዋን የምትገፋ ማርያ ኮርሱኖቫ የተሰኘች ሴት ፔላጌያን ገበያ አገኘቻት እና የሚከተለውን ነገረቻት ፦

«ፔላጌያ ፥ ልጅዎን ነቅተው ይጠብቁ!»

«ምነው ፥ ለምን?» በማለት እናት ጠየቀቻት ።

ማሪያ ቀስ ብላ በምስጢር በማሾክሾክ ለእናት የሚከተለውን ነገረቻት ፦

«ወሬው በየቦታው ይነፍሳል ። የኔ እናት ፥ ደስ የማይል ወሬ ነው የሚነፍሰው ። ልጅዎ አንድ የምሥጢር ቡድን ወገን ለይቶ እያቋቋመ ነው ይባላል ። ይኸንን በመሰለው ቡድንም እርስ በእርሳቸው ሊገራረፉ ነው ይባላል ...» አለች ።

እናትም የሚከተለውን መለሰችላት ፦

«አይ ፥ ማርያ ፥ እንደው የሰው ወሬ ነውኮ እባክሽ!» አለቻት ።

«መቼስ እኔማ እሳት ከሌለ ጭስ አይጨስም ብዬ ነዋ!» በማለት ምግብ ሻጪ ተናገረች ።

እናት እነዚህን ሁሉ ንግግሮች ለልጅዋ ነገረችው ። ልጅዋ ፓቬል ግን ትከሻውን ብቻ ሲያነቃንቅ ፥ ኰኰል በቀስታ እና በጥልቀት ሳቀ ። እናትም የሚከተለውን በማከል ተናገረች ፦

«ልጃገረዶቹም ቢሆኑ እኮ በእናንተ ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸዋል ። ለማንኛዋም ልጃገረድ ቢሆን የምትስማሙና ሳንክ የማይወጣላችሁ ጉብሎች ናችሁ ። ታታሪ ሠራተኞች ከመሆናችሁም በስተቀር ጠጪዎችም አይደላችሁም ። ነገር ግን ልጃገረዶችን ሁሉ ዞር ብላችሁም አታስተውሏቸውም ። አጓጉል የሆኑ ባለጌ ልጃገረዶች ከከተማ እየመጡ ይገናኟችኋል የሚባል ወሬም ይወራል » አለች ።

«ኧረ ምነው ፥ እባክሽ!» በማለት በማኩረፍ መልክ ተኮሳትሮ ፓቬል ተናገረ ። ከዚያም ኰኰል በረዥሙ እየተነፈሰ የሚከተለውን ተናገረ ፦

«ኩሬ ውስጥ ያለ ነገር ሁሉ ይከረፋል ። እምዬ ፥ ትዳር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለእነዚህ ለትንንሽ ጅሎች እርስዎ በሚገባ ሊያስረዷዋቸው ይችላሉ ። ከዚያም በኋላ አንገታቸውን ወጥመድ ውስጥ ለመክተት እንደዚህ አይቸኩሉም...» አለ ። እናትም ቀጠል አድርጋ ፦

«አይ የኔ ሸጋ! ኧረ እነርሱ ሁሉንም ነገር ደህና

አርገው ያስተውላሉ ፣ ያውቃሉ ፣ ከጋብቻ ሌላ ታድያ ምን ያድርጉ እንጂ?» አለችው ።
«የሚያስተውሉ-የሚያውቁ ከሆነ ፣ ከዚህ ሌላ የሚያደርጉት ነገር አለ!» በማለት ፓቬል መለሰ ።
እናቱም ኮስተር ያለ ፊቱን እየተመለከተች ፣ —
«ለምን አታስተምሯቸውም? ብልህ-ብልሆቹ እዚህ እናንተ ዘንድ እንዲመጡ ጠይቋቸው» አለች ።
«እርባና የለውም» አለ ልጅዋ ድርቅ ባለ አነጋገር ።
«ግን እኮ ፣ ዕውነትም ለምን አንሞክርም?» በማለት ኾኾል ጠየቀ ።
ለዚህ ጥያቄ መልስ ከመስጠቱ በፊት ፓቬል ጥቂት ዝም ብሎ ነበር ። ከዚያም ፣ —
«ፍቅረኛ ወዳጅ በማበጀት ጥንድ-ጥንድ እየሆኑ ሽርሽር መውጣት ይጀምራሉ ። ከዚያም ከመካከላቸው ገሚሶቹ ይጋባሉ ። ከእኛ ጋር ያላቸው ግንኙነትም ከዚሁ ላይ ያበቃል!» አለ ።
እናት በሃሣብ ተዋጠች ። እንዲህ ጠንካራ የሆነ የመናኝ ባሕታዊ ስሜቱ አሳሰባት ። ሁሉም ቢሆኑ ፣ በዕድሜ ከእርሱ ትላልቅ የሆኑት እንደ ኾኾል የመሳሰሉት ጓዶች ሳይቀሩ የሚያቀርበውን ምክር ሳያስተሀቅሩ እንደሚቀበሉ ታያለች ። ግን ደግሞ የሚፈሩት መሰላት ። ጠንካራ በሆነ መንፈሱ ምክንያትም ማናቸውም ቢሆኑ የማይወዱት መሰላት ።
አንድ ምሽት እናት አልጋዋ ላይ ተኝታ ሳለና ልጅዋ እና ኾኾልም ገና ያነብቡ በነበረበት ወቅት ፣ ድምፅ በሚያሰማው የመኝታ ቤት ክፍሏ አካፋይ በኩል ጎላ ባለ ድምፅ ሲነጋገሩ ሰማች ።
«ይቺን ናታሻን እወዳታለሁኝ» በማለት ኾኾል ድንገት ተናገረ ።
«እንደምትወዳት አውቃለሁኝ!» በማለት ፓቬል ትንሽ ቆየት ብሎ መለሰለት ።



ኾኾል ከተቀመጠበት ቀስ ብሎ በመነሳት በባዶ እግሩ ወለሉ ላይ በረዥም እግሩ ሲራመድ እናት ሰማች ። ከዚያም በቀስታና በትካዜ ያፏጭ ጀመር ። ከዚያም እንደገና ቀስ ባለ አነጋገር የሚከተለውን መናገር ቀጠለ ፣ —
«እንደምወዳት ተገንዝባ እንደሆነ መቸም እንጃ!» አለ ።
ፓቬል ምንም መልስ አልመለሰም ።
«ምን ይመስልሃል?» በማለት በጣም ቀስ ብሎ ፓቬልን ኾኾል ጠየቀው ።
«ተገንዝባዋለች ። እዚህ መምጣቷንም የተወችው በዚህ ምክንያት ነው...» በማለት ፓቬል መለሰ ።
ኾኾል ወለሉን በእግሩ ጫን አድርጎ በመርገጥ እንደገና በቀስታ የሚያፏጨው ፉጨት ቤቱ ውስጥ ይሰማ ጀመር ። በኋላም እንዲህ አለ ፣ —
«ብነግራት ምናለበት?»
«ምኑን ብትነግራት?» አለው ፓቬል ።
«እኔ እርሷን ፣ እኔ ...» በማለት ቀስ ብሎ ኾኾል ንግግሩን ጀመረ ።
«ለምን ትነግራታለህ?» በማለት ፓቬል ንግግሩን አቋረጠው ።
ኾኾል ወለሉ ላይ ከወዲያ ወዲህ መራመዱን ማቆሙን እናት ሰማች ። በመሳቅ ላይ ያለ መስሎም ተሰማት ።
«አንዲት ልጃገረድን ብትወዳት ፣ መውደድህን ለእርሷ መንገር ያለብህ ይመስለኛል ። አለበለዚያ ምንም ዋጋ የለውም!» አለ ኾኾል ።
ፓቬል የሚያነበውን መጽሐፍ አጠፈው ። ከዚያም ፣ —
«ታዲያ ስለነገርካት ምን እንዲሆን ትፈልጋለህ?» አለው ።
«እንዴት?» በማለት ኾኾል ጠየቀው ።

ከዚያም ፓቬል ቀስ ባለ አነጋገር የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«አንድሬይ ፣ ስለምትፈልገው ነገር ግልጽ ያለ አስተሳሰብ እንዲኖርህ ያስፈልጋል ። ለምሳሌ እኔ እንኳን ነው ብዬ አላምንበትም ፣ ብቻ ቢሆንም እርሷም ትወድሀለች እንበል ፣ ከዚያም ትጋባላችሁ ። እንዴት ያለ የተስማማ ጋብቻ ነው! እርሷ የተማረች ምህርት ነች ። አንተም ሠርቶ-አደር ነህ ። ልጆች ይወለዳሉ ። አንተ ብቻ እንደባርያ ብዙ ብዙ መሥራት አለብህ ። ኑሮአችሁ የዕለት እንጀራ ለማግኘት እና የቤት ኪራይ ለመክፈል ሲባል የምታሳልፉት የስቃይ ኑሮ ይሆናል ። ለቆምንለት ዓላማ የምታውሉት አንዳችም ጊዜ አይኖራችሁም ። ሁለታችሁም አንዳችም ጊዜ አይኖራችሁም!» በማለት ተናገረ ።

ፀጥታ ሰፈነ ። ከዚያም ፓቬል አሁንም እንደገና መናገር ጀመረ ። ድምፁም በጣም ለስለስ ብሎአል ።

«አንድሬይ ፣ እንዲህ ዓይነቱን ሃሣብ ብትተወው ይሻላል ። ለእርሷ ሸክም አትፍጠርባት ።»

ፀጥታ ። የግርግዳው ሰዓት መቂናጥ ከወዲያ ወዲህ እየተወዛወዘ ሰኮንዱን ሲቆጥር ቋ-ቋ-ቋ የሚል ቀጭን ድምፅ ያሰማል ።

«ግማሹ ልቤ ያፈቅራል ፣ ግማሹ ደግሞ ይጠላል ። አሁን ይኸንንም ልብ ነው ትለዋለህ?» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

የመጽሐፉ ገጾች መንኮሻኮሽ ጀመሩ ። ፓቬል ንባቡን ቀጥሏል ማለት ነው ። እናቱ መተንፈስ እንኳን ፈርታ ዐይኖቿን በመጨፈን ተጋድማለች ። በኾኾል ከልቧ አዘነችበት ። ከርሱ የበለጠ ደግሞ በልጅዋ አዘነችበት ።

«የኔ ምስኪን ልጅ!» በማለት አሰበች ።

«ስለዚህ ፤ አንዳችም ነገር ለርሷ መንገር የለብኝ



ም ብለህ ነው የምታስበው?» በማለት ኾኾል ፓቬልን ጠየቀው ።

«አዎን መንገር የለብህም» ብሎ ፓቬል በዝግታ መለሰለት ።

«ጥሩ ፤ እንግዳው አልነግራትም» አለ ኾኾል ። ከጥቂት ሰኮንዶች በኋላም ለስለስ ባለና ቅሬታ በተቀላቀለው አነጋገር ኾኾል ቀጠል አድርጎ የሚከተለውን ተናገረ ፡ — «ፓቬል ፣ አንተም ልክ እንደኔው ሲደርስብህ ትቸገራለህ» አለው ። ፓቬልም ፡ —

«አሁንም እየተቸገርኩ ነው...» አለው ።

የቤታቸውን ግድግዳ ነፋሱ ይወለውለዋል ። ግድግዳው ላይ የተሰቀለው ሰዓት መቂናጥ የጊዜውን ሂደት ሳያቋርጥ በመንቀሳቀስ ያመለክታል ።

«ቀልዴን እኮ አይደለም የምልህ!» አለው ኾኾል ዝግ ባለ አነጋገር ።

እናት ጭንቅላቷን ትራሱ ውስጥ ደብቃ ድምፅ ሳታሰማ በለቅሶ ትንሰቀሰቃለች ።

ጧት አንድሬይን ከቁመቱ አጠር ብሎና ይበልጥም ተወዳጅ ሁኖ ያገኘችው መሰላት ። ልጅዋ ግን ያው እንደዱሮው በቁመቱ ግትር ፤ በአካሉ ቅጥን ፤ እና በአኳኋኑም ፀጥ እንዳለ ነበር ። እናት ከዚህ ቀደም ኾኾልን ስትጠራው በሙሉ ስሙ በአክብሮት አንድሬይ ኦኒሲሞቪች ብላ ስሙን ከነአባቱ በመጥራት ነበር ። አሁን ግን ሳይታወቃት ስሙን ብቻ በማቆላመጥ በመጥራት የሚከተለውን ተናገረችው ፡ —

«አንድርዬ ፣ መጫሚያህን በጊዜ ብታስጠግነው ይሻልሃል ። አለበለዚያ ብርድ በእግርህ ገብቶ ጉንፋን ይይዝሃል!» አለችው ።

«በሚቀጥለው ደሞዝ ላይ ሌላ መጫምያ እገዛለሁኝ» አለ እየሳቀ ። ከዚያም ረዥም ክንዱን እናት ትከሻ ላይ ድንገት አሳረፈና የሚከተለውን ተናገራት ፡ —

«ምናልባትም እርስዎ ወላጅ እናቴ ሊሆኑ ይችላሉ ። 
መልከ-መልካም ስላልሆንኩኝ ልጄ ነው ብለው መቀ
በል ሳይፈልጉ ቀርተው ይሆናል ። አይደለም እንዴ?» 
አላት ።

መልስ ሳትመልስለት እጁን አሻሸችው ። የምትወ
ደው መሆኑን የሚገልጹ ብዙ ቃላት ልታሰማው ፈ
ልጋ ነበር ። ልቧ በሀዘን ስለተነካባት ከአንደበቷ ቃ
ላት ሊወጡላት አልቻሉም ።

## 9

ሶሻሊስቶች በሰማያዊ ቀለም የተጻፉ በራሪ ጋዜ
ጣዎችን ያሠራጫሉ የሚል ወሬ በሠፈሩ አካባቢ መ
ወራት ጀመረ ። እነዚህ ጋዜጣዎችም የፋብሪካውን አስ
ተዳደር ክፉኛ የሚያወግዙ ሲሆኑ ፤ በፒተርቡርግ ከ
ተማ እና በደቡባዊው ሩስያ ስለተካሄዱ የሥራ ማቆ
ም አድማዎች ዝርዝር ዜና ያቀረቡ ከመሆናቸውም 
በስተቀር የፋብሪካው ወዝ-አደሮችንም የራሳቸውን 
ጥቅም ለማስጠበቅ እንዲችሉ ኅብረታቸውን ያጠነክ
ሩ ዘንድ ጠይቀዋል ።

ከፋብሪካው ደህና የዐበል ገቢ ያላቸው እና በመካ
ከለኛ ዕድሜ ላይ ያሉ ሰዎች በድርጊቱ ተበሳጭተው 
የነበረ ከመሆኑም በስተቀር ፤ የሚከተለውን ዓይነት 
አባባልም ያሰሙ ጀመር ፡ —

«እነዚህ ሁከት ፈጣሪዎች! ለእንዲህ ያለ ድርጊታ
ቸውስ ግንባር-ግንባራቸውን መከስከስ ነው» እያሉ በድ
ብቅ የሚበትኑትን ጋዜጦች ለአለቆቻቸው እየወሰዱ 
ይሰጡ ጀመር ።

ወጣቶቹ ግን በታላቅ ስሜት ጋዜጦቹን ያነቡ የ
ነበረ ሲሆን የሚከተለውን ዓይነት አባባልም ያሰሙ 
ጀመር ፡ —



«የተጻፈው ሁሉ እርግጥ ነው!»

በየዕለቱ የፋብሪካ ሥራ አካላቸው ድቅቅ ይል 
የነበሩት አብዛኞዎቹ ወዝ-አደሮች ግን ስለጋዜጣው 
የሚሰሙትን አስተያየት ሁሉ ባለመደገፍም ባለመቃወ
ምም ዝም ብለው በማዳመጥ የሚከተለውን ይሉ 
ጀመር ፡ —

«እንደውኮ ነው ፤ ምንም ማድረግ ላይቻል! ማድረግ 
የሚቻል ነገር አለእንዴ?»

ይሁን እንጂ በራሪ ጋዜጦቹ ሰዎቹን ይቀሰቅሷቸ
ው ጀመር ። ጋዜጦቹ አንድ ሳምንት ሳይታዩ ከቀሩ ፡ —

«አዬ! ጋዜጣዎቹን ማተም አቆሙ መሰለኝ!» በማለት 
ሰዎቹ እርስ-በርሳቸው ይነጋገራሉ ።

የሚቀጥለው ሰኞ ላይ ግን አዲስ እትሞች 
ተዘጋጅተው ይሠራጫሉ ። ከዚያም ወዝ-አደሮቹ እርስ-በ
ርሳቸው እንደገና ቀስ እያሉ መንሾካሾካቸውን ይቀጥ
ላሉ ።

በፋብሪካው ውስጥ እና በየመሸታ ቤቱ ከዚህ 
ቀደም ታይተው የማይታወቁ ሰዎች መታየት ጀመሩ ። 
አንዳንድ ሁኔታዎችን መቃኘት እና ማነፍነፍ የጀመሩ 
ሲሆን ጥያቄዎችንም ያቀርቡ ነበር ። ይኸ ሁኔታቸው ፤ 
እንደዚሁም ይበልጥ ጠንቃቃ መሆናቸውና በየሰው 
አያገባቸው ጉዳይ እየገቡ ጥያቄ ማቅረብን ማዘውተራ
ቸው በአካባቢው ስለነርሱ ጥርጣሬ እንዲፈጠር አደ
ረገ ።

በሠፈሩ የደረሰው ይኸ ሁሉ ከፍተኛ ስሜት በ
ልጅዋ ተግባር ምክንያት መሆኑን እናት አሳምራ ታው
ቃለች ። ብዙ ሰዎች ወደርሱ የተሳቡ መሆናቸውን 
ተመልክታለች ። ይኸ በመሆኑ ለልቧ የተሰማት ኩራ
ትም ስለርሱ ደህንነት ከምታስበው ሃሣብ ጋር ተደ
ባልቆባታል ።

አንድ ምሽት ላይ ማሪያ ኮርሱኖቫ በመስኮት በ

ኩል አንኳኳች ። እናትም መስኮቱን እንደከፈተች የሚከተለውን ጎላ ባለ ሹክሹክታ ኮርሱኖቫ ነገረቻት ፡—

«ፔላጌያ ፥ ይጠንቀቁ! ነገሩ ሁሉ አልቆለታል! ዛሬ ማታ መጥተው ቤትዎን ይፈትሻሉ ። የእነ ማዚን እና የእነ ቬሶቭሺኮቭ ቤትም ዛሬ ማታ ሊፈተሽ ነው» አለቻት ።

ከዚያም የማሪያ ወፋፍራም ከናፍሮች ግጥም ብለው ተዘጉና ደፍጠጥ ባለ አፍንጫዋ ቁና-ያህል ከተነፈሰች በኋላ ከመንገዱ በኩል ሰው ማየት-አለማየቱን ለማረጋገጥ ዐይኖቿን ምልስ-ቅልስ በማድረግ አንዴ ግራውን አንዴም ቀኙን ከቃኘች በኋላ የሚከተለውን ለእናት እንደገና ተናረገች ፡ —

«አደራዎትን ፥ እንግዲህ ጉዳዩ በኔና በርስዎ መሀል ብቻ እንዲቀር! እኔ ምንም የማውቀው ነገር የለም ። አንዳችም የነገርኩዎት ነገር የለም ። የቀረው ቀርቶ እኔና እርስዎ ዛሬ አልተገናኘንም ነበር ማለት ነው ። አይደለም እንዴ? አዎ ፥ አደራዎትን እሺ?» አለች ።

ይኸንን ለእናት ነግራ ሄደች ።

እናት መስኮቱን ዘጋችና ቀስ ብላ ወንበሩ ላይ ኩርምት በማለት ተቀመጠች ። ልጅዋን አደጋ ላይ ሊጥለው የተቃረበው ሁኔታ ወዲያውኑ በሃሣብ አስፈንጥሮ ብድግ አደረጋትና ቆመች ። በፍጥነት ልብሷን ለበሰች ። ሻሿን አሠር አድርጋ ወደ ፌዎዶር ማዚን ዘንድ እየተፋጠነች ሄደች ። ፌዎዶር አሞት ስለነበር ወደፋብሪካው አልሄደም ነበር ። እናት ወደቤቱ ስትገባ ፌዎዶር አውራ-ጣቱ ከሌባ-ጣቱ ጋር አላግባቡ ተጣብቆ የሚገኝበትን የቀኝ እጁን እያሻሸ ከመስኮቱ ጥግ ቁጭ ብሎ መጽሐፍ ያነብባል ። ወሬውን እንደነገረችው በድንጋጤ ነጭ-አመዱ ወጣና ከተቀመጠበት ፍንጥር ብሎ ተነሳ ።

«እኪድዩ!» አለ በማጉረምረም ።



«ምን እናድርግ?» አለችው እናት በሚርበደበዱ እጆቿ ከግንባሯ ላይ ላቦቿን እየጠረገች ።

ከዚያም ፌዎዶር ፀጉሩን ወደኋላ እያሻሸ ፡ —

«ይቆዩ እስኪ ፥ አይደናገጡ» አላት ።

«ምን እደናገጣለሁኝ ፥ የተደናገጥከውማ አንተ ነህ!» አለችው ጎላ ባለ ድምፅ ። እርሱም እናት ባቀረበችው መልስ መደናገጡ ለራሱ ስለተሰማው ፊቱ ቀልቶ እና ፈገግም እያለ ፡ —

«ማን ፥ እኔ? እረ ይተው ። ሀ-ሀ ... ይልቁንስ ፓቬል እንዲያውቀው ማድረግ አለብን ። ወደርሱ ዘንድ ሰው እልካለሁኝ ። እርስዎ ግን ወደቤት ተመልሰው ይሂዱ ። አያስቡ ። አይደበድቡንም ። ይደበድቡናል እንዴ?» አላት ።

እቤት እንደደረሰችም መጻሕፍቶቹን ሁሉ ሰብስባ በደረቷ ላይ አስደግፋ በመሸከም አንዴ ወደ እሳት ማንደጃው በመሄድ ፥ ከዚያም ጎንበስ ብላ ከእሳት ማንደጃው ውስጥ ለመደበቅ ይቻል እንደሆነ በመመልከት ፤ አንዴ ደግሞ ውሃ ማከማቻው በርሚል እንኳን ሳይቀር በመመልከት ክፍሉ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ትንቆራጠጥ ጀመር ። ፓቬል ከፋብሪካው ወዲያውኑ ይመጣል ብላ ገምታ ነበር ። አልመጣም ። ከዚያም መንቆራጠጡ ድክም ስላላት ማዕድ ማዘጋጃው ክፍል በመሄድ ፓቬል እና ኾኾል እስኪመጡ መንቀሳቀስን እንኳን ፈርታ መጻሕፍቶቹን ከሥሯ ወለሉ ላይ አስቀመጠችና አግዳሚው ወንበር ላይ ተቀመጠች ። እነርሱ እንደመጡም ፡ —

«ሰማችሁ እንዴ?» አለቻቸው ከተቀመጠችበት ሳትነሳ ። ከዚያም ፓቬል ፈገግ እያለ ፡ —

«አዎን ሰማን ። ምነው ፈራሽ እንዴ?» አላት ።

«በጣም ነው የፈራሁት!...» አለችው ። ኾኾልም ፡ —

«መፍራት የለብዎትም! መፍራት ምንም አይጠቅምም» አላት ። ፓቬልም ቀጠል አደረገና ፡ —

«ሳሞቫሩን እንኳን ለሻዩ አላያያዝሺውም» አላት ፡፡
እናትም ሻይ ባለማፍላቷ ቅሬታ ለራሷ ተሰምቷት
ከተቀመጠችበት ቦታ ብድግ አለችና ፡ —

«ምን ላድርግ ብለህ ነው ፣ እነዚህን ሰብስቤ ተቀ
ምጨ እኮ ነው» በማለት መጻሕፍቶቹን እያሳየች መ
ለሰችለት ፡፡

ልጅዋና ኾኾል ለካ ቁጭ ብላ የነበረው መጽሐ
ፍቶቹን ከምራ በመደበቅ መሆኑን በማየታቸው በሳ
ቅ ተንከተከቱ ፡፡ ይኸ ሁኔታም ድንጋጤዋን መለስ
አደረገላት ፡፡ ፓቬል ከመጻሕፍቶቹ መካከል ጥቂቱን
መረጠና ውጪ ለመደበቅ ወጣ አለ ፡፡ ኾኾልም ሻይ
ለማፍላት ሳሞቫሩን እያቀጣጠለ የሚከተለውን
ተናገረ ፡ —

«እምዬ ፣ ምንም የሚያስፈራዎት ነገር የለም ፡፡ የሚ
ያሳዝነው ፣ ሰይፋቸውን በወገባቸው ላይ የታጠቁ ፣ የሚ
ጋልቡትን ፈረስ መኰርኰሪያ እንዲሆን መጫሚያቸው
ላይ የብረት ጉጥ የለጠፉ እና በዕድሜ ትልልቅ
የሆኑ ጉብሎች ይኸንን በመሰለ የእንከፍ ድርጊት
ጊዜያቸውን የሚያባክኑ መሆኑ ነው ፡፡ እዚህ ይመጡና
አንዳችም ነገር ሳይቀራቸው ያለ-የሌለውን በማመሳቀል
ይበረብራሉ — አልጋው ሥር ገብተው ይፈትሻሉ ፡፡ እ
ሳት ማንደጃው ሥር ይፈትሻሉ ፡፡ ምድር ቤቱ ውስጥ
ወርደው ይፈትሻሉ ፡፡ ጣራው ሥር ያለውን ቦታ ሳይ
ቀር ይፈትሻሉ ፡፡ ከወዲያ-ወዲህ እየተሯሯጡ ሲበረብሩ
ፊታቸውን የሸረሪት ድር ያደራበታል ፣ ከዚያም በመከ
ፋት ተውጠው ይደነፋሉ ፡፡ ይነጫነጫሉ ፡፡ ሃፍረትም
ስለሚይዛቸው ፣ አስፈሪዎች እና ቁጡዎች ለመምሰ
ል ይጥራሉ ፡፡ ሥራቸው የአራዊት ሥራ መሆኑን ራሳ
ቸውም ያውቁታል! አንድ ጊዜ በድርጊታቸው በጣም
ተከፍተው ስለነበረ ያለኝን ሁሉ አግበስብሰው ይዘው
ት ሄዱ ፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ እኔንም ጭምር ይዘውኝ



ሄዱ ፡፡ ከዚያም እሥር ቤት ወርውረውኝ አራት ወራት
ያህል እዚያው አቆዩኝ ፡፡ እሥር ቤት ምንም የሚደ
ረግ ነገር የለም ፡፡ ቁጭ ብሎ መጠባበቅ ብቻ ነው ፡፡
ከዚያም ይጠሩና ወታደሮች አጅበው በመንገዱ በኩ
ል ወደአለቃቸው ዘንድ ይወስዱዎታል ፡፡ ከፍተኛ ሹማ
ምንቶቻቸውም ጥያቄዎች ያቀርቡልዎታል ፡፡ እነዚህ
ሹማምንቶቻቸውም ብልሆች አይደሉም ፡፡ ብዙ ይለፈል
ፋሉ ፡፡ ከዚያም ወታደሮቹ እንደገና ወደእሥር ቤት
እንዲወስዱዎት ያደርጋሉ ፡፡ በዚህ ዐይነት ሁኔታ ከወዲ
ያ-ወዲህ ያመላልሱዎታል ፡፡ ምናለ ፣ ለሚከፈላቸው ደሞ
ዝ ትንሽም ቢሆን መሥራት አለባቸው አይደል! ከዚ
ያም የኋላ-ኋላ ይለቁዎታል ፡፡ ይኸው ነው እንግዲህ
ጉዳዩ!» በማለት ተናገረ ፡፡

«አንድርዬ ፣ የአነጋገርህ ሁኔታ ሁል ጊዜም እንዴ
ት ግሩም ነው!» በማለት እናት ተናገረች ፡፡

ሳሞቫሩን ለማቀጣጠል በርከክ ብሎ ከነበረበት
ቦታ የቀላ ፊቱን ቀና አደረገና ሪዙን በማሻሸት የ
ሚከተለውን ጠየቀ ፡ —

«እንዴት ዓይነት የአነጋገር ሁኔታ ነው ያለኝ?»
አለ ፡፡

«ማንም ምንም ጉዳት እንዳላደረሰብህ አድርገህ
ነው የምትናገር» አለችው ፡፡

ከዚያም በርከክ ካለበት ቦታ ብድግ ብሎ በመቆ
ም እና ጭንቅላቱንም በመነቅነቅ ፡ —

«ለመሆኑ በዚች ዓለም ላይ ያልተበደለች ነፍስ
ትገኛለችን? እነርሱ እኔን ከፉኛ የበደሉኝ በደል እጅ
ግ የከፋ በመሆኑ ምክንያት ዳግመኛ አላስታውሰው
ም ፡፡ ሰዎች ይኸንን ዓይነት እስከሆኑ ድረስ ምን
ማድረግ ይችላሉ? የደረሰብዎትን በደል የሚያስታውሱ
ት ከሆነ በሥራዎ መሀል ትውስቱ ጣልቃ እየገባ
ያውከዎታል ፡፡ ከዚህም በስተቀር ልብዎን በሀዘን ማስተ

ከዝ ጊዜ ማባከን ነው ። ኑሮ እንደሆን ልክ እንደዚህ
ነው! እኔም በሰዎች ድርጊት እበሳጭ ነበር ። በኋላ
ሳስተውለው ግን ፋይዳ የለውም ። ሁሉም ሰው ጎረ
ቤቱ ዘርጥጦ ጥሎ ሊደበድበኝ ነው ብሎ ስለሚፈራ
ሳልቀደም — ልቅደም በሚል መንፈስ ቀድሞ ሌላውን
ይወግረዋል ። የኔ እምዬ ፣ ይኸውልዎት እንግዲህ ሕይወ
ት ማለት ይቺው ነች!» አላት ።

እነዚህ ቃላት ከአንደበቱ የሚወጡት ያለመጨነ
ቅ ወዲያው-ወዲያው ስለነበረ የሚበረበሩ በመሆናቸ
ው አድሮባት የነበረውን ሥጋት አጠፋላት ። ትክል
ብለው የሚያስተውሉት ዐይኖቹ የመሳቅ ስሜት ያላ
ቸው ይመስላሉ ። ቅልጥፍጥፍ ያለ ባይሆንም እንኳን
ንቁ መሆኑን ተገነዘበች ።

እናት በረዥሙ ተነፈሰች ። ከዚያም ልብ በሚነካ
ሁኔታ ፣ —

«አንድርዬ ፣ እግዚአብሔር ደስታን ያጎናጽፍህ!»
አለችው ።

ኾኾልም ወደሳሞቫሩ መለስ ብሎ በመነካካት ፣ —

«ትንሽ ደስታን ብጎናጸፍ ቅር አይለኝም ። ይሁን
እንጂ እባካችሁ ደስታ አጎናጽፉኝ እያልኩ አልለም
ንም!» አለ ።

ፓቬል ከውጭ መጣ ። ከዚያም ፣ —

«ሲበረብሩ ቢውሉ አያገኟቸውም!» በማለት በሙ
ሉ ልብ እየተናገረ እጆቹን ይታጠብ ጀመር ። ከዚያም
እጆቹን እያደረቀ ወደ እናት ዞር አለና ፣ —

«መደናገጥሽን ከሁኔታሽ ላይ ከተመለከቱ ፣ እንዲህ
የሚያርበተብታት እዚህ ቤት ውስጥ አንድ የተደበ
ቀ ነገር ቢኖር ነው ብለው ይገምታሉ ። እኛ አንዳ
ችም ስህተት እንደማናደርግ ታውቂያለሽ ። ፍትህ
ከእኛ ጋር ነች ። መላ ሕይወታችንን የምንሠ
ራውም ለዚችው ለፍትሕ ስንል ነው ። ጥፋተኞች



የምንባልበት ምክንያት ይኸ ብቻ ነው ። ስለዚህ ፣ ምን
የሚያስፈራን ነገር አለ?» አላት ።

«ፓሻ ፣ ያለአንዳች ፍርሃት በብርታት እቆያለሁኝ»
በማለት ቃል ገባችለት ። በሚቀጥለው አነጋገርዋ ደግ
ሞ በመረበሽ አነጋገር ፣ —

«እንዴ ብቻ ወደዚያ የሚፈትሹትን ቶሎ ፈታት
ሸው በሄዱልኝ እንጂ!» አለች ።

በዚያን ምሽት ይመጣሉ የተባሉት አልመጡም ።
ጧት ሲነጋም ፣ እንዳትረበሽ በማለት ልጆቹ የቀለዱባ
ትን ቀልድ እርሷ የመጀመርያ ሁና በማሰማት ፣ —

«እነዚያ አስፈራሪዎች ገና ሳይመጡ እኔ ግን
ፈርቼ ነበር!» አለች ።

## 10

ያ አስጊ የነበረው ምሽት ካለፈ አንድ ወሩን
ሊይዝ በተቃረበበት ጊዜ ፖሊሶቹ መጡ ። ፓቬልን
እና አንድሬይን ለመጠየቅ ኒኮላይ ቬሶቭሺኮቭ መጥቶ
ስለነበረ ፣ ሦስቱም ስለጋዜጣቸው ጉዳይ ይወያዩ ነበር ።
በጣም መሽቶ ነበር — ዕኩለ-ሌሊቱ ተቃርቧል ።
እናት ወደ መኝታዋ ሂዳ ጋደም በማለት እንቅልፍ
ሊወስዳት ሽለብ እያደረገ ይሞካክራታል ። ያም ሆኖ
ግን ረጋ ያለ እና በሃሣብ የተመሰጠ ድምፃቸውን
ትሰማለች ። ከዚያም አንድሬይ ቀስ ብሎ ወደ ማዕድ
ክፍል ድምፅ ሳያሰማ ሄደና የማዕድ ክፍሉን በር ከ
በስተኋላው ዘጋው ። የባልዲ ድምፅ ሲንኳኳ ይሰማ ነ
በር ። በሩ ተበርግዶ ተከፈተ ። አንድሬይም ከማዕዱ ክ
ፍል ብቅ አለና ጎላ ባለ ድምፅ ፣ —

«አስበርጋጊዎቹ መጥተዋል!» አለ ።

እናት ከአልጋዋ ላይ እመር ብላ በመነሳት በሚ

ንቀጠቀጡት እጆቿ ልብሷን አፈፍ አድርጋ መልበስ ስትጀምር ፓቬል መጣና ከመኝታ ክፍሏ በር ላይ ቆሞ ረጋ ባለ ሁኔታ የሚከተለውን ተናገራት ፡—

«አንቺ ወደአልጋሽ ተመለሺና ያመመሽ ሁነሽ ተኚ!» አላት ።

ከበስተውጪ በኩል ኮሽኮሽታ ይሰማል ። ፓቬልም ወደ በሩ ሄደና ፡—

«ማነህ አንተ?» በማለት በሩን ከፈተው ።

ወዲያውኑም አንድ አመድማ መልክ ያለው ረዥም ሰው ሌሎች ሁለት ሰዎች አስከትሎ ብቅ ሲል ፥ ሁለት ዣንዳርሞች ደግሞ ፓቬልን ወደቤት ውስጥ ገፉትና እርሱን በመጠበቅ ሁኔታ ከግራና ቀኙ ቆሙ ። ከዚያም ጎላ ባለ ድምፅና በፌዝ አባባል ፡—

«ስትጠባበቃቸው የነበሩት ሰዎችህ አይደለንም ። እውን?» በማለት አንዱ ተናገረ ።

ይኸንን የተናገረው ሪዝ ያቀመቀመው ረዥሙና ቀጭኑ መኰንን ነበር ። ፌዲያኪን የተሰኘው የሠፈሩ የፖሊስ መኰንን ወደ እናት የመኝታ ክፍል ሄደ ። ከዚያም በአንድ እጁ መለዮውን እየነካካና በሌላ እጁ ደግሞ ወደ ፔላጌያ እየተመለከተ ፡—

«ክቡር ሆይ ፥ እናቲቱ ይህቺ ናት» ካለ በኋላ እጁን ወደ ፓቬል በማመልከት ደግሞ ፡—«ልጅዋ ደግሞ ይሄ ነው» አለ ። መኰንኑም ዐይኖቹን ጠበብ በማድረግ ሁኔታ ፓቬልን አትኩሮ እየተመለከተ ፡—

«ፓቬል ቭላሶቭ አንተ ነህ?» በማለት ጠየቀው ። ፓቬልም በንግግር ሳይሆን ራሱን በመነቅነቅ ፥ አዎ ነኝ የሚል ምልክት አሳየ ። ከዚያም መኰንኑ ሪዙን እያሻሸ ፡— «ቤታችሁን ልፈትሽ ነኝ ። ማነው እዚያ ያለው? ሴትዮ ይነሱ!» በማለት ወደክፍሏ እየተመለከተ ገባ ። ከዚያም ፡—

«ስማችሁ ማን ይባላል?» በማለት ጠየቀ ።



ሁለት እማኞችም መጡ ። አንደኛው ቀድሞ ብረት ቀጥቃጭ የነበረ ትቬርያኮቭ የተሰኘ ሽማግሌ ሲሆን ፥ ሌላው ደግሞ ትቬርያኮቭ ከሚኖርበት ቤት አንድ ክፍል በደባልነት ተከራይቶ የሚኖር ግዙፍ የሆነ እና የጠቆረ መልክ ያለው ሪቢን የተሰኘ ሰው ነው ።

«እንደምን አመሹ ፥ ኒሎቭና!» በማለት ባልተገራ ወፍራም ድምፅ ተናገረ ።

እናት ልብሷን እየለበሰች ከራሷ ጋር የሚከተለውን በማነብነብ ብርታት እንዲኖራት ጣረች ፡—

«ኤጭ ፥ እንዲህ ያለ ሰምቼም አላውቅ! እንዲህ በዕኩለ-ሌሊት ሰው ቤት ይኬዳል እንዴ! ሰው አልጋው ላይ ከተኛ በኋላ ምን ዘው ብለው ይገባሉ!» አለች ።

ክፍሉ በሰዎች ተሞልቶአል ። ቤቱ የጫማ ቀለም — የጫማ ቀለም መሽተቱ አለምክንያት አልነበረም ። ሁለት ዣንዳርሞች እና የሠፈሩ የፖሊስ አዛዥ አንድነት ሁነው በአጓጉል ሁኔታ መጻሕፍቶችን ከመጽሀፍ መደርደሪያው ላይ እያነሱ መኰንኑ ፊት ጠረጴዛ ላይ ከመሯቸው ። ሌሎቹ ሁለቱ ደግሞ በቡጢ ግድግዳዎቹን መታ-መታ በማድረግና ወንበሮቹ ሥርም በመመልከት ይበረብራሉ ። ከመካከላቸው አንደኛው የእሳት ማንደጃው ምድጃ ላይ ሳይቀር ወጥቶ ይበረብራል ። ኾኾልና ቬሶቭሺኮቭ ክፍሉ ውስጥ ካንዱ ጥግ በኩል ተጠጋግተው ቆመዋል ። ፈንጣጣ የጠቀጠቀው የኒኮላይ ፊት ጉብርብር ብሎ ቀልቶአል ። ትንንሽ የሆኑ አመድማ ዐይኖቹንም ከመኰንኑ ላይ ሳይነቅል በመጣል አተኩሮ ይመለከታል ። ኾኾል ሪዙን እያሻሸ ቆሞአል ። እናት ወደ ክፍሉ ውስጥ ስትገባ ለአፍታ ያህል ሳቅ ካለ በኋላ በማበረታታት ዓይነት መልክ ራሱን ነቅነቅ አደረገላት ።

ፍርሀቷን ለማስወገድ በማለት አቋቋሟ እንደቀድሞው አቋቋሟ የጎድን ዘንበል ያለ ሳይሆን ደረቷን

ወደፊት ነፍታ ቀጥ ያለ አቋቋም እንዲኖራት በማድረግ ሲሆን ፥ ይኸውም አኳኋኗ ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ጀነን ያለች እንድትሆን አድርጓታል ። ወለሉን ስትረግጥ እግሮቿ ኳ-ኳ እያሉ የሚሰሙ ሲሆኑ ፥ የዐይኖቿ ሽፋሽፍቶችም ይርገበገባሉ ።

መኮንኑም አመድ በሚመስል እጁ ላይ ባሉት ቀጫጭን እጣቶቹ መጻሕፍቶቹን ምንጭቅ-ምንጭቅ እያደረገ በማንሳት ገልበጥ-ገልበጥ አድርጎ ከተመለከታቸው በኋላ ወዲያውኑ ወረወራቸው ። ግማሾቹ መጻሕፍት ወለሉ ላይ ወደቁ ። ማንም ምንም አልተናገረም ። ላብ ያላባቸው ዣንዳርሞች በትልቁ እየተነፈሱ እና በየቦታው እየበረበሩ ፡ —

«እዚያ ዘንድስ ፈትሸሃል?» እየተባባሉ ይነጋገራሉ ።

እናት ጀርባዋን ለግድግዳው ሰጥታ እና እጆቿንም እንደልጅዋ አጣጥፋ ከፓቬል ጎን ቆማ ዐይኖቿ መኮንኑን ይከተላሉ ። ጉልበቷን ብርክ-ብርክ ያላት ሲሆን ፥ ዐይኖቿም እንባ አቅርረዋል ።

ሁሉም ሰው በፀጥታ ጭጭ-ምጭጭ ብሎ ይገኝ ከነበረበት ሁኔታ ድንገት ጎርነን ባለ ድምፅ ኒኮላይ ፡ —

«መጻሕፍቶቹን ወለሉ ላይ መወርወር ምን ያስፈልጋል?» በማለት ተናገረ ።

እናት ደነገጠች ። አንድ ሌላ ሰው የገፋው ይመስል ትቬርያኮቭ ጭንቅላቱን ድንገት ዞር አደረገ ። ሪቢን በማጉረምረም ኒኮላይን አተኩሮ ይመለከተው ነበር ።

መኮንኑ ዐይኖቹን ዘጋ በማድረግ ሁኔታ እንደ በድን የተገተረውንና ፈንጣጣ የጠቀጠቀውን የኒኮላይን ፊት በዐይኖቹ ገረፍ በማድረግ ተመለከተው ፤ ከዚያም ፈጠን-ፈጠን እያለ የመጻሕፍቶቹን ገጾች ያገላብጥ ጀመር ። አንዳንድ ጊዜ ፥ ሊቋቋመው ባልቻለው የሕመም ሥቃይ ተወጥሮ ግቢ-ነፍስ ውጪ-ነፍስ የሆነበት ይመስል ለጨኸት እንደተቃረበ በሽተኛ አመድማ ዐይኖቹን ብልጥጥ አድርጎ ይበረግዳቸዋል ።

«ስማ ፥ ወታደር የተወረወሩትን መጻሕፍት ከወለሉ ላይ አንሳቸው!» በማለት ቬሶቭሺኮቭ እንደገና ተናገረ ።

ከዚያም ዣንዳርሞቹ በሙሉ ዞር ብለው ቬሶቭሺኮቭን በግልምጫ ከተመለከቱት በኋላ መኮንኑን ተመለከቱ ። መኮንኑም ጭንቅላቱን ቀና አድርጎ የኒኮላይን ግዙፍ ሰውነት በግልምጫ አመለካከት ከተመለከተ በኋላ በአፍንጫው አየር ደህና አድርጎ በመሳብ ተነፈሰና ፡ —

«ኡ-ሆ-ሆ-ሆ! አንሷቸው?» በማለት ወለሉ ላይ የወደቁት መጻሕፍት እንዲነሱ ፖሊሱን አዘዘ ።

ከዚያም ከዣንዳርሞቹ መካከል አንዱ ተበታትነው የወደቁትን መጻሕፍት እየሰበሰበ ማንሳት ጀመረ ።

«ይሄ ኒኮላይ ዝም ቢል ይሻለዋል!» በማለት እናት ቀስ ብላ ለፓቬል ነገረችው ።

ፓቬልም ትከሻውን ነቅነቅ አደረገ ። ኾኾል ጭንቅላቱን ዘቅዘቅ አድርጎ ነበር ።

«መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነበው ደግሞ ማነው?» አለ መኮንኑ ።

«እኔ ነኝ!» አለ ፓቬል ።

«እነዚህ ሁሉ መጻሕፍት የማን ናቸው?»

«የኔ ናቸው!» አለ ፓቬል ።

«እ-ሀ! መልካም ነው!» አለ መኮንኑ ወንበሩ ላይ ለጠጥ ብሎ በመቀመጥ ። ከዚያም የቀጫጭን እጆቹን ጣቶች እያንቋቋ እና እግሮቹንም ጠረጴዛው ሥር ዘርግቶ ፥ ሪዙንም እያሻሸ ኒኮላይን ፡ —

«አንድሬይ ናኾድካ ማለት አንተ ነህ?» ብሎ ጠየቀው ። ኒኮላይም ፡ —

«አዎን ፤ እኔ ነኝ» በማለት ወደ መኮንኑ ተጠጋ ።

በዚህን ጊዜ ኾኾል ኒኮላይን ከትከሻው ላይ ያዝ አድርጎ ወደ ኋላ በማስቀረት ፡ —

«የለም ፣ እርሱ አይደለም ። አንድሬይ ማለት እኔ ነኝ!...» አለ ።

መኮንኑ እጁን ከፍ አድርጎ እጣቶቹን ቬሶቭሺኮቭ ላይ በዛቻ በማወዛወዝ ፡ —

«አንተ ሰው ፣ ብትጠነቀቅ ይሻልሃል!» አለው ።

ከዚያም መኮንኑ ወረቀቶቹን ያገላብጥ ጀመር ። የጨረቃ ብርሃን ያረበበት ምሽት ከመንገዱ በኩል ፍዝዝ-ድብዝዝ ብሎ በመስኮቱ ውስጥ ይታያል ። በቤቱ አጠገብ ቀስ ብሎ ያልፍ የነበረውን ሰው ኮቴ በረዶው ኋ-ኋ እያደረገ ያሰማል ።

«አንተ ማነህ ፣ ናኾድካ! ከአሁን በፊት በፖለቲካ ጉዳይ ወንጀል ፈጽመህ ነበር ። አይደለም?» በማለት መኮንኑ ጠየቀው ።

«አዎን ። አንድ ጊዜ ሮስቶቭ ከተማ ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሳራቶቭ ከተማ ውስጥ ፈጽሜአለሁኝ ። እዚያ ያሉት ዣንዳርሞች ግን ይበልጥ የተሻሉ ትሁቶች ናቸው» በማለት መለሰ ።

መኮንኑ የቀኝ ዐይኑን ዘጋ አድርጎ ማሻሸት ጀመረ ። ከዚያም ትንንሽ ጥርሶቹን ብልጭ እያደረገ ፡ —

«ስማ ፣ ናኾድካ ፣ ወንጀለኛ የሆኑ ጽሁፎችን በፋብሪካው ውስጥ የሚበትኑት ልክስክስ ሰዎች እነማን እንደሆኑ አታውቅምን?» በማለት ጠየቀው ።

ኾኾል ፈገግ በማለትና ከተረከዙም ከፍ በማለት መልስ ሊሰጥ ሲል ኒኮላይ እንደገና ፡ —

«ልክስክሶችን ማየት ስንጀምር ይኸው ይኼ የመጀመርያ ጊዜያችን መሆኑ ነው» በማለት ተናገረ ።

በክፍሉ ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ ። ለጥቂት ሰኮንዶች ሁሉም ጭጭ-ምጭጭ አሉ ።

እናት ጠባሳዋ ከነበረበት ቦታ ወደላይ ከፍ አለ ።



የቀኝ ቅንድቧም ብርግድ ብሎ ተበለጠጠ ። የሪቢን ጥቁር ጢም በሚያስደንቅ ሁኔታ ይንቀጠቀጣል ። ጢሙን በእጣቶቹ እያሻሸ ዐይኖቹን ወደመሬት ተክሎአል ።

«ይኼንን እንስሳ ከዚህ አስወጡልኝ!» በማለት መኮንኑ በጩኸት ድምፅ ተናገረ ።

ሁለት ዣንዳርሞች ኒኮላይን በእጃቸው ጨምድደው በመያዝ እያንገላቱ ወደ ማዕድ ክፍል ሲወስዱት እግሩን ከወለሉ ጋር ቀርቅቦ በመትከል ከመራመድ ካቆማቸው በኋላ ፡ —

«አንዴ ልቀቁኝ! ካፖርቴን ልልበስ!» በማለት ተናገረ ።

የፖሊሱ አዛዥ ከቤቱ ግቢ ከሚገኘው የአትክልት ሥፍራ ተመልሶ ከመጣ በኋላ ፡ —

«ውጪ ምንም አላገኘንም ። ሁሉንም ቦታ ፈተሽን!» በማለት ተናገረ ። መኮንኑም ትከሻውን ነቅነቅ በማድረግ ፡ —

«እንዴ ፣ ነው እንጂ! እንዴት አድርጎ ይገኛል! በጉዳዩ የሠለጠኑበት ሰዎች ዘንድ እኮ ነው ያለነው!» በማለት ተናገረ ።

እናት የዚህን ሰው ስልምልም እና ስብርብር ያለ ድምፅ እያዳመጠች እና ወደቢጫነት የተለወጠ አስፈሪ ፊቱንም እየተመለከተች በተራ ሰዎች ላይ ቂም በቀሉን ለመወጣት አሰፍስፎ የሚጠባበቅ ምህረት-የለሽ ጨካኝ ፍጡር እንደሆነ ተገነዘበች ። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎችን አልፎ-አልፎ ብቻ የምትገናኝ ስትሆን እስከመኖራቸውም ጭምር እርግፍ አድርጋ ዘንግታቸው ነበር ።

«እ-ህ! በሚበተኑ ወረቀቶች የሚሸበሩት እነዚህ ናቸው ማለት ነዋ!» በማለት እናት ከራስዋ ጋር ተወያየች ።

«አንተ ሚስተር አንድሬይ አኒሲሞቭ ናኾድካ የተሰኘህና ከሕጋዊ ጋብቻ ውጪ የተወለድክ ዲቃላ፣ ወደ እሥር ቤት እንድትሄድ በቁጥጥር ሥር ውለሃል!» በማለት መኮንኑ ኾኾልን ተናገረው። ኾኾልም ፡ —

«ምን ስላደረግሁኝ?» በማለት በረጋ ሁኔታ ጠየቀ።

«ግዴለም፣ ያደረከውን በኋላ እነግርሃለሁ!» በማለት መኮንኑ ከመለሰለት በኋላ ፡ — «አንቺ ትምህርት የተማርሽ ነሽ?» በማለት ፔላጌያን ጠየቃት።

«የለም፣ አልተማሩም!» በማለት ፓቬል መለሰ። ከዚያም ፡ —

«አንተን የጠየቀህ የለም!» በማለት መኮንኑ ቆጣ ብሎ ለፓቬል መለሰ። ከዚያም ፡ —

«ሴትዮ፣ ተናገሪ እንጂ!» በማለት መኮንኑ እናትን ጠየቀ።

እናት ይኸንን ሰው ክፉኛ ጠልታው ነበር። ቀዝቃዛ ውሀ ውስጥ የተነከረች ይመስል ድንገት መንቀጥቀጥ ጀመረች። ቀና ብላ በመቆም ጠባሳዋ በጉልህ እየታየና ቅንድቦቿም እየተርገበገቡ እጣቶቿን ወደ መኮንኑ ጠቁማ በማመልከት ፡ —

«ይኸንን ያህል መጮህ አያስፈልግዎትም! እርስዎ ገና ወጣት ነዎት። መከራ ምን እንደሆነ አልቀመሱም...» አለችው።

ፓቬልም ንግግሯን እንድታቆም በመሞከር ፡ —

«ተይው ዝም በይ እማማ!» በማለት ተናገረ።

«ተው እስኪ ቆይ፣ ፓቬል!» በማለት እናት መኮንኑ ወደሚገኝበት ጠረጴዛ በመገስገስ ተጠግታ ፡ — «እነዚህን ሰዎች የሚይዟቸው ለምንድነው?» በማለት ጠየቀችው።

«ኢሄ አንቺን የሚመለከት ጉዳይ አይደለም! ዝም በይ!» በማለት በቁጣ ድምፅ እየጮኸ መኮንኑ ከተቀመጠበት ተነሳ። ከዚያም ፡ —



«በቁጥጥር ሥር የዋለውን ቬሶቭሺኮቭንም ወደዚህ አምጡልኝ!» በማለት አዘዘ።

ይዞት የነበረውን ወረቀት አፍንጫው ሥር አስጠግቶ ማንበብ ጀመረ።

ኒኮላይ ከነበረበት እንዲመጣ ተደረገ። መኮንኑም ጀምሮ የነበረውን ንባብ በማቋረጥ ፡ —

«አውልቅ ይሄንን ቆብህን!» በማለት ጮኸ።

ሪቢን ወደ ፔላጌያ ጠጋ አለ። ከዚያም አይዞሽ እንዳትደነግጪ በሚል አኳኋን በትከሻው ነካ አደረጋትና ፡ —

«እናት፣ አይደናገጡ!» በማለት ነገራት። ከዚያም በቁጥጥር ሥር የዋሉበት ማዘዣ መነበቡ ሲቀጥል ኒኮላይ በማቋረጥ ፡ —

«ሁለቱም እጆቼ ተጠፍረው ተይዘዋል። ለመሆኑ ቆቤን የማወልቀው እንዴት አድርጌ ነው?» በማለት ጠየቀ።

«ና ፈርም እዚህ ላይ!» በማለት ወረቀቱን ጠረጴዛው ላይ እየወረወረ በቁጣ ድምፅ መኮንኑ ተናገረ።

ወረቀቱ ላይ ፈርማቸውን ሲያኖሩ እናት ትመለከት በነበረበት ጊዜ ብስጭቷ በረታ፣ ልቧ በሀዘን በትር ተመታ፣ በጉዳት እና በረዳት-አልባነትም ዐይኖቿ በእንባ ተመሉ። በትዳር ላይ በነበረችባቸው ሃያ ዓመታት ውስጥ እነዚህን መሳይ እንባዎች አንብታለች። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን አቃጣይ የነበሩትን የእንባዎቿን ግንፋሎት እስከመዘንጋቱም ተዳርሳ ነበር። መኮንኑ እርሷን ተመለከተና በሁኔታዋ ደስ ባልተሰኘ አመለካከት ፊቱን ኮስተር አድርጎ ፡ —

«ሴትዮ፣ ይኸንን እንባ ቆጠብ አድርጊ! አለበለዚያ ለወደፊቱ ሀዘን ምንም እንባ አይተርፍሽም!» አላት።

እንደገና ሌላ የቁጣ ብስጭት አካሏን ወረራት።

«እናት ምንግዜም ቢሆን ፣ ለማንኛውም ነገር ፣ ለማንኛውም ነገር በቂ እንባ አላት! እርስዎም እናት ካለዎት ፣ እናትዎ ይኽንን በሚገባ ያውቁታል!» አለችው ።

ከዚያም መኮንኑ የሚያንጸባርቁ ቁልፎች ባሉት በአዲስ የወረቀት መያዣ ቦርሳ ውስጥ ወረቀቶቹን ከተታቸውና ፡ —

«ቅደሙ ወደፊት!» በማለት በቁጥጥር ሥር ያዋላቸውን አዘዛቸው ። ፓቬልም በጋለ ስሜት ለመሰናበት እየጨበጣቸው ፡ —

«አንድሬይ ፣ በል ደህና ሁን! ኒኮላይ ፣ በል ደህና ሁን!» በማለት ተሰናበታቸው ። ከዚያም መኮንኑ ትንሽ ሳቅ ካለ በኋላ ፡ —

«አይዞህ አታስብ ፣ በቅርቡ አንድላይ ትቀላቀሉ ይሆናል!» በማለት ፓቬልን ተናገረው ።

ቬሶቭሺኮቭ በረዥሙ ተነፈሰ ። ወፍራም በሆነው አንገቱ ላይ ያሉት ሥሮቹ በደም አገሽበዋል ። ዐይኖቹም በቁጣ ተመልተዋል ። ኾኾል ፈገግታ አሳየና ደህና ሁኑ በሚል ሁኔታ ራሱን ነቅንቅ ካደረገ በኋላ ለእናት አንድ ነገር በጆሮዋ ነገራት ። እናትም አማተበች ። ከዚያም ፡ —

«ትክክለኛው ማን እንደሆነ ፈጣሪ ያያል…» አለች ።

በመጨረሻም ግራጫ የመለዮ ልብስ የለበሱት እነዚህ ሰዎች ወደበረንዳው እየወጡ በመኮልኮል በመጫምያቸው ላይ የተለጠፉትን ብረቶች ሲራመዱ እያንኳኩ መንገዳቸውን ሄዱ ። ከቤት በመጨረሻ የወጣው ሪቢን ነበር ። ፓቬልን በቀይታ ከተመለከተው በኋላ የገዛ ራሱን ጢም በመነካካት ሳሉን እየሳለ እና በማሰብ መንፈስ ተውጦ ፡ —

«በል እንግዲህ ደህና ዋል!» አለው ።

ፓቬልም እጆቹን ወደ ኋላው አድርጎ በዝግታ



ክፍሉ ውስጥ በመራመድ ወደ ተበታተኑት መጻሕፍትና ልብሶች ጠጋ ብሎ እየተመለከተ ፡ —

«አየሽ? እንዲህ ነው የሚያመሳቅሉት!» በማለት እናትን ተናገራት ።

እናትም ምስቅልቅላቸው የወጡትን መጻሕፍት በመገረም እያስተዋለች ፡ —

«ኒኮላይ ምነው እንዲህ ተዳፈረ?» በማለት በመፀፀት መልክ ተናገረች ።

«ፈርቶ ስለነበረ ሳይሆን አይቀርም» በማለት ፓቬል መለሰላት ።

«ወይ ጉድ! ድንገት መጡና ዘው ብለው ገቡ ። እያንጠለጠሉ ዝም ብለው ይዘዋቸው ይሂዱ!» በማለት ራሷን እየነቀነቀች አጉረምርማ ተናገረች ።

ልጅዋ ያልተያዘ ስለነበር የልቧ ትርታ ቀነስ ብሎ ነበር ። ይሁን እንጂ ፣ የተመለከተችውን ድርጊት በመቃወም ሁኔታ እያሰላሰለች በሃሣብ ተውጣ ነበር ።

«ያ ፊተ-ቢጫ በላያችን ላይ አናፋ እኮ! ሊያስፈራራንም ከጀለው እኮ!..» እያለች ስትናገር ፓቬል ድንገት በረጋ መንፈስ አቋረጣትና ፡ —

«በቃሽ እንግዲህ ፣ የኔ እናት ። ይልቁንስ እነዚህን የተበታተኑትን እንሰበሳስባቸው» በማለት ተናገረ ።

አንቱ ሳይሆን አንቺ በሚል አጠራር የኔ እናት አላት ። ይኽንን አጠራሩን የሚጠቀምበት በጣም ቅርብ በሆነ የመቅረብ መንፈስ በሚያነጋግራት ጊዜ ብቻ ነበር ። ወደርሱ ጠጋ ብላ ፊት-ፊቱን እየተመለከተች ፡ —

«ጎዱህ እንዴ?» በማለት ቀስ ብላ ጠየቀችው ።

«አዎን ጎድተውኛል ። በጣም ከባድ ሁኔታ ነው ። ከሌሎቹ ጋር አንድነት በወሰዱኝ ኖሮ ይሻለኝ ነበር…» አላት ።

ዐይኖቹ እንባ አቅርረው የተመለከተች መሰላት ።

ከዚያም በረኸሮሙ በመተንፈስና እንዲጽናና ለማድረግ በመሞከር ፡ —

«ትንሽ ጊዜ ጠብቃቸው ፣ አንተንም ይወስዱሃል!» አለችው ።

«እንደሚወስዱኝ አውቃለሁኝ!» በማለት መለሰላት ።

ለጥቂት ጊዜ ዝም አለች ። ከዚያም ፡ —

«ፓቬል ፣ እንዴት እንዲህ ጠንካራ ሆንክ ልጄ! ትንሽም እንኳን አታጽናናኝም እንዴ! እኔ ሊናገሩት የማይገባ አንድ አጉል ቃል ስናገር አንተ ደግሞ በላዩ ላይ ከዚያ የባሰ ትጨምርበታለህ!» አለችው ።

እርሷን-እርሷን ተመለከተና ወደርሷው ጠጋ በማለት የሚከተለውን በዝግታ ተናገረ ፡—

«እማማ ፣ እንዴት እንደሚቻል እኔ እንጃ! ይሁን እንጂ ፣ እንዲህ የመሰለውን ሁኔታ መላመድ አለብሽ» አላት ።

በረኸሮሙ ተነፈሰችና ድምጿ ስልቱን እንዳይስት እየሞከረች የሚከተለውን ጥያቄ አቀረበችለት ፡ —

«ለመሆኑ የሚይዟቸውን ሰዎች ያሰቃዩ ይሆን? ገላቸውን ይተለትሉት ይሆን? አጥንታቸውን ይሠባብሩት ይሆን? ስለዚህ ጉዳይ ባሰብኩኝ ቁጥር ይዘገንነኛል!..» አለችው ።

«ልብሽን ይቦጫጭቁታል ። በቆሻሻ እጃቸው ልብሽን ሲያጎድፉት ፣ ሕመሙ ከሁሉም ይበልጥ የከፋ ሁኖ ይሰማሻል!» አላት ።

## 11

ቡኪን ፣ ሳሞይሎቭ ፣ ሶሞቭ እና ሌሎች አምስት ሰዎችም መያዛቸው በማግሥቱ ሊታወቅ ቻለ ። ምሽቱ ላይ ፌዎዶር ማዚን እናት ቤት መጣ ። የእርሱም ቤ



ት ተፈትሾ ነበር ። ይኸም በመሆኑ እጅግ ተደስቶ የነበረ ሲሆን የጀግንነት ስሜትም ተሰምቶታል ።

«ፈርተህ ነበርን ፌዎዶር?» በማለት እናት ጠየቀችው ።

ደም መሰለ ። ሰውነቱን ሰገግ አድርጎ በማቆም አፍንጫው ይንቀጠቀጥ ጀመር ። ከዚያም ፡ —

«መኮንኑ ያላጋኛል ብዬ ፈርቼ ነበር ። ጥቁር ጢም ፊቱ ላይ ያጤመ ፣ እጣቶቹ በጠጉር የተወረሩ እና ዕውር ይመስልም ጥቁር መነጽር ያደረገ ወፍራም ሰው ነው ። እየጮኸ እግሮቹን ከወለሉ ጋር ያጋጭ ነበር ። ‘ወደ እሥር ቤት ነው የምወረውርህ!’ እያለ ይጮህ ነበር ። በሕይወቴ ማንም ሰው ደብድቦኝ አያውቅም ። እናት እና አባቴ እንኳን ደብድበውኝ አያውቁም ። አንድ ብቻ ልጃቸው እኔ ስለሆንኩኝ ይወዱኝ ነበር» በማለት ተናገረ ።

ለአፍታ ያህል ዐይኖቹን ዘጋና በሁለቱም እጆቹ ፀጉሩን ቶሎ-ቶሎ ወደኋላ እያሻሸ ከንፈሮቹን ግጥም አድርጎ ያዛቸው ። ከዚያም ደም በለበሱ ዐይኖቹ ፓቬልን እየተመለከተ ፡ —

«እኔን አንዱም ለመንካት ቢሞክር እንደጩቤ እላዩ ላይ ተወርውሬ ነው የምተክልበት ። በጥርሶቼ እቦጫጭቀዋለሁኝ ። ለምን እዛው አይገድሉኝም ፣ አልለቃቸውም!» በማለት ተናገረ ።

«እንዴት አድርገህ ትደባደባለህ ፣ አንተ ለራስህ ኩስስ ያልክ ከሲታ ነህ» አለችው እናት ።

«የፈለገው ይሁን እደባደባለሁኝ!» አለ ።

ፌዎዶር ከሄደ በኋላ እናት ፓቬልን እንዲህ በማለት ተናገረችው ፡ —

«ከሁሉም ቀድሞ በጠላት የሚፈታው ፌዎዶር ነው!» አለች ።

ፓቬል አንዳችም መልስ አልመለሰም ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የማዕዱ ክፍል በር ቀስ ብሎ ተከፈተና ሪቢን መጣ ። በጥቂቱ ፈገግ በማለትም ፡ —

«እንደምንድናችሁ! ይኸው እንደገና መጣሁኝ ። ትላንትና ማታ አስገደዱኝ ፣ ዛሬ ራሴ መጣሁኝ!» አለ ። የፓቬልን እጅ ስሜት በተሞላበት ሁኔታ አወዛውዞ ከጨበጠ በኋላ የፔላጌያን ትከሻም በእጁ ነካ-ነካ አደረገ ።

«አንድ ብርጭቆ ሻይ ብጠጣ እንዴት ደስ ባለኝ ነበር!» በማለት ተናገረ ።

ፓቬልም በጢም የተወረረውን የሪቢንን ሰፋ ያለ ፊት እና ጥቋቁር ዐይኖቹን በጥሞና እየተመለከተ ያጤናል ። በእንዲህ ያለ አመለካከቱ አንድ ነገር ለመረዳት የፈለገው ነበር ።

እናት ሳሞቫሩን ለማያያዝ ወደ ማዕድ ቤት ሄደች ። ሪቢን ክርኖቹን ጠረጴዛ ላይ አስደግፎ ተቀምጦአል ። ከዚያም ፓቬልን እየተመለከተ ቀደም ሲል ከጀመረው ንግግር የተቋረጠ ይመስል ፡ —

«እና ይኼውልህ ፣ ከአንተ ጋር በግልጽ መወያየት እሻለሁኝ ። ሁኔታህን ለጥቂት ጊዜያት እየተከታተልኩኝ ነበር ። የምኖረውም ያው ከቤትህ ጎን የማለት ያህል ነው ። ብዙ ሰዎች ወደቤትህ የሚመጡ መሆናቸውን ፣ ይሁን እንጂ የማይሰክሩ ወይንም የማይረብሹ መሆናቸውን ተገንዝቤአለሁኝ ። ይኼ አንዱ ጉዳይ ነው ። ደህና-ደህና ሰዎችን ወዲያውኑ ለይቶ ማወቅ ይቻላል ። እንዲህ መሆናቸው ለምንድነው ብለህ ትደነቃለህ ። እኔም ራሴ ብሆን ከሁሉም ነገር ተጠንቅቄ የምኖር ሰው ነኝ» በማለት ተናገረ ።

አነጋገሩ ጎተት ያለ ቢሆንም አንደበቱ ሳይገታ ቃላቶቹን ይሰነዝራል ። ጢሙን ጠቆር ባለ እጁ እያሻሸ የፓቬልን መልክ አተኩሮ ይመለከታል ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ —



«ሰዎች ስለአንተ ወሬ ማውራት ጀምረዋል ። ከእነዚህ ስለአንተ ከሚያወሩት ሰዎች መካከል አንዱ እኔ የምኖርበት ቤት ባለቤት ነው ። ቤተክርስቲያን የማትሄድ በመሆንህ ምክንያት መናፍቅ ነህ ይልሀል ። እኔም ራሴ ብሆን ቤተክርስቲያን አልሔድም ። ከዚያም እነዚያ ወረቀቶች መበተን ጀመሩ ። አንተ ነህ እንዴ ይኸን አስበህ ያደረግህ?» በማለት ጠየቀው ።

«አዎን እኔ ነኝ!» በማለት ፓቬል መለሰ ።

«ምን ይላል ኢሂ!» አለች እናት ጠንቀቅ ባለ ሁኔታ ድምጿን ከፍ አድርጋና ከማዕዱ ቤት በራፍ ላይ አንገቷን ብቅ አድርጋ በመናገር ። ከዚያም ፡ —

«ይኼ አንተ ብቻህን ያደረግኸው ሥራ አይደለም!» በማለት ቀጠለች ።

ፓቬል ሳቀ ። ሪቢንም ሳቀ ።

«እሺ!» አለ ሪቢን ።

አነጋገሯን ከምንም ባለመቁጠራቸው ምክንያት ገልመጥ አድርጋቸው እያጉረመረመች ወደማዕዱ ቤት ተመለሰች ።

«እነዚያን በምሥጢር የሚበተኑ በራሪ ወረቀቶች ማዘጋጀት ግሩም ሃሣብ ነው ። ሕዝቡን ያነቃሉ ። እስከ አሁን አሥራ ዘጠኝ እትሞች ተሠራጭተዋል ። አይደለም እንዴ?» በማለት ሪቢን ጠየቀ ።

«አዎን!» በማለት ፓቬል መለሰ ።

«ይህም ማለት ሁሉንም የተበተኑትን ወረቀቶች በሙሉ አንብቤአቸዋለሁኝ ማለት ነው ። በላያቸው ከሠፈሩት ጽሁፎች መካከል ገሚሶቹ ግልጽነት ኖሮአቸው የተብራሩ አይደሉም ። ገሚሶቹ ደግሞ አስፈላጊ አይደሉም ። ይሁን እንጂ አንድ ሰው እጅግ ብዙ ሃሣቦችን ማቅረብ በሚኖርበት ጊዜ አስፈላጊ ያልሆኑ አንድ-ሁለት በረፍተ-ነገሮችን መጨመሩ አይቀርም» አለ ።

ሪቢን ነጭ ጥርሶቹን ብልጭ አድርጎ ሳቀ ። ከዚያም ፡ —

«ከዚያም ፍተሻው ቀጠለ ። ይበልጥ የተደነቅሁት በዚህን ጊዜ ነበር ። አንተ እና ኾኾል እንደዚሁም ኒኮላይ ሁላችሁም ተገኝታችሁ ነበር...» አለ ።

ይህንን ከተናገረ በኋላ ተስማሚ የሆኑ ትክክለኛ ቃላት ለመፈለግ ንግግሩን ጋብ አድርጎ ጠረጴዛውን በእጣቶቹ ቋ-ቋ-ቋ እያደረገ በመስኮቱ ውስጥ ውጪውን አሻግሮ ያስተውል ጀመር ።

«የያዛችሁትን አቋም አሳይታችኋል ። 'ክቡር ሆይ እርስዎም በመሰለዎ መንገድ ይጓዙ ። እኛም በመሰለን እንጓዛለን ።' እንደማለት ያለ ነው ። ኾኾልም ጥሩ ሰው ነው ። አንዳንድ ጊዜ ፋብሪካ ውስጥ ሲነጋገር ስሰማው ፣ 'ይኽንን ሰው አንዳችም ነገር ድል አይነሳውም ። ሞት ብቻ ነው የሚገላግለው ። እንደብረት የጠነከረ ሰው ነው ።' በማለት ለራሴ አስባለሁኝ ። ታምነኛለህን ፓቬል?» በማለት ጠየቀ ።

«አዎን አምንሃለሁኝ!» በማለት ፓቬል ራሱን በአዎንታ እየነቀነቀ መለሰ ።

«ጥሩ! እኔን ተመልከተኝ ። አርባ ዓመቴ ነው ። ከአንተ ሁለት ጊዜ ሽማግሌ ስሆን ከአንተ የበለጠ ሃያ ዓመት ኖሬአለሁኝ ። ከሦስት ዓመት በላይ በወታደርነት እገልግዬአለሁኝ ። ሁለት ጊዜ አግብቻለሁኝ — የመጀመርያ ሚስቴ ሞተች ። ሁለተኛይቱን ፈታኋት ። ካውካሰስ በተሰኘው ክፍለ-ሀገር ኖሬ የነበር ሲሆን እዚያም ዱኾቦርትጽ* የተሰኙትን ተመልክቻለሁኝ ። ከህይወት ጋር እኩል መራመድ የሚችሉ አይደሉም ። ወንድሜ ፣ በፍጹም አይደሉም!» በማለት መለሰ።

---

* ዱኾቦርትጽ ፡ — የየራሳቸውን የሃይማኖት ዕምነት ተከታዮች ። (ተርጓሚው)



እናት ጠንከር ያለ አነጋገሩን በጉጉት ታዳምጣለች ። ይህ መካከለኛ ዕድሜ ያለው ሰው ከልጅዋ ጋር እንዲህ ያለ ንግግር መነጋገሩ አስደሰታት ። ይሁን እንጂ የፓቬል ጠባይ ድርቅ ያለ በመሆኑ እርሷ ይበልጥ እንግዳ ተቀባይ በመሆን ለማካካስ ሞከረች ። ስለዚህም ፡ —

«ሚኻኢሎ ኢቫኖቪች ፣ ትንሽ የሚጎረስ ብጤ ላቅርብልህ?» በማለት ሪቢንን ጠየቀችው ።

«አመሰግናለሁኝ እናት ። እራቴን አሁን ነው የበላሁት» በማለት ለእናት መልስ ከሰጠ በኋላ «እና ታዲያ ፣ ፓቬል ፣ ሕይወት እንደዚህ መሆን የለበትም ብለህ ነው የምታስበው?» ብሎ ፓቬልን ጠየቀ ።

ፓቬልም ከመቀመጫው በመነሳት እጆቹን ወደኋላው አድርጎ ክፍሉ ውስጥ ወዲያና-ወዲህ ይንጎራደድ ጀመር ። ከዚያም ፡ —

«ሕይወት ትክክለኛውን አቅጣጫ እየተከተለ ነው ። አንተ እኔን ግልጽ በሆነ ልቦናህ እንድትቀርበኝ ያደረገ ሕይወት አይደለምን? እኛን ሠርቶ-አደሮችን ሕይወት ቀስ-በቀስ እያስተባበረን ነው ። መላውን ሠርቶ-አደሮች በሙሉ በአንድ ላይ የሚያስተባብርበት ጊዜም ይመጣል ። ሕይወት ለእኛ ከባድ እና አድላዊ ነው ። ይሁን እንጂ ፣ መራራ የሆነ ምንነቱን በዐይናችን ፊት ጉልህ አድርጎ እያሳየን በመገኘት ላይ ሲሆን ፣ ሁኔታዎችን በፍጥነት ለማንቀሳቀስ እንዴት እንደሚቻልም ያመለክተናል» በማለት ተናገረ ።

«ልክ ነህ!» አለ ሪቢን ። ከዚያም ፡ — «ሰውን ተሃድሶ እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል ። አንድ ሰው ሰነፍ ከሆነ ገላ መታጠቢያ ቤት ወስደኸው ደህና አድርጎ ገላውን እንዲታጠብ ካደረግህ በኋላ ንጹህ ልብስ እንዲለብስ አድርገው ። ከዚያ በኋላ በተገቢ ሁኔታው ላይ እንደገና ሊገኝ ይችላል ። የአንድን ሰው ልብ ግን

እንደምን አድርጎ ማጠብ ይቻላል? ችግሩ ያለው እዚህ ላይ ነው!» በማለት ተናገረ ።

ፓቬል ስለ ፋብሪካው እና ስለ ፋብሪካው አለቆች ሁኔታ ፤ እንደዚሁም ወዝ-አደሮቹ ለመብታቸው እንደምን እንደሚታገሉ በስሜት ተውጦ ተናገረ ። ፓቬል በሚናገርበት ጊዜ ሪቢን የፓቬልን ዐረፍተ-ነገሮች በአራት ነጥቦች ይደመድማቸው ይመስል አልፎ-አልፎ ጠረጴዛውን በእጣቱ ቋ-ቋ ያደርጋል ። ብዙ ጊዜም በፓቬል ንግግር ጣልቃ እየገባ ፡ —

«እሺ! ወይ ጉድ!» ይላል ።

አንድ ጊዜ ደግሞ ሳቅ ካለ በኋላ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«አንተ ገና ወጣት ነህ! ስለሰው ብዙ አታውቅም!» አለው ። ፓቬልም ሪቢን አጠገብ በመሄድ ኮስተር ብሎ የሚከተለውን መለሰለት ፡ —

«እኩሌ ወጣት ነው ወይንም ሽማግሌ ነው በማለት አናውራ ። መገንዘብ ያለብን ትክክሉ አስተያየት የማን አስተያየት እንደሆነ ነው ።»

«እና ፤ ስለ እግዚአብሔር ምንነት ጭምርም ሲያሞኙን ነበር ብለህ ትገምታለህ ማለት ነዋ? ሀ! እኔም ሃይማኖታችን ፋይዳ-ቢስ ነው ብዬ አስባለሁኝ ።» አለ ።

እዚህ ላይ እናት ተሸበረች ። ፈጣሪን በሚመለከት ጉዳይ ላይ እና የተወደደ እና የተቀደሰ አድርጋ የምትቆጥረውን ፈጣሪ አምላኳን በሚመለከት ረገድ የምትከተለውን ዕምነቷን አንስቶ ባወሳ ቁጥር አላማኒ በሆነ አስተሳሰብ የልብ ቁስል እንዳይተክልባት ዐይኖቿን ከዐይኖቹ ጋር ተክላ ትመለከተዋለች ። ይሁን እንጂ ፤ ከእርሱ አላማኒነት በስተጀርባ በእርሱ ላይ አንድ ዓይነት ዕምነት ይሰማታል ። ይኸ ዕምነትም ያጽናናታል ።



«አስተሳሰቦቹን ልረዳ የምችለው ከቶውኑ እንዴት ይሆን?» በማለት ትደነቃለች ።

ይኸ በመካከለኛ የዕድሜ ዘመኑ ላይ የሚገኝ ሪቢንም በልጅዋ አነጋገር ቅር ይሰኝ ይሆናል ብላ ታስባለች ። ይሁን እንጂ ፤ ሪቢን ረጋ ብሎ ለፓቬል ይኸንን መሳዩን ጥያቄ ባቀረበለት ጊዜ ልትታገስ ካለመቻሏም በስተቀር በአጭሩ እና መረር ባለ አነጋገር የሚቀጥለውን ተናገረች ፡ —

«ፈጣሪ አምላክን በሚመለከት ረገድ ፤ የምትናገራቸውን ቃላት ዝግ ብለህ ብታስተውል ይሻላል! ያሻህን ሁሉ መመራመር ትችላለህ ። ከእኔ አሮጊት ከሆን ኩቷ ሴት ላይ ግን ፈጣሪ አምላኬን ከገፈፍክብኝ ከሀዘኔ እና ከትካዜዬ የሚያጽናናኝ አላገኝም!» አለችው ።

ሳሕኖቹን በምታጥብበት ጊዜ ዐይኖቿ በዕንባ ተመሉ ። እጣቶቿም ይንቀጠቀጣሉ ።

«እናቴ! እኛን ልትገነዘቢን አልቻልሽም!» በማለት ፓቬል አክብሮት ባልጎደለው ሁኔታ ተናገረ ።

«እናት! ይቅርታ አድርጊልን!» በማለት ጎላ እና ረጋ ባለ ድምፅ ሪቢን ተናገረ ።

በጥቂቱ ፈገግ ካለ በኋላ ፓቬልን መልከት አደረገው ። ከዚያም ፡ —

«ይህንን አስተሳሰብ ልትረጂው እንደማትችይ ዘንግቼው ነበር!» በማለት ተናገረ ።

«እኔ የተናገርኩት ደግ እና መሀሪ ስለሆነው ስለዚያ ስለምታምኝበት አምላክ አልነበረም ። እኔ የተናገርኩት መማቻ ዱላ ይመስል እኛን ለማስፈራራት ካህናት መጠቀሚያቸው ስለሚያደርጉት አምላክ ነው ። እፍኝ የማይሞሉ ሰዎች ለሚፈጽሟቸው ክፉ ምግባሮች ሕዝቦች በሙሉ እንዲሰግዱ ለማድረግ ስለሚጠቀሙበት አምላክ ነው» በማለት ፓቬል ተናገረ ። ሪቢንም ጠረጴዛውን በመደብደብ ፡ —

«ይኸውልህ! የሀሰት አምላክ ፈጥረውብናል! አጠገባቸው ያገኙትን ነገር ሁሉ እያነሱ ሊቀጠቅጡን ይሻሉ! እናት ፣ እስኪ ይኸንን ጉዳይ ዝግ ብለሽ አስተውይው ፡ — እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ፈጠረው ። ይህም ማለት ሰው ፈጣሪውን የሚመስል ከሆነ ፣ ፈጣሪ አምላክም ሰውን ይመስላል ማለት ነው ። እኛ ግን ፈጣሪን የምንመስል ሳንሆን እንደዱር አራዊቶች ነን ። አብያተ-ክርስትያናት በእኛ ላይ የማስፈራሪያ ቁራዎች ያስጮሁብናል ። አየሽ እናት ፣ ይኸንን ዓይነቱን አምላክ መለወጥ ያሻል ። ማጽዳትም ያሻል! ፈጣሪን የቅጥፈት እና የዘለፉ ልብስ አጎናጽፈውታል ። ነፍሳችንን ለማውጣት ሲሉ ካህናት የፈጣሪን መልክ ተልትለውታል!» በማለት ተናገረ ።

ይናገር የነበረው ረጋ ብሎ ነው ። ይሁን እንጂ ከአንደበቱ የሚወጡት እየአንዳንዳቸው ቃሎች እናትን አስደንግጠዋታል ። በጥቁር ጢም የተከበበውና ረጅም የሆነውን አስከሬን መሳይ ፊቱን ስታይ ትፈራዋለች ። ልቧን በድንጋጤ ድው-ድው የሚያደርጉትን የዐይኖቹን ጽልመታዊ አበራር አተኩራ መመልከት አልቻለችም ።

«ከዚህ ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ልሒድ ። እንዲህ ያለ ንግግር ማዳመጥ ለእኔ ከአቅሜ በላይ ነው!» በማለት ጭንቅላቷን እያወዛወዘች ተናገረች ።

ከዚያም ወዲያውኑ ወደማዕዱ ክፍል ሄደች ።

«አየህ ፓቬል ፣ የነገሮች ሁሉ መገኛ ማዕከል ጭንቅላት ሳይሆን ፣ ልብ ነው ። ልብ በሰው ነፍስ ውስጥ ይዞት የሚገኘው ቦታ እጅግ ልዩ የሆነ ቦታ ነው ። በዚያ ቦታ ውስጥም ሌላ የሚበቅል አንዳችም ነገር የለም» በማለት ሪቢን ተናገረ ።

«የሰውን ልጅ ነፃ የሚያወጣው የአዕምሮ ምርም



ር ብቻ ነው!» በማለት ፓቬል ጠንከር አድርጎ ተናገረ ።

«የአዕምሮ ምርምር ለሰው ልጅ ብርታትን የሚሰጥ አይደለም ። ብርታትን የሚሰጠው ልቡ እንጂ አዕምሮው አይደለም!» በማለት ሪቢን ድምፁን ከፍ አድርጎ መለሰለት ።

እናት ልብሶቿን አወላልቃ የምሽት ፀሎቷን ሳታደርስ ተኛች ። በርዷት የነበረ ከመሆኑም በስተቀር ደስ አልተሰኘችም ። ቀደም ሲል ብልህ ሰው መስሏት የነበረው እና ደስ አሰኝቷትም የነበረው ሪቢን አሁን እንድትጠላው አደረጋት ። ሪቢን በተናገረ ቁጥር ፣ እናት ፡ —

«ኧረ ጉድ በሉ ይሄን ከሃዲ! ኧረ ጉድ በሉ ይኸን አመጸኛ! እዚህ ምን ሊያረግ ይመጣል?» በማለት ከራሷ ጋር ትነጋገራለች ።

እርሱ ግን በተረጋጋ ሁኔታ እንደሚቀጥለው መነጋገሩን አላቋረጠም ፡ —

«ቅዱሱ ቦታ ባዶ መሆን የለበትም ። አምላክ ልብ ውስጥ የሚይዘው ቦታ እጅግ ገር የሆነ ቦታ ነው ። ያንን ቦታ ቆርጠህ ብታወጣው በምትኩ ትልቅ ቁስል ይቀራል ። ፓቬል ፣ አዲስ ዕምነት ማሰላሰል አለብህ ። ለሰው ጓደኛ የሚሆን አምላክን መፍጠር ያስፈልጋል!» አለ ሪቢን ።

«ክርስቶስ እኮ ነበር!» በማለት ፓቬል መለሰ ።

«ክርስቶስ ደካማ ነበር ። 'ይኸ ጽዋ ይለፈኝ' በማለት ተናገረ ። ቄሳርንም አወቀ ። በፈጠራቸው ፍጡሮቹ ላይ ሰው የበላይነት ሥልጣን እንዲኖረው ፈጣሪ እንዴት ይፈቅዳል? እርሱ ራሱ ሁለንታዊ ሥልጣን እኮ ነው! ከዚህ መለስ የፈጣሪ ነው ፣ ከዚህ መለስ ደግሞ የሰው ነው በማለት ፈጣሪ ነፍሱን ከሁለት ቦታ አ

ይከፍልም ። ፈጣሪ ግን ንግድን አልተቃወመም ። ጋብቻንም አልተቃወመም ። የበለስን ዛፍ መርገሙም ትክክል አልነበረም ። የበለስ ዛፍ ፍሬ ስላላፈራ ሊወቀስ ይገባዋልን? የሰው ልጅ ደግነትን የማያስገኝ እስከሆነ ድረስ ሊወቀስ እንደማይችል ሁሉ ይኸንን መሳይ ክፋት ነፍሴ ውስጥ ያለመለምኩት እኔ ራሴ ነኝን?»

የሁለቱ ሰዎች ድምፅ በከፍተኛ ስሜት በተዋጠ ክርክር በክፍሉ ውስጥ በተፈራረቂ ይሰማል ። ፓቬል በክፍሉ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ሲንጎራደድ ወለሉ ሲጥ-ሲጥ የሚል ድምፅ ያሰማል ። ፓቬል በሚናገርበት ጊዜ ሁሉም ነገር ፀጥ በማለት አንዳችም ድምፅ አይሰማም ። ሪቢን ግን ዝግተኛ በሆነ እና ረጋ ባለ ድምፁ በሚናገርበት ጊዜ የግድግዳው ሰዓት መቂና ጥ ከወዲያ ወዲህ ቋ-ቋ-ቋ የሚል ድምፅ ሲያሰማ እና በረዶ የተቀላቀለው ነፋስም የቤቱን ግድግዳ ታክኮ ሲነፍስ ንግግሩን ትሰማለች ።

«በእኔው በራሴ አባባል ፣ ማለትም በብረት አቅላጭ አባባል ሃሣቤን ላቅርብ — እግዚአብሔር የእሣት ነበልባል ነው ። እርሱም በሰዎች ልብ ውስጥ ያድራል ። ‘አስቀድሞ ቃል ነበረ ። ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ።’ ተብሎአል ። እና ስለዚህም ፣ ይህ ቃል መንፈስ ነው...»

«ቃል አዕምሮ ነው!» በማለት ፓቬል አጠንክሮ ተናገረ ።

«እሺ ይሁን ። እንደዚህም ከሆነ ፣ እንግዲህ የእግዚአብሔር መገኛ በልቦና እና በአዕምሮ ውስጥ ነው እንጂ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አይደለም ማለት ነው ። ቤተ-ክርስቲያን የፈጣሪ መካነ-መቃብር ነው ።»

እናት ተኝታ ስለነበረ ሪቢን ሲሄድ አልሰማችም ።

ከዚህም በኋላ ሪቢን አዘውትሮ መጪ ሆነ ። ሪቢን በሚመጣበት ጊዜ ከፓቬል ጓዶች መካከል አንደ



ኛቸው ቢኖሩ ፣ ሪቢን ከአንድ ጥግ ቦታውን ይዞ ከመቀመጥ በስተቀርና አልፎ-አልፎ ብቻ «እንዴታ ነው እንጂ!» ከማለት በስተቀር ሌላ ነገር አይናገርም ።

አንድ ቀን ከተቀመጠበት ጥግ ቦታ ሁኖ በቤቱ ውስጥ ያሉትን ሁሉ አተኩሮ እየቃኛቸው ጨፍገግ ባለው ሁኔታ ሪቢን የሚከተለውን ተናገረ ፡—

«ስለማናቸውም ጉዳዮች በሚወሳበት ጊዜ ጉዳዮቹ በሚገኙበት ሁኔታ ላይ ተመሥርቶ ማውሳት እንጂ ወደፊት ምን እንደሚሆኑ ገምቶ ማውሳት አያስፈልግም ። እነዚህ ጉዳዮች ወደፊት ምን እንደሚሆኑ ማን ያውቃል? ሕዝቦች አንዴ ነፃ ከወጡ ለራሳቸው የሚበጃቸውን ራሳቸው ይወስናሉ ። ምን እንደሚፈልጉ ሳይጠየቁ በጫንቃቸው ላይ እስከዛሬ በተደራራቢ ከባድ መርግ ድንጋይ ተጭኖባቸዋል ። ሕዝቦች የሚሹትን ያስቡ ይመራመሩ ዘንድ ከእንግዲህ ጊዜው ነው ። ምናልባትም እኮ ማናቸውንም ነገር ፣ ማለትም ኑሮንም ፣ ምርምርንም ይቃወሙ ይሆናል ። ምናልባትም እንደቤተ-ክርስቲያን አምላክ ሁሉንም ነገር ጠላታቸው አድርገው ይመለከቱት ይሆናል ። መጻሕፍቶቹን በሙሉ ስጧቸው ። ከዚያም እነርሱ ራሳቸው ያሻቸውን ይምረጡ ። ዋናው ነገር ይኸ ነው!»

ሪቢን እና ፓቬል ብቻቸውን ሲሆኑ ክርክራቸው ማብቂያ በሌለው ሁኔታ የሚቀጥል ሲሆን በሚከራከሩበት ጊዜም በመማረር እርስ-በርሳቸው አይናቆሩም ። እናት እነርሱ የሚለዋወጧቸውን እየአንዳንዳቸውን ቃላት በማዳመጥ ፍሬ-ሃሣቡን ለመገንዘብ በጥሞና ትጥራለች ። አንዳንድ ጊዜ ባለ ሰፊ-ትከሻው እና ጢም-ጥቁሩ ሪቢን ፣ እንደዚሁም ጠንካራው እና ረጅሙ ልጅዋ የታወሩ ይመስላታል ። የመውጫቸውን ቦታ በመፈለግ አንዴ ወዲህ አንዴም ወዲያ በመዳበስ ፣ ዐይን-አልባ በሆኑት ጠንካራ ጣቶቻቸው ያገኙትን

ሁሉ በመነካካት ፣ ከወዲያ ወዲህ በመንቆራጠጥ ዕቃ
ዎችን በመጣል በእግራቸው ይሰባብራሉ ። ያመኑበት
ን ሳይለቁና ተስፋቸውንም ሳይቆርጡ በተመስጦ ተው
ጠው ዕቃዎችን በመነካካትና በማተረማመስ ያመሰቃ
ቅላሉ ።

ሃቀኛነትን እና ቆራጥነትን የሚያረጋግጡ መግለ
ጫዎች የሆኑትን አስደንጋጭ ቃላትን እናት ለማዳ
መጥ እንድትችል ያበቋት ሲሆኑ ፣ እነዚህን የመሳሰ
ሉት ቃላት ቀደም ሲል ያሳድሩባት የነበሩትን ዓይ
ነት ኃይለ-ሥሜቶች አሁን ተላምዳቸዋለች ። እንዴት
እንደምትቋቋማቸው ተገንዝባለች ። አንዳንድ ጊዜ ፈጣ
ሪ-አምላክን ስለመካድ በሚገለጹት ቃላት ውስጥ ለፈ
ጣሪ-አምላክ ያላትን የማይናወጽ ዕምነት ትገነዘባለች ።
ከዚያም መለስተኛ በሆነ በይቅር-ባይነት ፈገግታ ፈገ
ግ ትላለች ። እና ደግሞ ፣ ምንም እንኳን ሪቢንን የማት
ፈቅደው ቢሆንም ፣ ባየችው ቁጥር ለርሱ ያላት ትልቅ
ጥላቻ መቀስቀሱ አብቅቷል ።

በየሳምንቱ ለኾኾል መጻሕፍቶችን እና የታጠቡ
ልብሶችን ወህኒ ቤት ትወስዳለች ። አንድ ጊዜ ከኾ
ኾል ጋር ተገናኝታ እንድትነጋገር ተፈቅዶላት ነበር ።
አነጋግራው ከተመለሰች በኋላም ስለርሱ ሁኔታ ስት
ናገር ፦

«ቅንጣት ታህል አልተለወጠም ። ለሰው ሁሉ የሚ
ያሳየው የተለመደ ደግነቱ እንዳለ ነው ። ሰው ሁሉ
ከርሱ ጋር ይቀልዳል ። ያለበት ሁኔታ ለርሱ ከባድ
ነው ። በጣም ከባድ ነው ። ያም ሁኖ ግን መከፋቱን
አያሳይም...» በማለት ለርሱ ባላት የመውደድ ሁኔታ
ተናገረች ። ሪቢንም በበኩሉ አስተያየቱን ሲሰጥ ፦

«ነው እንጂ! እንዲህ መሆን አለበት ። ሀዘን መሸሸ
ጊያ ነው ። እኛም በውስጡ ተሸሽገን እንገኛለን ። ይኸ
ንን መሳዩን የመሸሸጊያ ልብስ መልበስ ተላምደናል ።



የሚያስኮራ ነገር የለበትም ። ሰው ሁሉ ዐይኖቹ እንዳ
ያዩ ይሁነኝ ተብሎ በተጋረደበት ግርዶሽ የተከለለ
አይደለም ። አንዳንድ ሰዎች እንደው ዝም ብለው ዐይ
ኖቻቸውን ይጨፍናሉ ። ስለዚህም እንከፎች ከሆንን
እየሳቅን መከራችንን መቀበል ብቻ ነው!» በማለት
ተናገረ ።

12

በአካባቢው የሚገኘው ነዋሪ ግራጫማ ቀለም ወዳለ
ው ወደእነቭላሶቭ ትንሽ ቤት ከጊዜ ጊዜ ዐይኖቹን
ማማተር ቀጠለ ። ይኸ የማተኮሩ ዝንባሌ ሊደርስ የ
ቻለበት ምክንያት በጥርጣሬ እና ከውስጥ ተደብቆ
በሚገኝ የጠላትነት ስሜት ሲሆን ፣ ዕምነት በተጣለ
በት የመወደድ ስሜት ላይም የተመረኮዘ ነበር ። አንዳ
ንድ ጊዜ ፓቬልን አንዱ የማያውቀው ሰው ከመንገ
ድ ላይ አግኝቶት ያቆመውና የሚከተለውን ይጠይቀ
ዋል ፦

«ሰማኸኝ ወይ ወንድሜ ፣ አንተ መጻሕፍቶችን
የምታነብ ሰው ስለሆንክ ሕጉን የምታውቅ ነህ ። ከ
ዚህ ቀጥሎ በምገልጽልህ ጉዳይ ላይ ያለህን አስተያ
የት አትነግረኝምን?...»

ይኸንን በመሳሰለ ጥየቃ ፖሊስ ወይንም የፋብሪ
ካ አስተዳዳሪ ያደረሱባቸውን በደሎች ለፓቬል ዘር
ዝረው ያስረዱታል ። ፓቬል ጉዳዩን ፡ ውስብስብ ሁኖ
ሲያገኘው ለባለ ጉዳዩ ማስታወሻ ጽፎ በመስጠት
በከተማው ውስጥ ከሚገኘው እና ከሚያውቀው ጠበቃ
ዘንድ ባለጉዳዩ ሂዶ ጉዳዩን እንዲያስረዳ ያደርጋል ። እ
ርሱ ራሱ ሊያስረዳ የሚችለው ጉዳይ ሲሆን ደግሞ
ጉዳዩን ለባለ ጉዳዩ ያብራራለታል ።

ሁሉ በመነካካት ፤ ከወዲያ ወዲህ በመንቆራጠጥ ዕቃ
ዎችን በመጣል በእግራቸው ይሰባብራሉ ። ያመኑበት
ን ሳይለቁና ተስፋቸውንም ሳይቆርጡ በተመስጦ ተው
ጠው ዕቃዎችን በመነካካትና በማተረማመስ ያመሰቃ
ቅላሉ ።

ሃቀኛነትን እና ቆራጥነትን የሚያረጋግጡ መግለ
ጫዎች የሆኑትን አስደንጋጭ ቃላትን እናት ለማዳ
መጥ እንድትችል ያበቋት ሲሆኑ ፤ እነዚህን የመሳሰ
ሉት ቃላት ቀደም ሲል ያሳድሩባት የነበሩትን ዓይ
ነት ኃይለ-ሥሜቶች አሁን ተላምዳቸዋለች ። እንዴት
እንደምትቋቋማቸው ተገንዝባለች ። አንዳንድ ጊዜ ፈጣ
ሪ-አምላክን ስለመካድ በሚገለጹት ቃላት ውስጥ ለፈ
ጣሪ-አምላክ ያላትን የማይናወጽ ዕምነት ትገነዘባለች ።
ከዚያም መለስተኛ በሆነ በይቅር-ባይነት ፈገግታ ፈገ
ግ ትላለች ። እና ደግሞ ፤ ምንም እንኳን ሪቢንን የማት
ፈቅደው ቢሆንም ፤ ባየችው ቁጥር ለርሱ ያላት ትልቅ
ጥላቻ መቀስቀሱ አብቅቷል ።

በየሳምንቱ ለኾኾል መጻሕፍቶችን እና የታጠቡ
ልብሶችን ወህኒ ቤት ትወስዳለች ። አንድ ጊዜ ከኾ
ኾል ጋር ተገናኝታ እንድትነጋገር ተፈቅዶላት ነበር ።
አነጋገራው ከተመለሰች በኋላም ስለርሱ ሁኔታ ስት
ናገር ፡ —

«ቅንጣት ታህል አልተለወጠም ። ለሰው ሁሉ የሚ
ያሳየው የተለመደ ደግነቱ እንዳለ ነው ። ሰው ሁሉ
ከርሱ ጋር ይቀልዳል ። ያለበት ሁኔታ ለርሱ ከባድ
ነው ። በጣም ከባድ ነው ። ያም ሁኖ ግን መከፋቱን
አያሳይም...» በማለት ለርሱ ባላት የመውደድ ሁኔታ
ተናገረች ። ሪቢንም በበኩሉ አስተያየቱን ሲሰጥ ፡ —

«ነው እንጂ! እንዲህ መሆን አለበት ። ሀዘን መሸሸ
ጊያ ነው ። እኛም በውስጡ ተሸሽገን እንገኛለን ። ይኸ
ንን መሳዩን የመሸሸጊያ ልብስ መልበስ ተላምደናል ።



የሚያስኩራ ነገር የለበትም ። ሰው ሁሉ ዐይኖቹ እንዳ
ያዩ ይሁነኝ ተብሎ በተጋረደበት ግርዶሽ የተከለለ
አይደለም ። አንዳንድ ሰዎች እንደው ዝም ብለው ዐይ
ኖቻቸውን ይጨፍናሉ ። ስለዚህም እንከፎች ከሆንን
እየሳቅን መከራችንን መቀበል ብቻ ነው!» በማለት
ተናገረ ።

## 12

በአካባቢው የሚገኘው ነዋሪ ግራጫማ ቀለም ወዳለ
ው ወደእነሽላሶቭ ትንሽ ቤት ከጊዜ ጊዜ ዐይኖቹን
ማማተር ቀጠለ ። ይኸ የማተኮሩ ዝንባሌ ሊደርስ የ
ቻለበት ምክንያት በጥርጣሬ እና ከውስጥ ተደብቆ
በሚገኝ የጠላትነት ስሜት ሲሆን ፤ ዕምነት በተጣለ
በት የመወደድ ስሜት ላይም የተመረኮዘ ነበር ። አንዳ
ንድ ጊዜ ፓቬልን አንዱ የማያውቀው ሰው ከመንገ
ድ ላይ አግኝቶት ያቆመውና የሚከተለውን ይጠይቀ
ዋል ፡ —

«ስማኸኝ ወይ ወንድሜ ፤ አንተ መጻሕፍቶችን
የምታነብ ሰው ስለሆንክ ሕጉን የምታውቅ ነህ ። ከ
ዚህ ቀጥሎ በምገልጽልህ ጉዳይ ላይ ያለህን አስተያ
የት አትነግረኝምን?...»

ይኸንን በመሳሰለ ጥየቃ ፖሊስ ወይንም የፋብሪ
ካ አስተዳዳሪ ያደረሱባቸውን በደሎች ለፓቬል ዘር
ዝረው ያስረዱታል ። ፓቬል ጉዳዩን ፡ ውስብስብ ሁኖ
ሲያገኘው ለባለ ጉዳዩ ማስታወሻ ጽፎ በመስጠት
በከተማው ውስጥ ከሚገኘው እና ከሚያውቀው ጠበቃ
ዘንድ ባለጉዳዩ ሂዶ ጉዳዩን እንዲያስረዳ ያደርጋል ። እ
ርሱ ራሱ ሊያስረዳ የሚችለው ጉዳይ ሲሆን ደግሞ
ጉዳዩን ለባለ ጉዳዩ ያብራራለታል ።

መዘባነን የሌለበት አነጋገር ለሚናገር ፤ ለማናቸው-
ም ጉዳዮች ዐይኖቹን በተመልካችነት እና ጆሮዎቹን
በአድማጭነት ክፍቶ ለሚመለከት እና ለሚያዳምጥ ፤
አለመግባባትን በሚያስከትል በማናቸውም ክርክር ላይ
በግትርነት እስከመጨረሻው ድረስ ለሚከራከረው ፤ ሁሉ-
ንም ሰዎች አገናኝቶ የሚያቀራኛቸውን የጋራ የሆነ
ውን ውስብስብ የሕይወት ድርና ማግ ምንግዜም
እና በየትኛውም ቦታ ውሉን ፈልጎ ለሚያገኘው
ለዚህ ቁም ነገረኛ ለሆነ ወጣት ሕዝቡ አክብሮት
ይሰጠው ጀመር ።

በተለይም «የጨቀጨቅ (ጨፌ) ኮፔክ*» የተሰኘው
ግጭት ከደረሰ በኋላ ፓቬል ልዩ የሆነ አክብሮት
ማግኘት ጀመረ ።

ልምጭ እና አርዘ-ሊባኖስ ዛፍ የሚመስሉ ዛፎች
የተጠቀጠቁበት ጨቀጨቅ የሆነ ሰፊ ረግረጋማ መሬ
ት ፋብሪካውን ባሻገር ሁኖ ዙሪያውን ከብቦት ይገ
ኛል ። በበጋው ወራት ይህ ረግረጋማ መሬት ቢጫማ
ቀለም ያለው ተን እያምዘገዘገ የሚተፋ ከመሆኑም
በስተቀር ፤ የወባ ንዳድ የሚያዛምቱ የትንኝ መንጋዎ
ች ስለሚፈልቁበት የሠፈሩ ነዋሪዎች በትንኞቹ በመነ
ደፍ በወባ ንዳድ ይበከላሉ ። ይህ ረግረጋማ መሬት
ንብረትነቱ የፋብሪካው ነው ። ይኸንኑ ረግረጋማ ቦታ
አድርቆ ከውስጡ ነዳጅ ለማውጣት የፋብሪካው ዲሬ
ክተር ፈለገ ። ይሁን እንጂ ረግረጋማውን ቦታ የሚያ
ደርቀው የፋብሪካውን ሠራተኞች የኑሮ ሁኔታ ለማሻ
ሻል በማስመሰል ፤ ለየአንዳንዱ የፋብሪካው ሠራተኛ
ከሚከፈለው ከየአንዳንዱ የሩብል ዐበል ላይ አንዳን

---

* ኮፔክ ፡ — ምንዝር ገንዘብ ነው ። በአሁኑ ጊዜ 100 ኮፔክ 1 ሩብል ነው ። (ተርጓሚው ።)



ድ ኮፔክ ተቆራጭ ሁኖ ረግረጉ መድረቅ አለበት
ብሎ ዲሬክተሩ ትዕዛዝ አስተላለፈ ።

ወዝ-አደሮቹ በተቃውሞ ቁጣ ተዋጡ ። በተለይም
ያስቆጣቸው ጉዳይ ደግሞ ከእነርሱ ላይ ብቻ እንጂ
ቢሮ ውስጥ ተቀምጠው ከሚሠሩት የቢሮ ሠራተኞ
ች ላይ አንዳችም ገንዘብ ተቆራጭ ሁኖ ባለመ
ወሰዱ ነው ።

ይህ ከወዝ-አደሮች ላይ አንዳንድ ኮፔክ ተቆራ
ጭ እየሆነ ገቢ እንዲሆን በታዘዘበት ቅዳሜ ዕለት
ፓቬል አሞት እቤቱ ውሎ ስለነበር ፤ በዚያን ዕለት
ስለጉዳዩ ምንም አያውቅም ነበር ። በማግስቱ ፤ ሲዞቭ
የተሰኘ ነባር የፋብሪካው ሠራተኛ እና ማኾቲን የተ
ሰኘ አንድ ረዥም ነጭናጫ ሜካኒክ ፓቬልን ሊጠይ
ቁት ቤቱ መጥተው ስለነበር የፋብሪካው ዲሬክተር
ስላስተላለፈው ውሳኔ ነገሩት ። ሲዞቭም ስሜት በተመ
ላበት ሁኔታ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«እኛ ሽማግሌዎቹ በአንድ ላይ ሁነን በመሰብሰብ
በጉዳዩ ተነጋገርን ። አንተ አዋቂ ሰው በመሆንህ ዲሬ
ክተሩ ከእኛ ላይ ኮፔኮች ሰብስቦ የወባ ትንኞችን
ለማጥፋት የሚያስችለው ሕግ መኖር-አለመኖሩን እን
ድትገልጽልን ጓዶች እኛን ወደ አንተ ዘንድ ለመላ
ክ ባደረጉት ውሳኔ መሠረት ይኸው ከአንተ ዘን
ድ መጥተናል ።» ከዚያም ትናንሽ ዐይኖቹን ብሩህ
አድርጎ በመክፈት ማኾቲን የሚከተለውን ለፓቬል
ነገረው ፡ —

«እስኪ ልብ ብለህ አስተውለው ፤ የዛሬ አራት ዓ
መት እነዚያ ስግብግብ ሞሽላቆች የገላ መታጠቢያ
ቤት ለመሥራት ብለው ገንዘባችንን ወሰዱ ። ሦስት
ሺህ ስምንት መቶ ሩብል ሰበሰቡ! አሁን የት ደረሱ?
ይሠራል የተባለውን የገላ መታጠቢያ ቤት እስከዛሬ
ተሠርቶ አላየንም!»

ፓቬል ኮፔክ ተቆራጭ ሁኖ ለመወሰድ መታዘዙ ሕገ-ወጥ መሆኑን እና የረገረጋማው መሬት መድረቅ ለፋብሪካው ስለሚያስገኘው ጠቀሜታ ዘርዝሮ አስረዳ ። ሁለቱ ወዝ-አደሮች ፊታቸው በቁጣ ተኮሳትሮ ሄዱ ። እናት ከሸኘቻቸው በኋላ ፈገግ በማለት «ሽማግሎች የሆኑት እንኳን የአንተን ምክር መጠየቅ ጀመሩ» በማለት ፓቬልን ተናገረችው ።

ፓቬልም አንዳችም መልስ ሳይመልስላት ከመቀመጫው ላይ ተቀምጦ መጻፍ ቀጠለ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም የሚከተለውን ተናገረ ፡ — «እናቴ አንድ የማቀርብልሽ ጉዳይ አለኝ ። ፈቃድሽ ይሁንልኝ ። እባክሺን ከተማ ሂደሽ ይህንን የማስታወሻ ወረቀት አድርሺልኝ » አላት ።

«ወረቀቱ አደጋ የሚያስከትል ነውን?» በማለት ጠየቀችው ።

«አዎን ። ወረቀቱን እንድታደርሺልኝ የምልክሽ ጋዜጣችን በሕቡዕ ከሚታተምበት ቦታ ነው ። በሚቀጥለው የጋዜጣችን እትም ላይ ለጨቀጨቁ ቦታ ስለሚከፈለው ኮፔክ ጉዳይ በምንም መንገድ ቢሆን ታትሞ መውጣት አለበት ።»

«እሺ ። ሂጄ ወረቀቱን አደርሳለሁኝ » በማለት እናት ተናገረች ።

ልጅዋ ፓቬል በእናት ላይ ዕምነቱን ጥሎ ይኽንን ተግባር እንድትፈጽም ሲያደርጋት ይህ የመጀመርያ ጊዜው ነው ። ፓቬል ጉዳዩን የገለጸላት ፍጹም ግልጽ በሆነ ሁኔታ ስለነበረ እናት ተደሰተች ። ልብሷን እየለበሰች የሚከተለውን ለፓቬል ተናገረች ፡ —

«ፓሻ ፤ ጉዳዩ ይገባኛል ። ዐይን ያወጣ ዝርፊያ ነው! ስሙን ማን ነበር ያልከኝ? የጎር ኢቫኖቪች ነው?» አለች ።



ድክም ብሏት ነገር ግን ደግሞ ተደስታ መሸት ካለ በኋላ ወደቤት ተመለሰች ። ልጅዋንም እንዲህ በማለት ነገረችው ፡ —

«ሳሻን አየሁዋት ። ሰላም ብላሃለች ። የጎር ኢቫኖቪች አጉል መዘባነንን የማያውቅ ተጨዋች ሰው ነው ። ለዛ ያለው ቀልድ መቀለድ ያውቃል » አለችው ። ፓቬልም ረጋ ባለ ሁኔታ ፡ —

«ስለወደድሻቸው ተደስቻለሁኝ ። » በማለት መለሰላት ።

«ፓሻ ፤ እነርሱ እንደማንኛውም ተራ ሰው ያለ አንዳች መኩፈስ የሚኖሩ ናቸው ። ሰዎች በኩራት የማይወጠሩና የማይጀነኑ ሲሆኑ ጥሩ ነው ። አንተን ብዙ ያከብራሉ» አለችው ።

ፓቬል ሙሉ-በሙሉ ስላልተሻለው ሰኞ ዕለትም እቤት ዋለ ። ምሳ ሰአት ላይ ፌዎዶር ማዚን በደስታና በስሜት ተውጦ ቁና-ቁና እየተነፈሰ በሩጫ ርምጃ ወደፓቬል ቤት ገባ ። እንዲህም በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ፡ —

«ተነስ እንሂድ! መላው የፋብሪካ ሠርቶ-አደር ተንቀሳቅሶአል ። ወደ አንተ ዘንድ ልከውኝ ነው የመጣሁት ። ሲዞቭ እና ማኾቲን ጉዳዩን ለማብራራት ከማንም የበለጠ የምትችለው አንተ ነህ ብለዋል ። መቸም ተአምር ነው ፤ ታየዋለህ!» አለ ።

አንዳችም ቃል ሳይናገር ፓቬል ልብሶቹን መልበስ ጀመረ ።

«ሴቶቹ ሁሉ ተሰብስበው መጥተው ድምፃቸውን ያሰማሉ ።»

«እረ እኔም እመጣለሁኝ! አሁን እነርሱ ደግሞ ምን ሊያደርጉ ነው? እረ እኔም እመጣለሁኝ!» በማለት እናት ተናገረች ። ፓቬልም ፡ —

«ነይ ።» በማለት መለሰላት ።

በፍጥነትና በዝምታ መንገዱን ቁልቁል ተያያዙት ። እናት በስሜት ተውጣ ስለነበረ የሲቃ ትንፋሽ ትተነፍሳለች ። አንድ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ጉዳይ ሊከናወን የተቃረበ መሆኑ ተሰማት ። በፋብሪካው ደጃፎች ላይ የሚጯጯሁና የሚጣሉ ብዙ ሴቶች ቆመዋል ። ሦስቱ ወደ ፋብሪካው ምድረ-ግቢ ሲገቡ በስሜት የተዋጠ አያሌ ድምፅ ከሚያጉረመርምበት እና ጥቅጥቅ ያለ ሕዝብ ከሚገፋፋበት ጨለም ያለ ቦታ ላይ ደረሱ ። ከሸክላ የተሠራውን ግድግዳ ለጀርባቸው ሰጥተው ከብረት ክምር ላይ ሲዞቭ ፤ እነ ማኾቲን ፤ እነ ቪያሎቭ እና ሌሎችም አምስት ወይንም ስድስት ተደማጭ ወዝ-አደሮች ከቆሙበት ቦታ ላይ በዚያ የተሰበሰበው ወዝ-አደር ሁሉ ፊቱን ወደእነርሱ መልሶ የቆመ መሆኑን እናት ተገነዘበች ። ከተሰበሰቡት መካከል አንዱ ፡—

«ቭላሶቭ መጥቶአል!» በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ።

«ቭላሶቭ? ወደዚህ ይምጣ!» የሚል ሌላ ድምፅ ተሰማ ።

«ኡ-ሽ-ሽ! ዝምበሉ!» የሚል ድምፅ ከብዙ አኳያ ተሰማ ።

አንድ ቀረብ ካለ ቦታ ላይ መለስተኛ የሆነው የሪቢን ድምፅ መሰማቱን ቀጠለ ። እንዲህም አለ ፡—

«እኛ መታገል ያለብን ከእኛ ላይ ለሚቆረጥብን አንድ ኮፔክ አይደለም ። የምንታገለው ለፍትሕ ነው! ዋናው ጉዳይ ይኸ ነው! እጅግ ተወዳጅ አድርገን የምንንከባከበው ይኸንን አንድ ኮፔካችንን አይደለም — ምንም እንኳን ይሄ ኮፔክ ከሌሎች መከሊቶች የከበደ ቢሆንም ክብነቱ ከሌሎች መከሊቶች የተሻለ አይደለም ። ይሁን እንጂ ፤ ይኸ የእኛ አንድ ኮፔክ ከዲሬክተሩ ሩብል የበለጠ የሰዎች ደም በውስጡ



ይዞ ይገኛል ። ዋጋው የሚገኘው ከኮፔኩ ላይ ሳይሆን ፤ ከደሙ ፤ ከፍትሑ ውስጥ ነው» በማለት ተናገረ ።

ከአንደበቱ የሚፈልቁት ቃላት በተሰበሰበው ሕዝብ ጆሮዎች ውስጥ እየተንቆረቆሩ በመግባት ከፍተኛ አድናቆትን አተረፉ ።

«ሪቢን! የተናገርከው ሁሉ ልክ ነው!»

«ብረት አቅላጩ ፤ ልክ ብለሃል!»

«ቭላሶቭ ይኸውና!» የሚሉ ድምፆች ተሰሙ ።

የፋብሪካው መሣርያዎች ከሚያሰሙት ዱም-ዱምታ ድምፅ ጋር ፤ ተኑ ከሚያሰማው እሽ-እሽታ እንደዚሁም የተዘረጉ ገመዶች ከሚያሰሙት ክው-ክውታ ጋር የሰዎቹም የጉርምርምታ ድምፆች አንድነት ተደባልቀው ይነጉዱ ጀመር ። እጆቻቸውን በቁጣ የሚያነሱ ፤ የዘለፋ ቃላትን በመሠንዘር እርስ-በእርሳቸው በተቃውሞ የሚያብሩ ሰዎች ከየአቅጣጫዎቹ እየገሠገሡ ይመጡ ጀመር ። በተዳከመ ልቦና ውስጥ ብዙ ጊዜ በመጠራቀም ታጅሎ የቆየ ቅሬታ አሁን ሕይወት ዘርቶ መውጫ ቀዳዳ ፈለገ ። ይህ ቅሬታ ተበቃይ ወደሆነ ነበልባልነት በሚቀየርበት ጊዜ የጨለሙ አክናፎቹን እያሰፋ በመዘርጋት ፤ ሕዝቦችን አጥብቆ በመደገፍ እና እርስ-በርሳቸውም እንደሰምና ፈትል የተስማሙ እንዲሆኑ በማድረግ በድል-አድራጊነት ዓየሩን መላው ። ከተጥለቀለቁት ሰዎች ጭንቅላት በላይ የአቧራ እና የጥላሸት ደመና ያንዣብባል ። ላብ ያጠመቃቸው ፊቶቻቸው በመነሳሳት መንፈስ በስሜት የተቀሰቀሱ ሲሆኑ ፤ ጉንጮች በጥቋቁር የእንባ ዘለላዎች ታጥበዋል ። ሀዘንተኛ በሆኑት መልኮች ላይ ዐይኖች ፈጥጠው ጥርሶች ገጥጠው ይታያሉ ።

ሲዞቭ እና ማኾቲን ቆመውበት ከነበረው የብረት ክምር ላይ ፓቬል ሂዶ ቆመ ።

«ጓዶች!» በማለት ፓቬል ድምፁን ከፍ አድርጎ
ተናገረ ።
እናት የልጅዋ ፊት መጠውለጉን እና ከንፈሮቹም
የሚንቀጠቀጡ መሆናቸውን አስተዋለች ። ይሁንኝ ብላ
ሳይሆን ፤ ሳታውቀው የተሰበሰበውን ሕዝብ እየገፋፋች
ልጅዋ ወደቆመበት ቦታ መራመድ ቀጠለች ። ከቆሙት
መካከል የገፋቻቸው ፦
«እንዴ ፤ ወዴት ለመሄድ ነው ይኸ ሁሉ ግፊያ?»
በማለት በቁጣ ተናገሩ ።
እርሷንም መልሰው በተራዋ ወደመጣችበት ገፉ
ዋት ። ይሁን እንጂ ፤ ይኸም ቢሆን ወደፊት ከመራመ
ድ አልገታትም ። ልጅዋ አጠገብ ለመቆም በነበራት
ፍላጎት በመገፋፋት በትከሻዋም በጉልበቷም ሰዎቹን
እያተረማመሰች ወደፊት መራመዷን ቀጠለች ።
ለርሱ ጥልቅ የሆነ ትርጉም ያለውን ከላይ የተና
ገረውን ቃል ፓቬል ባሰማበት ጊዜ ከደስታው ብዛ
ት ትናጋው ሲገናኝ ተሰማው ። ፍትሕን በማለም ፍ
ሞ የተቀጣጠለውን ልቡን ለእነዚህ ሰዎች በመስጠ
ት ፍላጎት ተውጧል ።
«ጓዶች!» አለ እንደገና ይኸንን ቃል በመድገም
ና ከኃይለ-ቃሉም ብርታትን እና ደስታን በመጎና
ጸፍ ። ቀጠል አደረገናም ፦
«አብያተ-ክርስትያናትን እና ፋብሪካዎችን የምንሠ
ራ እኛ ሕዝቦች ነን! ሠንሠለቶችን አቆላልፈን የምን
ሠራና ብረት አፍስሰን መክሊት የምንቀጠቅጥ እኛ
ሕዝቦች ነን! ከዕለተ-ልደት እስከ ዕለተ-ሞት ላለው
ጊዜ ሰውን ሁሉ የምንመግብ እና ሕያው አድርገን
ም የምናቆይ ሕያዋን ኃይሎች እኛ ነን!» በማለት
ተናገረ ።
«እንዴታ! ልክ ነው!» በማለት ሪቢን በከፍተኛ
ድምፅ ተናገረ ። ከዚያም ፓቬል ንግግሩን በመቀጠል ፦



«ምንግዜም እና በየትኛውም ቦታ ቢሆን ሥራን
ለመሥራት ሲሆን የመጀመርያዎች የምንሆን ፤ ማናቸው
ንም ዓይነት የድኅማ ድጋፍ ለማግኘት ግን የመጨረ
ሻዎቹ የምንሆን እኛ ነን ። ለመሆኑ ለእኛ ደንታ
ያለው ማነው? ቅንጣት ታህል በጎ ነገርን ለእኛ ያደ
ረገልንስ ማነው? የቀረው ቀርቶ ፤ ከሰው እንኳን የሚ
ቆጥረን ይገኛልን? አንድም የለም!»
«ማንም ከሰው የሚቆጥረን የለም!» የሚሉት ቃላ
ት ከተሰበሰቡት ሰዎች አንደበቶች አስተጋቡ ።
ንግግሩን እየቀጠለ ሲዘልቅ ፓቬል ይበልጥ ግል
ጥ የሆነ ንግግር በተረጋጋ ሁኔታ በማሰማት የተሰ
በሰበው ሕዝብ አንድ ሺህ ጭንቅላቶች እንደ አንድ
አካል ተጠጋግቶ በመቆም አስተዋይ የሆኑ ዐይኖቹ
የተተከሉበትን የፓቬልን ፊት አንጋጠው በመመልከት
ከአንደበቱ የሚያዥጎደጉዳቸው ቃላቶች ሲንቆረቆሩ
በጥሞና ይመለከቱት ነበር ። እንዲህም እያለ ፓቬል ን
ግግሩን ቀጠለ ፦
«እኛ ሁላችንም አንዳችን ለሌላኛችን ጓዶች መሆ
ናችንን እስካልተገነዘብን ድረስ ፤ ለመብታችን በመታገል
ለአንድ ዓላማ የተሣሠርን የጓደኛሞች ቤተሰብ መሆና
ችንን እስካልተገነዘብን ድረስ የተሻለ ዕድል-ፈንታ
ኖሮን ድል አድራጊዎች ልንሆን አንችልም ።» አንድ
እናት አጠገብ ቆሞ የነበረ ሰው ጎርነን ባለ ድምፅ ፦
«ወደ ዋናው ነጥብ ዝለቅ!» በማለት ተናገረ ። ከሁ
ለት የተለያዩ አቅጣጫዎች ደግሞ ፦
«ንግግር አታቋርጥ!» የሚሉ ድምፆች ተሰሙ ።
ጥላሸት የለበሱት የሰዎቹ መልኮች ጥርጣሬ በተ
መላበት መንፈስ ጭፍግግ ያላቸው ሲሆን ፤ የብዙዎቹ
ሰዎች ዐይኖች ግን የፓቬልን መልክ በአንክሮ ያስተ
ውላሉ ። ከመካከላቸው አንዱ ፦
«ሶሻሊስት ነው እንጂ ጅላንፎ አይደለም!» በማለ

ት አንክሮውን ገለጸ ። አንድ ቁመተ-ረዥምና አንድ-ዐይና ሠራተኛ ደግሞ እናትን ጎነጥ አደረገና ፡ —

«እንዲህ ነው እንጂ! ጎበዝ-ተናጋሪ አይደለምን?» በማለት ተናገረ ። ፓቬልም ንግግሩን በመቀጠል ፡ —

«ጓዶች ፤ ራሳችንን የምንረዳው ራሳችን እንጂ ሌላ ማንም ሊረዳን እንደማይችል መገንዘቢያ ጊዜያችን አሁን ነው ። ጠላቶቻችንን ድል ለመንሳት ከፈለግን የምንመራበት ሕግ ‘ሁሉም ሰዎች ለአንዱ ሰው ደህንነት ፤ አንዱ ሰውም ለሁሉም ሰዎች ደህንነት የሚለው መመርያ ሕጋችን መሆን አለበት » አለ ። ማኾቲንም የገዛ ራሱን እጅ ጨብጦ ወደሰማይ በማወዛወዝ ፡ —

«ወገኖቹ ሆይ ፤ የሚናገረው ሀቁን ነው!» በማለት ተናገረ ። ፓቬልም ንግግሩን በመቀጠል ፡ —

«ዲሬክተሩ ይጠራ!» በማለት ተናገረ ።

ድንገተኛ ደራሽ ነፋስ የተሰበሰቡትን ሰዎች መጥቶ የገረፋቸው ይመስል ሰዎቹ ነቅነቅ የማለት ምልክት ካሳዩ በኋላ ብዙ-አሥር ድምፆች የሚከተለውን በጩኸት አሰሙ ፡ —

«ዲሬክተሩ ይጠራ!»

«የመልዕክተኛ ጓድ ይላክበት!» የሚሉ ድምፆች ተሰሙ ።

እናት ፊቷ በኵራት ተመልቶ ልጅዋ ወደአለበት ቦታ ይበልጥ ቀርባ በመጠጋት ቀና ብላ ዐይን-ዐይኖቹን ትመለከት ጀመር ። የርሷ ፓቬል ከእነዚህ ከተከበሩ ሽማግሎች ሠራተኞች ጎን አብሮ የቆመ ሲሆን የሚናገረውንም ሁሉም ያዳምጠው የነበረ ከመሆኑም በስተቀር የሚያቀርባቸው አስተያየቶችም ተቀባይነት ነበራቸው ። ሌሎቹ እንደሚያደርጉት ቁጡ ባለመሆኑ እና ፀያፍ ቃላትን የማይሰነዝር በመሆኑ ምክንያት ተደስታለች ።



ክዳኑ ቆርቆሮ በሆነ ቤት ላይ እየተኾጎደጎደ እንደሚወርድ የበረዶ ዝናም ዛቻዎች ፤ ፉከራዎችና ስድቦች እየተኾጎደጎዱ ይወርዱ ጀመር ። ፓቬል የተሰበሰቡትን ሰዎች ወደታች ይመለከት የነበረ ሲሆን ትላልቅ ዐይኖቹን ለአንድነገር ፍለጋ የሚቃኝ ይመስላል ።

«የመልዕክት ጓዶች!»

«ሲዞቭ!»

«ቭላሶቭ!»

«ሪቢን! የርሱ ጥርሶች የተሳሉ ናቸው!»

ዝግ ያለ የመገረም አነጋገር ድንገት መሰማት ጀመረ ።

«ዲሬክተሩ በገዛ ራሱ ፍላጎት መምጣት ላይ ነው!»

«ዲሬክተሩ መጣ!...»

በረዥም ቁመቱ ላይ ኾርግግ ብሎ የወረደ ጢም ላለው እና ፊተ-ረጅም ለሆነው ሰው ተሰብስቦ የነበረው ሁሉ የሚያልፍበትን መንገድ ይለቅለት ጀመር ።

በእጁ ሠራተኞቹን ላለመንካት በመሻት አኳኋን «እስኪ አሳልፉኝ» እያለ እና ገፉ-ገፉ እያደረጋቸው መንገዱን በተሰበሰቡት መሀል ሄደ ። ዐይኖቹን ጠበብ አድርጎ በመዝጋት ሁኔታ እልቅና ያላቸው ባለሥልጣኖች በሚያደርጉት የአመለካከት ሁኔታ የተሰበሰቡትን ሠራተኞች ከፍ-ዝቅ እያደረገ በዐይኖቹ ይቃኛቸዋል ። በዚያ የነበሩት ሰዎች ቆቦቻቸውን እያወለቁ እጅ ነሱ ። እርሱ ግን ላቀረቡለት ሰላምታ አፀፋውን ሳይመልስ ጉዞውን የቀጠለ ሲሆን ፤ ይኸ አድራጎቱም በሰዎቹ መሃል ዝምታ እና ግራ መጋባት እንዲፈጠር አደረገ ። በሃፍረት መንፈስ ፈገግ በማለት ጥፋት አጥፍተው የተገኙ ሕፃናት አጥፍተናል በሚል መልክ

የቀስታ አነጋገር እንደሚያቀርቡት ያለ ሁኔታ እንዲ ታይባቸው አደረጋቸው ።

ዐይኖቹን ጎረጥ አድርጎ የእናትን ፊት እየተመለከ ተ አልፏት ከሄደ በኋላ የብረት ክምር ካለበት ፊ ት-ለፊት ቆመ ። ከነበሩት ሰዎች መካከል አንዱ ሊደ ግፈው ፈልጎ ነበር ፤ እርሱ ግን ከቁም ነገርም ሳያገባ ው ቀረ ። ደህና አድርጎ ሰውነቱን ነቅነቅ በማድረግ የብረቱ ክምር ላይ ከወጣ በኋላ ፓቬል እና ሲዞቭ ከቆሙበት ፊት ለፊት ሂዶ ቆመ ።

«የሚካሄደው ስብሰባ ምንድነው? ሥራ መሥራታ ችሁን ያቆማችሁትስ ለምንድነው?» በማለት ጠየቀ ።

ለጥቂት ስኮንዶች በቦታው ላይ ፀጥታ ሰፈነ ። በ ዚያ የነበሩት ሰዎች ጭንቅላቶች እንደ ስንዴ እሸ ት ዛላ አንገቶቻቸው ቁልቁል ዝንብል ብለው ተደፉ ።

ሲዞቭ ቆቡን አንስቶ ከወዲያ ወዲህ በማንቃንቅ ትከሻውን ወዘወዝ ካደረገ በኋላ አንገቱን ደፋ ።

«ጥያቄዬን መልሱልኝ እንጂ!» በማለት ዲሬክተሩ ጮኸ ።

ፓቬል ወደዲሬክተሩ ቀረብ አለና ሲዞቭ እና ሪቢን ላይ ጣቱን እየቀሰረ ድምፁን ከፍ አድርጎ በማሰማት ፦

«ተቆራጭ ይሆናሉ ስለተባሉት ኮፔኮች የወጣው ትዕዛዝ እንዲፋቅ እኛ ሦስታችን በጓዶቻችን መልዕ ክተኞች ሁነን ተመርጠናል» በማለት ተናገረ ።

«ለምን?» በማለት ዲሬክተሩ ፓቬልን ሳይመለከት ጥያቄውን አቀረበ ።

«ምክንያቱም ይኸንን የመሰለው ተቆራጭ ገንዘብ ተገቢ ያልሆነ ነው ብለን ስለምንገምት ነው» በማለት ፓቬል ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ።

«ረግረጉን መሬት ለማድረቅ ያለኝ ፍላጎት የሠ ርቶ-አደሮችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል እንጂ እነርሱን



ለመበዝበዝ አቅጂ ነው ብለህ ታስባለህን? እኮ ለዚህ ብዬ ነውን?»

«አዎን!» በማለት ፓቬል መለሰ ።

«አንተም ነው ብለህ ታስባለህን?» በማለት ፊቱን ወደ ሪቢን መለስ አድርጎ ዲሬክተሩ ሪቢንን ጠየቀ ው ።

«ሁላችንም ነው ብለን እናስባለን» በማለት ሪቢን መለሰ ።

«አንተም ደህናው ሰው እንደዚህ ታስባለህን?» በማለት ወደ ሲዞቭ ዞር ብሎ ጠየቀ ።

«እኔም ነው ብዬ አስባለሁኝ ። ኮፔካችንን ላለማ ጣት እንሻለን» በማለት ሲዞቭ መለሰ ።

ሲዞቭ እንደገና አንገቱን ወደታች ደፋ አድርጎ በጥፋተኛ ሰው አሳሳቅ ፈገግ አለ ።

ዲሬክተሩ የተሰበሰቡትን ሰዎች በዐይኖቹ ገረፍ አደረገና ትከሻዎቹን አነቃነቀ ። ከዚያም ፊቱን ወደ ፓቬል መለስ አድርጎ አተኩሮ ይመለከተው ጀመር ። እንዲህም በማለት ተናገረው ፦

«በመጠኑ ትምህርት የተማርክ ሰው ትመስላ ለህ ። እንዲህ ዓይነት እርምጃ መወሰዱ ጠቀሜታ የ ሚያስገኝ መሆኑን አንተም አትገነዘበውምን?»

«ፋብሪካው በገዛራሱ ወጪ ረግረጋማውን መሬት ቢያደርቀው ሊያስገኝለት የሚችለውን ጠቀሜታ ማን ም ይገነዘበዋል» በማለት የተሰበሰበው ሁሉ እንዲሰማ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ።

ዲሬክተሩም ድርቅ ባለ አነጋገር ፦

«ፋብሪካው የበጎ አድራጎት ድርጅት አይደለም ። ወደሥራ ቦታችሁ እንድትመለሱ አዝዣለሁኝ!» በማለት ተናገረ ።

ማንንም ሳይመለከት የብረቱን ክምር በጥንቃቄ እያስተዋለ ወደ ምድር ወረደ ።

የተሰበሰቡት ሰዎች በትዕዛዙ አለመርካት የጉርምርምታ ድምፅ አሰሙ ። ከዚያም ዲሬክተሩ እነበረበት ቦታ ላይ ሳይንቀሳቀስ በመቆም ፡ —

«ምንድነው?» በማለት ጠየቀ ።

«በኛ ቦታ አንተ ሂድና ሥራ!..» የሚል ድምፅ ራቅ ካለ ቦታ በመሰማት ሠፍኖ የነበረውን ፀጥታ አደፈረሰው ። ከዚያም ዲሬክተሩ ንግግሩን ጠንክር አድርጎ ፡ —

«በአሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ ወደሥራ ቦታችሁ ባትመለሱ ሁላችሁም ላይ ቅጣት እንዲፈጸም ትዕዛዝ አስተላልፋለሁኝ» አለ ።

እንደገና ጉዞውን በተሰበሰቡት ሰዎች መካከል ቀጠለ ። ይሁን እንጂ ጉዞውን መቀጠል እንደጀመረ ጉርምርምታ የቀጠለ ሲሆን ፤ ዲሬክተሩ ከተሰበሰቡት ሰዎች ዘንድ እየራቀ በሄደ ቁጥር የጉርምርምታውም ድምፅ የዚያኑ ያህል ከፍ ይል ጀመር ።

«አነጋግሩት እንጂ!»

«የእኛ ፍትሕ እስከዚህ ድረስ ነው! አይ ኑሮ!»

ወደ ፓቬል ዞር በማለት የተሰበሰቡት ሰዎች እንዲህ ሲሉ ጠየቁት ፡ —

«ፕሮፌሰር ፤ አሁን ደግሞ ማድረግ ያለብን ምንድነው?»

«ያሰማኸው ንግግር ጥሩ ነበር ። ይሁን እንጂ ዲሬክተሩ ብቅ ሲል ሁሉም ነገር አበቃ!»

የሚሠነዘረው አስተያየት ይበልጥ እየጠነከረ ሲሄድ ፓቬል የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«ጓዶች ፤ ኮፔኮቹን መቁረጡን የሚያቆም መሆኑን ቃል እስኪገባልን ድረስ ሥራ መሥራት እንድናቆም አሳስባለሁኝ...»

እርሱ ባቀረበው በዚህ አስተያየት ላይ የሚሠነዘረው የአስተያየት መልስ በረታ ፡ —



«ምንም የማያውቁ ጅሎች አድርገኸናል እንዴ!»

«ይኸማ የሥራ ማቆም አድማ ማለት ነው!»

«እዚህ ግቡ ለማይባሉ ኮፔኮች!»

«የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ ምን አለበት?»

«ሁላችንም እንባረራለን!»

«ብንባረር ሥራውን ማን ያንቀሳቅስለታል?»

«ፈቃደኛ የሆኑ አያሌ ሰዎች ያገኛል!»

«እንደ ይሁዳ ከዳተኞች የሆኑትን ማለትህ ነውን?»

## 13

ፓቬል ከብረቱ ክምር ላይ ወርዶ እናቱ አጠገብ ቆመ ።

ተሰብስበው የነበሩት ሠራተኞች የመነሳሳት ሁኔታ ያሳዩ ጀመር ። ሁሉም ስሜት ብተመላበት ሁኔታ እርስ በርሱ ይከራከርና ይጯጯህ ጀመር ።

ሪቢን ወደ ፓቬል ዘንድ መጣና ፡ —

«ሥራ የማቆም አድማ እንዲመቱ ልታደርጋቸው አትችልም ። ስግብግቦች ብቻ ሳይሆኑ ፈሪዎችም ጭምር ናቸው! ድጋፍ የሚሰጡህ ሦስት መቶ ያህል ወዝ-አደሮች ቢሆኑ ነው ። የፍጉ ክምር ትልቅ ቁልል ስለሆነ በአንድ አካፋ አንድ ጊዜ ዝቀህ የምትጨርሰው አይደለም...»

ፓቬል ዝም አለ ። በዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ ቅር የተሰኙ ፊቶች እኮ ምን እናድርግ በሚል ስሜት ዐይን-ዐይኖቹን ይመለከቱታል ። ልቡ በተጠንቀቅ ይመታ ጀመር ። በተራበ ደረቅ መሬት ላይ የወረደ የዝናብ ጠብታ አንዳችም ምልክት ሳይተው እንደሚያልፍ ሁሉ ፤ ያሰማቸው ንግግሮችም አንዳችም ውጤት ሳያስገኙ ባክነው የቀሩ መስሎ ተሰማው ።

ደክሞትና ቅር ብሎት ወደቤቱ ተመለሰ ። እናቱ

እና ሲዞቭ ኋላ-ኋላው ይከተሉት የነበረ ሲሆን ሪቢ
ን ደግሞ በጆሮው የሚከተለውን አስተያየቱን እያንሾ
ኳሾከለት ጎን ጎኑ ይራመዳል ፡ —

«ጥሩ ትናገራለህ ። ንግግርህ ግን ልብ የሚነካ
አይደለም! እዚህ ላይ ነው ጉዳዩ! የሃሣብህን ብልጭታ
ልባቸው ውስጥ መሃል ቦታ ላይ አቀጣጥለህ ልባ
ቸውን በሚነካ ሁኔታ መናገር አለብህ ። ምክንያት አቅ
ርበህ በመከራከር ሰዎችን በሃሣብህ ልታሳምናቸው
አትችልም ። የአባባልህ መጫሚያው ለእግራቸው ተመ
ጣጣኝ አይደለም ። ይጠብባቸዋል ፤ እግራቸውን ይይዘ
ዋል!»

ሲዞቭም የሚከተለውን ሃሣብ ለእናት አቀረበ ፡ —

«ፔላጊያ ፤ እኛ በእድሜ የገፋነው ሰዎች ወደ
መቃብር ቤታችን መተላለፍያ ጊዜያችን ነው ። አዲስ
ዓይነት ሰው ብቅ እያለ ነው ። እርስዎ እና እኔ የኖ
ርነው ኑሮ ምንድነው? ከእኛ በላይ ለሆኑት በጉልበ
ታችን ተንበርክከን እየተንፏቀቅን ፤ አንገታችን ቅንጥ
ስ እስኪል በማጎብደድ መሬት ድረስ ወርደን እጅ
እየነሳን ኖርን ። አሁን ያለንበት ጊዜ ግን ተለውጦ
አል ። ምናልባት ሰዎች ዝግ ብለው ሁኔታዎችን ማሰ
ላሰል ስለጀመሩ ይሆናል ። ምናልባትም ደግሞ ከእኛ
የከፋ ስሕተት እየፈጸሙ ይሆናል ። ብቻ ግን ፤ አድራጎ
ታቸው እንደእኛ አይደለም ። ወጣቶቹን እንደምሳሌ
አድርገው ይውሰዷቸው ። ከዲሬክተሩ ጋር ሲነጋገሩ
ልክ እንደአቻቸው ቆጥረውት ነው... እሺ እንግዲህ
ወደ በኋላ ጊዜ ብቅ ብዬ አያችኋለሁኝ ፓቬል ሚ
ኻይሎቭ ። ወጣቱ ሰው ፤ ለሰዎች ስትል የወሰድከው
አቋም ጥሩ ነው ። እግዚአብሄር ካንተ ጋር ይሁን ።
ምናልባትም መግቢያ-መውጫ መንገዱን ፈልገህ
ታገኝ ይሆናል ። እግዚአብሔር ይባርክህ!» በማለት ሲ
ዞቭ ተናገረ ።



ትቷቸውም መንገዱን ሄደ ።

ሪቢንም ንግግሩን ቀጠል አድርጎ በማጉረምረም
መልክ ፡ —

«እርስዎም ሂዱና ሙቱ! እንደርስዎ የመሳሰሉት
ሰብአውያን ፍጡሮች እንኳን አይደሉም ። የሙጫ
መጣብቆች ናቸው ። የተሰነጣጠቀውን ለመጠጋገን የሚ
ሹ ናቸው ። ፓቬል ፤ አንተ የመልዕክተኛ ጓድ እንድት
ሆን ማን እንደጮኸ አስተዋልከውን? አንተን ሶሻሊስ
ት እና ረብሻ-ፈጣሪ ነህ እያሉ የሚቀጽሉህ ናቸው!
እነርሱ ናቸው! አንተ የመልዕክተኛ ጓድ እንድትሆን
በሚሹበት ጊዜ የሚከተለውን ዓይነት ሃሣብ ከራሳ
ቸው ጋር ይወያያሉ ፡ —

«ከሥራው ይባረራል — ይኸ ደግሞ ለርሱ ይገባ
ዋል!»

«ከእነርሱ አመለካከት አንጻር ሲታይ ያደረጉት
ትክክል ነው» በማለት ፓቬል ተናገረ ።

«ተኩላዎችም ወንድሞቻቸውን ብጭቅጭቅ አድር
ገው ሲከታትፏቸው ትክክል ናቸው...» በማለት ሪ
ቢን መለሰ ።

ሪቢን ፊቱን ጭፍግግ ብሎት የነበረ ሲሆን ድም
ፁም ስልቱን የሳተ ለመሆኑ ያስታውቃል ።

«ሰዎች ባዶ ቃላትን ብቻ አያዳምጡም ። መሰቃ
የት አለባቸው ። ቃላቶችህን ደም ውስጥ መንከር
አለባቸው...»

አንዳች ነገር የሚቃኙ የመሰሉት ዐይኖቹ በትኩሳ
ት ጋይተውበት ቀኑን ሙሉ ድክም ብሎት ፤ አዝኖና
ከዚህ ቀደም ሁኖ በማያውቀውም ሁኔታ ታውኮ
ፓቬል ቀኑን ሙሉ ከወዲያ-ወዲህ ሲንጎራደድ ዋለ ።
እናት ይኸንን ሁኔታ አስተውላለች ።

«ምነው ምን ሁነሃል ፤ ፓሻ?» በማለት ጠየቀችው ።

«ራስ ምታት አሞኛል» በማለት መለሰላት ።

«ጋደም በል ። ሃኪም እጠራለሁኝ...» አለችው ።

«የለም ግዴለም አትጨነቂ» በማለት ፈጥኖ መለሰላት ። ከዚያም ቀስ ብሎ በማነብነብ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«እኔ እጅግ ወጣት እና ደካማ ነኝ ። ችግሩ እዚህ ላይ ነው! እኔን አላመኑኝም ፤ እኔ ለቆምኩለት ዕውነት ሊቆሙ አልፈቀዱም ። ይኸም ማለት የቆምኩለትን ዕውነት በሚገባ ማብራራት አልቻልኩኝም ማለት ነው!.. ይኸ ለእኔ ጥሩ አይደለም ። በራሴው ሁኔታ አዝኛለሁኝ!»

በትካዜ የተዋጠውን ፊቱን ተመለከተችና ልታጽናናው ፈለገች ። የሚከተለውን ተናገረች ፡ —

«ትንሽ ታገስ! ዛሬ ያልተገነዘቡትን ጉዳይ ነገ ይገነዘቡታል...»

«መገንዘብ አለባቸው!» በማለት አጠንክሮ ተናገረ ።

«እኔ እንኳን ትክክል መሆንክን እገነዘባለሁኝ ።» በማለት እናት ተናገረች ።

ፓቬልም ወደርሷ መለስ አለና ፡ —

«እናት ፤ አንቺ ግሩም-ድንቅ የሆንሽ ነሽ!» አላት ። ከዚያም እንደገና መለስ ብሎ ዞረ ። ረጋ ያሉት ቃላቶቹ የቀሰቀሷት ይመስል በረገገች ፤ ከዚያም የእርሱን ልስላሴ በማስተዋል ልቧን በእጅዋ ይዛ በመደገፍ ከነበረበት ቦታ ትታው ሄደች ።

በዚያን ምሽት እናት ከተኛች ትንሽ ቆየት ብሎ ፤ ፓቬል አልጋው ላይ ጋደም ብሎ መጽሐፍ ሲያነብብ ፖሊሶች መጥተው ቁጣ በተመላበት ሁኔታ በቤቱ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ በመዘዋወር ዕቃዎችን በፍተሻ በማተማረስ ከቤቱ ጣራ በታች ያሉትን ትንንሽ ማጀቶች እና የጓሮ እርሻውን ጭምር ይፈትሹ ጀመር ። መልከ-ቢጫማ የሆነው መኮንን ቀደም ባለው ጊዜ አድርጎት እንደነበረው ሁሉ ፤ ይሁነኝ ተብሎ ልግጫ



በተመላበት ሁኔታ በማሾፍ ይበረብራል ። እናት ዐይኖቿን ከልጅዋ ላይ ሳትነቅል ከአንድ ጥግ በኩል በፀጥታ ቁጭ ብላለች ። ፓቬል ስሜቱን ለመቆጣጠር ይሞክር የነበረ ሲሆን ፤ መኮንኑ በሳቀ ጊዜ ግን እጣቶቹ ከፉኛ በብስጭት ይንቃነቁ ጀመር ። ፖሊሱ ፌዙን በቀጠለበት ጊዜ ዝም ማለቱ ለምን እንደሆነ እናት ተገንዝባለች ። በመጀመርያ ጊዜ ደርሶባት እንደነበረው ዓይነት ፤ በአሁኑ ጊዜ ሁኔታው እርሷን ይኸንንም ያህል የሚያስፈራራት አልነበረም ። ለእነዚህ ግራጫ ለሆኑ የሌሊት ወፎች መሳይ የሌሊት ጎብኝዎች ያላት ጥላቻ ከፍ-ከፍ እያለ የሄደ ሲሆን ፤ ይኸ ጥላቻዋም ፍራቻዋን ውጦላታል ።

«ይዘውኝ ይሄዳሉ» በማለት ፓቬል ቀስ ብሎ ነገራት ።

«አውቃለሁኝ» በማለት በዝግታ መልስ እናት ራሷን በአዎንታ ነቀነቀች ።

ማለዳው ላይ ተሰብስበው ለነበሩት ሠርቶ-አደሮች ባሰማው ንግግር ምክንያት እሥር ቤት እንደሚጨምሩት ተገንዝባለች ። ይሁን እንጂ ፤ ፓቬል ያሰማውን ንግግር ሁሉም ተስማምቶበት ስለነበረ ፤ እርሱን በመደገፍ መነሳሳታቸው እንደማይቀር ርግጥ ጉዳይ ነበር ። እርሱን ለረዥም ጊዜያት አሥረው ሊያቆዩት አይችለም ማለት ነው...

እጆቿን ልጅዋ ላይ ጥላ ለማልቀስ ከጀላት ። ይሁን እንጂ መኮንኑ ጩልጨል በሆኑት ዓይኖቹ እየቃኘት አጠገቧ ቆሞ ነበር ። የዚህ መኮንን ከናፍሮች ክፍት ክፍት እያሉና ሪዙም ነቅነቅ ነቅነቅ እያለ ስለነበር ፤ የእርሷን ማልቀስ በጥድፊያ የሚጠባበቅና የምትናገረውን ለመስማት ያሰፈሰፈ መስሎ ለፔላጊያ ታያት ። ያለ-የሌለ አቅሟን እንደምንም ብላ ካጠራቀመች በኋላ የልጅዋን እጅ ጠበቅ አድርጋ በመጨበጥ በዝግታ

ና ለስለስ ባለ አነጋገር ቀስ ብላ የሚከተለውን ተ ናገረች ፡ —

«ደህና ሁን ፓሻ ። የሚያስፈልጉህን ነገሮች ሁሉ ይዘሃልን?»

«አዎን ። አትዘኚ ።»

«እግዚአብሔር ካንተ ጋር ይሁን...»

ይዘውት ከሄዱ በኋላ አግዳሚ ወንበሯ ላይ ተቀ ምጣ በዝግታ ለቅሶዋን ቀጠለች ። ባሏ ይቀመጥ እን ደነበረው ዓይነት አቀማመጥ ጀርባዋን ለግድግዳው ሰጥታ በሀዘን ተቆራምዳ ረዳት-አልባ መሆኗም ተሰ ምቷት ኩርምት ብላ ተቀመጠች ። ራሷን ወደታች ቀለስ በማድረግ በሀዘን ከቆሰለው ልቧ የሚፈልቀው የሰቀቀን ሕመም እየተሰማት ረዘም ላለ ጊዜ ድምፅ ሳታሰማ በሀዘን እየተንሰቀሰቀች እንባዋን ታነባው ጀ መር ። በሃሣቧ ውስጥ ደግሞ ልቅም ያለ ሪዝ ያለው ያ መልከ — ቢጫ ሰው በደስታ መንፈስ ተመልቶ ይታያት ነበር ። ልጁ ፍትህን በመሻቱ ምክንያት ብ ቻ ከእናት ለሚነጥሉት ለእነዚያ ሰዎች ልቧ የምሬ ት እና የጥላቻ ደመናን ቋጠረ ።

ምሽቱ ቀዝቃዛ ሲሆን ፤ የዝናሙም ቸፈቸፍ መስኮቱ ን ይመታው ነበር ። ዐይን የሌላቸውና ባለ ረዣዥም እጅ የሆኑ ቀያይ ግራጫ መልኮች ከብረት የተሠራ መኮርኮርያ ያለበት ተጫምተው እና እንደ ዘበኛ የቤቷን ዙርያ ከበው በቀስታ የሚራመዱ መስሎ ተሰማት ።

«ምነው እኔንም በወሰዱኝ ኖሮ!» ብላ አሰበች ።

ሠራተኞችን ለሥራ የሚጠራው የፋብሪካ ጡሩም ባ የጩኸት ድምፁን አሰማ ። ይህ የፋብሪካው ጡ ሩምባ ያሰማው የዛሬ ጧቱ ድምፁ ዝቅተኛና ሙሉ በሙሉ ያልተጣራ ድምፁ ነበር ። በሩ ተከፈተና ሪቢ ን ወደቤት ገባ ።



«ወሰዱት እንዴ?» በማለት ከጺሙ ላይ የዝናሙ ን ወሃ እየጠራረገ ጠየቀ ።

«አዎን ወሰዱት ። እነዚህ እርጉሞች!» በማለት ጫ ን ተንፍሳ ተናገረች ።

«የተጠባበቀው ጉዳይ መሆን አለበት» በማለት ፈገ ግ ብሎ ተናገረ ። ከዚያም ንግግሩን በመቀጠል ፡ —

«የእኔንም ቤት ፈተሹ ። ያለ-የሌለውን ሁሉ አገላ ብጠው ተመለከቱ ። ብዙ ተሳደቡ ፤ ግን እዚህ ግቡ የሚሏቸው አይደሉም ። እና ፓቬልን ወሰዱት ማለት ነው? ዲሬክተሩ በዓይኖቹ ለትዕዛዝ ሲጠቅስ ፤ ፖሊሱ ራሱን በእሺታ ያወዛውዛል ። እና አሁንም አንድ ሌላ ሰው ወደ እሥር ቤት ወሰዱ ማለት ነው! በአንድነት መሥራት መልካም ነው ። አንዱ ላም የሆኑ ሠርቶ-አ ደሮችን ቀንዶች ገትሮ ሲይዝ ሌላው ደግሞ ተሟጥጠ ው እስኪያልቁ ያልባቸዋል ማለት ነው...» በማለት ተናገረ ።

«ፓቬልን መደገፍ አለብህ! የፈጸመው ተግባር ለሁ ሉም በማሰብ ነው!» በማለት እናት ድምጿን ከፍ አድርጋ አሰማች ።

«ማነው መደገፍ ያለበት?» በማለት ሪቢን ጠየቃት ።

«ማንም ቢሆን!» በማለት እናት መለሰችለት ።

«አሂሂ! እንዲህ ነው የምታስቢው ማለት ነው? ይኽ ግን የሚሆን ነገር አይደለም!» በማለት ሪቢን መለሰ ።

ፈገግታ በተመላበት ሁኔታ ከቤት ወጣ ። ተስፋ-ቢ ስ የሆኑት ቃላቶቹም እናትን ይበልጡኑ ሀዘንተኛ አደረጓት ።

«ቢወግሩት ፤ ቢያሰቃዩት ታዲያ ምንድነው?..» ብ ሏት ነበር ።

ልጅዋ ከተደበደበ በኋላ ሰውነቱ ሰምበር በማውጣ

ት ጓጉሎና በደም ተለውሶ ለሃሣቧ የታያት ሲሆን ፤
ይኸንን መሳዩ ግምቷም ከባድ ፍርሃት አሳደረባት ።
በዚያን ዕለት ምድጃውን አላቀጣጠለችውም ። ምሳ
ዋን አልበላችም ። ሻይ እንኳን አልጠጣችም ።
ምሽት ሲሆን ቁራሽ ዳቦ በላች ። ያንን ምሽት
ወደ አልጋዋ ሂዳ በተኛች ጊዜ ሕይወት እንደዚህ
ምሽት ባዶ እና ብቸኛ አድርጓት አያውቅም ።
በእነዚህ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ጥሩ እና
ጠቀሜታ ያላቸውን ጉዳዮች መምጣት በማያሰልስ
ሁኔታ በመጠባበቅ መቆየትን ተላምዳ ነበር ። ለዚያ
በጎ ቢሆንም አደገኛ ለሆነ አኗኗር ኃላፊነት የነበ
ረው በጥሞና የተመላ የልጅዋ መልክ ሁል ጊዜም
ከርሷ ፊት ሁኖ ይታይ በነበረበት ደስተኛ በሆነና
ሁካታ በተመላበት የወጣቶች ተግባር ተከብባ ነበር ።
አሁን ግን እርሱ ልጅዋ ወደ እሥር ቤት ሲወሰድ
ሁሉም ነገር ከእርሱ ጋር አብሮ አከተመ ።

## 14

አይነጋ የለም ፤ ነጋ ። ሌሊቱም ያለ አንዳች የእንቅ
ልፍ ሽልብታ አለፈ ። ይባስ ብሎ ደግሞ የሚቀጥለው
ቀን ከርሱ በፊት ከነበሩት ቀናት እና ሌሊቶች በከ
ፋ ሁኔታ እየተጎተተ አላልፍ አላት ። ድንገት ጠያቂ
ሰው ይመጣ ይሆናል ብላ ተጠባበቀች ። ማንም ብቅ
ያለ አልነበረም ። መሸ ። ጨለማም ሆነ ። የቀዝቃዛ ዓየር
ዶፍ ዝናም ግድግዳውን ሹ-ር-ር እያለ ይዶፍበት ጀ
መር ። ነፋሱ በማዕድ ቤቱ ጭስ መውጫ በኩል እያ
ቆለቆለ የሚያፏጭ ሲሆን ፤ አንድ ነገር ከወለሉ በታ
ች ድምፅ ያሰማል ። ቤቱ በማፍሰሱ ምክንያት ከቤቱ
ጣርያ ላይ የውሀ ጠብታዎች ጠብ-ጠብ ይላሉ ። ጠብ



ታዎቹ ወለሉ ላይ ደርሰው ጠብ-ጠብ ሲሉ የሚያሰ
ሙት ድምፅ የግድግዳው ሰአት መቂናጥ ቋ-ቋ ሲል
ከሚያሰማው ድምፅ ጋር ተዋህደው ለጆሮ የሚከብድ
አንዳች ዓይነት ቀፋፊ ድምፅ ነው ። ቀስ-በቀስ ቤቱ
በሙሉ ከወዲያ-ወዲህ የሚያዘምም መሰለ ። ሀዘን ማና
ቸውንም ነገር በድን እና ፍሬ-ቢስ አስመሰለው…
በስተመስኮቱ አንድ ጊዜ ተንኳኳ ። ከዚያም እንደ
ገና ደገመና ተንኳኳ ። እነዚህን የመሳሰሉትን የመስኮ
ት ኳኳታዎች ለምዳቸው ነበርና አላስፈራሩዋትም ። ይ
ኸን, ጊዜ ግን ትንሽ የደስታ ስሜት አደረባት ። ባዶ
ተስፋ ከተቀመጠችበት ብድግ አድርጎ እንድትቆም
አደረጋት ። ያንገት ልብሷን ከትከሻዋ ላይ ጣል አደ
ረገችና በሩን ከፈተች ።
ሳሞይሎቭ ወደ ቤት ገባ ። ከርሱም ጋር አብሮት
አንድ ሰው የመጣ ሲሆን የካፖርቱን ክሳድ ወደ
ላይ ዘርግቶ እና ቆቡንም ፊቱን በሚሸፍን ሁኔታ
ዝቅ አድርጎ ደፍቶት የነበረ ስለሆነ ማንነቱን ለመለ
የት አይቻልም ።
«ከእንቅልፍዎ ቀሰቀስንዎ እንዴ?» በማለት የጤና
ይስጥልኝ እንደምንድነዎት ሰላምታ ሳያቀርብ ተናገረ ።
ሳሞይሎቭ ቀድሞ ካለው ጠባዩ ጋር የአሁኑ ሁኔታ
ው ሲነጻጸር እንደጨነቀውና እንደከፋው ከአነጋገሩ
እና ከድምፁ ይታወቃል ።
«አልተኛሁም ነበር ።» በማለት እናት ከመለሰች
በኋላ ዐይኖቿን እነርሱ ላይ ጣል አድርጋ የሚሉትን
ለመስማት ትጠባበቅ ጀመር ።
የሳሞይሎቭ ባልደረባ ጫን ትንፋሹን ረዘም አድ
ርጎ ከተነፈሰ በኋላ በአጭር እና በደንዳና ክንዱ
ላይ የሚገኙትን አጫጭር ጣቶቹን ዘርግቶ ረዘም
ካለ ጊዜ አንስቶ እንደሚተዋወቁ ያህል በወዳጅነት
መንፈስ ለእናት የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«ጤና ይስጥልኝ ፤ እናት! አያስታውሱኝምን? ዘነጉኝ እንዴ?»

«ኧረገኝ ፤ አንተ ነህ እንዴ? የጎር ኢቫኖቪች ነህ እንዴ?»

«አዎን ፤ እኔው ነኝ!» በማለት እንደ ሃዋርያዊ መልዕክተኛ እስከ ትከሻው ተንዠርጎ በወረደ ፀጉሩ የተሸፈነውን ትልቅ ጭንቅላቱን ዝቅ አድርጎ እጅ በመንሳት ተናገረ ። ፊቱ ላይ ፈገግታ ይታይበት የነበረ ሲሆን ትንንሽ የሆኑት ግራጫ ዐይኖቹም በደግነት አስተያየት እናትን ይመለከታሉ ። ሁለንተናው የሻይ ማፍያ ሳሞቫር ይመስል ድብልብል ያለ ዶጮ ነው ። አጭር እና ወፍራም ሲሆን አንገተ-ደንዳናና አጫጭር ክንዶች አሉት ። ፊቱ ፈካ ያለ ፤ ከደረቱ ውስጥ አንዳች ኩ-ር-ር የሚል ድምፅ እየተሰማ ረዘም ያለና ጉልሕ የሆነ አተነፋፈስ ተነፈሰ ።

«ልብሴን እስክለብስ ድረስ እሌላኛው ክፍል ግቡ» በማለት እናት ተናገረች ።

«የምንጠይቅዎት ጉዳይ አለን» በማለት ሳሞይሎቭ በዐይኖቹ አተኩሮ እየተመለከተ እናትን ተናገራት ።

የጎር ኢቫኖቪች ወደሌላኛው ክፍል ሂዶ ከዚያ ሁኖ መናገሩን ቀጠለ ። እንዲህ በማለትም ንግግሩን ጀመረ ፡ —

«እናት ፤ ዛሬ ጧት ኒኮላይ ኢቫኖቪች ከእሥር ቤት ተለቀቀ ።»

«መታሠሩን አላወቅሁኝም ነበር» በማለት እናት መለሰች ።

«ለሁለት ወር ከአሥራ አንድ ቀን ታሥሮ ነበር ። ኾኾልንም እዚያው እሥር ቤት ውስጥ አግኝቶት ነበር ። ለእርስዎ ሰላምታ እንዲያደርስ ጠይቆታል ። ፓቬልም ሰላምታውን አቅርቦልዎታል ። እንዳያስቡ እንዳይሰጉ ብሎዎታል ። ልጅዎ ፓቬል የመረጠውን የሕይ



ወት ጉዞ ምርጫ የመረጠ ማንኛውም ሰው ቢሆን በእሥር ቤት ውስጥ ጊዜያዊ የዕረፍት ጊዜ እንዲያሳልፍ የሚደረግ መሆኑ እርግጠኛ የሆነ ጉዳይ መሆኑን እንዲገነዘቡት ፓቬል ይሻል ። ይኸ የዕረፍት ጊዜን በእሥር ቤት የማሳለፍ ጉዳይ ከእኛ ባለሥልጣኖች በሙሉ ዋስትና የተሰጠ ነው ። እና እናት ሆይ ወደ ዋናው ቁም-ነገር ልመለስ ። ትላንትና ምን ያህል ሰዎች ተይዘው እንደታሠሩ ያውቃሉን?»

«እንዴት ፤ ከፓቬል በስተቀር ሌሎችም ተይዘው ታሥረዋል እንዴ?» በማለት እናት በአንክሮ ጠየቀች ።

«ፓቬል ከታሠሩት መካከል አርባ ዘጠኝኛው ሰው ነበር ።» በማለት የጎር ኢቫኖቪች ዝግ ብሎ መለሰላት ። ከዚያም ቀጠል በማድረግ ፡ —

«የፋብሪካው አስተዳደር አሁንም ገና ብዙ ሰዎችን ሳያሣሥር አይቀርም ። ለምሳሌ ይኸም ሰው መታሠሩ አይቀርለትም ይሆናል» በማለት ተናገረ ፡ —

«አዎን ፤ እኔም ተይዤ እታሠር ይሆናል» በማለት ሳሞይሎቭ ከፍቶት ተናገረ ።

ፔላጊያ ሃሣቧ ከፈል ያለ መስሎ ተሰማት ። የእፎይታ ትንፋሽም ተነፈሰች ።

«ሌሎችም አብረውት አሉ ። ልጄ ብቻውን አይደለም» የሚል ሃሣብ በአዕምሮዋ ውስጥ ተመላለሰ ።

ልብሷን ከለበሰች በኋላ የደስተኛ ፈገግታ በማሳየት እንግዶቿ ወደአሉበት ክፍል ሂዳ ተቀላቀለች ።

«ይኸንን ያህል ብዙ ሰው ካሠሩ ለረዥም ጊዜ ይዘው የሚያቆዩዋቸው አይመስለኝም...» አለች ።

«አዎን አያቆዩዋቸውም! ይኸንን መሰል ተግባራቸውን ብናበላሽባቸው ጭራዎቻቸውን ከእግሮቻቸው መካከል ቀስረው እየቆሉ ያፈገፍጋሉ ። አንዱ መደረግ ያለበት ቁም-ነገር የሚከተለው ነው — የሚበተኑት ጽሁፎቻችን በፋብሪካው ውስጥ መሠራጨታቸው ከቆ

መ ፤ ይህ የሆነበት ምክንያት ፓቬል እና ጓዶቹ እሥ
ር ቤት በመያዛቸው ምክንያት ነው በማለት ፖሊሶ
ች መደምደምያ ለማበጀት እና እነርሱንም እሥር
ቤት በባርነት ጭቆና ለማሰቃየት ይመቻቸዋል» በማ
ለት የጎር ኢቫኖቪች ተናገረ ።

«እንዴት? ምን ማለትህ ነው?» በማለት እናት በማ
ሰላሰል ሁኔታ ድምጿን አጉልታ ተናገረች ። የጎር
ኢቫኖቪችም ዝግ ባለና በረጋ አነጋገር የሚከተለውን
መለሰ ፡ —

«ጉዳዩ ቀላል ነው ። አንዳንድ ጊዜ ፖሊሶች እን
ኳን ሳይቀሩ ማመዛዘን ይችላሉ ። እስኪ እርስዎ ራስ
ዎ ያስቡት ፡ — ፓቬል እሥር ቤት ሳይገባ ነፃ በነበ
ረበት ጊዜ የሚበተኑ ጋዜጦች ነበሩ ። አሁን ፓቬል
በታሠረበት ጊዜ ግን ጋዜጦችም ሆኑ በራሪ ጽሁፎ
ች አይበተኑም ። ይህም ማለት ተበታኝ ጋዜጦችን
እና በራሪ ጽሁፎችን የሚያዘጋጀው ፓቬል ነው ማ
ለት ነው ። አይደለምን? ከዚያም ሁሉንም መቀረጣጠፍ
ይጀምራሉ ። ፖሊሶች ፍርፋሪ እስኪቀር ድረስ ሰዎችን
ቁርጭምጭም አድርገው መቀረጣጠፍ ይወዳሉ ።»

«ይገባኛል ፤ እገነዘባለሁኝ ። የኔ ሆይ! ታዲያ ምን
ማድረግ ይሻለናል?» በማለት ሀዘን በተመላው አነ
ጋገር ጠየቀች ።

«ሰዎቻችንን ሁሉ ሰብስበው እሥር ቤት አጉረ
ዋቸዋል ፤ ሰይጣን ይጠራርጋቸውና! ለቆምንበት ዓላማ
ብቻ ሳይሆን ጓዶቻችንንም ለማትረፍ ሥራችንን ሳ
ናቋርጥ መቀጠል አለብን» የሚለው የሳሞይሎቭ ድም
ፅ ከማዕድ ማዘጋጃው ክፍል ተሰማ ። የጎርም መጠን
ባለ ፈገግታ ፈገግ በማለት ፡ —

«ሥራውን የሚያካሂድ ደግሞ አንድም የለም ።
እጅግ ብዙ የሆኑ ጥሩ-ጥሩ ጽሁፎች አሉኝ ። እኔ
ራሴ ያዘጋጀኋቸው ናቸው ። ችግሩ ፋብሪካው ውስ



ጥ አግብቶ የማሠራጨቱ ጉዳይ ነው» በማለት ተናገረ ።

«ፋብሪካው መግቢያ ላይ ሰውን ሁሉ መፈተሽ
ጀምረዋል» በማለት ሳሞይሎቭ ተናገረ ።

እርሷ አንድ ነገር እንድትረዳቸው የሚሹ መሆና
ቸውን እናት ተገነዘበች ።

«እንዴት አድርጎ ነው ሊከናወን የሚችለው?»
በማለት ወዲያውኑ በችኮላ ጠየቀች ።

ሳሞይሎቭ ከነበረበት ቦታ ወደበራፉ ዘንድ መጣ ።

«ፔላጊያ ኒሎቭና ፤ የሚበሉ ነገሮች እያዞረች ከም
ትሸጠው ከኮርሱኖቫ ጋር ትተዋወቃላችሁን?» አላት ።

«አዎን እንተዋወቃለን ። ምነው?» በማለት እናት
መለሰች ።

«ከእርሷ ጋር ይነጋገሩ ። ምናልባት እርሷ የሚበተ
ኑ ጽሁፎቻችንን ይዛልን ልትገባ ትችል ይሆናል ።»

ይኸንን የቀረበላትን ሃሣብ እናት አይሆንም በሚ
ል ምልክት ጣቶቿን በማወዛወዝ ገለጸች ።

«ኧረ ይሂስ የማይሆን ነው! ወሬኛ ነች! ወረቀቶ
ቹን ያገኘችው ከእኔ መሆኑን እንደተረዱ ፤ ከዚህ
ከእኔ ቤት መሆኑን እንደተረዱ … ኧረ እሷስ
አትሆንም!»

ከዚያም ድንገተኛ በሆነ የመነሳሳት ስሜት የሚከ
ተለውን ጨምራ ተናገረች ፡ —

«ለኔ ስጡኝ! እኔው ራሴ ተገቢውን እፈጽማለሁኝ ።
አስፈላጊውን ዘዴ እፈልጋለሁኝ ። ማሪያ ረዳቷ አድ
ርጋ እንድትወስደኝ አደርጋለሁኝ ። የዕለት እንጀራዬን
እየሠራሁ ማግኘት ይኖርብኛል ። የሚበሉ ምግቦች እያ
ዘጋጀሁኝ ወደ ፋብሪካው ለመሸጥ እሄዳለሁኝ ። ተግባ
ሬን መፈጸም እችላለሁኝ ።»

እጆቿን በደረቷ ላይ ጣል አድርጋ ፤ አንዳችም መ
ታወቅ ሳያስከትል ማናቸውንም ተግባሯን በሚገባ
የምታከናውን መሆኗን ወዲያውኑ ያረጋገጠችላቸው

ከመሆኗም በስተቀር በታላቅ ደስታ ልቧ ተመልቶ የሚከተለውን ተናገረች ፡—

«የፓቬል እጆች ከእሥር-ቤት ባሻገርም ተዘርግተው የሚደርሱ መሆናቸውን ይወቁት! ይኸንን ይወቁት!» አለች ።

ሦስቱም በፈገግታ ተመሉ ።

«ድንቅ ነው ፤ እናቴ! እንዴት ግሩም-ድንቅ እንደሆነ ባወቁት ኖሮ! እንደው በደፈናው ደስ የሚያሰኝ ነው!» በማለት እጆቹን እያሻሸ የጎር ተናገረ ።

«ይኸ ጉዳይ በሥራ ላይ ከዋለ ወደ እሥር ቤት ተይገቬ ስሔድ ወደ መኝታ አልጋዬ የመሄድ ያህል እቆጥረዋለሁኝ » በማለት ሳሞይሎቭ እጆቹን እያሻሸ ተናገረ ።

«እርስዎ ውቢት የተዋቡ ነዎት!» በማለት ጮክ ባለ ድምፅ የጎር ተናገረ ።

እናት ፈገግ አለች ። ተበታኝ ጋዜጦቹ ፋብሪካው ውስጥ መበተናቸው ከቀጠለ ለዚህ ጉዳይ ተጠያቂው ፓቬል ነው በማለት የፋብሪካው አስተዳደር ለመወንጀል እንደማይችል ለርሷ ግልጥ ነበር ። ይኸንን ተግባር ለማከናወን እንደምትችል የተሰማት ስለሆነ ሁለንተናዋ በደስታ ተዋጠ ።

«ፓቬልን እሥር ቤት ስታገኘው ግሩም-ድንቅ እናት ያሉት መሆኑን ንገረው» በማለት የጎር ተናገረ ።

«መጀመርያ ቀደም አድርጌ እኔ አየዋለሁኝ!» በማለት ሳሞይሎቭ እየሳቀ ተናገረ ።

«መከናወን ያለበትን ጉዳይ ሁሉ ! የማከናውን መሆኔን ንገረው ! ንገረው ይኸንን ይረዳው» በማለት እናት ተናገረች ።

«ሳሞይሎቭን እሥር-ቤት ባይከቱትስ?» በማለት የጎር ጠየቀ ።

«ታዲያ ምን ማድረግ ይቻላል?»



ሁለቱ ሰዎች በሳቅ ተንከተከቱ ። እርሷም አፋራ ምነት የተቀላቀለውና የቅሬታም ሳቅ ሳቀች ።

«የሌሎች ሰዎች ችግሮች እንዲሰሙህ መሆን ከባድ ነው» በማለት ዐይኖቿን ወደመሬት ጣል አድርጋ ተናገረች ። የጎርም የሚከተለውን ተናገረ ፡—

«ይኸ ምንግዜም ያለ ጉዳይ ነው ። እርስዎ ለፓቬል አያስቡ ፤ አይስጉ ። ከእሥር ቤት ሲወጣ ይበልጥ የተሻሻለ ሰው ሁኖ ይወጣል ። ሰው እሥር ቤት ውስጥ ሁኖ ጥሩ ዕረፍት ያገኛል ። ለማጥናት — ለመመራመርም ዕድል ይኖረዋል ። እንደኛ ዓይነት ሰዎች ደግሞ ከእሥር ቤት ውጪ እነዚህን ሁለት ጉዳዮች ለማሟላት ጊዜ አይኖረንም ። እኔ ሦስት ጊዜ እሥር ቤት ገብቼ ነበር ። ምንም እንኳን እሥር ቤት መግባት አስደሳች ነው ብዬ ባልናገርም ሦስቱንም ጊዜ ከእሥር ቤት ስወጣ ልቤ እና አዕምሮዬ በመርካቱ ደህና ተጠቅሜአለሁኝ ።»

«መተንፈስ ይቸግርሃል» በማለት ፊቱን በወዳጅነት መንፈስ እየተመለከተች ተናገረች ። እርሱም ሲመልስ ፡—

«ዚህ ምክንያቱ ፍጹም ሌላ ጉዳይ ነው ። እሺ ፤ እንግዲህ እናቴ ሁሉም ነገር መፍትሔ አግኝቶአል ማለት ነውን? ነገ የሚሠራጩትን ጋዜጦች እና መጣልዎታለን ። እና አሁንም እንደገና ተሽከርካሪው ዳማጭ ጎማ የዘመናትን ጭለማ እየዳመጠ መሽከርከሩን ይቀጥላል ። ረጅም ዕድሜ ለንግግር ነፃነት! ረጅም ዕድሜ ለእናት ልብ! ዳግመኛ እስከምንገናኝ!» በማለት ተናገረ ። ሳሞይሎቭም የእናትን እጅ አጥብቆ እየጨበጠ ፡—

«ደህና ያምሹ ። እኔ ለእኔ እናት እንደዚህ ያለ ሃሣብ ማቅረብና መወያየት አልችልም! አዩት እናት!» በማለት ተናገረ ።

«ሁሉም ቢሆኑ ጉዳዩን ወደፊት አንድ ቀን ይገ
ነዘቡታል» በማለት እርሱን ደስ እንዲለው በመሻት
ተናገረች ።

እነርሱ ከሄዱ በኋላ በሯን ቆለፈችና በክፍሉ ው
ስጥ አንድ መሀል ቦታ ላይ ተንበርክካ ከዝናሙ ድ
ምፅ ጋር ጸሎቷን ትጸልይ ጀመር ። ጸሎቷን ድምፅ
ሳታሰማ በለሆሳስ የምትጸልይ ሲሆን ታስብ-ታሰላስ
ል የነበረው ልጅዋ ፓቬል ከሕይወቷ ጋር ስላስተዋ
ወቃት ሰዎች በመጨነቅ ነው ። በጣም የቅርብ ግንኙ
ነት ያላቸውና ያም ሁኖ ደግሞ እያንዳንዳቸውም እ
ንዲህ ለየብቻ ተለያይተው የሚገኙ እነዚህ ሁሉ
አጉል ተዘባናኞች ያይደሉ ሰዎች እቤቱ ግድግዳ ላይ
በተሰቀሉት በቅዱሳን ሥዕሎች እና በእርሷ መካከል
የሚመላለሱ መስለው ታዩዋት ።

ጧት ማለዳው ላይ ማሪያ ኮርሱኖቫን ለመጠየቅ
ሄደች ።

ምግብ አዟሪዋ ያው እንደወትሮዋ ሁለንተናዋ
በቅባት ተለውሶ እና በተለመደው ጨዂነቷ እናትን
ርኅራኄ በተመላበት ሁኔታ ተቀበለቻት ። ከዚያም
በቅባት በተለወሰው እጅዋ የእናትን ትከሻ
ቸብ-ቸብ አደረገችና ፡ —

«አዘኑ እንዴ? ሃዘን እንዲረታዎ አያድርጉ! አንጠል
ጥለው በመያዝ ወሰዱት ። ወሰዱት አይደለም? ይሁን
ይውሰዱት ግዴለም ። አንዳችም የሚያሳፍር ጉዳይ የለ
በትም! ቀደም ባለው ጊዜ በሌብነት ምክንያት ሰዎ
ችን እሥር ቤት ይከቱ ነበር ። በአሁኑ ጊዜ ግን ለዕ
ውነት ለመብት የሚከራከሩትን ያሥራሉ ። ምናልባትም
ፓቬል መናገር የነበረበትን ንግግር ሁሉ አልተናገ
ረም ይሆናል ። የፈጸመው ድርጊት ግን ለሁሉም ሰ
ው ጠቀሜታ ሲል ነው ። ይኸንን ደግሞ ሁሉም ሰ
ው የሚያውቀው ነው ። ስለዚህ ሃሣብ እንዳይገባዎት ።



ምንም እንኳን ሰዎች አምነው ባይናገሩትም ክፉውን
እና በጎውን ለይተው ያውቃሉ ። መጥቼ ላይዎት ፈ
ልጌ ነበር ፤ ጊዜ በማጣቴ ነው ሳላይዎት የቀረሁት ።
ቀኑን ሙሉ ምግብ ሳዘጋጅና ያዘጋጀሁትንም ተሸክ
ሜ በመውሰድ ስሸጥ እውላለሁኝ ። እንደሚያዩት ግን
ያው መናጢ ደሀ እንደሆንኩኝ ሟች ነኝ! ውሽማ የሆ
ንኳቸው ናቸው ግጠው-ግጠው ያለችኝን የሚጨርሱ
ት ። ኧረ የጉድ ያለህ! የሚያሰኝ ነው ። ዳቦ ላይ እንደ
ሚረባረቡ በረሮዎች አንዱ ከዚህ ሌላው ደግሞ ከ
ዚያ በመምጣት ይቦጠቡጡኛል ። እንደምንም ብዬ አ
ሥር ሩብል ሳጠራቅም ሌላው ጃውሳ ይመጣና ያቺ
ኑ ያጠራቀምኳትን ምንትፍ አድርጓት ይሄዳል ። ሴት
ሁኖ መፈጠር ምንኛ አሳዛኝ ነው! ለማንም ቢሆን
የማልመኝላት ነው! ከነተረቱም አንድ አይነድ ፤ አንድ
አይፈርድ ነው!» ከዚያም ፔላጊያ ወሬዋን አቋረጠቻ
ትና ፡ —

«ረዳትሽ አድርገሽኝ ለአንቺ እንድሠራ ልጠይቅ
ሽ ነበር የመጣሁት» አለቻት ።

«እንዴት ፤ ምን ማለትዎ ነው?» በማለት ማሪያ ጠ
የቀች ። ፔላጊያ ምን ማለቷ እንደሆነ ስታብራራላት
ም ማሪያ በእሺታ ራሷን ነቀነቀች ። እንዲህም አ
ለች ፡ —

«እሺ ። ምንቸገረኝ ። እንዴት አድርገው ከዚያ ከባ
ሌ ይደብቁኝ እንደነበረ ትዝ ይልዎታልን? አሁን ደግ
ሞ እኔ ከረሀብ እደብቅዎታለሁኝ ... ልጅዎ ተይዞ የታ
ሠረው ለሁሉም ሰው ሲል ስለሆነ ማንም ቢሆን
እርስዎን ይረዳዎት ዘንድ ይገባዋል ። ልጅዎ ግሩም
ሰው ነበር ። ይኸንን ፤ ሰው ሁሉ የሚለው ነው ። ሁሉም
ሰው በመታሠሩ አዝኖለታል ። እነዚህ ሰዎች ስለታሠሩ
የፋብሪካው ባለሥልጣኖች አንዳችም ፋይዳ እንደማያ
ገኙ ይመኑኝ ። ፋብሪካው ውስጥ ምን እየተካሄደ

መሆኑን ብቻ እንኳን ያስተውሉ ። ኧረ የኔ ሆዬ ፤
ፋብሪካው ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለው በጎ
ነገር አይደለም ይባላል! እነዚህ ሹማምንት የተባሉ
ት የፋብሪካው አሠሪዎች ያስቸገራቸውን ሠራተኛ
እግር ሰንክለው ቢቸነክሩት የትም ሳይራመድ የሚሸ
መደመድ ይመስላቸዋል ። ሁኔታው ግን የተገላቢጦሽ
ነው ። ባለሥልጣኖች የተባሉት አንድ አሥሩን ቢወግ
ሩዋቸው በምትካቸው ብዙ መቶ ተከታዮቻቸው በተ
ቃዋሚነት እንደ አሸን ይፈላሉ!»
በዚህ ባደረጉት ውይይት መሠረት እናት በማግሥ
ቱ ቀትር ላይ የማሪያን የሚሸጡ ሁለት ቅርጫት
ሙሉ ምግቦች ይዛ ወደፋብሪካው ደጃፍ ፤ማሪያ ደግ
ሞ ለንግድ ወደ ገበያ ቦታ ሄደች ።

## 15

አዲሲቷን ምግብ ሻጭ ወዝ-አደሮቹ ወዲያውኑ
ለይተው አወቋት ።
«ፔላጊያ ፥ ሥራ ጀመሩ ማለት ነውን?» በማለት
ጥሩ አድርገዋል በሚል መልክ ራሳቸውን እየነቀነቁ
እናትን ይጠይቋት ጀመር ።
ከመካከላቸው አንዳንዶቹ ፓቬል በቅርብ ጊዜ
ውስጥ የሚፈታ መሆኑን ለማረጋገጥ ይቻኮሉ ነበር ።
አንዳንዶቹ ደግሞ ለእናት ያላቸውን የርኅራኄ መንፈ
ስ ይገልጣሉ ። ሌሎቹ ደግሞ የፋብሪካውን ዲሬክተር
ና ፖሊሶችን የሚያወግዙ ሲሆኑ ይኸው ድርጊታቸ
ውም በእናት ልብ ውስጥ ሠርጾ በመግባት ቦታ
ሊይዝ ችሎአል ። በጥላቻ ስሜት የሚመለከቷት አንዳ
ንድ ሰዎች የነበሩ ከመሆናቸውም በስተቀር ፥ የሥራ
ሰዓት ተቆጣጣሪ የሆነው ኢሳይ ጎርቦቭ ጥርሶቹን
እያፋጨ የሚከተለውን ተናገራት ፡—



«አገረ-ገዢው እኔ ብሆን ኖሮ ልጅሽን እሰቅለው
ነበር! ሰዎች እንዲኮበልሉ በማድረግ በወሰደው የመሪ
ነት ተግባሩ የሚገባውን ዋጋ እንዲያገኝ አድርገው
ነበር!»
ይኸንን የመሰለው መጥፎ ዛቻ እስከአጥንቷ ድረ
ስ ዘልቆ ተሰማት ። ለኢሳይ መልስ አልሰጠችውም ።
በጠቃጠቆ እንደወንፊት የተበሳሳች ኩባያ የምታክል
ፊቱን ቀና ብላ በማየት ጫን ከተነፈሰች በኋላ ዐ
ይኖቿን ቀለስ አድርጋ ምድር-ምድሩን ተመለከተች ።
ፋብሪካው ከዳር-ዳር ተነሳስቶአል ። ወዝ-አደሮቹ
በቡድን-በቡድን እየሆኑ እርስ-በእርሳቸው ይንሾካሾካሉ ።
ሃሣብ የገባቸው የፋብሪካው ወዝ-አደሮች ፎርማኖች
(የቡድን አለቆች) በየቦታው ያነፈንፋሉ ። የስድብ ድምፆ
ች እና የፌዝ ሳቆች ይሰማሉ ።
ሁለት ፖሊሶች ሳሞይሎቭን ይዘው በእናት ፊት
አልፈው ሄዱ ። ሳሞይሎቭ አንድ እጁን ኪሱ ከትቶ
ና በሌላኛው እጁ ደግሞ ቀይማ ፀጉሩን እያሻሸ
ሄደ ።
ብዛታቸው አንድ መቶ ያህል የሚሆኑ ወዝ-አደ
ሮች እየተከተሉ የስድብ ናዳና ጩኸት በፖሊሶቹ
ላይ አሰሙ ።
«ሳሞይሎቭ ፥ ለሽርሽር ነው እንዴ የምትሄደው?»
በማለት አንዱ ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰማ ።
«እንዴት ነው ጓል ፥ ይኸንን ሰሞን በአክብሮት
ይዘውናል!» በማለት ሌላው ወዝ-አደር ተናገረ ።
«ስንንሸረሸርም ዘበኛ እንዲኖረን አድርጉን!»
«ከእንግዲህ ሌቦችን አድኖ መያዝ ምንም ዋጋ
የሌለው ይመስላል ። ስለዚህም ሳይሆን አይቀርም
ንጹሕ ሰዎችን እያደኑ መያዝ የጀመሩት...» በማለት
ረዥም የሆነ አንድ ዐይና ወዝ-አደር ተናገረ ።
«ቢያንስ-ቢያንስ ማታ እያደኑ ቢይዙ እንኳን የተ

ሻለ ነበር ። እዚህ ግን እነዚህ ርጉሞች በጠራራ ፀሐይ ያድናሉ!» የሚል ድምፅ ከተሰበሰቡት ወዝ-አደሮች መካከል አንዱ አሰማ ።

ፖሊሶቹ አንዳችም ነገር ያላዩ በመምሰል በነርሱ ላይ የተንጎደጎደውን የስድብ ውርጅብኝ ከቶም ያልሰሙ በመምሰል ሽምቅቅ ብለው በመንቧከክ ተፋጥነው ሄዱ ። ሦስት ወዝ-አደሮች ትልልቅ የብረት ዚንጎ ይዘው ከፊት ለፊታቸው በመቆም—

«አሳልፉን አናንት አሳ አጥማጆች!» በማለት ጮሁ ።

ሳሞይሎቭ በእናት በኩል ሲያልፍ ጭንቅላቱን በተፈጸመው ድርጊት በማሾፍ ነቅነቅ አደረገላት ። ከዚያም ፈገግ በማለት —

«ይኸው መሄዳችን ነው!» አላት ።

ምንም ሳትናገር እጅ ነሳችው ። እነዚህ ሀቀኛ የሆኑና በአስተሳሰባቸው የሰከኑ ወጣቶች ወደ እሥር ቤት ታፍሰው ሲሄዱ ፊታቸው ላይ በሚያሳዩት ፈገግታ በጥልቅ ስሜት የተነካች ከመሆኗም በስተቀር ልቧም በእናትነት ፍቅር እና ርኅራኄ ተመላ ።

ከፋብሪካው እንደተመለሰች ማሪያን በሥራ በመርዳትና የምታወራውን ወሬም በማዳመጥ የተቀረውን ጊዜዋን አሳለፈች ። ደንገዝገዝ ሲል ቀዝቃዛ ፤ ባዶ እና ደስታ-ቢስ ወደሆነው ቤቷ ሄደች ። ረዘም ላለ ጊዜ ዓላማ-ቢስ በመሆን ፤ የመንፈስ ዕረፍት በማጣትና የምታደርገውም ግራ እየገባት ተጓዘች ። ሃሣብ ገብቷታል ። ምክንያቱም ከመሸ ቆየት ስላለና የጎር ኢቫኖቪችም ሊያመጣ ቃል ገብቶ የነበረውን ተበታኝ ጋዜጦች ባለማምጣቱ ነበር ።

ከበድ ያለ የበልግ በረዶ ይወርዳል ። በረዶዎቹ እስኪቀልጡና የውሀ ጠብ-ጠብታ ትተው በፀጥታ እስኪያልፉ ድረስ መስኮቱ ደፍ ላይ ቀስ-በቀስ ይጠራቀማሉ ። ልጅዋ ትዝ አላት…



በሩ ዝግ ብሎ ተንኳኳ ። እናት ፈጠን ብላ በመሄድ መቀርቀርያውን አነሳችው ። ሳሻ ወደውስጥ ገባች ። እናት ሳሻን ካየቻት ረዘም ያለ ጊዜ ስላለፈ የሳሻን ሁኔታ ስታስተውል ድምቡሽቡሽ ብላ የወፈረች መሰላት ።

«ጤና ይስጥልኝ ፤ እንደምን አመሸሽ? ረዘም ላለ ጊዜ አላየሁሽም ነበር ። ወደ ሌላ ቦታ ሂደሽ ነበርን?» በማለት እናት አንዲት ሰው ቤቷ ስለአገኘች እና የተቀረውን ምሽት ብቻዋን ስለማትሆን በመደሰት ሳሻን ጠየቀቻት ።

«የለም ወደሌላ ቦታ አልሄድኩም ። ከኒኮላይ ኢቫኖቪች ጋር ታሥሬ እሥር ቤት ነበርኩኝ ። ኒኮላይን ያስታውሱት የለምን?» በማለት ልጃገረዲቱ ሳሻ ፈገግ ብላ መለሰች ።

«እንዴ ፤ አዎን እንጂ ። አውቀዋለሁኝ! ትላንትና ከእሥር የፈቱት መሆኑን የጎር ኢቫኖቪች ነገረኝ ። ስለአንቺ መታሠር ግን አልሰማሁኝም ነበር ። አንቺም ታሥረሽ የነበረ መሆኑን ማንም አልነገረኝም…» በማለት እናት መለሰች ።

«አይ ፤ ምንም አይደለም ። እስኪ ፤ የጎር ኢቫኖቪች ከመምጣታቸው በፊት ልብሴን ልቀይር ።» በማለት ሳሻ መልከት-መልከት እያለች ተናገረች ።

«ርጥብ ብለሻል…» አለቻት እናት ።

«የሚበተኑትን ጋዜጦች እና በራሪ ወረቀቶች አምጥቻለሁኝ…» አለች ሳሻ ።

«ስጭኝ! ስጭኝ!» በማለት እናት በጉጉት ድምጿን ከፍ አድርጋ አሰማች ።

ልጃገረዲቱ ሳሻ የካፖርቷን ቁልፎች ፈታ-ፈታ አድርጋ ወዝወዝ-ወዝወዝ ስትል ከዛፍ ላይ እንደሚረግፉ ቅጠሎች ጋዜጦቹና በራሪ ወረቀቶቹ ዱብ-ዱብ ይሉ ጀመር ። እናት ስትሰበስባቸው በፈገግታ ተመላች ።

«ገና እንዳየሁሽ ምን እንደዚህ እንዳወፈረሽ አስገርሞኝ ነበር ። ባል አግብተሽ አርግዘሻል ብዬ አስቤ ነበር ። አቤት-አቤት! ስንቱን ነው ታቅፈሽ የመጣሽው! በእግርሽ እዚህ ድረስ አልመጣሽም ። እውን?»

«አዎን ። በእግሬ ነው » በማለት አሁን ጋዜጦቹን ስታራገፍ እንደቀድሞዋ ረዥም እና ቀጭን የሆነችይቱ ሳሻ ተናገረች ። የሳሻ ፊት ሰልከክ በማለት ዐይኖቿ ከቀድሞው የበለጠ ጎላ-ጎላ ያሉና ከዐይኖቿ በታችም ጥቁር ክበቦች ያረፉበት መሆናቸውን ተገነዘበች ።

«ከእሥር ቤት ገና እንደወጣሽ ማድረግ ያለብሽ ጥቂት ዕረፍት ማግኘት ሁኖ ሳለ ፤ ይኸንን ማድረግሽ ለምንድነው?» በማለት ጫን በመተንፈስና በመደነቅ ሁኔታ ራሷን በመነቅነቅ እናት ጠየቀች ።

«መደረግ አለበት!» በማለት ብርዱ እያንቀጠቀጣት ሳሻ ተናገረች ።

«ስለ ፓቬል ሚኻኢሎቪች ይንገሩኝ እስኪ ፤ በተያዘ ጊዜ ተረብሾ ነበርን?»

ይኸንን ጥያቄ ሳሻ ስታቀርብ አንገቷን አቀርቅራ በብርድ በሚንቀጠቀጡ ጣቶቹ ፀጉሯን ታስተካክል ስለነበረ እናትን አትመለከትም ነበር ።

«ይኸን ያህልም አልተሸበረም ። ራሱን እንዲህ በቀላሉ አይጥልም » በማለት እናት መለሰች ።

«ጠንካራ ጉልበታም ነው እንዴ?» በማለት ልጃገረዲቱ አለሰልሳ ጠየቀች ።

«በሕይወቱ ታሞም አያውቅም» በማለት እናት መለሰች ።

«አንቺ እኮ እዚህ በብርድ እየተንቀጠቀጥሽ ነሽ ። ቆይ አሁን ሻይ አፍልቼ በማር እሰጥሻለሁኝ» በማለት እናት ተናገረች ።

«እሱስ ጥሩ ነበር! ግን ብዙ ማስቸገር ነው ። በጣ



ም መሽቶአል ። እኔው ራሴ ላዘጋጀው» በማለት ሳሻ ተናገረች ።

«ለመሆኑ እንደ አንቺ ደክሞኛልን?» በሚል የአይሆንም — እኔ አዘጋጃለሁ አነጋገር የሻይ ማፍያውን ሳሞቫር ስታያይዝ እናት ተናገረች ። ሳሻም ወደማዕድ ማዘጋጃው ክፍል በመሄድ እጆቿን ከጭንቅላቷ ኋላ አድርጋ አግዳሚው ወንበር ላይ ተቀመጠች ።

«እሥር ቤት አንድን ሰው አማቅቆ ይጨርሰዋል ። የተረገመ ሥራ-ፈትነት ነው! አያሌ የሚሠራ ሥራ መኖሩን እያወቁ በወጥመድ ውስጥ እንደተያዘ የዱር አውሬ እሥር ቤት ውስጥ ተይዞ መቀመጥ...» በማለት ሳሻ ተናገረች ።

«ለዚህ ሁሉ ዋጋሽን የሚከፍልሽ ማነው?» በማለት እናት ሳሻን ጠየቀቻት ። ከዚያም ትንፋሿን በመተንፈስ ራሷው እናት መልሱን እንደሚከተለው መለሰች —

«ውለታሽን የሚከፍልሽ ሌላ ማንም አይደል ፤ እርሱ ፈጣሪያችን ነው! እንደምገምተው ደግሞ በፈጣሪ — አምላካችንም አታምኚም ። አይደለምን?» በማለት እናት ሳሻን ጠየቀቻት ።

«አዎን ። አላምንም » ብላ ራሷን እየነቀነቀች መለሰችላት ።

«ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? የገዛ ራስሽን ዕምነት ምንነት አትገነዘቢውም ማለት ነው ። በእግዚአብሔር የማታምኚ ከሆነ ይኸንን መሳይ ኑሮ እንደምን ትኖሪያለሽ?» በማለት እናት የከሰሉን አመድ ከእጆችዋ ላይ በሥራ ልብሷ እየጠራረገች በስሜት ተመልታ ጠየቀቻት ።

ድንገት አንድ ሰው ከውጪ በኩል ጉርምርምታ እያሰማ በቀስታ ከደጃፉ ላይ ደረሰ ። እናት መራመድ ልትጀምር ስትል ልጃገረዲቱ ሳሻ ተቀምጣ ከነበረች

በት ቦታ በመነሳት ቆመች ። እንዲህም በማለት ቀስ ብላ ተናገረች —

«ይቆዩ ፤ በሩን አይክፈቱ ። ፖሊሶቹ ከሆኑ እርስዎ እኔን ማን እንደሆንኩኝ አያውቁኝም ማለት ነው ። በምሽት ቤት አሳስቼ ከደጃፍዎ ላይ ስደርስ አዙሮኝ ወደቅሁኝ ። አስገብተውኝ ልብሴን ሲያወልቁልኝ ተበታኝ ጋዜጦቹን አገኙ ። ገባዎትን?» አለቻት ።

«የኔ ውድ የኔ ምስኪን ። ለምንድነው እንደዚህ የምለው?» በማለት እናት ጥልቅ በሆነ ስሜት ተነክታ ጠየቀቻት ።

«ቆዩ አንድ ግዜ ። ምናልባትም የጎር ይሆን ይሆናል...» በማለት ሳሻ ተናገረች ።

እንደተባለውም ውጪ የነበረው የጎር ነው ። በበረዶው በስብሶና በድካምም ዝሎ ነበር ።

«አሃ ፤ ሳሞቫሩን እያፈላችሁበት ነዋ! እናት ከሁሉም ከሁሉም ትልቁ ነገር እርሱ ነው! ሳሻ ፤ መጥተሻላ?» በማለት የጎር ተናገረ ።

ከበድ ያለ ካፖርቱን እያወለቀና ኩር-ኩር የሚል ትንፋሹን እየተነፈሰ ያለማቋረጥ ይናገር ጀመር ፡ —

«አዩ እናት ፤ ይህችን ትንሽ የሴት ወይዘሮ ባለሥልጣኖቹ አይወዷትም ። የእሥር ቤት ጠባቂው ሊሰድባት በቃጣበት ጊዜ ላደረገው ጥፋት ይቅርታ እስኪጠይቃት ድረስ እህል ውሀ ላትቀምስ መወሰኗን አስታወቀች ። ስምንት ቀናት ሙሉ አንዳችም ነገር አልቀመሰችም ነበር ። ቢላዋ አለማንሳቷም አንድ ምክንያት ቢኖራት ነው ። ኧረ መች ሞኝነት ነው? እንደኔ ዓይነት ቦርጭ አላዩምን?»

በሩን ከበስተጀርባው በዘጋው ጊዜ እንኳን ሳይቀር እያወራና ወደ ሌላኛው ክፍል እየገባ ፍጥጥ ብሎ የወጣ ቦርጩን ይዞ ነበር ።

«ኧረ ለመሆኑ ስምንት ቀናት ሙሉ ምግብ በእርግጥ አልቀመስሽም ነበርን?» በማለት እናት በመደነቅ ጠየቀች ።

«ይቅርታ እንዲጠይቀኝ አንድ ነገር ማድረግ ነበረብኝ!» በማለት አሁንም ከብርድ የተነሳ እየተንቀጠቀጠች ሳሻ መለሰች ። በልጃገረዲቷ የመረጋጋት መንፈስ እና በጠንካራነቷም ተደንቃ የመውቀስ ሁኔታ አሳየች ።

«ኧረ እንዴት ያለሽ ልጃገረድ ነሽ ልጄ! እስኪ ብትሞቺስ ኖሮ?» በማለት ድምጿን ከፍ አድርጋ እናት ማሰብ ጀመረች ።

«ምንም ማድረግ አይቻልም ነበር ። ይሁን እንጂ ሰውየው ይቅርታ ጠየቀ » በማለት ልጃገረዲቱ ድምጿን አለስልሳ ተናገረች ።

«አሄ-ሄ! እኛን ሴቶችን ሕይወታችንን ሙሉ መጫን ወንዶች ሁል ግዜ የሚፈጽሙት ጉዳይ ነው...»

«እንግዲህ ጭንቴን አራግፌአለሁኝ ፤ ሳሞቫሩ ዝግጁ ነው እንዴ? ቆይ ወደ እናንተ ዘንድ ላምጣው» በማለት የጎር በሩን አይቶ ተናገረ ።

ሳሞቫሩን ይዞ ወደ ሌላኛው ክፍል ሲገባም —

«ክብደቱ መቶ ኪሎ እየመዘነና በቮስክሬሴንስክ ከተማ በድቁና እያገለገለ ይኖር የነበረው ውድ አባቴ በሳባ-ሦስት ዓመት የእርጅና ዘመኑ በሰላም እና በተሟላ ጤንነት ለመኖሩ ክብር-ምሥጋና ይግባውና በቀን ከሃያ ብርጭቆ ሻይ ያላነሰ ይጠጣ ነበር...» በማለት ተናገረ ።

«እንዴ ፣ የቄስ ኢቫን ልጅ ነዎት እንዴ?» በማለት እናት በአንክሮ ጠየቀች ።

«አዎን ፣ ነኝ ። ከተከበሩት ጌታው አባቴ ጋር ይተዋወቃሉን?» አላት ።

«እኔም እኮ የቮስክሬሴንስክ ተወላጅ ነኝ!» በማለት እናት መለሰችለት ።

«እንዴ ፣ ከኔ የትውልድ ከተማ? የማን ልጅ መሆን
ዎ ነው?» በማለት ጠየቃት ።

«የእናንተ ጎረቤት የሆኑት የነሜሬጊን ልጅ ነኝ!»

«የአንካሣው ኒል ልጅ ነዎታ? ኧረ እሳቸውንማ
ደህና አድርጌ አውቃቸዋለሁኝ! ስንት ግዜ ጀሮዬን በር
በሬ እስኪመስል ለምዝገውታል…»

ፊት ለፊት በመቆም እየተሳሳቁ ብዙ-ብዙ ጥያቄ
ዎች ይጠያየቁ ጀመር ። ሳሻ ሻዩን እየቀዳችና የእነር
ሱንም ሁኔታ እየተመለከተች ትስቃለች ። የሻይ ብር
ጭቆዎቹ መንገጫገጭ እናትን እንደገና ወደቀድሞው
ሞቅ ያለ አኗኗር መለሳት ።

«ጉድ እኮ ነው! ይቅርታ አድርጉልኝ ። ሁሉንም
ነገር ረሳሁት እኮ! ከትውልድ ከተማ የመጣ ሰውን
ማግኘት ምንኛ ደስ ያሰኛል!» በማለት እናት ተናገ
ረች ።

«ሁሉንም ነገር ተቆጣጣሪ ሁኜ በመቆየቴ ይቅ
ርታ መጠየቅ የሚገባኝ እኔ ነኝ ። ገና ከአሁኑ ከምሽ
ቱ አምስት ሰዓት ሆነ ። ከፊት-ለፊቴ ረዥም ጉዞ ይ
ጠብቀኛል» በማለት ሳሻ ተናገረች ።

«የት ልትሄጂ ነው? ወደ ከተማ?» በማለት እናት
ተገርማ ጠየቀች ።

«አዎን » በማለት ሳሻ መለሰች ።

«እንዴ ፣ ኧረ ለምን ብለሽ? አሁን በጣም ጭለማ
ነው ። መንገዱ ሁሉ ርጥብ ነው ። ደግሞም በጣም ደ
ክሞሻል ። ምሽቱን እዚሁ አሳልፊው ። የጎር ኢቫኖቪ
ች ማዕድ ቤት ውስጥ ይተኛል ። እኔና አንቺ እዚህ
እንተኛለን…» በማለት እናት ተናገረች ።

«የለም አይሆንም ። መሄድ አለብኝ » በማለት ል
ጃገረዲቱ ሳሻ ተናገረች ።

«መጥፎ አጋጣሚ ሁኖ ፤ ይህቺ ወጣቷ ልጃገረድ
መሄድ አለባት ። እዚህ እርሷን ነዋሪው ያውቃታል ።



ነገ እዚህ በየመንገዶቹ መታየት የለባትም ።» በማለት
የጎር ኢቫኖቪች ተናገረ ።

«እኮ ግን እንዴት አድርጋ ትሄዳለች? ብቻዋን?»

«አዎን ብቻዋን መሄድ አለባት» በማለት የጎር
ሳቅ ብሎ መለሰ ።

ልጃገረዲቱ አንድ ብርጭቆ ሻይ ከቀዳች በኋላ
ዳቦ ላይ ጨው ነስንሳ እናትን በጥልቅ ስሜት
እየተመለከተች ሻይዋን እየጠጣች መብላት ጀመረች ።

«አንተ እና ናታሻ ይኸንን እንዴት ለማድረግ
ትችላላችሁ? እኔ ከቶውንም ላደርገው አልችልም ። እፈ
ራለሁኝ » በማለት እናት ተናገረች ።

እርሷም ትፈራለች ። አትፈሪም እንዴ ሳሻ?» በማለት
የጎር ጠየቃት ።

«አዎን ። እንዴታ እፈራለሁ እንጂ!» በማለት ልጃ
ገረዲቱ መለሰች ።

እናት ዐይኗቿን ሳሻ እና የጎር ላይ ጣል አድ
ርጋ ተመለከተቻቸው ።

«ኧረ መጥኔውን ይስጣችሁ — እንዴት እንደዚህ
ጠንካሮች ሆናችሁ!» በማለት እናት አደነቀች ።

ሳሻ ሻይዋን ጠጥታ ስትጨርስ የጎርን ሳታነጋ
ግር እጁን በመጨበጥ ከተሰናበተችው በኋላ ወደ
ማዕዱ ክፍል ገባች ። እናትም ተከትላት ገባች ።

«ፓቬል ሚኻኢሎቪችን የሚያገኙት ከሆነ ሰላም
ታዬን ያድርሱልኝ ። እባክዎን ፤ አደራ እንዳይዘነጉ» በማ
ለት ሳሻ እናትን ጠየቀቻት ።

እጅዋ ከበሩ መቀርቀርያ ላይ እንደሆነ ሳሻ ድን
ገት ዞር አለችና —

«ልሳምዎትን?» አለች ።

እናት ምንም ሳትናገር እቅፍ አደረገቻትና ስሜት
ባልተለየው ሁኔታ ሳመቻት ።

«አመሰግናለሁኝ» በማለት ሳሻ ጭንቅላቷን ነቅነቅ ካደረገች በኋላ ወጥታ ሄደች ።

እናት ወደክፍሉ ገባችና በመጨነቅ ስሜት በመስኮቱ በኩል ውጪ-ውጪውን ትመለከት ጀመር ። በጭለማው ውስጥ ርጥበት ያልተለየው በረዶ ይወርዳል ።

«ኧረ ለመሆኑ እኑ ፕሮዞሮቭስን ያስታውሷቸዋልን?» በማለት የጎር ጠየቀ ።

የጎር ሻዩን ፉ-ት ሲል ድምጽ እያሰማ እግሮቹን በርገድ አድርጎ ተቀምጦአል ። ፊቱ የቀላና የረጠበ ሲሆን ቅር ያለመሰኘት መልክ ይታይበታል ።

«አዎን እንጂ ፥ አስታውሳቸዋለሁኝ » በማለት ለወሬ በመጓጓት መንፈስ ወደ ጠረጴዛው ጠጋ አለች ። እናት ተቀመጠችና የጎርን ከፉ ብሎአት ትመለከት ነበር ።

«አሄ-ሄ! ይቺ ሳሻ እንዴት አድርጋ ከተማ ትደርስ ይሆን?» በማለት እናት ተናገረች ።

«ትደክማለች ። እሥር-ቤት ምንም ያስገኘላት ፋይዳ የለም ። ቀደም ሲል ጠንካራ ልጃገረድ ነበረች ። ከዚህም በስተቀር አስተዳደጓ የተቀማጠለ የመኳንንት ቤት አስተዳደግ ነበር ። አሁን ግን ሳንባዋን ምች ሳይመታው የቀረ አይመስልም » በማለት የጎር ተናገረ ።

«ለመሆኑ የማን ልጅ ነች?» በማለት እናት ለስለስ ባለ የርኅራኄ ድምጽ ጠየቀች ።

«የአንድ ባለርስት ልጅ ነች ። እርሷ እንደምታወራው ከሆነ ፤ አባቷ አሳማ እንጂ ሰው ነው ማለት አይቻልም ። ለመሆኑ ሊጋቡ እንደሚፈልጉ ያውቃሉን?» በማለት የጎር ተናገረ ።

«እነማን?» በማለት እናት ጠየቀች ።

«እርሷና ፓቬል ። እንደሚያዩት ግን ሊሳካላቸው



አልቻለም ። እርሱ ከእሥር ቤት ሲወጣ እርሷ ወደ እሥር ቤት ትገባለች ። እርሷ ስትወጣም እርሱ ይገባል...» በማለት ተናገረ ።

«ይኸንን አላወቅሁኝም ነበር ። ፓቬል ስለራሱ ምንም አይናገርም...» በማለት እናት ጥቂት ዝም ካለች በኋላ ተናገረች ።

ይኸን ከሰማች በኋላ ለልጃገረዲቷ እጅግ ርኅራኄ በተመላበት መንፈስ ታስብላት ጀመር ። ወደ እንግዳዋም ሳታስበው ዞር በማለት በመከፋት ሁኔታ ጮኻ የሚከተለውን ተናገረችው —

«ምነው ምን ነበረበት እቤቷ ድረስ ብታደርሳት?» አለችው ። እርሱም —

«ይኸን ማድረግ አልችልም ። እዚህ ሠፈርተኛው ውስጥ ማከናወን ያለብኝ ተግባር እጅግ ብዙ ነው ። ጧት ከማለዳ ጀምሬ ከአንዱ ቦታ ወደሌላኛው ቦታ እየተዘዋወርኩኝ ተግባሬን ማከናወን አለብኝ ። ይኸ ተግባር ደግሞ እንደኔ ትንፋሹ ቁርጥ-ቁርጥ ለሚልበት ሰው ቀላል ተግባር አይደለም » በማለት የጎር ረጋ ብሎ ተናገረ ።

«ግሩም ልጃገረድ ነች ።» በማለት የጎር ቀደም ሲል የነገራትን በአዕምሮዋ እያመላለሰች እናት ተናገረች ። ይኸንን ዜና ከልጅዋ አንደበት ሳይሆን ከሌላ በዕድ ከሆነ ሰው በመስማቷ ተከፍታና ባለመደሰት ፈርጠም ብላ ከንፈሮቿን ትነክስ ጀመር ።

«ግሩም ልጃገረድ ነች ። እርስዎም እንደሚያስቡላት ተገንዝቤዋለሁኝ ። ይኸ ዋጋ የሌለው ጉዳይ ነው ። ለእኛ አመጽ ለምናካሂደው ሁሉ እንደዚህ የሚያዝኑ ከሆነ ልብዎ መምታቱን ያቆማል ። ዕውነቱን እንናገር ከተባለ ከእኛ አመጽ ከምናካሂደው መሀከል የደላውኑሮ የሚኖር አንድም የለም ። ከጓዶቼ መካከል አንዱ አሁን በቅርቡ ከግዞት ተመለሰ ። ቀድሞ ወደሚኖርበ

ት ወደ ኒዥኒ-ኖቭጎረድ ቢሄድ ፤ ሚስቱ እና ልጁ
ስሞሌንስክ የተሰኘ ከተማ የሚጠብቁት መሆኑን
ተገነዘበ ። ወደ ስሞሌንስክ በሄደ ጊዜ ግን ሞስኮ ከተ
ማ እሥር ቤት ታሥረው የሚገኙ መሆናቸውን አወ
ቀ ። አሁን ወደ ሳይቤርያ ለግዞት የመሄዱ ተራ የሚ
ስቱ ተራ ነው ። እኔም እጅግ ድንቅ የነበረች ሚስት
ነበረችኝ ። ይኸንን የመሰለው የእሥር ቤት እና በግዞ
ት ወደ ሳይቤርያ የመጋዝ ሥቃይ ለሞት ዳርጓት
ዛሬ ሚስቴ ሞታ የመቃብር አፈር ለብሳለች...» በማ
ለት የጎር ተናገረ ።

ሻዩን አንዴ በመጎንጨት ጠጣ አደረገና ታሪኩ
ን ማውራት ቀጠለ ። እሥራት ተፈርዶበት በእሥር
ቤት ስላሳለፋቸው ወራትና ዓመታት ፤ እንደዚሁም በግ
ዞት ሰላሳለፋቸው ጊዜያት ነገራት ። በእሥር ቤት ስለ
ሚያጋጥሙ ሥቃዮች ፤ እሥር ቤት ስለመደብደብ ፤ ሳይቤ
ርያ በተሰኘው የግዞት ቦታ በሚኬድበት ጊዜ ስለሚ
ደርሰው ረሀብ አወራላት ። እጅግ ሥቃይና መከራ
የተመላበትን ታሪክ በሚነግራት ጊዜ ይታይበት በነ
በረው የረጋ መንፈስና ያለመኮፈስ ሁኔታ እናት እየ
ተመለከተች አደነቀችው ።

«እሺ ፤ እንግዲህ ወደዋናው ቁም-ነገር እንመለስ »
በማለት የጎር ተናገረ ።

አሁን አነጋገሩ የተለወጠ ሲሆን ፊቱም ኮስተር
አለ ። የሚበተኑትን ጽሁፎች እንዴት ወደፋብሪካው
ውስጥ ለማስገባት እንዳሰበች ጠየቃት ፤ ዝርዝር ሁኔታ
ዎችን ትንትን አድርጎ የሚያውቅ በመሆኑም እና
ት አደነቀችው ።

በዚህ ጉዳይ ላይ በሚገባ ከተነጋገሩ በኋላ ስለት
ውልድ ከተማቸው መመያየት ጀመሩ ። አነጋገሩ ቀ
ልድ የተቀላቀለው አነጋገር ነው ። እርሷ ግን ቀደም
ሲል ባሰለፈችው ኑሮዋ ትውስት ተመስጣለች ። ይ



ኸ ኑሮዋም ነጫጭ ልምጮች የሚበቅሉበት እንደ
ዚሁም ቅጠሎቹን ንፋስ በቀላሉ የሚያወዛውዛቸው
ዛፎች የሚወዛወዙበት ረግረጋማ መሬት መሰላት ። የአ
ርዘ-ሊባኖስ ዛፍ የሚመስሉት ዛፎች የሚበቅሉትና
የሚያድጉት ዝግ ብለው ሲሆን ለአምስት ዓመት
ያህል ቆይተው በረግረጋማ መሬት ላይ በስብሰው ወ
ደቁ ። ይኸ ሁኔታ በሃሣቧ እንደ ስዕል ሁኖ ያየች
ው ሲሆን ድርጊቱም ልቧን በመንካት አሳዘናት ። እን
ደገና በሃሣቧ ውስጥ የአንዲት ኮስታራና ቁጡ መል
ክ ያላት ወጣት ልጃገረድ መልክ ይታያት ጀመር ።
ብቻዋን ሁናና ተዳክማ ርጥብ በረዶ በሚወርድበት
መንገድ ትጓዛለች ። የእናት ልጅም በእሥር ቤት
ይገኝ መስሎ ታያት ። ምናልባትም ገና እንቅልፍ ሸ
ለብ አላደረገው ይሆናልና ጋደም ብሎ ያሰላስል ይሆ
ናል... ግን የሚያሰላስለው ስለርሷ ስለእናቱ አይሆን
ይሆናል ። አሁን ይበልጥ አጥብቆ የሚወዳት ልጃገረድ
አለችው ። እንደ ተባዘተ ደመና ነፍሷን ጨለማ ውስ
ጥ በመጠቅለል ስሜት የሚነኩ ሃሣቦች በአዕምሮዋ
ይመላለሱ ጀመር...

«እናት ደክሞዎታል ። ወደየመኝታችን እንሂድ» በማ
ለት የጎር ፈገግ ብሎ ተናገረ ።

«ደህና እደር» በማለት ልቧ በስሜት ተውጦና ትካ
ዜ ገብቷት ወደማዕድ ክፍል ሄደች ።

በማግስቱ ጧት ቁርስ ላይ የጎር የሚከተለውን
ተናገረ —

«እርስዎን ቢይዙዎትና እነዚህን የከሃዲዎች ተበታ
ኝ ወረቀቶች ከየት ነው ያመጡት ተብለው ቢጠየ
ቁ ለመሆኑ ምን ሊመልሱ ነው?» አላት ።

«እናንተን ምንም የሚያገባችሁ ነገር የለም አላቸ
ዋለሁኝ » በማለት መለሰች ።

«በዚህ አባባልዎ እነርሱ የሚስማሙ አይመስለ

ኝም ። ጉዳዩ የሚያገባቸው መሆኑን እነርሱ አሳምረው ያውቁታል ። ለረጅም ጊዜ እና ጠበቅ አድርገውም ጥያቄዎቻቸውን ለርስዎ ማቅረባቸውን ይቀጥላሉ!» በማለት በእናት አመላለስ የማይስማማ መሆኑን ገል ጾ ተናገረ ።

«የፈለጉትን ጥያቄ ያቅርቡልኝ እንጂ እኔ እንደ ሆን አንዳችም ነገር አልነግራቸውም!» አለች ።

«እሥር ቤት ይጨምሩዎታል!» አላት ።

«ታዲያ ቢያሥሩኝስ? ለዚህ በመብቃቴ ፈጣሪዬን አመሰግነዋለሁኛ! እኔን ማን ይፈልገኛል? ፈላጊም የለ ኝ! የሚያሰቃዩኝም አይመስለኝም ። እነርሱ እንደሚሉት ከሆነ...» ብላ ሳትጨርስ —

«እ! ሀ! ሀ! አይ አያሰቃዩዎትም ። ይሁን እንጂ ጥሩ ሰዎች ራሳቸውን ማዳን አለባቸው...» በማለት የእና ትን ሁኔታ በማጥናት መልክ ተመስጦ ተናገረ ።

«አንተ ይኸንን መናገርህ ጥሩ ሰው ብትሆን ነው!» በማለት ፈገግ ብላ ተናገረች ።

የጎር መልስ ሳይሰጥ ክፍሉ ውስጥ ተንጎራደደ ። ከዚያም ወደ እናት ቀረብ አለና የሚከተለውን ተና ገረ —

«እናት ሆይ ፤ ጉዳዩ ከባድ ጉዳይ ነው ። ለርስዎ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ አውቃለሁኝ!» አለ ። እናት ም እጅዋን እያወዛወዘች ፤

«ጉዳዩ ለማንም ከባድ እንደሆነ አውቃለሁኝ ። ምናል ባትም ጉዳዩን ለሚገነዘቡት ቀለል ያለ ይሆን ይሆና ል ። ጥሩ ሰዎች ምን ለማድረግ እንደሚጥሩ እኔም ብሆን ቀስ-በቀስ እየተገነዘብኩኝ ነኝ...» አለች ።

«እናት ሆይ ፤ ይኸንን ከተገነዘቡ ፤ ማንም ይፈልግ ዎታል ። ማንም!» በማለት በጥሞና ተናገረ ።

በዐይኖቿ ቃኘት አድርጋ ተመለከተችውና ፈገግ አለች ።



ዘዴኛ በሆነ መንገድ ተበታኝ ወረቀቶቹን በማይ ታወቅ ሁኔታ በመላ ሰውነቷ ጥፍር አድርጋ በማሠር ቀትር ሲሆን ወደፋብሪካው ለመሄድ ተዘጋጀች ። ወረ ቀቶቹን አደባበቋ እጅግ ዘዴኛ በሆነ ሁኔታ በመሆኑ የጎር አደባበቋን ሲመረምር ተደንቆ ጥርሱን ቀጭ-ቀ ጭ ያደርግ ነበር ።

«ደጋግ ጀርመኖች ደንበኛን ሙሉ ቢራ ከጠጡ በ ኋላ 'ዜር ጉት!' በማለት የጠጡትን የቢራ ጣዕም ያደ ንቃሉ ። እናት ሆይ ሥነ ጽሁፍ በርስዎ ላይ ያስከተ ለው አንዳችም ለውጥ የለም! አሁን እንደዚህ ለሚያ ይዎ ያው እንደቀድሞዎ ደግ ፤ መካከለኛ ዕድሜ ያለዎት ፤ ውፋሬ የጀመረዎት ቁመተ-ረዥም ሴት ነዎት! የርስዎን ጅምር አምላክ ይባርከው!...» በማለት ተናገረ ።

ከግማሽ ሰዓት በኋላ የተሸከመቻቸው ቅርጫቶች ስለከበዷት ጎበጥ ብላ ፤ ረጋ ባለ እና ሳትረበሽም በራ ሷ በመተማመን መንፈስ ጸንታ ከፋብሪካው ደጃፍ ደረሰች ። ሁለት ዘበኞች የፋብሪካውን ቅጥር-ግቢ የሚ ገባውን ሁሉ ፈተሽ-ፈተሽ እያደረጉ የሚያሳልፉ ሲሆ ን ፤ በሚይዟቸው ሰዎች እና በፋብሪካው ሠራተኞች ም የስድብ ናዳ ይንጎዳጎድባቸው ነበር ። በአንዱ አኳ ያ በኩል አንድ ፖሊስ እና አንድ ሌላ እግረ-ቀጭን የሆነ እና ፊቱ በርበሬ የመሰለ ዐይኖቹ ወዲያ-ወዲህ የሚቃኙ ሰው ቆሞአል ። እናት ሳጠራዎቹን የተሸከመ ችበትን እንጨት ካንደኛው ትከሻዋ ወደሌላኛው ትከ ሻዋ እያመላለሰች ይኸንን እግረ-ቀጭኑን ሰው ሰላይ ሳይሆን አይቀርም ብላ በማሰብ ቁልቁል ትመለከ ታለች ።

«እናንተ ጭራቆች መፈተሽ ያለባችሁ ኪሳችንን ሳይሆን ጭንቅላታችንን ነው» በማለት ልብሱን ነካ ነካ በማድረግ የሚፈትሹትን ዘበኞች አንድ ፀጉሩን

ረድፍ-ረድፍ እያበጀ ያስተኛ ረጂም ወጣት ሠራተኛ ተናገረ ።

«ጭንቅላታችሁ ቅማል እንጂ ሌላ ምንም የያዘው ነገር የለም » በማለት ከዘበኞቹ መካከል አንዱ መለሰለት ።

«እንግዳውማ ቅማሎቹን እያደናችሁ እኛን ተዉና!» በማለት ወዝ-አደሩ መለሰለት ።

ሰላዩ ወዝ አደሩን ከፍ-ዝቅ አድርጎ በማንጓጠጥ ከተመለከተው በኋላ በንቀት መልክ ምራቁን አክ ብሎ ተፋ ።

«ኧረ አሳልፉኝ ። በዚህ በተሸከምኩት ሸክም ትከሻዬ ሊወልቅ መድረሱን አታዩምን?» በማለት እናት ተናገረች ።

«ይለፉ! ይለፉ! ደግሞ ርስዎም እንዳቅምዎ የበኩልዎን መናገርዎ ነው!» በማለት በቅሬታ መልክ ዘበኛው እናትን እንድታልፍ ፈቀደላት ።

እናት ከቦታዋ እንደደረሰች ቅርጫቶቿን መሬት ላይ አስቀምጣ ከፊቷ ላይ ላቧን ጠራርጋ ግራ-ቀኙን ተመለከተች ።

ሁለቱም ሜካኒኮች የሆኑት የጉሴቭ ልጆች ወደርሷ ዘንድ መጡ ።

«የሚበላ ፒሮጊ አለዎትን?» በማለት ታላቀየው ወንድም ቫሲሊ ጠየቃት ።

«ነገ ነው የሚኖረኝ » በማለት መለሰችለት ።

ይኸ የምሥጢር መነጋገርያ ኮድ ነበር ። በአመላለሷ ወንድማማቾቹ ተደስተው በፈገግታ ተመሉ ።

«እሰይ የኔ እናት!» በማለት ኢቫን ፈነደቀ ።

ቫሲሊ ቅርጫቱን አሾልቆ ለማየት ቁጭ ሲል አንድ ፓኬት ሙሉ ተበታኝ ጋዜጦችን በኮቱ የውስጥ ኪስ ጨመረችለት ።

«ኢቫን ፤ እቤት ባንሄድ ይሻላል ። ከእርሳቸው ላይ



የሚበላ ምግብ እንገዛለን ። እኚህን አዲስ ምግብ ሻጭ መርዳት ያስፈልጋል...» በማለት ድምጹን ከፍ አድርጎ ተናገረ ። ይኸንን በሚናገርበት ጊዜም ሌላ ፓኬት ሙሉ ተበታኝ ጋዜጣ ቡት ጨማው ውስጥ ከተተ ።

«ኧረ እባክህን? ይሻላል እንዴ!» በማለት ኢቫን እየሳቀ ጠየቀ ።

እናት በመጠንቀቅ ሁኔታ ግራ-ቀኙን ተመለከተች ።

«መረቅ ፈላጊ! ትኩስ ፓስታ ስፓጌቲ!» በማለት እናት ድምጿን ከፍ አድርጋ ትጠይቅ ጀመር ።

ሊነቃባት በማይችል ሁኔታ ጋዜጦቹን ተራ-በተራ ከየተቀመጡበት ቦታ ከነፓኬታቸው እያወጣች ለወንድማማቾቹ ሰጠቻቸው ። እያንዳንዱን ፓኬት ወደ ወንድማማቾቹ ባስተላለፈችላቸው ቁጥር በጭለማ ቤት ውስጥ የተጫረ ክብሪት ጭለማውን ቤት ቦግ እንደሚያደርገው ሁሉ ፤ የመኮንኑ ቢጫ ፊት በአዕምሮዋ ውስጥ በመመላለስ ቦግ እያለ ይታያት ነበር ። ከዚያም ራሷ ከራሷው ጋር በመነጋገር — «ያውልህ! ውሰድ ያንን! የኔ ደግ!ያንንም ውሰድ! እንካ ይኸንንም ውሰድ!» አለች ።

ወዝ-አደሮቹ ሳህኖቻቸውን እየያዙ መጡ ። ከመካከላቸው አንደኛው ቀረብ ብሎ በተጠጋ ቁጥር ኢቫን ጉሴቭ ድምጹን ከፍ አድርጎ በመሳቅ ምልክት የሚሰጣት ሲሆን ፤ እናትም ፓኬቶቹን መስጠቷን ረጋ ባለ መንፈስ ታቆምና መረቋን ለመቅዳት ጭልፋዋን ታነሳለች ።

«ፔላጊያ ኒሎቭና! እንዴት ነው እባክዎን! እንዴ ፤ ይገርማል እኮ! በጣም ቀልጣፋ አይደሉም እንዴ!» በማለት ወንድማማቾቹ ይስቁባታል ።

«ችግር ነው ለዚህ ያደረሳቸው ። እነዚያ ርጉሞች ሠርቶ-የሚያበላቸውን አሠሩባቸው! እስኪ የሦስት ኮፔ

ከ መረቅ እንግዛቸው ። እናት ፤ አያስቡ ግዴለዎትም ይላመዱታል!» በማለት ከጥግ በኩል ቁሞ የነበረ አንድ ብረት አቅላጭ ወዝ-አደር ተናገረ ።

«ስለበጎ አነጋገርዎ እመሠግንዎታለሁኝ!» በማለት እናት ፈገግ ብላ ተናገረች ። ብረት አቅላጩም —

«ለምኑ ብለው ነው የሚያመሠግኑኝ ጥቂት በጎ ቃላት መናገር ምንም ዋጋ አይወጣበትም» በማለት ቀስ እያለ በመናገር መንገዱን ሄደ ።

«ትኩስ መረቅ! ፓስታ ስፓጌቲ! የዳቦ መረቅ! » እያለች እናት ጎላ ያለ ድምፅ ለገዥዎች ታሰማ ጀመር ።

ተበታኝ ጋዜጦቹን ለማድረስ የመጀመርያ ልምዷ እንዴት እንደነበረ ለልጅዋ እንደምን አድርጋ እንደምታስረዳው ማሰቧን የቀጠለች ሲሆን በሌላ ሃሳቧ ደግሞ ግራ የገባውና የተቆጣው ቢጫማው መኰንን ድቅን ብሎ ታያት ። ጥቁር ሪዙ ግራ ገብቶት ይንከራተት የነበረ ሲሆን ፤ ከከናፍሮቹ ውስጥም ነጫጭ ጥርሶቹ ብልጭ ብለው ይታዩ ነበር ። ደስታ ልቧ ውስጥ እንደወፍ ይዘምር ጀመር ። የምግብ መሸጥ ሥራዋን እያካሄደችም ፤ ለመኰንኑ የምትመልስለትን መልስ በአዕምሮዋ እያንገዋለለች ቅንድቦቿን ከፍ አድርጋ «እንካ ይኸንንም ውሰድ!» በማለት ከራሷ ጋር በሃሣቧ ትነጋገር ነበር ።

16

በዚያን ዕለት ምሽት ከውጪ በኩል ጭቃ ውስጥ ጮቅ-ጮቅ የሚል የፈረስ ኮቴ ድምፅ ሰማች ። ከዚያም ካሁን ቀደም አዘውትራ የምትሰማው የነበረ ዓይነት ድምፅ ተሰማት ። ከነበረችበት አፈፍ ብላ በ



መነሳት በማዕድ ክፍሉ በኩል አድርጋ ወደ በራፉ በፍጥነት እየተራመደች ሄደች ። በራፉ መግቢያ ላይ ፈጠን ያለ የእግር እርምጃ ድምፅ ተሰማ ። የምታየው ነገር ሁሉ ጭለማ ሆነባት ። በራፉን በእግርዋ ከፈተችና መቃኑን ተደግፋ ቆመች ።

«እንደምን አመሹ ፤ እምዬ» በማለት ከዚህ ቀደም የለመደችውን ድምፅ ሰማች ። ከዚያም ረዣዥም እና ቀጫጭን የሆኑት ክንዶቹ ትከሻዎቿ ላይ ጥምጥም አሉ ።

አንድሬይን በማየቷ መጀመርያ የሀዘን ከዚያም የደስታ ስሜት ተከታትሎ ዋጣት ። እነዚህ ሁለት ስሜቶች በአንድነት በመዋሃድ ከፍተኛ የጋለ ስሜት አሳደሩባት ። ይኸውም ስሜት ሁለንተናዋን በማሞቅ ሙቀት ያሳደረባት ስሜቷንም ትከሻዋ ላይ በተዘረጉት የአንድሬይ ክንዶች ላይ በሚገኘው ጉንጪ መጋል ተገነዘበችው ። በሚንቀጠቀጡ ክንዶቹ ጥብቅ አድርጎ አቀፋት ። እናት ቀስ እያለች በማልቀስ እንባዋን ታነባ ጀመር ። እርሱም ዘንበል ብለው የነበሩትን ፀጉሮቿን ቀና-ቀና እያደረገ ለርሷ ጆሮ የሙዚቃ ድምፅ በመሰላት የለሰለሰ ድምፅ —

«አያልቅሱ እምዬ! ልብዎን አያስቃዩት ። ከታሠረበት ቶሎ እንደሚፈቱት እርግጥ ነው ። እርሱን በማሠር እነርሱ የሚያገኙት አንዳችም ነገር የለም ። የታሠሩት ወገኖቻችን ሁሉ አንዳችም ነገር ባለመናገር እንደተጠበሰ አሣ ጭጭ-ምጭጭ ብለዋል...» በማለት ተናገረ ።

ክንዱን በእናት ትከዋሻዎች ላይ አውሎ ወደሌላኛው ክፍል ወሰዳት ። እንደ ትንሽ ድንቢጥ በፍጥነት እየተንቀሳቀሰችና እንባዎቿንም ከዐይኖቿ ላይ እየጠራረገች የሚናገራቸውን እያንዳንዳቸውን ቃላት እንደተራበ ሰው አንድም ሳታስቀር አፈፍ አድርጋ

በመዋጥ እያዳመጠችው ይበልጥ በመታከክ ትጠጋው ነበር ።

«ፓቬል ሰላምታ አቅርቦአል ። ደህንነትና ደስታ ለልተለዩትም ። እዚያ አሁን እርሱ ያለበት ቦታ በሰው ብዛት የተጣበበ ነው ። ከከተማውና ከእኛ የመኖርያ ሠፈር ከመቶ በላይ ሰዎችን ይዘው ያሠሩ ሲሆን በአንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ ከሦስት እስከ አራት ሰው ታሥሮአል ። የእሥር-ቤቱ ኃላፊዎች ጥሩ ሰዎች ናቸው ። ይሁን እንጂ እነዚያ ሰይጣን የሆኑ ፖሊሶች በረበረቡባቸው የሥራ ብዛት ተዳክመዋል ። አዛገሮቹ ይኸንን ያህልም በእኛ ላይ ጠንካሮች አይደሉም ። 'ከቡራን ፤ እኛን አደጋ ላይ እንዳትጥሉን እባካችሁ ዝም በሉ' በማለት አዘውትረው ይናገራሉ ። ከእነርሱ በኩል ለእኛ ማናቸውም ነገር ቢሆን በጥሩ ሁኔታ ይከናወናል ። እሥር-ቤት ያሉት እሥረኞች እርስ-በርስ ይወያያሉ ። መጻሕፍት ይለዋወጣሉ ። ምግቦች ይከፋፈላሉ ። እሥር-ቤቱ ያረጀ እና የቆሸሸ እሥር-ቤት ቢሆንም ለእሥረኞች ምቹ በመሆኑ ጥሩ እሥር-ቤት ነው! በወንጀል የታሠሩት እሥረኞችም ከመካከላቸው ጥሩ ሰዎች ያሉባቸው ሲሆኑ እኛንም በብዙ መንገድ ይረዱናል ። ቡኪን እና እኔ ፤ እንደዚሁም ሌሎች አራት ሰዎች ተለቀቅን ። በቅርቡም የፓቬል ተራ ይደርሳል ። ቬሶቭሺኮቭ የሚለቀቀው መጨረሻ ላይ ነው ፤ ክፉኛ የሰደባቸው በመሆኑ ሁሉም በክፉ ዓይን ይመለከቱታል ። ፖሊሶቹ እርሱን ለማየት አይሹም ። በእነዚህ በመጪው ቅርብ ቀናት ለፍርድ ያቀርቡታል ። ወይንም በድብደባ ያሰቃዩታል ። ይኸንን ጠባዩን እንዲተው ፓቬል ሁልጊዜም ይነግረዋል ። የርሱ መሳደብ አንዳችም የሚያስገኘው ለውጥ እንደሌለ ይነግረዋል ። እርሱ ግን 'ከቁስል ሰንኮፍ ላይ ቅርፊት እንደሚቀረፍ ፤ እነርሱንም ከምድረ-ገጽ እቀራርፋቸዋለሁኝ!' እያለ ይሳደ



ባል ። ፓቬል አመሉን አሳምሮ የሚገኝ ሲሆን ሃሣበ-ጽኑ እና ርጉ ነው ። በቅርቡ እንደሚፈቱት እርግጠኛ ነኝ » በማለት አንድሬይ ተናገረ ።

«በቅርቡ ይፈታል! እርግጠኛ ነኝ በቅርቡ እንደሚፈታ!» በማለት ተጽናንታ ለስለስ ባለ ሁኔታ እናት ፈገግ አለች ።

«ይኸው እንግዲህ ማናቸውም ነገር ጥሩ ነው ። እስኪ አንድ ብርጭቆ ሻይ ይስጡኝና እርስዎ እስከአሁን እንዴት እንደሆኑ ይንገሩኝ ።» አለ ።

ይኸ ዘንካታ ወጣት ለእናት ባለው ፍቅር ዓይኖቹ ፍክት ብለው በርተው እና ሀዘን የተመላበት ፊቱም በፈገግታ ተውጦ እርሷን-እርሷን ይመለከታል ። አስቂኝ በሆነ ሁኔታ በጢም የተወረረውን ሰልካካ ፊቱን እናት አተኩራ እያስተዋለች —

«አንድርዬ እወድሃለሁኝ » አለችው ። እርሱም ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ሁኖ ወደኋላና ወደፊት እየተወዛወዘ —

«እኔን ለማስደሰት ትንሽ ነገር ይበቃል ። እንደሚወዱኝ አውቃለሁኝ ። የርስዎ ልብ ሁሉንም ሰው ለመውደድ ሰፊ ነው!» በማለት ተናገረ ።

«እኔ ግን አንተን የምወድህ በተለይ ነው ። እናት ቢኖርህ ኖሮ በአንተ በልጃቸው ምክንያት ሁሉም ሰው በእናትህ ላይ ይቀናባቸው ነበር ።» አለችው ።

ኾኾል ራሱን ነቅነቅ እያደረገ በእጆቹ ፀጉሩን ያሻሽ ጀመር ።

«የትም ትሁን የት እኔ እናት አለችኝ» በማለት ድምፁን ዝቅ አድርጎ ተናገረ ።

«ዛሬ ምን እንዳከናወንኩኝ ገምት እስኪ!» በማለት በአንክሮ በመናገር እና ሁኔታውንም ስታደንቀው ትንሽ ጨመርመር እያደረገችበት ተበታኝ ጋዜጦቹን

እንደምን አድርጋ ወደ ፋብሪካው እንዳስገባቻቸው
በስሜት ሁኔታ ገለጸችለት ።

መጀመርያ በመደነቅ ዓይኖቹን ብልጥጥ አድርጎ
ከፈተ ። በኋላ ደግሞ በሳቅ ተንከተከተ ።

«ኧረግ-ኧረግ! ይኸማ መች ቀልድ ነው! ትልቅ
ጉዳይ እኮ ነው! አቤት ፣ ፓቬል እንደምን ይደሰት! እው
ን? እምዬ ለፓቬልም ሆነ ለማንም ቢሆን ግሩም-ድን
ቅ ተግባር ነው!» በማለት ተናገረ ።

መላ ሰውነቱ ወደፊት እና ወደ ኋላ እተቀመጠ
በት ሁኖ ይወዛወዝ ነበር ። ጣቶቹን ያንቋቋ ከመሆኑ
ም በስተቀር በደስታ ተውጦ ማፏጨት የጀመረ
ሲሆን እናትም አፀፋውን በመመለስ አብራው
በልቧ ታዜም ጀመር ።

ልቧ ውስጥ የሚገኘው የማዕበል ደጃፍ ተከፍ
ቶ ፍጹም በሆነ ደስታ የምትናገራቸው ቃላቶች ከል
ቧ ውስጥ እየዘለሉና እየተፈናጠሩ በመውጣት —

«አንት የተባረክ አንድርዬ! ስለ እኔ ኑሮ በማስብ
በት ጊዜ ፣ ዋ መሀሪው አምላክ! ለመሆኑ እኖር የነበረ
ው ለምንድን ነበር? በአገልጋይነት መንገላታት እና
በዱላ መነረት ነበር ። ከባሌ በስተቀር አንዳችም ሌላ
ሰው አላውቅም ፣ ከፍርሀት በስተቀር አንዳችም የማው
ቀው ሌላ ነገር አልነበረም! ፓቬል እንዴት እንዳደገ
እንኳን አላስተዋልኩኝም ። ባለቤቴ በሕይወቱ እያለ
ፓቬልን ልውደደው ወይንም አልውደደው ለይቼ እን
ኳን አላውቅም ነበር ። ሃሣቤና ሥጋቴ አንድ ነገር
ላይ ብቻ ያተኮረ ነበር ። ያንን ጨካኝ ባለቤቴን ምግ
ብ አዘጋጅቶ መመገብ ፣ እንዳይቆጣና እንዳይደበድበ
ኝ የደስታ ፍላጎቶቹን ሁሉ ገና ሳይጠይቀኝ ማሟላት ፣
አንዴም እንኳን ቢሆን ቅር እንዳይለው ማድረግ
ነበር! ቅር ብሎት ያልነበረበትን ጊዜ ግን ፍጹም አላ
ስታውስም ። የሚደበድበው እኔን ሚስቱን ሳይሆን ፣



አንድ ቂም በቀል የያዘበትን ሌላ ሰው እንደሚደበ
ድብ ያህል ቆጥሮ ይደበድበኝ ነበር ። ሃያ ዓመት ሙ
ሉ ይኸንን መሳይ ኑሮ ኖርኩኝ! ከማግባቴ በፊት
የነበረኝን የአኗኗር ሁኔታ ጭርሱኑ እርግፍ አድር
ጌ ረሳሁኝ ። የቀድሞ ኑሮዬን ወደኋላ መለስ ብዬ
ለማስታወስ ስሞክር ሁሉም ነገር ጭልም ብሎ ይጋ
ረድብኝ ነበር ። የጎር ኢቫኖቪች እዚህ መጥቶ ነበር ።
ሁለታችንም የአንድ መንደር ሰዎች ነን ። ስለመንደራ
ችን ብዙ ነገሮች አወራልኝ ። እኔስ? ቤታችን እና ሰ
ዎች ትዝ ይሉኛል ። ይሁን እንጂ ከመንደራችን ሰዎ
ች መካከል የማውቃቸው እንዴት ይኖሩ እንደነበረ ፣
ወይንም ምን-ምን ይናገሩ እንደነበረ ፣ ወይንም መጨረ
ሻቸው ምን እንደደረሰ ከቶውንም ትዝ አይለኝም!
እሳት ትዝ ይለኛል ። ሁለት እሳቶች ። እኔ ውስጥ የሚ
ገኘው ማናቸውም ነገር በድብደባ እንደተገደለ እና
ነፍሴም በመደንቆር እና በመታወር ታሽጋ የቀረች
ይመስለኛል...» በማለት ተናገረች ።

ከባሕር ውስጥ የወጣች አሣ ትመስል አየር ለመ
ሳብ ዙርያዋን ቃኘች ። ከዚያም ጥቂት ወደፊቷ ዘንበ
ል ብላ እና ድምጿንም ዝቅ አድርጋ ንግግሯን
እንደሚከተለው ቀጠለች ፡ —

«ባለቤቴ ሞተ ። እኔም ሃሣቤን ሁሉ ወደልጄ መ
ለስኩኝ ። ይሁን እንጂ ፣ እርሱ ደግሞ በዚህ ተግባሩ
ተጠምዶ ነበር ። ልቋቋመው የማልችለው ሁኔታ ገጠ
መኝ ። እጅግ በጣም እሰጋ ጀመር ... በርሱ ላይ አንዳ
ች አደጋ ቢደርስበት እኔ እንዴት አድርጌ ልኖር
ነው? ኧረ የተቀበልኩት ሥቃይ እንደምን ያለ ነበር!
እንደው ምን ይደርስበት ይሆን ብዬ ሳስብ ልቤ በሰ
ቀቀን ይፈርስ ነበር...» በማለት ተናገረች ።

ለጥቂት ጊዜ ዝም አለች ። ከዚያም ራሷን በመነቅ
ነቅ ትልቅ ቁም ነገር ባለው አነጋገር —

«የእኛ የሴቶች ፍቅርን የመሰለ ፍቅር ብቻ አይደለም… እኛ ሴቶች ለራሳችን የምንሻው ሲኖር ለራሳችን ስንል እናፈቅራለን ። እንዲህ አድርገህ ለእናትህ የምታዝነውን አንተን ስመለከትህ ግን ፤ እናትህ ላንተ ያደረጉልህ ነገር ከቶ የትኛው ነው? ለሌሎች ሲሉ ሥቃይ የሚቀበሉት የተቀሩት ሰዎችም በሙሉ … ወደ እሥር-ቤት የሚወረወሩት ። ወደ ሳይቤርያ በግዞት የሚጋዙት … የሚሞቱት … በጭቃ ውስጥ ፤ በዝናብ ውስጥ በበረዶ ውስጥ ፤ ከከተማው እስከቤታችን ርቀቱ ሰባት ቨርስታ* ነው! ይኸንን ሁሉ ርቀት ብቻቸውን በውድቅት ጭለማ ወጣት ልጃገረዶች የሚጓዙት! ይኸንን እንዲፈጽሙ የሚያደርጋቸው ከቶውኑስ ምንድነው? የዚህ ምክንያቱም ታላቅ የሆነ ንፁሕ ፍቅር ስለአላቸው ፤ የቆሙለት ዕምነት ስላላቸው ነው — ጥልቅ ዕምነት ስላላቸው ነው አንድርዬ ። እኔን በሚመለከት ረገድ ግን — እንደዚያ ማፍቀር አልችልም! እኔ የማፈቅረው የእኔ የራሴ የሆነውን ፤ ለእኔ ቅርብ የሆነውን ብቻ ነው!» በማለት ተናገረች ።

ኾኾልም ፊቱን ከእናት መለስ አድርጎ እና እንደዘወትር ልምዱም ፀጉሩን ፤ ፊቱንና ዐይኖቹን በቅጡ እያሻሸ ፡ —

«የለም ፤ እርስዎ የሚያፈቅሩት የራስዎ የሆነውን እና ቅርብዎ የሆነውን ብቻ አይደለም ። ማንም ቢሆን ለርሱ ቅርብ የሆነውን ያፈቅራል ። የአንድ ሰው ልብ ትልቅ ሲሆን ሩቅ የሆኑ ነገሮችም እኮ ቅርብ ናቸው! እርስዎ ያለዎት ልብ ትልቅ የእናትነት ልብ በመሆኑ ታላላቅ ተግባሮችን ማከናወን ይችላሉ ።» በማለት ተናገረ ።

---

* ቨርስታ — የርቀት መለኪያ ። ካንድ ኪሎሜትር ፡ በላይ ነው ። (ተርጓሚው)



«እስኪ እንዳፍህ አርጎት የእግዚአብሔር ፈቃድ ይጨመርበት!» አለችና ተነፈሰች ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ ፡ —

«ይኸንን ዓይነቱ አዲስ ሕይወት ለእኔ ጥሩ ሕይወት ሁኖ ይሰማኛል ። አንድሬይ ፤ ምናልባትም ከፓሻ የበለጠ አሁን አፈቅርሃለሁኝ ። እርሱ ብዙውን ነገር ለራሱ ደብቆ ይይዛል … እስኪ ልብ ብለህ አስተውል ። ሳሻን ለማግባት ይፈልጋል ። ይሁን እንጂ ፤ ለእኔ ለእናቱ አንድም ቃል አልነገረኝም…» በማለት ተናገረች ።

«አይ ፤ ይሄ ልክ አይደለም » በማለት ኾኾል በተቃውሞ ሁኔታ ተናገረ ። ከዚያም ንግግሩን በመቀጠል ፡—

«ይኸ ልክ እንዳልሆነ በእርግጠኝነት አውቃለሁኝ ። እርሱ ይወዳታል ። እርሷም ትወደዋለች ። ይኸ እርግጥ ነው ። ነገር ግን መቸም ቢሆን አይጋቡም ። እርሷ ለመጋባት ትሻለች ። እርሱ ግን አይሻም ።»

«እ-ሃ! ነው እንዴ?» በማለት ያዘኑ ዓይኖቿ ኾኾል ላይ አርፈው እና በሃሳብም ተውጣ ተናገረች ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ ፡ —

«ለካ እንደዚህ ነው! ሰዎች የገዛ ራሳቸውን ደስታ ይቃወማሉ …» አለች ።

«ፓቬል እንደማንኛውም ሰው አይደለም!» ኾኾል ሲናገር ድምፁ ለስለስ ብሎአል ። «ፓቬል መንፈሱ እንደ ብረት የጠነከረ ነው…» በማለት ተናገረ ።

«አሁን ግን እሥር-ቤት ታሥሮ ተቀምጧል!» በማለት እናት እያሰላሰለች ተናገረች ። «ሁኔታው ያስፈራል ። ነገር ግን ይኸንን ያህል በጣም የሚያስፈራ አይደለም ። ሕይወት የተለየ ሁኖአል ። የእኔ ፍርሀትም የተለየ ሁኖአል ። አሁን እኔ የምሠጋው ለማንም ነው ። ልቤም ከቀድሞው የተለየ ነው ። ምክንያቱም ነፍሴ የልቤን ዓይኖች ስለከፈተችልኝ እና ውጪውንም መመልከት ልቤ ስለቻለ ሲሆን ፤ ምንም እንኳን

ልቤ የሚተክዝ ቢሆንም ተደሳች ነው ። እኔ የማልገነ
ዘባቸው አያሌ ብዙ ጉዳዮች አሉ ። በፈጣሪ አምላክ
የማታምኑ መሆናችሁ ደግሞ ለእኔ መራራ የሆነብኝ
ጉዳይ ነው ። እኔ ግን ለዚህ ምን ማድረግ እችላለሁ
ኝ? ሁላችሁም በእርግጥ ጥሩ ሰዎች መሆናችሁን አያ
ለሁኝ ። ለሌሎች ሰዎች ደኅንነት ስትሉ ከባድ የሆነ
ኑሮን ለመኖር ወስናችኋል ። ለዕውነት ስትሉ አስቸጋ
ሪ የሆነ ኑሮን ለመኖር ወስናችኋል ። እና አሁን እና
ንተ የቆማችሁለትን ዕውነት ተገንዝቤአለሁኝ — እር
ሱም — ሀብታም ሰዎች እስካሉ ድረስ ተራ ሕዝቦ
ች አንዳችም ነገር ቢሆን ለማግኘት አይችሉም ።
ደስታ አይኖራቸውም ። ፍትህ አይኖርም ። ከቶ አንዳች
ም ነገር! የሚል ነው ። አሁን ከእናንተ ጋር እኖራለሁ ።
ቀደም ሲል ያሳለፍኩትን ጊዜ የወጣትነት ጉልበቴ
ከእግር በታች ውሎ የተረገጠበት መሆኑን ፤ የወጣትነት
ጊዜ ልቤ በቡጢ የተቀጠቀጠበት ጊዜ መሆኑን
በአንዳንድ ምሽት ላይ ትዝ እያለኝ ሳስታውሰው
ለገዛ ራሴ የማዝን ሲሆን ምሬትም ይሰማኛል! ይሁን
እንጂ ከቀድሞው ይልቅ አሁን ኑሮ ለኔ ቀለል ያለ
ነው ። ቀስ በቀስ ራሴን በመገንዘብ ላይ ነኝ...»

ረኸሙ ፤ ቀጭኑ እና በሃሣብ ባሕር የሚዋኘው
ኾኾል ከተቀመጠበት በመነሳት እና ሲራመድም የመ
ጫሚያ ድምፅ ላለማሰማት በመጣር ከወዲያ-ወዲህ
ይንጎራደድ ጀመር ። ለስለስ ባለ አነጋገርም ፡ —

«ሃሣብዎን ያቀረቡት ግሩም በሆነ አቀራረብ
ነው! በጣም ግሩም ነው! ግጥሞ ይደርስ የነበረ ባለ
ቅኔ ወጣት አይሁድ ኬርች ከተማ ውስጥ ይኖር
ነበር ። አንድ ጊዜ የሚከተለውን ቅኔ ጽፎ ነበር ፡ —

ያለቁት ንጹሀን ያላንዳች ጥፋት ፥
ይነሳሉ ከሞት በኃይለ-ዕውነት!



«ይህንን ግጥም የጻፈው ባለቅኔም የተገደለው
ኬርች ውስጥ በፖሊሶች ነበር ። ይኸንን እንኳን እዚህ
ላይ ማንሳቱ ቦታው አይደለም! ያ ባለቅኔ ዕውነትን
ተገንዝቦ የዕውነትን ዘር በሕዝቦች መሀል ዘራ ። እር
ስዎም ከእነዚያ 'ንጹሀን' መካከል አንዲቱ ነዎት...»

እናትም ንግግሯን በመቀጠል ፡ —

«አሁን ግን እናገራለሁኝ ። የራሴን ቃላት የምናገ
ርና የማዳምጥ ሲሆን ጆሮዬን ማመንም ያስቸግረኛ
ል ። ሕይወቴን ሙሉ የማስበው ስለአንድ ነገር ነበር ።
እየአንዳንዱ ቀን እንዴት ቶሎ ሊያልፍኝ እንደሚች
ል ፤ እየአንዳንዱ ቀን ሳይታወቀኝ እንዴት ልኖረው
እንደምችል እና በዚህም ምክንያት ማንም ሊነካኝ
እንዳይችል ለማድረግ ነበር ። አሁን ግን በሌሎች ሰ
ዎች ኤስተሳሰቦች ተመልቻለሁኝ ። ምናልባትም እናን
ተ የቆማችሁለትን ዓላማ ሙሉ-በሙሉ አልገነዘበውም
ይሆናል ። ይሁን እንጂ ለእኔ ሁላችሁም ተወዳጆቼ
ናችሁ ። ለሁላችሁም ስሜት ይሰማኛል ። ሁላችሁም ደስ
ተኞች እንድትሆኑ እሻለሁኝ ። በተለይም አንተ አንድ
ርዬ!...»

አንድሬይ ወደርሷ ዘንድ ቀረበ ። ከዚያም ፡ —

«አመሰግናለሁኝ!» አላት ።

እጅዋን በእጁ ይዞ በቀስታ ካሻሸ በኋላ ወዲያውኑ
ፊጥኖ ጀርባውን መለሰ ። እናት በስሜቷ ዝላ በዝግታ
እና በዝምታ ሁኖ በልቧ ውስጥ በሚፈስሰው ቀስተ
ኛ ደስታ ታጅባ ብርጭቆዎቹን አጣጠበች ።

ኾኾል አንዴ ወደፊት አንዴም ወደኋላ እየተን
ጎራደደ ፡ —

«እምዬ ፤ ቬሶቭሺኮቭን መውደድ አለብዎት! ፋይዳ-
ቢስ የሆነው ሽማግሌ አባቱ እሥር-ቤት ነው ። ኒኮ
ላይ በመስኮቱ በኩል በተመለከተው ቁጥር መሳደቡ
ን ይጀምራል ። ይኸንን ማድረግ መጥፎ ነው! ኒኮላይ

በተፈጥሮው ደግ ነው ። ውሾችን ፤ አይጦችን ፤ ማናቸውን
ም ዓይነት እንስሶችን ይወዳል ። ሰዎችን ግን ይጠላ
ል! ሰው የቱን ያህል ብልሹ እንደሚሆን እሱን አይ
ቶ መገንዘብ ነው!»

«እናቱ እስከለምንግዜውም የለችም… አባቱ ሌባ
እና ሰካራም ነው…» በማለት እናት እየተገረመች ተ
ናገረች ።

አንድሬይ ወደ መኝታው ሲሄድ እናት ቀስ ብላ
እጅዋን በማንሳት በትዕምርተ-መስቀል አማተበችበት ።
መኝታው ላይ ግማሽ ሰዓት ያህል ከቆየ በኋላ ለስ
ለስ ባለ ድምፅ የሚከተለውን ጠየቀችው ፡ —

«አንድርዬ ፤ ተኛህ እንዴ?» አለችው ።

«አልተኛሁም ፤ ምነው?» አላት ።

«ደህና እደር!» አለችው ።

«አመሰግናለሁ ፤ እምዬ ። አመሰግናለሁ » አላት በታ
ላቅ አመሰጋገን ።

17

ፔላጊያ በማግሥቱ ከፋብሪካው በር እንደደረሰች
ዘበኞቹ ካቆሟት በኋላ ቅርጫቶቿን እንድታስቀምጥ
አዝዘዋት አጥብቀው ፈተሿት ።

«ኧረ እንዴት ነው ፤ የያዝኩት ሁሉ ምግብ ፡ ይቀዘ
ቅዝብኛል!» በማለት እነርሱ በማጎሳቆል ልብሶቿን
በመነካካት በሚፈትሿት ጊዜ ተናገረች ።

«ዝም በይ!» በማለት ዘበኛው ጮኸባት ።

«ምነው ስነግርህ ብትሰማኝ ፤ እነዚያ ሰዎች በአጥ
ሩ በኩል ነው የሚወረውሩት አልኩህ እኮ!» በማለት
ሌላኛው ዘበኛ የፔላጌያን ትከሻ እለፊ በማለት ሁ
ኔታ በመጠኑ ገፋ እያደረገ ተናገረ ።



ፔላጌያ አንዴ ፋብሪካው ቅጥር-ግቢ ከገባች በኋ
ላ መጀመርያ ወደርሷ ዘንድ የሚመጣው ሽማግሌው
ሲዞቭ ነው ።

«እናት አልሰሙምን?» በማለት ግራ ቀኙን ከቃኘ
በኋላ ሲዞቭ ተናገረ ።

«ምኑን?» አለችው ።

«እነዚያ የሚበተኑ ወረቀቶች ። ይኸው አሁንም
መበተን ጀምረዋል ። በዳቦ ላይ ጨው እንደሚነሰነስ
ሁሉ ፤ ወረቀቶቹም በየትም ቦታ እየተነሰነሱ ናቸው ።
ይኸውልዎ እንግዲህ የፈታሾቹ እና የይዞ አሣሪዎ
ቹ ጉድ! የእህቴን ልጅ ማዚንን ወስደው ያሠሩት ም
ን ባደረጋቸው ነው? የእርስዎንም ልጅ ወስደው አሰሩ
ት ። አሁን ግን ለወረቀቱ ተጠያቂዎች እነርሱ ላለመሆ
ናቸው ሁሉም ይመለከተዋል!» አለ ።

ጢሙን እያሻሸ በመደነቅ የአጠያየቅ አመለካከት
ያስተውላት ጀመር ። ከዚያም ፡ —

«ለምን እኔ ዘንድ እየመጡ አይጫወቱም? አንድ
ብቻዎን ብቸኛ ይሆናሉ…» አላት ።

ስላቀረበላት ግብዣው ካመሠገነችው በኋላ አለወት
ሮው በፋብሪካው ውስጥ የሚታየውን ትርምስ እያስተ
ዋለች የምትሸጣቸውን ምግቦች ስም በመጥራት ትጮ
ህ ጀመር ። ሁሉም በስሜት ተውጦአል ። ወንዶቹ
በየፈና-በየፈናቸው የተሰበሰቡ ሲሆኑ ከአንደኛው የፋ
ብሪካ ክፍል ወደሌላኛው በመሯሯጥ ተበታተኑ ። አን
ዳች ጠንካራ የሆነ የማይበገር ጉዳይ እየተካሄደ መ
ሆኑ ተሰማት ። በመበረታታት አነጋገር የታጀበ የፌዝ
እና የልግጫ አባባል እየተደጋገመ ይሰማ ጀመር ።
ሽማግሎቹ ሠራተኞች በማይታወቅ ሁኔታ የሸሽግ
የሥውር ሳቅ ይስቃሉ ። የፋብሪካው አለቆች የመጨ
ነቅ ሁኔታ በፊታቸው ላይ ይታይባቸዋል ። ፖሊሶች
ከወዲያ-ወዲህ የሚሯሯጡ ሲሆኑ በየቡድን በየቡድን

ሁነው የቆሙ ሠራተኞች ሲመለከቷቸውም ዞር በማለት ወይንም ንግግራቸውን በመተው ቁጡና ብስጩ የሆነው መልካቸውን እያዩ ያሳልፉዋቸዋል ።

የሠራተኞቹ መልኮች ብሩኅ ናቸው ። ፈገግ ብሎ ኋላ-ኋላው ድክ-ድክ እያለ ወንድሙ የሚከተለውን ያንን ቁመተ-ረዥሙን አዛውንት ጉሴቭን ተመልክታ ዋለች ።

የአናጺ ክፍል ኃላፊው ቫቪሎቭ እና ሰዓት ተቆጣጣሪው ኢሳይ በዝግታ ጉዞ በእናት በኩል አለፉ ። ቁመተ ድባኖው ሰዓት ተቆጣጣሪ አንገቱን የተቻለውን ያህል በመምዘዝ የአናጺ ክፍሉ ኃላፊ ጺሙን እያሻሸ በፍጥነት ሲናገር ግዙፍ የሆነ ፊቱን ለማየት ይንጠራራል ።

«ኢቫን ኢቫኖቪች ፤ የተከበሩ ዲሬክተሩ እንደገለጡት ሁሉ ምንም እንኳን አፈጻጸሙ የመንግሥትን መጥፋት የሚያስከትል ቢሆንም እነርሱ ግን በሁኔታው ያላግጣሉ ። ኢቫን ኢቫኖቪች ፤ እዚህ ማድረግ የሚያስፈልገው አረምን ማረም ሳይሆን የበቀለውን ማረስ ነው...» በማለት ኢሳይ ተናገረ ።

ቫቪሎቭ እጆቹ ከበስተጀርባው ተቆላልፈውና ጣቶቹም በመቆላለፍ ተጣምረው ኋላ-ኋላ ድክ-ድክ እያለ ይሄዳል...

«እናንት የውሾች ልጆች ሂዱና የፈለጋችሁትን ጽሁፍ አትሙ! ስለ እኔ ግን አንዳችም ቃል እንዳትተነፍሱ!» በማለት ቫቪሎቭ በጩኸት ድምፅ ተናገረ ።

ቫሲሊ ጉሴቭ ወደ እናት ዘንድ መጣ ።

«እናት ፤ ምግብዎን እንደገና ደግሜ መቅመስ እሻለሁኝ ። ምግብዎ ግሩም ነው » በማለት ከተናገረ በኋላ ድምፁን ዝግ በማድረግ እና ዓይኖቹንም ጠገግ በማድረግ የሚከተለውን ጨምሮ ተናገረ ፡—



«ልክ የምንፈልገውን ነው ያደረጉት ። ግሩም ተግባር ነው እናት ሆይ!»

በመውደድ ስሜት ራሷን ነቀነቀችለት ። በሠፈሩ ከሚኖሩት መካከል ትልቁ ሸረኛ እርሱ ነው ተብሎ ከሚገመተው ከዚህ ሰው አንደበት ይኸንን በመስማቷ ተደሰተች ። ፋብሪካው ውስጥ በደረሰው የመንፈስ መነሳሳት የተደሰተች ከመሆኗም በስተቀር «አሁን ይኸ ሁሉ እኔ ባልሆን ኖሮስ...» በሚል ሃሣብ ተዋጠች ።

በፋብሪካ ሥራ በሚገባ ያልሠለጠኑ ሦስት ሠራተኞች ከእናት ብዙ ሳይርቁ ቆሙ ።

«የትም ላገኝ አልቻልኩኝም » በማለት ቅሬታ በተመላው ሁኔታ ከመካከላቸው አንዱ በዝግታ ተናገረ ።

«በውስጡ የተጻፈው ነገር ምን እንደሆነ መስማት እፈልጋለሁኝ ። እኔ ራሴ ማንበብ አልችልም ። ጉዳዩ ፍርጥርጥ ብሎ መቅረቡ ግን ግልጽ ነው!» በማለት ሌላኛው ተናገረ ።

«ወደ ብረት ማፍሊያው ክፍል እንሂድ» በማለት ግራ-ቀኙን ከቃኘ በኋላ ሦስተኛው ተናገረ ።

ጉሴቭ እናትን ተመለከተና ፈገግ አለ ።

«ምን እየተካሄደ እንደሆነ ይመለከታሉን?» በማለት ተናገረ ።

ፔላጊያ በከፍተኛ ስሜት መንፈሷ ተሞልቶ ወደ ቤት ተመለሰች ።

«ማንበብ የማያውቁ በመሆናቸው ሠራተኞቹ ቅሬታ ተሰምቶአቸዋል ። እኔ ወጣት በነበርኩበት ጊዜ ማንበብ እችል ነበር ። አሁን ግን ረስቻለሁኝ » በማለት ለአንድሬይ ነገረችው ።

«ለምን አይማሩም?» በማለት ኾኾል ሃሣብ አቀረበ ።

«በዚህ እድሜዬ? በራሴ መሳቂያ ለመሆን?» በማለት እናት ተናገረች ።

አንድሬይ መጽሐፍ መደርደርያው ላይ ካሉት መጻሕፍቶች መካከል አንዱን መጽሐፍ አነሳና ሽፋኑ ላይ ካሉት ሆሄያት መካከል አንዱን ጠንቁሎ ፦ —

«ይኸ ምንድነው?» በማለት ጠየቃት ።

«ኤር» ብላ ፈገግ በማለት መለሰችለት ።

«ይኸስ?» በማለት ጠየቃት ።

«አ» ብላ መለሰችለት ።

ጎሊናዋን ከበድ ብሏትና ሀፍረተሦ ተሰምቷታል ። የአንድሬይ ዓይኖች ምሥጢራዊ በሆነ ሁኔታ ሳይታወቅባቸው በርሷ ላይ የሚስቁባት መስሎ የተሰማት ሲሆን ዓይኖቹ እንዳያዩዋትም አደረገች ። ይሁን እንጂ ፤ ድምፁ ለስላሳና ረጋ ያለ ሲሆን ፊቱም ኮስታራ ነው ።

«በእርግጥ ልታስተምረኝ ታስባለህን ፤ አንድርዬ?» በማለት ከቁጥጥሯ ውጪ እና መለስተኛ በሆነ ፈገግታ ጠየቀችው ።

«እንዴታ! ቀደም ሲል ፊደሎቹን ያውቋቸው ከነበረ በቀላሉ ያጠኗቸዋል ። እንደሚባለው ሁሉ ፤ መሞከር ምንም ጉዳት የለበትም!» በማለት መለሰ ።

«ግን ደግሞ ሌላ ጥቅስ አለ — ለጽላት ስለሰገድክ ጻድቅ አትሆንም! ይባላል ።» አለችው ።

«እ-ሀ-ሀ!» በማለትና ራሱን የለም አይደለም በማለት የተቃውሞ እየነቀነቀ ኾኾል የሚከተለውን ተናገረ ። «ብዙ ዓይነት አባባሎች አሉ ። ዝቅተኛ ዕውቀት ባለህ ቁጥር የምትተኛው የሰላም ዕንቅልፍ ከፍተኛ ይሆናል ይባላል ። ይሁን እንጂ እንደዚህ ያለውን ሁኔታ የሚገምት ቢኖር ቦርጫም ብቻ ሲሆን እርሱም ቢሆን ይኸንን በመሰለው ጥቅስ ልቡን ለማጽናናት ነው ። ይኸ ፊደል ምንድነው?» በማለት ጠየቀ ።

«ኤል» ነው በማለት መለሰችለት ።

«ጥሩ ። ይኸኛውስ?» አላት ።



የተዘነጉትን ሆሄያት ለማስታወስ ዓይኖቿን ዘጋ አድርጋ እና ቅንድቦቿን ሸበብ አድርጋ ታስተውላለች ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ዓይኖቿ ደከሙባት ። መጀመርያ የድካም እንባ ፈሰሳት ፤ ከዚያም የቀቢፀ-ተስፋ እንባ ።

«ማንበብ መማር! የአርባ ዓመት ሰው ሁኖ ገና ሀ-ሁ መቁጠር!» በማለት ቀስ ብላ ተናገረች ።

«አያልቅሱ! ኑሮን እንዳሻዎ መርጠው መኖር አልቻሉም ነበር ። ይሁን እንጂ መጥፎ ኑሮ የኖሩ መሆንዎን ይገነዘባሉ! ቢሻቸው ኖሮ ፤ ብዙ ሺህ ሕዝቦች የተሻለ ኑሮን በኖሩም ነበር ። ይሁን እንጂ ኑሮአቸው እንደ እንስሳ ሲሆን ፤ ይኸንኑ መሳይ ኑሮአቸውንም ኸረ እኛ ምን አለብን ፤ ጥሩ እንኖራለን! እያሉ ያሞካሹታል ። ለመሆኑ ጥሩነቱ ከየቱ ላይ ነው? ዛሬ አንዱ ሰው ይሠራል ፣ የዕለት ምግቡን ይመገባል ፤ ነገም ይሠራል ፣ ይበላል ። ዕድሜ ልኩን መሥራት መብላት? በሕይወት ዘመኑ መካከል እያሰለሰ ልጆች ይወልዳል ። እነዚህ የሚወልዳቸው ልጆቹም ብዙ መብላትን በመሻት እስኪጠይቁት ድረስ ያስደስቱታል ። ከዚያም ይበሳጭባቸውና ሲያወግዛቸው ይኖራል ። እንደዚህም ይላቸዋል — እናንት ትናንሽ ሆዳሞች ፣ ቶሎ-ቶሎ እደጉ! እንግዲህ ሥራ መሥራት ሊኖርባችሁ ነው! የገዛ ልጆቹን የቤት እንስሳ ሊያደርጋቸው ይሻል ። እነርሱ ግን ሕይወታቸውን እንደሚለጠጥ ሙጫ በመሳብ ሆዳቸውን ለመሙላት ሲሉ ሥራ መሥራት ይጀምራሉ ። ብቁ ናቸው እንከን የማይወጣላቸው ናቸው የሚባሉት የሰውን አዕምሮ ነፃ ለማውጣት ሙሉ አገልግሎት የሚያበረክቱ ናቸው ። እርስዎም ቢሆኑ ፣ አቅምዎ እስከፈቀደ ድረስ ይኸንን እያከናወኑ ነዎት» በማለት ኾኾል በለሰለሰና ዝግ ባለ ሁኔታ ተናገረ ።

«እኔ?» በማለት ባያሌው ተነፈሰች ። ከዚያም «እኔ ምን አበረክታለሁ?» አለች ።

«ይኸንን አይበሉ ። እኛ እየአንዳንዱ ጠብታ አገር ዕቶቹን እንደሚያለመልም ዝናብ ነን ። እና እርስዎም ፊደሎችን ማንበብ ሲጀምሩ...» ብሎ ሳይጨርስ ሳቅ አቋረጠው ።

ከዚያም ከተቀመጠበት ተነሳና በወለሉ ላይ ይንጎራደድ ጀመር ።

«መማር አለብዎት ። ፓቬል በቅርቡ ይወጣል ። ከዚያም አሆ?» በማለት ተናገረ ።

«አይ አንድርዬ! በወጣትነት ሁሉም ነገር ቀላል ነው ። ስትሸመግል ግን የሚኖሩህ ብዙ የሚያሳስቡህ ጉዳዮች ፣ ጥቂት ጉልበት እና የማይመራመር ጭንቅላት ናቸው!» አለችው ።

## 18

በዚያን ምሽት ኾኾል ወደውጪ ሲወጣ እናት መብራት አብርታ የእግር ሹራብ መሥራት ጀመረች ። ወዲያውኑ ግን ከተቀመጠችበት በመነሳት በክፍሉ ውስጥ ግራ በመጋባት ስሜት ከተንጎራደደች በኋላ ወደ ማዕድ ክፍሉ በመሄድ በሩን ዘግታ እና ቅንድቦቿን ሽብሸብ አድርጋ ተመለሰች ። የመስኮቶቹን መጋረጃዎች ከጋረደች በኋላ ከመጽሐፍ መደርደርያው ላይ አንድ መጽሐፍ አነሳችና እንደገና ወደ ጠረጴዛው አጠገብ ሂዳ ተቀመጠች ። ከዚያም ጥንቃቄ ብታደርግም እንኳን አንገቷን ወደ መጽሐፉ ቀለስ አድር ጋ ከናፍሮቿን እያነቃነቀች ማንበቧን ከመጀመርዋ በፊት ዞር-ዞር ብላ መመልከቷን አልተወችም ። ከበስተውጪ በኩል ድምፅ መሰማት



ሲጀምር መጽሐፉን አጠፈችና ጆሮቿን ድምፅ ወደ ሚሰማበት አኳያ ቀሰረች ። ከዚያም ዓይኖቿን እየከፈተችና እየዘጋች ለራሷ ማነብነብ ጀመረች ፡ —

«ደብዳቤ ለማለት ፣ ደ ። ሳጥን ለማለት ፣ ሳ...» ትል ጀመር ።

ከውጪ አንድ ሰው አንኳኳ ። እናትም ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ መጽሐፉን ቀድሞ ወደነበረበት የመጽሐፍ መደርደርያ መለሰችው ። ከዚያም ፡ —

«ማነው?» በማለት በተጠንቀቅ ድምፅ ጠየቀች ።

«እኔ ነኝ ።» የሚል ድምፅ ተሰማ ።

ሪቢን ጢሙን እያሻሸ ወደቤት ገባ ።

«ዱሮ ማነህ ሳትይ በሩን ትከፍቺ ነበር ። ብቻሽን ነሽ እንዴ? እኔ ደግሞ ኾኾል ያለ መስሎኝ ነበር ። ዛሬ እርሱን አየሁት... እሥር-ቤት በእርሱ ላይ ጉዳት ያደረሰበት አይመስልም » አለ።

ቁጭ ካለ በኋላ ለእናት የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«እስኪ እንወያይ...» አላት ።

ጠንቀቅ እንድትል ሊያደርጋት በቻለ ሁኔታ እና ከባድ ጉዳይ ይዞ በመጣ ዓይነት አመለካከት ተመለከታት ። ከዚያም ረበብ ባለ ድምፁ በሚከተለው ሁኔታ ንግግሩን ጀመረ ፡ —

«ሁሉም ነገር የገንዘብ ወጪ ይጠይቃል ። ለመወለድ ገንዘብ ያስፈልጋል ። ለመሞትም ገንዘብ ያስፈልጋል ። ለመጻሕፍትና ለተበታኝ ጋዜጦችም ገንዘብ ያስፈልጋል ። ለመሆኑ እነዚህ ለተደረደሩት ለእነዚህ መጻሕፍት ገንዘብ ከየት እንደሚመጣ ታውቂያለሽን?»

«የለም ፤ አላውቅም » በማለት አንድ አጓጉል የሆነ ጉዳይ የደረሰ መሆኑን በመገመት ለስለስ አድርጋ ተናገረች ።

«እኔም ብሆን አላውቅም ። እሺ ፣ ሌላው ጥያቄ ደግሞ የሚጽፉቸውስ ማነው?» የሚለው ነው ።

«የመጽሐፍ ዕውቀት ያላቸው ሊቃውንት ናቸዋ...» አለችው ።

«እኮ እነ ክቡራን መኳንንት!» በማለት በጢም የተከበበ ፊቱ ቀላ እያለ ሪቢን ተናገረ ። ከዚያም አከታትሎ ፡ — «በሌላ አነጋገር ፣ እነ ክቡራን መኳንንት መጻሕፍቶችን እየጻፉ ያስተላልፉዋቸዋል ማለት ነው ። መጻሕፍቶቹ የተጻፉት ግን ራሳቸውን እነ ክቡራንን በመቃወም ነው ። እሺ ፣ እንግዲህ ጉዳዩ እንደዚህ ከሆነ ዘንድ ፣ ገንዘባቸውን እነዚህ ክቡራን መኳንንት በማውጣት ተራው ሕዝብ በእነርሱ ላይ እንዲነሳሳባቸው ማድረጋቸው የሚያስገኝላቸው ጥቅም ከቶ ምንድ ነው? ኧረ ከቶ ምንድነው?» በማለት ተናገረ ።

እናት በመሥጋት ሁኔታ ዐይኖቿን ታርገበግብ ጀመር ።

«ምን ይመስልሃል?» አለችው ።

«አሃሃ! ይኸውልሽ! እኔም ይኸው ሃሣብ ተሰምቶኝ ሳሰላስል ሁለንተናዬ ቀዝቅዞ ነበር » በማለት ድንገት ከወንበሩ እንደ ድብ ዞር ብሎ እያያት ተናገረ ።

«ታዲያ አንዳችስ ፍንጭ ቢሆን አገኘህን?» አለችው ።

«ተይኝ እባክሽ ። ተሞኝተናል!የተሞኘን መስሎ ይሰማኛል ። ማስረጃዎች የሉኝም ፣ ይሁን እንጂ ጉዳዩ ተሞኝነት አለበት ። ጉዳዩ ይኸው ነው! ክቡራኖቹ መኳንንት ብለጣ-ብልጥ ሸንጋዮች ናቸው ። እኔ ዕውነትን ተከታይ ነኝ ። እና አሁን ዕውነትን ተገንዝቤአለሁኝ ። ስለዚህም ከክቡራን መኳንንት ጋር ከእንግዲህ አብሬ አልጓዝም ። እነርሱ ምቹ ሁኖ ባገኙት ጊዜ ሁሉ ከእግራቸው በታች ረግጠውኝ በማበራየት ድልድይ እመስል በላዬ ላይ ይረማመዱብኛል...» በማለት መለሰ ።

ከአንደበቱ የሚወጡት ቃላት እናትን አስተካዥ የሆነ ሁኔታ ላይ ጣሏት ።



«ፈጣሪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ! ፓሻ አይገነዘብም ማለት ይሆንን? ሌሎቹም ሁሉ—» በማለት በሀዘን ተከዘች ።

በሃሣቧ ፊት-ለፊት ፍጹም ቁም-ነገራም የሆኑት የእነ የጎር ፣ የእነ ኒኮላይ ኢቫኖቪች እና የእነ ሳሻ መልኮች ድቅን ብለው ታዩዋት ። የልቧ ትርታ ከፍ እያለ ይመታ ጀመር ።

«አይደለም! አይደለም! ይኼን አላምንም! ህሊና ያላቸው ሰዎች ናቸው » በማለት ራሷን እየነቀነቀች ተናገረች ።

«እነማንን ማለትሽ ነው?» በማለት ሪቢን በሃሣብ ተውጦ ጠየቃት ።

«ከእነርሱ መካከል ሁሉም ። ከመካከላቸው እስከ መጨረሻው ሰው ድረስ ሁሉም ። ይኸንን ተመልክቻለሁኝ!» በማለት ተናገረች ።

«እናት ፣ አንቺ የምትመለከቺው ትክክለኛው ቦታ ላይ አይደለም ። ወደፊት አርቀሽ አስተውይ » በማለት ሪቢን ራሱን ቀለስ አድርጎ ተናገረ ። ከዚያም ቀበል አድርጎ ፡ — «ከእኛ ጋር አብረውን የሚገኙት ሁሉ ራሳቸው የሚያውቁት አንዳችም ነገር አይኖርም ይሆናል ። የራሳቸው ዕምነት አላቸው ። ይኸ ደግሞ ጥሩ ነው ። ከእነርሱ በስተጀርባ ግን ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ የቆሙ ሌሎች ሊኖሩ ይችላሉ ። አንድ ሰው ያለ አንዳች ምክንያት እንደው ዝም ብሎ ራሱን ለክፉ ነገር አሳልፎ አይሰጥም...» በማለት ተናገረ ።

ከዚያም በገበሬነት በጸና ዕምነት ቀጠል አደረገና ፡ —

«ከእነዚህ ክቡራን የሚገኝ አንዳችም ፋይዳ የለም!» በማለት ተናገረ ።

«ምን ለማድረግ ታስባለህ?» በማለት እናት አሁንም እንደገና ጥርጣሬ ላይ ወድቃ ጠየቀች ።

«እኔ?» አለ ሪቢን እርሷን-እርሷን እየተመለከተ ። ጥቂት ዝም ካለ በኋላም ቀጠል አድርጎ ፡ — «እነዚያ ክቡራንን መራቅ አለብኝ ። ይኸው ነው » በማለት ተናገረ ።

እንደገና ይተክዝ ጀመር ።

«ጓዶችን ለመቀላቀል እና ከእነርሱ ጋር ወደፊት ለመግፋት ፈልጌ ነበር ። ይኸንን ለመሰለ ጉዳይ ብቁ ነኝ ። ለሰዎች ምን እንደሚነገር አውቃለሁኝ ። አሁን የሚከተለውን እናገራለሁኝ ፡- ዕምነት አጥቻለሁኝ ። ስለዚህም መውጣት አለብኝ ።» በማለት ተናገረ ።

ራሱን ቀለስ አደረገ ። በሃሣብም ተዋጠ ።

«በየመንደሮች እና በየገጠሩ አንድ ብቻዬን በመሄድ ሕዝቦችን እቀሰቅሳለሁኝ ። ጉዳዮችን በቁጥጥራቸው ሥር ማዋል አለባቸው ። አንድ ጊዜ ከተገነዘቡት መፍትሔውን ያገኙለታል ። እንዲገነዘቡ ማድረግ ተግባሬ ይሆናል ። ሌላ አማራጭ የሌላቸው አንድ ተስፋ ቢኖራቸው እነርሱው ራሳቸው ናቸው ። ሌላ አማራጭ የሌለው አንድ ብቻ አዕምሮአቸው ያው የእነርሱ አዕምሮ ነው » በማለት ተናገረ ።

ይኸንን ሰው የተደሰተችበት ቢሆንም ሠጋችለት ። ቀደም ሲል ደስ የማይላት የነበረው ይኸ ሰው አሁን በአንዳች ምክንያት ውድ ሁኖ ታያት ። ከዚያም ለስለስ ባለ አነጋገር …

«ይይዙሃል…» አለችው ።

ሪቢን እርሷን ተመለከታት ።

«አዎን ይይዙኛል ። በኋላ ግን ይለቁኛል ። ከዚያም እንደገና እጀምራለሁኝ…» አላት ።

«ሙዢኮች* ራሳቸው ይዘው ያሥሩሃል ። እሥር-ቤት ይከቱሃል…» አለችው ።

---

* ሙዢክ — በሩስያኛ ፡ ቋንቋ ገበሬ ማለት ነው ። (ተርጓሚው)



«የእሥር-ቤት ጊዜየን ጨርሼ እወጣለሁኝ ። እንደገና ተግባሬን ሀ ብዬ እጀምራለሁኝ ። ሙዢኮችን በሚመለከት ረገድ ከሆነ ግን አንዴ ፣ ሁለቴም ፣ ሦስቴም እንደገናም ደጋግመው ያሥሩኝ ይሆናል ። ከዚያም በኋላ እኔን ከማሠር ይልቅ እኔ የምናገረውን ማዳመጥ የተሻለ መሆኑን ይገነዘባሉ ። እንዲህም እላለሁኝ — አትመኑኝ ። ብቻ ግን አድምጡኝ ። ካዳመጡኝ ደግሞ ያምኑኛል!» በማለት ተናገረ ።

ከአንደበቱ የሚወጣው እየአንዳንዱ ቃል እየተሰማው ዝግ በማለት ይናገር ጀመር ።

«ዘግየት ካለ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ተገንዝቤአለሁኝ ። አንድ ሁለት ቁም-ነገሮችም አስተውያለሁ…» አለ ።

«ሚኻኢሎ ኢቫኖቪች ፣ ይህ ፍጻሜህ ፣ ማብቂያህ ነው!» በማለት ራሷን በሀዘን እየነቀነቀች ተናገረች ።

ጉድጓዳቸው ውስጥ ጠልቀው በገቡት ጥቋቁር ዐይኖቹ እርሷን በማጤን እና በመመራመር አትኩሮ ይመለከታት ጀመር ።

«ፈጣሪያችን እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ የእህልን ዘር አስመልክቶ የተናገረውን ሰምተሻልን? ዘር እንደገና ፍሬ ሁኖ እንዲያፈራ መሞት አለበት ። ሞት ግን ወዲያውኑ አይወስደኝም ። እኔ ብልጥ ሽማግሌ ነኝ!» አላት ።

ከወንበሩ ቀስቀስ በማለት ዝግ ብሎ ተነሳ ።

«ወደ መሸታ ቤት ሂጄ ለጥቂት ጊዜ ከሰዎች ጋር ቁጭ ብዬ ልጫወት ። ኾኾል የሚመጣ አልመሰለኝም ። የቀድሞ ተግባሩን ጀመረ እንዴ?» አላት ።

«አዎን!» አለችው እናት ፈገግ በማለት ።

«ጥሩ ነው ። ንገሪው ስለ እኔ…» አላት ።

እርስ-በእርስ ሳይተያዩና ሃሣብ-ለሃሣብ እየተለዋወጡ ጎን-ለጎን ሁነው በዝግታ ጉዞ ወደ ምግብ ማዘጋጃው ክፍል አለፉ ።

«እሺ በይ እንግዲህ ደህና እምሺ!» አላት ።
«ደህና እምሽ ። ለፋብሪካው የምታስታውቀው መቼ ነው?» አለችው ።
«አስታውቄአለሁኝ ።» አላት ።
«መቼ ነው የምትሄደው?» አለችው ።
«ነገ ጧት በማለዳ ነው ። ደህና ሁኚ!» አላት ።
ትንሽ ዘግየት እና ቀረት በማለት ሁኔታ ደጃፉ ላይ ቆም እንደማለት ብሎ ሄደ ። ለደቂቃ ያህል እናት የእርሱን ኮቴ እና በልቧ ውስጥ የሚላወሰውን ጥርጣሬ እያንገዋለለች አስተዋለች ። ከዚያም በዝምታ መለስ በማለት ወደሌላኛው ክፍል ከሄደች በኋላ የመስኮቱን መጋረጃ ከፈተችው ። ውጪው ጨልሞአል ።
«በምሽት ነው የምኖረው!» በማለት አሰበች ።
እንደዚያ ዝርጋዳ እና ጠንካራ ለሆነው ለዚያ ሙዝክ አዘነችለት ።
አንድሬይ በከፍተኛ ደስታ ተውጦ መጣ ።
ስለ ሪቢን ነገረችው ።
«ተይው ፥ ስለፍትህ እየተጯጯኸ እና ሕዝቦችን እየቀሰቀሰ መንደር ለመንደር ይዙር ። ከእኛ ፥ ጋር አብሮ መዝለቅ ለእርሱ አስቸጋሪ ነው ። ጭንቅላቱ በሙዝክ አመለካከቶች የተሞላ ነው ። የእኛን አመለካከት የሚያሠፍርበት ቦታ ጭንቅላቱ ውስጥ የለም…» በማለት አንድሬይ ተናገረ ።
«ስለ እነዚያ ክቡራን መኳንንት አወራልኝ ። ከተናገረው ነገር ውስጥ ቁም-ነገር አለበት ። እንዳያታልሉህ ልብ ብለህ አስተውል!» በማለት እናት በተመራማሪ አስተዋይነት ተናገረች ።
«እነርሱ ክብር ይነኩ ይሆን እንዴ?» በማለት ኾኾል ሳቀ ። ከዚያም ፥ — «አዩ እምዬ ፥ ገንዘብ ነው ገንዘብ! ወይኔ ገንዘብ ቢኖረን ኖሮ! አሁንም ድረስ ተግባራችንን የምናከናውነው በሌሎች ሰዎች ወጪ ነው ። ለምሳሌ ኒኮላይ ኢቫኖቪች በወር ሰባ አምስት ሩብል ደሞዝ ያገኛል ። ለእኛ ሃምሳ ሩብል ይሰጠናል ። ሌሎቹም ልክ እንደዚሁ ። አንዳንድ ጊዜ በረሀብ የተቦረቦሩ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ኮፔክ ሳትቀር ተጠረቃቅሞ የተውጣጣ መዋጮ ገንዘብ ይልኩልናል ። እርግጥ ነው ብዙ ዓይነት ክቡራን መኳንንት አሉ ። አንዳንዶቹ ትተውዎት ይሄዳሉ ። ሌሎቹ ይሸነግሉዎታል ። ከመሃላቸው እንከን የማይወጣላቸው ደግሞ አብረውዎት ይዘልቃሉ…» በማለት ተናገረ ።
ከእጆቹ ካጨበጨበ በኋላ ፥ —
«የእኛ የመጨረሻው ድል አሁንም ገና ብዙ ሩቅ ነው ። ያም ሆኖ ግን ለሜይ ዴይ* አንድ መለስተኛ የሆነ በዓል እናከብራለን! ግሩም-ድንቅ በዓል ይሆናል!»
የእርሱ የመንፈስ ስሜት ሪቢን በልቧ ውስጥ ዘርቶባት የነበረውን ጥርጣሬ ነቀለላት ። ኾኾል ፀጉሩን እያስተካከለ እና ዐይኖቹን ወደ ወለሉ እየደፋ ከወዲያ ወዲህ ይንጎራደዳል ። ከዚያም የሚከተለውን ይናገር ጀመር ፥ —
«አንዳንድ ጊዜ መቆጣጠር እስኪያቅትዎ ልብዎ በደስታ ይመላል! የትም ሆነ የት ቢሄዱ ሁሉም ሰው ጓድዎ መስሎ ይሰማዎታል ። በየአንዳንዱ ልብ ውስጥ ይኸንን መሳይ እሳት ይንበለበላል ። ሁሉም ቢሆኑ ጥሩዎች ፥ ደጎች እና አስደሳቾች ናቸው ። እርስ-በእርስ ለመግባባት ማውራት የግድ አስፈላጊ አይደለም… እየአንዳንዱ ልብ የየራሱን ዜማ የሚያዜምበትን አንድ ቅልቅ ቅኝት በአንድነት ያቀነቅናሉ ። ሁሉም ዜማዎ

* ሜይ ዴይ ፥ — ዓለም አቀፍ የወዝ-አደሮች ዓመታዊ በዓል ። (ተርጓሚው)

ች ደግሞ ወደ አንድ ወንዝ እንደሚፈስሱ ልዩ-ልዩ
ምንጮች ሲሆኑ ፣ ይኸ ወንዝም በሰፊው ተንሠራፍቶ
ና ተስፋፍቶ በነፃነት ተደሳች ወደሆነ ወደ አዲስ
የሕይወት ባሕር ውስጥ ይፈስሳል » አለ ።

እናት ንግግሩን ላለማቋረጥና አስተሳሰቡን ላለማቃ
ወስ በማሰብ በንግግሩ መሃል ጣልቃ አልገባችም ። ሁ
ል ጊዜም ቢሆን ለማንም ከምታደርገው ይበልጥ እር
ሱ ሲናገር በከፍተኛ ጥሞና ታደምጠዋለች ። ከሌሎቹ
ይልቅ ንግግሩ ግልጽ የሆነ እና የሚጥላቸው ቃላትም
ልብ የሚነኩ ናቸው ። ወደፊት አርቆ ስለሚያስተውለ
ው ጉዳይ ፓቬል ምንም ቢሆን አይናገርም ። ይሁን እ
ንጂ የኾኾል ግማሽ እርሱነት የወደፊቱንም ኑሮ
የሚኖር ነው ። ሲናገርም ፣ ለመላው ዓለም ሕዝቦች ስለ
ሚመጣላቸው ታላቅ ክብረ-በዓል ይጠቅሳል ። ለእናት
የሕይወትን ትርጉም ያስገኘላት ፣ የልጅዋ እና የመላው
ጓዶቹ ተግባር ምንነትን የገለጸላት ይኸ የወደፊት
ጊዜ ትርኢት ነው ።

«ከዚያም ድንገት ሕሊናን ልብዎ ይዘራል » በማ
ለት ጭንቅላቱን እያወዛወዘ ኾኾል ንግግሩን በሚከ
ተለው ሁኔታ ቀጠለ ፦ «ግራ-ቀኙን ይቃኛሉ ። ሁሉም
ነገር ቀዝቃዛና ቆሻሻ ሁኖ ያገኙታል! ሁሉም ተዳከ
ሞአል ፣ ተቆጥቶአል...»

ድምፁ የማዘን ሁኔታ ነበረበት ።

«እምነትዎን በሰዎች ላይ መጣል የለብዎትም ። ይ
ኸንን ማድረግ እንደሚጎዳ አውቃለሁኝ ። ሰዎችን መፍ
ራት አለብዎት እንደውም የቀረው ቀርቶ መጥላት
አለብዎት ። ሰው ሁለት መልኮች አሉት ። ሊያፈቅሩት
ይሻሉ ። ይሁን እንጂ እንደምን አድርገው ያፈቅሩታ
ል? ሕያው ነፍስ ያለዎት መሆኑን ለመገንዘብ ባለመሻ
ትና ሰብአዊ ፊትዎን በመቀጥቀጥ እንደ በረሀ አው
ሬ ላይዎ ላይ ዘሎ ጉብ ያለብዎትን ሰው እንዴት



ይቅር ይሉታል? ይኸንን ይቅርታ ያደርጉለት ዘንድ
አይቻልዎትም! ስለራስዎ ሲሉ አይደለም ። ራስዎ ማና
ቸውንም ነገር ቢሆን ሊቋቋሙት ይችላሉ ። ይኸንን
ድርጊታቸውን እርስዎ ተቀብለውታል ብሎ እንዳያስብ
ነው ። ሌሎች ሰዎችን ለመደብደብ መጀመርያ በርስዎ
ላይ ሙከራ እንዲደረግብዎ ጀርባዎን አሳልፈው
የብድር መስጠት አይቻልዎትም ።»

ዐይኖቹ እሳት ጐርሰው በመለስተኛ ነበልባሎች
የተቀጣጠሉ ሲሆኑ ጭንቅላቱን ወደታች ቅልስ
አድርጎ ጠበቅ ባለ ሁኔታ ቃላቶቹን ረገጥ እያደረገ
ይናገር ጀመር ። ከዚያም ፦

«የማይጎዳኝ ቢሆንም እንኳን ለማናቸውም ስሕተ
ት ቢሆን ይቅርታ የማድረግ መብት የለኝም ። በዚች
ዓለም ላይ ያለሁት እኔ ብቻ አይደለሁም! ዛሬ አንዱ
ሰው እኔን ሲጎዳኝ ዝም ብዬ ባስተውል ፣ ወይንም
እዚህ ግባ የማይሉት ጉዳይ ስለሆነ ፣ በጉዳቱ ራሴው
መልሼ በራሴ ብስቅ ፣ በእኔ ላይ በዚህ ሁኔታ ከተለማ
መደ በኋላ ነገ ደግሞ ሌላውን ሰው ይደልቀው —
ይነርተው ይሆናል ። ሁሉንም ሰው እንደ አንድ አድ
ርገው መመልከት አይችሉም ። ረጋ ብለው መምረጥ —
ማማረጥ አለብዎት ። ይኸኛው ይመስለኛል ፣ ያኛው ግን
አይመስለኝም ብለው መለየት አለብዎት ። ሁኔታው ም
ቹ አይደለም ። እውን? ሀቁ ግን ይኸው ነው!» በማለት
ተናገረ ።

በአንዳች ምክንያት እናት ስለሳሻ አሰበች ። ከዚያም
ስለፖሊሱ መኮንን ።

«በወንፊት ተንገዋልሎ ያልተጣራ እህል እንደም
ን የመሰለ ዳቦ ይወጣዋል ብለህ ትገምታለህ?.»
በማለት ረዘም አድርጋ በመተንፈስ ተናገረች ።

«ችግሩ ያለው እዚህ ላይ ነው!» በማለት ኾኾል
መለሰ ።

«አዎን ።» አለች እናት ። የድንጋይ ሽበት ከብቦት የቆመ አንድ ትልቅ እና ደስታ-ቢስ ቋጥኝ ድንጋይ ባሏ መስሎ በትውስቷ ተመላለሰባት ። ኾኾል ናታሻን ቢያገባ ፣ ልጅዋም ሳሻን ቢያገባ ሁኔታዎች እንደምን የመሰሉ ሊሆኑ እንደሚችሉ በሃሣቧ ታዩዋት ።

«ግን እኮ ለምንድነው?» በማለት ኾኾል የተነሳበትን ንግግር እንደገና ለመቀጠል ጥያቄ አቀረበላት ። «ይኸ መቼም ግልፕ የሆነ ጉዳይ ስለሆነ ሁኔታውን ሲያስተውሉት አስቂኝም ነው ። ይህ እንደዚህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት ሰዎች ሁሉ ተመሳሳይ በሆነ ደረጃ ላይ የማይገኙ በመሆናቸው ነው ። እስኪ ሁሉንም እናስተካክላቸው! አዕምሮ የጸነሰውን እና እጅም ያበረከተውን ሁሉ እናከፋፍለው እስኪ! ሕዝቦችን የፍርሃት እና የምቀኝነት ባሮች የስግብግብነትና የጅላ-ጅልነት ምርኮኞች አናድርጋቸው...» በማለት ተናገረ ።

ከዚህ በኋላም ይኸንን የመሳሰሉ ብዙ ሃሣቦች ተለዋወጡ ።

ኾኾል ወደፋብሪካው ተመልሶ የተቀጠረ ሲሆን የሚቀበለውንም ደሞዝ በሙሉ አምጥቶ ያስረክባት ጀመር ። ልጅዋ ፓቬል ይቀበል የነበረውን ደሞዝ አምጥቶ ሲያስረክባት እንደምትቀበለው ዓይነት ፣ እርሱንም ልክ በዚያው መንገድ አንዳችም ይሉኝታ ሳይገባት ትቀበለዋለች ።

«እምዬ ፣ ትንሽ ንባብ ቢያነብቡ ምን ይመስልዎታል?» በማለት አንዳንድ ጊዜ አንድሬይ ዐይኖቹ ብልጭ-ድርግም እያሉ ይጠይቃታል ።

ትስቃለች ። ግን እምቢ ትለዋለች ። የዐይኖቹ ብልጭ-ድርግም ማለት ልቧን ይነካታል ።

«እንዲህ እንደቀልድ ከወሰድከው ለምን ትቸገራለህ?» በማለት ለራሷ ታስባለች ።



ብዙውን ጊዜ አዘውትራ ግን ፊቷን ዘወር አድርጋና ግዴለሽ በመሆን የአንዳንድ ቃላትን ትርጉም ትጠይቀዋለች ። ለብቻዋ ተደብቃ የምታጠና መሆኑን ስለገመተ እና የዘነጋቻቸውን ሆሄያት በፍጥነት መልሳ የማስታወስ ችሎታዋ ከፍተኛ በመሆኑ እያደነቀ ፊደሎችን እንድታነብብለት መጠየቁን ተወ ።

«አንድርዩ ፣ ዐይኖቼ ደከሙ ። የዐይን መነጽር ሊያስፈልገኝ ነው » በማለት አንድ ቀን ነገረችው ።

«ይኸ በቀላሉ መፍትሔ ማግኘት ነው ። በመጪው እሁድ ከተማ ወጥተን ሐኪም ከመረመረዎት በኋላ መነጽር እንገዛለን » አላት ።

19

ፓቬልን ለማየት ይፈቀድላት እንደሆነ ሦስት ጊዜ ሄዳ ጠየቀች ። ይሁን እንጂ ሦስቱንም ጊዜ ሀምራዊ ጉንጮች እና ሰልካካ አፍንጫ ያለው ፀጉረ-ሽበቶው የፖሊስ አዛዥ-ጀኔራል ጥያቄዋን የማይቀበለው መሆኑን በአክብሮት ነገራት ።

«እናት ሆይ ፣ ቢያንስ እስከ አንድ ሳምንት ድረስ መጠበቅ አለብዎት ። በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ መቻል-አለመቻሉን እናያለን ። አሁን ግን ምንም ማድረግ አይቻልም...» አላት ።

የፖሊሱ አዛዥ-ጀኔራል ፊተ-ድቡልቡል ሲሆን የደላው-የተመቸው ከመሆኑም በስተቀር ለረጅም ጊዜ በስሎ ከቆየ በኋላ የሻገተ እንኮይን የእርሱ ሁኔታ አስታወሳት ። ትንንሽ እና ነጫጭ የሆኑ ጥርሶቹን በቢጫ ስንጥር አሁንም-ምንግዜም ፋቅ-ፋቅ ያደርጋቸዋል ። አረንጓዴያማ ዐይኖቹ በርኅራኄ አስተያየት የሚርገበገቡ ሲሆኑ ፣ ድምፁም ምን ጊዜም የደግ ሰው እና የወዳጅ ድምፅ ነው ።

«በጣም ትሁት ሰው ነው ። ሁል ጊዜም ፈገግታ አይለየውም…» በማለት ለኾኾል ነገረችው ።

«ይኸንን አልጠራጠርም ።» በማለት ኾኾል መለሰላት ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ — «ሁሉም ቢሆኑ በጣም ጥሩ ሰዎች ናቸው ፣ ጨዋዎች እና ፈገግታ የማይለያቸው ናቸው ። የሚከተለውን እንዲፈጽሙ ተነግሮአቸዋል ፡ — ‘ጥቂት አደገኛ የሆነ ብልህ እና ሀቀኛ ሰው ይኸውላችሁ ። ውሰዱና ስቀሉት!’ እና እነርሱም ፈገግ እያሉ ያንን ሰው ይሰቅሉታል ። ከዚያ በኋላም መሳቃቸውን ይቀጥላሉ ።» አላት ።

«ቤታችንን ሊበረብር የመጣው ሰው ግን ከዚህ ፍጹም የተለየ ነበር ። እሱ ሰው እንዴት ያለ ቀበኛ አይጥ እንደሆነ በግልጽ ለይተህ ማወቅ ትችላለህ ።» በማለት እናት ተናገረች ።

«ከእነርሱ መካከል አንዳቸውም ቢሆኑ ሰብአውያን ፍጡሮች አይደሉም ፤ ሕዝበ-አዳምን ለመቀጥቀጥ የተሠሩ መዶሻዎች ናቸው ። እንደእኛ የመሳሰሉትን ሰዎች ፀጥ-ለጥ በማድረግ እንደሚመች አድርጎ ለመግዛት እንዲቻል የሚሠረሥሩን እና የሚቦረቡሩን የመገዝገዣና የመሞረጃ መሣሪያዎች ናቸው ። እነርሱ ራሳቸውም ቢሆኑ ለበላይ አለቆቻቸው እንደሚመቹ ተደርገው ተቦርቡረዋል ። መለስ አድርገው ባለማሰብና ለምን ይኸንን አደርጋለሁኝ ብለው ራሳቸውን ባለመጠየቅ የታዘዙትን ሁሉ ይፈጽማሉ » አላት ።

በመጨረሻም ልጅዋን ፓቬልን እንድታየው ፈቀዱላት ። እና አንድ እሁድ ቀን በእሥር ቤቱ ቢሮ ውስጥ በስተጥግ በኩል በትሁትነት ተቀምጣ ነበር ። በዚያች ጣራዋ ዝቅተኛ በሆነች አነስተኛና ጽዳት የጎደላት ቆሻሻ ቤት ውስጥ እሥረኞች ለመገናኘት ብዙ ሰዎች ይጠባበቁ ነበር ። ጠያቂዎቹ ውይይቶችን እንደሸረሪት ድር እርስ በርሱ ተረባርቦ በተጣበቀ



ሁኔታ እርስ በርሳቸው ይለዋወጡ የነበረ ስለሆነ እነዚህ የእሥረኞች ጠያቂዎች እዚህ ቦታ ሲገኙ የመጀመርያ ጊዜ ላለመሆኑ ያስታውቃል ።

«ዛሬ ማለዳው ላይ ቅዳሴ ሲቀደስ የቤተክርስቲያኑ ዐቃቢ ከመዘምራኑ መካከል የአንዱን ወጣት ጆሮ መቀርደዳቸውን አልሰሙም እንዴ?» በማለት አንዲት ወፍራም እና ጉንጯ ኩልኩልት ያወጣ ሴት የእቃ መያዣ ቦርሳ ጭኗ ላይ አስቀምጣ ሌላይቱን ጠየቀቻት ።

«ወጣት መዘምራኑ በሙሉ ብልሹዎች ናቸው!» በማለት ጡረታ የወጣ መኮንን የሚለብሰውን የክብር ልብስ የለበሰ አንድ አዛውንት ተናገረ ።

እግሮቹ አጠር-አጠር ያሉ ፤ ረዣዥም እጆች ያሉት ፤ ራሰ-መላጣ እና አገጨ-ረዥም የሆነ አንድ አጭር ሰው ከብስጭቱ የተነሳ ስልቱን በሳተ ድምፅ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«የገበያ ዋጋ እየናረ ይሄዳል ። ይኸ ሁኔታ ደግሞ ሰዎችን ክፉዎች ያደርጋቸዋል ። ዓይነቱ ሁለተኛ ደረጃ የሆነ ሥጋ ዋጋው አንዱ ፓውንድ አሥራ አራት ኮፔክ ሲሆን የዳቦ ዋጋም እንደገና በሁለት ተኩል ከፍ ብሎአል…» አለ ።

አንዳንድ ጊዜ እሥረኞች የሚመጡ ሲሆን ፣ ሁላቸውም ግራጫ የሆነ የእሥር-ቤት ልብስ የለበሱ እና ከባድ የቆዳ ጫማ የተጫሙ ናቸው ። ድብዝብዝ የሆነ መብራት በሚበራበት ክፍል ውስጥ ሲገቡ ዐይናቸው ይርገበገባል ። ከመካከላቸው አንዱ እግሮቹ ላይ ሰንሰለት አለበት ።

በእሥር-ቤቱ ውስጥ ያለው ሁኔታ ባልተለመደ መንገድ ሰላማዊ የሆነ ሁኔታ ሲሆን ፣ ማናቸውም ነገር ደስ የማያሰኝ ብቻ ነው ። እነዚህ ሰዎች ቀደም ካለ ጊዜ አንስቶ የተለማመዱት እና ዕድል-ፈንታቸው

ንም ተስማምተው የተቀበሉት ይመስላል ። አንዳንዶቹ
የእሥር ጊዜያቸውን በትዕግሥት ያሳልፋሉ ። ሌሎቹ
በሰነፍነት ዘብ የቆሙ ናቸው ። አሁንም ሌሎቹ ደግሞ
ሁለንተናቸው ተሟልቶና ደክመው እሥረኞችን ለመ
ጠየቅ የመጡ ናቸው ። የእናት ልብ በትዕግሥተ-ቢስነ
ት ተረበሸ ። በአካባቢዋ ያሉትን ነገሮች ሁሉ በመገረ
ም መመልከት የጀመረች ሲሆን ባየቻቸው ነገሮች
አልባሌነት ተደነቀች ።

ፊቷ የተጨማደደ እና ዐይኖቿ የወጣት ልጅ
ዐይኖች የሚመስሉ አንዲት አጭር አሮጊት ከእናት
ቀጥላ ተቀምጣለች ። ተሸብሽቦ የተጨራመተውን ቆዳማ
አንገቷን ማናቸውንም ንግግር ለማዳመጥ ከወዲያ-ወ
ዲህ ዞር-ዞር የምታደርግ ሲሆን ፥ ዐይኖቿን በደፋር
አመለካከት ክፍት-ዘጋ እያደረገች ማንንም ትመለከታ
ለች ።

«ማንን ለማየት ነው የመጡት?» በማለት ፔላጌያ
ዝግ ብላ ጠየቀቻት ።

«ልጄን ለማየት ነው ። የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነው ።»
በማለት አሮጊቷ ሴት ድምጿን ከፍ አድርጋ መለሰ
ች ። ከዚያም ፡ — «እርስዎስ?» በማለት እናትን ጠየቀ
ቻት ።

«እኔም ልጄን ለማየት ነው ። ወዝ-አደር ነው ።»
በማለት መለሰችላት ።

«ስሙ ማን ይባላል?» ብላ አሮጊቷ ጠየቀቻት ።

«ቭላሶቭ ይባላል » በማለት እናት መለሰች ።

«ስሙን እስከዛሬ አልሰማሁም ። ከታሠረ ቆይቷ
ልን?»

«ሰባት ሳምንታት ያህል ይሆናል ።»

«እዬ! የኔ ልጅ ከታሠረ አሥር ወር ሊጠጋው
ነው!» በማለት ኩራት በተመላው አነጋገር አሮጊቷ
ተናገረች ።



«አዎን ፥ አዎን! የሁሉም ትዕግሥት አልቋል ። ሁሉም
በሲጩ ሁኖአል ... ሁሉም ይቆጣል ። የዋጋዎች ተመን
ደግሞ እየናረ ይሄዳል ። ሰዎችም ከዚሁ ጋር በአንድ
ነት ርካሽ እየሆኑ ይሄዳሉ ። ይኸ ሁኔታ ማከተሚያ
እንዲኖረውም ተቃውሞ የሚያሰማ አንድም እንኳን
የለም ።» በማለት ፀጉረ-መላጣው ሽማግሌ ፈጠን ባለ
ሁኔታ ተናገረ ።

«ልክ ነዎት ። ከልኩ አልፎአል ማብቂያው ነው ።
ተደማጭ ድምፅ ያለው ሰው ዝም እንዲሉ ቢነግራ
ቸው ይሻላል ። እኛ የምንሻው ይኸንን ነው ። ተደማ
ጭ ድምፅ...» በማለት መኮንኑ ተናገረ ።

አስደሳች በሆነው ውይይት ላይ ሁሉም ተካፋይ
ሆኑበት ። ሁሉም የየራሱን አስተያየት ለማቅረብ ይሻ
የነበረ ሲሆን እየአንዳንዳቸው በሚናገሩበት ጊዜም
ድምፃቸው ዝግ ያለ ነበር ። እናት ሌሎቹ ባቀረቡዋ
ቸው አስተሳሰቦች አልተስማማችም ። እናት ቤት ውስ
ጥ ንግግሩ የተለየ ሲሆን ፥ ይበልጥ ግልጽ እና ቀላል
አቀራረብ የነበረው እንደዚሁም ድምፅ ከፍ ብሎ
የሚነገርበት ነበር ።

አራት ማዕዘናማ ቀይ ጢም ያጤመ ወፍራም የእ
ሥረኞች ጠባቂ የእናትን ስም ከጠራና ከእግሯ እስ
ከ ፀጉሯ ድረስ ከፍ-ዝቅ አድርጎ ካያት በኋላ ሽንከ
ል-ሽንከል እያለ በመጎተት ፡ —

«ይከተሉኝ » አላት ።

ተከትላው በምትሄድበት ጊዜ ፈጠን-ፈጠን ብሎ
እንዲሄድ ግፋው-ግፋው የሚል ስሜት መጣባት ።

ፓቬል ፈገግ ብሎ እና እጁን ዘርግቶ አንድ ት
ንሽ ክፍል ውስጥ ቆሞ ነበር ። እናቱ መለስ ባለ
ፈገግታ እጁን ይዛ በመጨበጥ ዐይኖቿ በፍጥነት
ተርገበገቡ ።

«እንዴት ነህ ... እንዴት ነህ...» አለችው የምትናገራቸው ቃላት ጠፍተዋት ።

«እናት ፣ በመረጋጋት ቻል አድርጊው ።» በማለት እጅዋን ጨብጦ ሲይዝ ተናገረ ።

«እኔ ደህና ነኝ » አላት ።

«ምናልባትኮ እናትህ ናቸው ።» በማለት የእሥረኛ ጠባቂው እየተነፈሰ ተናገረ ። «ይሁን እንጂ በመካከላችሁ ርቀት እንዲኖር ራቅ-ራቅ ብላችሁ ቁሙ ።» በማለት ጎላ ባለ ድምፅ ተናገረ ።

ፓቬል ስለጤናዋና ስለቤታቸውም አንዳንድ ነገሮች ጠየቃት ። ሌሎች ጥያቄዎችን ትጠባበቅ ስለነበረ የልጅዋን ዐይኖች ትቃኝ ጀመር ። ይሁን እንጂ ሌላ ጥያቄዎችን አላቀረበም ነው ። ምንም እንኳን ጥቂት የከሣ ቢሆንም እና ዐይኖቹም ጎላ-ጎላ ያሉ ቢሆኑም ያው እንደቀድሞው ፍጹም የረጋ ነው ።

«ሳሻ ሰላምታ አቅርባለች!» አለችው ።

የፓቬል የዐይን ሽፋሎች ተንቀጠቀጡ ፤ ፊቱ ይበልጥ ለስለስ አለ ። ከዚያም ፈገግ አለ ። እናቱ በልቧ ውስጥ ከባድ ውጋት ተሰማት ።

«ቶሎ የሚፈቱህ ይመስልሃልን?» በማለት ከፍቷትና ተበሳጭታ ጠየቀችው ። «እሥረው ያቆዩህ ለምንድ ነው? እነዚያ የሚበተኑ ጋዜጦች እንደሆኑ እንደገና ፋብሪካው ውስጥ መሰራጨታቸውን አሁንም ቀጥለዋል...» አለችው ።

የፓቬል ዐይኖች ብሩኅ ሁነው በሩ ።

«ዕውነት?» በማለት ፈጥኖ ጠየቀ ።

«ይኸንን ስለመሳሰሉ ጉዳዮች መወያየት ክልክል ነው » በማለት በተንጎላጀ ድምፅ ጠባቂው ተናገረ ። ቀጠል አደረገናም ፡— «መነጋገር የምትችሉት ስለቤተሰብ ጉዳዮች ብቻ ነው...» በማለት ተናገረ ።



«ይኸ የቤተሰብ ጉዳይ አይደለምን?» በማለት እናት በተቃውሞ መለሰች ።

«ለዚህ እኔ መልስ አልሰጥም ። ትሰሙ እንደሆን ስሙ ፤ ክልክል ነው ነው የምለው...» በማለት በግዴለሽነት ተናገረ ።

«እሺ ፤ እሺ እስኪ ስለቤታችን ንገሪኝ ። እስከዛሬ ምን-ምን ስታደርጊ ነበር?» በማለት ፓቬል ጠየቃት ።

እርሷም በጋለ የወጣትነት መንፈስ ዓይነት ስትመልስለት ፡—

«ኡ-ይ! እነዚያን ሁሉ ነገሮች ወደፋብሪካው እወስድ ነበር » በማለት በዐይኖቿ አንዳች የአዋኪነት ምልክት እየታየባት ተናገረች ።

ከዚያም ጥቂት ዝም እንደማለት ካለች በኋላ ፈገግ በማለት ንግግሯን ቀጠለች ፡—

«የቅጠላ-ቅጠል ሾርባ ፤ የሙቅ አጥሚት ፤ እንደዚሁም እንደ መረቅ የመሳሰሉ ልዩ ልዩ የምግብ ዝግጅቶችን...» ማለቴ ነው አለችው ።

ፓቬል ጉዳዩ ገባው ። እጁን ፀጉሩ ላይ አሳርፎ በማሻሸት ሊያሳየው ባልፈቀደው ፈገግታ ታጀበ ።

«አለሥራ ከመሆን አንዳንድ ነገሮችን በመሥራት በሥራ መጠመድ መልካም ነው ። ብቸኛ ከመሆን ያድናል » በማለት ከዚህ ቀድሞ ሰምታው በማታውቀው የርኅራኄ ድምፅ ተናገረ ።

«እነዚያ ተበታኝ ጋዜጦች እንደገና መታየት ሲቀጥሉ እኔንም ፈተሹኝ» በማለት ጥቂት ኩራት ብጤ እየተሰማት ተናገረች ።

«ይኸውላችሁ እንግዲህ! ደግሞ እንደገና ጀመሩ! እንዲህ ያለውን ነገር መነጋገር አይፈቀድም ብዬዎት የለም እንዴ! ሰውዬው እዚህ እንዲታሠር የተደረገው ከእሥር ቤት ውጪ ምን-ምን ተግባር እንደሚካሄድ እንዳያውቅ ተብሎ ነው ። እርስዎ አሁን የሚያደ

ርጉትን ግን እስኪ ያስተውሉት! አይ! እንግዲህ እንዲህ የመሳሰለው አነጋገርዎ ክልክል መሆኑን ቢገነዘቡት ይሻልዎታል!» በማለት በስጨት ባለ አነጋገር የእሥረኞች ጠባቂው ተናገረ ።

«ይበቃል ፣ እማማ ። እኚህ ጠባቂያችን ማትቬይ ኢቫኖቪች ልበ-ገር ሰው ስለሆኑ አናበሳጫቸው ። ጓደኛሞች ነን ። ዛሬ አንቺ እኔን ልትጠይቂ በመጣሽ ጊዜ የእርሳቸው እዚህ መሆን የአጋጣሚ ጉዳይ ነው ። ብዙውን ጊዜ እዚህ እንዲቆም የሚደረገው የእሥር ቤቱ ረዳት ኃላፊ ነው » በማለት ፓቬል እናትን ነገራት ።

«ሰዓት አልፏል ።» በማለት ጠባቂው ሰዓቱን እየተመለከተ ተናገረ ።

«ውድ እናቴ ፤ አመሰግንሻለሁኝ ። አታስቢ ። በቅርቡ ይፈቱኛል...» በማለት ፓቬል ተናገረ ።

በከፍተኛ ስሜት እቅፍ ካደረጋት በኋላ ፣ ሳማት ። እርሷም በስሜት ተነክታ ስለነበረ አለቀሰች ።

«ይምጡ በዚህ በኩል ፤ ግዴለም አያልቅሱ ። ይለቁታል ። ሁሉንም ይለቋቸዋል... እሥር-ቤቱ በሰው ብዛት ተጣብቧል...» በማለት የእሥረኞች ጠባቂው በመተላለፊያ ኮሪዶሩ በኩል ፊት-ፊት ቀድሞ እየመራት ሲሄድ ተናገረ ።

እቤት በደረሰች ጊዜ በፈገግታ ተመልታና ቅንድቦቿም እየተርገበገቡ አንድም ሳይቀር ከልጇዋ ጋር ያሳለፈችውን ጊዜ ዘርዝራ ለኾኾል ነገረችው ።

«ያንን ጉዳይ እንዲገነዘበው ለማድረግ ያቀረብኩለት አነጋገር ግሩም ነበር ። ተገንዝቦታል! መገንዘብ አለበት ። አለበለዚያማ አለወትሮው እንዲህ ለስላሳ ባልሆነም ነበር ። እንደዛሬው ሁኖም አያውቅ...» በማለት ተናገረች ።

«አይ! የእርስዎ ነገር!» በማለት ኾኾል ሳቀ ። ከዚ



ያም ቀጠል አደረገና ፡ — «ሰው ሁሉ የተለያዩ ነገሮችን ይሻል ። እናት ግን ምንግዜም የምትሻው ማፍቀርን ነው...» በማለት ተናገረ ።

«አንድርዬ ፣ እነዚያ ሰዎች ግን አድራጎታቸው ፍጹም ሌላ ነው ። ብታያቸው ትገረማለህ!» በማለት ድንገተኛ በሆነ መገረም ተናገረች ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ ፡ — «እረ ጉድ ነው! ሁሉንም ነገር ተላምደውታል! ልጆቻቸው ከየጉያዎቻቸው ተነጥቀው እሥር-ቤት ተወርውረዋል ። እነርሱ በሚያሳዩት ሁኔታ ግን አንዳችም ነገር የደረሰባቸው አይመስሉም! እሥር-ቤት ሂደው መቀመጥ ነው ። ከዚያም ከታሠሩት ጋር እስኪያገናኙዋቸው ድረስ መጠበቅ እና እስከዚያውም ድረስ ዝባዝንኬውን ወሬ ማውራት ። ይኸ ነው እንግዲህ ። ታዲያ የተማሩት ሰዎች እንዲህ ዓይነት ከሆኑ ከእኛ ከደንቆሮዎቹ የሚጠበቀው ምንድነው?..» በማለት ተናገረች ።

«ታዲያ ሌላ ምን ያድርጉ ብለው!» በማለት በምፀት አነጋገር ኾኾል ተናገረ ። ቀጠል አድርጎም ፡ — «ደግሞም እኮ ሕጉም ቢሆን እኮ ለእኛ አይበሉት እንጂ ለእነርሱ ሲሆን ምቹ ነው ። ሕጉ ከእኛ ይልቅ ይበልጥ መመኪያነቱም ለእነርሱ ነው ። አያደርገውም እንጂ ፤ ልክ እኛ ላይ እንደሚያደርገው ሁሉ እነርሱንም አልፎ አልፎ እያነቀ ቢደፍቃቸው ኖሮ ልክ በገቡም ነበር ። በሌላ ሰው ዱላ ከመነረት ይልቅ በራስ ዱላ መነረቱ ይቀላል...» በማለት ተናገረ ።

## 20

አንድ ምሽት ላይ እናት ሹራብ እየሠራች ጠረጴዛ አጠገብ ተቀምጣ ሳለ እና ኾኾልም በጥንታዊት ሮም ውስጥ ባርያዎች አካሂደውት ስለነበረ አመጽ

የሚያትት መጽሐፍ ሲያነብብላት አንድ ሰው ከውጪ በሩን በኃይል አንኳኳ ። ኾኾል በሩን ሲከፍተውም ቬሶቨሺኮቭ ትልቅ ጥቅል ከክንዱ ውስጥ እንደያዘ ገባ ። ያደረገው ቆብ ወደ ጭንቅላቱ ድረስ ተሠርጉዷል ። እግሮቹም እስከጉልበቱ ድረስ በጭቃ ተለውሰዋል ።

«መንገዴን በመሄድ ላይ ሳለሁኝ መብራት እዚህ ሲበራ በማየቴ እንደምናችሁ ለማለት መጣሁኝ ። ገና ከእሥር-ቤት መምጣቴ ነው» በማለት እንግዳ በሆነ ድምፅ አሰማ ። የፔላጊያን እጅም ስሜት በተመላበት ሁኔታ ጨበጠ ።

«ፓቬል የከበረ ሰላምታ አቅርቦአል...» በማለት ተናገረ ።

እየቀፈፈው ከተቀመጠ በኋላ ክፍሉንም ቅር በቱሰኝ እና በተጠራጣሪነት ስሜት ይመለከት ጀመር ።

እናት አትወደውም ። የአራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው የቁንጮ አለጫጨቱ እና ትናንሽ ዐይኖቹ ያስፈራሩዋታል ። ዛሬ ግን እርሱን በማየቷ የተደሰተች ስትሆን ስታነጋገረውም መውደድ በተመላበት ሁኔታ ትስቅ ነበር ።

«እንዴት ከሲታ ሁነሃል! አንድርዬ አንድ ብርጭቆ ሻይ እንስጠው...» በማለት ተናገረች ።

«ሳሞቫሩን እያቀጣጠልኩኝ ነው» በማለት ኾኾል ከማዕድ ክፍል ሁኖ መለሰ ።

«እሺ እባክህ ፤ ፓቬል እንዴት ነው ። አንተን ብቻ ነው ወይንስ ሌሎችንም ፈትተዋቸዋል?» በማለት ጠየቀችው ።

ኒኮላይ ጭንቅላቱን ወደመሬት ቀለስ አደረገ ።

«ፓቬል የመውጫያ ጊዜውን በትዕግሥት እየተጠባበቀ ነው ። የተፈታሁት እኔ ብቻ ነኝ ።» በማለት ከተናገረ በኋላ ዐይኖቹን ወደ እናት ቀና አድርጎ



ጥርሶቹ እንደተጋጠሙ በቀስታ አነጋገር የሚከተለውን ተናገረ ፡— «የእስካሁኑ ይበቃኛል ። ልቀቁኝ! የማትለቁኝ ከሆነ ግን እዚህ ካለነው መካከል አንዱን ገድዬ ራሴንም እገድላለሁኝ! አልኳቸው ። ስለዚህም ለቀቁኝ ።»

«አሆ!ነው እንዴ!» በማለት ትንሽ ፈቀቅ ብላ ተናገረች ። ተዋጊ የሆኑ ዐይኖቹን በተመለከተች ጊዜ ወዳ ሳይሆን የግዷን ዐይኖቿ ይርገበገቡ ነበር ።

«ፌኦዶር ማዚን እንዴት ነው?» በማለት ኾኾል ከማዕድ ክፍል ሁኖ ድምፁን ከፍ በማድረግ ጠየቀ ። ቀጠል አደረገምና ፡—

«አሁንም ግጥሞች ይጽፋልን?» አለው ።

«አዎን ። ይኸን ዓይነት አድራጎት ግን አይገባኝም!» በማለት ኒኮላይ ድርጊቱን ባለመቀበል መልክ ራሱን ነቀነቀ ። ከዚያም ፡— «እርሱ ለመሆኑ ፤ ራሱን ምን አድርጎ ነው የሚገምተው? ቢጨ-ወፍ ነው እንዴ? ለወፍ ከተሠራ ጎጆ ውስጥ ቢከቱት እዚያ ውስጥ ሁኖም ይዘምራል ። እኔ የማውቀው ግን አንድ ነገር ነው ፡— እቤት መሄድ አልሻም...» በማለት ተናገረ ።

«እቤት ብትሄድ ምን ታደርጋለህ? እና ቤት ነው ። ምድጃው ጭስ የለውም ። ሁሉም ነገር የቀዘቀዘበት ቤት ነው...» በማለት በትካዜ እያሰበች እናት ተናገረች ።

አንዳችም መልስ አልመለሰም ። እርሷን-እርሷን ብቻ ይመለከት ነበር ። በመጨረሻም ከኪሱ አንድ ፓኬት ሲጋራ አወጣና አንዱን ሃባ በማቀጣጠል ፈገግታ-ቢስ በሆነ የኩርፊያ መልክ ልክ የጨፈገገው ውሻ መስሎ ያንኮራፋ ጀመር ።

«አዎን ፤ ሁሉም ነገር ቀዝቃዛ ነው ።» በማለት ከአፉ ቡልቅ የሚለው ግራጫ-መሰል የሲጋራ ጭስ እየተነነ ሲጠፋ እየተመለከተ ተናገረ ። ከዚያም ፡— «እቤት

ብሔድ የሚጠብቁኝ ወለሉ ላይ ቀዝቅዘው የደረቁ በረሮዎች ናቸው ። ቀዝቅዘው የደረቁ አይጦችም ጭምር ። ፔላጊያ ኒሎቭና ፤ ምሽቱን እዚህ በመተኛት እንዳሳልፍ ይፈቅዱልኛል?» በማለት እርሷን ሳይመለከት ዝግ ብሎ ጠየቃት ። እርሷም ፡ —

«እንዴታ!» በማለት ፈጥና ፈቀደችለት ። ያም ሁኖ ግን እርሱ እቤቷ በመገኘቱ ብዙም ደስ አላላትም ነበር ።

«አሁን ያለንበት ጊዜ ልጆች በወላጆቻቸው የሚያፍሩበት ጊዜ ነው...» በማለት ተናገረ ።

«ምን አልክ?» አለችው እናት ደንገጥ በማለት ሁኔታ ።

እርሷን-እርሷን ይመለከት ጀመር ። በፈንጣጣ የተጠቀጠቀው ፊቱ ዐይኖቹን ሲከድን ዕውር አስመሰለው ። ከዚያም ፡ —

«ልጆች በወላጆቻቸው የሚያፍሩበት ጊዜ ነው!» በማለት ቀደም ሲል የተናገረውን አሁንም እንደገና ደግሞ ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ — «ፓቬል በእርስዎ ምንም ጊዜ አያፍርብዎትም ። እኔ ግን በሽማግሌው አባቴ አፍራለሁኝ ። ሁለተኛ እርሱ ቤት ድርሽም አልል ። አባት የለኝም ። ቤትም የለኝም ። ፖሊስ ጥበቃ ሥር ባልሆን ኖሮ ወደሳይቤሪያ እሄድ ነበር... እዚያ በግዞት ያሉትን ሰዎች ነፃ አወጣቸዋለሁኝ... እንዲያመልጡ እረዳቸዋለሁኝ...» በማለት ቷናገረ ።

የሚሰቃይ መሆኑን አስተዋይ ልቦናዋ ነገራት ይሁን እንጂ አላዘነችለትም ። ዝም በማለት እንዳታስቀይመው በማሰብ ፡ —

«የምታስበው እንደዚህ ከሆነ ብትሄድ የተሻለ ነው » አለችው ።

አንድሬይ ከማዕድ ክፍል መጣ ።



«ምንድነው የምትለው?» በማለት ሳቀ ።

«የሚበላ ነገር ላምጣልን...» በማለት እናት ከመቀመጫዋ ተነሳች ።

ኒኮላይ ኾኾልን በማስተዋል ከተመለከተው በኋላ ፤ ድንገት የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«አንዳንድ ሰዎች መገደል ያለባቸው ይመስለኛል ።»

«እሆ! ለምን?» በማለት ኾኾል ጠየቀው ።

«ለማስወገድ » ብሎ መለሰለት ።

ረዥም እና ቀጭን የሆነው ኾኾል በሲጋራ ጪስ ተከብቦ ወንበር ላይ ተደላድሎ የተቀመጠውን ኒኮላይን ወደታች እየተመለከተ ክፍሉ ውስጥ መሃል ቦታ ላይ ተረከዙን እያጋጨ ቆመ ። ፊቱ ደም ለበሰ ።

«የዚያን የኢሳይ ጎርቦቭን አንገት ቆርጬ አሽቀንጥረዋለሁኝ ። ይኸን ባላደርግ ደግሞ ምን አለ በለኝ!» በማለት ኒኮላይ ተናገረ ።

«ለምን?» አለው ኾኾል ።

«ሰላይ እና አሾክሿኪ ነው ። አባቴን ጆሮ-ጠቢ እንዲሆን አድርጎ ያበላሸብኝ እርሱ ነው » ብሎ በብስጭት አመለካከት አንድሬይን እየተመለከተ ቬሶቭሺኮቭ ተናገረ ።

«ነው እንዴ!» በማለት ኾኾል በአንክሮ ከተናገረ በኋላ ፡ — «ታዲያ በዚህ ምክንያት አንተን ጥፋተኛ የሚያደርግህ ማን ነው? ከመካከላችን ማን እንከፍ አለ!..» በማለት ተናገረ ።

«ብልሆቹ እና እንከፎቹ ሁሉም በአንድነት ይገኛሉ » በማለት ኒኮላይ በግትርነት ተናገረ ። ከዚያም ፡ — «አንተን እና ፓቬልን እንደምሳሌ አድርገህ ውሰድ ። ሁለታችሁም ብልሆች ናችሁ ። ነገር ግን እኔ እንደፌዎዶር ማዚን ወይንም እንደሳሞይሎቭ ወይንም እንደ እናንተ እንደሁለታችሁ ብልህ ነኝን? አትዋሽ ። ብትዋሽም ምን አለፋህ ፤ አላምንህም... ሁላችሁም እኔን ገለል

ታደርገኛላችሁ ። አለሁበት ለብቻዬ እንድቆይ ታደርጋ
ላችሁ ።» በማለት ተናገረ ።
«ኒኮላይ ፤ እንጃ ልብህን ያምሃል መሰለኝ ።» በማለት
ኾኾል አጠገቡ ከተቀመጠ በኋላ ቀስ ብሎ በልስላ
ሴ ተናገረ ።
«አዎን ፤ ያመኛል ። እናንተንም ያማችኋል ። የእናንተ
ህመም ከእኔ ሕመም ይልቅ በዓይነቱ ከፍተኛ ደረጃ
ያለው ሁኖ ይሰማችኋል ። ማለት የምችለው ቢኖር ፤
ሁላችንም እርስ በርሳችን የምንተያየው እንደውሾች
መሆኑን ነው ። እንደውሾች ነን ። አይደለምን? ተናገር
እንጂ!» በማለት ኒኮላይ ተናገረ ።
ዐይኖቹን አንድሬይ ፊት ላይ ተክሎ እና ጥርሱ
ን ገልጥጦ መልስ ይጠባበቅ ጀመር ። ደም የለበሰ
ፊቱ የቀድሞ ሁኔታውን ያልቀየረው ሲሆን ከንፈሮ
ቹ ግን አንዳች ነገር ያቃጠላቸው ይመስል አብጠዋ
ል ።
«ምንም የምናገረው የለኝም» በማለት ኾኾል የቬ
ሶቭሺኮቭን የተቆጣ መልክ እየተመለከተና በቅሬታ
ፈገግ እያለ ተናገረ ። ከዚያም ንግግሩን በመቀጠል ፡—
«ልቡ ውስጥ ያሉት ቁስሎች በሙሉ በመድማት
ላይ በሚገኙበት ጊዜ ከሰው ጋር መነጋገር ጉዳትን
ማስከተል መሆኑን አውቃለሁኝ ። ወንድሜ ሆይ ይኽ
ንን አውቃለሁኝ!» በማለት ተናገረ ።
«ከእኔ ጋር መከራከር አስቸጋሪ ነው ። ለምን እን
ደሆነ ግን አላውቅም!» በማለት ኒኮላይ ዐይኖቹን ወ
ደመሬት ደፍቶ ተናገረ ።
«እኔ እንደሚመስለኝ ፤ እየአንዳንዳችን እሾሃማ የሆ
ነ ጎዳናችንን በባዶ እግራችን የተጓዝን ነን ። እየአን
ዳንዱ ልክ አንተ እንደምታደርገው ሁሉ የየራሱን
ሥቃይ በጨለማ ውስጥ ተውጦ ያቃስተው ነው!»
በማለት ኾኾል ተናገረ ።



«ምንም የምትነግረኝ ነገር የለም ። የእኔ ልብ
ልክ እንደተኩላ በከፍተኛ ድምፅ ይጮኻል!..» በማለት
ኒኮላይ ተናገረ ።
«ምንም ነገር ልነግርህ አልሻም ። ብቻ ግን ፤ ይኽ
ሁኔታ እንደሚያልፍ አውቃለሁኝ ። ሙሉ በሙሉ
አያልፍም ይሆን ይሆናል ። ያም ሁኖ ግን ያልፋል!»
ከዚያም ትንሽ ሳቅ ካለ በኋላ ኒኮላይን ጀርባው
ላይ ቸብ-ቸብ እያደረገ በመምታት ንግግሩን ቀጠለ ፡—
«ይኽ ሁኔታ ፤ ህፃናትን እንደሚያማቸው እንደኩፍ
ኝ በሽታ ማለት ነው ። ሁላችንንም በሽታው ቀድሞ
ም ሆነ ዘግየት ብሎም ይይዘናል ። ጠንካራዎቹን ሕፃ
ናት በቀላሉ ይተዋቸዋል ። ደካማዎቹ ላይ ደግሞ ከ
ፋ ይልባቸዋል ። የሕይወትን ጠቅላላ ይትበሃል እና
እኛም በሕይወት ውስጥ የያዝነውን ቦታ ሙሉ በ
ሙሉ ባልጨበጥንበት እና ገና ራሳችንን ፈልገን
ለማግኘት በምንጥርበት ጊዜ በሽታው ይይዘናል ። አን
ዲት ትንሽ እና ምግቦችን ማጣፈጫ የሆነች ኮምጣ
ጤ በዓለም ውስጥ አንተ ብቻ ሁነህ የምትገኝ እና
በጣፋጭነትህም ምክንያት ሁሉም እየተሻማ ሊቧጨ
ቅህ የሚሻ ይመስልሃል ። ከጊዜ በኋላ ግን ፤ ሌሎ
ችም ካንተ ያላነሰ ሙዳ የሚያህል ልብ እንዳላቸው
የምትገነዘብ በመሆኑ ግንዛቤህ ሁኔታዎችን ቀለል
ያደርግልሃል ። ከዚያም በኋላ ትልቁ መረዋ ከተ
ንጠለጠለበት እና ግው! ግው! እያለ ድምፁን ከሚያሰ
ማበት ግንብ ላይ ያንተን ኪው! ኪው! የምትለዋን
ትንሿን ድምፀ-ደቃቃ ቃጭልህን አንተም ለወጉ ያህ
ል ይዘህ የወጣህ ሁኖ ስለሚሰማህ ሃፍረት ይውጥሃ
ል ። ምንም እንኳን ዘይት ዝምብን አስምጦ እንደሚ
ያስቀራት ሁሉ ፤ ያንተንም ቃጭል ትላልቆቹ መረዋዎ
ች ውጠው የሚያስቀሯት ቢሆኑም ፤ መረዋዎች ለሚያ
ሰሙት ጣዕመ-ዜማ ያንተም ቃጭል ተጨማሪ በመሆ

ን ለዜማው ተጨማሪ ውበትን የምትለግሥ መሆኗን ትገነዘባለህ ። ምን ለማለት እንደፈለግሁኝ ተገንዝበሽ ኛልን?» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

«ሳልገነዘብህ አልቀረሁም » ብሎ እራሱን በአ ዎንታ ነቅነቅ አድርጎ ኒኮላይ መለሰ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፦ «እኔ ፤ እኔ ግን ምንም ነገር አላምንም!» አለ ።

ኾኾል ሣቁን እየሣቀ ከተቀመጠበት ብድግ ብ ሎ በመነሳት ድምፅ እያሰማ መራመድ ጀመረ ። ከዚ ያም ፦ —

«አንት ያረጀህ የእጡብ ክምር! እኔም ምንም ነገር አላምንም ነበር!» በማለት ተናገረ ።

«የእጡብ ክምር ማለትህ ለምንድነው?» ብሎ ኾኾልን ሲጠይቀው ኒኮላይ የመደነቅ ፈገግታ አ ሳየ ።

«ምክንያቱም አንተ ልክ የእጡብ ክምር የምትመ ስል ነህና ነው » በማለት መለሰለት ።

ድንገትም ኒኮላይ አፉን በሰፊው ከፍቶ በሳቅ ይን ከተከት · ጀመር ።

«ምነው ፤ ምን ሆንክ?» በማለት ኾኾል በመገረም አጠገቡ ቆሞ ጠየቀው ።

«አንተን ለማስቀየም የሚከጅል ተመልሶ ጅላጅ ል እንደሚሆን ጉዳዩ በሃሣቤ ስለተመላለሰ ነው ።» በማለት ኒኮላይ መለሰ ።

«እንዴት አድርጎ ማን እኔን ለማስቀየም ይችላል?» ኾኾል ትከሻውን ነቅነቅ አድርጎ ጠ የቀ ።

«እኔ እንጃ» በማለት ለዛ ያለው ቀልድ በተቀላቀ ለው ፈገግታ ፈገግ ብሎ ቬሶቭሺኮቭ መለሰ ። ከዚያ ም ቀጠል አደረገና — «ሰው አንተን ባያስቀይምህ ይሻለዋል ማለቴ ነው ።» በማለት ተናገረ ።



«ምን ማለትህ ነዋ!» ብሎ ኾኾል ሳቀ ።

«አንድርዩ!» በማለት እናት ከምግብ ማዘጋጃው ክፍል ሁና ተጣራች ።

አንድሬይም ወደርሷ ዘንድ ሄደ ።

ብቻውን የቀረው ቬሶቭሺኮቭ ዙሪያውን ከቃኘ በኋላ በአረጀ ብጫ ቡት ጫማ የተሸፈነ እግሩን ከዘረጋ በኋላ አተኩሮ በመመልከት በቁርጭምጭሚቱ እና በሎሚው መካከል ያለውን የእግሩን ጡንቻ ይነካካ ጀመር ። እጁን ከፍ በማድረግም ወፍራም መዳ ፉን ከተመለካከተ በኋላ በቢጫ ፀጉር የተወረረውን የእጣቶቹንም አይበሉባ ይመለከት ጀመር ። አይበሉባው ን አየር ላይ ወዝወዝ አድርጎ ብድግ አለ ።

አንድሬይ ሳሞቫሩን ሲያመጣ መስተዋቱ ፊት ለፊት ቆሞ ነበር ።

«ይኸንን የእኔን ኩባያ ፊቴን ከተመለከትኩት ረ ዥም ጊዜ ነው...» በማለት ጥቂት ፈገግ ብሎ ተና ገረ ። ከተል አድርጎም ፦ —

«ኩባያ ፊቴ ጠፍጣፋ ነው ጃል!» በማለት ተናገረ ።

«ታዲያ ምን የሚያስቸግርህ ነገር አለ?» በማለት አንድሬይ በመደነቅ እየተመለከተው ጠየቀው ።

«ሳሻ ፤ የሰው ፊት የልቦናውን ምንነት ያንጸባርቃ ል እያለች ትናገራለች » አለ ።

«ዋጋ-ቢስ ነሽ በላት! የገዛ ራሷ አፍንጫ የአሣ ማጥመጃ መንጠቆ ይመስላል ። አገጯ ደግሞ እንደሰን ጢ የሾጠጠ ነው ። ልቧ ግን እንከን የማይወጣለት አንፀባራቂ ኮከብ ነው » ብሎ ተናገረ ።

ኒኮላይ ተመለከተውና ፈገግ አለ ።

ተቀምጠው ሻይ ይጠጡ ጀመር ።

ኒኮላይ ትልቅ ድንች ወሰደና ቁራሽ ዳቦውን ጨው ከነሰነሰበት በኋላ እንደበሬ ዝግ ብሎና ሳያ ቋርጥ ማመንዠግን ቀጠለ ።

«እዚህ ሁኔታው እንዴት ነው?» በማለት ምግብ በአፉ መልቶ ጠየቀ ።

ፋብሪካው ውስጥ የፕሮፓጋንዳ ሥራ እንዴት እንደሚያሠራጩ አንድሬይ ዘርዝሮ ባብራራለት ጊዜ ኒኮላይ እንደገና ባለመደሰት ከፋው ።

«ረዥም ጊዜ ይወስዳል ። በጣም ረዥም ጊዜ ይወስዳል! ፈጠን ባለ ሁኔታ መሥራት አለብን...» አለ ።

እናት እርሱን ስትመለከት የጥላቻ ስሜት ለልቧ ተሰማት ።

«ሕይወት በልምጭ እየተገረፈ የሚጋልብ ፈረስ አይደለም!» በማለት አንድሬይ ተናገረ ።

ኒኮላይ በግትርነት ራሱን ነቀነቀ ።

«በጣም ረዥም ጊዜ ነው! ይኸን ያህል መቆየት አልችልም! ምን ማድረግ ይሻለኛል?»

መልስ በመጠበቅ የኾኾልን ፊት በሚመለከትበት ጊዜ ግራ ገብቶት የመጨነቅ ሁኔታ ይታይበት ጀመር ።

«ሁላችንም መማር እና መልሰንም ሌሎችን ማስተማር አለብን!» በማለት አንድሬይ ጭንቅላቱን ወደመሬት ቀለስ አድርጎ ተናገረ ።

«መታገል የምንጀምረው ታዲያ መቼ ነው?» በማለት ቬሶቭሺኮቭ ጠየቀ ።

«ትግሉን መች እንደምንጀምር አላውቅም ። ትግሉን ከመጀመራችን በፊት ብዙ ጊዜ ደህና አድርገው እንደሚወቁን አውቃለሁኝ!» በማለት እየሳቀ መለሰለት ። ከዚያም ቀጠል አድርጎ ፡ — «እኔ እንደሚታየኝ ከሆነ ከጠመንጃው ትጥቅ በፊት የአእምሮ ትጥቅ እንዲኖረን ያሻል...» ብሎ ተናገረ ።

ኒኮላይ እንደገና መብል መመገቡን የቀጠለ ሲሆን ፤ እናትም ጠፍጣፋ የሆነ ግዙፍ አካሉን የሚያቻ



ችልለትን ዝርግ ፊቱን ቀስ ብላ በማሾለቅ ሠረቅ እያደረገች ትመለከት ጀመር ።

ተጋራፊ ከሆኑት ትናንሽ ዓይኖቹ ጋር ዐይን-ለዐይን ግጥም በማለቷ ምክንያት ሁኔታው ቅንድቦቿን አርበደበደው ። አንድሬይ ርጋታ-ቢስ ነው ። ድንገት መሳቅ እና መናገር ይጀምራል ። ከዚያም ማፏጨት ይቀጥላል ።

አንድሬይ ምን እንደሚያሳስበው አሰበች ። ኾኾል ለሚናገራቸው ንግግሮች ሁሉ የአንገራጋሪነት መልስ እየሰጠ ኒኮላይ በመተከዝ ተቀምጦአል ።

ትንሿ ክፍል ለእናት እንግዶች ምቾች የጎደላት የማታዝናና ክፍል የሆነችባቸው ስትሆን አንዴ አንድሬይ ሌላ ጊዜም እርሷ እየሆኑ በመሠረቅ እንግዳቸውን ይመለከቱታል ።

በመጨረሻም ቬሶቭሺኮቭ ከተቀመጠበት ተነሣ ።

«ወደምኝታ ቦታዬ ልሂድ ። እዚያ እሥር-ቤት በመቀመጥ ላብድ ምንም ያህል አልቀረኝም ነበር ። ይኸው ድንገት ስለለቀቁኝ ወጣሁኝ ። ደክሞኛል ።» በማለት ተናገረ ።

ወደ ምግብ ማዘጋጃ ቤቱ ክፍል ሄደ ። ከዚያም ጥቂት ዕርምጃ እንደተጓዘ ድንገት ዝም አለ ። እናት መራመድ አለመራመዱን ለማወቅ ጆሮቿን ቀሥራ ታዳምጥ ጀመር ። አንዳችም የሚሰማ ድምፅ አልነበረም ።

«አሥፈሪ በሆነ ሃሣብ ተውጧል ።» በማለት ለአንድሬይ ቀስ ብላ ነገረችው ።

«አስቸጋሪ ሰው ነው!» በማለት ኾኾል ራሱን በመገረም እየነቀነቀ ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ — «ይኸንን መሳዩ ሁኔታ ግን ያልፋል ። እኔም አንድ ጊዜ ልክ እንደዚህ ነበርኩኝ ። እሣት ልብዎ ውስጥ ብሩህ ሁኖ እስኪነድ ድረስ ብዙ አመድ አ

ለው ። እምዬ ወደመኝታዎ ይሂዱና ይተኙ ። ትንሽ ማንበብ እሻለሁኝ ።» በማለት ተናገረ ።

ከክፍሉ በስተጥግ በኩል ከጥጥ የተሠራ መጋረጃ ውስጥ ወደሚገኘው አልጋዋ ዘንድ ገባች ። እናት ስትተነፍስ እና ስትፀልይ አንድሬይ ረዘም ላለ ጊዜ ያዳምጣት ነበር ። ግንባሩን እያሻሸና በረዣዥም ጣቶቹ ሪዙን እየዳበሰ የመጽሀፎቹን ገጾች ቶሎ ቶሎ ይገለብጣቸው ጀመር ። ሰዓቱ የደወል ድምፅ አሰማ ። ነፋሱ በዛፎቹ ላይ ያፏጫል ።

«ወይ ጉድ! በዚች ዓለም የሚኖሩት ሕዝቦች አያሌ ናቸው ። ሁሉም ያጉረመርማሉ ። ደስተኞቹ ያሉት የት እንደሆነ ማወቁ ነው የሚገርመኝ ።» በማለት እናት ለስለስ ባለ ድምፅ ተናገረች ።

«እምዬ ፤ ደስተኞች አሉ! በቅርቡም ቁጥራቸው ይጨምራል ። ብዙ ፤ እጅግ ብዙ ይሆናሉ!» በማለት አንድሬይ መለሰላት ።

## 21

ድርጊቶች ያልተለዩዋቸው ቀናት በተፈራራቂ እየዘለቁ ኑሮ በፈጣን ሁኔታ ይገሰግስ ጀመር ። እየአንዳንዱ ድርጊት አዳዲስ ሁኔታዎችን ያስከተለ ሲሆን ፤ ሁኔታው ግን እናትን ሊያሰጋት አልቻለም ። ከዚህ ቀደም አይታቸው የማታውቃቸው በስሜት የተዋጡ ሰዎች ከአንድሬይ ጋር ለመወያየት በየምሽቱ አዘውትረው መምጣታቸውን ቀጠሉ ። ከዚያም የካፖርታቸውን ከሣድ ወደላይ ሰቅሰቅ አድርገውና ባርኔጣቸውንም ዝቅ አድርገው ዐይኖቻቸውን እስኪሸፍን ደፍተው ድምፅ ሳያሰሙ ወደመጡበት ይመለሳሉ ። እየአንዳንዳቸው በውስጣቸው ታምቆ ይሰማቸው የነበረውን



ስሜት ተገንዝባዋለች ። የጊዜ ዕጥረት እየሆነባቸው ነው እንጂ ፤ ሁሉም ለመዘመር እና ለመሳሳቅ ፍላጎት ያላቸው ይመስላሉ ። ሁልጊዜም ይቻኮላሉ ። ከመካከላቸው አንዳንዶቹ አዋኪዎች እና አልምጦች ናቸው ። አንዳንዶቹ ደግሞ በሳቅ ፍልቅልቅታ የተመሉና በወጣትነት ትኩስ ኃይል የተዋጡ ናቸው ። አንዳንዶቹ ደግሞ ጭምቶች እና በሃሣብ የተዋጡ ናቸው ። እየአንዳንዳቸው በከፍተኛ ደረጃ የየራሳቸው ጠባይ ቢኖራቸውም ሁሉም በራሳቸው የሚተማመኑና ቆራጦችም ሲሆኑ ፤ ፊታቸውም ከሲታ ፤ ጠባያቸው የረጋ ፤ ዐይኖቻቸው ጥቋቁር ሁነው በጥልቀት በርኅራኄ እና በንቁነት የሚያስተውሉ ፤ የእነርሱ ጠቅላላ መልክም ፈጣሪ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኤማሁስ ሲጓዝ ይታይበት የነበረውን መልኩን ይመስሏት ነበር ።

እናት የእነርሱን ብዛት በሃሣቧ በመቁጠር ልጅዋ ፓቬል በጠላት እጅ እንዳይወድቅባት በእነርሱ መካከል የሚገኝበትን ቦታ በአዕምሮዋ ታዘጋጅ ጀመር ።

አንድ ቀን አንዲት ፀጉረ-ከርዳዳ የሆነች ጮሌ ልጃገረድ ለአንድሬይ የሚሰጥ የታሸገ ቦስጣ ይዛ መጣች ። ተመልሳ በምትሄድበት ጊዜም የደስ-ደስ ያላቸውን ዐይኖቿን ፏ አድርጋ በማብራት ወደ እናት ዞር ካለች በኋላ እናትን ፡—

«ደህና ይዋሉ ጓዲት!» አለቻት እናትም ፈገግ በማለት ፡—

«ደህና ዋይ ።» አለቻት ።

ልጃገረዲቱን ከሸኘቻት በኋላ እናት ተመልሳ ወደቤት በመግባት ይህቺን እንደ ፀደይ አበባ በትኩስነት ያጋሸበችይቱን እና ክብደቷ እንደቢራቢሮ የቀለለ ሁኖ በመንገድ ላይ ቂብ-ቂብ እያለች በፍጥነት እርምጃ የምትጓዘውን ጓዲቷን ልጃገረድ በመስኮት ውስጥ ሁና እናት በፈገግታ ትመለከት ጀመር ።

«ጓዲት! አንቺ የኔ ውዷት! መላ፡ሕይወትሽን ከአን ቺ ጋር አብሮ የሚጓዝ ጓድ እግዚአብሔር ያድልሽ!», በማለት እናት በማጉረምረም ልጃገረዷቱ ከዐይኗ እ የራቀች ስትጓዝ ተናገረች ።

የሚመጡት ሰዎች እናት ራሷን ዝቅ አድርጋ እንድትስቅ የሚያስደርጉ አንዳንድ ምክንያቶች ነበሩ ቸው ። ይሁን እንጂ ፤ ራሳቸው ባላቸው ዕምነት እና ሀ ቀኝነታቸውም ከጊዜ ጊዜ የተረጋገጠ ሁኖ በማግኘቷ በደስታ ስሜት የተነካች እንድትሆን አብቅቷታል ። በፍትህ ድል አድራጊነት ሕልማቸው ልቧ የተቀሰቀ ሰና የተነካ ሲሆን ፤ በአንዳች ምክንያት ግን እነርሱ በተናገሩ ቁጥር ስታዳምጣቸው ትካዜ ይሰማታል ። በተለይም መዘባነን በሌለበት ጠባያቸውና እንደዚሁ ም ቸርነት በተመላው ሁኔታቸው ከልብ ተነክታ ለች ።

ሕይወትን በሚመለከት ረገድ ከሚናገሯቸው መካ ከል አብዛኛውን የተገነዘበች ከመሆኗም በስተቀር ፤ ለሰው ልጅ ሀዘን ዕውነተኛ ምንጩ ምን እንደሆነ ያገኙችው መሆኑ የተሰማት ሲሆን ፤ እነርሱ ከሚያቀ ርቧቸው አመለካከቶች ጋር መስማማትንም ተላመደ ች ። ይሁን እንጂ ፤ በልቧ ውስጥ በጥልቀት የሚገኘው ዕምነቷ ሕይወትን እነርሱ እንደገና አድሰው ያዘጋጁታ ል የሚል ዕምነት የሌለው ሲሆን ፤ እነርሱ ባቀጣጠሉት እሳት ዙሪያ መላውን ወዝ-አደሮች አከማችተው ለመሰብሰብ ይቻላቸዋል ብላ አታምንም ነበር ። ሁሉም ቢሆን ከርሱን ለመሙላት የተዘጋጀ ነው ። ማንም ቢሆን እስከሚቀጥለው ቀን ድረስ ይኸንን ለማስተላ ለፍ የሚሻ አልነበረም ። ያንን ረዥም እና አድካሚ የሆነ ጎዳና የሚዘልቁት ጥቂቶች ብቻ ነበሩ ። የሰብአው ያን ፍጡሮች የወንድማማችነት መንግሥት የኋላ-ኋላ የሚደረስበት የመሆኑን አስደናቂ ትርኢት በቅድሚያ



ለመቃኘት የሚችሉት ዐይኖች ጥቂቶች ናቸው ። ስለዚ ህም ፤ ምንም እንኳን ሁላቸውም ጢሞች ያጤሙና አመለካከታቸውም አብዛኛውን ጊዜ ከድካም የተነሳ የዛለ የብልህ ሰው አመለካከት ቢሆንም ፤ እነዚህ ሁሉ የተባረኩ ግሩም ሰዎች ለእርሷ እንደልጆቿ የሚቆጠ ሩ ናቸው ።

«እናንት ምስኪኖች!» በማለት ራሷን እየነቀነቀች አሰበች ።

ሁሉም ግን ቀጥተኛ የሆነ ፤ ጥሞና ያልተለየውና አስተዋይ የሆነ አኗኗር ይኖራሉ ። በጎ ተግባር ስለመ ፈጸም ይናገሩ የነበረ ሲሆን ፤ የሚያውቁትን ለሌሎች የማስተማር ጥረታቸውንም አላቋረጡም ። አደገኛ የሆነ ቢሆንም እንኳን ይኸንን መሳይ ኑሮአቸውን እንደም ን አድርገው እንደሚያፈቅሩት ያስተዋለች ሲሆን ፤ ት ንሽ ከተነፈሰች በኋላም የእርሷን የራሷን የሕይወት ዕላሎት መለስ ብላ አስታወሰች ። ለዚህ ለአዲሱ አኗ ኗር እርሷ ራሷም ጠቃሚታ ያላት መሆኗን ቀስ-በ ቀስ ሕሊናዋ እየተገነዘበው ይሄድ ጀመር ። ቀደም ሲል ማንም ይሻኛል ብላ የምትገምት ያልነበረች ስትሆን ፤ አሁን ግን ብዙ ሰዎች የሚሿት መሆኑን በግልጽ ያስተዋለች ስትሆን ፤ ይኸ ድርጊትም ለራሷ ተገቢ የሆነ ከፍተኛ ቦታ እንድትሰጥ ያደረጋት ትል ቅ ግንዛቤ ነው...

ተበታኝ ጋዜጣዎቹን ያለማሰለስ በየተወሰነው ጊዜ ወደፋብሪካው እየያዘች የምትሄድ ስትሆን ፤ ይኸንንም ተግባሯ አድርጋ ትቆጥረው ጀመር ። ሰላዮቹ አዘውትረ ው ይመለከቷት የነበረ በመሆኑ ከቁም-ነገርም አያገ ቧትም ። ብዙ ጊዜ የፈተሿት ሲሆን ፤ ሁሉንም ጊዜ ይፈትሿት የነበረው ተበታኝ ጋዜጦቹ በተበተኑበት ማግሥት ነው ። የያዘችው አንዳችም ተበታኝ ነገር ሳይኖራት ዘበኞቹ እንዲጠራጠሯት ለማድረግ እንዴት

እንደምትችል ታውቃለች ። እነርሱም ካቆሚት በኋላ የሚፈትሿት ሲሆኑ ከእነርሱ ጋር በመወዛገብም ከሰብአዊ ክብሯ የተደፈረች አስመስላ ታሳያለች ። ከዚያም አንዳችም ነገር ስላላገኙባት ሀፍረት ላይ እንዲወድቁ ካደረገቻቸው በኋላ በችሎታዋ ኮርታ ትሄዳለች ። ይኸንን መሳዩ ድርጊት የምታፈቅረው ተግባሯ ነበር ።

ቬሶቭሺኮቭን ፋብሪካው እንደገና መልሶ አልቀጠረውም ። የደን እንጨት ከሚሸጥ ድርጅት ውስጥ ሥራ አገኘ ። ሥራውም ግንዲላዎችን ፤ ሳንቃዎችን እና የማገዶ እንጨቶችን በመሰብሳሰብ ማጓጓዝ ነበር ። በየእለቱ ከእንጨቶቹ ጋር ሲጓዝ እናት ታየዋለች ። መጀመርያ ሁለት ከሢታ የሆኑ እና በሽክም ብዛትም እግሮቻቸው የሚንቀጠቀጡ ፤ ጭንቅላቶቻቸውም የተሰላቹ እና የተዳከሙ ዐይኖቻቸውን እያርገበገቡ የሚጓዙ ፈረሶች ይታያሉ ። ከእነርሱ በስተኋላም አንድ ላይ የተጠፈሩ ረዣዥም የረጠቡ ግንዲላዎች ወይንም የተደራረቡ ሳንቃዎቹ ኳ-ኳ-ኳ የሚል ድምፅ እያሰሙ ይጎተታሉ ። ከእንጨቶቹ በስተኋላም የፈረሶቹን ልጓም አጥብቆ ይዞ ኒኮላይ ኋላ-ኋላ ይጓዛል ። በጽዳት ጉድለት የቆሸሸ እና የተደራረተ ልብስ የለበሰ ፤ መጫሚያውም ትልቅ ቡት ሲሆን ፤ ባርኔጣው ወደበስተጭንቅላቱ አዘቅዝቆአል ። ሁኔታውን ለተመለከተው ከመሬት እንደተነቀለ ወፍራም ጉቶ ቀርፈፍ-ቀርፈፍ እያለ የሚጓዝ ነው ። እርሱም በሚጓዝበት ጊዜ ራሱን ወደመሬት ቀለስ አድርጎ በማዘቅዘቅ ዐይኖቹ መሬት-መሬቱን ያያሉ ። ፈረሶቹ የዕውር የድንብራቸውን ከሚጎትቱት ጋር እና ከአላፊ — አግዳሚ ሰዎች ጋር ይተረማመሳሉ ። በዚህም ምክንያት ሰዎቹ ኒኮላይ ላይ ቀፎው እንደተነካበት ንብ የቁጣና የስድብ ናዳ ያወርዱበታል ። እርሱ ግን አንዳችም የመልስ አጸፋ የማይሰጥ ከመሆኑም በስተቀር ቀና ብሎም አይመለከታቸውም ።



ፉጨቱን እያፏጨ ፈረሶቹን ፡ — «ሱ!መንገዳችሁን ያዙ!» እያለ በቁጣ ይናገራል ።

አዲስ የደረሱ የውጭ ሀገር ጋዜጦትን ወይንም ተበታኝ ወረቀቶችን ለማንበብ አንድሬይ ጓዶቹን በመጥራት በሚሰበስብበት ጊዜ ሁሉ ኒኮላይ ከበስተጥግ በኩል በመቀመጥ አንድ ወይንም ሁለት ሰዓት በፀጥታ ያዳምጣል ። ከንባቡ በኋላም ወጣቶቹ በተነበበው ላይ የጋለ ክርክር ያደርጋሉ ። ኒኮላይ ግን በክርክሩ አይሳተፍም ። ሁሉም ከሄዱ በኋላ እርሱ ቆጭ ብሎ ከአንድሬይ ጋር ንግግሩን ይቀጥላል ፡—

«በዚህ ጉዳይ ይበልጥ ሊወቀስ የሚገባው ማነው?» በማለት በማኩረፍ መልክ ጠየቀ ።

«የሚወቀሰው ሰው 'ይህ የእኔ ነው!' በማለት በመጀመሪያ ጊዜ ያስታውቀው ሰው ነው ። ያ ሰውም ከጥቂት ሺህ ዓመታት በፊት የሞተ ሲሆን አሁን እርሱን መቆጣቱ ከቶውንም አንዳችም የሚያስገኘው ጠቀሜታ የለውም!» በማለት ኾኾል ቀልድ በተመላበት ሁኔታ ፤ ነገር ግን ደግሞ ዐይኖቹ በማስተዋል ተመስጠው መለሰለት ።

«ሃብታሞችስ? ደጋፊዎቻቸውስ? ጥፋተኞች አይደሉምን?» በማለት ጠየቀ ።

ኾኾል ፤ ስለኑሮ እና ስለሰዎች ምን እንደሚያውቅ ቀላል በሆነ አገላለጽ ለማብራራት ቃላት በሚፈልገበት ጊዜ ጆሮውን እያፍተለተለ ሪዙን ያሻሻል ። በኾኾል አመለካከት ሰዎች ሁሉ በጥፋተኛነት ተጠያቂዎች ሲሆኑ ፤ ይኽ መልስ ደግሞ ኒኮላይን አላረካውም ። ወፋፍራም ከናፍሮቹን አገጣጥሞ ራሱን ባለመስማማት ምልክት ይነቀንቃል ። በመጨረሻም ያልረካና ያልተደሰተ በመሆን ተሰናብቶ ይሄዳል ።

«የተወሰኑ ሰዎች በጥፋተኛነት ተወቃሾች መሆን አለባቸው!» በማለት አንድ ቀን ተናገረ ። ከዚያም ፡ —

«እነዚህ ተወቃሽ ሰዎችም እዚሁ አለንበት የሚገኙ ናቸው ። አንዳችም ይቅርታ ባለማድረግ በአረም እንደ ተወረረ መሬት መላውን ሕይወታችንን መነቃቀል አለብን!» በማለት ተናገረ ።

«አንድ ቀን የጊዜ ተቆጣጣሪ የሆነው ኢሳይ ስለ እናንተ የተናገረው ይኸንን ነበር!» በማለት እናት አስታወሰች ።

«ኢሳይ?» ብሎ ቬሶቭሺኮቭ ጥቂት ዝም ካለ በኋላ ጠየቀ ።

«አዎን ። እርሱ ማናቸውንም ጥያቄ ከቦታ-ቦታ በማነፍነፍ የሚጠይቅ ክፉ ሰው ነው ። እዚህ መምጣትም የጀመረ ሲሆን ከበስተመስኮት በኩልም ያሾልቃል...» አለች ።

«በመስኮት በኩል ያሾልቃል?» በማለት አንድሬይ ደግሞ ጠየቀ ።

እናት አልጋዋ ላይ ስለነበረች የኒኮላይን ፊት አልተመለከተችም ። ይሁን እንጂ ፡ —

«ይኸንን ያህል ትርፍ ጊዜ ካለው እየመጣ ያሾልቅ!» ብሎ ሲናገር የአንድሬይ መልክ እንደምን እንደተለወጠ ልትገነዘብ ችላለች ።

«ኧረ ቆይ ፤ እስኪ ቆይ ፤ ጉዳዩ እንዲህ እኮ አይደለም ። ከተወቃሾቹ መካከል እርሱም አንደኛው ነው!» በማለት ኒኮላይ ተናገረ ። ከዚያም አንድሬይ ወዲያውኑ ቀበል በማድረግ ፡ —

«የእርሱ ተወቃሽነት ደግሞ ምን በሆነ ነው ፤ ጅል-እንከፍ በመሆኑ ነውን?» ብሎ ጠየቀ ።

ቬሶቭሺኮቭ መልስ ሳይሰጥ ተነስቶ ሄደ ።

ኾኾል ተቀምጦ ከነበረበት ተነስቶ በዝግታ እርምጃ ክፍሉ ውስጥ መራመድ የጀመረ ሲሆን ፤ እንደ ሸረሪት እግሮች እጥፍ-ዘርጋ የሚሉት ረዣዥም እግሮቹ በተራመደ ቁጥር ድምፅ ያሰማሉ ። ፔላጊያን ፀ



ጥታ ላለመንሳት በማለት ሁል ጊዜ እንደሚያደርገው ሁሉ ቡት ጫማውን አውልቆአል ። እርሷ ግን አልተኛችም ።

ኒኮላይ ከቤት ወጥቶ እንደሄደ ፡ —

«ይኸ ሰው ያስፈራኛል!» በማለት እናት በመጨነቅ መልክ ተናገረች ።

«አ-ዎን!» በማለት ትንፋሹን እየዋጠ፣ ኾኾል ተናገረ ። ከዚያም በመቀጠል ፡ — «እርሱ እጅግ ሲበዛ ቅን ነው ። እምዬ ፣ ሁለተኛ የኢሳይን ስም አያንሱበት ። ኢሳይ የለየለት ሰላይ ነው» በማለት ተናገረ ።

«ይኸ የሚያስገርም ጉዳይ አይደለም ። ያጎቱ ልጅም ዣንዳርም ነው » ብላ እናት መለሰችለት ። ከዚያም ኾኾል ንግግሩን በመቀጠል ፡ —

«በመጪው ቀናት ኒኮላይ ሳይደበድበው አይቀርም ። በተራ ሕዝቦች ላይ ሥልጣን ያለው ክቡሩ ሰው ያሳደረውን ስሜት ያስተውሉታልን? እንደ ኒኮላይ የመሳሰሉ ሰዎች የቱን ያህል ተሳስተው እንደነበረ ሲገነዘቡና ትዕግሥታቸው አብቅቶ ሲገነፍሉ ከቶ እንደምን ያለ ሁኔታ ይደርሳል? ሰማይና መሬቱ በደም ይጠልቀለቃል...» በማለት ተናገረ ።

«ፈራሁኝ ፤ አንድርዬ!» በማለት እናት አለስልሳ ተናገረች ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም አንድሬይ ፡ —

«አዩ ፤ ዝምብ ጥልቅ ብላ ካፍዎ ባልገባች ኖሮ ባላስመለሰዎትም ነበር! ይሁን እንጂ የአዛዦች እየአንዳንዱ ጠብታ ደም ደሀ ሕዝቦችን፡ እንዲያነቡ ባደረጉት እንባቸው ውስጥ ተደባልቆ ይዋሃዳል...» በማለት ከተናገረ በኋላ ለስለስ ባለ ሁኔታ በጥቂቱ ሳቅ በማለት ፡ —

«ሁኔታው የሚያዝናና ባይሆንም ዕውነት ነው!» በማለት ተናገረ ።

22

አንድ እሁድ ቀን እናት ለገበያ ወጥታ አንዳንድ ዕቃዎችን ከገዛች በኋላ የቤቷን በር ከፍታ ከመድረኩ እንደደረሰች በከፍተኛ ደስታ ተመላች — ከቤቷ የውስጥ ክፍል ጉልህ የሆነው የልጅዋ የፓቬል ድምፅ ተሰማት ።

«እኝሁና ፤ እናት መጡ!» በማለት ኾኾል ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰማ ።

ፓቬል በፍጥነት ዞር ብሎ ወደርሷ ሲመለከት እናት ያየች ከመሆኗም በስተቀር ፤ በፊቱ ላይም ብሩህ ገጽታ የረበበበት ሲሆን ይኸውም ትርኢት ለእርሷ ተስፋዋ ነበር ።

«ለቤትህ በቃህ!» በማለት በለሆሳስ ከተናገረች በኋላ ባልጠበቀችው ትርኢት በደስታ ድንጋጤ ውጧት ቁጭ አለች ።

ፓቬልም የገረጣ ፊቱን ከርሷ ሥር ዝቅ አድርጎ ተቀመጠ ። ከናፍሮቹ ይንቀጠቀጣሉ ። ዐይኖቹም ዕንባ አቅርረዋል ። ለአፍታ ያህል አንዳችም ነገር አልተናገረም ። እናትም አንዳችም ነገር ባለመናገር በፀጥታ ዝም ብላ እርሱን-እርሱን ትክ ብላ ታስተውላለች ።

ኾኾል ለስላሳ ፉጨት እያፏጨ ወደ ውጪ ወጣ ።

«እማማ ፤ አመሠግንሻለሁኝ!» በማለት ፓቬል በሚንቀጠቀጡ እጣቶቹ እጆቿን እያሻሸ ተናገረ ። እንደገና መልሶም ፡ — «የኔ ውድ እናት ፤ አመሠግንሻለሁኝ!» በማለት ተናገረ ።

ይኸንን የአገላለጽ ሁኔታውን በፊቱ ላይ በመመልከቷ እና ትህትና የተመላበት ድምፁንም በመስማቷ እናት በስሜት ተውጣ የልጇን ራስ በመደባበስ የልቧን የሞቀ ትርታ ለማስታገስ ሞከረች ፡ —



«ኧረ ስለፈጣሪ ብለህ ፤ ለምኑ ነው እንዲህ የምታመሠግነኝ?» በማለት ተናገረች ።

«ታላቁ ተግባራችንን በመርዳትሽ ። አመሠግንሻለሁኝ!» በማለት ደግሞ ከተናገረ በኋላ ቀጠል አድርጎም ፡ — «እንዲህ እንደኔ እና እንደ አንቺ ከእናቱ ጋር የመንፈስም ቅርበት አለኝ ብሎ መናገር የሚችል ሰው ቢኖር ጥቂት ነው!» አለ ።

እጅግ መልካም እና እጅግ ተወዳጅ በመሆን ከፊት ለፊቷ ቆሞ የነበረው ልጅዋ የሚናገራቸውን ቃላት በታላቅ ስሜት በጥሞና ለማድመጥ በመሻት ዝም ብላ ታስተውለው ጀመር ።

«እናት ፤ ተግባሩ ምን ያህል ችግር አድርሶብሽ እንደነበረ እገነዘበዋለሁኝ ። ከተግባሩ መካከል ምን ያህሉን ትሺው እንዳልነበረ እገነዘባለሁኝ ። መላ ሕይወትሽን እንደተሰቃየሽ ሁሉ የወደፊቱ ጊዜሽንም በዝምታ ስቃይን እየተቀበልሽ የምታሳልፊ እንጂ ፤ የእኛ አስተሳሰብ የአንቺም አስተሳሰብ ጭምር ይሆናል ብዬ ፍጹም አልገመትኩኝም ነበር ። ይኸንን ማሰብ ለእኔ ከባድ ነበር!..» በማለት ተናገረ ።

«ብዙ ነገሮችን እንድገነዘብ አንድርዬ ረዳኝ!» ብላ ተናገረች ።

«ስለአንቺ ነገረኝ!» በማለት ፓቬል እየሳቀ ተናገረ ።

«እንደዚሁም የጎርም ጭምር ። እርሱና እኔ የአንድ መንደር ሰዎች ነን ። አንድርዬ ማንበብ ሊያስተምረኝ እንኳን ፈልጎ ነበር…» አለች ።

«አንቺም ሀፍረት ተሰምቶሽ ነበር ። ስለዚህም ራስሽ በራስሽ ለመማር ፈቀድሽ?» አላት ።

«እንዲህ መሆኑን ገምቶ ነበራ!» በማለት በአንክሮ ተናገረች ። ከዚያም በደስታ የተዋጠው ልቧ አስጠብቧት ፡ — «እንጥራው እንጂ ወደቤት እንዲገባ ። እኛ ብቻችንን እንድንነጋገር ይሁነኝ ብሎ ነው የወጣው ።

የራሱ እናት የለውም…» በማለት ተናገረች ። ፓቬልም በሩን ከፈተና መድረኩ ላይ ብቅ ብሎ ፡—

«አንድሬይ ፤ የት ነው ያለኸው? ና እንጂ » በማለት ተጣራ ።

«እዚህ ነው ያለሁት ። እንጨት ትንሽ መፈላለጥ ፈልጌ ነው » በማለት አንድሬይ ተናገረ ።

«ና ግባ እንጂ!» በማለት ፓቬል ጠራው ።

ወዲያውኑ አልሄደም ። እቤት ውስጥ እንደገባም ስለቤት ዕቃዎች ጉዳይ ማውራት ጀመረ ።

«ኒኮላይ ጥቂት የማገዶ እንጨት እንዲያመጣልን መጠየቅ ሊኖርብኝ ነው ። የቀረን እንጨት ጥቂት ነው ። እምዬ ፡ ይኸንን ፓቬልን እስኪ ትክ ብለው ይመልከቱት ። ባለሥልጣኖቹ አመጸኞችን በመቅጣት ፈንታ እየቀለቡ ያደለቧቸው ይመስላል…» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

እናት ሳቀች ። አሁንም ከደስታ ብዛት እንደዛለች ነበረች ። ይሁን እንጂ ረጋ ያለ እና ሥርአት ያለው የሰከነ አስተሳሰቧ ልጅዋን አሁን ባለበት የስሜት ሁኔታው ሳይሆን ርጉ የሆነውን የእርሱነት ነባር ጠባዩን ለማየት እንድትሻ አስከጀላት ። ሁሉም ነገር ግሩም-ድንቅ ነበር ። ይኸ ለሕይወቷ የመጀመርያ ታላቅ የደስታ ጊዜ ፤ ልክ አሁን ባለው ሁኔታ እስከምንግዜውም ጠንካራና ከፍተኛ በመሆን በልቧ ማሕደር እንደተጠበቀ እንዲቆይ አስመኛት ። ይኸ ደስታ ይፈራርስ ይሆናል ብላ በመፍራት ፡ አንድ የትም የማይገኝን ወፍ በድንገት ያገኘ የአዕዋፍ ሰብሳቢ ወፉ እንዳያመልጠው የወፍ ጎጆውን እዚህም-እዚያም እያስተዋለ ለማጠባበቅ እንደሚጣደፍ ዓይነት ሆነች ።

«ምሳ እንብላ! ምንም የበላህ አይመስለኝም ፤ ፓሻ?» በማለት እናት ጉድ-ጉድ እያለች ተናገረች ።

«አዎን ። ትላንትና የእሥር-ቤቱ አዛዥ ሊለቅቁኝ



መወሰናቸውን ነገረኝ ። ስለዚህም አንዳችም ነገር ለመብላትም ሆነ ለመጠጣት አልቻልኩም ነበር…» በማለት ተናገረ ።

«ከእሥር-ቤት ስወጣ ያገኘሁት የመጀመርያው ሰው ሲዞቭ ነበር ።» በማለት ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አድርጎ ፡—«እኔን ባየኝ ጊዜም ሰላምታ ለመለዋወጥ መንገዱን አቋርጦ መጣ ። በአሁኑ ጊዜ እኔ በፖሊስ ዐይነ-ቁራኛ የምጠበቅ መዘዘኛ ሰው ስለሆንኩኝ ቢጠነቀቅ እንደሚሻለው ነገርኩት ። ይኸ እርሱን የማያሰጋው መሆኑን ከተናገረ በኋላ የእህቱ ልጅ እንዴት እንደሆነ ማናቸውንም ዓይነት ጥያቄዎች አቀረበልኝ ። ፌዎዶር በእሥር-ቤት ውስጥ ጠባዩን አሳምሮ ይገኝ እንደሆነ ጠየቀኝ ። 'እሥር-ቤት ሁነህ የሚኖርህ ጠባይ እንዴት ዓይነት ነው?' በማለት እኔ መልስ ሰጠሁት ። 'መቼም በማናቸውም እዚያ ባሉት ጓዶቹ ላይ እንደማይነጫነጭባቸው ተስፋ አለኝ' በማለት ተናገረ ። ፌዎዶር ዕውነተኛ እና ብልህ የሆነ ጥሩ ሰው መሆኑን ስነግረው ጢሙን እያሻሸ ኩራት በተመላው ሁኔታ 'ከእኛ ከሲዞቭ ዘርዮች መካከል አንዳችም ስም-አስጠፊ ጥቁር በግ አይገኝብንም!' በማለት ተናገረ ።» ብሎ ፓቬል ተናገረ ።

«ሽማግሌው አንጎሉ ያስባል » በማለት ኾኾል ራሱን እየነቀነቀ ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡—«ከእርሱ ጋር ብዙ ብዙ ተወያይቻለሁኝ ። ፌዎዶርን ቶሎ ይፈቱት ይሆን?» ብሎ ኾኾል ጠየቀ ።

«ሁሉንም የሚፈቷቸው ይመስለኛል ። ያ ሽማግሌ ኢሳይ ከሚያወራው በስተቀር አንዳችም ያገኙባቸው ነገር የለም ። የእርሱስ ወሬ ቢሆን ምን ሊሆን ይችላል?» በማለት ፓቬል መለሰ ።

እናት ዐይኖቿን ከልጅዋ ላይ ሳታነሳ ወደፊትና ወደኋላ ትወዛወዛለች ። አንድሬይ እጆቹን ወደኋላ አድ

ርጎ ፓቬል የሚናገረውን እያዳመጠ መስኮት አጠገብ ቆሞአል ። ፓቬል በወለሉ ላይ ይራመዳል ። ጢሙን ያሳደገ ሲሆን ፤ ጉንጮቹን ትናንሽ እና ረቂቅ የሆኑ ፀጉሮች ከብበውት የጠቆረ መልኩን መለስ እንዲል አድርገውለታል ።

«ቁጭ በሉ!» በማለት እናት ምሳ አቅርባ ተናገረች ።

ማዕድ ላይ ሁነው አንድሬይ ለፓቬል ስለሪቢን ነገረው ። አንድሬይ ንግግሩን እንደጨረሰም ፡ —

«እኔ በዚያን ጊዜ እቤት መጥቼ ቢሆን ኖሮ እንዲሄድ አላደርገውም ነበር!» በማለት በድርጊቱ እያዘነ ፓቬል ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አድርጎ ፡ — «ለመሆኑ ከርሱ ጋር አብሮ ይዞ የሚሄደው ምንድነው? ምንም ይዞ የሚሄደው የለም ። የተምታታበትን አዕምሮውንና ብዙ የጥላቻ ስሜቶቹን ብቻ ነው » በማለት ተናገረ ።

«አየህ ፤ አንድ ሰው የአርባ ዓመት ዕድሜ ሲጠጋው እና የዚህን ዕድሜውን አብዛኛውን ጊዜም መንፈሱ ውስጥ ጉብ ብለው ከሚገኙት ድቦች ጋር ሲተናነቅ እርሱን እንደአዲስ ሰው እንደገና ማነጽ አስቸጋሪ ነው...» በማለት ኾኾል እየሳቀ ተናገረ ።

የአብዛኛዎቹ ቃላት ትርጓሜ ለእናት አስቸጋሪ እየሆኑ የሚገኙት ክርክሮች በፓቬልና በኾኾል መካከል መካሄድ ጀመሩ ። ማዕድ ተነስቷል ። እነርሱ ሁለቱ ግን ከፍተኛ የብልሆች ቃላት እየተለዋወጡ መወያየታቸውን ፤ መከራከራቸውን ቀጠሉ ። አልፎ-አልፎም ቀላል የሆኑ ቃላትን በመጠቀም ይናገራሉ ።

«ወደፊት መግፋት አለብን ። አንዳችም እርምጃ ቢሆን ወደኋላ መሄድ የለብንም!» በማለት ፓቬል አጠንክሮ ተናገረ ።

«እንደጠላት ከሚቆጥሩን ብዙ አሥር ሚሊዮን



ሕዝቦች ጋርም ግጭት መፍጠር አለብን?» ብሎ ኾኾል ጠየቀ ።

እናት ክርክራቸውን ስታዳምጥ ፓቬል ገበሬዎችን የማይወድ መሆኑን የተገነዘበች ሲሆን ፤ ኾኾል በበኩሉ ደግሞ ገበሬዎችንም ትክክለኛውን መንገድ በማሳየት መምራት ያስፈልጋል በማለት አዘውትሮ ስለሚናገር ገበሬዎችን የሚደግፍ መሆኑን ተረዳች ። አንድሬይ ሲናገር ሃሣቡን ይበልጥ የምትረዳው ስትሆን ኾኾል የሚያቀርበው ሃሣብም ትክክለኛ ሃሣብ መስሎ ይሰማታል ። ይሁን እንጂ ኾኾል ለፓቬል ሃሣብ ሁልግዜም መልስ በሚሰጥበት ጊዜ ኾኾል ልጅዋን ያላስቀየመው መሆኑን ለማረጋገጥ የልጅዋን የመልስ ቃል እና ሁኔታ በንቃት ትጠባበቃለች ። እነርሱ ግን ሳይናቆሩ እና ሳይጣሉ ሁልግዜም እርስ-በርሳቸው የሞቀ ክርክራቸውን ያካሂዳሉ ።

«በእርግጥ እንዲህ ነውን ፤ ፓቬል?» በማለት አንዳንድ ጊዜ ልጅዋን ትጠይቃለች ።

«በእርግጥ እንዲህ ነው!» በማለት ልጅዋ በፈገግታ ይመልስለታል ። ኾኾል ለዛ በተመላበት ፌዝ የሚከተለውን ለፓቬል ተናገረ ፡ —

«ምነው ጌታው ፤ ጥሩ ምግብ ተመገበዋል ። ነገር ግን ደህና አድርገው በማላመጥ ምግብዎን አልዋጡም ። ከጉሮሮዎ ላይ ተንጠልጥሎ የቀረ ምግብ አለ ። ስለዚህም እስኪ በመጠጡ ያወራርዱበት!» አለው ።

«አንተ እኮ ቀልደኛ ነህ ። እውን?» በማለት ፓቬል ተናገረ ።

«አዎን እኔ እንደእንባ-አድርቅ የተዝካር በዓል ቀልደኛ ነኝ!» በማለት ኾኾል መለሰ ።

እናት ቀስ ብላ በመሳቅ ራሷን በመገረም ነቀነቀች ...

## 23

የፀደይ መምጫው ተቃረበ ። በረዶውም እየሟሟ
በመቅለጥ ከሥሩ የተነጠፈውን ጭቃና ቆሻሻ ያጋል
ጥ ጀመር ። ዕለት አልፎ ዕለት ሲተካ የጭቃው መ
ኖርም የዚያኑ ያህል ይታወቅ ጀመር ። የሠፈራው ቦ
ታ በሙሉ ያልታጠበ ቡትቱ ልብስ የለበሰ ይመስላ
ል ። ቀን-ቀን ግራጫ የሆኑት የቤቶቹ ግድግዳዎች ላብ
ይመስል እርጥበት የሚያገኙ ሲሆን ከጣራዎቹ ላይም
ውሃ ጠብ ጠብ ይልባቸዋል ። በምሽት ጊዜ ግን በረ
ዶዎቹ ነጭ ሁነው ይከመራሉ ። ፀሐይቱ በሰማዩ ላይ
ረዘም ላለ ጊዜ መታየት ጀመረች ። በረግረጋማው
መሬት ውስጥ ምንጮች ሹ-ር-ር እያሉ መፍሰስ
መጀመራቸውን ማንም አይጠራጠርም ።

ሜይ ዴይ የተሰኘውን የወዝ-አደሮች በዓል ለማክ
በር ዝግጅቱ ተጀምሮአል ።

የዚህን በዓል ምንነት ተንትነው የሚያብራሩ ወረ
ቀቶች በፋብሪካው ውስጥ እና በሠፈራ ቦታው ተበ
ትነዋል ። በፕሮፓጋንዳ ገና ያልተሳቡት ወጣቶች እን
ኳን የበዓሉን ምንነት የሚያበሥሩትን ወረቀቶች ሲያ
ነብቡ ፡ —

«ዝግጅቶች ማድረግ አለብን!» እያሉ ይናገራሉ ።

«እንግዲህ ጊዜው ነው ። እስካሁን ያሳለፍነው የድ
ብብቆሽ ጊዜ በቂ ነው!» በማለት መለስ ባለ ፈገግ
ታ ቬሶቭሺኮቭ ተናገረ ።

ፌዎዶር ማዚን በከፍተኛ ስሜት ተመልቶአል ።
ጎጆዋ ውስጥ ታሥራ ዊን-ዊን የምትል ድንቢጥ ወፍ
ይመስል ክስት ከማለቱም በስተቀር ሲራመድም ሆነ
ሲናገር ወፈፍ ያደርገዋል ። ከዕድሜው ይበልጥ አርቆ
አስተዋይ እና ዝምተኛም ከሆነው ከያኮቭ ሶሞቭ
ጋር አዘውትሮ ሲሄድ ይታያል ። ያኮቭ በአሁኑ ጊዜ



ከተማ ውስጥ ሥራ አግኝቶ ይሠራል ። እሥር-ቤት ገብ
ቶ ከወጣ በኋላ ፀጉሩ ይበልጥ ቀይ የሆነው ሳሞይ
ሎቭ እና እንደዚሁም ቫሲሊይ ጉሴቭ ፣ ቡኪን ፣ ድራጉ
ኖቭ እንደዚሁም ሌሎችም ጭምር በበዓሉ ላይ ትጥ
ቅ ታጥቆ መገኘት አስፈላጊ መሆኑን እንደሚያምኑ
በት ሲያስገነዝቡ ፣ ፓቬል ፣ ኾኾል ፣ ሶሞቭ እና ሌሎች
ም ግን ይኸንን ድርጊት ተቃወሙት ።

ያው እንደቀድሞው ድክም-ድክምክም ያለው ፣
ቋት-ቋት የሚተነፍሰውና ላብ ያሰመጠው የጎር መጥ
ቶ በተናገረው ቀልድ ምክንያት ጀምረውት የነበረው
የሰልፉ አወጣጥ ክርክራቸው ተቋረጠ ። እርሱም የሚ
ከተለውን ተናገረ ፡ —

«ጓዶች ፣ አሁን የሚገኘውን ማኅበራዊ ሥርዓት ለመ
ለወጥ የሚከናወነው ተግባር እጅግ ከፍተኛ የሆነ
ተግባር ነው ። ይሁን እንጂ ይኸ ተግባር በተሳካ ሁ
ኔታ እንዲቀጥል እኔ አዲስ ቡት ጫማ መግዛት
አለብኝ!» በማለት የተቀዳደደ እና በውሃ የራሰ ቡት
ጫማውን እያመለከተ ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አደረ
ገና — «በቡት ጫማዬ ውስጥ የማደርገው የላስቲኩ ተደ
ራቢ ጫማም ሊጠገን በማይችል ሁኔታ ተቀዳድዶ
አል ። ስለዚህም በየእለቱ እግሮቼ እንደረጠቡ ናቸው ።
ይኸንን ያረጀ ሥርአት በገሀድ እና ያለአንዳች ማ
ወላወል ሳናወግዝ ሦስት ክንድ ጉድጓዴ ውስጥ ገብ
ቼ በተኛሁበት ለመርጋት አልሻም ። እና ስለዚህም ፣
መሣርያ ታጥቀን የሰልፉን በዓል ማክበር አለብን
የሚለውን የጓድ ሳሞይሎቭን ሃሣብ የምቃወም ስሆ
ን ፣ በዚህ ምትክም አዲስና ጠንካራ የሆነ ቡት ጫ
ማዎች እንድታስታጥቁኝ እየጠየቅሁኝ ፣ ይኸውም ድር
ጊት ሶሻሊዝምን በገቢር አውሎ ለማሳየት የበለጠ
አፋጣኝ ሊሆን መቻሉን እና ከፍተኛ ከሆነ ድብደ

ባ ይበልጥ የሚሻል መሆኑን በመግለጽ የራሴን ሃሣብ አቀርባለሁኝ!..» በማለት ተናገረ ።

ይኸንን በመሰለ ያሸበረቀ አነጋገር ሌሎች ሀገሮች ውስጥ የሚኖሩ ወዝ-አደሮች የኑሮ ሁኔታቸውን ለማሻሻል እንደምን የመሳሰሉ ትግሎችን እንደሚያካሂዱ ለወዝ-አደሮች በንግግር ያሰማቸዋል ።

እናት ንግግሮቹን ማዳመጥ ደስ ይላታል ። እርሱ የሚያቀርባቸው ንግግሮች አንድ እንግዳ የሆነ ስሜት እንዲያድርባት ያደርጓታል ፡— እጅግ ጨካኝ የሆኑ የሕዝብ ጠላቶች ፤ ሕዝቦችን ብዙ ጊዜ የሚያታልሉ እና በሕዝቦች ላይም ጭካኔን የሚያበዙ የሕዝብ ጠላቶች ወፋፍራም እና ፊተ-ቀያይ የሆኑ ፤ ወራዶች ፤ ተንኮለኞች እና ጨካኞች የሆኑ ቁመተ-ድንክ ሰዎች መስለው ታዩዋት ። እነዚህ ሰዎች መሬታቸውን በማጣት በዛሩ (በንጉሡ) ሲበደሉ ፤ ተራ ሕዝቦችን በንጉሡ ላይ ያስነሱበታል ። ሕዝቦች በመነሳሳት ገዢያቸው የነበረውን ንጉሥ ሲገለብጡ ፤ እነዚህ ድንክ ሰዎች ሥልጣንን በአጭበርባሪነት እጃቸው ውስጥ ካስገቡ በኋላ ሕዝቦችን ወደ ቀድሞ መናኛ ኑሮአቸው እንዲመለሱ ያደርጋሉ ። ሕዝቦች ይኸንን ድርጊታቸውን የሚቃወሙዋቸው ከሆነ ደግሞ ከመካከላቸው ብዙ መቶ እና ብዙ ሺህ ሕዝቦችን በመጨፍጨፍ ይፈጅዋቸዋል ።

አንድ ቀን እናት ያለ-የሌለ የመንፈስ ጉልበቷን አጠናክራ በመሰብሰብ እርሱ ካደረጋቸው ንግግሮች በአዕምሮዋ የተቀረጸው ምስል እንደምን የመሰለ እንደሆነ ነገረችው ።

«የጎር ኢቫኖቪች ፤ ሁኔታው እንደዚህ ነውን?» በማለት ግራ በተጋባ ፈገግታ ጠየቀችው ።

ለመተንፈስ ደረቱን እያሻሸና ዐይኖቹንም ከወዲያ-ወዲህ ሽው-እልም እያደረገ በእናት አነጋገር የጎር ኢቫኖቪች በሳቅ ተንከተከተ ። ከዚያም ፡—



«እናት ፤ ልክ እርስዎ እንዳቀረቡት ነው! የታሪክን ኮርማ በሬ ቀንዱ ላይ ጨምድደው ነው የያዙት! እዚህ እርስዎ ያቀረቡት አመለካከት በአንዳንድ ጌጣ-ጌጥ ተጋጊጦአል ፤ በልበጣ ተለብጧል ። ሀቆቹ ግን ትክክለኛና ተገቢ የሆነ ቦታቸውን ይዘዋል! ከፍተኛ ሀጢአተኞች እና ሕዝቦችንም እጅግ መርዘኛ በሆነ መዥገርነታቸው የሚቦጠቡጡት እነዚህ ወፋፍራም የሆኑ ትናንሽ ሰዎች ናቸው ። እነዚህን የመሳሰሉ ሰዎችን ፈረንሳዮች ቡርዥዋ በሚል ቅጽል በሠመረ ሁኔታ ቀጽለው ይጠሩዋቸዋል ። እናት ሆይ እንዳይዘነጉት ቃሉን ያስታውሱት ። ቡርዥዋ ። የሰዎችን ድንቁርና ተገናቸው በማድረግ ክንዳቸውን አንስተው ብርብር እያሉ የሚቦረቡሩ ጨካኞች ናቸው ። ከወዲያ-ወዲህ ዥው-ዥው እያሉ የሕዝቦችን ደም የሚመጡ ዥዋ-ዥዌዎች ናቸው...» በማለት ተናገረ ።

«ሃብታሞች ይኸንን ያደርጋሉ ማለት ነው?» በማለት ጠየቀችው ።

«አዎን ። የእነርሱ ያለመታደል ሃብታምነታቸው ነው ። በሕፃን ምግብ ውስጥ መዳብ በትንሽ-በትንሹ መጨመርዎን ባለማቋረጥ ቢቀጥሉ መዳቡ የሕፃኑን አጥንት እንዳያድግ አድርጎ ያጨነግፈዋል ። በዚህም ምክንያት ሕፃኑ አጭር ድንክ ይሆናል ። አንድን ሰው በወርቅ ቢመርዙት ደግሞ ነፍሱ ኩርምት ብላ ታንሳለች ፤ ትንሽ ትሆናለች ። ሕይወት-አልባ እና ግራጫ በመሆን ሕፃናት ለመጫወቻቸው በአምስት ኮፔክ እንደሚገዙት የላስቲክ ኳስ ትሆናለች...» በማለት ተናገረ ።

አንድ ቀን ስለ የጎር በሚነጋገሩበት ጊዜ ፓቬል የሚከተለውን ተናገረ ፡—

«አየህ አንድሬይ ፤ ብዙ የሚቀልዱ ሰዎች ልባቸው በብዙ ሀዘን የተመሉባቸው ሰዎች ናቸው ።»

ኾኾል መልስ ከመስጠቱ በፊት ተንፈስ አለ ። ከዚያም ዐይኖቹን በመመራመር ሁኔታ ጠበብ አድርጎ በመሽብሸብ ፡ —

«ይኽ አባባልህ ትክክል ከሆነ ፤ መላው ሩስያ በሳቅ ተንከትክቶ በሞተም ነበር ማለት ነው...» በማለት ኾኾል መለሰ ።

ናታሻ መጣች ። ምንም እንኳን ሌላ ከተማ ውስጥ ቢሆንም ፤ እርሷም እሥር-ቤት ታሥራ ነበር ። ልምድ የለወጣት አትመስልም ። ናታሻ በመኖሯ ምክንያት ከሁሉም ጋር ቀልድ በመቀለድ እና በሁሉም ላይ በመሳቅ ኾኾል ይበልጥ ደስተኛ ሁኖ እንደነበረ እናት ተገንዝባለች ። ናታሻ እንደሄደች ግን የሀዘን እንጉርጉሮ የተመላበት ፉጨቱን ማፏጨትና ክፍሉ ውስጥ ላይና ታች መመላለሱን ቀጠለ ።

ሳሻ ብዙውን ጊዜ የምትመጣው ለጥቂት ሰዓቶች ብቻ ነው ። ሁልጊዜም ኮስታራና ቶሎ ለመሄድ የምትችኩል ነች ። በአንዳች ምክንያትም ይበልጥ ጎበጥ ያለች እና ተነጫናጭ ሁናለች ።

አንድ ጊዜ ፓቬል ደህና ሁኚ ብሎ ሊሰናበታት በሩን ሳይዘጋ ወደ መድረኩ ሲወጣ እናት በሁለቱ መካከል የተካሄደውን ንግግር አዳመጠች ፡ —

«አርማውን ትይዛለህን?» አለችው ሳሻ ።

«አዎን » አላት ፓቬል ።

«ይህ የመጨረሻ ውሳኔህ ነው?» አለችው ።

«አዎን ። ለእኔ መብቴ ነው» አላት ።

«እና እንደገና ወደ እሥር-ቤት መግባትህ ነዋ?!» አለችው ።

ፓቬል መልስ አልመለሰም ።

«አንትን ልታደርግ አትችልም እንዴ?..» በማለት ጀመረችና አቋረጠች ።

«ምን አልሺኝ?» በማለት ጠየቃት ።



«ሌላ ሰው አርማውን ቢይዝስ?» አለችው ።

«አይቻልም » ብሎ አጥብቆ መለሰ ።

«አስብበት ። ተደማጭነት ያለህ ሰው ነህ ። ማንም ሰው ያፈቅርሃል!.. አንተና አንድሬይ እጅግ ዕውቅ ተወዳጆች ናችሁ ። እዚህ በመሆንህ ምን ያህል ብዙ ቁም ነገር ልታከናውን እንደምትችል አስብ! አርማውን ብትይዝ ግን ሩቅ ወደሆነ ቦታ በግዞት ይልኩሃል ። ግዞቱም ለአጭር ጊዜ ሳይሆን ለረዥም ጊዜ ነው!»

እናት የሳሻን ስሜት ተገንዝባለች ። ስሜታዊ ፍርሃትና መረበሽ ነው ። የሳሻ ንግግር እናት ልብ ውስጥ እንደ በረዶ ውሃ ጠብ-ጠብ እያለ ይንቆረቆራል ።

«ወስኛለሁኝ! ይኽንን ውሳኔየን የሚያስቀይረኝ አንዳችም ምክንያት አይኖርም » በማለት ፓቬል ተናገረ ።

«እኔ ሃሣብክን እንድትቀይር ብጠይቅህ እንኳን አትቀይርምን?» በማለት ጠየቀችው ።

የፓቬል ድምፅ ድንገት ፈጣን እና ቁጡ ሆነ ፡ —

«እንዲህ መናገር የለብሽም ። አንቺ ማን መሆንሽ ነው? ተይ ፤ እንዲህ ብለሽ አትናገሪ!» አላት ።

«እኔማ ሰው ነኝ!» በማለት ድምፅዋን አለስልሳ መለሰችለት ።

«ግሩም ድንቅ ሰው ነሽ!» በማለት እርሱም ድምፁን አለስልሶ እና የሚናገረው ቃል እየተናነቀው ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ — «አየሽ አንቺ ለእኔ ውዲት የሆንሽ ግሩም-ድንቅ ሰው ነሽ ። እና ስለዚህ እንደዚህ ዓይነቱን ንግግር መናገር የለብሽም...» አላት ።

«ደህና ዋል!» ብላው ልጃገረዲቱ መንገዷን ሄደች ።

የጫማዋን ኮቴ እናት በመስማት ሳሻ ትራመድ

የነበረው የሩጫ ያህል እርምጃ እንደነበረ ተገነዘበች ። ፓቬል ተከትሏት ወደ ጓሮ ሄደ ።

የእናት ልብ በፍርሃት ተኮማተረ ። ይነጋገሩ የነበረው ስለምን እንደነበረ በሚገባ አልተገነዘበችም ። ያም ሆኖ ግን አንድ አደጋ የሚያስከትል ነገር ወደፊት ተደቅኖ የሚጠብቅ መሆኑን ገመተች ።

«ምን ለማድረግ እያቀደ ይሆን?» በማለት ለራሷ ተናገረች ።

ፓቬል ከአንድሬይ ጋር ወደቤት ተመለሰ ። ኾኾል ራሱን እየነቀነቀ ፡—

«ይኽንን ኢሳይ የተባለ ሰው ከቶ ምን ማድረግ ይሻላል ፣ እባካችሁን?» አለ ።

«ይኽንን ድርጊቱን እንዲያቆም ብናስጠነቅቀው ይሻላል!» በማለት ፓቬል በማጉረምረም ተናገረ ።

«ፓቬል ፣ ምን ለማድረግ እያውጠነጠንክ ነው?» በማለት ራሷን ወደመሬት ቀለስ አድርጋ እናት ልጅዋን ጠየቀች ።

«መቼ? አሁን?» በማለት መልሶ ጠየቀ ።

«አሁን አይደለም ። በሜይ 1 ቀን » አለችው ።

«ኧ! አርማችንን በመያዝ ከሰልፉ ፊት-ፊት ቀድሜ እሄዳለሁኝ ። ይኽንን በማድረጌም ምናልባት እንደገና እሥር-ቤት ይጨምሩኝ ይሆናል » አለ ።

የእናት ዐይኖች ግለት የተሰማቸው ሲሆኑ ጉሮሮዋም ደረቀ ። እጅዋን ይዞ ያሻሽ ጀመር ።

«ይኽንን ማድረግ አለብኝ ። እናት ፣ እንድትረጂልኝ እሻለሁኝ!» አላት ።

«እኔ ምን አልኩኝ! ምንም አላልኩኝም » አለች ። ቀስ ብላ ራሷን ቀና በማድረግ ። ዐይኖቿ የእርሱን ግትር ዐይኖች ሲመለከቱ እንደገና ኩርምት ብላ አንገቷን ቀለሰች ።

ጫን ትንፋሹን ከተነፈሰ በኋላ እጅዋን ለቀቀ ።



«ይኸ ፣ አንቺን ከማሳዘኑ ይልቅ የሚያስደስትሽ ጉዳይ መሆን አለበት ። ልጆቻቸውን ወደሞት በፈገግታ የሚልኩ እናቶችን የምናገኘው ከቶ መቼ ይሆን?..» በማለት ተናገረ ።

«ኡ-ሆ-ሆ-ሆ! ኧረ ዝም በሉ ጌቶች መጥተዋል ፣ ነጋሪቱን መጎሰም ያሻል!» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

«እኔ ምንም አልተናገርኩኝም ። ተናገርኩ እንዴ? ያሻህን አድርግ ። ለእኔ ግን ችግር ነው ። እናት ነኝ!» በማለት እናት ተናገረች ።

ከርሷ ፈቀቅ በማለት ራቅ አለ ። ከአንደበቱ የወጡት የሚከተሉት ቃላት ግን እናትን ክፉኛ ነደፏት ፡—

«አንድ ሰው የፈለገውን ነገር እንዳያደርግ የሚያግደው አንድ ዓይነት ፍቅር አለ...» በማለት ተናገረ ።

እናትም እንደገና የበለጠ በንግግሩ እንዳያቆስላት በመሥጋት ፡—

«ተወው ፣ ተወው ፓሻ ። ሁሉንም ነገር ተገንዝቤዋለሁኝ ። ለጓዶችህ ስትል ከዚህ የበለጠ ሌላም እንደምታደርግ አውቄአለሁኝ...» በማለት ተናገረች ።

«ለእነርሱ ስል ሳይሆን ፣ ለራሴ ስል ነው ።» በማለት አረማት ።

አንድሬይ ወደበሩ መተላለፊያ መጣ ። የበሩ ክፈፍ ለእርሱ ቁመት አጭር በመሆኑ ፣ እግሮቹን ወደታች አጠፍ አድርጎ አንደኛውን ትከሻውን ዝቅ በማድረግ ሌላኛውን ደግሞ ከፍ አድርጎታል ።

«ክቡር ጌታዬ ሆይ ፣ ይኽንን ሃሣብዎን ርግፍ አድርገው ቢተውት የተሻለ ሳይሆን አይቀርም!» በማለት ፓቬልን በእነዚያ ተዋጊ ዐይኖቹ አትኩሮ በመመልከት ተናገረ ። በቋጥኝ ላይ የተዘረጋ መንሽላሊት ይመስላል ።

እናት የእንባ ሲቃ ይተናነቃታል ።

«ውይ ፤ ልረሳው ምንም አልቀረኝም ነበር…» በማለት ልጅዋ ማልቀሷን እንዳያይባት አንድ የጣደችውን ነገር የረሳች ፣ ይመስል ሰበብ አሳብባ ወደበሩ መግቢያ እየተቻኮለች ሄደች ። አንዴ ከወጣች በኋላ ድምፅዋን ሳታሰማ በልቧ ትርታ የሚዘዋወረው ደም ከእንባዋ ጋር አብሮ ይፈስስ ይመስል ድክም ብላ እየዛለች አለቀሰች ።

በገሚስ ተከፍቶ በነበረው በር በኩል ሁለቱ ሲከራከሩ ትሰማቸዋለች ።

«አንተ ሰው ፤ ለመሆኑ ምን ማድረግህ ነው? እርሳቸውን እንዲህ ማሳዘን ደስታ ይሰጥሃልን?» በማለት ኾኾል ጠየቀ ።

«እንዲህ አትበል!» በማለት ፓቬል ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ።

«ባለመናገር አፌን ዘግቼ ብቀመጥና ራስህን ጅላጅል ስታደርግ ዝም ብዬ ብመለከት ጥሩ ጓደኛህ ሆንኩኝ ማለት ነዋ? እንዲህ የምትናገረው ለምንድነው? ይኸው እንግዲህ ንግግርህ ምን እንዳስከተለ አትመለከትምን?» አለው ።

«ጠንካራ ሁነህ መገኘት አለብህ ። ‘አዎን ፤ ነው ።’ ማለትን እና ‘የለም አይደለም’ ማለትን የምትፈራ ሰው መሆን የለብህም » አለው ፓቬል ።

«ለእርሳቸው?» በማለት ኾኾል ጠየቀው ።

«ለማንም ቢሆን ። እግሮችህ ላይ ታሥሮ የተንጠለጠለ ወይንም ወደኋላ የሚጎትት ፍቅርም ሆነ ጓደኝነት አልሻም…» በማለት ፓቬል ተናገረ ።

«ኡ-ሆ-ሆ! እንዴት ዓይነት ጀግና ነህ እባክህ! ጎሽ! ታዲያ ጓሮ ገዳይ ፤ ጓሮ ገዳይ እያልክ አቅራራ እንጂ! አየህ ፤ ይኸንን የምትነግረው ለኔ አይደለም ። ሂድና ለሳሻ ንገራት ። ለርሷ ነው ይኸንን መንገር…» በማለት



ኾኾል ተናገረ ።

«ነግሬአታለሁ!» በማለት ፓቬል መለሰ ።

«አሄሄ! እሱን እንኳን ተወው! ለርሷ የነገርካት እያቆላመጥክ በፍቅር መልክ ፤ በመለሳለስ ሁኔታ ነው ። እንዴት እንደነገርካት ባላዳምጥም አነጋገርህን እገምታለሁኝ ። እናትህ ፊት ሲሆን ግን በአጉል ጀግንነት ትደነፋለህ ። እዚህ ግባ የማትባል ቅንጣት መሆንክን ግን እወቀው!» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

እናት እንባዎቿን ከፊቷ ላይ ቶሎ ጠራረገች ። ኾኾል ከዚህ የከፋ ይናገር ይሆናል ብላ በመሥጋት ቶሎ ብላ በሩን ከፈተችና ወደማዕዱ ክፍል ገባች ።

«እ-ት-ት-ት-ት! እንዴት ይበርዳል እባካችሁን! አሁን ይኸ ወራት ፀደይ ነው ብሎ መናገር ይቻላል ብላችሁ ነው?» በማለት ፍርሀትና ሀዘን የተቀላቀለው ድምፅዋን ከፍ አድርጋ በማሰማት ተናገረች ።

ሌላኛው ክፍል የሚሰማውን ድምፅ ለማፈን በማሰብ ዕቃዎች በሚገባ ከተቀመጡበት ቦታ እያነሳች አንዱን እዚህ አንዱን እዚያ በማስቀመጥ ታንኳኳ ጀመር ። ከዚያም ይበልጥ ድምፅዋን ከፍ በማድረግ ፡—

«ይገርማልኮ! ሁሉም ነገር ተቀያየረ ። ሰዎች ትኩስ እየሆኑ ይሄዳሉ ፤ ዓየር-ንብረቱ ደግሞ እየቀዘቀዘ ይሄዳል ። የአሁኑ ጊዜ ሞቃት የሚሆንበት ጊዜ ነበር ። ፀሐዩ እና የጠራው ሰማይ…»

ድምፅዋ ተቋረጠ ። ከማዕድ ክፍሉ ውስጥ ከሚገኘው መሃል ቦታ ቆማ ታዳምጥ ጀመር ፡ —

«ትሰማለህ የሚናገሩትን? ትንሽ ለመረዳት ብትሞክር ጥሩ ነው! እርሳቸው ካንተ የበለጠ የመንፈስ ብርታት አላቸው!..» በማለት ኾኾል ቀስ ብሎ ተናገረ ።

«ሻይ ላምጣ እንዴ?» በማለት በሚንቀጠቀጥ ድምፅ ተናገረች ። ከዚያም ለምን እንደምትንቀጠቀጥ የሚከተለውን በጥድፊያ አከታትላ ፡ —

«ኧረ የፈጣሪ ያለህ! ቅዝቃዜው በረዶ አደረገኝ እኮ!» አለች ።

ፓቬል ቀስ ብሎ ወደእርሷ ዘንድ ሄደ ። ጭንቅላቱን ቁልቁል ቀልሶ የጥፋተኛ ሰው ፈገግታ ከናፍሮቹን ከብበውታል ።

«እናቴ ይቅርታ አድርጊልኝ! እኔ አሁንም ገና ልጅ እና ሞኝ ነኝ...» አላት ።

«ተወኝ! ተወኝ!» በማለት ራሱን ደረቷ ላይ ይዛ ምርር ብላ አለቀሰች ። ከዚያም ፡ — «ምንም ነገር አትናገር ። እግዚአብሔር ካንተ ጋር ይሁን ። የራስህ ነፍስ ነው ። የራስህ ተግባር ነው ። ልቤን ብቻ አታስረብሽብኝ ። ለመሆኑ እናት ማፍቀሯን መተው ትችላለችን? አትችልም... ሁላችሁንም አፈቅራችሁአለሁኝ! ሁላችሁም ለእኔ ተወዳጆቼ ናችሁ ። ሁላችሁም መፈቀር የሚገባችሁ ናችሁ! እኔ የማላፈቅራችሁ ከሆነ ፣ ማን ሊያፈቅራችሁ ነው?.. አንተ ትሄዳለህ ፣ ሌሎቹም አንተን ተከትለው እና ሁሉንም እርግፍ አድርገው ትተው ይሄዳሉ... ኧረ ተወኝ ፓሻ!» በማለት እያለቀሰች ተናገረች ።

ትልቅ የሚያቃጥል ሃሣብ ልቧ ውስጥ ተርመሰመሰ ። ልትገልጸው በማትችለው ሁኔታ ልቧ በሀዘን ደስታ ተመትቶ ነበር ። በዚህ ስቃይ ውስጥ እያለችም ትካዜ በተመላባቸው ዐይኖቿ ልጅዋን ተመለከተችው ...

«እሺ ፣ እሺ እናቴ ይቅርታ አድርጊልኝ! ሁሉንም ነገር አሁን ተገነዘብኩት! ለምንግዜውም አልዘነጋውም!» ብሎ ፈገግ በማለትና ሀፍረትም ተቀላቅሎበት ዞር አለ ።

ከርሱ ዘንድ ተነሳችና ወደሌላኛው ክፍል ገባች ።

«አንድርዬ» አለች ጨዋነት ባልተለየው የመለመን አጠራር ፡ — «አትቆጣው ። አንተ ለእርሱ ታላቅ ነህ...» አለች ።

«ኧረ እባክዎን ይተውኝ! መቆጣት ብቻ አይደለ



ም ። እየረገጥኩኝ ነው ልክ የማገባው!» በማለት ፊቱን ዞር ሳያደርግ አድምቆ ተናገረ ።

ወደ አንድሬይ ሄደችና እጅዋን ወደርሱ በመዘርጋት ፡ —

«አንተ በጣም ጥሩ ሰው ነህ!..» አለችው ።

እጆቹን ወደኋላው አድርጎና ጭንቅላቱንም እንደ በሬ ወደታች አዘቅዝቆ ዙርያዋን ከዞራት በኋላ አልፍት ወደ ማዕድ ክፍል ሄደ ። አስቂኝ በሆነ ሁኔታ የሚከተለውን ሲናገር ሰማችው ፡ —

«ፓቬል! ጭንቅላትህን ሳልፈጠፍጠው ከዚህ ቦታ ጥፋ ። እምዬ ቀልዴን ነው ፤ እውነት እንዳይመስልዎት ። ሳሞቫሩን እያቀጣጠልኩኝ ነው ። እሺ ፣ ከሰሉ ይኸውና ። አቤት አቤት ፣ ያርጥበውና ከሰሉ ሁሉ እርጥብ አይደለም እንዴ እባካችሁ!» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

ከዚያም ዝም አለ ። እናት ወደማዕድ ክፍል ስትገባ ኾኾል ቁጭ ብሎ ሳሞቫሩን ያቀጣጥላል ። እርሷን-እርሷን ሳያይ እንደሚከተለው ተናገረ ፡ —

«አይሥጉ ። አልነካውም ። እኔ እንደተቀቀለ ድንች ለስላሳ ነኝ! እኔ ደግሞ ፣ አሆሆ! ጀግና ነኝ ። በእውነት በጣም አፈቅረዋለሁኝ ። ይኸንን የተዋሃደውን አንጉል የባሕርይ ልብሱን ግን አልፈቀድኩትም ። አዩ ፤ አዲስ የባሕርይ ልብስ ለብሶአል ። ግሩም-ድንቅ ልብስ መስሎ ይታየዋል ። ስለዚህም ያቺኑ ሆዱን አንዘርጥጦ በየቦታው እየሄደ እንዴት ዓይነት ልብስ እንደለበስኩኝ ተመልከቱ ፣ ግሩም አይደለምን?» ማለት ይሻል ። «እሺ ልብሱ ይሁን ። ሁሉን እየሄዱ መጎነታተል ግን ምን ይባላል? ከእንደዚህ ዓይነት ሰዎችስ መራቁ የተሻለ ነው!» በማለት ተናገረ ።

ፓቬል እየሳቀ የሚከተለውን ጠየቀው ፡ —

«ስንት ጊዜ ነው ይኸንን የምትናገረው? አንዴ ነገርከኝ ። ያው የአንድ ጊዜው በበቃኝ ነበር!» አለ ።

ኾኾል ሁለት እግሮቹን በሳሞቫሩ መሀል ዘርግቶ በመቀመጥ ከምድር ሁኖ ፓቬልን ቀና ብሎ ተመለከተው ። እናት ከበስተኋላው በሩ አጠገብ ቆማ ኾኾልን በፍቅር ስሜት ትመለከተዋለች ። ሰውነቱን በእጁ ደገፍ አድርጎ እናትና ልጅን ዞር-ዞር እያለ ተመለከታቸው ። ድንገትም ዐይኖቹ እንባ አቀረሩ ።

«ሁለታችሁም እንዴት ደስ ታሰኛላችሁ!» በማለት ኾኾል ቀስ ብሎ ተናገረ ።

ፓቬል ወደ ኾኾል ሥር ጎንበስ ብሎ እጁን ያዝ አደረገው ። ኾኾልም ፡ —

«ተወኝ ታበሳጨኛለህ...» በማለት ቀስ ብሎ ተናገረ ።

«ምን አሳፈራችሁ ። ተሳሳሙ ። የቻላችሁትን ያህል እቅፍ እቅፍቅፍ በሉ...» በማለት እናት ተናገረች ።

«ኧረ!» በማለት ፓቬል ጠየቀ ።

«በል ና!» በማለት ኾኾል መለሰ ።

በጓደኛነት ነበልባል የሚንበለበል አንድ ልብ ያላቸው እነዚህ ሁለት አካሎች እጅጉን አጥብቀው እቅፍቅፍ አሉ ። በእናት ጉንጮች ላይ የእንባ ዘለላዎች ዱብ ዱብ እያሉ ይወርዱ ጀመር ። እነዚህ የአሁኑ እንባዎቿ ግን የደስታ እንባዎች ናቸው ።

እርሷም በእንባዋ መፍሰስ ሀፍረት እየተሰማት እንባዎቿን በመጠራረግ ፡ —

«ሴቶች ማልቀስ ይቀናቸዋል ። ሲደሰቱ ያለቅሳሉ ። ሲያዝኑም ያለቅሳሉ!...» በማለት ተናገረች ።

ኾኾል ቀስ ብሎ ፓቬልን ካጠገቡ ገፋ አደረገው ። ኾኾልም ዐይኖቹን እየጠራረገ ፡ —

«እንግዲህ ይበቃል! ለቀልድም ጊዜ አለው! ለሥራም ጊዜ አለው ። አሁን ደግሞ ሥራ ነው ። ኢሄ ከሰል እንዴት የተረገመ ነው እባካችሁ! ይኸው ከሰሉን እ



ፍእፍ እላለሁኝ ። አመዱ ዐይኖቼን ሞልቶት አስለቀሰው...» በማለት ተናገረ ።

«ይኸን በመሰለ ጊዜ የሚፈስ እንባ የሚያሳፍርበት ምንም ምክንያት የለም...» በማለት ፓቬል መስኮቱ አጠገብ ቁጭ ብሎ በዝግታ ተናገረ ።

እናትም ወደ መስኮቱ ዘንድ ሄዳ ከርሱ ጎን ተቀመጠች ። ከመከፋቷ በስተቀር ልቧ በአዲስ ብርታት የተመላ ሲሆን ይኸውም ሁኔታ የተረጋጋች እና የረካች እንድትሆን አድርጓታል ።

«እምዬ አይነሱ ። እኔ ሻዮቹን ይገቹ እሄዳለሁኝ ። ልብዎን እንደዚህ በሀዘን ከጨመቁ በኋላ ትንሽ ዕረፍት ማረፍ አለብዎት...» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

ወዛማ የሆነው ጉልህ ድምፁ በክፍሉ ውስጥ አስተጋባ ።

«አሁን የሕይወትን ጣዕም በሚገባ ቀመስን ። ሞቅ ያለ የሰብአውያን ሕይወት ጣዕምን ቀመስን!..» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

«አዎን!» አለ ፓቬል እናቱን እየተመለከተ ።

«ሁሉንም ነገር የተለወጠ እንዲሆን አደረገው ። ሀዘናችን የተለወጠ ሆነልን ። ደስታችንም የተለወጠ ሆነልን...» ብላ እናት ተናገረች ።

«መሆን ያለበት እንደዚህ ነው ። እምዬ ፣ የዚህ ምክንያቱ አዲስ ልብ እየተወለደ በመሆኑ ነው ። አዲስ ልብ ነፍስ ዘርቶ በመፈጠር ላይ ነው ። የሰው ልጅ በዓለም ላይ የምርምርን ብርሃን እያበራ በመራመድ እና በዚሁ ጊዜም ‘የመላው ዓለም ሕዝቦች ሆይ አንድ ቤተ-ሰብ በመሆን ተባበሩ!’ እያለ ድምፁን በማሰማት የሰው ልጅ ወደፊት በመገስገስ ላይ ነው ። ጠንካራ ድምፁን በታላቁ እንደሚያሰማ ከብር እንደተሠራ ደወል ይኸንን የጥሪ ድምፅ አድማጭ የሆኑ

ልቦች ሁሉ በመስማት አንድ ትልቅ ልብ በአንድነት ይፈጥራሉ...» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

እናት ከናፍሮቿ እንዳይንቀጠቀጡ ግጥም አድርጋ ከድናቸው እንባዎቿን ለመግታትም ዐይኖቿን ዘግታለች ።

ፓቬል ለመናገር የሚሻ ይመስል እጁን ከፍ ከፍ ያደርግ የነበረ ሲሆን እናት ግን ወደርሷ አስጠጋችው ።

«አታቋርጠው ፣ ይናገርበት...» በማለት ቀስ ብላ ተናገረች ።

ኾኾል መጣና በራፉ ላይ ቆመ ። ከዚያም ፡—

«ሰዎችን ገና ብዙ ሀዘን ከፊት-ለፊታቸው ይጠብቃቸዋል ። ገና ወደፊት ብዙ ደም ይፈስሳል ። ይሁን እንጂ እስከአሁን በልቤ እና በአዕምሮዬ ውስጥ ለያዝኩት የእኔ መሠቃየት እና የእኔ ደም የሚበረክተው ክፍያ ትንሽ ነው... ከመላው የብርሃን ፍንጣቂዎቿ ጋር እንደምትገኝ ኮከብ ምሉዕ ነኝ ። ከእኔ ላይ አንዳችም ነገር ሆነ ማንም ቢሆን ገፍፎ ሊወስድብኝ የማይቻለው ታላቅ ደስታን የተጎናጸፍኩኝ በመሆኔ ማናቸውንም ነገር ቢሆን መቋቋምና እንደአመጣጡም መመለስ እችላለሁኝ ። ይኸ ደስታ ደግሞ ለእኔ የጥንካሬዬ ምንጭ ነው!» በማለት ተናገረ ።

በቅርብ የወዳጅነት መንፈስ ስለ ኑሮ ፣ ስለ ሰዎችና ስለ ወደፊቱም ሁኔታ በመወያየት ሻያቸውን እየጠጡ እስከ እኩለ-ሌሊት ቆዩ ።

የሚጫወቱትን ጨዋታ ሙሉ በሙሉ ስትገነዘበው ፣ ይኸ የተገነዘበችው ሃሣብ እንዳያመልጣት ፣ ከእርሷ ከቀድሞው ካለፈው አስከፊና አሳዛኝ ኑሮ መካከል አንዳንዱን በማስታወስ ታንተርሰዋለች ።

ሞቃት በሆነው በዚህ ውይይታቸው አማካይነት ፍርሃቶቿ ሁሉ ሟምተው ቀለጡ ። ከአሁን ቀድሞ



ዱሮ አንድ ቀን አባቷ ኮስተር ባለ አመለካከት እየተመለከታት በተናገራት ጊዜ የተሰማትን ዓይነት ሁኔታ አሁንም ተሰማት ። ያን ጊዜ አባቷ የሚከተለውን ተናግሮአት ነበር ፡—

«ፊትን ማኮምጨጭ ምን ዋጋ አለው! አንቺን ለማግባት ፍላጎት ያለው ሞኝ መጥቶ ጠይቆ እንደሆን ሂጂና ዕድልሽን ሞክሪ! የሠፈሩ ማቲዎች ሁሉ እያገቡ ናቸው ። እነዚህ የሚያገቡት ሴቶች ሁሉ የሚፈለፍሏቸው ልጆች ሀዘንና ችግር እንጂ አንዳችም ሌላ ነገር የሚያስገኙላቸው ፋይዳ የለም ። ያው አንቺም ብትሆኚ ይኸው ሁኔታ ይገጥምሻል እንጂ ፤ ከሌሎቹ የተለየሽ አትሆኚም » በማለት ተናግሮአት ነበር ።

ከዚህ አነጋገር በኋላ ባዶ እና ጭለማ በሆነ ቦታ የተዘረጋ ተስፋ-ቢስ የመተላለፊያ መጓጓዣ ተደቅኖ ጠብቋት ተመለከተች ። በዚህ መተላለፊያ መጓጓዣ መጓዝ የግዶሽ መሆኑ ራሱ ጭለማማ በሆነ ሰላም እንድትመላ አደረጋት ። አሁን ሁኔታው እንደዚህ ነው ። የአዲስ ሀዘን መቃረብን ባሰላሰለች ቁጥር ግን ለራሷ በገዛ ራሷ እንዲህ ስትል ማን ይሁን ማን የማይታወቀውን በሚከተለው ሁኔታ ታነጋግረዋለች ፡—

«እንካ ውሰድ!»

እንደተወጠረ የበገና ክር ድምፅ የሚያሰማውን የሃሣብ ሕመምተኛ ልቧን ይኸ ሁኔታ ቀለል አደረገላት ።

ውስጥ-ውስጡን ግን ማናቸውንም ያላትን ነገር ሁሉ ፣ እስከመጨረሻው አንድም አሟጥጦ የማይወስድባት መሆኑን ተስፋ በማድረግ ይኸንን ያህል አስተማማኝ ባይሆንም ጽኑ የሆነ ተስፋ በልቧ ውስጥ ይገኛል...

## 24

አንድ ቀን ጧት ማለዳ ፓቬልና አንድሬይ ልክ ወደሥራ ቦታቸው እንደሄዱ ኮርሱኖቫ በመስኮት በኩል አንኳኳች ።

«ኢሳይን ገደሉት! እንሂድና እንይ!» በማለት ጮኸች ።

እናት ብድግ አለች ። በአዕምሮዋ ውስጥም የገዳዩ ስም ይመላለስ ጀመር ። የአንገት ልብሷን ጀርባዋ ላይ ጣል እያደረገች ፡—

«ማነው የገደለው?» በማለት ጠየቀች ።

«ገዳዩ ኢሳይ ጎን ቁጭ ብሎ ይገኛል ብለው ይጠብቃሉ እንዴ? ወዲያው እንደገደለው በርሮ ጠፋ እንጂ!» በማለት ኮርሱኖቫ መለሰች ።

በመንገዱ ቁልቁል በሚሄዱበት ጊዜም ፡—

«ገዳዩ ማን እንደሆነ ለማወቅ አዲስ ፍተሻ ይደረጋል ። የእርስዎ ሰዎች ባለፈው ምሽት ቤታቸው ውስጥ የነበሩ መሆኑ ጥሩ ነው ። እኔ ለዚህ ምሥክር ነኝ ።» በማለት ተናገረች ። «ወደቤቴ የተመለስኩት ዕኩለ-ሌሊት ላይ ነበር ። በመስኮታችሁ በኩል አሾልቄ ስመለከት ሁላችሁም ቁጭ ብላችሁ ነበር...» በማለት ተናገረች ።

«ኧረ ስለእግዚአብሔር ብለሽ ማሪያ! እነርሱ ይኸንን ዓይነት ተግባር ይፈጽማሉ ብሎ ማን ይጠረጥራቸዋል ብለሽ ነው?» በማለት እናት ፍርሀት ተቀላቅሎባት ተናገረች ።

«እንዴ ፥ ምን ማለትዎ ነው? ታዲያ ማን ገደለው ይባላል? ከእናንተ ሰዎች ጋር ግንኙነት ያለው አንዱ መሆን አለበት ። በእነርሱ ላይ ይሰልልባቸው የነበረ መሆኑን አገር ያወቀው ጉዳይ ነው...» በማለት በገዳዮች ማንነት እርግጠኛ በመሆን አኳኋን ተናገረች ።



እናት መተንፈስ አቅቷትና ልቧን በእጅዋ ይዛ ከጉዞዋ ላይ ቀጥ ብላ ቆመች ።

«ምነው ምን ሆኑ? አይፍሩ እንጂ! የተቀበለው ይጠብቀው የነበረውን ነው! እሬሳውን ሳያነሱት ይልቅ ፈጠን ፈጠን እያልን እንሂድ!..» አለች ኮርሱኖቫ ።

እናት ቬሶቭሺኮቭ ላይ ያላት ጥርጣሬ ወደኋላ እንደሚጎትት ከባድ እጅ ነበር ።

«ከሚገባው በላይ ሁኖ ነበር!» በማለት አሰበች ።

አንድ ቤት በእሳት ጋይቶ አመድ ከሆነበት ከፋብሪካው ብዙም ራቅ ከማይል ቦታ ብዙ ሰዎች የተሰበሰቡ ሲሆን እነርሱም ከሰል በሆነው የቤቱ ፍርስራሽ ላይ ይረማመዳሉ ። ከተሰበሰበ ት ሰዎች መካከል ብዙ ሴቶች እና ሕፃናት እንደዚሁም ባለሱቆች ፥ የመጠጥ ቤት አሳላፊዎች ፥ ፖሊሶች እና ደረቱን ሙሉ በሜዳይ ያጌጠ ሽማግሌው እና ጢማሙ ፔትሊን የተሰኘ ዣንዳርም ጭምር በቦታው ላይ ነበሩ ።

ኢሳይ መላጣ ጭንቅላቱ በስተቀኝ ትከሻው ላይ እዘቅዝቆ እና በግማሽ ተቀምጦ ፥ በግማሽም ጋለል ብሎ በእሳት የከሰለ ግንዲላ ላይ ወድቋል ። የቀኝ እጁ ከሡሪው ኪስ ውስጥ የገባ ሲሆን የግራ እጁ ጣቶች መሬቱን አንቀው ይዘዋል ።

እናት ፊቱን ተመለከተች ። አንደኛው ዐይኑ በተዘረጉት እግሮቹ በኩል የወደቀው ቆብ ላይ አተኩሮ አል ። በአድናቆት አንዳች ነገር የሚመለከት ይመስል አፉ በገሚስ ከፈት ብሎአል ፤ ቀይ ጢሙ ደግሞ ጋደድ ብሎአል ። ያሾጠጠ ጭንቅላቱ እና ኮስማና ፊቱ የሚገኝበት ኮሳሳ አካሉ በሞት ተኮማትረው ከምን ግዜውም ባነሰ ሁኔታ አነስተኛ ሁነዋል ። እናት አማተበችና ተነፈሰች ። በሕይወት በነበረበት ጊዜ ለእርሷ ቀፋፊ የሆነ ሰው ነበር ። አሁን ከሞተ በኋላ ግን አዘነችለች ።

«አንዳችም ደም አልፈሰሰውም!» በማለት ከተሰበ ሰቡት መካከል አንዱ ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አደ ረገና ፡ — «ገዳዩ በቦክስ ወግሮ የገደለው መሆን አ ለበት...» አለ ።

ከዚያም አንድ ብስጭት የነበረበት ድምፅ ዝቅ ባለ አነጋገር ፡ —

«ይኸንን ቁሻሻ ሰባቂ አፉን ዘጉለት ፤ አይደለም!..» በማለት ተናገረ ።

ዝግጁ ሁኖ የሚጠባበቀው ዣንዳርም ሴቶቹን ከተሰበሰቡበት ቦታ ገፋፋቸውና ፡ —

«ማነው እዚህ እንደዚህ የሚያወራው?» በማለት በማስፈራራት መልክ ተናገረ ።

ሰዎቹ ዣንዳርሙ እንዲያልፍ መንገድ ለቀቁለት ። ከመካከላቸው አንዳንዶቹም ፈጥነው ወደፊት ሮጡ ። አንድ ሰው የማሾፍ አሳሳቅ ሳቀ ።

እናት ወደቤቷ ተመለሰች ።

«ማንም ያዘነለት አይመስልም!» በማለት አሰበች ።

በአዕምሮዋ ውስጥ ግዙፉ ኒኮላይ ቀኝ እጁ የተን ዳበት ይመስል እየተወዛወዘ ቀዝቃዛ በሆነ አመለካ ከት ሲመለከታት ታያት...

ልጅዋ እና አንድሬይ ወደቤት ለምሳ እንደመጡ ስለሁኔታው ጠየቀቻቸው ።

«እስከአሁን የተያዘ ሰው አለን?» አለቻቸው ።

«አልሰማንም » በማለት ኾኾል መለሰ ።

ሁለቱም የቀፈፋቸው መሆኑን ተመልክታለች ።

«የኒኮላይን ስም የጠራ ሰው ነበር?» በማለት ጠየ ቀች ።

«ማንም አልነበረም ።» በማለት ልጅዋ መለሰላት ። ዐ ይኖቹ ቆጣ ያሉ ሲሆኑ አነጋገሩም ኮስተር ያለ ነ ው ። ቀጠል አደረገናም ፡ —

«እርሱን የሚጠረጥሩትም አይመስለኝም ። ትላንት ቀትር ላይ ወደ ወንዝ የወረደ ሲሆን እስከአሁን ድረስ አልተመለሰም ። ስለእርሱ ጠይቄ ነበር...» አለ ።

«ኧረ እሰይ ፣ ተመሥገን ነው ፣ ለእግዚአብሔር ክብ ር-ምሥጋና ይድረሰው! ክብር-ምሥጋና ይድረሰው!» በማ ለት በእፎይታ ተነፈሰች ።

ኾኾል ተመለከታትና አንገቱን ቀለስ አደረገ ።

«ምን ማድረግ ይሻለኝ ይሆን ብሎ እንደተቸገረ ሰው በሃሣብ እንደተዋጠ ተንጋልሎአል ። አንድም የሚ ያዝንለት ፣ አንድም ስለእርሱ ጥሩነት የሚያወራ የለም ። ኢምንት እና ዋጋ-ቢስ ነው ። እንደተቀረጠፈ እና ተ ጋድሞ እንዲቆይ እንደተደረገ አንዳች ነገር ተንጋልሎ አል...» በማለት እናት ተገርማ ተናገረች ።

ፓቬል የሚመገብበትን ማንኪያ ምሳ ላይ ድንገ ት ወረወረው እና አጉረመረመ ። ከዚያም ፡ —

«ይኼ እኔን ሊገባኝ አይቻለኝም!» አለ ።

«ምኑ?» በማለት ኾኾል ጠየቀው ።

«ምግብ ለማግኘት ሲባል ብቻ እንስሳትን እንገ ድላለን ። ይኸ ደግሞ መጥፎ ነው ። የዱር አራዊቶችም አደገኞች ከሆኑ መግደል አለብን ። እኔ ራሴም ብሆን ወገኖቹ የሆኑ ሰብአውያን ፍጡሮችን የሚያጠቃ የ ሰው እንስሳን እገድለዋለሁኝ ። ነገር ግን ደግሞ እንደ ዚህ ባለ ምስኪን እና ጭርንቁስ ደሀ ላይ እጅ ማን ሳት እንዴት ይገባል?» በማለት ፓቬል መለሰ ።

ኾኾል ትከሻውን ነቅነቅ አደረገ ። ከዚያም ፡ —

«እንደማንኛውም የበረሀ አውሬ ሁሉ አደገኛ ነበ ር ። ጥቂት የደም ጠብታን ከእኛ ላይ ትንኝ የምትመ ጥ በመሆኗ እንገላታለን!» በማለት ተናገረ ።

«ይኸ እርግጥ ነው ። እኔ ይኸንን ማለቴ አይኑለ ም ። አስጸያፊ ነው ማለቴ ነው!» አለ ፓቬል ።

«ምንም ማድረግ አይቻልም ።» በማለት አንድሬይ ትከሻውን ነቅነቅ አድርጎ መለሰ ።

«እንዲህ ያለውን ፍጡር አንተ ብትሆን ትገድለዋለህን?» በማለት ፓቬል ጥቂት ዝም ካለ በኋላ ጠየቀው ።

ኾኾል ትላልቅ ዐይኖቹን ፓቬል ላይ ተከለ ። ከዚያም ወዲያውኑ እናትን ተመለከተ ።

«ለጓዶቼ ደህንነት እና ለቆምንለትም ዓላማ ስል ማናቸውንም ነገር አደርጋለሁኝ ። የገዛ ራሴን ልጅ እንኳን እገድለዋለሁኝ...» በማለት አጠንክሮ ተናገረ ።

«ውይ-ውይ አንድርዬ!» በማለት እናት በቀስታ ንግግር በአባባሉ ተደነቀች ።

«እናት ፣ ምንም ማድረግ አይቻልም! ሕይወት እንዲህ ናት!..» በማለት በፈገግታ ኾኾል መለሰ ።

«ዕውነትህን ነው!.. ሕይወት እንደዚህ ናት...» ብሎ ፓቬል ተናገረ ።

ከውስጥ አንዳች የሚገፋፋ ኃይል ፈንቅሎት አንድሬይ ድንገት ለከፍተኛ ቅስቀሳ ብድግ አለ ። የሚከተለውንም እጆቹን እያንቃነቀ ተናገረ ፡ —

«ምን ማድረግ ይቻላል? ሰዎችን ለማፍቀር የምንችልበት ጊዜ እንዲመጣ ሰዎችን እንጠላ ዘንድ ተገድደናል ። በእድገት ፊት ለፊት ተደቅኖ መሰናክል የሚሆነውን ማንንም ቢሆን ፣ ለገዛ ራሱ ክብር እና ዋስትና ለመግዛት ሲል ሕዝቦችን ለሽያጭ የሚቸበችበውን ማንንም ቢሆን ከምድረ-ገጽ ለመጠራረግ ተገድደናል ። የሀቀኛ ሰዎችን መንገድ የሚያጥር መሰናክል የሆነ ይሁዳ ቢኖርና ሀቀኛ ሰዎችንም ለመክዳት ጊዜ የሚጠብቅ ይሁዳ ቢኖር ፣ ይኸንን መሳዩን ይሁዳ ሳልደመስሰው ብቀር እኔው ራሴ ይሁዳ መሆኔ ነው ። መብት የለህም ትሉኝ ይሆን? እነዚያ የእኛ አለቆችስ የሚፈጽሙት ምንድነው? ሠራዊቶቻቸውን እና አፋኞቻቸውን ፣ የማመንዘርያ ቤቶችን እና የእሥር-ቤቶችን ፣ ወደ ግዞት የሚያግዙባቸውን ቦታዎች እና እንደዚሁም ምቾቶቻቸውን እና ዋስትናዎቻቸውን ተንከባክበው የሚያቆዩባቸውን ማናቸውንም የተረገሙ ተግባሮቻቸውን ለመፈጸም መብት የሰጣቸው ለመሆኑ ማነው? አንዳንድ ጊዜ የእነርሱን ቆመጥ ዱላ በእጄ ውስጥ አግብቼ ብጠቀምበት ስሕተት ነውን? ያለአንዳች ማመንታት እወስደዋለሁኝ ። እነርሱ እኛን በብዙ አሥር እና በብዙ መቶ የሚጨፈጭፉን ከሆነ ፣ እኔም ክንዴን ከእነርሱ መካከል በአንደኛው ጭንቅላት ላይ የማንሳት መብት አለኝ ። እኔ የቆምኩበትን ዓላማ ለመቃወም ይበልጥ ተጠግቶኝ በሚገኘው እና ከሌሎች የበለጠም አደገኛ በሆነው ጭንቅላት ላይ ክንዴን የማንሳት መብት አለኝ ። ሕይወት እንዲህ ነው ። እኔ ግን እንደዚህ ዓይነቱን ሕይወት እቃወማለሁኝ ። እንደዚህ መሆን አልሻም ። ከእነርሱ ደም ምንም እንደማይገኝ አምናለሁኝ ። የእነርሱ ደም መካን የሆነ ደም ነው! ዕውነት በየሥፍራው የሚያቆጠቁጠው የእኛ ደም እንደ ከፍተኛ ዝናም በምድሩ ሁሉ ሲወርድ ነው ። የእነርሱ ደም ግን ይደርቃል ። ይኸንን አውቃለሁኝ! ይኸንን ሀጢአት ግን እኔው ራሴ አውቄ እፈጽመዋለሁኝ ። ማለትም ፣ መደረግ አለበት ብዬ ካመንኩኝ እገድላለሁኝ! ልብ ያድርጉ ፣ የምናገረው ስለራሴ ብቻ ነው ። የሠራሁት ሀጢአት አብሮኝ ከኔው ጋር ይሞታል ። በመጪው የወደፊት ሁኔታ ላይ ትቶት የሚያልፈው ዱካ የለውም ። እኔን ብቻ እንጂ ማንንም ቢሆን ፣ ሌላ ማንንም አንድ ሰውም ቢሆን አያጎድፍም!» በማለት ተናገረ ።

አንዳች ነገር እንደሚቀረጥፍ ሁሉ ፣ ቀርጥፎ እንዳበቃ ሁሉ በክፍሉ ውስጥ ከወዲያ-ወዲህ ተራመደ ። በእርሱነቱ ውስጥ አንዳች ነገር የፈነዳ መሆኑን እና ፡ ይኸውም ነገር በጎ ነገር አለመሆኑን በመገንዘብ እናት በሀዘን እና በተጠንቀቅ ሁና ንግግሩን እና ሁኔታ

ውን ትከታተላለች ። ጭለማ እና አደገኛ የሆኑት የግ ድያውን ጉዳይ የሚመለከቱት ሃሣቦች ትተዋት ሄዱ ። «ቬሶቨሺኮቭ ወንጀሉን ካልፈጸመ ፣ ሌሎቹ የፓቬል ጓደኞች ይኸንን መሳይ ወንጀል አይፈጽሙም» በማለ ት እናት አሰበች ። የኾኾልን ስሜታዊና ድምፀ-ጉ ልህ ንግግር ፓቬል አንገቱን አቀርቅሮ ያዳምጣል ።

«ወደፊት ለመራመድ ከፈለግህ አንዳንድ ጊዜ ራስህን መቃወም አለብህ ። ማናቸውንም ያለህን ሁሉ አሳልፈህ ለመስጠት የምትችል መሆን አለብህ ። ልብ ህን በሙሉ ለመስጠት የምትችል መሆን አለብህ ። ሕይወትክን ለቆምክበት ዓላማ መስጠቱ ቀላል ነው! ከሕይወትህ ይበልጥ ውድ የሆነውንም ለመስጠት የምትችል መሆን አለብህ ። ይኸንን ከሕይወትህ ይበል ጥ ውድ የሆነውን በመስጠትም የምትዋጋለትን ሀቅ ታጠናክራለህ ፤ ለአንተ በዓለም ላይ ካለው ነገር ሁሉ እጅግ ተወዳጅ የሆነውን ሀቅ ታጠናክራለህ!..» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

ግርጥት ብሎ ፣ ዐይኖቹ በገሚስ ከደን ብለውና በእጁም የከብር ቃል-ኪዳን እየገባ በክፍሉ ውስጥ ከሚገኝ መሃል ቦታ ላይ ቆመ ።

«ሰዎች ስለውበታቸው እርስ-በእርስ የሚዳነቁበት እየአንዳንዱ ለተቀሩት እንደ አንፀባራቂ ኮከብ የሚፈ ካበት ጊዜ እንደሚመጣ አውቃለሁኝ ። በዚያን ጊዜም ዓለም በነፃነታቸው ታላቅ በሆኑ ነፃ ሰዎች ትመ ላለች ። የመላው ሰዎች ልቦች ግልጽ የሚሆኑ ሲሆኑ ከምቀኝነት እና ከተንኮልም የፀዱ ይሆናሉ ። ከዚያም በኋላ ሕይወት ለሰብአውያን ፍጡሮች መገልገያ ወ ደመሆን ትለወጣለች ። ማናቸውም ነገሮች ነፃ ለሆኑ ት ሰዎች ዝግጁ ሁነው ስለሚገኙ የሰው ልጅ ግሩ ም እና ተደሳች ይሆናል ። ከዚያም የሰው ልጆች ለው በት ሲሉ በሃቀኝነት እና በነፃነት ይኖራሉ ። ታላቋ



ውበት በእነርሱ ላይ የተመካች ስለምትሆን ፣ ዓለምን አቅፈው-ደግፈው የሚይዙዋት እና የሚያፈቅሩዋትም ፣ እጅግ ነፃ የሆኑት ፣ ዓይነተኛዎቹ ሰዎች እነርሱ ይሆ ናሉ! እነዚያ የአዲሲቷ ሕይወት ሰዎች ታላላቅ ሰዎ ች ይሆናሉ...» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

ትንሽ አረፍ አለ ። ከዚያም እጅግ ከልቡ በመነ ጩ የዝግታ አነጋገር የሚከተለውን ተናገረ ።

«እና ለዚያች ሕይወት ስል ማናቸውንም ነገር ቢሆን ለማድረግ ዝግጁ ነኝ ።»

ፊቱ ኩስትርትር አለ ። የማያቋርጥ እንባ በጉንጮቹ ላይ ይፈስስ ጀመር ።

ፓቬል ቀና ካለ በኋላ ዐይኖቹን ብልጥጥ አድርጎ በመክፈት ተመለከተው ። እናት አንዳች መዓት ነገር መጥቶ በላይዋ ላይ ያደረ መስሎ ተሰማት ።

«አንድሬይ ፣ ምነው ምን ሆንክ?» በማለት ፓቬል ጠየቀው ።

ኾኾል ጭንቅላቱን ነቀነቀ ፣ ከዚያም ሙሉ በሙሉ ቀጥ ብሎ በመቆም እናትን በቀጥታ እየተመለከተ ፦ —

«ሲደርስ ታየኝ... ማናቸውንም ነገር አውቃለሁኝ...» አለ ።

ሮጠችና እጆቹን ያዘች ። የቀኝ እጁን ሊያስለቅቅ ሞከረ ። እናት ግን አጥብቃ ያዘች ።

«የኔ ሸጋ ፣ የኔ ውድ ልጅ ዝም በል!» አለችው ።

«ይቆዩ ፣ ይቆዩ ። እንዴት እንደነበረ እነግርዎታለ ሁኝ » በማለት አለዝቦ ተናገረ ።

«የለም ፤ አያስፈልግም ። አንድርዬ ፣ የለም ይቅር ግዴ ለም...» በማለት በእንባ ተመልታ ቀስ ብላ ተናግ ረች ።

ፓቬል ቀስ እያለ ተጠጋ ። እርሱም ግርጥት ብሎ ና ዐይኖቹም በእንባ ረጥበው ነበር ።

«እናት አንተ መስለሃቸው ደንግጠው ነበር...» በማለት ሳቅ በማለት ተናገረ ።

«አልፈራሁኝም! አላምንም! በዐይኖቼ ባይ እንኳን አላምንም!» በማለት እናት ተናገረች ።

እጆቹን ለማስለቀቅ እየሞከረና ጭንቅላቱንም እየነቀነቀ ኾኾል ፡ —

«ቆይ እኮ ይቆዩ ፥ ልንገርዎት እንጂ ፥ እኔ አልነበርኩኝም ። ግን ጉዳዩን ከመፈጸም ላቆመው እችል ነበር...» አለ ።

«ዝም በል ፤ አንድሬይ!» በማለት ፓቬል ተናገረ ።

የሚንቀጠቀጠውን ረዥም ሰውነት ለማቆም ይቻለው ይመስል ፤ ፓቬል በአንድ እጁ የጓደኛውን እጅ ፤ በሌላኛው እጁ ደግሞ ትከሻውን ያዝ አደረገ ። ኾኾልም ጭንቅላቱን ወደ ፓቬል ዝቅ አደረገ ።

«አየህ ፓቬል ፤ ጉዳዩ እንዲደርስ አልፈለግሁኝም ነበር» በማለት አንድሬይ በተሰባበረ ድምፅ ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ —

«ጉዳዩ የተከናወነው በሚከተለው ሁኔታ ነው ፡ — ከድራጉኖቭ ጋር ጥጉ ላይ ትተኸኝ እንደሄድክ ፤ ኢሳይ እኛ አጠገብ ተንቧክኮ በመምጣት ያሾልቅና ያነፈንፍ ጀመር ። ድራጉኖቭም የሚከተለውን ተናገረ ፡ — ‘ኤው ፤ ይኸን ጉድ አየኸውን? ምሽቱን በሙሉ ሲከተለኝ ነው ያደረው ። ተወው እንግዲህ አጠዘዋለሁኝ’ አለ ። ከዚያም ሄደ ። እቤቱ የሄደ መሰለኝ... ከዚያም ኢሳይ ወደኔ ዘንድ መጣ...» በማለት ኾኾል ተናገረ ። ከዚያም ቁና ተነፈሰና ፤

«ያ ውሻ እንደሰደበኝ ያለ ስድብ ማንም ሰድቦኝ አያውቅም!» በማለት ተናገረ ።

እናት በዝምታ ወደ ወንበሩ ዘንድ ከወሰደችው በኋላ እንዲቀመጥ አደረገችው ። እርሷም ትከሻዋ ትከሻውን እየነካ አጠገቡ ጥግት-ጥግትግት ብላ ቁጭ አለች ። ፓቬልም ባለመደሰት መንፈስ ጢሙን እየሻሸ በቆመበት ቀረ ።



«የሁላችንንም ስም የሚያውቁ መሆናቸውን ፤ ስሞቻችንም በጀንዳርሞች መዝገብ ውስጥ ሠፍሮ የሚገኝ መሆኑን እና የሜይ 1 ቀን ሠልፍ በዓል ከመደረጉ በፊት የሚይዙን መሆኑን ነገረኝ ። ምንም መልስ አልመለስኩለትም ። ዝም ብዬ ሳቅሁበት ። ከውስጥ ግን ቆሽቴ ተቃጥሎ ነበር ። እኔን ብልህ ሰው ነህ ካለኝ በኋላ ፤ ይኸንን የመሰለውን ጎዳና መከተሌ አሳዛኝ መሆኑን ነገረኝ ። ለእኔ ይኸን ከማድረግ ይልቅ ይሻለኝ የነበረው...»

ይኸንን ከተናገረ በኋላ ንግግሩን ቆም አድርጎ ዐይኖቹን ጠራረገ ። ዐይኖቹ የደረቁ የእንባ ቅርፊቶች አሉበት ።

«ገብቶኛል» በማለት ፓቬል መለሰ ።

«ሕግን እና ሥነ-ሥርአትን ማገልገል ይሻላል አለኝ» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

ኾኾል እጁን ጨብጦ በቁጣ አወዛወዘው ። እንዲህም አለ ፡ —

«ነፍሱን አይማረውና ሕግን ማገልገል ይበለኝ እንዴ!» በማለት ጥርሱን ነክሶ እያፋጨ ተናገረ ። ቀጠል አደረገናም ፡ —

«ይኸንን ከሚለኝ ፊቴን በጡጫ ቢያጎነው በተሻለኝም ነበር ። ለእኔ ፤ ምናልባትም ደግሞ ለእርሱም ጭምር ቀላል በሆነም ነበር ። ያንን ተናዳፊ የሆነውን ለሀጩን ልቤ ላይ አክ ብሎ መትፋቱን መታገስ አልቻልኩኝም!»

አንድሬይ እጁን ከፓቬል ላይ መንጭቆ ካስለቀቀ በኋላ ቅፍፍ ባለው ሁኔታ ንግግሩን ቀጠለ ፡ —

«ፊቱ ላይ አንዴ ከወገርኩት በኋላ ሄድኩኝ ። ከዚያም ድራጉኖቭ ከኔ በስተጀርባ ቆሞ ይጠብቅ የነበር ሳይሆን አይቀርም... የሚከተለውን ሲናገረው ሰማሁት ፡ — ‘ይኸው እንግዲህ ፤ አገኘሁህ አይደለም?’ አለው» በማለት ኾኾል ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ —

«ምንም እንኳን ድብደባ እሰማ የነበረ ቢሆንም
ወደኋላ ዞር ብዬ አልተመለከትኩኝም ። ዝም ብዬ ወደ
ፊት መሄዴን ቀጠልኩኝ ። ሥራ ቦታ ላይ ‘ኢሳይን
ገደሉት!’ እያሉ በመናገር ይንጋጉ ጀመር ። አላመንኩ
ኝም ። ይሁን እንጂ ለመሥራት ሊሳነኝ ምንም እስካ
ልቀረኝ ድረስ እጄን ቁርጥምጥም ያደርገኝ ጀመር ።
ምንም የሚጎዳ ጉዳይ አልነበረም ። ያጠረ-የተኮማተረ
ያህል ነበር የቆጠርኩት» በማለት ከተናገረ በኋላ እ
ጁን ከፉኛ ተመልክቶ የሚከተለውን በመጨመር
ተናገረ ፦

«ከእንግዲህ መላ ሕይወቴን ያንን ጉድፍ ከእጄ
ላይ የማጥብ አይመስለኝም...» አለ ።

«ዋናው ነገር ልብህ ንጹህ መሆኑ ነው!» በማለት
እናት በዝግታ አለስልሳ ተናገረች ።

«ኧረ ምን ሲደረግ ፣ ራሴን ለዚህ ለፈጸምኩት ተ
ግባር አልወቅሰውም!» በማለት ኾኾል አጠንክሮ ተና
ገረ ። ከዚያም ፦

«ከፉቱ ፣ ደስ አያሰኝም ። ከእንዲህ ዓይነቱ ድርጊት
ጋር መደባለቅ አልነበረብኝም» አለ ።

«አንተ ደግሞ ግራ ታገባኛለህ» በማለት ፓቬል
ትከሻውን እየነቀነቀ ተናገረ ። ከዚያም ፦

«ግድያውን የፈጸምከው አንተ አይደለህም ። ብትፈ
ጽመውም እንኳን — » ብሎ ሳይጨርስ ኾኾል ፦

«ወንድሜ ሆይ ፣ ግድያ የሚፈጸም መሆኑን እያወቅ
ህ እና ግድያውም እንዳይፈጸም ሳታደርግ ብትቀር —»
ብሎ እንደተናገረ ፣ ፓቬል ቀበል አደረገና ፦

«ምን ማለትህ ነው? ይኽ ያልከው እሺ እርግጥ
ነው ። ግድያው እንዳይፈጸም አደርግም ይሆናል ። እኔ
ን ግን አይመለከተኝም» በማለት ፓቬል ተናገረ ።

የፋብሪካው የጥሪ ሰአት አጓራ ። ኾኾል ራሱን



ዘመም አድርጎ ያዛኸ-ናዛዡን የጥሪ ድምፅ አዳመጠ ።
ከዚያም ፦

«ወደ ሥራ ተመልሼ አልሄድም» አለ ።

«እኔም አልሄድም» በማለት ፓቬልም ተናገረ ።

«ወደ ገላ መታጠቢያ ቤት እሄዳለሁኝ» በማለት
አንድሬይ በመጠኑ ፈገግ ካለ በኋላ ልብሶቹን መሰብ
ሰብ ጀመረ ። በቀዝቃዛነት ስሜት ከቤት ወጥቶ ሄደ ።

እናት ርኅራኄ በተመላበት አመለካከት በዐይኖቿ
ተከተለችው ። ከዚያም የሚከተለውን ለፓቬል ተናገረ
ች ፦

«ፓቬል ፣ የፈለግኸውን ማለት ትችላለህ ። ሰውን
መግደል ሀጢአት መሆኑን አውቃለሁኝ ። ማንንም ጥፋ
ተኛ ነው ብዬ ግን በኃላፊነት አልጠራም ። ኢሳይ
እዚህ ግባ የማይባል ኢምንት ሰው ስለነበረ በመሞ
ቱ አዝንለታለሁኝ ። ዛሬ ሬሳውን ባየሁ ጊዜ አንተን
ለመስቀል መዛቱን አስታወስኩኝ ፣ ይኸ ድርጊቱ ግን
እርሱን እንድጠላው ወይንም በመሞቱ እንድደሰት አ
ላደረገኝም ። እንደው ብቻ አዘንኩለት ። አሁን ግን ፣ የ
ቀረው ቀርቶ መሞቱ እንኳን አያሳዝነኝም...» በመደ
ነቅ ፈገግታ የሚከተለውን ጨምራ እስክትናገር ድረ
ስ በፀጥታ እና በማሰላሰል ሁኔታ ቆየች ። ከዚያም ፦

«የፈጣሪ ያለህ ፣ ፓሻ ፣ ለመሆኑ ምን እንደምናገር
ትሰማኛለህን?..» አለች ።

ዐይኖቹን ወደመሬት አቀርቅሮ በክፍሉ ውስጥ
ከወዲያ-ወዲህ ይመላለስ በነበረበት ጊዜ ፣ እርሷ የምት
ናገረውን አይሰማም ነበር ። እንዲህ በማለትም ተና
ገረ ፦

«ይኸውልሽ እንግዲህ ፣ ሕይወት ማለት ይህቺ ናት!
ሰዎች እርስ-በእርሳቸው እንዴት እንደሚናከሱ አስተ
ዋልሽን? ይሁነኝ ብለሽ ፈልገሽ ሳይሆን ፣ እንዳው በአ
ጋጣሚ አንዱን ሰው ስትቦጭቂው ትገኛለሽ ። ይህ

የምትቦጭቂው ሰው ማን ነው? ከአንቺ የበለጠ አንዳችም መብት የሌለውን አንድ ምስኪን አሳዛኝ ፍጡር ነው ። አሁን የምናወሳውን ሰው በሚመለከት ረገድ ከሆነ ደግሞ ሰውዬው ጅላንፎ ስለሆነ ከአንቺ ይበልጥ ምስኪን የሆነ ሰው ነው ። ፖሊሶች ፤ ዣንዳርሞች እና ሰላዮች ሁሉም ጠላቶቻችን ናቸው ። እነዚህ ሁሉም ቢሆኑ ደግሞ ደማቸው እንደኛው የተመጠጠ ፤ እንደኛው በዝቅተኛነት ተቆጥረው የሚገኙ ሰዎች ናቸው ። ሁላችንም ብንሆን አንድ ነን! የበላይ አዛዦቻችን ግን ሰዎችን በፍርሀት እና በፍሬ-ከርስኪ ጉዳዮች በማወር ፤ እግር-ተወርች ተብትቦ በማሠር ፤ በመጭመቅ እና ደማቸውን ምጥጥ በማድረግ እርስ-በእርሳቸው እንዲዋቁ እና እንዲጨራረሱ በማድረግ ሕዝቦችን እርስ-በእርስ ያጣሏቸዋል ። የበላይ አዛገሮች ሕዝቦችን ጠመንጃዎች ፤ ቆመጥ ዱላዎች እና ደንጊያዎች ወደመሆን ለውጠዋቸዋል ። ይኸንንም በማድረጋቸው ፡ — 'መንግሥት ማለት ይህ ነው!' እያሉ ያወሳሉ ።»

ፓቬል ወደ እናቱ ዘንድ ሂዶ ተጠጋ ። ንግግሩንም ቀጠለ ፡ —

«እናት ሆይ ፤ እነሱ የሚፈጽሙት ሁሉ ወንጀል ነው! ጭካኔ የተመላበት እያሌ ሚሊዮን ሕዝቦችን የመግደል ወንጀል ነው ። የሰብአውያንን መንፈሶች የመግደል ወንጀል ነው... አስተውለሺዋልን? የመንፈስ ገዳዮች ናቸው ። በእኛ እና በእነርሱ መካከል ያለውን ልዩነት አስተውለሽዋልን? እኛ አንድን ሰው ብናጠፋ አስጸያፊ ፤ አሳፋሪ እና ጎጂ የሆነ ተግባር ተደርጎ ይቆጠራል ። ብዙውን ጊዜ አስጸያፊ እንደሆነ ተግባር ይቆጠራል! እነርሱ ግን በምንቸገረኝነት ተዝናንተው እና ምህረት-የለሽ ሁነው ትንሽም ቅር ሳይሰኙና በከፍተኛ ሁኔታ ረክተው ብዙ ሺህ ሕዝቦችን ይፈጃሉ!



ሕዝቦችን በሞት የሚጨፈጭፉበት ሌላ አማራጭ የማይገኝለት ምክንያታቸውም ወርቆቻቸውን ፤ ብሮቻቸውን እና ዋስትናዎቻቸውንም ሳይነኩ እንደነበሩ ለማቆየት እና እኛንም ባርያ ሁነን እንድንቀር ያደረጉንን ንብረቶች ሁሉ እንደተጠበቁ ለማቆየት በመሻታቸው ነው ። ይኸንን አስቢ ። እነርሱ ሕዝቦችን በሚፈጁበት ጊዜ እና መንፈሳቸውንም በሚቦጫጭቁበት ጊዜ የሚንከባከቡት የገዛ ሕይወታቸውን ሳይሆን ፤ ንብረቶችን ነው! በሰው ሰውነት ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ሳይሆን ከሰው ሰውነት በስተውጪ የሚገኙትን ነገሮች ለመንከባከብ ነው...» በማለት ተናገረ ።

እጇቿን በእጆቹ ያዝ ካደረገ በኋላ ዝቅ ብሎ በመንተራስ እጆቿን ጫን ጫን እያለ ፡ —

«ይኸ ድርጊት እንዴት ወራዳ እና አሣፋሪ እንደሆነ ማስተዋል ብትችይ የምንታገልለትን ሀቅ ምንነት ትገነዘቢያለሽ ። ምን ያህል ግሩም-ድንቅ እና ታላቅ እንደሆነም ታስተውያለሽ!..» አላት ።

በልቧ ውስጥ የሚጋየው እሳት በልጅዋ ልብ ውስጥ ከሚጋየው እሳት ጋር በአንድነት ተቀላቅሎ አንድ ትልቅ ነበልባል እንዲወጣው እናት በልቧ እየተመኘች ከተቀመጠችበት ተነሳች ።

«ታገሰኝ ፤ ልጄ ፓቬል ። ታገስ ። እኔም በጊዜ ብዛት አየዋለሁኝ» በማለት ተናገረች ።

## 25

አንድ ሰው ድምፅ እያሰማ ከወደ በራፉ መድረክ ደረሰ ። እናትና ልጅ በተጠንቀቅ ሁነው እርስ-በእርስ ይመለካከቱ ጀመር ።

በሩ ቀስ ብሎ ተከፈተና ከበስተውጪ ሪቢን መጣ ።

«ይኸው መጣሁኝ» በማለት ጭንቅላቱን ቀና እያደረገ ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡—

«ተጠራጣሪው ቶማስ ዘሀንደኬ ፤ ቃሉን የሚያከብር እንደቡራኬ ፤ እዚህም-እዚያም ይጓዛል ፤ በየትም ቦታ ይገኛል!..» በማለት ተናገረ ።

በቅጥራን የተለወሰና ከበግ ቆዳ የተሠራ ካፖርት ለብሷል ፤ ከቃጫ የተሠራ መጫሚያ ተጫምቷል ፤ አሮጌ ባርኔጣ በራሱ ላይ ደፍቷል ። የእጆቹን ጥቋቁር ሹራቦች ካፖርቱን ጠፍሮ ካሰረበት ቀበቶ መሀል አስገብቶአቸዋል ።

«ለጤናህ እንዴት ነህ? ፓቬል ፤ ለቀቁህ ማለት ነዋ? አይ ፤ ጥሩ ነው ። ፔላጌያ ኒሎቭና እጅጉን እንደምን ነዎት?» በማለት ሪቢን ነጫጭ ጥርሶቹን ግልጥጥ አድርጎ ባያሌው ሳቀ ። ድምፁ ከቀድሞው ይበልጥ የጨዋ ድምፅ የሆነ ሲሆን ፤ ፊቱንም ጢም ወርሮታል ።

እናት እርሱን በማየቷ ተደሰተች ። ጥቋቁር ፈሳሽ ነገሮች የተጣበቁበትን ግዙፍ እጁን ለመጨበጥ ሄደች ። ከዚያም የቅጥራኑን የሚያውድ ሽታ አውጥታ ከተነፈሰች በኋላ ፡—

«ወይ አንተ ፤ ኧረ እንኳን መጣህ ፤ በጣም ነው ደስ ያለኝ!..» በማለት ተናገረች ።

ፓቬል ሪቢንን እየተመለከተ በመሳቅ ፡—

«ጥሩው ገበሬ ፤ ታዲያስ!» አለው ።

ጎብኛቸው የሆነው ሪቢን ቀስ በቀስ ካፖርቱን እና ቆቡን ማውለቅ ጀመረ ። ከዚያም ፡—

«አዎን እንደገና ገበሬ በመሆን ላይ ነኝ ። እናንተ ከቡራን መኳንንት መሆናችሁን ቀጠላችሁ ። እኔ በሌላው አቅጣጫ መጓዜን እቀጥላለሁኝ!» በማለት ሪቢን ተናገረ ።

ያሸበረቀ ሸሚዙን ሲያስተካክል በክፍሉ ውስጥ



ማናቸውንም ነገር በአትኩሮት እያስተዋለ ይራመድ ጀመር ።

«ከመጻሕፍት በስተቀር ሌላ አዲስ የተጨመረ ነገር እዚህ ክፍል ውስጥ የለም ። ሁሉም ነገር ያው የቀድሞው ነው ። እህህህ! እሺ ፤ እስኪ አውሩኝ እባካችሁ?» በማለት ተናገረ ።

እግሮቹን እዚያና-እዚህ አንፈራጥጦ ፤ እጆቹንም ጉልበቱ ላይ ጣል አድርጎ የፓቬልን ፊት በጥቋቁር ዓይኖቹ አተኩሮ እየተመለከተ እና ፈገግ በማለትም መልስ ይጠብቅ ጀመር ።

«የመሻሻል ዕርምጃ እያደረግን ነው!» በማለት ፓቬል መለሰ ።

«እኛ እናርሳለን ፤ እንዘራለን ፤ አዝመራችን ሲያብብ-ሲያሽት እንመለከታለን ። ጠላችንን እንጠምቃለን ። ዓመቱን እናሳልፋለን ። አያችሁ ፤ በእኛ በኩል ሁኔታው እንዲህ ነው» በማለት ሪቢን እየሳቀ ተናገረ ።

« ሚኻኢሎ ኢቫኖቪች ፤ ለመሆኑ ኑሮ እንዴት ነው?» በማለት ፓቬል ሪቢንን ጠየቀው ።

«ኑሮ ደህና ነው ። የጊልዴየቮ በተሰኘ ቦታ እኖራለሁኝ ። ሰምተው ያውቃሉ እንዲህ ተብሎ የሚጠራውን ቦታ? የጊልዴየቮ ይባላል ። ጥሩ የሆነ ትንሽ መንደር ነው ። በዓመት ሁለት ገበያ ይውልበታል ። ከሁለት ሺህ በላይ ነዋሪዎች ይገኙበታል ። ነዋሪዎቹ መናጢ ደሀዎች ናቸው! የራሳቸው መሬት የላቸውም ። መሬቱን የሚያርሱት ተከራይተው ነው ። ያም ሁኖ ደግሞ ፤ መሬቱም መጥፎ መሬት ነው ። እኔ ራሴም እዚያ ለሚገኘው ለአንዱ ደም-መጣጭ ሀብታም ተቀጥሬ እሠራለሁኝ ። በሙት አካል ላይ ትሎች በብዛት እንደሚርመሰመሱ ሁሉ ፤ በዚያ ቦታም እነዚያ ደም መጣጮች በብዛት ይርመሰመሳሉ ። ከሠል እያከሠልኩኝ ቅጥራን በማውጣት እሠራለሁኝ ። እዚህ አገኝ ከነበረው

አበል ጋር ሲነጻጸር እዚያ የማገኘው ሩቡን ያህል
ሲሆን ፤ የድካሜ ብዛት ደግሞ በሁለት እጅ የበለጠ
ነው ። ወይ ጉድ! ለዚያ ለደም-መጣጭ አሠሪያችን ፡ ሰባ
ት ሰዎች ተቀጥረን እንሠራለን ። ከእኔ በስተቀር ሁ
ሉም የሠፈሩ ተወላጆች ሲሆኑ ወጣቶች እና ጥሩ
ሰዎች ናቸው ። ሁሉም መጻፍ እና ማንበብ ያውቃሉ ።
ከመካከላቸው አንዱ የፊም ፤ በጣም ቁጡ ነው ። ምን
እንደማደርገው አላውቅም» በማለት ሪቢን ተናገረ ።

«እንዴት ነው ከእነርሱ ጋር ያለዎት ግንኙነት?
ውይይት ታካሂዳላችሁን?» በማለት ፓቬል በጉጉት ጠ
የቀ ።

«አፌን ዘግቼ አልቀመጥም ። በዚህ በኩል እርግጠ
ኛ መሆን ትችላለህ! ተበታኝ ጋዜጦቻችሁን በሙሉ
ወስጀአለሁኝ ። ሁሉንም ሠላሳ አራቱንም ጋዜጦች ወ
ስጃለሁኝ ። ብዙውን ጊዜ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ እጠቀ
ማለሁኝ ። መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ እጅግ ብዙ ቁ
ም-ነገሮችን መቅሰም ይቻላል ። መጽሐፍ ቅዱስ ጥራዝ-
ትልቅ መጽሐፍ ከመሆኑም በስተቀር ቅዱስ ሲኖዶ
ስ እንዲነበብ በኦፊሴል ያዘዘው ነው ። ዕምነትህን
ልትጥልበት ትችላለህ!» በማለት ተናገረ ።

ከዚያም ሳቅ አለና ፓቬልን በፈገግታ በዐይኖቹ
ጠቀስ አደረገው ።

«ይኸ ብቻ ግን በቂ አይደለም ። መጻሕፍቶች ልጠ
ይቅህ ነው የመጣሁት ። እዚህ የመጣነው ሁለት ነን ።
የፊምን ከኔ ጋር አምጥቸዋለሁኝ ። ብዙ ቅጥራን አስይዘ
ው ወደ እዚህ ስለላኩን እግረ-መንገዳችንን ልንጠይቃ
ችሁ መጣን! ያ የፊም ከመምጣቱ በፊት መጻሕፍቶ
ቹን ስጠኝ ። ብዙ ነገሮችን በእኛ መሀል ማወቅ የለ
በትም» በማለት ሪቢን ተናገረ ።

እናት ሪቢንን ስትመለከት የተለወጡት ልብሶቹ
ብቻ አለመሆናቸው ተሰማት ። በባሕርዩ የመደላደል



ሁናቴ የሚታይበት ሲሆን የዐይኖቹ አመለካከት እን
ደቀድሞው ብልጥጥ ያሉ ሳይሆኑ ፤ የብልኀ ሰው አመ
ለካከቶች ነበሩ ።

«እናት ፤ መጻሕፍቶቹን ታመጪልናለሽን? እዚያ የሚ
ሰጡሽ ሰዎች የትኞቹን መጻሕፍት እንደሆነ ያውቃሉ ።
ወደ ገጠር የሚላኩ ናቸው በያቸው» በማለት ፓቬል
እናትን ጠየቃት ።

«እሺ ። ሳሞቫሩ እንደፈላ እሄዳለሁኝ» በማለት እና
ት መለሰች ።

«ፔላጌያ ኒሎቭና ፤ አንቺም የዚህ ተግባር ተሳታ
ፊ ሁነሻል ማለት ነዋ?» በማለት ሪቢን ሳቀ ። ከዚያ
ም ፡ —

«እ-ሀ-ሀ! እዚያ ብዙ ሰዎች መጻሕፍት ይፈልጋሉ ።
ለዚህ ምክንያቱ ፤ የቀበሌው መምህር የሥራ ውጤት
ነው ። የቤተ-ክህነት ሰዎች ከሆኑ ቤተ ሰቦች አብራክ
የተከፈለ ሰው ቢሆንም ፤ ጥሩ ሰው ነው ይሉታል ።
እኛ ካለንበት አንድ ሰባት ኪሎ ሜትር ያህል ራቅ
ብሎ ከሚገኝ ቦታም አንዲት የሴት መምህርት አ
ለች ። ሕገ-ወጥ የሆኑ መጻሕፍቶችን ሁለቱም አያነብቡ
ም ። ከሥራቸው እንዳይባረሩ ይፈራሉ ። እኔ የምሻው
ግን እንደ ሚጥሚጣ ትንሽ ኮስተር የሚያደርጉ የተ
ከለከሉ መጻሕፍቶችን ነው… አንብቤ ለሌሎች የማስ
ተላልፋቸው መጻሕፍት መርማሪ ፖሊሱ እጅ ወይን
ም ቄሱ እጅ ድንገት ቢወድቁ ፤ የሚወቅሱት ማንን
ነው? እነዚያኑ የፈረደባቸውን አስተማሪዎች ነው ። በዚ
ህን ጊዜም እኔ እስከጊዜው እሸሸጋለሁኝ» በማለት
ተናገረ ።

በብልኀነቱ እጅግ ተደስቶ ጥርሶቹን ብልጥጥ አድ
ርጎ ባያሌው ፈገግ አለ ።

«እንዴት እባክህ! ላይ ላዩን ሲያዩህ ድብ ትመስላ

ለህ ። በርግጡ ግን ቀበሮ ነህ ማለት ነዋ!» በማለት
እናት ከራሷው ጋር ተወያየች ።
«የተከለከሉ ጽሑፎቹን ያሠራጩ እነርሱ ናቸው
ብለው መምህራኑን ቢጠረጥሩዋቸው እሥር ቤት ይከ
ቷቸዋልን?» በማለት ፓቬል ጠየቀ ።
«እንዴታ ፤ ይከትቷቸዋል እንጂ! ምነው?» በማለት
ሪቢን ጠየቀ ።
«ነገር ግን እኮ ጥፋተኞቹ እነርሱ ሳይሆኑ እርስ
ዎ ነዎት ። ወደ እሥር ቤት መግባት ያለብዎ እርስ
ዎ ነዎት...» በማለት ፓቬል መለሰ ።
«አንተ እንደው የምታስገርም ሰው ነህ!» በማለት
ሪቢን ጉልበቱን ቸብ-ቸብ እያደረገ በመመታታት ተ
ናገረ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ —
«እኔን በዚህ ዓይነት ተግባር ይሳተፋል ብሎ የሚ
ጠረጥረኝ እስከአሁን አንድም ሰው የለም! ገበሬ ይኸ
ንን በመሳሰሉ ጉዳዮች ውስጥ አይገባም ። መጻሕፍት
የከቡራን ሰዎች ፈንታ ስለሆኑ በዚህ ጉዳይ ተጠያ
ቂ የሚሆኑት እነርሱው መምህራኑ ናቸው...» በማለት
መለሰ ።
ፓቬል ሪቢንን ያልተገነዘበው መስሎ ለእናት ታያ
ት ። ልጅዋ ዐይኖቹን ጠበብ ሲያደርግ አየችው ። ይኸ
ንን ካደረገ ደግሞ ተበሳጭቶአል ማለት ነው ።
«ሚኻኢል ኢቫኖቪች ተግባሮቹን እርሱ ራሱ ለ
መፈጸም ፤ ወቀሳውና ተጠያቂነቱ ደግሞ በሌሎች ት
ከሻ ላይ እንዲወድቅ ይሻል...» በማለት እናት አለ
ዝባ ተናገረች ።
«ልክ ነው! አሁን ለጊዜው እንዲህ መሆን አለበ
ት» በማለት ሪቢን ጢሙን እያሻሸ ተናገረ ።
«ስሚ እናት ፤ ከእኛ ሰዎች መካከል አንደኛቸው ፤
ለምሳሌ አንድሬይ · አንድ ድርጊት እየፈጸመ ያ የሚ
ፈጸመው ድርጊት እንዳይታወቅበት ከእኔ ጀርባ ቢ



ሸጎጥ እና እኔ ደግሞ እርሱ ለፈጸመው ድርጊት እ
ሥር ቤት ብገባ አንቺን ደስ ይልሻልን?» በማለት
ፓቬል መረር አድርጎ ጠየቃት ።
እናት ጥቂት ደንገጥ ካለች በኋላ ልጅዋን በመደነ
ቅ ተመለከተችው ።
«እንዴት እንደዚህ ዓይነት ሥራ በጓድ ላይ ይፈ
ጽማል?» በማለት ሊሆን አይገባውም በሚል አመላለስ
እራሷን እየነቀነቀች መለሰች ።
«እህህ!» በማለት ሪቢን ድምፅ አሰማ ። ከዚያም ፡ —
«ፓቬል ፤ ምን ለማለት እንደፈለግህ ይገባኛል»
በማለት ሪቢን ከተናገረ በኋላ እናትን እየተመለከተ
በዐይኑ ጠቀስ አደረጋት ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ —
«እናት ፤ ይኸ ተግባር እጅግ ጥንቃቄ የሚያሻው
ተግባር ነው» በማለት ተናገረ ። ከዚያም ፊቱን ወደ
ፓቬል ዞር በማድረግና ድምፁን አደላድሎ የሚቀ
ጥለውን ተናገረ ፡ —
«ወንድሜ ሆይ አንተ የምታስበው እንደ ህፃን
ነው ። ምሥጢራዊ ተግባርን በምታከናውንበት ጊዜ
ሚዛናዊ ትክክለኛ መሆን አይቻልም ። እስኪ ራስህ
ፍረደው ፡ — መጀመርያ ወደ እሥር ቤት እንዲገቡ
የሚደረጉት አስተማሪዎቹ ሳይሆኑ በእጁ ላይ መጽሐ
ፉ የተገኘበት ሰው ነው ። የመጀመርያው ነጥብ ይኸ
ነው ። ሁለተኛ ፡ — ምንም እንኳን መምህራኑ የሚያስተ
ምሩት በሕግ የተፈቀዱ መጻሕፍትን ቢሆንም
የሚያስተላልፉት ሃሣብ ዞሮ-ዞሮ ተመሳሳይ ነው ።
ልዩነት ቢኖር ሃሣቦቹ የሚተላለፉባቸው ቃላት ተመሳ
ሳይ አለመሆናቸው ነው ። የእነርሱ ትምህርት ዕውነተ
ኛነት ትንሽ ዝቅ ያለ ነው ። በአጠቃላይ ግን እነር
ሱም የሚያደርጉት እኔ የማደርገውን ነው ። ልዩነቱ ፤
እኔ ዋናውን ጎዳና ይዤ ስጓዝ እነርሱ በተዘዋዋሪ
መንገድ ይሄዳሉ ። የበላይ ገዢዎቻችንን በሚመለከት

ረገድ ግን ሁለታችንም ጥፋተኞች ተደርገን እንቆ
ጠራለን ። አይደለም እንዴ? ሦስተኛ ፡— ወንድሜ ሆይ ፣
እኔ እነርሱን የማጥቃት ፍላጎት የለኝም! እግረኛ እና
ፈረሰኛ አብሮ አይዘልቅም ። ምናልባትም እኔን መሰል
በሆነው ገበሬ ላይ ይኸንን አላደርግም ይሆናል ። በእ
ነርሱ ላይ ግን ፣ — ከሁለቱ አንደኛው የቄስ ልጅ ነ
ው ፣ ሌላኛይቱ ደግሞ የሀብታም ባለመሬት ልጅ ና
ት — ሕዝቡን ምን ጨነቀን ብለው ይቀሰቅሱታል?
በእነርሱ ላይ ግን ምን እንደማደርግ እንጃ ። እነርሱ
ምን እንደሚያስቡ መመራመር የእኔ የገበሬው ጉዳ
ይ አይደለም ። እኔ ምን እንደማደርግ አውቃለሁኝ ። እነ
ርሱ ምን ዓላማ እንዳላቸው ግን አንዳችም የማውቀው ፡
ነገር የለኝም ። ለሽህ ዓመታት ክቡራን መኳንንት ማ
ድረግ ይገባቸው የነበረውን ሲያደርጉ ኑረዋል ፡— የገ
በሬዎችን የአካል ቆዳ እንደ ቁርበት እሽት አድርገው
አለፉት ። አሁን ድንገት ከተኙበት ተንቀሳቅሰው በገ
ዛ እጆቻቸው የገበሬዎች ዐይኖች ተሸፍነውባቸው የነ
በሩትን መከለያዎች ገልጠው ከዐይኖቻቸው ላይ ያነ
ሱላቸዋል! እኔ በተረት የማምን ሰው አይደለሁኝም ።
ይኸንን መሳዩ ደርጊት ደግሞ ልክ እንደ ተረት ነው ።
በእኔ እና በተከበሩት መኳንንት መካከል ሰፊ የሆነ
ልዩነት አለ ። ወደሩቅ መንገድ በክረምት በምትጓዝ
በት ጊዜ አንድ እንስሳ ከሩቁ ዐይኖቹ ብርት-ብርት
ሲሉ ታያለህ ። ያ እንስሳ ምን ይሆን? ማወቅ ይቻላልን?
ተኩላ ነው ፣ ወይንስ ቀበሮ ፣ ወይንስ ደግሞ ውሻ ነው?
ማወቅ አይቻልም ። በሁለታችሁ መካከል ያለው ርቀ
ት ብዙ ነው» በማለት ሪቢን ተናገረ ።

እናት ልጅዋን ተመለከተች ። ፊቱን ለተመለከተው
የከፋው ይመስላል ።

ሪቢን ጢሙንም በጣቶቹ እያሻሸ ጥቋቁር ዐይኖ



ቹን በብርሃን መልቶ እና ትክ አድርጎ ፓቬልን ይመ
ለከታል ።

«ስለ ጥሩ ባሕርያት ለማውሳት ጊዜ የለኝም» በማ
ለት ንግግሩን ቀጠለ ። ከዚያም ቀጠል አድርጎ ፡—

«ሕይወት ከባድ ነው ። የውሾች ግትልትል ፣ የበጎች
መንጋ አይደለም ። እያንዳንዱ ውሻ እንደየድምፁ ይ
ጮኻል...» በማለት ተናገረ ።

«ለተራ ሕዝቦች ዓላማ በመቆም የሞትን መስዋዕ
ትነት የሚቀምሱ ክቡራን መኳንንት አሉ ። መላ ሕይ
ወታቸውን በእሥር ቤት ውስጥ ለተራ ሕዝቦች ሲሉ
የሚያሳልፉ ከክቡራን መኳንንት መካከል ይገኛሉ»
በማለት እናት የአንዳንድ ሰዎች መልክ እየታወሳት
ተናገረች ።

«የተለየ መደብ ውስጥ የሚመደቡ ናቸው» በማለት
ሪቢን መለሰ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡—

«ከገበሬዎች መካከል ከብረው-በልጥገው ከክቡራን
መኳንንት ጋር ወደላይ አሽቅበው የሚስተካከሉ አሉ ።
ከክቡራን መኳንንት መካከል አጥተው-ነጥተው በመደ
ኸየት ከተራ ሕዝቦች ዕኩል ወደታች አቆልቁለው
የሚወርዱ አሉ ። ፓቬል ፣ እንዴት እንዳብራራህልኝ ት
ዝ ይልሃልን? የአንድን ሰው አስተሳሰብ የሚወስንለት
የአኗኗሩ ሁኔታ ነው ። ጉዳዩ ይኸ ነው! ወዝ-አደሩ ፣
'ነው' የሚል መልስ ቢሰጥ አሠሪው ፣ 'አይደለም' የ
ሚል አፀፋ ያቀርባል ። ወዝ-አደሩ ፣ 'አይደለም' ቢል
ደግሞ ፣ አሠሪው 'ነው' ይላል ። ጠባያቸው እንዲህ ሆድ
ና-ጀርባ ነው ። እንደዚሁም ደግሞ በገበሬና በመሬት
ከበርቴ መካከልም ተመሳሳይ የሆነ ልዩነት አለ ። ገበ
ሬው በበቂ እንዲመገብ የመሬት ከበርቴው እህል
ማግበስበስ የለበትም ። እርግጥ ነው እያንዳንዱ መደ
ብ የየራሱ የውሻ ልጆች አሉት ። እና እኔም የምከ
ራከረው ለሁሉም ገበሬዎች አይደለም...»

ጥንካሬ እና ኮስታራነት ሳይለየው ከመቀመጫው
ተነሳ ። ጥርሶቹን አንድነት አገናኝቶ ያፋጫቸው ይመስ
ል ጢሙ ይንቀጠቀጣል ።
«አምስት ዓመት ሙሉ ገጠሩ ምን እንደሚመስ
ል ሳልመለከት ከፋብሪካ-ፋብሪካ እየተዘዋወርኩ ሠራ
ሁኝ» በማለት ዝግ ባለ አነጋገር ሪቢን ንግግሩን ቀጠ
ለ ። ከዚያም ፡ —
«በመጨረሻም ወደ ገጠር ስመለስ ሁለተኛ እንደ
ቀድሞው እንደማልኖር አውቄአለሁኝ! ገባችሁ? በፍጹም
አልቻልኩኝም! እዚህ በምትኖሩበት ጊዜ እንደዚህ ዓይ
ነቱን አሳዛኝ ድርጊት መመልከት አትችሉም ። እዚያ
ገጠር ችጋር ሕዝቦችን እንደጥላቸው አብሮ ኋላ-ኋላ
ይከታተላቸዋል ። ምግብ የማግኘት ተስፋም የለም ። በጭ
ራሽ የለም! ችጋር የሕዝቦችን ነፍስ ቡጥቡጥ አድርጎ
የሚበላው ሲሆን ፊታቸውንም ከላያቸው ላይ ሙሽ
ልቅ-ግሽልጥልጥ አድርጎ ያጣጥመዋል ። ሕዝቦች የሚኖ
ሩት ኑሮ ኑሮ አይደለም ። ጉልቆ-መሣፍርት በሌለው
ችግር እና ችጋር ይበሰብሳሉ... ምንም የምትሰጡን
ሌላ ተጨማሪ ነገር የለም እንዴ በማለት ባለሥል
ጣናቹ እንደ ጥንብ-አንሳ ጆፌ አሞራ ዙርያውን ሕ
ዝቦች ላይ ያንዣብቡባቸዋል ። አንዳች ኢምንት ነገር
ገበሬው ይዞ ቢያገኙት ፤ ያችኑ ከእጁ ላይ መንትፈው
እና ፊቱን ቧጥጠውት ይበራሉ...»
ሪቢን ዙርያውን ተመለከተ ። ከዚያም ፓቬልን ጠ
ጋ ለማለት ወደ ጠረጴዛው ጎንበስ ብሎ በመጠጋት
የሚከተለውን ጨምሮ ተናገረ ፡ —
«ያንን ወደመሰለው አኗኗር ስመለስ የእኔ ሆድ
በትውስቱ ንዳድ ተቃጥሎ ነበር ። ልቋቋመው አልች
ልም ብየ ነበር ። ከዚያም ራሴው ለራሴ የሚከተለው
ን እንዲህ በማለት ነገርኩት ፡ — ‘መቋቋም አለብህ ።
ምግብ ልትሰጣቸው አትችልም ይሆናል ፤ ጥሩ ገንፎ



ልታገነፋ ግን ትችላለህ!’ እና ልቤ እስከአሁን የቋጠ
ረውን ቂም ዘርግፎ በማውጣት በገጠር ይኸው እስከ
አሁን ቆየሁ ። ቂሜ በልቤ ውስጥ እንደ ጩቤ ተሰክ
ቶ አሁንም አልተነቀለም ። ከተሰካበት እንዳለ ነው ።»
ቀስ ብሎ ፓቬል ወዳለበት ቦታ ቀረብ በማለት
እጁን ፓቬል ትከሻ ላይ አሳረፈ ። ላቡ በቅንድቦቹ
ላይ ይፈልቁ የነበረ ሲሆን እጁም ይንቀጠቀጥ ነበር ።
እንዲህ በማለትም ንግግሩን ቀጠለ ፡ —
«ያንተን ድጋፍ እሻለሁኝ ። አንድ ሰው ካነበባቸ
ው በኋላ እጅግ በመርካት እንቅልፍ ሳያሸልበው ፍ
ጥጥ ብሎ እንዲቆይ የሚያደርጉትን ዓይነት መጻሕ
ፍት ስጠኝ ። ሹል-ሹል እሾሆችን የያዙ ጃርቶች አዕ
ምሮአቸው ውስጥ እንዲቀፈቀፉ ለማድረግ እንሻለን ።
የእናንተን ጋዜጦች የሚጽፉት የከተማ ሰዎች ገጠሩን
በሚመለከት ረገድም እንዲጽፉ ንገሯቸው! ፊደሎቹ
በመጻፍ ብዛት ግለው እስኪንፈቀፈቁ ድረስ ይጻፉ!
በዚህም ምክንያት ሕዝቦች ለዓላማቸው በመስዋዕት
ነት ይሰው!» እጁን በማንሳት የሚናገረውን የእየአንዳ
ንዱን ቃል ኃይለ-ቃል ግልጽ እና ዝርዝር በሆነ
ሁኔታ አጠንክሮ ይገልጽ ጀመር ።
«ሞትን ሞት ይታገለዋል! በሌላ አባባል ለመግለ
ጽም ፤ የሕዝቦች ትንሳኤ እንዲኖር አንተ መስዋዕት
ሁን!በመላው ዓለም የሚገኙ አያሌ ሚሊዮን ሕዝቦ
ች እንዲነሳሱ እኛ ብዙ ሺህ ሰዎች መስዋዕት እን
ሁን! መሆን ያለበት እንዲህ ነው! መሞት ቀላል ጉዳ
ይ ነው ። ከባዱ ጉዳይ መነሳሳት ነው ። የሕዝቦች ትን
ሳኤ እንዲኖር ማድረግ ነው!» በማለት ተናገረ ።
እናት ሳሞቫሩን አመጣችና ሪቢንን የጎድን ተመለ
ከተችው ። ከእርሱ አንደበት ይፈልቁ በነበሩት ቃላት
ክብደት እና ኃይል እንክትክት ያለች መስሎ ተሰማ
ት ። እርሱን ስትመለከት ስለባሏም እንድታስታውስ

የሚያደርጋት ጉዳይ ነበር ። ባሏም ልክ እንደሪቢን
ጥርሶቹን ፣ ያገጥጥ የነበረ ሲሆን ሸሚዙን ሲጠቀልልም
ልክ ፣ እንደሱው ነበር ። የእሷ ባልም ልክ እንደሪቢን
በትዕግሥተ-ቢስነት ቁጣ የተመላ ነበር ። የእርሷ ባል
ትዕግሥተ-ቢስ ቢሆንም ሃሣቡን አሳክቶ ለመግለጥ
የሚችል አልነበረም ። ይኸኛው ሰው ግን ስሜቶቹን
አብራርቶ መግለጥ ይችል ነበር ። ይኸ ሁኔታም አስ
ፈሪ ከመሆን እንዲቆጠብ በመጠኑ አግዞታል ።

ፓቬል በእሺታ መንፈስ ራሱን እየነቀነቀ ፣ —

«ይኸንን ማድረግ አለብን ። እናንተ ዜናዎችን ከገ
ጠር አቅርቡልን ። እኛ ለእናንተ ጋዜጣ አትመን እና
ወጣላችኋለን...»

እናት ልጅዋን በፈገግታ ተመለከተችና በደስታ
ምልክት ራሷን ነቀነቀች ። ከዚያም አንዳችም ነገር
ሳትናገር የሙቀት ልብሶቿን ለባብሳና ከቤት ወጥታ
ሄደች ።

«እሺ ፤ እኛ ዜናዎቹን አጠናቅረን እናቀርብላችኋለ
ን ። እናንተ ግን በጣም ግልጽ እና ቀላል በሆነ አጻ
ጻፍ ፤ ላም እንኳን ብታነበው ልትረዳው በሚችል ሁኔ
ታ ጻፉልን!» በማለት ሪቢን ጮኽ ብሎ ተናገረ ።

የማዕድ ክፍሉ በር ተከፈተና ከውጪ አንድ ሰው
ወደ ቤት ገባ ።

«የፊም ነው» በማለት ሪቢን ወደማዕድ ክፍሉ እየ
ተመለከተ ተናገረ ።

«የፊም! ወደዚህ ዝለቅ! ተዋወቅ ፤ ፓቬል ይባላል ።
ስለእርሱ አጫውቸህ የነበረው ነው» በማለት ሪቢን
ተናገረ ።

ቁመተ-ረዥም ፤ ፀጉረ-ነጭ ፤ ፊተ-ዠርጋዳ የሆነ እና
ቡናማ ዓይኖች ያሉት ሰው ከበግ ቆዳ የተሠራ አጠ
ር ያለ ካፖርት ለብሶ እና ባርኔጣውንም በእጁ ይዞ
ከግንባሩ ዝቅ በማለት ፓቬልን ወደታች እየተመለከ



ተ ከፓቬል ፊት ቆሟል ። የጠንካራነት ሁኔታ በሰውየ
ው ላይ ይታይበታል ።

«ጤና ይስጥልኝ» በማለት ጎርነን ባለ ድምፅ ተና
ግሮና እጁን ዘርግቶ ከጨበጠው በኋላ ሉጫ ፀጉሮቹ
ን ይዳሰስ ጀመር ። ክፍሉን ግራና-ቀኝ ሲቃኝ ፤ ዐይኖቹ
መጽሐፍ ላይ ዐረፉ ። እርሱም ቀስ-ቀስ እያለ ወደመ
ጻሕፍቶቹ አኳያ ይጠጋ ጀመር ።

«አነባጠረባቸው!» በማለት ሪቢን ፓቬልን በዐይ
ኑ እየጠቀሰ ተናገረ ። የፊም አንዴ በዐይኖቹ ከቃኛ
ቸው በኋላ መጻሕፍቶቹን መመልከቱን ቀጠለ ።

«ኡይ! እንዴት ብዙ መጻሕፍት ናቸው! ምናልባት
ም እነዚህን ሁሉ ለማንበብ ጊዜ የለዎትም ይሆናል ።
ኑሮዎ ገጠር ቢሆን ኖሮ ግን መጻሕፍቶችን ለማን
በብ ጊዜ ይኖርዎታል...» በማለት ተናገረ ።

«የማንበብ ፍላጎትህስ ዝቅ ያለ ሊሆን አይችልም
ን?» በማለት ፓቬል ጠየቀ ።

«ኧረ በፍጹም ። የማንበብ ፍላጎትዬም ከፍተኛ ነ
ው የሚሆነው» በማለት ሰውየው አገጩን እያሻሸ ተ
ናገረ ። ከዚያም ፣ —

«ገጠር ያሉት ሰዎች መመራመር ጀምረዋል ። ጂ
ኦሎጂ ፤ ደግሞ ይኸ ምን ማለት ነው?» በማለት ጂኦ
ሎጂ የሚል ርእስ ያለውን መጽሐፍ እየነካካ ጠየቀ ።

ፓቬልም ምን ማለት እንደሆነ መለሰለት ።

«እንዲህ ዓይነቱ መጽሐፍ ለእኛ አይሆንም» በማ
ለት መጽሐፉን ወደ መደርደርያው እየመለሰ ተናገረ ።

ሪቢን ተንፈስ ብሎ ፣ —

«መሬት ከየት እንደተገኘች ለማወቅ ገበሬ አይጨ
ነቅም» በማለት የፈገግታ አነጋገር ተናገረ ። «ገበሬው
ሊያውቅ የሚሻው መሬት በሰዎች እጅ እንዴት ልት
ገባ እንደቻለች ነው ። የመሬት ከበርቴዎች መሬትን
ከገበሬው እጅ እንደምን አድርገው ሊነጥቁት እንደ

ቻሉ ማወቅን ነው የሚሻው ። መሬት ቢሻት ብትዞር ወይንም ባለችበት ረግታ የቆመች ብትሆን ለገበሬው ምኑ ነው?ለገበሬው የሚበላውን ነገር የምታቀርብለት ትሁን እንጂ ከፈለገች ሜንጦ ላይም ትንጠልጠል ።»

«የባርነት ታሪክ» በማለት የአንዱን መጽሐፍ ርእስ የፊም አነበበ ። ከዚያም ፡ —

«ስለእኛ ታሪክ የሚያወሳ መጽሐፍ ነውን?» በማለት ጠየቀ ። ፓቬልም ለጥያቄው ሲመልስ ፡ —

«የለም ፤ አይደለም ። በመጽሐፉ ውስጥ ስለሩስያ ገባርነት ሁኔታ የሚገልጥ አንድ ራሱን የቻለ ምዕራፍ ተጽፎ ይገኝበታል» በማለት እየተናገረ ሌላ መጽሐፍ ሰጠው ። የፊም መጽሐፉን ተቀብሎ ያገላብጠው ጀመር ።

«ይኸ ያለፈ ታሪክን የሚያወሳ ነው» በማለት መጽሐፉ ስለያዘው ሃሣብ ብዙም ባለመጓጓት መንፈስ መልሶ አስቀመጠው ።

«የራስዎ መሬት አለዎትን?» በማለት ፓቬል ጠየቀው ።

«እንዴታ ። እኔ እና ሁለቱ ወንድሞቼ አራት ዴስያቲና* መሬት አለን ። መሬታችን በሙሉ አሸዋ የለበሰ ነው ። ተዘርቶበት ሰብል ለማምረት ምቹ የሆነ መሬት ሳይሆን ፤ ነሐስ መወልወያ ሊሆን የሚችል ርባና-ቢስ መሬት ነው» በማለት ተናገረ ። ጥቂት ዝም አለ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ —

«እኔ ግን ግብርና ትቻለሁኝ ። ምን ጠቀሜታ አለው? አሥሮ-ተብትቦ ከማስቀረት በስተቀር የምትበላውን አያስገኝልህም ። ተቀጣሪ-ገበሬ በመሆን ለአራት ዓመታት አገልግያለሁኝ ። በበልግ ወራት የውትድርና ግል

---

* ዴስያቲና የመሬት መሥፈርት ። 1 ዴስያቲና 1.1 ሄክታር ነው ። (ተርጓሚው ።)



ጋሎት መስጠት ነበረብኝ ። አባባ ሚኻኢሎ አትመዝገብ ምን ያደርግልሃል አሉኝ ። በአሁኑ ጊዜ ወታደሮችን የሚያሠማሩዋቸው ሕዝብን እንዲፈጁ ነው አሉኝ ። እንደሚመስለኝ ግን ፤ ለውትድርና ሳልሄድ የምቀር አይመስለኝም ። በስቴፓን ራዚን እና በፑጋቾቭ* ጊዜም ቢሆን ወታደሮች ሕዝቦችን ጨፍጭፈዋል ። ይኸ ድርጊት እንዲያበቃ ማድረጉ አሁን ጊዜው ነው ። አይመስልህምን?» በማለት ፓቬልን እየተመለከተ ጠየቀ ።

«በጣም ጊዜው ነው! ግን ደግሞ ይኸንን ማድረግ እንዲህ ቀላል ጉዳይ አይደለም ። ለወታደሮች ምን መናገር እንዳለብህ እና መቼ እንደምትነግራቸውም ማወቅ ያስፈልጋል...» በማለት ፓቬል ፈገግ እያለ መለሰ ።

«ይኸንን መማር እንችላለን!» በማለት የፊም መለሰ ።

«መኮንኖቹ ድንገት ቢያውቁብህ ፤ በጥይት ደብድበው ይገሉሃል!» በማለት የፊምን አትኩሮ እየተመለከተ ፓቬል ተናገረ ።

«ከእነርሱ የምጠብቀው አንዳችም ርኅራኄ የለም» በማለት የተደረደሩትን መጻሕፍቶች እንደገና እያገላበጠ ወጣቱ ሰው በተረጋጋ መንፈስ መለሰ ።

«የፊም ፤ ሻይህን ጠጣ ። መሄጃችን ደርሶአል!» በማለት ሪቢን ተናገረ ።

«እሺ ፤ እጠጣለሁኝ» በማለት ወጣቱ ሰው መለሰ ። ከዚያም የሚከተለውን ጥያቄ አቀረበ ፡ —

«ለመሆኑ ሬቮሉሺን ማለት ግርግር ማለት ነውን?»

---

* ራዚን እና ፑጋቾቭ በሩስያ ውስጥ የገበሬዎችን አመጽ የመሩ ስመ-ጥር ገበሬዎች ናቸው ። (ተርጓሚው ።)

በእንፋሎት (ሳውና) ገላውን ታጥቦ ፤ ደም መስሎ እና ፊቱንም ጨፍግጎት እንድሬይ መጣ ። እንዳችም ቃል ሳይናገር የፊምን ከጨበጠ በኋላ ሪቢን አጠገብ በመቀመጥ እርሱን-እርሱን እያየ በጥቂቱ ከጉሮሮው አንኮራፋ ።

«ደስ ያለህ አትመስልም ። ምነው ምን ሆነሀል?» በማለት ሪቢን ጉልበቱ ላይ ቾብ-ቾብ እያደረገ ጠየቀው ።

«ምንም አልሆንኩም» በማለት ኾኾል መለሰለት ።

«እርሱም ወዝ-አደር ነውን?» በማለት ወደ ኾኾል እየተመለከተ የፊም ጠየቀ ።

«አዎን ነኝ ። ምነው?» በማለት ኾኾል መለሰ ።

«ካሁን ቀደም የፋብሪካ ሠራተኞችን አይቶ አያውቅም! ከሌሎቹ ሰዎች የተለዩ ሁነው አግኝቶአቸዋል...» በማለት ሪቢን መለሰ ።

«ልዩነታችን በምንድነው?» በማለት ፓቬል ጠየቀ ።

የፊም እንድሬይን ደህና አድርጎ ካስተዋለው በኋላ ፡ —

«እናንተ አጥንተ-ጠንካሮች ናችሁ ። ገበሬ ግን አጥንተ-ድቡልቡል ነው» በማለት የፊም መለሰ ። ከዚያም ሪቢን የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«ገበሬ አለበት ቦታ ላይ በእግሩ ተደላድሎ የሚቆም ነው ። ምንም እንኳን የቆመባት መሬት የርሱ ባትሆንም እላይዋ ላይ መቆሙ ይሰማዋል! የመሬት ምንነት ለስሜቱ ይታወቀዋል ። የፋብሪካ ሠራተኛ ግን እንደ ወፍ ነው ። እኔ የበቀልኩበት ነው የሚለው የራሱ መሬት የለውም ። የራሱ ቤት የለውም ። ዛሬ እዚህ ቢገኝ ፤ ነገ ይኸንን የነበረበትን የሥራ ቦታ ለቅቆ ይሄዳል! ሴት እንኳን ከአንድ ቦታ ላይ ይዛ አታቆየውም ። አንድ ነገር ተዛብቶ ሲገኝ ያንን የነበረበትን ቦታ ሲለቅቅ እርሷንም ትቷት ይሄዳል! የተሻለ



ፍላጋ ከቦታ-ቦታ ይናውዛል ። ገበሬ ግን ከወዲያ ወዲህ ሳይባክን የኑሮ ሁኔታው የተሻሻለ እንዲሆንለት እዚያው ባለበት ረግቶ ይጥራል ። እናትህ እኛውና መጡ!» አለ ።

«ከመጻሕፍቶችዎ መካከል አንዱን ያውሱኛልን?» በማለት የፊም ወደ ፓቬል ተጠግቶ ጠየቀው ።

«እንዴታ ፤ አውስሃለሁኝ» በማለት ፓቬል መለሰ ።

የወጣቱ ሰው ዐይኖች በጉጉት ብሩኅ ሆኑ ።

«መልሼ አመጣልዎታለሁኝ» በማለት ለፓቬል በጥድፊያ አረጋገጠ ተናገረ ።

«የእኛ ሰዎች ሁል ጊዜ እዚህ እየመጡ ቅጥራን ያራግፋሉ ። ለእነርሱ ሰጥቻቸው ያመጡልዎታል» በማለት የፊም ተናገረ ።

ከበግ ቆዳ የተሠራውን ካፖርቱን ለብሶ ቀበቶውን በካፖርቱ ላይ ጠበቅ-ጠበቅ ማድረግ የጀመረው ሪቢን ፡ —

«እንግዲህ እንሂድ!» በማለት ተናገረ ።

«ይኸን እንግዲህ እኔ በደንብ አነባለሁኝ!» በማለት መጽሐፉን በእጁ ይዞ እና በደስታ ተውጦ ባያሌው ፈገግ እያለ የፊም ተናገረ ።

እነርሱ ከሄዱ በኋላ ፓቬል በስሜት ተውጦ ወደ እንድሬይ ዞር ብሎ ፡ —

«እንዴት ይመስሉሃል?» በማለት ጠየቀው ።

«አ-ዎ-ን» በማለት እየአንዳንዱን ቃል ቀስ ብሎ ከተናገረ በኋላ ቀጠል አድርጎ ፡ —

«ነጎድጓድ እንዳዘለ ደመና ናቸው» በማለት ተናገረ ።

«አብሶ ሚኻኢሎማ? ጨርሶ ፋብሪካ ውስጥ ሠርቶ የማያውቅ ይመስላል ። የለየለት ገበሬ መስሏል! ኧረ እንዴት ያለ አስፈሪ ሁኗል!» በማለት እናት ተናገረች ።

ወንበሩ ላይ ቁጭ ብሎ ሻዩን ይጠጣ የነበረውን
አንድሬይን ፡ —

«እነርሱ በመጡ ጊዜ እዚህ ያለመኖርህ ደግም
አልሆነ ። ብዙውን ጊዜ ስለሰዎች ልቦና ታወራለህ ። እነ
ዚህን ሁለት ልቦች አሾልቀህ ውስጣቸው በመግባት
በተመለከትካቸው ኖሮ እንደምን ጥሩ በሆነ ነበር ። ሪ
ቢን አንዳችም ትንፋሽ እንዳልተነፍስ አድርጎኝ ሄደ!
ከእርሱ ጋር መከራከር አልቻልኩኝም!.. በሰብአውያን
ፍጡሮች ላይ አንዳችም ዕምነት የሌለው ከመሆኑ
በስተቀር የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ አለ ብሎም አ
ያምንም! እናት ያቀረብሽው አስተያየት ትክክል ነው ።
ሪቢን ላይ ዕውነትም አንድ አስፈሪ የሆነ ሁኔታ ይታ
ይበታል!..» በማለት ፓቬል ተናገረ ።

«ይኸንን ተመልክቻለሁኝ ። ገዢዎች የሰዎችን ልቦ
ና መርዘውታል ። ሰፊ ሕዝቦች ከተኙበት ሲንቀሳቀሱ
ማናቸውንም ነገር ድምጥማጡን ያጠፉታል! እርቃን-መ
ሬትን ይሻሉ ። እርቃን ካልሆነችም እንድትሆን ያደር
ጓታል ። ማናቸውንም ነገር ብጥብጥሱን ያወጡታል!»
በማለት ተናገረ ።

ቀስ እያለ ይናገር የነበረ ሲሆን ፤ ሀሣቡ በሌላ
ጉዳይ ተውጦ የነበረ መሆኑ በግልጽ ያስታውቃል ።
እናት አጠገቡ ሁና በቀስታ ነካ-ነካ በማድረግ ታሻ
ሸው ጀመር ።

«ምነው ፈዘዝክ አንድርዬ ፤ ነቃ በል እንጂ» በማ
ለት ተናገረች ።

«እናቴ ፤ ቆዩኝ ትንሽ» በማለት ፍቅር በተመላበት
አነጋገር መለሰላት ። ድንገት ቱግ በማለት ጠረጴዛው
ን በእጁ ደበደበ ። ከዚያም ፡ —

«ዕውነትክን ነው ፤ ፓቬል! ገበሬው አንድ ጊዜ ተረ
ጋግቶ በእግሩ ከቆመ መሬቱን ለራሱ መገልገያ ከፋ
ፍሎ ይይዛል! እስከጊዜው የተሰቃየበትን ማናቸውንም



ምልክት ከተሰቦ በሽታ በኋላ እንደሚደረግ የማቃጠል
ተግባር በእሳት ያጋያል...» በማለት ተናገረ ።

«ከዚያም በኋላ እኛ በቆምንበት አኳያ ይቆማል»
በማለት ፓቬል ተናገረ ።

«ይኸን እንዳያደርግ ማገድ የእኛ ፈንታ ነው! ወደ
እኛ እንዲሳብ ማድረግ የእኛ ፈንታ ነው ። ከማንም
የበለጠ እኛ ለእርሱ ቅርበት አለን ። ያምነናል ። ስለዚ
ህም ይከተለናል!» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

«ለገጠሩ የጋዜጣ ህትመት እንድናዘጋጅ ሪቢን
ጠይቆናል!» በማለት ፓቬል ተናገረ ።

«ልክ ነው ፤ ያስፈልጋል!» በማለት ኾኾል መለሰ ።

«ከእርሱ ጋር ክርክር አለመግጠሜ መጥፎ ነው!»
በማለት ፓቬል ፈገግ ብሎ ተናገረ ።

«አሁንም ገና ጊዜ አለህ» በማለት ኾኾል ረጋ
ብሎ የገዛ ፀጉሩን እያሻሸ መለሰለት ።

«መዘመርህን ቀጥል ።እግራቸው ከምድሪቱ ጋር ተቀርቅ
ቦ ያልተያያዘባቸው ያንተን ዜማ ተከትለው እስክስታ
ይወርዳሉ! የምድሪቱ ከእግራችን ሥር መኖር አይሰማ
ችሁም ብሎ ሪቢን የተናገረው ዕውነት ነው ። ሊሰማ
ንም አይገባም ። ምክንያቱም ፤ አንዴ ወዝውዞ ማደበላለ
ቁ የእኛ ተግባር ስለሆነ ። አንዴ ምድሪቱን እንወዘው
ዛታለን ። ከዚያም ሕዝቦች ላቀቅ-ላቀቅ ይላሉ ። ሁለተኛ
ጊዜ ስንወዘውዛት ሕዝቦች ነፃ ይወጣሉ!» በማለት
ኾኾል ተናገረ ።

«አንድሩሻ ፤ ለአንተ ሁሉም ነገር የሚታይህ እንዲ
ህ ቀላል ጉዳይ ሁኖ ነው!» በማለት እናት እየሳቀች
ተናገረች ።

«አዎን ። ቀላል ጉዳይ ሁኖ ይታየኛል ። እንደሕይወ
ት እንደራሷ ቀላል ጉዳይ ሁኖ ነው የሚታየኝ!»
በማለት ተናገረ ።

ጥቂት ደቂቃዎች ከቆየ በኋላ የሚከተለውን ተና
ገረ ፡ —

«ለሽርሽር ወጣ እላለሁኝ...»

«ገላህን ከታጠብክ በኋላ? ነፋስ ነው ። ጉንፋን ይይዘሃል!» በማለት እናት አስጠነቀቀችው ።

«ዓየር መቀበል እሻለሁኝ!» በማለት መለሰ ።

«ጉንፋን እንዳይዝህ ተጠንቀቅ ። እንቅልፍ ሸለብ ቢያደርግህ ይሻል ይሆናል» በማለት ፓቬል ፍቅር በተመላበት ስሜት ተናገረ ።

«የለም ወጣ እላለሁኝ!» በማለት ኾኾል መለሰ ።

የሙቀት ልብሶቹን ለባበሰና አንድም ቃል ሳይናገር ወጥቶ ሄደ...

«በጣም ነው የተከዘው!» በማለት እናት እየተነፈሰች ተናገረች ።

«ያ ጉዳይ ከደረሰ በኋላ ይበልጥ ያፈቀርሺው ይመስላል ። እኔም በጣም ነው ደስ ያለኝ» በማለት ፓቬል ተናገረ ።

እናት ልጅዋን በመገረም ሁኔታ ተመለከተችው ።

«ነው እንዴ? እኔ ደግሞ ልብ ብዬም እራሴን አላስተዋልኩኝም ። ልናገር ከምችለው የበለጠ እወደዋለሁኝ!» በማለት ተናገረች ።

«እናቴ ፤ ልብሽ ሩኅሩኅ ነው!» በማለት ፓቬል አለስልሶ ተናገረ ።

«አንተን እና ጓደኞችህን ትንሽም ቢሆን ፤ መርዳት ከቻልኩኝ ነዋ! እንዴት ልረዳችሁ እንደምችል ባወቅሁት ኖሮ ነበራ!» በማለት መለሰችለት ።

«ትማሪዋለሽ» በማለት መለሰላት ።

«ከመጨነቅ እንዴት ልገላገል እንደምችል መማር እሻለሁኝ!» በማለት በጥቂቱ ፈገግ እያለች ተናገረች ።

«እናይዬ ፤ ይኸንን ጉዳይ ሁለተኛ አንስተን ባንነጋገርበት ይሻላል ። እኔ የአንቺ ትልቅ-ትልቅ ውለታ አለብኝ!» በማለት ፓቬል ተናገረ ።

እንባዎቿን እንዳያይባት ወደማዕዱ ክፍል ገባች ።



ኾኾል ወደቤት ተመልሶ የመጣው ዘግይቶ ሲሆን ፤ በቀጥታ ወደምኝታው ሄደ ።

«አሥር ቬርስታ* ያህል ሳልጓዝ አልቀረሁም...» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

«ረዳህን?» በማለት ፓቬል ጠየቀው ።

«አናውራው ። መተኛቴ ነው!» በማለት ኾኾል መለሰ ።

ሌላ ምንም ቃል አልተናገረም ።

ያው እንደቀድሞው ብጭቅጭ ያለ ልብሱን ለብሶ ፤ ቁሽሽ ብሎ እና ቅፍፍ ብሎት ቬሶቭሺኮቭ ከጥቂት ጊዜ በኋላ መጥቶ ወደቤት ገባ ።

«ለመሆኑ ኢሳይን ማን እንደገደለው ሰምተሃልን?» በማለት አንዴ ወዲህ አንዴ ወዲያ በክፍሉ ውስጥ እየተመላለሰ ቅርፍፍ ባለ ሁኔታ ፓቬልን ጠየቀው ።

«የለም!» በማለት በአጭሩ መለሰለት ።

«ይኸንን ያደርጋል ተብሎ ሊገመት የማይችል ሰው ይዘዋል! እኔ ራሴም ልከሰክሰው ተዘጋጅቼለት ነበር ። እኔ አለመግደሌ የሚያሳዝን ነው! ይኸንን ማድረግ የሚገባኝ እኔ ነበርኩኝ!» በማለት ተናገረ ።

«ኒኮላይ ፤ ተው እንጂ ፤ እንዲህ ያለ ነገር አትናገር!» በማለት ፓቬል በወዳጅነት አነጋገር መለሰለት ።

«ለመሆኑ ይኸ ምን የመሆን ሁኔታ ነው! ልብህ ገራ-ገር ሁኖ አጫጪህህ ግን እንደአንበሳ ነው ። ይህን ማድረግ ምን ያስፈልጋል?» በማለት እናት ፍቅር በተመላበት ስሜት ተናገረች ።

በዚህ በዛሬው ምሽት ኒኮላይን በማየቷ ተደስታ ነበር ። ፈንጣጣ የበላው ፊቱ እንኳን አስደሳች መስሎ ታያት ።

---

* አንድ ቬርስታ ከአንድ ኪሎሜትር ትንሽ ይበልጣል ። (ተርጓሚው ።)

«እኔ ይኸንን ከማድረግ ሌላ ተግባር የለኝም» በማለት ትክሻውን ነቅነቅ እያደረገ ተናገረ ።

«ምን ላድርግ እያልኩኝ እጨነቃለሁኝ ። ምንም የማደርገው ነገር የለም! ከሰዎች ጋር መነጋገር ያስፈልጋል ። እኔ ደግሞ የአነጋገሩን ሁኔታ አላውቅበትም! ሁኔታዎች እንዴት እንደሆኑ እመለከታለሁኝ ። ሰዎች የሚፈጽሟቸውን ስሕተቶች አስተውላለሁኝ ። በቃላት አሳክቼ ማቅረብ ግን አልችልም! ዱዳ እንደማለት ነኝ» በማለት ተናገረ ።

ወደፓቬል ከተጠጋ በኋላ ቀደም ሲል ያሰማው በነበረው ዓይነት ድምፅ ሳይሆን ፤ የሚያሳዝን የሕፃን ልጅ ድምፅ በሚመስል አነጋገር ጠረጴዛውን በጣቱ እየቆረቆረ ፓቬልን የሚከተለውን ጠየቀው ፦

«ወንድሞቼ ሆይ ፤ የሆነውን ዓይነት ከበድ ያለ ሥራ እንድሠራ ስጡኝ! በዚህ ዓይነት ሁኔታ መኖር አልችልም! ሁላችሁም በተግባር የተጠመዳችሁ ስትሆኑ ተግባሩም እንዴት እንደሚራመድ አያለሁኝ ። እኔ ግን ከሁሉም ተግባር ውጪ ነኝ! ግንዲላ እና ሳንቃ መከመር ብቻ ነው ሥራዬ ። ይኸም ሥራ ነው ተብሎ ለዚህ ሲባል መኖር ይቻላልን? ከበድ ያለ ሥራ ስጡኝ» በማለት ጠየቀ ።

ፓቬል የኒኮላይን እጅ ይዞ ወደርሱ ሳብ አደረገው ።

«እንሰጥሀለን!..» አለው ።

በቤቱ ውስጥ ከሚገኘው አካፋይ ውስጥ የኾኾል ድምፅ እንዲህ ሲል ተሰማ ፦

«ኒኮላይ ፤ የህትመት ፊደሎች ለቃሚ እንድትሆን አስተምርሀለሁኝ ። እንዴት ነው ፤ አትፈልግምን?» አለው ።

ኒኮላይ ወደ ኾኾል ጠጋ ብሎ ፤ እንዲህ አለ ፦

«ይኸንን ብታደርግ ፤ እኔ ፤ እኔም ጩቤዬን እሰጥሃለሁኝ...»



«ከነጩቤህ ገሀነም ግቡ!» በማለት እየጮኸ ኾኾል በሳቅ ተንከተከተ ።

«ግሩም ጩቤ ነው!» በማለት ኒኮላይ አጥብቆ ተናገረ ።

ፓቬልም መሳቅ ጀመረ ።

«እንዴት ፤ በኔ ነው እንዴ የምትስቁብኝ?» በማለት ኒኮላይ ክፍሉ መሀል ቆሞ ተናገረ ።

«ታዲያስ ፤ ነውና» በማለት ኾኾል ከአልጋው እመር ብሎ እየተነሳ ተናገረ ። ከዚያም ፦

«ስማ ፤ ወደ መስክ ለሽርሽር እንውጣ ። ዛሬ ጨረቃ ወጥታለች ። አትሄድምን?» በማለት ጠየቀው ።

«እሺ!» በማለት ፓቬል ተናገረ ።

«እኔም አብሬአችሁ እሄዳለሁኝ! ኾኾል ስትስቅ ማዳመጥ ደስ ይለኛል» በማለት ኒኮላይ ተናገረ ።

«እኔም የገባኸውን ቃል ስታሟላ ደስ ይለኛል» በማለት ኾኾል መለሰለት ።

ልብሱን ለመልበስ ወደማዕድ ክፍል ሄደ ።

«ሙቀት የሚሰጥህን ልብስ ልበስ» በማለት እናት አጥብቃ ጠየቀችው ።

ሦስቱ ከቤት ወጥተው ሲሄዱ ለጥቂት ጊዜ በመስኮት በኩል ተመለከተቻቸው ። ከዚያም ቅዱስ ስዕሉ ወደተሰቀለበት ቦታ ዞር አለች ።

«ፈጣሪዬ ሆይ ፤ ቸርነትህ አይለያቸው ። እርዳቸው!» በማለት በለሆሳስ ተናገረች ።

## 26

ጊዜው በጣም ፈጣን በሆነ ሁኔታ የሚያልፍ ስለሆነ እናት ስለ ሜይ ዴይ በዓል መቃረብ ለማሰብ እንኳን ጊዜ አላገኘችም ። በዕለቱ ሥራ ሰውነቷ

ዝሎ እና ተዳክማ ሲመሽ አልጋዋ ላይ ጋደም ስትል ለልቧ አንጉል የሆነ መጥፎ ስሜት ተሰማት ፡—

«ምነው ቶሎ በደረሰ!» በማለት አሰበች ።

ጧት በማለዳ የፋብሪካው ሰዓት ይጮኻል ። ከዚያም ልጅዋ እና አንድሬይ ተቻኩለው ቁርሳቸውን ከበሉ በኋላ ፤ አያሌ የምትሠራውን ሥራዎች ለእርሷ ትተውላት ይሄዳሉ ። ቀኑን ሙሉ የወፍ ወጥመድ ውስጥ ገብታ እንደምትገኝ ድምቢጥ ወፍ ከወዲያ-ወዲህ በመሯሯጥ ፤ ምግብ በማዘጋጀት ፤ ለተለጣፊ ማስታወቂያቸው መጻፊያ የሚሆን ቀለም እና የወረቀት መለጠፍያ ሙጫ በማዘጋጀት ፤ ፈጽሞ የማታውቃቸው ሰዎች ድንገት በምሥጢር መጥተው ለፓቬል የምታስረክበውን የምሥጢር መልዕክት ከሰጧት በኋላ የእነርሱን መደነቅም ከእርሷ መደነቅ ጋር ተካፍለው ድንገት በምሥጢር ሹልክ ብለው የሚሄዱትን ሰዎች በመቀበል ጊዜውን ከወዲያ-ወዲህ ስትሯሯጥ ታሳልፋለች ።

በሜይ ዴይ የሰልፍ በዓል ላይ ወዝ-አደሮች በሙሉ እንዲገኙ የሚጠይቁት ተለጣፊ ወረቀቶች በየግድግዳዎቹ እና በፖሊስ ጣቢያ በራፎች ላይ ሳይቀር ይለጠፉ ጀመር ። በየቀኑም ፋብሪካው ውስጥ ተበታኝ ጋዜጦች እና ወረቀቶች ይገኙ ነበር ። የተለጠፉትን ማስታወቂያዎች ፖሊሶች ጧት-ጧት ከየሠራተኞቹ የሠፈራ ቤቶች ግድግዳዎች ላይ እያነሱ ሲቀድዱ እና ሲፈቀፍቁ ድርጊቱን ያወግዙ ነበር ። ምሳ ሰዓት ላይ ግን ሌላ ተበታኝ ወረቀትን ነፋስ እያንከወከወው አንድ ተጓዥ መንገደኛ እግር ሥር እንዲወድቅ ያደርገዋል ። ሰላዮች ከከተማ ወደዚሁ ቦታ የተላኩ ሲሆን ፤ በጎዳና አጠገብ ተሸጉጠው ወጪ-ወራጁን ወዝ-አደር በዓይነ-ቁራኛ ይከታተላሉ ። ይኸውም በምሳ ሰዓት ወዝ-አደሮቹ ከሥራ ቦታቸው በሚወጡበትና



ወደሥራቸው በሚመለሱበት ጊዜ ከመካከላቸው የትኞቹ የደስታ መልክ ይታይባቸው እንደነበረ ለመቃኘት ነው ። ሁኔታውን ለመቆጣጠር ፖሊስ ያልተቻለው በመሆኑ ማንም ቢሆን ተደስቶ ነበር ። ሽማግሎቹ ወዝ-አደሮች እንኳን በሁኔታው ተገርመው ይስቁ ነበር ።

«ጉድ እኮ ነው ፤ ምን እንደሚደረግ ታያላችሁ!» ይሉ ነበር ።

የቀረበውን ጥየቃ በከፍተኛ ስሜት ወዝ-አደሮች በየፊና-በየፊናቸው እየተሰበሳሰቡ ሲወያዩ ይታያሉ ። ከፍተኛ የስሜት መነሳሳት የሚታይ ሲሆን አዲስ ነገርን በውስጡ የያዘ በመሆኑ ከምንግዜውም የበለጠ የዚህ ዓመት የፀደዩ ወራት አስደሳች የሆነ ነበር ። አንዳንድ ሰዎች ከምንግዜውም የበለጠ ብስጩ የሆኑ ሲሆን ፤ አመጹን የሚያካሂዱትን ያወግዙ ነበር ። ሌሎቹ ደግሞ ግልጽ ሁኖ ባልታያቸው ሁኔታ ተስፋ አድርገው የነበሩ ሲሆን ፤ ጠንቃቃ ሁነውም ነበር ። ሌሎች ደግሞ ፤ እና እነዚህም ከሰዎቹ መካከል ብዛታቸው ጥቂት የሆኑት የጉዳዩ አነሳሺዎች እነርሱ መሆናቸውን በማወቅ ተደሳቾች ነበሩ ።

ፓቬል እና አንድሬይ እንቅልፍ አይተኙም ነበር ለማለት ይቻላል ። ግርጥት ብለው ፤ ዝለው እና ደክመው ሊነጋጋ ሲል ወደቤት ይመጣሉ ። ጫካ ውስጥ ስብሰባ እያካሄዱ የነበር መሆኑን እናት ታውቃለች ። ፈረሰኛ ፖሊሶች በምሽት የወዝ-አደሮቹን የሠፈራ ቦታ ዙርያውን ፓትሮል ያደርጉ ነበር ። ሰላዮችም አንዳንድ ወዝ-አደሮችን በየቦታው ይይዙ እና ይፈትሹ ነበር ። ሰዎች ተሰብስበው ካገኙ የተሰበሰቡትን ሰዎች ይበትኗቸዋል ። አልፎ-አልፎም ከመካከላቸው ሰዎችን ይይዙ ነበር ። ልጅዋ እና አንድሬይ ምን ጊዜም ቢሆን ሊያዙ በሚችሉበት አደጋ ላይ ሊገኙ የሚች

ሉ መሆናቸውን የተገነዘበች ስትሆን ፣ ለእነርሱ ይበጃ
ቸው ይሆናል ብላ በመገመት መያዛቸው እና መታሠ
ራቸውን ትመርጥ ነበር ።

በአንድ በአልታወቀ ምክንያት የሰዓት ተቆጣጣሪ
ው መገደል ምርመራ ክትትል ተድበስብሶ ቀረ ። ለሁ
ለት ቀናት የሠፈሩ ፖሊስ ምርምር ቀጥሎ ነበር ።
ጥቂት ሰዎች ተወስደው የምርመራ ጥያቄ ከቀረበላቸ
ው በኋላ ጉዳዩ ተዘጋ ።

ከፖሊሶች ጋር እንዳላት ጥሩ ግንኙነት ሁሉ ከማ
ንኛውም ሰው ጋር ጥሩ ግንኙነት ያላት ማሪያ ኮር
ሱኖቫ ፣ ምናልባትም ከፖሊሶች የሰማችውን ፣ በበኩሏም
ያላትን የግድያውን ምርመራ ሃሣብ ለእናት በሚከተለ
ው ሁኔታ ነገረቻት ፡—

«እንዴት አድርጎ ገዳዩ ሊገኝ ይችላል ይላሉ? ያን
ዕለት ጧት ኢሳይን መቶ ሰዎች አይተውት ይሆና
ል ። ነገር ግን ደግሞ ከመካከላቸው ዘጠና ያህሉ
ሰዎች ሊመቱት ይችሉ ነበር ። ለሰባት ዓመታት ሰዎ
ችን በሙሉ ይከታተል የነበረ ጆሮ-ጠቢ ነው...»
በማለት ተናገረች ።

ኽኾል ሊታወቅ በሚችል ሁኔታ ሰውነቱ እየመ
ነመነ ይሄድ ጀመር ። ፊቱ ሳሳ ። ጎረበጠ ። ሲሆኑ የዐይ
ኖቹ ሽፋሎችም ዐይኖቹን በገሚስ ሸፍነዋቸው አብጠ
ዋል ። ከአፍንጫዎቹ ቀዳዳዎች እስከ ከናፍሮቹ ዳርቻ
ዎች ድረስ በቀጭኑ የተዘረጉ መሥመሮች ተጋድመ
ውበታል ። አልባሌ ስለሆኑ ጉዳዮች ማውሳትን በይበል
ጥ የቀነሰ ሲሆን ፣ አንዳንድ ጊዜ በድንገት ስለ ምር
ምር እና ነፃነት ድል-አድራጊነት በሚያቀርባቸው አስ
ተሳሰቦች አዳማጮቹን ይማርክ ጀመር ።

የኢሳይን ግድያ የሚመለከተው ዜና ወዲያውኑ
ቀዘቀዘ ።

«እንኳንስ ለሕዝቦች ይቅርና እኛን ለመቃወሚያ



ለሚጠቀሙባቸው ሰዎች እንኳን ደንታ የላቸውም ።
ቅጥረኞቻቸውን በማጣታቸው ፈጽሞ የማይጸጸቱ ሲ
ሆኑ ሁልጊዜም የሚያስቡት ለሀብታቸው ብቻ ነው...»
በማለት አንድሬይ በመገረም ፈገግታ ፈገግ እያለ ተ
ናገረ ።

«አንድሬይ ፣ ለእንዲህ ያለው ንግግር እልባት ማበ
ጀት ይሻላል» በማለት ፓቬል ጠንከር አድርጎ ተና
ገረ ።

«ብስብሱ ገና ነካ ሲደረግ ፈራረሰ ። በቃ ፣ እንግዲ
ህ ምን ያስፈልጋል!» በማለት እናት ተናገረች ።

«ድርጊቱ ተገቢ ነው ። ግን ደግሞ የሚያዝናና ጉ
ዳይ አይደለም!» በማለት ኽኾል እየከፋው መለሰ ።

አዘውትሮ ይኽንን የሚናገር ሲሆን ፣ ይኽንኑ በሚ
ያወሳበት ጊዜ የሚሠነዝራቸው ቃላት ሰፊ የሆነ
የማጠቃለያ ሃሣብ ሁነው በመቀየር አቃጣይ እና መ
ራር ቃላትነት ወደመሆን ይለወጡ ነበር ።

...በመጨረሻም ፣ እስከአሁን ሲጠበቅ የነበረው ያ
ቀን ደረሰ — ሜይ ዴይ ። የወዝ-አደሮች ቀን ።

እንደወትሮው የፋብሪካ ሰዓት ጮኸ ። ምሽቱን በ
ሙሉ ዐይኗን ሳትከድን ያሳለፈችው እናት ፣ ካልጋዋ
ላይ ፍንጥር ብላ በመነሳት ቀደም ሲል ምሽቱ ላይ
አዘጋጅታው የነበረውን ሳሞቫር አቀጣጠለች ። እንደወ
ትሮው ልጅዋ እና አንድሬይ የሚተኙበትን ክፍል
ልታንኳኳ ነበር ። አሰብ አረገች እና ተወችው ። ከዚያ
ም ፣ ጥርሱን እንደታመመ ሰው አፏን በእጅዋ ይዛ
መስኮቱ አጠገብ ሂዳ ተቀመጠች ።

ፈዘዝ-ሰማያዊ በሆነው ሰማይ ላይ ፣ ፋብሪካው ፗ-ፗ!
ፗ-ፗ! እያለ በሚተፋው ተን ተደናግጠው በብዛት
ተሰባስበው እንደሚበሩ ወፎች ሁሉ ፣ ቢጫ እና ነጭ
ቀለም ያበጀ ደመና በሰማዩ ላይ ያንዣብባል ። እናት
በሕልም ሃሣብ ተውጣ ደመናውን ታስተውላለች ። እራ

ቧን የከበዳት ስትሆን ፤ ዐይኖቿ ደግሞ ዕንቅልፍ ሳይዞርባቸው በማለፉ ደርቀው ይቆጠቁጧታል ። አለወትሮዋ ድንገተኛ በሆነ መረጋጋት ተመልታለች ። ልቧ ያለማቋረጥ በትክክል ይመታል ። አዕምሮዋ በሃሣብ የተዋጠውም አልባሌ በሆኑ አስተሳሰቦች ነው ። እንዲህም ስትል በአዕምሮዋ አሰላሰለች ፡ — «ሳሞቫሩን የጣድኩት ተቻኩዬ ነው ። ውሀው ከውስጡ ያልቃል… ሁለቱም በድካም ደቀዋል ። እስኪ የዛሬዋን ጧት እንኳን ትንሽ እንቅልፍ ያግኙ…»

የማለዳ ፀሐይ የምትፈነጥቀው ጨረር የደስ-ደስ ተጎናጽፎ በመስኮቱ ውስጥ ዘልቆ ታየ ። እናት እጅዋን ወደመስኮቱ ዘረጋች ። ብሩኅ ሙቀት በእጅዋ ላይ አርፎ እጅዋን ሲያሞቀው በሃሣብ ተውጣ ፈገግ እያለች እጅና-እጅዋን አገናኝታ አሻሻቻቸው ። በመጨረሻም ከተቀመጠችበት ተነሳችና በፀጥታ ተመልታ ማስተላለፊያ ቧንቧውን ከሳሞቫሩ ላይ ነቀለችው ። ከዚያም ከተጣጠበች በኋላ በትዕምርተ-መስቀል አማትባ ስሜት በተመላው ሁኔታ በጥሞና ተጠሙና በለሆሳስ ከንፈሮቿን እያንቃነቀች ፀሎቷን መፀለይ ቀጠለች ። ፊቷ ብሩኅ ሆኖ በራ ። የቀኝ ዐይኗ ቅንድብ ይርገበገብ ጀመር…

ሁለተኛው የፋብሪካ ሰዓት ጩኸቱ እንደ መጀመርያው ጉልህ እና ግርማ-ሞገስ ያለው አልነበረም ። ወፈር ባለና በረጠበ ድምፁ በመጠኑ የመንቀጥቀጥ ሁኔታ ይሰማበት ነበር ። ከዘወትሩ ይልቅ ረዘም ላለ ጊዜ የሚጮህ መስሎ ለእናት ተሰማት ።

የኾኾል ጉልህ እና ጥልቀት ያለው ድምፅ ከሌላኛው ክፍል ተሰማ ፡ —

«ፓቬል ፤ ትሰማለህ?» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

ከሁለቱ የአንደኛቸው ባዶ እግር ወለሉ ላይ ሲያርፍ ተሰማ ። ከመካከላቸው አንዱ በረዥሙ አዛጋ…



«ሳሞቫሩ ፈልቷል» በማለት እናት በጉልህ ድምፅ ተናገረች ።

«ተነስተናል!» በማለት ፓቬል በደስታ አነጋገር መለሰ ።

«ፀሐይቱ እየወጣች ነች! በሰማዩ ላይም ደመና አንዣቦበታል ። ለዛሬው ቀን ደመናውም ባይኖር እኛ እንበቃለን…» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

ከእንቅልፉ ገና በመነሳቱ ጭርምትምት እና ድቁስቁስ ብሎ ፤ ነገር ግን ደግሞ በደስታ ስሜት ተመልቶ ወደ ማዕድ ክፍሉ ዘለቀ ።

«እናቴ ፤ እንደምን አደሩ! ደህና ተኙ?» በማለት ልጅዋ እናትን ጠየቀ ።

እናት ወደ ኾኾል ቀረብ በማለት ተጠጋች ።

«አንድርዬ ፤ ሰልፉ ላይ እንዳትለየው ጎን-ጎኑ ሁነህ ተሰለፍ» አለችው ።

«አብሬው እሆናለሁኝ ። እናቴ ፤ አብረን እስካለን ድረስ ሰልፋችንም በአንድነት ጎን-ለጎን ነው ። በዚህ ይተማመኑ» በማለት ቀስ ብሎ መለሰላት ።

«እናንተ ሁለታችሁ የምትመሣጠሩት ምንድነው?» በማለት ፓቬል ጠየቀ ።

«ምንም አዲስ ነገር የለም ፤ ፓሻ» በማለት እናት መለሰች ።

«ዛሬ ልጃገረዶቹ ስለሚያጅቡኝ ማጅራቴን እንድተጣጠብ ነው የሚነግሩኝ!» በማለት ኾኾል ወደ መጣቢያው ለመተጣጠብ እየሄደ መለሰ ።

«ተነሱ እናንት ወዝ-አደሮች!

ተነሱ እናንት ጎስቋሎች!» እያለ ፓቬል በቀስታ ማዜም ጀመረ ።

ሰዓቱ እየገፋ ሲሄድ አየር-ንብረቱም እየተሻሻለ መሄድ የጀመረ ሲሆን ፤ ደመናውም በነፋስ ተበተነ ። እናት ቁርስ በምታቀርብበት ጊዜ ጉዳዩ ሁሉ እንዴት

አስገራሚ መሆኑን እያሰላሰለች በመደነቅ ራሷን ትነቀንቅ ጀመር ፡ — ረፋዱ ላይ ምን እንደሚጠብቃቸው ባያውቁትም በዛሬው ጧት ሁላቸውም ይቀላለዳሉ ። ይሳሳቃሉ ። እርሷም የተረጋጋ የመንፈስ ሁናቴ የሚታይባት ከመሆኑም በስተቀር ደስ-ደስ ብሏት ነበር ።

ጊዜው ፈጠን ብሎ እንዲያልፍላቸው ምግባቸውን ቀስ እያሉ ያጣጥሙ ጀመር ። ፓቬል እንደወትሮው ሱካሩን በጥንቃቄ ቀስ ብሎ ሻዩ ውስጥ በመጨመር በዝግታ ካማሳለ በኋላ ሁል ጊዜም በሚያፈቅረው የዳቦው ቅርፊት ላይም ጨው ነሰነሰ ። ኾኾል ረዥም ከመሆኑ የተነሳ ምንም ጊዜ ቢሆን ሲቀመጥ ተመችቶት አይቀመጥም ። እግሮቹን በጠረጴዛው ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ባለመመቸት እያንቀራጠጠ የመስኮቱን መስተዋት ጠልቀው በመግባት በግድግዳው እና በጣራው ላይ የሚያንፀባርቁትን የፀሐይ ጨረሮች ያስተውላል

«የአሥር አመት ልጅ በነበርኩበት ጊዜ ፀሀይን በብርጭቆ ውስጥ አጥምጄ ለመያዝ እምችል መስሎኝ ነበር» በማለት ኾኾል ተናገረ ። ንግግሩን በመቀጠልም ፡ —

«ስለዚህም ብርጭቆየን ያዝኩኝና ተደብቄ የፀሀይ ጨረር ወዳለበት ቦታ ስሮጥ ከግድግዳ ጋር ተጋጭቼ ወደቅሁኝ ። የብርጭቆው ስብርባሪም እጄን ቀረጠኝ! ከዚህም በስተቀር ክፉኛ ተደበደብኩኝ ። ከተደበደብኩኝ በኋላ ወደ አትክልት ቦታ ዞር ብዬ ሄድኩኝ ። እዚያም ሁኜ ውሀ ያዘለ ቦታ ላይ የፀሐይ መልክ ተንፀባርቆ አየሁኝ ።ፀሐይዋን በእግሬ ረግጬ እይዛለሁኝ ብዬ ውሀውን ስረግጠው ውሀው ውስጥ በመንቦራጨቅ ልብሴ በጭቃና በውሀ ተለወሰ ። ወላጆቼ እንደገና ደበደቡኝ ። ስለዚህም ምላሴን ፀሀይዋ ላይ በስ



ድብ አወጣሁና ፡ — 'ኧረግ! አንቺ ቀይማ ሰይጣን! እኔ ፣ እንደሆን አላመመኝ! አ-ይ! አላመመኝ!' እያልኩኝ ፀሀይዋን ሰደብኳት ። በዚህ ሁኔታ ንዴቴ በረድ አለልኝ» በማለት ተናገረ ።

«ለምንድነው ቀይማ ብለህ የቀጸልካት?» በማለት ፓቬል እየሳቀ ጠየቀው ።

«እኛ ከምንኖርበት ቤት ባሻገር አንድ ደም የመሰለ ትልቅ ፊት ያለው ቀጥቃጭ ይኖር ነበር ። ጢሙም ቀይ ነበር ። በጣም ደግ እና ገር ሰው ነበር ። ታዲያ ፀሐይዋም ልክ እርሱን መስላ ታየችኝ...» በማለት መለሰ ።

እናት ትዕግሥቷ ሲያልቅባት የሚከተለውን ተናገረች ፡ —

«ይልቁንስ ዛሬ የምትሰለፉት እንዴት እንደሆነ ለምን አትወያዩም?» አለች ።

«ቀደም ሲል የተወሰነ ነገርን መልሶ መላልሶ ማውሳት ጉዳዮችን ያምታታቸዋል» በማለት ኾኾል ረጋ ብሎ ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ —

«እናቴ ፤ ድንገት እኛን ሁላችንንም ይዘው ካሡሩን ፤ እርስዎ ምን-ምን ማድረግ እንደሚገባዎት ኒኮላይ ኢቫኖቪች ይመጣና ይነግርዎታል» አላት ።

«እሺ ፤ ይሁን» በማለት እናት እየተነፈሰች መለሰች ።

«ለሽርሽር ወጣ ብንል ምን ይመስልሃል?» በማለት ፓቬል በሃሣብ ተውጦ ኾኾልን ጠየቀው ።

«አሁን ለጊዜው እቤት መቆየቱ የተሻለ ነው» በማለት አንድሬይ መለሰ ።

«ፖሊሶቹን ቀደም ብለህ ጎሽ እጃችን ሊገባ ነው እያሰኘህ በማጓጓት ለምን እንዲቋምጡ ታደርጋቸዋለህ? እነርሱ እንደሆን ባታጓጓቸውም እንዲሁ ያውቁሀል!» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

ፌዎዶር ማዚን እየሮጠ መጣ ። ፊቱ በደስታ ተመልቶ ብሩኅ ሁኖአል ። ጉንጮቹ ቀልተዋል ። የእርሱ የደስታ ስሜት የእነርሱን ምን ሊል ነው የሚል የጥድፍያ ጉጉት በጥሶ ተናገረ ፡ —

«ድርጊቱ ተጀምሮአል! ሕዝበ-አዳም እየተመመ ነው ። ወደ አደባባይ ሕዝቡ እየወጣ ነው ። ሁሉም እንደምሣር አፍጥጦአል ። ቬሶቭሺኮቭ እና ቫሲያ ጉሴቭ እንደዚሁም ሳሞኢሎቭ ፋብሪካው በራፍ ላይ ቁመው ንግግር ያደርጋሉ ። ብዙዎቹ ወዝ-አደሮች ወደየቤታቸው ተመልሰዋል ። ተነሱ እንጂ! ጊዜው እኮ ደርሶአል! አራት ሰዓት ሆነ እኮ!» አለ ።

«መጣሁኝ» በማለት ፓቬል ቁርጥ ባለ ቃል ተናገረ ።

«ታያለህ ፤ ከምሳ በኋላ የፋብሪካው ወዝ-አደሮች በሙሉ ሥራቸውን ያቆማሉ!» በማለት መንገዱን በሩጫ እየሄደ ተናገረ ።

«ነፋስ ላይ እንደሚበራ ሻማ ፌዎዶር ማዚን እየተቃጠለ በመቅለጥ ላይ ነው» በማለት እናት ተናገረች ። ከዚያም ልብሷን ለመቀየር ወደ ማዕድ ክፍል ሄደች ።

«እናቴ ፤ የት ሊሄዱ ነው?» በማለት ኾኾል ጠየቃት ።

«ከእናንተ ጋር ነዋ!» በማለት መለሰችለት ።

አንድሬይ ሪዙን እያሻሸ ፓቬልን ይመለከት ጀመር ። ፓቬልም ፀጉሩን በጣቶቹ አከክ-አከካ እያደረገ የሚከተለውን ተናገራት ፡ —

«እናት ፤ እንዳትሄጂ ለማድረግ አንዳችም ቃል አልተነፍስም ። አንቺም እኔን ምንም ነገር አትናገሪኝ! በዚህ እንስማማለን?» አላት ።

«እሺ ። እሺ ። ብቻ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋራ ይሁን!» በማለት በዝግታ ተናገረች ።



27

ውጪ እንደወጣች የሕዝቡ ጉርምርምታ አየሩን መልቶት በመስማቷ ፤ በየበራፋቸው እና በየመስኮቶቻቸው የቆሙት ሰዎች ልጅዋን እና አንድሬይን በዐይኖቻቸው ሲሸኟቸው ስትመለከት ፤ ሁሉም ነገር በዐይኗ ላይ አረንጓዴ እና ግራጫ የሚመስል ሁኖ ታየ ።

ሰዎቹ ከልጅዋ እና ከአንድሬይ ጋር ሰላምታ የሚለዋወጡ ሲሆኑ ፤ በዛሬው ቀን የሚናገሩት ቃል በቁም ነገር የተመላ ነው ። ልዩ ልዩ ዓይነት አስተያየቶች ሲሰነዘሩ ሰማች ፡ —

«እነዚያውላችሁ መሪዎቹ...»

«መሪዎቹ እነማን እንደሆኑ እኮ አናውቅም...»

«ጎጂ የሆነ ሃሣብ ማቅረቤ አይደለም!..»

አንዱ ደግሞ ከምድረ-ግቢው ውስጥ የሚከተለውን ኀላ ባለ ድምፅ አሰማ ፡ —

«ፖሊስ ይይዛቸዋል ። ከዚያ በኋላም አለቀላቸው ማለት ነው!..

«ካሁን በፊትም አንዴ ተይዘው ታሥረው ነበር!»

አንዲት ሴት ከመስኮቷ ውስጥ ሁና ያሰማችው ጥይታ መንገዱ ላይ ተሰማ ፡ —

«ምን በማድረግ ላይ እንደሆንህ ዞር ብለህ ብታስተውል ይሻላል! ትዳር-የሌለህ ሌጣ ነህ እንዴ?»

በሥራው ላይ ሳለ አካሉ ሽባ ሁኖ ስለተሸመደመደ ፋብሪካው በየወሩ ጡረታ የሚከፍለው ዞሲሞቭ የተሰኘው እግረ-ቆራጣ ቤት በኩል ሲያልፉ ጭንቅላቱን በመስኮት በኩል አሾልቆ በማውጣት የሚከተለውን በጩኸት ድምፅ ተናገረ ፡ —

«አንተ ፓቬል! ቆይ ጠብቅ ፥ ዋጋህን ታገኛታለህ ፤ ቆይ ግዴለም ድራሽህን ያጠፉታል ፥ ቆይ ጠብቅ!» አለው ።

እናት ደንገጥ ብላ አለችበት እንደቆመች ቀረች ። ሁለንተናዋ በቁጣ ተዋጠ ። ያንን ፊቱ በፈንጣጣ የተበሳሳ ሽባ አተኩራ ተመለከተችው ። እርሱም እየተሳደበ ጭንቅላቱን ወደውስጥ መልሶ አስገባ ። ከዚያም ልጅዋን እስክትደርስበት ድረስ እርምጃዋን ጨመር አድርጋ በፍጥነት በመራመድ ዘግይታ ወደኋላ ላለመቅረት የልጅዋን የዕግር ኮቴ በመከተል ኋላ-ኋላው ትራመድ ጀመር ።

ፓቬል እና አንድሬይ የሚፈጸመውን አንዳችም ነገር የሚያስተውሉ ካለመምሰላቸውም በስተቀር ፣ በጉዞ ላይ ሳሉ የሚሠነዘሩትን አስተያየቶችም የሚያዳምጡ አይመስሉም ነበር ። ረጋ ብለውና ሳይጣደፉ ጉዞአቸውን ይቀጥሉ ነበር ። የሰከነ ሰው በመሆኑና የአኗኗሩ ሁኔታም ተዘባናኝ ባለመሆኑ የሁሉንም ሰው አክብሮት ያገኘው ሚሮኖቭ የተባለ ሰው ጋር ተገናኙና ቆሙ ።

«ዳኒሎ ኢቫኖቪች እርስዎም በዛሬው ቀን ሥራ ላለመግባት ወስነዋል ማለት ነዋ?» በማለት ፓቬል ጠየቀ ።

«ባለቤቴ ልጅ ለመውለድ ምጥ ላይ ነች ። ከዚህም በስተቀር ይኸንን የመሰለው ቀን ቅብጥብጥ እንድትሆን ያደርግሀል ።» በማለት ተናገረ ። ጓዶቹን ትክ ብሎ እየተመለከተ ፣ የሚከተለውን ጥያቄ በቀስታ አነጋገር አቀረበላቸው ፡ — «በዛሬው ቀን እናንተ በዲሬክተሩ ላይ ጉድ ልታፈሉበት ነው ይባላል ። መስኮቶችን ልትሠባብሩ ነው ይባላል ። ዕውን?» አለ ።

«አልሰከርንም!» በማለት ፓቬል በአንክሮ መለሰ ።

«አርማችንን አንግበን መዝሙራችንን እየዘመርን በጎዳናው በሰልፍ ለማለፍ ነው የተነሳነው» በማለት ኾኾል መልስ ሰጠ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ — «መዝሙሮቻችንም ይኸንን የመሳሰሉ ናቸው ። ያድምጧቸው ። የዕምነታችን መግለጫዎች ናቸው» በማለት ተናገረ ።

«ዕምነታችሁን በሚገባ አውቃለሁኝ» በማለት ሚሮኖቭ በሃሣብ ተውጦ ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ — «ጋዜጦቻችሁን አነብባለሁኝ ። ወይ ጉድ ፣ ፔላጌያ ኒሎቭና» በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ እና ፈገግ በማለት በአስተዋይ ሰው ዐይኖች አመለካከት መልከት እያደረጋት ፡ — «እርስዎም የአመጹ ተካፋይ ሁነዋል ማለት ነዋ?» በማለት ጠየቃት ።

«ከመሞቴ በፊት በሕይወቴ አንድ ጊዜም ቢሆን ከፍትህ ጎን ቆሜ መሰለፍ አለብኝ!» በማለት ለሚሮኖቭ መለሰችለት ።

«ሕገ-ወጥ ናቸው የሚባሉትን ተበታኝ ወረቀቶች ወደ ፋብሪካው ውስጥ የሚያስገቡት እርስዎ ነዎት የሚባለው ትክክል ሳይሆን አይቀርም!» በማለት ተናገረ።

«ማነው እንዲህ የሚለው?» በማለት ፓቬል ጠየቀ ።

«እ-ሀ-ሀ! እንደው መቸም ጉዳዩ እንዲህ ነው እያሉ ሰዎች ያወራሉ ። ይሁን ብቻ በሉ ፤ ደህና ሁኑ ። ራሳችሁን ጠንቀቅ ብላችሁ ጠብቁ» በማለት ሚሮኖቭ ተናግሮ ሄደ ።

እናት ምንም ሳትናገር ፈገግ አለች ። ስለእርሷ ይህንን የመሰለ ወሬ የሚወራ መሆኑን በመስማቷ ደስ ብሏት ነበር ።

«እናቴ ፣ ገና እሥር ቤት መግባት ይጠብቅሻል ማለት ነው» በማለት ፓቬል እየሳቀ ተናገረ ።

የፀደዩን ወራት ንፁሕ አየር እያማሟቀች ፀሀይቱ ከፍ-ከፍ እያለች በሰማዩ ላይ ትወጣ ጀመር ። የደመናዎቹ እንቅስቃሴ ዝግ እያለ በመጓዝ እንደ ጥጥ ባዘቶ በስሱ ተባዝተው የብርሃን ነጸብራቅ ጠልቆ ያልፋቸው ጀመር ። በዘግታ ወደ ጎዳናዎቹ

እና ቤቶቹ መድረኮች ዝቅ ብለው በመውረድ ፣ በሰዎቹ ላይ በማጥላት ፣ የሠፈራ ቦታውንም በመጥረግ እና ከየቤቶቹ ላይም አቧራና ቆሻሻዎችን በማጽዳት ፣ ከሰዎች ፊቶች ላይም የመሰላቸው ገጽታዎቻቸውን ይገፍፉላቸው ጀመር ። ሁሉም ነገር ይበልጥ አስደሳች ሁኖ ይታይ ጀመር ። ከሩቅ የሚሰሙት ማሺኖች ድምፅ እስኪያፍኑት ድረስ የሰዎች ሆይ-ሆይታ እየጎላ ይሰማ ጀመር ።

አሁንም እንደገና ከየመስኮቶቹ እና ምድረ ግቢዎች ውስጥ የሚሰነዘሩት ቃላት — የብልግና እና አስቀጪ የሆኑ ቃላት ፣ የብልኅነት እና አስደሳች የሆኑ ቃላት ከእናት ጆሮ ጥልቅ ይሉ ጀመር ። አሁን ግን ፣ በዚህ በዛሬው አስገራሚ እና በልዩ ቀለማት ያሸበረቀ ቀን ለሚቀርበው አስተያየት ሁሉ አፀፋውን በመመለስ ፣ በማብራራት እና በማመስገን ንቁ ተሳታፊ ለመሆን ትሻለች ።

ብዛታቸው ወደመቶ የሚጠጉ ሰዎች ከተሰበሰቡባት ከአንዲት ጠበብ ያለች መንገድ ላይ የቬሶቭሺኮቭ ድምጽ ፡ —

«ከቅባት-እህል ላይ ቅባት እንደሚጨመቅ ሁሉ ከእኛ ላይም ደማችንን እስኪንጠፈጠፍ ይጨምቁታል» በማለት የተናገረው ጉትት የሆነ አነጋገሩ ከሰዎቹ ጭንቃላት በላይ አልፎ ተሰማ ።

«ልክ ነው!» በማለት ብዙ የሰዎች ድምፆች በአንድ ጊዜ አስተጋቡ ።

«ልጁ ጥረት እያደረገ ነው ። ሂጂ ልርዳው!» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

ቡሽ ውስጥ የቡሽ መክፈቻ ስተተት ብሎ እንደሚገባ ሁሉ ፤ ፓቬል ኾኾልን እንዳይሄድ ረገኾም እግሮቹን ሳብ-ሳብ እያደረገ ከማገዱ በፊት ስተት ብሎ ገባ ። ከዚያም ጉልህ በሆነው ድምፁ ፡ —



«ጓዶች! በዓለም ላይ የተለያዩ ሕዝቦች ይኖራሉ ይባላል ። አይሁዶች እና ጀርመኖች ፣ እንግሊዞች እና ታታሮች ። እኔ ግን በዚህ አባባል አላምንም! ሁለት ዓይነት ሕዝቦች ብቻ ይኖራሉ ። እነዚህ ሁለት ዓይነት ሕዝቦችም ምንም ቢሆን ሊጣጣሙ የማይችሉ ሕዝቦች ሲሆኑ እነርሱም ድሀ እና ሐብታም የሆኑ ሕዝቦች ናቸው! ሕዝቦች አለባበሳቸው የተለያየ ነው ። ቋንቋቸውም የተለያየ ነው ። ነገር ግን ሀብታም የሆኑት ፈረንሳውያን ፣ ጀርመናውያን እና እንግሊዛውያን ሠርቶ-አደር ሕዝቦችን እንደምን እንደሚበድሉ ብንመለከት ለእኛ ለሠርቶ-አደር ሕዝቦች ሁላቸውም ቢሆኑ ቀጣፊ ወስላቶች ናቸው ። በጉሮሮአቸው አጥንት ይቀርቀር!»

ከተሰበሰቡት መሃከል አንዱ ሳቀ ።

«በሌላ በኩል ደግሞ ፣ ረጋ ባለ ሁኔታ አስተውለን ብናየው የፈረንሳይ ሆነ የታታር እና የቱርክ ሠርቶ-አደሮች ቢሆኑ ፣ ሁሉም እኛ የሩስያ ወዝ-አደሮች እንደምንኖረው ዓይነት የውሻ ኑሮ የሚኖሩ ናቸው!» በማለት ተናገረ ።

ብዙ ሰዎች አንገታቸውን እያሰገጉ እና ተረከዛቸውን ከፍ እያደረጉ ምንም ነገር ሳይናገሩ ንግግሩን ለማዳመጥ ይጠጉ ጀመር ።

የአንድሬይ ድምፅ ይበልጥ ከፍ እያለ ይሰማ ጀመር ።

«ይኸንን ግልጥ ያለ ዕውነት በሌላው ሀገር የሚገኙት ወዝ-አዶሮች የተገነዘቡት ሲሆን ፣ በዛሬው ቀንም ፣ ማለትም በዛሬው በሜይ ዴይ...» ብሎ ሳይጨርስ ፣

«ፖሊሶች መጡ!» በማለት ከተሰበሰቡት አንዱ ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰማ ።

ፈረሶች ላይ የተቀመጡ አራት ፖሊሶች ፈረሶቻቸውን እየቋጉ ሰዎቹ ወደተሰበሰቡበት የመንገዱ ማቋረጫ ላይ ሂደው ፡ —

«ሂዱ ከዚህ! ተበታተኑ!» እያሉ ይጮኹ ጀመር ።

ሰዎቹም ፈራ በማለት ያለፍላጎታቸው ወደኋላ ያፈገፍጉ ጀመር ። ከመካከላቸው ጥቂቶቹም አቅራቢያቸው ባሉት አጥሮች ላይ ተንጠላጠሉ ።

«አሳማዎችን ፈረስ ላይ ጭነዋቸው ይኸው ጀግና ይመስል ያጓራሉ!» በማለት አንዱ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ።

ኾኾል ቀደም ሲል ከነበረበት መሃል መንገድ ላይ አልተንቃነቀም ። ሁለቱ ፈረሶች ራሳቸውን እየወዘወዙ ወደእርሱ አመሩ ። ወደጎን ቆም አለ ። በዚያን ጊዜም እናት እጁን ይዛ ጎተተችው ።

«ፓቬል አጠገብ እሆናለሁኝ ብለህ ቃል ገብተህ ነበር ። አሁን ግን ይኸው ራስህ ከውዝግብ ውስጥ ልትገባ ነው!» በማለት ተናገረችው ።

«አጥፍቻለሁኝ ፣ ይቅርታ እጠይቃለሁኝ » በማለት መለሰ ።

ደስታ እና ሀዘን የተቀላቀለበት ስሜት እየተመላለሰ የሚሰማት በመሆኑ የድካምና የቅሬታ ሁኔታ ፔላጊያን ይሰማት ጀመር ። የምሳ ሰዓት መድረሱን የሚያበሥረው የፋብሪካ ሰዓት ምነው ቶሎ በጮኸ ብላ ተመኘች ።

ቤተ-ክርስቲያኑ አጠገብ ወዳለው አደባባይ ሄዱ ። ቤተ-ክርስቲያኑ ቅጥር-ግቢ ውስጥ ይንቻቹ የነበሩ አምስት መቶ ያህል ወጣቶች እና ሕፃናት ይገኙ ነበር ። የተሰበሰበው ሕዝብ ወደፊት እና ወደ ኋላ ይንቀሳቀስ ነበር ። የአንዳች ነገርን መድረስ በትዕግሥት ዕጦት በመጠባበቅ ሁኔታ ሰዎች ራሳቸውን ስግግ በማድረግ በስተሩቅ እያማተሩ ይመለከታሉ ። አካባቢው በስሜት ተውጦአል ። አንዳንድ ሰዎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው የማያውቁ ይመስላሉ ። ሌሎቹ ደግሞ



የቆራጥነት ሁኔታ ይታይባቸዋል ። ሴቶች ያቀርቡት ለነበረው ሃሣብ ወንዶቹ የመቃወም ድምፅ እያሰሙ ዞር ይላሉ ። አንዳንድ ጊዜ ስድብ የተመላባቸው ቃላት በዝቅተኛ ድምፅ ይሰማሉ ። የተሰበሰበው ሕዝብ መካከል የመጣላት ሁኔታ ይታያል ።

«ሚቴኝካ ፣ ነግሬሃለሁኝ ይቅርብህ ። ኧረ ተው በኋላ ታዝናለህ!» የሚል የአንዲት ሴት ድምፅ ተሰማ ።

«ተይኝ ብዬሻለሁኝ!» የሚል ድምፅ መልስ ሰጣት ።

ግርማ-ሞገስ ያለው የሲዞቭ ድምፅ ረጋ ባለ ሁኔታ የሚከተለውን ሲናገር ተሰማ ፡ —

«የለም አይሆንም ፣ ወጣቶቹን ጥለን መሄድ የለብንም! ከእኛ ይበልጥ የሚያስተውሉና ብርታትም ያላቸው ናቸው! ለረግረጋማው መሬት እንዲከፈል ተወስኖ የነበረውን ኮፔክ በመቃወም የተቋቋመው ማን ሆነና ነው? እነርሱ ነበሩ ። ይኸንን መዘንጋት የለብንም ። በዚህ ምክንያትም ወደእሥር ቤት የተወረወሩ እነርሱ ሲሆኑ ፣ በዚህም ምክንያት ጠቀሜታን ለሁሉም ሊያስገኙ ችለዋል!..» በማለት ተናገረ ።

የፋብሪካው ሰዓት በመጮህ የሰዎቹን ድምፅ ዋጠው ። የተሰበሰበው ሕዝብ መነቃነቅ ጀመረ ። ተቀምጠው የነበሩት ተነሱ ። ለአንድ ለተወሰነ ጊዜ ፣ ሁሉም ዝም አለ ። በተጠንቀቅ የመታየት ሁኔታም ይታይባቸዋል ። ከተሰበሰቡት መካከል ፣ የአንዳንዶቹ መልክ በመቅላት ደም መስሎአል ።

የፓቬል ጠንካራና ጉልህ ድምፅ «ጓዶች!» የሚለውን ቃል አሰማ ። የእናት ዐይኖች በትኩስ እንባ ግጥም ብለው ተመልተው የነበረ ሲሆን የብርታት ስሜትም ተሰምቷታል ። ማግኔት ላይ የብረት ቁርጥራጮች ተደራርበው ጥግትግት እንደሚሉ ሁሉ ሰዎችም ተጠጋግተው ቆመው ከነበረበት ቦታ ፈጠን ብላ በመራመድ እናት ከልጅዋ ጎን ሂዳ ቆመች ።

በኩራት እና በጉብዝና የተመሉ ብሩኅ ዐይኖቹን ለማስተዋል እናት ልጅዋን ፊት-ፊቱን ትመለከት ጀመር ።

«ጓዶች! በዛሬው ቀን ማንነታችንን በይፋ ለመግለጽና እንደዚሁም የምርምር ፣ የፍትህ እና የነፃነት አርማችንን ለማንሳት ወስነናል!» በማለት ፓቬል ተናገረ ።

ረዥም ነጭ ሰንደቅ እየተምዘገዘገ በአየሩ ላይ ከፍ ሲል የታየ ሲሆን ይኸው ሰንደቅ እንደገና ተመልሶም የተሰበሰበውን ሕዝብ መሀል-ለመሀል በመሰንጠቅ ሕዝቡ ውስጥ ሰምጦ በመግባት በሕዝቡ ተሸፈነ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ፊታቸውን ወደላይ ቀና-ቀና አድርገው ከነበሩት ሰዎች አሻቅቦ ትልቅ ቀይ ወፍ የሚመስለው የወዝ-አደሮች አርማ በዓየሩ ላይ ተንሳፈፈ ።

ፓቬል ክንዱን ከፍ አድርጎ ሲያወዛውዝ አርማውም ይውለበለብ ጀመር ። አርማው የሚገኝበትን ለስላሳ ነጭ ሰንደቅ ብዙ ሰዎች በእጃቸው መዳሰስ የጀመሩ ሲሆን ከዳሳሺዎቹ መካከልም እናት አንዷ ነበረች ።

«የወዝ-አደሩ መደብ ለዘለዓለም ይኑር!» በማለት በጩኸት ድምፅ ፓቬል ተናገረ ።

ብዙ መቶ ድምፆች ይኸንኑ ቃል በመድገም ድምፃቸውን አጉልተው አሰሙ ።

«ጓዶች! የእስተሳሰባችን ምንጭ የሆነው ሶሻል ዴሞክራቲክ የወዛደር ፓርቲ ለዘለዓለም ይኑር!» በማለት ፓቬል ተናገረ ።

የተሰበሰበው ሕዝብ በስሜት ተሟሟቀ ። የአርማውን ታላቅነት የተገነዘቡ ሁሉ ወደአርማው ይጠጉ ጀመር ። ማዚን ፣ ሳሞይሎቭ እና ወንድማማቾቹ ጉሴቮች ወደ ፓቬል ዘንድ ተጠጉ ። ኒኮላይ የተገጠገጠውን ሕዝብ እያተራመሰ ወደ ፓቬል አንገቱን ዝቅ አድርጎ የተጠጋ ሲሆን ፣ እናትንም ካሁን ቀደም አይታቸው የማታውቃቸው እና ብሩኅ ዐይኖች ያሉዋቸው ወጣቶች ይገፏት ጀመር ።



«የዓለም ወዝ-አደሮች ለዘለአለም ይኑሩ!» በማለት ፓቬል ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰማ ።

ደስታ እና ብርታት የተቀላቀለው የብዙ ሺህ ሰዎች ድምፅ መፈክሩን በታላቅ የስሜት ድምፅ መልሶ አስተጋባው ።

እናት የኒኮላይን እና የአንድን ሌላ ሰው እጅ ጨብጣ ያዘች ። ድምፅ አሰምታ የማታለቅስ ብትሆንም ፣ ከዐይኖቿ እንባ ይፈስ ነበር ። ጉልበቶቿ ይንቀጠቀጡ ጀመር ። ከናፍሮቿ እየተንቀጠቀጡም የሚከተለውን በዝግታ ድምፅ ተናገረች ፡—

«የኔ ውዶች!...»

በፈንጣጣ የተበላው የኒኮላይ ፊት ከፍ ያለ ፈገግታ ታየበት ። አርማ እየተመለከተ አንድ ሰው በዝቅተኛ ድምፅ በመናገር እጁን ወደ አርማው ዘረጋ ። ድንገትም በእናት አንገት ላይ እጁን ጣል አደረገና እየሳቀ ሳም አደረጋት ።

«ጓዶች!» አለ ኾኾል ፣ ወዛማ ድምፁ ከተሰበሰቡት ሰዎች ድምፅ በላይ ከፍ ብሎ ። ከዚያም ፡ — «በአዲስ አምላክ ስም ዘመቻ ዘምተናል ። እርሱም የብርሃን እና የምርምር ፣ የበጎነት እና የዕውነት አዲስ አምላክ ነው! ግባችን ገና ሩቅ ነው! ራሳችን ላይ የምንደፋው የእሾህ አክሊል ግን በቅርባችን ይገኛል! ዕውነት ድል አድራጊ መሆኗን የሚጠራጠር ቢኖር ፣ ለዚች ዕውነት ሕይወቱን አሳልፎ ለመስጠት ማንም ቢሆን ብርታተ-ቢስ ሁኖ ቢገኝ ፣ የገዛ ራሱን ኃይል የሚጠራጠር እና ሥቃይን ለመቀበልም የሚፈራ ከመካከላችን አንድም ቢኖር ፣ ወደኋላ ይቅር! እኛ የምንፈልጋቸው በድል-አድራጊነታችን የሚያምኑትን ብቻ ነው!

የእኛን ዓላማ ለማስተዋል የሚሳናቸው በሚደርስባቸው የሚያዝኑ ስለሚሆኑ ከእኛ ጋር መሰለፍ የለባቸውም! ጓዶች ፣ ተሰበሳሰቡ ! የነፃ ሕዝቦች በዓል ለዘለዓለም ይኑር! ሜይ ዴይ ለዘለዓለም ይኑር!» በማለት ተናገረ ።

የተሰበሰበው ሕዝብ ብዛቱ ጨመረ ። ሰፊ በሆነ ብሩኅ ፈገግታዋ ፈገግ ያለችው ፀሐይ የምታበራብትን አርማ ከፍ አድርጎ በመያዝ ፓቬል ወደፊት ቀደመ...

ፌዎዶር ማዚን ፡—

«አሮጌዋን ዓለም ጥለናት እንለፍ...»

የሚለውን ዜማ ማዜም ሲጀምር የሌሎች ብዙ-አሥር ሰዎች ድምፆችም ለስለስ ብሎ ድምፃቸው በጉልህ እየተሰማ የሚከተለውን የግጥም ሀረግ ቀጠል አድርገውበት ያዜሙ ጀመር ፡—

«አቧራ-ትቢያዋን ከእግራችን እናራግፍ!...»

የእናት ዐይኖች ከፌዎዶር ጭንቅላት በላይ አርማውን እና ልጅዋን እየተመለከቱ ከናፍሮቿ ላይ ሰፋ ያለ ፈገግታ እየታየባት ከማዚን ኋላ-ኋላ መራመድ ቀጠለች ። ከፊት ለፊቷ ልጅዋ እና አንድሬይ ቀድመው በሰልፉ የሚጓዙ ሲሆን ፣ ዙርያውን የምትመለከታቸው ሰዎች በሙሉ ፈገግታ የተመላባቸው ሰዎች ናቸው ። ሁለቱም ሲያዜሙ የምትሰማቸው ሲሆን ፣ የልጅዋ ድምፅ እንደ ባስ የሙዚቃ መሣርያ ኩልል እያለ ሲፈስስ እና የአንድሬይ ድምፅም እንደ ቴኖር የሙዚቃ መሣርያ ጉልህ ሁኖ በመንቆርቆር የሚከተለውን ግጥም በዜማ ሲያዜሙ ይሰማታል ፡—

«ተነሳ ወዝ-አደር ፣ ተነሳና ታገል!
የተራብክ የታረዝክ ተነስ አንተ ጉስቁል!...»



ሕዝቡ ወደ ቀዩ አርማ እየሮጠ ይጎጋ ጀመር ። በሚሮጡበት ጊዜ ይንቻቹ የነበረ ቢሆንም ቻቻታቸው በመዝሙሩ ድምፅ ተውጦ ነበር ። ይኸውም መዝሙር በቤታቸው ውስጥ ሳሉ ከሌሎቹ መዝሙሮች ይልቅ ለስለስ ባለ ሁኔታ ይዘመር የነበረ መዝሙር ነው ። እዚህ ጎዳና ላይ ይኸ መዝሙር ሲዘመር በልስላሴ ያልተገታ ከመሆኑም በስተቀር ከፍተኛ በሆነ የኃይል ስሜት ይቃኝ ነበር ። እንደብረት የጠነከረ ጉብዝናን መዝሙሩ የሚያንቆረቁር ሲሆን ፣ ወደ ወደፊት የሚያመራውን ረዥም ጎዳና ሕዝቦች እንዲከተሉ ይጠይቃል ። ያ ረዥም ጎዳና ምንኛ አድካሚ እንደሚሆንም ግልጥ ባለ ሁኔታ ሕዝቦችን የሚነግራቸው መዝሙር ነው ። ሳያቋርጥ የሚንቦገቦገው ነበልባል ጊዜው ያለፈበትን ዝቃጭ ሁሉ ፣ አዲሱን የመፍራት ባሕል የሚያሳየውን ወጋዊ እምቢተኝነት እየለበለበ የሚያቃጥል ነው...

መልኳ በደስታ የተዋጠ ፣ ያም ሁኖ ግን ፍርሀት ያደረባት አንዲት ሴት እናት አጠገብ ቁማ የነበረች ስትሆን በሚንቀጠቀጥ ድምፅ የሚከተለውን አሰማች ፡—

«ሚትያ! የት ለመሄድ ነው?»

«ይተውት ይሂድ!» በማለት ወዲያውኑ ቀጠል አድርጋ እናት ተናገረች ። ከዚያም ቀጠል በማድረግ ፡— «ለርሱ አይስጉ ። እኔ ራሴም ብሆን መጀመርያ ፈርቼ ነበር ። ያውልዎ እዚያ ፊት-ፊት ቀድሞ አርማውን የያዘው የኔ ልጅ ነው!» በማለት እናት ተናገረች ።

«እናንተ ሞኞች ወዴት ነው የምትሄዱት? ወታደሮቹ እዚያ ናቸው እኮ!» የሚል ድምፅ ተሰማ ።

ረዥም እና ከሲታ የሆነችይቱ ሴትዮ ድንገት አጥንታማ በሆነ እጅዋ እናትን ጭብጥ አድርጋ ያዘቻት ።

«የኔ ውድ! ምን እንደሚዘምሩ ያድምጧቸው! የኔ

ሚትያም አብሮ ይዘምራል...» በማለት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ ተናገረች ።

«ግዴለዎትም አይሥጉ ። እነርሱ የቆሙለት ዓላማ የተቀደሰ ነው ። ለክርስቶስ ሲሉ ሰዎች ባይሞቱ ኖሮ ክርስቶስም ባልኖረ ነበር!» በማለት እናት ተናገረች ።

ይህ አባባል በአዕምሮዋ ውስጥ ፈጥኖ በመግባት ቀላል እና ግልጽ የሆነ ዕውነትነቱ ልቧን ነካው ። አሁንም እጅዋን የያዘችይቱን ሴትዮ መልከ እናት ቃኘችው ።

«ሰዎች ለፈጣሪ አምላክ ሲሉ ራሳቸውን አሳልፈው ባይሰጡ ኖሮ ክርስቶስ ባልነበረም ነበር!» በማለት በመደነቅ ፈገግ ብላ ሃሣቡን ደግማ ተናገረች ።

ሲዞቭ ወደ እናት ዘንድ መጣ ። ባርኔጣውን አውልቆና ከመዝሙሩ ጋር ወዝወዝ እያለ ፡ —

«እናት ፣ ሕዝቡ በግልጽ ተሰልፎ ወጣ ፤ አይደለም እንዴ? ይኸው መዝሙሩንም ይዘምረዋል ። ኧረ እንዴት ልብ የሚነካ መዝሙር ነው እባክዎን?» በማለት ተናገረ ።

«ንጉሥ ለጦርነት ይሻል ወታደሮች ፣
እንካ ውሰድ በሉት የናንተኑ ልጆች...»

«ኧረ ጉድ ነው ፣ ቅንጣት ታህል አይፈሩም እኮ! የእኔ ምስኪን ልጄ ይኸንን ሳያይ ሞቶ ተቀብሮአል...» በማለት ሲዞቭ ተናገረ ።

የእናት የልብ ትርታ ኃይለኛ ስለነበር ወደኋላ እየተንገዳገደች ወደቀች ። ሕዝቡ በብዛት እየተመመ በሚያልፍበት ጊዜ ወዲያውኑ ፈጥነው ካነሷት በኋላ አጥር ሥር አስጠጓት ። ሕዝቡ ብዙ በመሆኑ ተደሰተች ።

«ተነሳ ወዝ-አደር ፣ ተነሳና ታገል!...»



ሕዝቦችን ከነበሩበት በመቀስቀስ ፣ በአንዳንዶቹ ልብ ውስጥ ለትግል ዝግጁ ሁኖ ለመገኘት ስሜትን በማሳደር ፣ በአንዳንዶቹ ልብ ውስጥ ደግሞ ይኸንን አንዳች አዲስ ነገርን በማወቅ ጉጉት መላ-ቅጡ በጠፋ ደስታ ልባቸው እንዲግል በማድረግ ትልቅ የብረት ጡሩምባ ዜማውን እያንቆረቆረ በዓየሩ ላይ የሚነዛው ይመስል ነበር ። በአንዳንዶቹ ላይ ጉልህ ሁኖ የማይታይ ተስፋ እንዲያድርባቸው ሲያደርግ ፣ በሌሎቹ ላይ ደግሞ ረዘም ካለ ጊዜ ጀምሮ ውስጥ-ውስጡን ሲያብጥና ሲብላላ የቆየው የቁጣ ማዕበል ፈንድቶ እንዲወጣ አድርጎታል ። ነፋስ ያውለበልበው የነበረውን ቀዩን አርማ ሁሉም ያስተውላል ።

«እኛውና እንሂድ! እሰይ ምሥጉን ወገኖቼ!» በማለት አንድ ሰው በደስታ ስሜት ተውጦ ተናገረ ።

እንዲህ በቀላሉ በቀላል ቃላቶች ሊገለጽ በማይችሉ ስሜቶች ሰውየው ተውጦ ስለነበር ከፍተኛ የሆኑ የስድብ ናዳዎችን በማዥጎድጎድ ተሳደበ ። ይሁን እንጂ የሰውየው ስድብ የፀሐይ ጨረር ውጋጋኗን በላዩ ላይ የፈነጠቀችበት እባብ እንደሚያስማው ያለ ድምፅ ፣ በባርነት ሥር የሚገኝ ሰው የሚያሳየው ጥላቻ ፣ በጭለማ የተዋጠ ዕውር ጥላቻ እንደማለት ነበር ።

«እነዚህ ከሃዲዎች!» በማለት አንድ ሰው ቤቱ ውስጥ በመስኮት በኩል እጁን በቁጣና በዛቻ ወዘወዘ ።

«ወይ ጥጋብ ፣ ግርማዊ ንጉሠ-ነገሥትን በመቃወም መነሳሳት? ቄሳሩን ንጉሠ-ነገሥታችንን በመቃወም መነሳሳት? አመጽ ማካሄድ?» የሚል የሌላ ሰው የቁጣ ድምፅ ተሰማ ።

ወንዶቹ እና ሴቶቹ በብዛት እየተመሙ ሲጎርፉ ፊታቸውን የከፋቸው ሰዎች ባጠገቧ ሲያልፉ እናት አስተዋለች ። ከፊት-ለፊቱ የሚገኘውን ማናቸውንም ነገር እየጠራረገ ወደፊት እንደሚገሰግሥ እሳተ-ገሞራ

በውስጡ ይዞት በሚገኘው ኃይል መንገዱን እየጠራረገ የሕዝቡ ግፊያ ትርምስ እየጨመረ ወደፊት ይዘልቅ ጀመር ። እርማው ከሩቅ ሁኖ ወደፊት ሲገሰግሥ ተመለከተች ። ዐይኖቹ በዕምነቱ ብርሃን ብሩህ ሁነው በርተው ፣ ነሐስ የመሰለ ግንባሩ ፊክቶ የልጅዋ መልክ በአዕምሮዋ ውስጥ ቁልጭ ብሎ ታያት ።

አሁን እርሷ የምትገኝበት የሰልፍ ቦታ ወደ ኋላ መጨረሻው ላይ ሲሆን ይኸውም በምንቸገረኝነት ያለመቻኮል በሰልፉ ላይ ኋላ-ኋላ የሚገኙና የሰልፉ የመጨረሻ ውጤትም ምን እንደሚያስከትል ቀደም ሲል ጀምሮ የገመቱ ሰዎች የሚገኙበት ቦታ ነው ። ኋላ-ኋላ የሚገኙትም በጉዞአቸው ላይ ሁነው ርግጠኛ በሆነና ዝግ ባለ ድምፅ የሚከተለውን ተናገሩ ፡ —

«አንዱ የወታደር ጓድ ትምህርት ቤቱ ውስጥ መሽጎ የሚገኝ ሲሆን ፣ ሌላው ደግሞ ፋብሪካው ውስጥ ይገኛል...»

«አገረ-ገዥው መጥቷል...»

«ውነትክን ነው እንዴ?»

«በዐይኔ በብረቱ አየሁት ። ገና አሁን መጣ!»

«ይኸው እንግዲህ በመጨረሻ ፈርተውናል! እዩዋቸው እስኪ ሠራዊቶቹን እና አገረ-ገዢውን!» በማለት ከተሰበሰቡት መካከል አንዱ በደስታ ሁኔታ ተሳደበ ።

«አይ የኔ ውዶች!» በማለት እናት አሰላሰለች ።

የምታዳምጣቸው ቃላቶች ግን ቀዝቃዞች እና በድኖች ሁነው ተሰሟት ። ከእነዚህ ሰዎች ራቅ ብላ ወደፊት ለመቅደም ከእርምጃዎቿ ፈጠን ፈጠን በማለት እየነጠቀች ወደፊት ገፋች ። እነዚህ ሰዎች እጅግ ዝግተኛ የሰነፍ ጉዞ የሚጓዙ ስለነበሩ እነርሱን አልፎ መሄድ ቀላል ነበር ።

ድንገት ፣ የሰልፉ ግንባር ከአንዳች ነገር ጋር የተጋጨ ከመምሰሉም በስተቀር ፣ የፈራ በሚመስል ማጓራ



ትም ወደኋላ ሲያፈገፍግ ታየ ። መዝሙሩም እየተቋረጠ የሚሰማ ሲሆን ፣ ከቀድሞው በበለጠ በከፍተኛ ድምፅ እና ፈጣን በሆነ አዚያዚያም እንደገና ይዜም ጀመር ። አሁንም እንደገና ዝቅ እያለ ይሰማ ጀመር ። አንድ-በአንድ እያሉ ሰዎች መዝሙሩን መዘመራቸውን አቆሙ ። ቀደም ሲል ተጎናጽፎት የነበረውን ከፍተኛ የማዕርግ ቦታውን መዝሙሩ እንዲይዝ ለማድረግ ፣ የተለያዩ ድምፆች መዝሙሩን ያዜሙት ጀመር ፡ —

«ተነሳ ወዝ-አደር ተነሳና ታገል!
የተራብክ-የታረዝክ ተነስ አንተ ጉስቁል!..»

በዚህ መዝሙሩን የመዘመር ጥረት ላይ ግን ቀድሞ የነበረው የወል ፍላጎት ፤ ተጠናክሮ ተመሥርቶ የነበረው ጽኑ ሃሣብ አይታይም ።

ከፊት-ለፊት ቀድመው የሚገኙትን ሰልፈኞች እናት ለማየት የማትችል በመሆኑ እና ምን እንደደረሰም የማታውቅ በመሆኗ ሰልፈኞቹን ከወዲያ-ወዲህ እየገፋፋች ወደፊት ትገሰግስ ጀመር ። አንዳንዶቹ ሰዎች ፊታቸው ኮስተር ብሎ ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ጭንቅላቶቻቸውን ቀልበስ አድርገው ፣ አንዳንዶቹም ደስታ-ቢስ ፈገግታ ፈገግ እያሉ አሁንም ሌሎቹ የምጸት ፉጨት እያፏጩ ይታዩ የነበሩትን እያተረማመሰች በጉዞዋ ወደፊት ትገፋ ጀመር ። ዐይኖቿን በምርምር ፣ በመመሰጥ እና በመገንዘብ ሁኔታ አተኩራ የሰዎቹን ፊቶች ትቃኝ ጀመር...

ፓቬል የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«ጓዶች! ወታደሮች እንደኛው ዓይነት ሰዎች ናቸው! አይነኩንም ። ለምን ይነኩናል? ማንም የሚያውቀውን ሀቅ ይፋ አውጥተን ስለገለጽን ይቃወሙናል? እነርሱም ይኸንን ሀቅ ማዳመጥ አለባቸው ። አሁን

ለጊዜው አይገንዘቡት እንጂ ፣ የግድያ እና የዝርፊያ አርማቸውን አንግበው እኛን በመቃወም ፊንታ ፤ የነፃነትን አርማ አንግበው ከእኛ ጋር የሰልፋቸውን ረድፍ የሚያስተካክሉበት ጊዜ ይመጣል ። የዚህን ሀቅ መምጫ ጊዜ ለማፋጠንም ወደፊት መገሥገሳችንን መቀጠል አለብን ። ጓዶች! ወደፊት! ምንግዜም ወደፊት!»

የፓቬል ድምፅ የተረጋጋ ሁኔታ ይታይበታል ። ከአንደበቱ የሚወጡት ድምፆች ቁልጭ ያሉ ናቸው ። የተሰበሰበው ሕዝብ ግን እየተበተነ ነው ። አንድ በአንድ ሰዎቹ ቀደም ሲል ይዘውት የነበረውን የሰልፍ መሥመር በመተው እያፈገፈጉ ቤቶች ወደሚገኙበት አካባቢ እና ወደየአጥሮች ሥር ይታከኩ ጀመር ። አሁን በሰልፉ ላይ የነበረው ሰው ብዛት እየመነመነ በመቀነስ ሹጥጥ ያለ የሰልፈኛ ረድፍ ብቻ የቀረ ሲሆን የወዝ-አደሮችን ቀይ አርማ አንግቦ ወደላይ በማውለብለብ ፓቬል በግንባር ቀደምነት ሰልፉን ይመራው ጀመር ። የሰልፈኛው ሁኔታ ክንፎቹን ዘርግቶ ሊያኮበኮብ የተዘጋጀ ቁራ የሚመስል ሲሆን ከፊት የቀደመው ፓቬልም የቁራው አፍ እንደማለት ነበር ።

## 28

ከጎዳናው መጨረሻ ላይ ትከሻ-ለትከሻ የገጠሙ ፊት-የለሽ እና ሁላቸውም ተመሳሳይ የሆኑ ሰዎች ወደአደባባዩ የሚያስገባውን መዳረሻ በመዝጋት እንደግድግዳ መጠጋታቸውን እናት ተመለከተች ። የእየአንዳንዳቸው ትከሻ እንደወርቅ የሚያንጸባርቅ ሳንጃ የተሰካበት ጠመንጃ አንግቶአል ። እና ከዚያ ከማያንቀሳቅስ እንደግድግዳ የተገተረ እንደበረዶ ቀዝቃዛ የሆነ ወዝ-አደሮችን የሸፋፈነ እና የእናትን ልብ ያቀዘቀዘ ትንፋሽ ይተነፈሳል ።



አርማው የሚገኝበትን የማታውቃቸው ሰዎች የምታውቃቸውን ሰዎች ዙርያ ከብበው የእነዚህን ሰዎች ድጋፍ የሚጠይቁ በሚመስልበት ቦታ ለመድረስ ሰልፈኛውን እየገፋፋች ወደፊት ጉዞዋን ቀጠለች ። የተላጨው እና አንድ-ዐይና የሆነ ረዥም ሰው ሥር በግፊ የተጣበቀች ከመሆኗም በስተቀር ፣ ይኸ አንድ-ዐይና ሰውም እርሷን ለመመልከት በገሚስ ዞር ማለት ነበረበት ።

«ማን ነዎት?» በማለት ጠየቃት ።

«የፓቬል ቭላሶቭ እናት ነኝ» በማለት እግሮቿ እየተንቀጠቀጡ ፤ እራሷን እና ከንፈሯን መቆጣጠር አቅቷት ተናገረች ።

«ኡ-ሆ!» በማለት አንድ-ዐይናው ተናገረ ።

ፓቬል የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«ጓዶች! ሕይወታችንን በሙሉ ወደፊት በመግፋት መቀጠል አለብን ። ለእኛ ሌላ አቅጣጫ የለም!»

ሰልፉ ላይ የሚገኙት ሰዎች ፀጥ በማለት በጉጉት ይጠባበቁ ጀመር ። አርማው ከፍ ብሎ ከተነሳ በኋላ ለሰከንድ ያህል ከሰልፈኞቹ ጭንቅላት በላይ እንዲውለበለብ ተደረገ ። ግራጫ ወደሆኑት እንደግድግዳ የቆሙ ወታደሮች ዘንድ ያመራ ጀመር ። እናት እንደመንቀጥቀጥ ካለች በኋላ ዐይኖቿን ዘግታ ተነፈሰች — አራት ሰዎች — ፓቬል ፣ አንድሬይ ፣ ሳሞይሎቭ እና ማዚን — ከተሰበሰበው ሰልፈኛ ቀድመው ተጓዙ ።

የፌዎዶር ማዚን ግልጽ ድምጽ አየሩን ሰንጥቆ የሚከተለውን ሲያዜም ተሰማ ፡ —

«ከንድህን ተንተራስክ ክቡር መስዋዕት ሁነህ...»

የሚቀጥለው የመዝሙሩ ሀረግ ዝግ ባለ ድምፅ በሰልፈኞቹ ይሰማ ጀመር ።

«በወደር-የለሹ… በዚህ ታላቅ ትግልህ…»

አራቱም ከጣዕመ-ዜማው ስልት ጋር እግራቸውን እያስማሙ ወደፊት መጓዛቸውን ቀጠሉ ።

ውሳኔ የተመላበትን የሚከተለውን የግጥም ሀርግ ፌዎዶር በውሳኔ መልክ ሲያዜም የድምፁ ጣዕመ-ቃና እንደመረዋ ያስተጋባል ።

«ያለህን በሙሉ ሰጠህ ለሱ ብለህ…»

ከዚያም ጓዶቹ የሚከተለውን የግጥም ሀረግ አብ ረውት ያዜማሉ ፡ —

«ስለ ነፃነትህ… ስለነፃነትህ…»

«አሃ! ሙሾ ታወርዱ ጀመር እንዴ ፣ እናንት ፤ የውሻ ልጆች!» በማለት ከሰልፈኞቹ መካከል አንዱ ጉሮሮው እየተናነቀው ተናገረና ወደጥግ ወጣ አለ ።

«ውገረው!» በማለት አንድ ሌላ ድምፅ የቁጣ ቃል አሰማ ።

እናት ልቧን በእጆቿ ደገፍ አድርጋ ዙርያውን ት ቃኝ ጀመር ። አራቱ ሰዎች ከአርማው ጋር ወደፊት እየገፉ ሲሄዱ ፣ ቀደም ሲል ጎዳናውን አጥለቅልቀው የነ በረው ሕዝብ ቀስ-በቀስ ሲያፈገፍግ ተመለከተች ። አ ራቱን ሰዎች ጥቂት ሰዎች የሚከተሏቸው ሲሆን ፤ እየአንዳንዱን እርምጃ ወደፊት በተራመዱ ቁጥርም ጎዳናው እግራቸውን ያቃጥለው ይመስል አንዳንድ ሰው እየተንጠባጠበ ወደኋላ ይቀር ነበር ።

«አመጽም ያበቃል…»

የሚለውን የግጥም ሀረግ ፌዎዶር ሲያዜም ፡ —

«ሕዝቡም ይነሳሳል…»

በማለት በሰልፉ ላይ የተገኙት መዝሙሩን ቀበል አድርገው የሚያዜሙ ሲሆኑ ፣ እነዚህ የግጥም ሀረጎች



ም እርግጠኛ ማስጠንቀቂያ የሆኑ የመዝሙሩ አዝማቾ ች ናቸው ።

ከመዝሙሩ ጋር የመደነቅ ሹክሹክታ በአንድነት የሚከተለውን አባባል አሰማ ፡ —

«እርምጃ ለመውሰድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ነው!»

በእርግጥም ደግሞ ከፊት ለፊት ከሚገኙት ሰዎች፣ በኩል የትዕዛዝ ድምፅ የሚከተለውን አሰማ ፡ —

«ጠመንጃችሁን ደግኑ!»

እንደማዕበል የተሠማራው የሰልፍ መሥመር ጠ መንጃውን ደግኖ ሳንጃውን እያብለጨለጨ ወደፊት በመገስገስ ላይ ያለውን አርማ ተጋፈጠው ።

«ወደፊት በሰልፍ!» በመባል ታዘዘ ።

«መጡ!» በማለት አንድ-ዐይናው ሰውዬ እጆቹን ኪሶቹ ውስጥ ከትቶ ወደ አንዱ ጥግ ገሸሽ እያለ ተናገረ ።

እናት ዐይኖቿን ሳታርገበግብ ትመለከታለች ። ወታደ ሮቹ የአደባባዩን መዳረሻ ጠርዝ በሙሉ መልተው እና ሳንጃቸውን ሰድረው ፊት-ለፊት ይገሰግሱ ጀመር ። እናት ፈጠን ባሉ እርምጃዎች በመገስገስ ወደ ል ጅዋ ተጠጋች ። አንድሬይም በረዥሙ አካሉ ፓቬልን ለመጠበቅ ከፊት-ለፊቱ ቀድሞ ሲጓዝ አየችው ።

«ጓድ ፣ ወደ ቦታህ ተመለስ!» በማለት ፓቬል አጠ ንክሮ ተናገረ ።

አንድሬይ እጆቹን ወደኋላ አድርጎ እና ጭንቅላቱ ን ወደላይ ከፍ አድርጎ ያዜማል ። ፓቬል በትከሻው ወደጎን ከገፋው በኋላ አሁንም የሚከተለውን ጎላ ባለ ድምፅ ተናገረ ፡ —

«ወደ ኋላ ተመለስ! ከፊት-ለፊት ቀድመህ ለመሄድ መብት የለህም! አርማው መቅድም አለበት!»

«ተበታተኑ!» በማለት ቁመተ-አጭር መኮንን ስል ል ባለ ድምፅ ተናገረ ። መኮንኑ ወደፊት በሰልፍ በሚ

ሄድበት ጊዜ ጉልበቱን ሳያጥፍ እግሩን በረዥሙ እየ ከነዳ በመራመድ በቡት መጫሚያው ተረከዝ መሬቱን ይደቃዋል ። በዚያ መጫምያ ማብለጭለጭ እናት ተጠንቅቃ ነበር ።

ፀጉረ-ድምድም እና በዛ ያለ የሪዝ ጢም ያለው ረዥም ሰው ከጎን-ጎኑ የሚሄድ ሲሆን ፣ አንድ ግዙፍ ሰው ደግሞ ከበስተኋላው ተከትሎታል ። በቀይ መሥመር የተከፈፈ ረዥም ካፖርት የለበሰ ሲሆን የሱሪው ግራና-ቀኝ መሃል ለመሃል ከላይ ወደታች ቢጫ የጨርቅ ጥብጣብ አለበት ። እንደ ኾኾል እጆቹን ወደኋላ አድርጎ ይጓዛል ። ጎላ ባሉ ቅንድቦች የተመሉት ዐይኖቹ ተበልጥጠው በመከፈት ፓቬል — ፓቬልን ይመለከታሉ ።

የእናት አመለካከት ያየውን ሁሉ የሚያደንቅ ነበር ። እየአንዳንዱን ትንፋሿን በተነፈሰች ቁጥር ልቧ ድቅ-ድቅ እያለ ፈንድቶ ሊወጣ ይቃጣው ነበር ። በጩኸት ታፍና የነበረ ሲሆን ፣ ደረቷን አጥብቃ በመያዝ ተቋቋመችው ። ሰዎች ይገፏት የነበረ ሲሆን ራሷን ለመሳት ምንም ያህል ባልቀረው ሁኔታ ወደፊት ትንገዳገድ ጀመር ። ቀዝቃዛው የወታደሮቹ ሰልፍ እርሷን እየገፋፉ ከፊት ለፊት ሲገሰግስ ከበስተኋላዋ ያለው ሰልፈኛ ብዛቱ እየመነመነ የሚዘልቅ መሆኑን ተገነዘበች ።

ቀዩን አርማ ተከትለው ወደፊት በሚጓዙት እና ግራጫ በሆኑት ወታደሮች መካከል ያለው የመጠጋጋት ልዩነት ይበልጥ እየተቃረበ ይሄድ ጀመር ። አሁን የወታደሮቹን መልክ በሙሉ መመልከት ትችላለች ፡ — በጎዳናው ላይ ከዳር-ዳር የተዘረጋ የቆሻሻ-ቢጫ ተሰላፊዎች መልክ ሲሆን ልዩ-ልዩ ቀለሞች ያሏቸው ዐይኖቻቸውም በሰልፉ ላይ ወጣ-ገባ ሁነው ይታያሉ ። ወታደሮቹ ፊት-ለፊት ደግነው የያዙዋቸው



ሳንጃዎች እያብረቀረቁ ጠንቀኛ ሹል-አፋቸውን በሰልፈኞቹ ደረት ላይ ያሞጠሞጡ ሲሆኑ ሰልፈኞቹን ሳይነኩ አንደኛቸውን ከሌላኛቸው በማለያየት ሰልፉን በታተኑት ።

እናት ሰልፈኞቹ ከኋላዋ ሲሮጡ እና የተነሳሱ ድምፆችም የሚከተለውን ሲናገሩ ሰማች ፡ —

«ተበታተኑ! ተበታተኑ!»

«ቭላሶቭ ፣ ሩጥ!»

«ፓቬል ፣ ተመለስ!»

«ፓቬል ፣ አርማውን ጣለው!» በማለት ቬሶቭሺኮቭ ጨፍገግ ባለ ድምፅ ተናገረ ። «አርማውን ለኔ ስጠኝ ፣ እደብቀዋለሁኝ ።»

ሰንደቁን ከጨበጠ በኋላ አርማውን ወደኋላ ጎተተው ።

«ልቀቁኝ አርማው ይግፋ!» በማለት ፓቬል ድምፁን አጉልቶ ተናገረ ።

ኒኮላይ እጁን እሳት የለበለበው ይመስል አፈፍ አድርጎ መለሰው ። መዝሙሩ አበቃ ። ሰልፈኞቹ ባሉበት ቦታ በመቆም በፓቬል ዙርያ እንደግድግዳ ከበቡ ። ፓቬል ግን አሁንም ወደፊት ይገፋ ጀመር ። ድንገት እና ሳይታሰብ የማይታይ የማይዳሰስ ደመና ከላይ ዱብ ያለ ይመስል ፀጥታ ሰፈነ ።

ብዛታቸው አይብለጥ እንጂ ሃያ ያህል የሚሆኑ ሰዎች በጸና መንፈስ አርማውን ከብበው ቆሙ ። እናት በሥጋት አንዳች ነገር ለመንገር በመሻት ሁኔታ ወደሰልፈኞቹ ተጠጋች ።

«የመቶ አለቃ ፣ ያንን የያዘውን ነገር ውሰድ!» በማለት ወደ አርማው እያመለከተ ረዥሙ ሽማግሌ ተናገረ ።

ትንሹ መኮንን ወደ ፓቬል ዘንድ ሮጠና አርማውን ጨበጠ ።

«ልቀቅ!» በማለት ተፍጨረጨረ ።

«እጅህን ሰብስብ!» በማለት ፓቬል በጉልህ ድምፅ ተናገረ ።

አርማው አንዴ ወደቀኝ አንዴም ወደግራ በመዘዋወር አየር ላይ ይውዘገዘግ ጀመር ። ከዚያም ቀጥ ብሎ ይውለበለብ ጀመር ። ትንሹ መኮንን ወደኋላ ከለ በኋላ ወደቀ ። ኒኮላይ እጁን እያወዛወዘ እናትን አልፎ ሄደ ።

«ያዟቸው!» በማለት ሽማግሌው እግሩን ከመሬቱ ጋር እየደቃ በጩኸት ተናገረ ።

ብዙ ወታደሮች ወደፊት ገሰገሱ ። ከወታደሮቹ መካከል አንዱ የጠመንጃውን ሰደፍ ያወዛውዛል ። አርማው ተወዛወዘ ። ወደፊት ወደቀ ። ከዚያም በወታደሮቹ ትርምስምር ውስጥ ጠፋ ።

«ወይኔ እኔ!» በማለት አንዱ በምሬት ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ።

እናት እንደቆሰለ እንስሳ ወዮታ ታሰማለች ። ከወታደሮቹ መካከል የተከበበው ፓቬል በጉልህ ድምፁ የሚከተለውን መልስ አሰማ ፡—

«እናት ደህና ሁኚ! የኔ ውድ ደህና ሁኚ!..»

ሁለት ሃሣቦች በአዕምሮዋ መጡባት ፡— «በሕይወት ነው ያለው! ያስታውሰኛል!» የሚሉት ሃሣቦች ናቸው ።

«እምዬ ፣ ደህና ይሁኑ!»

በጨረፍታም ቢሆን እንኳን ፓቬልን እና ኾኾልን ለመመልከት በመጣር ተረከዞቿን ከፍ አድርጋ በእግር ጣቶቿ ተንጠራርታ በመቆም ተመለከተች ። ከወታደሮቹ ጭንቅላት በላይ የአንድሬይን ፊት ከፍ ብሎ ተመለከተች ። ፈገግ እያለ እጅ ይነሳት ነበር ።



«ወይኔ የኔ ውዶች... እንድርዩ! ፓሻ!» በማለት ጮኸች ።

«ጓዶች! ደህና ሁኑ!» በማለት በወታደሮቹ መካከል ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አሰሙ ።

እንደገደል ማሚቶ በአንድነት የተከማቸ ድምፅ በጉልህ ሁኖ መልስ መለሰላቸው ። ድምፁ ይሰማ የነበረው ከየመስኮቶቹ ፣ ከፍታማ ከሆነ ቦታ ሁሉ ፣ ከየቤቱ ጣራ ላይ ሁሉ ነበር ።

## 29

ማንነቱ ያልታወቀ ፣ እናትን ደረቷ ላይ ገጫት ። ከፊት ለፊቷ የቆመውን አጭር መኮንን በድካም የተዋጠ ቀይ ፊት ተመለከተች ።

«ሴትዮ! ከዚህ ሂጂ!» በማለት ጮኸ ።

በዐይኗ ገረፈችው ። የአርማው ሰንደቅ ከሁለት ላይ ተሰብሮ እና የአርማው ቀይ እራፊ ጨርቅም ከተሰበረው ሰንደቅ ላይ ተንጠልጥሎ ከእግሩ ሥር ወድቆ ተመለከተች ። ወደፊት ተራመደች እና አነሳችው ። መኮንኑ ከእጅዋ ላይ መንጭቆ ወሰደ እና ወደጎን ገፋት ።

«ሴትዮ! ኋላ ልብ አድርጊ! ሂጂ ከዚህ ብየሻለሁ!» በማለት እግሩን ከመሬቱ ጋር እየደቃ ጮኸ ።

ወታደሮቹ ከከበቡት ክበብ መሃል ፡—

«ተነሳ ወዝአደር ፣ ተነሳና ታገል!..»

የሚለው መዝሙር ሲዘመር ይሰማል ።

ሁሉም ነገር ይሽከረከር ፣ ይዞር እና ይንደቀደቅ ነበር ። የቴሌግራም ማስተላለፊያ መሣርያ እንደሚያሳየው ዓይነት የጩኸት እንቅጥቃጤ አየሩ በጫጫታ ተሞልቶ ነበር ። መኮንኑ ገስግሶ ሄደ ።

«ይኸንን መዝሙራችሁን አቁሙ!» በማለት በቁጣ ጮኸ ። ከዚያም ፡ — «ሳጂን-ሜጀር ክራይኖቭ!...» በማለት ተጣራ ።

እናት እየተንገዳገደች መኮንኑ የወረወረውን የዓርማ ሰንደቅ ሂዳ አነሳችው ።

«ይኸንን አፉቸውን ዝጋላቸው!» በማለት ተናገረ ።

መዝሙሩ ተቆራረጠ ፤ ተደነቃቀፈ ከዚያም አበቃ ። አንዱ የእናትን ትከሻ ገፉ-ገፉ በማድረግ ዞር ካደረጋት በኋላ እንድትሄድ ገፋ አደረጋት...

«ይሂዱ ፤ ይሂዱ...» በማለት ተናገረ ።

«ከመንገዱ ዞር በሉ!» በማለት መኮንኑ በጩኸት ተናገረ ።

እናት ሰዎቹ ትንሽ እርምጃዎች ርቀው ተመለከተች ። ቀስ-በቀስ መንገዱን እየለቀቁ በየቤቶቹ ምድረ-ግቢ በሚገቡበት ጊዜ ይጮኹ ፤ ይሳደቡ እና ያፏጩ ጀመር ።

«አንቺ የሴት ሰይጣን! ዞር በይ ከዚህ!» በማለት ሪዝ ያለው ወታደር ወደ እግረኛ መንገድ እየገፈታተራት እናት ላይ ጮኸባት ።

እቅሟ ሁሉ ሙጥጥ ብሎ በማለቁ የአርማውን ሰንደቅ ተመርኩዛ ከጎዳናው ወደጥግ ወጣች ። ከመውደቅ እንድትድን በሌላኛው እጅዋ ግንቦችን እና አጥሮችን ትደገፍ ጀመር ።

«ሂጂ! ሂጂ!..» እያሉ ወታደሮቹ ከበስተኋላዋ ሁነው ሲጮኹ ሌሎቹ ሰዎች ከርሷ ራቅ እያሉ ይሂዱ ጀመር ።

አሳለፈቻቸው ። ከዚያም ቆም ብላ ዙርያውን ተመለከተች ። በጎዳናው መጨረሻ ላይ ብዙ ወታደሮች ባዶ የነበረውን የአደባባዩን መዳረሻ በሰልፍ ሲዘጉት ተመለከተች ። ከርሷ ፊት ለፊት ያሉት ግራጫ መሰል ሰዎች ሰዎቹን ወደኋላ መመለሳቸውን ቀጠሉ...



ወደኋላ ለማፈግፈግ አሻች ። ይሁን እንጂ ከቁጥጥሯ ውጪ በሆነ ምክንያት ወደፊት መግፋቷን በመቀጠል ጠባብ ወደሆነች ማቋረጫ መንገድ ድረስ በመዝለቅ መንገዲቱን ይዛ ተጓዘች ።

እንደገና ቆመች ። በረዥሙ ከተነፈሰች በኋላ ታዳምጥ ጀመር ። ከፊት-ለፊት ያለ ቦታ ላይ የሕዝብ ጉርምርምታ ይሰማ ጀመር ።

ሰንደቁን በመመርኮዝ እንደገና መጓዝ የጀመረች ስትሆን በአሁኑ ጊዜ ግን በላብ ተጠምቃ ፤ ሽፋሽፍቶቿ እየተንቀጠቀጡ ፤ ከናፍሮቿ እየተርበደበዱ የተበታተኑ ቃላቶች እንደብልጭታ በአዕምሮዋ ውስጥ እየተመላለሱ በመጠራቀም መጠናቸው ጨምሮ የሰፌ ምኞት ነበልባል ሁነው በመፈንዳት ንግግር ወደመሆን ጉልህ በሆነ ሁኔታ መሰማት እስኪጀምሩ ድረስ እጆቿም ይወዛወዙ ነበር...

አቋራጩ መንገድ ድንገት ወደግራ የሚያመራ ሁኖ ያገኘችው ሲሆን ፤ ብዙ ሕዝቦች በዚሁ ቦታ ላይ ተሰብስበው ተመለከተች ።

«ወንድሞቼ ሆይ ፤ እንደው ለመቀለድ በማለት ሳንጃ የሰደሩት ላይ መዳፈር አይቻልም!» በማለት ጉልህ በሆነ እና ከበድ ባለ ድምፅ ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል አንዱ ተናገረ ።

«ለመሆኑ ይኸንን የመሰለ ሁኔታ አይታችሁ ታውቃላችሁን? ያ ሁሉ ሳንጃ ተሰድሮ ሲመጣባቸው ሰልፈኞቹ ከምደራቱ ንቅንቅ-ፍቅቅ ሳይሉ ባሉበት ቦታ ቆመው መመልከት እንዴት ይደንቃል! ቅንጣት ያህል ሳይሰጉ ፤ እንደቋጥኝ ባሉበት ሳይነቃነቁ ነበር የቆሙት!»

«ፓቬል ቭላሶቭ ነዋ!»

«ኾኾልስ ቢሆን?»

«ፍርሃት-አልባ የሆነው ጉደኛ እጆቹን ወደኋላው

አድርጎ ፈገግ እያለ መንገዱን ሲገሰግስ ኧረ እንዴ
ት ይገርማል እባካችሁ!»

«ጓደኞች!» በማለት እናት ወደተሰበሰቡት ሰዎች
መሃል በመዝለቅ ድምጿን ከፍ አድርጋ አሰማች ።
በአክብሮት እልፍ እልፍ በማለት ቦታ ለቀቁላት ። ከተ
ሰበሰቡት መካከል አንዱ ሳቀ ።

«ኧረ ተመልከቱ ፣ አርማውን ይዘዋል! አርማውን
ይዘዋል!» በማለት ተናገረ ።

«ዝም በል» በማለት አንዱ ኮስተር ባለ ድምፅ
ተናገረ ።

እናት እጆቿን ዘረጋች… ከዚያም የሚከተለውን
ተናገረች ፡ —

«ስለፈጣሪ ብላችሁ አዳምጡ! እናንት መልካም ሰ
ዎች ፣ እናንት ውድ ሰዎች ፣ የደረሰውን ሁኔታ መለስ
ብላችሁ መመልከት አትፍሩ ። የእኛው ልጆች ፣ የደማ
ችን ክፋይ-ደሞች ፍትሕን ለሁሉም በመጠየቅ ወደ
ፊት ገስግሰዋል! ለሁላችሁም ብሩኅ ጊዜን በመሻት ፣
ገና ላልተወለዱት ሕፃናትም ብሩኅ ጊዜን በመሻት
መስቀላቸውን ተሸክመዋል… የሚሹት ሌላ ሕይወት
ነው ። የሃቅ እና የፍትሕ ሕይወት ነው… ለመላው ሕ
ዝብ በጎ መሆንን ነው የሚሹት!»

ልቧ በግለት ሊፈነዳ ደረሰ ። ጉሮሮዋም ትኩስ
እና ደረቅ ሆኖአል ። በእርሷነቷ ውስጥ በጥልቅ ዘል
ቀው በመግባት ታላላቅ የሆኑ አዳዲስ ቃላት እየተ
ወለዱ ናቸው ። ምላሷን ገፍተው በመውጣት ምን
ም ነገር ሳያግዳት እና ሳያንገዳግዳት ሁሉን አቀፍ
በሆነ ፍቅር ላይ የተመሠረቱ ቃላት ከአንደበቷ ይፈ
ልቁ ጀመር ።

ሁሉም ሰዎች በዝምታ የሚያዳምጧት ፤ የሚያስተው
ሉ እና የሚያስቡ መሆናቸውን ትመለከታለች ። በአሁኑ
ጊዜ ቁልጭ ብሎ በተቀናበረ ሁኔታ ልጅዋን እና



እንደሬይን እንደዚሁም በወታደሮች እጅ የወደቁትን
ሁሉ ፣ ከእነርሱ ዕድል-ፈንታ ሥር የወደቁትን ሁሉ
እንዲከተሉ የማሳሰብ ሁኔታ በእርሷነቷ ውስጥ አድ
ሮ ተቀሰቀሰባት ።

ኮስታራ የሆኑ እና እርሷን-እርሷን በጥሞና የሚመ
ለከቱትን ፊቶች እየቃኘች ለስለስ ባለ ሁኔታ ንግግ
ሯን ቀጠለች ፡ —

«ልጆቻችን ደስታን ለማግኘት በዓለም ላይ ይጓ
ዛሉ ። ይኸንንም የሚያደርጉት ለእኛ ለሁላችንም ሲሉ
እና ለክርስቶስ ዕውነትም ሲሉ ነው ። ክፉ ሰዎች ፣
ቀጣፊ እና ስግብግብ ሰዎች እኛን ሸምቅቀው ያሠሩ
በትን ፣ ያጎሳቆሉበትን እና የደመሰሱበትን ማናቸውንም
ውትብትብ ለመቋቋም ወደፊት ገስግሰዋል!ውድ ሰዎች፤
ወጣቶች የተነሳሱት ለእኛ ጠቀሜታ ሲሉ — ለመላው
ዓለም ጠቀሜታ ሲሉ — በየትኛውም ቦታ ለሚገኙ
ሠርቶ-አደር ሕዝቦች ጠቀሜታ ሲሉ ነው! ብቻቸውን
አትተውአቸው ፣ ጀርባችሁን አትመልሱባቸው ፣ ልጆቻች
ሁ ብቻቸውን እንዲጓዙ አታድርጉአቸው! ስለራሳችሁ
አስቡ ። ዕውነትን ባወጁት ለዕውነት ሲሉ በሚሰቃዩ
ት ልጆቻችሁ ላይ ዕምነት ይኑራችሁ!»

ድምጿ በመሰባበር ራሷን ለመሳት ምንም ባልቀ
ረው ሁኔታ ዛለች ። ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል አ
ንዱ ደግፎ ያዛት…

«የፈጣሪን ሃቅ ነው የምትናገረው! ሰዎች ሆይ ፣
የፈጣሪን ሃቅ ነው የምትናገረው! አድምጧት!» በማለት
ከተሰበሰቡት መካከል መንፈሱ የተነሳሳ አንድ ሰው
ተናገረ ።

«ራሷን እንደምን እንደምታሰቃይ ተመልከቱ!»
በማለት ሌላው ሰው ለርሷ ያለውን ሀዘን በመግለ
ጥ ሁኔታ ተናገረ ።

«ራሷን አታሰቃይም ። ለእኛ ምንም ለማናውቀው

ትምህርትን ነው የምትሰጠን!» በማለት ቀደም ሲል የተሠነዘረውን አባባል አርሞ ሌላው ሰው ተናገረ ።

«ዕውነተኛ አማኞች ሆይ!» በማለት ኅላ ባለ እና በሚንቀጠቀጥ ድምፅ ሌላ ሴት ንግግሯን ጀመረች ፡ —

«የእኔ ልጅ ሚትያ ምስኪን ነው ። ምን ነገር ፈ ጸመ? ጓዶቹን ተከተለ ። እነርሱን አፈቀረ ። እርሷ የተና ገረችው ዕውነት ነው ። ልጆቻችን በችግር ላይ ሁነው እንዴት እንተዋቸዋለን? ስሕተት ነው የሚባል ነገር የፈጸሙት ምን አለ?»

እናት እነዚህን ቃላት ስትሰማ እየተንቀጠቀጠች ድምፅ ሳታሰማ አለቀሰች ።

«ፔላጊያ ኒሎቭና ወደቤት ይሂዱ ። ይበቃል በሀዘ ን ብዙ ተጎድተዋል» በማለት ሲዞቭ ተናገረ ።

ፊቱ የቀላ ከመሆኑም በስተቀር ጢሙም ይንቀ ጠቀጣል ። ድንገት ቀና በማለት ዙርያውን ይመለከት ጀመር ።

«ልጄ ማትቬይ ፋብሪካ ውስጥ መገደሉን ሁላችሁ ም ታውቃላችሁ» በማለት አጥብቆ ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ — «ይሁን እንጂ አሁን በሕይወት የሚገኝ ቢሆን ኖሮ እኔው ራሴ ከሌሎቹ ጋር ፣ ከእነ ርሱ ጋር አብሮ እንዲሄድ እልከው ነበር ። እንዲህ በማለትም እነግረው ነበር ፡ — 'አንተም አብረህ ሂድ እንጂ! ዕውነተኛው መንገድ ፣ ሃቀኛው መንገድ እነርሱ የሚጓዙበት መንገድ ነው!'»

እነዚህ የተሰበሰቡ ሰዎች አንዳችም ዓይነት ፍርሃ ትን ያስወገዱ ሲሆን ፣ ተናጋሪው ንግግሩን አቋረጠ ። በሁ ሉም ዘንድ ፀጥታ ሰፈነ ። ሲዞቭ እጁን ጨብጦ በማ ወዛወዝ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«ሽማግሌ ሰው ነኝ የምናገረው ። ሁላችሁም ታውቁ ኛላችሁ ። በዚች ምድር ላይ መኖር ከጀመርኩኝ ሃም ሳ ሦስት ዓመት የሆነኝ ሲሆን ፣ እዚህ ቦታ ላይ ስሠ ራ ሰላሳ ዘጠኝ ዓመት ሁኖኛል ። ዛሬ እንደገና ጥሩ እና ብልህ የሆነውን ዘመዴን ይዘውታል ። እርሱም ከቭላሶቭ ጎን ከአርማው ቀጥሎ በሰልፍ ይዘልቅ ነበር…»

እጁን ማወለብለብ የጀመረ ሲሆን ፣ ግማሽ ሕይወቱ እርሱን የተለየች መሰለ ። የእናትን እጅ ጨበጥ አድ ርጎ በመያዝ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«ይህች ሴት የተናገረችው ዕውነት ነው ። ልጆቻ ችን ሃቀኛ እና ትክክለኛ የሆነ ሕይወትን ለመኖር ይሻሉ ። እኛ ግን ድጋፋችንን በሚሹበት ጊዜ እንደው ዝም ብለን ትተናቸዋል ። በእርግጥ ትተናቸዋል! ነይ ፣ ፔላጊያ ኒሎቭና…»

በቀሉት ዐይኖቿ እየተመለከተች እናት የሚከተለ ውን ተናገረች ፡ —

«በጎ ሰዎች ሆይ ፣ ሕይወት የልጆቻችን ነች ። ዓለም የነርሱ ነች!…»

«ነይ ፔላጊያ ኒሎቭና ፣ ሰንደቅሽን ውሰጂ» በማለት ሲዞቭ የተሰበረውን ሰንደቅ እየሰጣት ተናገረ ።

እናትን በአክብሮት እና በሀዘን ፣ እየተመለከቷት የየበኩላቸውን በጎ አስተያየትም ያቀርቡ ጀመር ። ሲ ዞቭ በፀጥታ ሁኖ መንገዱን የለቀቀላት ሲሆን ፣ በአጠ ገቧ ያሉት ሰዎችም በፀጥታ ሁነው መንገዱን ለቀቁ ላት ። አንድ ሊቆጣጠሩት ያልቻሉት ኃይል እየገፋፋቸ ው እርሷ ይዛ የምትጓዘውን መንገድ በመከተል በጉዟቸው ላይ ሁነው አጠር ያሉ ውይይቶችን እየተ ወያዩ ኋላ-ኋላዋ ይከተሏት ጀመር ።

የእርሷን ቤት ግቢ ሰዎቹ እንደደረሱ ወደ እነር ሱ ዞር ብላ እነርሱን በመመልከት ከደጃፉ ላይ ዝቅ በማለት እጅ ነሳቻቸው ።

«አመሰግናለሁኝ…» አለች ለስለስ ባለ እና ባለውለ ተኛ በሆነ አነጋገር ።

እና አዲሱን ሃሣብ በማስታወስም — በልቧ ውስጥ በጥልቀት የተወለደውን አዲስ ሃሣብ በማስታወስ — የሚከተለውን ጩምራ ተናገረች ፡ —

«ለፈጣሪ አምላክ ክብርን ለማስገኘት ሰዎች ሕይወታቸውን አሳልፈው ካልሰጡት ፈጣሪ አምላክ ሊኖር አይችልም ።»

የተሰበሰበው ሕዝብ በፀጥታ ሁኖ እርሷን-እርሷን ተመለከታት ።

አሁንም እንደገና የተሰበሰበውን ሰው እጅ ከነሳች በኋላ ወደቤቷ ገባች ። ሲዞሽም እጅ ከነሳ በኋላ ተከተላት ።

የተሰበሰቡት ሰዎች በራፉ ላይ ቆመው ለጥቂት ጊዜያት ተወያዩ ።

ከዚያም በዝግታ እርምጃ ጉዞአቸውን ቀጠሉ ።

# ክፍል ሁለት

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

እና አዲሱን ሃሣብ በማስታወስም — በልቧ ውስጥ በጥልቀት የተወለደውን አዲስ ሃሣብ በማስታወስ — የሚከተለውን ጨምራ ተናገረች ፡ —

«ለፈጣሪ አምላክ ክብርን ለማስገኘት ሰዎች ሕይወታቸውን አሳልፈው ካልሰጡት ፈጣሪ አምላክ ሊኖር አይችልም ።»

የተሰበሰበው ሕዝብ በፀጥታ ሁኖ እርሷን-እርሷን ተመለከታት ።

አሁንም እንደገና የተሰበሰበውን ሰው እጅ ከነሳች በኋላ ወደቤቷ ገባች ። ሲዞሽም እጅ ከነሳ በኋላ ተከተላት ።

የተሰበሰቡት ሰዎች በራፉ ላይ ቆመው ለጥቂት ጊዜያት ተወያዩ ።

ከዚያም በዝግታ እርምጃ ጉዞአቸውን ቀጠሉ ።

# ክፍል ሁለት

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

## 1

ቀሪው ቀን የትውስቶችን ጭጋግ ለብሶ ነፍ
ስ እና ሥጋዋንም ጨምድዶ በያዛት ድካም አለፈ ።
ከዓይኖቿ ፊት-ለፊት የትንሹ መኮንን ግራጫ መልክ ፤
የፓቬል ነሐስ-መሰል መልክ እና የአንድሬይ የሚስ
ቁ ዐይኖች ውል-ውል እያሉ ይመላለሱባት ጀመር ።
በቤቱ ውስጥ ከወዲያ-ወዲህ ትመላለሳለች ። መስኮቱ
አጠገብ ቁጭ ብላ ውጪ-ውጪውን ትመለከታለች።
እንደገና ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ ትነሳና ትንሽ
ድምፅ ኳ ባለ ቁጥር ብንን በማለት ሁኔታ ዓይኖቿ
ን ወደላይ በመክፈት ሽብሽብ አድርጋ ከወዲያ-ወዲ
ህ እየተመለከተች ትንጎራደዳለች ። ወይንም እንደው
በዘፈቀደ ያንንም-ያንንም ዕቃ ታገላብጣለች ። የውሀ
ጥሟን የማያረካላትን ፤ የተቃጠለ ልቧን እና ቅሬታዋ
ን የማያቀዘቅዝላትን ውሃ ጉርጉጭ-ጉርጉጭ እያደረገ
ች ጠጣች ። ቀኑ ከሁለት ላይ ግምስ ብሎ ተከፍሎባ
ታል ። የመጀመርያው ዕኩለ-ቀን ረብ ያለው ፤ ቀሪው
ዕኩለ-ቀን ደግሞ ፋይዳ ቢስ በመሆን የደረቀ ሲሆ
ን ፤ ሁኔታውም የሚከተለውን ጥያቄ እንድታሰላስል
አድሮጎአታል ፡ —

«እንግዲህ ምን ማድረግ ይሻለኛል?»

ኮርሱኖቫ ልትጠይቃት መጣች ። እጆቿን በማወዛወ
ዝ በቁጣ በብስጭት ተናገረች ። ወዲህ ታለቅሳለች ፤
ወዲህም በደስታ ተውጣለች ። እግሮቿን ከመሬቱ ጋር

ትደቃለች ። እንዴ ዛቻ ትዝታለች ። እንዴም ደግሞ
ቃል ትገባለች ፤ ሃሣብም ታቀርባለች ። አንዱም ድርጊ
ቷ ቢሆን እናትን አልሳባትም ።

«ሆሆይ! ሕዝበ-አዳም መሣርያውን አንግቦ ተነስቶ
አል! መላው የፋብሪካ ሠራተኛ ተነሳስቶአል! መላው
የፋብሪካ ሠራተኛ!» በማለት የቸርቻሪቷ የኮርሱኖቫ
ጎርነን ያለ ድምፅ ተሰማ ።

«አዎን!» አለች እናት ጭንቅላቷን በአዎንታ ነቅ
ነቅ እያደረገች ። ዐይኖቿ ግን ቀደም ካለው ጊዜ ጀ
ምሮ ከፓቬል እና ከአንድሬይ ጋር አብረው በተሰወ
ሩት ሁኔታዎች ላይ ትክ ብለው ያሰላስሉ ነበር ። ል
ቧ በሀዘን ተኮራምቶ በመድረቁ ምክንያት ማልቀስ
አልተቻላትም ። ከናፍሮቿ ደርቀዋል ። አፏም አንዳች
ም ርጥበት የሌለው በመሆን ደርቆአል ። እጆቿ ይንቀ
ጠቀጣሉ ። ከበስተጀርባዋ በኩልም አንዳች ቀዝቃዛ ነ
ገር ላይና-ታች ፍስስ-ፍስስ ይልባታል ።

በዚያን ምሽት ዣንዳርሞቹ መጡ ። አንዳችም መደ
ነቅ ወይንም ፍርሃት ሳታሳይ ተቀበለቻቸው ። ወደቤ
ት ሲገቡ ይንጫጩ የነበረ ከመሆኑም በስተቀር ፣ ሁ
ኔታቸውም የደስተኞች እና የረኩ ሰዎች ሁኔታ ነበር ።
ቢጫማ ፊት ያለው መኮንን ጥርሱን እየገለፈጠ የሚ
ከተለውን ተናገረ ።

«እንደምን ሰነበቱ? ባልሳሳት ከአሁኑ ጋር ለሦስተ
ኛ ጊዜ መገናኘታችን ነው ።»

እርሷ ግን የደረቀ ምላሷን በከናፍሮቿ መሀል
ብቻ አላወሰችው ። መኮንኑ ተደማጭ ለመሆን እየሞከ
ረ ብዙ አወራ ። ብዙ በማውራት የሚደሰት መሆኑ
ን ተገንዝባለች ። ከአንደበቱ የሚወጡት ቃላት ግን
አላበሳጯትም ። የቀረው ቀርቶ ንግግሮቹ ስሜትም አል
ሰጧትም ። ነገር ግን ፡ — «ለእግዚአብሔር እና ለንጉሥ
ተገቢውን አክብሮት እንዲሰጥ አድርገው ልጅዎን



ካላሳደጉ ተወቃሿ እርስዎ ነዎት ፣ እሜቴ» በማለት
ሲናገራት ቆማ ከነበረችበት ከበራፉ ጥግ ሁና የሚከተ
ለውን መለሰችለት ፡ —

«ልጆቻችን እኛን የሚዳኙን ዳኞቻችን ናቸው ። ይ
ኸንን የመሰለ አስቸጋሪ ጉዞ ሲጓዙ እኛ እነርሱን
ባለመከተላችን ወደፊት በሚገባ በእኛ ላይ ይዳኛሉ ።»

«ምንድነው የሚሉት? እስኪ ይናገሩ!» በማለት መኮ
ንኑ ጮኸ ።

«ልጆቻችን እኛን የሚዳኙን ዳኞቻችን ናቸው ነ
ው ያልኩት » በማለት እናት በረዥሙ እየተነፈሰች
ተናገረች ።

መኮንኑ ፈጠን አድርጎ እና በስጨት ብሎ የወረ
ወራቸው ቃላት ከእናት ጆሮ ሊደርሱ አልቻሉም ።

ማሪያ ኮርሱኖቫ እንድትገኝ የተደረገው ፍተሻ
በሚደረግበት ጊዜ እማኝ እንድትሆን ነበር ። ከፔላጊያ
ቀጥሎ ተቀምጣ ነበረ ። ፔላጊያን ግን አትመለከታት
ም ። መኮንኑ ጥያቄ በጠየቃት ቁጥር ለጥ ብላ እጅ
ከነሳች በኋላ ቀደም ሲል የተናገረችውን መልሳ-መላ
ልሳ እንደገና እንደሚከተለው ደግማ ትናገራለች ፡ —

«ክቡር ሆይ! እኔ ምንም አላውቅ ። ኑሮዬን በችር
ቻሮ ንግድ የምገፋ እና አንዳችም ነገር ለማወቅ
የማይቻለኝ መሃይምኑ ነኝ...»

«ዝም በይ!» አላት መኮንኑ ሪዙን እያሻሸ ። እንደ
ገና እጅ ነሳች ። ይሁን እንጂ ፊቱን ዞር ሲያደርግ
አፍንጫዋን በማሾፍ ቀሰረችበት ። ከዚያም ወደ እናት
ዞር ብላ ፡ —

«ድንጋይ ብላ!» በማለት ቀስ ብላ ተናገረች ።

እናትን እንድትፈትሽ በታዘዘች ጊዜ ዐይኖቿን
በልጠጥ በማድረግ መኮንኑን ትኩር ብላ ከተመለከተ
ች በኋላ ፡ —

«ክቡር ሆይ ፣ እንዲህ ያለ ነገር ማድረግ ኧረ እኔ አይሆንልኝም!» በማለት በፍርሃት ተናገረች ።

እግሩን ከመሬት ጋር በመድቃት ጮኸባት ። ማሪያ ዐይኖቿን ወደመሬት ጣል አደረገች ።

«እንግዲህ ምን ላድርግ ፣ ፔላጊያ ኒሎቭና ቁልፎ ዎን ይፈታቱ...» በማለት እናትን ነገረቻት ።

የእናትን ልብሶች ስትደባብስ ፊቷ ቀልቶ ነበር ።

«አይ እነዚህ ውሾች!» በማለት ቀስ ብላ ተናገረች ።

መኮንኑ ፍተሻው ወደሚካሄድበት ማዕዘን እያማተረ ፦

«አንቺ ፣ ምንድነው የምትይው?» በማለት በጩኸት ድምፅ ጠየቀ ።

«ክቡር ሆይ ፣ የለም ሴትን የሚመለከት ጉዳይ ነው!» በማለት ማሪያ በፍርሃት ተውጣ ተናገረች ።

በመጨረሻም እናትን ወረቀት ላይ እንድትፈርም አዘዛት ። የመጻፍ ልምድ በጎደለው እጅዋ ፊደሎችን በትልልቁ በመጻፍ እንደሚከተለው ፈረመች ፦

«ፔላጊያ ቭላሶቫ ፤ የሟች ሠርቶ-አደር ሚስት ።»

«ምንድነው የጻፍሺው? ለምንድነው ይኸንን የጻፍሺው?» በማለት መኮንኑ ፊቱን እያጠቆረ ተናገረ ። ከዚያም በትንሹ ሳቅ ካለ በኋላ ፦ «አይ እናንተ ባላገር መደዴዎች!» በማለት ተናገረ ።

ሄዱ ። እናት እጆቿን እጥፍጥፍ አድርጋ በስተመስኮቱ በኩል ትክ ብላ ውጪ-ውጪውን ታስተውላለች ። ይሁን እንጂ ምንም በአስተውሎ የምትመለከተው ነገር የሌለ ሲሆን ፣ ቅንድቦቿ ተሸብሽበው ከፍ ብለዋል ። ከናፍሮቿ ተጋጥመዋል ። መንጋጋዎቿን እርስ-በእርስ አጋጥማ በኃይል የነከሰች ሲሆን ፣ ሁኔታውም የጥርስ ሕመም እንዲሰማት አደረጋት ። የፋኖሱ ጋዝ እያለቀ ሄደ ። ክሩም ከመድረቁ የተነሳ ይንጣጣ ጀመር ። ብርሃኑም ደበዘዘ ። ፋኖሱን እፍ ብላ ካጠፋችው በኋላ ጨለማ ውስጥ ተቀመጠች ። በልቧ ውስጥ ባደረው ምሬት የተነሳ ትንፋሿን የምትተነፍሰው በመጠኑ ነው ። ዐይኖቿን እና እግሮቿን ሕመም እስኪሰማቸው ድረስ ወዲያው-ወዲያው ደጋግማ ታነሳ ነበር ። ማሪያ በስተመስኮቱ በኩል መጥታ በሰከረ ድምፅዋ ስትጣራ ሰማቻት ። ከዚያም ፦



. «የኔ ሚስኪን ፔላጊያ ፣ ተኙ እንዴ? የኔ ግልቱ ፣ እባክዎን ተኙ!» አለቻት ።

እናት ልብሷን ሳታወላልቅ ወደአልጋዋ ሂዳ ተኛች ። ድብን ያለ እንቅልፍም ወዲያውኑ ይዟት ሄደ ።

ከረግረጋማው መሬት ባሻገር ወደከተማ በሚወስደው መንገድ በኩል አንድ አሸዋማ ቢጫ ኮረብታ የምትወጣ መስሎ በሕልሟ ታያት ። ሠርቶ-አደሮች አሸዋ ከሚያግዙበት ኮረብታ ላይ ፓቬል ቆሞ ረጋ ባለው በእንድሬይ ጣዕመ ዜማ የሚከተለውን ሲያዜም ይታያታል፥ —

«ተነሳ ወዝ-አደር ተነሳና ታገል!..»

እጇቿን የዐይኖቿ ሽፋሽፍቶች ላይ አሳርፋ ልጅዋን እየተመለከተች የአሸዋውን ኮረብታ ተጉዛ አለፈች ። ሰማዩ ሰማያዊ ቀለም የተቀባ ሲሆን የፓቬል ቁመና ወለል-ግልጥ ብሎ ይታያታል ። በሕልሟ እርጉዝ ስለነበረች እና ሌላ ሕፃንም በእጅዋ ይዛ ስለነበረ ወደ እርሱ ዘንድ ለመቅረብ አፍራ ነበር ። ሕፃናት ኳስ ወደሚጫወቱበት መስክ እስክትደርስ ድረስ ጉዞዋን ቀጠለች ። ብዙ ሕፃናት ይጫወታሉ ። የሚጫወቱበት ኳስም ቀይ ነበር ። እጅዋ ላይ የነበረው ሕፃን ወደኳሱ ሮጦ ከሄደ በኋላ ይጮህ ጀመር ። ጡት አጠባችው እና ተመለሰች ። አሁን ግን ሳንጃቸውን በእርሷ ላይ የሰደሩ ወታደሮች ኮረብታው ላይ ቆመዋል ። ቁመ

ቱ ሊለካ በማይችል ሁኔታ ረዥም የሆነ፣ ከደመና የተሠራ፣ ምድራዊ ያልሆነ እና የደስ-ደስ ያለው ነጭ ቤተ ክርስቲያን ወደሚገኝበት ወደ መስኩ መሃል ፈጥና ሮጠች። የአንድ ሰው ሥርአተ-ቀብር ይፈጸም ነበር። የአስከሬኑ ሳጥን ትልቅ እና ጥቁር ሲሆን በሚገባ ተሸፍኖአል። ቄሱ እና ዲያቆኑ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የሚሄዱ ሲሆኑ፣

«ሃሌ-ሉያ፣ ክርስቶስ ተንስአ እሙታን...»

የሚለውን ዜማ ያዜማሉ።

ዲያቆኑ ጽናውን በሚያወዛውዝበት ጊዜ ወደርሷ እጅ እየነሳ ፈገግ ይላል። ብሩሳ ቀይ ፀጉር ያለው ሲሆን መልኩም እንደሳሞይሎቭ መልክ የደስ-ደስ ያለው ነው። በቤተ ክርስቲያኑ ቁብታ ውስጥ የፀሐይ ሰፋፊ ፍንጣቂዎች እንደነጫጭ እራፊ ጨርቆች እዚህም-እዚያም ብትንትን ብለዋል። ግራና ቀኝ በሚገኘው የመዘምራን መድረክ ላይ ሕፃናት፡—

«ሃሌ-ሉያ፣ ክርስቶስ ተንስአ እሙታን...»

የሚለውን ዜማ ያዜማሉ።

ቄሱ ድንገት ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በስተመሃል በኩል ቆሞ፡—«ያዟቸው!» በማለት የጩኸት ድምፅ ያሰማል። የተጎናጸፈው ልብሰ-ተክሕኖ ከላዩ ላይ ተገፍፎ የጠፋ ሲሆን ከላይኛው ከንፈሩ ላይ ግራጫ ሪዝ ይታያል። ሁሉም ሰው ሸሸ። እንደ ኾኾል ጭንቅላቱን የሚደፋው ዲያቆንም ጽናውን ወርውሮ በረረ። እናት ከሚሸሹት ሰዎች እግር ሥር የያዘችውን ሕፃን ጣለች። የሚሸሹት ሰዎች የሕፃኑን ራቁት አካል በፍርሃት በመመልከት ሳይረግጡት ቀሩ። እናት ተንበርክካ ወደሰዎቹ እንዲህ ስትል ትጮህ ጀመር፡—

«ሕፃኑን ትታችሁት አትሂዱ! እባካችሁ ውሰዱት!»



«ሃሌ-ሉያ፣ ክርስቶስ ተንስአ እሙታን...»

የሚለውን ዜማ ኾኾል እጆቹን ወደኋላው አድርጎ ያዜማል።

ጎንበስ ብላ ሕጻኑን አነሳች እና ቁርጥራጭ እንጨት የጫነ ተጎታች ጋሪ ላይ አስተኛችው። ኒኮ ላይ ከጋሪው ጎን-ጎን ፈገግ እያለ ይጓዛል።

«ይኸውልዎ ከባድ ሥራ ሰጡኝ...» በማለት ተናገረ።

ጎዳናዎቹ ቆሻሻዎች ሲሆኑ፣ ሰዎችም ከየቤቶቻቸው በስተመስኮት በኩል አንገቶቻቸውን አስግገው እያወጡ ይንቻቻሉ፣ ያፏጫሉ፣ እጆቻቸውን ያወዛውዛሉ። ዓየሩን ብረቱ ግልጽ ነው። ፀሐይቱ በደመቀ ሁኔታ ፈኪታለች። የትም ቦታ የጥላ ምልክት አይታይም።

«እምዬ፣ ሕይወት ይኸው ነው! ያዚሙ-ይዘምሩ!» በማለት ኾኾል ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ።

የሌሎቹን ሰዎች ድምፅ በጉልህ ድምፁ ውጦ እርሱ ራሱም መዘመር ጀመረ። ከነበረበት ተነስቶ ሄደ። እናትም ተከተለችው። ድንገት አነቀፋትና አንድ መድረሻ-መጨረሻ የሌለው፤ ባዶነቱ ከግራና ቀኝ የሚሰማት ጉድጓድ ውስጥ ጭው ጭልጥ ብላ ትወርድ ጀመር ...

እናት በቀዝቃዛ ላብ ተጠምቃ ከሕልሟ ነቃች። ሻካራ እና ወፍራም-ጥፍጥፍ የሆነ እጅ ልቧን ጨምድዶ በመያዝ የሚጨምቀው መስሎ ተሰማት። የፋብሪካው ጡሩምባ ሠራተኞቹን ኧረ ቶሎ ኑ በሚል ሁኔታ ደጋግሞ ይጠራ ነበር። ሁለተኛው ጡሩምባ መሆኑ ገባት። መጻሕፍቶች ቤቱ ውስጥ እዚያ እና እዚህ ተበታትነዋል። ዕቃዎች ምስቅልቅላቸው ወጥቶአል። የዣንዳርሞቹ ቡት መጫሚያዎች የጭቃ ዱካዎችን ወለሉ ላይ ለጣጥፈው አልፈዋል።

ፊቷን ለመታጠብም ሆነ የጧት ፀሎቷን ለማድረስ ሳትጨነቅ ተነስታ ቤቱን ማዘገጃጀት እና ማጽዳት ጀመረች ። ማዕድ ቤት ውስጥ ስትገባ በተሰበረው የአርማ ሰንደቅ ላይ የአርማው እራፊ ጨርቅ ተንጠልጥሎበት ተመለከተች ። አነሳችው ። ከዚያም ከምድጃ ሥር ልትከተው ቃጣች ። መለስ ብላ በማሰብ ፣ ትንሽ ከተነፈሰች በኋላ የአርማውን እራፊ ከሰንደቁ ላይ ከፈታችው በኋላ በጥንቃቄ አጣጥፋ ወደኪሷ ከተተችው ። ሰንደቁን በጉልበቷ ከሰበረችው በኋላ ምድጃው ላይ ወረወረችው ። መስኮቶቹን እና ወለሉን በቀዝቃዛ ውሀ ካጠበች በኋላ ሳሞቫሯን አቀጣጥላ ልብሷን ለበሰች ። ከዚያም ማዕድ ቤቱ ውስጥ ከሚገኘው መስኮት አጠገብ ቁጭ ብላ እንደገና የቀድሞውን ጥያቄ በሃሣቧ ታወጣ-ታወርድ ጀመር ፡—

«እንግዲህ ምን ማድረግ ይሻለኛል?»

የጧት ፀሎቷን ያላደረሰች መሆኑን በማስታወስ ከተቀመጠችበት ተነሳችና ቅዱስ ስዕሉ ወደተሰቀለበት ግድግዳ ሄደች ። እዚያም ሂዳ ለጥቂት ሰኮንዶች እንደቆመች እንደገና ተቀመጠች ። ልቧ ባዶ ነው ።

ትላንትና በከፍተኛ ድምፅ በየጎዳናዎቹ ላይ ጩኸት ያሰሙ የነበሩት ሰዎች ዛሬ በየቤቶቻቸው ራሳቸውን ደብቀው የዘወትር ስላልሆኑት ድርጊቶች የሚወያዩ ይመስል ሁሉም ነገር በሚያስገርም ሁኔታ ጭጭ-ምጭጭ ብሎአል ።

በወጣትነቷ ጊዜ አጋጥሟት የነበረ ጉዳይ ድንገት ታወሳት ። ንብረትነቱ የዛኡሳይሎቭ በሆነው ርስት ክልል ውስጥ የውሀ ላይ አበቦች የሸፈኑት ኩሬ ነበር ። አንድ ቀን በበልግ ወር በኩሬው በኩል ስታልፍ አንድ ጀልባ ኩሬው መሃል ተንሳፍፎ ተመለከተች ። ኩሬው ጥቁር እና የረጋ ሲሆን ፣ ጀልባው በጠወለጉ ቅጠሎች ተተብትቦ የቆመ ይመስላል ። ይህ ጀልባ ሰው



ወይንም መቅዘፊያዎች ሳይኖሩት በዚህ በማይንቀሳቀስ ውሃ ላይ በጠወለጉ ቅጠሎች ተተብትቦ በብቸኝነት የመቆሙ ሁኔታ በሰው ላይ አንድ የሀዘን-የትካዜ ስሜት ያሳድራል ። ይኸንን ጀልባ ወደ ውሀው ውስጥ ገፍቶ ያስገባው ማን ይሆን ፣ ለምንስ ይሆን በማለት ረዘም ላለ ጊዜ ከነበረችበት ቦታ ላይ ቆማ ቀረች ። የዛኑ ዕለት ምሽት ጥቁር ፀጉር ያላት እና ስትራመድ ፈጠን-ፈጠን የምትል አንዲት ቁመተ አጭር የሆነች እና በባለርስቱ መሬት ላይ ተቀጣሪ ከሆኑት መካከል የአንደኛው ሚስት የሆነች ሴት ኩሬው ውስጥ ገብታ ራሷን ያጠፋች መሆኑን ሰማች ።

እናት በእጅዋ ቅንድቦቿን እያሻሸች ስላለፈው ቀን ሁኔታ በሃሳቧ ታሰላስል ጀመር ። ከፊት ለፊቷ የተቀመጠውን ቀዝቃዛ ሻይ ትክ ብላ እየተመለከተች እና በፍላጎቷ ግን ለጥያቄዋ ሁሉ መልስ የሚሰጣት ብልህ እና ያልተኮፈሰ ሰው ለማግኘት እያሻት ረዘም ላለ ጊዜ በሃሣብ ተውጣ ተቀመጠች ።

ስትመኘው የቆየችው የተሟላላት ይመስል ፣ ኒኮላይ ኢቫኖቪች ከምሳ በኋላ ሊጠይቃት መጣ ። እርሱን እንዳየችውም ድንገት ተደናገጠች ፣ ከዚያም እርሱ ላቀረበላት ሰላምታ አጸፋውን ሳትመልስ የሚከተለውን ጥያቄ አቀረበችለት ፡—

«ለምን መጣህ? የለም ደግ አላደረግህም እዚህ ቢያዩህ አንተንም ይይዙሃል!...»

እጅዋን ጠበቅ አድርጎ ከጨበጣት በኋላ ፣ መነጽሩን ከዐይኖቹ ላይ ከፍ አድርጎ ወደርሷ ጠጋ ብሎ ተቀመጠ ።

«ለፓቬል እና ለአንድሬይ እኔ ቃል የገባሁበት ጉዳይ ነበር ። ይኸውም ፣ እነርሱ ተይዘው እሥር ቤት ቢገቡ እርስዎን በሚቀጥለው ቀን ወደከተማ ይዤዎት ለመሄድ ነው» በማለት ፈጠን አድርጎ ተናገረ ። ድ

ሞፁ ረጋ ያለ እና ስለእርሷ ደህንነትም የሚያስብ
ነበር ። «ቤቱ ተፈተሸ እንዴ?» በማለት ጠየቀ ።

«አዎን ። ትንሽም ሳያፍሩ እና ለሕሊናቸውም ሳይከ
ብዳቸው ሁሉንም ነገር አመሰቃቀሉት» በማለት መለ
ሰችለት ።

«እነርሱ ለምን ያፍራሉ ብለው ነው?» በማለት ኒ
ኮላይ ትከሻውን እየወዘወዘ ጠየቀ ። ከተማ ሂዳ መኖር
ለምን እንዳለባት ያስረዳት ጀመር ።

በጓደኝነት መንፈስ የተመላ ቅን አስተሳሰቡን መለ
ስተኛ በሆነ ፈገግታ አዳመጠች ። የሚያቀርባቸውን
ምክንያቶች አትገነዘባቸውም ነበር ። ይሁን እንጂ በእ
ርሷ ላይ ባሳደረው ዕምነት እና ፍቅር ተነካች ።

«የፓሻ ፍላጎት ይህ ከሆነ እና እኔም ለአንተ አን
ዳችም ችግር...» ብላ ሳትጨርስ

«ለዚህ አያስቡ እኔ ብቻዬን ነው የምኖረው ። አን
ዳንድ ጊዜ እሕቴ እኔ ዘንድ ለማረፍ ትመጣለች»
በማለት ንግግሯን አቋርጧት ተናገረ ።

«እኔ ግን ባንተ ወጪ አልኖርም» አለችው ።

«ሥራ እንድናስይዝዎ ከፈለጉ ሥራ እናገኝልዎታ
ለን» በማለት ኒኮላይ መለሰላት ።

ለእርሷ የሥራ ትርጓሜው ተያይዞ የሚገኘው ሊለ
ያይ በማይችል ሁኔታ ከልጅዋ ፣ ከአንድሬይ እና ከጓዶ
ቻቸው ተግባር ጋር ነው ። ወደኒኮላይ ተጠጋችና ዐይ
ኖቹን ትክ ብላ ትመለከት ጀመር ።

«በእርግጥ ታገኝልኛለህን?» በማለት ጠየቀችው ።

«እኔ ወንደላጤ ስለሆንኩኝ ይኸንን ያህልም የሚ
ሠራ ነገር የለም...» በማለት መለሰ ።

«የለም እኔ ስለዚህ አልነበረም የማስበው! የቤት
ውስጥ ሥራ አልነበረም የማስበው!» በማለት አለሳል
ሳ መለሰችለት ።

ረዘም አድርጋ ተነፈሰች ። እርሱ ግን አልገባውም



ነበርና ቅር አላት ። ዐይኖቹን ቁልጭልጭ እያደረገ
ፈገግ በማለት በሃሣብ ተውጦ ፦

«ጋዜጣ እያዘጋጀን እንድናወጣላቸው የጠየቁንን
የእነዚያን ገበሬዎች አድራሻ ፓቬልን ጠይቀው የሚያ
ገኙልን ከሆነ...» ብሎ ገና ንግግሩን ሳይጨርስ ፦

«አውቃቸዋለሁኝ!» በማለት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ
ተናገረች ። ከዚያም ቀጠል አደረገችና ፦

፣ «አገኛቸዋለሁኝ! አድርጊ ያላችሁኝንም ሁሉ አደር
ጋለሁኝ! በሕግ የተከለከሉ ነገሮችን ታሠራጫለች ብ
ሎ እኔን የሚጠረጥር ማንም አይኖርም ። እግዚአብሔ
ር ያመልክትህና ፣ ከዚህ ቀደም ጋዜጦችን በሕቡዕ
እየወሰድኩኝ በፋብሪካው ውስጥ እንዲሠራጭ አስረክ
ብ አልነበረምን?» አለችው ።

ስልቻዋን በጀርባዋ አዝላና ሰንደቋን በእጅዋ ይዛ
ጫካዎችን እና መንደሮችን እያቋረጠች በመጓዝ ገጠ
ር-ለገጠር የመዘዋወር ፍላጎት ድንገት ተቀሰቀሰባት ።

«የኔ ሸጋ ፣ እባክህን በዚህ ተግባር እንድሠማራ
አድርገኝ የትኛውም ቦታ መጓዝ እችላለሁኝ ። በጠቅ
ላይ ግዛቱ ውስጥ የሚገኙ ማናቸውንም መንገዶች
ልጓዝባቸው እችላለሁኝ ። በጋም ሆነ ክረምት እስከዕ
ለተ-ሞቴ ድረስ ተጓዥ እና ገስጋሽ እሆናለሁኝ ። ኧ
ረ ምኑ ላይ ነው ለኔ ከባድነቱ?» በማለት ጠየቀችው ።

ቤት-የለሽ ተጓዥ በመሆን ገጠር በሚገኙ በየመን
ደሩ ጎጆዎች እየተዟዟረች «በእንተ ስሟ ለማርያም ፣
ስለቸሩ እግዚአብሔር» እያለች ስትለምን ሁኔታው እን
ዴት እንደሚሆን ድንገት ፊቷ ላይ ድቅን አለባትና
ልቧ በቅሬታ ተመላ ።

ኒኮላይ ቀስ ብሎ እጅዋን ያዝ አድርጎ ሞቃት
በሆነ የውስጥ እጁ አሸት-አሸት አበስ-አበስ ያደርግላ
ት ጀመር ። ከዚያም ወደግድግዳው ሰዓት ተመለከተና ፦

«እሺ እንግዲህ በዚህ ጉዳይ በኋላ እንነጋገራለን!»
አላት ።

«በልባችን ማሕደር እጅግ የተፈቃሪነት ቦታ ያላ
ቸው ልጆቻችን ፣ ለገዛ ራሳቸው ቅንጣት ያህል ሳይሳ
ሱ ሕይወታቸውን እና ነፃነታቸውን አሳልፈው የሚሰ
ጡ ከሆነ ፣ እኔ እናት የሆንኩት ማድረግ የሚገባኝ
ለመሆኑ ምንድነው?» በማለት አለቀሰች ።

ኒኮላይ ደነገጠ ። በፍቅር ዐይን እና በጥሞና በማ
ዳመጥ እርሷን-እርሷን እየተመለከተ ዝግተኛ በሆነ
ንግግር ፡ —

«ከዚህ ቀደም ማንም እንደዚህ ሲናገር አልሰማ
ሁኝም...» አላት ።

እናት ጭንቅላቷን በሀዘን እየነቀነቀች እና እጆቿ
ንም በሀዘን አገላለጽ እየወዘወዘች ፡ —

«መቼስ ሌላ ምን ልናገር? በደረቴ ውስጥ ዶቅ-ዶ
ቅ እያለ የሚጮኸውን የልቤን ስሜት የሚገልጹል
ኝ ቢኖሩ ፣ እነዚህ የምናገራቸው ቃላት ናቸው...»

በአዕምሮዋ ውስጥ በሚመላለሱ እና ቁጡ በሆነ
የቃላት ነጎድጓዶች ኃይል ተገፋፍታ ከተቀመጠችበ
ት ተነሳች ።

«ብዙዎች ባለቀሱም ነበር ። እጅግ ሀፍረተ-ቢስ የ
ሆኑት እና እጅግም ወራዳ የሆኑት ጭምርም ባለቀሱ
ም ነበር!» በማለት ተናገረች ።

ኒኮላይ ከተቀመጠበት ተነሳ እና እንደገና ሰዓቱ
ን ተመለከተ ።

«እና እንግዲህ ተስማምተናል ማለት ነው ። ወደከ
ተማ መጥተው ከእኔ ጋር ይኖራሉ ። አይደለም እንዴ?»
በማለት ጠየቃት ።

በአዎንታ ራሷን ነቅነቅ አደረገች ።

«መቼ? በተቻለ መጠን ፈጠን ብለው» በማለት ከተ
ናገረ በኋላ ጨመር አድርጎ ንግግሩን በመቀጠልም ፡—



«ይኸንን እስኪያደርጉ ድረስ ስለእርስዎ ከማሰብ
አላቋርጥም» በማለት ተናገረ ።

በመደነቅ ተመለከተችው ። ይኸን ያህል መጨነቁ
ለመሆኑ ምኑ ሁና ነው? ተራ ጥቁር ካፖርት ለብሶ ፣
የዐይነ-አፋር ፈገግታ ፈገግ እያለ ጭንቅላቱን በአንድ
ወገን ዘንበል አድርጎ ይኸ የቅርብ አሳቢዋ-አፍቃሪ
ዋ ቆሞአል ። አቋቋሙ ባሕርዩን ይቃረነዋል...

«ገንዘብ አለዎትን?» በማለት ዐይኖቹን ወደምድር
ጣል አድርጎ ጠየቃት ።

«የለኝም!» በማለት መለሰችለት ።

ወዲያውኑ እጁን ኪሱ ከትቶ ከገንዘብ መያዣ
ቦርሳው ገንዘብ አወጣና ፡ —

«እነሆ ፣ እባክዎ ይቀበሉኝ...» በማለት ጠየቃት ።

እናት ወዳ ሳይሆን ከቁጥጥሯ ውጪ ፈገግ አ
ለች ።

«ሁሉም ነገር ለአንተ የተለየ ነው!» በማለት ጭ
ንቅላቷን በአድናቆት እያወዛወዘች ተናገረች ። ከዚያም
ቀጠል አደረገችና ፡ —

«ገንዘብ እንኳን ቢሆን ለአንተ ቁም ነገር የለው
ም ። አንዳንድ ሰዎች ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ የገዛ
ራሳቸውን ነፍስ እንኳን ይሸጣሉ ። አንተ ግን ገንዘብ
ን ከመጤፍ እንኳን አትቆጥረውም! ለሰዎች በጎ ለመ
ዋል ስትል ብቻ ገንዘብን የምትይዝ ይመስላል...»
አለችው ።

ኒኮላይ በቀስታ እና መለስተኛ በሆነ ሁኔታ ከት
ከት ብሎ ሳቀ ። ከዚያም ፡ —

«እንደገንዘብ መጥፎ ነገር የለም ! ሲሰጡም ሆነ
ሲቀበሉ ደስ አያሰኝም...» በማለት ተናገረ ።

እጅዋን ያዝ አደረገና ጠበቅ አድርጎ ጨበጣት ።

«በተቻለዎት ቶሎ ይምጡ!» በማለት እንደገና ደግ
ሞ ነገራት ።

ከዚያም ዝግ ባለ እርምጃ ወጥቶ ሄደ ።

በሩ ድረስ ስትሸኘው የሚከተለው ሃሣብ በአዕምሮዋ ውስጥ ይመላለስ ጀመር ፡ —

«እንዲህ ያለ ደግ ሰው ። ምነው እንዲህ ባልተቸገረ...»

በሁኔታው ደስ የተሰኘችም ትሁን ወይንም የተደነቀች ለይታ ለማወቅ አልቻለችም ።

## 2

ኒኮላይ መጥቶ እናትን በጎበኘ በአራተኛው ቀን ቤቷን ለቅቃ ወደ እርሱ ቤት ገባች ። ሁለት ሰንዱቆቿን የተሸከመው ጋሪ የመኖርያ ቤቶቹን አካባቢ እየለቀቀ ሜዳ-ሜዳውን ሲጓዝ ፣ ዞር ብላ የመኖርያ ቤቶቹን አካባቢ ትመለከት ጀመር ። ይህ ጭለማማ እና አስቸጋሪ የሆነ ኑሮ ያሳለፈችበት ቦታ ፣ እንደገናም አዳዲስ ደስታዎችን እና ሀዘኖችን ተጎናጽፋበት ቀናቱ ቶሎ ቶሎ እንዲገፉ ለማድረግ ያበቃት የዚህ ቦታ ሁኔታ ድንገት በሃሣቧ ውል አለባት ።

ጥላሸት ለብሶ በጠቆረው መሬት ላይ የተንሠራፋው እና ጭሱ ወደሰማይ ቡል-ቡል የሚለው ፋብሪካ ባሻገር ሲመለከቱት ትልቅ ቀይ ሸረሪት ይመስላል ። ከበታቹ የወዝ-አደሮቹ ጎጆዎች ተገጥግጠዋል ። እነዚህ ግራጫ እና ዳሳሳ የሆኑ ትንንሽ ጎጆዎች ትናንሽ መስኮቶቻቸው ተከፍተው እርስ-በእርሳቸው በትካዜ እና በደስታ-ቢስነት እየተመለካከቱ የረግረጋማውን መሬት ጠርዝ ተጠግተው ፤ እርስ በእርስም ተጠጋግተው ተቀልሰዋል ። ከቤቶቹ በላይ ቤተ ክርስቲያኑ ይገኛል ። የጉልላቱ ቁመት ከፋብሪካው ጭስ መውጫዎች ቁመት ዝቅ ያለ ሲሆን ልክ እንደፋብሪካው ጥላሸት የለበሰ ቀይ መልክ አለው ።



እናት ትንፋሿን እየተነፈሰች አንገቷን አንቀው የያዟት የመሰላትን የቀሚሷን ከሳዶች ቁልፎች ፈታች ።

ጋሪ ነጂው ልጓሙን ያዝ-ለቀቅ ፣ ያዝ-ለቀቅ እያደረገ ፈረሱን ፡ — «ሱ ! ሂድ! ሂድ!» ይል ጀመር ። የጋሪ ነጂው እግሮች እንደ ደጋን የጎበጡ ፣ ዕድሜው ይኸን ያህል ነው ለማለት የማያመች ፣ ጭንቅላቱን እና ፊቱን የሳሱ የመነመኑ ፀጉሮች የወረሩት ፣ ዐይኖቹ ቀለም-አልባ የሆኑ አጭር ድንክ ነው ። አንዴ ከጋሪው በአንደኛው ጎን ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በሌላኛው ጎን እየሆነ ጋሪውን ተከትሎ በእግሩ ሸፈፍ-ሸፈፍ ወልከፍ-ወልከፍ እያለ ይሄዳል ። በስተግራም ሆነ ወይንም በስተቀኝ በኩል ሁኖ መጓዙ ለርሱ አንዳችም ልዩነት የሌለው ይመስላል ።

በጭቃ የተለወሱ ትልልቅ ቡት ጫማዎች ያጠለቁትን ኩርንችት የሚያካክሉ እግሮቹን በሚያስቅ ሁኔታ ከመሬቱ ጋር እየደቃ ፈረሱን በሰለለ ድምፁ ፡— «ሂድ! ሂድ!ሱ!» ይለዋል ። እናት ያለችበትን አካባቢ ትቃኛለች ። መስኮቹ ልክ እንደ ልቧ ባዶ ናቸው...

ፈረሱ የፀሐዩ ዋዕይ ባሞቀው አሸዋ ሥር አንገቱን ለብዙ ጊዜ ወደታች ቀልሶ ጎተት-ጎተት እያለ ይጓዛል ። አሸዋውን ፈረሱ እና ጋሪው ሲጓዙበት ይንኮሻኮሻል ። ውልቅልቁ የወጣው አሮጌ ጋሪ በአሸዋው ላይ ሲጓዝ ሲጢጥ-ሲጢጥ እያለ ይጮኻል ። እነዚህ ድምፆች ከአቧራው ጋር በአንድነት ተደምረው ኋላ-ኋላቸው ይቀራሉ...

ኒኮላይ ኢቫኖቪች በከተማው ዳርቻ አንድ ብቸኛማ ሁኖ ወጣ ያለ ቦታ ላይ ይኖራል ። በእድሜው አርጅቶ ሊፈነዳ የተቃረበውን ባለሁለት ፎቅ ቤት ፎቅ አነስተኛ ግራጫ ክንፍ ተጠግቶ የተሠራው ቤት ውስጥ የኒኮላይ መኖርያ ቤት ይገኛል ። ከመኖርያ

ቤቱ ፊት-ለፊት አነስተኛ የሆነ የአትክልት ቦታ የሚ
ገኝ ሲሆን ፣ ሦስት ክፍሎች ባሉት በዚህ ቤቱ መስኮ
ቶች በስተውጪ ጥግጥጉን መአዛቸው ደስ የሚያሰኝ
እና ብሩህ ወይን ጠጅ ቀለም ያላቸው ቅጠለ-ብዙ
አበባዎች እና የጥድ ዛፎች ፣ እንደዚሁም በረዥም ቁመ
ት ቶሎ የሚያድግ የዛፍ ተክል ቅርንጫፎች ደስ በ
ሚያሰኝ ሁኔታ በሦስቱ መስኮቶች በኩል ሰገግ ብለ
ው አሾልቀዋል ። ቤቱ ውስጥ የሚገኘው ማናቸውም
ነገር ንፁሕ ሁኖ ቦታ-ቦታውን ይዞ የሚገኝ ሲሆን
ወለሉ ላይም የዕቃዎች ጥላ አጥልቶአል ። በቤቱ ውስ
ጥ ያሉት ግድግዳዎች በመጽሐፍ መደርደርያዎች የተ
ከበቡ ሲሆኑ ከመጽሐፍ መደርደርያዎቹ በላይም ፊ
ት-ኮስታራ የሆኑ ሰዎች ፎቶግራፎች ተሰቅለዋል ።

አንዱ መስኮት በጓሮው አትክልት ፊት-ለፊት ፣ ሌ
ላው መስኮት ደግሞ የሳር ጨፌ በሚገኝበት በኩል
ወደተሠራበት ትንሽ ክፍል ኒኮላይ እናትን እየወሰዳ
ት ፦

«ይኽ ክፍል ይስማማዎታልን?» በማለት ጠየቃት ።
የዚች ክፍል ግድግዳዎችም በመጽሐፍ መደርደርያ
ተከብበዋል ።

«ምግብ ማብሰያው ክፍል ብኖር ይሻላል! የምግብ
ማብሰያው ክፍልም አስደሳች እና ንጹህ ነው...»
በማለት እናት ተናገረች ።

ከአንደበቷ የሚወጡት ቃላት የሚያስፈራሩት መ
ሰላት ። ምግብ ማብሰያው ክፍል ልኑር የሚለው ሃሣ
ቧን እንድትተው በመጨረሻ እንደምንም ተሟግቶ
ሊረታት ሲበቃ መልኩ ወዲያውኑ በደስታ ፈካ ።

የቤቱ ሦስቱም ክፍሎች ልዩ የሆነ ግርማ-ሞገስ
ያረበበባቸው ናቸው ። እነዚህ ክፍሎች ውስጥ ሁኖ
መተንፈስ ቀላል እና አስደሳችም ነው ። ይሁን እን
ጂ ፣ ጎላ ባለ ድምፅ መነጋገር ፣ በታላቅ ተመስጦ ተው



ጠው ከላይ ወደታች የሚመለከቱትን ግድግዳዎቹ ላይ
የተሰቀሉትን ፎቶግራፎች መረበሽ ይመስላል ።

ከመስኮቶቹ ክፈፍ ላይ በእንስራዎች የተቀመጡ
አበባዎችን ያቀፉትን አፈሮች በእጅዋ እየነካካች ፦

«አበባዎቹ ውሀ መጠጣት ያስፈልጋቸዋል!» በማለት
ተናገረች ።

«አዎን ፣ ዕውነትዎን ነው! አበባዎቹን በጣም እወዳ
ቸዋለሁኝ ። ተንከባክቦ ለመያዝ ግን ጊዜ አላገኘሁ
ኝም...» በማለት በጥፋቱ ተጸጽቶ የቤቱ ባለቤት ኒ
ኮላይ ተናገረ ።

ምቹ በሆነው በገዛ ቤቱ ውስጥ እንኳን የውጪ
እንግዳ ሰው ይመስል ኒኮላይ ሲራመድ ተጠንቅቆ የ
ሚራመድ መሆኑን እናት አስተዋለች ። ቀጫጭን በሆኑ
ት የቀኝ ጣቶቹ መነጽሩን ገፋ-ገፋ እያደረገ ከሚገኙ
ት ልዩ-ልዩ ዕቃዎች መካከል ዐይኑ ያረፈበትን አን
ደኛውን አተኩሮ ያስተውላል ። አንዳንድ ጊዜ አንዱን
ዕቃ በዐይኑ የሚዳስሰው ይመስል ፣ ፊቱ አጠገብ አስ
ጠግቶ ይመለከታል ። እርሱም ልክ እንደ እናት እቤ
ቱ ውስጥ ለመጀመርያ ጊዜ የገባ ይመስል በቤቱ
ውስጥ የሚገኘውን ማናቸውንም ነገር ልክ እንደ
እናት ለእርሱም አዲስ እና ካሁን ቀደም ያላየው ይመ
ስላል ። ይኽ ሁኔታ እናትን እንድትዝናና አደረጋት ።
ዕቃዎቹ የሚገኙባቸውን ቦታዎች አተኩራ በማስተዋ
ል እና ዕለታዊ ትዕዛዝ በመጠየቅ በክፍሉ ውስጥ
ትከተለው ጀመር ። ሊፈጽም ባለመቻሉ ምክንያት ጉዳ
ዮችን መፈጸም በሚገባው ሁኔታ የማይፈጽም ሰው
የሚያሳየውን ዓይነት የቅሬታ ድምፅ እያሰማ መልስ
ይሰጣት ነበር ።

አበባዎቹን ውሀ አጠጣቻቸው ፣ ፒያኖው ላይ ተበ
ታትነው የነበሩትን የዜማ ኖታዎች በወግ-በወጉ አድ
ርጋ አስቀመጠቻቸው ። ሳሞቫሩን ከተመለከተች በኋላ ፦

«መወልወል ያስፈልገዋል·.» አለችው ።

ሳሞቫሩን አንስቶ አፍንጫው ሥር በማስጠጋት መወልወል ማስፈለግ አለማስፈለጉን ይመለከት ጀመር ። እናት በሁኔታው ሳቀች ።

በዚያን ምሽት እናት ወደ መኝታ ክፍሏ ሂዳ እንደተኛች ቀኑን እንዴት እንዳሳለፈች ስታሰላስል ከትራሷ አንገቷን ቀና አድርጋ ግራ-ቀኙን በመገረም ትቃኝ ጀመር ። በሌላ ሰው ቤት ስታድር ይህ የመጀመርያ ጊዜዋ ቢሆንም የመጨነቅ ስሜት አልተሰማትም ። ስለ ኒኮላይ ደግ-አሳቢ መሆን አሰላሰለች ። ማናቸውም ሁኔታ ለእርሱ አስደሳች እንዲሆን ለማድረግ ፣ ለሕይወቱ ምቾት እና ደስታ ሊያስገኝለት የሚችል ፍቅሯን ልታሳየው ፈለገች ። ከአፈጣጠሩ ገልጀጅ ያለ መሆኑ ፣ ቅልጥፍና የሚጎድለው ሁኖ የማስደሰቱ ሁኔታ ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲነጻጸር የርሱ የባሕርይ ልዩነት ፣ የብልህ ሰው አመለካከቶች ቢሆኑም እንደ ሕጻን ልጅ ዐይኖች ክብልል-ክብልል በሚሉት በዐይኖቹ አመለካከቶች ልቧ ተነካ ። ከዚያም ሃሣቧ ወደ ልጅዋ ተመለሰ ። አዲስ ድምፅ እና አዲስ ትርጓሜ ለብሰው እንደገና የሜይ ዴይ ድርጊቶች ትውስት ትዝ ይላት ጀመር ። ልክ እንደዚያ ቀን ሁሉ ፣ በዚያን ቀን የደረሰው ሀዘንም የተለየ ሁኔታ ያለው ነው ። በጠንካራ ሰው የተሰነዘረ ቡጢ ከመሬት እንደሚደባልቅ ሁሉ ፣ በዚያን ዕለቱ ሀዘን በተሰነዘረው ቡጢ ዓለም ጭንቅላቷን ቀለስ እንድታደርግ አላበቃም ። መጠነኛ የሆነ ቁጣ እንዲነሳሳ በማድረግ ልብን ደጋግሞ እየጠቀጠቀ በመውጋት ጎብጦ የነበረው ትከሻ ቀና እንዲል አድርጎአል ።

«ልጆቻችን በዚች ዓለም ውስጥ ወደፊት እየገሰገሱ ናቸው» በማለት አሰላሰለች ፣ በአትክልቱ ስፍራ ውስጥ ያሉትን የዛፎች ቅጠሎች እያንኮሻኮሹ ድምፃ



ቸውን በስተመስኮቱ በኩል የሚያስተላልፉትን የከተማ ዝግተኛ እንቅስቃሴዎች እና ከዚህ ቀደም አድምጣ የማታውቀውን የከተማ የምሽት ድምፅ ለመጀመርያ ጊዜ አደመጠች ። ድምፆቹ መጥተው የሚሰሙት ከሩቅ ሲሆን ፣ ሁኔታቸውም የተዳከመ እና ከመስኮቱ ዘንድ ሲደርሱም እየሰለሉ የሚሄዱ ናቸው ።

በማግሥቱ ጧት ማለዳ ላይ ሳሞቫሩን ወለወለችው ። ለሻይ ውሀ ካፈላች በኋላ ድምፅ ሳታሰማ ጠረጴዛውን በማዘጋጀት ኒኮላይ እስኪነሳ ድረስ ማዕድ ማብሰያው ክፍል ሁና ትጠብቀው ጀመር ። በመጨረሻም በአንድ እጁ መነጽሩን ይዞ እና በሌላ እጁም የሸሚዙን ክሳድ ይዞ ሳሉን እየሳለ በሩን ከፈተ ። ከዚያም እንደምን አደሩ? በማለት ላቀረበላት ሰላምታ መልስ ከሰጠችው በኋላ ሳሞቫሩን ይዛ ወደሳሎን ገባች ። እርሱም ውሀውን ወለሉ ላይ እያንጠባጠበ ፣ ሳሙናው እና የጥርስ ብሩሹ ከእጁ እየወደቀበት ፊቱን ፉ-ር-ር ፣ ፉ-ር-ር እያለ ይታጠብ ጀመር ።

ቁርስ ላይ ሁነው የሚከተለውን ነገራት ፡ —

«ገበሬዎች እየወደቁ እየደቀቁ እንዴት እንደሚሄዱ ፣ በዜምስትቮ* ቦርድ ውስጥ አሳዛኝ የሆነ የታዛቢነት ተግባር አከናውናለሁኝ...» አላት ። የፀፀት ሀዘን በተሰማው ሁኔታ ፈገግ ካለ በኋላ ንግግሩን በመቀጠል ፡ —

«ምግብ ባለማግኘት በችጋር መቆላት ገበሬዎችን ለሞት አመቻችቶ ያቀርባቸዋል ። ልጆቻቸው ሲወለዱ ደካማ ሁነው ይወለዳሉ ። እንደ በልግ ዝምቦ

---

* ዜምስትቮ — በሩሲያ ውስጥ ገባርነት ከተፋቀበት ከ 1861 ዓ. ም. ጀምሮ በዛሩ መንግሥት ተቋቁመው የነበሩ ሥልጣነ-ውሱን የሆኑ የአካባቢ የአስተዳደር አካላት «ዜምስትቮ» በመባል ይጠሩ ነበር ። (ተርጓሚው)

ች እየተረፈረፉ ያልቃሉ ። ይኸንን ሁሉ እናውቃለን ።
የጉዳዩን መነሻ-ምክንያትም እናውቃለን ። የቀረው-ቀር
ቶ ፣ ሂደቱን የምንታዘብ በመሆናችን ደሞዝ ይከፈለናል ።
እንደዕውነቱ ከሆነ ደግሞ ተግባራችን ይኸው ነው
እንጂ ፣ ከዚህ ሌላ ምንም የምናደርገው የለም…» በማ
ለት ተናገረ ።

«አንተ ተማሪ ነህ እንዴ?» በማለት ጠየቀችው ።

«የለም ተማሪ አይደለሁም ። መምህር ነኝ ። አባቴ
ቪያትካ ውስጥ የፋብሪካ አስተዳዳሪ ነው ። እኔ ግን
መምህር ሆንኩኝ ። ገጠር ውስጥ ለገበሬዎች መጻሕፍ
ትን በማሠራጨቴ ምክንያት ተይዤ ታሥሬ ነበር ።
የእሥራት ጊዜየን ከፈጸምኩኝ በኋላ በአንድ መጻሕፍ
ት መሸጫ ሱቅ ውስጥ በመጽሐፍ ሻጭነት ተቀጠር
ኩኝ ። በገዛ ራሴው ደንታ-ቢስነት እንደገና ተይዤ ከታ
ሠርኩኝ በኋላ አርኻንገልስክ ወደተሰኘ ከተማ በግዞ
ተኛነት ተጋዝኩኝ ። እዚያም እንደዚሁ ከአገረ-ገዢው
ጋር ባጋጠመኝ ግጭት ምክንያት ነጭ ባሕር ዳርቻ
አጠገብ ወደምትገኝ አንዲት ትንሽ መንደር እንድጋ
ዝ ከተደረግሁኝ በኋላ በዚችው መንደር ለአምስት
ዓመታት በግዞተኛነት ኖርኩኝ ።»

የፀሐይ ብርሃን በክፍሉ ገብቶበት ብሩህ በሆነው
የቤቱ ክፍል ውስጥ ከአንደበቱ የሚወጡት ቃላት
ምንም ሳያግዳቸው ዱብ-ዱብ ይላሉ ። እናት በአሁኑ
ጊዜ እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ታሪኮችን አድምጣ
ለች ። ይሁን እንጂ ፣ ከቶ ምንም ቢሆን እስከአሁን
ድረስ ሊገባት ያልቻለው ጉዳይ ፣ ታሪካቸውን የሚያወ
ሷት ሰዎች ታሪካቸውን በሚያወሷት ጊዜ እንደ
ዘወትር አልባሌ ጉዳይ አንዳችም ብስጭት ሳያድርባ
ቸው በዝግታ እና ርጋታ ባልተለየው ሁኔታ የሚያ
ወሷት መሆናቸው ነው ።

«እህቴ ዛሬ ትመጣለች!» አላት ።



«ባለትዳር ነችን?» አለችው ።

«የሙት ሚስት ነች ። ባሏ በግዞተኛነት ወደሳይቤ
ርያ ተግዞ ነበር ። ይሁን እንጂ ጠፍቶ አመለጠ ። ከዚ
ያም ከሀገር ውጪ ሲኖር ፣ የዛሬ ሁለት ዓመት በሳም
ባ ነቀርሳ ሕመም ሞተ…» አላት ።

«እሕትህ ከአንተ ወጣት ናትን?» ብላ ጠየቀችው ።

«የስድስት ዓመት ታላቄ ነች ። ለእኔ እጅግ ባለው
ለታዬ ነች ። መጥታ ፒያኖ እንዴት እንደምትጫወት
ያዳምጧታል ። ያ ፒያኖ የእርሷ ነው ። አብዛኛዎቹ እ
ነዚህ ዕቃዎችም የእርሷ ናቸው ። መጻሕፍቶቹ የእኔ
ናቸው…» አላት ።

«እሕትህ የምትኖረው የት ነው?» በማለት ጠየቀ
ችው ።

«የትም ነው የምትኖረው!» በማለት ፈገግ እያለ
መለሰላት ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፦

«መንፈሰ-ጠንካራ የሆነ ሰው በሚፈለግበት ቦታ
ሁሉ እርሷ ምንግዜም ዝግጁ ሁና ትገኛለች» በማለት
መለሰላት ።

«እርሷም በዚሁ ጉዳይ — በተግባሩ ተሳታፊ ነች
ን?» አለችው ።

«እንዴታ!» በማለት መለሰላት ።

እርሱም ወዲያውኑ ቤቱን ወጥቶ ሄደ ። እናትም
«ጉዳዩን» አንስታ በማሰላሰል ፣ በዚሁ ጉዳይ ዕለት-በዕ
ለት ተጠምደው ያለአንዳች መሸበር በርጋታ እና
በጽናት ራሳቸውን ለጉዳዩ የሰጡትን ሰዎች ብርታት
ታወጣ-ታወርድ ጀመር ። ሁኔታውን በሃሳቧ ታወጣ-ታ
ወርድ በነበረበት ጊዜም ፣ በምሽት ተራራ ሥር የሚገ
ኝ ሰው ራሱን ከተራራው ጋር ሲያነጻጽር ድባኖ-ድ
ንክ የሆነ ያህል አድርጎ እንደሚገምት ሁሉ ፣ እናትም
ሁኔታውን ስታነጻጽር ጥፍሯ ውስጥ ኩርምትምት ብ
ላ የገባች አጭር ድንክ ያክለች ሁና ተሰማት ።

ቀትር ላይ አንዲት ጥቁር ቀሚስ የለበሰች መልከ-መልካም ረዥም ሴት የቤቱን ደወል ደወለች ። እናት በሩን ስትከፍት ሴቲቱ ይዛው የነበረውን የመጻሕፍት መያዣ ቢጫ የእጅ ቦርሳ ወለሉ ላይ ጣል አደረገች እና የእናትን እጅ ጨበጠች ።

«እንደሚመስለኝ እርስዎ የፓቬል ሚካይሎቪች እናት ነዎት ። አይደሉምን?» በማለት ጠየቀቻት ።

«አዎን ። ነኝ ።» በማለት በሴቲቱ ጥሩ ልብስ እናት ግራ ተጋብታ እያስተዋለች መለሰች ።

«ሁኔታዎን ልክ እንደገመትኩት ሁኖ ነው ያገኘሁዎት ። እዚህ መጥተው እንደሚኖሩ ወንድሜ ጽፎልኝ ነበር» በማለት ሴቲቱ ከመስተዋቱ ፊት-ለፊት ሁና ባርኔጣዋን እያወለቀች ተናገረች ። ከዚያም ቀጠል አደረገችና ፡—

«ረዘም ካለ ጊዜ ጀምሮ ፓቬል ሚካይሎቪች እና እኔ ጓደኛሞች ነን ። ስለርስዎ አውርቶልኝ ነበር» በማለት ተናገረች ።

ድምፀ-ወፍራም ሁና ሳለ ፣ አነጋገርዋ ግን ዝግ ያለ ነው ። ስትራመድ ፈጠን-ፈጠን ያለች እና ጠንካራም ነች ። እዩኝ-እዩኝ እያሉ ከሚጋብዙት ቡናማ የወጣትነት ዐይኖቿ ጋር ሲነጻጸር ግንባሯ ላይ በቀጭኑ የተሰመሩ መስመሮች የተሸበሸቡባት ሲሆን ፣ ከጆሮዎቿ በላይ ያሉት ፀጉሮቿንም ሽበት ጣል-ጣል አድርጎባቸዋል ።

«እርቦኛል! አንድ ሲኒ ቡና ባገኝ እንዴት ደስ ባለኝ ነበር...» በማለት ተናገረች ።

«አሁን አዘጋጃለሁኝ!» አለቻት እናት ። ከዚያም ቀጠል አደረገችና ፡—

«ፓቬል ስለ እኔ አውርቶኛል አሉኝን?» በማለት የቡና ማስቀመጫውን ከቁም ሳጥን ውስጥ እያወጣች ጠየቀቻት ።



«ብዙ ጊዜ ደጋግሞ ስለርስዎ አጫውቶኛል...» በማለት ሴቲቱ ከቆዳ የተሠራ አነስተኛ የሲጋራ ማስቀመጫ አውጥታ አንዱን ሲጋራ አቀጣጥላ ከወዲያ-ወዲህ በመንጎራደድ ሲጋራዋን እያጨሰች መለሰችላት ። ከዚያም ቀጠል አደረገችና ፡—

«ስለእርሱ እጅግ አድርገው ሰግተዋልን?» አለቻት ።

ቡናው የተጣደበት በአልኮሆል የሚሠራ የቡና ማፍያ ላንቃ የሚተፋውን ሰማያዊ የእሳት ትንታግ እናት በመገረም እያስተዋለች ፈገግ ትል ጀመር ። በዚች ሴት ፊት የደረሰባትን ሀፍረት ደስታ ዋጠላት ።

«የኔ የተባረከ ልጅ ስለ እኔ አጫውቷታላ!» በማለት ከራሷ ጋር እናት ተወያየች ። ከዚያም ሴቲቱ ለጠየቀቻት ጥያቄ ቀስ ብላ በመመለስ ፡—

«አዎን ። ሰግቻለሁኝ እንጂ ። እንዴት አልሰጋም ። ቀላል ጉዳይ አይደለም ። ይሁን እንጂ ፣ ጉዳዩ ቀደም ባለ ጊዜ ደርሶ ቢሆን ኖሮ ካሁኑ የባሰ በሰጋሁኝም ነበር ። አሁን ቢያንስ-ቢያንስ ብቻውን አለመሆኑን አውቃለሁኝ...» በማለት ተናገረች ።

እናት ሴቲቱን እያስተዋለች ስሟ ማን እንደሚባል ጠየቀቻት ።

«ሶፍያ እባላለሁኝ!» በማለት ሴቲቱ መለሰችላት ።

እናት ሶፍያን ትኩር ብላ በማስተዋል ታጠናት ጀመር ። ይህች ሴት ልዩ የሆነ የራሷ ባሕርይ የሚታይባት ሲሆን ፣ ይኸውም ጮሌነት ያልተለየው ብርቱነቷ እና ፈጠን-ፈጠን የማለት ቀልጣፋነቷ ነው ።

«ዋናው ቁም ነገር በተቻለ ፍጥነት ሁሉም የሚለቀቁ መሆናቸው ነው» በማለት በመተማመን ሁኔታ ሶፍያ ተናገረች ። ቀጠል አድርጋም ፡—

«ብቻ ፍርዳቸውን ቶሎ በሰጡዋቸው! ወደ ግዞት ቦታቸው እንዳጋዟቸው ወዲያውኑ ፓቬል ሚካይሎቪች ከተጋዘበት ቦታ ጠፍቶ እንዲያመልጥ እናደርግ

ጋለን ። እርሱ እዚህ ለሥራ ያስፈልጋል» በማለት
ተናገረች ።

እናት በሶፍያ አነጋገር እርግጠኛ ባለመሆን ሁኔ
ታ ዐይን-ዐይኗን ስትመለከት ፥ ሶፍያ ደግሞ የሲጋራ
ዋን እሳቂ ነፈስ ለማጥፋት ማጥፊያ ዕቃ ትፈልግ
ነበር ። በመጨረሻም በአበባ መያዣው የሸክላ ገል
ላይ አጠፋችው ።

«ኧረ የሲጋራው ትርኳሽ አበባዎቹን ያጠወልጋቸ
ዋል!» በማለት እናት ሳትወድ ተናገረች ።

«ይቅርታ ያድርጉልኝ! ኒኮላይ ሁልጊዜም ይኸንኑ
ይነግረኛል!» በማለት ሶፍያ መለሰች ። የሲጋራውን ነ
ፈስ ከገሉ ላይ አነሳች እና በመስኮት ወደውጪ
ወረወረችው ።

እናት ቀደም ሲል በተናገረችው ንግግር ቅር ተሰ
ኝታና በመፀፀት ሁኔታ ሶፍያን ትመለከታት ጀመር ።
ከዚያም ፡ —

«ይቅርታ አድርጊልኝ! የምናገረውን ሳላስብ ነው
የተናገርኩት ። ምን ማድረግ እንደሚገባሽ እነግርሽ
ዘንድ ለእኔ እንዴት አድርጎ ይገባኛል?» በማለት ተና
ገረች ።

«ጽዱ ካልሆንኩኝ ለምን አይገባዎትም?» በማለት
'መናገር አለብዎት እንጂ' በሚል ሁኔታ ትከሻዋን
ወዝወዝ እያደረገች ተናገረች ። ከዚያም ቀጠል አደረገ
ችና ፡ —

«ቡናው ደረሰ እንዴ? አመሰግናለሁኝ ። ምነው አን
ድ ሲኒ ብቻ? እርስዎስ አይጠጡም እንዴ?» በማለት
ጠየቀቻት ።

ድንገት እናትን ትከሻዎቿን ያዘች እና አጠገቧ
አቅርባ ዐይን-ዐይኖቿን ትክ ብላ ትመለከት ጀመር
«ያለመዝናናት ጭንቀት ይሰማዎታልን?» በማለት
ጠየቀቻት ።



እናት ፈገግ አለች ። ከዚያም ፡ —

«ሲጋራውን በሚመለከት ረገድ ያንን ሁሉ ከለፈ
ለፍኩኝ በኋላ እንደምን አድርጎ የመዝናናት ሁኔታ
ላይሰማኝ ይችላል? እስኪ ጉድ በይ!» በማለት ተናገረ
ች ። ከዚያም አድናቆቷን ባለመሸሸግ ሁኔታ ቀጠል
አድርጋ ፡ —

«እዚህ ቤት ገና ትላንት መምጣቴ ነው ። ነገር
ግን ገና ካሁኑ ልክ የራሴው ቤት የሆነ መስሎ ይሰ
ማኛል ። የምፈራው አንዳችም ነገር የለኝም ። አሬ እን
ዳመጣ ማናቸውንም ነገር እናገራለሁኝ...» አለች ።

«መሆንም ያለበት ልክ ይኸው ነው!» በማለት
ሶፍያ በአንክሮ ተናገረች ።

«ጭንቅላቴ መዞሩን አላቆመም ። እና እኔም ራሴን
አላውቀውም» በማለት እናት ንግግሯን እንደሚከተለ
ው ቀጠለች ፡ —

«አንድን ሰው ደግሜ-ደጋግሜ ማንነቱን እስካው
ቅ ድረስ የልቤን ገልጬ የማልወያይበት ጊዜ ነበር ።
አሁን ግን ልቤ ምን ጊዜም ለማንም ግልጽ የሆነ
ሲሆን ቀደም ባለ ጊዜ እናገራቸዋለሁኝ ብዬ የማላል
ማቸውን ነገሮች በአሁኑ ጊዜ በግልጽ እናገራለሁኝ...»
አለች ።

ሶፍያ ሌላ ሲጋራ አውጥታ አቀጣጠለች እና ደስ
በሚያሰኝ ሁኔታ በሚያንጸባርቁት ቡናማ ዐይኖቿ እ
ናትን ትመለከት ጀመር ።

«ከግዞት ቦታው ያመልጣል ብለሽኛል ። ካመለጠ
በኋላ ግን እንደምን ሁኖ ይኖራል? ተደብቆ እና ተ
ሸሽጎ ሊኖር ነውን?» በማለት ይኸንን ለልቧ አስጨ
ናቂ የሆነ ጥያቄ እናት አውጥታ ጠየቀች ።

«ይኸ ከባድ ጉዳይ አይሆንም!» በማለት ሶፍያ
እንደገና ቡና በሲኒዋ እየቀዳች ተናገረች ። ከዚያም
ቀጠል አድርጋ ፡ —

«እንደሌሎቹ ብዙ ሰዎች ተሸሽጎ እና ተደብቆ
ይኖራል ። እነዚህን ከመሳሰሉት ሰዎች መካከል አንዱ
ን አግኝቼው ነበረ ። የት መኖር እንዳለበት አሳይቼ
ዋለሁኝ ። እርሱም በጣም አስፈላጊ የሆነ ሰው ነው ።
አምስት ዓመት ግዞት ተፈርዶበት ነበር ። በግዞት ያሳ
ለፈው ጊዜ ግን ሦስት ወር ተኩል ነው...» በማለት
ተናገረች ።

እናት ለጥቂት ጊዜ ሶፍያን ተመለከተቻት ። ከዚያ
ም ፈገግ አለች ።

«ያ ሜይ ዴይ አንዳች ነገር ያደረገኝ ይመስለኛ
ል!» በማለት እናት እራሷን እየነቀነቀች በዝግታ አነጋ
ገር ተናገረች ። ቀጠል አድርጋም ፡ —

«ሁለት መንታ መንገዶችን በአንድ ጊዜ የምሄዳ
ቸው ይመስል ግራ ገብቶኝ እጨነቃለሁኝ ። አንዳንድ
ጊዜ ሁሉንም ነገር የምገነዘብ ይመስለኛል ። ወዲያው
ደግሞ ሁሉም ነገር ግራ በሚያጋባ ሁኔታ ድብስብስ
ይልብኛል ። አንቺ ግን ፣ በዚህ ተግባር ላይ የተሠማራ
ሽ የተከበርሽ ሴት ነሽ ... የኔን ፓቬልን ታውቂዋለሽ ።
ስለእርሱም በጎ አስተያየት አለሽ ። ለዚህም አመሰግን
ሻለሁኝ...» አለቻት ።

«ምስጋና የሚገባው ለእርስዎ ነው!» በማለት ሶፍ
ያ እየሳቀች ተናገረች ።

«እኔ ምን ስላደረግሁኝ ምስጋና ይገባኛል ። ይኸንን
ሁሉ ያስተማርኩት እኔ አይደለሁኝም!» በማለት እና
ት እየተነፈሰች ተናገረች ።

ሶፍያ ሲጋራዋን ሳህን ላይ እያጠፋች ወርቃማ
ፀጉሯ እስከደረቷ ወርዶ ዝንጥፍ እስኪል ድረስ ራ
ሷን ዝቅ አድርጋ እጅ ነሳች ።

«እነዚህን ሁሉ ጥሩ-ጥሩ ነገሮች የማወላለቂያ
ጊዜዬ ደርሶአል...» በማለት ብድግ ብላ እየሄደች ተና
ገረች ።



# 3

ኒኮላይ ምሽቱ ላይ ወደ ቤት መጣ ። እራት በሚ
በሉበት ጊዜ ከግዞት አምልጦ የነበረውን ሰው እንደ
ምን አድርጋ እንዳገኘችው እና እንደደበቀችው ፣ ያየች
ውን ሰው ሁሉ በመጠርጠር ሰላዮችን እንደምን አድ
ርጋ ትፈራ እንደነበረ ፣ ጠፍቶ የነበረው ሰውም አስቂ
ኝ የሆነ ሁኔታ እንደምን አድርጎ ያሳይ እንደነበረ
እየሳቀች ሶፍያ ዘርዝራ አጫወተቻቸው ። እጅግ ፡ ከባድ
የሆነ ሥራን በሚገባ አኳኋን ያገባደደ ወዝ-አደር ስለ
ሥራው በኩራት ሁኔታ እንደሚናገር ዓይነት ሶፍያም
ሁኔታውን በዚሁ መልክ የምትናገር መሆኗን እናት
ተገነዘበች ።

አሁን እራት ላይ ሶፍያ የለበሰችው ልብስ ግራ
ጫማ ረዥም የበጋ ቀሚስ ነው ። የለበሰችው ልብስ
ይበልጥ ረዥም ያደረጋት ሲሆን ዐይኖቿም ይበልጥ
ጠቆር ያሉ ሲመስሉ አረማመዷም ይበልጥ ሥርአት
የያዘ ነው ።

«ሶፍያ ! ሌላ ተግባር ተደቅኖ ይጠብቅሻል» በማለት
ኒኮላይ የእራት ጊዜ እንዳበቃ ነገራት ። ቀጠል አድር
ጎም ፡ —

«ለገበሬዎች ጋዜጣ ለማተም መስማማታችንን ነግ
ሬሻለሁኝ ። ሰዎቻችን በብዛት ስለተያዙብን ጋዜጣውን
ከሚያሰራጨው ሰው ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ሳንች
ል ቀረን ። ይኸንን ሰው ሊያገኙልን የሚችሉት ፔላጊ
ያ ኒሎቭና ብቻ ናቸው ። ወደገጠር ከእርሳቸው ጋር
አብረሽ ሂደሽ በተቻለ ፍጥነት ግንኙነቱ እንዲመሠ
ረት ማድረግ አለብሽ» አላት ።

«በጣም ጥሩ!» አለች ሶፍያ ሲጋራዋን እያወጣች ።
«ፔላጊያ ኒሎቭና ፣ እንሄዳለን ። አይደለምን?» በማለት
እናትን ሶፍያ ጠየቀቻት ።

«አዎን እንሄዳለን» በማለት እናት መለሰችላት ።

«ሩቅ ነውን?» አለቻት ሶፍያ ።

«ሰማንያ ቬርስታ ያህል ቢርቅ ነው» በማለት መለሰችላት ።

«አይ ጥሩ ነው! አሁን እስቲ ሙዚቃ ልጫወት ። ፔላጊያ ኒሎቭና ትንሽ ብጫወት ቅር ይልዎት ይሆን?» በማለት ሶፍያ ጠየቀቻት ።

«ስለእኔ ምንም አታስቢ ። እኔ እንደሌለሁ በመቁጠር እንዳሻሽ ተጫወቺ!» በማለት ከሶፋው ላይ በስተዳር ኩርምት ብላ በመቀመጥ እናት መለሰችላት ። ወንድም እና እሕት እናትን ዞር ብለው የሚያዩዋት አይመስሉም ። ይሁን እንጂ በጮሌነት ሁኔታ በውይይታቸው ውስጥ እንድትገባ ያደርጉዋት ነበር ።

«ኒኮላይ ይኽንን አድምጥ ። ግሪግ የደረሰው ሙዚቃ ነው ። ዛሬ ነው ያመጣሁት… መስኮቱን ዝጋው» አለችው ሶፍያ ።

የሙዚቃውን ኖታ ከፈተችው እና በግራ እጅዋ በቀስታ ፒያኖውን መጫወት ጀመረች ። የሙዚቃ ድምፅ የሚያሰሙት የፒያኖው ሽቦዎች ጉላት እና ጥልቀት ያለው ድምፅ ያስተላልፉ ጀመር ። ከዚያም የፒያኖውን ጣዕመ-ዜማ ሌላ ድምፅ በዝግታ ያጅበው ጀመር ። በቀኝ እጅዋ ፒያኖው ላይ ስትጫወት ልዩ የሙዚቃ ድምፆች እንደተደናገጡ ወፎች አሁንም-አሁንም ይሰማሉ ።

የሙዚቃው ጣዕመ-ዜማ ጩኸት እና ጫጫታ ብቻ መስሎ ስለተሰማት እናት መጀመርያ በስሜት አልተነካችበትም ነበር ። ውስብስብ በሆነ የሙዚቃ ኀብር የተቀናበረውን የዚህን ሙዚቃ ጣዕመ-ዜማ አጣጥማ ለመቅመስ ጆሮዋ ገና በሚገባ አልተገራም ። እግሮቹን አነባብሮ ሶፋው ላይ በስተጥግ በመቀመጥ በወርቃማ ፀጉር ያሸበረቀውን የሶፍያን ገጽታ በተመ



ስጠ የሚያስተውለውን ኒኮላይ እናት በሕልም ዓለም የተዋጠች መስላ ታስተውላለች ። የሶፍያን እራስ እና ትከሻዎች ጉልህ በሆነ ሁኔታ ፀሐይቱ የምታንጸባርቀው ሲሆን ጣቶቿን ለመዳሰስም እስከፒያኖው ቁልፎች ድረስ ዝቅ ብላ ፀሐይቱ ወርዳለች ። የሙዚቃው ድምጽ እየጎላ-እየደራ ቤቱን መላው ። እናት ልብ ውስጥም ሳታስበው እና ሳትጠይቀው ጥልቅ ብሎ ገባ ።

በአንዳች ምክንያት ፣ እናት ከዘነጋችው ብዙ ጊዜ ከሆነው ከአንድ ካለፈ የብሶት አዘቅት ውስጥ መራራ በሆነ ሁኔታ ግልጽ እየሆነ በመታየት ብሶቷ ይቀሰቀስባት ጀመር ።

አንድ ምሽት ላይ ባለቤቷ በጣም ዘግይቶ ጥንብዝ ብሎ ሰክሮ ወደቤት መጥቶ ነበር ። በእጁ አፈፍ አድርጎ ካንጠለጠላት በኋላ ካልጋው ላይ አሽቀንጥሮ በማንሳት ወለሉ ላይ ወረወራት ። በእግሩ ጎኗን እየረገጠ ፡ —

«ሂጅ ከዚህ አንቺ ውሻ! ዐይንሽን ማየት ነው የጠላሁት!» በማለት ይጮህባት ጀመር ።

ወለሉ ላይ እንደተንጋለለች ከባልየው ድብደባ ራሷን ለመከላከል የሁለት ዓመት ልጅዋን ጎትታ ከባሏ ፊት አቆመችው ። ሕፃኑ እርቃኑን ሁኖ እና በፍርሃት ተውጦ እጆቿ ላይ በመውተርተር ያለቅስ ጀመር ።

«ሂጂ ከዚህ!» በማለት ሚኻኢል ጮኸ ።

ከወደቀችበት ወለል ላይ አፈፍ ብላ በመነሳት ወደ ምግብ ማዘጋጃው ክፍል ሮጣ ከሄደች በኋላ ትከሻዋ ላይ ጃኬቷን ጣል አድርጋ ፣ ልጅዋን በሸማ ጠቅልላ ፣ ሳታለቅስ ወይንም ሳታጉረመርም የማታ ልብስ ብቻ ለብሳ እና ጃኬት በላይዋ ላይ ጥላ ባዶ እግሯን ቤቱን ለቅቃ ሄደች ። ወራቱ የሜይ ወር ሲሆን የምሽቱ ዓየር-ንብረትም ውርጭ የተቀላቀለው ቀዝ

ቃዛማ ነበር ። የመሬቱ ቀዝቃዛ አቧራዎች እግሯ ውስጥ ልጥፍ ብለው ሲጣበቁ በእግር ጣቶቿ መካከልም ተሰግስገው ገቡ ። እጅዋ ላይ ያለው ሕፃን ልጅዋ ያለቅስ እና ይወራጭ ነበር ። ሕፃን ልጅዋን እቅፍ አድርጋ ጃኬቷ ውስጥ በመያዝ በፍርሃት ተውጣ ሕፃኗን በሚከተለው ሁኔታ እያባበለች መንገድ-መንገዱን, ትገሰግስ ጀመር ፡ —

«እ-ይ-ዞ-ህ! አይ-ዞህ! እ-ሽ-ሽ-ሽ!»

ንጋት ሆነ ። እርቃኗን እንደዚህ በገሚስ ተጋልጣ ድንገት ሰው ቢያያት ሐፍረቱ እና ፍርሀቱ ተሰምቷት ፤ ወደ ረግራጋማው መሬት ሂዳ ከአንድ ቅጠላማ ለጋ ዛፍ ሥር ተቀመጠች ። ዐይኖቿን ብልጥጥ አድርጋ በመክፈት በነጋጋው ጨለማ ውስጥ እየተመለከተች ፤ በእንቅልፍ የሚያንጎላጀውን ልጅዋን እና ሆድ የባሰውን ልቧንም ጭምር ፡ —

«እ-ይ-ዞ-ህ! እ-ሽ-ሽ-ሽ! እ-ይዞህ!» በማለት እሹሩሩ ትል ጀመር ።

ድንገት አንዲት ጥቁር ወፍ ብር አለች ።እንድትደነግጥ ወፊቱ እንደአስገደደች ተረዳች ። ዘንጋ ብላ ከነበረበት ሁኔታ ነቅታ በብርድ እየተንቀጠቀጠች ያውየለመደችው የዱላ እና የስድብ መዓት ወደሚወርድባት መከረኛ ቤቷ ማምራቷን ቀጠለች…

የመጨረሻው የፒያኖ ጣዕመ-ዜማ ድምፁን አሰማ ። ለስላሳ በሆነ ድምፁ ሙዚቃው አበቃ ።

ሶፍያ ወደ ወንድሟ ዞር አለች ፡ —

«ወደድከውን?» በማለት ረጋ ብላ ጠየቀችው ።

«እጅግ በጣም!» በማለት ከእንቅልፉ ገና አሁን የነቃ ይመስል እየተንጠራራ መለሰላት ። አሁንም ደግሞ ፡ —

«እጅግ በጣም…» አላት ።

የቀድሞ ትውስቷ በእናት ልቦና ውስጥ ደወሉን እየደጋገመ ደወለባት ። በሕሊናዋ ውስጥ ደግሞ የሌላ ሃሣብ ውጋጋን በሚከተለው ሁኔታ ውል-ውል እያለ ይታሰባት ጀመር ፡ —

«በወዳጅነት ላይ የተመሠረተ ሰላማዊ ኑሮን የሚኖሩ ሰዎች አሉ ። በዚያ ጭለማማ በሆነ ኑሮ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች እንደሚያደርጉት እርስ-በእርስ አይጣሉም ፣ አይሰክሩም ፣ ለየዳበው ቅርፊት እርስ-በእርስ አይቧጨቁም…» በማለት ታስብ ጀመር ።

ሶፍያ ሲጋራ መዘዘች ። ሳታቋርጥ በላይ-በላዩ ብዙ ሲጋራ አጨሰች ።

«ኮስቲያ የሚወደው ያንን ነበር!» አለች ። የሲጋራዋን ጢስ ምዋዋ አድርጋ ወደውስጥ ሳበችው ። እንደገና ወደፒያኖዋ አመራች እና ለስላሳ እና አሳዛኝ የሆነ ጣዕመ-ዜማ ትቃኝ ጀመር ።

«ለእርሱ ፒያኖ መጨዋት እንዴት ያስደስተኝ ነበር! ለማናቸውም ነገር አጸፋ የሚመልስ እና ልቡም በስሜት የሚነደፍ እንዴት ያለ ከፍተኛ ስሜት ያለው ሰው ነበር!» አለች ።

«ስለባሏ መሆን አለበት የምታስታውሰው ። መሆን አለበት!» በማለት እናት ቀስ ብላ ለራሷ ተናገረች ። ቀጠል አድርጋ ደግሞ ፡ — «ስታስታውሰው ፈገግም ትላለች!…» በማለት በቀስታ ለራሷ ተናገረች ።

«እንዴት ደስተኛ አድርጎኝ ነበር!» በማለት ሶፍያ በዝግታ አነጋገር ንግግሯን ቀጠለች ፡ — «እንዴት መኖር እንደሚገባ ያውቅ ነበር…» አለች ።

«አዎን-አዎን በእርግጥ እንጂ! መንፈሱ የሚያዜም የሚዘምር መንፈስ ነበር!» በማለት ኒኮላይ ጢሙን እያሻሸ ተናገረ ።

አሁን ገና ያቀጣጠለችውን ሲጋራ ሶፍያ ወረወረችው እና ወደእናት ዞር አለች ።

«የሙዚቃ ጫጫታዬ እንደማያውክዎ ተስፋ አደርጋለሁኝ ።» አለቻት ።

እናት ልቧ የቋጠረውን ቅሬታ ሳትሸሽግ የሚከተለውን መለሰችላት ፡ —

«ስለእኔ ምንም ችግር አይግባሽ ። ሙዚቃው ምንም አይገባኝም ። በገዛ ራሴ ሃሣብ ተውጬ ዝም ብዬ በመቀመጥ ነው የማዳምጠው...» በማለት መለሰችላት ።

«እኔ ግን የሙዚቃውን ጣዕም እንዲቀስሙት እሻለሁኝ ። አንዲት ሴት በተለይም በሀዘን እና በትካዜ በምትገኝበት ጊዜ የሙዚቃን ጣዕም መቅሰምን መገንዘብ አለባት...» አለቻት ።

የፒያኖውን ድምፅ ማሰሚያ ቁልፍ ጠበቅ አድርጋ በጣቶቿ መታችው ። አንድ ሰው አስደንጋጭ የሆነ ዜና ሰምቶ የሚጮኽ ያህል ፒያኖውም ድምፁን ከፍ አድርጎ በማንባረቅ ጮኸ ። ይኸንን የመሰለ አስደንጋጭ ድምፅ እንዲያሰማ ቁልፉ እስከመጨረሻው ድረስ የተመታ መሆን አለበት ። ከዚያም የፈሩ የተንቀጠቀጡ የሚመስሉ ቀጫጭን ድምፆች ከፒያኖው ውስጥ ወጥተው ተሰሙ እና ወዲያው ደግሞ ድምፆቻቸው እየበረሩ ጥፍት አሉ ። አሁንም እንደገና ወፍራሙ ጉልህ የፒያኖ ድምፅ ሌሎቹን ቀጫጭን ድምፆች እየዋጣቸው የጩኸት ድምፁን ያሰማ ጀመር ። አንድ የደረሰ ትልቅ መጥፎ-ዕድል አለ ። ይሁን እንጂ ፣ የሚያሰማው ድምፅ የመፀፀት ሳይሆን የቁጣ ስሜት የተመላበት ድምፅ ነው ። ከዚያም ግልጽ እና አስደሳች የሆነ ዜማን የሚያቀነቅን ፣ አድማጭን ማራኪ እና መሳጭ የሆነ ጠንካራ ድምፅ ፒያኖው ያሰማ ጀመር ።

እናት ለእነዚህ ሰዎች በጎ ቃላትን ለመናገር ተጠባበቀች ። የሙዚቃውን ጣዕመ-ዜማ ተግታ ሞክራ ነበር ። እናም ለእሕትየዋ እና ለወንድምየው የሚያስፈልጋቸውን



ነገር ለመፈጸም እርግጠኛ በመሆን በፈገግታ ተውጣ ትጠባበቅ ነበር ።

ወዲያ-ወዲህ ተመለከተች ። ከቶ ምን በማድረግ ልታስደስታቸው ትችላለች? ቀስ ብላ ወደ ምግብ ማዘጋጃው ክፍል በመሄድ ሳሞቫሩን አቀጣጠለችው ።

ይሁን እንጂ ፣ ይኸንን ማድረጓ ብቻ ለእነርሱ አደርግላቸዋለሁኝ ብላ ያሰበችውን በሙሉ እንዳሟላች አድርጎ ሊያረካት አልቻለም ። የእርሷንም ሆነ የእነርሱን ልብ የምታጽናና ይመስል ሻይ እየቀዳች እና ሀፍረት የተቀላቀለው ሳቅ እየሳቀች ፡ —

«እኛ ኑሮአችን ጨለማ የሆነብን ሰዎች እንደማንም እንደሌሎች ሁሉ ማናቸውም ነገር ይሰማናል ። በቃላት ለመግለጥ ግን ያስቸግረናል ። እና ስለዚህም እናፍራለን ። ምክንያቱም ፣ ማናቸውንም ነገር የምንገነዘብ ሲሆን አብራርተን እና አሳክተን መናገር ግን አንችልም ። እና ብዙውን ጊዜ ደግሞ ፣ የአስተሳሰባችን ሁኔታ ቅር እንዲያሰኘን ህሊናችን ያስገድደናል ። ሕይወት እኛን በየማዕዘናቱ ይወግረናል ፣ ይነርተናል ። ዕረፍት ማረፍ እንሻለን ። ዕረፍተ-ቢሱ ሃሣብ በእኛ ውስጥ ሳያቋርጥ እየተመላለሰ ዕረፍት ያሳጣናል» በማለት ተናገረች ።

ኒኮላይ የእናትን ንግግር እያዳመጠ መነጽሮቹን ይጠራርጋል ። ሶፍያ ዐይኖቿን ብልጥጥ አድርጋ በመክፈት የእናትን ንግግር ስታዳምጥ አቀጣጥላው የነበረውን ሲጋራ ሳታጨስ ረስታው ማለቂያው ተቃረበ ። ሶፍያ አዘውትራ የፒያኖውን መጫወቻ ቁልፎች በቀጫጭኑ የቀኝ ጣቶቿ በመንካት በገሚስ ወደ ወንድሟ ዞር ብላ ተቀምጣለች ። የፒያኖውን ቁልፎች ሶፍያ በጣቶቿ ነካ ስታደርጋቸው እናት ስሜቷን ከምትገልጽባቸው ከልቧ የመነጩ ቀላል እና ግልጽ ቃላቶች ጋር ድምፃቸው ተሳክቶ ይሰማል ።

«አሁን ስለ ራሴ እና ስለመላው ሰዎችም ትንሽ ነገር መናገር እችላለሁኝ ። ምክንያቱም መገንዘብ እና ማነጻጸር መቻል የጀመርኩኝ ስለሆነ ነው ። ቀደም ሲል ፣ አንዳችም የማነጻጽረው ነገር አልነበረም ። በእኛ ሕይወት አስተሳሰብ ሁሉም በተመሳሳይነት ይኖራል ። አሁን ግን ሌሎች ሰዎች እንዴት እንደሚኖሩ እና እኔም እንዴት እንደኖርኩኝ ስመለከት ሁኔታው መራር የሆነ ነው ።» አለች ። ከዚያም ድምፅዋን ዝግ አድርጋ ፡ —

«ምናልባትም ሃሣቤን ትክክል በሆነ ሁኔታ አላስቀምጠውም ይሆናል ። ምናልባትም ለእናንተ የማታውቁት አዲስ ነገር ስለሌለ ይኸንን መሳይ አባባል ማውሳት ፍሬ-ቢስ ይሆን ይሆናል…» በማለት ተናገረች ። ድምፅዋን የእንባ ሲቃ ይተናነቀዋል ። ዐይኖቿ ግን እነርሱን እየተመለከቱ ይስቃሉ ።

«የልቤን ለእናንተ ግልጥ-ግልጥልጥ ማድረግ እሻለሁኝ ። ለእናንተ ጥሩ-ጥሩውን ፣ አስደሳች-አስደሳቹን የምመኝላችሁ መሆኔን እንድታውቁት እሻለሁኝ!» በማለት ተናገረች ።

«አዎን ። ይኸን እናውቃለን!» በማለት ኒኮላይ ለስለስ ባለ ድምፅ ተናገረ ።

ቀደም ሲል ልታደርግላቸው ያሰበችው ምኞቷ ያልተሟላ መስሎ ስለተሰማት አሁንም ያልረካች መሰላት ። ስለዚህም ለእርሷ አዳዲስ እና ወደር በማይገኝለት ሁኔታ ጠቀሜታ ያላቸው መስለው ስለሚታዩዋት ነገሮች ሁሉ ታወጋቸው ጀመር ። መራር በሆነ የጥላቻ ስሜት ሳይሆን ፣ ፌዝ በተመላበት ሁኔታ ከንፈሮቿን ሞጥሞጥ-ነቅነቅ እያደረገች መራር ስለነበረው ኑሮዋ እና በትዕግሥት ስለተቀበለችው ስቃይዋ አወሳቻቸው ። ሚቿ ባሏ በላይዋ ላይ ላወረደባት የዱላ ውርጅብኝ ምክንያቶቹ እንዴት ዓይነት ከንቱ እንደነ



በሩ እና ከመደብደብ ለመዳን የማትችል እንደነበረች አንድ-በአንድ እየዘከዘከች በመግለጥ የዚያን የክፉ ጊዜ አኗኗሯን ሁኔታ የሚያብራራውን የወሬ መቀነቷን ትፈታላቸው ጀመር ።

ፀጥ ብለው ይኸንን ታሪኳን በሚያዳምጡበት ጊዜ ፣ ከእንስሳት ጥቂት ሻል ባላለ ሁኔታ ትታይ የነበረች አንዷት ሰብአዊት ፍጥርት ይኸንን መሳይ አኗኗርን በትህትና ለጥ-ሰጥ ብላ መቀበል ሊያሳድርባት የቻለውን ይኸንን የሕይወት ታሪኳን ምንነት ጥልቀት በአንክሮ ያሰላስሉ ጀመር ። በእርሷ አማካይነት ብዙ ሺህ ሰዎች የሚናገሩ ይመስላል ። የኖረችው ኑሮ ሁሉ ተራ እና አልባሌ የሆነ ኑሮ ነበር ። በዚች ዓለም ላይ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ሕዝቦች እንደሚኖሩት ያለ ተራ እና አልባሌ ኑሮን ነበር የኖረችው። እና የእርሷ ታሪክም አንድ የናሙናነት አርአያ አለው ። ኒኮላይ ጉልበቱን ጠረጴዛው ላይ አስደግፎ ጭንቅላቱን በእጆቹ ደግፎ ይዞ ዐይኖቹን በመነጽሩ ውስጥ ጠበብ አድርጎ በአትኩሮት እርሷን-እርሷን ያስተውላል ። ሶፍያ አንዳንድ ጊዜ ነቅነቅ እያለች እና ራሷንም በመደነቅ እየወዘወዘች ወንበሯ ላይ ትንሽ ጋለል ብላ ተቀምጣለች ። ፊቷ የከሳ እና የገረጣ መምሰል የጀመረ ሲሆን ፣ ሲጋራም አላጨሰችም ።

«አንድ ጊዜ እኔነቴን ዕድለ-ስንካላ አድርጌ ቆጥሬው ነበር» በማለት ሶፍያ ዐይኖቿን ወደመሬት ጣል አድርጋ ተናገረች ። ንግግሯን በመቀጠልም ፡ — «በቅዠት ዓለም ውስጥ የምኖር መስሎኝ ነበር ። ይኸ ስሜት ተሰምቶኝ የነበረበት ጊዜም በአንድ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ በምትገኝ ትንሽ ከተማ ውስጥ በግዞተኛነት ተግዤ በነበረበት ጊዜ ነበር ። ለራሴ ካልሆነ በስተቀር ፣ የማደርገው አንዳችም ፋይዳ ያለው ነገር አልነበረም ። የማስበው አንዳችም ጠቃሚ ሃሣብ አልነበ

ረም ። ጊዜየን ለማሳለፍ በማለት በሕይወት ያጋጠሙኝን መጥፎ-መጥፎ አጋጣሚዎች እንደገና እየደጋገምኩኝ አሰላስል ነበር ፡ — ከምወደው አባቴ ጋር ተጣልቼ ነበር ። ከትምህርት ቤት ተወግጄ የነበረ ሲሆን ፣ እንደ አሳፋሪ ምሳሌ እጠቀስም ነበር ። ታሥሬ ነበር ። አምኜው የነበረ የቅርብ ወዳጄ ከድቶኝ ነበር ። ባለቤቴ ተይዞ ታሥሮ ነበር ። እኔ እንደገና ተይዤ ከታሠርኩኝ በኋላ ወደ ግዞት ተግዤ ነበር ። ከዚያም ባለቤቴ ሞተብኝ ። በዚህች ዓለም ላይ ደስታ-ቢስ የሆንኩኝ ፍጥርት እኔ ብቻ ሁኜ ተሰማኝ ። ነገር ግን ደግሞ ፣ አዩ ፣ ፔላጊያ ኒሎቭና እኔን በሕይወት ዘመኔ ያጋጠሙኝ መጥፎ ዕድሎች በሙሉ ቢጠራቀሙ ፣ እና አሥር እጥፍ ሰንካላ ዕድሎች በላያቸው ላይ ቢጨመሩባቸውም በእርስዎ ላይ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የደረሰብዎትን ሰንካላ ዕድል አይስተካከሉትም ። የእርስዎ ሰንካላ ዕድል ከዓመት-ዓመት ሳያሰልስ ይዘልቅ የነበረ የዕለት-በዕለት ስቃይ እና ፍዳ ነበር... ይኸንን መሳይ ስቃይ ለመቋቋም ሰዎች ብርታትን የሚያገኙት ከቶ ከየት ይሆን?» በማለት ሶፍያ ተናገረች ።

«ይለምዱታል» በማለት ፔላጊያ ቁና እየተነፈሰች መለሰች ።

«የሕይወት ትርጉሚ ደህና አድርጎ ገብቶኛል በማለት እራሴን በከንቱ እሸነግላለሁኝ» በማለት ኒኮላይ በሃሣብ ባሕር ተውጦ ተናገረ ። ከዚያም ፡ — «ይሁን እንጂ ፣ ከመጽሐፍ የተቃረመ አመለካከት ሳይሆን ፣ ከገዛ ራሴም ውልክፍክፍ አመለካከት ሳይሆን የሕይወትን ትርጓሜ ሕይወትን እንደዚህ ከቀመሷት ከራሳቸው ከሰዎቹ አንደበት ሳዳምጥ ፣ ሕይወት አስደንጋጭ-አስበርጋጊ ሁና ትሰማኛለች ። እና ደግሞ ተጠራቅመው-ተጠራቅመው ዓመታትን የሚሞሉት አልባሌ የሆኑት እነዚህ የጊዜ አፍታዎች ናቸው ፣ እነዚህ ጥቃቅን ነገሮች ናቸው አስደንጋጭ-አስበርጋጊ የሚሆኑት...» በማለት ተናገረ ።



ይህችን ጭለማ የሆነች ሕይወት ከየትኛውም አቅጣጫ አገላብጠው በማስተዋል ብዙ አወሱ ። የወጣትነት ጊዜዋን የስቃይ ጊዜ እንዲሆን ያደረጉባትን እነዚያን በየዕለቱ ይደርሱባት የነበሩትን ስድቦች በማስታወስ በቀድሞው ድንግዝግዝ ባለ የሕይወት ዘመኗ ትውስት ተዋጠች ።

«ወይ ጉድ ፤ ወደምኝታ የመሄጃችሁ ሰዓት ደርሶ ሳለ ፣ እኔ ግን ዝም ብዬ አሁንም-አሁንም አወራችኋለሁኝ!» በማለት ተናገረች ። ከዚያም ቀጠል አደረገችና ፡— «መነገር የሚገባውን ሁሉ ተናግሮ መጨረስ አይቻልም ። ማብቂያ የለውም...» አለች ።

ወንድም እና እህት ፀጥታ በተመላው ሁኔታ ተሰናብተዋት ወደምኝታቸው ሄዱ ። ኒኮላይ ከወትሮው ይልቅ ይበልጥ ለጥ ብሎ እጅ የነሳት ይመስላል ። ፍጹም ልዩ የሆነ የአክብሮት ፍቅር በተመላበት አጨባበጥ እጅዋን ጠበቅ አድርጎ ጨበጣት ። ሶፍያ እናትን እስከምኝታ ክፍሏ ድረስ ሸኘቻት ።

«ደህና ይደሩ ። መልካም ዕረፍት ይሁንልዎ!» አለቻት ሶፍያ እናትን ክፍሏ ካደረሰቻት በኋላ ። የሶፍያ ድምፅ በከፍተኛ ስሜት ተውጦአል ። ቡናማ ዐይኖቿም እናትን ትክ ብለው ይመለከታሉ ።

ፔላጊያ የሶፍያን እጅ በሁለት እጆቿ ጭብጥ አድርጋ ያዘች ። ከዚያም ፡ —

«አመሰግናለሁኝ!..» አለች ።

## 4

ከጥቂት ቀናት በኋላ እናት እና ሶፍያ ያረጀ አልባሌ ልብስ የለበሱ የከተማ ሴቶች መስለው ኒኮላይ ዘንድ ቀረቡ ። ያለቁ የጥጥ ቀሚሶች እና ጃኬቶች ለብ

ሰዋል ። በጀርባቸው ስልቻ ፣ በእጆቻቸውም ዱላ ይዘዋል ። ይኸ አለባበሷ ሶፍያን አጭር አድርጓታል ። የገረጣ ፊቷም ይበልጥ ኮስታራ ሁኖአል ።

ኒኮላይ እህቱን በሚሰናበታት ጊዜ እጆቿን ጠበቅ አድርጎ ጨበጣት ። በሁለቱ መካከል ባለው የይስሙላ ያይደለ እና ርጋታ ያልተለየው ግንኙነታቸውን በመመልከት እናት እንደገና አደነቀች ። ሲሰነባበቱ ሳይሳሳሙ እና በጎ-በጎ ቃላትን ሳይለዋወጡ እነዚህ ሰዎች እርሱ-በእርሳቸው ልባዊ እና ፍጹም የሆነ መተሳሰብን በልባቸው ውስጥ ቀርጸው ያስቀራሉ ። እናት ከዚህ ቀደም ትኖርበት በነበረው በዚያ የመኖርያ ሠፈር ግን ነዋሪዎቹ ብዙ ይሳሳማሉ ፣ አዘውትረውም ለጆሮ ደስ የሚያሰኙ ቃላቶችን ይለዋወጣሉ ። ነገር ግን ሁል ግዜም እንደተራቡ ውሾች እርስ-በእርሳቸው ሲናከሱ ይኖራሉ ።

ሁለቱ ሴቶች እርስ-በእርሳቸው ምንም ሳይነጋገሩ የከተማውን ጎዳና ተያይዘውት በመገስገስ ከከተማው ውጪ የሚገኘውን ሜዳ ካለፉ በኋላ የገረጀፉ ነጫጭ ዛፎች ጎን እና ጎን በተተከሉበት ሰፊ እና ረዥም የሆነውን ጎዳና ትከሻ-ለትከሻ ገጥመው በመራመድ ተያያዙት ።

«መንገድ መሄዱ አያደክምሽምን?» በማለት እናት ሶፍያን ጠየቀቻት ።

«እስከዛሬ ጥቂት የተጓዝኩኝ ይመስልዎታልን? ረዥም ጉዞ መጓዝ ልማዴ ነው...» በማለት ሶፍያ መለሰችላት ። ደስተኛ ሁና እና የልጅነት ጊዜዋን አንድ ሁለት እያለች የምታወሳ መስላ ፣ ሶፍያ ስላከናወነቻቸው ሬቮሉሺናዊ ተግባሮች ለእናት ታወራላት ጀመር ። በዚህ በሬቮሉሺናዊ ተግባሯ የራሷ ባልሆኑ ልዩ ልዩ የፈጠራ ስሞች ተጠቅማለች ። በሀሰት ዶኩሜንቶች ተጠቅማለች ። ሰላዮች እንዳይይዟት ልትታወ



ቅ በማትችልበት ሁኔታ በተለያዩ የአለባበስ ዘዴዎች ተጠቅማለች ። ልዩ ልዩ በሆኑ ከተማዎች ሕገ-ወጥ ተብለው የሚቆጠሩ አያሌ መጻሕፍትን በየቦታዎቹ እየወሰደች አድርሳለች ። የግዞት እሥራት የተፈረደባቸው ጓዶች አምልጠው እንዲጠፉ የሚቻልበትን ሁኔታ አሟልታለች ። እነርሱን በማጀብም ከሀገር ውጪ እያደረሰች ተመልሳለች ። በእርሷ የአፓርትመንት መኖርያ ቤት ውስጥ የህቡዕ ጋዜጦች እና ጽሁፎች ማተምያ መሣርያ በሽሽግ ገብቶ የሕትመት ተግባሩን ያከናውን ነበር ። ስለዚሁ ማተሚያ ጉዳይ ዣንዳርሞች ሰምተው ለፍተሻ ወደርሷ ቤት ሲመጡ ፣ ገና መኖርያ ቤቷ ከመድረሳቸው የጥቂት ደቂቃዎች ጊዜ ውስጥ እርሷነቷ ሊታወቅ በማይችል ዘዴ ልብሷን እንደ ቤት ሠራተኛ ገረድ በመልበስ ወደርሷ የሚመጡት ዣንዳርም እንግዶቿን በሩ መዳረሻ ላይ ለይተው ሳያውቋት በመተላለፍ ፣ ከላይ የሚደረብ ልብስ ሳትለብስ እና ራሷ ላይም ሞቃትነት የሌለው ሻሽ ጣል ሳታደርግ ጋዝ የምትገዛ በመምሰል በእጅዋ የጋዝ መግዣ ታኒካ ይዛ ፣ ቅዝቃዜው እጅጉን የሚያንዘፈዝፍ እና የሚያንቀጠቅጥ ብርድ በሚበርድበት በክረምት ወራት ከተማውን ከአንዱ ዳርቻ እስከሌላኛው ዳርቻ አቋርጣ ተጉዛለች ። ሌላ ጊዜ ደግሞ ወዳጆችዋ የሆኑ ሰዎች ወደሚገኙበት አንድ ከተማ እነርሱን ለመጠየቅ ሄደች ። እነርሱ ወደሚኖሩበት አፓርትመንት የሚያደርሰውን ፎቅ ስትወጣ ቤታቸው በመፈተሽ ላይ መሆኑን ልትገነዘብ ቻለች ። ተመልሶ ለመሄድ ጊዜው አጓጉል ስለነበረ እነዚህ ፍተሻ በመፈተሽ ላይ ካሉት ወዳጆቿ አንድ ፎቅ ወደታች ዝቅ ብለው ወደሚኖሩ ሰዎች ዘንድ በደፋርነት በራቸው ላይ የሚገኘውን የመጥሪያ ደወል ደወለች ። እነዚህ የማታውቃቸው ሰዎች ዘንድ ሻንጣዋን እንደያዘች ከገባች

በኋላ የደረሰባትን ሁኔታ ግልጥ አድርጋ ነገረቻቸው ።

«ከፈለጋችሁ አሳልፋችሁ ልትሰጡኝ ትችላላችሁ ። ይኸንን ግን አታደርጉትም ብዬ እገምታለሁኝ» በማለት በሙሉ ልብ በማመን ሁኔታ ተናገረች ።

የቤቱ ነዋሪዎች እጅግ በጣም ፈርተው የነበረ ከመሆኑም በስተቀር ካሁን-ካሁን ዥንዳርሞቹ መጥተው ቤታችንን እንኳኩት በማለት አንዳችም እንቅልፍ በዐይኖቻቸው ሳይዞር ፍጥጥ ብለው ሌሊቱን አሳለፉ ። ይሁን እንጂ ሶፍያን ለዥንዳርሞች አሳልፈው ለመስጠት አልፈለጉም ። ጧት ሲነጋም ስላሳለፉት የድንጋጤ ምሽት የቤቱ ነዋሪዎች ከሶፍያ ጋር ሁነው ተሳሳቁ ። አንድ ሌላ ቀን ደግሞ ሶፍያ ልክ እንደመነኩሲት የመነኩሲት ልብስ ለብሳ እርሷን ፈልጎ ለመያዝ ክትትል ያደርግ ከነበረ ሰላይ ጋር በአንድ የባቡር ፉርጎ በአንድ መቀመጫ ጎን-ለጎን ተቀምጣ ትጓዝ ጀመር ። ይኸ ሰላይ ,በሶፍያ ላይ እንደምን የመሰለ ረቂቅ የብልህነት ክትትል በማድረግ ላይ መሆኑን ጉራ በተመላበት የኩራት መንፈስ ለመነኩሲቷ ይነግራት ጀመር ። ሶፍያ እነርሱ በሚጓዙበት በዚህ ባቡር በሁለተኛ ማዕረግ ፉርጎ ውስጥ በመጓዝ ላይ ነች ብሎ ሰላዩ እርግጠኛ ሁኖ ነበር ። ባቡር በየጣቢያው ላይ በቆመ ቁጥር ሰላዩ ከባቡሩ ላይ ወርዶ ሲመለስ ለመነኩሲቷ የሚከተለውን ያወራላታል ፡—

«ላያት አልቻልኩም ። ተኝታ መሆን አለበት ። እነርሱም ቢሆኑ ይደክማቸዋል ። የእነርሱም ኑሮ ከእኛ ኑሮ የተሻለ አይደለም!» ይላታል ።

እናት ሶፍያ የምትነግራትን እነዚህን ታሪኮቿን በማዳመጥ ሶፍያን በመውደድ ሁኔታ ትመለከታለች ። ረዥሟ እና ቀጭኒቱ ሶፍያ ቅልጥመ-ረዥም በሆነው እግሯ ሳብ-ሳብ እያለች መንገዱን በቀላሉ ተያይዛዋለች ። በአካሄዷ ፥ በአነጋገሯ ፥ ምንም ጎርናና ቢሆንም



እንኳን በድምፅዋም ጭምር የደስ-ደስ ያላት ሸጋ ሴት ነች ። ማናቸውንም ነገር ዐይኖቿ በወጣትነት መንፈስ የሚቀበሉ ሲሆኑ ፥ ያየቻቸውን ነገሮችም በወጣትነት ደስታ ተመስጣ ትመለከታለች ።

«አ-ቤ-ት! እንዴት ደስ የሚያሰኝ ጥድ ነው!» በማለት ሶፍያ ከዛፎቹ መካከል አንዱን እያመለከተች ድምፅዋን ከፍ አድርጋ ተናገረች ። እናት ከጉዞዋ ቆም ብላ ተመለከተች ። ጥዱ ከሌሎቹ የተለየ ሳይሆን ያው እንደሌሎቹ ነው ።

«አዎን ። ደስ የሚያሰኝ ዛፍ ነው!» አለች እናት ፥ ፈገግ እያለች እና የሶፍያን ሽበት ጣል-ጣል ያደረገበትን ፀጉር ነፋሱ ጆሮዋ ላይ ምልስ-ቅልስ ሲያደርገው እየተመለከተች ።

«ውይ-ውይ! የመስቀል ወፍ!» አለች ሶፍያ ፍቅር በተመላበት መንፈስ ከጠራው ሰማይ ላይ ሳይታይ ወደሚንቆረቆረው የወፍ ሙዚቃ ቡናማ ዐይኖቿን ክብልል-ክብልል ፥ የሠራ አካሏንም ሳብ-ረገብ እያደረገች ። አንዳንድ ጊዜም እንደ ሀረግ የሚመዘዝ ሰውነቷን እጥፍ-ዘርጋ አድርጋ በማጎንበስ ወፍ-ዘራሽ አበባ ከቀጠፈች በኋላ ቀጫጭን የሆኑት ጣቶቿ እየተንቀጠቀጡ የአበባውን ቅጠሎች ዳሰስ-ዳሰስ ስታደርጋቸው ዝግ ያለ እና ደስ የሚያሰኝ የዘፈን እንጉርጉሮ ቀስ ብላ ታንጎራጉራለች ።

በእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎቿ ይህች ባለ ቡናማ ቀለም ዐይኖቿ ሴት እናትን ልትስባት በቃች ። እናትም እርምጃዋን ከሴቲቱ ጋር እያስተካከለች ጎን-ጎኗ ዕኩል ለመራመድ ሞከረች ። አንዳንድ ጊዜ ግን ሶፍያ ጠንከር ያሉ ንግግሮችን ትሰነዝራለች ። እናት ደግሞ ይኸንን አልፈቀደችም ።

«ሪቢን አይወዳትም ።» በማለት እናት አሰበች ።

ወዲያውኑ ደግሞ መለስ ብላ ለስለስ ባለ ሁኔታ

እና ግልጽ ባለ መንገድ በሙሉ ስሜት ንግግሯን
ትቀጥላለች ። እናትም ሶፍያን በፈገግታ ትመለከታታለ
ች ።
«አንቺ አሁንም ገና እንደምን ያለሽ ወጣት ነ
ሽ!» በማለት እናት እየተነፈሰች ተናገረች ።
«ኧረ እባክዎን ፣ ሰላሳ ሁለት ዓመት ሁኖኛል!»
በማለት ሶፍያ እያደነቀች ተናገረች ።
ፔላጌያ ፈገግ አለች ።
«ይኸንን ማለቴ አይደለም ። ቁመናሽን እንደምመለ
ከተው ከሆነ ፣ ዕድሜሽ ከዚህ በላይ ይሆናል ብዬ
መገመት እችላለሁኝ ። የአንቺን ንግግር ሳዳምጥ እና
ዐይን-ዐይንሽንም ስመለከት·ሽ ሁልግዜም እደነቃለሁኝ ።
ልክ እንደወጣት ልጃገረድ ነሽ ። በዚህ ዕድሜሽ ከባ
ድ እና አደገኛ የሆነ ኑሮ ኑረሻል ። ይሁን እንጂ ልብ
ሽ ሁል ጊዜም በደስታ ይፈካል» በማለት እናት ተና
ገረች ።
«ስለኑሮ ከባድነት ምን ግዜም ቢሆን አልጨነቅ
ም ። የትኛውም ሌላ ኑሮ ቢሆን እኔ ከምኖረው ከዚ
ህ ኑሮዬ የተሻለ ወይንም አስደሳች መስሎ ፈጽሞ
አይታየኝም ። በመጠርያ ስም ሳይሆን ፣ በቤተሰብዎ ስም
ኒሎቭና ብዬ እጠራዎት ዘንድ እሻለሁኝ ። ፔላጌያ
የሚለው ስም ከእርስዎ ጋር ስምም የሆነ መጠርያ
አይደለም» በማለት ሶፍያ ተናገረች ።
«እንዳሻሽ ጥሪኝ!» በማለት እናት በሃሣብ ተውጣ
ተናገረች ። ቀጠል አድርጋም ፡ —
«እንደው እንዳሻሽ ጥሪኝ ። አንቺን እየተመለከትሁ
ኝ እና አንቺ የምትናገሪውንም እያዳመጥኩኝ ከዚሁ
ጋር በአንድነትም አስባለሁ-አሰላስላለሁኝ ። ወደሰው ል
ጆች የሚያመራውን ጎዳና ማግኘትም እኔን ያስደስ
ተኛል ። አንዳችም ፍርሀት ሳያድርበት አንድ ሰው በ
ልቡ ውስጥ የሚንገዋለለውን ሁሉ ግልጥ-ግልጥልጥ



አድርጎ ይነግርሻል ። ነፍሱ በገዛ ራሷ ክፍት እና
ግልጽ ሁና ትቀበልሻለች ። ስለእናንተ ስለሁላችሁም
ሳስብም በሕይወት ውስጥ ያለውን ማናቸውንም ተን
ኮል እና ክፋት በአሸናፊነት እንደምትቋቋሙ እርግ
ጠኛ ነኝ! እርግጠኛ ነኝ!» በማለት እናት ተናገረች ።
«አዎን ። እንቋቋማለን ። ምክንያቱም ከሠርቶ-አደ
ሮች መካከል አንዶቹ ነን እና!» በማለት ጎላ ባለ
ድምፅ ሶፍያ ተናገረች ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ ፡ —
«በእነርሱ ውስጥ ታላቅ የተደበቀ ኃይል ይገ
ኛል ። ስለዚህም ማናቸውንም ያሻቸውን ሁሉ ማድረ
ግ ይቻላቸዋል! የእኛ ተግባር የእነርሱን ማንነት እን
ዲገነዘቡት ማድረግ እና በዚህ ምክንያትም ነፃ በሆ
ነ ሁኔታ ለመዳበር እንዲችሉ ማድረግ ነው…» በማ
ለት ሶፍያ ተናገረች ።
እነዚህ ከሶፍያ አንደበት የወጡት ቃላት በእናት
ልብ ውስጥ የተደባለቁ ስሜቶችን አሳደሩባት ። በአን
ዳች ምክንያት ፣ ቅሬታ ኖሮባት ሳይሆን በወዳጅነት
ላይ በተመሠረተ አንዳች ምክንያት ለሶፍያ አዘነች
ላት ። እና ስለዚህም ሌላ ቀለል ያሉ ንግግሮችን ከአ
ንደበቷ ለመስማት ፈለገች ።
«ላደረግሻቸው ጥረቶች ተገቢ ወሮታን የሚመልስ
ማን ነው?» በማለት እናት ረጋ ባለ ሁኔታ እና ከ
ፉ ብሎአት ተናገረች ።
«ተገቢ ዋጋችንን ካገኘን ቆየት ብሎአል» በማለት
ሶፍያ መለሰችላት ። ይኸንን ስትናገርም የድምፅዋ አ
ወራረድ የኩራት ስሜት የተቀላቀለበት መስሎ ለእና
ት ተሰማት ። ከዚያም ሶፍያ ንግግሯን በመቀጠል ፡ —
«ለሕይወታችን ተስማሚያችን የሆነ አኗኗርን
አግኝተናል ። መንፈስ በሚያበረክተው በመላው ክፍተ
ኛ ኃይሉ ተደግፈን እንኖራለን ። ከዚህ የበለጠ ሕይ

ወት እንድታበረክትልን የምንጠይቃት ኩቶ ምን ሊኖር ይችላል?»

እናት ሶፍያን መልከት አደረገቻትና አሁንም እንደገና በሀሳብ ተውጣ መሬት-መሬቱን ቁልቁል ትመለከት ጀመር ። እንዲህም ስትል አሰላሰለች ፡ —

«ሪቢን አይወዳትም…»

ጣፋጩን አየር ደህና አድርገው ወደውስጥ እየተነፈሱ ፤ ሳይጣደፉ ፈጠን-ፈጠን እያሉ በመራመድ ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። እናት ወደሚሳለሙት ወደሚሰግዱለት ቅዱስ ቦታ የምትሄድ መስሎ ተሰማት ። ተአምራትን የሚሠራ መስቀል ወደሚገኝበት ገዳም ክብረ-በዓሉን ለማድረስ በልጅነት ዕድሜዋ ከመንደሯ ተነስታ በምትሄድበት ጊዜ ይሰማት የነበረው ደስታ ድቅን ብሎ ታያት ።

አንዳንድ ጊዜ ሶፍያ ስለ ሰማይ ውበት ወይንም ስለ ፍቅር ለስላሳ በሆነ እና ጣዕመ-ዜማው በሚጥም-በሚጣፍጥ ድምፅ መዝሙር ታዜማለች ። አንዳንድ ጊዜም ስለ መስኮች ፤ ደኖች ፤ እንደዚሁም ስለ ቮልጋ የሚገልጹ ቅኔዎችን በቃሏ ታንጎደጉዳለች ። እናትም በስሜት በመመሰጥ ሳታውቀው የግዷን የቅኔው ስንኝ መምቻ የሆነው መጽፌያ ከሚያበረክተው ሙዚቃዊ ድምፅ ጋር በስሜት ተውጣ ራሷን ትነቀንቃለች ።

እጅግ ው ብ እና እዩኝ-እዩኝ በሚያሰኝ የአትክልት ሥፍራ ውስጥ በበጋ ወራት መሽትሸት ሲል መገኘት እንደሚያበረክተው የመንፈስ እርካታ ፤ የሀሣብ ፀጥታ እና በስሜት የመዋጥ ሁኔታ በእናት ላይ ደርሶ ተሰማት ።

5

በሦስተኛው ቀን ያመሩ ከነበረበት ሥፍራ ደረሱ ። አንድ በእርሻ ሥራ የተሠማራ ገበሬን የቅጥራን ማው



ጫ ፋብሪካው የት እንዳለ እናት ጠየቀችው ። ከዚያም የዛፎቹ ሥሮች ምቹ መረማመጃ ሁነው ወደሚገኙበት ዘቅዘቅ ወደአለና በዛፎች የተከበበ ዘብጥ ውስጥ ቁልቁል ይወርዱ ጀመር ። መንገዱም ከሠል እና ቅርጣኖች ወደሚገኙበት ወደ አንድ ክብ መስክ አደረሳቸው ።

«ይኸው ከቦታው ደርሰናል!» በማለት ዕረፍት አጥታ በመሸበር ሁኔታ እናት እየተመለከተች ተናገረች ።

ከአጠና እና ከጭራሮዎች ከተሠራ ጎጆ ፊት ለፊት የሦስት ሳንቃ አግዳሚ ጠረጴዛ ተዘርግቷል ። በቅርጣን የጠቆረው ሪቢን ሸሚዙን ከፍቶ በአግዳሚው ጠረጴዛ ላይ ከየፊም እና ከሌሎች ሁለት ወጣቶች ጋር ምሳ ይበላል ። ሴቶቹን መጀመሪያ የተመለከታቸው ሪቢን ሲሆን ፤ አንዱ እጁን ከዓይኖቹ በላይ ከፍ አድርጎ የፀሐይዋን ብርሃን እየተከላከለ እስኪመጡ ድረስ ምንም ሳይናገር ጠበቃቸው ።

«ወንድም ሚኻኢሎ ፤ ጤና ይስጥልኝ እደምን ሰንብተሃል!» በማለት እናት ከሩቅ ሁና ድምፅዋን ጎላ አድርጋ አሰማች ።

ከመቀመጫው ብድግ በማለት ሳይቻኮል ወደእነርሱ ዘኟ ያመራ ጀመር ። ቀረብ ብሎ ከተጠጋ በኋላ ማንነቷን ለይቶ ሲያውቅ ቆም ብሎ ፈገግ በማለት በቅጥራን በጠቆረው እጁ ጺሙን ያሻሽ ጀመር ። እናትም ወደ እርሱ እየተጠጋች ፡ —

«ወደ ቅዱስ ሥፍራ የምንጓዝ መንገደኞች ነን ። እግረ-መንገዳችንን እንደምን ነህ ብዬ ለመጠየቅ ስላሻሁኝ ነው ጎራ ማለታችን ። ይህቺ አብራኝ ያለችው መጠርያ ስሟ አና ይባላል ። ተዋወቁ…» በማለት አነጋገረችው ።

እንዲህ የመሰለውን ሃሣብ አስባ ለማቅረብ በመቻሏ የልብ ኩራት እየተሰማት ወደ ዓይኖቿ ማዕዝና

ት ዓይኖቿን ከብለል አድርጋ በማስጠጋት ኮስተር እና ጠንቀቅ የማለት ስሜት የሚታይባትን ሶፍያን ጨረፍ አድርጋ ታስተውል ጀመር ። ከዚያም ፡ —

«ጤና ይስጥልኝ ፤ እንደምን ሰንብተሻል!» በማለት ሪቢን ጨፍገግ ብሎት እየሳቀ እናትን ጨበጣት ። ቀጠል አድርጎም ሶፍያን እጅ ከነሳት በኋላ ወደ እናት ዞር ብሎ ፡ —

«አትዋሺ ። አሁን ያለሺው ከተማ ውስጥ አይደለም ። እዚህ አንዳችም ውሸት መዋሸት አያስፈልግም! እዚህ ያሉት ሁሉም ወገኖቻችን ናቸው…» በማለት ተናገረ ።

እነዚህን ወደቅዱስ ቦታ ተጓዥዎች የፊም እዚያው እነበረበት ቦታ ቁጭ እንዳለ በማስተዋል እና በማጥናት አጠገቡ አብረውት ለተቀመጡት ጓደኞቹ እንድ ነገር በዝግታ ነገራቸው ። ሴቶቹ ወደ እነርሱ ዘንድ ሲመጡም ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ምንም ሳይናገር እጅ ነሳቸው ። አብረውት ያሉት ጓደኞቹ አንዳችም እንግዳ መጥቶ ያላዩ ይመስል እዚያው እነበሩበት ንቅንቅም ሳይሉ ቁጭ እንዳሉ ቀሩ ።

«ይኸው ፤ እኛ እዚህ እንደመነኮሳት እንኖራለን» በማለት ሪቢን የፔላጌያን ትከሻ ቀስ ብሎ ቸብ-ቸብ እያደረገ በመምታት ተናገረ ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«እዚህ እኛ ዘንድ የሚመጣ ማንም የለም ። ባለንብረቱ እዚህ አለንበት አካባቢ የለም ። ሚስቱ ሆስፒታል ገብታለች ። እኔም ከሞላ-ጎደል ኃላፊ እንደማለት ነኝ ። የፊም ፤ እስኪ የሚጠጣ ወተት አምጣ» በማለት ተናገረ ።

የፊም ወደ ጎጆይቱ ውስጥ ሲገባ ወደ ቅዱስ ቦታ ተጓዥዎቹ በየትከሻቸው ተሸክመዋቸው የነበሩትን ከረጢቶች ማውረድ ጀመሩ ። ደረተ-ሰፊ እና ያልተበጠረ ፀጉር ያለው ጓደኛው እግሩን ሌላ እግሩ



ላይ እነባብሮ ፀጉሩን እያካከከ በማሰላሰል ሁኔታ እነርሱን እነርሱን እየተመለከተ በማንጎራጎር እነበረበት ቁጭ እንዳለ እንጉርጉሮውን በዝግታ ሲያንጎራጉር ፤ ሌላኛው ረዥምም እና ቀጭን ጓደኛው ከመቀመጫው ብድግ ብሎ በመነሳት ያግዛቸው ጀመር ።

የቅርጫኑ ከባድ ሽታ በመጠውለግ ላይ ካሉት የጭራሮ ቅጠሎች ሽታ ጋር ተቀላቅሎ የሴቶቹን ጭንቅላት አዞረው ።

«ያዕቆብ ይባላል» አለ ሪቢን ረዥሙን ሰውዬ በጣቱ እያመለከተ ። ከዚያም ወደሌላኛው ዞር ብሎ ፡—

«ያኛው ደግሞ ኢግናት ይባላል ። እሺ ፤ ለመሆኑ ልጅሽ ደህና ነውን?» በማለት እናትን ጠየቃት ።

«ታሥሮአል!» በማለት እናት ትንፋሿን ዋጥ አድርጋ ከተነፈሰች በኋላ መለሰችለት ።

«እንደገና አሁንም ታሠረ? ይኸ እሥር ቤት ጥሞታል ማለት ነው እንዴ…» በማለት ሪቢን ተናገረ ።

ኢግናት ያንጎራጉር የነበረውን እንጉርጉሮ ማንጎራጎሩን አቆመ ። ያዕቆብ እናት የያዘቻውን ከዘራ-መሳይ እንጨት ተቀበላት እና ፡ —

«ይቀመጡ!» አላት ።

«ምነው ፤ ለምን ይቆማሉ? ይቀመጡ እንጂ» በማለት ሪቢን ሶፍያን አናገራት ። እርሷም ሪቢንን አትኩራ በመመልከት እያጠናችው ምንም ሳትናገር አግዳሚው ወንበር ላይ ተቀመጠች ። ከዚያም ሪቢን ከእናት ፊት-ለፊት ተቀምጦ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ ፡ —

«ለመሆኑ መቼ ነው የያዙት? ወይ ጉድ ፤ እንደው እንቺ ዕድለ ቢስ ሆንሽ ማለት ነውን?» በማለት ተናገረ ።

«አይ ፤ ምንም አይደል ግዴለም» በማለት እናት መለሰች ።

«ለምደሽዋል ማለት ነው ። ዕውን?» በማለት ጠየቀ ።

«የለም አልለመድኩትም ። ምንም ማድረግ እንደማ
ይቻል ስለማውቅ ነው!» በማለት መለሰችለት ።

«ወይ ጉድ! እስኪ እንዴት እንደሆነ ንገሪን» በማ
ለት ሪቢን ጠየቀ ።

የፊም በጮጮ ወተት አምጥቶ እናት የምታወራ
ውን በጥሞና እያዳመጠ ከጠረጴዛው ላይ ያለውን ብ
ርጭቆ አንስቶ ካንጠፈጠፈ በኋላ ወተቱን ቀድቶ
ለሶፍያ ሰጣት ። ድምፅ በማሰማት እንዳያንኮሻኩሽ በ
ጣም ይጠነቀቅ ነበር ። እናት ታሪኳን ባጭሩ አቅርባ
ስትጨርስ እስከ አንድ እስኪተወሰነ ጊዜ ድረስ ማን
ም ምንም አልተናገረም ። ማንም ማንንም አይመለከት
ም ። ኢግናት የጠረጴዛውን ጠርዝ በጥፍሩ እየገፋፋ
ተቀምጦአል ። የፊም ክንዱን ትከሻው ላይ አድርጎ
ከሪቢን ኋላ ቆሞአል ። ያዕቆብ እጆቹን አጣጥፎ እና
ጭንቅላቱን ቀለስ አድርጎ ከአንድ ጉርድ ግንድ
ላይ ዘንበል ብሎአል ። ሶፍያ የገበሬዎቹን ሁኔታ በዓ
ይኖቿ ሽፋሽፍቶች ውስጥ እያጠናች ተቀምጣለች…

«እ-ሀሀ! ግልጥ ባለ ሁኔታ ጉዳዩ እንዲህ ነው
ማለት ነዋ!» በማለት ሪቢን ደስተኛ ባልሆነ ስሜት
ዝግ ብሎ ተናገረ ።

«እኛ እንዲህ ያለ ሠልፍ ተሰልፈን ቢሆን ኖሮ
ገበሬዎች ደብድበው በገደሉን ነበር!» በማለት በቅሬታ
ፈገግ እያለ የፊም ተናገረ ።

«እንዴታ ፤ በገደሉንም ነበር!» በማለት በአዎንታ
ራሱን ነቅነቅ እያደረገ ኢግናት የየፊምን ሃሣብ በመ
ደገፍ ከተናገረ በኋላ ፡ —

«ፋብሪካ ውስጥ ለመሥራት እሄዳለሁኝ ። እዚያ
መሥራት ይሻላል…» አለ ።

«ፓቬል ለፍርድ ይቀርባል አልሺን?» በማለት ሪቢ
ን ጠየቀ ። ከዚያም ቀጠል አድርጎ ፡ —



«ምን ይፈርዱበት ይሆን? ሰምተሻልን?» በማለት ጠ
የቀ ።

«ከባድ የጉልበት ሥራ እንዲሠራ ወይንም ሳይቤር
ያ በግዞተኛነት ተግዞ ለዘለቄታው እዚያው እንዲኖር
ይፈርዱበታል» በማለት ዝግ ባለ ሁኔታ መለሰችለት ።

ሦስቱ ወጣት ልጆች በአንድ ጊዜ ራሳቸውን
ቀና አድርገው እናት-እናትን ይመለከቱ ጀመር ።

«ይኸንን የፈጸመውን ተግባር በሚያከናውንበት ጊ
ዜ ይኸ ሊደርስበት እንደሚችል አውቆት ነበርን?»
በማለት ሪቢን ጭንቅላቱን ዝቅ አድርጎ ተናገረ ።

«አዎን አውቆት ነበር!» በማለት ሶፍያ ድምፅዋን
ከፍ አድርጋ መለሰችለት ።

ይኸ አባባል ድርቅ አድርጎ ያስቀራቸው ይመስል
ሁሉም ጭጭ-ምጭጭ አሉ ። ከዚያም ሪቢን አጠንክ
ሮ እና አበክሮ ፡ —

«አዎን! አውቆ እንደነበር እርግጠኛ ነኝ ። የተድ
በሰበሰ እና መላ-ቅጡ የጠፋ አንዳችም እርምጃ አይወ
ስድም ። እጅግ አስተዋይ የሆነ ሰው ነው ። ሰማችሁ
አይደል ወንድሞቼ? ሳንጃቸውን በደረቱ ላይ እንደሚሰ
ድሩበት ወይንም ወደሳይቤርያ በግዞተኛነት እንደሚያ
ግዙት ያውቅ ነበር ። ይሁን እንጂ ይኸ ደግሞ ድርጊቱ
ን ከማከናወን እንዲያፈገፍግ አላደረገውም ። እናቱ ራ
ሷ በሚራመድበት ጎዳና ላይ ተንጋልላ በመውደቅ
እባክህ ለእኔ ስትል ይቅርብህ ብላ ብትለምነው እን
ኳን ረግጧት በላይዋ ላይ በማለፍ ጉዞውን ወደፊት
ይቀጥላል ። አይደለምን ኒሎቭና?» በማለት ተናገረ ።

«አዎን ልክ ነው!» በማለት ደንገጥ ብላ ተናገረ
ች ። ትንፋሿን ዋጥ ካደረገች በኋላ ዙርያውን ዞር-ዞር
ብላ ተመለከተች ። ሶፍያ ፀጥ ብላ የእናትን እጅ በእ
ጆዋ እያሻሸች ግንባሯን ሸብሸብ አድርጋ ሪቢን-ሪቢ
ንን ትመለከታለች ።

«ሰው ማለት ይኸ ነው!» በማለት ሪቢን ጥቋቁር
ዓይኖቹን ከብለል-ከብለል እያደረገ ሁሉንም ይመለከት
ጀመር ። አሁንም እንደገና ስድስቱም ሰዎች አንዳችም
ቃል ሳይተነፍሱ ዝም አሉ ። የፀሐይቱ ቀጫጭን ጨረሮ
ች አየሩ ላይ እንደወርቅ ጥብጣቦች ፍንጥቅጥቅ ብለ
ው ተንጠልጥለዋል ። የቁራ ድምፅ ከወደአንድ ቦታ በኩ
ል ይሰማል ። እናት በሜይ ዴይ ትውስት እና እንደ
ዚሁም በፓቬል እና በአንድሬይ ናፍቆት ስሜቷ
ተቀሰቀሰ ። የቅርጣን ላይ በርሚሎች እና ከሥራቸው
የተመነገሉ ጉቶዎች ሜዳው ላይ እዚያ-እና-እዚህ ተበ
ታትነዋል ። ከበስተጥግ በኩል ወርካዎች እና ሌሎች
ም ነጫጭ ዛፎች ነፋስ ሽው-ሽው እያደረገ እያወዛወ
ዛቸው ምድሪቱ ላይ ግዝፈት ያለው ጥቁር ጥላቸውን
አጥልተው እና በብዛት እጅብ-እጅብ በማለት ደርተው
ቆመዋል ።

ያዕቆብ ድንገት ከዛፉ ሥር አፈፍ ብሎ በመነሳት
ወደ ሌላ አቅጣጫ ሄደ ። ከዚያም ፦

«ለወታደርነት ስንመለመል እኔን እና የፊምን የ
ሚልኩን እርሱን የመሳሰሉ ሰዎችን እንድናጠቃ ነው
ማለት ነውን?» በማለት ጭንቅላቱን እና ድምፁን ከ
ፍ አድርጎ ተናገረ ።

«ታዲያ እነማንን ለመቃወም የሚያሠማሩዋችሁ
መስሎሃል?» በማለት ሪቢን መለሰለት ። ቀጠል አድር
ጎም ፦

«በገዛ እጃችን ራሳችንን እንድናንቅ ይጠቀሙብና
ል ። ዋናው ዘዴያቸው ይኸው ነው!» አለ ።

«ያም ሆነ ይኸ ፤ እኔ ውትድርና እገባለሁኝ» በማለት
የፊም በግትርነት ተናገረ ።

«ማን ይከለክለኛል ብለህ ነው? ሂድ እና ግባ!»
አለ ኢግናት ጥቂት ፈገግ ካለ በኋላ ንግግሩን በመቀ
ጠል ፦



«በእኔ ላይ ጠመንጃህን ስታነጣጥርብኝ ጭንቅላቴ
ላይ አነጣጥረህ ተኩስ እንጂ ፤ እንደው ሳትገድለኝ ሽ
ባ አድርገህ አሽመድምደህ እንዳታስቀረኝ ። ወዲያውኑ
ተኩስ እና ግደለኝ» አለው ።

«ይኸንን ከአሁን በፊትም ተናግረኸል» በማለት
የፊም ጠበቅ አድርጎ በመጮህ ተናገረ ።

«እረ እስኪ ቆዩ እባካችሁ ሰዎች» በማለት ሪቢ
ን እጁን አንስቶ ቀስ አድርጎ በማወዛወዝ ተናገረ ።
ከዚያም በጣቱ ወደ እናት እያመለከተ ፦

«ይቻትላችሁ ይኸቺ ሴት! የርሷ ልጅ በአሁኑ ጊ
ዜ የሚገኝበት ቦታ...» ብሎ ሪቢን ሳይጨርስ ፤ እናት
ቆጣ ብላ እና ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ ፦

«ለምን እንዲህ ትናገራለህ?» በማለት ተናገረች ።

«አዎን ። እንዲህ መናገር ያስፈልጋል» በማለት ምር
ር ብሎ ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አድርጎ ፦

«ፀጉርሽ እንዲህ የሸበተው ያለምክንያት አይደለ
ም ። በልጅዋ ላይ ይኸንን በመፈጸም የገደሏት መስሏ
ቸው ይሆን? ኒሎቭና ፤ ለመሆኑ ተበታኝ ወረቀቶቹን አ
ምጥተሻልን?» በማለት ጠየቃት ።

እናት እርሱን-እርሱን ተመለከተች ። ከዚያም ትንፋ
ሿን ዋጥ ካደረገች በኋላ ፦

«አዎን...» አለችው ።

«አያችሁልኝ!» አለ ሪቢን ጠረጴዛውን በመገረም
በጡጫ እየደበደበ ፦

«እኔ ገና እንዳየሁሽ ጉዳዩ ገብቶኝ ነበር ። እንግዳ
ውማ እዚህ ድረስ የሚያመጣሽ ሌላ ምን ጉዳይ ኑሮ
ነው? አያችሁልኝ! ልጅዋን ከጓዶቹ ነጥለው አወጡት ።
እናቱ የልጅዋን ቦታ ምትክ ሁናው ያዘች!» በማለት
ተናገረ ።

ጠረጴዛውን አምርሮ በመደብደብ በልጅዋ ላይ በተ

ፈጸመው ድርጊት አምርሮ ፀያፍ-ፀያፍ ስድብ ይሳደብ
ጀመር ።

እናት በሁኔታው ደንገጥ ብላ ፊት-ፊቱን ብትመለ
ከት ፊቱ መለዋወጡን ተመለከተች ፡ — ፊቱ ከስቶአ
ል ። ጢሙ ጭብርር ያለ ሲሆን በጢሙ ውስጥም ጉ
ንጮቹ ክስት ብለው ጎርጉደው አጥንቶቹ ወጥተዋ
ል ። ለረዥም ጊዜ እንቅልፍ ያልተኛ ይመስል ሰማያዊ
ቀለም ባላቸው ዓይኖቹ ውስጥ ቀጫጭን ቀያይ የደ
ም ሥሮች ተረብርበው ተጋድመውበት ይታያሉ ። የእ
ርሱም አፍንጫ እንደ ማንቆርቆርያ አፍንጫ ተቀልም
ሞ አምጥሙጦአል ። ከዚህ ቀደም ባለ ቀይማ ቀለም
የነበረው እና አሁን ግን በቅርጣን ተለውሶ የጠቆረ
ው ክፍት የሸሚዙ ክሳድ አግጥጠው ያፈጠጡትን
ከማዱ ሥር ያሉትን አጥንቶች እና ደረቱ ላይ እን
ደ ስጥ የተሰጡትን ጥቋቁር ወፋፍራም ፀጉሮች ግል
ጥ አድርገው ያሳያሉ ። መላው አቋሙ ከቀድሞው ይበ
ልጥ ጭፍግግ ያለው እና የቀፈፈው ሁኖአል ። ተቀጣ
ጥለው የሚነድዱት ዓይኖቹ የቁጣ እሳት በመትፋት
የጠቆረ ፊቱን ቦግ አድርገው አብርተውታል ። ሶፍያ
ከእነዚህ ገበሬዎች ላይ ዓይኖቿን ማንሳት አቅቷት
ፍዝዝ እና ጭጭ ብላ እነርሱን-እነርሱን ትመለከታለ
ች ። ያዕቆብ ወደ ጎጆው ጠጋ ብሎ ሂዶ በብስጭት
ቅርፊት ሲቆርፍ ኢግናት ዓይኖቹን ሸውረር አድርጎ
ጭንቅላቱን ይነቀንቃል ። የፊም እናት ከተቀመጠችበት
ኋላ ቀስ እያለ ወዲያ-እና-ወዲህ ይንጎራደዳል ። ሪቢን
እንደገና መናገር ጀመረ ፡ —

«አሁን በቅርቡ የቀበሌያችን ኃላፊ አንድ መልዕክ
ተኛ ወደእርሱ ዘንድ እንድሄድ ላከብኝ ። እንዲህም
አለኝ ፡ — አንተ ክፉ ጠማማ ፤ ቄሱን ምን ብለህ ነ
ው የነገርካቸው?' እኔም ፡ — 'እንዴት? ምን ባደረግሁኝ
ነው ክፉ ጠማማ የምባል? የዕለት እንጀራዬን የማገኘ



ው ላቤን አንጠፍጥፌ ነው ። በማንም ላይ ያደረስ
ኩት ጉዳት የለም ። ምን ባደረግሁኝ ክፉ-ጠማማ ልባ
ል?' አልኩኝ ። እላዬ ላይ እንደእንስሳ እያጓሩ እና
ጥርስ-ጥርሴን በቡጢ እየመቱኝ ከመሬት ደባልቀ ወቃ
ኝ ። ለሦስት ቀናትም አሠሩኝ ። ከዚያም ፡ — 'ለሕዝቡ
የምታወራው እንዲህ-እንዲህ የመሳሰሉትን ጉዳዮች
ነው ማለት አይደለም? ቆይ ግዴለም! አንተ የጃጀህ
ሰይጣን! የምንረሳልህ እንዳይመስልህ! እኔም ባልሆን
ሌላ ሰው ለአንተ ወይንም ለልጆችህ የሚገባችሁን
ምስ ይሰጣችኋል ። ይኸንን ልብ ብለህ አስታውስ! በብ
ረት ጠፍሮችህ የሕዝቦችን ልብ ቧጥጠህ በመቆፈር
በልቦቻቸው ውስጥ ዘር ጥላቻን ዘርተሀል! ስለዚህም
አንተ ሰይጣን አንዳችም የይቅርታ ምህረት ከእኛ እ
ንዳትጠባበቅ! በቃ እንግዲህ!' አለኝ » በማለት ሪቢን
ተናገረ ።

ሰውነቱ ውስጥ በሚፈላው ቁጣ መልኩ ቀልቶአል ።
የአነጋገሩ ሁኔታም እናትን አሠጋት ። ከዚያም ረጋ ብ
ሎ የሚከተለውን ቀጥሎ ተናገረ ፡ —

«ቄሱን ምን አልኩት እና ነው? ቄሱ መንደሩን
ዞሮ ካዳረሰ በኋላ ጥቂት ገበሬዎች በተሰበሰቡበት
ተቀምጦ 'ተራው ሕዝብ በግ እንደማለት ስለሆነ ም
ንግዜም ቢሆን እረኛ ያሻዋል' በማለት ይናገር ነበ
ር ። እኔም እንደሚከተለው በመቀለድ ተናገርኩኝ ፡ —
'ተኩላን የእንስሳት ኃላፊ አድርገው ከሾሙት በዱ
ር ውስጥ ወፎች አልቀው አየር-ለአየር የሚበሩ ላባ
ዎቻቸው ይቀራሉ ።' እኔ ላይ ጭንቅላቱን ካወዛወዘብኝ
በኋላ ፤ ፍዳ እና መከራቸውን በመቻል የትዕግስተኝነት
ብርታቱን ፈጣሪ ይሰጣቸው ዘንድ ሕዝቦች ወደፈጣ
ሪ መጸለይ ይገባቸዋል በማለት ተናገረኝ ። እኔም የሚ
ከተለውን መለስኩኝ ፤ የጸሎት የጸሎትማ ሕዝቡ ብ
ዙ ይጸልያል ። ብቻ ክፉቱ ፈጣሪ ጊዜ ስለሌለው የሕ

ዝቡን ጸሎት አያዳምጥም! እኔ የማደርሰው ጸሎት እን
ደምን ያለ ጸሎት እንደሆነ ጠየቀኝ ። እኔም የሚከተለ
ውን መለስኩለት ፡ — ‘ሕይወቴን በሙሉ እንደማገኛው
ም ተራ ሕዝብ የማደርሰው ጸሎት አንድ ዓይነት
ሲሆን ፤ እርሱም ፡ — ፈጣሪ አምላኬ ሆይ ፤ ክቡራን መ
ኳንንቶችን ለማገልገል ይቻለኝ ዘንድ ድንጋይ እየዋ
ጥሁኝ ጣውላ-እንጨቶችን እንዴት ለመትፋት እንደም
ችል እባክህን ዘዴውን አስተምረኝ! እያልኩኝ ነው አ
ልኩት ። ቄሱ ግን ንግግሬን ለመቀጠል እችል ዘንድ
ፋታ አልሰጠኝም ።’ በማለት ሪቢን ከተናገረ በኋላ
ድንገት ወደ ሶፍያ ዞር ብሎ ፡ —

«እርስዎ ትውልድዎ ከሴት-ወይዛዝርቶች ወገን ነው
ን?» አላት ።

«ለምን ከሴት ወይዛዝርቶች ወገን?» በማለት በመ
ደነቅ ፈጠን ብላ ጥያቄውን በጥያቄ መለሰች ።

«ለምን?» በማለት ሪቢን ካንኮራፋ በኋላ የሚከተለ
ውን ተናገረ ፡ —

«ዕጣዎ ሁኖ ከሴት-ወይዛዝርት ወገን ተወልደው
እንደሆን ብዬ ነዋ! ምክንያቱ ይኸው ይመስለኛል ። መ
ሆን ያለበትን ሁኖ መወለድ የየአንዳንዱ ሰው ዕድ
ል-ፈንታ ነው ። ጭንቅላትዎ ላይ ይኸንን የገበሬ ሻ
ሽ ሽብ አድርገው ስላሠሩ የመኳንንት ሀጢአት ከቆ
ዳዎ ላይ እንዳይታይ አድርጎ መሸፈን ይቻል ይመስል
ዎታልን? ኬሻ ደርቦ ቢመጣ እንኳን ቄስን ቄስ መ
ሆኑን ገና ስንገናኘው እናውቀዋለን ። አዩ ፤ ፍሳሽ ተደፍ
ቶበት በረጠበው ጠረጴዛ ላይ ክንድዎን ሲያሳርፉ
ጨፍገግ በማለት ቀፍፎዎት እና ቅር ብሎዎት ነበር ።
ወገብዎም ቢሆን ቀጥ ብሎ የተለጠጠ እንጂ እንደሠ
ርቶ-አደሪት ሴት ወገብ የጎበጠ አይደለም ።»

ጎርነን ባለ ድምፁ ይኸንን በመሰለው የሹፈት
እና የልግጫ አነጋገሩ ሶፍያን ሊያስቀይማት ይችላል



ብላ በማሰብ እናት ንግግሩን ከመቀጠል አቋረጠች
ው ፡ —

«ሚኻኢሎ ኢቫኖቪች እርሷ ጓዴቴ ከመሆኗም
በስተቀር እጅግ ጥሩ የሆነች ሰው ነች ። ፀጉሯ እንዲ
ሀ ፣ ነጥቶ የሸበተው ለእኛ ዓላማ በመቆሟ ነው ። ግዴ
ለህም በዚህ አታስብ» በማለት እናት ተናገረችው ።

ሪቢን ትንፋሹን ሳብ አድርጎ በመዋጥ ፡ —

«ምነው? አነጋገሬ ከመሥመሩ ተዛነፈ እንዴ?» አለ ።

«አንድ ነገር ሊነግሩኝ ፈልገው የነበር መሰለኝ»
በማለት ሶፍያ እርሱን-እርሱን እየተመለከተች ያለ
መለሳለስ ደረቅ ባለ ሁኔታ ጠየቀችው ።

«ልናገር የፈለግሁት ነገር ነበርን? አዎን-አዎን ። የያ
ዕቆብ አጎት የሆነ አንድ እንግዳ ሰው ከጥቂት ቀና
ት በፊት እዚህ መጥቶአል ። የሳምባ በሽታ ይዞታል ።
እኛ ዘንድ እንዲመጣ መልዕክት ልላክበት ይሆን?»

«አዎን» አለች ሶፍያ ።

ሪቢን ለጥቂት ደቂቃዎች ዓይኖቹን አትኩሮ ተመ
ለከታት ።

«ፔሬ ማታ እኛ ዘንድ እንዲመጣ ሂድ እና ንገ
ረው» በማለት ሪቢን ለየፊም ነገረው ።

የፊም ባርኔጣውን ራሱ ላይ ደፋ እና አንዳችም
ቃል ሳይናገር ፤ ማንንም ሳይመለከት ዝግ ብሎ ወደ
ደኑ ውስጥ ገባ ። ሪቢን የፊም ወደሄደበት አቅጣጫ
ጭንቅላቱን ዞር አድርጎ እየተመለከተ ፡ —

«ያስባል-ይጨነቃል! እርሱ እና ያዕቆብ በቅርቡ
ለውትድርና ይመለመላሉ ። ያዕቆብ እቅጩን ፍርጥ አ
ድርጎ በመናገር ለእኔ ውትድርና አይሆነኝም ይላ
ል ። ለየፊምም ቢሆን አይሆነውም ። ይሁን እንጂ የፊ
ም ደግሞ ወታደር መሆን ይሻል... ወታደሮችን በመ
ቀስቀስ ሊያነሳሳቸው የሚችል መስሎት ይገምታል ።
እኔ ደግሞ ከፊት ለፊትህ የተጋረጠውን ግድግዳ በ

ጭንቅላትህ ገፍተህ መጣል አይቻልም እለዋሁኝ…
ጠመንጃ ለአንዱ እንደሰጡት አንግቦ እና እግሩን
ከሰልፉ ጋር አስተካክሎ ይሄዳል ። የፊም በጉዳዩ እያ
ሰበ — እየተጨነቀ ነው ። አዎን እንጂ ፤ እንዴታ! ኢግና
ት ግን ልቡን ያወልቀዋል ። ልቡን ቢያወልቀው ምን
ዋጋ አለው እና ነው?» በማለት ተናገረ ።

«ዋጋ አለው» በማለት ኢግናት ሪቢንን ሳይመለከ
ት ቀስ ብሎ በማጉረምረም ተናገረ ። ቀጠል አድርጎ
ም ፡ —

«እርሱን በውትድርና አሠልጥነው በሚያዘጋጁበ
ት ጊዜ ከሌላው ከማንኛውም ባላነሰ ሁኔታ ለእነር
ሱ ብዙ–ብዙ ሰዎችን ይገድልላቸዋል…» በማለት ተና
ገረ ። ሪቢን በሃሣብ ተውጦ የሚከተለውን ተናገረ

«አይመስለኝም ። ምንም እንኳን ውትድርና ባይገባ
ይሻላል ብዬ ብገምትም ፤ ይኸንን መሳይ ድርጊት ይ
ፈጽም አይመስለኝም ። ሩስያ ሰፊ ሀገር ነች ። ቢጠ
ፋ ከየት ብለው ፈልገው ሊያገኙት ይችላሉ? የሀሰት
መታወቂያ ወረቀት በመያዝ ከመንደር-መንደር መዘዋ
ወር ይችላል…»

«እኔ የማደርገው ይኸንን ነው» በማለት እግሩን
በልምጭ እየጠበጠበ ኢግናት ተናገረ ። ከዚያም ቀጠ
ል አድርጎ ፡ —

«አንድ ጊዜ ተቃውሞ ለማድረግ አስበህ አሰላ
ስለህ ከጀመርክ ወዲያ-ወዲህ ሳታወላውል በቀጥታ
ወደፊት መግፋት አለብህ ።»

ውይይቱ ተቋረጠ ። በቦታው የሰፈነውን ፀጥታ ንቦ
ች እና ተርቦች እየሩን ጥ-ዝ-ዝ-ዝ… በሚል ድምፃቸ
ው በመምላት አደቱ ። ወፎች ዙርያውን ጭው–ጭው ፤
ሽው–ሽው እያሉ ይበርሩ ጀመር ። ከመስኩ ባሻገር ራ
ቅ ካለ ቦታም የዜማ ሰመመን ይሰማ ጀመር ።

«እንግዲህ እኛ ለሥራ የመነሻ ጊዜያችን ነው»



በማለት ከጥቂት ዝምታ በኋላ ሪቢን ተናገረ ። ቀጠል
አድርጎም ፡ —

«ምናልባት ጥቂት ዕረፍት ያሻችሁ ይሆናል ። መ
ጠለያው ውስጥ ጥቂት የእንጨት አልጋዎች አሉ ።
ያዕቆብ ሂድ እና ጥቂት የደረቁ የጉዝጓዝ ቅጠሎች
ጎዝጉዝላቸው… እናት ደግሞ ተበታኝ ወረቀቶቹን ስ
ጪን…» በማለት ተናገረ ።

እናት እና ሶፍያ ቋጠሮአቸውን መፍታት ጀመሩ ።

«ኧረ እንዴት ብዙ ነው ያመጣችሁት ጃል!»
በማለት ሪቢን በደስታ ተውጦ ወደቋጠሮው ጎንበስ
ብሎ እየተመለከተ ተናገረ ። ከዚያም ፡ —

«በዚህ ጉዳይ ከተሠማሩ ረዘም ያለ ጊዜ ሆነዎ
ትን? ለመሆኑ ማን ይባላሉ?» በማለት ሶፍያን ጠየቃት ።

«አና ኢቫኖቭና እባላለሁኝ ። በዚህ ተግባር ከተሠ
ማራሁኝ አሥራ ሁለት ዓመት ሆነኝ… ምነው ፤ ለምን
ጠየቁኝ?» በማለት ሶፍያ መለሰችለት ።

«አይ ፤ እንደው ነው ። የተለየ ጉዳይ ኑሮኝ አይደለ
ም ። እሥር ቤት ገብተው ነበርን?» አላት ።

«አዎን» አለችው ።

«አየህ? አንተ ግን ስለርሷ ስትናገር ባለግ ብለህ
ነበር…» በማለት እናት ለቀድሞ ንግግሯ የሶፍያን
መልስ ማረጋገጫ አድርጋ በዝግታ ሪቢንን ተናገረች ።

ሪቢን ዝም አለ ። ከዚያም ከታሠሩት የመጻሕፍት
ጥራዞች አንዱን ብድግ አድርጎ በማንሳት ጥርሱን
እያሳየ ፈገግ በማለት ፡ —

«አደራ እንዳይቀየሙብኝ ፤ የመኳንንት ተወላጆች
እና ገበሬዎች ቅርጣን እና ውሀ እንደማለት ናቸው ።
አንድ ላይ ተስማምተው አይዋሃዱም!»

«እኔ ግን ከመኳንንት ወገን አይደለሁም ። ሰብ
አዊት ፍጥርት ነኝ!» አለች ሶፍያ መለስ ባለ ፈገግታ
ፈገግ እያለች ።

«ሊሆን ይችላል ። ውሾች ቀደም ባለው ጊዜ ተኩላዎች ነበሩ ይባላል ። ልሂድ እና ይኸንን ነገር ልሸሽግ» በማለት ሪቢን ተናገረ ።

ኢግናት እና ያዕቆብ እጆቻቸውን በስጠን መልክ ዘርግተው ወደ ሪቢን ዘንድ ሄዱ ።

«እስኪ ጽሁፎቹን እንያቸው» በማለት ኢግናት ተናገረ ።

«ሁሉም አንድ ዓይነት ተመሳሳይ ናቸውን?» በማለት ሪቢን ሶፍያን ጠየቃት ።

«የለም ፤ አይደሉም ። በውስጣቸው አንዳንድ ጋዜጠችም አለባቸው...» በማለት መለሰችለት ።

«እዚህ ላይ ጥሩ!» በማለት መለሰ ።

ሦስቱ ሰዎች ወደ ጎጆው ለመግባት ተጣደፉ ።

«ገበሬው ተነሳስቶአል!» በማለት በማሰላሰል ሁኔታ ሪቢንን እየተመለከተች እናት ዝግ ባለ ሁኔታ ተናገረች ።

«አዎን ። ይኸንን የመሰለ የሰማዕታት ገጽ ከዚህ ቀደም አይቼም አላውቅም! እዚያ እነርሱ ወደሚገኙበት እንሂድ ። ሁኔታቸውን መመልከት እሻለሁ...» በማለት ሶፍያ ተናገረች ።

«ከባድ በሆኑት አነጋገሮቹ ቅር አይበልሽ» በማለት እናት በትህትና ተናገረች ።

ሶፍያ ሳቀች ።

«ኒሎቭና ፤ እንዴት ያሉ ውድ ተወዳጅ ነዎት!» አለቻት ።

ጎጆው መግቢያ ላይ እንደተዳረሱ ኢግናት ጭንቅላቱን ቀና አድርጎ በዓይኖቹ አንዶ ተመለከታቸው ። ከዚያም በወጉ የተደመደመ ፀጉሩን በጣቶቹ እያሻሸ ጉልበቱ ላይ ያሉትን ወረቀቶች ያነብብ ጀመር ። ጎጆው ውስጥ በሚገኝ ቀዳዳ በኩል ወደጎጆው በሚተላለፈው የፀሐይ ብርሃን ጨረር ላይ አስተካክሎ ረቢ



ን ወረቀቱን በመያዙ ሲያነብብ ከንፈሮቹ ይላወሳሉ ። ያዕቆብ እንጨት አልጋ ላይ ከተከመሩት ጽሁፎች ጎን ቁጭ ብሎ ያነብባል ።

እናት ጎጆው ውስጥ ወደሚገኘው አንድ ጥግ ሂዳ ቁጭ አለች ። ሶፍያ በዝምታ ሰዎች-ሰዎቹን እየ ተመለከተች እጆቿን እናት ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጋ ከእናት ኋላ ቆማለች ።

«አጎት ሚኻኢሎ ፤ ከእኛ ከገበሬዎች ስሕተት እያገኙብን ናቸው!» በማለት ዞር ሳይል ያዕቆብ ዝግ ባለ ድምፅ ተናገረ ። ሪቢን እየተመለከተው ሳቀ ። ከዚያም

«ምክንያቱም ስለሚወዱን ነው» በማለት መለሰ ።

ኢግናት ደህና አድርጎ አየሩን ወደውስጥ ከዋጠ እና ራሱንም ቀና ካደረገ በኋላ ፡—

«ይኸውልህ ፤ እዚህ ላይ ምን የሚል መሰለህ ፡— ‘ገበሬው ሰብአዊ ፍጡር መምሰሉ አብቅቶአል’ ይላል ። ዕውነት ነው ሰብአዊ ፍጡር መምሰሉ አብቅቶአል!» በማለት ተናገረ ። የተበሰጨ ይመስላል ። ሰፊ በሆነ ግልጥ ፊቱ ላይ ጥላ አለፈበት ። ከዚያም ቀጠል አድርጎ ፡—

«እኮ ታዲያ ፤ እኔ ቆዳ ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ገብተህ ተቀመጥ እና እስኪ አንተ ማንን እንደምትመስል እንመለከትሃለን ። አይ የእኛ ብልጥ!» በማለት ተናገረ ።

«ትንሽ ጋደም ማለት እሻለሁ ። ደክሞኛል ። ይኸሽታ ደግሞ ናላዬን ያዞረዋል ። አንቺስ?» በማለት እናት ሶፍያን ጠየቀቻት ።

«አረፍ ማለት አልሻም» በማለት መለሰች ።

እናት እንጨት አልጋው ላይ ጋደም ብላ ማንጎላጀት ጀመረች ። ሶፍያ እናት ጎን ቁጭ ብላ እናትን ከማንቀላፋት የሚከሏትን ንቦች እና ተርቦች ትከላከ

ል ጀመረች ። እናት በሶፍያ አሳቢነት ተነክታ ዓይኖቿን በትንሹ ከፍታ ትመለከታታለች ።

ሪቢን ወደ እነርሱ ተጠጋ ።

«ተኛች እንዴ?» በማለት ጠየቀ ።

«አዎን» አለችው ሶፍያ ። በመጨረሻም ትንፋሹን እየዋጠ ፡ —

«እንደሚመስለኝ ፤ ልጅዋን በመከተል ይኸንን ጎዳና የምትጓዝ የመጀመርያይቱ እናት እርሷ ነች! የመጀመርያይቱ!» በማለት ተናገረ ።

«እንቅልፍ አንንሳቸው ። እንውጣ!» በማለት ሶፍያ ተናገረች ።

«አዎን እኛ አሁን ሥራችንን መሥራት አለብን ። ከእርስዎ ጋር መነጋገር ይሻኝ ነበር ። ግን እስከምሽት! ጎበዝ እንሂድ ወደሥራ...» በማለት ሪቢን ተናገረ ።

ሶፍያን ጎጆው አጠገብ ትተዋት ሦስቱም ወደሥራቸው ሄዱ ።

«ተመስገን ጌታዬ ሶፍያና ሪቢን ወዳጅ ሆኑልኝ» በማለት እናት አሰበች ።

እና የእንጨት እና የቅርጣን ሽታ አፍንጫዋን እያወዳት ዕንቅልፍ ወሰዷት ተኛች ።

## 6

የቅርጣን ሠራተኞቹ የሥራ ጊዜው በማብቃቱ ተደስተው ወደጎጆአቸው ተመለሱ ።

ድምፃቸው እናትን አነቃት ። እያዛጋች እና ፈገግ እያለች ከጎጆው ወጣች ።

«እናንተ ትሠራላችሁ ፤ እኔ ደግሞ እንደትልቅ ሴት-ወይዘሮ ተኝቼ ነበር!» በማለት በፍቅር ዓይን እየተመለከተቻቸው ተናገረች ።

«ለዚህ ይቅርታ ይደረግልሻል!» በማለት ሪቢን



መለሰላት ። ከዚህ ቀደም የነበረውን ተጨማሪ ጉልበት ድካም ሙጥጥ አድርጎ ጨርሶበት አሁን ፍጹም ሰላማዊ አድርጎታል ።

«ኢግናት ፤ እንዴት ነው የሻይ ጉዳይ!» በማለት ሪቢን ተናገረ ። ከዚያም ፡ —

«የማዕድ ቤትን ጣጣ በተራ ነው የምንወጣው ። ዛሬ ምግብ እና ሻይ አዘጋጅቶ ማቅረብ የኢግናት ተራ ነው» በማለት ተናገረ ።

«የዛሬውን ተራዬን ከእናንተ መካከል ከአንዳችሁ ጋር ብለዋወጥ ደስ ባለኝ ነበር» በማለት ጭራሮ እና ቅጠላ-ቅጠል ለእሳት ማገዶ እየለቃቀመ ኢግናት ተናገረ ።

«ከእንግዶቹ ጋር ለመቀመጥ የምትሻ አንተ ብቻ አይደለህም» በማለት የፊም ሶፍያ አጠገብ ተቀምጦ ተናገረ ።

«ኢግናት እኔ እረዳሃለሁኝ» በማለት ያዕቆብ ተናገረ ። ወደ ጎጆው ውስጥ ገብቶ የዳቦ ሙልሙል ካመጣ በኋላ በትንሽ-በትንሹ ሸንሽኖ በመቆራረስ ጠረጴዛው ላይ ወስዶ አስቀመጠው ።

«አዳምጥ አንድ ሰው ሳል ይስላል...» በማለት የፊም ተናገረ ።

ሪቢን ! ጆሮውን ቀሥሮ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ።

«እርሱ ነው ። ሕያው ምሥክር እየመጣ ነው...» በማለት ለሶፍያ አስረዳት ።

«እኔ ይኸንን ማድረግ በተቻለኝ ኖሮ ከከተማ-ከተማ ይገሮው ለመዞር እገበያ አደባባይ እያወጣሁት ሕዝቡ ሁሉ እንዲሰማው እንዲናገር አደርግ ነበር ። ሁልጊዜም መልሶ-መላልሶ ስለ አንድ ነገር ብቻ ያወሳል ። ይሁን እንጂ ይኸንን መላልሶ የሚናገረውን ጉዳይ ሁሉም ሰው ይሰማው ዘንድ የሚገባ ጉዳይ ነው...» በማለት ፡ ሪቢን ፡ ተናገረ ።

የጀንበሪቱ መጥለቅ እና የሰዎቹ ዝምታ እየሰፈነ ይሄድ ጀመር ። የሰዎቹ ድምፅ ዝግ ይል ጀመር ። በሚያስገርም ዓይነት ጥንቃቄ ቀስ እያሉ እየተጠነቀቁ የሚራመዱትን ሦስቱንም ሶፍያ እና እናት ትክ እያሉ ይመለከታሉ ። ሦስቱ ሰዎች በበኩላቸውም ሴቶቹን ይመለከቱዋቸዋል ።

ከጫካው ውስጥ ምርኩዝ ተመርኩዞ በዝግታ የሚራመድ አንድ ጎበጥ ያለ ረዢም ሰው ብቅ አለ ። ኩር-ኩር የሚል ጎርናና ድምፅ የሚያሰማው አተነፋፈሱን ሁሉም ይሰሙታል ።

«ይኸው መጥቻለሁኝ!» ካለ በኋላ ሳሉን ይስል ጀመር ።

መሬት ድረስ የሚጎተት ያረጀ ካፖርት ለብሶአል ። የተጨረማመተ ክብ ባርኔጣውን ቢጫማ ቀጫጭን ፀጉሩ አልፎ ወጥቶአል ። አጥንታማ የሆነው ቢጫ ፊቱ በነጭ ጢም ተሸፍኖአል ። ከናፍሮቹ ከመጋጠሚያ ቦታቸው ተለያይተው ተከፍተዋል ። በትኩሳት የተነደፉት ዓይኖቹም ከተቀበሩበት ጉድጓዳቸው ውስጥ ሁነው ክብልል-ክብልል እያሉ ያበራሉ ።

«መጻሕፍት ማምጣትዎን ሰማሁኝ» በማለት ሪቢን ከሶፍያ ጋር ሲያስተዋውቀው ሰውየው ሶፍያን አናገራት ።

«አዎን» አለችው ።

«በመላው ሕዝብ ስም... አመሰግንዎታለሁኝ! ሕዝቦች ዕውነትን ለመቅሰም አሁንም ገና ናቸው... ዕውነትን ለይቼ የማውቅ...እኔ ግን በእነርሱ ስም አመሰግናለሁኝ» አለ ።

ሲተነፍስ ፈጠን ባለ እና በተጣደፈ ሁኔታ ወዲያው ወዲያው ነው ። ሲናገር ድምፁ አሁንም-አሁንም የሚቋረጥ ሲሆን ፤ አጥንታቸው የወጣ የእጁ ቀጫጭን ጣቶችም የደረቱን ቁልፎች ለመቆለፍ ይውተረተራሉ ።



«ጊዜው እንደዚህ ደንገዝገዝ እስኪል ድረስ ጫካ ውስጥ ለእርስዎ መቆየት ጥሩ አይደለም ። ዛፎቹ አየሩን ቀዝቃዛ እና ከባድ ያደርጉታል» በማለት ሶፍያ ተናገረች ።

«ከእንግዲህ ለእኔ የሚስማማ አንዳችም ነገር የለም!» በማለት ትንፋሹን ቁርጥ-ቁርጥ እያደረገ በመሳብ መለሰ ። ቀጠል አድርጎም ፡—

«ለእኔ የሚስማማኝ ሞት ብቻ ነው...» አለ ።

ሲናገር ከአንደበቱ የሚወጣው ድምፅ አንድ ዓይነት ስሜት እንዲያድርባት አደረጋት ። ዕርባነ-ቢስ መሆኑን እንዲረዳው የሚያደርገው መላው የሠራ አካላቱ ከፍተኛ ጸጸት ያሳደረበት ሲሆን ፤ በደረሰበት ሥቃይም ይበልጥ ብስጩ እና ቁጡ እንዲሆን አድርጎታል ። ጉልበቶቹ ቆሽ ብለው የሚሰበሩ መስለውት የሚፈራ በመምሰል በጥንቃቄ እጥፍ-እጥፍ አድርጎአቸው እና በላብ የተጠመቀ ግንባሩን እየጠረገ በርሚል ላይ ቁጭ አለ ። ፀጉሩ ክው ብሎ ጭንቅላቱ ላይ በመድረቁ አይንቀሳቀስም ።

እሳቱ ቦግ ብሎ ተንቀለቀለ ። ሁሉም ነገር በእሳቱ አማካይነት እመር-እመር ሲል ይታይ ጀመር ። ቀደም ሲል አጥልተው የነበሩት ጥላዎች በእሳቱ አማካይነት ፊታቸውን ወደ ደኑ መለሱ ። ከእሳቱ በላይ ከፍ ብሎ የኢግናት ድቡልቡል አገጭ ብሩህ ሁኖ ይታያል ። እሳቱ እየጠፋ ሄደ ። አካባቢው በጢስ ሽታ ታወደ ። ቀስ-በቀስም የሕመምተኛውን ሰው ታሪክ ለማድመጥ የተቻኮለውን አካባቢ ጭለማ እና ፀጥታ ሰፈነበት ።

«እኔ ለተፈጸመ ታላቅ ወንጀል ሕያው ምሥክር በመሆን ሰፊውን ሕዝብ አሁንም ቢሆን ልጠቅም እችላለሁኝ... እስኪ ተመልከቱኝ... ዕድሜዬ ሃያ ስምንት ዓመት ብቻ ነው ። መሞቻ ጊዜዬ ግን ተቃርቦአ

ል ። ከዛሬ አሥር ዓመት በፊት ክብደቱ አሥራ ሁለት ፑድ* የሚመዝን ዕቃ ያላንዳች ችግር አፈፍ አድርጌ በማንሳት ተሸክሜ መሄድ እችል ነበር! እንደኔ ጥንካሬ ያለው ሰው እስከ ሰባ ዓመት ዕድሜ ኖሮት በሕይወት ሊቆይ ይችላል በማለት በዚያን ጊዜ እርግጠኛ ነበርኩኝ ። ይኸው ከዚያን ጊዜ በኋላ የኖርኩት አሥር ዓመት ብቻ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ የሕይወቴ ፍጻሜ ተቃርቦአል ። አሥሪዬ የነበረው ባለንብረት ከላዬ ላይ የእኔን የወደፊት ቀሪ የአርባ ዓመት ዕድሜ ገፍፎ ዘረፈኝ! አርባ ዓመት ቀሪ ዕድሜዬን!» በማለት ተናገረ ።

«ይኸንን ነው እርሱ የሚቃኘው ቅኝት!» አለ ሪቢን ።

ከቀድሞው ይበልጥ ብሩኅ እና ኃይለኛ በመሆን እሳቱ እንደገና ቦግ ብሎ ተንቀለቀለ ። አጥልተው የነበሩት ጥላዎችም ነበልባሉን እየከበቡ እና ድምፅ-የለሽ ጭፍሮ እየጨፈሩ እንደገና ወደ ደኑ ፈረጠጡ ። ርጥበት ያላቸው ግንዲላዎች እሳቱ ውስጥ ገብተው ሲያያዙ ጣ-ጣ-ጣ እያሉ ፍንጥቅጥቅ ይላሉ ። ሞቃትነት ባለው አየር አጫዋችነት ዛፎቹ ላይ ያሉት ቅጠሎች በስሜት ተውጠው ኮሽ-ኮሽ-ኮሽ በማለት እርስ በእርስ ይንሾካሾካሉ ። ወደ ላይ ከፍ-ከፍ እያሉ ሲነሱ አያሌ የእሳት ፍንጣቂዎች ርችቶችን በአየሩ ላይ በመበተን በደስታ የሚፈነድቁት ቀያይ የእሳት ላንቃዎች ከቅጠሎቹ ጋር በአንድነት ሁነው አሸሼ-ገዳሜ ይላሉ ። በእሳት የነደደ አንድ ቅጠል በአየሩ ላይ አሻቅቦ ወደላይ መጠቀ ። በምሽቱ ሰማይ ላይ ተንጣልለው የተሰጡት ከዋክብትም ከበታቻቸው የሚገኙትን

---

* ፑድ የክብደት መመጠኛ ። 1 ፑድ ከ 16 ኪሎ ግራም በለጥ ይላል ። (ተርጓሚው)



የእሳቱን ፍንጣቂዎች ከላይ ሁነው እየጠቀሱ በፈገግታ ተመልተዋል ።

«ይኸ እኔ የምቃኘው ቅኝት አይደለም ። በእነርሱ ላይ የደረሰው ሥቃይ እና ሀዘን ለሌሎች ምሳሌ ሊሆን መቻሉን ሳይገነዘቡ ብዙ ሺህ ሰዎች የሚቃኙት ቅኝት ነው ። በሥራ ቦታቸው ላይ ሥራቸውን ሲያከናውኑ የአካል ጉደለት እየደረሰባቸው ሽባ ሁነው የቀሩ ሰዎች ስንት እና ስንት ናቸው! በችጋር ተቆልተው ያለቁ ስንት እና ስንት ናቸው!..» በሳል ተወጥሮ ሲስል ከሁለት እጥፍ አለ ።

ያዕቆብ የከቫስ መጠጫ ጮጮ እና አረንጓዴ ቅጠሉ ሳይነቀል አብሮት ያለ የሽንኩርት እፍኝ አምጥቶ ጠረጴዛው ላይ ካስቀመጠ በኋላ ፦

«ሳቬሊይ ወደዚህ ቀረብ በል ወተት አምጥቼልሃለሁኝ» አለው ።

ሳቬሊይ በእምቢኝታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። ያዕቆብ ግን እጁን ደግፎ በመያዝ ወደ ጠረጴዛው አቀረበው ።

ሶፍያ በወቀሳ መልክ ቀስ ብላ ሪቢንን ፦

«ምነው ለምንድነው እኚህን ሰው እዚህ እንዲመጡ ያደረጋችሁት? በማንኛውም ጊዜ ድንገት ሊሞቱ ይችላሉ» በማለት ተናገረች ። ሪቢንም ፦

«ይኸንን አውቃለሁኝ ትንፋሹ ኖራ መናገር እስከቻለ ድረስ ግን ይናገር ። የከዚህ ቀደም ሕይወቱ መስዋዕት የሆነችው ረብ ላለው ተግባር አይደለም ። ጥቂትም ቢሆን ብርታት ኖሮት ለበጎ ተግባር አስተዋጽኦ ያበረክት ። ምንም አይደለም ። አያስቡ !» በማለት መለሰላት ።

«አሁን እርሳቸው የሚገኙበትን ሁኔታ እርስዎ የሚደሰቱበት ይመስላሉ!» በማለት ሶፍያ አጠንክራ ተናገረች ።

ሪቢን ሶፍያን መልከት ካደረገ በኋላ የሚከተለውን ቆጣ ብሎ ተናገረ ፡ —

«ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀሉ ላይ ተሰቅሎ ሲሰቃይ የነበረውን ሁኔታ በማድነቅ የምትደሰቱ እናንተ የመኳንንቶቹ ወገኖች ናችሁ ። እኛ ግን የምንፈልገው በዚህ ሰው ላይ ከደረሰው ሁኔታ ትምህርትን መቅሰም ሲሆን ፤ ከዚህ ትምህርት እናንተም በጥቂቱም ቢሆን እንኳን ትቀስሙ ዘንድ እንሻለን...»

እናት የአንድ ዓይኗን ቅንድብ ከፍ አድርጋ በተመስጦ ሸበሸበችው ።

«ተው ይበቃሃል!..» አለችው ሪቢንን ።

ሕመምተኛው ሰው ወንበሩ ላይ ተቀምጦ እንደገና ይናገር ጀመር ፡ —

«አሠሪዎች ሰዎችን በሥራ ለምን ይገድላሉ? የሰውን ዕድሜ ከላዩ ላይ የሚገፍፉት ለምንድነው? ባለንብረት ለሆነው የእኛ አሠሪ — እኔ ኔፌዶቭ ፋብሪካ ውስጥ ተቀጥሬ እሠራ ነበር — የእኛ አሠሪያችን ለአንዲት የመድረክ ተዋንይት ለሆነች ወዳጅ ውሽማው ገላዋን እንድትታጠብበት ከወርቅ የተሠራ የገላ መታጠቢያ ሳፋ እና እንደዚሁም ከመሽ በኋላ ለሽንት መቀበያ የሚሆን ከወርቅ የተሠራ ፓፓ ሳይቀር ሸለማት! ያለ-የሌለ ጉልበቴ እና ሕይወቴ ጭምር ተሟጥጦ ያለቀው በዚህ ፓፓ ላይ ነው! ሕይወቴን የሰጠሁት ለርሱ ነው! በእኔ ሕይወት ውስጥ በሚገኝ ደም ውሽማውን ለማስደሰት ሲል ያ ሰው እኔን በሥራ ገደለኝ! በእኔ የሕይወት ደም ለውሽማው ከወርቅ የተሠራ የሽንት መቀበያ ገዛላት!»

«ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል እና መልክ ሲሆን ፤ እነርሱ በሰው ልጅ ላይ የሚፈጽሙት ግን ይኸንን የመሳሰለውን ተግባር ነው...» በማለት የፊም በማፌዝ ተናገረ ።



«ዝም አትበል!» በማለት ሪቢን ጠረጴዛውን በቡጢ እየመታ ተናገረ ።

«አትታገስ!» በማለት ያዕቆብ ጨመር አድርጎ ተናገረ ።

ኢግናት ፈገግ በማለት ሳቀ ።

·እነዚህ ሦስት ሰዎች ዜናዎችን ሁልጊዜም የሚያዳምጡት ዜናዎችን ለማዳመጥ በተራቡ ልቦቻቸው በታላቅ ጉጉት ሲሆን ፤ ሪቢን በተናገረ ቁጥርም አድፍጠው ዓይን-ዓይኑን በመመልከት በተመስጦ ያዳምጡታል ። ከሳቬሊይ አንደበት የሚወጡት ቃላት በሰዎቹ ገጽታ ላይ የመሪር ሳቅ ፈገግታ እንዲያረብብ አደረጋቸው ። ለሕመምተኛው ሰው አንዳችም ሀዘን ያልተሰማቸው አስመሰላቸው ።

«ይኸ እርሳቸው የሚናገሩት ሁሉ እርግጥ የደረሰባቸውን ነውን?» በማለት እናት ወደ ሶፍያ ጠጋ ብላ ቀስ ብላ ጠየቀቻት ።

«አዎን ። እውነት ነው» በማለት ሶፍያ ድምፅዋን ከፍ አድርጋ ተናገረች ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ —

«ሞስኮ እየታተሙ በሚወጡት የሕቡዕ ጋዜጦች ስለእነዚህ ገጸ-በረከቶች ተጽፈው ነበር» በማለት ተናገረች ።

«ይሁን እንጂ ፤ ወንጀሉን የፈጸመው ሰው ግን አንዳችም ቅጣት አልተፈጸመበትም» በማለት ሪቢን ጠንከር አድርጎ ተናገረ ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«ቅጣቱን መቀበል አለበት ። ሕዝብ ፊት ቀርቦ ያለ የሌለ አካላቱን ክትፍ-ክትፍትፍ አድርጎ መቆራረጥ እና ያንን የበሰበሰ ቁርጥራጭ ሥጋውን ለውሾች መስጠት ያስፈልጋል! ግዴለም! ሕዝቦች ከተኙበት አንዴ ይንቀሳቀሱ እና ይነሱ እንጂ ፤ ከዚያ በኋላስ ከፍተኛ የቅጣት ፍርድ ይፈርዳሉ! በእነርሱ ላይ የተጋገረባቸውን እድፍ በደልን አጥበው ለማጽዳት አያሌ

ደምን ያፈስሳሉ! ያ የሚያፈስሱት ደምም ከገዛ ራሳ
ቸው የደም ሥሮች ተመጥጠው ተሟጥጠው የተቀዱ
የገዛ ራሳቸው ደሞች በመሆናቸው ያሻቸውን የፈለጋ
ቸውን ሊያደርጉ መብት አላቸው!» በማለት ተናገረ ።
«በረደኝ!» አለ ሕመምተኛው ሰው ።
ያዕቆብ ሕመምተኛውን ከተቀመጠበት ደግፎት
ከተነሳ በኋላ እሳቱ ወደሚነድድበት አጠገብ ወሰ
ደው ።
አሁን እሳቱ ብሩኅ ሁኖ ይነድዳል ። የእሳቱን ነበ
ልባሎች አስደሳች ጭፈራ እያስተዋሉ ደብዘዝ ያሉት
ጥላዎች በእሳቱ ዙርያ ከወዲያ-ወዲህ ይተምማሉ ። ሳ
ቬሊይ እሳቱ አጠገብ አንድ ግንዲላ ላይ ቁጭ ብ
ሎ የደረቁ የጠወለጉ እጆቹን እሳቱ ዘንድ ቀረብ አ
ድርጎ ያሞቅ ጀመር ።
ሪቢን ወደሕመምተኛው እየተመለከተ በመገረም
ሁኔታ ጭንቅላቱን በመነቅነቅ ለሶፍያ ፡ —
«ከመጻሕፍት ይልቅ እርሱ ግልጥ-ግልጥልጥ ባለ
ሁኔታ አብራርቶ ይናገራል ። አንድ የፋብሪካ መሣርያ
አንድን ወዝ-አደር ሲገድለው ወይንም እጁን ሲጎም
ደው አሠሪዎቹ የወዝ-አደሩ ጥፋት ነው ይላሉ ። ነገር
ግን ከአንድ ወዝ-አደር ላይ ያለ የሌለ ደሙን ምጥ
ጥ-ሙጥጥ አድርገው ከጨለጡት በኋላ እንደ ቆሻሻ
ወዲያ ,አሽቀንጥረው ሲወረውሩት ይኸንን ድርጊታቸ
ውን የሚያፈርሱበት አንዳችም ማስረጃ አይኖርም ። የ
ወዲያው-በወዲያው ግድያን መገንዘብ እችላለሁኝ ። ነገር
ግን አንድን ሰው ለደስታ ለፈገግታ ሲባል እስከ
ዕለተ-ሞቱ ድረስ እንዲህ አድርገው ለምን እንደሚያ
ሰቃዩ የፈለገውን ዓይነት ማብራርያ ቢቀርብ ሊገባኝ
አይችልም! ሕዝቦችን እንዲህ እያሰቃዩ ፍዳቸውን የ
ሚያሳዩዋቸው በምን ምክንያት ነው? ለምንድነው እኛ
ን ሁላችንንም እንዲህ የሚያሰቃዩን? ለመሳቅ-ለመደሰት



ሲሉ ነው ። በዚህ ዓለም የሞላቸው-የተረፋቸው ደልቃ
ቆች በመሆን እነርሱን እንዲደላቸው እንዲመቻቸው
ሲሉ ነው ። በሰብአውያን ፍጡሮች ደም ያሻቸውን
ሁሉ ለመግዛት እንዲችሉ ነው ፡ — የመድረክ ተዋንያ
ትን ፤ የጉግሥ ፈረሶችን ፤ ከብር የተሠሩ ቢለዋዎችን ፤
የወርቅ ሳህኖችን ፤ ዋጋቸው ውድ የሆኑ የሕፃናት አሻ
ንጉሊቶችን እነዚህን የመሳሰሉትን ለመግዛት እንዲ
ችሉ ነው! ‘ሥራ እንጂ!’ ይላል አሠሪው ። ‘በአንተ
የድካም ውጤት ገንዘብ አግበስብሼ ከምሬ ለውሽማ
ዬ የሽንት መቀበያ የወርቅ ሳህን እንድገዛላት ጠንክ
ረህ ሥራ እንጂ!’ ይላል አሠሪው» በማለት ተናገረ ።
እናት እያስተዋለች በምታዳምጥበት ጊዜ ፓቬል
እና ጓዶቹ የመረጡት ብሩህ መንገድ በዚህ በም
ሽቱ ጨለማ ውስጥ ወገግ ብሎ በርቶ ታያት ።
እራት ከተበላ በኋላ ሁሉም በእሳቱ ዙርያ ለመቀ
መጥ ሄዱ ። ነበልባሎቹ ከግንዲላዎቹ ውስጥ ተስገብግ
በው እየተንሰፈሰፉ ይወጣሉ ። ከጀርባቸው መጋረጃው
ጭለማ ጫካዎቹን እና ሰማዩን ጋርዶታል ። ሕመምተኛ
ው ሰው ዓይኖቹን ብልጥጥ አድርጎ በመክፈት እ
ሳት-እሳቱን እየተመለከተ ተቀምጦአል ። የሕይወቱ ቀ
ሪ ክፍሎች ሕመም አባክኖ ካበላሸው ሰውነቱ ለምን
ግዜውም ለመሰናበት በትዕግሥት-ቢስነት የሚጠባበ
ቁ ይመስል ያለማቋረጥ ይስላል ። በርዶት እየተንዘፈዘ
ፈ ይንቀጠቀጣል ። ሕይወት-አልባ የሆነ ቆዳውን በማ
ሳመር ሳያጋጊጡለት የነበልባሎቹ ብርሃኖች ፊቱ ላይ
ቦግ-ቦግ እያሉ ይበራሉ ። ዓይኖቹ ብቻ እሳት ለብሰው ፣
እሳት ጎርሰው ይነዱ ነበር ።
«ሳቬሊይ ፤ ወደ ጎጆው ብትገባ አይሻልህምን?»
በማለት ያዕቆብ ሕመምተኛውን ጎንበስ ብሎ ጠየ
ቀው ።

«ለምን?» አለ ሕመምተኛው ሰው እንደምንም እ
የጣረ ።

«እዚሁ እቆያለሁኝ ። ከእንግዲህ ከሰዎች ጋር አብ
ሮ ለመቆየት የቀረኝ ጊዜ ብዙም አይደለም!..» በማ
ለት ቀጠል አድርጎ ተናገረ ።

ሁሉንም ተመለካከታቸው ። ፈገግም አለ ። ከዚያም
በጥቂቱ ፈገግ በማለት ሁኔታ ቀጠል አድርጎ በመና
ገር ፡ —

«ለእኔ እዚህ ከእናንተ ጋር መሆኔ ጥሩ ነው ። እ
ናንተን ስመለከት ፤ በስግብግብነት የተዘረፉትን እና
የተገደሉትን ሰዎች የምትበቀሉላቸው መስሎ እየታየ
ኝ ተስፋ አደርጋለሁኝ ።»

ማንም መልስ አልመለሰለትም ። ወዲያውኑም ፤ እንቅ
ልፍ ያዘውና አንገቱ ሕይወት-አልባ ይመስል ደረቱ
ላይ ቅልስ ብሎ ተደፋ ።

«እዚችው እኛ አለንበት ቦታ እየመጣ በመቀመጥ
ሁልጊዜም ይኸንኑ እስካሁን የተናገረውን በመደጋገም
ይናገራል ። ማለትም ፤ በሰብአዊ ፍጡር ላይ የተፈጸመ
ውን ግፍ በመደጋገም ይናገራል» በማለት ሪቢን ሕመ
ምተኛውን አተኩሮ እየተመለከተ ረጋ ባለ ሁኔታ
ድምፁን ለስለስ አድርጎ ተናገረ ። ከዚያም ፡ —

«ነፍሱ በሙሉ ዘወትር የምታስተውለው በሰው
ልጆች ላይ የተፈጸሙትን ግፎች ነው ። በዓይኖቹ ላይ
የተለጠፉ ይመስል ከእነዚህ በስተቀር ሌላ አያስተው
ልም» በማለት ተናገረ ። እናት በሃሣብ ተውጣ ፡ —

«ከዚህ ሌላ ምን ይመልከት? ባለንብረቶች ገንዘብ
ወርውረው የረባ-ያልረባ ቅራቅንቦ ለመግዛት ሲሉ
ብዙ ሺህ ሕዝቦች በሥራ ብዛት በየዕለቱ የሚሞቱ
ከሆነ ከዚህ የበለጠ ሌላ ምን መመልከት ይቻላል?..»
አለች ።

«እርሱን ማዳመጥ ያሰለቻል ። አንድ ጊዜ ቢያዳ



ምጡት አይዘነጋም ። እርሱ ግን ያንኑ አንድ ዓይነት
ቅኝቱን መልሶ-መላልሶ ይቃኛል!» በማለት ኢግናት
ተናገረ ። ሪቢንም ቀበል አደረገና ፡ —

«በዚህ እርሱ በሚያሰማው ቅኝት ውስጥ ማንኛ
ውም ነገር ፤ መላው ሕይወት ተከማችቶ ታጭቆአል ።
ይኸንን መገንዘብ ያሻል ። ይኸንን በርሱ ላይ የደረሰበ
ትን ዕጣውን ብዙ አሥር ጊዜ ደጋግሞ ሲናገር ሰም
ቸዋለሁኝ ። ያም ሁኖ ደግሞ ብዙ ጊዜም ጥርጣሬ
ገብቶኛል ። ሰዎች ብስብሶች እና እርጉሞች ናቸው ብ
ሎ ማመንን የማትፈልግበት ጊዜ አለ ። እከሌ-ከእከሌ
ሳይባል ሀብታምንም ድሀንም የምትወድበት ጊዜ አ
ለ ። ሀብታሞችም ቢሆን... ተሳስተው በስሕተት ጎዳና
የሚመሩበት ጊዜ አለ! ከመካከላቸው አንዳንዶቹ ከችግ
ር ከፍላጎት የተነሳ በሚፈጽሙት ተግባር የታወሩ
ናቸው ። ሌሎቹ ደግሞ በስግብግብነት የታወሩ ናቸው ።
ይኸ ነው ጉዳዩ! አይ የሰው ነገር! አይ ወንድሞቼ!
እያላችሁ በማሰብ ፤ እስኪ መለስ ብላችሁ በዕውነተኛ
ነት አስተውሉ ለራሳችሁ ብቻ ሳይሆን እስኪ ለሁ
ሉም አስቡ! በል-በል! የሚያሰኝህ ጊዜ አለ» በማለት
ተናገረ ።

ሕመምተኛው ሰው ከእንቅልፉ ነቅቶ ዓይኖቹን
ከፈተ እና መሬቱ ላይ ተኛ ። ያዕቆብ ድምፅ ሳያሰ
ማ ጎጆው ውስጥ ከገባ በኋላ የበግ አጎዛ አምጥቶ
ወንድሙ ላይ ደረብ አደረገለት ። ከዚያም እንደቀድሞ
ው ሶፍያ ጎን ሂዶ ተቀመጠ ።

ደም-ግባት ኖሮት የተዋበው እሳት በጭለማ ተው
ጠው ዙርያውን በከበቡት የሰዎቹ አካላት ላይ ፈገ
ግ እያለ ብርሃኑን ያበራባቸዋል ። በሃሣብ የተዋጠው
የሰዎቹ ድምፅ ዝግተኛ ከሆነው ከእሳቱ ነበልባል
ሽውሽውታ እና ጣጣታ ጋር እርምጃውን አስተካክ
ሎ ይተምማል ።

የመላው ዓለም ሕዝቦች የሕይወታቸውን መብት ለማስከበር ሲሉ ስለሚያካሂዱአቸው ትግሎች ፤ ከብዙ ዓመታት በፊት የጀርመን ገበሬዎች አካሂደዋቸው ስለነበሩት አመጾች ፤ ነፃነታቸውን ለመቀዳጀት በማያሰልስ ሁኔታ በሚያካሂዱት ትግል በአየርላንዶች ላይ ስለሚደርስባቸው ስቃይ እና ስለፈረንሳዮች ጀግንነት… ሶፍያ ነገረቻቸው ።

ከፋይ ጨርቅ ምሽትን ተጠቅልሎ በለበሰው በዚህ ደን ውስጥ ፤ በዛፎች ግንብ ተገንብታ በተከበበችይቱ በዚች ትንሽ ሜዳ ላይ ፤ ጥቁሩ ሰማይ ከበላይዋ ዳስ ሁኖ በተዘረጋባት ፤ የእሳት ብርሃን ውጋጋን በሚበራባት ፤ ከወዲያ-ወዲህ የሚቁነጠነጡ ጥላዎች በከበቡዋት በዚች ትንሽ ሜዳ ላይ ፡— ያጡ-የነጡ መናጢ ድሆች እና የሞላቸው-የተረፉቸው ሀብታሞች መኖርያ የሆነችይቱን ይኸችን ዓለም በአመጽ ነውጽ እንድትንዘፈዘፍ አድርገዋት ስለነበሩ ድርጊቶች ተወሳባት ። ለዕውነት እና ለነፃነት የታገሉት ታጋዮች ስም ተጠቀሱባት ። በትግል የዛሉ እና በደም የተነከሩ የዓለም ሕዝቦች ስማቸው እየተጠቀሰ አንድ በአንድ በሰልፍ አለፉባት ።

የሴቲቱ ድምፅ ዝግ ያለ እና የደራ ነው ። በሌላ ምድር በሌሎች ሀገሮች የሚገኙ ወንድሞቻቸውን ታሪክ በፀጥታ ተውጠው የሚያዳምጡትን የእነዚህን ሰዎች ተስፋ ከፍ-ከፍ ለማድረግ እና ዕምነታቸውንም ለማጽናት ካለፈ የቀድሞ ጊዜ የተላለፈ ድምፅ ይመስላል ። የገረጣውን እና የከሳውን የሶፍያን ፊት ሲመለከቱ የመላው ዓለም ሕዝቦች የተቀደሰ ዓላማ ምን እንደሆነ ግልጽ የሆነ ግንዛቤ ሊኖራቸው ቻለ ፡— ለነፃነት የማያቋርጥ ትግልን ማካሄድ መሆኑ ግልጽ ሁኖ ተገነዘቡት ። በአሁኑ ጊዜ እነርሱ የሚያልሙት እና እንዲፈጸምም የሚሹት ሁሉ ፣ አሁን ካለው ጊዜ



ጋር በጭለማ እና በደም መጋረጃ በተሸፈነ ታሪክ አማካይነት እዚያ እና እዚህ ተራርቀው በመለያየት እይተዋቸው ሰምተዋቸው የማያውቋቸው ዘሮች ይሹዋቸው እና ያልሙዋቸው የነበሩ ምኞቶች የነበሩ መሆናቸውን ተገነዘቡ ። በዚች ዓለም ላይ ፍትህ እንድትሰፍን ለማድረግ መሠረተ ጽኑ በሆነ ወሳኝነታቸው ከተባበሩት ጋር ፣ የተሻለ የወደፊት ኑሮን ለመመሥረት የሚደርስባቸውን መከራ በመታገስ እና ደማቸውን በማፍሰስ ይኸንን የጸና ውሳኔያቸውን የተቀደሰ እንዲሆን ካደረጉት በሰፊው ዓለም ከሚኖሩት ሕዝቦች ጋር በልቦናዎቻቸው እና በአዕምሮዎቻቸው ውስጥ ጥብቅ ግንኙነቶችን በመመሥረት ወዳጆች አበጁ ። በመላው ዓለም ከሚገኙ ሕዝቦች ጋር የመንፈስ ግንኙነት ብርሃን በእነዚህ ልቦና ውስጥ የበራ ሲሆን ፣ ማናቸውንም ነገር ለማወቅ ትር-ትር የሚል ልብ ፣ ሁሉንም ነገሮች ሰብስቦ በገዛ ራስ ልብ ውስጥ ለማከማቸት የሚሻ ዓለምን የሚዳስስ አዲስ ልብ በእነዚህ ሰዎች ውስጥ ተፈጠረ ።

«የመላው ዓለም ሕዝቦች በአንድነት ሁነው በመነሳት ራሳቸውን አቅንተው ‘በቃን! ይኸንን መሳዩን ኑሮ ከእንግዲህ መኖር እንሻም! መርሮናል — አንገፍግፎናል!’ የሚሉበት ጊዜ ይመጣል!» በማለት ሶፍያ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ በመሆን ሁኔታ ተናገረች ። ቀጠል አድርጋም ፡—

«ከዚያም በኋላ ፣ በስግብግብነታቸው ብቻ ኃይለኛ የሆኑት የእነዚያ ኃይል ፍርክስክሱ ይወጣል ። ምድር ከድታቸው ከእግራቸው ሥር በመውጣቷ መንጠላጠያ በማጣት የሚይዙት — የሚጨብጡት ይጠፉቻዋል…» በማለት ሶፍያ ተናገረች ።

«እርግጥ ነው ። ያለንን ሁሉ አንዳችም ሳናስቀር የምናበረክት ከሆነ ለማድረግ የሚሳነን ምንም ነገር

አይኖርም!» በማለት ሪቢን አንገቱን ወደታች ቀለስ አድርጎ ተናገረ ።

እናት ቅንድቦቿን ወደላይ ሽብሽብ አድርጋ በማዳመጥ በደስታ ተውጣ ፈገግ አለች ። ቀደም ሲል ለእናት ከሶፍያ አንደበት የሚወጡት ሃሣቦች ቁርጥርጥ ያሉ ፣ ጩኸት የበዛቸው እና እዚያም-እዚህም እየገቡ የሚዘባርቁ መስሏት የነበረው ፣ ከሶፍያ ባሕርይ ጋር ስምም ያይደሉ ሁኔታዎች መስለዋት የነበሩት ሁሉ ፣ ሶፍያ ስሜት ባልተለየው እና አንዳችም ነገር ሳያግዳት ታሪኳን ስታወሳ የቀድሞው የእናት ግምት ተወገደ ። የምሽቱ ፀጥተኛነት ፣ የእሳቱ ፍንደቃ ፣ የሶፍያ ፊት እናትን አስደስተዋታል ። ከሁሉም ይበልጥ ያስደሰታት ግን የገበሬዎቹ በስሜት ተውጦ የማዳመጥ ሁኔታ ነው ። ሳያቋርጥ የሚንቀረቀረውን ታሪክ ላለማቋረጥ በመስጋት ፣ ከመላው ዓለም ጋር አቆላልፎ ያስተሳሰራቸውን ብሩኅ ክር እንዳይበጥስ በመፍራት ንቅንቅ ሳይሉ እዚያው አሉበት ቁጭ ብለዋል ። ከመካከላቸው አንደኛቸው ከጊዜ-ጊዜ አዳዲስ ግንዲላዎችን እሳቱ ውስጥ በጥንቃቄ የሚዶሉ ሲሆን ፣ ከእሳቱ ላይ የሚነሳው ፍንጥቅጣቂ እና ጭስ ሴቶቹ ላይ እንዳያርፍ እጃቸውን በመጋረድ ይከላከሉላቸዋል ።

«ይቅርታ ይደረግልኝ ለአንድ አፍታ ። አሁን እመጣለሁኝ...» በማለት ያዕቆብ ከተቀመጠበት ተነሳ ።

ፈጠን ብሎ ጎጆው ውስጥ ከገባ በኋላ ጥቅል ጨርቆች አምጥቶ ከኢግናት ጋር ሁነው እንግዶቹን ትከሻዎቻቸውን እና ክንዶቻቸውን አለበሷቸው ። ከዚያም ሶፍያ የድል ዕለቶችን እያነሳች በማውሳት ፣ አድማጮቿን በጥንካሬያቸው እንዲተማመኑ መንፈሳቸውን እያነቃቃች ፣ የተጠሙ ሰዎችን አልባሌ አምሮት ለማርካት በማለት እርባና-ቢስ በሆነ ተግባር ሕይወታቸውን አሚጥጠው ከሚጨርሱ ሰዎች ጋር አንድ



መሆናቸውን በማስገንዘብ መናገር ቀጠለች ። እናት ከሶፍያ አንደበት በሚወጡት ቃላት አልተነሳሳችም ነበር ። ይሁን እንጂ ከሶፍያ አንደበት የሚወጡት ቃላት በውስጣቸው ያዘሉት የወንድማማችነት መንፈስ ፣ ሕይወታቸውን መስዋዕት በማድረግ የፍቅርን ፣ የዕውነትን ፣ እና የሀቀኛነት አስተሳሰብን በየዕለት ሥራቸው ለተጠመዱ ሰዎች የሚያደርሱ በመሆናቸው ለእነርሱ ከፍተኛ ምሥጋና በልቧ እንድታቀርብ ለመሆን በቃች ።

«ፈጣሪ ሆይ ፣ እርዳቸው!» አለች እናት በሐሳቧ ዐይኖቿን ዘግታ ።

በድካም የደቀቀችይቱ ሶፍያ ንግግሯን ሲነጋጋ ጧት ማለዳው ላይ አበቃች ። በዙርያዋ የሚገኙትን ብሩኅ የሆኑ በሃሣብ የተዋጡ መልኮችን ፈገግ እያለች ትቃኝ ጀመር ።

«መሄጃ ጊዜያችን ደርሶአል!» አለች እናት ።

«አዎን ደርሶአል!» በማለት ሶፍያ መለሰችላት ።

ከልጆቹ መካከል አንዱ እ-ህህ! በማለት ተነፈሰ ። ሪቢንም አሰምቶት በማያውቀው ቀዝቀዝ ባለ የቅሬታ አነጋገር ፡ —

«መሄዳችሁ በመሆኑ ቅር ይለኛል ። ርስዎ ሲናገሩ ማዳመጥ ጥሩ ነው ። ሰዎች በማይለያዩ ሁኔታ አንድ— መሆናቸው እንዲሰማቸው ማድረግ ታላቅ ነገር ነው ። ብዙ ሚሊዮን ሕዝቦች ተመሳሳይ የሆኑ ነገሮችን እንደሚሹ መገንዘብ ልብን ያገራዋል ። ገርነት ደግሞ የማይበገር ኃይል ነው!» በማለት ተናገረ ።

«አንተ ለርሱ ደግ ስትውል ፣ እርሱ ግን አንተን ከኋላህ በካስማ ይቸነክርሃል!» በማለት የፌም ዝግ ብሎ እየሳቀ ከተቀመጠበት ተነሳ ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«አጎት ሚኻኢሎ ፣ ማንም ሳያያቸው ቀደም ብለው መሄዳቸው ይሻላል ። እነዚህን ተበታኝ ወረቀቶች

ማደል ስንጀምር ፣ ባለሥልጣኖቹ ያመጡትን ሰዎች፡ ፍለጋ ይቀጥላሉ ። እና ከመካከላቸውም አንዱ ፡ — ‘እነዚያ ወደ ቅዱስ ቦታ ተጓዥዎች ትዝ አይሏችሁምን?’ ሊል ይችላል…» በማለት ተናገረ ።

«እናት እንዲህ ለእኛ ብለሽ ስለተቸገርሽ አመሰግናለሁኝ!» በማለት ሪቢን የፊምን አቋረጠው ። «አንቺን ስመለከት ስለፓቬል አስታውሳለሁኝ ። ኸረ እንዴት ያለ በጎ ተግባር ነው የምትፈጽሚው!» አላት ።

አሁን አኳኋኑ የጨዋነት እና ትዕግሥትም ያለው ሲሆን ከትከት ብሎ ከልቡም ይስቃል ። አየሩ ቀዝቃዛ ነው ። አንዳችም ኮት በላዩ ላይ ሳይደርብ እና የሸሚዙ ቁልፍም ተከፍቶ ደረቱ ተገልጦ እየታየ ቆሞአል ። እናት የሰውነቱን ጥንካሬ እያደነቀች ፤

«አንድ ነገር እላይህ ላይ ደረብ ብታደርግ ይሻልሃል ። አየሩ ቀዝቃዛ ነው!» አለችው ።

«ውስጥ-አካሌ ሙቅ ነው!» በማለት መለሰላት ።

ሦስቱ ልጆች ረጋ ብለው እና በእሳቱ ዙርያ ሁነው ይወያያሉ ። ሕመምተኛው ሰው በበግ አጎዛው ተጠቅልሎ ከእነርሱ ሥር ተኝቶአል ። ሰማዩ ወገግ ማለት ጀመረ ። ጥላዎቹ እየጠፉ ሄዱ ። የፀሐይቱን ብቅ ማለት በመጠባበቅ ይንቀጠቀጡ ጀመር ።

«እሺ እንግዲህ ፣ መሄዳችሁ ነው መሰለኝ ። ጤና ይስጥልኝ!» አለ ሪቢን ሶፍያን ለመጨበጥ እጁን እየዘረጋ ። ከዚያም ቀጠል አድርጎ ፡ —

«ከተማ ውስጥ ልናገኛችሁ የምንችለው እንዴት ነው?» አላት ።

«እኔን ነው የምታገኙኝ!» በማለት እናት መለሰችለት ።

ሦስቱ ልጆች ወደሶፍያ ተጠግተው እና ቀርፈፍ-ቀርፈፍ ባለ ሁኔታ ምሥጋና እያቀረቡ ጨበጧት ። እየአንዳንዳቸው በየልቦናቸው ውስጥ የተሸሸገ ደስ የሚ



ያሰኝ እና በጓደኝነት የተመሠረተ ደስታ የተደሰቱ መሆናቸው እና ይኸም ስሜት አዲስ በሆነ ወረቱ አቅፎ የያዛቸው ይመስላል ። እንቅልፍ አጥተው ባደሩት ደረቅ ዐይኖቻቸው ሶፍያን እያዩ ፈገግ እያሉ እርሷን ለመጨበጥ በተራ በተራ ይተላለፉ ጀመር ።

«ከመሄዳችሁ በፊት ወተት አትጠጡምን?» በማለት ያዕቆብ ጠየቀ ።

«ወተት አለን?» በማለት የፊም ጠየቀ ።

«የለም ።» አለ ኢግናት ቅር ብሎት ፀጉሩን ወደ ኋላ እያሻሸ «ተደፋብኝ…» አለ ።

ሦስቱ ልጆች ሳቁ ።

ስለወተት ነበር የሚያወሩት ። ይሁን እንጂ ስለሌላ ነገር የሚያስቡ መስሎአት እናት ገመተች ፡ — ለእርሷ እና ለሶፍያ በጎ የሚመኙላቸው ከመሆናቸውም በስተቀር ሁሉም ነገር የተቃና እንዲሆንላቸው የሚመኙላቸው መሆናቸውን ታውቃለች ። ሶፍያም ይኸንኑ ሁኔታ ብትገነዘብም ግራ የተጋባች ከመሆኑዋም በስተቀር አፍራለች ። ስለዚህም ለመናገር የቻለችው ፡ —

«እሺ ጓዶች ፣ እናመሰግናለን!» ማለትን ብቻ ነው ።

ከአንደበቷ የወጡት እነዚህ ቃላት ገፋ-ገፋ ያደረጓቸው ይመስል ልጆቹ እርስ-በእርሳቸው ተያዩ ።

ሕመምተኛው ሰው ይስል ጀመር ።እሳቱ የነበረበት ቦታ ይነዱ የነበሩት ከሰሎች መንደዳቸውን አቁመዋል ።

«ደህና ሁኑ!» አሉ ገበሬዎቹ ዝግተኛ በሆነ ድምፅ ። ይህ የሀዘንተኛ ድምፅ የሚመስለው አነጋገራቸውም ከሴቶቹ ጆሮ ዘው ብሎ ገባ ።

ማለዳው ላይ ወገግ ባለው ብርሃን ታጅበው ሳይጣደፉ ዝግ ባለ ሁኔታ በዛፎቹ ውስጥ ባለች ጠባብ መንገድ መንገዳቸውን ይዘው ታች-ታቹን ይጓዙ ጀመር ።

«እንዴት ግሩም ድንቅ የሆነ ጊዜ ነበር ያሳለፍ
ነው!» በማለት ከሶፍያ ኋላ-ኋላ የምትሄደው እናት
ተናገረች ። ቀጠል አድርጋም ፡ —

«ልክ እንደህልም ግሩም-ድንቅ የሆነ ጊዜ ነበር ፤
የኔ ውድ ፥ ሕዝቦች ዕውነትን ለማወቅ ይሻሉ! በእርግ
ጥም ያውቃሉ ። የልደት ወይንም የትንሳኤ ክብረ-በ
ዓል ላይ ከቅዳሴ በፊት ጧት-ማለዳ ይመስል ነበ
ር ፡ — ቄሱ ወደ ቤተክርስቲያኑ ገና ስላልመጡ ፥ ሁሉ
ም ነገር ጭልም ያለ ፥ ፀጥ ያለ እና ጭር ያለ ነው ።
ቀስ-በቀስ ግን ሕዝቦቹ ይሰባሰባሉ ። እዚህ መስቀሉ
ፊት-ለፊት አንድ ሻማ ይቀጣጠላል ። እዚያም እንደዚ
ሁ ሌላ ሻማ ይቀጣጠላል ። እንደዚህ እያለ ቀስ-በቀ
ስም ጨለማው ተገፍፎ በመጥፋቱ ቤተ-እግዚአብሔሩ
በብርሃን ይመላል» በማለት ተናገረች ።

«እርግጥ እንጂ!» በማለት ሶፍያ ደስተኛ ሁና መ
ለሰች ። ቀጠል አድርጋም ፡ —

«ቤተ-እግዚአብሔር ማለት መላይቱ ምድር ሁና
የምትገኘው እዚህ ብቻ ነው!» በማለት ተናገረች ።

«መላይቱ ምድር!» በማለት እናት በሃሣብ ተውጣ
ራሷን በአወንታ እየነቀነቀች ሶፍያ የተናገረችውን
ቃል ደግማ ተናገረች ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ ፡ —

«ይኸ ዕውነት መሆኑ እጅጉን ጥሩ ነው ። የኔ
ውድ ፥ በጣም ግሩም በሆነ ሁኔታ ነበር ንግግር ያሰ
ማሽው ። በጣም ግሩም በሆነ ሁኔታ! አይወዱሽ ይሆና
ል ብዬ ፈርቼ ነበር... »አለች ።

ሶፍያ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብላ ነበር ። ቆየት ብ
ላም ፡ —

«ከእነርሱ ጋር መሆን አንድን ሰው መኮፈስ —
መዘባነን በሌለበት ሁኔታ ላይ እንዲገኝ ያደርገዋል...»
አለች ።

ስለ ሪቢን ፥ ስለ ሕመምተኛው ሰው ፥ እንደዚሁም



በተመሰጠ ፀጥ ብለው ነገር ግን ቀርፈፍ-ቀርፈፍ በ
ማለት ያዳምጡ ስለነበሩት እና አንዳንድ ግልጋሎቶ
ችን በመፈጸም ባለውለታ መሆናቸውን ስሜታቸውን
የገለጹትን እነዚያን ሦስት ልጆች እያነሱ በማው
ራት መንገዳቸውን ተያያዙት ። ጥቂት ከተጓዙ በኋላ
ም ወደ እርሻ ቦታዎች የደረሱ ሲሆን ፀሐይቱም
ትገናኛቸው ዘንድ በሰማዩ ላይ ከፍ ብላ ወጣች ። ገና
በሰማዩ ላይ ብቅ ብላ ትታይ ባልነበረችበት ጊዜ ፥
ብርሃን የሚያሳልፉ እና የሮዝ ቀለም ያላቸው የጨረ
ር ፍንጣቂዎቿን በሰማዩ ላይ ፈነጣጥቃ እንደማራገቢ
ያ ዘርግታቸው ነበር ። ፍንዶቃ በተመላው የፀደይ ደ
ስታ በየሣሮቹ ላይ የሚገኙት የጤዛ ውሀ ጠብታዎች
በአያሌ ቀለማት ነጸብራቆች ፈክተው ያበራሉ ። ወፎ
ቹ ከተኙበት የነቁ ሲሆኑ የጧቱን ማለዳ በአስደሳ
ች ዜማዎቻቸው ግርማ-ሞገስ ሰጥተውታል ። ወፋፍራም
ቁራዎች በመጣደፍ ቃተት-ቃተት እያሉ ትላልቅ ክን
ፎቻቸውን በመቅዘፍ ይበርራሉ። በጥቁር እና በቢጫ
ቀለማት ያጌጠችይቱ ወፍ የፉጨት ዜማዋን ታንቆ
ረቁረዋለች ። በርቀት የሚገኙት ሕዋዎች ከየኮረብታዎ
ቹ ላይ የጭለማ መጋረጃዎችን ገልጠው በማንሳት
ወደሰማዩ ላይ እየወጣች በመምጣት ላይ ያለችውን
ፀሐይ እንኳን ደህና መጣሽ ለማለት በራቸውን ከፍ
ተው ይጠባበቋት ጀመር ።

«አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰው ዝም ብሎ ሳያቋ
ርጥ ንግግሩን የሚቀጥል ሲሆን ፥ ማናቸውንም የሚናገ
ረውን ነገር ቁልጭ አድርጎ የሚያስረዱ ቀላል ቃላ
ትን እስኪሰነዝር ድረስ የሚናገረው ስለምን እንደሆ
ነ መረዳት አስቸጋሪ ነው!» በማለት እናት በሃሣብ
ተውጣ ተናገረች ።

«የሕመምተኛው ሰው ሁናቴም ልክ ይኸንኑ መሳ
ይ ነበር ። እኔ ብዙ-ብዙ ሰምቻለሁኝ ። ከፋብሪካዎች

እና ከሌሎች የሥራ ቦታዎች ወዝ-አደሮችን እንዴት እንደሚያባርሩዋቸው እኔ ራሴም አውቃለሁኝ ። ይሁን እንጂ ፣ ሁኔታው ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ የሚፈጸም በመሆኑ ስለሚለመድ ድርጊቱ ይኽን ያህልም በስሜት የሚነካ አይሆንም ። ሕመምተኛው ያሰማው ታሪክ እጅግ አሰቃቂ የሆነ ታሪክ ነበር! እጅግ አሳፋሪ የሆነ ታሪክ ነበር! አቤቱ የፈጣሪ ያለህ! አሠሪዎች እና ባለ ንብረቶች እንደዚያ የመሰለ ፌዝ እና ልግጫ እንዲያደርጉ ሲባል ሕዝቦች ሕይወታቸውን እንዲህ ሙጥጥ አድርገው እና አንጠፍጥፈው ይሰጣሉ ማለት ነውን? በዚህ ድርጊት ላይ አንዳችም ፍትህ አይገኝበትም!» በማለት እናት ተናገረች ።

እናት ከዚህ ቀደም ሰምታው ሳለ ነገር ግን ደግሞ ዘንግታው የነበረውን አንድ አሳዛኝ ድርጊት በዚህ ሰው ላይ የደረሰው ሁኔታ እንድታስታውሰው አደረጋት ።

«ኑሮ ቋቅ እስኪል ያንገፈገፋቸው ለመሆኑ ሁኔታቸው ያስታውቃል ። አንድ የገጠር ባለሥልጣን ፈረስ ነበረው ። ይኽ ፈረሱ በገጠር መንደር ባለፈ ቁጥር ገበሬዎች እጅ እንዲነሱት አዝዞአቸው ነበር ። እጅ ያልነሳ ቢኖር ተይዞ እንዲታሠር ያደርጋል ። ወይጉድ! ይገርማል እኮ! ይኽን ማድረጉ ከቶ ምን ጥቅም ያስገኝልኛል ብሎ በማሰብ ይሆን? ከቶ ለምን ብሎ ይኽን ያደርግ እንደነበረ መረዳት አስቸጋሪ ነው! ፍጹም አስቸጋሪ ነው!» በማለት እናት ተናገረች ።

ሶፍያ እንደማለዳ ንጋት ብሩኅ እና አንቂ የሆነ ዜማዋን ዝግ ባለ ድምፅ ታንቀረቁራለች…

## 7

የእናት ሕይወት በሚያስገርም አኳኋን በተረጋጋ ሁኔታ ይዘልቅ ጀመር ። አንዳንድ ጊዜም ይህ የመረጋ



ጋቷ ሁኔታ እራሷንም ያስገርማታል ። ልጅዋ እሥር ቤት ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ከባድ ቅጣት እንደሚጠብቀውም ታውቃለች ። ያም ሆኖ ግን ሁልጊዜም ስለ እርሱ ባሰበች-ባሰላሰለች ቁጥር አንድሬይ ፣ ፌዎዶር እና ሌሎቹም ጭምር ገጽታቸው ከፊት ለፊቷ በሃሣቧ መጥተው ድቅን ይሉባታል ። የልጅዋ ገጽታ ልክ እንደርሱው የእርሱን ዓይነት ዕድል-ፈንታ ካጋጠማቸው ጓዶቹ ገጽታ ጋር በአንድነት ዐይኖቿ ላይ ድቅን እያሉ ይመላለሳሉ ። ይኽ ሁኔታ ወደብዙ አቅጣጫዎች ቅርንጫፎች ያወጣ ሁኔታ እንደሆነ ዓይነት አድርጋ እንድታስብ ያደርጋታል ። በማናቸውም ክሥተት ላይ ብርሃን ለመፈንጠቅ እና ማናቸውንም ነገሮች አንድ-ወጥ በሆነ ሁኔታ አከማችቶ ለማካተት ተውተርትረው እንደተዘረጉ ቀጫጭን ጨረሮች የትኛውም ቦታ ደርሰው ይገኛሉ ። አዕምሮዋ በአንድ ነገር ላይ ብቻ ተወስኖ እንዳያስብ ያደረጉዋት ሲሆኑ ፣ በተለይም በዚህ ሁኔታ ልጅዋን ከመናፈቅ ከመጠባበቅ እና እርሱ ላይ ምን ይደርስበት ይሆን ብላ ከማሰብ እንድትቆጠብ አድርገዋታል ።

ወዲያው ብዙ ሳትቆይ ሶፍያ ከቤት ወደሌላ ቦታ ሄደች ። ከአምስት ቀናት በኋላም እጅግ ደስተኛ በሆነ መንፈስ ተመልሳ መጣች ። ጥቂት ሰዓቶች ብቻ ቆይታ እንደገና ሄደች ። እንደገና ደግሞ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ተመልሳ መጣች ። የወንድሟን ቤት ጠንካራ በሆነው መንፈሷ እና በሙዚቃ ጨዋታዋ ታውደው ዘንድ ፣ አንድ ሰፊ እና ክብ የሆነ የሕይወት መሥመርን ተከትላ በመዞር ሄዳ-ሄዳ ፣ ዞራ-ዞራ ወንድሟ ቤት የምትመለስ ይመስላል ።

እናት ሙዚቃ ታፈቅር ጀመረች ። ሙዚቃ ስታዳምጥ ሞቃት የሆኑ ሞገዶች ልቧ ውስጥ ድው-ድው እያሉ የሚመቱ መስሎ የሚሰማት ሲሆን ፣ ሙዚቃው

ልቧ ውስጥ እየተንቆረቆረ በመውረድ የልቧ ትርታም
ትክክል በሆነ ሁኔታ የሚመታ ከመሆኑም በስተቀር ፣
አስፈላጊውን እርጥበት እና ሙቀት አግኝቶ በሚገባ
መሬት ውስጥ እንደተዘራ ዘር የምታዳምጠው ጣዕመ-
ሙዚቃ ፈጣን በሆነ ሁኔታ ውበት ወደአለው ቃላት
ነት አብቦ የሚያቆጠቁጥ የሃሣብ እንቡጥ እንድታበ
ቅል ያደርጋት ጀመር ።

የሶፍያን የንጽሕና ጉድለት መቋቋም ለእናት አስ
ቸጋሪ ነው — የመኖርያው ቤት ሁል ጊዜም በሶፍያ
ልብሶች ፣ ሲጋራዎች እና የሲጋራዎች አመድ ይቆሽ
ሻል ። ከዚህም በስተቀር ፣ ረጋ ካለው እና በእርሱነቱ
ተማምኖ ሁልጊዜም የድምፁን አጣጣል ሳይቀይር
በተደላደለ ድምፅ ከሚነጋገረው ጨዋነት ካልተለየው
የኒኮላይ ለስለስ ያለ አነጋገር ጋር እናት ስታነጻጽረ
ው የሶፍያ አነጋገር በኃይለ-ቃላት የተመላ ነው ።
ጠበቅ አድርጋ ድምፅዋንም የምትረግጥ በመሆኑ ይኽ
ንን የሶፍያን የአነጋገር ሁኔታ እናት ተቀብላ መላመ
ዱ አስቸግሮአት ነበር ። እናት ሶፍያን የምትመለከታት
አደግሁ-አደግሁ እንደምትል ፣ ግን ገና ለአቅመ-ሄዋን
እንዳልደረሰች እና ሰዎችንም እንደአስደናቂ አሻንጉሊ
ት እንደምትመለከት ወጣት ልጃገረድ አድርጋ ነው ።
ሶፍያ ስለሥራ ክቡርነት ምን ግዜም ቢሆን የምታወ
ሳ ስትሆን ፣ እርሷ ራሷ ግን የቤት ንጽህናን የማትጠ
ብቅ በመሆኗ በእናት ላይ ተጨማሪ ሥራ ጭናባታ
ለች ። ግሩም በሆነ አቀራረብ ስለነፃነት ሁልጊዜም
ታወሳለች ። ይሁን እንጂ ፣ በትዕግሥተ-ቢስነት እና መ
ጨረሻ በሌላቸው ክርክሮቿ ሌሎችን የምትጫን መሆ
ኗን እናት አስተውላለች ። ሶፍያ እርስ-በእርሳቸው በ
ሚቃረኑ ባሕርዮች የተገነባች በመሆኗ እና እናትም
ይኽንን በመገንዘቧ ከሶፍያ ጋር ያላትን ማናቸውን
ም ግንኙነቶች ከኒኮላይ ጋር እንዳላት ምንግዜም የማ



ይለዋወጥ የመግባባት ግንኙነት ሳይሆን ተጠንቅቃ
እንደባሕርይዋ አመጣጥ ነው የምትቀበላት ።

ኒኮላይ አሰልቺ የሆነውን ኑሮውን ከዕለት-ዕለት
በሚገፋበት ጊዜ ምን ጊዜም ለሰዎች በማሰብ መንፈ
ስ የተዋጠ ነው ፡ — ከጧቱ ሁለት ሰዓት ላይ ኒኮ
ላይ ሻዩን እየጠጣ ጋዜጣውን ካነበበ በኋላ ለእናት
የጋዜጣውን ዜና ይተርክላታል ። እርሱ የሚያወራላትን
የጋዜጣ ታሪክ ስታዳምጥ የሕይወት መኪና ሰዎችን
ርኅራኄ በሌለው ሁኔታ እንደምን አድርጎ ወደገንዘ
ብነት እንደሚጨፈላልቃቸው ግልጥ ብሎ ይታያታል ።
ኒኮላይ ከአንድሬይ ጋር በብዙ ሁኔታዎች ተመሳሳይ
ነት እንዳለው ተገንዝባለች ። ልክ እንደኾኾል ስለሰዎ
ች የሚያወራው የተለየ ጥላቻ ኖሮት ሳይሆን በዓለ
ም ላይ ለሚፈጽሙት ስሕተቶች ሁሉንም በመውቀ
ስ ነው ። ወደፊት ለሚመጣው አዲስ ሕይወት ያለው
ዕምነት ግን እንደአንድሬይ ጠንካራ የሆነ እምነት
እና እንደመስተዋት ወለል ብሎ የሚታይ አይደለም ።
ሁልጊዜም ሲናገር እንደኮስታራ እና ሀቀኛ ዳኛ ረጋ
ባለ ድምፅ ሲሆን ፣ እጅግ አስፈሪ የሆኑ ነገሮችን ሲያ
ወራም በጉዳዩ በማዘን መልክ መለስተኛ ፈገግታዎች
በከናፍሮቹ ላይ ወርደው ይታያሉ ። ዐይኖቹም ጠንከር
እና ቀዝቀዝ ያለ አመለካከት ይመለከታሉ ። ይኽንን
በመመልከት ፣ ለአንዳችም ነገር ቢሆን ምህረት-የለሽ
መሆኑን ፣ እናት የተገነዘበች ስትሆን — ለአንዳችም ነገ
ር ምህረት የማያደርግ መሆኑን በመመልከት — እና
ይኽውም ለእርሱ ቀላል ጉዳይ አለመሆኑን በመመል
ከቷ እናት አዘነችለት ። ለእርሱ ያላት ፍቅር በየዕለቱ
እያደገ ይሄድ ጀመር ።

ሦስት ሰዓት ሲሆን ወደሥራ ቦታው ይሄዳል ።
ከሄደ በኋላ ቤቱን ታጸዳዳ እና ምሳ ታዘጋጃለች ። ተ
ጣጥባ ንጹሕ ልብስ ከለበሰች በኋላ ክፍሏ ውስጥ

ገብታ በመቀመጥ መጻሕፍት እያገላበጠች ስዕላ-ስዕሎችን ትመለካከታለች ። አሁን ንባብ ማንበብ ችላለች ። ይኸንን ለማድረግም ከፍተኛ ጥረት አስፈልጓት የነበረ በመሆኑ ወዲያው ስልችቷት ስለተወችው አንዱ ቃል ከሌላው ቃል ጋር ያለውን ግንኙነት መገንዘብ አልቻለችም ። ስዕሎችን መመልከት እንደህፃን ልጅ ደስ ያሰኛት ጀመር ። የምትመለከታቸው ስዕሎች ልትገነዘባቸው እና በተጨባጭ ልትረዳቸው ስለምትችላቸው አስደናቂ ነገሮች ያብራሩላታል ። በእነዚህ ስዕሎች አማካይነት ትላልቅ ከተማዎች ፣ አስደሳች ሕንፃዎች ፣ ማሺኖች ፣ መርከቦች ፣ የመታሰቢያ ሃውልቶች ፣ ሊቆጠሩ የማይችሉ እና የሰው ልጅ እጆች የፈጠራቸው አያሌ ሃብቶች ፤ የዓይነታቸው ብዛት እጅግ የሚያስገርሙ የተፈጥሮ ታላቅ ስጦታዎች ፣ ከፊት-ለፊቷ ተገጥግጠዋል ። ዐይኖቿን ከአንዱ አስደናቂ ነገር ወደ ሌላኛው በማዘዋወር ፣ እጅግ አስደናቂ በሆኑ የሀብት ትርእይቶች ፣ ማብቂያ ማለቂያ በሌላቸው ውጤቶች የተራበ ነፍሷን በመመገብ ማብቂያ በሌለው ሁኔታ ዕውቀቷን እያሰፋች ትዘልቅ ጀመር ። በተለይም ደግሞ የእንስሳት ሥነ-ፍጥረት ጥናት የተከማቸበት የዙዎሎጂ አትላስ መጽሐፍን አዘውትራ መመልከት የምትወድ ሲሆን ፣ ይኸው አትላስ ምንም እንኳን በባዕድ ቋንቋ የተዘጋጀ ቢሆንም የዚችን ዓለም ሀብት ፣ ውበት እና ሰፊነት እንድትገነዘብ አድርጎአታል ።

«ይህች ዓለም እንዴት ሰፊ ነች!» በማለት አንድ ቀን ለኒኮላይ ገለጸችለት ።

ይበልጥ እጅግ በደስታ ትዋጥ የነበረችው ነፍሳትን በመመልከት ሲሆን በተለይም ቢራቢሮዎች ያስደስቷታል ። የሚያስደንቅ በሆነ አኳኋን ስዕሎቹን ትመለከታለች ፡ —

«ኒኮላይ ኢቫኖቪች ፣ እነዚህ ቢራቢሮዎች አስደሳች አይደሉምን?» በማለት ኒኮላይን ጠየቀችው ። ቀጠል አድርጋም ፡ —

«ሳናያቸው እና ሳንገነዘባቸው በየቦታው ብር-ብር የሚሉ አስደሳች በሆነ ውበት የተከሸኑ ቢራቢሮዎች ስንት ናቸው ። ሰዎች አንዳችም ነገር ሳያውቁ ፣ አንዳችም ነገርን ሳይገነዘቡ ከወዲያ-ወዲህ ይሩዋሩዋጣሉ ። ለማወቅ እና ለመገንዘብ ጊዜም ፍላጎትም የላቸውም ። ይህች ዓለም ምን ያህል ባለፀጋ እንደሆነች እና በላይዋ እና በውስጧም እጅግ አስደናቂ የሆኑ ነገሮች የሚኖሩ መሆናቸውን ብናውቅ የቱን ያህል በተደሰትንም ነበር! ሁሉም ነገር ለማንም ፤ እየአንዳንዱ ነገርም ለሁሉም የተሰጠ ነው ። አይደለምን?» በማለት ተናገረች ።

«እንዴታ ፣ ነው እንጂ!» በማለት ኒኮላይ ስዕል ያለው ሌላ መጽሐፍ እያመጣላት ፈገግ በማለት መለሰላት ።

ብዙውን ጊዜ ምሽት ላይ እንግዶች ሊጠይቁት ይመጣሉ ። ከእንግዶቹ መካከልም — አሌክሴይ ቫሲሌቪች የተሰኘው አንዱ ሲሆን እርሱም መልኩ ገርጠት ያለ እና ጥቁር ጢም ያጤመ መልከ-መልካም ፣ ሰውነቱ-ደንዳና እና ረጋ ያለ ሰው ነው ። ሌላኛው የኒኮላይ እንግዳ ደግሞ ሮማን ፔትሮቪች የተሰኘው ሲሆን ፣ እርሱም ፊቱን ብጉር የወረረው ፤ ጭንቅላተ-ድቡልቡል እና በዚህም ሆነ በዚያ ነገር ሃዘን ገብቶት ሁል ጊዜም ቅር በመሰኘት የሚያጉረመርም ነው ። ኢቫን ዳኒሎቪች የተሰኘው ደግሞ ሹጥጥ ያለ ጢም ያጤመ ፣ ድምፀ-ጉልህ የሆነ ቀጭን እና አጭር ሲሆን እርሱም ቀልጣፋ ቻቻተኛ እና አፈ-ወስፌ የሆነ ሹል-አፍ ነገረኛ ነው ። የጎር የተሰኘው እንግዳ ደግሞ በገዛ ራሱ ፣ በጓደኞቹ እና እየጸናበት በሚሄደው ሕመሙ የሚቀልድ ነው ። ከሌሎች ከሩቅ ከተማዎችም እንግ

ዶች ይመጣሉ ። ኒኮላይ ሁልጊዜም በአንድ አርእስት
ላይ ተወስኖ ረዘም ላለ ጊዜ ረጋ ባለ ሁኔታ ከእነ
ርሱ ጋር የሚወያይ ሲሆን ይህ አርእስትም ፡ — የዓ
ለም ሠርቶ-አደር ሕዝቦችን የሚመለከት አርእስት
ነው ። በስሜት ተውጠው እጆቻቸውን እያወዛወዙ
እና ብዙ ሻይ እየጠጡ ረዘም ላሉ ጊዜያት ይከራ
ከራሉ ። አንዳንድ ጊዜ በውይይት ላይ እንዳሉ ፣ ኒኮ
ላይ አንድ መግለጫ አዋጅ ይጽፍ እና ለጓዶቹ ያነብ
ብላቸዋል ። ጓዶቹም ወዲያውኑ ይኽንን መግለጫውን
ከጻፉት በኋላ ፣ የመግለጫው ረቂቅ የተጻፈባቸውን የተ
ቀዳደዱ ወረቀቶች እናት በጥንቃቄ ልቅም አድርጋ
ሰብስባ እሳት ውስጥ ትከትታቸዋለች ።

ለእነዚህ ለሚመጡት ጓዶች ሻይ በምትቀዳላቸው
ጊዜ ስለሠርቶ-አደር ሕዝቦች ኑሮ እና ዕድል-ፈንታ ፣
በሠርቶ-አደር ሕዝቦች መካከል ዕውነትን ለማሠራጨ
ት ስለሚቻልበት እጅግ ጥሩ እና ፈጣን ሁኔታ እን
ደዚሁም የተነቃቃ መንፈሳቸውን በአንድነት ለማከማ
ቸት ስለሚቻልበት ሁኔታ ስሜት በተሞላው መንፈስ
የሚያቀርቡአቸውን ንግግሮች በማዳመጥ ትደነቃለች ።
እርስ-በእርሳቸው ሲከራከሩ ብዙውን ጊዜ የጋለ ስሜ
ት ተሰምቶአቸው እና በቁጣ መንፈስ ተውጠው ሲሆ
ን እርስ-በእርሳቸውም ይዘላለፋሉ ። ይሁን እንጂ መከራ
ከራቸውን ይቀጥላሉ ።

ከእነርሱ ይልቅ የወዝ-አደሮችን አኗኗር እና
ሕይወት እናት በበለጠ ሁኔታ የምታውቀው ሁኖ
ተሰማት ። እነርሱ የያዙት ተግባር እጅግ ሰፊ የሆነ
ተግባር መሆኑን ይበልጥ ግልጽ በሆነ ሁኔታ የተመ
ለከተችው መሰሎ ታያት ። ይኸው የእነርሱ ሁኔታም
በውስጡ አቅፎት የሚገኘው የግንኙነቱ ድራማ ምን
እንደሆነ ሳይገነዘቡ እንደው በልጅ አዕምሮ ሕፃናት
ልጆች ባልና-ሚስት እየሆኑ ሠርግ-ሠርግ ሲጫወቱ



በዕድሜ የበሰለ አዋቂ ሰው ቅር ብሎት እና በርኅራ
ኄ ሁኔታም እንደሚመለከታቸው ሁሉ እናትም ልክ
እንደዚሁ የእነርሱን ሁኔታ በዚሁ መንፈስ ትመለከተ
ዋለች ። ወዳ ሳይሆን እንደው የግዷን እነዚህ እን
ግዶች ሰዎች የሚያሰሙትን ንግግር ልጅዋ እና አን
ድሬይ ከሚያሰሙት ንግግር ጋር ስታነጻጽረው ፣ መጀመ
ርያው ላይ ልትገነዘብ ችላው ያልነበረውን በመካከላ
ቸው ያለውን ልዩነት ልትገነዘብ ችላለች ። በወዝ-አደ
ሮቹ የሠፈራ ቦታ ከሚገኙት ሰዎች ይልቅ እዚህ
አሁን እናት የምትኖርበት ቦታ የሚመጡት ሰዎች
ይበልጥ የሚጯጯሁ ሁነው አግኝታቸዋለች ።

«ብዙ የሚንጫጩት ብዙ የሚያውቁ በመሆናቸው
ነው...» በማለት ነበር ተገንዝባው የነበረ ።

ይሁን እንጂ ፣ እዚህ የሚገኘው እየአንዳንዱ ጓድ
ለሌሎቹ ጓዶቹ ዕውነተኛው አመለካከት የእርሱ እን
ጂ የሌሎቹ ጓዶቹ አለመሆኑን ለማስገንዘብ ይሁነኝ
ብሎ በመጣር ብዙውን ጊዜ እየአንዳንዱ የሚጯጯህ
መሆኑ ሊሰማት ችሎአል ። በዚህን ጊዜም የተቀሩት
ጓዶች ወደትክክለኛ ዕውነት የተጠጉት እነርሱ መሆና
ቸውን ለማሳየት በመጣር ከበድ ያሉ ቃላትን እና
ዘለፋዎችን ይሠነዝራሉ ። እየአንዳንዳቸው የበላይ ሁነው
ተደማጭነት እንዲኖራቸው የሚጥሩ መስለው ታዩዋ
ት ። ይኸውም ሁኔታ ግራ-አጋብቶ አሳዝኖአታል ።

«ፓሻን እና ጓዶቹን በሙሉ ዘንግተዋቸዋል...»
በማለት እነርሱን ቅንድቦቿን ሸብሸብ አድርጋ እና
ዐይኖቿን ተኮር አድርጋ ስታስተውላቸው ታሰላስላ
ለች ።

ምንም እንኳን በሚከራከሩባቸው ጉዳዮች ላይ የሚ
ለዋወጡአቸውን ሃሣቦች ሙሉ በሙሉ ልትገነዘብ
ባትችልም ፣ ክርክሮቻቸውን በሙሉ በከፍተኛ ተመስጦ
ታደምጣለች ። የሚሠነዘሩት ቃላት የሚያሳድሩትን ስሜ

ት ለመገንዘብ ትጥራለች ። ወዝ-አደሮች በሚኖሩበት የሠፈራ ቦታ በጎ-በጎ ነጥቦችን ያዘለ ንድፈ-ሃሣብ በሚወሳበት ጊዜ እንደ አንድ እንደ ሙሉ ጉዳይ ተደርጎ በመወሰድ አጠቃላይ በሆነ ሁኔታ የሚወሳ ሲሆን ፣ እዚህ አሁን የምትኖርበት ቦታ ግን ይኸው ነጥብ የሚወሳው በአጠቃላይ እንደ አንድ ሙሉ ጉዳይ ሳይሆን ፣ ብዙ ቦታዎች ላይ ተሸራርፎ ነው ። እዚያ ፣ ሰዎቹ የሚሰሙአቸው ስሜቶች ጥልቀት ያላቸው እና ጠንካሮችም ናቸው ። እዚህ ግን ለሰዎቹ የሚሰሙአቸው ስሜቶች ከቅን አሳቢነት የተነሳ የተከማቹ ስሜቶች ናቸው ። እዚህ አብዛኛውን ጊዜ የሚወሳው አሮጌውን ሥርአት ስለማፈራረስ ሲሆን እዚያ ግን አብዛኛውን ጊዜ የሚወሳው ስለአዲሱ ሥርአት ነው ። በዚህ ምክንያትም ከልጅዋ እና ከአንድሬይ አንደበት የሚፈልቁት ሃሣቦች ለእርሷ ይበልጥ ተወዳጅ የሆኑ እና ቅርበት ኖሮአቸው ይበልጥ ልትገነዘባቸው የምትችላቸው ሃሣቦች ነበሩ ።

ኒኮላይን ለመጠየቅ አንድ ወዝ-አደር በመጣ ቁጥር ፣ ኒኮላይ እንግዳውን የሚቀበለው እንደወትሮው ሳይሆን በፈገግታ ተመልቶ ገላጭ የሆኑ ቃላቶችን በመሠንዘር ነው ። ቀድሞ ከጓዶቹ ጋር ሁኖ እንደሚያሳየው ሁኔታ ሁሉ ቆጣ የማለት ወይንም የግብር ይውጣ አነጋገር ላለመናገር ተጠንቅቆ አልነበረም ።

«ይኸ የመጣው እንግዳው ሊገነዘበው በሚችለው ሁኔታ ለመናገር እየጣረ ነው!» በማለት እናት ታሰላስላለች ።

ይኸ ሁኔታ ግን አያረካትም ። በእንግድነት የመጣው ወዝ-አደር አንዲት ሠርታ-አደሪት ከሆነችው ከእርሷ ጋር እንደልቡ ተዝናንቶ የሚናገረውን ያህል ከኒኮላይ ጋር የማይነጋገር ከመሆኑም በስተቀር ቆጠ



ብ በማለት ሁኔታ መናገር የሚፈልገውን በሆዱ ይዞ ለመቆየት የሚገደድ መሆኑን አስተውላለች ። አንድ ጊዜ ኒኮላይ ከክፍሉ ውስጥ ወጣ ሲል ፣ በእንግድነት መጥቶ የነበረ አንድ ወጣት ወዝ-አደርን እናት የሚከተለውን ጠየቀችው ፦

«ምነው ለምን ትፈራለህ? ያጠናኸውን ትምህርት ለመምህርህ የምታሰማ የትምህርት ቤት ተማሪ አይደለህም...» አለችው ።

ወዝ-አደሩ ፈታ ብሎ ፈገግ አለ ።

«የቀረው ቀርቶ ጎርምጥ* እንኳን አያውቀው ቦታ ገብቶ ሲገኝ እንደበርበሬ ይቀላል ። በዚህ ላይ ደግሞ እርሳቸው እኮ መሰላችን አይደሉም...» በማለት መለሰላት ። —

አንዳንድ ጊዜ ሳሻ ትመጣለች ። ከመጣች በኋላ ብዙ የማትቆይ ሲሆን ፣ ፈገግታ በተለያት ሁኔታ ስለ መጣችበት ጉዳይ ከተነጋገረች በኋላ ልትሄድ ስትነሳ እናትን ፦

«ፓቬል ሚኻኢሎቪች እንዴት ነው?» በማለት ትጠይቃታለች ።

«እግዚአብሔር ይመስገን! ደህና ነው ። ሃዘን አልገባውም!» በማለት ትመልስላታለች ።

«ሰላምታዬን ያድርሱልኝ!» በማለት ሳሻ ከተናገረች በኋላ ወጥታ ትሄዳለች ።

ፓቬልን ለፍርድ ሳያቀርቡት ለረዥም ጊዜ እሥር ቤት ማቆየታቸው ቅር ያሰኛት መሆኑን እናት አንድ ጊዜ ለሳሻ አዋየቻት ። ሳሻ ምንም መልስ አልመለሰችም ። ፊቷን ኮስተር ያደረገች ከመሆኗም በስተቀር ጣቶቿም ከወዲያ ወዲህ ተወዛወዙ ።

---

* ጎርምጥ (ጎርምድ) ባሕር ውስጥ የሚኖር ፣ ስምንት እግር ሁለት ጥፍሮች ሰፌ ቅርፊት ያለው ሸረሪት-መሰል ሸርጣን ። (ተርጓሚው)

«የኔ ውዷት ፣ እርሱን እንደምትወጇው አውቃለሁ
ኝ...» ብላ ለመናገር እናት ቃጥቷት ነበር ።

ይሁን እንጂ ይኸንን ለመናገር ብርታት አላገኘች
ም ። የልጅቱ ኮስታራ መልክ ፣ ግጥም ብለው የተሳሳ
ሙት ከናፍሮቿ ከአንደበቷ የሚፈልቁት እቅጩን
የሚገልጹ ቃላቶቿ የመወደድን አቅል አድለዋታል ።
የተዘረጋውን እጅዋን በመጨበጥ በከባድ እየተነፈሰች ፤

«አይ የኔ ብስጩ...» በማለት እናት አሰበች ።

አንድ ቀን ናታሻ መጣች ። እናትን እዚያ በማግኘ
ቷም ተደሰተች ። ከዚያም ናታሻ እናትን ከሳመቻት
በኋላ ፡ —

«የእኔ ምስኪን እናቴ ሞተችብኝ!..» በማለት
ድንገት ተናገረች ። ራሷን በቅሬታ እየነቀነቀች ዐይኖ
ቿን ፈጠን-ፈጠን አድርጋ ከወዲያ-ወዲህ በማንገዋ
ለል ፡ —

«በጣም የሚያሳዝን ነው ። ሃምሳ ዓመት እንኳን
አልሞላትም ነበር ። ብዙ ዘመን መቆየት ትችል ነ
በር ። በሌላ በኩል ደግሞ እርሷ ከኖረችው ኑሮ ይል
ቅ ሞት የሚመረጥ መስሎ ይሰማኛል ። ምን ጊዜም
ብቻዋን ነበረች ። ማንም የሚያፈቅራት አልነበረም ። ማ
ንም አስታዋሽ አልነበራትም ። አባቴ ሳያስልስ በላይ
ዋ ላይ ይጮኽባት ስለነበረ ሁል ጊዜም መንፈሷ
እንደተሸበረ ትኖር ነበር ። ይኸን መሳዩ ኑሮ ኑሮ
ይባላልን? ሌሎች ሰዎች ከዛሬ-ነገ የተሻለ ኑሮ ይመጣ
ል ብለው ተስፋ በማድረግ ይኖራሉ ። እናቴ ተርፏት
የነበረ ወደፊት ተስፋ ግን ስድብ እንጂ ሌላ ምንም
አልነበረም...» በማለት ናታሻ ተናገረች ።

«ናታሻ ፣ የተናገርሽው ንግግር ዕውነት ነው!» በማለት
እናት እያሰላሰለች ተናገረች ። ቀጠል አድርጋም ፡ —

«ሰዎች የተሻለ ኑሮ ይመጣል ብለው በማሰብ
ይኖራሉ ። የወደፊቱ ሁኔታ ተስፋ የሌለው ከሆነ ግን



ኑሮ ምኑን ኑሮ ሆነው?» በማለት እናት የልጃገረዲቱ
ን እጅ አሸትሽት አደረገችው ። ከዚያም ንግግሯን
በመቀጠል ፡ —

«እኘ አሁን ብቻሽን ነሽ ማለት ነውን?» በማለት
ጠየቀቻት ።

«አዎን ብቻዬን ነኝ!» በማለት ናታሻ ለስለስ ባ
ለ ድምፅ መለሰችላት ።

«ግድየለም! ምንም አይደለም» ብላ እናት ከተናገረ
ች በኋላ ጥቂት ቆየት ብላ ፡ — «ጥሩ ሰዎች ምን
ጊዜም ቢሆን ብቻቸውን አይሆኑም ። ሰዎች ሁልግዜም
አብረዋቸው ይገኛሉ...» በማለት መለሰችላት ።

## 8

ናታሻ በአንድ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ የጨርቃ-ጨ
ርቅ ፋብሪካ ጎን በሚገኝ ትምህርት ቤት ውስጥ
ማስተማር ጀመረች ። በኅቡዕ እየታተሙ የሚወጡትን
ተበታኝ ወረቀቶች ፣ አዋጆች እና ጋዜጦች እናት ለና
ታሻ ትሰጣለች ።

ይኸ ተግባር የእናት ተግባር ሁኖአል ። በየወሩ
ለብዙ ጊዜያት እንደ መነኩሲት የመነኩሲት ልብስ
በመልበስ ወይንም ጥልፉ-ጥልፎች እና እቤት ተፈት
ለው የተሠሩ ጨርቃ-ጨርቆችን የምትሸጥ አስመስላ
ራሷን በማቅረብ ወይንም ሃብታም የከተማ ሴት
ወይንም ሃይማኖተኛ የሆነች ተጓዥ በመምሰል እንደ
የሁኔታው ተገቢ በሆኑ በልዩ-ልዩ የአለባበስ ዘዴዎ
ች በመጠቀም እንዳትታወቅ ትሆናለች ። ስልቻዋን
በትከሻዋ ተሸክማ ወይንም ሻንጣዋን በእጅዋ አንግባ
በጠቅላይ ግዛቱ ውስጥ በመዞር ተግባሮቿን ታከናው
ናለች ። በባቡር ላይ ፣ በጀልባ ላይ ፣ በትላልቅም ሆኑ

በትናንሽ ሆቴሎች ውስጥ ምን ጊዜም የመሸበር የመ
ደናገጥ ሁኔታ ሳይታይባት በኖረችበት የሕይወት ዘ
መኗ ብዙ የተመለከተች በመሆኗ በራሷ በመተማ
መን እና ከማንኛውም እንግዳ ሰው ጋር በቀላሉ የ
ምትላመድ ጨዋተኛ ሁና ትቀርባለች ።

ከሰዎች ጋር መወያየት ደስ ይላታል ። የሌሎችን
ታሪክ እና ቅሬታቸውንም ማድመጥ ደስ ይላታል ።
ግራ የሚያጋቡዋቸው ጉዳዮች ምን-ምን እንደሆኑ
መርምራ ማወቅ የሚያስደስታት ነች ። እጅጉን ቅር
የተሰኘ ሰውን አግኝታ ማነጋገር ለልቧ ደስታ የሚ
ያስገኝላት ሲሆን ፣ ለዚህ ቅሬታ መነሾ በመሆን ሊደር
ስ የቻለውን የዕድል-ፈንታ ውርጅብኝ የምትቃወም
ስትሆን ፣ ለቅሬታው መፍትሔ የሚሆነውን መልስ
በአዕምሮዋ ውስጥ ቀደም ሲል ገብቶ ከሚገኝ አመለ
ካከት ለማግኘት ትሻለች ። የዕለት እንጀራን ለማግኘት
ፋታ-ቢስ ሁኖ የትግል ጥረት የሚጥር የሰዎች አ
ኗኗር ትርኢቶች በዐይኖቿ ላይ ይመላለሳሉ ። ሰዎች
ን ለማታለል ፣ በሰዎች ላይ ለመጠቀም ፣ ደማቸውን
መጥጦ ለመጠጣት እና የመጨረሻዋን ትርፍ የማግኘ
ት ጠብታ አንጠፍጥፎ ለመጠጣት እርቃኑን የተጋለ
ጠ ድርጊት እና በሚያስቅቅ ሁኔታ ግልጽ የሆኑ
ተግባሮች ሲፈጽሙ ብዙ ሰዎችን ተመለከታለች ። በ
ዚች ዓለም ላይ ማናቸውም ነገር ተትረፍርፎ የሚገ
ኝ መሆኑን ያስተዋለች ስትሆን ፣ በዚህች ሁሉ ነገ
ር ሞልቶ-ተርፎ በሚገኝባት ዓለም ውስጥ ሰፊ ሕዝ
ቦች በእጦት ተጎሳቁለው ፣ በችጋር ተቆልተው የሚገ
ኙ መሆናቸውን ተመልክታለች ። በከተማዎች ውስጥ
የሚገኙ አብያተ-ክርስቲያኖች ፈጣሪ በማይሻቸው አያ
ሌ የወርቅ እና የብር ክምር የታጨቁ ሲሆኑ ፣ ከእነ
ዚህ አብያተ-ክርስቲያኖች በራፎች ላይ ግን ያጡ-የነ
ጡ ድሆች በቀን ሀሩር እየቀለጡ በጧት ቁር እየተን



ቀጠቀጡ እጸድቅ ያለ የሚጥልላቸው ቤሳ ቢኖር ብ
ለው እጆቻቸውን ዘርግተው ዋይ-ዋይ ይላሉ ። ይኸን
ን ሁሉ ከዚህ ቀደም ተመልክታለች ፡ — ሃብታም
የሆኑ አብያተ-ክርስቲያኖችን እና በወርቅ የተንቆጠ
ቆጡ የካህናት ልብሰ-ተክህኖዎችን ፤ መናኛ የሆኑ የድ
ሆች ደሳሳ ጎጆዎችን እና ያረጁ የተበጣጠሱ ልብሶቻ
ቸውን … ይኸንን ሁሉ ከዚህ ቀደም ተመልክታለች ።
ያኔ ቀደም ባለው ጊዜ ግን እነዚህን የመሳሰሉትን
ስትመለከት መሆን ያለበት ጉዳይ ነው ብላ ትገምት
የነበረ ሲሆን ፣ በአሁኑ ጊዜ ግን ይኸንን መሳዩን ድር
ጊት ዝም ብላ በመመልከት ችላ ማለት የማትችል
ከመሆኑም በስተቀር ከሀብታሞች ይልቅ ለቤተ-ክርስ
ቲያን ይበልጥ ቅርበት ያላቸውን እና ቤተ-ክርስቲያ
ንም ለእነርሱ አስፈላጊያቸው በሆኑት በድሆች ላይ
እንደማፌዝ ያህል ትቆጥረው ጀመረች ።

ከዚህ ቀደም ከተመለከተችው ከክርስቶስ ሥነ-ስዕ
ል እና ስለክርስቶስም ከሰማችው ታሪክ እንደተረዳ
ችው ክርስቶስ በአለባበሱ አልባሌ የሆነ እና የድሆ
ች ወዳጅ መሆኑንም ተረድታዋለች ። ይሁን እንጂ ፣
በአብያተ-ክርስቲያኖች ውስጥ እርዳታውን የሚሹ ድሆ
ችን በመጸየፍ ሁኔታ የክርስቶስ ስዕሎች በወርቅ
እና በሀር ተንቆጥቁጠው ሲያብረቀርቁ ትመለከታለች ።
ወዳ ሳይሆን እንደው ድንገት ሪቢን ፡ —

«ስለ ፈጣሪያችን ምንነትም ሳይቀር አሞኝተውና
ል!» በማለት የተናገራቸው ቃላት ትዝ አሉዋት ።

ለራሷ ሊታወቃት ባልቻለ ሁኔታ በየዕለቱ የምታ
ደርሰው ፀሎት እየተቀነሰ ሄደ ። በዚህ ምትክ ግን
ስለክርስቶስ ብዙ ማሰብ ከመቀጠሏም በስተቀር ፣
እንደዚሁም ደግሞ የክርስቶስን ስም አንድ ጊዜም
እንኳን በማንሳት ሳይጠሩ ፣ ስለርሱም አንዳችም ነገር
የሚያውቁ ሳይመስሉ ፣ የክርስቶስን ጠባይ ተከትለው

እና የእርሱንም ፍላጎት አሟልተው በመኖር ዓለምን
የድሆች ዓለም አድርገው በመመልከት እና በውስጧ
አቅፋ የያዘቻቸውን ሀብቶችም ለመላው ሕዝቦቿ በእ
ኩል ለማካፈል ስለሚጥሩት ሰዎች ብዙ ማሰቧን
ትቀጥል ጀመር ። ይኸንን በሚመለከት ረገድ ብዙ
የምታስብ ሲሆን እነዚህ አስተሳሰቦቿም ጥልቀት
ኖሮአቸው ወደውስጥ በማደግ ሥር-መሠረት አበጁ ።
ያየቻቸውን እና የሰማቻቸውን በሙሉ በማቀፍ ቅርን
ጫፎቻቸው እየሰፉ እየተንሰራፉ ያድጉ ጀመር ። አስተ
ሳሰቦቿ የማያቋርጥ ብርሃናቸውን በመፈንጠቅ በመላ
ው ጭለማ ዓለም ላይ በመላው ሕይወት ላይ እና
እንደዚሁም በመላው ሕዝቦች ላይ ቦግ ብሎ የሚበ
ራ ፀሎት ያለውን ብሩኅ የብርሃን መልክ የያዙ ይመ
ስላሉ ። ምን ግዜም ቢሆን ግልጽ ያልሆነ ፍቅርን
ለይታው የማታውቀው እና ፍርሃትን ከተስፋ ጋር ፣
ደስታን ከሀዘን ጋር አቀላቅላ በስሜት የምትይዝበት
ክርስቶስ ራሱም ቢሆን ለእርሷ እጅግ ውድ ተፈቃ
ሪዋ እያደረገችው ትሄድ ጀመር ። ሕይወት ዘርቶ እን
ደገና የተነሳ ይመስል ፣ ይኸንን የእርሱን ስም ፣ የሰው
ወዳጅ የተሰኘውን ይኸንን የእርሱን ስም ከመጥራት
ወደኋላ ባፈገፈጉ እና በእርሱ ስም እጅግ በብዛት
በፈሰሰው ደም ታጥቦ የቀረበ ይመስል ይበልጥ ብሩ
ኅ እና ደስተኛ ሁኖ ፣ ይበልጥ ተመሥጋኝ እና ቅርበት
ም ያለው ሁኖ አገኘችው ። ከእየአንዳንዱ ጉዞዋ በኋላ
በመንገድ ላይ በሰማችው እና ባየችው ተደስታ ፣ የተ
ጣለባትን ግዳጅ በማሟላቷም ረክታ እና በስሜት
ተውጣ ወደ ኒኮላይ ዘንድ ትመለሳለች ።

ብዙ ጊዜ በምሽት ላይ ለኒኮላይ የሚከተለውን
ነገረችው ፣ —

«ይኸንን የመሰለ ጉዞ እየተጓዙ ብዙ መመልከ
ት ጥሩ ነው ። ሕይወትን ለመገንዘብ እንዲቻል ያደር



ጋል ፣ ተራ-ሕዝቦች ተገፍተው-ተገፍተው በሕይወት
ጠርዝ ላይ ተጥለው በመንጠላጠል በጭለማ ተውጠ
ው ይኸ ለምን እንደደረሰባቸው ያሰላስላሉ ። ለምንድ
ነው ተገፍተው የሚጣሉት? የተትረፈረፈ እህል እያለ
ለምን ይራባሉ? ብዙ ዕውቀት ተስፋፍቶ የሚገኝ ሲ
ሆን ' እነርሱ ግን ለምን መሃይማን ሁነው ይገኛሉ?
ተወዳጅ የሆኑ ልጆች እንጂ በፈጣሪ ፊት ሃብታም
ወይንም ደሀ የተሰኙትን የማያውቀው ይቅር ባዩ
ፈጣሪ የት ነው ያለው? ስለአኗኗራቸው ሁኔታ ሲያስ
ቡ ሕዝቦች በቁጣ በመነሳሳት ላይ ናቸው ። በጊዜ
አንድ ዘዴ ፈልገው ለሕዝቦች ካልፈጠሩላቸው በስተ
ቀር ፍትሕ-አልባነት ጠራርጎ የሚያጠፋቸው መሆኑ
እየተሰማቸው ነው ።»

አኗኗራቸው ፍትሕ-አልባ የሆነ መሆኑን ለሕዝ
ቦች መንገር ያለባት ሁኖ ከጊዜ-ጊዜ ይበልጥ ይሰማ
ት ጀመር ። ይኸንን ገፍቶ የመጣ ስሜቷን ለመግታ
ት አንዳንድ ጊዜ ችግር ይሆንባታል...

ኒኮላይ ስዕል የመላባቸው መጻሕፍትን ባሸከማት
ቁጥር በዓለም ላይ ስላሉ አስደናቂ ነገሮች ፈገግ
እያለ ያጫውታታል ። የሰው ልጅ ባከናወናቸው ጥንካ
ሬ ባላቸው ተግባሮች ትደነቃለች ።

«ለመሆኑ ይኸንን የመሰለውን ድርጊት መፈጸም
ይቻላልን?» በማለት ማመን ተስኗት ኒኮላይን ትጠይ
ቀዋለች ።

በትንቢቶቹ ሀቀኛነት የማይናወጽ ጠንካራ ዕምነት
ኖሮት በርኅራኄ ሁኔታ በመነጽሮቹ ውስጥ እየተመለ
ከታት ወደፊት ስለሚደርሱ ሁኔታዎች አንዳንድ ነገ
ሮችን ይነግራታል ።

«የሰው ልጅ ፍላጎቶች ሥፍር-ቁጥር የሌላቸው
ሲሆኑ ፣ ጥንካሬውም ፍጻሜ የለውም! በአሁኑ ጊዜ ነፃ
ለመሆን የሚሻ ማንም ቢሆን ከዕውቀት ይልቅ ገን

ዘብ ማከማቸት ስላለበት ዓለም ራሷን በመንፈስ ለማደስ የምታደርገው ጉዞ ዝግተኛ የሆነ ነው ። የሰው ልጆች ስግብግብነትን እና የግዳጅ ሥራን ሲያስወግዱ...»

ከአንደበቱ የሚፈልቁትን እነዚህን የመሳሰሉትን ቃላት የሚሰጡትን ትርጉም የምትገነዘባቸው በመጠኑ ሲሆን ፣ ቀስ-በቀስ ግን ቃላቱ እንዲገለጽ የሚያደርገውን ረጋ ያለ ዕምነት ለመገንዘብ ቻለች ።

«የሚበቃውን ያህል ነፃ የሆኑ ሕዝቦች በዓለማችን ላይ የሉም ። ችግሩ ይህ ነው!» በማለት ተናገረ ።

ይኸንን ትገነዘባለች ። ከስግብግብነት እና ከጨካኝነት ከተላቀቁ ሰዎች ጋር ተዋውቃለች ። እነዚህን የመሳሰሉ ሰዎች በብዛት ቢኖሩ ሕይወት እንደዚህ ጨለማ እና አሳዛኝ ባልሆነም እንደነበረ ተገንዝባለች ። ሕይወት ቀላል ፣ ብሩህ እና የተከበረ ሊሆን በቻለም ነበር ።

«ሰዎች ጨካኞች እንዲሆኑ ተገድደዋል!» በማለት ኒኮላይ ቅር ብሎት ተናገረ ።

የኾኾል ንግግሮች ትዝ ብለዋት እና በአነጋገሩም ተስማምታ ራሷን ነቀነቀች ።

9

ምን ጊዜም ቢሆን እጅግ ሰዓትን አክባሪ ሁኖ በተገቢው ሰዓት ወደ ቤት ይመጣ የነበረው ኒኮላይ አንድ ቀን አለወትሮው ዘግይቶ ከሥራ ቦታው ወደ ቤቱ መጣ ። ከዚያም ካፖርቱን ሳያወልቅ በሃሣብ ተውጦ እጆቹን እያሻሸ ፡ —

«ኒሎቭና ፣ ከጓዶቻችን መካከል አንዱ ከእሥር ቤት ዛሬ አመለጠ ። ማን ሊሆን ይችላል? ማን እንደሆነ ለማወቅ አልቻልኩኝም...» በማለት ተናገረ ።



«ፓቬል ይሆን ይሆን?» በማለት እናት እተቀመጠችበት ቦታ ሁና በቀስታ ተናገረች ።

«ሊሆን ይችላል!» በማለት ማን ያውቃል በሚል ሁኔታ ትከሻውን ነቅነቅ አደረገ ።

«እንዲሸሸግ ለማድረግ እንዴት እንችላለን? እንዴትስ እናገኘዋለን? ላገኘው እችል ይሆናል ብዬ በመገመት በየጎዳናዎቹ ከወዲያ-ወዲህ ስመላለስ ነበር ። እርግጥ ነው ይኸ ሞኛ-ሞኝ መሆን ነው ። ቢሆንም አንድ ነገር ማድረግ አለብን! እንደገና ወጣ እላለሁኝ...» አላት ።

«እኔም አብሬህ እወጣለሁኝ!» በማለት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ እናት ተናገረች ።

«እርስዎ የጎር ዘንድ ሂደው በጉዳዩ የሚያውቀው ነገር መኖሩን ያጣሩ» በማለት ለመውጣት እየተቻኮለ ተናገረ ።

እራሷ ላይ ሻሽ ብጤ ጣል አደረገች እና በተስፋ ተመልታ ኋላ-ኋላው በጎዳናው በፍጥነት ትራመድ ጀመር ። ዐይኖቿ ፊት-ለፊት ቀያይ ነቁጦች የሚጨፍሩ ሲሆኑ የልቧ ትር-ትርታም ለመሮጥ ምንም ያህል ባልቀረው ሁኔታ እየፈጠነች እንደትራመድ አደረጋት ። ጭንቅላቷን ወደመሬት ዝቅ አድርጋ እና ራሷ ያለችበትን ሁኔታም ዘንግታ የአጋጣሚ ነገር ቢያገናኘኝ ብላ ትጓዝ ጀመር ።

«የጎር ዘንድ ባገኘውስ!» የሚል የተስፋ ስሜት ነበር በሃሣቧ ደጋግሞ የሚመላለስባት ።

ጊዜው ሞቃት ነበር ። ከድካም የተነሳ ቁና-ቁና ትተነፍሳለች ። የጎር የሚኖርበት አፓርትመንት የፎቅ ደረጃ ላይ ስትደርስ ደረጃዎቹን እየወጣች ወደፊት ጉዞዋን ለመቀጠል አልቻለችም ። ቆመች ። ግራ-ቀኙን ዞር-ዞር ብላ ተመለከተች ። ድንገት እንባ ተናንቋት ድምፅዋን ሳታሰማ ዐይኖቿን ጨፍና አለቀሰች ። እጆቹ

ን ኪሶቹ ውስጥ ከትቶ ኒኮላይ ቬሶቭሺኮቭን እበራ
ፉ ላይ ቆሞ የተመለከተችው መሰላት ። እንደገና ብት
መለከት ግን ማንም ሰው የለም…

«በሃሣቤ ነው የታየኝ!» በማለት ፎቁን እየወጣች
እና ድምፅ እያዳመጠች አሰበች ። ከበስተውጪ በኩል
እምድር ወለሉ አጠገብ ዝግ ብሎ የሚራመድ የአን
ድ ሰው የእግር ኮቴ ይሰማታል ። መራመዱን ትታ
ቆመች እና ካለችበት ፎቅ ቁልቁል ወደታች ትመለከ
ት ጀመር ። አሁንም እንደገና የፈንጣጣ ምልክት ያለ
በትን ሰው ኒኮላይ ቬሶቭሺኮቭን የተመለከተች ሲሆን
አሁን ግን ፈገግ በማለት ይስቅ ነበር ።

«ኒኮላይ! ኒኮላይ!» በማለት ጮኽ ብላ በመጣራት
እርሱን ለመገናኘት በፍጥነት እርምጃ ቁልቁል ፎቁ
ን ትወርድ ጀመር ። ልቧ በተስፋ መቁረጥ ቆሰለ
ባት ።

ኒኮላይ ጭንቅላቱን እመት-እመት በሚል ሁኔታ
ነቅነቅ ነቅነቅ እያደረገ ፡ —

«ይመለሱ ወደላይ!» በማለት ተናገራት ።

ከዚያም ፈጥና ፎቆቹን ወደላይ በመወጣጣት የጎ
ር ከሚኖርበት ክፍል ገባች ። የጎርንም ድንክ አልጋው
ላይ ተጋድሞ አገኘችው ።

«ኒኮላይ ከእሥር ቤት አመለጠ!» በማለት ትንፋ
ሿ ቁርጥ-ቁርጥ እያለ ተናገረች ።

«የትኛው ኒኮላይ? ሁለት ኒኮላዎች ናቸው ያሉት…»
በማለት የጎር ጭንቅላቱን ከትራስ ላይ ቀና አድር
ጎ በጎርናና ድምፅ ጠየቃት ።

«ኒኮላይ ቬሶቭሺኮቭ ። አሁን እዚህ ይመጣል!..»
አለችው ።

«ጥሩ ነው!» አላት ።

በዚህ ጊዜ ኒኮላይ ራሱ ወደ ክፍሉ ውስጥ ገባ ።
በሩንም ከዘጋ በኋላ አጥልቆት የነበረውን ኬፒ ቆብ



አውልቆ ቀስ ብሎ እየሳቀ እና ፀጉሩን እያሻሸ ቆ
መ ። የጎር ከትራሱ ላይ አንገቱን ቀና አድርጎ ተነሳ ።

«እንኳን ደህና መጣህ!» አለው ራሱን ነቅነቅ እያ
ደረገ ።

ኒኮላይ ፈገግ በማለት ወደ እናት ዘንድ ቀረብ
አለ እና ጨበጣት ።

«አንቺን ባለገኝሽ ኖሮ እንደገና ወደ እሥር ቤት
እመለስ ነበር ። ከተማው ውስጥ የማውቀው አንዳች
ም ሰው የለም ፤ ወደ ወዝ-አደሮች ሠፈራ ቦታ ብሄድ
ኖሮ በደቂቃ ውስጥ ይይዙኝ ነበር ። ስለዚህም መን
ገድ በምጓዝበት ጊዜ ከእሥር ቤት ማምለጤ ምን
ዓይነት ሞኝ ብሆን ነው በማለት አሰላስል ነበር ።
ድንገትም ፔላጊያ ኒሎቭና እየተቻኮሉ ሲራመዱ አየ
ኋቸው… እኔም ኋላ-ኋላቸው ሁኜ እጓዝ ጀመር…» በማ
ለት ኒኮላይ ቬሶቭሺኮቭ ተናገረ ።

«እንዴት አመለጥክ?» በማለት እናት ጠየቀችው ።

ሶፋው ጫፍ ላይ ሳይዝናና ተቀምጦ ትከሻውን
ነቅነቅ እያደረገ ፡ —

«እንደው አጋጣሚ አጋጥሞኝ ነው!» በማለት ተና
ገረ ። ከዚያም ቀጠል አደረገ እና ፡ —

«ተራ ወንጀለኞች ዘበኛውን መደብደብ ሲጀምሩ
እኔ አየር የመቀበያ ጊዜዬ ስለነበረ ከእሥር ቤቱ
ክፍል ውጪ ነበርኩኝ ። ይኸ ዘበኛ በሥርቆት ምክ
ንያት ከዣንዳርምነት የተባረረ ነበር ። አሁን በማን
ም ላይ የሚሰልል ሲሆን ባገኘው ሰው ላይ ሁሉ
የሚጮህ እና ሰውንም ዕረፍት የሚነሳ ነው ። ስለዚህ
ም ይደበድቡት ነበር ። ሁሉም ነገር ምስቅልቅሉ ወጣ ።
ዘበኞቹ ፊሽካቸውን እየነፉ ከወዲያ-ወዲህ ይሯሯጣሉ ።
ዞር ብዬ ስመለከት የእሥር ቤቱ መግቢያ በሮች
ተከፍተው አደባባዩ እና ከተማው ይታያል ። ልክ ሕል
ም ላይ ያለሁኝ ይመስል ጎተት-ጎተት በማለት ቀስ

እያልኩኝ ከእሥር ቤቱ እየወጣሁ መራመድ ጀመርኩኝ… ከእሥር ቤቱ ወጥቼ መንገድ መንገዴን ይገፔ ራቅ በማለት ከተጓዝኩኝ በኋላ መንፈሴ መለስ ብሎ ረግቶ ሕሊናየን ገዛሁኝ ። ከዚያም ለመሆኑ የት ነው የምሄደው?ብዬ አስብ ጀመር ። ዞር ብዬ እሥር ቤቱን ስመለከት በሮቹ ተዘግተዋል…» በማለት ኒኮላይ ቬሶቭሺኮቭ ተናገረ ።

ከዚያም የጎር ሆ-ሆይ! በማለት ካደነቀ በኋላ ፡ —

«ታዲያ ለምን ተመልሰህ ወደ እሥር ቤቱ በመሄድ በሩን ካንኳኳህ በኋላ ‘ክቡራን ሆይ ፤ ሲያቀብጠኝ ትንሽ ተሳስቼአለሁኝ’ በማለት እንደገና ይዘው እንዲያሥሩህ አላደረግህም’» አለው ኒኮላይ ሳቅ እያለ ፡—

«አዎን ። ዕውነትክን ነው ። ይኸንን ማድረግ ሞኝነት ነው ። ይሁን እንጂ ፣ ከጓዶቼ መካከል አንዳቸውንም እንኳን ቢሆን ተገናኝቼ ሳላነጋግር እንደው እብስ ብሎ መጥፋት ለጓዶቼ ትክክል መስሎ አይታያቸውም ። ብቻ ያም ሆነ ይህ ፣ ዝም ብዬ በመንገዱ ላይ መጓዜን ቀጠልኩኝ ። አስከሬን የተከተሉ ሀዘንተኞች ይጓዛሉ ። ሕፃን ልጅ ሞቶ ነው ። አንገቴን ወደመሬት ዝቅ አድርጌ ቀልሼ ማንንም ወዲያ-ወዲህ ዞር ብዬ ሳልመለከት ከሀዘንተኞቹ ጋር አብሬ መጓዜን ቀጠልኩኝ ። ከዚያም መካነ-መቃብሩ ውስጥ አየር ለማግኘት ለጥቂት ጊዜ ቁጭ አልኩኝ ። ድንገትም አንድ ሃሣብ መጣልኝ…» በማለት ኒኮላይ ተናገረ ። የጎርም ፡ —

«አንድ ሃሣብ ብቻ? በዚህ በአንተ ጭንቅላት ውስጥ ብዙ ሃሣቦች ገብተው ቦታ በማጣት እንዳልተጨናነቁ እርግጠኛ ነኝ…» አለው ።

ቬሶቭሺኮቭ በየጎር አነጋገር ልቡ ቶነክቶ እየሳቀ በመገረም ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። ከዚያም ፡ —

«እንደቀድሞው ጭንቅላቴ በአሁኑ ጊዜ ባዶ አይደለም! የጎር ኢቫኖቪች ፣ እንደማየው ከሆነ ግን አንተ



አሁንም አልጋህ ላይ ሁነህ እያገገምክ ነህ …» አለው ።

«ሁሉም እንደየአቅሙ ማድረግ የሚችለውን ያደርጋል!» በማለት የጎር ሳሉን እየሳለ ተናገረ ። ከዚያም ፡— «በል እስኪ ይልቅ ታሪክህን ቀጥልና አውጋን!» አለው ። ኒኮላይም ፡ —

«ከዚያም ወደ ከተማው ሙዚየም ሄድኩኝ ። ወዴት ብሔድ ይሻለኝ ይሆን? በማለት እያሰላሰልኩኝ ሙዚየሙ ውስጥ ያሉትን ነገሮች ከወዲያ-ወዲህ እየተዟዟርኩኝ እመለከት ጀመር ። በገዛ ራሴው በጣም ተበሳጭቼ ነበር ። ረሀብ ደግሞ ቡርቡር አድርጎኛል! በጣም ቅሬታ ተሰምቶኝ ከሙዚየሙ ውስጥ ወጣሁኝ እና መንገዱን ይገፔ ቁልቁል እጓዝ ጀመር ። ፖሊሶች አላፊ-አግዳሚውን ትክ ብለው ይቃኛሉ ። እኔም እንዲህ በማለት አስብ ጀመር ፡ — አይ እንግዲህ እኔን የመሰለ ጅላንፎ ኩባያ-ራስ ውዬ ሳላድር ተይዤ ፍርድ ቤት መቅረቤ የማይቀርልኝ ነው ። ከዚያም ድንገት ፔላጊያ ኒሎቭና በፍጥነት እርምጃ ወደእኔ ሲጓዙ ተመለከትኩኝ ። እንዳያዩኝ ጥግ በመያዝ ሠወር ብዬ ቆሜ አሳለፍኳቸው እና ኋላ-ኋላቸው ሁኜ እከተላቸው ጀመር ። ይኸው ነው!» በማለት ኒኮላይ ተናገረ ።

«እኔ ግን በፍጹም አላየሁህም ነበር!» በማለት ባለማየቷ ቅር ተሰኝታ እናት ተናገረች ። ዝግ ብላ ስታስተውለው ኒኮላይ ቬሶቭሺኮቭ ከስቶአል ።

«ጓዶች ስለእኔ ሃሣብ ይገባቸዋል…» በማለት ኒኮላይ ራሱን እያካከከ ተናገረ ።

«የእሥር ቤቱ ሹማምንቶችስ? አያሳዝኑህምን? እነርሱም ስለአንተ ሃሣብ ይገባቸዋል!» በማለት የጎር ተናገረ ። አየሩን የሚያኝክ ይመስል አፉን ከፍቶ ከንፈ

ሮቹን ክፍት-ዝግት ያደርግ ጀመር ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፡ —

«ይልቅስ አሁን መቀለዱ ይብቃን እና ፣ ምንም እንኳን አስደሳች ድርጊት ቢሆንም ቀላል ጉዳይ ያልሆነውን ተግባር መፈጸም ያለብን ሲሆን ይኸውም አስተማማኝ የሆነ ቦታ ፈልጎ አንተን የመደበቁ ተግባር ነው ። ይኸውም ሊሆን የሚችለው ከተኛሁበት መነሳት ብችል ነው!» በማለት ወደላይ ወደላይ ከተነፈሰ በኋላ እጆቹን ደረቱ ላይ አድርጎ ደረቱን ድክም ባለ ሁኔታ አሸት-አሸት ያደርግ ጀመር ።

«የጎር ኢቫኖቪች ፣ ክፉኛ የታመምክ ትመስላለህ!» በማለት ኒኮላይ ራሱን ወደመሬት ደፍቶ ተናገረ ። እናት እየተነፈሰች የተጣበበውን የየጎርን ክፍል ትመለካከታለች ።

«ይኸ የኔ ጉዳይ ነው ። እናት ፣ ይልቅ ያልተጨነቁ መምሰልዎን ትተው ስለፓቬል ይጠይቁት!» በማለት የጎር ተናገረ ።

ኒኮላይ ፈገግ አለ ። ከዚያም ፡ —

«ፓቬል ደህና ነው! ደህና ነው ። እሥር ቤት ውስጥ ለእኛ ልክ እንደ አለቃችን ማለት ነው ። ከእሥር ቤቱ አለቆች ጋር የሚነጋገር እና በአጠቃላይም የሚሰጠውን ትዕዛዝ የሚያቀርብልን እርሱ ነው ማንም ስለእርሱ ብዙ ያስባል…» በማለት ተናገረ ።

ኒኮላይ የሚናገረውን እያዳመጠች እናት ራሷን የምታነቃንቅ ስትሆን ፤ የጎር ወደሚገኝበት አቅጣጫ ዐይኖቿን ዞር በማድረግም በሕመም ገርጥቶ ወደሰማያዊ ቀለምነት የተለወጠውን መልኩን ትመለከታለች ። ፊቱ በሚያስደንቅ ሁኔታ ጥፍጥፍ ብሎ የተጨራመተ ከመሆኑም በስተቀር የማይንቀሳቀስ እና የስሜት ሁኔታም የማይታይበት ነው ። ዐይኖቹ ግን የሕይወት ምልክት የሚታይባቸው አስደሳች ዐይኖች ናቸው ።



«ትንሽ የምበላው ብትሰጡኝ እንዴት መልካም ነበር ። ረሀብ ሞርሙሮኛል!» በማለት ኒኮላይ ድንገት ተናገረ ።

«እናት ፣ እዚያ መደርደርያው ላይ ትንሽ ዳቦ አለ ። ያምጡለት ። ከዚያም ከቤት ሲወጡ ኮሪዶሩ ውስጥ በስተግራ በኩል የሚገኘውን ሁለተኛውን ቤት ያንኳኩት ። አንዲት ሴት ትከፍትልዎታለች ። የተገኘውን ያህል የምግብ ቀለብ ይዛ እንድትመጣ ይንገሩዋት» በማለት የጎር ተናገረ ።

«ይኸንን ያህል ብዙ ምግብ ለምን ያስፈልጋል?» በማለት ኒኮላይ ጠየቀ ።

«ግዴለህም ። ብዙ አይሆንም…» በማለት የጎር መለሰ ።

እናት ወጥታ ከሄደች በኋላ የተነገራትን በር አንኳኳች ። ከውስጥ እስኪከፈት ድረስም የሚከተለውን ስለየጎር በሃሣቧ አሰላሰለች ፡ —

«መሞቻ ጊዜው ተቃርቦአል…»

«ማነው?» የሚል ድምፅ ከውስጥ ተሰማ ።

«ከየጎር ኢቫኖቪች ዘንድ የመጣሁ ነኝ» የሚል ድምፅ እናት አሰማች ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ ፡ —

«ወደ እርሱ ዘንድ እንዲመጡ ይጠይቅዎታል» በማለት ተናገረች ።

«እሺ ። አሁኑኑ እመጣለሁኝ» በማለት ሴትዮይቱ በሩን ሳትከፍት መለሰች ። እናት ጥቂት ቆየት አለች እና እንደገና አንኳኳች ። በሩ ወዲያውኑ ተከፈተ ። ከዚያም አንዲት መነጽር ያደረገች ረዥም ሴት ክንዶቿ ላይ የተጨረማመቱትን የልብሷን እጅጌዎች ተቻኩላ እያስተካከለች ከበራፉ ወጥታ ቆመች ።

«ምን ነበር የሚሹት?» አለቻት እናትን ቀዝቀዝ ባለ ሁኔታ ።

«የጎር ኢቫኖቪች ልከውኝ ነው…» በማለት እናት መለሰችላት ።

«ይግቢ ወደቤት! እርስዎን የማውቅዎት መሰለኝ ። አይደለምን? እዚህ ጭልም ያለ ሁኖ ነው እኮ ። እንደ ምን ሰነበቱ ፤ እንደምን ነዎት?» በማለት ለስለስ ባለ ሁኔታ እናትን አነጋገረቻት ።

እናትም ተመለከተቻት እና ኒኮላይ ቤት አልፎ አልፎ ትመጣ የነበረች መሆኑን አወቀች ።

«ሁሉም የእኛው ሰዎች ናቸው ማለት ነው» በማለት እናት በሃሳቧ አሰላሰለች ። ሴትዮይቱ እናትን አስቀድማት እና እርሷም ከኋላዋ ተከትላት ፤ —

«ምነው አመመው እንዴ?» በማለት ጠየቀች ።

«አዎን ። አልጋው ላይ ተኝቶአል ። የሚበላ ነገር ይዘው እንዲመጡ ንገሪ ብሎኛል» በማለት መለሰች ።

«የለም አያስፈልግም» አለች ።

ወደ የጎር ክፍል ሲገቡ ኩር-ኩር የሚለው አተነፋፈሱ ይሰማቸዋል ።

«ወዳጄ ሆይ ፣ የቀደሙ ዝርያዎቼን ለመቀላቀል መጓዜ ነው ። አሆ! ሉድሚላ ቫሲሌቭና! ይኸውልዎ ይኸ ደፋር ወጣት አሣሪዎቹ ባለሥልጣኖች ሳይፈቅዱለት ከእሥር ቤት በድፍረት ወጥቶ እዚህ ይገኛል ። መጀመርያ ትንሽ የሚበላ ነገር ይፈልጉለት ። ከዚያም አንድ ቦታ ፈልገው ይሸሽጉት» በማለት የጎር ተናገረ ።

ሴቲቱ ጭንቅላቷን በቅሬታ ሁኔታ ነቅነቅ አደረገች እና ፈጠን ባለ አመለካከት ሕመምተኛውን የጎር ተመለከተችው ። ከዚያም ፡ —

«ምነው ፣ የጎር! ወዲያውኑ እርስዎ ዘንድ እነርሱ እንዲመጡ መልዕክት ወደእኔ መላክ ነበርዎ» አለችው ። ከዚያም ንግግሯን ቀጠል አደረገች እና ፡ —

«መድሀኒትዎን ሁለት ጊዜ አለመውሰድዎን ይኸው አያለሁኝ ። በጣም የሚያሳፍሩ ሰው ነዎት! ጓድ ፣ ይከተ



ሉኝ! የሆስፒታሉ ሰዎች የጎርን ወደሆስፒታል ለመውሰድ በአሁኑ ጊዜ በማንኛውም ሰዓት ሊመጡ ይችላሉ ።»

«እና እርስዎ በእርግጥም ሆስፒታል ሊያስገቡኝ አስበዋል ማለት ነውን?» በማለት የጎር ጠየቀ ።

«አዎን ። ከእርስዎ ጋር ሆስፒታል እሆናለሁኝ ።» በማለት ሴቲቱ ተናገረች ።

«እርስዎም ሆስፒታል ከእኔ ጋር ገብተው ሊቆዩ? ኧረ የፈጣሪ ያለህ!» አለ የጎር ።

«እንግዲህ ሞኛ-ሞኝ አይሁኑ!» አለችው ።

ይኸንን በምትመልስበት ጊዜ ሴቲቱ የብርድ ልብሱን ወደ የጎር ትከሻ ላይ ከፍ አድርጋ ያለበሰችው ስትሆን ኒኮላይንም በጥንቃቄ ትክ ብላ ተመለከተችው ። ከዚያም ምን ያህል መድሀኒት እንደቀረ የመድሀኒቱን ጠርሙስ ተመለከተች ። ከፍ-ዝቅ በማይል እና ተመሳሳይ በሆነ ድምፅ የምትናገር ሲሆን አረማመዷም ግርማ-ሞገስ ያለው ነው ። ፊቷ ገርጣ ያለ ሲሆን ፣ ጥቋቁር የሆኑት ቅንድቦቿም በረዥሙ ተነጥፈው ከአፍንጫዋ ሰርን ላይ ሊጋጠሙ ምንም ያህል አልቀራቸውም ። እናት የሴቲቱን አመለካከት አልወደደችውም ። እጅግ የደፋር አመለካከት ነው ። የሴቲቱ ዐይኖች ፍጹም የማይስቁ ወይንም ብልጭ-ብልጭ እያሉ የሚያበሩ አይደሉም ። አነጋገሯም የአዛዥነት ሁኔታ ይታይበታል ።

«አሁን እኛ ትተናችሁ እንሄዳለን» አለች ። ከዚያም ቀጠል አደረገች እና ፡ —

«እኔ ግን ቶሎ ተመልሼ እመጣለሁኝ ። ከዚህ መድሀኒት ላይ በሾርባ ማንኪያ አንዴ ቀድተው የጎርን ያጠጧቸው ። እንዳይነጋገሩም ያድርጓቸው…» በማለት እናትን ነገረቻት ።

ከዚያም ኒኮላይን ይዛ ወጣች ።

«ግሩም-ድንቅ የሆኑ ሴት ናቸው!» በማለት የጎር እያቃሰተ ተናገረ ። ከዚያም ንግግሩን በመቀጠል ፡—

«እንደው ባጭሩ ዕጹብ-ድንቅ የሆኑ ሴት ናቸው... እርስዎን እናትን ከእርሳቸው ጋር አገናኝቼአችሁ አብራችሁ በኖራችሁ ግሩም ነበር ። እጅጉን አድርገው በመዋተት ድክም ያሉ ሴት ናቸው...» አለ ።

«ዝም በል አታውራ!.. እንካ ይኸንን መድሀኒት ጠጣ!..» በማለት ለስለስ ባለ ሁኔታ እናት መለሰችለት ።

መድሃኒቱን ጠጣ እና አንድ ዐይኑን ጨፈነ ።

«አወራሁም-አላወራሁም መሞቴ እንደሆን አልቀረም...» አለ ።

ከናፍሮቹ ሳቅ እያሉ ፣ እናትን ባልተጨፈነው ዐይኑ ይመለከታት ጀመር ። እናት አንገቷን አቀርቅራ መሬት-መሬቱን ትመለከት ጀመር ። ስለእርሱ በሀዘን ልቧ የተነካ በመሆኑም ዐይኗ በእንባ ተመላ ።

«አይ ይተዉ ። ይኸ ምንም አይደለም ። መሆን ያለበት ጉዳይ ነው...» በማለት ተናገረ ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«በሕይወት የመኖር አስደሳችነት ሟች የመሆን አስፈላጊነትንም ያዘለ ነው...» አለ ።

እናት እጅዋን ግንባሩ ላይ አሳረፈች ። አሁንም ዝግ ባለ አነጋገር ፡ —

«አታውራ ነው እኮ የምልህ ። ዝም በል » አለችው ።

ደረቱ ውስጥ ኩር-ኩር የሚለውን ኩርፍታ የሚያዳምጥ ይመስል ዐይኖቹን ጨፈነ ።

«እናት ፣ ዝም ማለት ምንም ጠቀሜታ የለውም !» በማለት በግትርነት ተናገረ ። ንግግሩን በመቀጠልም ፡ —

«ዝም በማለቴ ምን አገኛለሁኝ? ከመሞቴ በፊት ትንሽ ሰኮንዶች እንዲተርፉኝ ነውን? እርስዎን ከመሰለች ጥሩ ሴት ጋር በመወያየት ግን ከፍተኛ ደስታ



ማግኘት እችላለሁኝ ። በላይኛው ዓለም ያሉት ሰዎች እዚህ እንዳሉት ሰዎች ጥሩ ሰዎች አይመስሉኝም ።» አለ ።

«እኛ፣ ዘንካታ እመቤት ይመጡ እና ለምን እንዲናገር አደረግሺው ብለው ይቆጡኛል...» አለችው ።

«ዘንካታ እመቤት አይደሉም ። ሬቮሉሺናዊት ናቸው ። ጓዲት ናቸው ። ግሩም ሴት ናቸው ። እርግጥ ነው ይቆጡዎታል ። እሳቸው ማንንም ይቆጣሉ...» አለ ።

ዝግ ብሎ እና የግዱን ከናፍሮቹን እያንቃነቀ ጎረቤቱ ስለሆነችይቱ ሴት ታሪክ ለእናት ይነግራት ጀመር ። ዐይኖቹ ፈጣን በሆነ ሁኔታ ጭፍን-ክፍት ፣ ጭፍን-ክፍት ይሉ ስለነበረ የሚያሾፍባት መስሎ ተሰማት ።

«መሞቻው ተቃርቦአል» በማለት ርጥበት ያልተለየውን ቀለም-አልባ ሁኖ የገረጣ ፊቱን እየተመለከተች አሰላሰለች ።

ሉድሚላ መጣች ። በጥንቃቄ በሩን ዘግታ ወደ እናት ዘንድ ዞር አለች ።

«የእርስዎ ጓደኛ ልብሱን መለወጥ እና በተቻለ ፍጥነት ከእኔ ቤት ወደሌላ ቦታ መሄድ አለበት ። የሚለብሰው ልብስ ሂደው ይፈልጉለት ። ሶፍያ እዚህ አለመኖሯ በጣም መጥፎ ሆነ ። ሰዎችን መደበቅ የእርሷ የሥራ መደብ ነበር» አለች ።

«ነገ ትመጣለች» አለች እናት ትከሻዋ ላይ ሻሽ ብጤ ደረብ እያደረገች ።

አንድ ተግባር እንድታከናውን በተሰጣት ቁጥር እንዳችም ሌላ ነገር ባለማሰብ ያንኑ የተሰጣትን ተግባር በፍጥነት እና በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን እናት ትጥራለች ።

«እንዴት ያለ ልብስ መልበስ አለበት ብለው ያስ

ባሉ?» አለች እናት ግንባሯን ሸብሸብ አድርጋ በጉዳ
ዩ በመመሰጥ ሁኔታ ።

«የሆነውን ዓይነት ቢሆንም ግዴለም ። ከቤት ወጥ
ቶ የሚሄደው ምሽት ላይ ነው...» አለች ሴቲቱ ።

«በምሽት መሄድ ደግሞ አይደል ። አጉል ነው ። ም
ሽት ሲሆን በመንገዶች ላይ የሚመላለሱት ሰዎች
ጥቂት ከመሆናቸውም በስተቀር ፖሊሶችም ይበልጥ
አድፍጠው የሚጠባበቁት ሲመሽ ነው ። እርሱ ደግሞ
እንደሚያዩት ብልጣ-ብልጥ ቀልጣፋ አይደለም...»
አለች እናት ።

የጎር ድምፁ ከፍ ብሎ እየተሰማ ሳቀ ።

«ሆስፒታል መጥቼ ልጠይቅህ እችላለሁን?» በማ
ለት እናት ጠየቀችው ።

በአዎንታ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ ሳሉን ሳለ ።

«ሆስፒታል ከእኔ ጋር እየተፈራረቁ መቆየት ይሻ
ሉን?» በማለት ሉድሚላ በጥቋቁር ዐይኖቿ እናትን
እየተመለከተች ጠየቀቻት ። ቀጠል አድርጋም ፡ —

«አይ ጥሩ ነው ። ይፈልጋሉ ማለት ነዋ? አሁን
ግን የተቻለዎትን ያህል ወደተግባርዎ ፈጥነው ይሂ
ዱ...» አለቻት ።

በመውደድ ስሜት ፣ ይሁን እንጂ በአዛኝነት መን
ፈስም ጭምር የእናትን እጅ ጨበጥ አድርጋ ይዛ
በሩ ድረስ ሸኘቻት ። ከቤቱ ውጪ እንደወጡም ፡ —

«በአድራጎቴ እንዳይቀየሙኝ ። ንግግር መናገር የለ
ባቸውም እና ነው ። ከሕመማቸው ይድናሉ የሚል
ተስፋ አሁንም አለኝ...» በማለት ለእናት ሉድሚላ
ነገረቻት ።

አጥንቶቿ እስኪንቋቁ ድረስ የእናትን እጆች ጥ
ብቅ አድርጋ ሉድሚላ ጨበጠች ። ዐይኖቿንም ድካም
በተሰማው ሁኔታ ጭፍን-ጭፍንፍን አደረገቻቸው ። የሉ
ድሚላ አነጋገር የእናትን ልብ ነካው ።



«የኔ ውድ ምንድነው የምትይው?» በማለት እና
ት ጎረምረም ባለ ሁኔታ ተናገረች ።

«ሰላዮችን መጠንቀቅ ያስፈልጋል!» በማለት እጆቿ
ን አንስታ ግንባሯን እየጨፈገገች ዝግተኛ በሆነ
ድምፅ ሴቲቱ ተናገረች ። ከናፍሮቿ ይንቀጠቀጡ የነ
በሩ ሲሆኑ ፊቷም ለወጥ አለ ።

«ስለእነርሱ ብዙ አውቃለሁኝ!» በማለት እናት
ኩራት በአለበት ሁኔታ ተናገረች ።

በመግቢያው በር በኩል ስታልፍ ለጥቂት ጊዜያ
ት ቆም እንደማለት ብላ ግራ-ቀኙን ቶሎ በመመልከ
ት የአንገት ልብሷን በሚገባ አስተካከለች ። ብዙ ሕዝ
ቦች ከሚገኙባቸው ቦታዎች መካከል ሰላዮችን ነጥ
ላ በማውጣት ብዙውን ጊዜ ሳትሳሳት ማንነታቸው
ን ለይታ ታውቃቸዋለች ። የግዴለሽነት አረማመዳቸው
ን ፣ ልዩ በሆነ ሁኔታ የተዝናኝነት መልክ የሚታይበ
ትን የአረማመዳቸውን ሁኔታ ፣ ጥፋተኛነታቸው ተሰም
ቶአቸው እና ከአደጋ ለመጠባበቅ ከወዲያ-ወዲህ የሚ
ቅበዘበዙ ዓይኖቻቸው የመዳከም እና የመሰላቸት ሁኔ
ታቸውን ጥሩ አድርጋ በመለየት ታውቅባቸዋለች ።

እነዚህን ከመሳሰሉት ሰዎች መካከል አንዳቸውንም
ባለመመልከቷ ባለ ጋሪ አቁማ ወደ ገበያ ቦታ እን
ዲያደርሳት ጠይቃ ተሳፈረች ። ለኒኮላይ የሚሆን ልብ
ስ እየመረጠች በዋጋው ላይ ከተከራከረች በኋላ ሁል
ጊዜ እየሠከረ ልብሱን የሚያበላሽ ባል ስላላት ለእ
ርሱ ልበስ መግዛት በየጊዜው የምትገደድ መሆኗን
በማስመሰል ሁኔታ እየፈጠረች ተናግራ የምትፈልገው
ን ልብስ ገዛች ። እየፈጠረች የምታወራቸው ንግግሮች
ለነጋዴዎቹ ከቁም ነገር የማይገቡ ናቸው ። ጋሪው ላይ
ሁና ከኒኮላይ ይበልጥ ብልጥ በመሆን አሳድዶ ለመ
ያዝ ፖሊሶች ሰላዮችን ወደገበያ ቦታ ይልኳቸዋል
ብላ እርግጠኛ ስለነበረች በዚህ የፈጠራ ወሬዋ ተደ

ስታ ነበር ። ልክ እንደቀድሞው ተመሳሳይ በሆነ ጥንቃቄ ወደየጎር መኖሪያ ስትሄድም ጥንቃቄ ያደረገች ስትሆን ፣ ከዚያም ወደከተማው ዳርቻ ሂዳ ኒኮላይን መገናኘት ነበረባት ። እንደማይተዋወቁ ሁሉ በመንገዱ ግራና ቀኝ ሁነው ይራመዱ የነበረ ሲሆን ፣ ኒኮላይ ጭንቅላቱን ወደመሬት ደፋ አድርጎ ፣ ረዥም እና ቡናማ የሆነ ካፖርቱ እግሩ ድረስ ተንዘርፍፎ ወርዶ እና ባርኔጣውም እስከ አፍንጫው ድረስ ወርዶ ፊቱን ሸፍኖት ይሄድ የነበረው አካሄዱ ለእናት አስደሰታት ። ጭር ያለ ማቋረጫ መንገድ ላይ ሲደርሱ ከሳሻ ጋር ተገናኙ ። እናት አንዳችም የድምፅ ምልክት ሳታሰማ ደህና ሁን በሚል ሁኔታ ለኒኮላይ ራሷን ከነቀነቀች በኋላ ወደቤቷ ተመለሰች ።

«ፓቬል ግን አሁንም እሥር ቤት ነው... አንድሬይም ጭምር...» በማለት መንገዷን ስትጓዝ አሰላሰለች ።

## 10

ኒኮላይ እናትን በታላቅ ስሜት ተውጦ ተቀበላት ፡—

«የጎር ሕመሙ በጣም ብሶበታል!» በማለት አጠንክሮ ተናገረ ። ቀጠል አድርጎም ፡ — «እጅግ ብሶበታል! ወደ ሆስፒታል ወስደውታል ። ሉድሚላ እዚህ ነበረች ። ወደእርሷ ዘንድ ሆስፒታል እንዲሄዱ ትሻለች...» በማለት ተናገረ ።

«ሆስፒታል እንድሄድ ነውን?» አለችው ።

ኒኮላይ በስጨት ባለ መልክ መነጽሩን ገፋ ካደረገ በኋላ እናት ኮቷን ስትለብስ አገዛት ።

እጣቶቿን ሞቃት እና ደረቅ በሆነው እጁ ገፋ እያደረገ ፡ —



«እንሆ ይኸንንም ጥቅል ፓኬት ይዘው ይሂዱ ። ቬሶቭሺኮቭ ደህና ሁኔታ ላይ ነውን?» አላት ።

«አዎን...» አለችው ።

«የጎርን ለማየት እመጣለሁኝ» አለ ።

እናት ድክም ብላ ነበር ። በዚህ ድካሟ ላይ የኒኮላይ በስሜት መዋጥ ይበልጡኑ ሀዘን ላይ ጣላት ።

«የጎር መሞቻው ተቃርቦአል» የሚል አባባል ነበር በአዕምሮዋ ውስጥ ይመላለስ የነበረው ።

ይሁን እንጂ የጎር በተከመሩ ነጫጭ ትራሶች ላይ ጋለል ብሎ እያስካካ በሚስቅበት ንጹሕ በሆነ ትንሽ ክፍል ውስጥ ስትደርስ ሥጋቷ መለስ አለላት ። እበሩ አጠገብ ቆማ የጎር ዶክተሩን ምን እንደሚለው አዳመጠች ።

«ሕመምተኛን ማከም ማለት የጥገና ለውጥ እንደ ማለት ነው» አለ የጎር ።

«የጎር ፣ ተው እንጂ ፣ ቀልዱን ትተህ ቁም ነገራም ሁን!» በማለት ዶክተሩ ለየጎር ሕመም እየተጨነቀለት ተናገረ ።

«እኔ ሬቮሉሺናዊ ስለሆንኩኝ ጥገናዊ ለውጥን እጠላለሁኝ...»

ዶክተሩ የየጎርን እጅ ወደ እግሩ ላይ ቀስ አድርጎ አሳርፎ እና የሕመምተኛውን የከሳ መልክ በመመልከት በሃሣብ ተመስጦ ከተቀመጠበት ቦታ ተነሳ ።

እናት ዶክተሩን አውቃዋለች ። የኒኮላይ ቅርብ ወዳጆች ከሆኑት መካከል አንዱ ሲሆን ፣ ስሙም ፡ ኢቫን ዳኒሎቪች ይባላል ። እናት ወደየጎር ጠጋ ብላ የሄደች ስትሆን እርሱም ምላሱን ብቅ አድርጎ ሰላም አላት ። ዶክተሩ ፊቱን መለስ አደረገ ። ከዚያም ፡ —

«እህ ፣ ኒሎቭና! እንደምንነዎት? ምንድነው የያዙት?» በማለት እናትን ተናገረ ።

«መጻሕፍት ይመስለኛል» በማለት የጎር መለሰ ።

ስታ ነበር ። ልክ እንደቀድሞው ተመሳሳይ በሆነ ጥንቃቄ ወደየጎር መኖሪያ ስትሄድም ጥንቃቄ ያደረገች ስትሆን ፣ ከዚያም ወደከተማው ዳርቻ ሂዳ ኒኮላይን መገናኘት ነበረባት ። እንደማይተዋወቁ ሁሉ በመንገዱ ግራና ቀኝ ሁነው ይራመዱ የነበረ ሲሆን ፣ ኒኮላይ ጭንቅላቱን ወደመሬት ደፋ አድርጎ ፣ ረዥም እና ቡናማ የሆነ ካፖርቱ እግሩ ድረስ ተንዘርፍፎ ወርዶ እና ባርኔጣውም እስከ አፍንጫው ድረስ ወርዶ ፊቱን ሸፍኖት ይሄድ የነበረው አካሄዱ ለእናት አስደሰታት ። ጭር ያለ ማቋረጫ መንገድ ላይ ሲደርሱ ከሳሻ ጋር ተገናኙ ። እናት አንዳችም የድምፅ ምልክት ሳታሰማ ደህና ሁን በሚል ሁኔታ ለኒኮላይ ራሷን ከነቀነቀች በኋላ ወደቤቷ ተመለሰች ።

«ፓቬል ግን አሁንም እሥር ቤት ነው... አንድሬይም ጭምር...» በማለት መንገዷን ስትጓዝ አሰላሰለች ።

## 10

ኒኮላይ እናትን በታላቅ ስሜት ተውጦ ተቀበላት ፡—

«የጎር ሕመሙ በጣም ብሶበታል!» በማለት አጠንክሮ ተናገረ ። ቀጠል አድርጎም ፡ — «እጅግ ብሶበታል! ወደ ሆስፒታል ወስደውታል ። ሉድሚላ እዚህ ነበረች ። ወደእርሷ ዘንድ ሆስፒታል እንዲሄዱ ትሻለች...» በማለት ተናገረ ።

«ሆስፒታል እንድሄድ ነውን?» አለችው ።

ኒኮላይ በስጨት ባለ መልክ መነጽሩን ገፋ ካደረገ በኋላ እናት ኮቷን ስትለብስ አገዛት ።

እጣቶቿን ሞቃት እና ደረቅ በሆነው እጁ ገፋ እያደረገ ፡ —



«እንሆ ይኸንንም ጥቅል ፓኬት ይዘው ይሂዱ ። ቬሶቭሺኮቭ ደህና ሁኔታ ላይ ነውን?» አላት ።

«አዎን...» አለችው ።

«የጎርን ለማየት እመጣለሁኝ» አለ ።

እናት ድክም ብላ ነበር ። በዚህ ድካሟ ላይ የኒኮላይ በስሜት መዋጥ ይበልጡኑ ሀዘን ላይ ጣላት ።

«የጎር መሞቻው ተቃርቦአል» የሚል አባባል ነበር በአዕምሮዋ ውስጥ ይመላለስ የነበረው ።

ይሁን እንጂ የጎር በተከመሩ ነጫጭ ትራሶች ላይ ጋለል ብሎ እያስካካ በሚስቅበት ንጹሕ በሆነ ትንሽ ክፍል ውስጥ ስትደርስ ሥጋቷ መለስ አለላት ። እበሩ አጠገብ ቆማ የጎር ዶክተሩን ምን እንደሚለው አዳመጠች ።

«ሕመምተኛን ማከም ማለት የጥገና ለውጥ እንደ ማለት ነው» አለ የጎር ።

«የጎር ፣ ቱው እንጂ ፣ ቀልዱን ትተህ ቁም ነገራም ሁን!» በማለት ዶክተሩ ለየጎር ሕመም እየተጨነቀለት ተናገረ ።

«እኔ ሬቮሉሺናዊ ስለሆንኩኝ ጥገናዊ ለውጥን እጠላለሁኝ...»

ዶክተሩ የየጎርን እጅ ወደ እግሩ ላይ ቀስ አድርጎ አሳርፎ እና የሕመምተኛውን የከሳ መልክ በመመልከት በሃሣብ ተመስጦ ከተቀመጠበት ቦታ ተነሳ ።

እናት ዶክተሩን አውቃዋለች ። የኒኮላይ ቅርብ ወዳጆች ከሆኑት መካከል አንዱ ሲሆን ፣ ስሙም ፡ ኢቫን ዳኒሎቪች ይባላል ። እናት ወደየጎር ጠጋ ብላ የሄደች ስትሆን እርሱም ምላሱን ብቅ አድርጎ ሰላም አላት ። ዶክተሩ ፊቱን መለስ አደረገ ። ከዚያም ፡ —

«እህ ፣ ኒሎቭና! እንደምንነዎት? ምንድነው የያዙት?» በማለት እናትን ተናገረ ።

«መጻሕፍት ይመስለኛል» በማለት የጎር መለስ ።

«ማንበብ የለበትም!» በማለት ቁመተ-አጭሩ ዶክተር ተናገረ ።

«ወደ ድንቁርና ሊመልሰኝ ይሻል!» በማለት ሕመምተኛው ቅሬታውን ገለጠ ።

ኒኮላይ ቁርጥ-ቁርጥ የሚል ትንፋሹን ሲተነፍስ የሚፍለቀለቅ እና የሚንጫጫ ዓይነት ድምፅ ከደረቱ ውስጥ ይሰማ ጀመር ። ፊቱ በላብ ችፍታዎች የተመላ ሲሆን ግንባሩን ለመጥረግ እጁን ማንሳት የሚችለው በታላቅ ጥረት ነው ። ጭርምት ያሉት ጉንጮቹ የማይንቀሳቀሱ መሆናቸው ሰፊ እና ርኅሩኅ ፊቱን ሕይወት የለሽ ምስል አስመሰለው ። ጉድጓዳቸው ውስጥ በጥልቀት የገቡት ዐይኖቹ ብቻ ብሩኅ እና ፈገግታማ ናቸው ።

«ሰሙኝ ወይ ሃኪሙ! ደከመኝ ። ጋለል ብዬ ልተኛን?»

«የለም ። አይሆንም!» በማለት ዶክተሩ ባጭሩ መለሰ ።

«እሺ ግዴለም ። ምን አስቸገረኝ ፣ እርስዎ ወጣ ሲሉ እተኛ የለም!»

«ኒሎቭና ፣ ጋለል ብሎ እንዳይተኛ ያድርጉት ። ትራሶቹን ወደላይ ደራርቡበት ። እና ደግሞ ፣ እባክዎ እንዳይናገር ያድርጉት ። መናገር ይጎዳዋል» በማለት ሀኪሙ ተናገረ ።

እናት በእሺታ ራሷን ነቀነቀች ። ዶክተሩም ከእግሩ ነጠቅ-ነጠቅ እያለ አጫጭር እርምጃዎችን በመራመድ ሄደ ። የጎር ጭንቅላቱን መለስ ካደረገ በኋላ ዐይኖቹን የጨፈነ ሲሆን ፣ ከሚንቀጠቀጡት እጣቶቹ በስተቀር የሚንቀሳቀስ አይመስልም ነበር ። የትንሹ ክፍል ነጫጭ ግድግዳዎች ቀዝቃዛ እና ለስሜት ደስ የማያሰኙ ነበሩ ። በትልቁ መስኮት በኩል የኖራ ክምር ኮረት ይታያል ፤ በጥቋቁር አቧራማ ቅጠሎች



መካከል ቢጫ-ቢጫ ነቁጦች የሚታዩ ሲሆኑ ይኸውም የበልግ ቅዝቃዜ ምልክት ነው ።

የጎር ዐይኖቹን ሳይከፍት ፣ —

«ሞት እኔን ቀስ እያለ እና እያንገራገረ ሊወስደኝ ይሻል... ሞት ለእኔ የሚያዝንልኝ ይመስላል... እኔ ምንግዜም ከአካባቢ ጋር ተስማምቼ የምኖር ሰው ነበርኩኝ እና ሳይሆን አይቀርም!»

«የጎር ኢቫኖቪች ። መናገርህን አቁም» በማለት እናት በቀስታ እጁን እያሻሸች ለመነችው ።

«እኔ ከጥቂት ጊዜ በኋላ...»

ትንፋሹን የግዱን እየሳበ እና በየጊዜው ንግግሩን እያቋረጠ ፣ —

«እርስዎ ከእኛ ጋር መሆንዎ ግሩም-ድንቅ ነው — ፊትዎን ማየት እጅግ ያስደንቃል ። አንዳንድ ጊዜ በእርስዎ ላይ ምን ይደርስብዎት ይሆን በማለት በመገረም ራሴን እጠይቃለሁኝ ። እርስዎም እንደሌሎች ሁሉ ወደ እሥር ቤት መግባትዎ አይቀርም ብሎ መገመት ያሳዝናል ። እሥር ቤት ገብቶ መታሠር ይፈራሉን?» አላት ።

«አልፈራም» በማለት በቀላሉ መለሰችለት ።

«እርግጥ ነው ፣ አይፈሩም ። ያም ሁኖ ግን እሥር ቤት ገብቶ መታሠር የአራዊት ኑሮ መኖር ነው ። እኔን ለእዚህ ያበቃኝ እሥር ቤት ነው ። ዕውነቱን ለመናገር ከሆነ ፣ መሞት አልሻም...» አለ ።

«አትሞትም ይሆናል» ብላ ለመናገር እናት ፈልጋ ነበር ። ይሁን እንጂ የፊቱ ላይ አመለካከት ይኸንን ሃሣቧን እንድትለውጥ አደረጋት ።

«አሁንም መሥራት እችል ነበር... ለመሥራት የማልችል ብሆን ኖሮ መኖር ዋጋ የሌለው ይሆን ነበር ። ዋጋ-ቢስ ነው...» አለ ።

እናት ትንፋሿን በረዥሙ ከተነፈሰች በኋላ አንድሬይ ፡ —

«ዕውነት ነው ። የሚያዝናና ግን አይደለም» የሚለው አነጋገሩ ትዝ አላት ። ቀኑ አድካሚ ሁኖባት የነበረ ከመሆኑም በስተቀር ፥ እርቧታል ። የሕመምተኛው ሰው አሰልቺ የሆነ ማነብነብ ክፍሉን ሞልቶት ለስላሳ ከሆኑት ግድግዳዎች ጋር እየተጋጨ ይሰማ ጀመር ። በመስኮቱ ውጪ የሚገኙት ዛፎች ጠቆር ያሉ እና ያዘኑ የሚመስሉ ዝቅ ብለው ያንዣበቡ ደመናዎች ይመስላሉ ። የማይንቀሳቀሱት እና የፀሐይ ጥልቀት የሚፈነጥቃቸው ነጸብራቆች ከምሽቱ መዳረስ ጋር በአንድነት ተደምረዋል ። ማንኛቸውም ነገር በሚያስገርም ሁኔታ በየነበረበት ረግቶ ይገኛል ።

የጎር ዐይኖቹን ጨፍኖ እና ከጊዜ ጊዜ ከመናገር እየተቆጠበ ፡ —

«ኧረ እንዴት ጠናብኝ!» በማለት ተናገረ ።

«ተኛ ። ምናልባት ብትተኛበት ይሻልህ ይሆናል» አለችው ።

አተነፋፈሱን አዳመጠች ። ሁኔታውን ተመለካከተችው ። ከዚያም ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ከነበረችበት ሳትነቃነቅ በሀዘን ኩርምትምት ብላ ተቀመጠች ። ከዚያም እዛው እተቀመጠችበት እንቅልፍ ሸለብ አደረጋት ።

የበሩ ድምፅ ሸለብ አድርጓት ከነበረ እንቅልፏ አነቃት ። ብድግ ብላ ተመለከተች ። የጎር ዐይኖቹን ገልጦአል ።

«እንቅልፍ ሸለብ አድርጎኝ ነበር ። ይቅርታ አድርግልኝ» በማለት በለሰለሰ ድምፅ ተናገረች ።

«ይቅርታ ሊደረግልኝ የሚገባ ለእኔ ነው» በማለት እርሱም በለሰለሰ አነጋገር ተናገረ ።

በመስኮት በኩል ጨለማ ይታያል ። ክፍሉ ቀዝቃዛ ሲሆን ማናቸውም ነገር ድብዝዝ ብሎአል ። በሕመምተኛው ሰው ፊት ላይ ጥቁር ጥላ አጥልቶ ይታይበታል ።

እናት የልብስ ኮሽኮሽታ እና የሉድሚላን ድምፅ ሰማች ።

«በጭለማ ውስጥ ተቀምጣችሁ ትንሾኳሾኳላችሁ እንዴ? የት ነው ማብሪያው?» አለች ።

ድንገት ክፍሉ በሚያንፀባርቅ ብርሃን ተዋጠ ። በክፍሉ መሀከል የሉድሚላ ረዥም ፥ ቀጥ ብሎ የወጣ መለሎ ቁመት እና ቅርጽ ወለል ብሎ ጎልቶ ይታያል ።

የየጎር ሰውነት በሙሉ ይንቀጠቀጥ ጀመር ። እጁን አንስቶ ደረቱ ላይ አደረገው ።

«ምነው? ምንሆንክ?» በማለት ሉድሚላ እየጮኸች ወደእርሱ ዘንድ በፍጥነት ተጠጋች ።

በዚህን ጊዜ ትልልቅ እና በማይታመን ሁኔታ ብሩኅ በሆኑት ዐይኖቹ እናትን ትክ ብሎ ይመለከታት ጀመር ።

አፉን ከፈት አድርጎ አንገቱን ቀና አደረገ እና እጁን አንቀሳቀሰ ። እናት እጁን ይዛ መትንፈስ ፈርታ ፊት-ፊቱን ትመለከተው ጀመር ። ገተት ባለ የሰውነቱ እንቅስቃሴ ጭንቅላቱን ወደ አልጋው እንደገና መለስ አድርጎ ከፍ ባለ ድምፅ ፡ —

«አልችልም! አበቃ-አለቀ!..» በማለት ተናገረ ።

የሠራ አከላቱ በትንሹ ነቅነቅ አለ ። ጭንቅላቱ ትከሻው ላይ ዘርፈጭ ብሎ ወደቀ ። ከአልጋው በላይ ያለው መብራት ቀዝቃዛ ብርሃን በአካሉ ላይ በማብራት በትልቁ የተከፈቱት ዓይኖቹን ሕይወት-የለሽ በሆነ ሁኔታ ያንጸባርቃሉ ።

«ምነው የኔ ውድ!» በማለት እናት ቀስ ብላ ተናገረች ።

ሉድሚላ ቀስ ብላ በመራመድ ወደመስኮቱ ሄደ
ች እና ውጪ ውጪውን እየተመለከተች ቆመች ።
«ሞተ!» አለች ከዚህ ቀደም እናት ሰምታው በማ
ታውቀው ጉልህ በሆነ ድምፅ ። መስኮቱ ደርብ ላይ
ክንዶቿን አስደግፋ ጎንበስ በማለት ድንገት አንድ
ሰው ጭንቅላቷ ላይ የመታት ይመስል እጆቿን ፊ
ቷ ላይ አድርጋ ከጉልበቷ ተሽመድምዳ ወረደች ።
የየጎርን ትላልቅ እጆች አጣፍታ ደረቱ ላይ ካነ
ባበረቻቸው በኋላ እና ጭንቅላቱንም ትራሱ ላይ በ
ሚገባ አስተካክላ ካኖረችው በኋላ እናት እንባዎ
ቿን ጠራርጋ ወደ ሉድሚላ ሄደች ። ወደታች ዝቅ
ብላ በቀስታ ክምር ፀጉሮቿን ደበሰበስ ታደርግላት
ጀመር ። ሉድሚላ ቀስ ብላ ራሷን ቀና ካደረገች በ
ኋላ እናትን ባዘኑ እና በቀሉ ዐይኖቿ መልከት በ
ማድረግ ከመሬቱ ላይ ተነሳች ።
«ግዞት በተጋዝን ጊዜ አብረን ነበር የኖርነው...»
በማለት በዝግታ ለእናት ነገረቻት ። ከዚያም ቀጠል
አድርጋ ፡ —
«ግዞቱ ቦታ አብረን በመሄድ የተፈረደብንን የእ
ሥራት ጊዜ ጨረስን... አንዳንድ ጊዜ ሁኔታው አሰቃ
ቂ ነበር ...ሊቋቋሙት የማይቻል ነው ። ብዙ ሰዎች
ተሸንፈው መንፈሳቸው ይፈታል...» በማለት ተናገረች ።
በመንፈስ-ጠንካራነት አፍና ይዛው የነበረው ብርታ
ቷ ፈንቅሏት በመውጣት ጉልህ ድምፅ በሚያሰማ ደ
ረቅ ልቅሶ ትንሰቀሰቅ ጀመር ። ወደ እናት ይበልጥ
ተጠግታ ቆመች ። ፊቷም በሀዘን የተዋጠ ልስላሴ የሚ
ታይበት ሲሆን ፣ ሁኔታውም ይበልጥ ወጣት እንድትመ
ስል አደረጋት ።
«እርሱ ምን ጊዜም ደስተኛ ነበር ። ደካሞችን ለ
ማበረታታት ብሎ የገዛ ራሱን ጭንቀት በመሸሸግ
ሁልጊዜም ይስቅ እና ይጫወት ነበር ። ምን ግዜም



ጥሩ ፣ ደግ እና አሳቢ ሰው ነበር... እዚያ ሳይቤርያ
የተሰኘው የግዞት ቦታ ሥራ-ፈትነት ብዙውን ጊዜ
ሰዎችን በማበላሸት ወራዳ ባሕርይ እንዲኖራቸው ያደ
ርጋቸዋል ። በዚህ ሁሉ ሳይበከል ምንኛ ከፍተኛ በሆ
ነ ሁኔታ ተቋቋመው መሰለዎ! እንደምን የመሰለ ግሩ
ም ድንቅ ጓድ እንደነበረ ማውሳት ያስቸግራል! የገዛ
ራሱ የኑሮ ሕይወት እጅግ ደስታ-ቢስ የሆነ ነበር ።
ይሁን እንጂ የኑሮዬ ሁኔታ መረረኝ — አንገፈገፈኝ
የሚል ቃል ከአንደበቱ ሲወጣ አንድም የሰማው ሰ
ው አይገኝም! በፍጹም! እኔ የቅርብ ጓዲቱ ነበርኩኝ ።
የደግነቱ ብዙ ውለታ አለብኝ ። እጅግ ከበለጸገው ዕ
ውቀቱ የቻለውን ያህል አካፍሎኛል ። ይሁን እንጂ ፣
በአኗኗሩ ድክም ብሎ እና ብቸኛ ሁኖ ሳለ ፣ ለሚያ
ደርገው በጎ ተግባር በአጸፋው የሚጠይቀው አንዳ
ችም የግል ፍላጎት ወይንም ተደማጭነት አልነበረው
ም...» በማለት ሉድሚላ ተናገረች ።
ወደየጎር ተጠጋችና እጁን ለመሳም ጎንበስ አለች ።
በሀዘን ተውጣ ረጋ ባለ ድምፅ ፡ —
«ጓድ ፤ የእኔ ውድ ጥሩ ጓድ አመሰግንሃለሁኝ ። በ
ሙሉ ልብ አመሰግንሃለሁኝ ። ደህና ሁንልኝ! ልክ አን
ተ ትሠራ በነበረው ሁኔታ እኔም ያለ አንዳች ድካ
ም እና ያለአንዳች ማወላወል መላ ሕይወቴን ተግባ
ሬን ማከናወኔን እቀጥላለሁኝ!.. ደህና ሁንልኝ!» አለ
ችው ።
በልቅሶ ስትንሰቀሰቅ አካሏ እርግፍ-እርግፍ እያለ
ይንዘፈዘፍ ነበር ። የየጎር እግር ከሚገኝበት አኳያ አን
ገቷን አልጋው ላይ ደፋች ። እናት ድምፅ ሳታሰማ
ምርር ብላ ታለቅስ ነበር ። በአንዳች ምክንያት ላለ
ማልቀስ ሞከረች ። ሉድሚላን ለማጽናናት ፣ ጥሩ-ጥሩ
የፍቅር እና የሀዘን ቃላት ለመናገር ፈለገች ። እንቅ
ልፍ ሸለብ ያደረጉት ይመስል በግማሽ የተከፈቱ ዐይ

ኖቹን ፣ በፈገግታ የተነኩ ሰማያዊ ከንፈሮቹን በእንባ በተሸፈኑት ዐይኖቿ ተመለከተች ። ሁሉም ነገር ፀጥ ያለ እና በሚያሳዝን ሁኔታ ብሩኅ ነበር…

ኢቫን ዳኒሎቪች ፈጣን በሆኑ እና እዛው-እዛው በሚረግጡ እርምጃዎቹ እየተራመደ መጣ ። ድንገት ክፍሎ መካከል ቆመ እና እጆቹን ኪሶቹ ውስጥ ከተተ ።

«መቼ ነው ይኸ የሆነው?» በማለት ጎላ ባለ እና በተበሳጨ ድምፅ ጠየቀ ።

ማንም የመለሰለት የለም ። ግንባሩን ጠረገ እና በትንሹ ገድገድ እያለ ወደ የጎር ዘንድ ጠጋ አለ ። እጇን ጫን አድርጎ ነካው እና ወደ ጥግ ቆመ ።

«ያልተጠበቀ ነገር አይደለም ። እንደርሱ ልብ ቢሆን ኖሮ ከስድስት ወራት በፊት በደረሰ ነበር… ቢያንስ-ቢያንስ…» በማለት ተናገረ ።

ድንገትም ከፍተኛ እና ባልተስተካከለ ሁኔታ ጉልህ የሆነ ድምፁ ፣ ረጋ እንዲል አድርጎ የሚያሰማው ድምፁ ቁርጥ-ቁርጥ አለ ። በአልጋው ዙርያ ያሉትን እየተመለከተ ግድግዳውን ፣ ለጀርባው ሰጥቶ ዐይኖቹን አፍጥጦ እና ጢሙንም እያሻሸ ቆመ ።

«ሌላው ሰው ተሰናበተ ማለት ነው» በማለት በዝግታ ተናገረ ።

ሉድሚላ ከተቀመጠችበት ተነስታ መስኮቱን ልትከፍት ሄደች ። የበልግን ምሽት ጥቁር መልክ እየተመለከቱ ሁሉም ቅርብ-ለቅርብ ተጠጋግተው ቆመዋል ። ጥቋቁር ከሆኑት የዛፎች ጫፎች በላይ የሰማዩን ወሰን-የለሽ ሕዋዎች ሰንጥቀው ጠልቀው ከዋክብት ያበራሉ ።

ሉድሚላ የእናትን እጅ ጨበጠች እና ድምፅ ሳታሰማ ትከሻዋ ላይ ጣል አደረገችው ። ዶክተሩ ጭንቅላቱን ወደመሬት አዘቅዝቆ መነጽሩን እየጠረገ ቆሞአል ። በፀጥታው መሀል የከተማው የተዳከሙ



የምሽት ቻቻታዎች ይሰማሉ ። ቀዝቃዛ አየር ያለበት ነፋስ ፊቶቻቸውን ነካ-ነካ እያደረገ በማበስ ፀጉራቸውንም መስቀልቀል አደረገው ። እንባዎቿ በጉንጮቿ ላይ ከብለል-ከብለል እያሉ እየወረዱ ሉድሚላ በብርዱ ትንቀጠቀጣለች ። ከኮሪዶሩ በስተውጪ በኩል የሚያስፈሩ ድምፆች ጩኸቶች ፣ ሹክሿኬዎች እና የእግር ኮቴዎች ይሰማሉ ። ይሁን እንጂ ሦስቱም ምሽቱን እያስተዋሉ በፀጥታ ቆመዋል ።

እዚህ የምትገኘው ያለቦታዋ መሆኑን በማሰብ እናት እጅዋን ከሉድሚላ ትከሻ ላይ ቀስ ብላ አነሳች እና እግረ-መንገዷን ልትወጣ ስትል የየጎርን አስከሬን እጅ ነስታ ወደበሩ ሄደች ።

«መሄድዎ ነውን?» አላት ዶክተሩ ረጋ ባለ ድምፅ ዞር ብሎ ሳይመለከታት ።

«አዎን…» አለችው ።

ውጪ ከወጣች በኋላ ሉድሚላ እንዴት ተንሰቅስቃ ታለቅስ እንደነበረ አስታወሰች ።

«እንዴት እንደሚለቀስ እንኳን አታውቅበትም…» በማለት አሰ ።

የጎር ከሙቱ በፊት የተናገረው ትዝ እያላት እ-ሀ-ሀ በማለት በሀዘን ተነፈሰች ። በጎዳናው ላይ ቀስ ብላ በምትጓዝበት ጊዜ ፣ ብልጭ-ድርግም የሚሉ ዐይኖቹን ፣ ፍልቅልቅነቱን ፣ የነገራትን አስደሳች ንግግሮች አስታወሰች ።

«ለጥሩ ሰው መኖር ከባድ ነው ። መሞት ግን ቀላል ነው ። የሚደንቀኝ እኔ የምሞተው እንዴት ባለ ሁኔታ እንደሆነ ነው?..» በማለት ፣ አሰበች ።

የየጎር ሙት ዐይኖች ከጀርባቸው ሁነው በዚያ በነጩ እና በሚያበራው ክፍል ውስጥ ሉድሚላ እና ዶክተሩ ቁመው በሀሣቧ ተመለከተቻቸው ። ድንገትም በሰው ልጅ ትልቅ አሳዛኝነት ልቧ ተነካ ። እንግዳ

በሆነ ስሜት ተገፋፍታ እርምጃዋን በመጨመር ፈጠን-ፈጠን ብላ ትራመድ ጀመረች ።

«ፈጠን ማለት አለብኝ!» አለች ቅር በተሰኘ ነገር ግን ደግሞ ከበስተውስጥ በሚገፋፋት ብርቱ ኃይል ታግዛ ።

11

እናት የሚቀጥለውን ቀን በሙሉ ለሥርአተ-ቀብሩ የሚያስፈልገውን መሰናዶ ስታዘጋጅ ዋለች ። ምሽቱ ላይ እርሷ ፣ ሶፍያ እና ኒኮላይ ሻይ በሚጠጡበት ሰዓት ከቀድሞው በተለየ ሁኔታ ደስተኛ እና ለፍላፊ ሁና ሳሻ መጣች ። ጉንጮቿ በደስታ ተመልተዋል ። ዐይኖቿ የደስ-ደስ ባለው ሁኔታ ክብልል-ክብልል ይላሉ ። በአንድ አስደሳች በሆነ ተስፋ የተመላች ትመስላለች ። ሀዘን ሰፍኖ ስለ የጎር ይወያዩ በነበረበት በዚህ ወቅት የእርሷ ሁኔታ ለዚያን ጊዜ ምቹም አልነበረ ። ሁኔታዋን እነርሱ ካሉበት ሁኔታ ጋር ሊያዛምዱት የማይችሉ በመሆኑ ቅር ከመሰኘታቸውም በስተቀር ፣ ድንገት በጭለማ ቦግ-ቦግቦግ ብሎ እሳት ሲነድ እንደሚያሳድረው የማንጸባረቅ ሁኔታ በእነርሱ ላይም ተመሳሳይ ሁኔታ አሳደረችባቸው ።

ኒኮላይ በሃሣብ ተውጦ ጠረጴዛውን በጣቶቹ ይደቃል ።

«ሳሻ ፣ እንዴት ነው ፣ ዛሬ የቀድሞይቱ አይደለሽም ፤ ልዩ ሁነሻል?» በማለት ኒኮላይ ተናገራት ።

«ለወጥ ብያለሁ እንዴ? ይሆናላ!» በማለት አስደሳች በሆነ አጭር ፈገግታ መለሰችለት ።

እናት በሳሻ አኳኋን አሁንም ደስ ባለመሰኘት ሁኔታ ምንም ሳትናገር ትመለከታት ጀመር ።

«ስለ የጎር ኢቫኖቪች እየተወያየን ነበር…» በማለት ያሉበት ሁኔታ እንዲገባት አድርጋ ሶፍያ ተናገረች ።



«ግሩም ሰው ነበር!» በማለት ሳሻ አደነቀች ። ከዚያም ፡ — «ፊቱ ላይ ፈገግታ ሳይኖርበት አይቼውም አላውቅ ። ሁልግዜም ይቀልድ ይጫወት ነበር ። ተግባሩን የሚያከናውነውስ እንዴት ግሩም በሆነ ሁኔታ ነበር! የሬቮሉሺን አርቲስት ፣ የሬቮሉሺናዊ አስተሳሰብ ሊቅ ነበር ። ስለ አመጽ ፣ ስለ ሀሠት እና ኢ-ፍትሕ ሁኔታ ያቀርባቸው የነበሩት አስተሳሰቦቹ እጅግ ጥንካሬ የተመላባቸው እና ግልጽ የሆኑ ነበሩ!» በማለት ተናገረች ።

አነጋገሯ ረጋ ያለ እና በሃሣብም ተውጣ ፈገግትል የነበረ ሲሆን ፣ ይኸ ፈገግታዋ ግን ፣ ምክንያቱን ሊረዱት ባይችሉ እንኳን በግልጽ የሚያስተውሉትን የደስታዋን ጥማት ሊያረካላት የሚችል ፈገግታ አልነበረም ።

የእነርሱ ሀዘን በሳሻ የደስተኝነት ስሜት እንዲተካ ያልፈለጉ ሲሆን ለእነርሱ የሚሰማቸውን ያለ ሀዘን እርሷንም እንዲሰማት ለማድረግ ወደውን ሳይሆን ያሉበት ሁኔታ አስገደዳቸው ።

«እርሱ ግን ይኸው ከዚህች ዓለም በሞት ተለየ!» በማለት ሳሻን ትክ ብላ በማስተዋል ተናገረች ።

ሳሻ ሁሉንም በማጤን ሁኔታ ቶሎ-ቶሎ መልከት-መልከት ካደረገቻቸው በኋላ ፊቷ ለውጥ ብሎ ተኮሳተረች ። ራሷን ወደመሬት ዝቅ ካደረገች በኋላ በዝምታ ከተዋጠችበት ሁኔታ ፀጉሯን ቀስ ብላ ወደኋላዋ ከልበስ አድርጋ ድንገት ቀና በማለት ትንሽ ቆየት ብላ ጎላ ባለ ድምፅ የሚከተለውን ተናገረች ፡ —

«ሞተ? ምን ማለት ነው ሞተ ማለት? ምን ሞተ? ለመሆኑ ለየጎር ያለኝ አክብሮት ሞቶአልን? ወይንም እንደጓድነቱ ለእርሱ ያለኝ ፍቅር ፣ የእርሱን አስተሳሰቦች የመገንዘቤ ሁኔታ ሞቶአል አብቅቶአል

ማለት ነውን? በልቤ ውስጥ የቀሰቀሰው ስሜት ጠና
ቶአልን? ስለእርሱ ሀቀኛነት እና ብርቱ ሰውነት ያለ
ኝ ግንዛቤ ጠፍቶአል ማለት ነውን? ይኽ ሁሉ ሁኔ
ታው ሞቶአል ማለት ነው እንዴ? ለእኔ ምንም ጊዜ
ቢሆን አይሞትም ። እና እኔ እንደሚመስለኝም እኛ
ቶሎ ብለን 'እከሌ ሞተ' ለማለት ፈጣኖች ነን ። ከናፍሮ
ቹ አይንቀሳቀሱም ሞተዋል! ከአንደበቱ ይፈልቁ የነበ
ሩት ቃላት ግን በሕይወት ባሉት ሰዎች ልቦች ው
ስጥ ተመዝግበው ይኖራሉ!»

በስሜት ተውጣ እንደገና ወንበሩ ላይ ክርኗን
አስደግፋ እንባ በወረራቸው ዐይኖቿ ጓዶቿን ይበ
ልጥ ፀጥታ በተመላው ሁኔታ እና በሃሣብም ተመስጣ
እየተመለከተቻቸው ንግግሯን ቀጠለች ፦ —

«ጓዶች ፥ ምናልባትም የእኔ አባባል የሞኝ አባ
ባል ይሆን ይሆናል ። እኔ ግን ፤ ሀቀኛ ሰዎች ለዘለአ
ለም ህያው በመሆናቸው አምናለሁኝ! ይኽንን ግሩም
ድንቅ የሆነ ሕይወት በደስታ እንድኖር ባደረጉኝ
ሀቀኛ ሰዎች ፥ እጅግ በሚያስደንቅ ሁኔታ ውስብስብ
የሆነውን ፥ በክቶቶች የተመላውን ፥ እንደእኔው እንደራሴ
ው ልብ ውድ የሆኑ የሃሣብ ዕድገቶች የሚገኙበትን
ይኽንን ሕይወት እንድኖር ያደረጉኝን ሰዎች ለዘለአ
ለም ሕያው መሆናቸውን እኔ አምንበታለሁኝ ። ምናል
ባትም እኛን ስሜታችን ከድቶን ብዙ እናስብ እናሰላ
ስል ይሆናል ። ይኽም ሁኔታ በበኩሉ ማንነታችንን
ይገታብን ይሆናል ። አስተያየታችንን እናቀርባለን እንጂ
ስሜት አያድርብን ይሆናል» በማለት ተናገረች ።

«ደስ የሚያሰኝ ነገር አጋጠመሽን?» በማለት
ሶፍያ ፈገግ በማለት ሳሻን ጠየቀቻት ።

«አዎን ። እንደሚመስለኝ በጣም ደስ የሚያሰኝ
ነገር አጋጠመኝ ። ሌሊቱን ሙሉ ከቬሶቭሺኮቭ ጋር
ሳወራ አመሸሁኝ ። አልወደውም ነበር ። ያልታረመ እና



አላዋቂ ሰው ይመስለኝ ነበር ። በእርግጥም ነበር ። በማ
ንም ሰው ላይ ጥላቻ ነበረው ። በማናቸውም ጉዳይ
ውስጥ ምንጊዜም እራሱን ጣልቃ ማስገባት እና
አስነዋሪ እና አጓጉል ድፍረት በተመላበት ሁኔታ እኔ!
እኔ! ማለት ይወድ ነቦር ። ጠባብ አስተሳሰብ ይታይበት
ነበር» በማለት ፈገግ እያለች እና ዐይኖቿ ብሩህ
ሁነው በርተው ተናገረች ፤ ቀጠል አድርጋም ፦ —

«አሁን ግን 'ጓዶች!' በማለት ይናገራል ። ጓዶች
ብሎ ሲጣራ የአጠራሩ ሁኔታ እንዴት እንደሆነ ማ
ድመጥ ይቻላል! ቃላት ሊገልጡት የማይችሉት የዐይ
ን-አፋርነት እና የደግነት ድምፅ የተቀላቀለበት አጠራ
ር ነው ። አሁን እርሱ ያለመዘባነን እንደማንኛውም
ተራ ሰው ሀቀኛ ጠባይ ኖሮት የሚገኝ ከመሆኑም
በስተቀር የመሥራት ከፍተኛ ስሜትም ይታይበታል ።
የጠፋውን እርሱነቱን አግኝቶታል ። ተሰጥአውን እና
ጉድለቱን ተገንዝቦአል ። ዋናው ቁም ነገር ግን ሀቀኛ
የሆነ የጓድነት ስሜት በእርሱነቱ ውስጥ መሥረጹ
ነው» በማለት ተናገረች ።

እናት ሳሻን እያዳመጠች ፥ እርሷን የመበለተ ጠባ
የ-ምቱ ያልሆነች ሰው እንዲህ ረጋ ያለች ጨዋ እና
ተደሳች በመሆን ተሻሽላ በመመልከቷ ተደሰተች ። ይ
ሁን እንጂ እናት ከዚሁ ጋር በአንድነትም ፦ — «የፓ
ቬልስ ጉዳይ?» የሚል ሃሣብ ልቧ ውስጥ ተወሽቆ
ከሚገኝበት ጉራንጉር ይንቀሳቀስባት ጀመር ።

ሳሻ ንግግሯን በመቀጠል ፦ —

«የሚያስበው የሚያሰላስለው ስለጓዶች ብቻ
ነው ። ምን እየነገረኝ ሊያሳምነኝ እንደፈለገ ታውቃላ
ችሁን? ከእሥር ቤት እንዲያመልጡ እነርሱን መርዳት
አለብን አለኝ ። ያለ አንዳች ችግር በቀላሉ ይኽንን
ማድረግ ይቻላል አለኝ» አለች ።

ሶፍያ ራሷን ቀና አደረገች ። ከዚያም ፦ —

«ሳሻ ፥ ይኸ ግሩም ሃሣብ ነው! ምን ይመስልሻል?» በማለት መልስ በጉጉት በመጠበቅ መንፈስ ተውጣ ጠየቀች ።

እናት እጅ ላይ የሚገኘው የሻይ ሲኒ እጅዋ እየ ተንቀጠቀጠ ይንኳኳ ጀመር ። ሳሻ ግንባሯን ሽብሸብ በማድረግ ስሜቷን ለመሸሸግ ሞከረች ። ጥቂት ዝም ካለች በኋላ በደስታ ፈገግ እያለች ፡ —

«እርሱ የሚለው እርግጥ ከሆነ ሙከራ ማድረግ አለብን ። መሞከር ግዳጃችን ነው!» በማለት ተናገረች ።

ድንገት ፊቷ ልውጥውጥ ብሎ ቀላ ። ምንም ሳትናገር ተቀመጠች ።

«አይ አንቺ የኔ ሸጋ!» በማለት እናት እያሰላሰለች ምንም ሳትናገር ፈገግ አለች ። ሶፍያም ፈገግ ያለች ስትሆን ኒኮላይም ሳሻን እየተመለከተ ቀስ ብሎ ሳቀ ። ሳሻ ቀና አለች እና በመኮሳተር ሁሉንም ትመለከታቸው ጀመር ። አኮረፈች ። ዐይኖቿ ደም ለበሱ ። ድምፅዋም ደረቅ ብሎ በቁጣ ተዋጠ ።

«ለምን እንደምትስቁ ይገባኛል ። ይኸንን ለማድረግ የፈለግሁት የራሴ የግል ምክንያት ስላለኝ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ» አለች ።

«ለምን? ሳሻ!» በማለት ሶፍያ ወደ ሳሻ ተነስታ በመሄድ እየተጠጋቻት ተናገረች ። ሳሸ ቅር የተሰኛች መሆኗን እናት ተመለከተች ። ሶፍያ ይኸን ማለት አልነበረባትም ። እናት ትንፋሿን ከዋጠች በኋላ ሽፋሽፍቶቿን ከፍ አድርጋ አጥፍተሻል በሚል ስሜት ሶፍያን ትመለከታት ጀመር ።

«ይኸ ከሆነ ደግሞ እኔ በድርጊቱ አልሳተፍበትም! በምንም ዓይነት መንገድ በጉዳዩ አልገባበትም! እናንተ ጉዳዩን የምትመለከቱት እንደዚህ...» በማለት ሳሻ መናገር እንደቀጠለች ኒኮላይ ፡ —



«ተይ እንጂ ፥ ምነው ሳሻ!» በማለት ዝግ ብሎ ተናገረ ።

እናት ወደእርሷ ዘንድ ሄደች እና ፀጉሯን ትደባብሳት ጀመር ። ሳሻ የእናትን እጅ ጨብጣ በመያዝ ፍም የመሰለ ፊቷን ቀና አደረገች ። እናትም ቃላት አጥረዋት ፈገግ በማለት ትንፋሿን ትውጥ ጀመር ። ሶፍያ እጅዋን ሳሻ ትከሻ ላይ ጣል አድርጋ ከሳሻ ጎን ተቀምጣለች ። በመደነቅ ፈገግታ ሶፍያ የሳሻን ዐይኖች እየተመለከተች ፡ —

«አንቺ የምታስደንቂ ፍጥርት ነሽ!» አለቻት ።

«አዎን ምናልባት ሞኝቷ እኔ ሳልሆን አልቀረሁም...» አለች ።

«እንዴት እንደዚህ ታስቢያለሽ?» በማለት ሶፍያ መናገር ስትጀምር ኒኮላይ ቀጠል አድርጎ ቁም-ነገር በተመላበት አነጋገር ፡ —

«ይኸንን ማድረግ የሚቻል ከሆነ ከእሥር · ቤት እንዲያመልጡ ማናቸውንም መሰናዶ ማድረግ አለብን ። ነገር ግን ከሁሉ አስቀድሞ እሥር ቤት ያሉት ጓዶቻችን ይኸንን እንድናደርግ ፍላጎታቸው መሆን-አለመሆኑን ማወቅ አለብን...»

ሳሻ ጭንቅላቷን ወደ መሬት ቀለስ አደረገች ።

ሶፍያ ሲጋራ አቀጣጠለች ። ከዚያም ወንድሟን መልከት እያደረገች ክብሪቱን ወደ ጥግ ወርወር አደረገችው ።

«ይኸንን እነርሱ እንደማይቃወሙ እርግጥ ነው ። የመቻሉን ነገር ፡ ግን አላምንም» በማለት እናት ተናገረች ።

ይቻላል የሚል መልስ እንዲመልሱላት እናት አፍ-አፋቸውን ትጠባበቅ ነበር ። እነርሱ ግን አንዳችም መልስ ሳይመልሱ ቀሩ ።

«ቬሶቭሺኮቭን ማግኘት አለብን!» በማለት ሶፍያ ተናገረች ።

«በስንት ሰዓት እና የት ቦታ ልታገኚው እንደምትችይ ነገ እነግርሻለሁኝ» አለቻት ሳሻ ።

«እቅዶቹ ምን-ምን ናቸው?» በማለት ሶፍያ በክፍሉ ውስጥ ከወዲያ-ወዲህ እየተንጎራደደች ተናገረች ።

«በአዲሱ ማተምያ ቤት ፊደል ለቃሚነት እንዲቀጠር ሊደረግ ነው ። እስከዚያውም ድረስ ከደን ጠባቂው ጋር ይኖራል» አለች ።

ሳሻ ግንባሯን ቋጠረች ። ፊቷም እንደቀድሞው ኮስታራ ሆነ ። ንግግሯም ድርቅ ያለ ሆነ ። ሲኒዎችን በማጠብ ላይ ወደነበረችይቱ ወደ እናት ዘንድ ኒኮላይ በመሄድ ፡ —

«ከነገ ወዲያ ፓቬልን ለመጠየቅ ሲሄዱ አንድ የተጻፈ ማስታወሻ ይሰጡታል ። የእነርሱን ሃሣብ ማወቅ አለብን...» አላት ።

«አዎን ፣ አዎን ይገባኛል! ማስታወሻውን አሰጣለሁኝ...» በማለት ስታረጋግጥለት ተቻኮለች ።

«እሺ ፣ እንግዲህ ልሂድ» አለች ሳሻ ። እየአንዳንዳቸውን ከጨበጠቻቸው በኋላ በቁመናዋ ቀጥ ብላ እና ሙሉ ዕምነት ያለው አረማመድ እየተራመደች ወጥታ ሄደች ።

ሳሻ ከሄደች በኋላ ሶፍያ እጆቿን እናት ትከሻ ላይ ጣል አድርጋ ወንበሩ ላይ ከወዲያ-ወዲህ ወዝወዝ-ወዝወዝ ታደርጋት ጀመር ።

«ኒሎቭና ይህቺን የመሰለችይቱን ልጅ ይወዷታልን?» በማለት ሶፍያ እናትን ጠየቀቻት ።

«አዎን ። ለአንድ ቀን እንኳን አብረው ሁነው ባየሁዋቸው!» በማለት እናት ለማልቀስ እየቃጣት መለሰች ።



«አዎን ። ጥቂት ደስታ ማንንም አይጎዳም!..» አለ ኒኮላይ ለስለስ ባለ አነጋገር ። ቀጠል አድርጎም — «ይሁን እንጂ ፣ ለጥቂት ደስታ የሚረካ ማንም የለም ። እና ደግሞ ደስታ ተንዛዝቶ ሲበዛ ይረክሳል» አለ ።

ሶፍያ ወደ ፒያኖው ሂዳ አሳዛኝ የሆነ ሙዚቃ ትሞዝቅ ጀመር ።

## 12

በማግሥቱ ጧት የጓዳቸውን እስከሬን አጅበው ለመሄድ ብዛታቸው ሰላሳ ወይንም አርባ የሚሆኑ ሰዎች ከሆስፒታሉ በራፍ ላይ ይጠባበቁ ነበር ። በእነርሱ ውስጥም ሰላዮች ታሰበጣጥረው የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ሰላዮችም የሰዎቹን ሁኔታ ትክ እያሉ በማጥናት ፊታቸውን የሚመለከቱ ከመሆናቸውም በስተቀር የሚናገሩትን ያዳምጣሉ ። ሁኔታቸውንም ያስተውላሉ ። ከመንገዱ ባሻገር ሽጉጥ የታጠቁ ፖሊሶች በተጠንቀቅ ሁነው ይገኛሉ ። በሰላዮቹ በጥባጭነት እና በማናቸውም ሰዓት የኃይል እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ ሁነው በሚገኙት የፌዝ ሳቅ በሚስቁት ፖሊሶች ፣ ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች ተበሳጩ ። ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ ብስጭታቸውን በቀልድ ለመሸፈን የሚጥሩ ናቸው ። ሌሎቹ ደግሞ በእነርሱ ላይ የሚፈጸምባቸውን ልግጫ ላለመመልከት ፊታቸውን ወደ መሬት ቀልሰዋል ። አሁንም ሌሎቹ ደግሞ ይፋ አውጥተው ከሚናገሩት አስተሳሰባቸው ሌላ አንዳችም ትጥቅ የሌላቸውን ሕዝቦች በመፍራት ማናቸውንም የኃይል እርምጃ ከመውሰድ ወደኋላ የማይሉትን ባለሥልጣኖችን በመዝለፍ ብስጭታቸውን ይወጡ ነበር ። ግራጫ ቀለም ያላቸው የድንጋይ እጦብ መንገዶችን የሸፈኑት ቢጫ የዛፍ ቅጠል ርጋፊዎች ነፋሱ እየገፋ

ፋቸው በየሰዎቹ እግሮች ሥር የሚውለበለቡ ሲሆኑ፣ ፈዛዝ ሰማያዊ ቀለም ያለው የበልግ ወራት ሰማይም ብሩኅ ብርሃኑን ፈንጥቆአል ።

እናት በተሰበሰቡት ሰዎች መካከል ቆማለች ። ቀድሞም የምታውቃቸውን ሰዎች እየተመለከተች ፡—

«ብዙዎቻችሁ አልተገኛችሁም ። ብዙዎቻችሁ የላችሁም...» በማለት አሰበች ።

በሩ ተከፈተ ። ከዚያም በቀይ ጥብጣብ የታበተውን አስከሬን ይዘው ወጡ ። ጥቋቁር ወፎች ድንገት ክንፍ ያወጡ በሚመስል ሁኔታ አስከሬኑን በመጠባበቅ የተሰበሰቡት ሰዎች ወዲያውኑ ባርኔጣዎቻቸውን ከየጭንቅላቶቻቸው አወለቁ ። ቀይ በሆነ ፊቱ ላይ በዛ ያለ ሪዝ ያለበት ረዥም የፖሊስ መኮንን ፈጠን ብሎ በመሄድ ሰዎቹ መካከል ገብቶ የቆመ ሲሆን ከበስተኋላውም ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ሰዎቹን ወዲያ እና ወዲህ እየገፋፉ እና ትልቅ ቡት ጫማቸውን ኳ-ኳ እያደረጉ በመርገጥ ወታደሮች ይከተሉ ጀመር ።

«ቀዩን ጥብጣብ ፍቱ!» በማለት መኮንኑ በጎርናና ድምፅ ተናገረ ።

በስሜት ተውጠው እያወሩ፣ እጆቻቸውን እያወዛወዙ እና እርስ-በእርሳቸው እየተገፋፉ ወንዶች እና ሴቶች ሰዎች መኮንኑን እያለፉት ይሄዱ ጀመር ። የፈዘዙ እና በቁጣ የተነሳሱ መልኮች በእናት ዐይን ፊት ያልፉ ጀመር ። በአንዲት ሴትዮ ጉንጭ ላይ እንባዎቿ ዱብ-ዱብ እያሉ ይወርዱ ነበር...

«አመጽ ይደምሰስ!» በማለት አንድ ወጣት ሰው ጮክ ብሎ የተናገረ ሲሆን፣ ይኸ ንግግሩ ወዲያውኑ በተፈጠረው ክርክር ጠፋ ።

የእናት ልብ በሀዘን ተነክቶአል ። መናኛ ልብስ ለብሶ አጠገቧ የቆመውን አንድ ወጣት ዞር ብላ ተመለከተችው ።



«ሥርአተ-ቀብርን እንኳን ጓዶች በሚፈልጉት ሁኔታ እንዲያካሂዱ አይፈቅዱላቸውም ። እረ እንዴት ያለ አሳፋሪ ድርጊት ነው!» በማለት እናት ቀስ ብላ ተናገረች ።

የብስጭነት ስሜት እያደር ከፍ-ከፍ እያለ ያድግ ጀመር ። የአስከሬኑ ሳጥን ከሰዎቹ ጭንቅላት በላይ ሁኖ ይጓዝ ጀመር ። ነፋስ የሚያውለበልባቸው ጥብጣቦች በሰዎቹ ጭንቅላቶች እና ፊቶች ላይ ይወዛወዛሉ ። ሀሩ ኮሽ-ኮሽ ሲልም ይሰማል ።

እናት ግጭት ሊኖር ይችላል ብላ ሠጋች ። በመቻኮል ሁኔታ ግራና-ቀኝ ትመለከት ጀመር ።

«ገሀነም ይግቡ! ጥብጣቦቹን እንደሆን ይውሰዱ ። ከፈለጉ እንተውላቸዋለን!..» በማለት ተናገረች ።

ከጫጫታው መካከል የአንድ ሰው ጉልህ ድምፅ ፡—

«እስከሞት ድረስ ፍዳ እና ስቃይ ያሳያችሁትን ጓዳችንን፣ ይኸንን ጓዳችንን ወደ ዘለአለማዊ ቦታው ልንሸኘው እንሻለን!» በማለት ተናገረ ።

ጉልህ የሆነ ሌላ ድምፅ ፡—
«ክንድህን የተንተራስከው፣
ለታከበረ መስዋዕትነት...»

የተሰኘውን መዝሙር ማሰማት ጀመረ ።

«ጥብጣቦቹን አንሳቸው!ያኮቨሌቭ፣ በጥሳቸው!» የሚል ድምፅ ተሰማ ።

አንድ ሰይፍ ከአፎቱ ሿ-ሿ-ሿ እያለ ተመዘዘ ። ዋይታ ይኖራል ብላ በመገመት እናት ዐይኖቿን ጨፈነች ። ይሁን እንጂ፣ በቦታው የሚገኙት ሰዎች እንደ ቁጡ ተኩላዎች ያጉረመርሙ እና ይሳደቡ ጀመር ። ጓ-ጓ-ጓ የሚል ድምፅ መጫሚያዎቻቸው በማሰማት አየሩን መልተውት ጭንቅላቶቻቸውን ወደታች ቀልሰው እና በፀጥታ ተውጠው ወደፊት ጉዞአ

ቸውን ይቀጥሉ ጀመር ። የተረገጡ አበቦች እና ጥብጣቦቹም ተበጣጥሰው የተነሱበት አስከሬን ከሰዎቹ ጭንቅላት በላይ ሁኖ የሚጓዝ ሲሆን ፤ ከሰዎቹ ጎን ደግሞ ፈረሰኞች ፖሊሶች ይጓዛሉ ። እናት የምትጓዘው በእግረኛ መሄጃ መንገድ ስለሆነ አስከሬኑ አይታያትም ። አስከሬኑን የሚከተለው ሀዘንተኛ አስከሬኑን እስኪከልለው ድረስ ተበራከተ ። በፈረስ የተቀመጡ ግራጫ መልክ ያላቸው ፈረሰኛ ፖሊሶች ኋላ-ኋላ የሚከተሉ ሲሆን ፤ ግራ እና ቀኝ ደግሞ እጆቻቸውን ከሰይፋቸው እጀታ ላይ የደፉ ፖሊሶች ይጓዛሉ ። የሀዘንተኞቹን ሁኔታ በጥንቃቄ ትክ እያሉ የሚቃኙ ሰላዮች በየቦታው ተሰበጣጥረው ሲጓዙ እናት ታስተውላለች ።

ደህና ሁን ጓድ! በል ደህና ሁን...

የሚለውን መዝሙር ሁለት በሀዘን የተሞሉ ድምፆች አሰሙ ።

«ይኸ አያስፈልግም! ዝም ብለን መጓዝ ነው ያለብን ክቡራን!» የሚል ድምፅ ሲያናፋ ትሰማ ።

በዚህ የጩኸት አነጋገር የፍርሃት ስሜት መኖሩ ይታወቅ ነበር ። አሳዛኙ መዝሙር መዘመሩ አበቃ ። የሰዎቹም ውይይት አከተመ ። ሰልፉን አስተካክሎ ጓ-ጓ-ጓ የሚለው የጫማ ድምፅ ብቻ ይሰማል ። ይህ ድምፅ ከሩቅ እንደሚያጉረመርም ማዕበል አየሩን ሰንጥቆ በጠራው ሰማይ ላይ በመንሳፈፍ ከሰዎቹ ጭንቅላት በላይ ይሰማ ነበር ። እየተጠናከረ መንፈስ የጀመረው ቀዝቃዛ አየር የጎዳናውን አቧራ እና ጉድፍ እያነሳ ሰዎቹን ያለብሳቸዋል ። በየፀጉራቸው እና በየልብሳቸው ውስጥ ይገባ ጀመር ። ዐይናቸውን ይከልላቸው ፤ ደረታቸው ላይ ይገርፋቸው ፤ በእፎቻቸው ሥርም እየተሽከረከረ ይነፍስ ጀመር ።



ይህ ያለ ቄሶች አጃቢነት እና ዜማ በፀጥታ የሚሸኝ አስከሬን ፤ እነዚህ በሃሣብ የተዋጡ መልኮች እና ኮስተር ያሉ የሀዘንተኞች ግንባሮች እናትን አሳዘኗት ። በአዕምሮዋ ውስጥ ቀስ-በቀስ ሃሣቦች መርመስመስ የጀመሩ ሲሆኑ ፤ አሳዛኝ በሆኑት በሚከተሉት ቃላት ትሸፍናቸው ጀመር ፡ —

«ለዕውነት የቆማችሁት ብዙዎች አይደላችሁም።»

አንገቷን ወደመሬት ቀልሳ የምትጓዝ ስትሆን ፤ ለመቅበር የሚሄዱት የጎርን ሳይሆን ሌላ መስሎ ተሰማት ። ለእርሷ እጅግ ቅርብ ፤ ውድ እና ምንግዜም አስፈላጊዋ የሆነ ሌላ መስሎ ተሰማት ። ብቸኝነት እና ሀዘን ተሰማት ። የጎርን ለመቅበር ከሚጓዙት ከእነዚህ ሰዎች ጋር ያለመግባባት ሁኔታ በማጉረምረም መልክ ከልቧ ገባ ።

«የጎር በእግዚአብሔር አያምንም ። እነዚህ ሌሎቹም አያምኑም» በማለት አሰላሰለች ።

ይኸንን ሃሣቧን ለረጅም ጊዜ ማሰላሰል አልፈለገችም ። ስለዚህም እ-ሁ-ህ በማለት ትንፋሿን በመዋጥ ነፍሷን የተጫናትን ሸክም ለማቅለል ትሞክር ጀመር ።

«አቤቱ ፈጣሪዬ! አቤቱ እግዚእነ እየሱስ ክርስቶስ! እኔም እንደዚህ እሆን ይሆን...» በማለት አሰበች ።

መካነ-መቃብሩ ደረሱ ። በመቃብሮች መካከል በሚገኝ ጠባብ መንገድ ለጥቂት ጊዜ የጥምዝ ከተጓዙ በኋላ አነስ ያለ ነጭ መስቀል ከሚገኝበት ገላጣ ቦታ ደረሱ ። ግልጽ ሁኖ የሚታየውን ክፍት የመቃብር ጉድጓድ ከብበው ቆሙ ። በመቃብሮቹ መካከል ፀጥ ብለው የቆሙት ሕያዋን ሰዎች ሁኔታ የእናትን ልብ እንዲቆም ያደረገ አንድ አሰቃቂ ስሜት አሳደረባት ። ነፋሱ በየመቃብሮቹ መስቀሎች ላይ እያፏጨ የሚ

ነፍስ ሲሆን በአስከሬኑ ሳጥን ላይ ጠውልገው የሚገኙትን አበባዎችም ያወዛውዛቸዋል ።

ፖሊሶቹ የአዛዣቸውን ዐይን-ዐይን በተጠንቀቅ እያስተዋሉ ቆመዋል ። መልኩ የገረጣ ፤ ጥቋቁር ቅንድቦች ያሉት እና ፀጉረ ረዥምም የሆነ አንድ ረዥምም ወጣት ከአስከሬኑ ፊት ቀደም ብሎ ቆመ ።

«ከቡራን!» በማለት የፖሊሱ መኮንን ጎርነን ባለ ድምፅ ጮኸ ።

«ጓዶች!» በማለት ወጣቱ ሰው ጉልህ እና ግልጽ በሆነ ድምፅ መናገር ጀመረ ።

«ቆይ አንድ ጊዜ!» በማለት መኮንኑ ተቆጣ ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«እንዳችም ንግግር እንዲደረግ የማልፈቅድላችሁ መሆኑን ላስጠነቅቃችሁ እሻለሁኝ...» በማለት ተናገረ ።

«ጥቂት ቃላት ብቻ ነው የምናገረው» በማለት ወጣቱ ሰው ረጋ ብሎ መለሰለት ። ከዚያም ንግግሩን በመቀጠል ፡ —

«ጓዶች! ያስተማረንን የማንዘነጋ ለመሆናችን ፤ እናት ሀገራችን ለምትሰቃይባቸው ሕመሞች ሁሉ ምንጭ የሆነውን ሥልጣን ለመቅበር የመቃብር ጉድጓዱን ያለመታከት የምንቆፍር ለመሆናችን ፤ ማለትም ፤ ፈላጭ-ቆራጭነት የተሰኘውን ክፉ ጨቋኝ ሥልጣን ለመቅበር የመቃብር ጉድጓዱን የምንቆፍር ለመሆናችን እዚህ ፊታችን በሚገኘው ጓደኛችን እና መምህራችን መቃብር ፊት ቃል-ኪዳን እንግባ!» በማለት ተናገረ ።

«ያዙት!» በማለት መኮንኑ አጓራ ። ይሁን እንጂ ፤ የርሱ ማጓራት ፡ —

«ፈላጭ-ቆራጭነት ይደምሰስ!» በሚል አያሌ ድምፅ ተዋጠ ።

ጓደኞቹ ከብበውት እንዳይነካ ወደሚከላከሉለት ተናጋሪ ዘንድ ፖሊሶቹ የተሰበሰቡትን ሰዎች እያተረማመሱ መዝለቅ ጀመሩ ።



«ነፃነት ለዘለአለም ይኑር!» በማለት እጁን ከፍ አድርጎ እያወዛወዘ በጉልህ ድምፅ አሰማ ።

እናት ወደጎን ተገፋች ። በፍርሀት ተውጣ መቃብሮቹ ላይ ከሚገኙት መስቀሎች መካከል አንዱን ተደግፋ እና ዐይኖቿን ጨፍና ድብደባ ይኖራል ብላ መጠባበቅ ጀመረች ። በድምፆች ሁካታ ጆሮቿ ታወኩ ። መሬቱ ከእግሮቿ ሥር ያመልጣት ጀመር ። በንፋሱ እና በፍርሃቷ ምክንያትም አየር ስባ ትንፋሽ መተንፈስ ተሳናት ። የፖሊስ ፊሽካዎች እየተነፉ የማስጠንቀቂያ ድምፅ ሲሰጡ ፤ ያልተገሩ የአዛዦች ድምፆች ደግሞ ትዕዛዝ ማስተላለፍ ጀመሩ ። የሴቶች ድምፆች በድንጋጤ ሲጮሁ ተሰሙ ። የአጥር ብረቶች ተሰባበሩ ። ትላልቅ ቡት ጫማዎች ደረቁ መሬት ላይ ተንጓጉ ። ይኸ ሁኔታ ረዘም ላለ ጊዜ በመቆየቱ እናት መዐቱን ለመቋቋም ዐይኖቿን እንደጨፈነች ለመቆየት አልቻለችም ።

ቀና ብላ ተመለከተች ። ከዚያም እያለቀሰች እጆቿን ዘርግታ ወደፊት ሮጠች ። ብዙም ሩቅ ሳይሆን በመቃብሮች መካከል በሚገኝ ጠባብ መተላለፊያ ላይ ወጣቱን ሰው ከብበው የያዙት ሲሆን ፤ እርሱን ለማስለቀቅ የሚጠጓቸውን ሰዎችም እየደበደቡ ወደኋላ ይመልሳሉ ። ከአፎቶቻቸው የተመዘዙ ሰይፎች አንዱ ከጭንቅላት በላይ ፤ አንዱ ደግሞ መሃል-ለመሃል እየተወዛወዙ ያንፀባርቃሉ ። ጣሳዎች እና የተጎመዱ የአጥር ብረቶች እንደመሣርያ መገልገያ ሁነዋል ። የቁጣ ድምፅ የሚያሰሙት ሰዎች የገረጣ መልክ ያለውን ወጣት ሰው ከብበው ዙርያውን ይዞሩታል ። ይኸንን በመሰለው የስሜት ማዕበል የወጣቱ ሰው ድምፅ ከፍ ብሎ የሚከተለውን አሰማ ፡ —

«ጓዶች! ጉልበታችሁን አታባክኑ!»

ንግግሩን ተቀበሉት ። ሰዎቹ ዱላዎቻቸውን ወርውረ
ው መሸሽ ጀመሩ ። እናት ግን በአንድ ልትቋቋመው
ባልቻለችው የውስጥ ኃይል ምክንያት ወደፊት ተራም
ዳ ቆመች ። ኒኮላይ ባርኔጣውን ወደኋላው ይዞ የተበ
ሳጨትን ሰዎች ሲገፋ ተመለከተች ።

«አብዳችኋል እንዴ? ቀዝቀዝ በሉ!» በማለት ከስሕ
ተታቸው ያርማቸው ጀመር ።

በአንደኛው እጁ ላይ ደም ያየች መሰሎ ተሰማት ።

«ኒኮላይ ኢቫኖቪች! ከዚህ ቦታ ሂድ!» በማለት ወደ
ርሱ እየገሰገሰች ጮክ ብላ ተናገረች ።

«ወዴት ይሄዳሉ? እዚያ ቦታ ይደበድቡዎታል...»

ትከሻዋ ላይ የሰው እጅ ሲያርፍ ተሰማት ። አንድ
ወጣት ልጅ በእጅዋ የያዘች ፣ ፀጉሯ ተመሳቅሎ እና
ባርኔጣ ሳታደርግ ሶፍያ አጠገቧ-ቆማ አየቻት ። ከሕፃ
ንነት ዕድሜው ብዙም ያልገፋው ልጅ ፊቱ ላይ
የሚፈስሰውን ደሙን ይጠርጋል ።

«ልሂድ... ግዴለም...» በማለት ከንፈሮቹ እየተንቀ
ጠቀጡ ተናገረ ።

«ከእርስዎ ጋር ይሁን ። ወደ እኛ ቤት ይውሰዱ
ት ። ፊቱን በዚህ መሃረብ ይሠሩለት» በማለት ሶፍያ
በፍጥነት ተናገረች ። የልጁን እጅ ለእናት አስረከበች
እና ፡—

«በፍጥነት ይሂዱ ። አለበለዚያ ይይዙዎታል!» በማ
ለት እየተናገረች ሸሸች ።

ሀዘንተኞቹ መካነ-መቃብሩ ውስጥ በተለያዩ አቅጣ
ጫዎች ተሰበጣጥረዋል ። ዘርፋፋ ካፖርት ያጠለቁት
ፖሊሶች በየመቃብሩ መሃል እየተሳደቡ እና ሰይፋቸ
ውን እያወዛወዙ ከባድ በሆነ እርምጃ ይራመዳሉ ። ት
ንሹ ልጅ እንደተኩላ ይመለከታቸዋል ።

«ቶሎ በል!» አለችው እናት የልጁን ደም ከፊቱ
ላይ እየጠረገችለት ።



«ስለ እኔ አያስቡ ። አይጎዳኝም » አለ ደሙን እየ
ተፋ ።

«በሰይፉ እጄታ መታኝ ። እርሱም ምሱን አገኘ!
እኔም ኡ! ኡ! እስኪል ድረስ በዱላ ወገርኩት! ቆይ
ግዴለም!» በማለት በደም የተለወሰ እጁን እያወዛወዘ
ተናገረ ። ከዚያም

«ከወደፊቱ መጪ ሁኔታ ጋር ሲተያይ ይኸ ምን
ም አይደለም! እኛ ወዝ-አደሮች በሙሉ አንድ ጊዜ
ከተነሳን ከምድረ-ገጽ ጠራርገን እናጠፋችኋለን!» በማ
ለት ተናገረ ።

«ቶሎ-ቶሎ ና!» አለች እናት መካነ መቃብሩ ውስ
ጥ ወደሚገኘው ወደትንሹ መግቢያ እያመራች ። በለ
ላኛው አጥር በኩል ገላጣው ቦታ ላይ ፖሊሶች አድ
ፍጠው የሚጠባበቁዋቸው እና ገስግሰው በመምጣትም የ
ሚጨፈጭፉአቸው መሰሎ ታያት ። ይሁን እንጂ የበል
ጉ የምሽት ብርሃን በአረንጓዴው መስክ ላይ የሚያበ
ራበትን ቦታ ከመግቢያው በር ላይ ደርሳ ስትመለ
ከት ፀጥ ያለ እና ጭር ያለ ቦታ ሁኖ አገኘችው ።

«ቆይ አንድ ጊዜ ፊትህን ልሠርልህ» አለችው ወ
ጣቱን ልጅ ።

«አይቸገሩ ። አላፍርበትም ። ሀቀኛ በሆነ ድብድብ
ምክንያት የደረሰብኝ ቁስለት ነው ። ደበደበኝ ፣ እኔም
ምሱን አቀመስኩት...» አለ ።

እናት ቶሎ ተፋጥና ቁስሉን አሠረችለት ። የፈሰሰ
ውን የልጁን ደም መመልከቱ ለልጁ እንድታዝን
ያደረጋት ሲሆን በደሙ ሞቃትነት እና ሙጫማነት
ደግሞ ልቧ በሀዘን ስቃይ ተዋጠ ። ምንም ሳታናግረ
ው በመስኩ በኩል አቋርጣ በፍጥነት እንዲገሰግስ
ታደርገው ጀመር ።

«ጓዲት! ወዴት ነው የሚወስዱኝ? እኔው ራሴ መሄ

ድ እችላለሁኝ!» በማለት የታሠረለትን ከአፉ ላይ አላ
ቅቆ በየዋህ አነጋገር ተናገረ ።
ይሁን እንጂ ፣ የእጁ መንቀጥቀጥ የተሰማት ከመሆኑ
ም በስተቀር እግሩም ይብረከረክ ነበር ። አንዳችም መ
ልስ ሳይጠብቅ ባለማቋረጥ ይናገር እና ጥያቄም ያቀ
ርብ የነበረ ሲሆን ድምፁም ከጊዜ ጊዜ እየተዳከመ
ሄደ ።
«እርስዎ ማን ነዎት? እኔ ቆርቆሮ ሠራተኛ ነኝ ።
ኢቫን እባላለሁኝ ። የጎር ኢቫኖቪች የጥናት ክበብ ው
ስጥ ሶስት አባሎች እንገኝ ነበር ። ማለት ፣ በጥናት ክበ
ቡ በጠቅላላው አሥራ አንድ ሰዎች ስንገኝ ፤ ከአሥራ
አንዱ መካከል ሶስታችን የቆርቆሮ ሠራተኞች ነን ።
የጎር ኢቫኖቪችን እጅግ አድርገን እናፈቅራቸው ነበ
ር ። ምንም በእግዚአብሔር ባላምንም ፤ ነፍሳቸውን ይማ
ራቸው!» በማለት ተናገረ ።
መንገድ ላይ አንድ ቦታ እንደደረሱ ጋሪ አስቆ
መች እና ኢቫንን እንዲቀመጥ ካደረገችው በኋላ ፡—
«እንግዲህ ምንም እንዳታወራ!» በማለት የአፉን
ቁስል በመሃረቡ አሠረችለት ።
የታሠረለትን እሥር ለመነካካት በጣም ደክሞ ስ
ለነበር እጁን ጥቂት ወደፊቱ ከፍ ካደረገ በኋላ ወዲ
ያውኑ ጭኑ ላይ መልሶ ጣል አደረገው ። የታሠረው
አፉ አሁንም ሲያወራ መንቃነቁ ይታወቃል ።
«የኔ ደጎች ይኸንን የደረሰብኝን የምዘነጋው አይ
ደለሁም ። የጎር ኢቫኖቪች ከመምጣታቸው በፊት ቲቶ
ቪች የተሰኘ ተማሪ እኛን ያስተምረን ነበር ። …ፖለ
ቲካዊ ኤኮኖሚ ያስተምረን ነበር …በኋላ ግን ተያዘ
እና ታሠረ…»
እናት እጅዋን ኢቫን ላይ ጣል ፤ ጭንቅላቱን ወደ
ደረቷ ቀልበስ አድርጋ አቀፈችው ። ድንገት ልጁ እመ
ር እንደማለት አለ እና በተቀመጠበት ረጋ ። በፍርሃ



ት ተዋጠች ። ትመለከተው ጀመር ። ከተሸጎጡበት ከአን
ዱ ሥርቻ ፖሊሶች መጥተው የኢቫንን ቁስል ከተመ
ለከቱ ወስደው ይገድሉታል ብላ ፈራች ።
«ሠክሮ ነው እንዴ?» በማለት ጋሪ ነጂው በበጎ
መንፈስ የቀልድ ሳቅ እየሳቀ ዞር ብሎ ተመለከተ ።
«እ-ሁ! እ-ሁ! እ-ሀ-ሀ! አዎን ከአቅሙ በላይ ጠጥቶ
ነው!» በማለት ትንፋሿን እየዋጠች ለጋሪ ነጂው መለ
ሰችለት ።
«ልጅዎ ነው?» በማለት ጠየቃት ።
«አዎን ልጄ ነው ። ጫማ ሰፊ ነው ። እኔ ደግሞ
ወጥ ቀቃይ ገረድ ነኝ…» አለችው ።
«አሄሄ! ኑሮዎ የችግር ኑሮ ነዋ!» አለ ።
የፈረሱን ፡ አለንጋ ይዞ ጋሪ ነጂው እንደገና ዞር
በማለት ፡ —
«መካነ መቃብር ውስጥ ድብድብ ነበር አሉ ። አል
ሰሙም እንዴ!»በማለት ዝቅ ባለ ድምፅ ጠየቃት
ቀጠል አድርጎም «የፖለቲካ ሰዎች ከሆኑት መካከል
የአንዱ ቀብር ነበር መሰለኝ ። እነዚህን ከፍተኛዎቹን
ባለሥልጣኖች ከሚቃወሙት መካከል የአንዱ ቀብር
ነበር መሰለኝ ። ከእነዚህ ከከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር
እነርሱ አይስማሙም ። ለቀብር የተሰበሰቡትም እንደሚ
መስለኝ እንደሚቹ ፖለቲከኞች ሳይሆኑ አይቀሩም ።
'ባለሥልጣኖች ይደምሰሱ! ሕዝቦችን የሚመዘብሩት
እነርሱ ናቸው!' በማለት ፖለቲከኞቹ ቀባሪዎች የተቃው
ሞ ድምፅ ሳያሰሙ አልቀሩም ። ከዚያም ፖሊሶች መ
ጡ እና ይደበድቡአቸው ጀመር ። አንዳንዶቹን እስኪሞ
ቱ ድረስ ደበደቡአቸው ይባላል ። ከፖሊሶችም የተጎ
ዱ አልቀሩም!» በማለት ከተናገረ በኋላ ለጥቂት ጊዜ
ዝም አለ ። ከዚያም ቀጠል አደረገ እና ፡ —

«ሙታንን መቀስቀስ ምን ያደርጋል!» አለ ። ከዚያም በጉዳዩ ባለመስማማት ሁኔታ ራሱን በሀዘን እየነቀነቀ «ሙታንን ሰላም መንሳት ከቶ ለምንድነው!» በማለት ተናገረ ።

በንጥፍ ድንጋዩ ላይ የሚጓዘው ጋሪ ነቅነቅ ሲል የኢቫን ጭንቅላት እናት ደረት ላይ ጥግት ብሎ ተጠጋ ። ጋሪ ነጂው ከፊት በሚገኘው መቀመጫው ላይ በገሚስ ዞር ብሎ ተቀምጦ የሚከተለውን ተናገረ ፡—

«ሕዝቡ እየተንቀሳቀሰ ነው ። ሁከት እየተስፋፋ ነው ። ባለፈው ምሽት ጃንዳርሞች እኛ ሠፈር የሚኖር አንድ ጎረቤት ቤት መጥተው እስከንጋት ድረስ ቤቱን ሲያመሳቅሉ ከቆዩ በኋላ አንዱን አንጥረኛ ይዘውት ሄዱ ። ሰዎቹ እንደሚሉት በውድቅት ላይ ወደወንዝ ወስደው ወንዙ ውስጥ ይጥሉታል ነው ። አይ! አንጥረኛው እንዴት ያለ ጥሩ ሰው ነበር!» አለ ።

«ማን ይባል ነበር?» በማለት እናት ጠየቀች ።

«ማን ፣ አንጥረኛው? ሳቬሊ የቭቼንኮ ይባላል ። ገና ወጣት ሰው ነው ። ግን ብዙ ብዙ ዕውቀት አለው ። የማይፈቀዱ ነገሮችን ተመራምሮ የሚያውቅ ይመስላል ። እኛን ለመጠየቅ ይመጣ ነበር ። ከዚያም ፡— ‘እናንተ ጋሪ ነጂዎች ለመሆኑ ምን ዓይነት ኑሮ እንደምትኖሩ ታውቁታላችሁን?» ይለናል ። እኛም ‘ከውሻ ኑሮ የባሰ ኑሮ ነው የምንኖረው’ እንለዋለን ።» አላት ።

«እሺ ፣ ያቁሙልን እዚህ እንወርዳለን!» አለችው ።

ንቅናቄው ኢቫንን አነቃው ። በጥቂቱ አቃሰተ ።

«ጥንብዝ ብሎ ሰክሮ የለ እንዴ! አይ አረቂያም አረቄኛ!» በማለት ጋሪ ነጂው ተናገረ ።

ኢቫን የግዱን ከጋሪው ላይ ወደ መሬት ወረደ ።

«ደህና ነኝ ። ብቻዬን መሄድ እችላለሁኝ...» እያለ እናትን መከራከሩን ቀጠለ ።





ሶፍያ ቀድማ እቤት ገብታ ነበር ። ብስጩ እና ቁጡ ሁናለች ። ሲጋራዋን በጥርሶቿ መሃል እኝካ ይዛለች ።

ቁስለኛውን ልጅ ሮቱው ላይ ካስቀመጡት በኋላ ዐይኖቿን ከሲጋራዋ ጢስ እየተከላከለች እና ትዕዛዝ እየሰጠች የጭንቅላቱን እሥር ቶሎ ብላ ትፈታለት ጀመር ። ከዚያም ፡—

«ኢቫን ዳኒሎቪችን አምጥተውታል! ኒሎቭና ደከመዎት እንዴ? ፈርተው ነበር ። አይደለምን? አሁን እስኪ ትንሽ አረፍ ይበሉ ። ኒኮላይ ፣ እስኪ ለኒሎቭና አንድ ብርጭቆ ወይን ጠጅ ስጣቸው!» አለች ።

እናት እስካሁን በደረሰው ድርጊት ከላይዋ ላይ ሀዘኑ እና ድንጋጤው አልበረደላትም ። የምትተነፍሰው የግዷን ሲሆን ልቧንም በጣም ሕመም ይሰማት ጀመር ።

«ስለእኔ አትቸገሩ...» በማለት ተናገረች ። ይሁን እንጂ መላ ሁኔታዋ የደግነት የክፉ አይንካዎ ባይነት እንክብካቤ እንዲደረግላት የሚጠይቅ ነው ።

ኒኮላይ ከሌላኛው ክፍል የመጣ ሲሆን እጁም በፋሻ ተጠቅልሎ ተመለከተች ። አብሮትም ሃኪሙ ዶክተር ኢቫን ዳኒሎቪች የሚገኝ ሲሆን እርሱም ፀጉሩ እንደ ጃርት ተመሰቃቅሎ እና ተቆጥቶ ቆሞአል ። በቀጥታ ወደኢቫን ሄደ እና ጎንበስ ብሎ ተመለከተው ። ከዚያም ፡—

«ውሃ ብዙ ውሃ ። ጥቂት የጥጥ ጨርቅ እና ጥጥ አምጡልኝ!» አለ ።

እናት ወደ ምግብ ማዘጋጃው ክፍል ለመሄድ ስትነሳ ኒኮላይ በእጁ ደገፍ አድርጎ ከያዛት በኋላ ወደ ምግብ ማዘጋጃው ክፍል እየወሰዳት ፡—

«ሶፍያ ነች አምጪ የተባለች እንጂ ፤ እርስዎ አይደሉም ። የኔ ውድ ፤ ተረብሸው ነበር ። አይደለምን?» በማለት ለስለስ ባለ አነጋገር ተናገረ ።

ይሁን እንጂ ፣ ትክ ብለው ተመልካች እና ርኅሩኅ የሆኑ ዐይኖቹን ስተመለከት ራሷን መቆጣጠር አልቻለችም ።

«የኔ ሸጋ ፣ ምን ነበር ይደረግ የነበረው! ሰዎችን ቆራረጡአቸው! ቆራረጡዋቸው እኮ!» በማለት አለቀሰች ።

«ተመልክቻለሁኝ!» አለ ኒኮላይ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ እና ወይን ጠጅ በብርጭቆ እየሰጣት ። ቀጠል አድርጎም ፣ —

«ሁለቱም ወገኖች ራሳቸውን ስተው ነበር ። ይኸ ግን አያሳስብዎ ። በሰይፋቸው ይማቱ የነበረው በስሉ በኩል ሳይሆን በዱልዱሙ በኩል ነበር ። እንደመሰለኝ ክፉኛ የቆሰለ አንድ ሰው ብቻ ነበር ። ሁኔታው ሲደርስ የተመለከትኩኝ ስሆን ከግርግሩ ውስጥም አውጥቼ ዋለሁኝ...» በማለት ተናገረ ።

እናት በኒኮላይ ድምፅ ፣ በክፍሉ ሞቃትነት እና ድምቀት ተጽናናች ። በባለውለታነት ትመለከተው ጀመር ።

«አንተንም መቱህን?» በማለት ጠየቀችው ።

«እንደሚመስለኝ ይኸንን ጉዳት ያደረስኩት ራሴው ነኝ ። በድንታ ቢስነት እጄን ከአንድ ነገር ጋር አጋጭቼ ቆዳዬ ተላጠ ። እንሆ ሻይ ይጠጡ ። ውጪው ይበርዳል ። ሙቀት የሚሰጥ ልብስ ደግሞ አልለበሱም...» አለ ።

ሲኒውን ለመቀበል እጅዋን ስትዘረጋ የደረቀ ደም እጅዋ ላይ ተመለከተች ። ወዲያውኑ እጅዋን ወደ ጭኗ ስብስብ አድርጋ መለሰችው ። ቀሚሷ ርጥብ ነበር ። ጣቶቿን ስትመለከት የዐይኖቿን ሽፋል ከፍ አድርጋ



በመሽብሽብ ዐይኖቿን ብልጥጥ አድርጋ ከፈተቻቸው ። ልቦቿ ይመቱ ጀመር ። ዞረባት ።

«ፓቬልንም ቢሆን ያው እንደዚህ ማድረጋቸው አይቀርም!» በማለት አሰበች ።

ኢቫን ዳኒሎቪች የሸሚዙ እጅጌ ተሰቅስቆ እነርሱ ወደአሉበት ክፍል ገባ ። ለኒኮላይ ዝምታ የተመላበት የአጠያየቅ አመለካከት በጉልህ ድምፅ እንደሚከተለው መለሰ ፣ —

«የፊቱ ቁስል ይኸን ያህል ከባድ አይደለም ። የራስ ቅሉ ግን በጣምም ባይሆን በመጠኑ ተፈንክቶአል ። ጠንካራ ወጣት ነው ። ይሁን እንጂ ፣ ብዙ ደም ፈስሶታል ። ወደሆስፒታል እንላከው ይሆን?» አለ ።

«ለምን? እዚሁ ይቆይ!» አለ ኒኮላይ ።

«ለዛሬ እና ምናልባትም ለነገ ጭምር ። ከዚያ በኋላ ግን ለእኔ ምቹ የሚሆንልኝ ሆስፒታል ባክመው ነው ። እዚህ እየተመላለስኩኝ ለማከም ጊዜ የለኝም ። በመካነ-መቃብሩ ቦታ ስለደረሰው ግጭት ተበታኝ ወረቀት ታዘጋጃለህን?» አለው ።

«አዎን ። አዘጋጃለሁኝ!» በማለት ኒኮላይ መለሰ ።

እናት በዝምታ ተነስታ ወደ ማዕድ ክፍል መሄድ ጀመረች ።

«ኒሎቭና ፣ ወዴት ይሄዳሉ?» በማለት እየተጨነቀ ኒኮላይ ጠየቀ ። ቀጠል አድርጎም ።

«ያለ እርስዎ አጋዥነት ማናቸውንም ነገር ሶፍያ ማከናወን ትችላለች!» አለ ።

ተመለከተችው እና በጥቂቱ ትከሻዋን ነቅነቅ አደረገች ።

«ሰውነቴ ሁሉ በደም ተለውሶአል...» በማለት ፈገግ እንደማለት ብላ መለሰች ።

ክፍሏ ሂዳ ልብሶቿን ስትቀይር እነዚህ ሰዎች ያላቸውን ያለመበገር ጥንካሬ እና እንደዚህ አሳሳ

ቢ የሆኑ ከፍተኛ ሁኔታዎችን እንዴት በቀላሉ እንደ
ሚወስዱት በመገረም ትደነቅ ጀመር ። ይኸንን በመሰለ
ው ሁኔታ የምታደርገው ማሰላሰል ፍርሃቷን ከላይዋ
ላይ የገፈፈላት ሲሆን ልቧንም አበረታለት ። ቁስለኛ
ው ልጅ ወደተኛበት ክፍል ስትሄድ ሶፍያ ልጁን
ጎንበስ ብላ ስትመለከተው አስተዋለች ።

«ጓድ! ይኸማ ሞኝነት ነው!» ትለዋለች ሶፍያ ።

«አዎን ፤ እርስዎን አስቸግርዎታለሁ!» በማለት በተዳ
ከመ ድምፅ ተናገረ ።

«ይልቅ ዝም ይበሉ ። ይኸ የበለጠ ይጠቅምዎታ
ል...» ትለዋለች ።

እናት እጅዋን ሶፍያ ትከሻ ላይ ጣል አድርጋ ከበ
ስተኋላዋ ቆማ ጋሪው ላይ በነበሩበት ጊዜ አስደንጋ
ጭ የሆኑ ቃላቶችን በመናገር እንዴት ያስፈራራት
እንደነበረ የልጁን የገረጣ ፊት እየተመለከተች በመሳ
ቅ ለሶፍያ ትነግራት ጀመር ። የኢቫን ዐይኖች በትኩሳ
ት ጋይተዋል ።»

«እንደምን ያለሁ ሞኝ ነኝ!» አለ ሀፍረት በተሰማ
ው ሁኔታ ።

«አሁን ትተንሀ መሄዳችን ነው ። በል እንግዲሀ
ተኛ» እያለችው የብርድልብሱን አስተካከለችለት ።

ምግብ ቤት ሂደው ያሳለፉትን የዕለቱን ሁኔታ
በመነጋገር ረዘም ላለ ጊዜ ቆዩ ። ያለፈውን ድርጊት
እንዳለፈ ድርጊት በመቁጠር ስለወደፊቱ ሁኔታ በ
ሙሉ ልብ እያሰላሰሉ ስለወደፊቱ ምን ማድረግ እን
ደሚገባቸው ዕቅድ እያወጡ ይወያዩ ጀመር ። ፊቶቻ
ቸው በድካም ዝለዋል ። አስተሳሰቦቻቸው ግን ብርታት
ያልተለያቸው አስተሳሰቦች ሲሆኑ ስለ ተግባራቸው
በሚወያዩበት ጊዜም በራሳቸው ላይ ያላቸውን ያለመር
ካት ስሜት አይሸሽጉም ። ዶክተሩ ብስጩ ሁኖ ወንበ
ሩ ላይ ይንቆራጠጣል ።



«በአሁኑ ጊዜ ፕሮፓጋንዳ ብቻውን በቂ አይደለ
ም!» በማለት ጉልህ እና ከፍተኛ የሆነ ድምፁን ለመ
ግራት እየሞከረ ተናገረ ። ቀጠል አድርጎም «ወጣት
ወዝ-አደሮች ትክክል ናቸው ። የፕሮፓጋንዳችንን መጠ
ን መጨመር አለብን የምነግራችሁን ስሙኝ! ወዝ-አደ
ሮቹ ልክ ናቸው ነው የምለው!» አለ ።

ኒኮላይ ኮስተር ብሎ የዶክተሩን ድምፅ በመሰለ
ሁኔታ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«የሥነ-ጽሁፍ እጥረት አለ የሚል ቅሬታ ከየቦታ
ው ይሰማል ። ያም ሁኖ ግን አሁንም ድረስ ሻል ያለ
ነው የምንለው ማተምያ ለማቋቋም አልቻልንም ። በዚ
ህ ተግባር የተሠማራችይቱ ሉድሚላ በድካም እየዛለ
ች ነች ። ረዳት ካላደረግንላት በቅርቡ ራሷን ስታ
ትወድቃለች» አለ ።

«ቬሶቭሺኮቭስ?» በማለት ሶፍያ ጠየቀች ።

«እርሱ ከተማ ውስጥ ሊኖር አይችልም ። አዲሱ
ማተምያችን ሥራውን ሲጀምር ብቻ ሥራ መሥራት
ይጀምራል ። ያንን ከመጀመራችን በፊት ደግሞ አን
ድ ሌላ ተጨማሪ ሰው ያስፈልገናል» አለ ።

«እኔ ልሠራ አልችልምን?» በማለት እናት ረጋ
ብላ ጠየቀች ።

ሦስቱም ለጥቂት ሰኮንዶች ሳይነጋገሩ ይመለከ
ቷት ጀመር ።

«ጥሩ ሃሣብ ነው!» በማለት ሶፍያ አድንቃ ተናገ
ረች ።

«ኒሎቭና ፥ ሥራው ለእርስዎ ከባድ ይሆንብዎታል»
በማለት ኒኮላይ መረር አድርጎ ተናገረ ። ቀጠል አድር
ጎም «ከከተማ ውጪ መኖር ይኖርብዎታል ። ይኸም
ማለት ፓቬልን ሊያዩት አይችሉም ማለት ነው ። እና
በአጠቃላይ ደግሞ...» ብሎ ሳይጨርስ ፥ እናት ንግግሩ
ን ቀበል አድርጋ ፡ —

«የኔ ፓቬልን አለመጎብኘት ለፓቬል ይኸን ያህል
ም የሚያጎድልበት ነገር የለም ። ዕውነቱን ለመናገር
ከሆነ ደግሞ ፣ ለእኔም ቢሆን ፓቬል ዘንድ መሄዱ
ልቤን ማሸበር ብቻ ነው ። አንዳችም ነገር ቢሆን
መነጋገር አይፈቀድም ። ክልክል የሆኑ ያልተፈቀዱ ነገ
ሮች ከአንደበቴ ወጥተው እናገር እንደሆን ብለው
እነርሱ አፍ-አፌን ሲያስተውሉ እኔ እንደሞኝ ተገትሬ
መቆም ብቻ ነው የተረፈኝ» አለች ።

በእነዚህ ጥቂት ቀናት ድርጊቶች ድክም ብላ
ዝላ የነበረች በመሆኗ ፣ አሁን ራቅ ብላ የመኖር
አጋጣሚ እንዳጋጠማት ስትገነዘብ በአጋጣሚው ለመ
ጠቀም ጓጓች ።

ይሁን እንጂ ፣ ኒኮላይ ይኸንን የሚወያዩበትን አርዕ
ስት ለወጥ አደረገው ።

«ኢቫን ፣ በአዕምሮህ ውስጥ ምን እየተጉላላ ነው?»
በማለት ኒኮላይ ዞር ብሎ በመመልከት ዶክተሩን
ጠየቀው ።

ዶክተሩ ወደመሬት ቀለስ ብሎ የነበረውን ጭንቅ
ላቱን ቀና አደረገ ። ከዚያም ፡ —

«ብዛታችን የቱን ያህል አነስተኛ እንደሆነ እያሰላ
ሰልኩኝ ነው» አለ ቅር በተሰኘ ሁኔታ ፤ ከዚያም ቀጠ
ል አድርጎ «ይበልጥ ጠንካራ በሆነ ሁኔታ መሥራት
አለብን ። ፓቬል እና አንድሬይም ከእሥር ቤት ማምለ
ጥ እንዳለባቸው አስረድተን ማሳመን አለብን ። እዚያ
ያለ አንዳች ተግባር እንዲሁ ታሥረው መቀመጥ
የለባቸውም ። እነርሱ በጣም ለእኛ ጠቀሜታ ያላቸው
ናቸው» አለ ።

ኒኮላይ ኮስተር አለ ። ጭንቅላቱን ነቅነቅ እያደረገ
እናትን ይመለከት ጀመር ። እርሷ ባለችበት ስለልጅዋ
ለማውራት ማመንታታቸውን በመመልከቷ ፣ የእርሷን
ምኞት ከቁም ነገር ባለመቁጠራቸው አዝና ተነስታ



ወጥታ ሄደች ። ዝቅ ባለ ድምፅ የሚሰሙትን ንግግሮ
ች ዐይኖቿ ተከፍተው እያዳመጠች አልጋዋ ላይ
ጋደም እንዳለች ነቃ ብላ ታሰላስል ጀመር ።

ቀኑ ለእናት ልትረዳው ባልቻለችው ሁኔታ ጭልም
ልም ያለ እና የደስ ደስ የሌለው ሁኖባት የነበረ
ቢሆንም ስለዚህ ለማስታወስ አልፈቀደችም ነበር ።
የሚያውኳትን አስተሳሰቦች በሙሉ ወደጎን ትታ ስለ
ፓቬል ታስብ ጀመረች ። ከእሥር ቤት እንዲወጣ ፈል
ጋለች ። ነገር ግን ፈርታለታለች ። በእርሷ አካባቢ ያሉ
ት ሁኔታዎች ከጊዜ ጊዜ ከፍ-ከፍ እያሉ የሚሄዱ
እና ወደ ግጭት የሚያመሩ መሆናቸውንም ተገነዘበ
ች ። የሰዎች በዝምታ የተመላ ታጋሽነት ቦታውን
ለተጋጋለ ተሳታፊነት ይለቅቅ ጀመር ። ብስጩነታቸው
ከጊዜ-ጊዜ እየጨመረ ይሄድ ጀመር ። ከሁሉም ዘንድ
ጠንከር ያሉ ቃላት ሲሰነዘሩ የምታዳምጥ ሲሆን ሁሉ
ም ነገር መረጋጋት የጎደለው ሁኖ ይታይ ነበር ። እየአ
ንዳንዱ አዋጅ በገበያ ቦታዎች ፣ በየሱቆች ፣ በአሽከ
ሮች እና በእደ ጥበባት ሠራተኞች መካከል ውይይ
ትን ያስከትል ጀመር ። በከተማዎች ውስጥ ሰዎች በ
ተያዙ ቁጥር ሁኔታው አስፈሪ እና ውስብስብ የሆኑ
አስተያየቶችን አንዳንድ ጊዜም እንደየሁኔታው በቅሬ
ታ የተመሉ የሀዘን ምልክቶችን ያስከትሉ ጀመር ።
እንደመነሳሳት ፣ እንደ ሶሻሊስቶች ፣ እንደ ፖለቲካ የመ
ሳሰሉት ቀደም ባሉት ጊዜዎች ስትሰማቸው ያስፈራ
ሩዋት የነበሩትን ቃላቶች ከጊዜ ጊዜ ተራ ሕዝቦች ሲ
ጠቀሙባቸው ትሰማቸው ጀመረች ። ቃላቶቹ የሚቀርቡ
ት በምጸት መልክ ቢሆን ፣ ከምጸቱ በስተጀርባ የማወ
ቅ የመረዳት ጉጉት ይታይበታል ። በስድብ መልክ
ቃላቶቹ የሚቀርቡ ቢሆኑም ስድቡ የሚቀርበው ከፍ
ርሃት የተነሳ መሆኑ ያስታውቅ ነበር ። ቃላቶቹ የሚቀ
ርቡት በአስተሳሰብ ጥልቀት ተመልተው ከሆነ ደግሞ

አስተሳሰቦቹ ተስፋ ያዘሉ እና ማስጠንቀቂያ በውስጣቸው ይዘው የሚገኙ ነበሩ ። ቀስ-በቀስ በዚህ በረጋ ጥቁር ውሃ ውስጥ ያለመረጋጋት ክበቦች እየሰፉ ይታዩ ጀመር ። በድን ሁነው ቆይተው የነበሩ አስተሳሰቦች መንቀሳቀስ የጀመሩ ሲሆን ፥ አሜን-አሜን ይሁን-ይሁን ተብሎ ተቀባይነት ያገኝ የነበረው የየዕለቱ ድርጊት ሁሉ ከመሠረቱ መናጋት ጀመረ ። የሕይወትን ከባድ ገጽታ የማወቅ ችሎታዋ ከፍተኛ በመሆኑ ከሌሎች ሰዎች ይበልጥ ይኸንን ግልጥ በሆነ ሁኔታ ትመለከታለች ። በአሁኑ ጊዜም ይኸ ሁኔታ በአስተሳሰብ እና ባለመርካት ቅርተኛነት ተደራርቦ በማየቷ በአንድ በኩል የተደሰተች ስትሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሥጉ ሁናለች ፡ — ተደሳች የመሆኗ ምክንያት በዚህ ጉዳይ ውስጥ የልጅዋ ድርጊት የሚገኝበት በመሆኑ ነው ። ሥጉ የመሆኗ ምክንያት ደግሞ ፤ ልጅዋ ከእሥር ቤት ቢያመልጥ የግንባር-ቀደምትነቱን ቦታ የሚይዝ በመሆኑ እና ይኸም ከፍተኛ የመደምሰስ አደጋን ሊያስከትልበት እንደሚችል ስለምታውቅ ነው ።

አንዳንድ ጊዜ የልጅዋ ምስል ከአሁን ቀደም ሰምታው የማታውቀው ባለታሪክ ሰው ታሪክ ፤ ከዚህ ቀደም በከፍተኛ ደረጃ ያደነቀቻቸው፡ ትላልቅ ሰዎች ከዚህ ቀደም ያወቀችውን ብሩኅ እና ጀግና ምስል ተመስሎ ይታያታል ። በዚህን ጊዜም በኩራት እና በርኅራኄ ልቧ የሚመላ ሲሆን በታላቅ ደስታም ታሰላስለዋለች ።

«ሁሉም ነገር ይሳካል!» በማለት ታስባለች ።

ይሁን እንጂ ፥ በውስጧ የሚገኘው የእናትነቷ ስሜት ታላቅ ሰብአዊነትን አዝሎ ብቅ በማለት ባላት ከፍተኛ ስሜት ላይ አሳዛኝ እና አስጊ የሆኑ አስተሳሰቦችን አዝላ ትገኛለች ።

«ይገድሉታል... ይገድሉታል!» በማለት ታሰላስላለች ።



# 14

አንድ ቀን ቀትር ላይ እሥር ቤቱ ቢሮ ውስጥ ከፓቬል ፊት-ለፊት ተቀምጣ የእንባ ጭጋግ በከበቧት ዐይኖቿ ያልተላጨ ጉንጩን እየተመለከተች በጣቶቿ ውስጥ ተጨረማምቶ የሚገኘውን የማስታወሻ ጽሁፍ ለመስጠት የምትችልበትን አጋጣሚ ትጠባበቅ ጀመረች ።

«እኔ ደህና ነኝ ። ሌሎቹም ደህና ናቸው!» አላት ረጋ ባለ አነጋገር ። «አንቺስ እንደምንድነሽ?» አላት ።

«ደህና ነኝ ። የጎር ኢቫኖቪች አረፈ!» በማለት ወዲያውኑ ፈጥና መለሰች ።

«እረ?» በማለት በሀዘን ጠየቀ ። ቀስ ብሎ አንገቱን ወደ መሬት ደፋ ።

«ፖሊሶች በቀብሩ ሥነ-ሥርአት ላይ ሰዎችን መደብደብ ጀምረው አንድ ሰው ይዘው አሠሩ!» በማለት እናት በቅንነት ንግግሯን ቀጠለች ። የእሥር ቤቱ ምክትል ሹም ምላሱን ወጣ እንደማድረግ አድርጎ ከተቀመጠበት አፈፍ ብሎ ብድግ አለ ።

«ይኸንን መሳይ ንግግር መነጋገር አይፈቀድም ። ይኸንን ማወቅ ያስፈልጋል! የፖለቲካ ጉዳይ አንስቶ ማውራት አይፈቀድም!» በማለት ተናገረ ።

እናትም ከተቀመጠችበት ብድግ አለች ።

«እኔ ያወራሁት ስለፖለቲካ ሳይሆን ስለድብድብ ነው» በማለት በይቅርታ አጠያየቅ መንፈስ ተናገረች ። ቀጠል አድርጋም «በእርግጥም ደግሞ ተደባድበዋል ። እንደውም የአንድ ልጅ ጭንቅላት ፈንክተዋል...» አለች ።

«ምንም ሆነ ምን ያው ነው ። ይኸንን ጉዳይ እንደገና አንስተው እንዳያወሩ አጠይቅዎታለሁ ። ይኸም ማለት ፥ እርስዎን በግል የማያገባዎትን ጉዳይ

እንስተው አይነጋገሩ ማለት ነው ። ማለትም ቤተሰቦችዎን ፣ ቤትዎን ፣ እና የመሳሰሉትንም ነገር የማይመለከቱ ጉዳዮችን እንስተው አይነጋገሩ!» አለ ።

ነገር ማማታቱ ተሰማው እና ወደ መቀመጫው ሂዶ ከተቀመጠ በኋላ ወረቀቶች ያገላብጥ ጀመር ።

«በኋላ ለእንደዚህ ዓይነቱ ጉዳይ በኃላፊነት የምጠየቀው እኔ ነኝ...» በማለት በመጨነቅ ሁኔታ ጨመር አድርጎ ተናገረ ።

ዓይኖቿን ከእርሱ ላይ ሳትነቀል ቶሎ ብላ የማስታወሻ ወረቀቱን ለፓቬል ከሰጠች በኋላ እናት የእፎይታ ትንፋሿን ተነፈሰች ።

«ምን እንደምናገር አላውቅም...» በማለት እናት ተናገረች ።

«እኔም እንደአንቺው ነኝ...» በማለት ፓቬል እየሳቀ መለሰላት ።

«እንግዳው እዚህ መምጣት ፋይዳ የለውም» በማለት ምክትሉ ሹም በስጨት ብሎ ተናገረ ። ቀጠል አድርጎም «ምን እንደሚናገሩ አያውቁም ። ይሁን እንጂ እዚህ መምጣትዎ ደግሞ አይቀርም ። መጥተውም ደግሞ ሰውን ያውካሉ...» አለ ።

«ፍርዱ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ይሰማልን?» በማለት እናት ጠየቀች ።

«ከጥቂት ቀናት በፊት ሕግ-አስከባሪው መጥቶ ነበር ። በቅርቡ ቀን ፍርዱ ይሰማል ብሎአል...» በማለት ፓቬል መለሰ ።

ጥቂት አልባሌ የሆኑ ሃሣቦችን ተቀያየሩ ። ፓቬል በእፍቅሮት ሁኔታ የሚመለከታት መሆኑን ተገነዘበች ። ያው እንቀድሞው ረጋ ያለ እና የተደላደለ ባሕርዩን የያዘ ነበር ። እጆቹ ከመንጣታቸው በስተቀር እና ጺሙንም ካለመላጨቱ የተነሳ ሁኔታው ሽማግሌ ከማስመሰሉ በስተቀር አልተለወጠም ። አስደሳች የሆነ



ዜና ፡ — ስለ ኒኮላይ ፡ — ልትነግረው ፈለገች ። ቅንነት ባልተለየው ሁኔታ እስተያየቶቿን ታቀርብ እንደነበረው ሁሉ የሚከተለውን ንግግርም ተመሳሳይ በሆነ ድምፅ አቀረበች ፡ —

«ባለፈው ቀን የክርስትና ልጅህን አየሁት...» አለችው ።

ማንን እንደሆነ ለማወቅ ትክ ብሎ በዝምታ ዐይን-ዐይኖቿን ፓቬል ይመለከት ጀመር ። ቬሶቭሺኮቭን ማለቷ እንደሆነ እንዲረዳው ብላ የቬሶቭሺኮቭን ፈንጣጣ የጠቀጠቀውን ፊት ለማመልከት በጣቷ ፊቷን ጠቅ-ጠቅ እያደረገች አሳየችው ።

«ልጁ እየተሻሻለ ነው ። በቅርቡ ሥራ ያገኛል» አለችው ።

ልጅዋ ጉዳዩን ተገነዘበው ። ዐይኖቹ በደስታ ተመልተው ይስቁ ጀመር ።

«ጥሩ ነው!» አለ ።

«እሺ ፣ እንግዲህ ይኸው ነው» አለች በራሷም ተደስታ እና በልጅዋ መደሰትም ልቧ ተነክቶ ።

በመሰናበት መልክ እጅዋን አጥብቆ ጨበጥ አድርጎ ከያዘ በኋላ ፡ —

«እናት አመሠግናለሁኝ» አለ ።

የመቀራረባቸው አስደሳች ግንዛቤ እንደጠንካራ የወይን መጠጥ ከጭንቅላቷ ላይ ወጣ ። የምትመልስለት ቃላት በማጣቷ በዝምታ እጁን ያዝ አደረገችው ።

እቤት ስትመለስ ሳሻ እናትን ትጠብቃት ኖሮ አገኘቻት ። እናት ወደ እሥር ቤት በሄደችበት ቀን ሳሻም ከእናት ደህንነቱን ለመረዳት ትመጣለች ። ስለፓቬል አትጠይቅም ። እናት ስለፓቬል ሳታወራላት ከቀረችም የእናትን ዐይኖች ለረጅም ጊዜያት በመመልከት ጉጉቷን ትወጣለች ። አሁን ግን ጉጉት በተመላበት ሁኔታ ሳሻ እንደሚከተለው ጥያቄ አቀረበች ፡ —

«እንዴት ነው?»

«ደህና ነው!»

«የማስታወሻውን ወረቀት ሰጡትን?»

«አዎን ። እንዴት አድርጌ አሾልኬ እንዲደርሰው እንዳደረግሁኝ ባየሽ ኖሮ ጥሩ ነበር!»

«አነበበውን?»

«እዚያ? እንዴት አድርጎ?»

«ውይ! ዕውነት ነው ። ዘንግቼ ነው!» አለች ልጃገረዲቱ ቀስ ብላ ። ከዚያም ቀጠል አደረገች እና «ሌላ ሳምንት መጠበቅ አለብን ማለት ነው ። አንድ ሙሉ ሳምንት! እሺ ብሎ በጉዳዩ የሚስማማ ይመስልዎታልን?»

ሳሻ ኮስተር ብላ የእናትን መልስ በመጠበቅ እናትን ትመለከት ጀመር ።

«ይኸ ነው ብዬ መናገር አልችልም ። አደጋ የማያስከትል ጉዳይ ከሆነ ለምን አይስማማም?» በማለት እናት ቀስ ብላ ተናገረች ።

ሳሻ ራሷን ነቀነቀች ።

«በሽተኛው ምን መመገብ እንደተፈቀደለት ያውቃሉን? እርቦታል ።» አለች ።

«የሆነውን መመገብ ይችላል ። አንድ ጊዜ ቆይኝ እኔ...»

አለች እና ወደ ማዕድ ክፍል ሄደች ። ሳሻም ተከተለቻት ።

«ላግዝዎትን?»

«ኧረ ስለእግዚአብሔር ። ግዴለም!»

እናት ጎንበስ ብላ ከማብሰያው ውስጥ ድስት አወጣች ።

«ይቆዩ...» አለች ልጃገረዲቱ ፈጠን ብላ ።

በሚንቀጠቀጡ ከናፍሮቿ ስትናገር ፊቷ ገርጠት ብሎአል ፤ ዓይኖቿም በስሜት ተነክተው ቀልተዋል ።



«ልጠይቅዎት ፈልጌ የነበረው ፤ እሺ ብሎ በጉዳዩ እንደማይስማማ እርግጠኛ ነኝ ። በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲያነጋግሩት እማጸንዎታለሁኝ! በጣም ያስፈልገናል! ለቆምንበት ዓላማ የሚያስፈልገን በመሆኑ ምክንያት መሆኑን ይንገሩት! ለጤናው የምፈራለት መሆኔን ይንገሩት ። የፍርዱ ቀን እንኳን ገና ያልተወሰነ መሆኑን እርስዎ ራስዎም መገንዘብ ይችላሉ...» አለች ።

ይኸንን ከአንደበቷ እውጥታ ለመናገር መጣር አስፈልጓት እንደነበረ እርግጥ ነው ። አንደበቷ ተሳሰረ ። እዛው እቆመችበት ቀጥ ብላ በመገተር ቀረች ። ዐይኖቿን ዞር አደረገች ። እንደገና ዐይኖቿን በመጨፈን ከንፈሮቿን ትነክስ ጀመር ። የተጨበጡ ጣቶቿ ሲንቋቋ እናት ይሰማት ነበር ።

በዚህ ፍንዳታ ፔላጊያ የታወከች ስትሆን የሳሻን ሁኔታ የምትገነዘብ በመሆኗ እጆቿን ሳሻ ላይ ጣል አደረገች ።

«የኔ ውዲት ልጃገረድ! እርሱ እንደሆነ ያው ራሱ የሚናገረውን ካልሆነ በስተቀር ሌላ ማንንም እሺ ብሎ አያዳምጥም ። ማንንም እሺ አይልም!» አለች ።

እርስ በእርሳቸው ተጠጋግተው እና በዝምታ ታውከው ቆሙ ። ከዚያም ሳሻ ቀስ ብላ የእናትን እጅ ከላይዋ ላይ አወረደች ። ከዚያም ፡ —

«ልክ ነዎት!» በማለት ትከሻዋን ነቀነቀች ። ቀጥላም «ይኸ ሁሉ አባባል ሞኝነት ነው ። የነርቭ መነካት ነው...» አለች ።

ከዚያም ረጋ ባለ ሁኔታ ፡ —

«እሺ ይሁና ። ሕመምተኛችንን እንመግበው...» አለች ።

ኢቫን አጠገብ ተቀመጠች እና ራሱን ያመው እንደሆነ ጠየቀችው ።

«በጣም አይደለም ። ይሁን እንጂ ሁሉም ነገር

ይዞርብኛል ። ድካምም ይሰማኛል» በማለት በብስጭት የብርድ ልብሱን ወደ አገጩ እያስጠጋ እና መብራቱ በኃይል ይበራ ይመስል ዐይኖቹን ጭልምልም እያደረገ መለሰ ። እርሷ ባለችበት እንደልቡ ለመመገብ በጣም ዐይን-አፋር መሆኑን ሳሻ በመገንዘቧ ከተቀመጠችበት ተነስታ ሄደች ።

ኢቫን ቁጭ ካለ በኋላ በዐይኖቹ ይከተላት ጀመር ።

«እንዴት ያለ ውበት ነው ያላት!» በማለት አደነቀ ።

ደስ የሚያሰኙ ሰማያዊ ዐይኖች ፤ ክርክም ብለው የተስተካከሉ ጥርሶች እና ልውጥውጥ የሚል ድምፅ አለው ።

«ስንት አመትህ ነው?» በማለት እናት ጠየቀችው ።

«አሥራ ሰባት ።»

«ቤተሰቦችህ የት ናቸው?»

«ገጠር ናቸው ። የአሥር አመት ልጅ ከሆንኩኝ ጀምሮ እዚህ እኖራለሁኝ ። ትምህርት ቤት እንደጨረስኩኝ መጣሁኝ ። ጓዲት ፣ የእርስዎ ስም ማን ይባላል?» አላት ።

«ጓዲት» በማለት እናትን ሰዎች ሲጠሯት ምን ግዜም ትደሰታለች ፤ ልቧም ይነካል ።

«ለምን ለማወቅ ትሻለህ?» አለችው ፈገግ እያለች ።

«አዩ» አለ ጥቂት በማፈር ቆየት ካለ በኋላ ። ከዚያም ቀጠል አደረገ እና «እኛ ጥናት ክበብ ውስጥ ካሉት መካከል አንዱ ተማሪ ፣ ማለትም ከሚያስተምሩን መካከል አንዱ ስለ ወዝ-አደሩ ስለ ፓቬል ቭላሶቭ እናት ነግሮን ነበር ። የሜይ አንድ ቀን ሰላማዊ ሰልፍ ትዝ ይልዎታልን?» አላት ።

እናት ወዲያውኑ ነቃ በማለት አዎን በሚል ሁኔታ ራሷን ነቀነቀች ።



«አርማችንን በአደባባዩ በግንባር-ቀደምትነት ይዞ ይመራ የነበረው የመጀመርያው ሰው እርሱ ነበር!» በማለት ልጁ ኩራት በተመላው ሁኔታ ተናገረ ። ይኸ የእርሱ ኩራትም እናት ልብ ውስጥ ገብቶ አስተጋባ ።

«እኔ በዚያን ጊዜ እዚያ አልነበርኩኝም ። የራሳችንን ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ፈልገን ነበር ። ሳይሳካ ቀረ ። ጥቂቶች ነበርን ። ያያሉ ፣ በሚቀጥለው ዓመት ግን እናደርጋለን!» አለ ።

በስሜት ተውጦ ስለነበረ መተንፈስ እንኳን ተሳነው ።

«አሁን የምነጋገረው ስለቭላሶቭ እናት ብዬ ነው» በማለት ማንኪያውን እያነቃነቀ በሃሳቡ ደመደመ ። ቀጠል አድርጎም በሃሳቡ ፦ —

«ከዚያን ጊዜም በኋላ የቭላሶቭ እናት የፓርቲው አባል ሆኑ ማለት ነዋ ! እንደው ምን አለፉችሁ ፤ ግሩም ድንቅ የሆኑ ሴት ናቸው ይባላል!» በማለት አሰላሰለ ።

እናት በሰፊው ፈገግ አለች ። የልጁን የአድናቆት አነጋገር ማዳመጥ ለእርሷ አስደሳች ነበር ። አነጋገሩ አስደሳች እና አሳፋሪም ነበር ። «የቭላሶቭ እናት ማለት እኔ ነኝ» ብላ ልትነግረው ፈልጋ ነበር ። በዚህ ፈንታ ግን በምጸት አስተሳሰብ «ጅላጅል አሮጊት ነሽ ። ሌላ ምንድነኝ ልትይ ነው?» በሚል ሁኔታ አሰላሰለች ።

«ትንሽ ልጨምርልህ እና ብላ ። ለቆምንበት ዓላማ ስትል ቶሎ መዳን አለብህ!» በማለት መንፈሷ ተቀስቅሶ ዝግ ባለ ሁኔታ ተናገረች ።

የመንገዱ በር በመከፈት የበልጉን ወራት ቀዝቃዛ አየር ወደውስጥ አመጣው ። እናትም ሶፍያን አምራ እና አሽብርቃ ቆማ ተመለከተቻት ።

«ዕውነቱን ነው እኮ የምልዎት ። ሰላዮቹ እኔን በመከታተል የአንድ የታወቀ የሀብታም ሚስት እመስል ሊያሸኮረምሙኝ ያጅቡኛል ። በጊዜ ወደሌላ ቦታ መሄዱ ሳይሻል አይቀርም… እሺ ፡ ኢቫን ፣ ታዲያስ እንዴት ነህ? ተሻለህ? ኒሎቨና ፡ ከፓቬል ዘንድ ምን አዲስ ወሬ አለ? ሳሻ አለች እንዴ እዚህ?» አለች ሶፍያ ።

አንዳችም መልስ የማትጠብቅላቸው ጥያቄዎቿን እያቀረበች እና ሲጋራዋን እያቀጣጠለች በፍቅር መንፈስ እናትን እና ልጇን ትመለከታለች ። እናት እርሷን-እርሷን እየተመለከተች ፈገግ ትላለች ።

«እንደነዚያ ጥሩ ሰዎች እኔውም እየተቆጠርኩኝ ነኝ!» በማለት አሰላሰለች ።

አሁንም እንደገና ወደ ኢቫን ጎንበስ ብላ ተመለከተች ።

«ልጄ ቶሎ ፈጥነህ ዳን!» አለችው ።

ከዚያም ሶፍያ ከሳሻ ጋር ሁና ወደምታወራበት ወደ ምግቡ ቤት ሄደች ።

«ገና ከአሁኑ ሦስት መቶ ኮፒዎች አዘጋጅታለች ። በዚህ ሁኔታ ራሷን ትገድላለች ማለት ነው ። እንደው በአጭሩ ለመግለጥ የዐርበኛነት ተግባር ነው! ሳሻ ፣ እነዚህን በመሳሰሉት ሰዎች መካከል ተገኝቶ መኖር ፣ ጓዳቸው መሆን አብሮ ከእነርሱ ጋር መሥራት እንደምን መታደል ነው!» አለች ።

«እንዴታ መታደል ነው!» በማለት ልጃገረዲቱ መለሰች ።

ያንን ምሽት ሻይ በሚጠጡበት ጊዜ ሶፍያ ወደ እናት ዞር አለች እና ፡ —

«ኒሎቨና ገጠር እንደገና መሄድ ሊኖርብዎ ነው» አለቻት ።

«በጣም ጥሩ ። መቼ?» አለች እናት ።



«በሦስት ቀናት ውስጥ ለመሄድ የሚችሉ ይመስልዎታልን?» አለቻት ።

«እችላለሁኝ…»

«በአሁኑ ጊዜ ፈረስ ተከራይተው በሌላ መንገድ ፣ በኒኮልስኮዬ መንደር በኩል ማለፍ አለብዎት» በማለት ኒኮላይ ተናገረ ። ለእርሱ ባሕርይ በማይገባ ሁኔታ ኮስተር ብሎ እና ፊቱንም ጨፍገግ ብሎት ክፍቶት ነበር ። የወትሮውን የእርሱን የተረጋጋ የመንፈስ ፀጥታ ይኸ ገጽታው አበላሽቶበታል ።

«በኒኮልስኮዬ መንደር በኩል መንገዱ ረዥም ነው ። ፈረሶች መከራየት ደግሞ…» ብላ እናት ስትናገር ፣ ኒኮላይ ቀበል በማድረግ ፡ —

«ዕውነቱን ለመናገር ከሆነ ይኸንን የአሁኑን ጉዞ እኔ የምቃወም ነኝ ። እዚያ ሁኔታዎች በአሁኑ ጊዜ ጥሩ አይደሉም ። ሰዎች ተይዘው ታሥረዋል ። አንድ አስተማሪ ይዘው ያሠሩ ይመስለኛል ። ብዙ መጠንቀቅ አለብን ። ጊዜያችንን እየተመለከትን ብንራመድ የተሻለ አይሆንምን?» አለ ።

«ምን ጊዜም ሥነ-ጽሑፎችን ለእነርሱ ማቅረብ አለብን» በማለት ሶፍያ በሃሣብ ተውጣ ጠረጴዛውን በጣቶቿ ኳ-ኳ-ኳ እያደረገች ተናገረች ። ከዚያም «ኒሎቨና ፡ መሄድ ይፈራሉን?» በማለት ድንገት እናትን ጠየቀቻት ።

እናት ቅር ተሰኘች ።

«ከዚህ ቀደም ፈርቼ አውቃለሁኝን? መጀመርያ ጊዜ ስሄድም አልፈራሁኝም ። አሁን አንቺ ይኸንን ለምን…» ካለች በኋላ ዐረፍተ ነገሩን ሳትጨርስ ጭንቅላቷን ወደመሬት ቀለስ አደረገች ። ትፈራ እንደሆን ወይንም ግድ የላት እንደሆን በተጠየቀች ቁጥር ወይንም ይኸንን-ይኸንን የመሰለ ጉዳይ ለማድረግ ትችል እንደሆነ ስትጠየቅ አንድ በጎ ነገር ፈጽሚ

ልን ብለው የሚጠይቋት መስሎ ስለሚሰማት እና
እነርሱ እርስ-በእርሳቸው እንደሚያከናውኑአቸው ተግባ
ራት እርሷን እንደነርሱ አድርገው የሚቆጥሩዋት
ስለማይመስላት ቅር ትሰኛለች ።

«ፈርተሻል ወይ ብለሽ አንቺ ለምን ትጠይቂኛ
ለሽ?» በማለት እናት ሶፍያን ድምፅዋ እየተናነቃት
ጠየቀቻት ። ከዚያም ቀጠል አደረገች እና«እናንት ስት
ሆኑ ግን ይኸንን የመሰለውን ጥያቄ እርስ-በእርሳችሁ
አትጠያየቁም» አለች ።

ኒኮላይ መነጽሩን በማውለቅ እህቱን አትኩሮ ከተ
መለከተ በኋላ መነጽሩን መልሶ አደረገ ። በቤቱ ውስ
ጥ የሰፈነውን ዝምታ ለመቋቋም ባለመቻል እናት
የጥፋተኛነት ቅሬታ ተሰምቷት ከተቀመጠችበት ብድ
ግ ብላ አንድ ነገር ለመናገር ፈለገች ። ይሁን እንጂ
ሶፍያ እጅዋን በመያዝ ገታቻት ።

«ይቅርታ ያድርጉልኝ! ሁለተኛ ይኸንን አልደግ
ምም!» በማለት ለስለስ አድርጋ ሶፍያ ተናገረች ።

ይህ አነጋገር እናትን ፈገግ እንድትል አደረጋት ።
ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም ሦስቱም በሃሣብ ተመስ
ጠው ስለጉዞው ሁኔታ ይወያዩ ጀመር ።

15

ጧት ማለዳ እናት በፖስታ ማመላለሻ የፈረስ
ሠረገላ ላይ ተቀምጣ በበልግ ዝናብ በታጠበው መን
ገድ ላይ እየተናጠች-እየተወዘወዘች ትጓዝ ጀመር ።
ጠንከር ያለ ነፋስ ይነፍሳል ። ጭቃው በየሥፍራው
ይረጫል ። ሠረገላ ነጂው ከመቀመጫው ዞር ብሎ
ነፍነፍ ባለ አነጋገሩ ቅሬታውን እንዲህ ሲል ይገል
ጽላት ጀመር ፡—

«እና ይኸውልዎ እንዲህ አልኩት ወንድሜን ።



እንካፈል አልኩት ። እና ስለዚህ መካፈል ጀመርን
እልዎታለሁ...»

በግራ በኩል ሠረገላውን የሚጎትተውን የተጫነ
ፈረሱን ፡—

«ሂድ ብየሃለሁ! መጋኛ! ሠይጣን ይሂድብህና!»
በማለት በቁጣ እየተናገረው በያዘው አለንጋ ይገር
ፈው ጀመር ።

ቀዝቃዛው ነፋስ በምድሪቱ ላይ ዙርያውን ሲያ
ፏጭ የበልጉ ወራት ወፋፍራም ቁራዎች የተተለመ
ውን ገላጣ የእርሻ መሬት ይሁነኝ ብለው ይረማ
መዱታል ። ላባዎቻቸውን ከላያቸው ላይ እየነጩ ከእ
ግሮቻቸው ሥር የሚጥለውን እና የጎድን እንደሰነፍ
የሚያጋድላቸውን የነፋሱን ግርፊያ ለመቋቋም ቁራዎቹ
ጎን-ጎናቸውን ለነፋሱ ሰጥተዋል ።

«እና ይኸውልዎ በዚህ ምክንያት የኔን ድርሻ
ይገፈኛል ። ምንም ለእኔ እንዳልቀረኝ እያለሁኝ» ይላል ።

እናት ንግግሩን ልክ ሕልም የምታይ እየመሰላት
ታደምጣለች ። በትውስቷ ከጥቂት ዓመታት ጀምሮ
የሚካሄዱት እና እርሷ እራሷም የምትሳተፍባቸው
ድርጊቶች ድቅን እያሉ ይታውሱዋት ጀመር ። ቀደም
ሲል ሕይወት እንደው በሰፊው በሩቁ የተዘረጋች
ስትሆን ይኸች ሕይወትም በማን እና ለምን ዓላማ
እንደቆመች የሚገነዘብ አልነበረም ። አሁን ግን አብዛ
ኛዎቹን እነዚህን ሁኔታዎች በዓይኗ እያየች እና እር
ሷ ራሷም እየተሳተፈችባቸው በመቀየር ላይ ናቸው ።
ምንም እንኳን እርሷ ባላት ኃይል የማትተማመን
ብትሆንም ሁኔታው እንድትደሰት አድርጎአታል ። ግራ
የተጋባች ከመሆኗም በስተቀር በቅሬታ ተመልታለች ።

ሁሉም ነገር ዝግ እያለ የሚንቀሳቀስ ይመስላታል ።
ሰማዩ ላይ እንደባዘቶ ጥጥ የተከመሩት ጥቋቁር ደ
መናዎች እርስ-በእርሳቸው ጎምለል-ጎምለል እያሉ

በዝግታ ይተላለፋሉ ። በመንገዱ ግራና ቀኝ የሚገኙት
ርጥብ ዛፎች ቅጠል-አልባ ቅርንጫፎቻቸውን ሰላምታ
የሚሰጡ አስመስለው በዝግታ ያወዛውዛሉ ። ሜዳማ
የነበሩት የእርሻ ቦታዎች በአቀበት ተተኩ ። እነዚህ
አቀበቶችም በተራቸው ተወገዱ ።

የባለሠረገላው ነፍናፋ ድምፅ ፤ ፈረሶቹ ላይ የሚንቃ
ጨሉት ቃጭሎች ፤ የቀዝቃዛው ነፋስ ፉጨት በአንድ
ነት ተደባልቀው በምድሪቱ ላይ አንድ ዓይነት
የሚነዝር ድምፅ ያሰማሉ ።

«ገነትም ብትሆን ለሀብታም አትበቃውም!» አለ
ባለሠረገላው ከተቀመጠበት ዞር እያለ ። ቀጠል አድርጎ
ም «ይኸዋ ምናለ ፤ ባለሥልጣኖቹ እንደሆኑ ጓደኞቹ
ናቸው ።»

ጣቢያ ላይ ሲደርሱ ፈረሶቹን ከጭነታቸው ፈትቶ
አናፈሳቸው ።

«አምስት ኮፔክ ለመጠጫ ቢሰጡኝ!» አላት እና
ትን በሚያሳዝን አኳኋን ።

ኮፔኩን ሰጠችው ። እርሱም በእጁ የኮፔኩን መሃ
ለቅ ዱብ-ዱብ እያደረገ ፦ —

«ሦስቱ ኮፔክ ለቮድካ ፥ ሁለቱ ደግሞ ለዳቦ ነ
ው...» አላት ።

ከሰአት በኋላ እናት በርዶአት እና ድክም ብሎ
አት ኒኮልስኮዬ ከተሰኘችው ትልቅ መንደር ደረሰች ።
አንድ ብርጭቆ ሻይ ለመጠጣት ወደጣቢያው ከሄ
ደች በኋላ ከባድ ሻንጣዋን አግዳሚ ወንበር ሥር
አስቀምጣ መስኮት አጠገብ ሻይዋን ይዛ ተቀመጠች ።
አንድ አነስተኛ የሆነ ሜዳ በቢጫማ ሣር ተውጦ
እና እንደዚሁም የከተማው አስተዳደር ጽሕፈት ቤት
የሆነው አንድ ጠቆር ያለ ግራጫማ ሕንፃ በስተመስ
ኮቱ በኩል ባሻገር ይታያታል ። በረንዳው ላይ እራሰ
መላጣ እና ጢማም የሆነ ሰው ፒፓ እያጨሰ ኮት



ሳይለብስ በሸሚዝ ብቻ ተቀምጦአል ። ሜዳው ላይ
አሳማ ይግጣል ። ያልተመቸው መስሎ ጆሮዎቹን ቅሥ
ር አድርጎአቸዋል ። ራሱን የሚነቀንቅ ሲሆን አፉንም
ከመሬቱ ጋር ቀርቅቦታል ።

ደመናዎቹ ጠቁረው እና በትልቁ ተከማችተው
ይጓዛሉ ። ሕይወት ለጊዜው ወደሌላ ቦታ ወጣ ያለች
ይመስል ሁሉም ነገር ጭጭ-ምጭጭ ፤ ጭልም-ጭልምል
ም ፤ ስልችት-ስልችትችት ብሎአል ።

ድንገት አንድ የፖሊስ ሳጂን ሜጀር በሜዳው
በኩል በፈረሱ እየጋለበ መጣ እና ወደ ቀበሌው
መሥሪያ ቤት ፊት-ለፊት ፈረሱን አቆመ ። የያዘውን
አለንጋ አየር ላይ እየቆጋ መላጣው እና ጢማሙ
ሰውየ ላይ ይጮኸበታል ። ድምፁ በስተመስኮቱ
በኩል መስኮቱን ሲነዝር ይሰማል ። ምን እንደሚነ
ጋገር ግን አይሰማም ። ሰውየው ከመቀመጫው ብድግ
ብሎ በርቀት ያመለክት ጀመር ። ሳጂን ሜጀሩ ከፈረሱ
ላይ ወረደ ። ልጓሙን ለሰውየው ሰጥቶ በረንዳውን
ከተወጣጣ በኋላ በበሩ ውስጥ ወደክፍሉ ገባ ።

እንደገና ሁሉም ነገር ጭጭ አለ ። ሁለት ጊዜ
ፈረሱ ለስላሳው መሬት ላይ ፉር-ፉር እያለ አናፋ ።
ቢጫማ ቀለም ያለውን ፀጉሯን በወርቀ ዘቦ በተጠ
ለፈ ሻሽ ሸብ ያደረገች ዐይኖቿ የሚለሳለሱ እና
ፊተ-ክብ የሆነች አንዲት ገና ለአቅመ-ሄዋን ሙሉ
በሙሉ ያልበቃች ልጃገረድ ከበስተበሩ በኩል ሳህኖች
የተመሉበት የዕቃ መያዣ ቋ-ቋ-ቋ እያለ ይዛ
ከንፈሯን እየነከሰች እና ራሷን እየነቀነቀች መ
ጣች ።

«ጤና ይስጥልኝ የኔ ውድ!» አለቻት ፡ እናት ።

«ጤና ይስጥልኝ!» አለች ልጃገረዲቱ ።

የሻይ እቃዎቹን ጠረጴዛ ላይ እንዳስቀመጠች ልጃ
ገረዲቱ በስሜት ተውጣ የሚከተለውን ተናገረች ፦ —

«አሁን አንድ ዘራፊ ያዙ ። እዚህ ሊያመጡት ነው!» አለች ።

«ማነው?»

«እኔ እንጃ…»

«ማንን ዘረፈ?»

«እኔ እንጃ…» በማለት ልጃገረዲቱ ደግማ ተናገረች ። ቀጠል አድርጋም «የያዙት መሆናቸውን ብቻ ነው የሰማሁት ። ዘበኛው የፖሊሱን አዛዥ ሊጠራ ሂዶአል ።»

እናት በስተመስኮቱ በኩል ተመለከተች ። ሜዳው ላይ ገበሬዎች ተሰብስበዋል ። አንዳንዶቹ ቆርሰስ እያሉ በመጨመት የሚጓዙ ሲሆን ፣ ሌሎቹ ደግሞ ከበግ ቆዳ የተሠራ ካፖርታቸውን ቁልፍ እየቆለፉ በመቻኮል ይሄዳሉ ። ከሕንፃው ፊት-ለፊት ከተሰበሰቡ በኋላ ወደ ግራ በኩል እየተመለከቱ ቆሙ ።

ልጃገረዲቱም በስተመስኮቱ በኩል ከተመለከተች በኋላ በሩን ከበስተኋላዋ ዘግታ እየሮጠች ወደውጪ ወጣች ። እናት በሚሰማው ድምፅ ሸክ ገባች እና ሻንጣዋን ወደ አግዳሚው ወንበር ውስጥ ገፋ አድርጋ በማስገባት ሻሿን ሸብ አድርጋ ካሠረች በኋላ በዝግጁ ሁኔታ ለመሮጥ ተዘጋጂ ተዘጋጂ የሚላትን ሃሣብ እየተቋቋመች ከበስተበራፉ በኩል ቆመች ።

በረንዳው ዘንድ ስትደርስ ድንገተኛ መብረቅ ዐይኖቿን እና ልቧን የመታት ያህል ተሰማት ። ትንፋሿን ለመተንፈስ እየተጣጣረች ሳለ እግሮቿን ብርክ ያዛቸው ። ከበስተሜዳው በኩል ሪቢን እጆቹን ታሥሮ ግራና ቀኝ ፖሊሶች አጅበውት በያዙት ዱላ መሬቱን ቸብቸብ እያደረጉ ይሄዳሉ ። የተሰበሰቡት ሰዎች በፀጥታ ከበረንዳው አጠገብ ሁነው ይጠባበቃሉ ።

እናት ክው ብላ በመደንገጧ ከወዲያ-ወዲህ መመልከት ባለመቻሏ አንድ ቦታ ላይ ትክ ብላ ትመለከት



ጀመር ። ሪቢን አንዳች ነገር ይናገራል ። እርሷ ግን ምንም እንኳን ድምፁን የምታዳምጥ ብትሆንም ልቧ ባዶ ሁኖ በመጨለሙ የሚናገረውን መዝግቦ መቀበል አልቻለም ።

ደህና አድርጋ ትንፋሿን ከዋጠች በኋላ ራሷን ተቆጣጥራ መግራት ጀመረች ። በረንዳው አጠገብ አንድ ዐይነ ሰማያዊ የሆነ ሰፋ ያለ ጺም ያለው ሰው እርሷን-እርሷን ትክ ብሎ ይመለከታታል ። ሳሏን ከሳለች በኋላ ከፍርሃቷ የተነሳ በዛሉት እጆቿ ጉሮሮዋን ታሻሽ ጀመር ።

«ምንድነው ጉዳዩ?» በማለት እንደምንም ተበረታትታ ጠየቀች ።

«ራስዎ ይመልከቱት!» በማለት ተናገረ እና ዞር ብሎ ሄደ ። ሌላ ሰው መጣ እና አጠገቧ ቆመ ።

ምንም እንኳን ሰዎቹ በዝምታ የተዋጡ ቢሆኑም ቁጥራቸው ከጊዜ-ጊዜ እየጨመረ የሚዘልቅ ሲሆን አንድ ሪቢንን ፊት-ፊት ቀድሞ የሚመራ ፖሊስ ከተሰበሰበው ሕዝብ ፊት ቆመ ። ድንገት የሪቢን ድምፅ ከሰዎቹ ጭንቅላት በላይ ይሰማ ጀመር ።

«ዕውነተኛ የሆናችሁ አማኞች ሆይ! ስለ እኛ ስለገበሬዎች ሀቁን የሚያወሱ ተበታኝ ጽሁፎች መኖራቸውን ሰምታችኋልን? ይኸው አሁን እኔ የተያዝኩት በእነዚያ ተበታኝ ጽሁፎች ምክንያት ነው ። እነዚያን ተበታኝ ጽሁፎች በሕዝቦች መካከል አሠራጭ የነበርኩት እኔ ነኝ!»

የተሰበሰቡት ሰዎች ወደ ሪቢን ተጠጉ ። ድምፁ መረበሽ የሌለበት እና ረጋ ያለ ነው ። ይኸ ሁኔታውም እናትን ረጋ ብላ ነፍሷ መለስ እንዲልላት አደረጋት ።

«ትሰማለህን?» አለው ሁለተኛው ሰው ባለሰማያዊ

ዐይኑን ሰው ጎንተል እያደረገው ። ሁለተኛው ሰው ራሱን ቀና አደረገ እና መልስ ሳይሰጥ እናትን ተመለከተ ። ሌላኛውም ሰው እናትን ተመለከተ ። ከመጀመርያው ሰውዬ ይልቅ ይኸኛው ወጣት ሲሆን እንደከሰል የጠቆረ ጢም እና ቆዳውም ላይ ጥቋቁር ነቁጦች አሉበት ። ከዚያም ሁለቱም ሄዱ ።

«ፈርተዋል!» በማለት እናት አሰበች ።

ይበልጥ ጥንቁቅ ትሆን ጀመር ። ከበረንዳው ላይ ሁና የሚኻኢሎ ኢቫኖቪችን ጠየም ያለ እና የተጨራመተ መልክ እንደዚሁም ብሩኅ ሁነው ቁልጭ-ቁልጭ የሚሉትን ዐይኖቹን ትመለከታለች ። እርሱም እንዲያስተውላት ፈለገች ። ስለዚህም በእግሯ ጣቶች ከተረከዟ ከፍ ብላ በመቆም አንገቷን ሰገግ አድርጋ መዘዘች ።

ሰዎቹ ዕምነት ባልጣሉበት በክፉ አመለካከት ሪቢንን ይመለከቱታል ። አንዳችም ነገር አይናገሩም ። ከሰዎቹ በስተጀርባ በኩል ብቻ የሹክሹክታ ንግግር ይሰማል ።

«ገበሬዎች ሆይ!» አለ ሪቢን በስጨት እና ጎላ ባለ ድምፅ «በእነዚያ ወረቀቶች ላይ የተጻፉትን እመኑ ። እና ምናልባትም እነዚያ ወረቀቶች ለያዙት ሃሣብ ሕይወቴን እከፍል ይሆናል ። እነዚያን ወረቀቶች ከየት እንዳገኘኋቸው ለማወቅ ሲሉ ደበደቡኝ ። አሰቃዩኝ ። እንደገናም ይደበድቡኛል ። በእነዚያ ወረቀቶች ላይ የሠፈሩት ሃሣቦች ዕውነት በመሆናቸው እና ዕውነት ደግሞ ከዕለት እንጀራችን የበለጠ ውድ ዋጋ ሊሰጠው ስለሚገባ ማናቸውንም ሙከራ በቆራጥነት ለመቋቋም ዝግጁ ነኝ ። ይኸ ነው!» በማለት ተናገረ ።

«ይኸንን ለምን ይናገራል?» በማለት በረንዳው አጠገብ የቆመ አንድ ሰው ተናገረ ።



«ተናገረ አልተናገረ ለርሱ ከእንግዲህ ሁሉም ነገር ለውጥ የማያመጣ ያው ስለሆነ ነው ። አንድ ሰው የሚሞተው አንድ ጊዜ ብቻ ነው…» በማለት ሰማያዊ ቀለም ዐይኖች ያሉት ሰው ተናገረ ።

የተሰበሰቡት ሰዎች አሁንም አንዳችም ቃል ሳይተነፍሱ ሪቢንን እየተመለከቱ ቆመዋል ። እንደው አንዳች ውጪያዊ ኃይል በላያቸው ላይ መጥቶ የተጫናቸው ይመስል ተደብተዋል ።

የፖሊሱ ሳጂን ሜጀር እየተውተረተረ ወደበረንዳው መጣ ።

«ማነው እዚህ የሚያወራው?» በማለት በሰካራም አነጋገር ጠየቀ ።

ድንገት ደረጃውን ወረድ እንደማለት ብሎ የሪቢንን ፀጉር ጨምድዶ ጎተተው ።

«አንተ ነህ የምታወራው! አንተ የውሻ ልጅ!» እያለ ጮኸበት ።

የተሰበሰበው ሰው አፈገፈገ ። ያጉረመርምም ጀመር ። እናት ታደርገውን አጥታ በማዘን አንገቷን ወደታች ቀልበስ አደረገች ። እንደገና የሪቢን ድምፅ ከፍ ብሎ ተሰማ ።

«ተመልከቱ ፤ የተወደዳችሁ ሕዝቦች!…» አለ ሪቢን ።

«ዝም በል!» በማለት ሳጂን ሜጀሩ ጆሮ ግንዱ ላይ መታው ። ሪቢን ወዝወዝ ብሎ ትከሻዎቹን ነቀነቀ ።

«የሰውን እጅ እንደዚህ ሸምቅቀው እያሠሩ ያሻቸውን ይፈጽማሉ…» በማለት ሪቢን ተናገረ ።

«ፖሊሶች! ውሰዱት ከዚህ! እናንተ እዚህ የተሰበሰባችሁትም ሰዎች በሉ እኮ ወደየቤታችሁ ሂዱ!» እያለ ሳጂን ሜጀሩ ልክ አጥንት እንደሚግጥ ውሻ ሪቢን ላይ እየተረባረበበት አንዴ ጆሮ ግንዱን ፤ አን

ጆም ደረቱን ፤ አንጆም ሆድ ሆዱን በቡጢ ይመታዋል ።

«ድብደባህን አቁም!» በማለት ከተሰበሰቡት መካከል አንዱ በከፍተኛ ድምፅ ተናገረ ።

«ለምን ትደበድበዋለህ?» የሚል ሌላ ድምፅ የመጀመርያውን ተናገሪ በመደገፍ ሲናገር ተሰማ ።

«እንሂድ» አለ ሰማያዊ ቀለም ዐይኖች ያሉት ሰው ጭንቅላቱን ወዝወዝ እያደረገ ። ሁለቱም መዘዝ ብለው ሄዱ ። የእናት የደግነት ዓይኖቿ ተከተሏቸው ። የፖሊሱ ሳጂን ሜጀር ልፍስፍስ በሆነ ሁኔታ የበረንዳውን ደረጃ ሲወጣጣ እናት የእፎይታ ትንፋሽ ተነፈሰች ።

«እምጡት ወደዚህ! አሳየዋለሁኝ!» እያለ እጁን በመወዝወዝ ሳጂን ሜጀሩ ያጓራ ጀመር ።

«ተው አይሆንም!» የሚል ጠንከር ያለ ድምፅ ከተሰበሰቡት መካከል አንዱ አሰማ ። ሰማያዊ ዐይኖች ያሉት ሰው ሳይሆን አይቀርም የተናገረው በማለት እናት ገመተች ። ቀጠል አድርጎም «ወገኖች ሆይ! እነዚህ ፖሊሶች ይኸንን ሰው ይዘውት እንዲሄዱ አታድርጉ ። ይዘውት ከሄዱ ቀጥቅጠው ይገድሉታል ። ከዚያም በኋላ እኛን እናንተ ናችሁ ብለው ያሳብቡብናል ። ስለዚህም ይዘውት እንዲሄዱ አትፍቀዱላቸው!» አለ ።

«ገበሬዎች ሆይ!» አለ እንደገና ሪቢን «እንደምን የመሰለ አኗኗር እንደምትኖሩ አትመለከቱምን? እንደምን እንደሚዘርፉአችሁ ፤ እንዴት እንደሚያታልሉዋችሁ ፤ እንዴት ደማችሁን እንደሚመጥጡ አትመለከቱምን? ሁሉንም ነገር አስገኚዎች እናንተ ናችሁ ። በዓለም ላይ ወደር የማይገኝላችሁ ኃይሎች እናንተ ናችሁ ። ነገር ግን ምን መብት አላችሁ? እናንተ ያላችሁ መብት በችጋር እየተቆላችሁ ማለቅ ብቻ ነው!»



በማለት ተናገረ ።

ከዚያም ድንገት ገበሬዎቹ እርስ-በእርሳቸው አንዱ ሌላውን እየተቀባበለው በከፍተኛ ድምፅ ይናገሩ ጀመር ፡ —

«እኚህ ሰው የሚናገሩት ሀቁን ነው!»

«ጥሩት የፖሊሱን አዛዥ! የት ነው የፖሊሱ አዛዥ ያለው?»

«የፖሊሱ ሳጂን ሊጠራው ሂዶአል…»

«የቱ? ያ ሰካራም?»

«ባለሥልጣኖችን መጥራት የእኛ ጉዳይ አይደለም…»

ጩኸቱ ተበራከተ ።

«ተናገር! አንድም የሚነካህ አይኖርም!»

«እጁን ፍቱለት!»

«አየህ ፣ የሚይዝህ የለም!»

«የታሠርኩበት ገመድ እጆቼን እየገዘገዙት ናቸው!» በማለት የሌሎቹን ድምፅ ጥልቀት ባለው ድምፁ ውጦ ሪቢን ተናገረ ።

«ሰዎች ሆይ! አልሸሽም! ከእውነት ሸሽቼ አልጠፋም! ዕውነት እኔው ውስጥ ትገኛለች!» በማለት ሪቢን ተናገረ ።

ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል ጥቂቶቹ ፈንጠር ብለው በመውጣት ራሳቸውን እየነቀነቁ ሃሣብ ለሃሣብ ይለዋወጣሉ ። ይሁን እንጂ የታረዙ ሰዎች ቁጥራቸው ከጊዜ-ጊዜ እየጨመረ በመብዛት በስሜት ተውጠው ይሰበሰቡ ጀመር ። እጁን ከጭንቅላቱ በላይ እያወዛወዘ እንደ መለሎ ዛፍ ምዝዝ ብሎ የወጣ የሚመስለው ሪቢን ንግግሩን ቀጠለ ፡ —

«አመሰግናለሁኝ! ደጋግ ሰዎች አመሰግናችኋለሁኝ! እኛ እርስ-በእርሳችን ተባብረን ትከሻ-ለትከሻ ካልገጠምን ማን ይተባበርልናል?» አለ ።

ጢሙን ጠራረገ እና በደም የተለወሰውን እጁን ከፍ እያደረገ በማወዛወዝ ፡ —

«ለዕውነት ሲል የተዘራው ደሜ ይኽውላችሁ!» አለ ።

እናት በረንዳውን ወርዳ ወደተሰበሰበው ሕዝብ ሄደች ። ሚኻኢሎን ለማየት ባለመቻሏ ግን እንደገና ወደ በረንዳው ላይ ወጣች ። ልቧ ውስጥ ልትገልጠው የማትችለው ደስታ ተሠራጨባት ።

«ገበሬዎች ሆይ! እነዚያን የሚበትኑ ወረቀቶች እየተጠባበቃችሁ ስታገኙ አንብቡአቸው! ጨካኝ አረመኔዎችን እና ዘራፊዎችን የሀቅ አዋጅ ነጋሪዎች ናቸው እያሉ ቀሳውስት እና ባለሥልጣኖች ሲሰብኳችሁ አትመኑዋቸው! በሕዝቦች ልቦና ውስጥ ጎጀዋን ለመቀለስ ዕውነት በሕቡዕ በምድሪቱ ውስጥ-ለውስጥ በስውር እየዞረች ነች ። ባለሥልጣኖችን የምትለበልብ እሳት እና የምትቆራርጥ ሰይፍ እንደማለት ነች ። ሊበቀሏት አይችሉም ። ትቆራርጣቸዋለች ። ምድምድ አድርጋ ታነዳቸዋለች! ለእናንተ ዕውነት ጥሩ ጓደኛችሁ ነች! ለእነርሱ መራራ ጠላታቸው ነች! በዚህም ምክንያት ነው ውስጥ-ለውስጥ በስውር የምትጓዘው!» በማለት ተናገረ ።

አሁንም እንደገና የተሰበሰቡት ሰዎች አንክሮ የተመላባቸው አስተያየቶች ያወርዱ ጀመር ፡ —

«ዕውነተኛ አማኞች! እህ ብላችሁ አድምጡ!»

«ወንድም ሆይ መጨረሻህ አያምርም ...»

«ማነው ለፖሊስ አሳልፎ የሰጠህ?»

«ቄሱ ነው!» በማለት ከፖሊሶቹ መካከል አንዱ ተናገረ ።

ሁለቱ ገበሬዎች ከፉኛ ተባደቡ ።

«ወገኖች ፥ ተጠንቀቁ!» የሚል ማስጠንቀቂያ ከአንድ ሰው ድምፅ ተሰማ ።



## 16

የፖሊሱ አዛዥ ወደ ተሰበሰቡት ሰዎች ዘንድ መጣ ። ቁመተ-ረዥምም እና ፊተ-ሞላላ የሆነ ሰውነተ-ግዙፍ ሰው ነው ። መለዮውን ከወደ አንድ በኩል ዘመም አድርጎ ያጠለቀ ሲሆን ከንፈሩ ላይ ያለው ሪዝ ካንድ በኩል ወደላይ ፥ ከሌላ በኩል ደግሞ ወደታች ከፍ እና ዝቅ ያለ በመሆኑ ፥ ፊቱ እስከለመ ይቴውም ደስታ ቢስ የሆነ ፈገግታ ፈገግ የሚል ይመስላል ። በግራ እጁ ሰይፍ ይዞአል ። የቀኝ እጁን ደግሞ ኃይል በተመላበት ሁኔታ ያወዛውዛል ። ጠንከር እና ጎላ ያለ አረማመዱን በማዳመጥ ወደእነርሱ የመቃረቡን ሁኔታ ሁሉም ተረዳው ። የተሰበሰበው ሰው እርሱን ለማሳለፍ ከሁለት ላይ ግምስምስ እያለ ሲከፈል ድምፁ ጉድጓድ ውስጥ የሚጠልቅ ውሀ ይመስል ነበር ። በቦታው ያለው ሰው ሁሉ ፊቱ ተኮሳተረ ። እናት ዐይኖቿ የሚቃጠሉ እና ግንባርዋም የሚርገበገብ መሰሎ ተሰማት ። አሁንም እንደገና ወደ ተሰበሰበው ሕዝብ ለመቀላቀል ፈለገች ። ወደፊት ገፋ ብላ ከገባች በኋላ ሳትነቃነቅ አንድ ቦታ ላይ ቆመች ።

«ምንድነው ነገሩ?» አለ የፖሊሱ አዛዥ ሪቢንን በበላይነት ዐይን-ዐይኑን እየተመለከተው ። ቀጠል አድርጎም «ለምንድነው እጆቹ ያልታሠሩት? እሠሩት እኮ!» አለ ።

ድምፁ ጎርናና እና እንደመረዋ የሚጮህ ነው ። ነገር ግን ወዝ-የለሽ ደረቅ ድምፅ ነው ።

«እጆቹ ታሥረው ነበር ። ሕዝቦቹ ናቸው የፈቱት!» በማለት አንድ ፖሊስ መለሰ ።

«ምን አልክ? ሕዝቦች? የቶቹ ሕዝቦች?» አለ የፖሊሱ አዛዥ እየተቆጣ ።

ከእርሱ ፊት-ለፊት በግማሽ ክበብ የቆሙትን ሰዎች የፖሊሱ አዛዥ በዐይኖቹ እየገረፈ ይቃኛቸው ጀመር ። ከዚያም ፡ —

«የቶቹ ናቸው ለመሆኑ ፤ ሕዝቦቹ?» በማለት የድምፁን ደረጃ ጥቂትም ሳይለውጥ ተናገረ ።

ባለሰማያዊ ዐይኑን ሰው በሰይፉ ጫፍ ንጎጥ አደረገው ።

«እንደሚመስለኝ ሕዝብ የተሰኛችሁት እናንተ መሆናችሁ ነው መሰለኝ ፥ ቹማኮቹ? እሺ ፥ ደግሞ ሌላውስ ሕዝብ የተሰኘው ማን መሆኑ ነው ፥ ሚሺን አንተ መሆንህ ነው?» አለ ። ከሁለቱ አንደኛቸውን በቀኝ እጁ ጢሙን አፈፍ አድርጎ ወደላይ ሰቀሰቀው ። ከዚያም ቀጠል አደረገ እና ፡ —

«አሁን ከዚህ ድራሻችሁ ቢጠፉ ይሻላችኋል ። እናንት መድረሻ-ቢሶች ! ዋ! እምቢኝ ካላችሁ ደግሞ ዋጋችሁን ነው የምሰጣችሁ!» አለ ።

አነጋገሩ የቁጣ ወይንም የዛቻ አይደለም ። ረጋ ብሎ እየተናገረ እንደተለመደው በረዥም እጁ ሰዎቹን ይገፋፋል ። አንገታቸውን ወደመሬት ቀለስ አድርገው እና ፊታቸውንም ዞር-ዞር እያሉ ማፈግፈግ ጀመሩ ።

«እኮ ምንድነው የምትጠብቁት? እጆቹን አታሥሩም እንዴ! እሠሩ እኮ ነው የምላችሁ!» አላቸው ፖሊሶቹን ።

ጥቂት ከተሳደበ በኋላ ሪቢንን እንደገና ተመለከተው ። ከዚያም ፡ —

«አንተ ፥ እጅህን ወደኋላህ አድርግ!» አለው ።

«እጄን እንድታሥሩ አልሻም ። አልሸሽም ። አልደባደብም ። ለምንድነው እጄን የምታሥሩኝ?» አለ ሪቢን ።

«ምን አልክ? ምን አልክ?» አለው የፖሊሱ አዛዥ ጠጋ እያለው ።

ሪቢንም ድምፁን ከፍ አድርጎ «እናንት አረመኔ



ዎች ሕዝቦችን ማሠቃየት ብታቆሙ ይሻላችኋል ። እናንተም ተመሳሳዩን አጸፋ በቅርቡ ታገኙታላችሁ!» አለው ።

የፖሊሱ አዛዥ ሪዙ እየተንቀጠቀጠ የሪቢንን ፊት ይመለከት ጀመር ።

«አንተ የውሻ ልጅ! እንደዚህ ነዋ ንግግርህ!» እያለ የፖሊሱ አዛዥ በመገረም አንድ እርምጃ ወደኋላ አፈገፈገ ።

ከዚያም ሪቢንን ድንገት ፊቱ ላይ በቦክስ መታው ።

«በቡጢ በመምታት ዕውነትን መግደል አትችልም!» በማለት ሪቢን ወደፊት እየተጠጋው በጩኸት ድምፅ ተናገረ ። ቀጠል አድርጎም ፡—

«አንተ ቆሻሻ ውሻ እኔን ለመምታት መብት የለህም!» አለው ።

«እኔ መብት የለኝም? እኔ?» ብሎ ጮኸ የፖሊሱ አዛዥ ።

አሁንም እንደገና የሪቢንን ጭንቅላት በቦክስ ለመምታት እጁን ሠነዘረ ። ሪቢን ጎንበስ አለ ። ስለዚህም የፖሊሱ አዛዥ ሳይመታው ሳተው ። በዚህም አዛዡ ቁጣው ጋለ ። ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል አንደኛው ሳቀ ። አሁንም እንደገና የሪቢን የስድብ ድምፅ ይሰማ ጀመር

«እንዳትነካኝ ብዬሃለሁኝ ፥ አንተ ጋኔን!» አለው ።

የፖሊሱ አዛዥ ዙርያውን ሲቃኝ የተሰበሰቡት ሰዎች ጠጋ-ጠጋ እያሉ በመከበብ ላይ መሆናቸውን ተገነዘበ ።

«ኒኪታ! አንተን እኮ ነው ፤ ኒኪታ!» በማለት የፖሊሱ አዛዥ እየጮኸ ተጣራ ።

ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል አንድ ቁመተ-አጭር የሆነ እና የበግ ቆዳ የለበሰ ሰው ብቅ አለ ። ትልቅ ገመሞ ራሱን ወደ መሬት ጎንበስ አድርጎአል ።

«ኒኪታ!» አለ የፖሊሱ አዛዥ ረጋ ብሎ እሪዙን እየቋጨ ። «ጆሮ-ግንዱ ላይ ደህና አድርገህ በቦክስ በልልኝ!» አለው ።

ሰውየው ወደፊት ተራመደ ። ወደሪቢን ተጠጋ ። ከዚያም ቀና ብሎ ሪቢንን ተመለከተው ። ሪቢን እየተመለከተው ጠንከር ባሉ ቃላቶች በሚከተለው ሁኔታ ያጣድፈው ጀመር ፡ —

«ሰዎች ሆይ! እስኪ ተመልከቱት! አረመኔዎች በገዛ እጃችን እኛኑ መልሰው እንዴት እንደሚያንቁን እስኪ ጉድ ብላችሁ ተመልከቱት! ልብ ብላችሁ አስተውሉ! አስቡ!» በማለት ተናገረ ።

ሰውየው ቀስ ብሎ እጁን ካነሳ በኋላ ሪቢንን በትንሹ ራሱ ላይ ነካ አደረገው ።

«አንተ መናጢ አደበዳደብ እንደዚህ ነው እንዴ!» በማለት የፖሊሱ አዛዥ ጮኸ ።

«ስማ ኒኪታ! ፈጣሪ አምላክ መኖሩን አትዘንጋ!» የሚል ድምፅ ከተሰበሰቡት ሰዎች መሃከል አንዱ አሰማ ።

«ውገረው ብዬሃለሁኝ!» በማለት የፖሊሱ አዛዥ የሰውየውን የአንገት ክሳድ ጨምድዶ ጮኸ ። ኒኪታ ግን ራሱን ወደመሬት ዝቅ አድርጎ እምቢኝ በማለት ሁኔታ ፡ ሄደ ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«ከዚህ በላይ አልመታውም ።» አለ ።

«ምን አልክ?» አለው የፖሊሱ አዛዥ ።

የፖሊሱ አዛዥ ፊት ደም ለበሰ ። መሬቱን በእግሩ እየደቃ እና እየተሳደበ ወደ ሪቢን ገሰገሰ ። ከዚያም ሪቢንን ወገረው ። ሪቢንን አንከባለለው ። ሪቢን ለመከላከል እጁን አነሳ ። የፖሊሱ አዛዥ ለሁለተኛ ጊዜ የሰነዘረው ጡጫ ሪቢንን ከመሬት ደባለቀው ። ከዚያም የፖሊሱ አዛዥ ሪቢንን ደረቱን ፣ ጭንቅላቱን ፣ ጎን እና ጎኖቹን እያፈራረቀ ይረግጠው ጀመር ።



ከተሰበሰቡት ገበሬዎች መካከል የቁጣ ጉርምርምታ ይሰማ ጀመር ። ገበሬዎቹ በቁጣ የፖሊሱን አዛዥ እየተቃወሙ ጠጋ-ጠጋ ይሉ ጀመር ። የፖሊሱ አዛዥ ይኸንን ስለአስተዋለ ለመር ብሎ በመቆም ሰይፉን ከአፎቱ መዝዞ ካወጣ በኋላ ወደኋላ ያፈገፍግ ጀመር ።

«ምንድነው የምትፈልጉት? በአመጸኝነት መነሳሳታችሁ ነው እንዴ? እኔ ነኝ እና! ቆይ-ቆይ!» በማለት የፖሊሱ አዛዥ ያስፈራራ ጀመር ።

ድምፁ ከመደንገጡ የተነሳ ቁርጥ-ቁርጥ የሚል ሲሆን የመርበድበድ ሁኔታም ይታይበታል ። ሲናገርም ሲቃ ይዞት ድምፁ በመጠኑ ሲጥ-ሲጥ ይላል ። ድምፁ እየከዳው ሲሄድ ጉልበቱም ጭምር ከዳው እና ብርክ-ብርክ አለው ። ጭንቅላቱን ወደመሬት ቀለሰ ። ትከሻው ከበደው ። መሬቱን ተጠንቅቆ በእግሩ እየረገጠ እና ከወዲያ-ወዲህ እየተመለከተ ወደኋላው ያፈገፍግ ጀመር ። ከዚያም የሚከተለውን በማጓራት ድምፅ ተናገረ ፡ —

«እሺ ፣ ግዴለም ። ውሰዱት ። እኔ እሄዳለሁኝ ። እኮ ለዚህ አይደለም? የትአባታችሁንስና! ለመሆኑ የፖለቲካ ወንጀለኛ መሆኑን አታውቁም እንዴ? እናንተ መናጢዎች! ሕዝቦች በንጉሡ ላይ እንዲያምጹ የሚያነሳሳ መሆኑን አታውቁም ማለት ነው? ደግሞ እርሱን ትደግፉታላችሁ! ቆይ ግዴለም! እናንተም አመጸኞች ናችሁ ማለት ነዋ! እ?» አላቸው ።

እናት በቅዥት ውስጥ ያለች ይመስል ጭንቅላቷ ባዶ ሁኖ በፍርሃት እና በሀዘን አቅሟ ድክምክም ያለ ከመሆኑ በስተቀር ፣ ሳትንቀሳቀስ እዛው ያለችበት ቆማ ቀረች ። ቁጣ የተመላበት የሰዎቹ ማጉረምረም ጭንቅላቷ ውስጥ እንደ ተርብ ጭዝ-ዝ-ዝ! እያለ ይጮ

ኸባት ጀመር ። የፖሊሱን አዛዥ የተርበደበደ ድምፅ ከመስማቷም በስተቀር ከሰዎቹ መካከል አንዳንዶቹ ፤

«ወንጀለኛ ከሆነ ወደ ፍርድ ቤት ይውሰዱት…»

«ክቡር ሆይ ፤ ይዘኑለት እንጂ…»

«ምነው ምነው ፤ ያለአንዳች ፍርዮ ሰውን እንዲህ ማድረግ ተገቢ ነውን?»

«ምን ፍርድ ምን ሕግ አለ እና ነው! አንድን ሰው እንዲህ ማድረግ ከተቻለማ ማንም ማንንም ሊመታ ይችላል ማለት ነው ። እንዲህ ከሆነማ ጥሩ ነው!» በማለት ተናገሩ ።

የተሰበሰቡት ሰዎች ከሁለት ላይ ተከፈሉ — በአንድ በኩል ያሉት ሰዎች የፖሊሱን አዛዥ ከብበው በመጮኸ እየተቆጡ ድርጊቱን እንዲተው ይጠይቁታል ። በሌላ በኩል ደግሞ ሰብሰብ ብለው የቆሙት ብዛታቸው ይኸን ያህልም ሳይሆን ፤ ተደብድቦ መሬት በተዘረረው ሰው ዙርያ ቆመው በቁጣ ያጉረመርማሉ ። ብዙ ሰዎች አንድነት ሁነው ሪቢንን ከወደቀበት ደግፈው አነሱት ። የፖሊሱ አዛዥ የሪቢንን እጆች እንደገና ሊያሥር ፈለገ ። ሰዎቹ ፡ —

«እናንተ ጭራቆች ሰውን ለማሠር እንደዚህ አትቻኮሉ!» በማለት ጮኹበት ።

ሚኻኢሎ ደሙን ከፊቱ እና ከጢሙ ላይ ከጠራረገ በኋላ የፖሊሱን አዛዥ ፀጥ ብሎ ያስተውለው ጀመር ። እናትን ተመለከተ ። ነቃ አለች ። ከዚያም ከቁጥጥሯ ውጪ በሆነ ሁኔታ እጅዋን እየዘረጋች ወደርሱ ታመራ ጀመረች ። እርሱ ግን ዞር አለ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ዐይኖቹ እናትን ይፈልጉ ጀመር ። ቀጥ ካለ በኋላ ጭንቅላቱን ቀና አደረገ ። በደም የተነከሩ ጉንጮቹም ይንቀጠቀጣሉ ።

«ለይቶ አውቆኛል ። ዕውነት እኔ መሆኔን ለይቶ አውቆኝ ይሆን?» በማለት አሰበች ።



ፍርሃት እና ሃዘን በተቀላቀለው ደስታ እንደምን ነህ በሚል ሁኔታ ድምፅ ሳታሰማ ራሷን ነቀነቀች ። ከዚያም በኋላ ባለ ሰማያዊ ዐይኑ ገበሬም እርሷን-እርሷን እየተመለከተ አጠገቡ የቆመ መሆኑን አስተዋለች ። ለአንድ ሰኮንድ ያህል አመለካከቱ በፍርሃት ዋጣት ።

«ምን ማድረጌ ነው? ኧረ እኔንም ይዘውኝ እንዳይሄዱ!» በማለት አሰበች ።

ገበሬው ሪቢንን አንድ ነገር አናገረው ። ሪቢንም በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ ። ከዚያም ከመንቀጥቀጡ በስተቀር ግልጽ እና ብርቱ በሆነ ድምፅ ሪቢን ፡ —

«ግዴለም ፥ ምንም አይደለም ። በምድሪቱ ላይ ብቻዬን አይደለሁም! ዕውነትን በሙሉ ማፈስ አይችሉም ። ባለሁበት ቦታ ሁሉ ትውስቴ ተመዝግቦ ይቀራል ። የቀረው ቀርቶ ጎጆን አፈራርሰው ጓዶችን በሙሉ ለቅመው ቢያፍሱዋቸው እንኳን …» በማለት ተናገረ ።

«ይኸ አባባሉ የደረሰውን ሁኔታ ለእኔ መንገሩ ነው» አለች እናት ። ከዚያም ሪቢን ንግግሩን በመቀጠል ፡ —

«ይሁን እንጂ አሞራዎቹ በነፃነት የሚበርሩበት ጊዜ ይመጣል ። ሕዝቦች የታሠሩበትን የጭቆና ሰንሰለት ከላያቸው ላይ ይበጣጥሳሉ!» በማለት ተናገረ ።

አንዲት ሴት በባልዲ ውሀ አምጥታ እያለቀሰች የሪቢንን ፊት ታጥብለት ጀመር ። የለቅሶዋ ስቅስቅታ ሚኻኢሎ ከሚያሰማው ንግግር ጋር ተሳክቶ በመግጠም አብሮ ይንቆረቆር ስለነበረ እናት ስቅስቅታውን እና ድምፁን ለይታ ለማድመጥ አልቻለችም ። የፖሊሱ አዛዥ ከፊት-ለፊታቸው ቀድሞ ጥቂት ገበሬዎች ሪቢንን ወደአለበት ቦታ ያመሩ ጀመር ።

«እሥረኛውን ይዞ ለመሄድ ሠረገላውን አምጡ!

በአሁኑ ጊዜ ሠረገላ ማምጣት የማን ተራ ነው?» በማለት ከሰዎቹ መካከል አንዱ ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰማ ።

ከዚያም የፖሊሱ አዛዥ የተበሳጨ ሁኔታ በሚታይበት አዲስ ድምፅ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«መንገጭላህን አወልቀዋለሁኝ! አንተ ግን ንክች ልታደርገኝ አትችልም! ከቶ ምንም ቢሆን አትችልም! አንት ደደብ ድንጋይ ራስ!» አለው ።

«ነኝ እንዴ? ለመሆኑ አንተ ምንድነህ? ፈጣሪ-አምላክ ነህ ማለት ነው?» በማለት ሪቢን ጮኸ ።

እሽ-ሽ! በማለት ተው አይሆንም ዝም በል በሚል ሁኔታ የእርሱን የጩኸት አነጋገር የተሰበሰቡት ሰዎች ድምፅ ዋጠው ። ከሰዎቹ መካከል አንዳንዶቹ የሚከተለውን ተናገሩ ፡ —

«ወንድሜ ሆይ ፤ ለርሳቸው እንደዚህ ያለ መልስ መስጠት ይቅርብህ ። እርሳቸው ከባለሥልጣኖቹ መካከል አንዱ ናቸው እኮ!»

«ክቡር ሆይ አይቀየሙት ። ማንነቱን ባለማወቁ ነው...»

«ኧረ ዝም በል አንተ ጉደኛ!»

«ያውልህ እንግዲህ ወደከተማ ይወስዱሃል!»

«ከዚህ ይልቅ ከተማ ውስጥ ያለው ሕግ ይሻላል!»

የሰዎቹ የጩኸት ድምፅ ተራ-በተራ የሚሰማ እና አንዱ ሌላውን በመደገፍ የሚያቀርበው ነው ። ተስፋ የሌለው ሁኔታ መሆኑን በሚያመለክት ረገድ የሚቀርብ አነጋገር ነው ። ፖሊሶቹ ሪቢንን እጆቹን ይዘውት ወደ ቀበሌው ጽሕፈት ቤት በበሩ በኩል አመሩ ። ቀስ-ቀስ እያሉ የተሰበሰቡት ሰዎች መበተን ጀመሩ ። ባለሰማያዊው ዐይን ሰውዬ ግን በሽፋሽፍቶቹ መካከል እናትን እየተመለከተ ወደ እርሷ ዘንድ ያመራ



ጀመር ። ጉልበቶቿ የሚሙ ሲሆኑ ልቧም በተስፋ መቁረጥ ተመልቶ ቅልሽልሽ አላት ።

«መሄድ የለብኝም! መሄድ የለብኝም!» በማለት አሰላሰለች ።

ከዚያም የመደገፊያውን ብረቶች ጨብጣ ትጠባበቅ ጀመር ።

የፖሊሱ አዛዥ በረንዳው ላይ ቆሞ ድምፁ ያው እንደቀድሞው አሰልቺ እና ወኔ-ቢስ ሁኖ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«እናንት ደደቦች የውሾች ልጆች! በማታውቁት በማያገባችሁ ጉዳይ ገብታችሁ አፍንጫዎቻችሁን ታነፈንፋላችሁ! እናንት አሳማዎች! ይኸ የመንግሥት-ነክ ጉዳይ እኮ ነው! እኔ ለእናንተ እንዲህ ደግ ሰው በመሆኔ በእንብርክካችሁ ልትሰግዱልኝ ይገባችኋል! ከፈለግሁኝ ሁላሺንም አግበስብሼ ለቅሜ በቅጣት መልክ ከባድ ሥራ ወደሚሠራበት ወደግዞት ቦታ እንድትጋዙ ማድረግ እችላለሁኝ!» አላቸው ።

ጥቂት ገበሬዎች ባርኔጣቸውን አውልቀው ንግግሩን ያዳምጣሉ ። ደመናዎቹ ዝግ እያሉ ይወርዳሉ ። ቀኑም ጨለም ይል ጀመር ። ባለሰማያዊ ዐይኑ ሰውዬ እናት ወደቆመችበት በረንዳ መጥቶ ጠጋ አላት ።

«የሚሠራውን ሥራ ያያሉን?» አላት ።

«አዎን...» በማለት እናት ለስለስ ባለ ድምፅ መለሰችለት ።

«እርስዎ እዚህ ምን ጉዳይ አለዎት?» በማለት ዐይን-ዐይኖቿን ትክ ብሎ እየተመለከተ ጠየቃት ።

«ከገበሬ ሴቶች ላይ ጥልፉ-ጥልፍ እና ከተልባ እግር የተሠሩ ጨርቆችም እገዛለሁኝ...» በማለት መለሰችለት ።

ሰውየው ቀስ ብሎ አንገቱን ወደመሬት ቀለስ አደረገ ።

«የእኛ ሴቶች እነዚህን ነገሮች አይሠሩም...» በማለት የሕንጻውን በር ፍዝዝ ብሎ እየተመለከተ መለሰላት ።

እናት ድንገት ከተመለከተችው በኋላ ወደ ውስጥ ለመግባት ምቹ ጊዜ ትጠባበቅ ጀመር ። የሰውየው መልክ የደስ-ደስ ያለው አስተዋይ መልክ ሲሆን ዐይኖቹም የሀዘንተኛ ዐይኖች ናቸው ። ቁመተ-ረዥም እና ትከሻው ሰፊ ነው ። የተጣጣፈ ረዥም ኮት እና ንጹህ የጥጥ ሸሚዝ እንዲሁም ቡናማ መልክ ያለው እቤት የተሰፋ ሱሪ የለበሰ ሲሆን የእግር ሹራብ ሳያደርግ የተቀዳደደ የቡት ጫማ አጥልቆ አል ።

በአንድ ምክንያት እናት የእፎይታ ትንፋሽ ተነፈሰች ። የማሰላሰል ሁኔታዋን የሚከተለው ንግግሯ ቀድሟት ፡ —

«አንተ ዘንድ ሂዶ ማደር ይቻላልን?» በማለት ጠየቀችው ።

ይኸን እንዳለች ወዲያውኑ ሁለንተናዋ አጥንቶቿም ሆኑ ጡንቻዎቿ ተወጣጠሩ ። ቀጥ ብላ ቆመች ። ሳትንቀሳቀስ ሰውየውን ትመለከተው ጀመር ። የሚያሰቃዩ ሃሣቦች በሃሣቧ ይጉላሉ ጀመር ፤

«የኒኮላይ ኢቫኖቪች መዘዝ ያጠፉኛል ። ለረዥም-ረዥም ጊዜም ፓቬልን አላየውም ። ይደበድቡኛል!» በማለት አሰበች ።

ሰውየው ኮቱን ወደደረቱ ሳብ-ሳብ እያደረገ ዐይኖቹን መሬት ላይ ተክሎ እና ባለመቻኮል ሁኔታ የሚከተለውን መለሰላት ፡ —

«ምሽቱን እኔ ዘንድ እንዲያሳልፉ ነውን? ምንቸገረኝ ። ከፉቱ ግን ጎጆዬ ምቾት የሌላት ደሳሳ ጎጆ ነች» አላት ።

«በምቾት የምኖር ሰው አይደለሁኝም!» በማለት



እናት መለሰችለት ።

እሺ አለ ሰውየው ራሱን ቀና አድርጎ በዐይኖቹ ሁኔታዋን እያስተዋለ ። ጊዜው መሽቶ ፊቱ እና ዐይኖቹም ቀዝቀዝ ባለ ፡ ሁኔታ ምሽቱን ያስተውላሉ ።

«እንግዳውስ ቶሎ እመጣለሁኝ ። ሻንጣዬን ይይዙልኛልን?» በማለት ቁልቁለት የምትወርድ መስሎ እየተሰማት ተናገረች ።

«እሺ» አለ ።

ትከሻዎቹን ነቅነቅ አድርጎ ኮቱን እንደገና አስተካከለ ።

«ሠረገላው መጥቷል...» አላት ።

ሪቢን በረንዳው ላይ ብቅ አለ ። አንድ ቡናማ በሆነ ጨርቅ ፊቱ እና ራሱ የተሸፈነ ሲሆን እጆቹም ታሥረዋል ።

«ደጎች ሰዎች ደህና ሁኑ!» የሚለው ድምፁ በቀዝቃዛው ምሽት ውስጥ ተሰማ ። ቀጠል አድርጎም «ዕውነትን ፈልጋችሁ አግኟት እና በክብር አኑሯት! ሀቀኛ ቃልን ይዞ የሚያመጣላችሁን ሰው እመኑት! ለራሳችሁ ሳትሳሱ ዕውነትን መክቱላት!» በማለት ተናገረ ።

«አንተ ውሻ ፤ ዝጋ ይኸን አፍክን!» በማለት የፖሊሱ አዛዥ እየጮኸ ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አድርጎ ፡ —

«አንተ ደደብ ፖሊስ ፈረሶቹን ግረፋቸው እንዲሄዱ!» አለ ።

ሠረገላው ተንቀሳቀሰ ። በሁለት ፖሊሶች መካከል የተቀመጠው ሪቢን ፡ —

«ምን ይቀርባችኋል? እንዴት እንደምትኖሩ ትመለከታላችሁ! እስከሞት ድረስ በችጋር ለምን ትቆላላችሁ? ነፃነታችሁን ካገኛችሁ የእለት እንጀራ እና

ፍትህ የእናንተ ይሆናል! ደህና ሁኑ ደጎች ሰዎች!» በማለት ተናገረ ።

የሡረገላው እግሮች በሚያሰሙት ድምፅ በፈረሶቹ ኮቴ ድምፅ እና በፖሊስ አዛዡ ጩኸት የሪቢን ድምፅ ተዋጠ ።

«እንግዲህ አበቃ!» በማለት ሰውየው ራሱን እየነቀነቀ ተናገረ ።

«እዚህ ጣቢያው ላይ ይጠብቁኝ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እመጣለሁኝ...» በማለት ሰውየው እናትን ተናገራት ።

እናት ክፍሉ ውስጥ ከሄደች በኋላ ሳሞቫሩ አጠገብ ወንበር ላይ ተቀመጠች ። ቁራሽ ዳቦ ከተቀመጠበት አነሳች እና ተመለከተችው ። ከዚያም መልሳ ወደነበረበት አስቀመጠችው ። የምግብ ፍላጎት የላትም ። የቀድሞው የማቅለሽለሽ ስሜቷ እንደገና ተቀስቅሶባታል ። አጓጉል ሙቀት ተሰማት ። የሕመሟ ስሜት አዳከማት ። ልቧ ውስጥ ያለውን ደም መጠጠባት ። ዛል አደረጋት ። የዚያን ሰው እንግዳ የሆነ መልክ ታስተውል ጀመር ። ለእርሷ ሙሉ በሙሉ ያላስተማመናት ሲሆን ጥርጣሬንም አሳድሮባታል ። ይከዳኝ ይሆናል ብላ ለማሰብ አልፈለገችም ፤ ይሁን እንጂ ይኸ ሃሣብ አዕምሮዋ ውስጥ በመጉላላት ላይ ሲሆን ልቧንም ሠርሥሮ ገባ ።

«ለይቶ አወቀኝ! ለይቶ አወቀኝ! ከዚያም እኔ መሆን አለብኝ ብሎ ገመተ...» በማለት ድክም ባለ ሁኔታ ታሰላስል ጀመር ።

በማቅለሽለሽ እና በተስፋ መቁረጥ ተወጥራ ስለነበረ ይኸ አስተሳሰቧ ሊቀጥል እና አዕምሮዋ ውስጥ ሊንገዋለል አልቻለም ።

ከጥቂት ጊዜያት በፊት ሜዳው ላይ ይታይ የነበ



ረው ብጥብጥ በአሁኑ ጊዜ በፀጥታ የተዋጠ መሆኑ ፤ ገበሬዎቹ መፍራታቸውን ለእናት እንድትገነዘበው ያደረጋት ሲሆን ይኸውም ሁኔታ እናትን አመደ. ወጥቶ በሀዘን የተዋጠች ብቸኛ እንድትሆን አደረጋት ።

ልጃገረዲቱ እንደገና በራፉ ላይ ብቅ አለች ።

«የተጠበሱ እንቁላሎች ላምጣልዎትን?» አለቻት ።

«ግዴለም አይጨነቁ ። መመገብ አላሰኘኝም ። በጩኸታቸው እና በጫጫታቸው ልቤን አሸብረውኛል!» በማለት እናት መለሰችላት ።

ልጃገረዲቱ ወደ ወንበሩ መጣች ። ከዚያም ፡ —

«የፖሊሱ አዛዥ እንዴት ይመታው እንደነበረ ሳያዩ አልቀሩም!» አለች በመደነቅ መንፈስ ለእናት ቀስ ብላ በመናገር ። ቀጠል አደረገችናም «ጠጋ ብዬ ቆሜ ነበር ። ጥርሱን በቡጢ መታው ። ሰውዬውም ደም ሲተፋ ተመለከትኩኝ ። ደሙ ወፍራም እና ደማቅ ቀይ ነበር ። ዐይኖቹ በድብደባው አበጡ! ቅርጣን የሚያወጣ ሰው ነው ። የፖሊሱ ሳጂን ሜጀር ጥንብዝ ብሎ ሰክሮ ላይኛው ፎቅ ቤት ተንጋሏሎአል ። እንደዚህ ሰክሮ አሁንም የሚጠጣ ቢኖ መጠጥ አምጡ ይላል ። አመጸኞቹ ብዙ ነበሩ ። የእነርሱ ዋና ቀንደኛ መሪያቸው ፤ ግን ይኸ ጢማሙ ነው ይባላል ። ከመሃላቸው ሦስቱን የያዟቸው ሲሆን አንደኛው ግን አመለጠ ። የእነርሱው ተባባሪ የሆነ አንድ የትምህርት ቤት መምህርም ይዘዋል ። በእግዚአብሔር አያምኑም ። ሌሎች ፡ ሰዎችም አብያተ ክርስቲያናትን እንዲዘርፉ በእግዚአብሔር ያለማመን ሁኔታ የተመላበት ንግግር ያደርጋሉ ። ሰዎቹ እንዲህ ያሉ ሰዎች ናቸው! ከሰዎቻችን መካከል አንዳንዶቹ ያዘኑለት ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ መሰቀል ይገባዋል ይላሉ ። እንደዚህ ያሉ በስባሳ የሆኑ ሰዎች እኛ ዘንድ ብዙ ናቸው!» በማለት ፡ ተናገረች ።

እናት ፍርሃቷን እና ጭፍግግ ያላት ስሜቷን ለማስወገድ እየሞከረች ቁርጥ-ቁርጥ የሚለውን የልጃገረዲቱን ንግግር በተመስጦ ታደምጥ ጀመረች ። ልጃገረዲቱ ወሬዋን የሚያደምጥላት ሰው በማግኘቷ ተደስታ ወሬዋን በስሜት ትሰልቀው ታዥጎደጉደው ቀጠለች ። ቀጠል አድርጋም ፡—

«አባቱ የዚህ ሁሉ ምክንያቱ የሰብል መበላሸት ነው ይላል ። ይኸው ምድሪቱ ሰብል መስጠት ከተወች ሁለተኛ ዓመቷ ነው ። የገበሬዎቹ ኑሮም ከባድ ሁኖአል ። ለዚህ ነው እንዲህ ብስብስ ብለው የተበሳበሉት ። በየመንደሮቹ ስብሰባዎች ላይ ይጯጯሃሉ ። ይደባደባሉ ። አንድ ቀን ቫሱኮቭ ያለበትን ዕዳ እንዲከፍል የመንደሩ አባት-ሽማግሌ ዘንድ አቅርበውት ሽማግሌው ክፈል እንጂ ብለው ቢጠይቁት ፤ ሽማግሌውን ‘ልክፈል እንዴ? ይኸንን ነው የምከፍለው ’ ብሎ በጥፊ አጮላቸው!» አለች ።

ከበራፉ ውጪ ከበድ ያለ የጫማ ድምፅ ተሰማ ። እናት ጠረጴዛውን ደገፍ ብላ ተነሳች ።

ሰማያዊ ቀለም ያላቸው ዐይኖች ያሉት ሰውዬ ባርኔጣውን ከራሱ ላይ ሳያወልቅ ወደውስጥ ገባ እና እናትን ፡—

«ሻንጣዎ የት ነው ያለው?» አላት ።

በቀላሉ ብድግ አደረገው እና አወዛወዘው ።

«ባዶ ነው! ማርካ እኚህን ሴትዮ ወደ ጎጆዬ ውሰጃቸው» አለ ።

ወደኋላው ሳይመለከት ወጥቶ ሄደ ።

«ምሽቱን የሚያሳልፉት እዚህ ነውን?» በማለት ልጃገረዲቱ እናትን ጠየቀቻት ።

«አዎን ። ጥልፉ-ጥልፎች ለመግዛት ነው የመጣሁት ። ጥልፉ-ጥልፎች እገዛለሁኝ...» በማለት እናት መለሰችላት ።



«እዚህ ጥልፉ-ጥልፎች አይሠሩም ። ቲንኮቮ እና ዳሪና የተባሉት ቦታዎች ጥልፉ-ጥልፎች እየሠሩ ይሸጣሉ ። እዚህ ግን የለም!» በማለት ልጃገረዲቱ ለእናት አስረዳቻት ።

«እንግዲያው ነገ ወደ እነዚያ ቦታዎች እሄዳለሁኝ» በማለት እናት መለሰች ።

እናት የሻይ ዋጋ ስትከፍል ልጃገረዲቱን ሦስት ኮፔክ ጉርሻ በመስጠት አስደሰተቻት ። ከዚያም ከቤቱ ውስጥ ወጡ ። ልጃገረዲቱ መጫምያ በሌለው ባዶ እግርዋ ቀዝቃዛውን መሬት ትራመዳለች ።

«ከፈለጉ እኔ ዳሪና ሂጄ ሴቶቹ ጥልፉ-ጥልፎቻቸውን እንዲያመጡልዎ ላደርግ እችላለሁኝ ። እዚያ ድረስ ከመንዝ ያድንዎታል ። ቦታውም እኮ ሩቅ ነው ። አሥራ ሁለት ቬርስታ ያህል ይርቃል...» በማለት ልጃገረዲቱ ተናገረች ።

«የኔ ውድ ግዴለም አትቸገሪ!» አለቻት እናት ከልጃገረዲቱ ጎን-ጎን እየተራመደች ። ቀዝቃዛው አየር መንፈሷን አደሰላት ። በልቧ ውስጥ ልትገነዘበው ያልቻለችው ውሳኔ ቀስ እያለ ይሠፍር ጀመር ። ሃሣቧ ቀስ ብሎ እና እርግጠኛ ባልሆነ ሁኔታ የሚያድግ ሲሆን የኋላ-ኋላ ግን ረግቶ የሚቀመጥ ይመስላት ጀመር ። በሃሣቧ ፡—

«ምን ማድረግ ይሻላል ። ለሕሊናዬ ስል በትክክል ብናገርስ...» አለች ።

ምሽቱ ቀዝቃዛ እና እርጥብ ነበር ። በየጎጆዎቹ መስኮቶች ቀላ ያሉ መብራቶች ብዥ-ብዥ ይላሉ ። የአካባቢው ፀጥታ በእረኞች ድምፅ እና በከብቶች ጩኸት ደፈረሰ ። መንደሩ በጭለማ ፡ እና ረጭ ባለ ድፍጠት ተጠቅሎአል ።

«ይኸው እንግዲህ ደርሰናል ። ምሽቱን ለማሳለፍ የመረጡት ጎጆ ያጣ-የነጣ የመናጢ ጎጆ ነው ። ሰው

ዬው ምንም የሌለው መናጢ ደሀ ነው…» አለች ልጃገረዲቱ ።

በሩን ገፋች እና ከፈተችው ።

«አክስቴ ታትያና!» በማለት ተጣራች ። ከዚያም ፡ —

«በሉ ደህና ሁኑ!» ካለች በኋላ በጭለማ ውስጥ እየሮጠች በመሄድ ለዐይን ተሠወረች ።

## 17

እናት ወደውስጥ ገባች እና ደህና አድርጋ ጎጆውን ለማስተዋል ዐይኖቿ ላይ እጅዋን ጣል አደረገች ። ትንሽ ጎጆ ነች ። ነገር ግን በቤቱ የንጽህና እያያዝ ወዲያውኑ ተደነቀች ። ከእሳት ማንደጃው በስተጀርባ አንዲት ወጣት ሴት ብቅ ብላ ድምፅ ሳታሰማ እጅ ከነሳች በኋላ ወደመጣችበት ተመልሳ ሄደች ። ጠረጴዛው ላይ የሚበራ ፋኖስ ተቀምጦአል ።

የቤቱ ባለቤት የእናትን ዐይኖች ትክ ብሎ እያስተዋለ እጣቶቹን ጠረጴዛው ላይ እያንኳኳ በብስጭት መልክ ተቀምጦአል ። ትንሽ እንደቆየም ፡ —

«ይምጡ እንጂ ። ታትያና ቶሎ ሂጂ እና ፒዮትርን ጥሪው!» አለ ።

ከሰውየው ፊት-ለፊት አግዳሚው ወንበር ላይ የተቀመጠችይቱን እናትን ሳትመለከት ሴቲቱ ወጥታ ሄደች ። የልብስ ሻንጣዋ የት እንደሆነም አይታይም ። ጎጆው አልፎ-አልፎ በሚሰማው የፋኖሱ ጧ-ጧ የማለት ድምፅ እንጂ አለበለዚያ ረጭ ባለ ፀጥታ ተውጦአል ። በዐይኖቿ ላይ አሁንም አሁንም ግጥም በሚለው ሰውዬ ኮስታራ ፊት ናደድ ብላለች ።

«ሻንጣዬ የት ነው ያለው?»በማለት በራሷ ላይ ፍርሃት እና ሀፍረት ባሳደረባት ጎላ ባለ ድምፅ ጠየቀች ።



ሰውዬው ትከሻውን ወዝወዝ አደረገ ።

«ግዴለም አይጠፋም…» አላት ። ከዚያም ዝግ ባለ ድምፅ ቀጠል አድርጎ ፡ —

«ቅድም እዚያ ጣቢያው ውስጥ ሁነን ሻንጣው ባዶ ነው ማለቴ ልጃገረዲቱ እንድትሰማ ይሁንኝ ብዬ አውቄ ነው እንጂ ሻንጣዎ ባዶ አልነበረም ። በጣም ይከብድ ነበር!» አለ ።

«እና ታዲያስ?» አለችው ።

ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ወደ እርሷ ተጠጋ ። ዝቅ ብሎ ጎንበስ ካለ በኋላ ቀስ ባለ የሹክሹክታ አነጋገር ፡ —

«ያንን ሰው ያውቁታልን?» አላት ።

«አዎን አውቀዋለሁኝ!» አለችው እናት በተረጋገጠ አመላለስ ። ጥያቄው ግን አስደነቃት ። ይኸ አጭር መግለጫ ነገሮችን ግልጥ-ግልጥልጥ በማድረግ ከውስጥ ላለ ስሜታቸው ፋናውን ቦግ አድርጎ ያበራላቸው ይመስላል ። በእፎይታ ከተነፈሰች በኋላ አግዳሚው ወንበር ላይ ተዝናንታ ተቀመጠች ።

ሰውየው ፈገግ ብሎ ሳቀ ።

«እዚያ ሁነን ለእርሱ ጭንቅላትዎን በማወዛወዝ ምልክት ሲሰጡት እና እርሱም በጭንቅላቱ ምልክት ሲመልስዎ ጉዳዩን ተገንዝቤው ነበር ። በረንዳው ላይ ከቆሙት ከእርስዎ ጋር ትውውቅ እንዳለው ቀስ ብዬ በማሾክሾክ ሁኔታ ጠይቄው ነበር ።»

«እና ምን አለ?» በማለት እናት ፈጠን ባለ ሁኔታ ጠየቀችው ።

«ወገናሞች ብዙ ነን አለኝ ። አዎን ብዙ ነን በማለት መለሰልኝ…» አላት ።

ሰውዬው በማጥናት መልክ የእናትን ዐይን-ዐይኖች ትክ ብሎ ይመለከት ጀመር ። ቀበል አድርጎም ፈገግ በማለት ፡ —

«የማይበገር ኃይል ያለው ሰው ነው! የሆነውን
ያህል ቢደበድቡት መናገር የሚፈልገውን ነገር ሳይ
ናገር አይተውም...» በማለት ተናገረ ።

ድምፁ የመድከም እና የመጠራጠር ሁኔታ የሚታ
ይበት ሲሆን ፍዝዝ ያሉ የሀቀኛ ዐይኖቹ እናትን
ከጊዜ-ጊዜ ይበልጥ ያዝናኗት ጀመር ። ቀስ-በቀስም ጥን
ቃቄ እና ደስታ-ቢስነቷ ጠፍቶ ለሪቢን ታስብ ጀመር ።

«ዘራፊዎች! ጨካኞች!» በማለት እያለቀሰች ተና
ገረች ።

በሀዘን ተውጦ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ ሰውዬው
ከነበረበት ብድግ ብሎ ተነሳ ።

«ባለሥልጣኖቹ ራሳቸውን ሕዝብ እንዳያፈቅራ
ቸው አድርገዋል!» አለ ። ከዚያም ወደ እናት ዞር ካለ
በኋላ ረጋ ብሎ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«እኔ የምለው እሻንጣዎ ውስጥ ጋዜጣዎች የሉ
ምን? በበኩሌ ያሉ ይመስለኛል» አላት ።

«አሉ!» አለች እናት እንባዎቿን እየጠራረገች ።

ኮስተር በማለት ጢሙን እያሻሸ ከበስተጥግ በኩ
ል ቆመ ። ትንሽ ቆየት ካለ በኋላም ፡ —

«ጋዜጣዎቹ እና መጻሕፍቶችም ጭምር ይደርሱን
ጀመር ። ያንን ሰውም እናውቀዋለን ። ከዚህ ቀደም
አይተነዋል!» አለ ።

ቆመ እና ለጥቂት ሰኮንድ አሰበ ።

«አሁን ታዲያ ሻንጣዎ ውስጥ ያለውን ዕቃ ምን
ሊያደርጉት ያስባሉ?» አላት ።

«ለእናንተ እተዋቸዋለሁኝ!» አለችው እናት ኃላፊ
ነት መቀበል አለብህ በሚል መልክ እርሱን እርሱ
ን እየተመለከተችው ።

የመቃወምም ሆነ የመደነቅ ሁኔታ አላሳየትም ።

«ጥሩ ነው...» አላት ።

ጭንቅላቱን እሺ ጥሩ ነው በሚል መልክ እየነ



ቀነቀ እና ጢሙን በእጁ እያሻሸ ወንበሩ ላይ ተቀመ
ጠ ።

በደም የተነከረው እና የተደበደበው ሪቢን ሁኔታ
የተቀሩትን ሃሣቦቿን አስወግዶ በአዕምሮዋ ውስጥ
ብቅ እያለ ይታያት ጀመር ። የተቀሩትን ስሜቶቿን
በሙሉ ቅሬታ እና ሃዘን የዋጠባት በመሆኑ ስለሻ
ንጣውም ሆነ ስለማንኛውም ሌላ ነገር አታሰላስልም ።
እንባዎቿ እንደውሀ ይጎርፋሉ ። ፊቷ የመኮሳተር ሁኔ
ታ የማይታይበት ከመሆኑም በስተቀር በተስተካከለ
ድምፅዋ የሚከተለውን ትናገር ጀመር ፡ —

«በሰብአውያን ፍጡሮች ላይ እንደዚህ አድርገው
ለሚፈጽሙዋቸው ዝርፊያዎች እና ዘለፋዎች ለምንግ
ዜውም ተወቃሽ-ተከሳሽ ያድርጋቸው!» አለች ።

«ጠንካሮች ናቸው! በጣም ጠንካሮች ናቸው!» በማ
ለት ሰውዬው ረጋ ብሎ ተናገረ ። እናትም ቆጣ በማ
ለት ሁኔታ ፡ —

«ጥንካሬውን የሚያገኙት ከየት ነው? ከእኛው ላይ
ነው ጥንካሬውን የሚያገኙት!» ብላ ተናገረች ።

የደግነት ሁኔታ የሚነበብበት ቢሆንም ምሥጢር
አዘል በሆነው በሰውዬው ፊት ተበሳጭታለች ፡ —

«አዎን ጎማዎቹ...» አለ ።

ድንገት ጆሮውን ቀሠረ እና ወደበሩ አቀና ።

«እየመጡ ናቸው...» አለ ።

«እነማን?» አለችው ።

«ወዳጆቻችን ይመስሉኛል» አላት ።

ሚስቱ ወደውስጥ ገባች ። ከእርሷው ጋር ተከት
ሎም አንድ ሌላ ሰው ከገባ በኋላ ባርኔጣውን ወደ
ጥግ አስቀምጦ ከወንበር ላይ ተቀመጠ ።

«እሺ?» አለ ።

የመጀመርያው ራሱን ነቅነቅ አደረገ ።

«ስቴፓን» በማለት ሚስቲቱ ቆማ ከነበረበት ከማብሰያው ቦታ ሁና ተጣራች ። ከዚያም «እንግዳችን ምናልባት እርቦአቸው ይሆናል እኮ?» አለች ።

«የለም ፣ አልራበኝም!» በማለት እናት መለሰች ።

ሁለተኛው ሰው ወደ እርሷ ዘንድ ዞር አለ ።

«እንተዋወቅ ። ስሜ ፒዮትር የጎሮቭ ሪያቢኒን የሚባል ሲሆን የቅጽል ስሜም ወስፌ ይባላል ። ስለእርስዎ ተግባር ጥቂት አውቃለሁኝ ። መጻፍ እና ማንበብ እችላለሁኝ ። እና ጅል አይደለሁም ማለቴ ነው...» አላት ።

የዘረጋችለትን እጅዋን ጨበጠ ። ከዚያም የሚከተለውን ፡ ተናገረ ፡—

«አየህ ስቴፓን ፣ እንደሚመስለኝ ቫርቫራ ኒኮላየቭና ደግ ሴት ነች ። ነገር ግን ይኽ ተግባር አጓጉል እና ጎጂ ነው ትላለች ። ወጣቶች እና ተማሪዎች ባልረባ ውጥንቅጥ ነገር የሕዝቡን አዕምሮ ይበክሉታል ትላለች ። ዛሬ ይዘው ያሠሩት ሰው ግን አዛውንት ሰው መሆኑን እኔ እና አንተ እንመለከታለን ። አሁን ደግሞ ይኸው እዚህ እሳቸውን ተመልከታቸው ፡— እንደምገምተው እርሳቸው የሴት ወይዘሮ ያይደሉ እና በመካከለኛ የዕድሜ ደረጃቸው ላይ የሚገኙ ናቸው ። ነዎት ። አይደለምን?» በማለት ጠየቀ ።

ትንፋሹን ለመተንፈስ ሳይጠባበቅ ችኩል በሆነ ሁኔታ የሚነጋገር ሲሆን ፣ ንግግሩ ግን ግልጽ ነው ። ጺሙ በብስጭት የሚንቀጠቀጥ ሲሆን ዐይኖቹ ደግሞ የእናትን ፊት እና ቁመና ትክ እያሉ ይቃኛሉ ። ልብሱ የተቀዳደደ ነው ። ፀጉሩም ገና አሁን ከፀብ ቦታ በአሸናፊነት የተመለሰ ይመስል ተመነጫጭሮአል ። ስለመንፈሰ ጠንካራነቱ እና ዳግመኛም የሚናገረው የመጣለትን ሃሣቡን በግልጽነት በመሆኑ እናት ወደደችው ። ያቀረበውን ጥያቄ ስትመልስለት ፈገግ አለች ።



እርሱም እጅዋን እንደገና ጨበጥ አድርጎ ደረቅ ያለ የማስካካት ሳቅ ሳቀ ።

«ንጹሕ ተግባር ነው ። ጥሩ ተግባር ነው ፣ ስቴፓን» በማለት ተናገረ ። ከዚያም ቀጠል አድርጎ ፡—

«ከሕዝቦች ከራሳቸው ይመጣል ብዬ አልነገርኩህ ምን? ያቺ መልካም ሴት ግን ዕውነቱን አትነግርህም ። እርግጥ ነው አከብራታለሁኝ ። ይኽ ጥርጥር የለውም ። ጥሩ ሴት ከመሆኗም በስተቀር እኛን ልትረዳን ትሻለች ። በእርሷ ላይ አንዳችም ጉዳት ሳታስከትል በመጠኑም ቢሆን ልትረዳን ትሻለች ። ተራ ሕዝቦች ግን ለራሳቸው አንዳችም ቅንጣት እንኳን ሳይሰጉ በግንባር ቀደምትነት ፊት-ለፊት ይጋፈጣሉ ። ልዩነቱን አስተዋልከውን? የሆነውን ነገር ቢያደርጉ ፣ እነርሱ ምንግዜም ይጎዳሉ ። ስለዚህ ለእነርሱ ሁሉም ያው አንድ ነው ። በየትኛውም መንገድ ቢዞሩ ምንግዜም የሚሰሙት ቃል 'ቁም!' የሚለውን ነው» በማለት ተናገረ ።

«አዎ አዎ» አለ ስቴፓን ራሱን እየነቀነቀ ። ከዚያም ቀጠል አደረገ እና «ስለ ሸንጣቸው እያሰቡ ነው» አለ ።

ፒዮትር አውቆ እናትን ጠቀስ አደረገ ። ከዚያም ዋስትና ባለው አነጋገር ፡—

«አያስቡ ። እናት ፣ ሁሉም ነገር የተሳካ ይሆናል ። ሸንጣዎ እኔ ዘንድ ነው ። ዛሬ እርሱ እርስዎ በዚህ ጉዳይ ውስጥ የሚገኙበት መሆኑን እና ያንን ሰውም የሚያውቁት መሆኑን ሲነግረኝ ፣ እንዲህ አልኩት ' ስቴፓን ደህና አድርገህ አስተውል! ይኸንን በመሰለ ጉዳይ ውስጥ ስሕተት ላይ መውደቅ የለብንም ።' እርስዎ ሳን እኛ በቆምንበት ጊዜም እኛ እነማን እንደነበርን የተገነዘቡ ይመስል ነበር ። ቅን ሰዎች በሁኔታቸው ይታወቃሉ ። እንደዕውነቱ ከሆነ ደግሞ በአደባባይ

ወጥተው የሚታዩት ብዙም አይደሉም ። ስለሻንጣዎ አያስቡ...» አላት ።

አጠገቧ ከተቀመጠ በኋላ ሁለንተናዋን በማጥናት ይመለካከታል ።

«ሻንጣዎ ውስጥ ያሉትን ነገሮች ለማውጣት የሚሹ ከሆነ እጅጉን ደስተኞች እንሆናለን ። እነዚያን መጻሕፍት ልንጠቀምባቸው እንችላለን...»

«ሁሉንም ለእኛ ሊተውልን ይሻሉ» በማለት ስቴፓን ነገረው ።

«እናት ፥ በጣም ጥሩ ነው ። ቦታ እናገኝለታለን...» አለ ።

ጥቂት ሳቅ ካለ በኋላ እመር ብሎ በመነሳት ከወዲያ ወዲህ እየተንጎራደደ ፥ —

«ግሩም የሆነ አጋጣሚ ነው! ምንም እንኳን ያልተለመደ ነገር ባይሆንም! የግንኙነት ገመዳችን ካንድ በኩል ሲበጠስብን ከሌላ በኩል ደግሞ ይኸው ተቀጠለልን ። እናት ፥ ጋዜጣው ጥሩ ከመሆኑም በስተቀር መልካም ተግባርን እያከናወነልን ነው ። የታወረን ዐይን ያበራል ። ከቡራን መኳንንት ስለእርሱ ብዙም አያስቡበትም ። ከዚህ ሰባት ቬርስታ ርቆ ከሚገኝ ቦታ ለአንዲት የሴት ወይዘሮ በአናጢነት ተቀጥሬ እሠራለሁኝ ። ጨዋ ነች ። እንደውም የምናነበው መጻሕፍትም ትሰጠናለች ። አንዳንድ ጊዜ በዕርግጥ ዐይንን የሚያበራ መጽሐፍ ማንበብ ይቻላል! በአጠቃላይ እርሷን እናመሠግናታለን ። አንድ ጊዜ ግን እኔ ይኸንን የእኛን ጋዜጣ አሳየኋት ። እንዴት እንደተቀበለችው ሊገምቱ ይችላሉ ፥ — ‘ፒዮተር ፤ ይኸንን ነገር አታንብብ ፤ ይኸንን የሚጽፉት እዚህ ግቡ የማይባሉ ደደብ የሆኑ የትምህርት ቤት ልቃሞ ልጆች ናቸው ። ይኸንን በማንበብ ለአንተ የሚተርፍህ ጣጣ ውስጥ መግባት ብቻ ነው ። እሥር-ቤት መግባት እና ሳይቤ



ርያ በግዞተኛነት መጋዝ ብቻ ነው የሚተርፍህ’ አለችኝ» በማለት ተናገረ ።

እንደገና ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም አለ ። ከዚያም ፥ —

«እናት ፤ ያ የዛሬው ሰውዬ ከእርስዎ ጋር ዝምድና ያለው ነውን?» በማለት ጠየቃት ።

«አይደለም!» በማለት እናት መለሰችለት ።

በአንዳች ነገር የተደሰተ ይመስል ፒዮትር ድምፅ ሳያሰማ ሳቀ ።

«ዝምድና የለንም ። ነገር ግን ለረዥም ጊዜ የማውቀው ከመሆኔም በስተቀር ፤ እንደታላቅ ወንድሜ አከብረዋለሁኝ!» በማለት እናት ተናገረች ። ከዚያም እናት ከሪቢን ጋር ዝምድና የለኝም ማለት ስሕተተኛ ክህደት እንደሆነ ጉዳይ በመቁጠር በተጨማሪ ለመናገር ተቻኮለች ።

ስሜቷን የሚገልጹላት ትክክለኛ የሆኑ ቃላትን ለማግኘት አልቻለችም ። ስለዚህም ሁኔታው ቅር ስላሰኛት እንደገና ዝም ብላ ታለቅስ ጀመር ። በጎጆው ውስጥ የሚጫጫን ዝምታ ሰፈነበት ። ፒዮትር አንዳች ነገርን ያደምጥ ይመስል ጭንቅላቱን ወደታች እንደቀለሰ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ተነሳ ። ስቴፓን ክንዱን ጠረጴዛው ላይ አስደግፎ እና ብስጩ በሆነ ሁኔታ ጣቶቹን ከጠረጴዛው ጋር እየቆረቆረ ተቀምጦአል ። ሚስቱ ወደ ምድጃው ጠጋ ብላ ያጐነበሰች ስትሆን እናትም እርሷን-እርሷን የምትመለከታት መሆኗን ተገነዘበች ። እናት አንዳንድ ጊዜ ይህችን ፊት — ድቡልቡ የሆነችይቱን ፤ ጠየም ያለ የቆዳ ቀለም ያላትን ፤ አፍንጫዋ ቀጥ ብሎ የወረደ እና አገጩ-ረዥም የሆነች ሴት ትክ ብላ ታስተውላታለች ። የሚስቲቱ አረንጓዴ ዐይኖች ቅን እና አስተዋዮች ናቸው ። ከዚያም ፒዮትር በመደነቅ ሁኔታ ፥ —

«ወይ ጉድ ፤ እና ጓደኛዎ ነው ማለት ነዋ? የራሱ

ጭንቅላት ያለው ሰው ነው ። በራሱ የሚያስብ! በራሱ ላይ ከፍተኛ ውሳኔ ያሳርፋል! ይኸ ደግሞ ጥሩ ነው ። እውን ታትያና ፤ እንዴት ያለ ሰው ነው ጃል? እና አንቺ የምትይው ግን...» ብሎ ሳይጨርስ ታትያና ጠባብ የሆኑ ከናፍሮቿን አገጣጥማ ንግግሩን በማቋረጥ ፡ —

«ባለትዳር ነውን?» አለች ።

«ሚስቱ ሞታበታለች!» አለች እናት ሀዘን በተቀላቀለው ሁኔታ ።

«ለዚህ ነዋ እንዲህ ብርቱ የሆነው!» አለች ታትያና ጥልቀት ባለው ጉልህ አነጋገር ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ ፡ —

«ባለትዳር የሆነ ሰው ይኸንን የመሰለ መንገድ መርጦ አይከተልም ። ይፈራል...» አለች ።

«እኔ ምንድነኝ? ባለትዳር አይደለሁምን?» በማለት ፒዮትር ጮክ ብሎ ተናገረ ።

«እ-ሽ-ሽ! ቀስ በል! ጎረቤቶች እንዳይሰሙ!» በማለት እርሱን-እርሱን ሳትመለከት ፈገግ እያለች ተናገረች ። ከዚያም ንግግሯን በመቀጠል ፡ —

«አንተ ምን የምትፈጽመው ጉዳይ አለህ? ማውራት ብቻ ነው ። ቢበዛ አንዳንድ ጊዜ አንድ ወይንም ሁለት መጻሕፍት ታነብባለህ ። አንተ እና ስቴፓን አንድ ጨለም ያለ ሥርቻ ሥር ሁናችሁ ወሬ ብታወሩ ለሕዝቡ የሚጠቅም ፋይዳ የምትፈይዱ አይደላችሁም » አለችው ። ሰውዬው በእርሷ የንቀት አነጋገር በስጨት ብሎ ፡ —

«ብዙ ሰዎች የምናገረውን እህ ብለው ያደምጡኛል ። እኔን እዚህ እንደ እርሾ ጥንስስ የምትሠራ ነህ ነው ማለት ያለብሽ እንጂ ይኸንን ማለት የለብሽም...» በማለት በተቃውሞ ተናገረ ።

ስቴፓን ሚስቱን ምንም ሳይናገር መልከት ካደ



ረገ በኋላ እንደገና ጭንቅላቱን ወደመሬት ቀለስ አደረገ ።

«ሰው ለምን ትዳር ይይዛል?» በማለት ታትያና ጠየቀች ። ከዚያም እራሷው ለጥያቄው በመመለስ ፡ —

«ምክንያቱም የምትሠራለት ሴት ታስፈልገዋለች እና ነው ። ምን ለመሥራት?» አለች ።

«በቂ ሥራ አላገኘሺምን?» በማለት ስቴፓን ጠየቃት ።

«ይኸ ምን ሥራ ይባላል? በየዕለቱ በገሚስ በችጋር ተቆራፍዶ መኖር? ልጆች ቢኖሩህ ፤ ሌላውን ሥራ እየሠራህ እነርሱን ለመጠበቅ ጊዜ አይኖርም ። ያም ሁኖ ደግሞ የምትበላውም በበቂ አይኖርህም» አለች ።

እናት ዘንድ ሂዳ ከተቀመጠች በኋላ ቅሬታም ሆነ ሀዘን ሳታሳይ መነጋገሯን ቀጠለች ።

«ሁለት ሕፃናት አሉኝ ። አንደኛው ገና የሁለት ዓመት ሕፃን ሁኖ በሞት ተቀጠፈብኝ ። ሌላኛው ደግሞ በዚሁ በተረገመ ሥራ ምክንያት ማኅፀኔ ውስጥ ሞቶ ተወለደ ። የተረፈኝ ደስታ አለን? ማግባት ምንም ፋይዳ የለውም ባይ ነኝ ። አንዳሻው ለመኖር እና የተሻለ ኑሮ ለመኖር ሲል እጆቹን አሣሥሮ ይቀራል ። ከዚያም በኋላ እንደዚያ ሰውዬ ዕውነትን ተከትሎ በቀጥተኛው መንገድ ይዘልቃል ። እናት ሆይ ፤ አይደለምን?» አለቻት እናትን ። እናትም ፡ —

«አዎን ነው ። ነው የኔ ውድ ። ይኸ ካልሆነ ይኸንን አኗኗር ለመለወጥ በፍጹም ተስፋ ማድረግ አንችልም» አለቻት ።

«ባል አለዎትን?» አለቻት ።

«ሞቶአል ። ልጅ አለኝ...» በማለት መለሰችላት ።

«አብሮዎት ከእርስዎ ጋር ይኖራልን?»

«እሥር ቤት ነው!» አለቻት እናት ።

ቀደም ሲል እሥር ቤት ነው የሚሉት ቃላት ያሳ

ድሩባት የነበረው የሀዘን ስሜት አሁን ኩራትን አሳ
ደሩባት ። እናት ቀጠል አድርጋ ፡ —

«እሥር ቤት ሲጨምሩት ይኸ ሁለተኛ ጊዜው
መሆኑ ነው ። እሥር ቤት የጨመሩትም የዕውነትን
ዘር በሕዝቦች መካከል የሚዘራ በመሆኑ ምክንያት
ነው… ልጄ ወጣት ነው! መልኩቀና እና ብልህ ነው!
ለእናንተ ጋዜጣ ስለማዘጋጀት ጉዳይ መጀመርያ
ያሰበ እርሱ ነው ። ምንም እንኳን የሚኻኢሎ ኢቫኖ
ቪች ዕድሜ ከልጄ ዕድሜ ሁለት እጥፍ የሚበልጥ
ቢሆንም ሚኻኢሎ ኢቫኖቪች አሁን የሚከተለውን
ጎዳና መርቶ ያመለከተ ልጄ ነው ። በቅርቡ ለፍርድ
ይቀርብ እና ልጄ በግዞተኛነት ወደ ሳይቤርያ ይላ
ካል ። ይሁን እንጂ ተግባሩን ለመቀጠል ከዚያ ቦታ
ጠፍቶ ይመለሳል…» አለቻት ።

ይኸንን እናት በምትናገርበት ጊዜ የኩራት ስሜ
ቷ ይበልጥ እየተቀሰቀሰ ከፍ-ከፍ ያለ ሲሆን ይኸው
ም ሁኔታ የጀግናውን ልጅዋን ምንነት ለመግለጽ ቃላ
ቶች ዱብ-ዱብ እያሉ ከናፍሮቿ ላይ እየፈለቁ ለመው
ጣት ይተናነቋት ጀመር ። ሃሣበቢስ የሆነ ሽብር እና
አሳፋሪ የሆነ ጭካኔ ተጭኗት የነበረ በመሆኑ ምክ
ንያት ይታይ የነበረውን የዚያን ዕለት ጭለማ
ለመግፈፍ እና በምትኩም የሚቋቋመው አጸፋ
ለማቅረብ ብሩኅ እና በቂ ምክንያት ያለው አቀራ
ረብ ማቅረብን አስፈላጊ ሁኖ አግኝታው ነበር ።
ለዚህ እንደዚህ የተሟላ የሆነውን መንፈሷን በማከ
በር ፤ የእሳት ኃይል እስኪያውራት ድረስ ብሩኅ እና
ንጹህ የሆነውን ሁሉ በአንድነት ሰብስባ ወደ ነበ
ልባልነት ታቀጣጥለው ጀመር ። ቀጠል አድርጋ በመና
ገርም ፡ —

«እርሱን የመሰሉ አያሌ ናቸው ። በላይ በላዩ
እየጨመሩ በመወለድ ላይም ናቸው ። ለዕውነት እና



ለነፃነትም እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ ድረስ ትግ
ላቸውን ይቀጥላሉ…» አለች ።

ቆጠብ ከማለት ተዘናጋች ። ስሞችን ሳትጠራ ሰፊ
ሕዝቦችን ከጭቆና ለማላቀቅ እርሷ የምታውቃቸውን
በመካሄድ ላይ ያሉትን ምሥጢራዊ ተግባሮች ዝር
ዝር አድርጋ አወራችላቸው ። ለልቧ ውድ የሆኑ ሰዎ
ችን ሁኔታ ስትገልጽ ፤ እንዲህ ዘግይቶ ለማበብ የሕይ
ወት ዕድል ያጋጠማትን ማናቸውንም ሁሉ ባለ በሌ
ለ አቅሟ እና ችሎታዋ በቃላት አማካይነት ለመግ
ለጥ ትጥር ጀመር ። በዐይነ-ልቦናዋ ብቅ እያሉ የሚ
ታዩዋት ፤ በስሜቷ ውስጥ ብሩኅ እየሆኑ በትላቅነት
የሚታሰቧት ሰዎችን በደስታ አቅፋ ታስታውሳቸው
ጀመር ።

«እና ይኸ ተግባር በመላው ዓለም ውስጥ በማና
ቸውም ከተማ እና መንደር ይካሄዳል ። የመልካም
ሰዎች ጥንካሬ ወሰን የለውም ። የድል-አድራጊነት ጊዜያ
ችን እስኪመጣ ድረስ ይኸ ተግባር የሚያድግ እና
በየጊዜውም ዕድገቱ እየጨመረ የሚሄድ ነው» አለች ።

ድምፅዋ ከፍ-ዝቅ ሳይል ተስተካክሎ የሚንቆረ
ቆር ሲሆን የዚያን ዕለቱን ደም እና ጉድፍ ከልቧ
ውስጥ ለመፋቅ ቀለማማ የሆኑት የምኞቷ ቱባ ክሮ
ች የሚጠነጠኑባቸው ይመስል ሃሣቧን የምትገልጥባ
ቸው ቃላቶች ሳያጥሩዋት ወዲያው-ወዲያው ይተነተኑ
ላት ነበር ። በተናገረቻቸው ቃላት እነዚህ ገበሬዎች
በስሜት የተነኩ መሆናቸውን ታስተውላለች ። ፊት-
ፊቷን እየተመለከቱ ካሉበት ቦታ ሳይንቀሳቀሱ ዐይኖ
ቻቸውን እርሷ ላይ ተክለው የምትናገረውን የሚያዳ
ምጡ ሲሆኑ ፤ አጠገቧ የተቀመጠችይቱ ሴት በስሜት
ተውጣ ቁና ቁና ስትተነፍስም ታደምጣታለች ። እና
ይኸ ሁኔታም የምትናገረውን እና ለሰዎቹ የምታወ

ራሳቸውን ጠንካራ በሆነ ዕምነት እንድታሰማቸው
አበረታታት...

«ኑሮአቸው ከባድ የሆነ ሰዎች ሁሉ ፤ በፍላጎት
እና በእጦተ የተጎሳቆሉ ሁሉ ፤ በሀብታሞች እና በሀብታ
ሞች አገልጋዮች ሕገ-ወጥ በሆነ ሁኔታ የሚረገጡ
ሁሉ — እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ ፤ ለወንድሞቻቸው
ሲሉ በየእሥር ቤቱ የሚሞቱትን እና ሥቃይ-ፍዳቸ
ውን የሚቀበሉትን ሰዎች መከተል አለባቸው ። ለራ
ሳቸው ሳይሳሱ እና ሳያስቡ የደስታ ጎዳና በየት
በኩል እንደሆነ ለሕዝቦች ያመለክታሉ ። ያለአንዳች
የማጭበርበር ሙከራ ‘ጎዳናው አድካሚ እና ውጣ-
ውረድ የሞላበት ነው’ በማለት እቅጩን የሚናገሩ
ሲሆኑ ይኸንን መሳዩን ጎዳናም ማንም ቢሆን ያለ
ፍላጎቱ እንዲጓዝ አያስገድዱትም ። ይሁን እንጂ አን
ድ ሰው ከእነርሱ ጋር በጎዳናው ላይ መጓዝ ከጀ
መረ ከቶ ምንም ቢሆን ከእነርሱ አይለይም ። ምክንያ
ቱም ፤ ጎዳናው ትክክለኛ የሆነ ጎዳና መሆኑን ይመለ
ከታልና ፤ ከዚህ ትክክለኛ ከሆነ ጎዳና በስተቀር ሌላ
ትክክለኛ የሆነ ጎዳና ከቶም የለም እና ነው!» በማ
ለት ተናገረች ።

ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ ለመፈጸም ስትመኘው የቆ
የችውን ጉዳይ በመፈጸም ላይ በመሆኗ ምክንያት
በስሜት ተዋጠች ። እርሷ ራሷ ለሕዝቦች ዕውነትን
በመግለጽ ላይ ነች!

«እነዚህን የመሳሰሉትን ሰዎች ያለ አንዳች ሥ
ጋት መከተል ትችላላችሁ ። ጥቃቅን በሆኑ ድሎች
የሚረኩ አይደሉም ። ማናቸውንም ዓይነት አታላይነ
ትን ፤ ስግብግብነትን እና ክፉ ተግባሮችን ጨርሰው
ሳያወድሙ የቆሙበትን ዓላማ የሚያቆሙ አይደሉም ።
‘እኔ የራሴ አዛዥ-ናዛዥ ነኝ! ለሁሉም በትክክል የሚ
በይን ሕግን እኔው ራሴ አወጣለሁኝ!’ በማለት ሰዎች



ትከሻ ለትከሻ ገጥመው በአንድ ድምፅ እስካላሰሙ
ድረስ እጃቸውን አጣጥፈው ተግባራቸውን ከማከናወን
አይቆጠቡም!» በማለት ተናገረች ።

ድንገት ድካም ተሰማት ። ንግግሯን አቋረጠች እና
አድማጮቿን ትመለከት ጀመር ። የተናገረቻቸው ቃላት አን
ዳቸውም መሬት አለመውደቃቸውን በመገንዘቧ በደ
ስታ ተመላች ። አሁንም-አሁንም ትናገራለች እያሉ
ሰዎቹ እርሷን-እርሷን ይመለከቷታል ። ፒዮትር አሁ
ንም እናት እየተናገረች የሚያዳምጥ ይመስል እጆቹን
ደረቱ ላይ አድርጐ ዐይኖቹን ጠበብ አድርጐ እና
ፈገግ ብሎ ስቴፓን አንድ እጁን ደረቱ ላይ ሌላኛ
ውን ደግሞ ጠረጴዛው ላይ አስደግፎ ያዳምጣል ። ፊ
ቱ ላይ ጥላ ስለአረፈበት ፊተ ሙሉ መስሎአል ።
እናት አጠገብ የተቀመጠችይቱ ሚስቱ ክንዶቿን
ጭኖቿ ላይ አድርጋ መሬት-መሬቱን በማስተዋል
ተቀምጣለች ።

«ጉዳዩ እንዲህ ነው ማለት ነዋ!» አለ ፒዮትር
አግዳሚው ወንበር ላይ ጠጋ እያለ ።

ስቴፓን ቀጥ ብሎ ቀና አለ ። ሚስቱን ተመለከተ ።
ከዚያም በዚያ ያሉትን ሁሉ ለማቀፍ የከጀለ ይመስል
እጆቹን ዘረጋ...

«ይኸንን በመሰለ ተግባር አንዴ ከተጠመድክ ፤
ሁለንተናህን ለእርሱ መስጠት አለብህ ማለት ነው»
በማለት በሃሣብ ተውጦ ተናገረ ።

«ወደኋላ መመልከት አይኖርም!» በማለት ፒዮትር
አባባሉን በመደገፍ ተናገረ ።

«ብዙ ሰዎችን በውስጡ የሚያካትት ተግባር
ይመስላል!» በማለት ስቴፓን ተናገረ ።

«መላውን ዓለም በውስጡ ያካትታል!» በማለት
ፒዮትር መለሰ ።

## 18

አንዳንድ ነገሮችን የሚያደንቁባቸውን ቃላት እናት
በመስማት ግድግዳውን ለጀርባዋ ሰጥታ እና እራሷን
ቀና አድርጋ ተቀምጣለች ። ታትያና ከተቀመጠችበት
ተነሳች ። እናትን መልከት አደረገቻት እና እንደገና
ተቀመጠች ። ሰዎቹን በጥላቻ እና ደስተኛ ባለመሆን
ስትመለከታቸው አረንጓዴ ቀለም ያላቸው ዐይኖቿ
ቀዝቀዝ የማለት ሁኔታ ይታይባቸው ነበር ። ድንገት
ወደ እናት ዞር ካለች በኋላ ፡ —

«በጊዜዎ ብዙ ሀዘን የቀመሱ መሆን አለብዎ!»
አለቻት ።

«አዎን ። ብዙ ቀምሻለሁኝ!» በማለት እናት መለሰ
ችላት ።

«ሲናገሩ መስማት እሻለሁኝ ። ከአንደበትዎ የሚወ
ጡት ቃላት የልብ ውጥረትን ያረግባሉ ። አቤቱ ፈጣ
ሪ ! እርስዎ እንደዚህ የሚያወሩላቸውን ሰዎች በጭላ
ንጭል ውስጥ እንኳን ለመመልከት ኧረ ምን-ዋጋ
በከፈልኩኝ ፤ እና ከራሷ ከሕይወትም እንጂ ። እኛ እዚ
ህ ምን እናያለን? እኛ የበግ መንጋ እንደማለት ነን!
ሌላ ምንም አይደለንም! እኔን እንደምሳሌ አድርገው
ይውሰዱኝ ። መጻፍ እና ማንበብ አውቃለሁኝ ። መጻሕ
ፍት አነብባለሁኝ ። ብዙም እመራመራለሁኝ ። በሃሣብ
እየተዋጥኩኝ እንቅልፍ የማልተኛበት ጊዜ አለ ። ግን
ምን-ዋጋ አለው? ማሰብ-ማሰላሰሌን ብተው ያለ አንዳ
ች ፋይዳ እጠወልጋለሁኝ ። ማሰቤን ብቀጥልም እንደው
ዋጋ ቢስ ለሆነ ጉዳይ ነው» አለች ።

ዐይኖቿ ላይ ምጸት ይታይ ነበር ። አንዳንድ ጊዜ
ም ከአንደበቷ የሚወጡትን ቃላት ትረግጣቸው
ነበር ። ወንዶቹ ምንም አልተናገሩም ። ነፋሱ በስተመ
ስኮቱ በኩል አፏጨ ፤ በቤቱ የጭስ ማውጫ በኩል
የሚያጉረመርም ሲሆን ጣራው ላይ ያለውን



ሣርም ያመሳቅላል ። ውሻ ጮኸ ። አሁንም-አሁንም የዝ
ናብ ጠብታ መስኮቱን ይገርፈዋል ። የፋኖሱ ብርሃን
እንደገና ብሩኅ እና ድምቅ ሁኖ ለመብራት ድብዝዝ
ፍዝዝ ከማለቱ የተነሳ ሊጠፋ ምንም አልቀረውም ።

«እርስዎ ሲናገሩ ስሰማዎት ከራሴ ጋር እንዲህ
በማለት ተወያየሁኝ ፡ — ሰዎች ከተፈጠሩ አይቀር እን
ዲህ ነው! የሚገርም ነው ። ግን ያሉትን ሁሉ የማውቅ
መሰለኝ ። ይሁን እንጂ ከዚህ ቀደም ይኸንን እርስዎ
የተናገሩትን የማላውቅ ከመሆኑም በስተቀር እኔ
ራሴም ብሆን ይኸንን የመሰለ ሀሣብ በአዕምሮዬ
ውስጥ አላመላልስም ነበር...» አለች ።

ስቴፓን ኮስተር ብሎ እና ዝግ ባለ ድምፅ የሚ
ከተለውን ተናገረ ፡ —

«ታትያና ፤ የሚበላ ነገር ቀማምሰን መብራቱን
ብናጠፋ ይሻላል ። በዛሬው ምሽት የነቹማኮብ መብ
ራት አለወትሮው ምሽቱን ሙሉ ምነው ያበራል ብለ
ው ጎረቤቶች ይገነዘቡ ይሆናል ። እኛን አይጎዳንም ።
እርሳቸውን ግን ሊጎዳቸው ይችላል ።»

ታትያና ከተቀመጠችበት ተነስታ ወደምግብ ማብ
ሰያው ሄደች ።

«አዎን ጎረቤት ፤ በእነዚህ ቀናት እርምጃችንን አስተ
ውለን መራመድ አለብን» በማለት ፒዮትር ፈገግ
በማለት ተናገረ ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«እነዚህ ጋዜጦች እንደተገኙም...» እንዳለ ስቴፓን
ቀበል አደረገ እና ፡ —

«የማስበው ስለራሴ አይደለም ። እኔን ቢይዙኝ ይኸ
ንንም ያህል ትልቅ ጉዳት አላደርስም» አለው ።

ሚስቱ ወደጠረጴዛው መጣች ።

«ተነስ» አለችው ።

ከተቀመጠበት ተነስቶ ጠረጴዛውን ስታዘጋጅ ተመ
ለከታት ።

«እኔ እና አንተ የምናወጣው ዋጋ ቢኖር በየነፍስ ወከፍ አምስት-አምስት ኮፔክ ሲሆን ፤ ይኸውም ብዙዎች ስንሆን ነው...» በማለት በምጸት ንግግር እየሳቀ ተናገረ ።

እናት አዘነችለት ። ይበልጥ ባየችው ቁጥር ይበልጥ ደስ ይላት ጀመር ። ካደረገችው ንግግር በኋላ የእለቱን ጉድፍ አጽድታ የታጠበች መስሎ ተሰማት ። በራሷ የተደሰተች ከመሆኗም በስተቀር ለማንም ሰው ቢሆን በጎ ታስብ ጀመረች ። ከዚያም የሚከተለውን ተናገረች ።

«እርስዎ ልክ አይደሉም ። ደምዎን የሚመጥጡት ሰዎች የተመኑልዎትን ዋጋ እሺ ብለው መቀበል የለብዎትም ። የገዛ ራስዎን ዋጋ አውጥተው መተመን አለብዎት ። በገዛ ራስዎ ውስጥ የሚገኘውን የሚያወጡበትን ዋጋ መተመን አለብዎት ። ጠላቶችዎ ስለእርስዎ የተመኑትን ሳይሆን ወዳጆችዎ ስለእርስዎ የተመኑትን ዋጋ ማወቅ አለብዎት...» አለችው ።

«እኛ ምን ጓደኞች አሉን እና ነው?» በማለት ለስለስ ባለ ሁኔታ ሰውዬው ተናገረ ።

«እስከመጀመርያው ኩርማን ድረስ...» አለ ።

«ጓደኞች አለን ነው ብዬ የምናገር እኮ...» አለችው ።

«አዎን ። ምናልባትም ይኖሩን ይሆናል ። ግን እዚህ የሉንም!» በማለት እያሰበ መለሰ ስቴፓን ።

«እዚህ ያገኟቸው ዘንድ ለምን አይሞክሩም?» አለች ።

ስቴፓን መልስ ከመመለሱ በፊት ለአፍታ ያህል አሰበ ። ከዚያም ፡ —

«እ? አዎን ማድረግ ያለብን ይኸንን ሳይሆን አይቀርም...» አለ ።



«ቁጭ በሉ እራት ደርሶአል!» በማለት ታትያና ተናገረች ።

እራት በሚበሉበት ጊዜ ፤ ቀደም ሲል እናት በተናገረችው ንግግር በጥልቅ በመነካቱ ፒዮትር እንዲገና በደስታ ተዋጠ ።

«እናት ፤ ማንም እንዳያስተውልዎ ጧት ማለዳው ላይ መሄድ አለብዎ ። እስከሚቀጥለው ጣቢያ ድረስ ከተማውን ሳይነኩ እንደው ዝም ብለው ቀጥታውን ይገስግሱ ። በፖስታው ጋሪ ይጓዙ...» አለ ።

«ለምን ብለው? እኔ አደርሳቸዋለሁኝ» በማለት ስቴፓን ተናገረ ።

«የለም! አንተ ማድረስ የለብህም ። ‘ምሽቱን ያሳለፈችው አንተ ዘንድ ነው ወይ?’ ‘አዎን እኔ ዘንድ ነው ።’ ‘የት ነው ያለችው አሁን?’ ‘መሳፈርያው ጣቢያ ድረስ አድርሼአታለሁኝ ።’ ‘አሃ! እንድታመልጥ ያደረግሃት አንተ ነህ ማለት ነዋ! መባባል ይመጣል! ከዚያም ወደ እሥር ቤት ትወርዳለህ!’ ገባህ? እሥር ቤት ለመግባት መቸኮል ምንም ዋጋ የለውም ። ለሁሉም ጊዜ አለው ። እንደሚተረከው ሁሉ ጊዜው ሲደርስ ኮከብም ቢሆን ይሞታል ። አሁን ግን ምሽቱን አሳልፉ ፤ ነገ ሠረገላቸውን ተከራይተው ራሳቸው ይሄዳሉ ። የእኛ መንደር ዋናው መንገድ ላይ ስለሆነ ብዙ ሰዎች እያረፉ ይሄዳሉ ። በዚህ በኩል አያሳስብም» አለ ፒዮትር ።

«ፒዮትር ፤ ለመሆኑ ፈሪነትን እንዲህ ማን አስተማረህ?» አለችው ታትያና ።

«ጎረቤቴ ሆይ ፤ አንድ ሰው ሁሉንም ነገር ማወቅ አለበት ። መቼ ፈሪ እንደሚሆን መቼ ደግሞ ደፋር እንደሚሆን ማወቅ አለበት!» በማለት ፒዮትር ጉልበቱን እየነካካ ተናገረ ። «ያንን ጋዜጣ ቫጋኖቭ ይዞ ስለተገኘ ሰማይ-ምድሩን እንዳዞሩበት አታስታውስምን? አሁን ለፍቅርም ሆነ ለገንዘብ መጽሐፍ በእጁ እንዲ

ይዝ ልታደርገው አትችልም ። እናት ፤ ይመኑኝ ። የወጣልኝ ዱርዬ ነኝ ። እነዚያን የእናንተን ጋዜጦች እርስዎ የፈለጉትን ያህል ቢያሸክሙኝ በየተገቢው ቦታዎች ማዳረስ እችላለሁኝ ። የእኛ ሰዎች ብዙዎቹ የማያነብቡ መሆናቸው ዕውነት ከመሆኑም በስተቀር በተጨማሪ ደግሞ ፍርሃት አለባቸው ። አንዳንድ ጊዜ ግን በጣም መጨመት የሚበዛብዎት በመሆኑ ምክንያት ዐይኖችዎን ከፍተው ኧረ ምን ማድረግ ይሻላል የሚሉበት ጊዜ አለ ። እና እነዚህ ጽሁፎችም ግልጽ ባለ ሁኔታ ምን ማድረግ እንደሚሻል ይናገራሉ ፡ — አስብ! አዕምሮህን አሠራው! ማንበብ ከሚችሉት ይልቅ የማይችሉት ፤ በተለይም ደግሞ ሙሉ ዕምነት ያላቸው ይበልጥ ይመራመራሉ ። በዚህ ሀገር ውስጥ በሚገኙት ቦታዎች ሁሉ ተዟዙሬ ብዙ ተመልክቻለሁኝ ። ማናቸውንም ነገር ማድረግ እንችላለን ። ይሁን እንጂ ፤ ገና በውጥናችን ላይ እንዳንያዝ ከፈለግን ማናቸውንም ነገር ብልጠት በተመላበት ሁኔታ ማከናወን አለብን ። ገበሬዎች ወዳጅ እንዳልሆኗቸው ባለሥልጣኖቹ የወሬ-ወሬ ሳይሰሙ አልቀሩም ። ፍቅር አልባ የነበረውን ፈገግታ ገበሬዎች ፈገግ ማለታቸውን አቁመዋል ። እና በአጠቃላይ ገበሬው ከባለሥልጣኖች ጋር ያለውን ግንኙነት ለማቋረጥ የሚሻ ይመስላል ። አሁን በቅርቡ ስሞላኮቮ በተሰኘ ቦታ — እዚህ እኛ አጠገብ የሚገኝ መንደር ነው — ባለሥልጣኖቹ ግብር ሊሰበስቡ መጡ ። ገበሬዎቹም ዱላዎቻቸውን አንግበው ተቀበሏቸው! የፖሊሱ አዛዥ ምንም የሚሸሽገው ነገር የለም ። ሁሉንም አውጥቶ በመናገር 'እናንት ውሪ ውሾች! ንጉሡን በመቃወም ላይ ናችሁ ማለት ነው?' በማለት ያጓራል ። አንድ ገበሬ ነበር ። ስፒቫኪን ይባላል ። 'ከንጉሡ ጋር አብራችሁ ገሀነም ግቡ!' በማለት ፊት ለፊት ነገረው ። 'የለበስከውን ሸሚዝ ከላ



ይህ ላይ የሚገፍህ ንጉሥ ምን ንጉሥ ይባላል?' ይል ነበር ። እናት ፤ ይኸውልዎ ጉዳዩ እየገፋ እዚህ ደረጃ ደርሶአል ። እርግጥ ነው ስፒቫኪንን እሥር ቤት ወርውረውታል ። ከአንደበቱ የሚወጡትን ቃላት ግን ማንም ሊያጠፋቸው አልቻለም ። ወጣቶቹ እንኳን የተናገራቸውን ያስታውሱአቸዋል ። ከአንደበቱ የወጡት ቃላት ከአጽናፍ አጽናፍ እየጮሁ ይዘልቃሉ!» በማለት ተናገረ ።

ከቀረበው ምግብ አንዳችም አልበላም ። ከብልል — ከብልል በሚሉት አስደሳች በሆኑት በጥቋቁር የገበሬ ዐይኖቹ እናትን በመውደድ ስሜት ትክ ብሎ ያስተውላታል ። የመሀለቅ ገንዘቦች ከቦርሳ ውስጥ እንደሚያወጣ ሰው ስለገጠር ኑሮ የሚያውቀውን ሁሉ ዘርግፎ በለጋስነት አጫወታቸው ።

«ትንሽ ብትበላ ይሻልሃል...» በማለት ስቴፓን ሁለት ጊዜ ፒዮትርን ከንግግሩ አቋረጠው ።

ፒዮትር ሁለቱንም ጊዜ ቁራሽ ዳቦ እና ማንኪያውን ካነሳ በኋላ እንደምትዘምር ወፍ ተዝናንቶ ታሪኩን ያወራ ጀመር ። እራት እንዳበቃ ድንገት ከመቀመጫው ብድግ አለ ።

«እሺ ፤ እንግዲህ ልሂድ! እናት ደህና ይደሩ!» አላት እጅዋን እየጨበጠ ። ከዚያም ቀበል አድርጎ ፡ —

«ምንአልባትም እንደገና አንገናኝም ይሆናል ። አንድ ነገር ልገልጽልዎ እሻለሁኝ ። ከእርስዎ ጋር መገናኘቴ እና ንግግርዎን ማዳመጤ ለእኔ እጅግ ጥሩ ነው ። በሻንጣዎ ውስጥ ከወረቀቶቹ በስተቀር ሌላ ነገር አለበትን? የሱፍ ሻሽ ነው ሻንጣው ያለበት ። ይኸንን እንዳትረሳ ስቴፓን ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሻንጣዎን ስቴፓን ያመጣልዎታል ። እንሂድ ስቴፓን ። ደህና ይደሩ ። መልካም ጉዞ ይሁንልንዎ!» በማለት ፒዮትር ተናገረ ።

ከሄዱ በኋላ የበረሮዎቹ ውርውርታ ይሰማ ነበር ፡፡
ነፋሱ በጣርያዎቹ ላይ ሽው የሚል ከመሆኑም በስ
ተቀር በጭስ መውጫዎቹ ላይም ያፏጫል ፡፡ የካፊያ
ዝናብም መስኮቶቹን ይገርፋቸዋል ፡፡ ታትያና የእንጨት
ርብራብ አልጋ ከምግብ ማብሰያው ላይ አንስታ አግዳ
ሚው ላይ በመረብረብ የእናትን ምኝታ አዘጋጀችላት ፡፡

«የደስ-ደስ ያለው ወጣት ነው!» በማለት እናት
ተናገረች ፡፡ ታትያና ኮስተር ብላ አየቻት ፤ ከዚያም ፡ —

«ብዙ ይንቻቻል ፡፡ ምንም የሚያመጣው ለውጥ
ግን የለውም» አለች ፡፡

«ያንቺ ባለቤትስ?» በማለት እናት ታትያናን ጠየ
ቀቻት ፡፡

«ደህና ነው ፡፡ ጥሩ ሰው ነው ፡፡ አይጠጣም ፡፡ ደህና
ተስማምተን እንኖራለን ፡፡ ባሕርዩ ግን ደካማ ነው...»
በማለት ታትያና መለሰችላት ፡፡ ከዚያም ወደላይ ቀና
ብላ ቆመች ፡፡ ጥቂት ቆየት ካለች በኋላም ፡ —

«አሁን እኛ ምን ማድረግ አለብን? ማመጽ የለብ
ንምን? አለብን እንጂ! እየአንዳንዱ ለየራሱ ብቻውን
ቢያስበውም ፤ ሁሉም የሚያስበው ይኸንኑ ነው ፡፡ ሁሉም
ሰዎች ጉልህ ድምፅ እያሰሙ ይኸንን ማሰብ አለባ
ቸው ፡፡ አንዱ የመጀመርያውን እርምጃ መውሰድ አለ
በት...» አለች ፡፡

አግዳሚው ወንበር ላይ ተቀመጠች ፡፡ ቀጠል አደ
ረገች እና ፡ —

«ከወዝ-አደሮች ውስጥ ተደባልቀው እና ለወዝ-
አደሮችም ጽሁፎችን በማንበብ የመኳንንት ወገን
የሆኑት ወጣት ልጃገረዶቹም በዚህ ተግባር ይሳተፋሉ
ብለዋል ፡፡ ለመሆኑ እነርሱ የሀብታም ወገን ሁነው
ሳለ ሠርቶ-አደሮችን አይጸየፋምን? አይፈሩምን?» በማለት
ጠየቀች ፡፡



የእናትን መልስ ስትሰማ ታትያና ደህና አድርጋ
ትንፋሿን ተነፈሰች ፡፡ ዕይኖቿን እና ራሷን ወደመሬት
ቀለስ አደረገች ፡፡

«ካነበብኳቸው መጻሕፍት መካከል አንደኛው ላይ
'ትርጉም-የለሽ ሕይወት' የሚል አባባል ተጽፎ አገኘ
ሁበት ፡፡ ውዲያው አባባሉን ተገነዘብኩት ፡፡ ይኸንን መ
ሳዩ ሕይወት ምን ዓይነት ሕይወት እንደሆነ በሚ
ገባ አውቃለሁኝ ፡፡ ያለ እረኛ እንደተበታተኑ
በጎች ፤ የሕይወት ትርጉም ቢኖርም ብትንትኑ የወጣ
ነው ፡፡ ይኸ ነው የሕይወት ትርጉም ማለት ፡፡ እኔ ብች
ል ኖሮ አንዴም እንኳን ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳል
መለከት ወደፊት ሸምጥጬ ይህንን መሳይ ሕይወት
በሩጫ ባመለጥኩም ነበር ፡፡ ነገሮችን መገንዘብ ሲቻል
ሀዘንተኛ ያደርጋል!» አለች ፡፡

እናት ይኸንን አሳዛኝ ኑሮ በሴቲቱ አረንጓዴ ቀለ
ም ባላቸው ደረቅ ዐይኖቿ ነጸብራቆች እና ቅርተኛ
በሆነው ፊቷ ላይ ትመለከታለች ፡፡ ከአንደበቷ የሚወጣ
ውን ድምፅም ታደምጣለች ፡፡ ታጽናናት ዘንድ ፈለገች ፡፡
ስለዚህም ፡ —

«የኔ ውድ ፤ መውጫ መንገዱ ምን እንደሆነ ማወ
ቅ ከጀመርሽ ግን ቆይቶአል...» አለቻት ፡፡ ታትያና
የእናትን ንግግር በማቋረጥ ፡ —

«ይኸ ብቻውን በቂ አይደለም ፡፡ እንዴት መላቀቅ
እንደሚቻልም ማወቅ ያስፈልጋል ፡፡ እሺ ፤ አልጋዎ ተዘጋ
ጅቶአል!» አለቻት ፡፡

በሃሣብ ተውጣ እና ቀጥ ብላ በመቆም አንዳ
ችም ነገር ሳትናገር ማብሰያው አጠገብ ተገተረች ፡፡
እናት ከነልብሶቿ ጋደም አለች ፡፡ አካላቷ ከድካም
የተነሳ ዃትሎአል ፡፡ ስለዚህም በጥቂቱ አቃሰተች ፡፡ ታት
ያና መብራቱን አጠፋችው ፡፡ ከዚያም ኅጀዋ በጨለማ
ሲወረር ዝቅ ባለ ድምፅ እናትን ታወራ ጀመር ፡፡ ድም

ፅዋ የጭለማውን ጠፍጣፋ መልክ አንዳች ነገር ይጠርግለት ይመስል ነበር ።

«እርስዎ የመኻታ ፀሎት አያደርሱም ማለት ነው ። እኔም በእግዚአብሔር አላምንም ። በተአምራትም አላምንም» አለች ።

እናት በአንድ ጎኗ ገልበጥ አለች ። መጨረሻውን የማታየው ጭለማ በስተመስኮቱ በኩል አፍጥጦ ይመለከታታል ። ረጭ ባለው ፀጥታ ውስጥ ትናንሽ ድምፆች ፤ ትናንሽ ኮሽታዎች ይሰማሉ ። በፍርሃት ተውጣ ለታትያና የማንሾካሾክ ያህል እንደሚከተለው መልስ መለሰችላት ፡ —

«አምላክን በሚመለከት ረገድ ለማመን ላለማመኔ ይኸን ያህልም እርግጠኛ አይደለሁም ። በክርስቶስ ግን አምናለሁኝ ። ‘ጎረቤቶችህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ’ የሚሉትን የእርሱን የክርስቶስን ቃሎቹን አምንባቸዋለሁኝ ። በዚህ አምናለሁኝ!» አለቻት ።

ታትያና ዝም አለች ። እናት በሃሣቧ የታትያናን ቀጥ ያለ ቁመና ከማብሰያው አጠገብ ሁና በዚያ ጭለማ ታሳላስላለች ። የማትንቃነቅ ሁና አለችበት በመርጋት ቆማለች ። እናት ዐይኖቿን በሀዘን ጨፈነች ። ድንገት ሴቲቱ የሚከተለውን ቀዝቀዝ ባለ አነጋገር ስትናገር ሰማቻት ፡ —

«በልጆቼ ላይ ባደረሱባቸው ሞት ምክንያት ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሰው ከቶ ምንም ጊዜ ይቅርታ አላደርግላቸውም ። ምንግዜም ቢሆን!» አለች ።

ከእነዚህ ቃላት በስተጀርባ ያለው የታትያና ሕመም እናትንም ተሰምቷት ጋደም ካለችበት ቀና አለች ። ከዚያም ፡ —

«አንቺ አሁንም ገና ወጣት ነሽ ። ሌሎች ልጆች ትወልጃለሽ» አለቻት ትሕትና ባልተለየው ሁኔታ ።

ታትያና ለጥቂት ጊዜ ዝም አለች ። ከዚያም ፡ —



«የለም! ከእንግዲህ ልጆች አልወልድም ። ስንኩል የሆነ ነገር ማሕፀኔን አጋጥሞታል ። ከእንግዲህ ልጆች እንደማልወልድ ዶክተሩ ነግሮኛል...» አለች ።

ወለሉ ላይ አይጥ ያንጎዳጉድ ጀመር ። በማይታይ የድምፅ ነፀብራቅ አንድ ነገር ወደቀ እና ሰፍኖ የነበረውን ፀጥታ አደፈረሰው ። አሁንም አላርፍ ብለው እንደሚቅበጠበጡ ጣቶች የዝናሙ ድምፅ ጣርያው ላይ ቿ-ቿ-ቿ ሲል ይሰማል ። በበልግ ምሽት የውሀ መሥመር ሠርተው በዝግታ የሚንቆረቆሩት የዝናብ ፍሳሾች ድምፅም ጩሩር ሲሉ ይሰማሉ ...

እናት እንቅልፍ ይዞአት ማንጎላጀት እንደጀመረች ከበስተውጪ በኩል ከበድ ያለ የጫማ ድምፅ ተሰማት ። ከዚያም ድምፁ እየተጠጋ ከበራፉ ደረሰ ። በሩ በጥንቃቄ ሲከፈት ተሰማት ።

«ታትያና ፤ ተኝተሻል እንዴ?» የሚል የወንድ ድምፅ ተሰማ ።

«አልተኛሁም ።»

«እርሳቸውስ ተኙ እንዴ?»

«አዎን ። ሳይተኙ አልቀሩም ።»

ፋኖሱ በራ ። ብዥ-ብዥ እያለ በጨለማው ተዋጠ ። ገበሬው ሰው ወደ እናት ዘንድ ሂዶ ተጠጋ እና እግሯ ላይ ደርባው የነበረውን ኮት አመቻችቶ አስተካከለላት ። ለእርሷ ባለው አሳቢነት ልቧ ተነካ ። ፈገግ እያለች ዐይኖቿን እንደገና ጨፈነች ። አንዳችም ቃል ሳይተነፍስ ስቴፓን ልብሱን አወላልቆ ርብራቦ አልጋው ላይ ወጣ እና ተኛ ። ሁሉም ነገር ጭጭ-ም ጭጭ አለ ።

እናት እዛው እተጋደመችበት ሁና ወዲያ-ወዲህ ሳትንቀሳቀስ ሕልም ውስጥ ያለች የሚመስለውን ፀጥ ያለ ምሽት ይሁነኝ ብላ የምታዳምጥ ስትሆን ፤ ከፊት-ለፊቷ ዐይኖቿ ላይ በደም የተነከረው የሪቢን ፊት ድቅን ብሎ ይታያታል ።

እርብራቦው አልጋ ላይ ባል እና ሚስት ሲንሾ
ካሾኩ ይሰማል ፡ —

«በእንደዚህ ዓይነቱ ተግባር እንደምን የመሰሉ
ሰዎች እንደሚሳተፉበት አስተዋልክ ፤ አይደለምን? ሕይ
ወታቸውን ሙሉ ሲዋትቱ የኖሩ እና የችግርን ጽዋ
የቀመሱ አዛውንቶች ይሳተፉበታል ። የእነርሱ ዕድሜ
ዕረፍት ማድረግ የሚፈቅድላቸው ሲሆን እነርሱ ግን
ደከመኝ ማለት ሳያውቁ በዚህ ተግባር ይሳተፋሉ ።
ስቴፓን ፤ አንተ እኮ ወጣት እና ብልህ ነህ!»

«መጀመርያ በጉዳዩ ማሰብ ማሰላሰል አለብኝ...»
በማለት ገበሬው ጎላ ባለ ድምፁ መለሰ ።

«እርሱንማ ከዚህ ቀደምም ነግረሽኛል...» አለ
ችው ።

ለጥቂት ጊዜያት ድምፃቸውን አጠፉ ። ከዚያም ስ
ቴፓን የሚከተለውን ይናገር ጀመር ፡ —

«የአጀማመሩ ሁኔታ እንደሚከተለው ይሆናል ፡ —
መጀመርያ ገበሬዎቹን ለየብቻ ማነጋገር ። ለምሳሌ አሌ
ክሴይ ማኮቭን ። እርሱ ማንበብ ይችላል ። መንፈሰ-
ጠንካራ ነው ። በባለ ሥልጣኖች ላይ ያለው ጥላቻ
ከፍተኛ ነው ። ሠርጌይ ሾሪን ቢሆንም እንደ አሌክ
ሴይ ማኮቭ ነው ። ብልህ ገበሬ ነው ። ክንያዜቭም
ቢሆን ሀቀኛ ከመሆኑም በስተቀር ፈሪ አይደለም ።
ለመጀመር ከእነዚህ ጋር ይበቃል ። እናት የነገሩንን
ዓይነት ሰዎች ተገናኙትን ግንኙነት መፍጠር አለ
ብን ። እኔ ተጨማሪ አበል ለማግኘት በእንጨት ፈላ
ጭነት ተግባር የተሠማራ ሰው በመምሰል መጥረቢ
ያዬን ትከሻዬ ላይ አንግቤ ወደ ከተማ በመሄድ
እነዚህን ዓይነት ሰዎች እፈልጋለሁኝ ። በጣም ጠን
ቃቃ መሆን አለብን ። አንድ ሰው ዋጋው የሚገመተ
ው በሥራው መጠን ነው በማለት እናት የተናገሩት
ንግግር ትክክል ነው ። እስኪ ያንን የዛሬውን ሰውዬ



እንደምሳሌ አድርገሽ ውሰጂው ። ከፈጣሪ አምላክ
ፊት ቢያቆሙት እንኳን የሚበገር ሰው አይደለም ።
ያ ኒኪታ ቢሆንስ? ሕሊና ያለው መሆኑን አሳይቶ
አል ። ይኽንን ለመሆኑ ማን ያሰበው ነበር!» አለ ።

«ዐይናችሁ እያየ አንድን ሰው አፈር-መሬት ሲያ
ስግጡት ፤ እናንተ ግን አፋችሁን ከፍታችሁ ዝም ብላ
ችሁ ታስተውላላችሁ» አለችው ።

«ቆዪ እንጂ ፤ ምነው አንቺ ደግሞ! ያንን ሰው እኛ
ው ራሳችን መልሰን ባለመደብደባችን ልተደሰቺ
ይገባል ። ምን ማለትሽ ነው! ወይ ጉድ!» አላት ።

ረዘም ላለ ጊዜ ለሚስቱ ማውራቱን ቀጠለ ። አን
ዳንድ ጊዜ ሲያወራ ዝቅተኛ በሆነ ድምፅ ስለሆነ
እናት የምትሰማው ድምፁን እንጂ ምን እንደሚናገር
ለማዳመጥ አትችልም ። እንደገና ደግሞ ጎላ ባለ ጎር
ናና ድምፁ ያወራል ። ብዙውን ጊዜ ሚስቱ ፡ —

«ሽ! ቀስ ብለህ አውራ እንዳትቀሰቅሳቸው!» ትለዋ
ለች ።

ደመና ከሰማይ ወርዶ ይዞአት የሄደ ያህል እናት
ን እንቅልፍ ይዞአት ጭልጥ አለ ።

ነግቶ ቡናማው የጧት ማለዳ በጭላንጭሎቹ ወደ
ጎጆው ማሾለቅ ሲጀምር ታትያና እናትን ከምኝታዋ
ቀሰቀሰቻት ። የምሽቱን ማብቃት የሚያበሥረው የቤተ
ክርስቲያን ደወል ቀዝቃዛውን ፀጥታ እየሰነጠቀ በመን
ሳፈፍ ድምፁ ኪው! ኪው! ኪው! ሲል ይሰማ ጀመር ።

«ሳሞቫሩን አያይዣለሁኝ ። አንድ ብርጭቆ ሻይ
ይጠጣሉ ። ወዲያው እንደተነሱ ጉዞ ቢጀምሩ ብርዱን
አይችሉትም...» አለች ታትያና ።

ስቴፓን የተንጨበረረ ጢሙን እያበጠረ የእናትን
የከተማ አድራሻ ጠየቃት ። ፊቱ ሌሊቱን ከበፊቱ
ይበልጥ ሞላ ብሎ አድሮ መገኘቱን አስተዋለች ።

«ወይ ጉድ ፤ ግርም የሚል አጋጣሚ ነው እኮ!

ይገርማል!» አለ ስቴፓን ሻይ በመጠጣት ላይ በነበሩበት ጊዜ ፈገግ እያለ ።

«ምኑ?» አለችው ታትያና ።

«እንደው እንዲህ በቀላሉ በቀናነት ልንተዋወቅ መብቃታችን...» በማለት መለሰላት ።

«ከተግባራችን ጋር በተያያዘው በማናቸውም ነገር ውስጥ ይኸንን የመሰለ መዘባነን የሌለበት የቀናነት ሁኔታ ይገኝበታል» በማለት እናት በሃሣብ ተውጣ ተናገረች ።

እናትዅ ሊሰናበቱ ሲቃረቡ ባል እና ሚስት ዝምታ ውጦአቸው አደብ ገዝተው ነበር ። የሚያወሩት ወሬ ብዙም አልነበረም ። ይሁን እንጂ ለየጥቃቅኑ ጉዳዮች ሁሉ ለእናት ምቾት ምን ያህል እንደሚያስቡ ያስታውቅ ነበር ።

ይኸ ገበሬ ተግባሩን ማከናወን የሚጀምረው ጠንቃቃ ሁኖ ፤ አንዳችም ኰሽታ ሳያሰማ እንዳይነቃበት ልክ እንደፍልፈል ተጠንቅቆ እና አድፍጦ ሲሆን ፤ ነገር ግን ደግሞ ደከመኝን በማያውቅ ረገድ እንደሆነ ገና ካሁኑ ሁኔታው እናትን በሃሣቧ እየመጣ በፈረስ የሚጎተተው ሠረገላ ላይ እንደተቀመጠች ታያት ። የሚስቱ የቅሬታ ድምፅ ደግሞ ሁል ግዜም ጆሮዋ ውስጥ እየገባ ደወሉን ይደውልባታል ። አረንጓዴማ ዐይኖቿ የሚንቦገቡጉትን እሳት ማንደዳቸውን የሚቀጥሉ ሲሆኑ ፤ በልጆቿ መሞት ምክንያት በልቧ ማጎደር የተቀረጸው የተኩላ መሰል ቁጭትም በሕይወት እስካለች ድረስ ከቶ ምንም ቢሆን ከልቧ አይፋቅም ።

ሪቢን ትዝ ብሏት አስታወሰችው ። ቁስሎቹ ፤ ፊቱ ፤ እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው የነበሩት ዐይኖቹ እና ከአንደበቱ ይወጡ የነበሩት ቃሎቹ ትዝ እያሏት ድቅን ይሉባት ጀመር ። ይኸንን የመሰለ ጭካኔ ሲፈጸም ረዳት-አልባ ሁኖ መገኘት እጅጉን አሳዘናት እና



ልቧ ኩምትርትር አለ ። ወደከተማ በምታደርገው ጉዞዋ በሙሉ ያንን እንደቡና ግራጫ የሆነ ቀን ዘልሎ እየተራመደ የሪቢን ምስል ከፊቷ ላይ እየመጣ ድቅን ይልባት ጀመር ። ጠንካራ የሆነ ግትርነቱ ፤ ጥቁር ጢሙ ፤ የተቀዳደደ ሸሚዙ ፤ ደም የሚፈስስበት ግንባሩ ፤ ወደኋላው የታሠሩት እጆቹ — ለቆመለት ዕውነት በቁጣ እና በተስፋ የተመላው ይህ ሰው ከፊት-ለፊቷ ድቅን ብሎ በሃሣቧ ታያት ። በዚች ዓለም ላይ በየቦታው እንደነገሩ ሸንጥ-ሸንጥ ተደርገው የተቀለሱ አያሌ መንደሮች ፤ የፍትሕን መምጣት መቃረብ በምስጢር ሁነው የሚጠባበቁ ሰዎች ፤ እና እንደዚሁም ያለ አንዳች የተሻሻለ የወደፊት ተስፋ ትርጉም-የለሽ በሆነ መንገድ መላ ሕይወታቸውን በዝምታ ስለሚያሳልፉት ሥፍር-ቁጥር ስለሌላቸው ብዙ ሺህ ሕዝቦች ሁኔታ እናት ታስብ-ታሰላስል ጀመር ።

ሕይወት ገና እንዳልታረሰች ድንግል መሬት ልሳኑ-ድፍን ዱዳ በመሆን አራሽ ገበሬዋን ፡ —

«የዕውነትን እና የዕውቀትን ዘር በውስጤ ዝራብኝ ፤ ከዚያም በኋላ የድካምህን ዋጋ ብዙ መቶ እጥፍ አድርጌ እከፍልሃለሁኝ!» በማለት ነፃ እና ሀቀኛ የሆኑ ሰዎችን የምትጠይቃቸው መስሎ ተሰማት ።

እርሷ በበኩሏ ያደረገችው ጥረት ያስገኘላትን መሳካት ስታሰላስል ፤ አይ ፤ ይኸን ያህል ምን ፈጸምኩ እና ነው በሚል በቅን-ትሁትነት ከቁም-ነገር ላለመቁጠር ብትሽም ሁኔታው ትንሽ የደስታ ስሜት ለልቧ ፈነጠቀላት ።

## 19

ኒኮላይ መጽሐፉን እጁ ላይ አጠፍ አድርጎ በሩን ከፈተላት ። በደስታ ተውጦ ሰላምታ እየሰጣት ፡ —

«እንዴት እንዲህ አፈጠነዎት? እንዲህ ቶሎ ይመጣሉ ብዬ አልጠበቅሁኝም ነበር!» አላት ።

የደግነት ሁኔታ የሚታይባቸው ዐይኖቹ በመነጽሩ ውስጥ ክፍት-ዝግት በማለት ይርገበገባሉ ። የምታስቀምጠውን እና የምታወልቀውን በመቀበል እያገዛት በማፍቀር ፈገግታ ይመለከታታል ።

«ትላንትና ማታ ቤታችንን ፈተሹት ። በእርስዎ ላይ አንድ ነገር ደርሶብዎት ይሆናል ብዬ ሰግቼ ነበር ። እኔን ግን ይዘው አላሠሩኝም ። እርስዎ ተይዘው ቢሆን ኖሮ እኔንም ይወስዱኝ ነበር!» አላት ።

ወደ ምግብ ቤት እየወሰዳት ወሬውን ማውራቱን ቀጠለ ፡ —

«ከሥራዬ የምባረር መሆኔ እንደሆን የማይቀር ጉዳይ ነው ። ይኸ ግን እኔን አያበሳጨኝም ። ወንበር ላይ ተወዝፌ ፈረስ የሌለውን ገበሬ ብዛት መቁጠሩ ስልችት ብሎኛል!» አላት ።

አንድ በቁጣ የተዋጠ እና እንደ ጎልያድ ጠንካራ የሆነ ሰው መጥቶ የቤቱን ግድግዳዎች ያወዛወዛቸው ይመስል ፤ በቤቱ ውስጥ ያሉት ነገሮች ሁሉ ምስቅልቅላቸው ወጥቶ እዚያ እና እዚህ በመበታተን ተዘበራርቀዋል ። የግድግዳ ስዕሎች መሬት ተወርውረዋል ። የግድግዳ ወረቀቶች ተቀዳድደዋል ። ገሚሶቹ በክር መሳይ ታብተዋል ። አንዱ ቦታ ላይ የወለሉ ሳንቃ ተፈንቅሎአል ። የመስኮቱ ደፍ ተነቅሎአል ። ምግብ ማብሰያው ላይ ያለው አመድ ተዝቆ ወለሉ ላይ ፈስሶአል ። ለእናት እንግዳ ባልሆን እና ከዚህ ቀደምም እየተፈጸመ ባስተዋለችው ይኸንን መሳይ ድርጊት በመገረም ራሷን እየነቀነቀች በኒኮላይ ላይ ከዚህ ቀደም ያላየችበትን አዲስ ባሕርይ ትክ-ብላ ታስተውላለች ።

ሳሞቫሩ ቀዝቅዞ ካልታጠቡ ሲኒዎች ጋር ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦአል ። በሳህን ላይ ሳይሆን በወረቀት ላይ አይብ እና ቋሊማ ተቀምጦአል ። በጠረጴዛው ልብስ ላይ መጻሕፍት ፤ የዳቦ ፍርፋሪዎች



እና የከሰል ፍርካሾች ተበታትነዋል ። እናት በመጠኑ ሳቅ እንደማለት አለች ። ኒኮላይም ሀፍረት በተሰማው ሁኔታ ሳቅ አለ ። ከዚያም ፡ —

«እናት ፤ እርግጥ ነው ። እነርሱ ያመሰቃቀሉት ሳያንስ እኔ ደግሞ ይባስ ብዬ ቤቱን ዝርክርኩን አውጥቼዋለሁኝ ። ዕቃዎቹን ከየተበታተኑበት ቦታ ሰበሳስቤ በወግ-በወጉ እስካሁን ሳላዘጋጅ የቀረሁት እንደገና ሊፈትሹ ይመጣሉ ብዬ በማሰብ ነበር ። እሺ ፤ ለመሆኑ ጉዞዎ እንዴት ነበር?» አላት ።

ጥያቄው ልቧ ውስጥ ገብቶ እንደ አሎሎ ተጫናት ። አሁንም እንደገና የሪቢን ምስል ፊቷ ላይ ድቅን ብሎ የታያት ሲሆን ፤ ልክ እንደመጣች ስለ ደረሰው ሁኔታ ባለመንገሯ ሀፍረት ተሰማት ። ወንበር ላይ ቁጭ ብላ ወደ ኒኮላይ ጎንበስ በማለት እና የመረበሽ ስሜት እንዳያድርባት በመጣር አንድም ሳታስቀር የደረሰውን ድርጊት ሁሉ ዘክዝካ መንገር ጀመረች ።

«ሪቢን ተያዘ...» አለች ።

የኒኮላይ ፊት ልውጥውጥ አለ ።

«ኧረ?» አለ ።

እናት የኒኮላይን ንግግር እጇዋን በማንቀሳቀስ አቋረጠችው ። ከዚያም ፍትሕ ፊት ቀርባ በአንድ ሰብአዊ ፍጡር ላይ ሲፈጸምበት ያስተዋለችውን ግፍና ስቃይ እየዘረዘረች በማስረዳት ላይ ያለች በሚመስል ሁኔታ ንግግሯን ቀጠለች ። ፊቱ የገረጣው ኒኮላይ ወንበሩ ላይ ወደኋላው መዘዝ እያለ ከንፈሩን ይነክሳል ። መነጽሩን ዝግ ባለ ሁኔታ አወለቀ እና ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ ። ከዚያም የማይታይ የሸረሪት ድር እየፈለገ የሚጠርግ ይመስል ፊቱን ቀስ እያለ ያብስ ጀመር ። ድንገት ፊቱ ኩስትር አለ ። አገጩ ሹጥጥ ብሎ ወጣ ። የአፍንጫው ቀዳዳዎች ይርገበገቡ ጀመር ።

ከዚህ ቀደም እናት እንደዚህ ሁኖ አይታው አታውቅም ነበር ። አኳኋኑ አስፈራራት ።

አውርታ እንደጨረሰችለት ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ በመነሳት የተጨበጡ እጆቹን ሱሪው ኪሶች ውስጥ በጣም አስገብቶ ክፍሉ ውስጥ ከወዲያ-ወዲህ ይንቆራጠጥ ጀመር ። ከዚያም ጥርሶቹን አጋጥሞ እያፋጨ ፡ —

«ትልቅ ሰው መሆን አለበት ። የእሥር ቤቱ ሁኔታ ሊያስቸግረው ይችላል ። እርሱን ለመሳሰሉት ሰዎች እሥር ቤትን መላመድ ያስቸግራቸዋል!» አለ ።

ብስጭቱን ለማስታገስ እጆቹን በኃይል እየጨበጠ ወደታች መጫኑን የቀጠለ ሲሆን ይህ እርሱ የሚታይበት በብስጭት የመነሳሳት ሁኔታ እናትንም አነሳሳት ። እንደአንካሴ ጫፍ ሹል እስኪሆኑ ድረስ ዐይኖቹን ጨልጨል በማድረግ ዘጋቸው ፣ ሲናገር ቀዝቀዝ ባለ ቁጣ ሲሆን ከወዲያ ወዲህ መመላለሱንም ቀጠለ ። ከዚያም ፡ —

«እንዴት አሰቃቂ እንደሆነ እስኪ ያስተውሉት! እፍኝ የማይሞሉ ደደቦች በስብሶ ፍርክስክሱ የወጣ የገዢነት ሥልጣናቸውን በሕዝቦች ጫንቃ ላይ ዘፍዝፈው ለማቆየት ሲሉ ያሻቸውን ሰው እያፈሱ ይደበድባሉ! ያሰቃያሉ! ይገድላሉ! አረመኔነት እየጨመረ የሄደ ሲሆን ጭካኔም የዘወትር ተግባር ሁኖአል ። እስኪ ልብ ብለው ያስተውሉት! አንዳንዶቹ ከሕግ በላይ መሆናቸውን ስለሚያውቁት ማን አለብኝ ፣ ማን ይጠይቀኛል በማለት በሰዎች ላይ እንደዱር አራዊት ይረባረቡባቸዋል ። የባርነት ስሜታቸውን እና የእንስሳነት ጠባያቸውን ከላያቸው አወላልቀው ለመሰባበር ጥረት የሚያደርጉትን እና በጭቆና ሰንሰለት በባርነት የተያዙትን ሰዎች ማሰቃየት ደስ የሚላቸው ሰዎች አሉ ። ሌሎቹ ደግሞ በቀላቸውን በመበቀል ፍላጎት



የተመረዙ ናቸው ። አሁንም ሌሎች ደግሞ በራሳቸው ላይ በተፈጸመባቸው ግርፋት በመደነዛቸው የደደቡ እና የደነቆሩ ናቸው ። ሕዝብ እየባለገ ነው ። መላው ሕዝብ!»

ቆም አለ እና ጥርሱን ያፋጭ ጀመር ።

«በዚህች ዓለም ወደው ሳይሆን የግድዎን ጨካኝ ይሆናሉ!» አለ ።

ጥረት ካደረገ በኋላ ተቆጥቶ የነበረውን ስሜቱን በመቋቋም ብርት-ብርት የሚሉ ዐይኖቹን ጣል አድርጎ ወደ እምታለቅሰው እናት ዘንድ ሄደ ።

«ይሁን እንጂ ፣ እናት ጊዜ ማባከን የለብንም! የኔ ውድ ጓዲት ፣ በጊዜ መዘጋጀት ይኖርብናል!» አላት ።

ሀዘን ባልተለየው ፈገግታ ወደ እርሷ ዘንድ ጠጋ ካለ በኋላ እጅዋን ጭብጥ አደረገው ። ከዚያም ፡ —

«ሻንጣዎ የት ነው?» አላት ።

«ማዕድ ክፍል ነው!» አለችው ።

«በራፋችን ላይ የቆሙ ሰላዮች አሉ ። ይኸንን ያህል የበዙ ጽሁፎች ሳይታወቅብን በሥውር ይዘን መውጣት አንችልም ። የምንደብቅበት ቦታ ደግሞ የለንም ። ዛሬ ማታም እንደገና ለፍተሻ የሚመጡ ይመስለኛል ። ስለዚህም ፣ ምንም እንኳን አሳዛኝ ቢሆንም ሌላ ምርጫ ስለማይኖረን ሁሉንም ማቃጠል አለብን» አለ ።

«ምኑን ነው የምናቃጥለው?» አለችው ።

«ሻንጣዎ ውስጥ ያለውን ጽሁፍ በሙሉ ማቃጠል አለብን» አላት ።

ወዲያውኑ ፣ እርሱ ምን እንደገመተ ስለተረዳች ምንም እንኳን አዝና ቢሆንም በኩራት ተመላች ።

«ሻንጣው ውስጥ አንዳችም ነገር የለም ። አንድ እንኳን ወረቀት የለም!» አለችው ። ከዚያም ያጋጠማትን ታሪክ ሁሉ ዘርዝራ ትነግረው ጀመር ። ንግግር

ስትጀምር ቀስ-በቀስ ብርታቷ ተመልሶ ይሰማት ጀመር ።

መጀመርያ በስሜት ተውጦ ኒኮላይ ተኮሳትሮ ነበር ። ወዲያውኑም መኮሳተሩ በመደነቅ ተለወጠ ። በመጨረሻም ስሜቱ ከፍ በማለት ንግግሯን ፡ —

«ኧረ ግሩም ድንቅ ነው! እንዴት ያሉ ዕድለኛ ነዎት!» በማለት አቋረጣት ። እጇን ያዘ አደረጋት ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«በሰዎች ላይ ያለዎት ዕምነት እጅግ አድርጎ ልብን የሚነካ ነው ። እርስዎን የማፈቅርዎት ልክ እንደ — ልክ እንደ እናቴ አድርጌ በማፍቀር ነው!» አላት ።

ለምን እንደዚህ የተሟሟቀ እና ጠንካራ ስሜት ሊኖረው እንደበቃ እያስተዋለችው ትስቅ ጀመር ። እጆቿን እያሻሸ እና መለስ ባለ ፈገግታ ፈገግ እያለ ፡ —

«በአጠቃላይ ጉዳዮች ብሩኅ ይመስላሉ ። በእነዚህ ጥቂት ቀናት ውስጥ እኔም ስዝናና ነበር ። መጻሕፍት አነብብ ነበር ። ከወዝ-አደሮች ጋር እወያይ ነበር ። ስለእነርሱም አጠና ነበር ። ከእነርሱ ጋር የሚሰነባበቱት ምንግዜም ንጹህ እና ሙሉ በሆነ ስሜት ነው ። ኒሎቭና ፣ ወዝ-አደሮች እንደምን ያሉ ጥሩ ሰዎች ናቸው! ለመማር ብርቱ ጉጉት ያላቸው ፣ እጅግ ጠንካሮች እና ስሜት የተሞላባቸው የሆኑትን ወጣት ወዝ-አደሮችን ማለቴ ነው! እነርሱን ሲመለከቱ ፣ አንድ ቀን ሩስያ ከዓለም እጅግ ዴሞክራሲያዊት የሆነች ሀገር እንደምትሆን አይጠራጠሩም!» ጥቂት ዝም ካለ በኋላ ፣ ቃለ-መሀላ የሚፈጽም ይመስል አንድ እጁን ወደላይ ከፍ አደረገ ። ከዚያም ፡ —

«ይሁን እንጂ ፣ ይኸው እኔ እዚህ ተወዝፌ መጻሕፍት በማገላበጥ ፣ በመጻፍ እና የአሀዝ ሰንጠረዦችን በመቀመር ዓመት ሊጠጋኝ ነው ። ይኸ አካለ-



ስንኩልነት ማለት ነው! ወዝ-አደሮች መካከል መኖርን ለመድኩኝ ። ከእነርሱ-ውጪ ተለይቶ መኖር ግን ፈጽሞ አይስማማኝም ። ስሜቴ ሁለንተናዬ ወደ እነርሱ የተሳበ ወደ እነርሱ ያዘነበለ ነው ። አሁን ግን እንደገና እንደነፃ ሰው እኖራለሁኝ ። ሁል ጊዜም ከእነርሱ ጋር ከመሆኔም በስተቀር ፣ ከእነርሱ ጋር ሁኜም እሠራለሁኝ ። የምለው ይገባዎታልን? ወጣትነት እና አዳዲስ ነገሮችን የማስገኘት ችሎታ ያለው ኃይል በሚገኝበት የአዳዲስ ሃሣቦች ማፍለቂያ ምንጭ መካከል እገኛለሁኝ ። ሠርቶ-አደሩ ሕዝብ መኮፈስን የማያውቅ ልበ-ቅን እና አስደሳች የሆነ ውብ ከመሆኑም በስተቀር ዕጹብ-ድንቅ በሆነ አኳኋን የሰውን መንፈስ የሚያነቃቃ ነው ። አንድ ሰው ወጣት እና ጠንካራ እንዲሆን ያደርጋል ። ኒሎቭና ፣ የበለጸገ የሕይወት ጎዳና ነው!»

ደስ ብሎት እና እርሱነቱ ተሰምቶት ተፍለቅልቆ ሳቀ ። እናት የደስታውን ምክንያት ተገነዘበች ። አብራው በመደሰት እና በመሳቅም ደስታውን ተካፈለችው ።

«እርስዎስ? እርስዎም ቢሆኑ አጽብ ድንቅ የሆኑ እንከን የማይወጣልዎ ግሩም ሰው ነዎት! የሰውን ምንነት የሚገልጹት እንደምን ግሩም ድንቅ በሆነ ሁኔታ ነው! የሰውን ምንነት የሚገነዘቡት እንደምን በሚያስደንቅ ሁኔታ ነው!» በማለት ኒኮላይ በአንክሮ ተናገረ ።

መጀመርያ በደስታ የሚፍለቀለቅ ፊቱን ሸሸጎ ከዚያም ሀፍረቱን ለመደበቅ በመሞከር እጁን በራሱ ላይ በማሳለፍ ራሱን አሸት-አሸት እያደረገ ፣ ከዚያም ስለራሷ ታሪክ ግልጽ ባለ ሁኔታ ስታወሳው ወደ እርሷ ዞር እያለ አጠገቧ ቁጭ ብሎአል ።

«ትልቅ መታደል ነው! እርስዎም ተይዘው ሊታ

ሠሩ ይችሉ ነበር ። በዚህ ፈንታ ግን… አምን ገበሬዎች በመንቃት በማወቅ ላይ ያሉ ይመስላሉ ። እና ይኸ ደግሞ መሆን ያለበት ጉዳይ ነው ። ያች ያጫወቱኝ ሴትዮ — ቁልጭ ብላ አኳኋኒ ይታየኛል!… ገጠር ሂደው የሚሠሩ የተለዩ ሰዎችን መላክ ያስፈልገናል ። ሰዎች! ይኸንን ያህልም በቂ ሰዎች የሉንም! ብዙ መቶ ሰዎች ያስፈልጉናል!» አለ ።

«ፓቬል ቢወጣ ነበራ! አንድሬይም!» አለች እናት ለስለስ ባለ አነጋገር ።

እርሷን-እርሷን ተመለከተ ። ከዚያም ዐይኖቹን ወደመሬት ጣል አደረገና ፤

«አዩ ኒሎቭና ፤ ምናልባትም ይኸንን መስማቱ ለእርስዎ ከባድ ይሆን ይሆናል ። ያም ሆኖ ግን ልናገረው ፡ — ፓቬልን ደህና አድርጌ አውቀዋለሁኝ ። ከእሥር ቤት ማምለጥን ምርጫው አድርጎ በፍጹም አይሻም ። እዚያ ቆይቶ መመርመርን ይሻል ። ማንነቱን ሙሉ-በሙሉ የማሳየት ዕድሉን ሊጠቀምበት ይሻል ። ይኸንን መሳዩን አጋጣሚ ከመቋቋም እምቢኝ ብሎ አያፈገፍግም ። ለምንስ ብሎ? ከሳይቤርያ ማምለጥ ይችላል» አለ ።

«አይ ፤ እንግዲህ መቸስ የሚሻለውን የሚያውቅ እርሱ ነው» አለች እናት ትንፋሿን በረዥሙ ዋጥ እያደረገች ። ኒኮላይ ጥቂት ቆየት ካለ በኋላ በመነጽሮቹ ውስጥ አትኩሮ እየተመለከታት …

«ይኸንን የእርስዎን ሰው በቅርብ ጊዜ መጥቶ እንደምንገናኘው ተስፋ አለኝ ። ስለሪቢን ለገበሬዎች የሚበተን ወረቀት ማዘጋጀት አለብን ። እርሱ ራሱ እጅግ ዝነኛ ታጋይ ስለሆነ ይኸንን ማድረጋችን አይጎዳውም ። ጽሁፉን እኔ ዛሬ አዘጋጃለሁኝ ። ሉድሚላ ወዲያውኑ ታትመዋለች ። ችግሩ ግን የሚዘጋጀውን ተበታኝ ወረቀት እንዴት ለገበሬዎቹ ለማድረስ እንደሚቻል ነው ። እንዲደርሳቸው ለማድረግ እንዴት ይቻል ይሆን?» አላት ።



«እኔ ወስጄ አደርስላቸዋለሁኝ ።»

«የለም ። አይቻልም ። አመሰግናለሁኝ!» አለ ኒኮላይ ፈጠን ብሎ በአንክሮ በመናገር ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«ቬሶቭሺኮቭ ሊያደርስ አይችልም ይሆን እንዴ?» አለ ።

«በጉዳዩ ከእርሱ ጋር መነጋገር ይኖርብኛል?» አለችው ።

«ይነጋገሩ ። እንዴት በመሰለ ሁኔታ ወስዶ እንደሚያደርስም ዘዴ ዘዴውን ያስተምሩት» አላት ።

«እኔስ ታዲያ ምን ልሠራ ነው?» አለችው ።

«ሆሆይ! ግዴለም ፤ እርስዎም የሚያከናውኑት ሌላ ተግባር እንፈልግልዎታለን!» አላት ።

ወደ የጽሕፈት ጠረጴዛው ዘንድ ሂዶ ተቀመጠ ። ጠረጴዛውን ስታጸዳዳ ወደእርሱ ሠረቅ አድርጋ አስተዋለች ። በሃሣብ ተመስጦ ብዕሩ ጣቶቹ ላይ ይንቀጠቀጣል ። አንዳንድ ጊዜ አንገቱ ላይ ያሉት ጡንቻዎች ይውተረተራሉ ። ጭንቅላቱን ከፍ አድርጎ ዐይኖቹን ሲጨፍን አገጩ ሲንቀጠቀጥ ትመለከታለች ። ይኸ ሁኔታው አሳሰባት ። በመጨረሻም ከተቀመጠበት በመነሳት ፡ —

«አዘጋጅቻለሁኝ ። እነሆ ይኸንን ወረቀት እርስዎ ዘንድ አንድ ቦታ ይሸሽጉ እና ያስቀምጡ ። ብቻ ግን ደግሞ ዣንዳርሞቹ ከመጡ እርስዎንም ይፈትሹዎታል ።»

«ገሀነም ይግቡ!» አለች ረጋ ባለ አነጋገር ።

የዚያን ዕለት ምሽቱ ላይ ሃኪሙ ኢቫን ዳኒሎቪች እነርሱ ዘንድ መጣ ። ፈጠን ባለ እርምጃ ከወዲያ-ወዲህ ክፍሉ ውስጥ እየተንጎራደደ ፡ —

«ባለሥልጣኖቹን እንዲህ ድንገት ቁጡ ያደረጋቸው ምክንያት ምንድነው? ትላንት ማታ የሰባት ሰዎች ቤት ተፈተሸ ። ለመሆኑ ሕመምተኛዬ የታል? እ?» በማለት ጠየቀ ።

«ትላንትትና ሄደ ። ዛሬ ቅዳሜ ነው ። በጥናት ክበቡ ላይ ሳይሳተፍ መቅረት አይሻም» በማለት ኒኮላይ መለሰለት ።

«አይ ፤ ይኼ አጉል ሞኝነት ነው ። የራስ ቅሉ ተፈልጦ ጥናት ክበብ ሂጄ የግድ መሳተፍ አለብኝ ማለት አይገባም...» አለ ዶክተሩ ።

«ለጊዜው ከመሄድ እንዲቀር የተቻለኝን ሁሉ ሞክሬ ነበር ። ይሁን እንጂ ፤ ጥረቴ አልተሳካልኝም...» አለ ኒኮላይ ።

«ግዴላችሁም ፤ ጥናት ክበቡ ለመሄድ የፈለገው ለሌላ ጉዳይ ሳይሆን 'እዩኝ እንዴት እንደሆንኩኝ — ገና ከአሁኑ ተሳታፊ ሁኜ ቆስያለሁኝ!' እያለ ለጓዶቹ በመናገር እንዲታይ ፈልጎ ነው ። እንጂ ለሌላ ነው ብላችሁ ነው?» አለች እናት ።

ዶክተሩ ፈጠን ብሎ እናትን ተመለከታት እና ምፀታዊ በሆነ ፈገግታ ጥርሶቹን እያሳየ ።

«አቤት-አቤት! እንደው ለመሆኑ እርስዎ እንዴት ያሉ ጨካኝ ነዎት ማለት ነው!..» አለ ።

«ኢቫን ፤ እሺ እንግዲህ ፤ ይበቃሃል ፤ እዚህ አንተን ምንም የሚያቆይህ ጉዳይ የለም ። እንግዶች እየተጠባበቅን ነን ። ሂድ! ኒሎቭና ጽሁፉን ይስጡት...» አለ ኒኮላይ ።

«ሌላ ጽሁፍ!» አለ ዶክተሩ በአንክሮ በመናገር ።

«አዎን! ውሰድ እና እንዲታተም ወደማተምያ ክፍላችን አድርስ» አለው ኒኮላይ ።

«እሺ ተቀብያለሁኝ ። እሰጣለሁኝ ። ሌላስ?» አለ ዶክተሩ ።



«ይኸው ነው ። ምንም የለም ። በራፉ ላይ ሰላይ ቆሞ ይጠባበቃል» አለው ።

«አይቼዋለሁኝ ። እኔ በራፍ ላይም እየተጠባበቀ ነው ። እሺ እንግዲህ ደህና አምሹ ። በሉ ደህና ሁኑ ፤ እርስዎ ደም ጨካኝቷ ሴትዮ» አለ ዶክተሩ ከዚያም ቀጠል አደረገ እና ፡—

«ኧረ ጓዶች ፤ በነገራችን ላይ መካነ መቃብሩ ላይ የተካሄደው ግብ-ግብ ጥሩ ውጤት አስከትሎአል! ከተማው በሙሉ የሚያወራው ስለዚሁ ጉዳይ ነው ። አንተ ያቀረብከው ጽሁፍም ጥሩ ጽሁፍ ሲሆን ፤ የቀረበውም በተገቢው ጊዜው ነው ። እኔ ሁል ግዜም አጓጉል ከሆነ ሰላም ይልቅ ደህና ግብ-ግብ ይሻላል እላለሁኝ...» በማለት ተናገረ ።

«እሺ አሁን እንግዲህ ሂድ» አለው ኒኮላይ ።

«እንግዳ ደህና አድርጋችሁ የምታስተናግዱ ናችሁ ብዬ መናገር አልችልም! ይጨብጡኝ ኒሎቭና! በዕውነት ነው የምለው ያ ልጅ መሄዱ ደግ አላደረገም ። የት እንደሚኖር ታውቃለህን?» አለ ዶክተሩ ።

ኒኮላይ የልጁን አድራሻ ሰጠው ።

«ነገ ሄጄ ጤንነቱ እንዴት እንደሆነ አያለሁኝ ። ጥሩ ልጅ ነው ። አይደለምን?» አለ ዶክተሩ ።

«በጣም...» አለ ኒኮላይ ።

«ልንጠነቀቅለት ይገባል ። ትክሻው የተሸከመው ጭንቅላት ጥሩ ጭንቅላት ነው!» አለ ዶክተሩ ለመውጣት እየተራመደ ። ቀጠል አድርጎም ፡—

«የመደብ ልዩነቶች አይኖሩባቸውም ብዬ የማምንባቸውን ዳርቻዎች ስንደርስ የእኛን ቦታ ወስደው በእኛ ምትክ በመግባት ዕውነተኛዎቹ ከወዝ-አደሩ አብራክ የሚወጡት ምሁራን እርሱን የመሳሰሉት መሆን ፡ አለባቸው» በማለት ተናገረ ።

«ኢቫን ፤ ምነው ልጄ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ

ደህና ለፍላፊ ወጥቶሃል...» አለው ኒኮላይ ዶክተሩን ።

«የዚህ ምክንያቱ ደስ-ደስ ስለአለኝ ነው ። አንተ ተይዘህ ወደ እሥር ቤት ለመሄድ እየተዘጋጀህ ነው ማለት ነዋ? መቸስ ምን ይደረጋል ፤ በል መልካም ዕረፍት ይሁንልሃ!» አለው ዶክተሩ ።

«አልደከመኝም ። ቢሆንም አመሰግናለሁኝ» በማለት ኒኮላይ መለሰለት ።

ከወዝ-አደሩ መደብ አብራክ ለወጣው ለዚህ ልጅ የሚያስቡለት በመሆናቸው እናት ተደሰተች ።

ዶክተሩን ከሸኙ በኋላ እናት እና ኒኮላይ እራት ብጤ እየቀመሱ እና ሻይ እየጠጡ የምሽት እንግዶቻቸውን በመጠበቅ በዝግታ ይወያዩ ጀመር ። ኒኮላይ በግዞት ስለሚኖሩት ጓዶቹ ፤ ከግዞት አምልጠው በአሁኑ ጊዜ በሌላ መጠርያ ስም እየተጠቀሙ ተግባራቸውን በመፈጸም ላይ ስላሉት ጓዶቹ በሰፊው እየዘረዘረ ያጫውታት ጀመር ። ይህችን ዓለም እንደገና እንደአዲስ ለመገንባት ያለ የሌለ ኃይላቸውን ያለመቆጠብ ራሳቸውን አሳልፈው ለዚህ ተግባር የሰጡትን የእነዚህን እንታወቅ-እንታወቅ የማይሉ ጀግኖች ታሪክ ሲወሳ የሚያደንቁ እና ለማመንም የሚቸገሩ ይመስል እርቃናቸውን የሚገኙት የቤቱ ግድግዳዎች የኒኮላይን ድምፅ እየተቀበሉ ያስተጋቡታል ። ግርማ-ሞገስ ያልተለየው ጥላ እናት ላይ የደስ-ደስ ባለው ሁኔታ ያጠላባት ሲሆን ፤ በእነዚህ አይታቸው በማታውቃቸው ሰዎች ልቧ ተነክቶ በሃሣቧ የሁሉም መልክ ድቅን እያለ ይታዩዋት ጀመር — ሕዝቦች ንጽሁን እና ተገቢውን የሕይወት ህቅ ይመለከቱ ዘንድ ለዘመናት ሙሉ የተጋገሩ የሀሠት ቅርፊቶችን እየፈቀፈቀ ጥርጊያ ጎዳና በመክፈት ዝግ ባለ ነገር ግን ደግሞ እርግጠኝነት ባልተለየው ሁኔታ የሚራመድ እና በማይበገር በወንድነት ሮኔ እንደ አንድ



የታላቅ ሰው ሰውነት ተመስለው ኒኮላይ የነገራትን ሰዎች መስሎ ከፊትዋ ተደቅኖ ይታያት ጀመር ። ይህም ህቅ በተሀድሶ ዳግመኛ ከተወለደ በኋላ እገሌ-ከእገሌ ሳይል ሁሉንም በአንድነት የሚሰበስብ ሲሆን በዓለም ላይ ሽብር የሚነዙትን እና ዓለምን በባርነት ቀንበር ሥር የሚያውሉትን ሦስቱን ጭራቆች — ማለትም ስግብግብነትን ፤ ጥላቻን እና ቅጥፈትን ደምስሶ ሰዎችን ነፃ ያወጣቸዋል... ይኽንን የመሰለውን ታላቅ ሰው ምስል ስትመለከት የሚያድርባት የደስታ ስሜት ፤ ከሌሎች የሕይወት ዘመኗን ካሳለፈችባቸው ቀናት ይልቅ የዛሬው ቀኗ ቀለል ያለላት ደህና ቀን መሆኑን እያስታወሰች ዕለቱን ለመሰናበት ከቅዱስ ሥዕሉ ሥር ተንበርክካ የምሥጋና ፀሎት ስታደርስ የሚሰማትን ዓይነት የደስታ ስሜት ተሰማት ። እነዚያ የቀድሞዎቹ አስከፊ ቀናት አሁን ተዘንግተዋታል ። ይሁን እንጂ እነርሱ የፈለፈሉዋቸው እነዚህ አዳዲስ የሆኑ የእፎይታ ቀናት እየበዙ እየተባዙ ፤ ይበልጥ ብሩኅ እና አስደሳች እየሆኑ ልቧ ውስጥ በጥልቀት ሥር እየሰደዱ እና የሕያውነት ነፍስ እየዘሩ ይለመልማሉ ።

«እና እንግዲህ ዣንዳርሞቹ አይመጡም ማለት ነዋ!» በማለት ኒኮላይ በአንክሮ ተናገረ ።

«ገሀነም ይግቡ ብያለሁኝ እኮ!» በማለት እናት ፈጠን ብላ እየተመለከተችው ተናገረች ።

«እነርሱ ገሀነም ይግቡ ። ኒሎቭና ፤ እርስዎ ግን ወደምኝታዎ መሄጃ ጊዜዎ ነው ። በጣም የደከመዎ መሆን አለብዎ ። ኧረ ጉድ ነው! እንዴት ያለ ጠንካራ አካል ነው ያለዎ እባክዎ! ይኽንን ሁሉ አደጋ እና ሥጋት እንደው ከምንም አይቆጥሩት! ፀጉርዎ ግን እየሸበተ ነው ። በሉ እሺ ፤ ይሂዱ እና እስኪ ትንሽ እንቅልፍ ይተኙ» አላት ኒኮላይ እናትን ።

## 20

ከማዕድ ክፍሉ በኩል ጎላ ባለ ሁኔታ በሩ ሲን
ኳኳ እናት ከእንቅልፏ ተቀሰቀሰች ። ትዕግሥት በተመ
ላበት ሁኔታ በሩ ሳያቋርጥ ይንኳኳል ። አሁንም ገና
ባለመንጋቱ ጭለማ ነበር ። የበሩ ሳያቋርጥ መንኳኳት
ደግሞ አሳሳቢ ነው ። እናት ቶሎ ብላ ጀርባዋ ላይ
ጨርቅ ብጤ ጣል አደረገች እና ወደማዕዱ ክፍል
በሩን ልትከፍት ሄደች ። ከዚያም ፡ —

«ማነው?» አለች ።

«እኔ ነኝ!» አለ አንድ ከዚህ ቀድሞ ሰምታው
የማታውቀው ድምፅ ።

«ማን?» አለች ።

«በሩን ይክፈቱት!» በማለት ዝቅ ባለ ድምፅ
ከውጪ ያለው ሰው ጠየቀ ።

እናት መደንቀርያውን አነሳች እና በእግሯ በሩን
ገፋ አድርጋ ከፈተችው ። ኢግናት ከውጪ ወደውስጥ
ገባ ።

«እና አልተሳሳትኩም ማለት ነዋ!» በማለት ድም
ፁን ከፍ አድርጎ አሰማ ።

እስከወገቡ ድረስ በጭቃ ተለውሶአል ። ፊቱ ቡና
ማ ሁኖአል ። ዐይኖቹ ጉድጓዳቸው ውስጥ ተደብቀ
ዋል ። ድምድም ፀጉሩ በባርኔጣው ውስጥ ምንጭርጭር
ብሎ ተመነጫጭሮአል ። በሩን እየዘጋ ፡ —

«አደጋ ላይ ነው ያለነው!» በማለት ቀስ ብሎ
ተናገረ ።

«አውቃለሁኝ...» በማለት መለሰችለት ።

ልጁ ይኸንን በማዳመጡ ተደነቀ ።

«እንዴት አወቁ?» አላት ዐይኖቹን እያርገበገበ ።

በአጭሩ አብራራችለት ።

«ሌሎቹን ሁለቱን ጓዶችህንም ያዙዋቸውን?» አለችው ።

«አልነበሩም ። ሪፖርት ሊያደርጉ ሂደው ነበር ።



የተገዙ ሰላዮች ናቸው! አጎት ሚኻኢሎን ጨምሮ
አምስት ሰዎች ተያዙ...» አላት ።

ደህና አድርጎ ትንፋሹን ከዋጠ በኋላ ፈገግ በማ
ለት ፡ —

«የቀረሁት እኔ ብቻ ነኝ ። አሁን እኔን ለመያዝ
እየፈለጉኝ መሆን አለበት» አላት ።

«እንዴት ልታመልጥ ቻልክ?» በማለት እናት ጠየ
ቀችው ።

የሌላኛው ክፍል በር ቀስ ብሎ ተገፋ እና ተከ
ፈተ ። ከዚያም ኢግናት አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀም
ጦ ግራ-ቀኙን እየተመለከተ ፡ —

«ማን ፤ እኔ?» በማለት በአንክሮ ጠየቀ ። ከዚያም ቀጠ
ል አድርጎ ፡ —

«እነርሱ ከመምጣታቸው አንድ-ሁለት ደቂቃዎች
በፊት ደን ሠራተኛው መጥቶ በመስኮት ካንኳኳ በኋ
ላ ፡ — ‘ወንድሞች ሆይ ተጠንቀቁ ፤ እየተከታተሉዋችሁ
ነው...’ በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ» አለ ።

ረጋ ባለ ሁኔታ ሳቀ ። ከዚያም ፊቱን በኮቱ እየ
ጠረገ ፡ —

«አጎት ሚኻኢሎን እንደሆነ የፈለገው ነገር ቢመ
ጣ አያስደነግጣቸውም ። ‘ኢግናት ፤ ፈጥነህ ወደከተማ
ብረር’ አሉ ። ከዚያም ቀጥለው ‘ያቺን አዛውንት ሴት
ታስታውሳት የለም እንዴ?’ አሉኝ እየተናገሩ እና
ወዲያውም አንድ የማስታወሻ ወረቀት እየጻፉ ። ከዚ
ያም ፡ — ‘እንካ ይኸን ለእርሷ ስጣት’ አሉኝ እና
የጻፉትን ወረቀት ሰጡኝ ። ከዚያም በጫካዎቹ ውስጥ
ተሽሎኮለኩኝ ። እነርሱ ወደጎጆው እንደገቡም እርግ
ጠኛ ነኝ ። ሲመጡ ሰማኋቸው ። እነዚያ ጭራቆች
ከየቦታው ሁነው ይጮሁ ነበር ። ብዙ ነበሩ ። የቅር
ጣን መሥሪያ ቦታችንን ከበቡት ። ቁጥቋጦዎቹ ውስጥ
ዝቅ ብዬ ተደበቅሁኝ ። ሳያዩኝ አልፈውኝ ሄዱ ። ከዚ

ያም ብድግ አልኩኝ እና የቻልኩትን ያህል እግሬ-አውጭኝ ብዬ ሸመጠጥኩኝ ። አንድም ቦታ እፎይ ብዬ ሳላርፍ ሁለት ምሽት እና አንድ ቀን ሙሉ ተጓዝኩኝ» አለ ።

በራሱ ድርጊት ተደስቶ እንደነበረ ታስተውላለች ። ፀጉር የወረሩት ዐይኖቹ በፈገግታ ተውጠው የነበሩ ሲሆን ከናፍሮቹም ይንቀጠቀጣሉ ።

«ሻይ አሁን አመጣልሃለሁኝ» አለችው ሳሞቫሩን እየወሰደች ።

«የማስታወሻው ደብዳቤ ይኸው...» አለ ።

ከዚያም ሕመም እየተሰማው እና ኮስተር ብሎ እህ እያለ እግሩን ካረፈበት ቦታ በችግር ካነቃነቀ በኋላ አግዳሚ ወንበሩ ላይ አስቀመጠው ።

ኒኮላይ ወደ በራፉ መጣ ። ከዚያም ዐይኖቹን ጠበብ አድርጎ እንደመጨፈን እያለ ፡—

«ጓድ ፤ እንደምን አመሸህ?ቆይ ልርዳህ» አለው ኢግናትን ።

ከዚያም ኢግናት እግር ላይ የተጠመጠመውን የቆሸሸ ጨርቅ ይፈታለት ጀመር ።

«የለም ይተዉ» አለ ልጁ እግሩን ወደኋላ እየሳበ እና በመደነቅ እናትን እየተመለከተ ። እናትም የእርሱን መመልከት ዘንጋ በማድረግ ፡—

«እግሩን በአልኮል ማሸት ያስፈልገናል...» አለች ።

«አዎን ። ነው እንጂ!» በማለት ኒኮላይ መለሰ ።

ኢግናት ቅር ብሎት አንኮራፋ ።

ኒኮላይ የማስታወሻ ወረቀቱን ከተቀመጠበት ብድግ በማድረግ እጥፍጥፍ በማለት ተጨረማምቶ የነበረውን ይኸንን ቡናማ ወረቀት ዐይኖቹ ሥር አስጠግቶ ያነብብ ጀመር ።

«እናት ፤ ተግባራችንን እንዳታቋርጪ ። እኛ ረዢም የሴት ወይዘሮ ደግሞ ከምንግዜውም በበለጠ ሁኔታ



ስለተግባራችን በሰፊው መጻፉቸውን እንዳይዘነጉ ንገሪያቸው ። ደህና ሁኝ እያልኩኝ እሰናበትሻለሁኝ ። ሪቢን ።»

ወረቀቱን ይዞበት የነበረውን እጁን ኒኮላይ ወደ ታች ጣል አደረገው ።

«ግሩም-ድንቅ እኮ ነው ፤ እባካችሁ!» በማለት ኒኮላይ በአድንቆት መልክ አጉረመረመ ።

ኢግናት እነርሱን-እነርሱን እየተመለከተ በጥንቃቄ ባዶ እግሩ ተረከዝ ላይ ያለውን ጭቃ ያስለቅቃል ። እናት በታዛ ውሀ አምጥታ እግሩን ለመድረስ ጎንበስ ስትል እንባዋ እንዳይታይባት ትሞክር ነበር ።

«ኡይ! በፍጹም አያደርጉትም!» በማለት እግሩን ወደ አግዳሚ ወንበሩ ሥር እያስገባ ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰማ ።

«ይልቅ ፈጠን ብለህ እግርህን አቅርብልኝ!» አለችው ።

«አልኮል ላምጣ» አለ ኒኮላይ ።

ልጁ አሁንም እግሩን ከአግዳሚው ሥር ይበልጥ ወደኋላ በእምቢታ ይሸሽግ ጀመር ።

«ምንድነው ነገሩ ፤ ሆስፒታል ነው እንዴ?» አለ ዝግ ባለ ንግግር ።

እናት የተጠመጠመውን ጨርቅ ከሌላኛው እግሩ ላይ ፈታች ።

ኢግናት ጎላ አድርጎ ባፍንጫው አየር እየሳበ እና እናትን ወደታች እየተመለከተ አንገቱን መለስ-መለስ በማድረግ ያዟዙር ጀመር ።

«ሚኻኢሎ ኢቫኖቪችን ደበደቡት!» በማለት ሲቃ በያዘው ድምፅዋ ተናገረች ።

«እረ?» አለ ልጅየው ረጋ ባለ ሁኔታ ።

«አዎን ። ኒኮልስኮዬ ከተባለው ሥፍራ ሲያመጡ

ትም ተደብድቦ ስለነበረ አንጉል በሆነ ሁኔታ ላይ ይገኝ ነበር ። እዚያም የፖሊሱ ሳጂን እና የፖሊሱ አዛዥ ሁለመናው በደም እስኪለወስ ድረስ ፊት-ፊቱን ደበደቡት!» አለች ።

«አዎ ። ይኸንን ማድረግማ መች አጡበት! ሥራቸው ነው ፤ ያውቁበታል!» አለ ልጁ በተኮሳተረ መልክ ትከሻውን ወዝወዝ እያደረገ ። ከዚያም ቀጠል አደረገ እና ፦

«ከአንድ ሺህ አጋንንት ይልቅ እኔ እነርሱን እፈራቸዋለሁኝ ። ለመሆኑ ገበሬዎቹም አብረው ደበደቡትን?» አላት ።

«ከመካከላቸው አንዱ የፖሊሱ አዛዥ ደብድብ ብሎ ስለጠየቀው መታው ። የተቀሩት ግን ደህና ነበሩ ። እንደውም እርሱን ይደግፉ ነበር ። እርሱን ለመምታት መብት የላችሁም እያሉ በፖሊሶቹ ላይ ጮኹባቸው…» አለችው ።

«እህህ! ገበሬዎች ማን የማን ወገን እንደሆነ እና ለምንስ የማን ወገን እንደሆነ መለየት ላይ ናቸው ማለት ነው» አለ ።

«አስተዋይ የሆኑ ሰዎች ከመካከላቸው ይገኛሉ…» በማለት ተናገረች ።

«በየትም ቦታ ቢሆን አስተዋይ የሆኑ ሰዎች ይገኛሉ ። የሆኑትን እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው ችግር ነው ። አስተዋይ የሆኑ ሰዎች እዚያም ይኖራሉ ። ይኸስ ይሁን ፤ ግዴለም ። ችግሩ ግን እነዚህን አስተዋዮቹን ከመካከላቸው መርጦ ማግኘቱ ነው» አለ ።

ኒኮላይ አንድ ጠርሙስ አልኮል አመጣ ። ከዚያም ሳሞቫሩ ውስጥ ትንሽ ከሰል ጨመረበት እና ምንም ሳይናገር ወጥቶ ሄደ ። ኢግናት በዝምታ ያስተውለዋል ። ከዚያም ፦

«እኚህ ጌታው ማን መሆናቸው ነው? ዶክተርናቸው እንዴ?» በማለት ኢግናት እናትን ጠየቃት ።

«እዚህ እኛ መሀል ጌቶች የሉም ። ሁላችንም ጓዶች ነን» በማለት መለሰችለት ።

«ወይ ጉድ! ይገርማል እኮ!» በማለት ኢግናት ተናገረ ።

«ምኑ ነው የሚገርምህ?» አለችው እናት ።

«አይ ፤ እንደው ሁሉም ነገር በአጠቃላይ ግርም ይለኛል ። አንዳንዶቹ የሰውን አፍንጫ በቡጢ ያናፍጣሉ ። ሌሎቹ ደግሞ የሰውን እግር ዝቅ ብለው ወርደው ያጥባሉ ። እነዚህን ሁለቱንም የማይመስሉ እና በመሀል ሠፍረው የሚገኙትስ?» አለ ።

ቤቱ ውስጥ ያለው የክፍል በር ተከፈተ ። ከዚያም ኒኮላይ የሚቀጥለውን ተናገረ ፦

«በመሀል ሠፍረው የሚገኙት የእናንተን አፍንጫዎች በቡጢ እያነገሉላችሁ ደም-በደም የሚያደርጓችሁን ሰዎች እጆች የሚልሱ እና አፍንጫዎቻቸው በደም የተለወሱ ሰዎችን ደም የሚጠጡ ናቸው ። በመሀል ሠፋሪነት መሀል ሁነው የሚገኙ ማለት እነዚህ ናቸው!» አለ ።

ኢግናት ኒኮላይን በአክብሮት ተመለከተው ። ጥቂት ዝም በማለት ከቆየ በኋላ ትንፋሹን ወደውስጥ እየዋጠ ፦

«ወደ ዕውነት በጣም የተጠጋ አባባል ይመስለኛል» አለ ።

ልጁ ከተቀመጠበት ተነሳ እና ጠንከር ያሉ ጥቂት እርምጃዎች ተራመደ ።

«እግሮቼ አዳዲስ እግሮች ሆኑ ፤ አይደል እንዴ! አመሰግናለሁኝ!» አለ ።

ከዚያም ወደ ምግብ መመገቢያ ክፍል ሻይ ለመጠጣት ሄዱ ። ኢግናት ተደማጭ በሆነ እና ጥልቀት ባለው ድምፅ የሕይወቱን ታሪክ ይተርክላቸው ጀመር ።

«ጋዜጦቻችንን ከቦታ-ቦታ እየገሰገስኩ የማሠራጭ
እኔ ነበርኩኝ ። ጉዞ በመኀዝ የሚስተካከለኝ ማንም
የለም» አለ ኢግናት ።

«ገጠር ያሉ ብዙ ሰዎች ጋዜጦቻችንን ያነብባሉ
ን?» በማለት ኒኮላይ ጠየቀው ።

«ማንበብ የሚችሉት ሁሉ ፤ ሀብታሞች የሆኑትም
ጭምር ያነብባሉ ። ሀብታም-ሀብታሞቹ ጋዜጣችንን
የሚያገኙት ከእኛ ላይ አይደለም… ገበሬዎች መሬትን
ከመሬት ከበርቴዎች እግር መንጭቀው በደማቸው
የሚያጥቧት መሆኑን የመሬት ከበርቴዎች አሳምረው
ያውቁታል ። ገበሬዎቹ ይኽንን እንደፈጸሙ ወዲያው
ኑም የመሬት ከበርቴዎች እና ተቀጣሪ ገበሬዎች
የሚባሉ እንዳይኖሩ ለማድረግ መሬትን በሙሉ እየ
ሸነሸኑ ያከፋፍላሉ ። ይኸ ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነው ።
አለበለዚያማ ትግል ለምን ይጀመር ነበር?» አለ ኢግ
ናት ።

በስጨት ያለ መሰለ ። ኒኮላይን በማጥናት እና
በመጠራጠር መልክ ትክ እያለ ያስተውለዋል ። ኒኮ
ላይ ፈገግ አለ ። አንዳችም ቃል አልተናገረም ።

«ዛሬ መላዋን ዓለም ታግለን ድል ብናደርግ እና
ነገ ደግሞ እንደገና ሀብታም እና ደሀ ተመልሶ የሚ
በቅል ከሆነ የመታገሉ ጠቀሜታ ምኑ ላይ ነው?
አይ! እንዲህ ያለ ነገር እኛ አናውቅም! ልታሞኙን
አትችሉም ። ሀብታሞች መቸም ቢሆን ደረቅ አሸዋ
እንደማለት ናቸው ። አንድ ቦታ ረግተው መቆየት አይ
ሆንላቸውም ። በየትኛውም አቅጣጫ እየሰፋ-እየተንሠ
ራፋ ይዘልቃሉ! ኸረ ምን ሲደረግ! ይኽንን ዓይነቱን
እኛ አንሻም!» አለ ኢግናት ።

«እኮ ተው ፤ እንዲህ አትበሳጭ» በማለት እናት ሳ
ቀች ።

ኒኮላይ በሀሳብ ተመስጠ ፡ —



«አሁን እኔን የሚያሳስበኝ ስለ ሪቢን መታሠር
የሚገልጸውን ተበታኝ ጽሁፍ በእናንተ ሰዎች መሃ
ል በተቻለ ፈጠን ብሎ ለማሠራጨት እንዴት እን
ደሚቻል ነው» በማለት ተናገረ ።

ኢግናት ጆሮዎቹን በስሜት ተውጠው ቅስር አደረ
ጋቸው ። ከዚያም ፡ —

«ይኽንን የመሰለ ተበታኝ ጽሁፍ ተዘጋጅቶአል
እንዴ?» በማለት ጠየቀ ።

«አዎን» አለው ኒኮላይ ።

«ለእኔ ይስጡኝ ። እኔ ወስጄ አሠራጫለሁኝ» በማ
ለት ልጅየው እጆቹን እያሻሸ ተናገረ ።

እናት ልጅየውን ሳትመለከት ረጋ ባለ ሁኔታ
ትስቅ ጀመር ።

«አንተ ደክሞሀል ። ደግሞም ፈርቼ ነበር ስትል
ነበር» አለችው እናት ።

«መፍራት አንድ ነገር ነው ። የተሠማሩበትን ተግ
ባር ማከናወን ደግሞ ሌላ ነገር ነው» በማለት ጠፍ
ጣፋ በሆነው እጁ ፀጉሩን ወደኋላ እያሻሸ በማስተ
ኛት ኮስተር መረር ባለ ሁኔታ ተናገረ ። ከዚያም
ቀጠል አድርጎ ፡ —

«አሁን እዚህ ላይ ምን የሚያስቅ ነገር አለ?
ምነው እባክዎ? ደህና ሰው አልነበሩም እንዴ ፤ እርስ
ዎም ይስቃሉ እንዴ?» አለ ኢግናት ።

«አይ አንተ! አይ የኔ ሕፃን!» በማለት በልቧ
ውስጥ ኢግናት ያሳደረባትን ደስታ እንዳይታወቅ
ለማድረግ እየሞከረች ተናገረች ።

«ይኸውልዎታ! ሕፃን አሉ ፤ አይደለም?» አለ ።

«አንተ ወደዚያ ተመልሰህ አትሄድም» አለው ኒኮ
ላይ ረጋ ባለ ሁኔታ ኢግናትን መልከት እያደረገ ።

«ምንአሉ? ታዲያ እኔ እንደው ተቀምጬ ምን
ልሠራ ነው?» አለ ኢግናት ቅር በተሰኘ መንፈስ ።

«ተበታኝ ጽሁፎቹን አንተ ሳትሆን ሌላ ሰው
ይዞ ይሄዳል ። አንተ ብቻ ምን-ምን ማድረግ እንደሚገ
ባው ፤ የት እና እንዴት እንደሚሄድ ዘርዝረህ አብራ
ራለት ። እሺ?» አለው ኒኮላይ ።

«እሺ» አለ ኢግናት ቅር በተሰኘ አነጋገር ።

«አዲስ የመታወቂያ ወረቀት እንሰጥሃለን ። የደን
ተጠባባቂነት ሥራም እናስይዝሃለን» አለው ።

ልጁ ፈጠን ብሎ ኒኮላይን ተመለከተው ። ከዚ
ያም ፡ —

«ገበሬዎች የማገዶ እንጨት ሲሠርቁ ባገኛቸው
ምን ላደርግ ነው ። ልይዛቸው? የለም-የለም ። እንዲህ
ያለው ሥራ ለእኔ አይስማማኝም» አለ ቅር በተሰኘ
ሁኔታ ።

እናት በሁኔታው ሳቀች ። ኒኮላይም ሳቀ ። ሁለቱም
መሳቃቸው ደግሞ ልጁን ቅር አሰኘው ፤ በስጨትም
አደረገው ።

«ገበሬዎቹን እንድትይዝ አትደረግም ። ስለዚህ ጉዳ
ይ አታስብ» አለው ።

በዚህ ጊዜ ኢግናት እፎይ በሚል ስሜት ፈገግ
ብሎ ፡ —

«ይኸ ከሆነ ጥሩ ነው ። ግን እኔ የፋብሪካ ሥራ
ባገኝ እመርጣለሁኝ ። የፋብሪካ ሠራተኞች በጣም ብል
ህ ሰዎች ናቸው ይባላል…» አለ ።

እናት ከተቀመጠችበት ብድግ አለች እና ወደ
መስኮቱ ሄደች ።

«ወይ ኑሮ! በጣም የሚገርም ነገር ነው ። ደስታ
እና ሃዘን ይፈራረቅበታል ። አምስት ጊዜ በቀን ስቀ
ህ እንደሆን ፤ አምስት ጊዜ ደግሞ ታለቅሳለህ ። እሺ ፤
ኢግናት ፤ ጨረስክ ፤ አይደለም? በል እንግዲህ ትንሽም
ቢሆን ጋደም በል…» አለች ።

«እኔን አሁን እንቅልፍ አይሻኝም…» አለ ።



«ኧረ እባክህ ናና ተኛ…» አለችው ።

«እርስዎ በጣም ጥንቁቅ ነዎት ። አይደሉምን? እሺ
መጣሁኝ ። ለሻዩ አመሰግናለሁኝ ።… ለደግነትዎም ጭም
ር…» አላት ።

ወደ እናት የመኝታ ክፍል እንደደረሰ እራሱን
እያካከከ የሚከተለውን በልቡ ማሰላሰል ቀጠለ ፡ —

«አሁን እንግዲህ ክፍሉ ሁሉ ቅርጣን-ቅርጣን ሊ
ሸት ነው…አይይ! እዚህ እርስዎ ክፍል ልተኛ! አሄ
ሄ! ኤጭ! ኧረ ደግም አይደል! እኔ እንደሆንኩ እንቅ
ልፌ አልመጣ! እርሱ ግን ስለ እነዚያ መሀል ሠፋ
ሪዎች እንዴት ፈጥኖ ነው ሃሣብ ያቀረበ… እነዚያ
ጭራቆች…» እያለ አሰላሰለ ።

ሳይታወቀው ወዲያውኑ እንቅልፍ ይዞት ጭልጥ
አለ ። አፉን በግማሽ ከፈት አድርጎ እና ቅንድቦቹ
ትንሽ ከፍ እንደማለት ብለው በእንቅልፍ ድብን
ብሎ ተውጦ በጉልህ ያንኮራፋል ።

## 21

በዚያን ምሽት ከምድር ቤት በታች በሚገኝ
አነስተኛ ክፍል ውስጥ ከኒኮላይ ፊት ለፊት ተቀምጦ
ዝግተኛ በሆነ አነጋገር ምሥጢራዊ በሆነ ሁኔታ የሚ
ከተለውን ተናገረ ።

«መካከለኛውን መስኮት አራት ጊዜ…» አለ ።

«አራት ጊዜ?» አለው ልጁን ኒኮላይ ምን ማለቱ
እንደሆነ ለመረዳት በጓጓ ሁኔታ እየተመለከተው ።

«መጀመርያ እንደዚህ ባለ ፍጥነት እና ድምፅ
ሦስት ጊዜ…» አለው መስኮት የሚያንኳኳ መስሎ
በጣቶቹ ጠረጴዛውን እያንኳኳ ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«ከዚያም ትንሽ ቆየት ካልክ በኋላ አንዴ ታንኳኳ
ለህ» አለው ።

«እ-ህ!» አለ ኒኮላይ ነገሩ ገብቶት ።

«ቀይ ፀጉር ያለው ገበሬ ከቤቱ ውስጥ ወጥቶ በሩን ይከፍትልሃል ። ከዚያም ‘ምጥ አዋላጂቱን ነውን የሚፈልጉት?’ በማለት ይጠይቅሃል ። አንተም ፡ — ‘እዎን ከባለ ፋብሪካው ሚስት ዘንድ ነው የመጣሁት’ በማለት ትመልስለታለህ ። ከዚህ በኋላ ምስጢራዊ በሆነው በኮድ ንግግራችሁ ስለተግባባችሁ ማንነትህን ይረዳል» በማለት ልጅየው ኒኮላይን ነገረው ።

እናት እጆቿን እጥፍጥፍ አድርጋ እነርሱን-እነርሱን ስትመለከታቸው ጠንካሮች የሆኑት ሁለቱ ጭንቅላቶቻቸውን አስጠግተው ዝግ እና ቀስ ባለ ሁኔታ ይወያያሉ ። ምሥጢራዊ በሆነ ኮድ እንዴት እንደሚንኳኳ እና በምሥጥራዊ ኮድ ተነጋግሮ መግባባት እንዴት እንደሚቻል በመስማቷ ተደነቀች ።

«ገና ልጅነታቸውን አልጨረሱም» በማለት በሃሣቧ ታወጣ-ታወርድ ጀመር ።

ግድግዳው ላይ የሚበራው መብራት ወለሉ ላይ በሚገኙት አንዳንድ የወላለቁ ባልዲዎች እና ቆርቆሮዎች ላይ ብርሃኑን ፈንጥቆባቸዋል ። ክፍሉ እና-እና ፤ ቀለም-ቀለም እና የርጥበት ሽታም አለው ።

ኢግናት ከሚወደው እና ጠጉራማ ከሆነ ጨርቅ የተሠራ ወፍራም ካፖርት ለብሶአል ። የእጆቹን እጅጌዎቹ ከፍ-ከፍ ማድረግ እንዴት ደስ እንደሚለው ፤ አንገቱን መለስ-ቀለስ እያደረገ ግዙፍ ትከሻዎቹን እንዴት እንደሚመለከት እናት አስተውላዋለች ።

«ገና ልጅነታቸውን ያልጨረሱ እኮ ናቸው… የተባረኩ ልጆች እኮ ናቸው…» እያለች ታሰላስላለች ።

«ይኸው ነው» አለ ኢግናት ከተቀመጠበት እየተነሳ ። ከዚያም ቀጠል አድርጎ ፡ —

«መጀመርያ ሙራቶቭ ዘንድ ሂደህ አያቱን መጠየቅ ያለብህ መሆኑን አትዘንጋ» አለው ።



«አስታወስኩ!» አለ ቬሶቭሺኮቭ ።

ኢግናት ግን ቬሶቭሺኮቭ ሁሉንም ነገር በሚገባ የተገነዘበው መስሎ ስላልታየው ሊሰናበተው እጁን አንስቶ ከመጨበጡ በፊት እንደገና እየደጋገመ የማንኳኳት ኮድ ፤ የምስጢር ንግግር ኮዶችን ያብራራለት ጀመር ። ከዚያም —

«ሰላምታዬን አድርስልኝ ። እነዚያ ሰዎች እንዴት ያሉ ግሩም ሰዎች እንደሆኑ ታያቸዋለህ…» አለው ።

ካፖርቱን ዝቅ ብሎ እየተመለከተ አባባሉ ትክክል መሆኑን በሚያረጋግጥ ሁኔታ ዳበስ-ዳበስ ያደርግ ጀመር ። ከዚያም እናትን መልከት አድርጎ ፡ —

«ልሂድን?» አለ ።

«መንገዱ አይሳሳትህምን?» አለችው ።

«አይሳሳተኝም ። እሺ ደህና ሁኑልኝ ጓዶች!» ብሎ ተሰናበታቸው ።

እና ከትከሻው ኮራ ከደረቱ ደራ ብሎ ፤ አዲስ ባርኔጣውን በአንድ ጆሮው በኩል ጣመም አድርጎ አጥልቆ እጆቹ በደፋርነት መንፈስ ኪሶቹ ውስጥ ጠለቅ ብለው ገብተው ወጥቶ ሄደ ። ቅንጥ እና ቅንጡ በድምድም ፀጉሮች ተከብበዋል ።

ቬሶቭሺኮቭ ወደ እናት ዘንድ ሂዶ ቀረብ ካለች በኋላ ለስለስ ባለ አነጋገር ፡ —

«ይኸው እንግዲህ እኔም የተግባሩ ተካፋይ ሁኜ ሥራ ተሰጠኝ ማለት ነው ። ከዚያ ከእሥር ቤት የወጣሁት እንደው ነው ለካ እያልኩኝ ያለ ሥራ በመቀመጤ በመሰልቸቴ ምክንያት አዝን ነበር ። ከእሥር ቤት እንደአመሰጥሁ ቀን ሌሊት እንዳልያዝ ተሸሽጌ መቀመጥ እንጂ ሌላ የምሠራው ነገር አልነበረም ። እሥር ቤት ሁኜ ግን ብዙ ነገሮች እማር ነበር ። ፓቬል ጭንቅላታችንን እንድንጠቀምበት ያደርገን ነበር ። እናት ፤ እረ ለመሆኑ ፤ ከእሥር ቤት ስለማምለጣቸው ጉዳይ ምን ተወሰነ?» በማለት ጠየቀ ።

«እኔ እንጃ» አለች ትንፋሿን ዋጥ እያደረገች ።

ኒኮላይ እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጎ ተጠጋት ። ከዚያም የሚከተለውን ተናገራት ፡ —

«እንግዲህ በጉዳዩ እርስዎ እነሱን አነጋግሩአቸው ። እርስዎን ይሰሙዎታል ። ከእሥር ቤት እነርሱ እንዲያመልጡ የተዘጋጀው ዕቅድ በጣም ቀላል የሆነ ዕቅድ ነው ። ለምሳሌ ፤ የእሥር ቤቱ ግድግዳ ፤ ይሄ ግድግዳ ነው ብለን እንገምት ። ግድግዳውን ተታክኮ ደግሞ የመንገድ መብራት ተተክሎአል ። ከመንገዱ ባሻገር ባዶ ቦታ ይገኛል ። በስተግራ በኩል መካነ-መቃብሩ ይገኛል ። በስተቀኝ በኩል ደግሞ ጎዳናዎች እና ሕንፃዎች ይገኛሉ ። በየቀኑ የጎዳናዎችን መብራት አምፑሎች የሚያጸዳው ሰው በጎዳናዎች ላይ ያሉትን መብራቶች ይወለውላል ። አሁን የእኛ ዕቅድ በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ አምፑሎቹን የሚያጸዳው ሰው መሰላሉን የመብራቱ ምሰሶ ላይ ሳይሆን የእሥር ቤቱ ግድግዳ ላይ አስደግፎ ይወጣል ። ከዚያም ለመወጣጫ እንዲሆን ልክ እንደመሰላል ተጠላልፎ የተሠራውን የገመድ-መሰላል ግድግዳው ጫፍ ላይ ከቋጠረ በኋላ ወደ እሥር ቤቱ ግቢ ቁልቁል ይለቅቀዋል ። በቃ! ጉዳዩ እስከዚህ ድረስ ነው! ይኸ ጉዳይ መች እንደሚከናወን እሥር ቤት ያሉት ጓዶቻችን አስቀድመው እንዲያውቁት ይደረጋል ። ከዚያም እሥር ቤት ያሉት ጓዶች ፤ ተራ ወንጀለኞችን ብጥብጥ እንዲፈጥሩ ያደርጓቸዋል ። ወይንም እነርሱው ራሳቸው አውቀው ብጥብጥ እና ሁካታ ይፈጥራሉ ። ይኸም የሚደረግበት ምክንያት ፤ የእሥር ቤቱ ዘበኞች ሁካታ እና ብጥብጡን ለማብረድ ከወዲያ ወዲህ ሲሯሯጡ ጓዶቻችን በተዘጋጀላቸው የገመድ መወጣጫ መሰላል ግንቡን እየወጡ እንዲያመልጡ ለማድረግ ነው ። ምንም የሚያስቸግር ጉዳይ አይደለም ። ተዘጋጅ! አንድ-ሁለት-ሦስት!



ብሎ ብቻ ግድግዳውን በመሰላሉ እየተረማመዱ መጥፋት ነው ። ይኸው ነው!» አለ ።

ይኸንን ግልጽ የሆነ ፤ ቀላል እና በሚገባ የተጠና ዕቅዱን ለእናት ለማስረዳት እጁን ስዕሎች እንደሚስል ሰው ከወዲያ ወዲህ እያወዛወዘ ድርጊቱ እንዴት እንደሚከናወን አስረዳት ። ከዚህ በፊት ፤ ኒኮላይ ለእርሷ ሁል ጊዜም ቅፍፍ የሚለው እና ጎታታ የሆነ ሰው መስሎ ይታያት ነበር ። ዐይኖቹም ማናቸውንም ነገሮች የሚቃኙት በአኩራፊነት እና በተጠራጣሪነት ስሜት መስሎ ይሰማት ነበር ። አሁን ግን ዐይኖቹ ፍጹም ልዩ የሆነ አመለካከት ያላቸው መሰላት ፡ — እርሷን በእቅድ ለማሳመን ሲጥር ዐይኖቹም ስሜት በተመላበት ብሩኅ አመለካከት ተውጠዋል ።

ቀጠል አድርጎም ኒኮላይ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«እና ዋናው ነገር ደግሞ የሚከተለው ነው ፡ — ከእሥር ቤት እንዲያመልጡ የሚደረገው በምሽት ሳይሆን በቀን ነው ። ልብ አድርጉ ፤ የሚያመልጡት ማታ አይደለም ። ቀን ነው! መላው እሥር ቤት ነግቶለት ሽር-ጉድ በሚልበት ቀን ሰአት ላይ እሥረኞች ከእሥር ቤት ይጠፋሉ ብሎ የሚጠረጥር ከቶ ማን ሊኖር ይችላል?» አላት ።

«ተኩስ የከፈቱባቸው እንደሆንስ?» አለች እናት ሁኔታው ታይቶአት ስቅጥጥ እንደማለት ብላ ።

«እነማ? ወታደሮች እዚያ የሉም ። የእሥር ቤት ዘበኞችም ቢሆኑ የሪቮልቨር ሽጉጣቸውን ሰደፍ የሚጠቀሙበት በየእንጨቱ ላይ ያፈጠጠ ምስማር ለመቀጥቀጫ ነው…» አላት ።

«ጉዳዩ በጣም ቀላል ጉዳይ ይመስላል…» አለችው ።

«ግዴለዎትም ያዩታል ። ብቻ እርስዎ በጉዳዩ እነርሱን አነጋግሩአቸው ። እኔ ማናቸውንም የሚያስፈልገ

ውን መሰናዶ አዘጋጅቻለሁኝ ። የገመድ መሰላሉን አዘጋጅቻለሁኝ ። ግድግዳው ጫፍ ላይ ገመዱን ቋጥሮ በማነቅ እንዲያንጠለጥል የሚያደርገውን ሜንጦ አዘጋጅቼአለሁኝ ። እኔ የምኖርበት ቤት ባለቤት ደግሞ የመንገዶቹን አምፑል የሚወለውል ሠራተኛ በመምሰል በተግባሩ ይሠማራል» አላት ።

በሌላኛው የቤታቸው በር በኩል አንድ ሰው ጉሮሮውን በመጥረግ ሁኔታ እ-ኸ-ኸ! የማለት ሳል ሳለ ። እግሮቹን መሬቱ ላይ ከመድቃቱም በስተቀር የቆርቆሮ ድምፅ እያንኳኳ አሰማ ።

«እሱ ነው የመጣው!» አላት ኒኮላይ ።

በሩ ሲከፈት ቀጠን ያለ የመታጠቢያ ሳፋ ብቅ አለ ። ከዚያም አንድ ጎርናና ድምፅ ፡ —

«በል እንግዲህ ሁሉም ነገር ተዘጋጅቶአል ። አንተ ሰይጣን...» የሚል ድምፅ አሰማ ።

ከዚያም ከያዘው ሳፋ በኋላ ዐይኖቹ ጎረጥ-ጎረጥ ብለው የወጡ እና የደግነት መንፈስ ያለበት የሚመስል ፤ ራሱ ላይ ባርኔጣ ያላደረገ እና ፀጉሩ የሸበተው ሰው ብቅ አለ ።

ኒኮላይ ሳፋውን ተቀበለው ። ከዚያም ጎርነን ባለ ድምፅ ሳሉን የሚስል ፤ አክታውን መሬት ላይ ትፍ እያለ የሚተፋ አንድ ቁመተ-ረዥምም ሰው ወደ ቤት ገባ ። ከዚያም በቤት ውስጥ ካሉት ጋር በጎርናና ድምፁ የእንደምን አላችሁ ሰላምታ ተለዋወጠ ።

«ጤና ይስጥልኝ እንደምን ነዎት?»

«ይኸውልዎ ፤ ይጠይቁት!» አላት ኒኮላይ እናትን ።

«ምንድነው የሚጠይቁኝ?» በማለት እንግዳው ሰው ኒኮላይን ጠየቀው ።

«ከእሥር ቤት ጓዶች እንዲጠፉ ዝግጅቱ እንዴት እንደሆነ» አለ ኒኮላይ ።

«አሃ!» አለ ቆርቆሮ ሠራተኛው ሪዙን በቆርቆሮ



እድፍ በተበከሉ ጣቶቹ አሸትሽት እያደረገ ።

«ያዕቆብ ቫሲሌቪች ፤ ጉዳዩ ቀላል ጉዳይ መሆኑን እናት አላመኑበትም» አለው ኒኮላይ ለቆርቆሮ ሠራተኛው ።

«እንዴ! እንዴት? አላመኑበትም? ይኸ ከሆነማ እነርሱ እንዲያመልጡ እርሳቸው አይፈልጉም ማለት ነው ። እኔ እና አንተ ግን እንዲያመልጡ እንፈልጋለን ። ስለዚህም ጉዳዩ ቀላል ነው ብለን እናምናለን!» በማለት ረጋ ብሎ ተናገረ ቆርቆሮ ሠራተኛው ። ድንገትም ሳሉ መጣበት እና ሰውነቱ ከሁለት ላይ እጥፍ ብሎ ታጥፎ ይስል ጀመር ። ሳሉን ስሎ ካበቃ በኋላ ደረቱን እያሻሸ ጎረጥ-ጎረጥ ባሉት ዐይኖቹ እናትን ትክ ብሎ እየተመለከተ በማጥናት ክፍሉ ውስጥ ከሚገኝ መሃል ቦታ ላይ ሂዶ ለጥቂት ጊዜ ቆም አለ ።

«ይኸንን ጉዳይ ፓቬል እና ጓዶቹ ውሳኔ ያሳርፉበታል» አለች እናት ።

ኒኮላይ ጭንቅላቱን ወደ መሬት ቀለስ አደረገ ።

«ፓቬል ማለት የቱ ነው?» በማለት ቆርቆሮ ሠራተኛው ወደ መቀመጫው ሂዶ እየተቀመጠ ጠየቀ ።

«ልጄ ነው» አለችው ።

«የአባቱ ስም ማን ይባላል?» አላት ።

«ቭላሶቭ ይባላል» አለችው ።

እህ! በሚል ሁኔታ ጭንቅላቱን ወዝወዝ አደረገ ። የትምባሆ ማስቀመጫ ቆርቆሮውን ከኪሱ አውጥቶም ትምባሆውን ፒፓው ውስጥ ይሰገስግ ጀመር ። ከዚያም ፡ —

«አዎ ፤ ስለእርሱ ሰምቻለሁኝ ። የወንድሜ ልጅ ያውቀዋል ። የወንድሜም ልጅ እሥር ቤት ነው ። የቭቸንኮ ይባላል ። ያውቁታልን? እኔ ጎቡን እባላለሁኝ ። ባለሥልጣኖቹ ወጣት-ወጣቶቹን በሙሉ እየለቀሙ እሥ

ር ቤት ሳያጉሯቸው አይቀሩም ። እኛ ሽማግሎቹን
እንዳያጣብቡን ቦታው እንዲሰፋን መሆኑ ነዋ! አንድ
ጃንዳርም የወንድሜ ልጅ ሳይቤርያ ለግዞት የሚላክ
መሆኑን ነግሮኛል ። እነዚህ ውሾች ግዞት ይሰዱታል!»
አለ ።

ቆርቆሮ ሠራተኛው ፒፓውን እያጨሰ እና አሁ
ንም-አሁንም አክታውን ወለሉ ላይ ትፍ እያለ ኒኮ
ላይ-ኒኮላይን ይመለከታል ። ከዚያም ኒኮላይን ፡—

«እና እንግዲህ እርሳቸው የእነርሱን ከእሥር ቤት
መጥፋት አይፈልጉም ማለት ነዋ? ይኸ የርሳቸው ጉዳ
ይ ነው» አለ ሰውነቱን ጎነጥ እያደረገ ። ቀጠል አድር
ጎም ፡—

«አንድ ሰው ከተያዘበት ወጥቶ ነፃ ሲሆን ፤ መቀ
መጥ ቢደክመው ይንሸራሸራል ። መንሸራሸር ቢደክመ
ውም ይቀመጣል ። ሊዘርፉህ ሲሉ ዐይንን መጨፈንን ።
ሊደበድቡህ ሲሉ አለመጮህን ። ሊገድሉህ ሲሉ መንጋ
ለልን ። ይኸን ማድረግ ቀላል ነው ። ሁሉም ያውቅበ
ታል ። እኔ ግን የወንድሜን ልጅ ከዚያ ከታሠረበት
አወጣዋለሁኝ ። ለዚህ አትጠራጠሩ» በማለት ተናገረ ።

እናት እነዚህን ዐረፍተ ነገሮቹን እንደምን ባለ
ሁኔታ አድርቆ እንዳቀረባቸው በማሰብ ተገረመች ።
የመጨረሻዎቹን ቃላቶች ያቀረባቸው በሙሉ ልብ
እርግጠኛ ሁኖ በመሆኑ ደግሞ ቀናችበት ።

ያ ቀዝቃዛ ነፋስ እየነፈሰ እና ዝናቡም ፊት-
ፊቷን እየገረፋት በመንገዱ ላይ ስትጓዝ የኒኮላይ
ሁኔታ እያስደነቃት ፡—

«እንዴት እንዲህ ልውጥ ብሎ ተለወጠ ። የሚገ
ርም እኮ ነው!» በማለት በሃሳቧ ታሰላስላለች ።

ጎቡንን ስታስታውስ ፤ «እኔ ብቻ አይደለሁም አዲ
ስ ሕይወት የጀመርኩት!…» ብላ አሰበች ።

ከዚያም በሃሣቧ ፡—



«ብቻ ልጄ በጉዳዩ ተስማምቶበት እሺ ባለን!»
እያለች ታሰላስል ጀመር ።

22

በማግሥቱ እሁድ ቀን ፓቬልን እሥር ቤቱ
ውስጥ በሚገኝ ክፍል ውስጥ ተገናኝታው ስትሰናበ
ተው የተጠቀለለች ትንሽ ወረቀት የእጅ መዳፏ ውስ
ጥ ጫን አድርጎ ሲያስቀምጥላት ተሰማት ። እጅዋን
እሳት የሚፈጃት ያህል የተሰማት ከመሆኑም በስተ
ቀር አንድ ምልክት የሚሰጣት መስሎአት ትክ
ብላ እርሱን-እርሱን ትመለከተዋለች ። እርሱ ግን ምን
ም ምልክት አላሳያትም ። የፓቬል ሰማያዊ ዐይኖች
ያው እንደቀድሞአቸው ረጋ ያለ የወሳኝነት ፈገግ
ታቸውን ፈገግ ይላሉ ።

«በል ደህና ሁን!» አለችው ቸንፋሿን እየዋጠች ።

እጁን እንደገና ዘረጋ እና ያዝ አደረጋት ። በፊቱ
ላይ የደግነት የርኅራኄ ባሕርይ ረብቦበታል ።

«እናትዬ ደህና ሁኚ!» አላት ።

በእጁ እንደያዛት ቆየት አለች ።

«አታስቢ ። አትበሳጪ!» አላት ።

ያዳመጠችውን እነዚህን ቃላት እና የግትርነት
መሥመር ያሠመሩትን የግንባሩን ሽብሽቦች ብቻ ኩ
ምትርትር አድርጎ ሸብሽቦአቸዋል ።

«የኔ ሸጋ ። ምን አልክ…» አለች ዝግ ባለ አነ
ጋገር ራሷን ወደመሬት ቀለስ አድርጋ ።

ከዐይኖቿ የሚፈስሱትን እንባዎቿን እና የሚን
ቀጠቀጡ ከናፍሮቿን እንዳያይባት በማሰብ እንደገና
ፊቱን ዞር ብላ ሳትመለከተው ዝም ብላ ተፋጥና
ሄደች ። እቤት እስክትደርስ ድረስ በእጅዋ ያስጨበጣት
ወረቀት እንደ ቁርጥማት የሚቆረጥም ፤ እንደ አሎሎ

ር ቤት ሳያጉሯቸው አይቀሩም ። እኛ ሽማግሎቹን እንዳያጣብቡን ቦታው እንዲሰፋን መሆኑ ነዋ! አንድ ጃንዳርም የወንድሜ ልጅ ሳይቢርያ ለግዞት የሚላክ መሆኑን ነግሮኛል ። እነዚህ ውሾች ግዞት ይሰዱታል!» አለ ።

ቆርቆሮ ሠራተኛው ፒፓውን እያጨሰ እና አሁንም-አሁንም አክታውን ወለሉ ላይ ትፍ እያለ ኒኮላይ-ኒኮላይን ይመለከታል ። ከዚያም ኒኮላይን ፡ —

«እና እንግዲህ እርሳቸው የእነርሱን ከእሥር ቤት መጥፋት አይፈልጉም ማለት ነዋ? ይኽ የርሳቸው ጉዳይ ነው» አለ ሰውነቱን ጎነጥ እያደረገ ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«አንድ ሰው ከተያዘበት ወጥቶ ነፃ ሲሆን ፤ መቀመጥ ቢደክመው ይንሸራሸራል ። መንሸራሸር ቢደክመውም ይቀመጣል ። ሊዘርፉህ ሲሉ ዐይንን መጨፈንን ። ሊደበድቡህ ሲሉ አለመጮህን ። ሊገድሉህ ሲሉ መንጋለልን ። ይኽን ማድረግ ቀላል ነው ። ሁሉም ያውቅበታል ። እኔ ግን የወንድሜን ልጅ ከዚያ ከታሠረበት አወጣዋለሁኝ ። ለዚህ አትጠራጠሩ» በማለት ተናገረ ።

እናት እነዚህን ዐረፍተ ነገሮቹን እንደምን ባለ ሁኔታ አድርቆ እንዳቀረባቸው በማሰብ ተገረመች ። የመጨረሻዎቹን ቃላቶች ያቀረባቸው በሙሉ ልብ እርግጠኛ ሁኖ በመሆኑ ደግሞ ቀናችበት ።

ያ ቀዝቃዛ ነፋስ እየነፈሰ እና ዝናቡም ፊት-ፊቷን እየገረፋት በመንገዱ ላይ ስትጓዝ የኒኮላይ ሁኔታ እያስደነቃት ፡ —

«እንዴት እንዲህ ልውጥ ብሎ ተለወጠ ። የሚገርም እኮ ነው!» በማለት በሃሳቧ ታሰላስላለች ።

ኅቡንን ስታስታውስ ፤ «እኔ ብቻ አይደለሁም አዲስ ሕይወት የጀመርኩት!...» ብላ አሰበች ።

ከዚያም በሃሣቧ ፡ —



«ብቻ ልጄ በጉዳዩ ተስማምቶበት እሺ ባለን!» እያለች ታሰላስል ጀመር ።

22

በማግሥቱ እሁድ ቀን ፓቬልን እሥር ቤቱ ውስጥ በሚገኝ ክፍል ውስጥ ተገናኝታው ስትሰናበተው የተጠቀለለች ትንሽ ወረቀት የእጅ መዳፏ ውስጥ ጫን አድርጎ ሲያስቀምጥላት ተሰማት ። እጅዋን እሳት የሚፈጃት ያህል የተሰማት ከመሆኑም በስተቀር አንድ ምልክት የሚሰጣት መስሎአት ትክ ብላ እርሱን-እርሱን ትመለከተዋለች ። እርሱ ግን ምንም ምልክት አላሳያትም ። የፓቬል ሰማያዊ ዐይኖችያው እንደቀድሞአቸው ረጋ ያለ የወሳኝነት ፈገግታቸውን ፈገግ ይላሉ ።

«በል ደህና ሁን!» አለችው ችንፋሿን እየዋጠች ።

እጁን እንደገና ዘረጋ እና ያዝ አደረጋት ። በፊቱ ላይ የደግነት የርኅራኄ ባሕርይ ረብቦበታል ።

«እናትዬ ደህና ሁኚ!» አላት ።

በእጇ እንደያዛት ቆየት አለች ።

«አታስቢ ። አትበሳጪ!» አላት ።

ያዳመጠችውን እነዚህን ቃላት እና የግትርነት መሥመር ያሠመሩትን የግንባሩን ሽብሽቦች ብቻ ኩምትርትር አድርጎ ሽብሽቦአቸዋል ።

«የኔ ሸጋ ። ምን አልክ...» አለች ዝግ ባለ አነጋገር ራሷን ወደመሬት ቀለስ አድርጋ ።

ከዐይኖቿ የሚፈስሱትን እንባዎቿን እና የሚንቀጠቀጡ ከናፍሮቿን እንዳያይባት በማሰብ እንደገና ፊቱን ዞር ብላ ሳትመለከተው ዝም ብላ ተፋጥና ሄደች ። እቤት እስክትደርስ ድረስ በእጅዋ ያስጨበጣት ወረቀት እንደ ቁርጥማት የሚቆረጥም ፤ እንደ አሎሎ

የሚከብድ ሁኖ ተሰማት ። ውዲያውኑ እቤት እንደደ
ረሰች ልጂ በተስፋ ተመልቶ ምን መልዕክት እንደ
ያዘ ለማዳመጥ እየተቻኮለች ወረቀቱን ለኒኮላይ ሰጠ
ችው ። ኒኮላይ ግን ይኸንን ተስፋ በዕውን የሚረጋገጥ
አላደረገውም ። የሚከተለውን ነገራት ፤ —

«ቀድሞውኑም ቢሆን እኔ ምን እንደሚል አው
ቄዋለሁኝ ። ይኸውልዎት የጻፈው ፤ — ‘ጓዶች ፤ ከእሥር
ቤት የመጥፋት ሙከራ አናደርግም ። ይኸንን ማድረግ
አንችልም ። ከእኛ መሃል አንዳችንም ብንሆን ይኸን
ን ማድረግ አንችልም ። ይኸንን ብናደርግ ይዘነው ያለ
ውን የራሳችንን ክብር ከላያችን ላይ መግፈፍ ይሆ
ንብናል ። ይሁን እንጂ ፤ አሁን በቅርቡ ተይዞ የታሠ
ረውን ገበሬ ለመርዳት ሞክሩ ። የእናንተ እርዳታ ያስ
ፈልገዋል ። ማናቸውም የምታደርጉለት ዕርዳታ ደግሞ
ለእርሱ ይደረግለት ዘንድ የሚገባ ነው ። እርሱ እዚ
ህ የሚገኝበት ሁኔታ አንጉል ነው ። በየዕለቱ ከባለ
ሥልጣኖች ጋር ይጋጫል ። ገና ካሁኑ ጭለማ ቤት
ውስጥ ቀን እና ሌሊት በቅጣት ታሥሮ እን
ዲቆይ ተደርጎአል ። እስኪሞት ድረስ ያሰቃዩታል ።
እርሱን እንድትረዱት ሁላችንም እንጠይቃችኋለን ።
እናቴን አጽናኑልኝ ። ማናቸውንም ነገር ንገሯት ። ይገባ
ታል ። ትገነዘበዋለች ።’»

እናት ጭንቅላቷን ቀና አደረገች ።

«ምኑን ነው የምንነገረው ። ቀድሞውንም ቢሆን
የማውቀው ነው»በማለት በሚንቀጠቀጡ ድምፆቿ
እናት ተናገረች ።

ኒኮላይ ድንገት ዞር አለ ። ከኪሱ መሀረብ አውጥቶ
አፍንጫውን ተናፈጠ ።

«ጉንፋን ሳይዘኝ አልቀረም...» በማለት የዐይኖ
ቹን መነጽር ገፋ እያደረገ እና ወለሉ ላይ ጎርደድ
እያለ ተናገረ ። ከዚያም ፤ —



«ያም ሆኖ ደግሞ ፤ ጉዳዩን ለማከናወንም ጊዜው
አይበቃንም ነበር» አለ ።

«አይ እንግዲህ ፤ ምን ይደረጋል ። ፍርዳቸውን ይጠብ
በቋ!» አለች እናት ሀዘን ልቧ ገብቶ እና ፊቷም
በቅሬታ ኮስተር ብሎ ።

«ይኸውልዎ ፤ ከፒተርበርግ ገና አሁን አንድ
ደብዳቤ ደረሰኝ...» አላት ኒኮላይ ።

«የሆነው ይሁን እንጂ ፤ ሳይቤርያ በግዞት ከተላከ
በኋላ ከዚያ ማምለጥ ይችላል ። አይችልም እንዴ?»
አለችው ።

«እንዴታ ይችላል እንጂ! ይህንን ደብዳቤ ከፒተር
ቡርግ የጻፈልኝ ጓድ በቅርቡ ፍርዳቸውን የሚቀበሉ
መሆኑን እና የፍርዱም ዓይነት የተወሰነ መሆኑን ገል
ጾልኛል ። — ሁሉም ጓዶች በግዞት እንዲጋዙ ይደረ
ጋሉ ። ይኸውልዎ እነዚህ ሞኝላቆች የእነርሱ ፍትህ
አስቂኝ የሆነ መዘባበቻ መሆኑን እያስመሰከሩ ነው ።
እስኪ ልብ ብለው ያስተውሉት ፤ — የሰዎቹ ጉዳይ
እዚህ በፍርድ ከመታየቱ በፊት የሚቀበሉት ቅጣት
የፍርድ ውሳኔ እዚያ ፒተርቡርግ ተበይኖ አብቅቶ
አል!» በማለት ኒኮላይ ተናገረ ።

«ግዴለም አትጨነቅ ፤ ኒኮላይ ኢቫኖቪች!» አለች
እናት ጠንከር ባለ መንፈስ ተበረታትታ ። ቀጠል
አድርጋም ።

«ይኸንን ለእኔ ማስረዳት ወይንም እኔን ማጽናናት
አያስፈልግም ። ፓቬል የሚያከናውነው ማከናወን ያለበ
ትን ተገቢ ተግባር ነው ። እርሱ እና ጓዶቹ ያለ
በቂ ምክንያት እሥር ቤት በመቆየት እንዲሰቃዩ አያ
ደርግም ። አሁንም ይወድደኛል ። ስለእኔ እንዴት እን
ደሚያስብ ከደብዳቤው ማየት ይቻላል ። ጉዳዩን አብ
ራሩላት ። አጽናኑአት ብሎ ጽፎአል...» አለችው ።

ልቧ በፍጥነት ይመታ ጀመር ። በሃሣብ እና በቅ

ሬታ ራሷ ዞረባት ። ኒኮላይ ከዚህ ቀደም አሰምቶት በማያውቀው ጉልህ ድምጽ ፡ —

«ልጅዎ ግሩም-ድንቅ የሆነ ሰው ነው ። እኔ እርሱን የቱን ያህል እንደማከብረው ልገልጽልዎ አልችልም!» አላት ።

«ሪቢንን ልንረዳው የምንችልበትን መንገድ እና ስብ» በማለት እናት ኒኮላይን አሳሰበችው ።

በዚህ በአሁኑ ቅጽበት ልትረዳው የምትችልበትን አንድ ነገር ለማድረግ በጣም ፈለገች ። ሰውነቷ ዝሎ እስኪያልቅ ድረስ የትም ቦታ ቢሆን ሳትታክት ለመጓዝ ፈለጋት ። አሁንም ወለሉ ላይ የሚንጎራደደው ኒኮላይ ፡ —

«እሺ ጥሩ ነው ። ለማናቸውም ጉዳይ ሳሻ ታስፈልገናለች…»አላት ።

«ሳሻ ትመጣለች ። እኔ ፓቬልን እሥር ቤት ልጠይቅ የሄድኩ ቀን ሁል ጊዜም ያንኑ ዕለት ሳሻ እቤት ትመጣለች…» አለችው ።

ኒኮላይ ፎቴው ላይ እናት አጠገብ ተቀመጠ ። በሃሣብ ተውጦ ጭንቅላቱን ወደታች ቀለስ አደረገ ። ከንፈሮቹን ይነክሳል ። ጢሙንም ያሻሻል ።

«ክፋቱ እህቴ እዚህ አለመገኘቷ ነው…» አለ ።

«ፓቬል ወደ ግዞት ሳይጋዝ እዚያው እሥር ቤት እንዳለ ጉዳዩን ብናከናውነው የተሻለ ይሆናል ። ድርጊቱ ሊያስደስተው ይችላል!» በማለት እናት ተናገረች ።

ለጥቂት ጊዜያት ምንም ሳይነጋገሩ እዚያው እነበሩበት ቦታ ዝም ብለው ቁጭ አሉ ።

«እኔ ግን የማይገባኝ ለምን ለማምለጥ እንደማይፈልግ እኮ ነው…» በማለት እናት ድንገት ተናገረች ።

ኒኮላይ ከተቀመጠበት ቦታ አፈፍ ብሎ ብድግ



አለ ። ይሁን እንጂ የቤቱ መጥሪያ ደወል ወዲያው ተደወለ ። እናት እና ኒኮላይ እርስ-በእርሳቸው ተያዩ ።

«ምንአልባት ሳሻ ሳትሆን አትቀርም» አለ ኒኮላይ ቀስ ብሎ ።

«ምን ብለን እንንገራት?» አለች እናትም ቀስ ባለ አነጋገር ።

«እ-እ!» አለ ኒኮላይ ።

«እኔ በጣም ነው የማዝንላት» አለች እናት ።

የመጥሪያው ደወል እየተደጋገመ ይጣራ ጀመር ። አሁን ግን የደወሉ አጠራር ጨርሶ ባለ ማቋረጥ ተስፋ የመቁረጥ ዓይነት አጠራር ነው ። ኒኮላይም እናትም ወደበሩ አመሩ ። ማዕድ ማዘጋጃው ክፍል ሲደርሱ ኒኮላይ ቀረት ብሎ ፡ —

«እርስዎ ብቻዎን ሂደው ቢከፍቱ ይሻላል…» አላት ።

«ታዲያስ ። እምቢ አለ እንዴ?» በማለተ ገና እናት በሩን እንደከፈተችላት ልጃገረዲቱ ጠንከር አድርጋ እናትን ጠየቀቻት ።

«አዎን» በማለት እናት መለሰችላት ።

«እኔ ቀድሞም ቢሆን አውቄዋለሁኝ!» በማለት ቀዝቀዝ ባለ የቅሬታ አነጋገር ሳሻ ተናገረች ። ይሁን እንጂ ፊቷ በቅሬታ አመድ መስሎ ነበር ። የካፖርቷን ቁልፍ መፍታት ጀመረች ። ግማሹን እንደፈታች ካፖርቷን ከትከሻዋ ማውለቅ ሞከረች ።

«አቤት ንፋሱ እና ዝናቡ ። ብሽቅጥቅጥ ያለ ነው! ለመሆኑ እንዴት ነው ጤናው ። ደህና ነውን?» አለቻት ሳሻ እናትን ።

«አዎን» በማለት እናት መለሰችላት ።

«በጣም ጥሩ ። ይኸ ደስ የሚያሰኝ ነው» አለች ሳሻ እጆቿን እየተመለከተች ቀስ ባለ አነጋገር ።

«ሪቢንን ከታሰረበት ፡ እንዲያመልጥ ለማድረግ

እንድንሞክር ጽፎአል» በማለት እናት ሳሻን ሳትመለከታት ተናገረች ።

«ይኸ እንዲሆን ይሻልን? ይኸን የምናደርግ ከሆነ ደግሞ የቀድሞውን ፕላናችንን በተግባር ላይ ማዋል ይኖርብናል» በማለት ሳሻ ቀስ ብላ ተናገረች ። ኒኮላይ ድንገት ወደበሩ ብቅ ካለ በኋላ ፡ —

«እኔም ይኸው ይመስለኛል ። ሰላም ነሽ ሳሻ!» በማለት ተናገረ ።

ሳሻ እርሱን ለመጨበጥ እጅዋን ዘረጋች ።

«ለምን ፕላናችንን በተግባር ላይ አናውለውም? ሰው ሁሉ ግሩም ፕላን ነው ይላል!» አለች ።

«ግን ማን በሥራ ላይ ያውለው? ሁላችንም ፋታ በማይሰጡ ተግባሮች ተጠምደናል» አለ ኒኮላይ ። ሳሻ ፈጠን ብላ ከተቀመጠችበት በመነሳት ፡ —

«እኔ በሥራ ላይ ላውለው!እኔ ጊዜ አለኝ» አለች ።

«እሺ ። ግን ደግሞ ከሌሎቹ ጋር መገናኘት አለብሽ...» አላት ።

«እገናኛለሁኝ ። አሁኑኑ እሄዳለሁኝ» አለች ።

ካፖርቷን ለብሳ ቁልፎቿን መቆለፍ ጀመረች ። የአሁኑ ጊዜ አድራጎቷ ቀጫጭን የሆኑ ጣቶቿን ካፖርቱን ለብሳ ለመቆለፍ እርግጠኛ በሆነ ሁኔታ በማነቃነቅ ነበር ።

«እስኪ መጀመርያ ትንሽ እረፍ በይ!» አለቻት እናት ።

«አልደከመኝም...» አለች ሳሻ ረጋ ባለ ፈገግታ ።

ያው እንቀድሞዋ ቀዝቀዝ ባለ እና ኮስተር ባለ ሁኔታ ጭጭ ብላ እጅ-ለእጅ ከእነርሱ ጋር ከተጨባበጠች በኋላ ከቤት ወጥታ ሄደች ።

እናት እና ኒኮላይ በስተመስኮቱ በኩል ቆመው ሳሻ የጓሮውን የአትክልት ሥፍራ አልፋ በመግቢያው ዋና በር በኩል ለዐይን እስክትሰወር ድረስ ቆመው ተመለከቷት ። ኒኮላይ በዝግታ እያፏጨ ወደ ወንበሩ ሂዶ ከተቀመጠ በኋላ መጻፍ ጀመረ ።

«በሥራ እንድትጠመድ የሚያደርጋት እንዳች ተግባር ካገኘት ሻል ሊላት ይችላል» በማለት እናት በሃሣብ ተውጣ ተናገረች ።

«እንዴታ! ቀለል ይልላታል» በማለት ኒኮላይ መለሰላት ። ከዚያም ሩኅሩኅ በሆነ መልኩ ፈገግ በማለት ወደ እናት ዞር ካለ በኋላ ፡ —

«ኒሎቭና ፤ ይኸ ጽዋ እርስዎን ያለፈዎት ይመስላል ። በፍቅር ስሜት ተነድፈው ለሚያፈቅሩት ሰው የተሰቃዩ አይመስለኝም ። እውን?» አላት ።

«ፑህ!» አለች እናት እጅዋን እያወዛወዘች ።

«ምን ጊዜም አስብ-እስጋ የነበረው ካሁን-ካሁን አግብተው ወሰዱኝ በማለት ነበር!» አለች ።

«ያፈቀሩት ወንድ አንድም አልነበረምን?» አላት ።

«ትዝ አይለኝም ። እንደሚመስለኝ አንድ ያፈቀርኩት ነበር ። አንድ ያፈቀርኩት ሰው መኖር ነበረበት ። ብቻ ግን ትዝም አይለኝ ። ያገባሁት ባለቤቴ ይኸ ነው በማይባል ሁኔታ ይደበድበኝ ስለነበረ ፤ ከጋብቻ በፊት ቀደም ሲል የነበረው ትዝታ ሁሉ በድብደባ ምክንያት ከጭንቅላቴ ውስጥ ተወገደ» በማለት አዘኝ ብላ እርሱን እየተመለከተች ቀላል በሆነ አገላለጽ ተናግራ አበቃች ።

ኒኮላይ ወደ ጽሁፍ ጠረጴዛው ዞር አለ ። እናትም ለጊዜው ከክፍሉ ወጣ አለች ። ስትመለስ ኒኮላይ በሃሣብ በትዝታ ባሕር ሰጥሞ አገኘችው ። እናት-እናትን በፍቅር ስሜት እየተመለከታት ፡ —

«እኔ ግን ልክ የሳሻን ዓይነት ዕድል ደርሶብኝ ነበር ። አንዲት ልጃገረድ አፍቅሬ ነበር ። ግሩም የሆነች ልጃገረድ! ከእርሷ ጋር ተገናኝተን ስንተዋወቅ የሃያ ዓመት ሰው ነበርኩኝ ። ከዚያን ከተዋወቅንበት

ጊዜ ጀምሮ አፈቀርኳት ። ያኔ አፈቅራት የነበረውን ያህል አሁንም አፈቅራታለሁኝ ። በሙሉ ልቤ ፤ ታላቅ በሆነ ሁኔታ እና ለምንግዜውም አፈቅራታለሁኝ…» በማለት ተናገረ ።

በኒኮላይ ዐይኖች ውስጥ ቦግ ብለው የሚያበሩት የስሜት ብሩኅ ፋናዎች አጠገቡ ከተቀመጠችበት ቦታ ይታዩዋታል ። አበባ እየተውተረተረ ሰውነቱን ወደፀሐይ ብርሃን ሳብ-መዘዝ እንደሚያደርግ ሁሉ ፤ ኒኮላይም ወንበሩ ላይ ወደኋላ ዘርጋ በማለት ደገፍ ብሎ እና ሁለት እጆቹን በስተኋላው በኩል ጭን ቅላቱ ላይ አነባብሮ ፤ ጠንካራ አካሉ ተንሠራርቶ ተዘርግቶ በሩቅ ፤ በጥልቀት ተመስጦ ያሰላስላል ።

«ለምን አታገባትም?» በማለት እናት አሳሰበችው ።

«ካገባች አራት ዓመት ሆናት…» አላት ።

«አንተ መጀመርያውኑ ለምን አላገባሃትም?» አለችው ።

ለጥቂት ጊዜ አሰብ እንደማድረግ አለ ።

«አዎን ። ሳይሳካ ቀረ ። እኔ ከእሥር ቤት ስለቀቅ እርሷ ወደ እሥር ቤት ትገባለች ወይንም ግዞት ትጋዛለች ። እርሷ ደግሞ ነፃ ስትሆን እኔ እሥር ቤት እገባለሁኝ ። ልክ በሳሻ እና በፓቬል ላይ የደረሰውን ዓይነት ጉዳይ ይመስላል ። አይደለምን? በመጨረሻም እሥር ዓመት የግዞት እሥራት ተፈርዶባት ሳይቤርያ ውስጥ እጅግ ዳርቻማ ከሆኑት ቦታዎች ወደ አንድ ቦታ ተጋዘች ። ተከትያት ልሄድ ፈለግሁኝ ። ይሁን እንጂ ይኸን ለማድረግ ደግሞ አፈርኩኝ ። እርሷም እንደዚሁ ። እዚያ በግዞት የነበረችበት ቦታ ከሌላ ሰው ጋር ተዋወቀች ። በጣም ግሩም ከሆነ ሰው ጋር ። ከጓዶቹ መካከል አንዱ ነው ። በግዞት ከነበሩበት ቦታ ጠፍተው አመለጡ ። በአሁኑ ጊዜ ሁለቱም ውጪ ሀገር ናቸው…» በማለት ታሪኩን አጫወታት ።



ኒኮላይ መነጽሩን ከዐይኑ ላይ አወለቀ እና ጠራረገው ። ወደመብራቱ ቀረብ አድርጎ መነጽሩን እየተመለከተ አሁንም እንደገና ጠረገው ።

«የኔ ምስኪን ጓድ!» በማለት እናት በደረሰበት አጋጣሚ እያዘነችለት ራሷን ነቀነቀች ። ሁኔታው አሳዘናት ። ነገር ግን እናት በልጅዋ እንደምትስቅበት ሁሉ የኒኮላይም አንዳች ሁኔታ እንድትስቅበት አደረጋት ። ከተቀመጠበት ቀንጥንጥ ብሎ ዞር አለ ። ከዚያም ብዕሩን ብድግ በማድረግ ከንግግሩ ጋር አሳክቶ እያንቃነቀ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«አግብቶ ቤተሰብን መመሥረት የአንድን ሬቮሉሺናዊ ጉልበት ማጥጥ አድርጎ ይጨርሰዋል ። ሁኔታው ያስገድደዋል ። ልጆች ይወለዳሉ ። ከዛሬ-ነገ ምን ይደርስ ይሆን በማለት ያስባል ። ቤተሰቡን ለመቀለብ መሥራት ያስፈልገዋል ። ተግባሮቹን ይበልጥ እያስፋፋ ለመዝለቅ እንዲችል አንድ ሬቮሉሺናዊ ጉልበቱን አከማችቶ መኖር አለበት ። ይኸንን ጊዜው የሚጠይቀው ጉዳይ ነው ። አሮጌዋን ዓለም አፈራርሰን በምትኳ አዲሲቷን ዓለም ለመገንባት የታሪክ አደራ የተጣለብን ወዝ-አደሮች እኛ በመሆናችን ምንግዜም ቢሆን ከማንም በፊት በግንባር ቀደምትነት ወደፊት ቀድመን የምንገኝ መሆን አለብን ። በተቀዳጀናቸው በአንዳንድ በጥቃቅን ድሎች መነጠቅ ምክንያት ወይንም ደግሞ ታክቶን እና ደክሞን ወደኋላ የምናፈገፍግ ከሆነ የቆምንለትን ዓላማችንን የመክዳት ያህል ጥፋተኞች እንሆናለን ። የቆምንለትን ዓላማ ሳናሰናክል አብረነው ጎን ለጎን የምንራመደው ሌላ ማንም የለም ። የእኛ ተግባር አንዳንድ አነስተኛ የሆኑ ድሎችን መቀዳጀት ሳይሆን የተሟላ ድልን መጎናጸፍ መሆኑን መዘንጋት የለብንም» በማለት ተናገረ ።

ድምፁ ጠንካራ ሆነ ። ፊቱ ኮስተር አለ ። ዐይኖቹም እንደቀድሞው የብርሃን ፍልቅልቅታ ይፈነጥቁ ጀመር ። እንደገና ሌላ የደወል ጥሪ ከበራፉ ተሰማ ። ሉድሚላ ነበረች ። ጉንጮቿ በብርድ ቅልት ብለዋል ። ለወራቱ የማይስማማ ስስ ካፖርት የለበሰች በመሆኗ ሰውነቷ በሙሉ በብርድ ይንቀጠቀጣል ። ያረጀ የላስቲክ ቡት ጫማዋን እያወለቀች ፡ —

«ዳኞቹ ተሰይመዋል ። ፍርዱ በሚቀጥለው ሳምንት ሊሰጥ ነው!» አለች ።

«እረ ፣ እርግጠኛ ነሽ?» በማለት ኒኮላይ ከሌላኛው ክፍል ድምፁን ከፍ አድርጎ በመናገር ጠየቀ ።

ይኸን የመሰለ ጉልህ የጩኸት ድምፅ እንዲያሰማ ያደረገው ፍርሃት ይሁን ደስታ ለይታ ለማወቅ እናት ኒኮላይ ወደሚገኝበት ክፍል ፈጥና ሄደች ። ሉድሚላም ተከትላት ሄደች ። እንዲህም አለች ፡ —

«አዎን እርግጠኛ ነኝ ። ፍርዱ ቀደም ሲል ተፈርዶ ያበቃ መሆኑን ከፍርድ ቤት አካባቢ ያሉት ያሰማሉ» በማለት የምጸት አነጋገር በሚታይበት ሁኔታ ጥልቀት ባለው ድምፅ ተናገረች ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ ፡ —

«እህ ፣ ታዲያ ምን ይመስላችኋል? ባለሥልጣኖች ጠላቶቼን እጅግ ቸልተኛ በሆነ ሁኔታ ይመለከቱብኛል ብሎ መንግሥት በመፍራቱ ምክንያት ይሆን? መንግሥት አገልጋዩ የሆኑ አሽከሮቹን አስተሳሰብ ለማዛባት ይኸንን ያህል ጊዜ እና ጉልበት ካባከነ በኋላ ፣ እነዚህ አገልጋይ አሽከሮቹ ለጥ-ፀጥ የማይሉለት ደህና ሰዎች ሊሆኑም ይችላሉ ። አይደለም እንዴ?» አለች ።

ሶፋው ወንበር ላይ ተቀምጣ ኮሳሳ የሆኑ ጉንጮቿን በእጆቿ ታሻሽ ጀመር ። ከዐይኖቿ የመናቅ አስተያየት ፣ ከጠቅላላ ሁኔታዋ ደግሞ ቁጣ እና ተናዳ



ጅነት ይታይባታል ። ኒኮላይ ከብስጭቷ ሊያበርዳት በመጣር ፡ —

«ሉድሚላ ፣ እንደው ዝም ብለሽ ጉልበትሽን አታባክኚ ። እነርሱ እንደሆን እንደማያደምጡሽ ታውቂያለሽ» አላት ።

እናት ሉድሚላ የምትናገረውን ታደምጥ ነበር ። ይሁን እንጂ ምን እንደምትል ልትገነዘብ አልቻለችም ። በአዕምሮዋ ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ይንገዋለል የነበረው ሃሣቧ ፡ —

«ፍርዳቸውን የሚቀበሉት በመጪው ሳምንት ነው!» የሚለው ሃሣቧ ነበር ።

አንድ ምህረት-የለሽ የሆነ ኢ-ሰብአዊ ኃይል የመምጫ ጊዜው የተቃረበ መስሎ ድንገት ተሰማት ።

## 23

እናት የሚቀጥሉትን አንድ-ሁለት ቀናት በጭንቀት እና ሀዘን በተመላበት ጉጉት አሳለፈች ። በሦስተኛው ቀን ላይ ሳሻ መጣች ።

«ሁሉም ነገር ዝግጁ ነው ። ዛሬ ከቀኑ በሰባት ሰዓት ላይ ጉዳዩ ይከናወናል» አለችው ሳሻ ኒኮላይን ።

«እንዲህ ፈጥኖ?» በማለት እየተደነቀ ጠየቃት ።

«ይኸ ለመሆኑ ተፋጥኖአል ማለት ነውን? አሁን የቀረኝ ሪቢን የሚለብሰውን ልብስ እና የሚሸሸግበትንም ቦታ ፈልጎ ማግኘት ነው ። የተቀረውን ጉዳይ ጎቡን አከናውኖአል ። ሪቢን ጥግ ጥጉን በማዕዘን በኩል መሸሽ ይኖርበታል ። ቬሶቭሺኮቭ ካፖርት እና ባርኔጣ ይዞለት ከተገናኘው በኋላ መንገድ መንገዱን እያሳየው ይሄዳሉ ። እኔ ራቅ ካለ ሥፍራ ላይ ባሻገር ሆኜ እና ሌላ የሚለውጠውን ልብስ ይዤለት ከተገናኘሁት በኋላ ልብሱን ለውጦ አብሬው ተሳፍረን እንሄዳለን» አለች ።

«ጥሩ ነው ። ጎቡን የተሰኘው ሰው ግን ማን ነው?» በማለት ኒኮላይ ጠየቃት ። እርሷም ፡ —

«ታውቀዋለህ ። ከሜካኒኮች ጋር የጥናት ክበብ ታካሂድ የነበረው እርሱ ቤት ነበር» አለችው ።

«አ! አስታወስኳቸው! እኛ ጭልፊት የሆኑ ሽማግሌ ናቸው...» አለ ።

«ጡረታ የወጡ ወታደር ናቸው ። አሁን የቆርቆሮ ሠራተኛ ሁነዋል ። መሃይም ናቸው ። ይሁን እንጂ ማናቸውንም ዓይነት አመጽ አይሹም ። ይቃወማሉ ። ፈላስፋነትም ይቃጣቸዋል» አለች ሳሻ በሃሣብ ተውጣ እና በስተመስኮቱ ውጪ-ውጪውን እየተመለከተች ። እናት ይኸንን ስታዳምጥ በአእምሮዋ አንዳች ውሳኔ ይመላለሳል ። ከዚያም ፡ —

«ጎቡን የወንድሙን ልጅ ከእሥር ቤት እንዲጠፋ ለማድረግ ይሻል ። የቭቼንኮን ታስታውሰው የለ? አንተ ትወደው ነበር ። ልታይ-ልታይ ባይ እና ንጹህ ልጅ ነው ትዝ አይልህምን?» አለች እናት ።

ኒኮላይ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ ።

«ማናቸውንም ሁሉ አዘጋጅቶአል» በማለት ሳሻ ንግግሯን ቀጠለች ። ከዚያም ፡ —

«ሙከራችን መሳካቱን እየተጠራጠርኩኝ ነኝ ። ሬቢን እንዲያመልጡ የሚደረጉት እሥረኞች ነፋስ ለመቀበል በሚወጡበት ሰአት ስለሆነ ከገመድ የተሠራውን መሰላል ሲመለከቱ ብዙዎቹ እሥረኞች ሊያመልጡበት በመሻት ይንጠላጠሉበት ይሆናል...» አለች ።

ሳሻ ዐይኖቿን ጨፍና ጭጭ አለች ። እናት ሳሻን ተጠጋቻት ።

«እና እርስ-በእርሳቸው ሲራኮቱ ሁሉም ነገር ሳይሳካ ከሽፎ ይቀራል» አለች ።

ሦስቱም መስኮቱ አጠገብ ቆመዋል ። እናት ከኒኮላይ እና ከሳሻ በስተጀርባ ቆማለች ። ፈጠን ያለ



አነጋገራቸው በአዕምሮዋ ውስጥ የተደባለቁ ሃሣቦችን አሳሰባት ። ከዚያም ድንገት ፡ —

«እኔም እሄዳለሁኝ!» በማለት ተናገረች ።

«ለምን?» አለቻት ሳሻ ።

«የኔ ውድ አይሂዱ ። አንድ ነገር ሊደርስብዎ ይችላል ። አይሂዱ!» በማለት ኒኮላይ መከራት ።

እናት ተመለከተችው ።

«የለም ፤ እሄዳለሁኝ...» በማለት ቁርጥ ሃሣብ ማድረጓን በሚገልጽ እና ለስለስ ባለ ድምፅ ተናገረች ።

ወዲያው ዐይን-ለዐይን ተያዩ ።

«ይገባኛል» አለች ሳሻ ትከሻዋን እርግፍ-እርግፍ እያደረገች ። ከዚያም ወደ እናት ዘንድ ዞር ብላ እጅዋን ያዝ አደረጋት ። ከዚያም ፡ —

«ነገር ግን አንዳችም ተስፋ ማድረግ እንደሌለብዎ ማወቅ አለብዎት» አለች የእናትን ልብ በነካ ለስላሳ አነጋገር ። እናትም በሚንቀጠቀጥ እጅዋ ሳሻን ወደእርሷ ሳብ እያደረገቻት ፡ —

«የኔ ውድ ፤ ይኸንን አውቃለሁኝ ። ግን ከአንቺ ጋር አብረሽ ውሰጂኝ ። አላስቸግርሽም! መሄድ አለብኝ! ይኸንን ማድረግ የሚቻል — ከእሥር ቤት ማምለጥ የሚቻል — ነው ብዬ አላምንም!» አለቻት ።

«እንግዲህ ከእኛ ጋር መሄዳቸው ነው» በማለት ሳሻ ለኒኮላይ ነገረችው ።

«አንቺ እንዳልሽ ይሁን» አለ ኒኮላይ ጭንቅላቱን ወደመሬት ቀለስ እያደረገ ።

«ግን ከእርስዎ ጋር አንድ ላይ መታየት የለብንም ። እርስዎ በአትክልቱ ሥፍራ ዳርቻ ባለው ገላጣ ቦታ በኩል አድርገው ይሂዱ ። ከዚያ ሁነው የእሥር ቤቱን ግድግዳ መመልከት ይችላሉ ። ቢጠየቁ ግን ምን ሊሉ ነው?» አለቻት ሳሻ እናትን ።

«አንድ የምለውን ነገር አስቤ አዘጋጃለሁኝ!» በማለት በጉጉት ሁኔታ እናት ተናገረች ።

«የእሥር ቤቱ ዘበኞች የሚያውቁዎት መሆኑን እንዳይዘነጉ! እና እዚያ እርስዎ የሚሄዱበት ቦታ ቢያዩዎት...» አለቻት ሳሻ ።

«ግዴለም ፤ አያዩኝም!» አለች እናት ።

ለጥቂት ጊዜያት ልቧ ውስጥ ይመላለስ በነበረው ተስፋ ተመልታ እናት በደስታ ተዋጠች ። አሁን የልቧ ተስፋ እንደገና በአዲስ ሁኔታ ተነሳሳባት ።

«እርሱም አብሮ ያመልጥ ይሆናል!» እያለች ታስብ ጀመር ።

ከአንድ ሰአት በኋላ እሥር ቤቱ አጠገብ ወደ ሚገኘው ባዶ ቦታ ሄደች ። ኃይለኛ ነፋስ ይነፍሳል ። ልብሷን ያውለበልበዋል ። ቀዝቃዛውን መሬት ያፏጭበታል ። በአጠገባቸው የምታልፍባቸውን በአትክልቱ ሥፍራ ያሉትን ውልቅልቅ አጥሮች ያወዛውዛቸዋል ። የነፋሱ ኃይለኛነት እናትን ወደእሥር ቤቱ ፈጠን-ፈጠን እያለች እንድትጓዝ ይገፋፉታል ። ከእሥር ቤቱ ሜዳ ላይ የሰዎችን የጩኸት ድምፅ ነፋሱ እየተቀበለ ወደሰማይ አሻቅቦ በማውጣት የሚያሰማ ሲሆን ፤ ፈጠን-ፈጠን እያሉ የሚጓዙት ደመናዎች ባሻገራቸው ያለውን ሰማያዊ ሰማይ ይቃኛሉ ።

ከእናት በስተኋላ የአትክልቱ ሥፍራ የሚገኝ ሲሆን ከበስተፊቷ ደግሞ መካነ-መቃብሩ ይገኛል ። አንድ እሥር እርምጃ ያህል ርቆ በስተቀኝ በኩል ደግሞ እሥር ቤቱ ይገኛል ። መካነ መቃብሩ አጠገብ አንድ በፈረስ የተቀመጠ ወታደር ይገኛል ። ሌላው ወታደር ደግሞ አጠገቡ ቆሞ መሬቱን በእግሩ እየደቃ ይጯጯሃል ። ይስቃል ። ያፏጫል ። እሥር ቤቱ አጠገብ ሌላ ማንም ሰው የለም ።

እነዚህን ወታደሮች በአጥሩ በኩል ተጠግታ ካለፈቻቸው በኋላ ወደ ኋላዋ እና ወደ ቀኟ ዞር-ዞር እያለች በጥንቃቄ እየተመለከተች ወደፊት ተጓዘች ።



ድንገት ጉልበቷን ብርክ ያዛት ። የረገጠችው ቀዝቃዛ መሬት እግሯን እንደበረዶ ያቀዘቀዘው መስሎአት ቅዝቃዜው ብዙ ተሰማት ። መብራት ሠራተኞች ለሥራ ተጣድፈው ከወዲያ-ወዲህ እንደሚዋከቡ ሁሉ ፤ አንድ የመብራት ሠራተኛ በትከሻው መሰላል አንግቦ ሲጣደፍ ድንገት ተመለከተች ። በፍርሃት ዐይኖቿን እያርገበገበች እናት ወታደሮቹን ትመለከት ጀመር ። ፈረሱ ዙርያቸውን እየዞራቸው ወታደሮቹ አንድ ቦታ ቆመዋል ። መሰላል የያዘውን ሰው ተመለከተች ። ግድግዳው ላይ ባስደገፈው መሰላል ተዝናንቶ መወጣጣት ጀምሮአል ። ግድግዳው ጫፍ ላይ ወጥቶ ከደረሰ በኋላ እጁን አወዛወዘ ። ከዚያም ቶሎ-ቶሎ ፈጥኖ በመሰላሉ ከወረደ በኋላ በስተጥግ በኩል አድርጎ በመሄድ ከዐይን ተሠወረ ። የእናት ልብ ዶጭ-ዶጭ ይላል ። የጊዜው ሰኮንዶች እየዘገዩ ያልፋሉ ። መሰላሉ ደብዛዛ ቀለም ካለው ከጥቁሩ የእሥር ቤት ግድግዳ በኩል ምንም ያህል አይታይም ። ድንገት ከእሥር ቤቱ ግድግዳ ጫፍ ላይ የአንድ ሰው ጠቆር ያለ ጭንቅላት ብቅ አለ ። ከዚያም ግድግዳውን ከፍ ብሎ የሚወጣው ሰውነቱ መታየት ጀመረ ። አሁንም እንደገና መናኛ የሆነ ባርኔጣ ራሱ ላይ የደፋ ሰው ከግድግዳው ጫፍ ብቅ አለ ። ጠቆር ያለ ኳስ ብጤ መሬቱ ላይ ከብለል ካለ በኋላ በስተጥግ በኩል ተሽሎክሉኮ ተሠወረ ። ሚኻኢሎ ቀጥ ብሎ ቆመ ። ዙርያውን ተመለከተ ። በመደነቅ ራሱን ነቀነቀ...

«እሩጥ! እሩጥ!» በማለት እናት እግሮቿን መሬቱ ላይ እየደቃች ቀስ ብላ ተናገረች ።

ጆሮዋ ውስጥ አንዳች የሆነ ነገር ይደውል ነበር ። ከፍተኛ የጩኸት ድምፆች ሰማች ። እንደገና ሌላ ሦስተኛ ሰው ግድግዳው ጫፍ ላይ ብቅ አለ ። እናት ደረቷን ደገፍ አድርጋ ይዛ ትንፋሿ ቁርጥ-

ቁርጥ እያለ ትመለከታለች ። አንድ ደም-የለሽ የሆነ
ፀጉረ-ነጭ ወጣት ሰው ብቅ አለ ። ይሁን እንጂ ወዲ
ያውኑ ዱብ ብሎ ወርዶ ከዐይን ተሠወረ ። ሁካታው
ይበልጥ እየተፋፋመ ይሰማ ጀመር ። የሁካታውን ድም
ፅ እየሩ ወደሰማይ እያሻቀበ እያወጣው እንደሰመ
መን ያሰማዋል ። ሚኻኢሎ ግድግዳውን አልፎ ሄደ ።
እሥር ቤቱን እና የከተማውን ቤቶች በሚያገናኘው
ባዶ ቦታ አለፈ ። ፈጠን ብሎ ቢራመድ እና ጭንቅ
ላቱንም ወደላይ ከፍ ማድረጉን ቢተው እንዴት
መልካም ነበር! እንዴ የተመለከተው ሰው መልኩን
ሊዘነጋው አይችልም ።

«ፈጠን በል! ፈጠን በል!» በማለት እናት ቀስ
ብላ ተናገረች ።

ከእሥር ቤቱ ሌላኛ አቅጣጫ አንድ ነገር ኳ
ብሎ ወደቀ ። መስተዋት እንክትክት ብሎ ሲሰበር ድም
ፁ ይሰማታል ። ከወታደሮቹ መካከል አንዱ የፈረሱን
ልጓም እየጎተተ መሬቱ ላይ እግሩን ቸክሎ ቆሞ
አል ። ሌላኛው ወታደር እጁን ወደ አፉ አስጠግቶ
ወደ እሥር ቤቱ በጩኸት ድምፅ ይናገራል ። ተናግሮ
ከጨረሰ በኋላ ከበስተ እሥር ቤቱ በኩል የሚሰማ
ውን የንግግር መልስ ለማዳመጥ ጆሮውን ከንፋሱ ዞ
ር አድርጎ በመቀሥር ያዳምጣል ።

እናት በጥንቃቄ ወዲያ እና ወዲህ እየተመለከ
ተች አንድ ቦታ ሳትነቃነቅ ቆማለች ። ዐይኖቿ ማና
ቸውንም ድርጊቶች የሚያስተውሉ ሲሆኑ ከምታየው
መካከል አንዱንም ማመን ግን ተስኗታል ። ውስብስ
ብ የሆነ እና አደጋ የሚያስከትል ጉዳይ ነው ብላ
ገምታው የነበረ ድርጊት እንዲህ በቀላሉ እና ፈጣን
በሆነ ሁኔታ ሲከናወን በማየቷ እና የድርጊቱ በፍጥ
ነት መከናወንም አዕምሮዋን አደነዘዘው ። ሪቢን ከዐ
ይኗ ተሠወረ ። አንድ ረዥም ካፖርት የለበሰ ረዥም



ሰው በጎዳናው ወደታች የሚጓዝ ሲሆን አንዲት ሴት
ደግሞ ከፊት-ፊቱ ቀድማ ትገሠግሣለች ። ሦስት የእ
ሥር ቤት ዘበኞች በቀኝ እጃቻቸው ተያይዘው እና
ተጠጋግተው በእሥር ቤቱ ጥግ ይገሠግሣሉ ። ከወታ
ደሮች መካከል አንዱ ሊገናኛቸው ፈጥኖ ሄደ ። ሌላ
ኛው ወታደር ፈረሱ ላይ ለመውጣት እመር እመ
ር እያለ የሚዘል ሲሆን ፈረሱም በበኩሉ አሻፈ
ረኝ ብሎ ወደላይ የሚዘል በመሆኑ ሁሉም ነገር
አብሮት እመር እያለ ከፈረሱ ጋር የሚዘል ይመስ
ላል ። በተደናገረ ድምፅ ፉጨት ተደጋግሞ ይሰማል ።
ተስፋ የመቁረጥ ሁኔታ የሚሰማበት የፉጨት ድምፅ
አደጋ ሊያስከትል የሚችል ሁኔታ መኖሩን እንድትገ
ነዘብ አደረጋት ። እየተንቀጠቀጠች እና ዘበኞቹን በጥን
ቃቄ እያስተዋለች በመካነ መቃብሩ በኩል አድርጋ
ተጓዘች ። የእሥር ቤቱ ዘበኞች እና ወታደሮቹ ወደ
እሥር ቤቱ ሌላ ማዕዘን ሄደዋል ። ካፖርቱን ያልቆ
ለፈ አንድ ሌላ ሰው እነርሱን ተከትሎ ይሄዳል ።
የእሥር ቤቱ ረዳት ኃላፊ መሆኑን ለይታ አወቀ
ችው ። ቦታው ላይ ፖሊሶች መጡ ። ከዚያም የተመል
ካች ሰዎች ብዛት እየጨመረ ይበራከት ጀመር ።

ተደስቶ የሚፈነድቅ ይመስል የጩኸት እና የፉ
ጨት ፡ ድምፆችን በእናት ጆሮ ሽው እያደረገ ነፋሱ
በኃይል በመንፈስ ዳንኪራ ይረግጣል... ሁከቱ አስደስ
ቷታል ። እርምጃዎቿን ከእግሯ ፈጠን-ፈጠን እያደረ
ገች ትነጥቅ ጀመር ።

«እርሱም ልክ እንደእነርሱ በቀላሉ ሊያደርገው
ይችል ነበር!» በማለት በሃሣቧ አሰላሰለች ። ድንገት
ከአንድ ጥግ በኩል ሁለት ፖሊሶች እየገሰገሱ ወደ
እርሷ ዘንድ መጡ ። ከመካከላቸው አንደኛው ትን
ፋሹ ቁርጥ-ቁርጥ እያለ ፡ —

«ቁሚ!» በማለት ጮኸ ። ከዚያም ፡ —

37-596

«አንድ ጺም ያለው ሰውዬ አላየሽም?» አላት ። ወደ አትክልቱ በእጅዋ እያመለከተች ባለመረበሽ ሁኔታ እንደው ዝግ ባለ አነጋገር ፡ —

«ወደዚያ እየሮጠ ሄደ ። ምነው ፤ ምንድነው?» በማለት ተናገረች ። ከዚያም አንደኛው ፖሊስ ፡ —

«የጎሮቨ! ፊሽካህን ንፋ!» በማለት ተናገረ ።

እናት ወደ ቤቷ ሄደች ። አንዳች ምክንያት አሳዝኖአታል ። የመቆጨት እና የመጸጸት ስሜት አሳድሮባታል ። ገላጣውን ቦታ ካለፈች በኋላ ጎዳናው ላይ ደርሳ ስትጓዝ አንድ በፈረሶች የሚሳብ ሠረገላ አልፎአት ሄደ ። ሠረገላው ውስጥ ተመለከተች ። ቀለሙ-ነጭ ሪዝ ያለው ፤ የገረጣ እና የደከመ ወጣት ሰው ተቀምጦ ተመለከተች ። እርሱም ተመለከታት ። የጎድን የተቀመጠ በመሆኑ ከግራ ትከሻው ይልቅ የቀኝ ትከሻው ጉብ ብሎ ኮርቶአል ።

ኒኮላይ በደስታ ተውጦ ተቀበላት ።

«እሺ ፤ እንዴት ነበር?» አላት ።

«ያለ አንዳች ችግር ተሳካ...» አለችው ።

የድርጊቱን ዝርዝር ለማስታወስ እየጣረች እንዴት በመሰለ ሁኔታ እንዳመለጡ አንድም ሳታስቀር ዘርዝራ አወራችለት ። ይሁን እንጂ ታወራለት የነበረው የድርጊቱን ዕውነት መሆን እንደምትጠራጠር እና ከሌላ ሰው እንደሰማችው ወሬ አድርጋ ነበር ።

«ዕድል ከእኛ ጋር ነች» አለ ኒኮላይ እጆቹን እያሻሸ ።

«በእርስዎ ላይ አንድ ጉዳት ይደርስብዎታል ብዬ እንዴት ሠግቼ ነበር መሰለዎ! ይልቅ እኔ የምልዎት ፤ አዩ ኒሎቭና ፤ የጓደኝነት ምክሬን ይስሙኝ ። ስለ ፍርዱ ሁኔታ ምንም አያስቡ አይጨነቁ ። የፍርዱ ቀን መቃረብ ፓቬልም ቶሎ ነፃ እንዲሆን ጊዜውን የሚያቃርብለት ነው ። ምናልባትም ወደ ግዞት ቦታ በሚጓዝበት



ጊዜ ጠፍቶ ሊያመልጥ ይችል ይሆናል ። ፍርዱን በሚመለከተው ረገድ ከሆነ ግን ፤ ሁኔታው እንደዚህ ነው...»

የፍርድ አፈጻጸሙን ሥርአት ማስረዳት ጀመረ ። ይኸንን ማብራሪያውን ሲያሰማ ምንም እንኳን ሊያበረታታት ቢጥርም ፤ እርሱ ራሱም የሠጋበት አንድ ጉዳይ መኖሩን ከሁኔታው ተገነዘበች ።

«የፍርድ ቤቱን ዳኞች መናገር የማይገባኝን ጉዳይ እናገራለሁ መስሎህ ሠግተህ ነውን?» በማለት ድንገት ጠየቀችው ። ቀጠል አድርጋም ፡ —

«ወይንስ ደግሞ አንዳች ነገር እንዲያደርጉልኝ ዳኞቹን እጠይቅ መስሎህ ነው?» አለችው ።

ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ በመነሳት ቅይም ባለ ሁኔታ ጣቱን ወደ እርሷ እያመለከተ ፡ —

«ምን ማለትዎ ነው! እኔ ይኸንን ማለቴ አይደለም!» አላት ።

«እርግጥ ነው ። የምክደው ነገር አይደለም ። ፍርሀት-ፍርሀት የሚያሰኘኝ ምን እንደሆነ መገንዘብ አልቻልኩም!...» አለች ። መናገሯን አቆመች ። ዐይኖቿ ክፍሉን ከወዲያ ወዲህ ይቃኙ ጀመር ።

«አንዳንድ ጊዜ ፓቬልን በማመናጨቅ ይናገሩት ይሆናል እያልኩኝ እሠጋለሁኝ ፡ — ‘አንተ ገበሬ! አይ አንተ!’ ይሉት ይሆናል ። ‘አንተ የገበሬ ልጅ! ለመሆኑ ምን ልሁን ባይ ነህ?’ ይሉት ይሆናል ። ፓቬል ኩሩ ሰው ነው ። ተገቢውን መልስ ይመልስላቸው ይሆናል ። ወይንም አንድሬይ ጠንከር ያለ አነጋገር ያሰማ ይሆናል ። ሌሎቹም ቢሆኑ ቁጡዎች ናቸው ። እና ይኸንን መሳይ አባባል ሲናገሩት መታገስ አቅቶት መልስ ቢመልስላቸው እና ፍርዱን አጥፈው ሌላ ፍርድ ቢፈርዱበትስ? ዳግመኛ እርሱን ለማየት የማንችል ብንሆንስ?» አለች ።

ኒኮላይ አንዳችም መልስ ሳይመልስላት ጢሙን እያሻሸ ተኮሳተሮአል ።

«እንዲህ ያለውን ሃሣብ ከአዕምሮዬ ማስወገድ አልቻልኩኝም» በማለት አለስልሳ ተናገረች ። ቀጠል አድርጋም ፡ —

«ለዚህ ነው የፍርዱ ቀን በጣም በጣም አስጊ የሆነብኝ! እንዴ ማናቸውንም ነገር ዳኞቹ መመርመር እና ማመዛዘን ከጀመሩ በኋላ ግዴለም! ለዚህ ነው የሚያስፈራኝ! እና የሚያስፈራኝ የሚፈረደው ቅጣት ሳይሆን የፍርድ መስጫው ጊዜ ነው ። እንዴት አድርጌ ልገልጸው እንደምችል አላውቅም...» አለች ።

ኒኮላይ አባባሏን ያልተረዳላት መስሎ ተሰምቷታል ። ይኽ ሁኔታም የእርሷ ፍርሃት ምን እንደሆነ በቃላት አማካይነት አብራርታ ለመግለጽ እንዳትችል ይበልጥ መሰናክል ሆነባት ።

24

ይኽ ሥጋቷ ልቧ ውስጥ ቤቱን ሠርቶ ካሁን ካሁን ያንቃት እየመሰላት ትጨነቅ ጀመር ። የፍርዱ ውሳኔ በሚሰጥበት ዕለት ወደ ፍርድ ቤት ስታመራ ጭንቅላቷን ማንቀሳቀስም ሆነ መራመድ የምትችለው የግዷን ነበር ።

በፋብሪካው መኖርያ ሠፈር የሚኖሩ እና እርሷንም የሚያውቋት እንዴት ነዎት በማለት ሰላምታ አቀረቡላት ። ፊቶቻቸው አኩርፎ የተሰበሰቡትን ሰዎች ጭንቅላቷን ብቻ እንደምን ናችሁ በሚል ሁኔታ እያወዛወዘች ታልፍ ጀመር ። ፍርድ ቤቱ ውስጥ እና ኮሪዶር ላይ የታሠሩት ሰዎች ቤተሰቦች ዝቅተኛ በሆነ ድምፅ አነጋገሯት ። ምን እንደሚሉ ልትረዳቸው አልቻለችም ። ሁሉም ተመሳሳይ የሀዘን ማቅ ተከናንቧል ። እናት ይኽንን ተገንዝባለች ። ሁኔታው ይበልጡኑ አሳዘናት ።

«ነይ እዚህ አጠገቤ ቁጭ በይ!» አላት ሲዞቭ ከተቀመጠበት አግዳሚ ወንበር ላይ ፎቀቅ እያለላት ።

ትሁትነት ባልተለየው ሁኔታ ተቀመጠች ። ልብሷን አስተካክላ ግራ-ቀኙን ቃኘት አደረገች ። አረንጓዴ እና ቀይ ነቁጦች አግዳሚ ጥብጣቦች እና ቀጫጭን ቢጫ ክሮች ዐይኗ ላይ ብዥ-ብዥ ይሉባታል ።

«የእኛን ግሪሻ እዚህ ጉድ ውስጥ የጨመረው የእርስዎ ልጅ ነው!» በማለት አጠገቧ የተቀመጠች አንዲት ሴት ተናገረች ።

«ናታልያ ፤ ይኽንን ዓይነቱን ንግግርሽን አቁሚ!» በማለት ሲዞቭ ኮስተር ብሎ ተናገረ ።

እናት ሴትዮዋን ተመለከተቻት ። የሳሞይሎቭ እናት ነች ። ፀጉረ-መላጣ የሆነ እና የፊት አወራረዱ ቀጠን ያለ ፤ ግርማ-ሞገስ ያለው እና ቀላ ያለ ጢም ያጨመው ባሏ አጠገቧ ተቀምጦአል ። ወደፊት-ለፊት ሲመለከት ዐይኖቹን ጠበብ አድርጎ ዘጋ እንደማድረግ ያደረገ ሲሆን በሥጋት ላይ የሚገኝ በመሆኑም ጢሙ ይንቀጠቀጣል ።

በበረዶ በተሸፈኑት እና ከፍ ብለው በሚገኙት መስኮቶች በኩል ደብዘዝ ያለ ብርሃን ወደ ክፍሉ ውስጥ ዘልቆ ገብቶአል ። በመስኮቶቹ መካከል የቄሳሩ ፎቶግራፍ በሚያንጸባርቅ የወርቅ ፍሬም ተሰቅሎአል ። ቀይ በሆኑት የመስኮቶች መጋረጃዎች ፍሬሙ ተሸፍኗል ። ከፎቶግራፉ ፊት ለፊት አረንጓዴ ጨርቅ የለበሰ እና ከክፍሉ ጻር እስከጻር ሊደርስ ምንም ያልቀረው ጠረጴዛ ተዘርግቶአል ። በስተቀኝ በኩል የሚገኘውን ግድግዳ ተደግፈው ሁለት የእንጨት አግዳሚ ወንበሮች ተቀምጠዋል ። በስተግራ በኩል ደግሞ ሁለት ቡናማ ቀለም ያላቸው ወንበሮች

ተቀምጠዋል ። አረንጓዴ ክሳድ እና ወርቅማ ቁልፎች
ያሉት የደንብ ልብስ የለበሱ ሥነ-ሥርአት አስከባ
ሪዎች ከወዲያ-ወዲህ ይሯሯጣሉ ። በክፍሉ ውስጥ
ያለው አየር በሹክሹክታ እና በመድኃኒት ሽታ ታውዶ
አል ። ይኸ ሁሉ — ቀለማቶች እና ነጸብራቆች ፤ ድም
ፆች እና ሽታዎች — ስትተነፍስ ባዶ በሆነ ፍርሀት
ውጦአት ዐይኖቿን እና ጆሮዋን ጎዳቸው ። ሰውነቷ
ውስጥም ሰተት ብሎ ገባ ።

ድንገት አንድ ሰው ጎላ ባለ ድምፅ ተናገረ ። እ
ናት በርገግ አለች ። ሰው ሁሉ ከተቀመጠበት ሲነሳ
እናትም የሲዞቭን እጅ ጨበጥ አድርጋ ተነሳች ።

በስተግራ በኩል ከፍ ብሎ የሚገኘው በር ተከ
ፈተ ። አንድ መነጽር ያደረገ ሽማግሌ ሰው በዝግታ
እየተንተተ ገቡ ። ግራጫ ቀለም ባላቸው ጉንጮቻ
ቸው ግራና ቀኝ አነስ-አነስ ያሉ ነጫጭ ጢሞች
በቀጭኑ መሥመር አበጅተው በቅለውባቸዋል ። በንጹህ
የተላጨው የላይኛው ከንፈራቸው ጥርስ-የለሽ የሆነ
ድዳቸው ላይ ሙጭጭ ብሎ ተጣብቆአል ። አገጫቸው
እና መንጋጨላዎቻቸው ክሳዶ-ትልቅ በሆነ የዳኛ ልብ
ሳቸው ተሸፍነዋል ። ይኸ ሁኔታም ሰውዬውን አንገት-
የለሽ ሰው አስመስሎአቸዋል ። አንድ ቁመተ-ረዥም እ
ና እንደሸክላ የቀላ ፊተ-ድቡልቡል ወጣት ሰው ሽማ
ግሌውን ደግፎአቸዋል ። ከእነርሱ በኋላ በወርቀ-ዘቦ
ጥብጣብ የተከፈፈ የደንብ ልብስ የለበሱ ሦስት ሰ
ዎች ይከተሏቸዋል ። ሌሎች ሦስት ሰዎች ደግሞ የዘወ
ትር ልብስ ለብሰው አብረዋቸው ይገኛሉ ።

ረዥሙ ጠረጴዛ ላይ ለመቀመጥ ብዙ ጊዜ ፈጀ
ባቸው ። ይኸ ከተከናወነ በኋላ ግን ፤ የደንብ ልብሱ ቁል
ፎች የተፈቱ ፤ ጢም ያላጨመ እና ፊቱ የልግመኛ ሰ
ው ፊት የሚመስል ከተቀመጡት መካከል አንዱ
ወደ ሽማግሌው ጠጋ ብሎ ንግግሩ በማይሰማ ሁኔታ



ከንፈሮቹ እየተንቃነቁ ለሽማግሌው ያንሾካሹክላቸዋል ።
ሽማግሌው የሰውየውን ሹክሹክታ በሚያስገርም ሁኔ
ታ እንደ አጠና እንጨት ድርቅ ብለው ቀጥ በማ
ለት ያዳምጣሉ ። በመነጽራቸው ውስጥ የሚንከባለሉ
ትን ሁለት ቀለመ-ቢስ ነቁጦች ዐይኖቻቸውን እና
ት ታስተውላለች ።

በጠረጴዛው መጨረሻ በሚገኝ የመጻፍያ ጠረጴዛ
ላይ የተከመሩትን ዶሴዎች እያገላበጠ እና ጉሮሮው
ንም እ-ኸ-ኸ በማለት እየጠራረገ አንድ ረዥም
እና ፀጉረ-መላጣ የሆነ ትልቅ ሰው ቆሞአል ።

ሽማግሌው ወደፊት ጎንበስ እንደማለት ብለው
መናገር ጀመሩ ። ከተናገሯቸው ንግግሮች መካከል የመጀ
መርያዎቹ ቃላት ግልጽ በሆነ ሁኔታ የተሰሙ ሲሆ
ኑ የተቀሩት ግን ዝብርቅርቅ ያሉ እና መያዣ-መጨ
በጫቸው የጠፉ ዐረፍተ ነገሮች ናቸው ።

«ችሎት ማስቻሉ ተጀምሮአል… ሰዎቹ ይቅረቡ…»
አሉ ።

«ያውልሽ» አለ ሲዞቭ ከተቀመጠበት ብደግ ሲል
እናትን ጎንተል እያደረገ ።

ከማገጃ ብረቶቹ በስተጀርባ ያለው በር ተከፈተ ።
ከአፎቱ የተመዘዘ ሰይፍ ትከሻው ላይ ያጋደመውን
ወታደር ተከትለው ፓቬል ፤ አንድሬይ ፤ ማዚን ፤ የጉሴቭ
ሁለቱ ወንድማማቾች ፤ ሳሞይሎቭ ፤ ቡኪን ፤ ሶሞቭ እና
እናት ስማቸውን የማታውቃቸው ሌሎች አምስት ወጣ
ቶች ወደውስጥ ገቡ ። ፓቬል ፍቅር በተመላበት ሁኔ
ታ ፈገግ አለ ። አንድሬይ እየሳቀ እንደምን አላችሁ
በሚል ሁኔታ ጭንቅላቱን ያወዛውዛል ። እንደዚያም
ሆኖ ፤ ፈገግታቸው ፤ የደስ-ደስ ያለው ፊታቸው እና
እረማመዳቸው ጭንቅ-ጥብብ ብሎት የነበረውን የፍርድ
ቤቱን ሁኔታ ብሩኅ መልክ ሰጠው ። የደንብ ልብስ
የለበሱት ሰዎች ላይ የሚያብረቀርቀው የወርቅ ጥልፍ

ደበዘዘ ። እሥረኞቹ አብረው ይዘው በመጡት የልብ ልብ ስሜት እና ኃይል የእናት መንፈስ የመጠናከር ኃይል አገኙ ። እስከ አሁን በሀዘን ተኮራምተው ከነበሩት እና በስተኋላ ከተቀመጡት ሰዎች ዘንድ መለስተኛ ጉርምርምታ ይሰማ ጀመር ።

«ፍርሃት የሚባል የለባቸው!»በማለት ሲዞቭ ቀስ ብሎ ተናገረ ። በስተቀኝ በኩል የተቀመጠችው የሳሞይሎቭ እናት በልቅሶ ትንሰቀሰቃለች ።

«ፀጥታ!» በማለት ኮስታራ ድምፅ ተሰማ ።

«አስጠንቅቄአችኋለሁኝ...» አሉ ሽማግሌው ሰው ።

ፓቬል እና አንድሬይ መጀመርያው አግዳሚ ወንበር ላይ ጎን-ለጎን ተቀምጠዋል ። አብረዋቸውም ማዚን ፤ ሳሞይሎቭ ፤ እና የጉሴቭ ወንድማማቾች ተቀምጠዋል ። አንድሬይ ጢሙን ተላጭቶአል ። ሪዙ ግን እንዳለ ነው ። ሪዙ ግራና ቀኝ ወደታች የወረደ በመሆኑ ክብ ፊቱን ልክ የድመት ፊት አስመስሎታል ። ከሁኔታው አዲስ ነገር ይታይበታል — አፉ ሾል ያለ እና ለነገር ያሞጠሞጠ ይመስላል ። ዐይኖቹ ጠቆር ብለዋል ። በማዚን የላይኛው ከንፈር ላይ ጥቁር መሥመር ተጋድሞበታል ። ፊቱም ተድቦልቡሎአል ። ሳሞይሎቭ ያው እንደቀድሞው ፀጉረ-ድምድም ነው ። ኢቫን ጉሴቭም ያው እንደቀድሞው ፈገግ እያለ ይስቃል ።

«ወይ የኔ ፌዎዶር! የኔ ፌዎዶር!» በማለት ሲዞቭ ራሱን አቀርቅሮ የትካዜ ድምፅ አሰማ ።

ሽማግሌው ዳኛ እሥረኞቹን ሳይመለከቱ የአንገታቸው ክሳዶች አቅፈው የያዙዋቸውን ጭንቅላታቸውን ቀጥ አድርገው ባለመነቃነቅ ገትረው በአቀራረባቸው ግልጽነት የጎደላቸው ጥያቄዎችን ለእሥረኞቹ ሲያቀርቡ እናት ታደምጣለች ። ልጅዋ የሚመልሳቸውን ረጋ ያሉ እና እጥር-ምጥን ያሉ መልሶች እያዳመጠች የመሀል ዳኛው እና ረዳቶቻቸውም በልጅዋ ላይ



አይጨክኑበት ይሆናል ብላ ገመተች ። የፍርዱ ውጤት ምን ዓይነት ይሆን ብላ ለመገመት በረኸሙ ጠረጴዛ ላይ የተኮለኮሉትን ዳኞች ፊት ፊታቸውን ትክ ብላ እያስተዋለች ስታጠና ልቧ በተስፋ ይመላ ጀመር ።

ጉንጨ-ወፍራሙ ባለሥልጣን ማራኪ ባልሆነ ድምፅ አንድ ዶኩሜንት ሲያነብ ሁኔታው እጅግ አሰልቺ ከመሆኑ የተነሳ በክፍሉ ውስጥ ያለው ሰው ሁሉ በእግር ብረት የታሠረ ይመስል ተሰላችቶ ነበር ። በፍርድ ላይ ካሉት እሥረኞች ጋር አራት ጠበቆች ዝግ ባለ እና መንፈስ በሚቀሰቅስ ሁኔታ ንግግር ተለዋወጡ ። እንቅስቃሴያቸው ፈጣን እና ጠንካራ በመሆኑ ሁኔታቸው የትላልቅ ጥቋቁር ወፎችን ሁኔታ አስታወሳት ።

በአንድ በኩል የሚገኘው የሽማግሌው ወንበር እጀታ አንድ ወፍራም የሆነ እና ትናንሽ ዐይኖቹ በሞራ የተሸፈኑ ሰው ሰውነት ተሞልቶአል ። ከሽማግሌው ሌላ ጎን ደግሞ ቀይ ሪዝ ያለው እና ፊቱ የገረጣ ትከሻው ድቡልቡል ያለ ዳኛ ተቀምጦአል ። ድከም ባለው ሁኔታ እጁን ከወንበሩ ጀርባ እንዘፍ አድርጎ የጣለ ከመሆኑም በስተቀር ዐይኖቹን ጨፈን እንደማድረግ አድርጎ በሃሣብ ተውጦአል ። ዐቃቤ ሕጉም የመድከም እና የመሰላቸት ሁኔታ ይታይበታል ። ከዳኞቹ በስተጀርባ አዘውትሮ ጉንጩን የሚያሻሽ ፤ ሰውነተ-ወፍራም እና አካለ ጠንካራ የሆነው የከተማው ከንቲባ ተቀምጦአል ። ከጎኑ ደግሞ ትውልዱ ከመኳንንት ወገን የሆነ ፀጉረ-ሽበቶ እና ጉንጮቹ ቀያይ የሆኑ ፤ ረዢም ጢም ያጤመ ትላልቅ ጉርጥርጥ ዐይኖች ያሉት ሌላ ሰው ተቀምጦአል ። ዘርጣጣ በርጭ ያለው በመሆኑ ምክንያት ቅር እየተሰኘ አሁንም-

አሁንም ኮቱ ከቦርጩ ላይ እያፈተለከበት በኩቱ ሊሸፍነው የሚሻው የቀበሌው ገዢ ይገኛል ።

«እዚህ አሁን በምንገኝበት ቦታ ወንጀለኞችም ሆኑ ዳኞች የሉም ። እዚህ የሚገኙት ምርኮኞች እና ማራኪዎች ናቸው...» በማለት ኀላ ባለ እና ጠንካራ በሆነ ድምፁ ፓቬል ተናገረ ።

ክፍሉ በዝምታ ተዋጠ ። ለተወሰኑ ሰኮንዶች እናት ታደምጥ የነበረው ሌላ ምንም ሳይሆን የብዕር ኮሽኮሽታ እና የልቧን ዶጭ-ዶጭታ ነበር ።

መሀል ዳኛውም ንግግሩን የሚያደምጥ እና ደግሞ ምን ይከተል ይሆን ብሎ የሚጠባበቅ ይመስላል ። ረዳቶቹ ተደናገጡ ። በመጨረሻም መሀል ዳኛው ፡ —

«እህህ! እንድሬይ ናኽድካ!ጥፋተኛ መሆንህን ታምናለህ?» አለው ።

ኣንድሬይ ቀስ ብሎ ከተቀመጠበት ተነሳ ። ትከሻውን ጎበር አድርጎ ሪዙን እያሻሸ ሽማግሌውን በዐይኖቹ ሽፋሽፍት ተኩሮ እያስተዋለ እና ትከሻውን እያወዘወዘ ያው እንደቀድሞው ጣዕመ-ዜማ ባልተለየው አስደሳች ድምፁ ፡ —

«እንዴት ጥፋተኛ ነኝ እላለሁኝ? የገደልኩት ሰው የለም ። በሌብነት አልተያዝኩም ። ሕዝቦችን የሚዘርፍ-የሚቀማ ፤ እርስ-በእርስ የሚያጋድላቸውን የአኗኗር ሁኔታ ብቻ ተቃዋሚ ነኝ» በማለት ተናገረ ።

«መልስ ስትመልስ አታንዛዛ ። ባጭሩ መልስ» አለው መሀል ዳኛው ።

ከበስተኋላ የተቀመጡት ሰዎች ማጉረምረም ጀመሩ ። ጉንጩ ወፍራሙ ሰው በላያቸው ላይ የጠመጠመ ባቸውን ቃላት የሚፈቱ ይመስል ተመልካቾቹ ሰዎች እርስ-በእርስ መንሾኳሾክ እና መቁነጥነጥ ጀመሩ ።

«የሚናገሩትን ትሰሚያለሽን?» አላት ሲዞቭ ።

«ፌዎዶር ማዚን ፤ ቃልህን ስጥ...» አለ ዳኛው ።

ፌዲያ ከተቀመጠበት ፍንጥር ብሎ በመነሳት ቆመ ። ፊቱ ደም መስሎአል ። ዐይኖቹ ብሩኅ ሁነው ያበራሉ ። እጁን በአንዳች ምክንያት ወደኋላው አድርጓል ።

«አልሰጥም» በማለት ግልጥ ባለ አነጋገር መለሰ ።

ሲዞቭ ቀስ ብሎ ወይጉድ በሚል ሁኔታ የመገረም ድምፅ አሰማ ። የእናት ዐይኖች በመደነቅ ብልጥጥ ብለው ተከፈቱ ። ፌዲያ ንግግሩን በመቀጠል ፡ —

«ለእኔ ቆሞ የሚከራከርልኝ ጠበቃ የማልሻ መሆኔን ተናግሬአለሁኝ ። አንዳችም ነገር መናገርም አልሻም ። ይኸ የተሰየመው ፍርድ ሰሚ ሕገ-ወጥ ነው እላለሁኝ! ለመሆኑ እናንተ እነ ማን ናችሁ? በእኛ ላይ ፍርድ እንድታስተላልፉ ሕዝቦች መርጠዋችኋልን? የለም ሕዝቦችስ አልመረጡዋችሁም! እናንተ ያላችሁንም ሥልጣን አምኜ የምቀበል አይደለሁም!» በማለት ተናገረ ።

ተቀመጠ ። ቀይ የሆነ ፊቱ በአንድሬይ ጀርባ ተሸሸገ ።

ወፍራሙ ዳኛ ወደ መሃል ዳኛው አጎንብድዶ በጆሮው አንዳች ነገር ያንሾኳሹክላቸዋል ። የገረጣ መልክ ያለው ዐይኖቹን ብልጥጥ አድርጎ በመክፈት ወደ እሥረኞቹ አተኩሮ እየተመለከተ ከጠረጴዛው ላይ እርሳስ አንስቶ በወረቀት አንዳች ነገር ይጽፍ ጀመር ። የቀበሌው ገዢ ወይ ጥጋብ ፤ ይገርማል እኮ በሚል ሁኔታ ጭንቅላቱን እየወዘወዘ ቦርጩ ጭኑ ላይ ዘርፈጥ ብሎ እንዲቀመጥለት ከእግሮቹ ፈርጠጥ ፈርጠጥ አለ እና ቦርጩን በእጆቹ ሸፈናቸው ። ሽማግሌው ዳኛ ጭንቅላታቸውን ዞር ሳያደርጉ መላ ሰውነታቸውን የገረጣ መልክ ወደአለው ዳኛ ዞር አድርገው ቀስ ባለ አነጋገር ከንፈሮቻቸውን ያነቃንቁ ጀመር ። የገረጣው ዳኛ ጭንቅላቱን ቁልቁል ቀልሶአል ።

የመኳንንት ወገን ተጠሪ የሆነው ሰው ለሕግ-አስከባ
ሪው አንዳች ነገር ነገረው ። አሁንም አገጩን የሚያ
ሻሽው ከንቲባ ንግግሩን ለማዳመጥ ይጥራል ። ከዚያ
ም አሰልቺ በሆነው ድምፃቸው መሀል ዳኛው መና
ገር ቀጠሉ ።

«አየሽ እንዴት እንደመለሰላቸው! ከሁሉም የተ
ሻለ ነው!» በማለት ሲዞቭ ለእናት በጆሮዋ ነገራት ።

እናት ግራ እየገባት ፈገግ አለች ። በመከናወን
ላይ ያለው ነገር ሁሉ ሁላቸውንም ሥቃይ ላይ
ሊጥላቸው በሚችል መንገድ አስጊ ሁኔታን ሊያስ
ከትል የሚችል በመሆኑ አድካሚ እና የማያስፈልግ
ሁኖ ተሰማት ። ይሁን እንጂ ከፓቬል እና ከአንድሬይ
አንደበቶች የወጡት ቃላት በወዝ-አደሮች የሠፈራ
በታ በምትገኘው ጎጆአቸው ውስጥ ሁነው የሚያወ
ሩት እንጂ ዕውነትስ በዚህ በፍርድ ቤት ውስጥ
የተናገሩት በማይመስል ሁኔታ ቃላቶቻቸው ፍርሀት-
አልባ እና ጠንካሮች ቃላት ነበሩ ። ፌዎዶር ስሚቱ
ፈንቅሎት ባሰማው መልስ ልቧ ተቀሰቀሰ ። እዚህ
ፍርድ በታ ላይ አንድ ብርታት ያልተለየው ሁኔታ
እየታየ ሲሆን ከእርሷ ኋላ የተቀመጡትን ሰዎች
እንቅስቃሴ ስታስተውልም ይኸንን ሁኔታ እርሷ ብቻ
የተሰማት አለመሆኗን ገመተች ።

«የምታቀርበው ሃሣብ ምንድነው?» በማለት መሃ
ል ዳኛው ጠየቁ ።

ራሰ-መላጣው ዐቃቤ ሕግ ከተቀመጠበት ተነስቶ
አሀዞች እየጠቀሰ ፈጠን ባለ ሁኔታ ይናገር ጀመር ።
በአነጋገሩ አንዳችም የአስፈሪነት ሁኔታ አይታይበትም ።

የእናት ልቧ በስሜት ተቀስፎ ተይዞአል ። ድምፅ
አሰምቶ እና አካል ገዝቶ በጉልሁ ባይታይም ውስ
ጥ-ውስጡን ሁኔታው የማያምር ነገር በክፍሉ ውስጥ
የሚያንዣብብ መሆኑ ተሰማት ። ይኸ ሁኔታ ከማናቸ
ውም ውጪ ከሚገኘው ነገር ሊገናኙ በማይችሉበት
ሁኔታ ሊጣስ በማይችል ደመና የዳኞቹን አካባቢ
አጎናጽፎት የሚገኝ መስሎ ተሰማት ። ዳኞቹን ተመለ
ከተቻቸው ። ምን እንደሚያስቡ ልትገነዘብ ግን አል
ቻለችም ። እንደገመተችው ፤ በፓቬል እና በፌዎዶር
ንግግር የተበሳጩ አልመሰላትም ። አልሰደቧቸውም ።
ስለዚህም የቀረበላቸውን ጥያቄ ከቁም-ነገር ያልቆጠ
ሩት ፤ መስሎ ተሰማት ። ሁሉንም ነገር ቀደም ሲል
የሚያውቁት ከሆነ እና የሚያስከትለው አንዳች ለው
ጥ የሌለ መሆኑን ከተገነዘቡ ዝንባሌያቸው ፈንገጥ
ያለ ቢሆንም የሚቀርበውን መልስ ለመስማት ይገ
ደዳሉ ።

አሁን አንድ ጃንዳርም ከፊት-ለፊታቸው ቆሞ ጥል
ቀት ባለው ጎርናና ድምፅ የሚከተለውን ተናገረ ፦—

«የአመጺ ዋና ቆስቋሽ ፓቬል ፡ ቭላሶቭ መሆኑ
ታውቆአል ።»

«ናኾድካስ ቢሆን?» በማለት ወፍራሙ ዳኛ ደክሞ
እና ፍዝዝ ብሎ ተናገረ ።

«እርሱም ጭምር...» አለ ጃንዳርሙ ።

ከጠበቆቹ መካከል አንዱ ከተቀመጠበት ብድግ
ብሎ ተነሳ ። ከዚያም ፦ —

«አንድ ቃል እንድናገር ይፈቀድልኛልን?» በማለት
ጠየቀ ።

«የሚቃወም አለ?» በማለት መሀል ዳኛው ጠየቀ ።

ዳኞቹ በሙሉ ጤና ያጡ ይመስላሉ ። በአኳኋናቸው
እና በድምፃቸው ስልችት እና ድክም ያላቸው ይመስ
ላሉ ። ይኸው ድካማቸው እና ስልችት ያላቸው መሆ
ኑም ከፊታቸው ላይ ይነበባል ። የዳኝነት ልብሳቸው ፤
ፍርድ ቤቱ ፤ ጃንዳርሞቹ ፤ ጠበቆቹ ፤ እጂታዎች ያለው
ወንበር ላይ ተቀምጠ ጥያቄዎች ማቅረቡ እና የፍርድ

አፈጻጸሙን ሥነ-ሥርአት ማከናወን — ይኸ-ይኸ ሁሉ
እንደልብ እንዳይዝናኑ ችግር ፈጥሮባቸዋል ።
እናት ቀደም ሲል ጀምሮ የምታውቀው ያ ቢጫ
መልክ ያለው መኮንን ከዳኞቹ ፊት-ለፊት ቆሞ
ስለ ፓቬል እና ስለ አንድሬይ የሚያውቀውን ሁሉ
ጉልህ በሆነ ጎርናና ድምፅ ይተርክላቸዋል ።
«ይኸን ያህልም ስለ እነርሱ የምታውቅ አይደ
ለህም» በማለት የሚተርከውን እየሰማች እናት በአዕም
ሮዋ አሰላሰለች ።
ከታጠረው ብረት ጀርባ ለሚገኙት እሥረኞች
ፍርሃት ሳትፈራላቸው እና ሀዘንም ሳይገባት ትመለከ
ታቸው ጀመር ። አታዝንላቸውም ። እነርሱን ታፈቅራቸ
ዋለች ። ትደነቅባቸዋለች ። በዝምታ የተዋጠ መደነቅ ።
ግልጽ የሆነ ፍቅር ። እነዚህ ወጣቶች እና ጠንካሮች ፤
ምሥክሮች እና ዳኞች የሚያቀርቧቸውን አሰልቺ
ዝብዝቦች ከቁም-ነገር ሳያገቡ ፤ ጠበቆቻቸው ከሕግ
አስከባሪው ጋር የሚያደርጓቸውን ክርክሮች ከመጤፍ
ሳይቆጥሩ ጀርባቸውን ለግድግዳው ሰጥተው ተቀምጠ
ዋል ። አልፎ-አልፎ ከመካከላቸው አንደኛው የፌዝ
ሳቅ እየሳቀ ለጓዶቹ አንዳች ነገር የሚነግራቸው ሲ
ሆን ፤ የጓዶቹ ፊቶችም ተመሳሳይ በሆነ የፌዝ ፈገግ
ታ ይመላሉ ። ፓቬል እና አንድሬይ ለእነርሱ ከቆሙ
ላቸው ጠበቆች መካከል ባለፈው ምሽት ኒኮላይ ቤት
መጥቶ ከነበረው አንዱ ጠበቃ ጋር ሳያቋርጡ ብዙ
ሃሣብ ይለዋወጣሉ ። ከተቀሩት ጓዶች ይበልጥ የሚቁነ
ጠነጠው እና በስሜት የተዋጠው ማዚን ውይይታቸ
ውን ያዳምጣል ። አንዳንድ ጊዜ ሳሞይሎቭ ኢቫን ጉሴ
ቭን አንዳች ነገር ይነግረዋል ። ኢቫንም ጎንተል ያደ
ርገው እና አፍኖ የያዘውን ሳቁን ላለመሳቅ እየሞ
ከረ ውስጥ-ውስጡን ሲስቅ ጉንጩ በአየር ተሞልቶ
ፊቱ ደም ይመስል እና እንዳይታወቅበት ወደላይ



ከአንገቱ ቀና ይላል ። ሁለት ጊዜ ግን በሳቅ ተንከተ
ከተ ። ከዚያም ራሱን ለመቆጣጠር ከፍጠን ብሎ ተቀ
መጠ ። እሥረኞቹ ወጣቶች ናቸው ። ወጣትነታቸውም የወ
ጣትነት አፍላ ጊዜያቸውን ለማፈን የሚደረገውን ማና
ቸውንም ጥረት ውድቅ አድርጎታል ።
ሲዞቭ እናትን ቀስ ብሎ በጉልበቱ ጎነጥ አደረ
ጋት ። ዞር ብላ ተመለከተችው ። ፊቱ ላይ የደስታ ምል
ክት ይነበባል ። ቢሆንም ደግሞ ትንሽ ቅር ያለው ይ
መስላል ።
«እስኪ. እነዚያን ወጣቶች ተመልከቺአቸው ፤ ምን
ያህል መንፈሰ ጠንካሮች እንደሆኑ! መኳንንት አይደ
ሉም እንዴ! እ?» አላት ።
ፍርድ ቤቱ ውስጥ ምሥክሮቹ በተቻኮለ እና ቅጥ-
የለሽ በሆነ ሁኔታ የምሥክርነት ቃላቸውን ይሰጣሉ ።
ዳኞችም ያለፈቃደኛነት እና ደንታ-ቢሶች ሁነው የምሥ
ክርነቱን ቃል ያደምጣሉ ። ወፍራሙ ዳኛ ዶለዝ በሆ
ነ መዳፉ አፉን ከድኖ ያዛጋል ። ቀይ ሪዝ ያለው ዳኛ
ከቀድሞው ይበልጥ ገርጥቶአል ። አሁንም-አሁንም ጣቶ
ቹን ቅንጡ (የራሱ ጎን እና ጎን) ላይ በማሳረፍ የፍ
ርድ ቤቱን ጣራ ቀና እያለ የሚያስተውል ቢመስ
ልም ሃሣቡ ግን ፍርድ ቤቱ ውስጥ የለም ። ሕግ
አስከባሪው አልፎ-አልፎ አንድ ማስታወሻ ይጫጭር
እና የመኳንንቱ ወገን ተጠሪ የሆነውን ሰው ምልክት
በመስጠት ድምፅ ሳያሰማ ያነጋግረዋል ። የመኳንንቱ
ወገን ተጠሪም ቡናማ ጺሙን እያሻሸ ፤ ጉርጥርጥ
ያሉ አስደሳች ዐይኖቹን ከወዲያ-ወዲህ እያንከባለለ
ፈገግ ይል እና አንገቱ ይቀሥራል ። ከንቲባው አን
ዱን እግሩን በሌላኛው እግሩ ላይ አነባብሮ ጉልበቱ
ሎሚ ላይ የሚያነቃንቃቸውን የእጁን ጣቶች እያ
ስተዋለ ተቀምጦአል ። ቦርጩን እግሮቹ ጭኖች ድረስ
ዘርፍጦ የዘረገፈው እና በእጆቹ ከብቦ የያዘው የቀበ

ሌው ገገር አሰልቺ የሆነውን የፍርድ ቤት ቻቻታ የሚያደምጥ እርሱ ብቻ ይመስላል ። ወደላይ በረዥሙ የተንጠለጠለ እና የዶሮ ምስል ያለበት የአየር መቆጣጠርያ መዘውር ዘንግ ነፋስ በሌለበት ጊዜ ከፍ ብሎ ሳይንቀሳቀስ አንድ ቦታ እንደሚቆም ሁሉ ሽማግሌው የመሀል ዳኛም ሳይንቀሳቀሱ አንድ ቦታ ድብር ብለው ከመቀመጣቸው በስተቀር እንደቀበሌው ገዥ እርሳቸውም የማዳመጥ ፍላጎት ያላቸው ይመስላሉ ። ይኸንን መሳዩ የፍርድ አፈጻጸም ሥነ-ሥርአት ረዢም ለሆነ ጊዜያት የተካሄደ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ደብቷቸው ተሰላቹ ።

«ችሎቱ ለጥቂት ሰአት ዕረፍት ..» አሉ መሀል ዳኛው ከተቀመጡበት ብድግ ብለው ። ከሳሱት ከንፈሮቻቸው የሚሰማው የተቀረው ንግግራቸው የመልጎምጎም እና የማይሰማ ንግግር ነው ።

እሮይታ ፤ መደነቅ ፤ ሳል መሳል ፤ እግርን መሬቱ ላይ መድቃት ይከናወን ጀመር ። እሥረኞቹ እንዲወጡ ተደረገ ። ፈገግ በማለት በቦታው ለተገኙት ለቤተ ሰቦቻቸው እና ለጓዶቻቸው ጭንቅላቶቻቸውን በመነቅነቅ ሰላምታ ሰጡ ።

«የጎር ፤ ቅር አትሰኝ!» በማለት ኢቫን ጉሴቭ ተናገረ ።

እናት እና ሲዞቭ ወጥተው ወደ ኮሪዶሩ ሄዱ ።

«ሻይ ለመጠጣት ወደ ቡና ቤቱ እንሂድ ይሆን? አንድ ሰአት ተኩል ይቀረናል» አላት ሲዞቭ እናትን ።

«እኔ አላሰኘኝም» አለች እናት ።

«እኔም አላሰኘኝም ። እንዴት ናቸው እነዚህ ልጆች? እ? በዓለም ላይ ያሉ እነርሱ ብቻ ይመስል ሌሎችን ከምንም ሳይቆጥሩ እዚያ መቀመጫቸው ላይ ተዝናንተው ቁጭ ብለው ነበር ። ያ ፌዎዶር እማ!» አለ ።



የሳሞይሎቭ አባት ባርኔጣውን በእጁ ይዞ ወደ እነርሱ ዘንድ መጣ ። ፈገግ እያለም የሚከተለውን ነገራቸው ፣ —

«የኔን ግሪጎሪ አያችሁትን? አንዳችም ጠበቃ የማይሻ መሆኑን ከመግለጡም በስተቀር ጠበቆቹን ሊያነጋግርም አልፈቀደም ። ይኸንን ለማድረግ የመጀመርያው እርሱ ነበር ። ፔላጌያ ፤ የእርስዎ ልጅ ጠበቆች መኖራቸውን ይሻ ነበር ። የእኔ ልጅ በፍጹም አይሻም ነበር ። ከዚያ በኋላም ከመካከላቸው አራቱ የሚከራከሩላቸው ጠበቃዎች አንሻም ብለው እምቢኝ አሉ…» አለ ።

ሚስቱ አጠገቡ ቆማለች ። እንባዋን እየዋጠች በመሀረቧ ጫፍ አፍንጫዋን ትናፈጣለች ። ሳሞይሎቭ ንግግሩን በመቀጠል ።

«ወይ ጉድ ፤ የሚገርም እኮ ነው! እነዚህ ሰይጣኖች የሚያደርጉትን አድራጎት ስትመለከቱ እንዲህ ያለ ወጥመድ ውስጥ ገብተው መገኘታቸው በገዛ ራሳቸው ምክንያት በመሆኑ ምንም አያሳዝኑም ያሰኛሉ ። ግን ደግሞ የሚፈጽሙት ነገር ሁሉ ትክክል ነው የሚያሰኝ ነው! በተለይም ብዛታቸው ፋብሪካው ውስጥ ከጊዜ-ጊዜ እየጨመረ ሲታይ ፤ ዕውነትም የቆሙለት ዓላማ ትክክለኛ ነው የሚያሰኝ ነው ። ፖሊሶች አሁንም-አሁንም ያፍኗቸዋል ። እነርሱ ግን ውሀ ውስጥ እንዳለ አሣ ከጊዜ ጊዜ እጥፍ በእጥፍ ብዛታቸው እየጨመረ በመራባት ይባዛሉ ። ኃይል እና ጥንካሬ ያለው በእነርሱ በኩል ሳይሆን አይቀርም የሚያሰኝ ነው» አለ ።

«ስቴፓን ፔትሮቪች ፤ በዚህ ጉዳይ ውስጥ ገብተን እኛ ይኸ ነው ብለን ፣ ተገንዝበን ለመናገር ያዳግተናል» አለ ሲዞቭ ።

«ዕውነት ነው ያዳግተናል!» በማለት ሳሞይሎቭ በሃሣቡ ተስማምቶ መለሰ ።

ሚስቱ በአፍንጫዋ አየሩን ደህና አድርጋ ከሳ
በች በኋላ ፡ —
«እነዚህ እርጉሞች ሁሉም ቁልጭ እንዳሉ ጤነ
ኞች አይደሉም እንዴ!» አለች ።
ከዚያም ሰፊ የሆነ እና ልግልግ-ልግልግ እያለ
ከወዲያ-ወዲህ የሚዋልል ፊቷን ወደ እናት ዞር አድ
ርጋ ፈገግ በማለት ፡ —
«ኒሎቭና ፤ አይቀየሙኝ ። ከጥቂት ጊዜያት በፊት
ለዚህ ሁሉ ጉዳይ ተወቃሹ የርስዎ ልጅ ነው ብዬ
አማርሬ ነበር ። እንደ ዕውነቱ ከሆነ ግን ተወቃሹ
ማን እንደሆነ እግዚአብሔር ይወቀው ። ስለ እኛ
ልጅ ስለ ግሪጎሪ ጃንዳርሞች እና ሰላዮት ምን እን
ዳሉ ሰምተዋልን? ይኸንን የእኛን ሰይጣንም በጉዳዩ
አለበት አሉ!»
ስሜቷን ሳታዳንቅ በልጅዋ ኮርታበታለች ። እናት
ግን አደነቀቻት ። ደግነት በተመላው ፈገግታ እና ከል
ቧ በፈለቁ ቃላት እናት የሚከተለውን መለሰችላት ፡ —
«የወጣቶች ልብ ዕውነትን ፈጥኖ ለመያዝ ሁል
ጊዜም ብቃት አለው...» አለች ።
ሰዎች በኮሪዶሩ ከወዲያ-ወዲህ እየተመላለሱ እና
በቡድን ሰብስብ እያሉ በስሜት በተዋጠ ቀስተኛ
ድምፅ ይወያያሉ ። ብቻውን የቆመ አንድም ሰው የለ
ም ብሎ ለመናገር የሚያስደፍር ሲሆን ሁሉም ቢሆ
ን የየራሱን ሃሣብ ለማቅረብ የሚሻ እና ሌሎች
የሚናገሩትን ለማድመጥም የሚጓጓ ነው ። ኃይለኛ
ነፋስ ፡ የሚያወዛውዛቸው ይመስል ሰዎቹ በግድግዳዎች
መካከል በሚገኘው ነጭ ጠባብ መንገድ በኩል ከወ
ዲያ ወዲህ ይንጎራደዳሉ ። አንድ ጠንካራ የሆነ ቦታ
ፈልገው ካስማቸውን ለመትከል የሚሹ ይመስላሉ ።
ቁመተ-ረዥምም የሆነው እና እንደወንድሙ እንደቡ
ኪን ቆዳው ነጣ ያለው የቡኪን ወንድም የሚናገረ



ውን አንዳች ነገር በማስረጃ ለመደገፍ እየጣረ እጁ
ን ያወዛውዛል ።
«ያ የቀበሌው ገገር ከሌፓኖቭ እዚህ ጉዳይ ውስ
ጥ የሚያገባው አንዳችም ነገር የለም» አለ ።
«ኮንስታንቲን ፤ ዝም በል» አለው ቁመተ አጭር
የሆነው አባቱ ግራ ቀኙን ጠንቀቅ ባለ ሁኔታ በመ
ቃኘት ።
«ለምን ዝም እላለሁኝ! ዝም አልልም! ባለፈው ዓ
መት ከፀሐፊዎቹ መካከል የአንደኛውን ሚስት በመወ
ሽም ፀሐፊውን ገድሎታል እየተባለ ይወራል ። አሁን
ከእርሷ ጋር ይኖራል ። ይኸ እንግዲህ ከቶ ምን ይባ
ላል? ከዚህም በስተቀር ፤ ሞሽላቃ ሌባ መሆኑን ማንም
የሚያውቀው ጉዳይ ነው» በማለት ተናገረ ።
«ኮንስታንቲን ፤ እባክህ ስለፈጠረህ! ይኸንን አፍህን
ዝጋ ነው የምልህ!» በማለት አባቱ ተናገረ ።
«ልክ ነው ። ልክ ነው ። ፍርዱ ትክክለኛ ፍርድ
ነበር ብሎ መናገር አይቻልም» በማለት ሳሞይሎቭ
ተናገረ ።
ሳሞይሎቭ ሲናገር ቡኪን አዳመጠ እና ከሌሎቹ
ጋር አብሮ ሁኖ ወደሳሞይሎቭ ተጠጋ ። ፊቱ እንደበ
ርበሬ ቀይ ሁኖአል ። እጁን ከወዲያ-ወዲህ ያወዛው
ዛል ።
«ድርጊቱ የግድያ እና የሌብነት ድርጊት ሲሆን
ሰዎች ፍርዳቸውን የሚቀበሉት በሕዝባዊ የፍርድ
ሸንጎ ፤ ማለትም በገበሬዎች ፤ በከተማ ነዋሪዎች እና
በሠርቶ-አደሮች የዳኝነት ብያኔ ነው» በማለት ድም
ፁን ከፍ አድርጎ አሰማ ። ቀጠል አድርጎም ፡ —
«ሰዎች ባለሥልጣኖችን የመቃወም ድርጊት ሲፈ
ጽሙ ግን ባለሥልጣኖቹ ራሳቸው ዳኞች ፈራጆች
ሁነው ቁጭ ይላሉ! እሺ እንግዲህ ፤ ከቶ ይኸ ምን
ይባላል? እኔን ብትሰድበኝ እና እኔም መንገጭላህን

ባንነው ፤ ከዚያም ለተፈጸመው ድርጊት ፍርድ ፈራጁ አንተው ብትሆን እኔን ጥፋተኛ አድርገህ እንደምትፈርድብኝ የማያጠራጥር ጉዳይ ነው ። በእኔ እና በአንተ መካከል ለተፈጸመው ድርጊት የመጀመርያው ተጠያቂ ግን ማን ነው! አንተ ነህ!» በማለት ተናገረ ።

ፀጉረ-ሽበቶ ፤ አፍንጫው እንደማንቆርቆርያ አፍ የተቆለመመ እና ደረቱ በሜዳልያ የተጌጠ ዘበኛ የተሰበሰቡትን ሰዎች እየበተናቸው ቡኪን ላይ ጣቱን ቀስሮ ፡ —

«ይኸን ጩኸትህን አቁም ። መሸታ ቤት አይደለም ያለኸው!» አለው ።

«እሺ ይሁን ግዴለም ። የት እንዳለሁኝ ይገባኛል ። እኔ ግን የምለው ፤ ደብዳቢም እኔ ፤ ዳኛም እኔ ብሆን ምን ይሰማሃል...» አለው ።

«ከዚህ ቦታ ባስወጣህ ሳይሻል አይቀርም ። ነው ፤ የምትሻው ይኸንን ነው መሰለኝ!» በማለት ዘበኛው በዛቻ ተናገረ ።

«ላስወጣህ? ምን ስላረግሁኝ?» አለ ቡኪን ።

«እየጮኸክ ስለምትረብሽ ። ከግቢው ውጪ መንገዱ ላይ እንድትወጣ አደርግሀለሁኝ» አለው ዘበኛው ።

ቡኪን አብረውት ያሉትን ተመለከተ ።

«እነርሱ የሚፈልጉት ነገር ቢኖር ሰዎች ምንም ሳይናገሩ አፋቸውን እንዲዘጉ ነው» በማለት ዝቅተኛ በሆነ ድምፅ አሰማ ።

«እንዴታ! ታዲያ ሌላ ምን ይሽ መስሎሃል?» በማለት ሽማግሌው ሰው ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰማ ።

ቡኪን ትከሻውን ወዝወዝ አድርጎ ለስለስ ባለ ዝቅተኛ ድምፅ መናገር ቀጠለ ።

«ታዲያ ተመልካቹ ሕዝብ በፍርዱ ሥነ-ሥርአት ላይ እንዳይገኝ የሚከለከለው ለምንድነው? ለምን ቤተሰቦች ብቻ እንዲገኙ ይደረጋል? ፍርዱ ሀቀኛ ከሆነ ሌሎች እንዳይገኙ መከልከል ምን ያስፈልጋል? ሁሉም ይስማው እንጂ! ምን የሚያስፈራ ጉዳይ አለ?» በማለት ተናገረ ።



«ፍርዱ ትክክለኛ የሆነ ፍርድ አይደለም ። ይኸ ምንም የሚያጠራጥር ጉዳይ አይደለም!» በማለት ሳሞይሎቭ አረጋግጠ በጉልህ ድምፅ ተናገረ ።

እናት ቀደም ሲል ኒኮላይ ስለ ፍርዱ አፈጻጸም የነገራትን ለሳሞይሎቭ ልትነግረው ፈልጋ ነበር ። ይሁን እንጂ የነገራትን ሁሉንም ያልተረዳችው ከመሆኑም በስተቀር አንዳንዶቹን ቃላትም ስለዘነጋቻቸው ሳትነግረው ቀረች ። ለማስታወስ እየሞከረች እልፍ ብላ ስትራመድ ፤ እርሷን-እርሷን አንድ መለስተኛ ሪዝ ያለው ወጣት ሰው ሲመለከታት አየች ። ቀኝ እጁን ሱሪው ኪስ ውስጥ የከተተ ሲሆን ፤ ይኸ ሁኔታውም ቀደም ሲል የምታውቀው በሚመስል ረገድ ከቀኝ ትከሻው ይልቅ የግራ ትከሻው ዝቅ ያለ እንዲሆን አድርጎታል ። በራሷ ሃሣብ የተመሰጠች በመሆኑ ምክንያት እርሱን-እርሱን መመልከት ትታ ወዲያውኑ ዞር አለች ።

ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ግን ከሰዎቹ አንዱ ፡ —

«እርሷን?» በማለት ሲጠይቅ ሰማች ።

«አዎን!» የሚል መልስ ቀጠለ ።

ዙርያውን ተመለከተች ። አንደኛውን ትከሻውን ጉብር ያደረገ ሰው ቀረብ ካለ ቦታ ቆሞ ጥቁር ጢም ካጤመ እና አጠር ያለ ካፖርት ለብሶ እስከጉልበቱ ረዥም የሆነ ቦት ጫማ ከተጫማ ወጣት ሰው ጋር ያወራል ።

ግራ ገብቷት ማንነቱን ለማስታወስ ትሞክር ጀመር ። አልሆንላትም ። ልጅዋ ስለቆመበት ዓላማ ለሰዎች ለማስረዳት ከፍተኛ ፍላጎት አላት ። የፍርዱ ሁኔታ ምን እንደሆነ ለመገመት እንድትችል እርሷ የምታቀ

ርበውን ሃሣብ በመቃወም ምን እንደሚናገሩ ለመስማት ትሻለች ።

«ለመሆኑ የፍርድ አፈራረድ እንደዚህ ነውን?» በማለት ንግግሯን ለሲዞቭ ጭንቅ እያላት ማቅረብ ጀመረች ። ከዚያም ፡ —

«አብዛኛውን ጊዜያቸውን ያባከኑት የተፈጸመው ድርጊት ለምን እንደተፈጸመ ለማወቅ ሳይሆን ፤ ማን ምን እንዳደረገ ለማወቅ በመጣር ነበር ። ሁሉም ዳኞች ደግሞ ሽማግሌዎች ናቸው ። ወጣቶች ፍርዳቸውን ይቀበሉ ዘንድ የሚገባቸው እንደእነርሱው ወጣት በሆኑ ሰዎች ነው» አለች ።

«ልክ ነው ። መሆን አለበት» አለ ሲዞቭ ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«እንዲህ የመሰለውን ጉዳይ ለእኛ መገንዘቡ አስቸጋሪ ነው ። በጣም አስቸጋሪ ነው!» በማለት በሀሣብ ተውጦ ጭንቅላቱን ነቀነቀ ።

ዘበኛው የፍርድ ቤቱን በራፍ ከፈተው ። ከዚያም ፡ —

«ቤተ ሰቦች የሆናችሁ! ወደ ውስጥ የመግቢያ ቲኬታችሁን አሳዩ!» በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ ዘበኛው አሰማ ።

«ቲኬት አሳዩ ይበል! ወይ ጉድ ፤ ልዩ ልዩ ጨዋታ ለማየት ሰርከስ የምንሄድ ይመስል!» በማለት አንዱ በልግጫ መልክ ተናገረ ።

በሰዎቹ ፊት ላይ ብስጭት ይነበብባቸዋል ። ብዙ የሚያወሩ ሲሆን ትዕግሥታቸው ጥቂት ነበር ። ከዘበኞቹ ጋርም ይወዛገቡ ጀመር ።

## 25

ሲዞቭ ወደአግዳሚ ወንበሩ ላይ ለመቀመጥ ሲሄድ አንዳች ነገር ለመናገር ያጉመተምታል ።



«ምነው ፤ ምንድነው የምትል?» በማለት እናት ጠየቀችው ።

«አይ ፤ ምንም አዲስ ነገር የለም ። ሰዎች ጅሎች ናቸው…» አለ ።

ደወሉ ተደወለ ።

«የዳኞች መምጫ ተቃርቦአል ። ፀጥ በሉ!» ተባለ ።

ዳኞቹ መጥተው እንደቀድሞ ቦታ-ቦታቸውን ሲይዙ በፍርድ ቤቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች በሙሉ ፀጥ በማለት ከመቀመጫቸው ብድግ ብድግ አሉ ። እሥረኞቹም ወደ ቀድሞ ቦታቸው ሄደው እንዲቀመጡ ተደረገ ።

«ዝም በይ! ሕግ አስከባሪው ንግግሩን ሊያሰማ ነው» በማለት ሲዞቭ ቀስ ብሎ ተናገረ ።

አንዳች አስፈሪ የሆነ ሁኔታ በመጠባበቅ እናት ሰውነቷን ወደፊት አጉብጣ ትጠባበቀ ጀመር ።

ዐቃቤ ሕጉ ከዳኞቹ በስተቀኝ ሁኖ ፊቱን ወደ ዳኞቹ መለስ አድርጎ እና አንድ እጁን ጠረጴዛው ላይ አሳርፎ ቆሞአል ። ትንፋሹን ደህና አድርጎ ከዋጠ በኋላ እና ቀኝ እጁንም ጥቂት ካወዛወዘ በኋላ ንግግሩን ቀጠለ ። እናት ዕቃቤ ሕጉ መጀመርያ የሠነዘራቸውን ቃላት ለመገንዘብ አልቻለችም ። የድምፁ አወራረድ ወፈር ያለ ቢሆንም አጣጣሉ አንድ ደረጃ የተከተለ አልነበረም ። ሲናገር አንዴ ይፈጥናል ። አንዴም ዝግ ይላል ። አንዳንድ ጊዜ ከአንደበቱ የሚወጡት ቃላት ጥንቁቅ ሰው ድሪቶ ልብስ የሚደርት ይመስል ቀስ እያለ በማላዘን ነው ። ከዚያም ስኳር ከብበው ውር-ውር እንደሚሉ ዝምቦች ከአንደበቱ የሚፈልቁትን ቃላት በፍጥነት ቷ-ቷ-ቷ እያደረገ ያዥጎደጉዳቸዋል ። ከሚናገራቸው ቃላት ውስጥ አንዳችም አሥጊ ቃላት አልሰማችም ። እንደማያስደስት ደቃቅ ደረቅ አቧራ የሚናገራቸው ቃላት እንደበረዶ ቀዝ

ቅዘው እና እንደ አመድ ቡላ መስለው በክፍሉ ውስጥ ይንሳፈፉ ጀመር ። ይህ እንደዚህ በአንደበተ-ርቱዕነት የሚቀርብ አነጋገር ፤ እንደዚህ ስሜት አልባ ሁኖ እርቃኑን የቀረ አነጋገር ፓቬልን እና ጓዶቹን ሊያረካቸው ያልቻለ አነጋገር ይመስላል ። በዕርግጥም ደግሞ እነርሱ ላይ አንዳችም ስሜት ሊያሳድርባቸው አልቻለም ። አንዳንዱ እርስ-በእርሳቸው እያወሩ ፤ አንዳንዱም እየተሳሳቁ ፤ አንዳንዱም ሳቃቸውን ለመሸሸግ ኮስተር እያሉ እዚያው እነበሩበት ፍንክች ሳይሉ ተቀምጠዋል ።

«ይዋሻል!» በማለት ሲዞቭ ቀስ ብሎ ተናገረ ።

እናት እርግጠኛ አልነበረችም ። ዐቃቤ ሕጉ እገሌ-ከእገሌ ሳይል እሥረኞቹን በሙሉ ወንጀሏቸዋል ። ስለፓቬል ከተናገረ በኋላ ስለ ፌዎዶር መናገሩን ቀጠለ ። ከዚያም ስለ ፌዎዶር ተናግሮ ሲያበቃ ስለ ቡኪን መናገሩን ቀጠለ ። ሁሉንም አንድ ስልቻ ውስጥ እያሳመረ የሚያጭቃቸው ይመስላል ። ይሁን እንጂ ፤ ስሜቷን ለመቀስቀስም ሆነ ለማስበርገግ ባልቻሉት አልባሌ በሆኑት ንግግሮቹ አልረካችም ። አንዳች አሥፈሪ ነገር ሊኖር ይችላል ብላ በመገመት ትጠባበቅ ጀመር ። ፊት-ፊቱን ፤ ዐይን-ዐይኖቹን ፤ ድምፁን ፤ እና ግርማ-ሞገስ ባለው ሁኔታ ከወዲያ-ወዲህ የሚያወዛውዘውን እጅ-እጁን ትመለከት ጀመር ። እናትም አንድ አስጊ የሆነ ሁኔታ ታይቶአታል ። አሥጊ ጉዳይ መኖሩን ታውቃለች ። ይሁን እንጂ ልቧን ወዮልሽ እያለ ከማስጠንቀቁ በስተቀር ይኸ ነው ብላ ቀንድ እና ጅራቱን በመጨበጥ ልታውቀው ከቶም አልቻለችም ።

ዳኞቹን ተመለከተቻቸው ። ሁሉም በሚደረገው ንግግር ተሰላችተዋል ። ሕይወት-አልባ በሆነው ግራጫ እና ቢጫ ፊቶቻቸው ላይ አንዳችም ስሜት አይነበብም ። ከዐቃቤ ሕጉ የሚሠነዘሩት ቃላት ለዐይን የማይታዩ ጭጋጎችን እየፈጠሩ በግዴለሽነት እና ከመሰላቸት የተነሳ የማብቂያውን ጊዜ በመጠባበቅ የድካም ደመና አከናንቦአቸዋል ። መሀል ዳኛው ሳይነቃነቁ እዛው አሉበት አንድ ቦታ ላይ ተገትረው የተቀመጡ ሲሆን ፤ ከጊዜ-ጊዜም መነጽራቸው ውስጥ እንደ ነቁጥ ቁጭ-ቁጭ ያሉት ሁለቱ ዐይኖቻቸው በመነጽሩ ውስጥ ቀለም-አልባ ሁነው ብዥ-ብዥ ይላሉ ።

እናት ይኸንን የመሰለ ቀዝቃዛ ግድየለሽነት ፤ ይኸንን የመሰለ የስሜት መገነጣጠል ስትመለከት ፤ —

«አሁን በእርግጥ እነዚህ ሰዎች ዳኞች ተብለው በዳኝነት የተሰየሙ ናቸውን?» በማለት በአዕምሮዋ ውስጥ ታሰላስል ጀመር ።

ይኸንን የመሰለው ጥያቄ ቀስ በቀስ ፍርሀቷን እያባባሰው እና ጠንካራ ግራ-መጋባት እያስከተለባት ልቧን ስቅል አድርጎ ትር-ትር ያደርግባት ጀመር ።

ድንገት ሳይታሰብ የዐቃቤ ሕጉ ንግግር አበቃ ። ለመደምደሚያ ያህል ጥቂት የቃላት ድሪቶዎቹን ደራርቶ ካበቃ በኋላ ለጥ ብሎ ዳኞቹን እጅ በመንሳት እጆቹን እያሻሸ ወንበሩ ላይ ተቀመጠ ። የመኳንንቱ ወገን ተጠሪ በማድነቅ ጭንቅላቱን ወዝወዝ-ወዝወዝ ፤ እነዚያን ጎረጥ ዐይኖቹንም ከብለል-ከብለል አደረገለት ። ከንቲባው እጁን ዘረጋ ። የቀበሌው ኀገርም በበኩሉ የገዛ ራሱን ቦርጭ እያስተዋለ ፈገግ አለ ።

ያም ሁኖ ግን በዐቃቤ ሕጉ ንግግር ዳኞቹ የረኩ አይመስሉም ። ስሜታቸው አልተቀሰቀሰም ። ከዚያም ሰብሳቢው ዳኛ አንድ ወረቀት ፊታቸው ድረስ አስጠግተው በማቅረብ ፤ —

«ከዚህ ቀጥሎ ፍርድ ቤቱ በፌዶሴዬቭ ፤ በማርኮቭ እና በዛጋሮቭ ስም የቆመው ጠበቃ የሚያሰማውን የመከላከያ ቃል ያደምጣል» አሉ ።

ከዚህ ቀደም ኒኮላይ ቤት መጥቶ አይታው የነበ

ረው ጠበቃ ከተቀመጠበት ተነሳ ። የደስ-ደስ ባለው
ሰፊ ፊቱ ላይ የሚገኙት ዐይኖቹ አየሩን በመቀስ
ይሰነጥቁት ይመስል እንደምላጭ ስለታም ሁነው ከቀ
ያይ ቅንድቦቹ ሥር የሚገኙት ዐይኖቹ ከጉድጓዶቻ
ቸው ብቅ በማለት ብሩኅ ፋናቸውን ይፈነጥቃሉ ።
ድምፁን ጎላ አድርጎ ፤ ግልጽ በሆነ ሁኔታ እና ያለ
መጣደፍ ይናገራል ። እናት ግን ንግግሩን መከታተል
አልቻለችም ።

«ገባሽ ምን እንደሚናገር?» አላት ሲዞቨ በጆሮዋ
ቀስ ብሎ እያንሾካሾከ ፡ —

«ገባሽ? ማሰብ ማሰላሰል የማይችሉ ፤ ጥቂት ወፈፍ
ያደረጋቸው ንኮች ናቸው ነው የሚለው ። ፌዎዶርም እን
ደዚህ ነውን?» አለ ሲዞቨ ለእናት ።

በጣም አዝና ስለነበረ ለሲዞቨ መልስ መመለስ
አልፈለገችም ። ልቧ ውስጥ እንደአሎሎ ሸክሙ እስኪ
ከብዳት ድረስ ሃዘን እና ትካዜ ተጫጫናት ። አሁን
ፍትህን እንደምትጠባበቅ ግልጽ ሁኖ ታያት ። የልጅዋ
ከሳሾች በሆኑት ላይ የሚያወላውል እና ሀቀኛ የፍት
ህ ሚዛን ይመዛዘናል ብላ ተጠባበቀች ። በምን ሁኔታ
ላይ ይገኝ እንደነበረ ዳኞቹ ረዘም ላለ ጊዜ በጥን
ቃቄ የምርመራ ጥያቄ ለልጅዋ የሚያቀርቡለት መስሎ
ተሰማት ። አስተሳሰቦቹን እና ድርጊቶቹን ቀና በሆነ
መንፈስ ይመለከቱለታል ብላ ገመተች ። ከዚያም ሀቁ
ን አስተውለው ከደረሱበት በኋላ ፡ —

«ይኸ ሰው የፈጸመው ድርጊት ትክክለኛ ድር
ጊት ነው!» ብለው ይፈርዱለታል ብላ ገመተች ።

ይሁን እንጂ እርሷ እንደገመተችው ያለ ሁኔታ
አልደረሰም ። ፍርዳቸውን በሚጠባበቁት ሰዎች እና
ፈራጆች በሆኑት ዳኞች መካከል ይኸ ነው ተብሎ
ሊገለጽ የማይችል ርቀት በመካከላቸው የሚገኝ መስ
ሎ የሚታይ ሲሆን ፤ እሥረኞቹም ለእነዚህ ዳኞች



ፋይዳ ያላቸው ሰዎች መስለው የማይታዩ ይመስላሉ ።
በድካም በመዛሏ ምክንያት እናት ለፍርዱ ሥነ-ሥር
አት ያላት ስሜት እየጠፋ ሄደ ። ፍርድ ቤቱ ውስጥ
የሚነገረውን ንግግር ማድመጥ ትታለች ።

«አይ! አሁን ይኸም ፍርድ ነው ሊባል ነውን?»
እያለች በመቆጨት ሁኔታ ታሰላስላለች ።

«በእነርሱ ዘንድ ፍርድ ማለት ይኸ ነው!» በማለ
ት ሃሣቧን በመደገፍ ሲዞቨ ቀስ ብሎ ተናገረ ።

ጉርድ ያለ እና ግርዋት ያለ አስቂኝ ፊት ያለው
ሌላ ጠበቃ መናገር ጀመረ ። ዳኞቹ ንግግሩን በየጊ
ዜው ያቋርጡበታል ።

ዐቃቤ-ሕጉ ከተቀመጠበት አፈፍ ብሎ በመነሳ
ት የአነጋገር ደንብ እና ሥነ ሥርአት ተፋልሷል
በሚል ሁኔታ በቁጣ አንዳች ነገር መናገር የጀመረ
ሲሆን ዳኛውም ስሕተት መፈጸሙን ደከም ባለ
ሁኔታ አሰማ ። ከዚያም የተከሳሾች ጠበቃ የሚሠነ
ዘረውን እርማት በአክብሮት አንገቱን ዝቅ ብሎ
እያዳመጠ በመቀበል ንግግሩን ቀጠለ ፡ —

«እሰይ! እንዲህ ጎርጉርልኝ!» አለ ሲዞቨ ።

አንድ ላይ ታፍገው በመኮልኮል አኩርፈው እና
ጨፍግገአቸው የነበሩትን ዳኞች ውስጥ አጥንታቸው
ድረስ ገብቶ በሚሰማቸው ሁኔታ ጠበቃው አንደ
በተ ርቱዕ በሆነ አነጋገሩ ጠንከር አድርጎ እየከሰ
ሳቸው ልክ ልካቸውን መናገር ሲጀምር ፤ ክፍሉ ው
ስጥ የነበረው ተመልካች ስሜቱ ተቀሰቀሰ ። ቁጣው እየ
ጠና-እየጋለ ሄደ ።

አሁን ፓቬል ከተቀመጠበት ብድግ አለ ። ድንገት
ም ክፍሉ ውስጥ ያለው ሰው ሁሉ ፀጥ አለ ። እናት
ከሰውነቷ ወደፊት-ወደፊት ሳብ-ሳብ አለች ። ፓቬል
እጅግ ርጋታ በተመላበት ሁኔታ ፡ —

«እኔ የፓርቲዩ አንዱ አባል እንደመሆኔ ሁሉ

የምቀበለው ብያኔ ፓርቲዬ በእኔ ላይ ያሳለፈብኝን
ብያኔ ብቻ ነው ። ስለራሴ በመከላከል የማቀርበው አንዳ
ችም ንግግር የለም ። ይሁን እንጂ ፤ ልክ እንደእኔው
ሁሉ ለራሳቸው መከላከያ የማይሹት ጓዶቼ ባላቸው
ፍላጎት መሠረት አንዳንድ ለእናንተ ግልጽ ያልሆኑ
ላችሁን ጉዳዮች ላብራራላችሁ እሞክራለሁኝ ። የሶሻል
ዴሞክራሲን ዐርማ አንግበን ያካሄድነውን ሰላማዊ
ሰልፋችንን ዐቃቤ ሕጉ በሥልጣን ላይ ባለው መንግ
ሥት ላይ አመጽ ማካሄድ ነው ብሎታል ። ከዚህም
በስተቀር ፤ እኛ የዛሩን የቄሣሩን መንግሥት እንደምንገለ
ብጥ ሰዎች አድርጎ ቆጥሮናል ። ሀገራችንን ሸምቅቆ
የሚያማቅቀው እግር ብረት ፈላጭ-ቆራጩ መንግሥት ብ
ቻ አድርገን የማንገምት መሆናችንን ልገልጽ እሻለሁ
ኝ ። ይህ ፈላጭ-ቆራጭ አገዛዝ ከእግር ብረቱ ሰንሰለ
ቶች አንዱ ዘለበት ሲሆን ፤ እርሱን ፈልቅቀን በማውለ
ቅም ሕዝባችንን ከታሠረበት እንፈታዋለን...» በማለት
ተናገረ ።

ጠንካራ በሆነ ድምፁ ንግግሩን ሲቀጥል በፍ
ርድ ቤቱ ውስጥ የሰፈነው ፀጥታ ይበልጡኑ ጭጭ-
ምጭጭ አለ ። ግድግዳው አብጦ የሚሰፋ-የሚነሠራፋ
መሰለ ። ፓቬልም በታላቅ እፎይታ ከላይ ከፍ ብሎ
ጉብ ያለ መሰለ ።

ዳኞቹ ከብዶአቸው እና ቀፍፎአቸው በየተቀመጡ
በት ወንበር ከወዲያ-ወዲህ በመንፏቀቅ ይቁነጠነጣሉ ።
የመኳንንቱ ወገን ተጠሪ የሆነው ሰው የልግመኛ
መልክ ላለው ዳኛ አንድ ነገር አሾኩሾኮ ነገረው ።
ከዚያም ልግመኛ መሳዩ ዳኛ በእሺታ ጭንቅላቱን
ወዝወዝ እያደረገ ለሰብሳቢው ዳኛ በቀኝ ጆሮአቸው
በኩል አንሾኳሾከላቸው ። እጀሽኛው የጃጁ ዳኛም
በበኩላቸው በግራ ጆሮአቸው በኩል ላለው ዳኛ
አንሾኳሾኩ ። የጃጁት ዳኛ ግራ እና ቀኝ ተዋክበው



አንዳች ነገር እ-ኝ-ኝ-ኝ በማለት አነበነቡ ። ይሁን
እንጂ የእርሳቸው ድምፅ ጉልህ በሆነው እና ስል
ቱን ሳይስት ደረጃውን ጠብቆ በሚዘልቀው በፓቬል
ድምፅ ተዋጠ ። ፓቬልም ንግግሩን በመቀጠል ፡ —

«እኛ ሶሻሊስቶች ነን ። ይህም ማለት ፤ ኅብረተሰ
ብን ገነጣጥሎ የሚፈረካክሰውን ፤ ሕዝቦችን እርስ-በእ
ርስ የሚያበጣብጠውን ፤ ሊታረቅ የማይችል የጥቅም
ግጭት የሚፈጥረውን ፤ ይኸንን ግጭት ለመሸሸግም
ሆነ ትክክለኛ አድርጎ ለማቅረብ በመጣር በሀሰት
የሚደነበቀውን ፤ መላውን ሰዎች በቅጥፈት ፤ በግብዝነት
እና በጥላቻ የሚያባልጋቸውን የግል ሀብት እና ንብ
ረት ይዞታን እንቃወማለን ። አንድን ግለ-ሰብ እንደ
ሌላ ሳይሆን ሌሎችን ሀብታም ለማድረግ መጠቀሚያ
አድርጎ የሚመለከት ኅብረተሰብን ኢ-ሰብአዊ እንደ
ሆነ ኅብረተሰብ እና ከእኛ ጥቅም ጋርም የሚቃረን
አድርገን እንቆጥረዋለን ። ስሕተተኛ እና ግብዝ የሆነ
ሥነ-ምግባራዊ አመለካከቱን አንቀበለውም ። በግለሰቡ
ላይ የሚያሳየውን ተጠራጣሪነት እና ጭካኔ እናወግ
ዛለን ። ይኸንን የመሰለው ኅብረተሰብ በግለሰቡ ላይ
የሚፈጽማቸውን ማናቸውንም ሥጋዊም ሆነ ሥነ-
ምግባራዊ ጭቆና ፤ በራስ ወዳድነት ላይ በተመሠረተ
ስግብግብነት ሰብአውያን ፍጡሮችን ለመደምሰስ የሚ
ፈጸመውን ማናቸውንም ድርጊት አጥብቀን እናወግዛ
ለን ። እኛ ወዝ-አደሮች ነን ። የሕፃናት መጫወቻዎች
ከሆኑ አሻንጉሊቶች አንስቶ ግዙፍ እስከሆኑ ማሺ
ኖች ድረስ ማናቸውም ነገሮች ቢሆኑ ተሠርተው የሚ
ቀርቡት በእኛ የጉልበት ውጤት ነው ። ያም ሁኖ
ግን ፤ እኛ ሰብአዊ ክብራችንን ከማስጠበቅ የታገድን
ሰዎች ነን ። የገዛ ራሱን ጥቅም ለማሟላት ሲል ማን
ም ያሻው ሁሉ ተነስቶ ይበዘብዘናል ። መላውን ሥል
ጣን እጃችን ውስጥ ለማስገባት እንድንችል የሚያበቃ

ንን የተወሰነ የነፃነት ደረጃ በአሁኑ ጊዜ ለመወጣ
ጣት እንሻለን ፡፡ መፈክሮቻችን ግልጽ ያሉ ናቸው ፡ —
‘የግል ሀብት እና ንብረት ይውደም!’ ‘ማናቸውም የማ
ምረቻ መሣርያዎች ወደ ሕዝቦች ይዛወሩ!’ ‘ሥልጣን
የሰፌው ሕዝብ ይሁን!’ ‘ማንም ቢሆን የመሥራት
ግዴታ አለበት!’ እነዚህን ከመሳሰሉት መፈክሮቻችን
ተራ አመጸኞች አለመሆናችንን መመልከት ትችላላ
ችሁ!» በማለት ተናገረ ፡፡

ፓቬል ሳቅ እንደማለት አለ ፡፡ ከዚያም ቀስ ብሎ
ፀጉሩን በጣቶቹ ያሻሽ ጀመር ፡፡ ሰማያዊ ዐይኖቹ ብሩ
ኅ በሆነ ፍልቅልቅታ ከምን ግዜውም ይበልጥ ጉ
ልህ ሁነው አበሩ ፡፡

«ወደ ዋናው ቁም-ነገር ግባ ብዬሀለሁኝ» በማለት
ሽማግሌው ዳኛ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚሰማ
ሁኔታ ተናገሩ ፡፡ ፓቬልን ለመመልከት ዞር አሉ ፡፡ ከሽ
ማግሌው የግራ ዐይን አስጠሊታ የሆነ የተንኮለኛ እ
ና የስግብግብ አመለካከት የሚታይባቸው መስሎ ለእ
ናት ታያት ፡፡ ሁሉም ዳኞች ልጅዋን በመመልከት ዐይ
ናቸውን ፊቱ ላይ ትክ አድርገው ያስተውላሉ ፡፡ በድ
ካም የዛለ አካላቸውን ያበረታ-ያንቀሳቅስላቸው ይመስ
ል ደሙን ለመጠጣት ጉልበቱን አሟጥጠው ለመቅሰ
ም ተጣድፈው በመመልከት ሁኔታ ያስተውሉታል ፡፡
እርሱ ግን ወይ ፍንክች! ደርቶ-ኮርቶ ቀጥ ብሎ ቆሞ
አል ፡፡ በጥንካሬ እና በጉብዝና እጁን ከፍ አድርጎ በመ
ዘርጋት እያመለከተ ፡ —

«እኛ ሬቮሉሺናውያን ነን ፡፡ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚ
ኖሩት አንዳንዶቹ ሰዎች ማዘዝን እንጂ እነርሱ ራሳ
ቸው አንዳችም ተግባር የማይፈጽሙ እስከሆኑ ድረስ ፣
ሌሎቹ ደግሞ ሌላ ሳይሆን ምን ግዜም ሠራተኞች
ሁነው እስከቀሩ ድረስ ሬቮሉሺናዊ በመሆን ተግባራ
ችንን ከማከናወን ወደኋላ አናፈገፍግም ፡፡ በእናንተ የፍ



ርድ ግምት ሙሉ ጠቀሜታው ተጠብቆ መቆየት አለ
በት ብላችሁ የምትገምቱትን ኅብረተሰብ እኛ እንቃ
ወማለን ፡፡ እኛ ከዚህ ኅብረተሰብ ጋር እንደዚሁም ከእ
ናንተም ጋር ጭምር እንደ ገበያ ዕቃ የውጣ-ውረድ
ስምምነት የማናደርግ እና ማደግደግም የማናውቅ
ጸበኞች ነን ፡፡ የመጨረሻ ትግላችንን ታግለን ድልን
እስካልተቀዳጀን ድረስ ፤ በመካከላችን አንዳችም እርቅ
ሊወርድ አይችልም ፡፡ እኛ ወዝ-አደሮች ድልን እንደ
ምንቀዳጅ ደግሞ እርግጠኞች ነን! ገዢዎቻችሁ እን
ደሚገምቱት ይኸንን ያህል ጠንካሮች አይደሉም! እየ
ሰበሰቡ ለማከማቸት በመቋመጥ በሥራቸው ያሉትን
አያሌ ሚሊዮን ሕዝቦች መስዋዕት አድርገው የሚያቀ
ርቡለት ያ የግል ሀብት ይዞታ ፤ በእኛ ላይ የበላይ
ነትን እንዲቀዳጁ የሚያደርጋቸው ያ ኃይል እራሱ ፤
በመካከላቸው አለመግባባት እና መበጣበጥ እንዲፈ
ጠር አድርጎ በአካልም ሆነ በሥነ-ምግባር ድምጥማጣ
ቸው እንዲጠፋ ያደርጋቸዋል ፡፡ የግል ሀብት ይዞታን
እንደነበረ ተንከባክቦ ለማቆየት የሚከፈለው ክፍያ
እጅግ ከፍተኛ ነው ፡፡ እንደ ዕውነቱ ከሆነ ደግሞ ፤ የእኛ
ጌቶች የሆናችሁት እናንተ ሁላችሁም በሙሉ ከእኛ
ይልቅ እናንተ እንደ ባሮች ማለት ናችሁ ፡፡ በላያችሁ
ላይ የመንፈስ ባርነት አድሮባችኋል ፡፡ እኛ ግን ሥጋ
ዊ ባርነት ብቻ ነው ያለብን ፡፡ መንፈሳችሁን አኮላሽቶ
የገደለውን አጉል ልምድ እና አጉል አመለካከትን ከላ
ያችሁ ላይ አሽቀንጥራችሁ ማስወገድ አትችሉም ፡፡
የእኛ መንፈስ ነፃ እንዳይሆን እኛን የሚያግደን አን
ዳችም ኃይል የለም ፡፡ ወዳችሁ ሳይሆን የግድ ሁኖ
ባችሁ አዕምሮአችን ውስጥ ከምታጠጡን የመርዝ
ማርከሻ ይልቅ የምትግቱን መርዝ ደካማ ነው ፡፡ ዕውነ
ትን የሚመራመረው ዕውቀታችን ከጊዜ ጊዜ እያደገ
የሚገሰግስ ሲሆን ፤ ምርጥ የሆኑ ሰዎችንም ወገናቹ

እንዲሆኑ በመሳብ እየማረካቸው ነው ። ከእናንተው
አካባቢ እንኳን ሳይቀር የመንፈስ ጥራት ያላቸውን
በሙሉ እየሳባቸው ነው ። እስኪ ልብ ብላችሁ አስ
ተውሉት — የእናንተን መደብ መመርያዎች አስከብሮ
ሊከራከርላችሁ የሚችል አንድም እንኳን አይገኝም ። የ
ታሪክ ፍትህ ፍርዱን አሳርፎባችው ድምጥማጣ የመርዝ
ማርከሻ ይልቅ የምትግቱን መርዝ ደካማ ነው ። ዕ
ውነትን የሚመራመረው ዕውቀታችን ከጊዜ-ጊዜ እያ
ደገ የሚገሰግስ ሲሆን ፤ ምርጥ የሆኑ ሰዎችንም ወገ
ኖቹ እንደሆኑ በመሳብ እየማረካቸው ነው ። ከእናን
ተው አካባቢ እንኳን ሳይቀር የመንፈስ ጥራት ያላቻ
ውን በሙሉ እየሳባቸው ነው ። እስኪ ልብ ብላችሁ
አስተውሉት — የእናንተን መደብ መመርያዎች አስከብ
ሮ ሊከራከርላችሁ የሚችል አንድም እንኳን አይ
ገኝም ። የታሪክ ፍትህ ፍርዱን አሳድሮባችሁ ድምጥ
ማጣችሁን ከማጥፋት ለመዳን እንድትችሉ የምታቀ
ርቧቸው ምክንያቶቻችሁ በሙሉ ሙጥጥ ብለው አል
ቀዋል ። አዳዲስ ሃሣቦችን ለመፍጠር ችሎታ ያላችሁ
አይደላችሁም ። መንፈሳችሁ ባዶ እና ነው ። የእኛ አስተ
ሳሰቦች ታዳጊዎች ናቸው ። ኃይል እያበጁ የሚዘልቁ
ናቸው ። ሰፊ ሕዝቦችን የሚያነቃቃቸው ከመሆኑም
በስተቀር ለነፃነታቸው እንዲታገሉ በአንድነት ያከማ
ቻቸዋል ። በወዝ-አደሩ መደብ ስለሚከናወነው ታላቅ
ሚና የሚኖር ዕውቀት የመላውን ዓለም ወዝ-አደሮች
ወደአንድ የማይበገር ታላቅ ኃይልነት አጣጥሞ የሚ
ያዋህድ ሰሆን ፤ ጭካኔን እና ፌዝን ካልሆነ በስተቀር
እነርሱ የሚያስገኙትን ሃሜት እና ደስታ የምታግዱ
በት ከቶ ምንም ቢሆን አንዳችም ኃይል የላችሁም ።
ይሁን እንጂ ፌዝ እና ልግጫ ግልጥ የሆነ ድርጊት
ሲሆን ጭካኔም አስቀጪ ነው ። ዛሬ የእኛን ማንቁ
ርት ለማነቅ በእኛ ላይ የተቃጡት እጆች ነገ በጓ



ድነት መንፈስ የእኛን እጅ በመጨበጥ ይታጠፋሉ ።
እናንተ ያላችሁ ኃይል የወርቅን ክምችት የሚያበረ
ክት ሜካኒካዊ ኃይል ነው ። እርስ-በእርስ በየቡድን-
በየቡድን ከፋፍሎአችሁ አንዱ ሌላውን ለመዋጥ የሚ
ንሰፈሰፍ ስግብግብ እንድትሆኑ ያደርጋችኋል ። የእኛ
ኃይል እና ጉልበት የተመሠረተው ከጊዜ-ጊዜ ን
ቃተ-ኅሊናቸው እየጨመረ በሚሄደው የመላው ዓለም
ሠርቶ-አደር ሕዝቦች ኅብረት እና ወንድማማችነት
ላይ የተመሠረተ ነው ። እናንተ የምትፈጽሟቸው ተግባ
ሮች ሁሉ ሕዝቦችን ወደ ባርነት የሚለውጥ በመሆኑ
አድራጎቶቻችሁ ሁሉ የወንጀለኛ አድራጎቶች ናቸው ።
ቅጥፈታችሁ ፤ ስግብግብነታችሁ ፤ ደካማነታችሁ እርኩስ
መንፈስ ያላቸው ጨካኝ ፍጥረቶችን እና የሰው ጭ
ራቆችን በመፍጠር ሕዝቦችን እንዲያስበረግግ አድር
ጎአል ። ሕዝቦችን ከእነዚህ የሰው ጭራቆች አላቅቆ
ነፃ ማውጣት ተግባራችን ነው ። የሰውን ልጅ ከሕይ
ወት አለያይታችሁ በመገነጣጠል ድራሹን አጥፍታች
ሁታል ። እናንት የበከላችኋትን ዓለም ሶሻሊዝም ነጥቆ
በመውሰድ እንደገና አድሶ ወደ አንድ ውሁድ የሆነ
ታላቅ ሙሉነት ይቀይራታል ። የፈለጋችሁትን ያህል
ብትጥሩም ይኸንን ከማድረግ የሚገታ አንዳችም ኃይ
ል የላችሁም!» አለ።

ፓቬል ትንሽ ዝም አለ ። ከዚያም ፡ —

«ይኸን ከማድረግ የሚገታ አንዳችም ኃይል የላች
ሁም!» በማለት እንደገና ደግሞ ተናገረ ።

ዳኞቹ ዐይኖቻቸውን ከፓቬል ላይ ሳይነቅሉና
እርስ በእርሳቸው በመንሾኳሾክ ፊታቸውን ቀፍፎአ
ቸው በጥላቻ አኩሳተሩ ። እናት ጤናማ የሆነውን ፤ ጠን
ካራ እና ንጹህ የሆነውን የልጇዋን አካል አንጉል
በሆነ አመለካከታቸው የሚበክሉባት መስሎአት ተሰ
ማት ። እሥረኞች ፊታቸው ኮስተር ብሎ ፤ ዐይኖቻቸው

በደስታ ፈክተው ጓደኞቸው ያሰማውን ንግግር በጥሞና ሆነው አዳመጡ ። እናት ልጅዋ ያሰማውን ንግግር እያጣጣመች የተጋተችው ስትሆን ከልቧ ውስጥ ሊፋቅ በማይችል ሁኔታ ተቀረጸ ። አንዳንድ ነገሮችን ገሀድ ለማድረግ ሽማግሌው ዳኛ ፓቬልን ከንግግሩ ብዙ ጊዜ ያቋርጠው የነበረ ሲሆን ፤ እንዲሁም አንድ ጊዜ ሀዘን በተመላው ሁኔታ ፈገግ ብሎ ነበር ። ዳኛው ባቋረጠው ቁጥር ፓቬል ንግግሩን የሚያቆም ሲሆን ፤ የዳኛውን ፍላጎት በራሱ ፍላጎት ድል ነስቶ በተረጋጋ መንፈስ የአድማጮቹን ስሜት እየማረከ ንግግሩን ይቀጥላል ። መጨረሻ ላይ ግን ሽማግሌው ዳኛ ድምፁን ከፍ አድርጎ በመጮህ እጁን ዘረጋ ። ከዚያም የፓቬል ድምፅ በምፀት አነጋገር ለወጥ በማለት ፡ —

«ንግግሬን ወደ መጨረሱ ገደማ ነኝ ። እርስዎን በግል ላስቀይምዎ አልሻም ። እንደውም በተገላቢጦሽ ፤ እናንተ የፍርድ አፈጻጸም ብላችሁ የምትጠቅሱትን ይኸንን ቅጥፈት እዚህ ቆም ብዬ ሳስተውል ከእናንተ ጋር አብሬ የሀዘናችሁ ተካፋያችሁ ለመሆን ምንም አይቀረኝ ። ምንም ቢሆን እናንተም ሰብዓውያን ፍጡሮች ናችሁ ። እና ደግሞ ፤ ምንም እንኳን እኛ የቆምንለትን ዓለማ የምትቃወሙ ብትሆኑም ጨካኝ ለሆነ አገዛዝ እንደዚህ ከሰብአዊ ክብራችሁ ዝቅ ብላችሁ በመውረድ ተዋርዳችሁ ሰብአዊው ክብራችሁ ተገፍፎ ስመለከት ሁልግዜም ያሳዝነኛል...» አለ ።

ዳኞቹን ሳይመለከት ወደ መቀመጫው ሂዶ ተቀመጠ ። እናት ግን ትንፋሿን ቁርጥ-ቁርጥ እያደረገች ዳኞቹን ትመለከት ጀመር ።

አንድሬይ የፓቬልን እጅ ጥብቅ አድርጎ ሲጫን ፊቱ በደስታ ብሩህ ሁኖ አብርቶአል ። ሳሞይሎቭ ፥ ማዚን እና ሌሎቹም ፓቬልን በማድነቅ ወደ እርሱ



ጎንበስ ብለው ሲያዩት እነርሱ ለእርሱ ባሳዩት የመደነቅ ሁኔታ ቅር በመሰኘት መንፈስ ፈገግ አለ ። ወደ እናቱ ዘንድ መልከት እንደማለት ብሎ ፡ —

«ረካሽን?» በሚል ሁኔታ ጭንቅላቱን ባሻገር ከተቀመጠበት ነቅነቅ አደረገላት ።

የደስታ ትንፋሿን እየተነፈሰች እርሷም መልኳ በደስታ ብሩህ ሁኖ ፈክቶ ጭንቅላቷን አዎን በሚል ሁኔታ ነቅነቅ አደረገችለት ።

«ዕውነተኛው ፍርድ የጀመረው አሁን ነው! ግልጥ-ግልጥልጥ አድርጎ ነው ሃሣቡን ያስቀመጠው! አይደለም?» በማለት ሲዞቭ ቀስ ብሎ ተናገረ ።

ልጅዋ እንደዚህ መንፈሰ ጠንካራ በሆነ ሁኔታ ንግግሩን በማሰማቱ ተደስታ — ምናልባትም ደግሞ ንግግሩን በማብቃቱም ጭምር ተደስታ እንዳችም ድምፅ ሳታሰማ ራሷን በማነቃነቅ ሲዞቭ ላቀረበው ጥያቄ መልስ ሰጠች ። ይሁን እንጂ ፤ አንድ ጥያቄ አዕምሮዋ ውስጥ አሁንም የሚንገዋለል ሲሆን ፤ እርሱም ፡ —

«አሁን እንግዲህ ዳኞቹ ምን ሊያደርጉ ይሆን?» የሚለው ሃሣቧ ነው ።

## 26

ልጅዋ የተናገረው ለእርሷ አዲስ የሆነ ነገር አልነበረም ። አስተሳሰቡን በሙሉ ተላምዳዋለች ። ይሁን እንጂ ፤ እዚህ ፍርድ ቤት ውስጥ ዕምነቱ ያለው የመሳብ ኃይል እስከምን ድረስ እንደሆነ ለመጀመርያ ጊዜ ልትገነዘብ በቃች ። በፓቬል ጠቅላላ አቀራረብ የተደነቀች ስትሆን ያሰማው ንግግርም የቆመለትን ዓላማ ጽናቱን እና የኋላ-ኋላ ድል አድራጊነቱንም ምን ያህል እንደሚያምንበት እንደሚያሳይ እንደ አንድ እንደሚያንፀባርቅ ኮከብ ቀጠረችው ። ዳኞቹ አሁን

በቁጣ ተውጠው ያቀረባቸውን ሃሣቦች ውድቅ እያደረጉ እና የራሳቸውን ዕምነት እያቀረቡ ከእርሱ ጋር በሞቀ ክርክር ውስጥ ይገባሉ ብላ ገመተች ። ይሁን እንጂ ፤ ተቀምጦ ከነበረበት ቦታ እንድሬይ ብድግ ብሎ ቆመ ። ዳኞቹን በግንባሩ ሥር ቃኘት አደረጋቸው እና ፡ —

«የተከበራችሁ ጠበቆች...» ብሎ መናገር ሲጀምር የጃጁት ዳኛ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በተበሳጨ ሁኔታ ፡ —

«ከፊት-ለፊትህ የሚገኙት ዳኞች እንጂ ጠበቆች አይደሉም!» አለው ። እናት እንድሬይ መልክ ላይ አንድ ወርበላ በመሆን የበጥባጭነት ሁኔታ እንደከጀለው አይታበታለች ። ሪዙ የሚንቀጠቀጥ ሲሆን የዐይኖቹ ሁኔታም ቀደም ሲል የለመደችውን የብልኅ ድሙት አመለካከት ይታይበታል ። ረዥም በሆነው ቀጭን እጁ ራሱን በኃይል ካከከ በኋላ ትንሽ ተንፈስ ብሎ ፡ —

«ኧረ እባክዎን? ጠበቆች አይደላችሁም እንዴ? እኔ ደግሞ እኮ እናንተ ዳኞች ሳትሆኑ ጠበቆች መሰላችሁኝ ነው...» በማለት ራሱን በመሳሳቱ ያዘነ አስመስሎ በምጸት እየነቀነቀ ተናገረ ።

«ወደምትናገረው ነጥብ ቀጥ ብለህ ዝለቅ ብዬሃለሁኝ!» በማለት ሽማግሌው ዳኛ ድርቅ ባለ አነጋገር ተናገሩ ።

«ወደ ዋናው ነጥብ በቀጥታ ልዝለቅ እንዴ? እሺ! ለምሳሌ እናንተ ክብራችሁን ጠብቃችሁ የምትገኙ እና ሙሉ ነፃነት ያላችሁ ዕውነተኛ ዳኞች ናችሁ ብሎ ራሴ በገዛ ራሱ እንዲያምን አደረግሁት ብዬ ልገምት...» ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ ፡ —

«ፍርድ ቤቱ ስለእኛ አስተያየት እንድትሰጥ አልጠየቀኽም!» በማለት ዳኛው ንግግሩን አቋረጡት ።



«ኧረ? እሺ ። ብቻ ባይሰጠኝም አስተያየቴን እኔ እሰጣለሁኝ ። እና እንግዲህ እናንተ 'የእኔ' እና 'የእንተ' ብላችሁ አንዳችም ነገር ላይ ቢሆን ልዩነት የማታደርጉ አድልዎ የማታውቁ ሚዛናዊ የሆናችሁ ሰዎች ናችሁ እንበል ። ከፊት-ለፊታችሁ ሁለት ሰዎች ቀርበውላችኋል ። ከሁለቱ ሰዎች መካከል አንዱ ሌላኛውን ሰው ዘረፈኝ ፤ ቅጥቅጥ ድቅቅ አድርጎ ደበደበኝ በማለት ከሰሰው እንበል ። ሌላኛው ደግሞ መግረፊያ ጅራፍ ያለኝ በመሆኔ ሰውን ለመዝረፍም ሆነ ቅጥቅጥ ድቅቅ አድርጌ ለመደብደብ መብት አለኝ ብሎ ተናገረ እንበል...» ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ ሽማግሌው ዳኛ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በማሰማት ፡ —

«ለተነሳህበት ጉዳይ የምታቀርበው ነጥብ የለህምን?» በማለት በቁጣ ቃል ተናገሩ ። እጆቹ ይንቀጠቀጣሉ ። ምን ያሕል ቁጡ መሆኑን በማየት እናት ደስ ተሰኘች ። ይሁን እንጂ እንድሬይ የሚያሳየው ጠባይ ደስ አላላትም ። ልጅዋ ካሰማው ንግግር ጋር ስምም ሁኖ የሚገጥም አቀራረብ አልነበረም ። የሚያቀርቡት ክርክር ቁም-ነገር የተመላበት እና ተደማጭ እንዲሆን ትሻለች ።

ኾኾል ንግግሩን ከመቀጠሉ በፊት ፀጥ ብሎ ሽማግሌውን ዳኛ አስተዋለው ። ከዚያም ፡ —

«ወደ ዋናው ነጥብ ልመለስ?» አለ ቀዝቀዝ ባለ ሁኔታ ግንባሩን እያሻሸ ። ከዚያም ቀጠል አደረገ እና ፡ —

«አሁን እኔን ከእርስዎ ጋር ወደ ዋናው ነጥብ የሚመልሰኝ ምን ምክንያት አለኝ? አሁን ለጊዜው ማወቅ የሚገባዎትን አንድም ሳያስቀር ጓዴ ዘርዝሮ አስረድቶዎታል ። ጊዜው ሲደርስ ደግሞ ሌሎቹ ጓዶቼ ያስረዱዎታል...» አለው ።

ሽማግሌው ዳኛ ከተቀመጠበት ተነሳ እና ፡ —

«ቁጭ በል ብዬሃለሁኝ!»በማለት እንድሬይ ላይ ጮኸበት ። ከዚያም ፡ —

«ተረኛ ተናጋሪ — ግሪጎሪ ሳሞይሎቭ!» በማለት እየ ተበሳጨ ተጣሩ ።

ኾኾል ከናፍሮቹን ሞጥሞጥ አድርጎ እያጠጋጋ ሳይቻኩል ቀስ ብሎ ተቀመጠ ። ሳሞይሎቭ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ተነሳ እና ድምድም ፀጉሩን እያካከከ ኾኾል አጠገብ ቆመ ።

«ዐቃቢ-ሕግ የእኔን ጓዶች ደንቆሮዎች ፤ የባሕል እንቅፋቶች ናችሁ እያለ በመስደብ...» ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ ።

«አሁን አንተን ስለሌሎቹ የሚያገባህ ጉዳይ የለም! አንተ የተከሰስክበትን የሚመለከት ጉዳይ ብቻ ተናገር!» አለው ዳኛው ።

«ይኼ እኔ የተከሰስኩበትን ጉዳይ የሚመለከት ነው ። ሀቀኛ ሰዎችን የማይመለከታቸው አንዳችም ጉዳይ የለም ። እና ደግሞ ፤ እባክዎን ንግግሬን አያቋርጡኝ ። እርስዎን ልጠይቅዎት የምሻው ፤ ለመሆኑ ባሕል ማለት ምን ማለት ነው?» አለው ዳኛውን ።

«አሁን እኛ እዚህ የተሰየምነው ከአንተ ጋር ለመከራከር አይደለም! ወደ ዋናው ነገር ግባ!» አለው ሽማግሌው ዳኛ ጥርሳቸውን ብልጥጥ አድርገው በመገልፈጥ ።

የአንድሬይ ሁኔታ በዳኞቹ ላይ የመለወጥ ስሜት አስከተለባቸው ። እርሱ የሠነዘራቸው ቃላት ከላያቸው ላይ ቀልቦቻቸውን ገፍፎ አነሳባቸው ። ቡናማ የነበሩት መልኮቻቸው አመድ ለበሱ ። ዐይኖቻቸው ቀዝቃዛ አረንጓዴ ውሀ አዘሉ ። ፓቬል ባሰማው ንግግር ተበሳጭተው ነበር ። የንግግሩ ኃይለ ቃል እርሱን እንዲያከብሩት እና ራሳቸውንም ተቆጣጥረው ጭጭ እንዲሉ አስገድዶአቸው ነበር ። ኾኾል ያቀረበው ንግግር ግን ውስጥ አካላቸው ድረስ ጠልቆ በመግባት ቀልባቸውን ገፍፎ እርቃናቸውን ተጋልጠው እንዲቀሩ አደረጋቸው ። ለእነርሱ ኃይለኛ በሆነ ሁኔታ ፊቶቻቸውን በጥላቻ በማኮሳተር እና ሰውነቶቻቸውንም ከወዲያ-ወዲህ በማቁነጥነጥ እርስ-በእርሳቸው ይንሾካሾኩ ጀመር ።

«ሰዎችን ሰላዮች እንዲሆኑ ታሰለጥኗቸዋላችሁ ። ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ታባልጋላችሁ ። ሰዎች ቀማኞች እና ነፍሰ-ገዳዮች እንዲሆኑ ታደርጋላችሁ ። በቮድካ መጠጥ ፤ በዓለም-አቀፍ ጦርነቶች ፤ በቅጥፈት ፤ ወራዳ በሆነ ግብረ-ገብነት እና በደንቆሮነት ትመርዛላችሁ ። እንግዲህ የእናንተ ባሕል ማለት ይኸው ነው! እኛ ይህንን ለመሰለው ባሕል ጠላቶች ነን!» በማለት ሳሞይሎቭ ተናገረ ።

«ጓላ ልብ አድርግ ነው የምልህ!...» በማለት ሽማግሌው ዳኛ በጩኸት ተናገሩ ። ፊቱ ቀይ የሆነው እና ዐይኖቹ ብሩህ ሁነው የሚያንጸባርቁት ሳሞይሎቭ ግን መልሶ በመጮህ ፡ —

«እዚያው በሰብሰው እንዲቀሩ ፤ ወይንም እብድ እንዲሆኑ እሥር ቤት የምትወረውሩአቸውን የሌሎቹን ሰዎች ባሕል እናከብረዋለን ። የማዕርግ ቦታም እንሰጠዋለን» በማለት ሳሞይሎቭ ንግግሩን ቀጠለ ። ይሁን እንጂ ዳኛው ፡ —

«ቁጭ በል! ተረኛ ተናጋሪ — ፌዎዶር ማዚን!» በማለት በቁጣ ተጣራ ።

እንደ ወስፌ ቀጥ ያለው ቀጭን ቁመተ-ትንሹ ማዚን ከተቀመጠበት ፈንጠር ብሎ ተነሳ ። ከዚያም ፡ —

«እኔ... እኔ እየማልኩ ነው የምነግራችሁ! እናንተ በእኔ ላይ ከፈረዳችሁብኝ ቆይቶአል!» አለ ። ከዚያም ትንሽ ዝም ብሎ ትንፋሹን ዋጥ አደረገ ። ኩስትርትር ከማለቱ የተነሳ ዐይኖቹ ብቻ ናቸው የሚታዩት ።

ከዚያም እጁን እያወዛወዘ ፡ —

«እኔ ፤ የዕውነቱን ነው የምምልላችሁ! የፈለጋችሁበት ቦታ ብታደርሱኝ ሕይወቴ እስከአለች ድረስ ሥራዬን መሥራቴን ከቶ ምንም ቢሆን አላቆምም ። ዕውነቱን ነው የምምል!» በማለት የሚምል ይመስል አንድ እጁን ብድግ አድርጎ አነሳ ።

ሲዞቭ ጎላ ባለ ድምፅ ጉሮሮውን እ-ኽ-ኽ በሚል ሁኔታ ጠረግ አድርጎ እዚያው እተቀመጠበት ቆነጥነጥ አለ ። ፍርድ ቤቱ ውስጥ የተሰበሰቡት ሰዎች አደገኛ በሆነ ሁኔታ ያጉረመርሙ ጀመር ። አንዲት ሴት እየተንሰቀሰቀች አለቀሰች ። አንድ ሌላ ሰው አጠር ላለ ጊዜ ሳሉን ይስል ጀመር ። ዣንዳርሞቹ ቅፍፍ ብሎአቸው እየተደነቁ እሥረኞቹን እና የተበሳጨውን ሰው ተኩረው ይመለከቱ ጀመር ። ዳኞች ከወዲያ-ወዲህ ይቁነጠነጣሉ ።

«ተረኛ ተናጋሪ — ኢቫን ጉሴቭ!» በማለት ዳኛው ጮኸው ተናገሩ ።

«እኔ አንዳችም ነገር መናገር አልሻም!» አለ ።

«ተረኛ ተናጋሪ — ቫሲሊይ ጉሴቭ!» አለ ዳኛው ።

«እኔም መናገር አልሻም!» አለ ።

«ፌዎዶር ቡኪን!» አለ ዳኛው ።

የፊቱ ቀለም ከላዩ ላይ እየለቀቀ ነጭማ መልክ የቀረው ከበድበድ ያለው ሰው ከተቀመጠበት ቀስ ብሎ ተነሳ ።

«ስለራሳችሁ ትንሽም ቢሆን ሃፍረት ይሰማችሁ ዘንድ በተገባችሁ ነበር!» በማለት ስለዳኞቹ ሁኔታ እየተገረመ ራሱን በመነቅነቅ መናገር ጀመረ ። ከዚያም ቀጠል አድርጎ ፡ —

«እኔ ብዙም ትምህርት የተማርኩኝ ሰው አይደለሁኝም ። ይሁን እንጂ ፤ ፍትህ ምን እንደሆነች አውቃለሁኝ» አለ ። ከዚያም እጁን ከጭንቅላቱ በላይ ከፍ



አድርጎ ፤ ዐይኖቹን ግማሽ-በግማሽ ዘግቶ ባሻገር እንዳች ነገር ይመለከት ይመስል ለጊዜው ዝም አለ ።

«ምንድነው? ምን መሆንህ ነው?» አሉት ሽማግሌው ዳኛ ወንበሩ ላይ ወደኋላ ደገፍ ብለው በመደነቅ እና በመበሳጨት እየተመለከቱት ።

«ገሀነም ይግቡ!» በማለት ቡኪን መለሰላቸው ።

ቡኪን ፊቱ አኩርፎ ቀድሞ ወደነበረበት ቦታ ተመልሶ ተቀመጠ ። እነዚህ የሠነዘራቸው ቃላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ሃሣቦችን የያዙ ፤ የዋህ የሆኑ ፤ ዘለፋ እና ወቀሳ በውስጣቸው ያቀፉ ቃላት ነበሩ ። በቦታው የነበሩት ሰዎች አንዳቸውም እንኳን ሳይቀሩ ይኸንን ተገንዝበውታል ። የቀረው ቀርቶ ዳኞቹ እንኳን ቡኪን ከተናገረው ይበልጥ ግልጥ በሆነ ሁኔታ ቃሉን እንደገና የገደል ማሚቶ ደግሞ የሚያሰማቸው መስሎአቸው ጆሮዎቻቸውን አሾጥጠው ቀሥረው እንደገና ለማዳመጥ ይጠባበቁ ነበር ። ክፍሉ ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ ። ይኸ ፀጥታም ስቅስቅ በማለት በሚለቀስ ዋይታ ደፈረሰ ። መጨረሻ ላይም ዐቃቤ ሕጉ ትከሻውን ወዝወዝ እያደረገ ፈገግ ይል ጀመር ። የመኳንንቱ ተጠሪ ሳሉን መሳል የጀመረ ሲሆን በቦታው ላይ የተገኙት ሰዎችም ቀስ እያሉ ማውራት ቀጠሉ ።

«ዳኛው ይናገር ይሆን?» በማለት እናት ሲዞቭን ቀስ ብላ ጠየቀችው ።

«የፍርዱን ቃል ከማሰማት በስተቀር ሁሉም ነገር አብቅቶአል...» በማለት መለሰላት ።

«ሁሉም ነገር?» አለችው ።

«አዎን ፤ ሁሉም ነገር...» አላት ።

ማመን አልቻለችም ።

የሳሞይሎቭ እናት አግዳሚው ወንበር ላይ ከወዲያ-ወዲህ እየተቁነጠነጠች እናትን በትከሻዋም በጉልበቷም ትጎንጣታለች ።

«ምንድነው ነገሩ? አበቃ እንዴ? ገና ነው ፤ አይደል እንዴ?» በማለት ባለቤቷን ጠየቀችው ።

«አብቅቶአል ። ቆይ አሁን ትመለከቻለሽ!» አላት ።

«በእኛ ልጅ በግሪሻ ላይ ምን ሊፈርዱበት ይሆን?» አለችው ።

«ዝም በይ!» አላት ።

ስለ ሥነ-ሥርዓት መቃወስ ፣ ስለሕግ መፍረስ ፣ ስለአንዳች የተቃወሰ ነገር መኖር ሁሉም ያውቃል ። መውጫው ገና ያልታወቀ ፤ ጠቀሜታው ከፍተኛ የሆነ ፤ ኃይሉን ግን ሊቋቋሙት የማይቻል አንዳች ነገር የተቃጠለ መስሎ ተሰማቸው ። ወዲያውኑ ግልጽ ሁኖ ሊገነዘቡት የቻሉትን ነገር ለጊዜው ሊረዱት ባለመቻላቸው ምክንያት ጥቃቅን የሆኑ እና ሊገነዘቡዋቸው የሚችሉዋቸው ጉዳዮች ላይ በቦታው የተሰበሰቡት ሰዎች ያተኩሩ ጀመር ። ታላቅየው ወንድም ቡኪን አንዳችም ሃፍረት ሳይሰማው ጎላ ባለ ድምፅ ፡ —

«እኔ የምለው ፤ ለምን እንዲናገሩ አይፈቅዱላቸውም? ዐቃቤ-ሕጉም የፈለገውን ነገር ያሻውን ያህል ይናገር» በማለት ተናገረ ።

አንድ ባለሥልጣን ወንበሮቹ አጠገብ ቁሞ ፡ —

«ፀጥታ! ፀጥታ!» እያለ ተናገረ ።

ሳሞይሎቭ ከሚስቱ ጀርባ ፊታ ብሎ ወደኋላው በመንጠራራት ቁርጥርጥ ባሉ ቃላት ፡ —

«እሺ ፤ ይሁን ግዴለም ። ጥፋተኞችም ናቸው ይባሉ ። ግን ሃሣባቸውን እንዲያስረዱ ለምን አይፈቀድላቸውም! ማንን ተቃወሙ? እኔ ለማወቅ የምሻው ይኸንን ነው! እኔም ብሆን የራሴ ፍላጎት በልቤ ውስጥ ይገኛል…» ብሎ ሳይጨርስ ፤ ባለሥልጣኑ ጣቱን ሳሞይሎቭ ላይ በመቀሰር እያወዛወዘ ፡ —

«እ-ሽ-ሽ!» በማለት ዝም እንዲል አስጠነቀቀው ።

ሲዞቭ ሀዘን በተመላው ሁኔታ ራሱን ነቀነቀ ።



እናት ዳኞቹን ትኩር ብላ የምትመለከታቸው ስትሆን እንድነት ሁነው ዳኞቹ ሲወያዩ ስሜታቸው ክፍክፍ በማለት ሲግል አስተዋለች ። ቀዝቃዛ እና ውልክፍክፍ የሆነ ድምፃቸው ፊቷ ድረስ ደርሶ እየነካካት ጉንጮቿን ይህን መሳዩ የድምፃቸው ቅዝቃዜ ያንቀጠቀጠባት ሲሆን አፏ ላይም ጣዕሙ መራር የሆነ እሬት የነሰነሰባት መስሎ ተሰማት ። አንዳች በሆነ ምክንያት እነዚህ ዳኞች በመወያየት ላይ ያሉት ስለ ልጅዋ እና ስለ ጓዶቹ ሰውነት መስሎ ተሰማት ። ትኩስ በሆነ ደም እና ብርታት ስለተመሉት ገና ወጣት ስለሆኑት የአካሎቻቸው መለያልዮች እና ጡንቻዎች ጉዳይ የሚወያዩ መስሎ ተሰማት ። እነዚህን መሳይ አካላት ሊያዩዋቸው የሚፀየፉዋቸውን ድሆች ፤ የሕመምተኞችን እና እልቅ-ድቅቅ ያሉ መውደቂያ-ቢሶች ሰዎችን ሰፍሳፋነት ለእነዚህ ዳኞች ያስታውሳቸዋል ። ሠራተኛ እና አበልጻጊ የሆኑትን ፤ ደስታን የሚፈጥሩትን እና የሚያውቁትን እነዚህን አካላት ሽፈኗቸው ። ክናፍሮቻቸውን አሸጉዋቸው ። አሁን እነዚህ አካላት ከዕለት በዕለት ተግባሮቻቸው ሊገለሉ ነው ። እየተቃወሚቸው ነው ። እናም ሌሎችንም የአካላቱ አዛዦቻቸው ይሆኑ ዘንድ ፤ ጉልበታቸውን ይበዘብዙት ዘንድ ፤ ምጥጥ-ልጥልጥ ያደርጉዋቸው ዘንድ እንዳይችሉ እያገዱዋቸው ነው ። በዚህም ምክንያት ፤ ከፊት ለፊታቸው ትኩስ ምግብ ተንጣልሎ ተጋድሞላቸው አቅም በማጣታቸው ብቻ አፈፍ አድርገው ለመገሸለጥ እንደሚሳናቸው ውልቅልቃቸው ወጥቶ ያረጁ የዱር አራዊቶች እነዚህንም በበቀል እልህ ተውጠው ዋጥ-ስልቅጥ ለማድረግ እየቋመጡ የሚጠባበቁ ሽማግሌዎች ዳኞች አዕምሮ ውስጥ ይኸንን መሳይ ስሜት እንዲያድርባቸው እነዚህ ወጣቶች ፡ ይገፋፉዋቸው ጀመር ። የሚያስቋምጥ ምግብ እያዩት ሲያመልጣቸው እየጉረመ

ረሙ እና እየተጉመለመሉ ማጓራት እንጂ የሌሎችን ፍጥረታት ጥንካሬ እና አቅም መዝኖ ለማወቅ ችሎታ የጎደላቸው አራዊቶች ማለት ናቸው ።

ዳኞቹን ይበልጥ አተኩራ በመመልከት ስታጠናቸው ፤ ይኸንን መሳዩ እንግዳ የሆነ እና ጥሬ ሃሣብ በአዕምሮዋ ውስጥ እየተላወሰ ነፍስ ይዘራ ጀመር ። ድግስ ደግሶ በዓል ማድረግ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሚያውቅ እና ነገር ግን ደግሞ በረሀብ አለንጋ የሚገረፍ ሰውን እያዩ በስግብግብነታቸው ያላቸውን ላለመስጠት የሚሹ ንፉጎች መስለው ታዩዋት ። ነፍስ ከሚባለው ይልቅ የልጅዋን አካል እጅግ ውድ አድርጋ ለምትቆጥረው ሴቲትም እናትም ለሆነችው ለእርሷ ፤ የእነዚህ ዳኞች አሰልቺ አመለካከት በልጅዋ መልክ ላይ እንዲመላለሱበት ፤ ደረቱን ፤ ትከሻውን ፤ እጆቹን እንዲታኙባት ፤ ክፉ እና በጎ መለየት ያቃታቸውን የጃጁ የደም ሥሮቻቸውን እና በተኮመታተሩ ጅማቶቻቸው ውስጥ የረጉትን ደሞቻቸውን ያሞቅላቸው ይመስል ሕያው የሆነ አካሉን ሲያሻሹባት መመልከት እጅግ አሰቃቂ የሆነ ጉዳይ ነው ። አካላቸውን ለምንግዜም ገነጣጥሎ ለመለየት አሁን ሊያወግዙአቸው የተዘጋጁላቸውን እነዚህን ወጣቶች በመቋመጥ እና በበቀል ልብ ተዘጋጅተው በመጠባቅ ዳኞቹ ነቃ ብለዋል ። ይኸንን ርጥብ እና አስደሳች ያልሆነ ንክኪ. ፓቬል የተገነዘበው መስሎ ተሰማት ። እርሷንም በትክሻው እየተንቀጠቀጠ ተመለከታት ።

በአመለካከቱ ላይ የመድከም ምልክት እየታየበት ረጋ ብሎ እና ፍቅር በተመላበት ሁኔታ እርሷን-እርሷን ይመለከታታል ። አሁንም-አሁንም እርሷን-እርሷን እየተመለከተ ፈገግ ይላል ። የማቀፍ ያህል ከሚቆጠረው ከሳቁ ላይ የሚነበበው ፡ —

«ከቅርብ ጊዜ በኋላ ነፃ እወጣለሁ!» የሚል ይመስላታል ።



ልክ በዚህን ጊዜ ዳኞቹ ከተቀመጡበት ተነሱ ። እናትም ከተቀመጠችበት ተነሳች ።

«ይኸውልሽ መሄዳቸው ነው!» አለ ሲዞቭ ።

«በፍርዱ ላይ ለመምከር?» አለችው ።

«አዎን» አላት ።

የነበረችበት የጭንቀት ሁኔታ ድንገት ተባባሰ ። ከመዛሏ የተነሳ ራሷን የሳተች መሰላት ። ሽፋሽፍቶቿ የሚርገበገቡ ሲሆኑ ከግንባሯ ላይም ላብ እንደውሀ ይንቆረቆር ጀመር ። ልቧ ውስጥ የጉዳት እና የቅሬታ መንፈስ ገብቶ የተጫናት ሲሆን በፍርድ ቤቱ እና በዳኞቹ ላይም ፈጣን የሆነ ጥላቻ ወዲያውኑ እንድትመሠርት አደረጋት ። የራስ ምታት ራሷን የሚፈልጣት መሆኑን ስለተገነዘበችው ግንባሯን ያዝ ካደረገች በኋላ ወደላይ ቀና ብላ አስተዋለች ፡ — የእሥረኞቹ ቤተዘመዶች እሥረኞቹ ወደሚገኙበት የብረት አጥር ሂደው ክፍሉ በቻቻታ እና በውይይት ተመልቶአል ። እርሷም ወደፓቬል ዘንድ ከሄደች በኋላ ሃዘንም ደስታም ተቀላቅሎባት ፤ በሁለት ዓይነት ስሜቶች ተውጣ እጁን ያዝ አድርጋ ታለቅስ ጀመር ። ፓቬል ረጋ ባለ ሁኔታ የሚያወራት ሲሆን ፤ ኾኾል ደግሞ ይስቃል ፤ ይቀልዳል ።

ሴቶቹ በሙሉ ያለቅሳሉ ። ይሁን እንጂ ፤ ለቅሶአቸው ከሀዘን ብዛት ሳይሆን ከልምድ የተነሳ ነው ። ቀደም ሲል ያልተስተዋለ ፣ ያልታየ እና አስደንጋጭ የሆነ አዲስ ሀዘን አልነበረም ። ከየልጆቻቸው ጋር የሚለያዩ የመሆናቸው አሳዛኝ ሁኔታ ነበር ያለው ። ይኸም ሁኔታ እንኳን ቢሆን በዕለቱ በታየው ስሜት ሊቃለል ችሎአል ። አባቶች እና እናቶች ልጆቻቸውን ድብልቅ በሆኑ ስሜቶች ይመለከቷቸዋል ። ወጣቶችን የመጠራጠር እና ምንግዜም እነርሱ ራሳቸውን የበላይ አድርገው የመቁጠር ሁኔታ ከአክብሮት ጋር በተመ

ሳሳይነት ተቀያይጦ ይገኛል ። ከዚህ የተሻለ ሌላ አዲስ ኑሮ የሚመጣ መሆኑን ወጣቶቹ በጥንካሬ እና ያለአንዳች ፍርሃት በሚያሰሙአቸው ንግግሮች ከእንግዲህ ወዲህ የሚኖሩት ኑሮ እንዴት ያለ ኑሮ ይሆን የሚለው አሳዛኝ አስተሳሰብ በመደነቅ ድቅን ብሎ ወላጆችን አጅቦአቸዋል ። ሊገለጹ የማይችሉ በመሆናቸው ምክንያት ስሜቶች እንዳይወጡ ሁነው ወደውስጥ ተቀብረዋል ። ቃላት ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ሊኸሩን ደጎዱ ችለው የነበረው ልብሶችን ፣ ጽዳትን እና ጤናን የሚመለከቱ ጉዳዮችን አስመልክተው ነው ።

ታላቁ ቡኪን ታናሽ ወንድሙን ሲያነጋግረው እጆቹን ያወዛውዛል ።

«ዋናው ቁም ነገር ፍትሕ ነው! የተቀረው ሁሉ ከንቱ ነው!» አለው ።

«ዘፋኝ ወፌን አደራህን ፤ ጠብቅልኝ» አለው ታናሽ ወንድምየው ታላቁን ።

«እሺ ። ግዴለህም...» አለው ታላቁ ።

ሲዞቭ የወንድሙን ልጅ እጁን ጨብጦ ያዘው ። ከዚያም ፡ —

«እሺ ፤ ፌዎዶር ጥለኸን ልትሄድ ነው...» አለው ።

ፌዎዶር ፈገግ እያለ እየሳቀ ለሲዞቭ አንዳች ነገር በጆሮው እያንሾኳሾከ ነገረው ። ዘበኛውም ይስቅ ጀመር ። ይሁን እንጂ ፤ ወዲያውኑ ሳቁን ቻል አድርጎ ኮስተር በማለት ጉሮሮውን እ-ኸ-ኸ በማለት ይጠራርግ ጀመር ።

ሌሎቹ ሴቶች እንደሚያደርጉት ሁሉ እናትም ከልጅዋ ጋር ትነጋገር ነበር ። ስለልብስ እና ስለጤናው ጉዳይ ። ይሁን እንጂ ፤ ስለ ሳሻ ፣ ስለ እርሷ እና ስለ እርሱም ጭምር ብዙ-ብዙ ጥያቄዎችን ልትጠይቀው ፈለገች ። ግን ከዚሁ ሁሉ በላይ በልጅዋ ፍቅር ወሰን-የለሽ ጥያቄ ፤ እርሱን የሚያስደስትም ፍላጎት ፤ የእርሱ



ውድ አፍቃሪው የመሆን ፍላጎት አድሮባታል ። ወደፊት የሚመጣው አስፈሪ ሁኔታ እየተገለለ ሂዶአል ። ዳኞቹን በማስታወስ አስደሳች ያልሆነ ስሜትን በማሳደር እና የፍርዱንም ጭለማ ትውስት በማስታወስ ምልክቱን ትቶ አልፎአል ። እጅግ አስደሳች የሆነ ሁኔታ በመንፈሷ ውስጥ ተቀረጸ ። ምን እንደሆነ ሙሉ-በሙሉ ጠንቅቃ አልተገነዘበችውም ። እንደው ብቻ እንደአመጣጡ ተቀበለችው ። ኾኾል ከሰዎች ጋር ሲወያይ በመመልከቷ እና ከፓቬል የበለጠ የመውደድ ፍላጎት ያለው መሆኑን የምታውቅ በመሆኗ ፡ —

«በዚህ በእናንተ ፍርድ ብዙም አናስብም!» አለችው ።

«ወፍጮው አሮጌ ነው ። አሁንም ግን እየገረደፈ ይፈጫል...» በማለት መለሰላት ።

«ማንንም ሊያስፈራራ አልቻለም ። ይሁን እንጂ ፤ የተረዱት አንዳችም ነገር የላቸውም ። ማነው ትክክለኛው? ማንስ ነው ጥፋተኛው?» በማለት ንግግሯን ቆም እንደማድረግ ብላ ተናገረች ።

«አሃ! ይኸንን ነበር የፈለጉት ማለት ነዋ?» በማለት አንድሬይ በአንክሮ ተናገረ ።

«ዕውነትን ለማወቅ ፍላጎት ያላቸው ይመስልሃልን?» አላት ።

«አስፈሪ ይሆናል መስሎ» አለችው ትንፋሿን ደህና አድርጋ እየሳበች እና ፈገግ እያለች ።

«ዳኞቹ ሊወጡ ነው! ፀጥታ!» የሚል ድምፅ ተሰማ ።

ሰዎች ወደየቦታቸው ፈጥነው ሄዱ ።

ሰብሳቢው ዳኛ በአንድ እጁ ጠረጴዛው ላይ ደገፍ ብሎ በሌላ እጁ ደግሞ ወረቀት ይዞአል ። እንደ ስልብ ቀጭን በሆነ ሰላላ ድምፅ ማንበብ ጀመረ ።

ሲዞቭ ወደፊት ሳብ-ሳብ እያለ ፡ —

«የፍርዱን ቃል እያነበበ ነው» በማለት ተናገረ ።

ክፍሉ ውስጥ ፀጥታ ሠፈነበት ። ሁሉም ሽማግሌውን ሰው እያስተዋለ ከተቀመጠበት ተነሳ ። አጭር ፤ ቀጭን እና ቀጥ ብሎ የተገተረ በመሆኑ በአንድ በማይታይ ሥውር እጅ የተያዘ ከዘራ ይመስላል ። ሌሎቹ ዳኞችም ከተቀመጡበት ብድግ ብለው ተነሱ ። የቀበሌው ገገር ጭንቅላቱ ወደ አንድ ማዕዘን አጋድሎ ዐይኖቹ ደግሞ ጣራ-ጣራውን ያስተውላሉ ። ከንቲባው እጆቹን ደረቱ ላይ አጣጥፎአል ። የመኳንንት ተጠሪ የሆነው ሰው ጢሙን ያሻሻል ። ሕመምተኛ መሳዩ ዳኛ ፤ ዘርጣጣው ባልደረባው እና ዐቃቤ ሕጉ ሁሉም እሥረኞቹን ይመለከታሉ ። ከዳኞቹ በላይ ግድግዳው ላይ ከፍ ብሎ የቁሳሩ ፎቶግራፍ በቀይ የበዓል ልብስ አሸብርቆ የተሰቀለ ሲሆን ፤ በፊቱ ላይም የግዴለሽነት ሁኔታ የሚታይበት ከመሆኑም በስተቀር አንዳች ዝምብ ላዩ ላይ ትዞረዋለች ።

«ግዞት!» አለ ሲዞቭ በእፎይታ ሁኔታ ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«ምነው! ተመሥገን አምላኬ እንግዲህስ አለፈ! ከባድ የግዞት እና የሥራ ቅጣት ይሆናል ብዬ ሠግቼ ነበር ። እናት ፤ ይኸ ይሻላል!» በማለት ተናገረ ።

«ይህ እንደሚሆን ቀድሞውንም አውቄዋለሁኝ» በማለት እናት ድክም ባለ ድምፅ ተናገረች ።

«አይ ፤ እንግዲህ ይኸው ዕውን ሆኖአል ። ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚነገሩ አይደለም» አለ ።

ወደ ውጪ እንዲወጡ በመደረግ ላይ ወደአሉት እሥረኞች ፊቱን መለስ አደረገ ።

«ፌዎዶር! ደህና ሁን! የተቀራችሁትም በሙሉ ደህና ሁኑ! እግዚአብሔር ይጠብቃችሁ!» በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰማ ።

እናት ምንም ሳትናገር ዝም ብላ ልጅዋን እና



ሌሎቹንም ራሷን በማነቃነቅ ተሰናበተቻቸው ። ማልቀስ ቃጥቶአት ነበር ። ግን አፈረች ።

## 27

ፍርድ ቤቱን ለቅቃ ስትወጣ መምሸቱን በመመልከቷ ተደነቀች ። የመንገድ መብራቶች እና የሰማይ ኮከቦች በርተዋል ። ፍርድ ቤቱ አጠገብ ጥቂት ሰዎች ተሰበሳስበዋል ። ቀዝቃዛው ዓየር በረዶ ተጋግሮበታል የወጣቶች ድምፆች ይሰማሉ ። ግራጫ ቆብ ብጤ የደፋ ሰው ሲዞቭን ተመለከተው ። አለውም ፡ —

«ምን ተፈረደ?»

«ግዞት ።»

«ለሁሉም?»

«አዎን ።»

«ተመሥገን!»

ሰውየው ሄደ ።

«አየሽ? ሰዎች ፍርዱን ለማወቅ ይሻሉ…» አለ ሲዞቭ ።

ድንገት ወጣቶች ወንዶች እና ልጃገረዶች ከበቡዋቸው ። ተሰብስበው ወደነበሩት ሰዎችም እየተመለከቱ ጠጋ-ጠጋ ይሉ ጀመር ። እናት እና ሲዞቭ ቆም አሉ ። ምን እንደተፈረደ ፤ የእሥረኞቹ ሁኔታ እንደምን እንደነበረ ፤ ማን ንግግር እንዳሰማ እና ንግግሩም ምን እንደነበረ ፤ ጠየቁዋቸው ። ይቀርቡ የነበሩት ጥያቄዎች በሙሉ ከልብ የመነጩ ጥያቄዎች ስለነበሩ ፤ እናት ለጥያቄዎቹ ትመልስ የነበረው በደስታ ተውጣ ነበር ።

«ክቡራን! እኚህ ሴት የፓቬል ቭላሶቭ እናት ናቸው!» በማለት ከመካከላቸው አንዱ ተናገረ ። ወዲያውኑ ፀጥታ ሠፈነ ።

«እጅዎን እንድጨብጥ ይፍቀዱልኝ!» በማለት ጠየቀ ።

አንድ ጠንከር ያለ እጅ የእናትን እጅ ጨበጣት ። ሌላ በስሜት የተዋጠ ድምፅ ደግሞ ፡ —

«የእርስዎ ልጅ ለእኛ ለሁላችንም የብርታት እና የጥንካሬ አርአያ ነው…» በማለት ተናገረ ።

«የሩስያ ወዝ-አደሮች ለዘለዓለም ይኑሩ!» የሚል የብዙ ሰዎች ጉልህ ድምፅ አስተጋባ ።

ጩኸቱ አንዴ እዚህ አንዴ እዚያ እየተሰማ ይበራከት ጀመር ። ሰዎቹ ከየማዕዘናቱ እየተሯሯጡ እየወጡ እናት እና ሲዞቭ የሚገኙበትን ቦታ ከበቡት ። ፖሊሶች ፊሽካዎቻቸውን ነፉ ። ይሁን እንጂ ፤ ይኸ ሁኔታ ሰዎቹን ሊበትናቸው አልቻለም ። ሲዞቭ ይስቃል ። ሁኔታው ለእናት አስደሳች ሕልም መስሎ ታያት ። ዐይኖቿ በደስታ እንባ ተሞልተዋል ። ትስቃለች ። እጅ ትነሳለች ። የሰዎችን እጆች ትጨብጣለች ። እግሮቿ በድካም ዝለዋል ። ይሁን እንጂ ልክ እንደ ሀይቅ ብሩኅ ፈሰሳ ልቧ በደስታ ተውጦ ፍስስ ይላል ። አንድ ሰው አጠገቧ ቀረብ ብሎ ተጠግቶ ግልጽ በሆነ እና የብስጩነት ሁኔታ በሚታይበት መንፈስ ፡ —

«ጓዶች ፤ በዛሬው ቀን የሩስያ ሕዝቦችን ለመዋጥ ያስፈሰፈው ርጉም አውሬ ስግብግብ መንጋጋውን ከድኖታል…» በማለት ተናገረ ።

«እናት ፤ ከዚህ ቦታ ብንሄድ ይሻላል!» በማለት እናትን ሲዞቭ አናገራት ።

በዚህን ጊዜ ሳሻ መጣች እና የእናትን እጅ ያዝ አድርጋ መንገዱ ላይ ወደ አንድ ጥግ እየወሰደቻት ፡ —

«ይምጡ ፤ ድብደባ ከመጀመራቸው በፊት ወይንም ሰዎችን ከማፈሳቸው በፊት መሄድ ይሻለናል» አለች ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ ፡ —

«ግዞት ነው የፈረዱበት? ሳይቤርያ ነው የሚጋዘው?» በማለት እናትን ጠየቀቻት ። እናትም ፡ —



«አዎን!» በማለት መለሰች ።

«እንዴት ነበር ይናገር የነበረው? አይ ፤ እኔ እርሱን አውቀው የለ ። መች አጣሁት ። ከሁሉም ጠንካራ የሆነ እና በአቀራረቡም ግልጽ የሆነ ሰው ነው ። ይኸ ብቻ አይደለም ። ኮስታራ ሰውም ነው ። ለስላሳ እና በስሜት የተመላ ባሕርይ አለው ። ይኸን ባሕርዩን ለሰው ለማሳየት ግን ይፈራል» አለች ።

ሳሻ ለፓቬል ያላትን የፍቅር ቃል ታሰማ የነበረው እንደዚህ ጥልቅ በሆነ ስሜት ስለነበረ አነጋገርዋ እናትን ያበረታታት ከመሆኑም በስተቀር አዲስ ጉልበት እንዲኖራትም አደረጋት ። የሳሻን እጅ እናት ፍቅር በተመላበት ሁኔታ ጫን አድርጋ በመያዝ ፡ —

«ከእርሱ ጋር ለመኖር ወደ እርሱ ዘንድ የምትሄጂው መቼ ነው?» በማለት ጠየቀቻት ።

«የያዝኩትን ሥራ የሚተካኝ ሰው እንዳገኘሁኝ ።» በማለት ሳሻ በልበ-ሙሉነት እየተናገረች እናትን ትመለከታት ጀመር ። ቀጠል በማድረግም ፡ —

«አዩ ፤ እኔም የፍርድ ጊዜዬን እየተጠባበቅሁኝ ነኝ ። ምናልባትም ወደሳይቤርያ በግዞተኝነት እላክ ይሆናል ። ይኸ ከሆነ ደግሞ ፤ እርሱ ወደሚኖርበት ወደማገኘውም ቦታ በግዞተኝነት እንዲያግዙኝ ባለሥልጣኖቹን እጠይቃቸዋለሁኝ» አለች ።

«እንደዚህ ከሆነ ሰላምታዬን አድርሺልኝ!» በማለት ሲዞቭ ተናገረ ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«የፌዎድር ማዚን አጎት የሆነው ሲዞቭ ሰላም ብሎሃል ብለሽ ብትነግሪው ያውቀኛል…» በማለት ተናገረ ።

ሳሻ ዞር ብላ እጅዋን ዘረጋች ። ከዚያም ፡ —

«ፌዎድርን አውቀዋለሁኝ ። ስሜ ሳሻ ይባላል ።» በማለት ተናገረች ።

«የአባትሽ ስምስ?» አላት ሲዞቭ ። ትክ ብላ አስተዋለችው ። ከዚያም ፡ —

«አባት የለኝም ።» አለችው ።

«ሞተዋልን?..» በማለት ጠየቃት ።

«አልሞተም ። በሕይወት ነው ያለው!» በማለት ተናገረች ። ሳሻ በሁኔታዋ ላይ አንድ የግትርነት እና የድርቅነት ባሕርይ በተለይም በፊቷ ላይ ይነበብባታል ።

«አባቴ የመሬት ከበርቴ ነው ። ከዚህም በስተቀር በአሁኑ ጊዜ በገጠር ውስጥ አገር ገዢ ነው ። ገበሬዎችን ይዘርፋል...» በማለት ተናገረች ።

«እ! ሀ!» አለ ሲዞቭ ጨነቅ እያለው ። ፀጥታ የሠፈነበት ጉዞአቸውን እየተጓዙ ከልጅቱ ጎን-ጎን እየተራመደ የጎድን እርሷን-እርሷን ይመለከታታል ። ከዚያም ጥቂት ከተጓዙ በኋላ ፡ —

«እሺ እንግዲህ ፤ እናት በይ ደህና እምሺ ። በዚህ በስተግራ በኩል ጠምዘዝ ብዬ አቀናለሁኝ ። የኔ ልጃገረድ ፤ በይ አንቺም ደህና ሁኚልኝ ። አባትሽ እንደ ዚያ ያሉ ሰው ሁነው ሳለ አንቺ ደግሞ እንዲህ ያለ አቋም መያዝሽ ትንሽ ሳይከብድሽ አይቀርም ። አይደለምን? እርግጥ ነው ይኸ አንቺን ራስሽን የሚመለከት ጉዳይ ነው...» አለ ።

«ልጅዎ ጥሩ ልጅ ባይሆን እና በጎ ያይደሉ ተግባሮችንም በሕዝብ ላይ የሚፈጽም ሁኖ ቢያገኙት ፤ በተግባሩ የሚነቅፉት በመሆን አያወግዙትምን?» በማለት በስሜት ተውጣ ሳሻ ሲዞቭን ጠየቀችው ።

«አዎን ። ምንአልባትም አወግዘው ይሆናል!» በማለት ሽማግሌው ሲዞቭ ጥቂት በማሰላሰል ቆየት ካለ በኋላ ተናገረ ።

«ፍትህን ከልጅዎ ይበልጥ ውድ አድርገው የሚመለከቱ ከሆነ ፤ ልጅዎን ያወግዙታል ። ለእኔ ከአባቴ ይልቅ ፍትሕ ትበልጥብኛለች...» በማለት ሳሻ ተናገረች ።



ሲዞቭ በመገረም ፈገግ ብሎ ጭንቅላቱን ወዘወዘ ። ከዚያም ትንፋሹን ደህና አድርጎ ዋጥ ካደረገ በኋላ ፡ —

«አንቺ ብርቱ የሆንሽ ጠንካራ ሰው ነሽ! ይኸንን አቋምሽን ጥንካሬ አግኝተሽ እንደተጠበቀ የምታቆይው ከሆነ ሽማግሌችን ወደፊትም ድል እየነሳሽ የአንቺ ወገን ታደርጊያለሽ!... በጣም ጠንካራ ሰው ነሽ! እሺ ደህና እምሺ! መልካም ምኞቴን እገልጣለሁኝ ። ግን ለሰዎች ትንሽ መለስ ያልሽ ለምን አትሆኝም? እ? ኒሎቭና ደህና እምሺ! ፓቬልን ስታገኚው ንግግሩን ማዳመጤን ንገሪልኝ ። የተናገረውን በሙሉ አልተገነዘብኩኝም ፤ ካሰማው ንግግር ውስጥ አንዳንዱን ለመገንዘብ ያዳግታል ። በአጠቃላይ ግን ግሩም ንግግር ነበር!»

ባርኔጣውን ከጭንቅላቱ ከፍ አድርጎ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ ወደግራው ዞር ብሎ መንገዱን አቀና ።

«ጥሩ ሰው ይመስላሉ!» አለች ሳሻ ፈገግ እያለች እና ጎላ-ጎላ ያሉት ዐይኖቿ ሲዞቭን እየተከተሉ ።

በዛሬው ቀን ከምንግዜውም ይልቅ የሳሻ መልክ በደስታ የተዋጠ እና ርኅሩህነት የሚታይበት ሁኖ እናት ተመለከተች ።

እቤት ከደረሱ በኋላ ሶፋው ወንበር ላይ ጎን-ለጎን ተቀምጠው ፓቬል በግዞት ወደሚላክበት ቦታ ሳሻ ስለምታደርገው ጉዞ ይወያዩ ጀመር ። ዝምታቸው የበዛ ነው ። ሳሻ ትላልቅ ቅንድቦቿን ከፍ አድርጋ በሕልም ዓለም በሚዋልሉ ዐይኖቿ በርቀት እየተመለከተች በጥልቅ ሃሣብ ተውጣ የምትገኝ ስትሆን ግርጥት ያለ ፊቷ ረጋ ብሎ በሀሳብ የመዋኘት ሁኔታ ይታይበታል ።

«ልጆች ስትወልዱ እናንተ ዘንድ እመጣ እና ልጆቻችሁን አሳድጋለሁኝ ። እዚያ የምንኖረው ኑሮ

እዚህ ከምንኖረው የከፋ አይሆንም ። ፓቬልን ሥራ የማግኘት ችግር አይገጥመውም ። ማናቸውንም ሥራ አሳምሮ የሚሠራ እጅ-ወርቅ ነው…» አለች እናት ።

ሳሻ እናትን በመመራመር ሁኔታ ትክ ብላ ተመለከተቻት ፤ ከዚያም ፡ —

«አሁን ከእርሱ ጋር አብረው ለመሄድ አያስቡምን?» በማለት ሳሻ ጠየቀቻት ። እናትም ትንፋሿን ዋጥ ካደረገች በኋላ ፡ —

«ምን አደርግለታለሁኝ? ከተጋዙበት ቦታ የሚያመልጥ ከሆነ እርሱ ዘንድ በመሆኔ ለእርሱ መሰናክል እንቅፋት እሆንበታለሁኝ ። እርሱ ዘንድ ለመኖር አብሬው እንድሄድ የሚፈቅድ አይመስለኝም…» አለቻት ።

ሳሻ ጭንቅላቷን ነቀነቀች ። ከዚያም ፡ —

«ዕውነትዎን ነው ። እሺ አይልዎትም» አለች ።

«ከዚህም በስተቀር የራሴ ተግባር ፊት-ለፊቴ ተደቅኖ ይጠብቀኛል!» አለች እናት ኩራት በተመላበት ሁኔታ ። ሳሻም ፡ —

«አዎን ዕውነትዎን ነው! ዋናው ቁም-ነገር የሚያከናውኑት ተግባር ነው…» አለቻት ።

ድንገት ፤ አንዳች ነገር የምትወረውር ይመስል ቀስቀስ ካለች በኋላ ረጋ ባለ እና ቀለል ባለ አነጋገር ፡ —

«እርሱ እዚያ ለረዥም ጊዜ አይኖርም ። ማምለጡ እንደሆን የማይቀር ጉዳይ ነው…» አለች ።

«ታዲያ አንቺስ? ልጅ የወለዳችሁ እንደሆን ደግሞ ልጃችሁስ ፤ እንዴት ትሆናላችሁ?» አለቻት እናት ።

«ጊዜው ሲደርስ እናስብበታለን ። ስለ እኔ መቸገር አይኖርበትም ። እኔ ለእርሱ እንቅፋት አልሆንበትም ። ከእርሱ ተለይቶ መኖር ለእኔ ችግር ሊሆንብኝ ይችላል ። ነገር ግን መኖር እችላለሁኝ ። ምንም ቢሆን እንቅፋት አልሆንበትም!» በማለት ተናገረች ።



ሳሻ የምትናገረውን በተግባር የምታውል መሆኗን እናት የምታውቅ ስለሆነች ለዚች ምስኪን ልጃገረድ አዘነችላት ። ከዚያም እናት ሳሻን እቅፍ አድርጋት ፡ —

«የኔ ውድ ትቸገርያለሽ!» አለቻት ።

ሳሻ ለስለስ ባለ ሁኔታ ፈገግ ብላ እየሳቀች ወደ እናት ዘንድ ጥግት-ጥግትግት አለች ።

ልክ በዚህን ጊዜ ኒኮላይ ድክም ብሎት እና ዝሎ ወደቤት ገባ ። ከዚያም ካፖርቱን እያወለቀ ፡ —

«ሳሻ አሁኑኑ ከዚህ ቦታ ብትሄዱ የተሻለ ነው! ከጧት ጀምሮ ሁለት ሰላዮች ይከታተሉኛል ። ክትትላቸው በደንብ የሚያስታውቅ እና ግልጥ የሆነ ስለሆነ ምናልባትም ሊይዙኝ ሳያስቡ አልቀሩም ። እኔ ይሆናል ብዬ የማስበው ሁል ጊዜም ይደርሳል ። አንድ የሆነ ነገር አለ ። በነገራችን ላይ ፤ ፓቬል ያሰማው ንግግር ይኸውና ። አትመን ልናሠራጨው አስበናል ። ለሉድሚላ ውሰጂላትና በተቻለ ፍጥነት ይታተም ። ኒሎቭና ፤ ፓቬል ያሰማው ንግግር ግሩም ንግግር ነበር!.. ሳሻ ፤ ሰላዮችን ተጠንቀቁ!» አለ ።

ኒኮላይ ሲናገር በብርድ የተቆራፈዱ እጆቹን ያሻሽ ነበር ። ከዚያም ወደ መጻፊያ ጠረጴዛው ዘንድ ሂዶ ከመሳቢያዎቹ ውስጥ ወረቀቶች ያወጣ ጀመር። ከወረቀቶቹ መካከል አንዳንዶቹን ቀደዳቸው ። ሌሎቹን ደግሞ ወደጎን አስቀመጣቸው ። ድክም ያለ እና ሃዛብ የገባው ይመስላል ።

«እነዚህን መሳቢያዎች ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ ወረቀቶች ካስወገድኩኝ ረዥም ጊዜ አልሆነም ። እንደገና ይኸንን ያህል መአት ወረቀት ሊጠራቀም እንዴት እንደቻለ ሊገባኝ አልቻለም! ኒሎቭና ፤ ይኸንን ምሽት እዚህ ባያሳልፉ የተሻለ ሳይሆን አይቀርም ። ምን ይመስልዎታል? ድርጊቱን መመልከቱ ደስም አይልም ።

ከዚህም በስተቀር ፤ እርስዎንም ጭምር ይዘውዎት ሊሄዱ ይችላሉ ። የፓቬል ንግግር የታተመባቸውን ጽሁፎች ከቦታ-ቦታ እንዲያሠራጩልን እርስዎ ለእኛ ያስፈልጉናል…» በማለት ተናገረ ።

«እነርሱ እኔን ምን አድርጌአቸው ይይዙኛል?» አለች እናት ።

ኒኮላይ እጁን ወደ ዓይኑ አስጠግቶ እያወዛወዘ ፡ —

«እንዲህ ያለ ነገር ከመድረሱ በፊት የሚደርስ መሆኑን በትክክል አውቃለሁኝ ። እና እርስዎ ደግሞ ሉድሚላን ብዙ ሊረዱት ይችላሉ ። የመያዝ አደጋ እንዲደርስብዎ አያድርጉ…» አለ ።

የልጅዋ ንግግር ሲታተም እንድትረዳ ሃሣብ በመቅረቡ እናት ተደሰተች ። ከዚያም ፡ —

«ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ እሄዳለሁኝ» አለች እራሷ በራሷ እየተደነቀች ፡ —

«ለፈጣሪ ክብር-ምሥጋና ይድረሰው እና ፤ ከእንግዲህ አንዳችም የምፈራው ነገር የለም!» በማለት ተናገረች ። ኒኮላይ ቀና ብሎ ሳይመለከት ፡ —

«በጣም ጥሩ! ሻንጣዬ እና የውስጥ ልብሴ የት እንደሆነ ቢነግሩኝ ጥሩ ነበር ። በዚህ ደባቂ በሆነ እጅዎ ሸሽግ ቦታ አስቀምጠው የገዛ ራሴን ዕቃዎች እንኳን ፈልጌ ማግኘት ተሳነኝ!» አላት ኒኮላይ ።

ሳሻ ወረቀቶቹን እሳት እየጨመረች የተቃጠለውን አመድ እንደገና ከከሰሉ ጋር እያደቀቀች ትበታትናለች ። ኒኮላይ ሳሻን ለመሰናበት እጁን ዘርግቶ ፡ —

«ሳሻ ፤ በይ እንግዲህ ሂጂ ። ደህና ሁኚ ። ደህና-ደህና መጻሕፍት ስታገኚ ላኪልኝ ። አትርሺ ። ውድ ጓዷት ፤ ደህና ሁኚልኝ! ተጠንቀቂ…» አላት ።

«ለረዥም ጊዜ አሥረው የሚያቆዩህ ይመስልሃልን?» አለችው ።

«ማን ያውቃል? ምናልባትም ብዙ ያቆዩኝ ይሆና



ል ። እኔን መቃወሚያ አዘጋጅተዋል ። ኒሎቭና ፤ ከሳሻ ጋር አብረው ቢሄዱ አይሻልምን? ሁለት ሰዎችን በአንድ ጊዜ በስለላ መከታተል ለሰላዮቹ ከባድ ይሆንባቸዋል» በማለት ኒኮላይ ተናገረ ።

«እሺ ካፖርቴን እና የአንገት ልብሴን ልልበስ…» በማለት እናት ተናገረች ።

እናት ኒኮላይን ተጠንቅቃ ታስተውለዋለች ። እርሱ ግን በቀድሞ ሩኅሩኅ የሆነ ኩራ-ደራ ያለ መልኩ ላይ ጥቂት በስጨት የማለት ስሜት የሚታይበት ከመሆኑ በስተቀር ያው እንደቀድሞው ነው ። አልተለወጠም ። ከሌሎች ይልቅ እጅግ ተወዳጅዋ በሆነው በዚህ ሰው መልክ ላይ የመቆጣትም ሆነ የመደናገጥ አንዳችም ሁኔታ አይታይበትም ። እከሌ-ከእከሌ ሳይል ኒኮላይ ምን ግዜም ማንንም በዕኩልነት ሁኔታ የሚቀበል ሰው ሲሆን ፤ ምን ግዜም ቢሆን ደግ እና የማይለዋወጥ ባሕርይ ያለው ፤ ሰላማዊ በሆነ ብቸኝነት የሚኖር ሰው ነው ። ያው እንደቀድሞው እርሱነቱ አሁንም እርሱነቱን ለማንም ጠብቆ የሚገኝ ሲሆን ፤ ይኸው እርሱነቱም ከሌሎች ሰዎች ቀድሞ እና መጥቆ የሚገኝ አንድ ምሥጢራዊ የሆነ ሸሽግ ውስጣዊ ኑሮን በልቡ ቋጥሮ የሚኖር ሰው መሆኑ ነው ። ከሌሎቹ ይበልጥ ለእርሷ ቅርብ እና ግልጽ መሆኑን እናት የተገነዘበች ከመሆኗም በስተቀር ፤ እርሷም እርሱን ለራሷ እንኳን እርግጠኛ መሆኑን ልትገነዘበው በማትችለው ሁኔታ ተጠንቅቃ ታፈቅረዋለች ። አሁን ለእርሱ የተሰማት ሃዘን እጅግ ከፍተኛ ሲሆን ፤ ይኸንን ሃዘኗን ግን ኒኮላይ እንዲያውቅባት አትሻም ። ካወቀባት ብስጩ እና ግራ የሚገባው ስለሚሆን ፤ ግራ ከገባው ደግሞ ሁኔታው በጥቂቱ አስቂኝ ስለሚሆን ኒኮላይን እንዲህ ሁኖ ለመመልከት አልፈቀደችም ።

እንደገና ወደ ክፍል ስትገባ ኒኮላይ የሳሻን እጅ ጨብጦ ይዞአል ።

«ግሩም-ድንቅ ነው! ለእርስዎም ሆነ ለእርሱ ሁኔታው ተስማሚ እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ ። ትንሽ ግላዊ ደስታ ማንንም አይጎዳም ። ኒሎቭና ፤ ተዘጋጅተዋልን?» በማለት ኒኮላይ ተናገረ ።

ፈገግ እያለ እና መነጽሩን ወደአፍንጫው ገፋ እያደረገ ወደ እናት ዘንድ መጣ ።

«በሉ እንግዲህ ፤ ደህና ይሁኑልኝ ። ሦስት ወይንም አራት ወራት ቢያቆዩኝ ነው ። ግፋ ቢል ስድስት ወር ብቆይ ነው! ከሕይወት ላይ ተገንድሶ የሚወሰድ ረዥም ጊዜ ነው... ተጠንቅቀው ራስዎን ይጠባበቁ ። እሺ? በሉ ልሳምዎት...» በማለት ተናገረ ።

ቀጭን እና ለስላሳ የሆነው ኒኮላይ እቅፍ አድርጎአት ዐይን-ዐይኖቿን ይመለከታታል ።

«እንደዚህ እቅፍ ሳደርግዎት ከእርስዎ ጋር በፍቅር የተነደፍኩኝ እመስላለሁኝ!» በማለት እየሳቀ ተናገረ ።

እናት አንዳችም ቃል ሳትናገር ግንባሩን እና ጉንጮቹን ሳመችው ። እጆቿ ግን ይንቀጠቀጣሉ ። የእጆቿን መንቀጥቀጥ እንዳያስተውልባት አፈፍ አድርጋ ሳበቻቸው ።

«በተለይ ነገ በጣም ይጠንቀቁ ። ጧት አንድ ትንሽ ልጅ ሁኔታውን እንዲቃኝ ይላኩት ። ሉድሚላ የምታውቀው ትንሽ ልጅ አለ ። እሺ እንግዲህ ፤ ጓዶች ደህና ሁኑ! ሁሉም ነገር መሆን እንዳለበት ይሆናል!...» በማለት ተናገረ ።

ከቤት ወጥተው ሳሻ እና እናት ጉዞዋቸውን እንደጀመሩ ሳሻ ረጋ ባለ ሁኔታ ፡ —

«ወደሞት የሚሄድ ቢሆንም የኒኮላይ ሁኔታ ልክ እንዲህ በቀላሉ እና ጥቂት ጣደፍ-ጣደፍ የሚል ሁኔታ እየታየበት ነው ። ሞትም ከፊቱ ቀርቦ ዐይን-ዐይኑን ቢመለከተው ፤ ኒኮላይ መነጽሩን ወደ አፍንጫው ገፋ እያደረገ ከመሞቱ በፊት 'ግሩም-ድንቅ ነው!' በማለት መናገሩ የማይቀር ነው» አለች ።

«እጅጉን አድርጌ ነው የወደድኩት!» በማለት እናት ተናገረች ። ሳሻም በበኩሏ ፡ —

«አደንቀዋለሁ ። ግን አልወደውም ። እጅግ አድርጌ አከብረዋለሁኝ ። ደግ ሰው ነው ። እንደውም አንዳንድ ጊዜ ለስላሳ ሰው ነው ። ነገር ግን አንድ ጉድለት አለበት ። በቂ በሆነ ሁኔታ ሰብአዊነት ይጎድለዋል... ሰላዮቹ ይከታተሉናል መሰለኝ ። ብንለያይ ሳይሻል አይቀርም ። የሚከታተሉዎ መስሎ ከተሰማዎ ወደሉድሚላ ዘንድ አይሂዱ» በማለት ተናገረች ።

«ግዴለም ፤ አልሄድም!» በማለት እናት መለሰች ።

«ይጠንቀቁ ። እንዳይሂዱ ። እርሷ ዘንድ በመሄድ ፈንታ ወደ እኔ ዘንድ ይምጡ ። አሁን ለጊዜው ግን እንለያይ» በማለት ሳሻ እንደገና አጥብቃ ተናገረች ።

ፈጠን ብላ ከታጠፈች በኋላ ወደመጣችበት አኳያ መራመድ ቀጠለች ።

28

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እናት ሉድሚላ ትንሽ ክፍል ውስጥ የምግብ ማብሰያውን ምድጃ ተጠግታ ትሞቃለች ። ሉድሚላ ክፍሉን በቀሚሷ ኳኳታ እና ጉልህ በሆነው ድምፅዋ በመምላት ጥቁር ቀሚስ ለብሳ እና የብረት ቀብቶ ታጥቃ በዝግታ እርምጃ ከወዲያ-ወዲህ ትንጎራደዳለች ።

የሉድሚላ ድምፅ ከፍ ዝቅ ሳይል ያው አንድ ዓይነት የአወራረድ ደረጃውን ጠብቆ ሲንቀረቀር ፤ የምድጃው እሳት ደግሞ እየተንጣጣ አየሩን ይመላዋል ።

«ሰዎች ከክፉነታቸው ይልቅ ይበልጥ ጅሎች ናቸው ። ከፊት-ለፊታቸው ያለውን ብቻ በመመልከት ወዲያውኑ ይመሰጡበታል ። ፊት-ለፊት ቅርብ ሁኖ ሊደረስበት በመቻል የሚገኝ ነገር ሁሉ መናኛ የሆን ቀላል ነገር ነው ። ተወዳጅ የሆኑ ነገሮቹ ፤ በርቀት የሚገኙ እና እንደው በቀላሉ የማይደረስባቸው ነገሮች ብቻ ናቸው ። ደርሰውበት ሲይዙት እና ሕይወትም የተለወጠ ሁኖ ሲገኝ ሁሉም ሰው ተደሳች ይሆናል ። ቀላል ከሆነ እና ሰዎችም ይበልጥ አስተዋይ ከሆኑ ። ይሁን እንጂ ቀላል እንዲሆን እኛ ራሳችንን ማዘጋጀት አለብን...»

ድንገት እናት አጠገብ ተጠግታ ቆመች ።

«ብዙ ጊዜ ከሰዎች ጋር አልገናኝም ። ከሰዎች ጋር ስገናኝ ወሬዬን እከሰክሳለሁ ። ንክ ሳትሆን አትቀርም ብለው ያስቡ ይሆናል» በማለት ይቅርታ በመጠየቅ ሁኔታ ተናገረች ።

«ለምን?» አለች እናት ። ይህች ልጅ ጽሁፎችን የምታትመው የት ቦታ እንደሆነ ለማወቅ ሞከረች ። ይሁን እንጂ አልቻለችም ። ፊታቸውን ወደ መንገዱ የመለሱ ሦስት መስኮቶች የሚገኙበት በዚህ ክፍል ውስጥ አግዳሚ የፎቴ ወምበር እና የመጻሕፍት መደርደሪያ ፤ አንድ ጠረጴዛ ፤ ወንበሮች እና አልጋ ይገኛሉ ። ክፍሉ ውስጥ በአንድ ጥግ የፊት መታጠቢያ የተሰቀለ ሲሆን በሌላኛው ጥግ ደግሞ የምግብ ማብሰያ ምድጃ ይገኛል ። ማናቸውም ክፍሉ ውስጥ የሚገኝ ነገር ሁሉ አዳዲስ ፤ ንጹህ እና በሚገባ የተጠገነ ሲሆን ፤ በዚህ ዕቃ ላይም ጌጣ-ጌጥ የሌለው የቤቱ ባለቤት ቁመና ቀዝቃዛ ጥላውን አጥልቶበታል ። አንዳች የተደበቀ ነገር መኖሩ ለእናት ተሰምቶአታል ። ከቶ የት ቦታ እንደተደበቀ ግን ልታውቅ አልቻለችም ። ወደ በሮቹ ተመለከተች ። ወደ አንድ ትንሽ ክ



ፍል የሚያስገባውን በር ከፍታ ገባች ። ምድጃው አጠገብ አንድ ሌላ ትልቅ እና ጠበብ ያለ በር አለ ።

ሉድሚላ ጠንቀቅ ብላ የምታስተውላት መሆኑን በመመልከቷ እናት ሁኔታው ተሰምቷት ፡ —

«ለጉዳይ ነበር የመጣሁት!» አለች ።

«አውቃለሁኝ! ለጉዳይ ካልሆነ በስተቀር እኔን ለመጠየቅ ሰዎች አይመጡም...» በማለት ሉድሚላ መለስችላት ።

በሉድሚላ አነጋገር እናት አንድ እንግዳ የሆነ ሁኔታ አስተዋለች ። ፊቷን ተመለከተቻት ። ቀጫጭን በሆኑት ከናፍሮቿ ላይ ፈገግ የማለት ሁኔታ ይታይባታል ። ከመነጽሯ በስተውስጥ በኩል ደግሞ ዐይኖቿ ሰልቸት ብሎአቸው ያንጸባርቃሉ ። እናት መልክት ካደረገቻት በኋላ የፓቬል ንግግር የተጻፈበትን ሰጠቻት ።

«ይኽንን በተቻለ ፍጥነት እንድታትሚው ይሻሉ...» አለቻት ።

ከዚያም ኒኮላይ ተይዞ የሚታሠር መሆኑን እየተጠባበቀ ነው አለቻት ።

ሉድሚላ ዝም ብላ ወረቀቱን ቀበቶዋ ውስጥ አስገባች እና ተቀመጠች ። እሳቱ መነጽሯ ላይ አጓጉል በሆነ ሁኔታ የሚያበራ ሲሆን ሞቃት ብርሃኑም የማይነቃነቀው ፊቷ ላይ ያበራል ። እናት ንግግሯን ስታበቃ ፡ —

«እኔን ለመያዝ ሲመጡ ተኩሼ እገድላቸዋለሁኝ!» አለች ረጋ ባለ እና ወሳኝ በሆነ ሁኔታ ። ቀጠል አድርጋም ፡ — «ራሴን ከአደጋ ለመከላከል መብት አለኝ ። ሌሎች እንዲያደርጉ የምጠይቀው ይኽንን እስከሆነ ድረስ ደግሞ የመታገል ግዴታ አለብኝ» በማለት ተናገረች ።

የእሳቱ ግለት ከምንጊዜውም ፊቷን ይበልጥ ኮስታራ እና ቁጡ አደረገው ።

«እንዲህ ያለው ኑሮስ ኑሮ አይባልም!» በማለት እያዘነች ድንገት እናት በአዕምሮዋ አሰላሰለች ።

ሉድሚላ በግማሽ ልብ የፓቬልን ንግግር ማንበብ ጀመረች ። ማንበቧን ስትቀጥል ግን ይበልጥ እየተሳበች የሄደች ስትሆን በመጨረሻም በስሜት በመዋጥ እየአንዳንዱን ገጽ ትዕግሥት ባጣ ሁኔታ እየተቻኮለች ለማንበብ ታገላብጥ ጀመር ። ንባቧን እንደጨረሰች ከተቀመጠችበት ተነሳች ። ትከሻዋን ጉብ አድርጋ ወደላይ በመቆለል ወደእናት ዘንድ ተጠጋች ።

«እጅግ ጥሩ ንግግር ነው!» አለቻት ።

አንገቷን ቀለስ አድርጋ ለተወሰነ ጊዜ ታደንቅ ጀመር ።

«ስለ ልጅዎ ለእርስዎ መናገር አልሻም ። እንዴም እንኳን ተገናኝተን ስላላየሁት አላውቀውም ። ሀዘን ላይ የሚጥል ንግግር መናገርም አልወድም ። የእርስዎ አንድ ውድ የሆነ ልጅዎ ወደ ግዞት ሲጋዝብዎ ምን እንደሚሰማዎት አውቃለሁኝ ። ግን የሚደንቀኝ እና ከእርስዎ ለማወቅም የምሻው ፤ ይኸንን መሳይ ልጅ ያለዎት በመሆኑ ደስ አይልዎትምን?» አለቻት ።

«በጣም እንጂ!» በማለት እናት መለሰች ።

«አይፈሩምን?» አለች ሉድሚላ ።

«ከእንግዲህ ምንም አልፈራም...» አለቻት እናት ።

ሉድሚላ በአንድ እጅዋ ለጥ ያለ ፀጉሯን እያስተካከለች ወደ መስኮቱ ዘንድ ሄደች ። ፊቷ ላይ ጥላ አረበበበት ። ምንአልባትም አፍና የያዘችው የሳቂ ጥላ ሳይሆን አይቀርም ።

«ፊደሎቹን አሁኑኑ ለቅሜ እጨርሳለሁኝ ። ጋደም ይበሉ ። ቀኑ ለእርስዎ አድካሚ ቀን ስለነበረ ሳይደክምዎት አይቀሩም ። እዚህ አልጋው ላይ ጋደም ይበሉ ። እኔ አልተኛም ። ምሽቱ ላይ እንዲያግዙኝ እቀ



ሰቅስዎት ይሆናል... የመኝታ ጊዜዎ ሲደርስ መብራቱን ያጥፉት» አለቻት ።

ሁለት የግንድ ጉማጆች ምድጃው ውስጥ ከተተች እና በጠባቡ በር አድርጋ ወደ ውስጥ ገባች ። ከዚያም አጥብቃ ዘጋችው ። እናት ሉድሚላ ስትሄድ ተመለከተች ። ከዚያም ልብሷን እያወለቀች ፡ —

«አንድ ያዘንችበት ነገር አለ...» በማለት አሰበች ።

እናት ድክም ብሎአታል ። ይሁን እንጂ ፤ ነፍሷን ከብቦ በዋጠው ለስላሳ እና ብሩኅ ብርሃን ማናቸውም ነገር የሚያበራ መስሎ ስለታየት በላይዋ ላይ ሰላም ሰፍኖባታል ። ይኸንን መሳይ ሰላም ከአሁን ቀድሞም ታውቃለች ። አንዳች ታላቅ በሆነ ስሜት የመዋጥ ሁኔታ ደርሶባት ካለፈ በኋላ ይኸንን መሳዩ ድርጊት ሁል ጊዜም ያጋጥማታል ። ሁኔታው ያስፈራራት የነበረበት ጊዜ ነበር ። አሁን ግን ታላቅ እና ጠንካራ በሆነ ስሜት እያጠናከራት መንፈሷ እንዲዳብር አደረጋት ። መብራቱን አጠፋች እና ቀዝቃዛው አልጋ ውስጥ የብርድ ልብሱን ለብሳ እና ተደላድላ ድብን ያለ እንቅልፍ ወሰዳት...

ዐይኗን ከፈት ብታደርግ ክፍሉ ግልጽ በሆነ የክረምት ቀን ነጣ ያለ ብርሃን ተመልቶአል ። ሉድሚላ መጽሐፍ በእጅዋ ይዛ ጋደም ካለችበት አግዳሚ ሶፋ ላይ ቀና አለች እና በማይመስል ሁኔታ ፈገግ አለች ።

«የኔ ውድ!» አለቻት እናት በስጨት ባለ ሁኔታ ። «ኸረ እንደምን ያለሁት ነኝ ። በጣም ረፍዶ ይሆን?» አለች ።

«ደህና አደሩ ወይ? አራት ሰአት ሊሆን ነው ። ይነሱ እና ሻይ እንጠጣለን» አለቻት ሉድሚላ ።

«ምነው ሌሊት አልቀሰቀስሺኝም?» አለቻት እናት ።

«ልቀሰቅስዎት መጥቼ ነበር ። ወደ እርስዎ ዘንድ ቀረብ ስል በከባድ እንቅልፍ ተውጠው ደስ በሚያ

ሰኝ ሁኔታ ፈገግ ብለው ስለነበረ ለልቤ እርስዎን ከእንደዚህ ዓይነት እንቅልፍዎ ለመቀስቀስ እሺም አላለኝ» አለቻት ።

ተኝታ ከነበረበት ከአግዳሚው ፎቴ ላይ ሉድሚላ ከተነሳች በኋላ ጎንበስ በማለት ወደ አልጋው ዘንድ ሂዳ ጎብደድ አለች ። በዚች የወጣት ልጅ ዐይኖች የፍቅር አመለካከት እናት ከዚህ ቀደም የምታውቀውን እና የምታፈቅረውን ሁኔታ ተመለከተች ።

«ምንአልባትም በዚያን ጊዜ ጥሩ ሕልም ያዩ ነበር እና እርስዎን መቀስቀሱ አሳዛኝ መሰለኝ…» አለቻት ።

«ሕልም አላይም ነበር!» በማለት እናት መለስ ችላት ።

«ቢያዩም-ባያዩም ምንም አይደለም ። ፈገግታዎ ደስ ብሎኝ ነበር ። በጣም ረጋ ያለ እና ግሩም ፈገግታ ነበር ።… እና ሁሉን-አቀፍ የሆነ ፈገግታ ነበር!» አለቻት ።

ሉድሚላ ሳቀች ። አሳሳቋም የተለሳለሰ እና ደስተኛ የሆነ ነው ።

«ስለእርስዎ እንዳስብ አደረገኝ ። ለመሆኑ ኑሮዎ ከባድ ነውን?» አለቻት ።

እናት ኑሮዋ ከባድ መሆን-አለመሆኑን ስታሰላስል የዐይኖቿ ሽፋሽፍቶቹ ተርገበገቡ ።

«መሆን አለበት!» አለች ሉድሚላ ። ከዚያም እናት ዝግ ባለ አነጋገር ፡ —

«እርግጠኛ አይደለሁኝም ። አንዳንዴ ኑሮዬ ከባድ ይመስለኛል ። ይሁን እንጂ በኑሮዬ ውስጥ የሚገኘው ማናቸውም ነገር ጠቀሜታ ያለው እና አስደናቂ በመሆኑ ፤ አንዱ ነገር ሌላኛውን ነገር ፈጠን ብሎ የሚተካው በመሆኑ ሕይወቴ በድርጊቶች የተመላ ነው…» አለች ።



ብዙውን ጊዜ እንደሚደርስባት ሁሉ ፤ አሁንም ድንገት በስሜት ተዋጠች ። ሃሣቦች እና ምስሎች አዕምሮዋ ውስጥ ይመላለሱ ጀመር ። አልጋዋ ላይ ቁጭ ብላ ሃሣቦቿን የቃላት ልብስ በትዕግሥት ታለብሳቸው ጀመር ፡ —

«ሁሉም ነገር ወደአንድ አቅጣጫ ሳያቋርጥ ይገሰግሳል ። አንዳንድ ጊዜ ግን ሁኔታው ከባድ ነው ። ሰዎች ይሰቃያሉ ። ይደበደባሉ ። ጭካኔ በተመላበት ሁኔታ ይደበደባሉ ። ደስተኞች እንዲሆኑም አይፈቀድላቸውም ። ይኽ ከባድ ጉዳይ ነው!» አለች ።

ሉድሚላ ራሷን ወደእናት መለስ አድርጋ በፍቅር አመለካከት ትመለከታታለች ።

«አንቺ ግን ስለራስሽ ምነው አታወሪም?» አለቻት ።

እናት ከአልጋው ላይ ተነስታ ልብሷን መለባበስ ጀመረች ።

«ይኽንንም ፤ ያንንም የሚያፈቅሩ ሲሆኑ እና በልብዎ ውስጥ ያንን ያህል ለብዛቱ ሥፍር-ቁጥር የማይገኝለትን ሕዝብ በማፍቀር ለመላው ሕዝብ የሚያስቡ እና የሚያዝኑ ሁነው ሲገኙ ራስዎን ከሌሎቹ ለይተው ስለራስዎ ማውሳት እንዴት ይቻልዎታል?… እንዴትስ ራስዎን ከእነርሱ መለየት ይቻልዎታል?» በማለት ሉድሚላ ተናገረች ።

እናት ልብሷን በገሚስ ለብሳ እና በሃሣብ ተውጣ ለተወሰነ ጊዜ ክፍሉ መሃል ቆማ ቀረች ። ለልጅዋ ብዙ ትሰጋ እና ታስብ የነበረችይቱ ፤ አካሉን ከጉዳት ለማዳን ከፍተኛ ፍላጎት የነበራት ያች የቀድሞይቱ ሴት አለመሆኗ ተሰማት ። ያች የቀድሞይቱ ሴት ከእንግዲህ የለችም ። ወጥታለች ። ሩቅ-ሩቅ ወደሆነ ቦታ ሂዳለች ። ወይንም በስሜቷ እሳት ተውጣለች ። ይኽ ሁኔታም አብስሎ በመለብለብ አዲስ ጥንካሬ እንዲኖራት አድርጎአታል ።

የቀድሞውን ዓይነት ሥጋት ተመልሶ ይመጣባት መስሎአት በመፍራት የልቧን ድው-ድውታ በማዳመጥ ትመራመር ጀመር። ሉድሚላ ወደ እናት ዘንድ ተጠግታ

«ምንድነው እንዲህ የሚያስቡት?» አለቻት።

«እኔ እንጃ!» በማለት እናት መለሰችላት።

ሳይነጋገሩ እርስ-በእርሳቸው ተመለካከተው ፈገግ አሉ። ከዚያም ሉድሚላ ፡—

«ሳሞቫሬ እስካሁን እንዴት እንደሆነ እንጃልኝ!» በማለት ካሉበት ክፍል ወጥታ ሄደች።

እናት በመስኮቱ ውጪ-ውጪውን ትመለከታለች። የፀሐይ ብርሃን የሚታይበት ቀዝቃዛ ቀን ነው። ልቧም እንደ ቀኑ ፀሃያማ ብሩኅ ነው። ሞቃትም ነው። ስለማንኛውም ነገር መናገር ፈለገች። ነፍሷ ውስጥ እንዲህ ጥልቅ ብሎ በመግባት የፀሐይን መውጣት ደስ በሚያሰኝ ብሩኅ ፋና እንዲያበራ ያደረገላትን ሰው ባለውለታው መሆኗን በመግለጽ ለማመሥገን ለረዥም ጊዜ እና ተደሳች በሆነ ሁኔታ ለመናገር ከጀለች። ረዘም ካለ ጊዜ ጀምሮ የተወችው የፀሎት ማድረስ ፍላጎቷ አሁን ተቀሰቀሰባት። አዕምሮዋ ውስጥ የአንድ ወጣት ሰው ምስል ተቀርጾ የታያት ሲሆን ፣ ግልጽ ሁኖ በሚሰማ ድምፅ ደስ በሚያሰኝ ብሩህ ፋና እንዲያበራ ያደረገላትን ሰው ባለውለታው መሆኗን በመግለጽ በማመሥገን ለረዥም ጊዜ እና ተደሳች በሆነ ሁኔታ ለመናገር ከጀለች። ረዘም ካለ ጊዜ ጀምሮ የተወችው የፀሎት ማድረስ ፍላጎቷ አሁን ተቀሰቀሰባት። አእምሮዋ ውስጥ የአንድ ወጣት ሰው ምስል ተቀርጾ ታያት። ግልጽ ሆኖ በሚሰማ ድምጹም ፡— «የፓቬል ቭላሶቭ እናት እኛ ናቸው!..» ሲል ተሰማት። የሚንቦገቦጉት የሳሻ ዐይኖች ፊቷ ድቅን ብለው ታዩዋት። የሪቢን ጠቆር ያለ ገጽታ



ታያት። እንደ ብረት ጠንካራ የሆነው የልጇዋ መልክ ታያት። ዐይነ-አፋር እና እርግብግብ የሆነው የኒኮላይ አመለካከት ታያት። አስተሳሰቧን በሙሉ አቅፈው በያዙ እና የሰላም ሁኔታ ባወረዱባት ፣ በማርያም-መቀነት በታበቱ እና እንደ መስታወት በሚያሳይ ደመና ታግዞ ይኸ ሁሉ ሃሣቧ በአንድነት ተከማችቶ ወደ አንድ ጥልቀት ወደ አለው ሃሣብ ተቀየረ።

ሂዳ ከነበረችበት ክፍል ሉድሚላ እየመጣች ፡—

«ኒኮላይ የተናገረው ልክ ነበር። ያዙት። እንደመከሩኝ ሕፃኑን ልጅ ዙርያውን እንዲያንጃብብ እና ሁኔታውን እንዲመለከት ልኬው ነበር። አትክልቱ ውስጥ ፖሊሶች የነበሩ መሆናቸውን እና አንድ ፖሊስ ደግሞ ደጅ-አፍ ላይ ተደብቆ ያየ መሆኑን ነገረኝ። ሰላዮች በየቦታው ተበታትነው ይገኛሉ። ልጁ ሰላዮቹን ያውቃቸዋል» አለች ሉድሚላ።

«ወይ የኔ ምሥኪን!» አለች እናት ራሷን በሀዘን እየነቀነቀች። በሀዘን አኳኋን እ-ሀ-ሀ አለች። ይሁን እንጂ የሀዘንተኛነት ስሜት አልተቀሰቀሰባትም። ይኸ ሁኔታዋም ውስጥ-ውስጡን ለእርሷ አስደነቃት።

«አሁን መጨረሻው ገደማ ወዝ-አደሮችን ከተማ ውስጥ ያስተምር ነበር። የሚያዝበት ጊዜ መቃረቡን እኔም ገምቼ ነበር!» አለች ሉድሚላ ቀላል በሆነ አነጋገር። ይሁን እንጂ ፊቷ ኮስተር ብሎ። ቀጠል አድርጋም ፡—

«ከዚህ ቦታ እንዲሄድ ጓዶቹ ነግረውት ነበር። እርሱ ግን እሺ አላላቸውም። ይኸንን የመሰለ ሁኔታ ሲያጋጥም ማድረግ የሚያስፈልገው ሰዎችን ማስገደድ እንጂ ማግባባት አይደለም...» አለች።

ልክ በዚህን ጊዜ ፀጉረ-ጥቁር ፣ ጉንጨ-ቀይ ፣ እና ደስ የሚያሰኙ ሰማያዊ ዐይኖች ያሉት አፍን

ጫው ጉብር ጉልድማ የሆነ ልጅ ወደ በራፉ መጣ ።

«ሳሞቫሩን ላምጣውን?» በማለት ጠየቀ ።

«ከቻልክ እባክህን ሥርጌይ!» አለችው ሉድሚላ ። ከዚያም ወደ እናት ዞር ብላ ፡—

«እኔ የማሳድገው ልጅ ነው» አለቻት ።

እናት ሉድሚላን ዛሬ ልውጥ ብላ ነው ያገኘቻት ። ከምንጊዜውም ይበልጥ ግልጥ እና ቅርብ ሁናለች ። ግርማ-ሞገስ ያለው የሰውነቷ እንቅስቃሴ አንድ ከፍተኛ ውበት እና ጥንካሬ ይታይበታል ። ይኸ ሁኔታም የገረጣ እና የተኮሳተረ ፊቷን ለስላሳ እንዲሆን አድርጎላታል ። የምሽቱ ሥራ ከዐይኗ ሥር ያሉትን ክበባት አጥቁሮባታል ። ልቧ በውጥረት በጭንቀት የተጠመደ መሆኑን መገመት አዳጋች አይደለም ።

ልጁ ሳሞቫሩን አመጣ ።

«ሥርጌይ ፤ ላስተዋውቃችሁ ። እርሳቸው ፔላጌያ ኒሎቭና ይባላሉ ። ትላንት ከተፈረደባቸው ወዝ አደሮች መካከል የአንደኛው እናት ናቸው» አለችው ።

ሥርጌይ ምንም ሳይናገር እጅ ከነሳ በኋላ እናትን ጨብጦ ከክፍል ወጣ ። ከዚያም በኋላ ዳቦ ይዞ በመምጣት ወንበር ላይ ተቀመጠ ። ፖሊሶቹ ማንን በመጠባበቅ ላይ እንደሆኑ እስኪረጋገጥ ድረስ እናት ተመልሳ እንዳትሄድ ሻዩን እየቀዳች ሉድሚላ እናትን ታግባባት ጀመር ።

«ምናልባትም እዚያ አድፍጠው የሚጠብቁት እርስዎን ይሆን ይሆናል! ለጥየቃ ይፈልጉዎት ይሆናል...» አለቻት ።

«ኧረ እንዳሻቸው ። ቢፈልጉ ይዘው ይሡሩኝ ። በኔ ላይ የሚያደርሱት ይኸን ያህልም ጉዳት የለም ። ብቻ የፓቬልን ንግግር መጀመሪያ በየቦታው ባሠራጩን!» አለች እናት ።

«ፊደሎቹ ተለቅመዋል ። ነገ በከተማ ውስጥ የሚሠራጩት እና በወዝ-አደሮች የመኖሪያ ሠፈሮች



የሚበተኑት ዝግጁ ሁነው ይደርሳሉ ። ለመሆኑ ናታሻን ያውቋታልን?» አለች ሉድሚላ ።

«እንዴታ ፤ አውቃታለሁኝ!» በማለት መለሰች ።

«እርሷ ዘንድ ይውሰዷቸው » አለች እናትን ሉድሚላ ።

ልጁ ጋዜጣ ያነብብ ስለነበረ የሚነጋገሩትን የሚያዳምጥ አይመስልም ። ይሁን እንጂ አሁንም-አሁንም ቀና እያለ እናትን ይመለከታታል ። ብሩህ ዐይኖቹ ደስ ያሰኟት ሲሆኑ እርሱን እየተመለከተች እናት ፈገግ ትላለች ። ሉድሚላ ያለ ሀዘን ስሜት ስለኒኮላይ ታወራ የነበረ ሲሆን እናትም ይኸንን ሁኔታ የተለመደ ሁኔታ አድርጋ ቆጠረችው ። ጊዜው ይሮጣል ። ቁርሳቸውን በልተው ሲጨርሱ ወደ ስድስት ሰዓት ሊጠጋ ምንም ያህል አልቀረውም ።

«ኧረ እንዴት ረፍዷል!» አለች ሉድሚላ በመገረም ።

ልክ በዚህን ጊዜ አንድ ሰው ከውጪ በተቻኮለ ሁኔታ አንኳኳ ። ልጁ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ሉድሚላ እንዲያደርግ የምትጠይቀውን በተጠንቀቅ ይጠባበቅ ጀመር ።

«ሥርጌይ በሩን ክፈተው ። ማን ሊሆን ይችላል?» አለችው ሉድሚላ ።

ባለመደናገጥ እጅዋን ቀሚሷ ኪስ ውስጥ ከተተች ። እና እናትን ፡ —

«ዣንዳርሞች ከሆኑ የመጡት እርስዎ ፔላጌያ ኒሎቭና እዚያ ጥጉ ዘንድ ሂደው ይቁሙ ፤ አንተ ደግሞ ሥርጌይ...» ብላ ሳትጨርስ ፡ —

«አውቃለሁኝ!» አለ ልጁ በሩን ሊከፍት እየሄደ ።

እናት ፈገግ አለች ። ይኸ ዝግጅት የሚያሳስባት መሆኑ አብቅቶአል ። ክፉ መከራ ይደርስብኛል ብላ የመሥጋት ሁኔታ የላትም ።

ወደ እነርሱ ዘንድ የመጣው ግን ሌላ ማንም ሳይሆን ቁመተ አጭሩ ዶክተር ነው ። እርሱም በተቻኮለ አነጋገር ፡ —

«መጀመርያ ነገር ኒኮላይ ተይዞ ታሥሮአል ። አሃ! እና በዚህ ምክንያት ነው ማለት ነዋ እርስዎ እዚህ የመጡት ፤ ኒሎቭና! ኒኮላይ ተይዞ በታሠረበት ጊዜ እርስዎ እቤት አልነበሩምን?» አላት ።

«እዚህ እንድመጣ ልኮኝ ነበር» አለችው ።

«እ-ሀ! ይኸ ምንም ያህል ጠቀሜታ ያለው ጉዳይ አይመስለኝም!.. ሁለተኛው ነገር ደግሞ የፓቬልን ንግግር ጥቂት ወጣቶች አንድ አምስት መቶ ኮፒ ያህል አራብተዋል ። የተባዙትን ጽሑፎች አይቻቸዋለሁኝ ። መጥፎ አይደሉም ። ግልጽ የሆኑ እና ሊነበቡ በሚችሉ ሁኔታዎች ነው ያራቡዋቸው ። ዛሬ ማታ ከተማው ውስጥ በመበተን ሊያሠራጩዋቸው ይፈልጋሉ ። እኔ ግን ድርጊቱን ተቃውሜአለሁኝ ። ከተማ ውስጥ መበተን የሚሻለው በማተምያ የተለቀመውን ሲሆን ይኸንን እነርሱ ያራቡትን ደግሞ ለሌላ ቦታ መጠቀሙ የሚሻል ይመስለኛል» አለ ።

«ስጡኝ ። እኔ ለናታሻ እወስድላታለሁኝ!» አለች እናት በችኩልነት መንፈስ ።

የልጅዋ የፓቬልን ንግግር በተቻለ ፍጥነት በከተማው ውስጥ ለመበተን በጣም ተቻኩላለች ። ከልጅዋ አንደበት የፈለቁትን ቃላቶች በመላው ዓለም ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ለማዳረስ ተቻኩላለች ። እና ስለዚህም የሚሰጠውን መልስ እየተጠባበቀች ዐይኖቿን ዶክተሩ ፊት ላይ ትክል አድርጋ እባክህን እኔ ይዤ ልሂድ በሚል ሁኔታ ትመለከተዋለች ።

«ይኸንን አሁን ማድረግ ይኑርብዎ-አይኑርብዎ እግዚአብሔር ይወቀው! አሁን ለስድስት ሰዓት ሃያ ጉዳይ ነው ። ከቀኑ በስምንት ሰዓት ከአምስት ደቂቃ



ተነስቶ አሥራ አንድ ተሩብ እዚያ ሊያደርስዎ የሚችል ባቡር አለ ። ያን ጊዜ ሰዓቱ መሸት ይላል ። ይሁን እንጂ ይኸን ያህልም ገፋ ያለ ምሽት አይደለም ። ዋናው ቁም ነገር ይኸ አይደለም…» አለ ዶክተሩ ።

«አዎን ቁም ነገሩ እርሱ አይደለም!» አለች ሉድሚላ ከስተር ብላ ።

«ታዲያ ምንድነው?» በማለት እናት ወደ ዶክተሩ እየተጠጋች ጠየቀች ። ቀጠል አድርጋም ፡ —

«ሥራው በሚገባ መከናወኑ ነው ዋናው ነገር…» አለች ሉድሚላ። የእናትን ሁኔታ ትክ ብላ ታስተውላለች ። ከዚያም እጅዋን ግንባሯ ላይ ጣል እያደረገች ፡ —

«ለእርስዎ ይኸንን ተግባር ማከናወን አደገኛ ነው ።» አለቻት ።

«ለምን?» በማለት እናት አጥብቃ ጠየቀች ። ዶክተሩ ፈጣን በሆነ እና ቁርጥ-ቁርጥ በሚል ድምፅ ፡ —

«ምክንያቱም ከቤት የወጡት ኒኮላይ ከመያዙ ጥቂት ሰዓት ቀደም አድርገው ነው ። የናታሻ አክስት ነዎት በመባል ወደሚታወቁበት ፋብሪካ ይሄዳሉ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም በሕግ እንዳይሠራጩ የሚከለከሉ የሕቡዕ ጋዜጦች ፋብሪካው ውስጥ ተሠራጭተው ይገኛሉ ። ይኸ ሁሉ ሁኔታ እርስዎን ለማስጠርጠር ትናንሽ ፍንጮች ሁነው ይገኛሉ» በማለት ተናገረ ።

«ማንም እኔነቴን ለይቶ አያውቅም!» በማለት እናት በጉጉት ተናገረች ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ ፡ —

«ወስጄ ጽሑፎቹን ካስረከብኩኝ በኋላ ስመለስ ተይዤ የት እንደነበርኩኝ ብጠየቅ…» ካለች በኋላ ለጥቂት ጊዜ ምንም ሳትናገር ቆየች ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ ጉልህ በሆነ ድምጽ ፡ —

«ምን እንደምመልስላቸው አውቃለሁኝ ። ጽሑፉን ካስረከብኩኝ በኋላ በቀጥታ ወደ ወዝ-አደሮች የሠፈራ ቦታ እሄዳለሁኝ ። እዚያ አንድ ጓደኛ አለኝ ። ሲዞቫ ይባላል ። ከፍርዱ በኋላ እርስ በእርሳችን ለመጽናናት እርሱ ቤት ሄድኩኝ እላለሁኝ ። የእርሱ የወንድሙ ልጅም ተይዞ ታሥሮ ነበር ። ሲዞቫ እኔን ይደግፋል» አለች ።

የእርሷን ምኞት እንዲያሟላላት እና ድርጊቱንም ለማፋጠን በመጓጓት አጥብቃ መጠየቋን ቀጠለች ። በመጨረሻ እሺ ይሁን አሏት ።

«እሺ ይዘው ይሂዱ!» በማለት ዶክተሩ ቅር እያለው ፡ ተናገረ ።

ሉድሚላ ምንም አልተናገረችም ። በሃሣብ ተውጣ ከወዲያ-ወዲህ ትንጎራደዳለች ። ፊቷ ክስት እና ጥውልግ ያለ ከመሆኑም በስተቀር የተወጣጠሩት የአንገቷ ጅማቶች ጭንቅላቷ ቅንጥስ ብሎ ደረቷ ላይ እንዳይወድቅ ምንኛ ተውተርትረው ለመደገፍ እንደሚጣጣሩ ይታወቅባቸዋል ። እናት ይኸንን አስተውላለች ። ፈገግ አለች ፡ —

«እናንተ ስለእኔ ነው የምትሠጉት! ስለራሳችሁ ግን በፍጹም አትሠጉም...» አለች ።

«እንዴ ! እንሠጋለን እንጂ ! የመሥጋት ግዴታ አለብን» አለ ዶክተሩ ። ቀጠል አድርጎም ፡ —

«ጉልበታቸውን ጠቀሜታ ለሌለው ጉዳይ የሚያባክኑትን ስንመለከትም እጅግ አድርገን እንቃወማቸዋለን ። እሺ ። እንግዲህ የንግግሩን እትሞች ባቡር ጣቢያ አምጥተን እንሰጥዎታለን...» አላት ።

እንዴት በመሰለ ሁኔታ እንደሚሰጣትም አብራርቶ አስረዳት ።

«እሺ እንግዲህ መልካም ዕድል እመኛለሁኝ!» አለ ንግግሩን ሲጨርስ ።



ከቤት ወጥቶ ሲሄድ ግን በአንዳች ነገር ቅር የተሰኘ ይመስላል ። ሉድሚላ ወደ እናት ዘንድ መጣች ።

ረጋ ብላ እየሳቀች ፡ —

«የእርስዎን ሁኔታ ተገንዝቤዋለሁኝ...» አለች እናትን ።

የእናትን እጅ ጨብጣ ያዘች ። ከዚያም አሁንም እንደገና ከወዲያ-ወዲህ ትንቆራጠጥ ጀመር ። በኋላ !

«እኔም ልጅ አለኝ ። አሥራ ሶስት ዓመቱ ነው ። የሚኖረው ግን ከአባቱ ጋር ነው ። ባለቤቴ ረዳት ዐቃቤ-ሕግ ነው ። እና ልጄም ከእርሱ ጋር አብሮ ይኖራል ። ምን ይሆን ይሆን? ብዙውን ጊዜ የማስበው ይኸንን ነው...»አለች ድምፅዋ ተቋረጠ ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ

«በዓለም ላይ ወደር የማይገኝላቸው ጥሩ ሰዎች ናቸው ብዬ ለምገምታቸው ሕዝቦች ጠላት በሆነ ሰው አስተዳደግ ሥር ልጄ ያድጋል ። የገዛ ራሴው ልጅ ተመልሶ የኔው ጠላት በሚሆንበት ሁኔታ ሊያድግ ይችል ይሆናል ። ከእኔ ጋር ላኖረው አልችልም ። እኔ የምኖረው በሕቡዕ እና በፈጠራ የመጠሪያ ስም ነው ። ካየሁት ስምንት ዓመት ሆነኝ ። ስምንት ዓመት! ጊዜው እንዴት እንዲህ ይበርራል!» አለች ።

ወደ መስኮቱ ሄዳ ቆመች ። ከዚያም የገረጣውን ባዶ ሰማይ ታስተውል ጀመር ። ቀጠል አድርጋም ፡ —

«ከእኔ ጋር አብሮኝ የሚኖር ቢሆን ኖሮ ጠንካራ እሆን ነበር ። እንዲህ ሳያሰልስ ልቤን የሚቆረጣጥመኝ የልብ ቁርጥማት ይተወኝ ነበር... ሞቶ ቢሆን ኖሮ ደግሞ ለእኔ ሁኔታው ቀላል በሆነልኝም ነበር...» አለች ።

«የእኔ ውድ ምሥኪን!» በማለት እናት አየሩን

ደህና አድርጋ ወደ ውስጥ ዋጥ አደረገች ። ልቧ በህፀን ስቅጥጥ አለ ። ሉድሚላ መራር ፈገግታ ፈገግ እያለች ፡ —

«እርስዎ እንደምን ያሉ ዕድለኛ ነዎት! እናት እና ልጅ ተመሳሳይ የሆነ ዓላማ ኖሮአቸው ጎን-ለጎን መቆማቸው ግሩም ድንቅ የሆነ ጉዳይ ሲሆን ፤ ይኸንን መሳይ ድርጊት ደግሞ ሁልጊዜ የማይደርስ እና አልፎ-አልፎ ብቻ የሚደርስ ድርጊት ነው!» አለች ።

«አዎን ። ግሩም ነው!» አለች እናት በራሷ እየተደነቀች ። ከዚያም ምሥጢር የምታወራ ይመስል ድምጿን ዝቅ አድርጋ ፡ —

«እኛ ሁላችንም — አንቺ ፤ ኒኮላይ ኢቫኖቪች እና ዕውነትን የሚከተል ማንኛውም ሰው ቢሆን ፤ ሁላችንም ጎን-ለጎን የቆምን ነን! ድንገት ሁላችንም ተወላጅ ዘመዳሞች ሁነናል ። እና ሁላችሁንም እገነዘባችኋለሁኝ ። የምትናገሩትን ሁሉ ሁልጊዜ አልገነዘበውም ። ማናቸውንም ሌላውን ነገር ግን እገነዘባለሁኝ!» አለች ።

«አዎን ። ሁኔታው እርስዎ እንዳሉት ነው...» በማለት ሉድሚላ ቀስ ብላ ተናገረች ።

እናት እጅዋን ሉድሚላ ክንድ ላይ ጣል አድርጋ የምትናገራቸውን ነገሮች በአእምሮዋ ውስጥ የምታስተውላቸው ይመስል ቀስ እያለች በማንሾኳሾክ ሁኔታ ንግግሯን ትቀጥል ጀመር ።

«ልጆቻችን በዚች ዓለም ወደ ፊት ገስግሰው ዘልቀዋል ። እኔ ጉዳዩን የማስተውለው እንዲህ ነው ። ከየትኛውም ማዕዘን እየፈለቁ በመምጣት ለአንድ ዓላማ ተነስተው በዚች ዓለም ወደ ፊት እየገሰገሱ ይጓዛሉ። ከልቦች ሁሉ ንጹሃን የሆኑት ልቦች ፤ ከአእምሮዎች ሁሉ እጅግ ግሩም የሆኑት አእምሮዎች ክፉ ተግባርን በመቃወም ሃሠትን በጠንካራ እግሮቻቸው እያዳሽቁ ወደ ፊት ይገሠግሣሉ ። ወጣቶች እና ጤነኞች ናቸ



ው ። ያለ-የሌለ ጉልበታቸውም በተግባር ላይ የሚውለው አንድ ነገርን ለማከናወን ነው ። ይኸውም አንድ ነገር ፍትሕ ነው! የሰዎችን ሀዘን ለማስወገድ ፤ ከምድር ገጽ ላይ አንጉል እኗኗርን ለመጠራረግ አስቀያሚነትን ታግሎ ድል ለመንሳት ወደ ፊት ገሥግሠዋል ። ድልም ያደርጋሉ! ከመካከላቸው አንዱ እንዳለው አዲስ ፀሐይ ለኩሰው እንድታበራ ለማቀጣጠል ነው ። እና ደግሞ ያቀጣጥላሉ! ልበ-ሰባራዎችን በአንድነት ለማከማቸት ነው ። ያከማቻሉም!» በማለት ተናገረች ።

አዲስ ዕምነትን በልቧ ውስጥ በማቀጣጠል በልቧ እንደ ፍንጣቂ ፍንጥቅጥቅ እያለ የተነሳሳውን እና ለረዥም ጊዜያት ዘንግታው የቆየችውን የፀሎት ቃላት ታስታውስ ጀመር ።

«ልጆቻችን በሰዎች ልቦናዎች ውስጥ ፍቅርን እየዘሩ ፤ አዲሱን የሰማየ-ሰማያት መንገድ በመምራት መንገድ-መንገዱን እያሳዩ ፤ ከጥማቱ በማይረካ የመንፈስ እሳት ዓለምን በአዲስ የእሳት ብርሃን እያበሩ በሀቅ እና በምርምር ጎዳና ይጓዛሉ ። ለመላው ሰብአውያን ፍጡሮች ሲባል በልጆቻችን ፍቅር በተወለደው ነበልባል ውስጥ አዲስ ሕይወት ይበቅልበታል ። ከቶ ለመሆኑ ይኸንን ፍቅር ሊያጠፋው-ሊያዳፍነው የሚችለው ማን ነው? እኮ ማን? እንደምን ያለ ኃይል ሊደመስሰው ይችላል? እንደምን ያለ ኃይል ሊቋቋመው ይችላል? ይህች ዓለም እህ ብላ አምጣ የወለደችው ሲሆን ፤ ሕይወት ራሱም ድል አድራጊነቱን እየተጠባበቀ ነው ። ሕይወት ራሱ!»

በስሜቷ ኃይል የተዳከመች በመሆኗ ቁና-ቁና እየተነፈሰች እልፍ ብላ ሂዳ ተቀመጠች ። ሉድሚላ ራሷም ብትሆን አንዳች ነገር ከአግባብ ውጪ ጥሳ የምትገኝ እንዳትሆን በመፍራት ሁኔታ ፀጥ ብላ እና

ጥንቁቅ ሁና ተራመደች ። ዐይኖቿ ከፊት ለፊቷ ትክ ብለው እያስተዋሉ ክፍሉ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ትንጎራደድ ጀመር ። ያለወትሮዋ ረዝማለች ። ቀጥ ብላለች ። ይበልጥ ሎጋ ሁናለች ። ሰልካካ የሆነው እና ያልተጌያጌጠው ፊቷ በጥልቀት በሃሣብ የተዋጠ ሲሆን ፤ ከና ፍሮቿም በብስጩነት እርስ-በእርስ ግጥምጥም ብለዋል ። በክፍሉ ውስጥ የሠፈነው ፀጥታ እናትን ወዲያውኑ አረጋጋት ።

«ምናልባትም መናገር የማይገባኝን ይሆን እንዴ የተናገርኩት?» አለች እናት የሉድሚላን ቅር የመሰኘት ሁኔታ እያስተዋለች ረጋ ባለ እና ይቅርታ በመጠየቅ አኳኋን ።

ሉድሚላ ወደ እናት ዞር ብላ ፍርሃት በተቀላቀለው ሁኔታ መልከት አደረገቻት ። ከዚያም አንዳች ነገር የምትቆጣጠር በሚመስል ሁኔታ እጅዋን ዘርጋ አድርጋ ፈጠን ባለ ሁኔታ በመነጋገር ፡ —

«የለም ፤ የለም ። ልክ ነው የተናገሩት ። ይሁን እንጂ ሁለተኛ ስለዚህ ጉዳይ አናወራም ። ልክ እርስዎ በገለጹት ሁኔታ ይኑር ።» አለች ። ከዚያም ፡ —

«ቶሎ መነሳት ይኖርብዎታል ። ብዙ ጉዞ ከፊት ለፊትዎ ይጠብቅዎታል» በማለት ጨመር አድርጋ ስትናገር ድምፅዋ በጣም ረጋ ያለ ሁኔታ ነበረበት ።

«እንዴት እንደተደሰትኩኝ ባወቅሽው! የገዛ ልጄን ንግግር ፤ የሥጋዬ ቁራጭ ፤ የአጥንቶቼ ፍላጭ የሆነውን ልጄን ንግግር የታተመበትን ጽሑፍ ይዤ መሔድ ምንኛ አስደሳች ነው! የገዛ ራሴን ነፍስ እንደመስጠት ያለ ነው!» አለች ።

ፈገግ አለች ። ይሁን እንጂ ፤ ፈገግታዋ ግን ሉድሚላ ፊት ላይ ብቻ ያንጸባርቅ ነበር ። በወጣቲቱ ሴትነቺነት ደስታዋ እየቀዘቀዘባት መሆኑ ተሰማት ። እና ድንገትም በዚያ ኮስታራ በሆነ ልብ ውስጥ የራሷን



እሳት አፍስሳ ልትከትትባት ከፍተኛ ፍላጎት ተሰማት ። በደስታ በመፈንደቅ ላይ ያለውን ልቧን ይህቺኛይቱ ሴት እያስተዋለች ከደስታው እንድትካፈላት ከጀለች ። የሉድሚላን እጅ ያዝ አደረገችና ቀስ ብላ በማሻሸት ፡ —

«ውድ የኔ ልብ! ለመላው ሕዝቦች መንገድ-መንገዱን የሚመራቸው ብርሃን መኖሩን ማወቅ እንደ ምን ያለ ጥሩ ነገር ነው! እና ይህንን ብርሃንም ሁሉም ሰዎች የሚያስተውሉት ፤ የሚከተሉበት ጊዜ የሚመጣ መሆኑን ማወቅ እንደምን ያለ ታላቅ ደስታ ይሰጣል!» አለቻት ።

በእናት ትልቅ እና ደግ ፊቷ ላይ የፍርሃት ሁኔታ አረበበት ። ዐይኖቿ ጋሉ ። ቅንድቦቿ ለብልጭልጭታው ክንፍ ሰጥተው ያበርሩት ይመስል እርግብግብ-እርግብግብ አሉ ። እርዷነቷን ፤ ሁለንተናዋን ፤ እስካሁን ያወቀችውን እና የተሰቃየችበትን ማናቸውንም ነገር ሁሉ አዕምሮዋ በአንድ በትልቅ የማሰብ መጠቅለያ ጠቅልሎ ያንከባልለው ጀመር ። በፀደዩ ፀሐይ ተመራማሪ ሐይል ብሩኅ ሁኖ በበራው ልቧ ፤ ከጊዜ ጊዜ ብሩኅነቱ እየጨመረ እና እየሞቀ ፤ እየጋለ በሚሄደው ፤ እየበዛ-እየተራባ በሚዘልቀው በዚህ የበልግ ወራት ልቧ ውስጥ የእነዚህን ሃሣቦች ፍሬ ነገር ለቅሟ በመቋጠር ግልጽ-ጥርት ወደአሉ ቃላት ነት እያንገዋለለች በመልቀም ልቧ ውስጥ ትቋጥር ጀመር ።

«አዲስ አምላክ ለሰው ልጆች የተፈጠረላቸው ያህል ነው! ማንኛውም ነገር ለሁሉም — ሁሉም ነገር ለማንኛውም! እኔ ጉዳዩን የምመለከተው ይኸንን በመሰለ ሁኔታ ነው ። በሀቅ ፊት እኛ ሁላችንም ጓዶች ነን ። ሁላችንም የተዛመዱ ልቦች አሉን ። ሁላችን ዕውነት የተሰኘችው ወላጅ እናት ልጆች ነን!»

አሁንም እንደገና በስሜት ማዕበል ተዋጠች ። ንግግ
ሯን አቋረጠች ። አየሩን ደህና አድርጋ ዋጠች ። እጆ
ቿን በሰፊው ዘረጋች ፡ —

«እና እኔ ራሴ ‘ጓዶች’ የሚለውን ቃል ስሰማ
ልቤ ውስጥ ሆሄያቱ ጠልቀው ሲገቡ ይሰማኛል!»
አለች ።

ለማድረግ የፈለገችውን አደረገች ፡ — የሉድሚላ
ፊት እንደ በርበሬ ቀይ ሆነ ። ከናፍሮቿ ተንቀጠቀጡ ።
ረዣዥም እና ድቡልቡል የእንባ ዘለላዎች በጉንጮቿ
ላይ ዱብ-ዱብ እያሉ ይፈስሱ ጀመር ።

በልቧ ድል-አድራጊነት ለስላሳ የሆነ ደስታ ተደ
ስታ እና ረጋ ባለ ሁኔታ ፈገግ እያለች እናት ሉድ
ሚላን እቅፍ አደረገቻት ።

ሲሰነባበቱ ሉድሚላ የእናትን ፊት እየተመለከተች
ለስለስ ባለ አነጋገር ፡ —

«ከእርስዎ ጋር አብሮ መሆን ምንኛ ጥሩ እንደ
ሆነ ያውቁታልን?» አለቻት ።

## 29

ገና ከቤት እንደወጣች ቀዝቃዛው አየር ይገርፋት
ጀመር ። አፍንጫዋን ቀዝቃዜው ነደፈው ። ትንፋሿን
ከላይዋ ላይ ገፈፈው ። ቆም ብላ ‘ግራ-ቀኙን ተመለ
ካከተች ። ጥጉ ላይ አንድ መናኛ ልብስ የለበሰ የሠረ
ገላ ጋሪ ነጂ ቆሞአል ። ራቅ ብሎ ደግሞ አንድ ሰው
ዬ ጉብጥ-ጉብጥብጥ ብሎ መንገዱን ይሄዳል ። ከፊት
ለፊቱ ደግሞ አንድ ወታደር ጭንቅላቱ ትከሻዎቹ
ውስጥ ጥልቅ ብለው ገብተዋል ። እያሻሸ በፍጥነት
እርምጃ ይጓዛል ።

«ወደ ሱቅ የተላከ ወታደር ይሆናል» በማለት እያ
ሰበች እና በረዶው እግሯ ሥር ሿ-ሿ ማለቱ



እያስደሰታት ጉዞዋን ቀጠለች ። የባቡሩ መነሻ ሰዓት
ከመድረሱ በፊት ቀደም ብላ ባቡሩ ጣቢያ የደረሰች
ሲሆን በጽዳት ጉድለት ቆሻሻ የሆነው እና በጥቀርሻ
የተመላው የሶስተኛ ማዕርግ ተጓዦች ማረፍያ ክፍል
በሰዎች ተሞልቶ ተጨናንቆአል ። የመንገድ ሠራተኞ
ችን ፤ የሠረገላ ጋሪ ነጂዎችን እና ብዙ ቤት-የ
ለሽ የሆኑ እና ሕመምተኞች ምሥኪኖችን የውጪው
ብርድ የሶስተኛ ማዕርግ ተጓዦች ማረፍያ ክፍል
ውስጥ ገብተው እንዲጠጉ አስገድዶአቸዋል ። ክፍሉ ውስ
ጥ ተጓዦችም ጭምር የሚገኙ ሲሆኑ ፤ ከመካከላቸው
ም ጥቂት ገበሬዎች ፤ አንድ ከትንሽ አውሬ ቆዳ
የተሰራ ካፖርት የለበሰ ወፍራም ነጋዴ ፤ አንድ ቄስ
እና ፊቷ ላይ ጠቃጠቆ ያለባት ልጁ ፤ አምስት ወይን
ም ስድስት ያህል ወታደሮች እና ጥቂት አዟሪ
ነጋዴዎች ይገኙባቸዋል ። ሰዎቹ ሲጋራ ያጨሳሉ ። ያወ
ራሉ ። ገሚሶቹ ሻይ ገሚሶቹም ቮድካ ይጠጣሉ ። ምግብ
እና መጠጥ መሸጫው ውስጥ ካሉት መካከል አንዱ
ተንከትክቶ በሳቅ ፈነዳ ። የሲጋራ ጭስ ሁሉም ነገር
ላይ ይተንናል ። በሩ በተከፈተ ቁጥር ሲ-ጢ-ጢ-ጢ
እያለ የሚጮህ ሲሆን የመስኮቱ እጀታዎች ሲዘጉ
ቋ-ቋ በማለት ይንኳኳሉ ። ክፍሉ በትምባሆ እና
በአሣ ሽታ ተበክሏል ።

እናት መግቢያው ላይ ከሚገኝ ቦታ ተቀምጣ የባ
ቡሩን ሰዓት ትጠባበቅ ጀመር ። በሩፉ በተከፈተ ቁጥ
ር ቀዝቃዛ አየር ዘልሎ በመግባት ይገርፋታል ። ይኸ
ሁኔታ ስላስደሰታት በሩ በተከፈተላት ቁጥር ከቀዝቃ
ዛው አየር ሳብ አድርጋ ትውጣለች ። ብዙዎቹ ሰዎች
ቋጠሮዎች የያዙ ሲሆኑ ፤ ከሳዳቸው እና ከንዳቸው ላይ
የተጋገሩትን የበረዶ ክምሮች ሲያራግፉ ፤ ከዚያም ከጺ
ሞቻቸው እና ከሪዞቻቸው ላይ በረዶውን ሲያራግፉ
እየተቆጡ እየተነጫነጩ እና እየተሳደቡ የያዙዋቸው

ን ቋጠሮዎች ወለሉ ላይ ወይንም አግዳሚ ወንበር ላይ ይወራውሯቸዋል ።

አንድ የቆዳ ሻንጣ የያዘ ወጣት ሰው ወደ በሩ መጣ ። ወዲያው ፈጥኖ መልከት-መልከት በማድረግ በቀጥታ ወደ እናት ዘንድ ሄደ ።

«ወደ ሞስኮ ነውን የሚሄዱት?» በማለት ጠየቃት ።

«አዎን ታንያን ልጠይቅ ነው የምሄድ» አለችው ።

«እንሆ!» አላት ።

አጠገቧ ከሚገኝ አግዳሚ ወንበር ላይ ሻንጣውን አስቀመጠ ። ሲጋራውን አቀጣጠለ ። ባርኔጣውን አስተካከለ ። ከዚያም በሌላኛው በር ወጥቶ ሄደ ። እናት ቀዝቃዛውን የቆዳ ሻንጣ ዳሰስ-ዳሰስ እያደረገች ክንዷን ሻንጣው ላይ ካሳረፈችበት በኋላ በመርካት ሁኔታ ተውጣ በአካባቢዋ ያሉትን ሰዎች ዞር-ዞር እያለች ትቃኝ ጀመር ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ በመነሳት መውጫው አጠገብ ሂዳ ተቀመጠች ። በምትራመድበት ጊዜም ከባድ ያልነበረውን ሻንጣ ያለችግር አንጠልጥላ በመያዝ ራሷን በማቅናት የምታልፋቸውን ሰዎች ትመለከታለች ።

አንድ አጠር ያለ ካፖርት የለበሰ እና የአንገቱን ክሳድ ወደላይ የቀለበሰ ወጣት ሰው ፈጥኖ ወደ እርስዋ ዘንድ መጣ ። በዝምታ ወደጎን ከተራመደ በኋላ ባርኔጣውን ከራሱ ለማውለቅ እጁን ወደ ባርኔጣው ላከ ። ከዚህ ቀደም የምታውቀው መስሎ ተሰማት ። መልከት ስታደርገው በክሳዱ ውስጥ አንደኛው ዐይኑ እርሷን-እርሷን መልከት-መልከት የሚያደርግ መሆኑን አስተዋለች ። ትክ ብሎ ዐይኑን ሳይነቅል የሚያደርገው አመለካከት በጩቤ የመውጋት ያህል የሚሰማ ነበር ። ሻንጣውን የያዘችበት እጅዋ ይንቀጠቀጥ ጀመር ። ድንገትም ጭንቀቷ እየባሰ ሄደ ።

«ይኸን ሰው ከዚህ ቀደም አንድ ቦታ አይቸዋ



ለሁኝ» በማለት የት እንደሆነ ያየችው ለማስታወስ ታሰላስል ጀመር ። የሽንን አስተሳሰቧን ደስ ባልተሰኘችበት በእርሱ አመለካከት በመተካት ፤ ቀስ በቀስ ልቧን ሊያቀዘቅዛት የተነሳውን ሁኔታ እምቢኝ ለማለት እየሞከረች በማሰላሰል ተካችው ። ይሁን እንጂ ይኸ አስተሳሰብ አፏን እሬት-እሬት እያለው ጉሮሮዋ ውስጥ ይሞላ ጀመር ። እንደገና ዞር ብላ እርሱን ተመለከተችው ። ምን ማድረግ እንደሚያስፈልገው የሚያሰላስል በመምሰል አንዴ እዚህ አንዴም እዚያ እግሮቹን እያፈራረቀ በመትከል እዛው ቀድሞ እነበረበት አንድ ቦታ ላይ ቆሞአል ። ግራ እጁን ኪሱ ውስጥ ከተተ ። ቀኝ እጁን ካፖርቱ ላይ በሚገኙ ቁልፎች መሃል ከተት ያደረገ ሲሆን ይኸውም ሁኔታ ከግራ ትከሻው ይልቅ የቀኝ ትከሻውን ጎበር አድርጎታል ።

በእርሷነቷ ውስጥ ያለ አንዳች ነገርን ገንጥላ በመጣል የሚወድቅባት በመምሰል ተጠንቅቃ እና ዝግ ብላ ወደ አግዳሚ ወንበር ዘንድ ሄዳ ተቀመጠች ። ባለባት ጭንቀት ምክንያት አዕምሮዋን እንደምንም ለማስጨነቅ የኋላ-ኋላ ይኸንን ሰው ካሁን ቀደም ሁለት ጊዜ የት እንዳየችው ልታስታውስ ቻለች ፡ — አንድ ጊዜ ሪቢን ከእሥር ቤት ሲያመልጥ ገላጣው ሥፍራ ላይ በአጥር ጥግ በኩል ተታክኮ ቆሞ አይታዋለች ። ሌላ ጊዜ ደግሞ ፍርድ ቤት ውስጥ አይታዋለች ። ፍርድ ቤቱ ውስጥ ተቀምጦ የነበረው ሪቢንን ወደዬት እንደሄደ ሲጠይቃት ስህተተኛ በሆነ መንገድ መርታው ከነበረ የፖሊስ መኮንን ነበር ። ሰላዮች የሚከታተሉዋት መሆኑን ተገነዘበች ። ይኸ ምንም አያጠራጥርም ።

«ተያዝኩኝን?» በማለት ራሷን-በራሷ ጠየቀች ።

«ገና አልተያዝኩም ይሆናል»ብላ ትከሻዋን እየነቀነቀች ለራሷው መለሰች ።

«ተይዣለሁኝ!» አለች ከጥቂት ጊዜ በኋላ እውነትን እንደአመጣጡ ለመቀበል እየተገደደች ።

ሃሣቦች እንደ ነጸብራቅ አዕምሮዋ ውስጥ ፍንጥቅ-ፍንጥቅ እያሉ ሲመላለሱ ፤ አንዳችም ነገር ሳታስተውል ግራ-ቀኙን ትቃኝ ጀመር ።

«ሻንጣውን ትቼ ከዚህ ቦታ ልውጣ እና ልሂድ ይሆን?» በማለት አሰበች ።

ይኸኛው ሃሣቧ ደግሞ በሌላ በተሻለ ብሩኅ ሃሣብ ተቀየረ ፡ —

«እንዴት? የልጁን ቃል ትቼ ልሂድ? የልጁ ቃል በእነዚህ እጅ እንዲወድቅ ላደርግ?» በማለት አሰበች ።

ሻንጣውን አጥብቃ ያዘች ።

«ሻንጣውን ይዤው ልውጣና ልሂድ ይሆን? ሻንጣዬን እንደያዝኩኝ ልሩጥ ይሆን?» በማለት ታሰላስል ጀመር ።

እነዚህን የመሳሰሉት ሃሣቦች ከውጪ መጥተው የተጫኑዋት ጠላቶች ናቸው ። አዕምሮዋን የሚሠረሥሩት ሲሆኑ ልቧንም እንደ ጠንካራ ክር እየጠቀጠቁ ይደርቷታል ። የሃሣቦች ሕመም ከእርሷነቷ አራቋት ። ከፓኬል እና ከማናቸውም ለእርሷ ውድ ተወዳጅ ከሆኑት ሁሉ እንድትርቅ አደረጓት ። አስፈሪ በሆነ የሞት መዳፉ እየደጠጣት አንዳች አመጸኛ ኃይል ጫንቃዋን የሚጫናት ደረቷን የሚወግራት መስሎ ተሰማት ። ማጅራቷ ላይ ያሉት የደም ሥሮች በደም ተመልተው ትር-ትር ማለት የጀመሩ ሲሆን የደሟ ሙቀትም እስከጠጉሯ ጫፍ ወጥቶ በመንዘር ይሰማት ጀመር ።

ድንገትም አንድ ከፍተኛ ጥረት ለማድረግ አዕምሮዋ ውስጥ የሚጉላሉትን ሃሣቦች ወዲያ በመጣል ፤ እነዚህን ሁሉ እዚህ ግቡ የማይባሉ ሽባ የሆኑ ኢምንት የሀሣብ ፍንጣቂዎች በማስወገድ ራሷን ለራሷ ፤—



«ምን ያለሁ ነውረኛ ነኝ!» አለች ።

ወዲያውኑ ተሻላት ። በእርግጥም ደግሞ በብርታት የተመላች ከመሆኗም በስተቀር ፡ —

«ልጅሽን አታዋርጂ! ማንም የሚፈራ የለም!» በማለት አሰላሰለች ።

ዐይኖቿ አንድ አሰልቺ የሆነ አመለካከት ያስተውላሉ ። አዕምሮዋ ውስጥ የሪቢን መልክ ታያት ። የጥቂት ሰኮንዶች ማቅማማት ስለዚህ ሰው ማንነት ይበልጥ ዕውነተኛ እንድትሆን አደረጋት ። አሁን ልቧ ረጋ ብሎ ይመታል ።

«አሁን እንግዲህ ምን ሊከተል ነው?» በማለት ግራ-ቀኙን ስትቃኝ አሰላሰለች ።

ሰላዩ እርሷን-እርሷን በዐይኖቹ እየተመለከተ ለባቡር ጣቢያው ዘበኛ አንዳች ነገር በጆሮው ያሾኮሹክለት ጀመር ። ዘበኛው ሰላዩን ተመለከተው እና ወደኋላው ተመለሰ ። ሌላ ዘበኛ መጣ ። ሰላዩ የሚናገረውን ካዳመጠ በኋላ ፊቱን ኮስተር አደረገ ። ቁመት-ረዥም ፤ ፀጉረ-ሽበቶ እና ያልተላጨ ሽማግሌ ሰው ነበር ። ለሰላዩ በእሺታ መልክ ጭንቅላቱን ካወዛወዘለት በኋላ እናት ወደ ተቀመጠችበት አግዳሚ ወንበር አመራ ። ሰላዩ ተሠወረ ።

ዘበኛው ሳይቸኩል ኮስተር ብሎ እና እናትን እየተመለከተ ተጠጋ ።

«ብቻ ባልደበደቡኝ!» በማለት አሰበች ።

ፊት ለፊቷ ከቆመ በኋላ ለጊዜው አንዳችም ነገር አልተናገረም ።

«ምንድነው የምትመለከቺው?» አላት ።

«ምንም» አለችው ።

«ኧረባክሽ! አንቺ ሌባ! እንዴት አንቺ! በዚህ ዕድሜሽ ደግሞ እንዲህ ዓይነት ማጭበርበር ከየት ነው የለመድሽው! እ?» ብሎ ጮኸባት ።

ከአንደበቱ የሚወጡት ቃላት ፊት-ፊቷን እንዲ-
ሁለቱ ገረፏት ። የስድቡ አሰቃቂነት አገጩን ገንጣጥ
ለው የነቀሉት ያህል ፤ ዐይኖቿን ፡ ጎልጉለው ያወጧቸው
ያህል የሚሰማት ነበር ።

«እኔ? እኔ ሌባ አይደለሁም! አንተ ውሸታም!» በማ
ለት ከፍ ባለ ድምጽ ተናገረች ። ማናቸውም ነገር
ተለዋውጦባት ቁጡ እንድትሆን አደረጋት ። ሻንጣውን
ነካ አድርጋ ከፈተችው ።

«ተመልከቱ! ሁላችሁም ተመልከቱ!» በማለት ከተቀ
መጠችበት ተነስታ እና እፍኝ ሙሉ ወረቀቶችን
ከጭንቅላቷ በላይ ይዛ በጩኸት ተናገረች ። ከየአቅጣ
ጫው የመጡ ሰዎች ንግግር በጆሮዋ ውስጥ ይሰ
ማታል ።

«ምንድነው ነገሩ?»

«ምንድነው እርሱ?»

«ሌባ ነች ይላሉ...»

«ይቺን የመሰለች አዛውንት መሳይ ሴት? አበስኩ!
ወይ ጉድ!»

«እኔ ሌባ አይደለሁኝም!» በማለት እናት ድምፅዋን
ከፍ አድርጋ ተናገረች ። ስሜቷ እርሷን በከበቧት
ሰዎች ተዋጠ ።

«ትላንትና በፖሊቲካ እሥረኞች ላይ ፍርድ ተፈረ
ደባቸው ። ከመካከላቸው አንዱ የእኔ ልጅ ፓቬል
ቭላሶቭ ይገኝበታል ። ፍርድ ቤቱ ውስጥ ንግግር
አሰምቶ ነበር ።ያሰማው ንግግር ይኸው! ሕዝቦች አንብ
በው ሀቁን እንዲገነዘቡ በማለት ልወስድላቸው ነው...»
አለች ።

ከተሰበሰቡት መካከል አንዱ ሲፈራ-ሲቸር ወረቀቱ
ን ብድግ አድርጎ ወሰደ ። ወደላይ ከፍ አድርጋ ለተሰበ
ሰበው ሕዝብ በተነችው ።



«ይኸንን በማድረግዎ ይቀጡዎታል!» በማለት የአ
ንድ የፈራ ሰው ድምጽ ተሰማ ።

እናት ሰዎቹ ወረቀቶቹን እየተሻሙ በየካፖርቶቻ
ቸው እና ኪሶቻቸው ውስጥ ሲከትቱ ተመለከተች ።
ይኸ ሁኔታ አዲስ ብርታት ሰጣት ። በርሷነቷ ውስጥ
በሚፈስሰው ኩራት በደስታ ተመልታ ልቦና ገዝታ
እና ቀዝቀዝ ብላ በመርጋት ትናገር ጀመር ። ንግግ
ሯን በምትናገርበት ጊዜም ከሻንጣዋ ውስጥ ተበታኝ
ወረቀቶቹን እያወጣች አንዴ ወደ ግራ ፤ አንዴም ወደ
ቀኝ በየሰዎቹ አቅጣጫ ትበትናለች ። በእጃቸው ከእርሷ
ተቀብለው ለመውሰድ ለሚሻሙትም ትሰጣቸዋለች ።

«ልጄን እና ጓዶቹን ፍርድ ቤት ለምን እንዳቀ
ረቡዋቸው ታውቃላችሁን? እነግራችኋለሁኝ ። የእናትነ
ትን ልብ እና የሸበተ ፀጉሯን ማመን አለባችሁ ። ፍር
ድ ቤት እንዲቀርቡ ያደረጓቸው በሌላ በምንም ም
ክንያት ሳይሆን ዕውነትን አፍርጠው ለሕዝቦች የገ
ለጹ በመሆናቸው ነው! እና ደግሞ ይኸንን ዕውነት
የሚክድ አንድም ሰው አለመኖሩን በትላንትናው ቀን
ተገንዝቤአለሁኝ! አንድም ሰው!» አለች ።

የተሰበሰበው ሕዝብ ብዛቱ እየጨመረ ሄደ ። እና
ትን ሕዝቡ ክብብ አድርጎ በመክበብ ፀጥታ
በአካባቢው ሠፈነ ።

«ድህነት ፤ ረሀብ እና በሽታ! እነዚህ ናቸው ለሠርቶ-
አደር ሕዝቦች የተረፏቸው! ሁሉም ነገር ቢሆን እኛ
ን የሚቃወም ነው ። መላ ሕይወታችንን ዕለት-በዕ
ለት የመጨረሻ ጉልበታችንን እሚጥጠን በሥራ ላይ
እኖውላለን ። ምንጊዜም ጽዱ ሳንሆን ቆሽሸን ፤ ምንጊዜ
ም ተታልለን እንኖራለን ። ሌሎቹ ግን በእኛ የድካም
ውጤት ማናቸውንም ደስታ እና ጠቀሜታ የሚጎና
ጸፉ ሲሆኑ ፤ እኛን ግን በሰንሰለት ተሸምቅቆ እን
ደታሠረ ውሻ በድንቁርና ማጥ ውስጥ ወትፈው ያስቀ

ሩናል ። ምንም የምናውቀው ነገር የለም ። በፍርሃት እንድንዋጥ ያደርጉናል ። ማናቸውንም ነገር እንፈራለን! የኛ ሕይወት አንድ ረዥም እና ጭለማ የሆነ ሕይወት ማለት ነው!» አለች ።

«ዕውነት ነው!» የሚል ምላሽ ከተሰበሰቡት ሰዎች ዘንድ ይሰማ ጀመር ።

«ይኽን አፏን ዝጋላት!» አለ ሌላው ።

ከተሰበሰቡት ሰዎች ጀርባ እናት በፊት የነበረውን ሰላይ እና ሌሎችን ሁለት ጃንዳርሞች ተመለከተች ። በሻንጣዋ ውስጥ ተርፈው የነበሩትን በራሪ ወረቀቶች ለተሰበሰቡት ለመስጠት ትፋጠን ጀመር ። ይሁን እንጂ እጅዋ ወረቀቶቹን ለማውጣት ወደ ሻንጣው ሲቻኮል የሌላ ሰው እጅ ነካ አደረጋት ።

ጎንበስ እንደማለት እያለች ፡ —

«ውሰዱ ፤ ውሰዱ!» አለች ።

«ሂዱ ከዚህ!» በማለት ጃንዳርሞቹ የተሰበሰቡትን ሰዎች እየገፈታተሩ ጮኹ ። የተሰበሰበው ሕዝብ ወዶ ሳይሆን የግዱን ጃንዳርሞቹን መልሶ እየገፋ ቦታ በመልቀቅ ዞር ዞር ይል ጀመር ። የተሰበሰበው ሕዝብ ይህችን ጎላ-ጎላ ያሉ ዐይኖች ያሏትን ፀጉረ-ሽበቶ ሴት በታላቅ ፍቅር ጠጋ-ጠጋ በማለት ይቀርቧት ጀመር ። በሕይወት ውስጥ ለየብቻቸው ተገነጣጥለው የተገለሉ በመሆናቸው ፤ እርስ በእርሳቸው የተለያዩ እንዲሆኑ የተደረጉ በመሆናቸው ፤ በአሁኑ ጊዜ በአንድነት ተሰብስበው እንደነበልባል እየተንበለበሉ ከአንደበቷ የሚፈልቁትን ቃላት ምናልባትም ከተሰበሰቡት ሰዎች መሃከል የአብዛኛዎቹ ልብ በፍትህ መነፈግ ሲጠባበቅ የቆየውን ይኽንን መሳይ ንግግሯን ጥልቀት በተመላበት ስሜት ያዳምጣሉ ። እናት አጠገብ ተጠግተው የቆሙት ሰዎች በታላቅ ስሜት ተውጠው ዐይኖቻቸውን ዐይኖቿ ላይ ተክለው በፀጥታ ቆምዋል ።



ሞቃት የሆነ ትንፋሻቸው ከፊታቸው ላይ ረብቦ ታስተውላለች ።

«እርስዎ አሮጊቷ ቢሄዱ ይሻላል!»

«በደቂቃ ውስጥ ይይዙዎታል!»

«ኧረ እንዴት ያሉ ብርቱዋ ሴት ናቸው!»

«ከዚህ ቦታ ወይዱ! በየነበራችሁበት ቦታ ተመለሱ!» በማለት ጃንዳርሞቹ ሰዎቹን እየገፈታተሩ ወደ ፊት መጡ ። እናት ፊት ያሉት ሰዎች አለፍ-አለፍ ካሉ በኋላ እርስ-በእርሳቸው ይመለካከቱ ጀመር ።

ሰዎቹ የምትናገራቸውን ቃላት የሚያምኗት እና የሚገነዘቡ መሆናቸውን አወቀች ። ስለዚህም ቶሎ ቶሎ እየተፋጠነች ማናቸውንም የምታውቀውን ሁሉ ፤ እስከአሁን ኃያልነታቸውን የፈተነቻቸውን ሃሣቦች ሁሉ ዘክዝካ ትነግራቸው ዘንድ ፈለገች ። ንግግሮቿ የሚፈልቁት ከልቧ ከሚመነጭ ስሜት ነው ። የመዝሙር ዜማ ይፈጥሩ የነበሩ ቢሆኑም ድምፅዋ የተዘጋ እና ሻካራ በመሆኑ ልትዘምር አለመቻሏን በሀዘን ተገነዘበች ።

«የልጄ ንግግሮቹ ነፍሱን አሳልፎ ያልሸጠ እና ዕውነተኛ የሆነ የአንድ ወዝ-አደር ሰው ቃላት ናቸው! ዕውነተኛ የሆኑ ቃላትን በጥንካሬያቸው ለይታችሁ ልታውቋቸው ትችላላችሁ!» አለች ።

የጥቂት ወጣት ሰዎች ዐይኖች ፍርሃት እና ደስታ በተቀላቀለው ስሜት ይመለከቷታል ።

አንድ ሰው ደረቷን መታት ። አግዳሚው ወንበር ላይ ወደቀች ። የጃንዳርሞቹ እጆች የተሰበሰቡትን ሰዎች ትከሻ እና ክሳድ ጨምድደው በመያዝ ፤ ባርኔጣቸውን ከላያቸው ላይ እየገፈፉ ወደሌላ ክፍል በመወርወር በየሰዎቹ ጭንቅላቶች ላይ ይረባረቡባቸው ጀመር ። ማናቸውም ነገር እናት ዐይን ላይ ብዥ-ብዥ

በማለት ይዋልል ጀመር ይሁን እንጂ የመጨረሻ ጉል በቷን እንደምንም በማጠራቀም ፡ —

«ደጋግ ሰዎች ሆይ ፤ አንድ ታላቅ ኃይል ለመሆን በአንድነት ተባብራችሁ አብሩ!» አለች ።

አንድ ጃንዳርም እንደ ዲጅኖ ጠፍጣፋ በሆነ እ ጁ ክሳዷን አንጠልጥሎ ወደላይ ካነሳት በኋላ እያ ወዛወዛት ፡ —

«ይኸንን አፍሽን ዝጊ!» አላት ።

ጭንቅላቷ ከግድግዳው ጋር ተጋጨ ። ለአንድ ቅጽ በት የፍርሃት ጭጋግ ልቧን ዞረው ። ይሁን እንጂ ብርታት የፍርሃትን ጭጋግ ጠራርጎ ስሜቷ ከፍ ከፍ በማለት ተነሳሳ ።

«ሂጂ!» አለ ጃንዳርሙ ።

«እንዳችም ነገር አትፍሩ! ከምትኖሩት ከዚህ ኑሮ የበለጠ መራር ነገር የለም...» አለች ለሰዎቹ ።

«ዝም በይ ብየሻለሁ!» አለ ጃንዳርሙ ።

ጃንዳርሙ እጅዋን ይዞ ገፋት ። ሌላኛው ጃንዳርያ ሌላኛውን እጅዋን ይዞ ለሁለት ሁነው ይዙዋት ሄዱ ።

«...በየዕለቱ ልብህን ከሚሠረሥራት እና ነፍስ ህን ከሚጎረድማት የበለጠ የለም!»

ሰላዩ ፊቷ ላይ እጁን በዛቻ እየወዘወዘባት ፊቷ-ፊት ከእርሷ ቀድሞ ሂዶ ፡ —

«ዝም በይ አንቺ ውሻ!» እያለ ጮኸ ።

ዐይኖቿ ብሩህ ሁነው ጎልተው አብርተዋል ። ከና ፍሮቿ ይንቀጠቀጣሉ ።

«መንፈሴን ሊገድሉት አይችሉም! ሕያው መንፈ ሴን ከቶ ምንም ቢሆን ሊገድሉት አይችሉም!» በማ ለት በሚያዳልጠው የድንጋይ መንገድ ላይ በእግሮቿ ቆንጠጥ አድርጋ በመርገጥ ድምፅዋን ከፍ አድርጋ አሰማች ።

«አንቺ ውሻ!» ይላታል ሰላዩ ።



ሰላዩ ፊቷን በቡጢ መታት ።

«ይችን አስቀያሚ አሮጊት እንዲህ ምቧን አቅም ስልኝ!» የሚል የስድብ ድምፅ ተሰማ ።

ለአንድ ለተወሰነ ጊዜ እናት በአንዳች ጥቁር እና ቀይ ቀለም ዐይኗ የታወረ መሰላት ። ጨው-ጨው የሚል የደም ጣዕም አፏን ሞላው ።

አጫጭር በሆኑ የእንክሮ ንግግሮች ተነሳሳች ፡ —

«እንዲህ ብለህ እንዳትነካት!»

«ሰዎች ፤ ወደዚህ ሰብሰብ በሉ!»

«አንተ ፈሪ ቡከን! ቀይ አንተ!»

«ምሱን አቅምሱት!»

«አስተሳሰባችንን ማቁሰል-ማድማት አይችሉም!»

አንገቷን ጀርባዋን እየጨመደዱ ያንገላቷት ጀመር ። ጀርባዋ ላይ ፤ ጭንቅላቷ ላይ ይወግሯት ጀመር ። በጩ ኸት ፤ በዋይታ ፤ በፉጨት ማዕበል ሁሉም ነገር በግ-በግ እያለ ይመሰቃቀል ጀመር ። አንዳች ከባድ ነገር ጆሮዋ ላይ መትቷት ጭው አለባት ። ጉሮሮዋን ተሰማ ት ። አነቃት ። መሬት ከዳት ። ጉልበቶቿ ተብረከረኩ ። ስል እና ሹል የሆነ የሀኪም መቅደጃ ቢላዋ ላይ ባዶ እግሯን የቆመች መሰላት ። ሰውነቷ ከበዳት ። ረዳት-አልባ ሁና ትወዛወዝ ጀመር ። ዐይኖቿ ግን ብሩህነታቸው አላከተመም ። ከዚህ ቀደም በምታውቃ ቸው እና በምታፈቅራቸው ጠንካራ እና ብሩህ የሆኑ የጓዶች አመለካከቶች ጋር የእርሷ አመለካከቶች በሃሣቧ ተያይተው ገጠሙ ።

እጅዋን ከጃንዳርሙ ላይ መንጭቃ በማውጣት የበ ራፉን እጀታ አጥብቃ ያዘች ።

በበሩ በኩል ገፉአት ።

«ዕውነትን የቀረው ቀርቶ የደም ውቅያኖስ እን ኳን ሊያሰምጣት አይችልም!» አለች ።

እጅዋ ላይ መቷት ።

«እናንተ ደደቦች! ይበልጥ እንድንጠላችሁ ብቻ ፣ ነው የምታደርጉት! ማንኛውም ነገር በእናንተው ጭን ቅላት ላይ ተመልሶ ያርፋል!» አለች ።

አንድ ጃንዳርም አንገቷን አነቃት ።

«አሳዛኝ ፍጥረቶች» አለች ። ግቢ-ነፍስ ፤ ውጪ-ነፍስ ወደላይ-ወደላይ እየተነፈሰች ።

ይኸንን ንግግሯን የሰማ አንድ ሰው ስቅስቅ በማለት አምርሮ አለቀሰ ።

እ. ኤ. አ. 1906 — 1907 ዓ. ም.።

## ድህረ መቅድም ።

«እናት» የተሰኘው ይኸ መጽሐፍ የተጻፈው በ1906 ዓ. ም. ማብቂያ እና በ1907 ዓመተ-ምህረት መጀመሪያ ላይ ሲሆን ይኸውም ጊዜ ጎርኪይ ከሀገሩ ውጪ ይኖር የነበረበት ጊዜ ነበር ። የመጽሀፉ ክፍል አንድ የተጻፈው ጎርኪይ አሜሪካ በነበረበት ጊዜ ሲሆን ፤ ክፍል ሁለት ደግሞ የተጻፈው ጣልያን ሀገር በነበረበት ጊዜ ነበር ።

ይኸ መጽሐፍ ለመጀመርያ ጊዜ ታትሞ ለአንባብያን የቀረበው ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ሲሆን ፤ ይኸውም ከ 1906 — 1907 ዓ. ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ «አፕልተን ማጋዚን» በተሰኘው መጽሔት ላይ አሜሪካን ሀገር ኒውዮርክ ውስጥ ነበር ። በአፕሪል ወር 1907 ዓ. ም. ደግሞ በመጽሐፍ መልክ ተዘጋጅቶ ኒውዮርክ ከተማ ውስጥ በዲ አፕልተን እና ኩባንያው የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት ታትሞ ወጣ ። በጁን ወር 1907 ዓ. ም. በርሊን ከተማ ውስጥ በሩስያኛ እና በጀርመንኛ ቋንቋ ታትሞ ወጣ ። በዚሁ ዓመት ደግሞ «ጓዶች» በሚል ርእስ የሆደር እና ስቱይ ግንታን ማተምያ ድርጅት መጽሐፉን ሎንዶን ውስጥ አትሞ አወጣው ። በ 1908 እና 1912 ዓ. ም. መጽሐፉ በተጻፈበት በሩስያኛ ቋንቋ በርሊን ውስጥ እንደገና ለ 2 ኛ እና ለ 3 ኛ ጊዜ ታተመ ።

ሩስያ ውስጥ መጽሐፉ ለመጀመርያ ጊዜ የታተመው ከ 1907 — 1908 ዓመተ ምህረት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ «ዝናንዬ» («ዕውቀት») በተሰኘው መጽሔት

ላይ ቢሆንም መጽሐፉ «ዝናንዬ» በተሰኘው መጽሔት
ላይ ልክ ጎርኪይ እንደጻፈው ታትሞ የወጣ ሳይሆን
በጊዜው በነበረው የሳንሱር ቁጥጥር ምክንያት ፣ ተሠ
ርዞ እና ተደልዞ ነበር ። ይኸም ሁሉ ከተፈጸመ በ
ኋላ እና «እርማት» ከተደረገበትም በኋላ ፤ በዚያን ጊዜ
የዛሩ መንግሥት መናገሻ ከተማ በነበረው ፒተርቡ
ርግ ውስጥ ተቋቁሞ ይገኝ የነበረው «የፐሬስ ኮሚቴ»
በጁላይ ወር 1907ዓ. ም. መጽሐፉ በየጊዜው ታትሞ
የወጣበት «ዝናንዬ» መጽሔት ቅጂዎች እንዲታፈሱ፡ ትዕ
ዛዝ ያስተላለፈ ከመሆኑም በስተቀር የመጽሐፉ ደራሲ
ም ተይዞ እንዲመረመር እንዲደረግ ትዕዛዝ ተላለፈ ።
በደራሲው ጎርኪይ ላይ ተንጠልጥሎ ያንዣብብበት
የነበረው ቅጣት የስምንት ዓመት ከባድ የእሥራት
ቅጣት ነበር ።

መጽሐፉ ሳይሠረዝ እና ሳይደለዝ ሙሉ-በሙሉ
በሩስያኛ ቋንቋ ታትሞ የወጣው የጥቅምቱ የሩስያ
ሶሻሊስት ሬቮሉሺን ከፈነዳበት ከ 1917 ዓ. ም. በኋላ
ነው ። የመጽሐፉ አታሚዎችም «ዥዝን ኢ ዝናንዬ»
(«ሕይወትና ዕውቀት») የተሰኙት ነበሩ ።

ጎርኪይ በሕይወት በነበረበት ዘመኑ ደጋግሞ በደብ
ዳቤዎቹ አማካይነት እንደገለጠው ሁሉ ፤ ይህ ልብ
ወለድ መጽሐፉ ዕውነተኛ በሆኑ ታሪካዊ ድርጊቶች
ላይ ተመሥርቶ የተጻፈ ሲሆን ፤ ከዕውነተኛ ድርጊ
ቶች መካከልም ኒዥኒ ኖቭጎሮድ ከተማ ወጣ ብሎ
በሚገኝ የፋብሪካ አካባቢ ሶርሞቮ በተሰኘ ቦታ ሜ
ይ ፡ 1 ቀን 1902 ዓ. ም. የተካሄደው የወዝ-አደሮች ቀን
የሰልፍ በአል ይገኝበታል ። ይሁን እንጂ «እናት» የተሰ
ኘው ይኸ የጎርኪይ መጽሐፍ ሰፋ ያለ ታሪካዊ
ድርጊቶችንም ያቀፈ ነው ። የእነዚህን ድርጊቶች መሠ
ረተ-ምክንያት ጠልቆ በመመራመር እና የሩስያ ወዝ-
አደር መደብ በትግሉ ያከማቻቸውን ልምዶች በማጠ



ቃለል ፤ በወዝ-አደሩ መደብ እና በገዢ መደቦች መካ
ከል ወሳኝ የሆነ ትግል መካሄዱ ከቶ ምንም ቢሆን
የማይቀር መሆኑን እና የበዝባዥ ሥርዓትም መደም
ሰሱ የማይቀር መሆኑን ጎርኪይ በዚህ መጽሐፍ
ሊያሳይበት ችሎአል ። ምንም እንኳን መጽሐፉ በአብዛ
ኛው የሚያተኩረው የመጀመርያው የሩስያ ሬቮሉሺን
ሊፈነዳ ውስጥ-ውስጡን ይብላላ በነበረበት ጊዜ ይ
ታይ የነበረውን አንድ የተወሰነ ታሪካዊ ወቅት ቢ
ሆንም ፤ ለወዝ-አደሩ ሬቮሉሺን ይደረግ የነበረውን አጠ
ቃላይ መሰናዶም መጽሐፉ ያመለክታል ። የወዝ-አደሮች
እና የገበሬዎች የፖለቲካ ንቃተ-ሕሊና እንደምን በመ
ሰለ ሁኔታ ተመሥርቶ ይዳብር እንደነበር እና እንደ
ዚሁም ተግባራቸው ሬቮሉሺን ማካሄድ የነበረ የለ
የላቸው ሬቮሉሺናዊ ካድሬዎች እንዴት እንደተመሠ
ረቱም መጽሐፉ ያሳያል ።

ጎርኪይ ይኸንን መጽሐፉን መጻፍ በጀመረበት
ጊዜ መጽሐፉን ለመጻፍ እንዲችል የሚያበቁት እያ
ሌ ተጨባጭ መረጃዎች ነበሩት ። እርሱ ራሱም ለብ
ዙ ዓመታት በሬቮሉሺናዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ
ተሳታፊ ነበር ።

በሬቮሉሺናዊ ተግባሩ ምክንያት ከአንድ ጊዜ በላ
ይ ተይዞ የተመረመረ ከመሆኑም በስተቀር ፤ ሁለት
ጊዜያት ተይዞ ኒዥኒይ ኖቭጎሮድ እሥር ቤት ታሥሮ
አል ። ከዚያም በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ታጅቦ ቲፊሊስ
ወደተሰኘች ከተማ ከተጋዘ በኋላ የሜቴኺ ግንብ
ቤት ተብሎ ይጠራ በነበረ እሥር ቤት ውስጥ ታሥ
ሮአል ። አርዛማስ በተሰኘ ቦታ በግዞተኛነት ተግዞ የነ
በረ ከመሆኑም በስተቀር ፒተርቡርግ ከተማ ውስጥ
የጴጥሮስ እና የጳውሎስ ምሽግ እየተባለ ይጠራ በነበ
ረ እሥር ቤት የተፈረደበትን የእሥራት ጊዜ አገባድ
ዶአል ። ከየእሥር ቤቶቹ ከተለቀቀ በኋላም ፤ ቀንም ሆነ

ሌሊት ሰላይ የሆኑ ነጭ ለባሾች ክትትል የማይለየው የነበረ ከመሆኑም በስተቀር ፤ ዣንዳርሞች በየጊዜው ለጥየቃ ትፈለጋለህ እያሉ ይወስዱት ነበር ። «የተረፈኝ ነገር ቢኖር በየጊዜው ዣንዳርሞች ዘንድ እየቀረብኩ በብዕሬ አማካይነት ቃሌን መስጠት ብቻ ነው ። በብዕሬ ለምጽፈው ለየአንዳንዱ መሥመር አምስት-አምስት ኮፔክ መሀለቅ ቢከፈለኝ ኖሮ እንኳን ብዙ የገንዘብ ክምችት ሊኖረኝ በቻለም ነበር» በማለት ጎርኪይ ጽፎአል ።

ሬቮሉሺናዊ ፓርቲ እንዲመሠረት የታገለው «ኢስክራ» («ብልጭታ») የተሰኘው የሌኒን ጋዜጣ ጎርኪይ በአስተሳሰቡ ሬቮሉሺናዊ እንዲሆን ታላቅ አስተዋጽኦን አበርክቶለታል ። «ፍጹም ሬቮሉሺናዊ የሆነ መንፈስ በላዬ ላይ ሊሰርጽብኝ የቻለው በቦልሸቪኮች ፤ ሌኒን ያቀርባቸው በነበሩት ጽሁፎች እና የሌኒንን አመራር ይከተሉ የነበሩ ምሁራን ያሰሙዋቸው በነበሩት ንግግሮች ፤ እንደዚሁም ያቀርቡዋቸው በነበሩት ጽሁፎቻቸውም አማካይነት ነበር» በማለት ጎርኪይ በስተኋላ ጊዜ ጽፎአል ። «ከ 1903 ዓ. ም. ጀምሮ ፤ እንደውም ከዚያም ጥቂት ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ ከቦልሸቪኮች ጋር በአንድነት አብሬ ነበርኩኝ» ብሎአል ። የመጀመርያው የሩስያ ሬቮሉሺን ከፍተኛ ደረጃው ላይ ደርሶ ሲቀጣጠል ጎርኪይም የሩስያ ሶሻል ዴሞክራሲያዊ ሠራተኞች ፓርቲ አባል ሆነ ።

«እናት» የተሰኘው ይኸ መጽሐፉ ታትሞ መውጣት በጀመረበት ጊዜ ፤ አንዳንድ ሂሥ-አቅራቢዎች ጎርኪይ ሊጽፍ በተነሳሳበት ነጥብ ላይ ያለው ዕውቀት መጠነኛ ከመሆኑም በስተቀር በመጽሐፉ ላይ፣ እንዲህ በግልጽ ያቀረባቸውን ዓይነት ባሕርያት በዕውን ሕልው ሁነው አንዳቸውንም ያየ አይደለም በማለት ተጣድፈው አሄሱት ። ይኸንን አባባላቸውን በመቃወም ጎርኪይ አንድ ጊዜ ሲናገር ፤ — «የሩስያን አኗኗ



ር እና የሩስያን ሥነ-ጽሁፍ እንደውም ደህና አድርጌ ጠንቅቄ አውቃለሁኝ ። ኧረ እንደውም ስለሚያውቀው ጉዳይ ከእኔ ይልቅ አሳንሶ የሚያቀርብ አለ ብዬ አላምንም ። ወደፊት የራሴን የሕይወት ታሪክ በምጽፍበት ጊዜ ስሞችን እና ቦታዎችን በዶኩሜንታዊ ማመሣከርያ እያጣቀስኩኝ በማቅረብ ፤ በታሪክ ውስጥ ሊደርሱ እንዴት ቻሉ ተብለው አሁን የሚገመቱትን ድርጊቶች እና ሁኔታዎች በተረጋገጠ ሁኔታ አመሳክራለሁኝ» ብሎአል ።

«እናት» የተሰኘው ይኸ የጎርኪይ መጽሐፍ ታትሞ ከወጣ በኋላ በመጽሐፉ ላይ ሂሥ ያቀርቡ የነበሩት ሰዎች ለወሰዱት አቋም ጎርኪይ ብዙ ጊዜ ደግሞ-ደጋግሞ በመጽሐፉ ውስጥ ስላቀረባቸው ቅጂ-ባሕርያት(prototypes) ጉዳይ ተናግሮአል ። በ1911 ዓ. ም. ባቀረበው ጽሁፍ ፤ የእናትን ባሕርይ ወርሳ በመጽሀፉ ላይ የቀረበችው «ኒሎቭና በ 1902 ዓ. ም. ሶርሞቮ ውስጥ በተደረገው የሜይ 1 ቀን የወዝ-አደሮች ሰልፍ ተሳትፈሻል ተብላ በመያዝ ለታሠረችው ለፒዮትር ዛሎሞቭ እናት ምስሏ ነች ። የፒዮትር ዛሎሞቭ እናት ድርጅቱ ውስጥ ተሳታፊ የነበረች ከመሆኑም በስተቀር ለሃይማኖት በዓል ወደ ገዳም የምትሄድ በመምሰልም ኢቫኖቮ-ቮዝኔሴንስክ ቀበሌ አካባቢ በጊዜው ሕገወጥ የነበሩ ልዩ-ልዩ ሥነ-ጽሁፎችን ታሠራጭ ነበር» ብሎአል ።

እና ኪሪሎቭና ዛሎሞቫ (1849 — 1938 ዓ. ም.) ከአያቱ ከካሺሪን ጋር ራቅ ያለ ዝምድና ያላቸው ሲሆን ጎርኪይ በሕፃንነት ዘመኑ ቤታቸው ይሄድ ስለነበር ያስታውሳታል ። የመጠጥ ሱሰኛ የነበረው የፋብሪካ ሠራተኛ ባሏ ሰባት ልጆች አስታቅፎአት ያለጊዜው ሞተ ። ልጅዋ ፒዮትር ሬቮሉሺናዊ በመሆን የሬቮሉሺኑን ፈለግ ሲከተል እናቱ እና ኪሪሎቭናም የ

እርሱን ፈለግ በመከተል በሬቮሉሺናዊ ድርጅቶች ተሳታፊ ሆነች ።

«እናት» በተሰኘው በዚህ በጎርኪይ መጽሐፍ ውስጥ ፓቬል ቭላሶቭ የተሰኘውን የእናትን ልጅ ባሕርይ ወርሶ የሚያንጸባርቀው ከ 1877 — 1955 ዓ. ም. ድረስ የሕይወት ዘመኑን ያሳለፈውን ፒዮትር ዛሎሞቭን ነው ። ፒዮትር ዛሎሞቭ በሕይወት ዘመኑ ያከናወናቸው አብዛኛዎቹ ድርጊቶች በዚህ መጽሐፍ አጽሙ-ታሪክ የተዘረዘሩት ይገኙበታል ።

በ 1892 ዓ. ም. ፒዮትር ዛሎሞቭ ኩርባቶቭ በተሰኘ ፋብሪካ ውስጥ በወዝ-አደርነት ተቀጥሮ ይሠራ ነበር ። በእነርሱ እርዳታም የወዝ-አደሮች የጥናት ክበብ ሊያቋቁም ችሎአል ። ከጥቂት ጊዜያት በኋላም ሰላዮች ማንነቱን ደርሰውበት እርሱ ሳያውቅ በምሥጢር በዓይነ-ቁራኛ ይከታተሉት ጀመር ። ከዚያም በኋላ በ 1898 ዓ. ም. የወዝ-አደሮች የተቃውሞ አድማ አደራጅ ተሃል በመባል ይሠራበት ከነበረው ፋብሪካ ተባረረ ። ከ 1900 ዓ. ም. ጀምሮ ሶርሞቮ በተሰኘ ፋብሪካ ውስጥ ይሠራ ጀመር ። ኒዥኒ ኖቭጎሮድ ውስጥ የሩስያ ሶሻል ዴሞክራሲያዊ ሠራተኞች ፓርቲ የመጀመሪያው ኮሚቴ አባል ነበረ ። በ 1902 ዓ. ም. የተካሄደውን የወዝ-አደሮች ሜይ ዴይ (ሜይ 1 ቀን) ሰላማዊ ሠልፍ ካደራጁት ንቁ እና ብርቱ ታጋይ ጓዶች መካከል አንዱ ከመሆኑም በስተቀር የወዝ-አደሮችን አርማ በግንባር ቀደምነት አንግቦ የመራ ሰው ነው ።

ጎርኪይ ይኸ ሰላማዊ ሰልፍ ከመካሄዱ ቀደም አድርጎ ጭምር ስለፒዮትር ዛሎሞቭ ማንነት ያውቅ ነበር ።

በበጋው ወራት 1902 ዓ. ም. ላይ የፒዮትር ዛሎሞቭ እጮኛ የሆነችይቱ ጆሴፊን ጋሸር ጎርኪይን ለመጠየቅ አርዛማስ ከተሰኘ ቦታ ሂዳ ነበር ። በስተኋላ ጊዜም በጻፈችው ትውስቷ «ከሶሻል ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ለጎርኪይ መልዕክት ማድረስ ነበረብኝ» በማለት ጆሴፊን ጽፋለች ።

ምንም እንኳን ጎርኪይ ፒዮትር ዛሎሞቭን እና ጓዶቹን በዓይነ-ሥጋ ተያይቶ የማያውቃቸው ቢሆንም ሶርሞቮ ውስጥ ሰላማዊ ሠልፍ በማድረጋቸው ምክንያት ተይዘው ከታሠሩ በኋላ ፤ ጎርኪይ ብዙ የሞራል እና የማቴርያል እርዳታ ያደርግላቸው ነበር ። ይኸንኑ ጉዳይ አስመልክቶ ሴትያጊን ረዘም ካለ ጊዜ በኋላ ሲጽፍ ፦ —

«የእሥር ቤቱ ኑሮ ለእኛ የፖለቲካ እሥረኞች ለሆንነው ሰዎች ከባድ ሆኖብን ነበር ። በእሥር-ቤቱ ምድረ-ግቢ መንሸራሸር ተከልክለን ነበር ። ጎብኝዎች እኛን እንዳይጠይቁም ተከልክለው ነበር… ስለዚህም ድርጊቱን በመቃወም እና ሁኔታውም ሊሻሻልን ይችላል ብለን ተስፋ በማድረግ ምግብ ላለመመገብ አደምን ። ይሁን እንጂ እርዳታቸው አይለየንም ብለን በአብዛኛው ተስፋ አድርገን የነበረው ወዝ-አደሮችን እና አሌክሴይ ማክሲሞቪችን (ጎርኪይ) ነበር ። በእርግጥም ጎርኪይ ረድቶናል… እኛ የምግብ አለመቅመስ አድማ አድርገን በነበረበት ጊዜ ኒዥኒይ ኖቭጎሮድ ውስጥ የተስቦ በሽታ ገብቶ ነበር ። የተስቦ በሽታ ገብቶ ስለነበር ፤ በሕይወት ጤናማ ሁኖ ለመቆየት የሚኖረን እድል አነስተኛ ስለሚሆን የምግብ አለመቅመስ አድማችንን አስጊነት የሚያሳስብ የማስታወሻ ጽሁፍ ጎርኪይ በሥውር ወደታሠርንበት ቦታ እንዲደርሰን አደረገ ። ዕውነትም ደግሞ ፤ ጓድ ዛሎሞቭ ከአምስት ቀናት በፊት ታሞ እሥር ቤቱ ሆስፒታል ውስጥ ይገኝ ነበር ። የምግብ አለመቅመስ አድማውን ከማድረጋችን በፊት አገረ-ገዥው ጥያቄዎቻችንን አሟላልን ። አሌክሴይ ማክሲሞቪች ጎርኪይ በዚህ ተግባሩ ብቻ

አልተወሰነም ። ለቤተ-ሰቦቻችንም የገንዘብ እርዳታ ያደር ግላቸው ነበር... ለፍርድ ስንቀርብ ከእኛ ጎን ቆመው የሚከራከሩልን ጥሩ-ጥሩ ጠበቆች እንዲኖሩንም አድር ጎአል» በማለት ገልጸአል ።

በኦክቶበር ወር 1902 ዓ. ም. ዛሎሞቭ ፍርድ ቤት የሚያሰማውን ንግግር ጽሁፍ ጎርኪይ ተመልክቶ ተገ ቢውን እርማት ያደረገበት ከመሆኑም በስተቀር የ ፍርዱን ሁኔታም በቅርብ ሁኖ ይከታተል ነበር ። ዛሎሞቭ በግዞት ይገኝ በነበረበት ጊዜ ጎርኪይ ሳይ ቋርጥ በየወሩ አስራ አምስት ሩብል ይልክለት የነበረ ከመሆኑም በስተቀር ተግዞ ከነበረበት ቦታ እንዲጠ ፋም ሦስት መቶ ሩብል ልኮለታል ። ዛሎሞቭ በግዞት ይገኝበት ከነበረበት ቦታ ካመለጠ በኋላ ሁለቱ ለመ ጀመሪያ ጊዜ ተገናኙ ። «ለመጀመርያ ጊዜ የተገናኘነው በ 1905 ዓ. ም. ፊንላንድ ውስጥ ነው ። አምሮበት በተሽ ቀረቀረው የበጋ ጊዜ የማረፍያ ቦታ የተገናኘን ሲሆ ን ለረዥም ጊዜ እንደሚተዋወቁ ጓደኞሞች ናፍቆት በተመላበት ስሜት ተሳሳምን ። ረዘም ላለ ጊዜ ተወያ የን ። በመካከላችንም ቅርብ የሆነ የመተሳሰብ እና የመ ግባባት መንፈስ ይታይ ነበር ። ይኸንን በሙሉ አ ፌ ለመናገር አችላለሁኝ ። ምክንያቱም ጎርኪይ አንድ ጊዜ ሲያጫውተኝ ጦርነት ላይ እኔን ለማዳን በመላ አካሉ አካሌን የሚሸፍንልኝ መሆኑን ገልጦልኝ ነበር...» በማለት ጽፎአል ።

«እናት» የተሰኘው የዚህ መጽሐፍ አጽመ-ታሪክ በአ ብዛኛው የተመሠረተው ሶርሞቮ ውስጥ በተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ቢሆንም የኒዥኒ ኖቭጎሮድ ፣ የፒ ተርቡርግ ፣ የኢቫኖቮ-ቮዝኔሴንስክ እና ሌሎችም ቦታ ዎች የሚገኙ እና ከእነርሱም ጋር ግንኙነት ያበጀ ባቸው የቦልሸቪክ ድርጅቶች ባከናወኗቸው ፡ ድርጊቶች እና መረጃዎች ላይም ጭምር ነው ።



የፓቬል ቭላሶቭ ገጸ-ባሕርይ በሕይወት በዕውን ይኖር ከነበረው ዛሎሞቭ ከተሰኘው ታጋይ ሬቮሉሺ ናዊ በስተቀርም ከሌሎች ታጋይ ቦልሸቪኮች ጋር ተመሳሳይነት አለው ። ጎርኪይ በሕይወት በነበረበት ዘመን የነበሩ ብዙ ሰዎች ሶርሞቮ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የተካፈሉ ፣ ተአምራዊ በሆነ ሁኔታ ከመያዝ ያመ ለጡ ፣ በ 1905 ዓ. ም. ላይ ሞስኮ ውስጥ ተካሂዶ በነበ ረው በትጥቅ አመጽ ላይ ንቁ ተሳታፊ የነበረውን እና የጎርኪይም ታጋይ ጓደኛው የነበረው ዲሚትሪ ፓቭሎቭም መጽሐፉ ላይ ፓቬል በተሰኘ ስም የተ ገለጸውን ገጸ ባሕርይ ትክክል ሁኖ የሚስማማው መሆኑን አንዳንዶች የሚናገሩት ያለምክንያት አይደ ለም ።

«ለረግረጋማው መሬት እንዲከፈል በተጠየቀው ኮፔክ» ምክንያት የተነሳውን ግጭት በሚመለከት ረ ገድ የቀረበው ዋናው ገጸ-ባሕርይ አሌክሳንደር ኒኮላየ ቪች ዶሮፌየቭ ነበር በማለት የገለጸ ከመሆኑም በስተ ቀር ፣ «እናንተ በበኩላችሁ ያሻችሁን ለማለት ትችላላ ችሁ ። ፓቬል ቭላሶቭ በመባል መጽሐፉ ላይ የቀረ በው የመጀመርያው ገጸ-ባሕርይ የሚጠቅሰው እኔን ሳይሆን አሌክሳንደር ኒኮላየቪች ዶሮፌየቭን ነው» ብሎአል ። ኒዥኒ ኖቭጎሮድ ውስጥ በሕቡዕ ሬቮሉሺናዊ ተግባሮችን ያከናውኑ የነበሩ እና በመጽሐፉ ላይ የተጠቀሰው ፓቬል ቭላሶቭ የሚያከናውናቸውን ዓይ ነት ተግባሮችም በዕውን ያከናውኑ የነበሩ ብዙ ሰዎ ችን ስም ዲሚትሪ ፓቭሎቭ ገልጸአል ።

«እናት» በተሰኘው የጎርኪይ መጽሐፍ የመጀመር ያው ክፍል ላይ የተዘረዘረው ድርጊት የሚያመለክተ ው እኛን ነው በማለት የሶርሞቮ ወዝ-አደሮች እርግ ጥኞች ሁነው ይናገሩ ነበር ። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ ባኩ ከተማ ውስጥ ይገኙ የነበሩት ወዝ-አደሮችም በበኩ

ላቸው ጎርኪይ «እናት» በተሰኘ መጽሐፉ ያንጸባረቀው
እኛ ያከናወንናቸውን ተግባሮች እና በእኛ ላይ የደ
ረሱብንንም ድርጊቶች ነው ይሉ ነበር ። ይኸንኑ አስመል
ክቶ ፓቬሴንኮ የተባለ ሰው ሲጽፍ ፡ — «መጽሐፉን
ገና የአሥራ አንድ ዓመት ልጅ ሁኜ አነብበው
ነበር ። በመጽሐፉ ውስጥ ተዘርዝሮ የቀረበው ሁሉ
ባኩ እና ቲፊሊስ በተሰኙ ከተማዎች ውስጥ ስመ-
ጥር የሆነው ፒዮትር ሞንቲን የተሰኘው ቦልሸቪክ
እናት ታሪክ ነው ብዬ አምን ነበር ። ትዝ እንደሚ
ለኝም የኔኑ ዓይነት ተመሳሳይ ዕምነት የነበራቸው
ሰዎች አያሌ ነበሩ ። ከዚያም በኋላ ባኩ ከተማ ው
ስጥ በነበርኩበት ጊዜ ሌሎች የበኩላቸውን አስተያየት
ሲሰጡ ፤ መጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት ባሕርያት (ገባ
ርያን-ታሪክ) የሚያንጸባርቁት የጎርኪይ ጥሩ ወዳጆ
ች የነበሩትን እና ከባኩ ወጣ ብሎ በሚገኘው ባይ
ሎቭ በተሰኘ ቦታ በዕውን ይኖሩ የነበሩትን ወዝ-
አደሮች ታሪክ ነው ሲሉ ሰማሁኝ» በማለት ጽፎአል ።
እና ኪሪሎቭና ዛሎሞቫ ፤ ልጅዋ ፒዮትር ፤ ጓደኞቻቸ
ው እና በቅርብ የሚያውቋቸውም ከጻፏቸው ትውስቶ
ች እንደምንገነዘበው ከሆነ ደግሞ ጎርኪይ «እናት»
በተሰኘው መጽሐፉ ላይ የአንዲት ሬቮሉሺናዊት ሴት
ባሕርይን አሟልቶ ለማቅረብ ከዛሎሞቫ የሕይወት ታ
ሪክ ብዙ ወስዶ በመጽሐፉ ውስጥ ባሕርይዋን አን
ጸባርቆአል ። ይሁን እንጂ በመጽሐፉ ውስጥ የተገለጸች
ይቱ ኒሎቭና ከዛሎሞቫ የዕውን የሕይወት ታሪክ
በስተቀርም ገጸ-ባሕርይ የታከለበት መሆኑን እና
ከእነርሱ መካከል አንዷም የዲሚትሪ ፓቭሎቭ እና
ት ቮሳ ዕውን የሕይወት ታሪክ በገጸ-ባሕርይ መልክ
ኒሎቭናን ተመስሎ የቀረበ መሆኑን ጭምር ጎርኪይ
ራሱ በጻፈው ደብዳቤ ገልጾአል ።
«እናት» በተሰኘው የጎርኪይ መጽሐፍ ላይ የቀረ



በው የጎር ኢቫኖቪች የተባለው ገጸ-ባሕርይ በዕውን
በሕይወት ይኖር የነበረውን እና የሌኒን የመጀመርያ
ተማሪዎች ከነበሩት መካከል አንዱ የነበረውን እናቶ
ሊ አሌክሳንድሮቪች ቫኔዬቭ (1879 — 1899 ዓ. ም.) የተ
ባለውን ሬቮሉሺናዊ ያስታውሰናል ። የቫኔዬቭ ቤተ-
ሰቦች ኒዥኒ ኖቭጎሮድ ውስጥ ይኖሩ የነበረ ሲሆን
ጎርኪይም የዚህ ቤተሰብ የቅርብ ቤተኛ ነበር ። በመ
ጽሐፉ ውስጥ የጎር ኢቫኖቪችን ሁኖ የተንጸባረቀው
ገጸ-ባሕርይ ደግሞ በዕውን በሕይወት ይኖር ከነበ
ረው እና ኩርናቶቭስኪይ (1868 — 1912 ዓ. ም.) ከተሰኘው
ሬቮሉሺናዊ ጋር ስምም ሁኖ ይገጥማል ። ይኸ ሬቮ
ሉሺናዊ ሰው ለብዙ ዓመታት በጸና ታሞ የነበረ
እና ሕመሙም ሳያሰልስ የሚያሰቃየው የነበረ ቢሆ
ንም ፤ ይኸንን ሕመሙን እና ሥቃዩን ችላ ብሎ በመ
ታገስ መንፈስ-ጠንካራ እና በጎ-አሳቢ በመሆን ከሬ
ቮሉሺናዊ ተግባሩ ወደኋላ ሳይል ተሳትፎአል ። ስለዚ
ህ ሬቮሉሺናዊ ሰው አቻሬንኮ ሲጽፍ «ይህ ተወዳጅ
እና አስደሳች የሆነ ሰው በአነጋገሩ ረጋ ያለ እና
በአኳኋኑም ብልህ ዘዴኛ የሆነ ዐመለ-ጭምት ሰው
ቢሆንም ፤ የሰዎች አክብሮት ያልተለየው ነበር ። በእ
ርሱ ላይ የሚደርሱበትን ችግሮች ብዙም ከቁም ነገ
ር ባለመቁጠር እየቀለደ በማለፍ የሚያወሳ ነበር ። ከ
ዚሁ ጋር በአንድነትም ለሌሎች ሰዎች እጅጉን አድ
ርጎ የሚያስብ ሰው ነበር» በማለት ጽፎአል ።
በጎርኪይ አገላለጽ ለመጠቀም ፤ ኒኮላይ ኢቫኖቪች
«የፓርቲ ቴክኒሺያኖች» ወካይ ነው ። ኒኮላይ ኢቫኖ
ቪችን የመሳሰሉ ሬቮሉሺናውያንን በሚመለከት ረገድ
ጎርኪይ አንድ ጊዜ የሚከተለውን አስተያየት አቅ
ርቦ ነበር ፡ — «በ 20 ኛው ክፍለ-ዘመን መጀመርያ
ላይ የሩስያ ሶሻል ዴሞክራሲያዊ የሠራተኞች ፓርቲ
ልዩ ልዩ እና አስቸጋሪ የሆኑ ተግባሮችን ማከናወን

ነበረበት ። በኅቡዕ ተግባሮቹን ያከናውን የነበረው ፓርቲ ሥነ ጽሁፎችን ማግኘት ነበረበት ። እነዚህ ለፓርቲው አስፈላጊ የሆኑ ሥነ-ጽሁፎች ሩስያ ውስጥ ተዘጋጅተው መታተም ነበረባቸው ። እንደዚሁም ከስዊዘርላንድ እና ከጀርመን ወደ ሩስያ በሥውር መግባት ነበረባቸው ። ለፓርቲው የሚያስፈልገው ገንዘብ መሰብሰብ ነበረበት ። በኅቡዕ ተግባሮቻቸው ለሚያከናወኑት ወዝ-አደሮች በምስጢር የመገናኛ ቦታዎች መዘጋጀት ነበረባቸው ። ከዚህም በስተቀር ብዙ ብዙ መከናወን የነበረባቸው ተግባሮች ነበሩ ። እነዚህ ተግባሮቻቸውን በኅቡዕ ያከናውኑ የነበሩ ሬቮሉሺናውያን ምሁራን በጭምትነታቸው ለቆሙለት የፓርቲ ዓላማ ይህ ቀረሀ በማይባል ታማኝነታቸው እንደዚሁም የወዝ-አደሩ መደብ ድል አድራጊ ለመሆኑ በነበራቸው የማይናወጽ ዕምነታቸው የታወቁ ነበሩ ። እነዚህን ከመሳሰሉት ሬቮሉሺናውያን መካከል ብዙዎቹን በግል አውቃቸው ነበር» ብሎአል ።

ቭላዲሚር ኢሊች ሌኒን ራሱ ያሠለጥናቸው የነበሩት ከኔቭዞሮቭ ቤተሰብ የሚወለዱት ሁለት እህትማማቾች ከምሁራን ቤተሰብ አብራክ የወጡ ሬቮሉሺናውያት ሴቶች እንደምን የመሳሰሉ ገጸ-ባሕርያት እንዳላቸው ጎርኪይ በመጽሐፉ ላይ ለማንጸባረቅ እንዲችል ብዙ ማቴሪያሎች ለግሠውታል ። «የወዝ-አደሩን መደብ ነፃ ለማውጣት የተቋቋመ የትግል ማኅበር» ውስጥ ተሳታፊዎች ናቸው በመባል ሁለቱ እህትማማቾች ከፔትሮግራድ ውጪ የተጋዙ ቢሆኑም ፤ እህትማማቾቹ ኒዥኒ ኖቭጎሮድ ውስጥ ከሚገኙ የፋብሪካዎች እና የማተሚያ ቤቶች ወዝ-አደሮች ጋር ግንኙነቶችን ሊመሠርቱ ችለዋል ። ተግባሮቻቸውንም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ከፍ-ከፍ አድርገዋል ። እህትማማቾቹ ያከናውኗቸው የነበሩትን ተግባሮች ጎርኪይ ደህና አድርጎ ያውቅ ነበር ።



«እናት» ላይ የተንጸባረቀችይቱ ሳሻ በዕውን ይኖሩ የነበሩ የሁለት ገጸ-ባሕርያት ምስል ነች ። እነርሱም አሌክሳንድራ ኪኪሼቫ (1875 — 1958 ዓ. ም.) እና ጆሴፊን ጋሸር (1878 — 1963 ዓ. ም.) የተሰኙት ሴቶች ሬቮሉሺናውያት ገጸ-ባሕርይ ነች ።

የፋብሪካ ባለንብረት የሆነ የአንድ ሃብታም ሰው ልጅ የነበረችይቱ አሌክሳንድራ ሬቮሉሺናዊት ሆነች ። ኒዥኒ ኖቭጎሮድ ውስጥ የነበራት የራሷ የመኖርያ ቤት አፓርተማ በከተማ ውስጥ የሚገኙ የፖለቲካ ሥነ-ጽሁፎች ተከማችተው ከሚገኙበት ቤት አንዱ እንዲሆን ከማድረጓም በስተቀር ፤ የሩስያ ሶሻል ዴሞክራቲክ የሠራተኞች ፓርቲ ኮሚቴም በእርሷ መኖርያ በሕቡዕ ስብሰባዎቹን ያካሂድ ነበር ።

ጆሴፊን ጋሸርን በሚመለከት ረገድ ፒዮትር ዛሎሞቭ የሚከተለውን ጽፎ ነበር ፡ — «የአክስቱ ልጅ ነኝ እያለች እኔን ለመጠየቅ ከእናቴ እና ከእሕቶቼ ጋር ኒዥኒይ ኖቭጎሮድ እሥር ቤት ትመጣ ነበር ። የዕድሜ ልክ የግዞት እሥራት ተፈርዶብኝ እገኝ ወደ ነበረበት የኒሴይስክ ጠቅላይ ግዛት በዣንዳርሙ ፈቃድ ከታሠረችበት ከሮስቶቭ-ዶን ከተማ ተዘዋውራ መጣች ። ከማክላኩቭካ የግዞት ቦታ ካመለጥኩኝ በኋላ ከእህቴ ከጋሊና ጋር አብራ እዚያው ቆየች» በማለት ጽፎአል ። እነዚህን ሁለቱንም ሴቶች ጎርኪይ ደህና አድርጎ ያውቃቸው እንደነበረ ዛሎሞቭ ጠቅሶአል ።

ጎርኪይ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረጻቸው ባሕርያት በዕውን በሕይወት ከነበሩ ሰዎች ጋር ስምም ሁነው በተመሳሳይነት የሚገጥሙ ከመሆናቸውም በስተቀር በመጽሐፉ ውስጥ ደርሰው የታዩት ድርጊቶች እና ሁኔታዎችም በዕውን ደርሰው ከነበሩ ድርጊቶች እና ሁኔታዎች ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው ። ይሁን እን

ጂ በጎርኪይ መጽሐፍ ውስጥ የተንጸባረቁት ባሕር
ያት በዕውን የነበሩ እነ እገሌ እነ እገሌ የተባሉ
ሰዎችን የሚመለከቱ ባሕርያት ናቸው ተብለው ከማ
ንም ሰው ጋር ተማስለው መተንተን የሌለባቸው መሆ
ኑን በጎርኪይ ጊዜ የነበሩ ሰዎች አስታውቀዋል ።
ጎርኪይ ራሱም ቢሆን ይኸንኑ በሚመለከት ጉዳይ
ሲጽፍ ፡ — «አንድ ደራሲ አንድን መጽሐፍ ሲደርስ
የአንድን የሚያውቀውን ሰው ምስል እርሱ ይኸው
ላችሁ ብሎ በመሳል የሚያቀርበው ሳይሆን ይኸንን
አንድ ሰው የሚመስሉ አያሌ ሰዎችን ስሎ ለማቅረብ
ይጣጣራል» በማለት በመጽሐፉ ውስጥ የሚገለጹ ባሕር
ያትን ለአንድ ለተወሰነ ሰው ለብቻው መቀጸል የማይ
ገባ መሆኑን አስጠንቅቆአል ።

«እናት» በተሰኘው በጎርኪይ መጽሐፍ ውስጥ «ኒሎ
ቭና በዕውን ሕልው ሁና የነበረች ሴት ነችን? በሬ
ቮሉሺኑ መሰናዶ እና በሕቡዕ ይካሄዱ በነበሩ ሬቮ
ሉሺናዊ ተግባሮች እናቶችም ተካፋይ የነበሩ ሲሆን
ቁጥራቸውም ጥቂት አልነበረም ።

ፓቬል ቭላሶቭ አንድ በዕውን የነበረ ሰው ባሕ
ርይ ነውን? እርሱን የመሰሉ ሰዎችም በዕውን ኑረ
ው ታይተዋል ። በእርግጥም ደግሞ ፤ የቦልሸቪክ ፓርቲን
የመሠረቱት እርሱን የመሳሰሉ ወጣቶች ነበሩ» በማ
ለት ጎርኪይ ገልጾአል ።

ጎርኪይ በዚህ ድርሰቱ ውስጥ ሰፊ የሆነ ኪነታዊ
ማጠቃለያን ለማቅረብ ይጣጣር ነበር ። በወቅቱ የ
ነበረውን ዓይነተኛ የክስተት መታወቂያ ለማመል
ከት ይሻ ነበር ። ብሩኅ የሆኑ የብርሃን ነጸብራቆች
ፍንድትድት እንዲሉ ለማድረግ የሚያስችሉ ብልጭ
ታዎችን አቅፈው የሚገኙትን ማናቸውንም ነገሮች
በድርሰቱ የቅኔ ቁጨቶች እየቋጨ ሊያመለክታቸው
ፈልጎ ነበር ። ይኸ ድርጊቱም «እናት» በተሰኘው በዚህ



መጽሐፉ ላይ እጅግ ግሩም በሆነ ሁኔታ ያቀረባቸው
ባሕርያት በዕውን የነበሩ ሰዎችን የሚመስሉ ባሕርያ
ት እየሳሉ እንዲያንጸባርቁ ያበቁት ከመሆናቸውም
በስተቀር በመጀመርያው የሩስያ ሬቮሉሺን ወቅት
ይታይ የነበሩውን ጠቅላላ ሁኔታ ጨምቆ ለማቅረብ
እንዲችል አብቅቶታል ።

«እናት» የተሰኘው መጽሐፉ በሌላ ድርሰት በሰ
ፊው ሊቀጥል የታቀደ ድርሰት እንደነበረ ጎርኪይ ከ
ጻፋቸው ልዩ ልዩ ደብዳቤዎች እና ሌሎችም ማቴሪ
ያሎች ለመረዳት ይቻላል ። «እናት» ከተሰኘው ከዚህ
ድርሰቱ በኋላ «ልጅ»የተሰኘ ሌላ ሁለተኛ መጽሐፍ
ለመድረስ እቅድ ነበረው ። በዚህ በሁለተኛው መጽ
ሐፉ ላይም የፓቬል ቭላሶቭን የግዞት ኑሮ ፤ ከግዞት
ማምለጡን ፤ እና በመጀመርያው የሩስያ ሬቮሉሺን
መሳተፉን ሊገልጽበት አቅዶ ነበር ። በአፕሪል ወር
1908 ዓ. ም. ላይ ጎርኪይ ከቭላድሚር ሌኒን ጋር ተገ
ናኝቶ ሲወያይ «አሁንም ደግሞ እንደ ‘እናት’ የመሰለ
ሌላ መጽሐፍ መጻፍ ይኖርብዎታል...» በማለት ሌኒ
ን ገልጦለት ከነበረው ሃሣብ ጋር የተስማማ ሃሣብ
ነበር ለማለት ይቻላል ።

1933 ዓ. ም. ጎርኪይ በጻፈው አንድ ደብዳቤ ላይ
«እናት» ከተሰኘው ድርሰቱ በኋላ «ልጅ» የተሰኘ ድር
ሰት ልደርስ ነበር ። ይኸንን ለማድረግም ዛሎሞቭ ያከና
ወናቸው ሥነ-ጽሁፋዊ ጥረቶቹ ፤ በሁለቱም ፓርቲዎች
ውስጥ አባሎች ከነበሩት ወዝ-አደሮች ጋር የነበረውን
መተዋወቅ የሚገልጹት ዛሎሞቭ ግዞት ላይ ሁኖ የጻ
ፋቸው ደብዳቤዎች ነበሩኝ ። ይሁን እንጂ ፤ እነዚህ
የነበሩኝ ማቴሪያሎች ሁሉ ሁለተኛውን መጽሐፍ ለመ
ጻፍ ሳያበቁኝ ቀሩ ። «በጋ» ፤ «የሞርዶቭያዋ ሴት» ፤
«ሐላሚ» ፤ «የማይነዛነዘው ሰው» የተሰኙት ድር
ሰቶቹ «ልጅ» በሚል ርእስ ልጽፍ አስቤ ለነበረው ድር

ሰት እንደ አጠቃላይ ንድፍ ሊቆጠሩ ይችላሉ ። ከዚህም በስተቀር «ልጅ» በሚል ርእስ ለመጻፍ ያሰብኩትን ድርሰት ደህና አድርጌ ለማሟላት አለመቻሌን ያሳያሉ ። ደግሞም ጉዳዩ ይኸው ነው» በማለት ጎርኪይ ጽፎአል ።

ጎርኪይ ስለድርሰቶቹ እጅግ ጠንካራ የሆኑ ብያኔዎችን የሚያቀርብ መሆኑ በአጠቃላይ የታወቀ ነው ። «እናት» በተሰኘው ድርሰቱ ላይ ያቀርብ የነበረው ብያኔ ከሁሉም የበለጠ ነበር ። ለዚህ መጽሐፍ ይሰጥ የነበረው አስተያየት በመጽሐፉ ያልረካበት መሆኑን የሚገልጽ ነበር ። ያም ሁኖ ግን መጽሐፉ በሬቮሉሺናዊዎች አካባቢ ወዲያውኑ እና በሰፊውም ተወዳጅ ሊሆንለት በቃ ።

የሌኒን ባለቤት ናዴዥዳ ክሩፕስካያ የሌኒን ትውስቶችን ባቀረበችበት ጽሁፍ ላይ «ሌኒን 'እናት' የተሰኘውን መጽሐፍ በጣም ይወድደው ነበር...» በማለት ጽፋለች ። የሌኒን እሕት ማሪያ ኡልያኖቫ በበኩሏም «'እናት'ን ማንበብ እንዴት ያስደስተን ነበር!» በማለት ጽፋለች ።

ቭላዲሚር ሌኒን ስለመጽሐፉ አስተያየቱን የሰጠው 1907 ዓ. ም. ነበር ። ከዚያም በኋላ ጎርኪይ በሩስያ ሶሻል ዴሞክራቲክ የሠራተኞች ፓርቲ አምስተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ከሌኒን ጋር ያደረገውን ውይይት ሲገልጥ ፡ — «እጅግ አስደሳች የሆኑትን ዓይኖቹን ሌኒን እኔ ላይ በደግነት አመለካከት እርግብግብ እያደረገ 'እናት' የተሰኘው ድርሰቴ በውስጡ የሚጎድሉትን ነገሮች በቀጥታ የነገረኝ ሲሆን ፤ ሌኒን ራሱ ይኸንን ድርሰቴን ገና ሳይታተም የእጅ ጽሁፉን ከላዲዥኒኮቭ ተውሶ ያነበበው መሆኑን ያመለክታል ። እኔም መጽሐፉ ቶሎ ተጽፎ እንዲወጣ ተቻኩዬ የነበረ መሆኑን ነገርኩት ። ይሁን እንጂ ፤ ለምን ተቻኩዬ እንደ



ነበረ ገና ሳላብራራለት ሌኒን ጭንቅላቱን በመነቅነቅ ምክንያቱን አብራራልኝ ፡ — መጽሐፉን ለመጻፍ መጣደፌ ጥሩ እንደነበረ ፤ ለወቅቱ አስፈላጊ የነበረ ድርሰት መሆኑን ፤ ብዙ ወዝ-አደሮች በሬቮሉሺናዊ እንቅስቃሴው የተሳተፉት በግብታዊነት እንጂ ፤ ይሁነኝ ብለው በመገንዘብ አለመሆኑን እና 'እናት' የተሰኘውን መጽሐፍ ማንበባቸው ጠቀሜታን የሚያስገኝላቸው መሆኑን በመግለጽ 'ለወቅቱ እጅግ ጠቃሚ የሆነ መጽሐፍ ነው' በማለት ነገረኝ ። ስለመጽሐፉ ያቀረበልኝ አድናቆት ይኸንን በመናገር ብቻ ሲሆን ፤ ይኸ አነጋገሩም ለእኔ እጅግ ጠቀሜታ ያለው አነጋገር ነበር ። ከዚያም 'እናት' ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ይተረጎም እንደሆነ እና የሩስያ እና የአሜሪካ ሳንሱሮች የመጽሐፉን ይዘት ምንኛ እንደጎዱትም ጠየቀኝ...» በማለት ጎርኪይ ጽፎአል ።

ገና በ 1907 — 1908 ዓ. ም. ላይ መጽሐፉ አሜሪካ ፤ እንግሊዝ ፤ ፈረንሳይ ፤ ጀርመን ፤ ጣልያን ፤ ስፔይን ፤ ቱርክ ፤ ስዊድን ፤ አልባንያ ፤ ዴንማርክ ፤ ቼኮዝሎቫኪያ እና በሌሎችም ሀገሮች ታትሞ ተሠራጭቶ ነበር ። ይኸ ልብ ወለድ መጽሐፍ ለብዙ ጊዜያት በመጽሔቶች እና በጋዜጦች ላይ ከወጣ በኋላ በመጽሐፍ መልክ ታትሞ ወጣ ። ይኸንኑ ጉዳይ አስመልክቶ ሉናቻርስኪይ ሲጽፍ ፡ — «የሠራተኞች ፓርቲ ፕሬስ ፤ በአብዛኛውም የጀርመን ፕሬስ ይኸንን መጽሐፍ ወስዶ እንደ ተጨማሪ ማከያ በብዙ ሚሊዮን ኮፒዎች በጋዜጣ ላይ አሠራጭቶታል ። ለአውሮጳ ወዝ-አደሮች 'እናት' የተሰኘው መጽሐፍ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሊቆጠር ቻለ» ብሎአል ።

ከጥቂት ጊዜያት በኋላም በሌሎች ሀገሮች ለሚገኙ ወዝ-አደሮችም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሊቆጠር በቅቶአል ።

ሩስያ ውስጥ የዚህ መጽሐፍ ሕትመት ለብዙ ዘመናት ቆይቶ ከነበረው የስቶሊፒን የሽብር ጊዜ ጋር ገጥሞ ነበር ። «እናት» እንዳይነበብ የተከለከለ መጽሐፍ ነበር ። መጽሐፉን ያነብቡ የነበሩት ሬቮሉሺናውያን አንባቢዎች ስለመጽሐፉ ያላቸውን አስተያየት በገሀድ መግለጽ አይችሉም ነበር ። አድሀሪ የሆኑት የመጽሐፉ ሃያሲዎች መጽሐፉ ኪነታዊ ብቃት ይጎድለዋል በማለት መጽሐፉን ተቃውመውታል ።

«ዝናኒዬ» በተሰኘው መጽሔት ላይ ሁለት ጊዜ የወጣውን «እናት» የተሰኘውን መጽሐፍ የመጀመርያ ክፍል የቡርዧ ሃያሲዎች ካነበቡ በኋላ «ጎርኪይ አለቀለት» በማለት አሄሱት ። በእነርሱ ግምት የጎርኪይን «ውድቀት» ያስከተለው እና «ወንጀል» እንዲፈጽምም ያበቃው ኪነታዊ በሆኑ አምሳላት ውስጥ ማርክሲዝምን ማዋሀድ መጀመሩ ፤ ሬቮሉሺናዊው የወዝ-አደር መደብ እና ንቃተ ሕሊናው እየጎለመሰ በመሄድ ላይ የነበረው የገበሬ መደብ የሩስያን የተሟላ ነፃነት ለማስገኘት የሚያበቁ ኃይላት መሆናቸውን መግለጹ ነው ይሉ ነበር ።

ይሁን እንጂ ጭካኔ በተመላበት በዚያን ወቅት ውስጥ እንኳን የጎርኪይ ብቁ ችሎታ የደረሰበትን ደረጃ ነባራዊ በሆነ መልኩ የሚያብራሩ ሃሣቦች በየጋዜጣው እየወጡ ለአንባብያን ይቀርቡ ነበር ።

ታላቁ የጥቅምቱ የሩስያ ሬቮሉሺን ድልን ከተጎናጸፈ በኋላ «እናት» የተሰኘው ይህ የጎርኪይ መጽሐፍ በሰፊው ተናኝቶ በብዙ ሺህ አዳዲስ አንባብያን እጅ ሊገባ ቻለ ።

በሀገሪቱ ውስጥ ከቦታ-ቦታ ካደረጋቸው ጉዞዎች እና አዲሱን ኅብረተሰብ ከሚገነቡት ዜጋዎች ጋር ባደረጋቸው የደብዳቤ ልውውጦች ጭምር «እናት» የተሰኘው መጽሐፉ በሶቭየት ኅብረት ውስጥ በብዛት



ከሚነበቡት ልብ ወለድ መጻሕፍት መካከል አንዱ መሆኑን ጎርኪይ ሊገነዘበው በቅቶአል ። በ 1935 ዓ. ም. አንድ የመጽሐፉ አንባቢ በደብዳቤ ላቀረበለት ጥያቄ ጎርኪይ ሲመልስ ፡ — «ደራስያን ስለራሳቸው ድርሰቶች ጥሩ ሃያሲዎች አይደሉም ። ለድርሰቶቻቸው የሚያቀርቡአቸው አስተያየቶችም ስሜታዊ አስተያየቶች ስለሆኑ አስተማማኝ ሊሆኑ አይችሉም ። የሥነ-ጽሁፍ ሃያሲዎች እና አንባብያን የአንድን ደራሲ ልብ-ወለድ መጽሐፍ ወይንም አጭር ልብ ወለድ ታሪክ ያልተዋጣለት ድርሰቱ ነው ብለው ሲገምቱ ፤ ደራሲው ግን ይኸንኑ ድርሰቱን ከሌሎች ድርሰቶቹ ይበልጥ ብዙውን ጊዜ እጅግ የሚወደው ሁኖ ይገኛል ። እስከነተረቱም ለወላጅ እናት ከመልከ-መልካም ልጅዋ ይልቅ መልከ-ጥፉው ይብስባታል ይባላል ። ከዚህም በስተቀር ፤ የአንድን መጽሐፍ ምንነት መፍረጃ ሌላ ትክክለኛ መንገድም ይገኛል ። ይኸውም ፤ በአንባቢዎች ዘንድ መጽሐፉ እስከምን ድረስ ተወዳጅ ሁኖ መገኘቱ ነው ። በዚህ ዓይነት አፈራረድ ከሆነ ‘እናት’ ከድርሰቶቼ ‘ዋና-ዋናዎቼ’ ከሚባሉት መካከል እንደአንደኛው ወይንም ‘እንደ ዋነኛው’ ሊቆጠር ይችላል ። ምክንያቱም በማናቸውም ቋንቋዎች ተተርጉሞ የታተመ በመሆኑ እና በየትኛውም ሀገር ቢሆን ተደጋሞ-ተደጋግሞ የሚታተም በመሆኑ ነው» በማለት ጽፎአል ።

ከታላቁ የጥቅምቱ የሶሻሊስት ሬቮሉሺን በኋላ «እናት» ላይ ተጭኖ የነበረው የሳንሱር ቁጥጥር ሲነሳ ድርሰቱ በቲያትር እና በሲኒማም ጭምር እየተዘጋጀ ይቀርብ ጀመር ።